Periodical Publication - Addis-Abeba

K

መጀመሪያ ዓመት ፤ ቁጥር ፩ ።
1^re^ ANNÉE № 1

ሐሙስ ታኅሣሥ ፳፫ ቀን ፲፱፻፲፯ ዓ ም።
JEUDI 1 JANVIER 1925

ብርሃንና ሰላም

LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voi regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraissant tous les jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

የጋዜጣው ዲረክተር ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት
ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲረክተሩ ያስታውቁ ።
Gabré Christos Taklé Haymanot
Diréteur

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ብርሃንና ሰላም ።

ብርሃን የጨለማ ተቃራኒ ነው ሰላምም ደግሞ የጠብ ተቃራኒ ነው ።

ብርሃን በሌለበት ጨለማ ይሰለጥናል ሰላም በሌለበትም ጠብና ሁከት ጦርነት ይሰለጥናል ።

የፀሐይ ብርሃን ለሰውና ለእንስሳ ለተክል ሕይወት ሊሆን የሚያስፈልግ ነገር ነው ።

የሌሊት፡ ጨለማ ማለዳ ፀሐይ ስትወጣ ይርቃል ፀብና ሁከትም ሰላም ሲመጣ ይጠፋል ።

በሌሊት ደግሞ ጨለማን ለማራቅ ብንፈልግ መብራት እናበራለን ሥራ ሁሉ የሚሠራ በብርሃን ነው በጨለማ የሚሠራ ግን የክፋት ሥራ ብቻ ነው ሌባና ወምበዴ በቀን ይተኛል በሌሊት ግን ወደሌብነቱና ወደቅምያው ይገሠግሣል ክፉ የሚሠራ ሁሉ ክፉ ሥራው እንዳይገለጥበት ወደብርሃን ሊመጣ አይወድም ።

እኛም የኢትዮጵያ ሕዝብ እጅግ ጤናማ የሆነ የፀሐይ ብርሃን በየጊዜው እናገኛለን እንዲሁ ደግሞ ለነፍሳችን ብርሃን የሚሆን ፀሐያችን ክርስቶስ በልባችን ሊያበራ ያስፈልጋል እኔ ብርሃን ሁኜ ወደ ዓለም መጣሁ የመኒበኝ ሁሉ በጨለማ እንዳይኖር ብሎ እርሱ ራሱ እንደተናገረ ።

ወደስልጣኔ የሚያደርስ ጥሩ የትምሕርት ብርሃን ደግሞ ያስፈልጋል ።

በትምሕርት አእምሮ ይበራል ካለመማር ግን አእምሮ ይጨልማል እንግዲህም የኢትዮጵያ ሕዝብ የበራ አእምሮ እንዲያገኝ ለትምርት በሙሉ ኃይሉ ይጣጣር ።

የኢትዮጵያ መ እ ወራሽና እንደራሴ ልዑል ተፈሪ መኰንን የትምርት ብርሃን ላገራቸው ለኢትዮጵያ ሕዝብ በጣም የሚያስፈልግ መሆኑን አውቀው ሊያበሩለት እንደሚጣጣሩ ለትምርት ቤትና ለመጻሕፍት አዕላፋት ገንዘባቸውን ማውጣታቸው ያስረዳል ።

እንግዲህ የኢትዮጵያ መንግሥት መኳንንት ሆይ በሚቻላችሁ ነገር ተግታችሁ ለትምርት በመጣጣርና ገንዘባችሁን በሙሉ ፈቃድ በመሠዋት ለምትገዙት ኗጋር የትምሕርት ብርሃን አውጡለት ።

እንዲህ ብታደርጉ ባገራችን ብርሃንና ሰላም ይሰለጥናል የድንቁርና ጨለማና ሴራ ጠብ ወምበዴና ሌባም ይርቃል ።

ይኸንም ጋዜጣ የጻፍንበት ምክንያት እንደሚቻለን ያህል ለሕዝባችን ጥቅም የሚሆነውን ነገር በየሳምንቱ ለማመልከትና ምክር ለመስጠት ለማንቃትና አዕምሮውን ለማበርታት ነው እንጂ ሰውን ለማሳዘንና ለመንቀፍ አይደለም።ሰውን ከማሳዘንና ከመንቀፍ የሚጠቅም ፍሬ አይገኝም በዚህስ የሚገኘው ቂምና ቁጣ ሁከትና ጠብ ነው ።

ልብ አድርጋችሁ ብትመለከቱ ማናቸውንም ክፉ አድራጊ አንተ እንዲህ ነህ ብለው በቁጣ ቃል ቢሰድቡት ይጣላል ይሳደባል ይማታል እንጂ ከክፉ መንገዱ ይመለሳልን።እንዲያውም ከመናደዱ የተነሣ በክፋት ላይ ክፋትን ይጨምራል ።

ነገር ግን መሳደቡ ቀርቶ በለዘበ መላስ ከክፉ ሥራ የተነሣ የሚመጣውን ጉዳት ቢያስታውቁት ዳግመኛም ዕውቀት የሚሆነውን ነገር ቢመለከቱ የሚገኘውን ጥቅምና መልካሙን ጤና ቢያስረዱት ምናልባት ይመለስ ይሆናል ማን ያውቃል ባይመለስም ለጊዜው ልቡ ሳይነካ አይቀርም ሁሉም ቢቀር አይጣላም ።

ስለዚህ የጻፈውን ነገር በዚህ ጋዜጣችን ሊያሳትም የፈለገ ሰው ቢኖር ለሕዝባችን ምክርና ዕውቀት ትምሕርትም የሚሆን ነገር ጽፎ እንዲያመጣልን እንለምነዋለን ።

የልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት አኳኋን ።

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና እንደራሴ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት የተመሠረተበት ፲፱፻፲፬ ዓመተ ምሕረት በመስከረም በመጀመኛው ወር ነው ።

ከዚያን ጊዜም ጀምሮ ሳያቋርጥ መንፈሳዊና ሥጋዊ ዕውቀትን የሚሰጡ መጻሕፍትና ሌላም ጉዳይ ይታተምበታል አሁንም ብርሃንና ሰላም የተባለ ጋዜጣ መታተም ይኸው ተጀምሯል ።

ለወደፊትም እየጨመረ የሚጠቅም ፍሬ እንዲገኝበት ተስፋ እናደርጋለን ፤ ከማተሚያ ቤታችን እየወጡ በያገሩ የተዘረጉ መጻሕፍት ፫ ሺ ፻ ፳፩ ያህላሉ ።

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና እንደራሴ ልዑል ተፈሪ መኰንን ለማተሚያ ቤት ሠራተኞች የተናገሩት የምሥጋና ቃል ተጽፎ ለዲሬክተሩ የሰጡት ይህ ነው ።

ወንጌል ማለት ትርጓሜው የምሥራች ማለት ስለሆነ እናንተም የወንጌልን ንባቡንና ትርጓሜውን በትጋት በጥንቃቄ አትማችሁ መጨረሳችሁ ትልቅ የምስራች ነውና እጅግ ደስ ብሎኛል ። ወደፊትም ለስሜ መጠሪ ለነፍሴ መታሰቢያ እንዲሆኑ ብዬ ያስጻፍኋቸውን የመጻሕፍትን ንባብና ትርጓሜ ሁሉ በትጋት አትማችሁ ለመጨረስ እንድትችሉ አልጠራጠርም ደግሞ ከዚህ በፊት በኢትዮጵያ ያልተለመደውን ይህን አዲስ የመጽሐፍ ማተሚያ ሥራ የውጭ አገር ሰው ሳይጨመርባችሁ እናንተው ራሳችሁ ብቻ ለመሥራት በመቻላችሁ እጅግ አመሠግናችኋለሁ ። እኔም በሚቻለኝ ነገር ሁሉ የሚገባችሁን እርዳታ አላጐልባችሁም ብለው ፬፻ ብር ጉርሻ ሰጧቸው ።

የካቲት ፲፩ ቀን ፲፱፻፲፯ ዓመተ ምሕረት ።

በማተሚያ ቤት የታተሙ መጻሕፍትን አብዝተው የገዙትንም ሰዎች መጽሐፍና ዕውቀትን ስለ መውደዳቸው እናመሠግናቸዋለን ።

ክቡር ራስ ኃይሉ ።

ወደ አውሮፓ ከመሄዳቸው አስቀድሞ በ፲፱፻፲፮ ዓ ም መጋቢት ፳፯ ቀን ወደ ልዑል የኢ መ አ ወ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት መጥተው የመኪናውን አኳኋንና የሥራውንም መከናወን አይተው ሲመለሱ ለማተሚያው ቤት ዲሬክተር እንዲህ ብለው ተናገሩ ። እኔ አሁን የመጣሁት የመኪናውን አኳኋን ብቻ ለማየት ነበር ። አሁን ግን ምንም ድንገት ብመጣ በዚህ የሚገኘውን የመጻሕፍት ጥቅም አይቻለሁና ብለው በ፫፻ ብር ከያይነቱ መጽሐፍ ገዝተው ሄዱ ።

ደግሞ ከአውሮፓም ከተመለሱ በኋላ በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት የታተሙትን መጻሕፍት በማስታወቂያ ላይ ተጽፈው ቢያዩዋቸው ዕውቀትን ከመውደዳቸው የተነሣ በ፲፱፻፲፯ ዓመተ ምሕረት ታሕሣሥ ፲፯ ቀን ወደ ማተሚያ ቤት በታላቅ ደስታ መጡና በማተሚያው ቤት የታተሙትን መንፈሳዊና ሥጋዊ ዕውቀት የሚገኝባቸውን መጻሕፍትን ተመልክተው በሺህ ፳፰ ብር ከያይነቱ ሁሉ ገዙ ።

የማተሚያውም ቤት ዲረክተር አብዝተው መግዛታቸውን ባየ ጊዜ በወርቅ የተደጐሰና ያጌጠ ፩ ቅዱስ ወንጌል ፩ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ፩ማር ይስሐቅ ስለ መታሰቢያ ብሎ አበረከተና ደስ አሰኛቸው ማንኛውም ሰው እውቀትን የሚፈልግ እንደ ዚሁ መጻሕፍትን አብዝቶ ቢገዛ ዕውቀት መውደዱን ያስረዳል ።

የንግድ ወሬ ።

ከኢትዮጵያ መንግሥት ውስጥ ከቤገምድር ከጎጃም ከወሎ ከየጁ ከትግሬ ከወልቃይት ወደ ሐማሴን ወደ አስመራ ብዙ ነጋዴዎች ሲነግዱ በያይነቱ ብዙ ዕቃ ይዘው ይሔዳሉ ።

ያገሩ ገዥ ደግሞ የውጭ አገር ነጋዴዎች ሲመጡ የሚሠፍሩበት ቦታና ቤት በልዩ አድርጎላቸዋል ።

ነጋዴዎቹ ወደሠፈሩበት እየመጣ ከወዴት አገር እንደመጡ የተጐዱትም ጉዳት እንዳለ ይጠይቃቸዋል ።

ከነርሱም ውስጥ ገንዘቡ በግፍ የሔደበት ነጋዴ የተገኘ እንደሆነ በቶሎ ያስመልስለታል ።

የነጋዴው ገንዘቡ በሸፍጥ ቢሔድበት ወይም ቢያዝበት ዕለቱን ያሰጠዋል ።

ደግሞ አንድ ጊዜ የተገናኙትን ነጋዴዎች ሁለተኛ ሲመለሱ እንደ ዘመድ አድርጎ በናፍቆት ይጠይቃቸዋል ።

ስለዚህ ነጋዴ በየሔደበት አገር ስለ አገረ ገዢው ደግነት ወሬውን ይለቃል። ሌላውም ነጋዴ ሁሉ ዝናውን ሰምቶ ወደዚያ አገር ሊሔድ ያምረዋል ።

አገረ ገዢውም እንደዚህ ማድረጉ በሚገዛው አገር ንግድ እንዲሰፋና የራሱን ጥቅም ፈልጎ ነው ። ይህም ሳይቀር ድሀው ነጋዴ ለጊዜው ስለተጠቀመ ደስ ብሎት ይመርቀዋል ።

በኢትዮጵያ መንግሥት ያሉ አገረ ገዥዎችም በሚገዙት አገር ሁሉ መንግሥታቸውና ሕዝባቸው እንዲጠቀም ንግድም በገራቸው እንዲለማ ነጋዴውም አገሩንና መንግሥቱን እንዲወድና እንዲመርቅ ለነጋዴውና ለገበሬው መንገዱን ሊያቀኑለትና መሰናክሉን ሊያስወግዱለት ይገባል ።

ይኸንንም ሹማምት እንዲያስቡትና እንዲ ፈጽሙት እንዲ በረታቱም ተስፋ እናደርጋለን ።

ሥራና ትምህርት ።

የዓለም ነገሥታት ሁሉ ከፍ ወዳለ ሥልጣኔ የደረሱ በሥራና በትምህርት ነው ። እኛም የተሰጠችንን ጊዜ በሥራና በትምህርት ብንፈጽማት ደስ ታሰኘናለች እንጂ ቁም ነገር ሳንሠራባት እንዲያው አባክነናት ብንቀር በኋላ ጸጸትና ቅርታ ፤ ኃዘንና ትካዜ ይሆንብናል ነገር ግን አሳባችን ሁሉ በሥራና ለትምርት ቢሆን የደስታ ፋና በልቡናችን ይበራልናል ፤ ዕረፍታችንም ይጣፍጣል ።

ለሥራ ለምትህርት የማይጣጣር ሕዝብ ግን ከሚገባው ሥልጣኔ ደረጃ ሳይደርስ ወደኋላ ሆኖ ይቀራል ። ይኸም በሥጋዊ ብቻ አይደለም በመንፈሳዊም ነገር እንደዚህ ነው ።

MAY

አንድ መጽሐፍ እንደሚል የማይሠራና የማይማር፡ክንፍ ሳለው እንደማይበር አሞራ ወይም ክንፍ አግኝቶ እንደማይዋኝ አሣ ነው ይላል ። ስለዚህ እኛም የኢትዮጵያ ልጆች ወደ ትልቁ ሥልጣኔ ደረጃ እንድንደርስ ሥራና ትምርት ያስፈልገናል ።

ለሥራና ለትምርት የልባችንን ኃይል ብናሰንፈው ግን ሥልጣኔውን እንኳን ልናገኘው በሩቅ ልናየው እንኳ አንችልም

አሁንም ወደ ዕውቀት ጎዳና ለመሔድ የሚያግደንን መሰናከል እንድናርቀውና እንድናስወግደው ተስፋ አለን ።

ስለ ዘንድሮ አዝመራ ከሀገር ውስጥ የመጣልን ወሬ ።

ጅሩ በሚባል አገር ነጭ ስንዴና ጥቁር ስንዴ ባቄላና ተልባ አተርና ሽንብራ ጓያ ይበቅልበታል ጥቁር ጤፍም አልፎ አልፎ ጥቂት ጥቂት ይገኛል ። ነገር ግን የጅሩ ዋና አዝመራው ስንዴ ነው ። በሁሉም ዘመን እጅግ አድርጎ አምሮበታል ያበቃቀሉንም ነገር ሲያዩት ያስገርማል ፡ ያገሩ መሬት መረሬ ስለሆነ ስንዴው በነሐሴ ይዘራል ። በሕዳርና በታሕሣሥ ዝርዝር ይሆናል ፡ በዚህም ጊዜ ከከፍተኛ ቦታ ላይ ሆኖ የጅሩን ሜዳ ላያት ሰው ከልምላሜዋ ማማር የተነሣ ልክ በባሕር መሃከል ያለ ይመስለዋል ። ነገር ግን ወደ እርሻው ውስጥ ገብቶ ያዩት እንደሆነ መረሬው አፉን ለቆ ክንድ ክንድ ያህል ተሰንጥቆ ይገኛል ። ወይ ግሩም ከእንደዚህ ያለ ንቃቃት መሬት ላይ ያንን ያህል ልምላሜ መገኘቱ እግዚአብሔርን ያስመሰግናል ያገሩም መሬት ውድ ስለ ሆነ በመላው ጅሩ ከእርሻ በቀር እዳሪ መሬት በብዙ አይገኝም ።

ዳሩ ግን አንዳንድ ዘመን ብርድ የሚባል በሽታ አለበት በታሕሣሥና በጥር እየተነሣ እህሉን ሁሉ ያጠፋዋል ። ይኸን ካለፈ በኋላ ግን ምንም ጥፋት የለበትም ፡ እንዲህ አድርጎ በየካቲትና በመጋቢት መከሩን ይሰበስባል ፡ ዛሬም በዚህ ወራት ባንድ ብር አንዳንድ ዳውላ ይሸመታል ። በጅሩ ዙሪያ ያሉትም የቄላ አገሮች ማሽላ ዘንጋዳ ጤፍ ኑግ ሰሊጥ ሱፍ ሙዝና ሎሚ ጥጥ ያበቅላሉ ። በዚያም አገር የሚኖሩ ሰዎች ሞረት ከጥዱ ፡ ደብብ ከጸጋ እንወለዳለን እያሉ የሚመኩ ጥንት ክርስቲያን ናቸው ። ነገር ግን ዝንጀሮ የሚባል ዋና ባላንጣ ስላ ወደቀባቸው ከጧት እስከ ማታ ድረስ እሱን ሲጠብቁ ፍጹም ዕረፍት አያገኙም ።

ከከተማ ውጭ ስላሉ አገሮች አኳኋን ።

ከበረህ ወዲያ ፡ ላይ ጊዳ ፡ ታች ጊዳ ፡ ወበሬ የሚባሉ ክፍ ክፍ ያሉ አገሮች አሉ በለዚህም አገሮች የሚገኘው ዋናው አዝመራ ገብስ ነው ። ወደ ተራራም አጠገብ ከሆነው ላይ ባቄላ አተር ስንዴም ጥቂት ጥቂት ይገኛል ።

ይኸም አገር በልግ ከመከር የሚያውቅ ስለሆነ ካመቱ ፪ጊዜ አዝመራ ያበላል ዛሬም ባሁኑ ወራት ባ፩ብር አንዳንድ ዳውላ ገብስ ይሸመታል ።

ዳግመኛ ከዚያም ከዚያም ብዙ ወንዞች የሚገኙበት ሳር የሞላበት አገር ስለ ሆነ ለላምና ለበሬ ለፈረስና ለበቅሎ ለባዝራና ለበግ የተመቸ አገር ነው ። ይልቁንም ከብዙ ዘመን ወዲህ የስናር አህያ መጥቶ የስናር በቅሎ የሚያረቡ ስለሆነ ከስናሩ አህያ የተወለደውን በቅሎ ለ፪ ብር (ወይም ለ፻፯) እየሸጡ የዚያ አገር ሰዎች በገንዘብ ከብረዋል ።

በውነትም ይህ ከስናር አህያ የተወለደው በቅሎ ስለ ቁመቱ ርዝመትና ስለ መልኩ ማማር ብዙ ዋጋ ሊያወጣ የተገባው ነው ።

የዚያም አገር ሰዎች ቀድሞ ምንም በአረሚ ሥርዓት ቢኖሩ ከብዙ ዘመን ወዲህ በወንጌል አምነው ቤተ ክርስቲያን ታንጸላቸው በክርስቲያን ሥርዓት ይኖራሉ ።

በቴሌግራም የመጣ ወሬ ።

የኢጣልያ መንግሥት ሌጋሲዮን ።

አዲስ አበባ ፳ ዲሴምበር ሺ፱፻፳፬ ።

የ፲፱ ዲሴምበር የለት ወሬ ።

ሮማ ። በሴናተሮች ቤት የእርሻ ሚኒስቴር ያመት ከሳራ ሂሳብ ተመረመረ ። የጦር ሚኒስቴርን ያመት ከሳራ ሂሳብ ሴናተሮች ተቀበሉ ።

በፓርላሜንት የትምሕርት ሚኒስቴር ያመት ከሳራ ሂሳብ ተመረመረ ። የትምሕርት ሚኒስትሩ በኢጣልያ አገር የትምሕርት ቤት እየተሻሻለ በመሔዱ ራፖር አደረገ ።

ዱራትዞ ። በዩጎስላቢያና በአልባኒያ ወሰን ላይ ብርቱ ጦርነት ሆኑዋል በመድፍና በመትረየስ ። ከአልባኒያ መንግሥት ወታደርና ከዩጎስላቢያ ሸፍታ ወታደር ጋራ ። የአልባንያ መንግሥት ወታደሩን ሁሉ እንዲከት አዘዘ ።

የ፳ ዲሴምበር የለት ወሬ ።

ሮማ ። በኢጣልያ መንግሥትና በጀርመን መንግሥት መካከል የንግድ ውል ለመዋዋል የተጀመረው ስለ ልደት ዓመት በዓል ክብር ተዘጋ ። ሁለተኛ ደግሞ በ፫ ገንቢዮ ይከፈታል ።

ከአልባኒያ በአሬሲየል የመጣ ወሬ እንዲህ ይላል የአልባኒ መንግሥት ወታደሮች የዩጎስላቢያን ሸፍታ ወታደሮች አሸንፈው አንድ መድፍ አንድ መትረየስ ሀያ ሶስት ወታደሮች ማርከው የክሩኔን ከተማ አስለቀቁ ከነዚህ ከሀያ ሶስት ወታደሮች ሶስቱ የሴርቢያ ወታደሮች ናቸው ። ይህ ሁሉ የሴርቢያ መንግሥት እነዚህን ሸፍቶች መርዳቱን ያስረዳል ።

አዲስ አበባ ፳፫ ዲሴምበር ሺ፱፻፳፬

የ፳፩ ዲሴምበር የለት ወሬ ።

ሮማ ። ዛሬ በፓርላሜንት ስለ ገንዘብ ነገር ምክር ተደርጎ ነበር ። ሚኒስትሩ ዴስቴፋኒ ከዛሬ ሶስት ዓመት ጀምሮ በኢጣልያ አገር የገንዘብ ገቢና ወጭ ጥቂት በጥቂት እየተሻሻለ ሔዷል ብሎ ራፖር አደረገ ። በሚመጣው ዓመት ደግሞ ሚኒስትሩ ገቢና ወጭ ትክክል ይሆናል ብሎ ተስፋ ሰጠ ። ማለት ባለፈው ዓመት ወጭ ከገቢ ይበዛ ነበር ። ፓርላሜንትም የገንዘብ

ሚኒስትሩ ባቀረበው ራፖር በጣም ደስ ብሏቸው አመሠገኑት ራፖሩንም ተቀበሉ ።

ከዚያ በኋላ ሙሶሊኒ ስለ ልደት ዓመት በዐል ክብር ፓርላሜንት እስከ ዠንበዬ (ጥር) ድረስ ይዘጋል ብሎ አስታወቀ ።

ሴናተሮችም የገንዘብ ምኒስቴሩን ራፖር ተቀብለው ስለ ልደት ክብር የምክር ቤታቸው ተዘጋ ።

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና እንደራሴ ተፈሪ መኰንን ላገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሊሆኑ ያሳተሙዋቸው በማተሚያ ቤታቸውም የሚሸጡ መጻሕፍት የሚከተሉ ናቸው

የቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ተግሣጽ ንባቡ ከነ ትርጓሜው	፲፪ ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነ ትርጓሜው	፲ ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሲራክ ንባቡ ከነ ትርጓሜው ።	፯ ብር
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነ ትርጓሜው	፫ ብር
መጽሐፈ ሲራክ ንባቡ ከነ ትርጓሜው	፫ ብር
የሕይወት ታሪክ	፪ ብር ተኩል
የቁጥር ትምርት	፩ ብር
ያማሪኛ ሰዋስው	፩ ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩ ብር
የብዙ መኳንንቶች ሥዕል ያለበት ካርት ፖስታል ፳፬ቱ	፩ ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የአደን መንገዳቸው አኳኋን	አላድ
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ፡	አላድ
አጭር የዓለም ታሪክ	አላድ
ያማሪኛ ፊደል	ሩብ
አሳብና ምኞት	ሩብ
የበገና ግጥም	፪መ
ለኢትዮጵያ ልጆች ማመልከቻ	፪መ
የምክር ቃል	፪መ
የልብ አሳብ ግጥም	፩መ

ስሙን በደብዳቤ ወረቀትና በእንቤሎፕ በካርት ብዚትም ለማሳተም ፤ ወይም የሠርግ መጥሪ ለሌላ ድግሥም መጥሪ ሊያሳትም ደብተርም ሊያሠራ የሚፈልግ ። በፈረንጅ ቋንቋም በዓረብና በግሪክም ሆነ ባማሪኛም እንደ ፈለገው ዓይነት ይታተምለታል ። ቀለምና ጌጥ ያለው ኀረግ ሥእል ዋጋውን እየከፈለ ይሠራለታል ።

መጽሐፍ አሳትማለሁ ያለ ሰው ድሀ ቢሆን ጥሩ ሐሳብ ያለው የሚጠቅም መጽሐፍ ካወጣ ። መጽሐፉ ያለ ዋጋ ታትሞለት መጽሐፉ እየተሸጠ ዋጋው ለማተሚያ ቤት ይገባል ። ጻፊውም ደግሞ ከጻፈው መጽሐፍ ልዑል የኢትዮጵያ መ አ ወራሽና እንደራሴ ተ መ የፈቀዱለትን ያህል ጕርሻ ይቀበላል ።

መጽሐፍ የጻፈ ሰው የማኅተሙን ዋጋ ከፍሎ ለማሳተም የሚችል ከሆነ ግን የሥራውና የወረቀቱ ታስቦ ዋጋውን ከፍሎ ይታተምለታል ። የሚጠረዝ መጽሐፍ ወይም ደብተር ያለው ዋጋውን እየከፈለ እንደ ፈለገው እንጠርዝለታለን ።

የአዲስ አበባ ገበያ አኳኋን ባለፈው ሳምንት ።

	በብር	በመሐ	ዳውላ	ቁና
ነጭ ስንዴ ።				
ጥቁር ስንዴ	፩			፱
ነጭ ጤፍ	፡			፲
ጥቁር ጤፍ	፡			፯
ገብስ	፡			፯
ሽንብራ	፡			፲፬
ባቄላ	፡			፲
አተር	፡			፲
ቡና	፡			፲
ሙዝ	፰		፩ ፈረሱላ	
ሎሚ		፩	፲፪ በቍጥር	
ትርንጎ		፡	፲፭ በቍጥር	
ድንች		፡	፩ በቍጥር	
ነጭ ሽንኩርት		፡	በትንሽ እርቦ	
ቀይ ሽንኩርት	፪		፩ ትልቅ ሰልቻ	
ኮረሪማ	፪		ደኸው እንደዚሁ	
ዝንጅብል		፡	፴፪ በቍጥር	
ነጭ አዝሙድ		፡	፴ በቍጥር	
ጥቁር አዝሙድ		፡	፫ ኩባያ	
ኦበሽ		፡	፫ ኩባያ	
ሰናፍጭ		፡	፬ ኩባያ	
የጎመን ዘር		፡	፬ ኩባያ	
ድንብላል		፡	፫ ኩባያ	
ጌሾ	፪	፡	፯ ኩባያ	
ውቅጥ በርበሬ	፩	፬	፩ የሀያ ጭንት	
ዛላ በርበሬ	፫		፳፪ ኩባያ	
ቃሪያ በርበሬ			፩ ጁሽ	
ማር	፯	፩	፶ በቍጥር	
ቅቤ	፪		፩ ጉንዶ	
የወለዥ ቅቤ			፩ አገልግል	
ቅባኑግ	፩	፡	፩ እንክብል	
እንቁላል			፪ ጠርሙዝ	
ወተት	፩	፡	፲፪ በቍጥር	
			፲፬ ጠርሙዝ	
	፻፹		፩ ፈረሱላ	
የዘሆን ጥርስ	፱	፰	፩ ፈረሱላ	
የበሬ ቆዳ	፲		፩ ኮረጆ	
እንጋሬ	፩		፻፹ ወቄት	
ጥጥ	፩		፲፬ ኩባያ	
አሸበ	፩		፬ በቍጥር	
አሞሌ ጨው	፲፱			
በሬ ፍሪዳ	፱			
ላም የወተት	፰			
ላም መሲና	፬			
በግ ሙክት	፪			
በግ መሲና	፩	፬		
በግ ጠቦት	፭			
ፍየል ሙክት	፩	፰		
ፍየል ወጠጤ	፡			
ስምንት ደሮ ሱካክ	፺፭			
ፈረስ ማስፊያ	፳፫			
ፈረስ መጠናኛ	፶			
በቅሎ ማስፊያ	፲፯			
በቅሎ አጋሰስ	፬			
አህያ				

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

መጀመሪያ ዓመት ፣ ቍጥር ፪ ።
1re ANNÉE №. 2

ሐሙስ ታኅሣሥ ፴ ቀን ፲፱፻፲፯ ዓመተ ምሕረት ።
JEUDI 8 JANVIER 1925

ብርሃንና ሰላም
LUMIÈRE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ ሲገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

የጋዜጣው ዲሬክተር ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የራሱን ጉዳይ የሚያሳትም ሰው ዋጋውን እየከፈለ እናትምለታለን ።

ስነ በዓል ።

ባለፈው ሳምንት ታሕሣሥ ፳፱ ቀን ዓርብ ያባታችን የአቡነ ተክለ ሃይማኖት የልደታቸው በዓል ስለሆነ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን በዓሉን ለማክበር ከብዙ መኳንንትና ሠራዊት ጋራ አዲስ አበባ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን ሔደው ነበር አባታችን አቡነ ማቴዎስም መጥተው ነበረ ። ፫ሰዓት ሲሆን ታቦት ወጣና ዑደት ተደረገ ከዑደቱም በኋላ አባታችን አሳረጉና በዓሉ በደስታ ተፈጸመ ። ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንንም በታላቅ ዓጀብ ሆነው ወደ ግቢ ተመለሱ ።

ስለ በዓለ ልደት ።

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት የዓለም ድኅነት የተገኘበት እጅግ የከበረ ዋና በዓል ነው ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ቅድስት ድንግል ከሆነች ከመቤታችን በሥጋ በመወለዱ እኛ የእግዚአብሔር ልጆች ለመሆንና መንግሥተ ሰማያትን ለመውረስ እድል አገኘን ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተወለደ ጊዜ በሰማይ ታላቅ ደስታ ሆኖ እንደነበረ እነሆ በቅዱስ መጽሐፍ እንዲህ ሲል ተጽፎ እናያለን ።

በዚያ አገር ብዙ እረኞች ነበሩ መንጋቸውን በሌሊት ተግተው ይጠብቁ ነበር እነሆ የእግዚአብሔር መልአክተኛ መጥቶ በፊታቸው ቆመ ። የእግዚአብሔርም ክብር በርሳቸው ላይ በራ ፍጹም ፍርሃትም ፈሩ ፤ መልአኩም ለሕዝቡ ሁሉ ታላቅ ደስታ የሚሆን ምሥራች እነግራችኋለሁ አትፍሩ አላቸው ፤ እግዚአ ብሩክ የሚሆን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዛሬ ተወልዶላችኋልና ምልክቱም እንደዚህ ነው ፤ ሕፃኑን በጎል ተጥሎ ታገኙታላችሁ አላቸው ከዚህም መልአክ ጋራ ብዙ የሰማይ ጭፍሮች መጡ እግዚአብሔርን እንዲህ እያሉ እያመሰገኑ በሰማይ ለእግዚአብሔር ምስጋና ተደረገ በምድርም ሰላም ሆነ ለሰዎችም በጎ ሥምረት ሆነ እያሉ ከዚህም በኋላ መላእክት ወደሰማይ አረጉ ።

ከዚህ በላይ በተጻፈው ቃል እንደምናየው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በበረት መጣሉ በትሕትናው እኛን ሊያከብረን እንደሆነ እስበን የእግዚአብሔር ፍቅር አንድ ልጁን እኛ እንድን ዘንድ ወደ ዓለም በመላኩ ተገልጧልና ። ይኸንን በዓላችንን በተድላ በደስታና በምሥጋና ልንቀበለው ይገባናል ።

ስለዚህ እግዚአብሔር እኛን በማፍቀሩ አንዱን ልጁን ቤዛ ሊሆነን አሳልፎ እስከ መስጠት ደርሶ ትልቅ የማዳን አድራጎት እንዳደረገልን የምናስብበት በዓል ነውና የልደትን በዓል የደስታና የምሥጋና በዓል ልናደርገው ይገባናል ።

በዕለተ ልደት ለእረኞች በቤተ ልሔም ያበራላቸው ብርሃን በገራችን እንዲያበራልን ዳግመኛ መላእክት በሰማይ ምስጋና በምድርም ሰላም ለሰዎችም በጎ መስማማት ሆነ ብለው ሲያመሰግኑ እረኞች የሰሙት የምሥራች ቃል ለኛም እንዲፈጸምልን እየተመኘን እንኳን ብርሃነ ልደቱን ለማየት አበቃችሁ እንላለን ።

ሰውነትህን ከሚጎዳ ተጠበቅ ።

ሰውነትህ በጤና ቢጠበቅና ቢኖር እጅግ መልካም ነው በዚህ ዓለም በጤንነት ከመኖር የሚበልጥ ሌላ ነገር የለም ነገር ግን ብዙ ሰዎች ገንዘባቸውን ሰጥተው ሰውነታቸውን የሚጎዳ በሽታ ያመጣሉ ለዚሁም ዋና ምክንያት የሚያሰክር መጠጥ መጠጣት ነው ።

አያሌ ሰዎች ጧት ጧት ደህና ሰዎች ማታ ግን እንደ ዕብዶች ሁነው አእምሮዋቸውን አጥተው ይገኛሉ በልክ ሊሔድ የሚገባው አእምሮዋቸው ከመጠጡ ብርታትና ሙቀት የተነሣ ያለ ሥርዓት ይንጋጋል፤ ቆይቶ ቆይቶ የሰውነቱ መዘወር ሁሉ ይላላል ከዚያ በኋላ አካላቸው ይዝላል መላሳቸው ይታሰራል አፋቸው ይዘጋል አእምሮዋቸው ይጨልማል ቀድሞም የሚጠየቁትን ሁሉ ከማድረግ አይመለሱም ይህ የሚያሳዝንና ላድራጊው የሚያቀል ነገር አይደለምን ።

ግን እጅግ የሚያሳዝን እንዲህ ያለ ነገር አይተው ሲያበቁ ትንሽ የማይሰጉ ተመልሰው እንዲህ የሚያደርገውን መጠጥ የሚጠጡ ሰዎች ቢገኙ ነው።

የመጠጥ አመል ያለበት ሰው ሐሳቡ ሁልጊዜ ትክክል ሊሆን አይችልም ። የሚያቃጥለውን መጠጥ ያጣ ጊዜ እንደ ሞኝ ሆኖ ራሱን ደፍቶ ይንዘረፈፋል ወይም በትንሽ ነገር ይናደዳል።መጠጥ ያገኘ እንደሆነ ግን ያለልክ ደፋርና አፈኛ ብልህም ይሆናል።ስለዚህ እንደዚህ ያለ ሰው የገዛ አእምሮውን ሊያቀና አይቻለውም ።ነገር ግን እርጥቡን ቂጠማ ወደ ፈቀዱት እንደሚጠመዝዙት መጠጡ ወደ ፈቀደው ያቃናዋል ።

ታድያስ ስለምንድር ነው ብዙ ጭዎች ታላላቆችም የሚጠጡት የሚል ሰው ቢኖር ።

መጠጥ ከማብዛትስ ምን ጥቅም አገኙ ትላለህን የሚያሰክር መጠጥ ጠጥተው የተጐዱ እንጂ በስካር የተጠቀሙ ሰዎች አታገኝም ።

ወደ መሸታ ቤት የሚያዘውትር በልፋት ያመጣውን ገንዘቡን ለውሀ ይለውጣል ። በለመሸታውም ጋኑና ጠርሙሱ ይጋባለታል ያም የኪሱን ገንዘብ ያራግፋል ። ያንን የሚፈስ ነገር ሲሰጥ ያም የሚከተት ገንዘብ ይሰጣል።አንዱ ይጠግባል አንዱ ግን ይደኸያል ባለመሸታ ባለፎቅ ቤት ይሰራል መሸተኛ ግን ልብሱን እያወለቀ ሽጦ እስከ መብላት ይደርሳል።

አንድ ምሳሌ እንደሚል፤ወደ መሸታ ቤት ባንድ ደጅ ይገባል በሶስቱ ይወጣል ።አንዱ ደጅ ወደ ወህኒ ይወስዳል ሁለተኛውም ወደ ሆፒታል ያደርሳል ። ሶስተኛውም ወደ ጉድጓድ ያወርዳል ።

ብዙ ሰዎች ከሥጋ ከወተትና ከቅቤ ይከለከላሉ ። ሥጋቸው በልዩ ልዩ በሽታ ከሚያበላሽና ዘር ከሚያሳጣ ሰውነታቸውን አቃጥሎ ወደ ከፉ ግዝሙት ስርቆት ወደ ነፍስ መግደል በሚያደርሱ ነፍሳቸውን ከሚያጠፋ መርዛም መጠጥ ቢከለከሉ እጅግ በተጠቀሙ ።

ከሁሉ የበለጠ መጠጥ ውሀ ነው ። ጠጅ ጠላ የወይን ጠጅ የመሰለውን በልክ ቢጠጡት ምን ይጐዳል የሚሉ ሰዎች አሉ ። ነገር ግን በጥቂት ተጀምሮ ስካርን እያሳደገ የሚሄድ ነው ። የሚያሰክርም ከሆነ መጨረሻው ክፉ ነውና ይቅርብኝ ብሎ መተው ይሻላል ።

እንደሰማሁት በመጠጥ ንግድ ብዙ ትርፍ ይገኛል ። ነገር ግን ገንዘብ ተገኝቶ ሕዝቡ በመጠጥ መርዝ ሲሰንፍና ሲጐዳ ጊዜ ምንድር ነው ትርፉ ። በእውነተኛ ልብ ለሚያስብ ሰው ትልቅ ኪሳራ ሁኖ ይታየዋል ።

አያሌ ሰዎች አረቄና የአረቄ ዓይነት መጠጥ ሲጠጡ ሰውነታቸው ግሉ የአካላቸው መኪና ከሚገባው አልፎ ስለሄደ በአእምሯቸው ውስጥ የተከተተ የፈቀዱትንና ያልፈቀዱትን ነገር ሲያስለፈልፋቸው ከሣቴ ብርሃን ይሉታል ። ይህ ግን ትልቅ ስሕተት ነው ። ተኝተው አድረው ሲነሱ ያ ሙቀት ለብዙ ቀን የሚበቃ ኃይላቸውን ስለ ጨረሰው ያለልክ ደክመው ይገኛሉ።አንዳች ሳይሠሩም ደክመው ልቤን ልቤን ይላሉ ።

ባዲስ አበባ አንዳንድ ነጋዴዎች ዕቃ ለገዙላቸው የባላገር ሰዎች ጉርሻ እያሉ አለዋጋ አረቂ ያጠጥዋቸዋል ። ብዙ እንግዶች ባላገርም የአረቂን መርዛምነት ሳያውቁ በከንቱ መልካም መጠጥ አገኘን ብለው ይጨልጡታል ። አያሌ ሰዎችም ሰክረው መሔድ አቅቶዋቸው ይወድቃሉ። ወዲያው እንኳን ባይሞቱ እንዲታመሙ እርግጥ ነው ። የበለጠ ጉዳትም በእድሜ ያልበሰሉ ልጆች እንዲህ ባለ ነገር ቢጸመዱ ነው።ይህ ነገር ላገራችን ትልቅ የጠላት ጦር እንደሆነ አስተውሉ።ይህ ነገር ብርቱ ጉዳት መሆኑን አወቅን።እንግዲህ ራሳችንን መጠበቅ ይገባናል።

ሐኪሞች ከመጠጥ ነው ምክንያቱ የሚሉት ስንት ዓይነት በሽታ ነው።የበሽታውን ብዛት ዓይነት ልታውቅ ብትፈልግ ሐኪሞችን ጠይቅ።እንግዲህ ኢትዮጵያዊ ጐበዝ ሆይ ይህንን ካወቅን የሚያሰክረንን መጠጥ ትተን ለሰውነታችን ጥቅም የሚሆን ጉልበትና ጤንነት የሚሰጠንን መጠጥ እንጠጣ።በድካም የምናመጣውን ገንዘባችንንም ለመርዝ አንለውጠው ።

ብዙ የኢትዮጵያ ልጆችና ትልልቅ ሰዎች ሕዝባቸው በመጠጥ ጦር በመወጋቱና በመቍሰሉ ያዝናሉ።ይህ የመጠጥ ነገርም በገራቸው ዋና ጥፋትና ጉዳት መሆኑን ያውቃሉ ግን የሚያሰክርን መጠጥ ትተው ውሀና ብርዝ ወተትም ቢጠጡና ሌላውንም ቢያስጠጡ ምን ኪሣራ አለው፤እባካችሁ ሰውነታችንን የማይጐዳ የማያሰክር መጠጥ እንጠጣ ። ጀግና የኢትዮጵያ ልጅ በመጠጥ የተማረከ እንደሆነ ትልቅ ነውር ይሆናል ግን እንግዴህ ወዲያ የገሬ ልጆች በመጠጥ ድል እንዳይሆኑና የሚጐዳቸውን መጠጥ ከቤታቸው በር እንኳን እንዳያደርሱት እለምናቸዋለሁ ።

ወይታ ለማን ነው፤ኃዘን ለማን ነው፤ ፀብ ለማን ነው ጨኸት ለማን ነው፤ ያለ ምክንያት መቍሰል ለማን ነው የዓይን ቀላት ለማን ነው።ጠጅ በመጠጣት ለሚዘገዩ አይደለም።የወይንን ጠጅ ይፈትኑ ዘንድ ለሚ...... ። ወደ ጠጅ አትመልከት በቀላ ጊዜ መልኩም በብርሌ ባንጸበረቀ ጊዜ ኢያጻፈጠም ይገባል ። ከጠጡት በኋላ እንደባብ ይነድፋልና እንደ ጉበናም መርዙን ያፈሳል ዓይኖችኽ አመንዝሮችን ያያሉ ልብኽም ጠማማ ነገር ይናገራል ። በባሕር ውሥጥም እንደ ተኛ ትሆናለኽ እንዳንቀላፋም በምሰሶ ላይ ። ትላለኽም መቱኝ ያውም አልተሰማኝም ጐተቱኝ አላወቅሁምም ። መቼ እነሣለሁ ደግሞ አብዝቼ እሻታለሁ ።

መጽሐፈ ምሳሌ ም ፳፫ ቍ ፳፱—፴፭ ።

መበላለጥ (ኮንኩራንስ) ።

አንድ ሠራተኛ ሥራ አስተካክሎ የሚአውቅ ቢገኝ እንዲ ደግሞ ሥራ መሥራት አይችልም ።

ግን ሠራተኛውን ከርሱ የበለጠ ትርፍ እንዳያገኝ በብዙ ጭቅጭቅና በነገር ሥራውን ቢያስፈታው ምን ይጠቀማል ባልንጀራውንና ራሱን ይጎዳል እንጂ ጥቅም አያገኝም ።

ግን ባልንጀራው የሆነውን ሥራ ሁሉ ለመሥራት የሚችል ቢሆን እርሱ በትጋቱና በትምሕርቱ በለጠኝ እኔም በትጋት ሆኜ ብማር ያንጊዜ እንደርሱ እሆናለሁ ወይም እበልጣለሁ ብሎ በመጣጣር ባልንጀራው ወደ ደረሰበት ደርሶ የበለጠ ሥራ ቢሠራ በለጠ ይባላል ።

ብዙ ሰዎች ሥራ ለሚያውቁና ለሚሠሩ እንደነርሱ ለመሆን ስለመጣጣር ፈንታ እነዚያ የሚችሉት እንዳይሠሩ ለሥራም እንዳይረዱቸው በሥራቸው ሁሉ መሰናክል እያበጁ ከሥራ የሚያግዱ ሰዎች አይጠፉም ።

እንዲህ የሚያደርጉ ሰዎች የእውራንን ዓይን ለማብራት የማይችሉ ፈሪሳውያን የእውራንን ዓይን ያበራ ክርስቶስን እንደ ተቃወሙት ይመስላሉ ።

አሁንም ሥራ ለመሥራት የሚችሉትን ሰዎች በሥራ እንምሰላቸው እንብለጣቸው እንጂ ሥራቸው እንዲፈርስ አንጣጣር ።

በደብዳቤ የመጣልን ቃል ።

ይህ ጋሴጣ እንደምናየው ብርሃንና ሰላም ተብሎ ተጠርቷል፤ ከብዙ ዘመን በፊት ባገራችን ብርሃን ቢወጣ እንዴት ያለ ሰላም ይሆንልን ነበር የሚል ተሥፋ ስለ ነበረኝ ስሙን ስሰማ ብልቤ ተኝቶ የነበረ ተስፋ ተንቀሳቀሰብኝ ። ብርሃን ማለት ሁላችን እንደምናውቅ ክፉውንና መልካሙን የሚጎዳህንና የሚጠቅምህን ለይተህ እንድታይ የሚገልጽልህ ከሁሉ የሚበልጥ ስጦታ ነው ። ይኸንንም ለይተህ ለማየት የማትችልበት ጊዜ ሌሊት ነው ። በሌሊት በጨለማ ወዳንተ የሚመጣብህን ነገር አታውቅምና የሚጎዳህ ሲመጣ የሚጠቅምህ ይምስልሀል። የሚጠቅምህ ሲመጣም የሚጎዳህ የመጣ ይመስልሃል ። ዳግመኛ የሆነ ይሁንና ሰው በበረሃ በጨለማ ተቀምጦ ሳለ የሚገዛው ፍርሃትና ጥርጣሬ ነው እንጂ ሰላም አጠገቡ ልያርፍ ከቶ አይችልም ።

ብርሃን ማለት እውቀት መሆኑን ሁላችን እናውቀዋለን ሰሎሞን በመክብቡ "ብርሃን ከጨለማ እንዲበልጥ እንዲሁም ጥበብ ከድንቁርና እንድትበልጥ ለይቼ አወቅሁ" ይላል። ስለዚህ የእውቀት በረከት ከሁሉ ከፍ ያለ መሆኑን የሚመሰክርልን ሠጽሐፍ ልክ የለውም ። ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ብርሃንና ሰላም ስለሚመኙልንና እንድናገኘው ሰለሚደክሙልን ለልዕልናቸው የተገባ ምሥጋና እያቀረብሁ ዕድሜ እንዲሰጣቸውና የልባቸውን ሐሳብ እንዲያስፈጽማቸው እለምናለሁ ።

ተወልደ ብርሃን መድኅን ።

በቴሌግራም የመጣ ወሬ
የኢጣሊያ መንግሥት ሌጋሲዮን ።

አዲስ አበባ ፴፩ ዲሴምበር ፲፱፻፳፬ የ፳፱ ዲሴምበር

የለት ወሬ ።

ጀኖአ ። የልደት ቀን ሌሊቱን ሌቦች አንድ የንግድ ባንክ የሚባል ባንክ ቆፍረው ገብተው ብዙ ገንዘብና ብዙ እንቍ ወሰዱ ።

ባሬ ። ባንድ መርከብ የአልባንያ ጠቅላይ ሚኒስትር ፋኖሊ ሚኒስትሮችና መኳንንቶች ሹማምንቶች ወደ ባሬ መጡ ።

ትሪኤስት ። ዛሬ በሞንፋልኰና አዲስ የሞተር መርከብ መሄድ ጀመረ ።

አቴን ። የግሪክ መንግሥት በቡልጋሪያ ስለሚኖሩ ግሪኮች የቡልጋሪያ መንግሥት ደምብ አጕደለባቸው ብሎ ያቀረበውን ጩኸት የመንግሥታት ማኅበር እንዲቆርጥለት ይለምናል ።

እስፔዚያ ። ሊዮናርዶ ደ ቢንቺ የሚባል አዲስ የተሠራ ትልቅ መርከብ ዛሬ መሄድ ጀመረ ።

ሮማ ። በፓርላሜንት የአዲስ ዴፑቴዎች መሾም ነገር ምክር ተይዟል። በፓርላሜንት ከንግዴህ ወዲህ የዴፑቴዎች ቁጥር ፫፻፰ ነው ።

ቶኪዮ ። በአታሮ መርከብ መቆሚያ መርከብ ሲራገፍ ፳፭ ሳጥን ድናሚት ፈንድቶ ፱ ሰው ሞቶ ፫፻ ሰዎች ቆሰሉ ። በዚያም በመርከቡ መቆሚያ የነበረ ቤት ተቃጠለ ።

አዲስ አበባ ፫ ዣንቢዬ ፲፱፻፳፭ ።

የ፴፩ ዲሴምበር ። (ታሕሣሥ) ፲፱፻፳፬ ።

የለት ወሬ ።

ቤልግራድ ። ትላንት ቲራና ስኵታሪን ያዙ ። ከስድስት መቶ በቡራምትስር የሚታዘዙ እነሱም በፋኖሊ ሠራዊት በከፉና አገር የተከበቡ ሰዎች በተቀር አልባኒ ሁላቸው ከገር ወጥተዋል ።

በርሊን ። ከኢጣልያ ጋራ የንግድ ውል የሚዋዋሉ የጀርመን መልእክተኞች ከበርሊን በጃንቢዬ (ጥር) ፩ ቀን ይነሣሉ ። በጀንቢዬ ፫ ቀን ወደ ሮማ ገብተው እንደገና የውሉን ነገር ይጀምራሉ ።

ምንዛሬ ።

ፓሪ	፩	ብር	፲፫	ፍራንክ	፳፭	ሳንቲ
ጂቡቲ	፩	,,	፲፫	,,	፳	,,
አስመራ	፩	,,	፲፯	ሊሬ	፺	,,

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና እንደራሴ ተፈሪ መኰንን ላገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሊሆኑ ያሳተሙዋቸው በማተሚያ ቤታቸውም የሚሸጡ መጻሕፍት የሚከተሉ ናቸው

የቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ተግሣጽ ንባቡ እስከ ትርጓሜው	፲፪ ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ እስከ ትርጓሜው ።	፲፪ ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ እስከ ትርጓሜው ።	፲ ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሲራክ ንባቡ እስከ ትርጓሜው ።	፯ ብር
ውዳሴ ማርያም ንባቡ እስከ ትርጓሜው ።	፫ ብር
መጽሐፈ ሲራክ ንባቡ እስከ ትርጓሜው ። . . .	፫ ብር
የሕይወት ታሪክ ።	፪ ብር ተኩል
የቊጥር ትምሕርት ።	፩ ብር
ያማሪኛ ሰዋሰው ።	፩ ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር ።	፩ ብር
የብዙ መኳንንቶች ሥዕል ያለበት ክርት ፖስታል ፳፬	፩ ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የአደን መንገዳቸው አኳኋን ።	አላድ
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ ፣	አላድ
አጭር የዓለም ታሪክ ።	አላድ
ያማርኛ ፊደል ።	ሩብ
አሳብና ምኞት ።	ሩብ
የበገና ግጥም ።	፪ መ
ለኢትዮጵያ ልጆች ማመልከቻ ።	፪ መ
የምክር ቃል ።	፪ መ
የልብ አሳብ ግጥም ።	፩ መ

ስሙን በደብዳቤ ወረቀትና በእንቬሎፕ በካርት ብዚትም ለማሳተም ። ወይም የሠርግ መጥሪ ለሌላ ድግሥም መጥሪ ሊያሳትም ደብተርም ሊያሠራ የሚፈልግ ። በፈረንጅ ቋንቋም በዓረብና በግሪክም ሆነ በማሪኛም እንደፈለገው ዓይነት ይታተምለታል ። ቀለምና ጌጥ ያለው ኅረግ ስእል ዋጋውን እየከፈለ ይሠራለታል ።

መጽሐፍ አሳትማለሁ ያለ ሰው ድሀ ቢሆን ጥሩ ሐሳብ ያለው የሚጠቅም መጽሐፍ ካወጣ ። መጽሐፉ ያለዋጋ ታትሞለት መጽሐፉ እየተሸጠ ዋጋው ለማተሚያ ቤት ይገባል ። ጻፊውም ደግሞ ከጻፈው መጽሐፍ ልዑል የኢ መ አ ወራሽና እንደራሴ ተ መ የፈቀዱለትን ያሀል ጉርሻ ይቀበላል ።

መጽሐፍ የጻፈ ሰው የማኅተሙን ዋጋ ከፍሎ ለማሳተም የሚችል ከሆነ ግን የሥራውና የወረቀቱ ታስቦ ዋጋውን ከፍሎ ይታተምለታል ። የሚጠረዝ መጽሐፍ ወይም ደብተር ያለው ዋጋውን እየከፈለ እንደፈለገው እንጠርዝለታለን ።

የአዲስ አበባ ገባያ አኳኋን ባለፈው ሳምንት ።

		በብር	ቁና
ነጭ ስንዴ	.. ..	፩	፱
ጥቁር ስንዴ	.. ..	፩	፲
ነጭ ጤፍ	.. ..	፩	፯
ጥቁር ጤፍ	.. ..	፩	፯
ገብስ	.. ..	፩	፲፬
ሽንብራ	.. ..	፩	፲
ባቄላ	.. ..	፩	፲
አተር	.. ..	፩	፲

የአዲስ አበባ ገባያ አኳኋን ባለፈ ሳምንት ።

		በብር	በመሐልቅ	ልክ
ቡና	.. ..	፰		፩ፈረሱላ
መግዝ	.. ..		፩	፲፪በቁጥር
ሎሚ	.. ..		፩	፲፭በቁጥር
ትርንጎ	.. ..		፩	፭በቁጥር
ድንች	.. ..		፩	በትንሽ እርቦ
ሽንኩርት	.. ..	፪		፩ ትልቅ ስልቻ
ኮረሪማ	.. ..		፩	፴፪በቁጥር
ዝንጅብል	.. ..		፩	፴ በቁጥር
አዝሙድ	.. ..		፩	፫ ኩባያ
አብሽ	.. ..		፩	፬ ኩባያ
ሰናፍጭ	.. ..		፩	፬ ኩባያ
የጎመን ዘር	.. ..		፩	፫ ኩባያ
ድንብላል	.. ..		፩	፯ ኩባ
ጌሾ	.. ..	፪	፬	፩ ያህያ ጭነት
ዛላ በርበሬ	.. ..	፫		፩ ኬሻ
ውቅጥበርበሬ	.. ..	፩		፳፪ ኩባያ
ማር	.. ..	፯		፩ ጉንዶ
ቅቤ	.. ..	፪		፩ እገልግል
የወለዬ ቅቤ	.. ..		፩	፩ እንክብል
ቅባኑግ	.. ..	፩		፪ ጠርሙዝ
እንቁላል	.. ..		፩	፲፪ በቁጥር
ወተት	.. ..	፩		፲፬ ጠርሙዝ
የዝሆን ጥርስ	.. ..	፻፹		፩ ፈረሱላ
የበሬ ቆዳ	.. ..	፪	፰	፩ ፈረሱላ
እንጋሬ	.. ..	፲		፩ ኮረጃ
ሰም	.. ..	፲		፩ ፈረሱላ
ጥጥ	.. ..	፩		፻፹ ወቄት
አሸበ	.. ..	፩		፲፬ ኩባያ
አቡጀዲድ	.. ..	፪		
ሻማ	.. ..	፩		፴፪ በቁጥር
ሳሙና የልብስ	.. ..	፩		፲፫ በቁጥር
ሳሙና የገላ	.. ..	፩		፲፯ በቁጥር
ዕጣን	.. ..	፯		፩ ፈረሱላ
ቁንዶ በርበሬ	.. ..	፪		፩ ፈረሱላ
ጋዝ	.. ..	፬		፩ ቆርቆሮ
ሚካ	.. ..	፩		፭ ቱባ
አሞሌ ጨው	.. ..	፩		፬ በቁጥር
በሬ ፍሪዳ	.. ..	፲፱		
ላም የወተት	.. ..	፱		
ላም መሲና	.. ..	፳		
በግ ሙክት	.. ..	፬		
በግ መሲና	.. ..	፪		
በግ ጠቦት	.. ..	፩	፬	
ፍየል ሙክት	.. ..	፭		
ፍየል ወጠጤ	.. ..	፩	፰	
ስምንት ደሮ ቢካካ	.. ..	፩		
ፈረስ ማስፈያ	.. ..	፵፭		
ፈረስ መጠናኛ	.. ..	፳፫		
በቅሎ ማስፈያ	.. ..	፶		
በቅሎ አጋሰስ	.. ..	፲፯		
አህያ	.. ..	፬		

በልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና እንደራሴ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

መጀመሪያ ዓመት ፤ ቍጥር ፫ ።
1^{re} ANNÉE №. 3

ሐሙስ ጥር ፯ ቀን ፤ ፲፱፻፲፯ ዓ ምሕረት ።
JEUDI 15 JANVIER 1925

ብርሃንና ሰላም
LUMIÈRE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፰ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፲ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፬ መሐልቅ ይሸጣል ።

የጋዜጣው ዲሬክተር ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የራሱን ጉዳይ የሚያሳትም ሰው ዋጋውን እየከፈለ እናትምለታለን ።

ስለ ክርስቶስ ልደት የበዓል አከባበር ።

ባለፈው ሳምንት ታሕሣሥ ፳፱ ቀን ፤ ሌሊቱ ተፈጽሞ ጎሕ ሲቀድ ስለ በዓሉ ደስታ በቤተ መንግሥት የመድፍ ነጕዳ ተሰማ፡ነጋሪትም ይጐሸም ጀመረ።

ይኸም ሲሆን በየአድባራቱ ካህናቱም ሕዝቡም ሲዘምሩና ሲያመሠግኑ አድረው ነበርና መድፉ ከተተኰሰ በኋላ ግን በትልቅ ደስታ ሁሉም በየቤታቸው ሔዱ።

በቤተ መንግሥት ለመኳንንትና ለወታደር ስለ በዓለ ልደት ክብር ትልቅ ግብር ተደርጎ ነበርና መኳንንትና ወታደር በፍቅርና በደስታ ተሰብስበው በየማዕርጋቸው እየተቀመጡ ግብር ሲበሉ ዋሉ ። ግብር ምላሽም በሆነ ጊዜ መኳንንት ሁሉ በብዙ ወታደር ታጅበው በየቤታቸው ሔዱ. ለወታደሮቻቸውም ግብር አድርገው የበዓሉን ደስታ ፈጸሙ ።

ዱሮ በቀድሞ ዘመን በእንደዚህ ያለው ትልቅ በዓል አንዳንድ ሞኝ ሰዎች ያለልክ በልተው ጠጥተው ይሰክሩ ነበር ። ከሰከሩም የተነሣ ጠብ ይነሣና በከተማው ውስጥ አምባጓር ይበዛ ነበር ።

ዘንድሮ ግን በትልቁ የልደት በዓል መብሉና መጠጡ ብዙ ሲሆን ስካር አልገነነም አምባጓር አልተሰማም ። በአገራችን ውስጥ እንደዚህ የመሰለ ነገር እየባከነ እንዲጠፋና ትምርት ሰልጥኖ ብርሃንና ሰላም እንዲሆን ሙሉ ተስፋ አለን።

ስለዚህ ሕዝባችን ልኩን መጠበቅና ጉዳት የሚሆነውን ነገር ማወቅ እንደ ጀመረ ያስረዳል ። የከተማ ጠባቂዎችም ከዱሮው ይልቅ እየተሻሉ መሔዳቸውን ስለ ልደት በዓል ደስታ በደመቀ የጨረቃ ብርሃን ሽርሽር የሚሉ ሰዎች ያለ ስጋት መመላለሳቸው ይመሠክራል ።

በዚህም ቀን የሚያሸበርቅ ሰስት መልክ ያላት የኢትዮጵያ ሰንደቅአላማ በትልቁ ግቢና በሌላውም ቦታ ሁሉ ተሰቅላ ደስታዋን ትገልጽ ነበረች ።

እሷም የመንግሥታችን ጽናትና የነፃነታችን ምስክርናትና በመላው ኢትዮጵያ የልደት በዓል ትልቅ ደስታዋ እንደሆነ መሰከረች ።

ታሕሣሥ ፴ቀን የአውሮጳ መንግሥታት ሌጋሲዮኖችና ክቡራን ሰዎች ከትልልቆች መኳንንቶች ጋራ ስለ በዓለ ልደት ደስታ ለግብር ተጠርተው በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ፊት የደስታ ምሳ አደረጉ ።

የልደት በዓል በኢትዮጵያ እጅግ የከበረ ነው ፡ የደስታውም ጨዋታ ከሌሎች አገሮች ፈጽሞ የተለየ ነው በሌሎች አገሮች የልደትን በዓል ሲያከብሩ ጌታም ቢሆን ፡ ድኃም ቢሆን የገና ዛፍ ከሚባለው ከትልቁ ዛፍ አንዱን ክንፍ ቆርጠ አምጥቶ በየክንፉ ላይ ልዩ ልዩ ጌጥ ያስጌጠዋል ። ትንንሽም የመጨዋቻ ዕቃ ያንጠለጥልበታል ።

ከዚህም በኋላ በልደት በዓል ጢት በማለዳ ትንንሾች ልጆች ሁሉ ሴቶችም ወንዶች ልጆች የልጅ ልጆችም ይሰበሰቡና ያንን የገና ዛፍ ከበው ይቆሙና ባለቤቶች ያንን በዛፍ ላይ የተንጠለጠለውን ጌጥ ሁሉ ያከፋፍሏቸዋል ።

ይህም የገና ዛፍ የሚባለው የጥድ ዛፍ ነው ። በኢትዮጵያ ግን የልደትን በዓል ለማክበር ሳይነጋ በማለዳ ሕዝቡ ሁሉ ወንዱም ሴቱም ሕፃናቱም ወደ ቤተ ክርስቲያን ይሔዳሉ ። ከቅዳሴም በኋላ በየቤታቸው ሔደው የበዓል ምግብ ተመግበው ጥቂት አርፈው የገና ጨዋታ ለመጨዋወት ይወጣሉ ። ይህንንም ጨዋታ ተጨዋቾቹ ከሁለት ተከፍለው እሩር ወይም ጥንግ የሚባለውን ኳስ በበትር እየመቱ ይጨዋወታሉ እሩሩን ወደ አንድ ወገን ያገቡ ሰዎች እንደ አሸናፊ ሆነው እየጨፈሩ ይጫወታሉ ።

ይህንኑም ምንም በመጽሐፍ ተጽፎ ባናገኘው አባቶቻችን ቃል ለቃል ሲነግሩን በዕለተ ልደት እረኞች በቤተ ልሔም አውራጃ መንጎቻቸውን ሲጠብቁ መልአክ እግዚአብሔር ተገልጦ የዓለም መድኃኒት ተወልዶላችኋል ብሎ ስፍራውንና

ምልክቱን በነገሩቸው ጊዜ ለማየት ሔደው ጌታችንን ከእናቱ ከድንግል ማርያም ጋራ ዓይተው ሲመለሱ ከደስታቸው ብዛት የተነሣ ይህን የመሰለ ጨዋታ ተጫውተው ነበረና ያንን ለማሳሰብ ነው ይሉናል ።

ይህንም ጨዋታ በኢትዮጵያ ብቀድሞ ዘመን ነገሥታቱ ሳይቀሩ ይጫወቱት ነበረ ይባላል ። የሚጀመረውም በዓለ ልደት ሳይደርስ የታኅሣሥ ወር ሲገባ ነው ። ከሰባት ዓመት በላይ የሆኑ ልጆች ሁሉ ከታኅሣሥ ወር መግቢያ ጀምረው ይህን ጨዋታ ለመጫወት በጣም ይተጋሉ ።

በመርሀቤቴ ቆፍና በሚባል ሀገር ታቦቱ አማኑኤል ነውና የገና ዕለት ታቦት ወጥቶ ካህናቱ ሲዘምሩ ቀዳሹ ቄስ መጀመሯ እሩሩን ባርኮ ለተጫዋቾች ይሰጣቸዋል ይባላል ።

ጃንሆይ ዳግማዊ ምኒልክም ይህንኑ የገና ጨዋታ ለማክበር ሲሉ የልደት እለት በጧት የሥጋ ቤቱ የሻለቃ እሩርና መለጊያውን በትር አምጥቶ ሲሰጣቸው ተቀብለው እሩሩን መጀመሪያ ይለጉት ነበረ ። ከዚያም በኋላ የግቢው አሽከሮች ሁሉ ተቀብለው ወደመጫዋቻቸው ወደሰፊው ሜዳ ሔደው ሲጫወቱ ይውሉ ነበረ ።

አሁንም የልደት ዕለት በዚያው ልማድ የሥጋ ቤቱ የሻለቃ እሩሩን ከነመለጊያው አምጥቶ ለልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን እንደ ተለመደው ሰጣቸው ። አሽከሮችም ተቀብለው ሔደው በየሜዳው ሲጫወቱ ዋሉ ።

በአዲስ አበባ ከተማ ስፍራው ስለጠበበ የከተማው ልጆች በየመንገዱ ዳር የገና ጨዋታ ሲጫፉቱ ዋሉ ። ጨዋታውንም ለማየት ብዙ ሰዎች ተሰብስበው ነበር ።

በልዑል አልጋ ወራሽ ቤት የልደት በዓል አከባበር ።

ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንንና ልዕልት ወይዘሮ መነን ይህን የልደት በዓል ለማክበር በአዲስ አበባ በየሌጋሲዮኑና በከተማ የሚኖሩትን ትልልቆቹን የውጭ አገሮች መኳንንቶችና ወይዛዝሮች ፡ ትንንሾቹንም ልጆች ጠርተው ነበረ ። ከኢትዮጵያም መኳንንት ብዙዎች ተጠርተው ነበረ ። ልዕልት ወይዘሮ መነንም ብዙ የውጭ አገር መኳንንቶችንና ወይዛዝሮችን ለልደት በዓል መጥራታቸውን ስለ አወቁ እንደ አውሮጳ ልማድ የጥድ ዛፍ ትልቁን ክንፍ አስመጥተው በልዩ ልዩ በሚያብረቀርቅ ነገር አስጊጠው በትልቁ አዳራሽ እንዲቆም አዘው ነበረ ። በየጥዱም ክንፍ የሻምዓ መብራት ተንጠልጥሎበት ነበረ ።

ቀኑን ሙሉ የልዑል አልጋ ወራሽ ልጆችና ከውጭ ያመጡ የመኳንንቶ ልጆች ያንን የቆመውን የጥድ ዛፍና ጌጡን በማየት ታላቅ ደስታ አድርገው ዋሉ ። ወደ ማታ ግን ለልደት በዓል የተጠሩት የውጭ አገር መኳንንቶችና ወይዛዝሮች ፡ ልጆችም ተሰብስበው መጡ ። ቁጥራቸውም እስከ ሰማኒያ ይሆናል ። ከነዚህም ጋራ ብዙ የኢትዮጵያ መኳንንት ነበሩ ። እነዚህም የልደትን በዓል ከልዑል አልጋ ወራሽና ከልዕልት ወይዘሮ መነን ጋራ ለማክበር የመጡ የውጭ አገሮች መኳንንቶችና ወይዛዝሮች ይህን የጥዱን ዛፍ አምሮ አጊጦ ፡ ከመብራቱ ጋራ ሲያንፀበርቅ ባዩት ጊዜ እንደ ኤውሮጳ ልማድ ትክክል በመሆኑ እጅግ አደነቁ ። ከዚህም በኋላ ልዑል አልጋ ወራሽና ልዕልት ወይዘሮ መነን በዚያ ለተሰበሰቡት ልጆች ሁሉ ልዩ ልዩ የሆነ የወርቅና የሌላም ዓይነት ጌጥና መጫዎቻ ሰጡ ።

ደግሞ ልዑል አልጋ ወራሽ ከኢየሩሳሌም ያመጡዋቸው አባት እናታቸው የሞቱባቸው አርባ የሚሆኑ የአርመን ልጆች ጥሩምባና ሙዚቃ እየመቱ ተጫወቱ ።

የበዓሉም ደስታ ከተደረገ በኋላ የተጠሩት እንግዶች ሁሉ በየቤታቸው ሔዱ ።

የልደት በዓል በደስታ ስለተፈጸመልን እግዚአብሔርን እናመሠግናለን ።

ባለፈው ሳምንት ጥር ፩ቀን ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን በአቃቂ አጠገብ በፉሪ ሜዳ የተዘራው ጤፍ ሲታጨድ ለማየት ሔደው ነበር ።

በሥራውም ላይ የዋለው ሠራዊት እጅግ ብዙ ነበር ።

መንግሥትም የእርሻን ጥቅም ማሳየቱ የሕዝቡን ልቡና ለማነቃቃትና ጀማሪ ለመሆን እንደሆነ የተረገጠ ነገር ነው

በኢትዮጵያ ከጥንት ጀምሮ ሣር አጨዳና እህል አጨዳ በሆነ ጊዜ እንጨት ቆረጣና ድንጋይም ማጋዝ በሆነ ጊዜ ነገሥታቱ ሥራውን ለማክበርና ሠራተኞቹን ደስ ለማሰኘት ወደ ሥራው እየሔዱ ያያሉ ሠራዊቱም ጃንሆይ ያዩኛል እያለ ደስ ብሎት ይሠራል ብዙ ቀን የሚያቆየውም ሥራ በፍጥነት ያልቃል ። ይኸውም ዘወትር ቢደረግ የሕዝቡን ስም በምስጋና የሚያስጠራ ላገራችንም ትልቅ ጥቅም የሚሆን ነገር ነው ።

አሁን በጥር የተጀመረው የሠራዊት አብሮ መሥራት ወደፊት በሙሉ ፈቃድና ትጋት እየሰፋና እየተፈጸመ እንዲሔድ ተስፋ እያደረግን ለሥራ እንትጋ እንላለን ።

እንደ ምሳሌ ከሥራ በኋላ ዕረፍት ይጣፍጣል ወግም ደስ ያሰኛል ይላል ።

ሥራ አይወዱም ተብለን እንዳንታማ ሥራን በጣም እንውደድ ።

ከውጭ አገር የመጣ ወሬ ።

የሞንቲቸሎ አገር ክፍል በዮዋ አውራጃ አሜሪክ በሰሜን በኩል በመጡ ቁጥር በሌላቸው በተራቡ ውሾች ወራሪነት ምክንያት ሕዝቡ ደንግጠዋል ።

እጅግ የተለየ የዚህ ወራሪነት አላፊ ውሾችን የሚያረብ ሰው ነው ። ስለምን ብትሉ እነዚህን ውሾች በዱር ውስጥ እንዲረቡ ስለ ተዋቸው የሚጠብቃቸውም ስለሌለ ተመልሰው እንደ አራዊት ሆነዋልና ትልቅ ጉዳት ጎድተዋል ።

እነሱም ለማጥፋት ለሚረዱዋቸው ሰዎች ገንዘብ ይሰጣሉ የሚል ጋዜጣ አገኘን ።

በከተማ ውስጥ ባለቤት የሌላቸው በየአደባባዩ ሲዞሩ የሚውሉ ብዙ ውሾች አሉ ። ይኸም ብቻ አይደለም እከክ የያዛቸው የሚያጸይፉ በሽታ ያደረባቸው ያበዱ ውሾች በከተማው ውስጥ ስለበዙ ትልቅ ጉዳት እንዲያመጡ ጥርጥር የለበትም ። እነዚህንም ውሾች አለማጥፋት እጥፍ ጉዳት ነው ።

ጀመሪያ በበሽታና በራብ ሲሳቀይ እንስሳውን ዝም ብሎ ት አይገባም ።

፪ኛም በውሾቹ ምክንያት በሕዝብ ላይ በሽታ ይመጣልና ሊያስፈራ ነው ። በእንደዚህ ያለ በሽታ ሰው ታሞ ቢሞት ትልቅ ጉዳታችን ነው ።

ግን እንደዚህ ያሉ ውሾች ከከተማችን እንዲጠፉ ክቡር ከንቲባ ነሲቡና ዲሬክተሩ ነጋድራስ አስታጥቄ ሊያስቡበት እንዲገቡቸው እናምናለን ።

ይህንንም በቶሎ የፈጸሙት እንደሆነ ለከተማችን አንዱን ወገን ጉዳቱን አራቁለት ማለት ነው ።

ፈያማ የተባለ አንድ ብልህ የኢጣልያ ሰው እጅግ የሚያስደንቅ ብልሃት አግኝቷል ።ያገኘውም ብልሃት ያለ አንዳች ሽቦ ወይም ሌላ የሚታይ መገናኛ ሳይኖረው በሩቅ ያለውን መርከብ በውስጡ ሰው ሳይኖርበት በራድዮ ኃይል እንዲሔድ ማድረግ ነው ።

ይህ ድንቅ የሆነ ተአምራት የሚደረገው በሁለት መኪና ነው ።

አንዱ መኪና በመርከቡ ላይ ነው ።ሁለተኛ መኪና ደግሞ በባሕሩ ጠረፍ ላይ ነው ።ሰውየው በጠረፍ ያለውን መኪና ቁም በሚል መደቅደቂያ የነካው እንደሆነ መርከቡ ይቆማል ።ወደግራ በሚል መደቅደቂያ የነካው እንደሆነ ወደ ግራ ይሔዳል ። ወደ ቀኝ በሚል መደቅደቂያ የነካው እንደሆነ ወደ ቀኝ ልክ እንደ ትእዛዙ ይሔዳል ።የፈያማ አዲሱ ብልሃት ፈጽሞ ሲሰናዳ ለብዙ ጥቅም ይሆናል ከሚል ጋዜጣ መጣልን ።

በደብዳቤ የመጣ ቃል ።

ይድረስ ከክቡር አቶ ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ የልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ዲሬክተር ።የከበረ ሰላምታ ለርስዎ ይሁን ፤

ብርሃንና ሰላም ጋዜታ አሳትማለሁና የምትገዛ እንደሆነ በየሳምንቱ ሐሙስ ይወጣል ዋጋውም ባመት አምስት ብር ነውና አስታውቀን ብለው ስለላኩብኝ የተጻፈውንም የጋዜታውን ዓይነት አየሁት አዠማመሩም እጅግ መልከም ነው በሀገራችን እየተጀመረ የቀረ ሥራ ብዙ ነውና አሁንም ይህ የጋዜታ ሥራ ተዠምሮ እንዳይቀር እግዚአብሔር ብርታቱን ይስጥዎ ሀገር በጋዜታ መታተም እንዲሰለጥን የታወቀ ነው ።አሁንም ስለ ሀገራችን ስለ ኢትዮጵያ ዋና የሚያስመሰግን እርዳታ ነው ። እኔም እርስዎ ያሉበትን የማተሚያ ቤት ሥራ እንዳየሁት የሥራው መከናወን እጅግ የሚመሰገን ስለሆነ ይህም የብርሃንና ሰላም መታተም እየበረታ መሔዱን እረዳዋለሁ ።ለወደፊቱም እኔም የሚታሰበኝን በጋዜታ የሚታተም ቃል እየጻፍኩ እልክልዎታለሁ ። ይልቁንም የልዑል አልጋ ወራሽን ማተሚያ ቤት ያስወደደውና ያስመሰገነው የሥራው ጥራትና የመጻሕፍቱን ዋጋ ገንዘብም የሌለው ሰው ለመግዛት እንዲቻለው ዋጋውን ያለማብዛትዎ ነው ፤ሰላምና ጤና ለርሰዎ ይሁን ፤ታሕሣሥ ፳፱ ቀን ፲፱፻፲፯ ፤ዓ ም

አስታጥቄ ኀብተ ወልድ ።

ለክቡር አቶ ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት የብርሃንና የሰላም ጋዜታ ዲሬክተር፤ሰላም ለርስዎ ይሁን ።

የኢትዮጵያ ልጆች ከአያሌ ሺ ዓመታት ዠምረው በእምልክተ እግዚአብሔር ጽንተው ስለ ሀገራቸውና ስለ ክርስቲያን ሃይማኖት ደማቸውን በማፍሰስ ከባቶቻቸው እየተቀበሉ በመካከላቸው ልዩነት ሳይኖር በመተባበር የጀግንነት ሥራቸውን ሲያሳዩ እስከዚህ ዘመን ደረሱ ለወደፊትም የሥልጣኔና የጥበብ ስጦታ ከመንፈሳቸው እየፈለቀ መምሕር በማጣት ከጓደኞቻቸው ወደኋላ ዝግ እያሉ የሔዱ የኢዮጵያ ልጆች በክሂዳቸው የወንጌልን ትምርት የሚያከብሩ ።ኢየሱስ ክርስቶስን በማወቅ ብርሃን የሚመላለሱ ናቸውና የዚህን ዓለም ጥበብ ወደማወቅ አቃንተው በሂሣብ ምንጭ ላይ ቆመው ይጓዛሉ ።ስለሆነ አለስንፍና እርስ በርሳቸው መበላለጥ ለማይሹ ለኢትዮጵያ ልጆች በፍቅርና በትህትና የሚሸቀዳደሙ ጠባቆቻቸው ከድንቁርና ጉድጓድ የሚነጥቁ ከለማወቅ ወደማወቅ የሚመሩ በመሆናቸው ሕዝባቸውን በትምርት ዜግነት መጐተት ይገባቸዋል ።

እንደዚሁ ወንጌል ወደዚህች ምድር ኢትዮጵያ በደረሰች ጊዜ የሆነውን ድክም አንድ ታሪክ ሲናገር አገኘሁ ።በቆስታንቲኖስ ዘመን አንድ አዋቂ ከጢሮስ አገር ስሙን ሜርጽዮስ የሚሉት በኤርትራ ባሕር ዞረ ።ባሕርንና ምድርን ሰዎችንም ብልሀታቸውንም ይመረምር ዘንድ ። ወደ ዳርቻም በመጣ ጊዜ በመርከቡ ያገር ሰዎች ቀማኞች ሆነው የመርከቡን ሰዎች ሁሉ ከሜርጽዮስ ጋራ ገደልዋቸው ።

ለሁለት ብላቴኖች ብቻ አዝነው ስማቸውን ፍሩሜንትዮስ ኤዴሲዮስ የሚሉት ፤ ሁለቱንም ወደ ንጉሥ አመጡዋቸው ንጉሡም ወደ ቤቱ ተቀበላቸው ኤዴሲዮስን አሳላፊ አደረገው ፍሩሜንትዮስም ጸሐፊ ሆነ ። ንጉሡም በሞተ ጊዜ ንግሥቲቱ ፍሩሜንትዮስ ልጇዋን ሐዜን ያሳድግ ዘንድ አመነችው ፤ ፍሩሜንትዮስም የሐዜ እንደራሴ እንደ ሆነ ይላሉ ።ፍሩሜንትዮስ የተቻለውን ያህል አደረገ የሃይማኖትን ዘር በኢትዮጵጵያ ይዘራ ዘንድ ከሌላ አገርም ለመጡ ነጋዶች ቤተ ክርስቲያንን አሠራ ።ክርሳቸውም ጋራ እግዚአብሔርን አመለከ ።ቄስ ግን አልተገኘም ነበር ። ንጉሡም በኋላ ሁለታቸውን ወዳገራቸው እንዲመለሱ አሰናበተ ኤዴሲዮስም ወደ ጢሮስ ሔደ ከዚያም ቄስ ሆነ ።ፍሩሜንትዮስ ግን በዚህ አገር ፍሬምናጦስ አባ ሰላማ የተባለ የኢትዮጵያ መንግሥት በክርስቶስ እስክትድን ድረስ ዕረፍት አልነበረውም ወደ እስክንድርያ ሄዶ ከዚያ አትናስዮስ ሊቀ ጳጳሳት ሁኖ ሳለ በ፫፻፳፯ ዓመተ ምሕረት ከአትናስዮስ ኤጲስ ቆጶስነትን ለመነ ።

አትናስዮስም ለኢትዮጵያ ከፍሩሜንትዮስ የሚሻል አይገኝም ብሏልና እርሱ ለዚች አገር ኤጲስ ቆጶስ ይሆን ዘንድ ቀደሰው ሾመው ። ቀሳውስትንና መነኮሳትን ባንድ ይዞ መጥቶ በኢትዮጵያ ወንጌልን አስተማረ ። እንዲሁም የቤተ ክርስቲያን ሥራ በኢትዮጵያ ተጀመረ ። በኋላም ቴዎፍሎስ መጣ ። እርሱም ህንዳዊ የአርዮስ ወገን ነበረ ። ቆስታንቲኖስ በኋላ የኒቅያ ወገን በኢትዮጵያ ያሳድድ ዘንድ የኢትዮጵያውን ንጉሥ ፍሩሜንትዮስን ወዶ እንዲሰደው ጌዎርግዮስ ሃይማኖቱን ይመረምር ዘንድ ጻፈለት ።

ነገር ግን አልሆነለትም ። በዩስቲኑስና በዩስቲኒያኑስ ዘመን የአይሁድ ንጉሥ ዙንዋስ የሚሉት በዓረብ አገር በየመን ክርስቲያንን አሳደደ ። የኢትዮጵያም ንጉሥ ይህነን ሰምቶ ወደ የመን ዘምቶ በዙንዋስ ጦርነት አደረገ፡፡እርሱንም ድል አድርጎ መንግሥቱን ወሰደ ። ክርስቲያንን አብርሃም የተባለውን እንገሡ ከዚያ ወዲያም አብርሃም ሲሞት ዙንዋስ ተመልሶ መንግሥቱን ወሰደ ክርስቲያንንም አሳደደ ። ከመገርመሪያው ጊዜ ይልቅ የኢትዮጵያ ንጉሥ ግን ሁለተኛ ተመልሶ ዙንዋስን ገደለው ሌላም መኰንን በዚያ አገር ላይ ሾመ ይላል ።

እንደዚህ ከጥንት ገምሮ እስከሁን ችሎት ያላት ሬሷን ለበዕድ አሳልፋ ያልሰጠች የኢትዮጵያ መንግሥት የልጆቿ አለመጣጣር ያስገርም የለምን ። የሆነ ሆኖ ምንም በንጉሡ ነገሥትነታቸው መልካቸውን ባላውቅ ዳግማዊ ምኒልክ ከቀናት ይልቅ እንደ ወንጌል የዕውቀትን የምሥራች ብቻቸውን አለ ረዳት በረቂቅነት ለኢትዮጵያ ለማብራትና ለማጽደቅ የደከሙ ናቸውና የማይረሳ ሐውልት ሊቀረጽላቸው ይገባል ። ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንንም ከአፍሪክ ተራራ ተነሥተው አውሮፓ ዘልቀው የወዳጅነትን ማሠሪያ ማጥበቃቸው ኢትዮጵያውያንን ወደ ዕውቀት ለመጥቀስ መሆኑን በማሰብ ከእንቅልፋችሁ መንቀሳቀስ ይገባችኋል ።

ከበዘንተኝነት ብዛት የተነሣ በመብልና በመጠጥ ተሸንፈን ብንኖር የሥጋ ጥቅማችንን እንጂ ዕረፍቷን ባንፈልግ ኢትዮጵያን የተቃለለች ማድረጋችን ነው ። ይቺም በዓይናችን ድንቅ ናት ታናሽ የምትመስለኝ አካሌኝ እርሷን ይልቅ ትፈልጋታለኝ እንደ ተባለ፡ለዚህ ሁሉ መጠቅለያው ኢትዮጵያ ዕውቀትን ለማግኘት እንድትደርስ የፍርድን ሚዛን ልዩ በሆነ አደራረግ ጠንክረው እንዲያነቡ ለጠበቆቻቸው የውነት መንፈሳቸውን መርማሪነት በዚህ ይቀሰቅስባቸዋል።

ደግሞ ማንም ሰው ቢሆን ፍርድ ማጉደሉ ድሀ መበደሉ ትምርትና ዕውቀት ከማጣቱ የተነሣ ነውና በኢትዮጵያ መንግሥታችን የትምህርት ቤት እንዲያቆሙልን ተስፋ እናድርጋለን፡፡ከዚህም በኋላ የጻድቅ ደስታ ፍርድ ማደረግ ነውና የከፉ ልማድን ከረፍታ የኢትዮጵያ ልጆች በትምህርትና በዕውቀት ሳያፈርሱት አይቀርም ።

አሁንም እግዚአብሔር በቸርነቱ ሀሳባቸውንና ምኞታቸውን ወደ ጥበብ እንዲስበው በውነት ፍርድ ለሕዝቡም እንዲሆንላቸው በፍጹም ልብ ሥልጣኔን እንዲፈልጓት ማድላት የሌለው አምላክ ባንድነት ያትጋቸው ጥቂት ዕውቀት ከብዙ ዕንቁ ትበልጣለች የሚሉ ሐዋርያችን ያልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንንም ስንፍናን ለማራቅ በብርቱ ጦርነት የመጋደል ጅግንነታቸው እያስደነቀኝ አመሠግናቸዋለሁ።

ለሰውነታችን እረፍትህ ሕግህ ።
ህማብህ ደፈጸም ደከናወንልህ ።
ጥበብን ለማስፋት ሆኖዋል ድካምህ ።
ዕድሜሁን ያርዝመው ሕይወቱን ይስጥህ
ፍቅር ደዞ ቆሚል ታላቁ ማርማህ ።
ሳመነህ ለሕዝብህ ተፈሪ አንተው ነህ ።
በፍቅር ተጋዳይ ባጂስ ከዳን ላሉ ።
የውነት ማሰሪያው ነው አደፈታም ወሉ
ራሳችን ከብደዋል ከወንጌል ነው ቃሉ
የማይጠፋ መብራት ያሳያል በሩቁ ።
እሱን ለሐበሻ የሰጠን መርቁ ።
አደልዎ የሌለው ላገሩ ነው ጭንቁ ።
በፊዚው ክርስቶስ ነው ከንቱ ተሳለቁ ።
እንሳደህስ እኛ እንልበስ ጸጥታ ።
ተፈሪ መኰንን ከሰጠን ዕርዳታ ።
ሠርቶ ያበላናል ሁሉንም በተርታ ።
ዕውቀት ታዘግማለች ከርሱ ተጠግታ ።
እንግር እንጠንክር ስንፍናን እንምታ
ለማደሪ ምድር ሁለቱ ከፍላት ።
ተፈሪ መኰንን የሐበሻ እናት ።
ያመሠግንሃል አውሮፖች በውነት ።
ደህን ጥሻ ጥሰህ አገር በማየት ።
ለሐገሩ ትጉ ጠንቃቃ በውቀት ።
ለድኃ ርኅራኄ ተፈሪ ሲሉት ።
ጎሕ አየን በርዛጡ ሲነጋ ጥቂት ።
ተልኮ የመጣ እንደ ነቢያት ።
ሐሳቡ ድካሙ በክርስቶስ ፊት።
ቆማ ስትፋረድ ላበሻ መንግሥት ።
አድባራት ለማቆም የገነት አትክልት ።
እንደህ ያስልፋት አላንድ ረዳት
ተስፋችን ጽኑ ነው ቆና መሠረት
ስጦታው ካምላኩ ከክርስቶስ ቤት
ምሥክር ልቡ ነው ለዚህ ምክንያት
መከራው ሐላፊ የለውም ጥልቀት ።
ዕድሜ ለጌታችን እንለምንለት ።
የሃበሻ ብርሃን ተፈሪ እንዳይሞት ።
ታሕሣሥ ፴ ቀን ፲፱፻፲፯ ዓ ም ።
አየለ ገዳ ።

በቴሌግራም የመጣ ወሬ
ከኢጣልያ መንግሥት ሌጋሲዮን ።

ኦስሎ ። ከ፲፮፻፳፬ እስከ ፲፱፻፳፬ ። ኦስሎ በተባለ ስም ታውቃ የነበረች ክሪስቲያንያ የምትባል ከተማ ወደ ፊት ኦስሎ ተብላ ትጠራለች ። ይህነንም ስም ከሺ ፵፯ እስከ ፲፮፻፳፬ የነበራት ስም ነው ። መለወጡም ከ፩ ጥር ጀምሮ ነው ። ይህነን አኳሆን የዋና ከተማው አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ደወል በመደወልና መድፍ በመተኰስ ተቀበሉት ።

ማስታወቂያ ።

በግማሽ ዋጋ የባቡሩን ወረቀት ለመቀበል ጥዋት የሚመጣ ሰው ከሌላ መንገደኛ ጋራ እየተደባለቀ ግፊያና ችግር ስላገኘው ለወደፊት ባቡር በደህና ያለችግር እንዲሳፈር ብለን ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ለሕዝብ ማስታወቂያ አድርገናል ።

ከዛሬ ቀን ጀምሮ ለወደፊት በግማሽ ዋጋ በባቡር በስስተኛ ማዕረግ እንዲሄድ ተብሎ ከኢትዮጵያ መንግሥት ስልጣን ካላቸው መኳንንቶች የፈቃድ ወረቀት የተቀበለ ሰው ሁሉ ባቡሩ ነገውን ሊሄድ አንድ ቀን አስቀድሞ ከማታው ከስምንት ሰዓት ተኩል ጀምሮ እስከ አስራ አንድ ሰዓት ድረስ የባቡሩን ዋጋ ይዞ ወዲያውም በባቡሩ በግማሽ ዋጋ ለመሄድ የሚፈቅድለትን ወረቀት ጨምሮ ከባቡሩ መቆሚያ መጥቶ ይህን ስራ ለሚሰራ ከኢትዮጵያ መንግሥት ከምድር ባቡር ተቆጣጣሪ እንዲቀበልና የተቀበለውን የባቡሩን ወረቀት በማግሥቱ ባቡር ለመሳፈር ሲመጣ እበሩ ላይ ለቆሙት ዘበኞች አሳይቶ እባቡሩ መቆሚያ በቀጥታ ገብቶ እንዲሳፈር እናስታውቃለን ፡ በመጀመርያና በሁለተኛ ማዕረግ የሚሄዱ ባለግማሽ ዋጋ ግን እንደልማዱ ጥዋት መጥተው የሚገባውን ከፍለው እባቡር እንዲሳፈሩ አድርገናል ።

ይህ ማስታወቂያ ከወጣ ቀን ጀምሮ ለወደፊት ባለግማሽ ዋጋ ተቀባይ እስኪአውቀው ድረስ ካንድ ወር በኋላ ይጸናል ይህ የተቆረጠው ቀን ካለፈ ወዲያ ግን በ፫ተኛ ማዕረግ የሚሄድ ሰው ጥዋት የመጣ እንደሆነ ሙሉ ዋጋ ይከፍላል እንጂ በግማሽ ዋጋ ለመሄድ አይችልም ፡ ጥዋትም ባቡሩ ሊሄድ አስር ደቂቃ ሲቀረው የተቆጣጣሪ መስሾ ቤት ይዘጋል ከዚያም በኋላ ምንም ወረቀት ሊሰጥ አይቻልም ።

ጥር ፩ቀን፲፱፻፲፯ ዓመተ ምሕረት ።

የኢትዮጵያና የፈረንሳዊ ኩፒንያ የምድር ባቡር ተቆጣጣሪ ።
መኰንን እንዳልካቸው ።

በልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

መጀመሪያ ዓመት ፡ ቍጥር ፬ ፡፡
1^re ANNÉE № 4

ሐሙስ ጥር ፲፬ ቀን ፡ ፲፱፻፲፯ ዓ ምሕረት ፡፡
JEUDI 22 JANVIER 1925

ብርሃንና ሰላም
LUMIÈRE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ፡፡

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ፡፡

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፫ ብር ፡፡ በውጭ አገር ባመት ፮ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ፡፡ በየሳምንቱ ሲገዛ ለፊስን በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ፡፡

የጋዜጣው ዲሬክተር ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ፡፡

የራሱን ጉዳይ የሚያሳትም ሰው ዋጋውን እየከፈለ እናትምለታለን ፡፡

ስለ በዓለ ጥምቀት አከባበር ፡፡

ከቀድሞ አባቶች ጀምሮ ባገራችን የጥምቀት በዓል ክብር ፪ቀን እንዲደረግ የተለመደ ነገር ነው መዠመሪው ቀን ከተራ ይባላል ፡፡ ከተራ የተባለበትም ምክንያት በዚህ ቀን መኳንንቱና ካህናቱ ወደወንዝ ወርደው ፈሳሹን ውሀ ባሕር እንዲሆን ከተረው በወንዙም ዳር ድንኳን ተክለው የሚያድሩ ስለሆነ ነው ይባላል ፡ በዚህም ልማድ በመላው ኢትዮጵያ ያሉ ታቦታት ወደ ወንዝ ወርደው ያድራሉ ፡፡ ይህም መደረጉ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሊጠመቅ ወደ ዮሐንስ እንደሄደ ለማሳሰብ ነው ፡ ጥር ፲ቀን ፲፱፻፲፯ ዓመተ ምሕረትም በአዲስ አበባ ዙሪያ ያሉ ቍጥራቸው ፲፯ የሚሆን ዋና ዋናዎቹ አድባራት እንደ ልማዱ በየአውራጃቸው ወዳለው ወንዝ እየወረዱ አድረው ነበር ፡፡

በዚሁም ቀን እሁድ በ፱ ሰዓት ተ፴ ደቂቃ የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ወደ ጥምቀት ባሕር የሚወርዱትን ታቦታት ለመሸኘት ከግቢ ወጡ ፡፡

መውጣታቸውም በተለማ ጊዜ ሠራዊቱ በግራና በቀኝ ተራወጠ በግቢው አጠገብ በተሠራው በኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን ያሉ ካህናት በፍሥሐ ወበሰላም ወረደ ወልድ ውስተ ምጥማቃት እያሉ ይዘምሩ ነበር ፡ ትርጓሜው በደስታና በሰላም ወልድ ወደመጠመቂያው ወረደ ማለት ነው ፡፡ ይህም ሁሉ ሲሆን ወደ ጓዳ በሚያወርደው መንገድ ግራና ቀኝ ወታደር እያመረ ተሰልፎ ይጠባበቅ ነበር ለ፲ ሰዓት ሩብ ሰዓት ሲቀረው የግቢ ኪዳነ ምሕረት ታቦት ወጣ ልዑል አልጋ ወራሽም ታቦቱን ተሳለሙና በታላቅ ግርማ ሆነው ታቦቱን አጅበው በጓዳ በኩል ባለው በር ወጡ ታቦቱም ሲሔድ በግራና በቀኝ የተሰለፈው ወታደርና የቀረውም ሕዝብ ሁሉ ታቦቱን ለመሳለም እንደ ቅጠል ይረግፍ ነበር ፡፡
የሥርዓቱንና የአካሔዱንም ነገር ሥላሴ ማርገጃ ቆመን ስናየው ላይናችን ድንቅ ሆኖ አምሮ ይታየን ነበረ ፡፡ አካሔዱም እንደዚህ ነበር በፊት በፊት ወታደር አበባ መስሎ አምሮ አጊጦ ይሄድ ነበር ፡፡ ቀጥሎም ሰይፍ ጃግሬዎች ጠመንጃቸውን በቀይ መለዮ አስጊጠው ሲሄዱ እጅግ ደስ ያሰኛል ፡ ቀጥሎም ቀሳውስትና ዲያቆናት የወርቅ ልብሰ ተክህኖዋቸውን ለብሰው ታቦቱን ይዘው በመካከል ይሔዱ ነበር

ከዚህም ቀጥሎ የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን የወርቅ ዕቃ ባስጌጡት በቅሎ ተቀምጠው በለወርቅ አሽከሮች የሆነ በራሶ ለነገሥታት የሚገባ ቀይ ጥላ አስይዘው ብቅ አሉ ጥላ ያዡውም ጥላውን ወደ ላይ ክንድ ያህል ከፍ አድርጎ ይዢት እንዴት ታምር ነበር ፡፡

ቀጥሎም ከበራን መኳንንት እንደ ማዕርጋቸው ፈቅ ፈቅ እያሉ ልዑልን አጅበው ነበር በግራና በቀኝም ዘበኛ እንደ አጥር ሁኖ ይጓዝ ነበር የኋላ ዘበኛ ግን ሃምሳ ሜትር ያህል ርቆ ተደርድሮ ሲሔድ እጅግ ያምር ነበር ፡፡
፲ ሰዓት ሲሆን ከግቢው ወጡና ከግቢው ውጪ ባለው ሜዳ ላይ ቆመው የቅዱስ ገብርኤል ታቦት እስኪመጣ ይጠብቁ ነበር በዚህም ጊዜ የሥላሴ ታቦት ወጣ ፡፡

የሥላሴ ታቦት ሲወጣ ለማጀብ በጅሮንድ ሣህሉ ድንግል መለዮ የለበሰ ስልሳ ስድስት ዘበኛና ሌላም ብዙ ወታደር ይዘው መጥተው ተቀበሉ ፡፡

በ፲ ሰዓት ከ፲ ደቂቃ የቅዱስ ገብርኤል ታቦት ወጣ ፡፡

፲ ሰዓት ከሩብ ሲሆን የቅዱስ ገብርኤል ታቦት በብዙ አጀብ ሆኖ ከሚጠብቁት ቦታ ደረሰና ተቀላቅሉ በአንድነት ይጓዝ ጀመረ ፡፡

በ፲ ሰዓት ከ፳ ደቂቃ የሥላሴ ታቦት መጣና ወደ ልዑል አልጋ ወራሽ ቤት በሚያወጣው በትልቁ መንገድ ላይ ተገናኝተው በአንድነት ይጓዙ ጀመረ ፡፡

በዚህም ጊዜ የእልልታውና የእምቢልታው የከበሮውንም ድምፅ መለየቱ እስኪቸግር ድረስ እጅግ ደምቆ ነበር ከግቢም ጀምሮ እስከ ጃን ሜዳ ድረስ ሠራዊት ይፈልቅ ነበር ጃን ሜዳም በደረስን ጊዜ ክቡር ፊታውራሪ ገብረ ማርያም

ጭፍሮቻቸውንና የመትረየስ ዘበኞችን አሰልፈው በታላቅ አቀባበል ታቦቱን ተቀበሉ የሰልፉም ስርዓት አራት ማዕዘን ሆኖ በቀጥታ ስለ ሆነ ለማየት እጅግ የሚያስገመጅ ነበር ።

ለ፲፩ ሰዓት ሩብ ጉዳይ ሲሆን ክቡር ክንቲባ ነሲቡ የአራዳን ዘበኛ ግሩም በሆነ አካሔድ አሰልፈው የጊዮርጊስን ታቦት ይዘው መጥተው ተቀላቀሉ ።

ባ፲፩ ሰዓት መድኃኔ ዓለም ታቦት መጥቶ ጃንሜዳ ላይ ተቀላቀለ በዚህም ጊዜ ጃንሜዳ በሠራዊት ተጨንቃ መተንፈሻ አጥታ ነበር።

በጃንሜዳም ያሉቱ አድባራት ካህናት ወረብ ወርበው ያሰረግጡ ጀመር፤ በዚህም ጊዜ ልዑል አልጋወራሽ በወምበር ተቀምጠው ነበር፤ ወረቡም ከተጨረሰ በኋላ አሳረጉና ጉዞ ሆነ። ልዑል አልጋ ወራሽም ጥቂት ሸኝተው ተሳለሙና ባ፲፩ ሰዓት ተሩብ ተመልሰው ወደግቢያቸው ገቡ ። የአዲስ አበባ አብ ካህናትም ታቦታቸውን ይዘው የጥምቀት ሥርዓት በሚደረግበት በቀበና ወንዝ ዳር ሆነው ይጠብቁ ነበርና እነዚሁ ፫ ታቦታት ከመጡ በኋላ ሁሉም ባንድነት ወደ ድንኳን ገቡ የከተራ በዓል ዕሁድ በ፲፩ ሰዓት ተኩል ተፈጸመ ።

ጥር ፲፩ ቀን ሰኞ ከጧቱ በኩል ሰዓት የኢ መ አ ወ ተ መ በብዙ ሠራዊት ሆነው ኒጋሪት እየተጎሸመ መለከት እምቢልታ እየተነፋ ታቦታቱ ወደአደሩበት ሥፍራ በ፩ ሰዓት ደረሱ። አባታችን አቡነ ማቴዎስና እጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስም በሙቶሞቢል ሆነው በ፩ ሰዓት ተኩል ከተፍ አሉ ።

ልዑል አልጋ ወራሽም ከክቡራን መኳንንቶቻቸው ጋራ በጥምቀት ባሕሩ ዳር ተቀምጠው ነበር አባታችንም ከመጡ በኋላ ልብሰ ተክህኖ ለብሰው በወንዙ ዳር ይጠብቁ የነበሩት ቀሳውስትና ዲያቆናት የመጽሐፈ ጥምቀቱን ሥርዓት አድርሰው ፈጸሙ ። ከዚህም በኋላ አባታችን በውሀው ላይ ጸሎት አድርገው ባረኩትና በሕዝቡ ላይ ረጩት ።

በ፪ ሰዓት ታቦታቱ ወጡ ካህናቱም ኃዲጎ ፺ ወተስዓተ ነገደ ቆመ ማዕከለ ባሕር እያሉ ወረቡ ። ትርጓሜው ፺፱ኙን ነገድ ትቶ በባሕር ላይ ቆመ ማለት ነው ። ልዑል አልጋ ወራሽም ከክቡራን መኳንንቶቻቸውና ከውጭ አገር ሰዎች ጋራ ሆነው ይኸን የዝማሬውን ቃል ይሰሙ ነበርና ወረቡ ከተፈጸመ በኋላ መንገዝ ገመሩ ።

በ፫ ሰዓት ተ፲ ደቂቃ የአዲስ አበባ አብ ካህናት ታቦታቸውን ይዘው በአጀብ ሆነው ወደስፍራቸው ሔዱ ።

እኛም በ፫ ሰዓት ተኩል ጃን ሜዳ በደረስን ጊዜ ታቦታቱ ምዕራፍ አደረጉና ካህናቱ ወረብ ይወርቡ ጀመር። ልዑል አልጋ ወራሽም በታላቅ ግርማ ሆነው በወምበር በተቀመጡ ጊዜ ልዩ የሆነች የኢትዮጵያ ባንዲራ በልዑልና በመኳንንቱ ፊት ቁማ ታሸበርቅ ነበር ።

፬ ሰዓት ወረቡ ተፈጸመና አባታችን አሳረጉ፡የውጭ አገር ሰዎችም ሰላምታ ሰጡ ። ልዑል አልጋ ወራሽም ከዚያ ተነሱና መንገዝ ሆነ ። በ፬ ሰዓት የመድኃኔ ዓለም ታቦት ተለይቶ በብዙ ዓጀብ ወደ ቦታው ሔደ ።

ያአራዳ ጊዮርጊስ ታቦት ደግሞ በ፬ ሰዓት ተልየና በብዙ ዓጀብ ሔደ ።

ልዑል አልጋ ወራሽም የቀሩትን ታቦታት ሸኝተው የጥምቀትን በዓል በደስታ አክብረው ከጨረሱ በኋላ ባራት ሰዓት ወደ ትልቁ ግቢ ገቡና ለመኳንንቱና ለሠራዊቱ አዳራሽ ተገኝተው ዋሉ ።

ባገራችን ስለጥምቀት በዓል መታሰቢያ ከብዙ ዘመን ጀምሮ ነገሥታቱና መኳንንቱ ጳጳሱና ካህናቱ ወደ ወንዝ ወርደው ባሕር ባለበት ቦታ ይጠመቃሉ ይህንም ማድረጋቸው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮርዳኖስ ባሕር እንደ ተጠመቀ ለማሳሰብ ነው እንጂ የጥምቀትን ጸጋ በሕፃንነት እንደተቀበሉ ማንም ያውቃል ። ይህም መታሰቢያ እጅግ መልካም ነው።ነገር ግን ያልተማሩ ሰዎች ምሥጢሩን አያውቁትምና የጥምቀት ኪዳን ምን እንደሆነ ጥቅሙም ምን እንደሆነ ካህናት ከመጽሐፍ እያነበቡ ባማርኛ ቢያስታውቋቸው መልካም ነበር።

የጥምቀት ምሥጢር ምን እንደሆነ ሳያውቁ ቢረጩበት ግን ጥቅም አያገኙበትም ።

በጥምቀት ቀን ዘፈኑንና ፈንጠዝያውን አይቶ ደስ እንዲለው ብቻ እንጂ ጥምቀት ምን እንደሆነ በውሣጣዊ ሐሳቡ የማያውቅ ብዙ ነው። ይህን ያህል ቀሳውስትና ሊቃውንት ሞልተው ብዙ የክርስቲያን ነፍስ በጥምቀት ቀን በእግዚአብሔር ቃልና በጸጋው ትሩፋት መነከር ቀርቶ አንዳንድ ነጥብ ሳታገኝ ተጠምታ መዋሏ ምን ይሆን ።?

ከዚህ በላይ በተጻፈው ቃል ቄሶች እንዲያስቡበትና ለእንግዲሁ ለተጠሙ ነፍሳት ክክርስቶስ ቃል ከሚገኘው ከሕይወት ውሀ እንዲያረኳቸው እናሳስባቸዋለን ። ይህንን ቢያደረጉ ባልታመኑ በእግዚአብሔር መንጋ ጠባቂዎች ከሚወርድባቸው ከዘለዓለማዊ መቅሠፍት ይድናሉ ።

ይህ የጥምቀት ሥርዓት ጌታችን ሥራውን ሳይጀምር የተጀመረ ነገር ነው ጌታችንም ተማሪዎቹ ሕግ አድርገው እንዲጠብቁት አደረገ ። ይህም በሰስቱ ሥላሴ ስም የሚሆን የጥምቀት አደራረግ ከኀጢአትና ከርኵሰት ለመንጻት ምልክት ሆነ ። በዚህ ሥራም የተጠመቀ ሰው ከክርስቶስ አንድነትን ያገኛል። ግዝረት ለብሉይ ምልክት እንደሆነች ጥምቀትም ለሐዲስ ምልክት ናት ።

ሰው በእግዚአብሔር መንግሥት ሥራ ገብቶ እየታዘዘ ሥራውን እንዲፈጽም የሚገባበት ውል እግዚአብሔርም የኀጢአትን ሥርየትና የማዳን ተስፋ የሚሰጥበት የጸጋ ኪዳን መደምደሚያ ናት ።

በጥር ፲፪ ቀን ፲፱፻፶፯ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቃና ዘገሊላ ለሠርግ ተጠርቶ ውኃውን ጠጅ አድርጎ የመጀመሪያ ተአምራቱን የገለጸበት ቀን መታሰቢያ በዓል ነበር ። ወዲያውም የቅዱስ ሚካኤል የወር በዓሉ ስለ ሆነ በጥምቀት ባሕር አድሮ በዚያ በበዓሉ ቀን እንዲገባ ልማድ ነበረና በዚያ ቀን ልዑል አልጋ ወራሽ ከመኳንንቶቻቸው ጋራ በብዙ ሠራዊት ታጅበው የቅዱስ ሚካኤልን ታቦት ከቤተ ክርስቲያኑ ድረስ በትልቅ ክብር አድረሰው ተመለሱ ።

በደብዳቤ የመጣ ቃል ።

ብርሃንና ሰላም የሚባል ጋዜታ ልዑል አልጋ ወራሽ ከባሕር ሲመለሱ መጀመሩ በኖኅ ዘመን ርግብ ለምለም ይዛ የምስራችና የተስፋ ምልክት እንዳመጣችው ምሳሌ ሆኖ ያሳስባል ፤ ኦሪት ዘፍ ምዕ ፫ ቍ ፲፩ ። ይልቁንም ይህን በሰላም የተዋሐደ ብርሃን ከልቤ አቁሜ ባስተዋልኩት ጊዜ በዮሐንስ ወንጌል አስቀድሞ ስለ ብርሃን የተነገረው ቃል ትዝ አለኝ ምዕ ፩ ቍ ፱ ምዕ ፫ ቍ ፳፩ ። እውነተኛ ብርሃን ነበረ ለሰው ሁሉ የሚያበራ ወደ አለም የመጣው እውነት ሕግን የሚያደርግ ወደ ብርሃን ይመጣል እንዳለው ። እንግዲህ ብርሃንን ካገኘን በሰላም ከቆየን ልዑል አልጋ ወራሽ ያደረጉልንን ወረታ እናስተውል ። ይህም ጋዜታ በልዑል ስም መታተሙ እኛን ለመምከር እርስበርሳችን በፍቅር ለማስተሳሰር በሰላም ለማጽናት እንደሆነ በጣም ያስረዳናል ስንፍናና ድንቁርና እንዳያንቅፉን በብርሃን እንድንመላለስና በሰላም እንድንኖር ተስፋ እናደርጋለን ።

ልጅ አበበ ወልዴ ።

ሰላም ለከ ብርሃን የጨለማ ንጉሥ ።

በጉልህ ፈደል ከሌሎቹ ቃላት ይልቅ ተጽፈህ ብትወጣ ኃይልህ ተገልጾ ያበራህበትን ቀን ወዳጆችህ በታላቅ ደስታ አከበሩት ። ደግሞ ይህቺ ቀኝ የማትሞትና ሁሌተኛ የማትጨልም ስለሆነች በሚመጣው ትውልድ የበለጠ ክብሯን ታገኛለች

ይህንን ያህል ዘመን እንደ ጊዜ ሳትደክም እንደ ጊዜ ሳትሰለች ጭለማንና ስቃይን ታገለህ ስምህ በጉልህ ፈደል ስለታየ ከሁሉ የበለጠ አክሊል ላንተና ለወንድምህ ሰላም ይገባችኋል ስል ምስጋናዬን ከኢትዮጵያ ልጆች ጋራ አቀርባለሁ ።

ደግሞ በምሥጋናህ ልክ ነውርህን መግለጽ ስለአስፈለገ ልናገረው ዘንድ የግድ ሆነብኝ ምስጢርህን ያወቁት ሥራህን የመረመሩት ሰዎች በአንድ ሰከንድ ፫፻ሺ ኪሎሜትር ኃይልህ ይወረወራል እያሉ መሰከሩብህ ። በአንድ ሰዓት ፫ሺ፮፻ ሰከንድ ሲኖር ጊዜ ፤ ፩ ሚሊያር ፹ ሚሊዮን ኪሎሜትር በሰዓት መወርወርህ ነው ። እንደዚህ ያለ ኃይል ተሰጥቶህ እስከ ዛሬ በዚያች ቦታ ያልተገለጽክበት ምክንያት ምንድር ነው ። ?

ከዓለም ከምስቱ ክፍሎች ሮጳ እስያ አፍሪካ አሜሪካ አስትራሊያ ከነዚህ አምስቱንም የብርሃን ኃይል ሲያበራቸው ከአንደኛው ክፍል አንድ ነጥብ መሬት በጂኦግራፊ አቀማመጧ ብርሃን የማይደርስበት ሆኖ ብትኖር ከዚያም በኋላ በዚያች በመሬት ላይ ከሉት አንድ አዋቂ ሰው ተነስቶ ለዚያች ለመሬት ብርሃን እንዲበራላት ተጨንቆ ተጠበ ያለውን ዕውቀትና ያለውን ኃይል ቢሰዋላት የዚያም የአዋቂ መሐንዲስ ሠራተኞች የሱን ሐሳብ ተከትለው ከዕውቀታቸውና ከኃይላቸው የበለጠ ሕይወታቸውን ጭምር ብርሃን እንድታገኝ ቢሠውላት ብርሃንም እዚያች ቦታ ለመድረስ በተሰጠው ኃይል ፩ ሚሊያር ፹ ሚሊዮን ኪሎሜትር በሰዓት ቢወረወር ያች ቦታ ከፈጣጠር (ማለት በጂኦግራፊ አቀማመጧ) ብርሃን የማይደርስባት የሆነች እንደሆነ ለዚያ ለአዋቂ መሐንዲስና የሱንም ንድፍ (ፕላን) ተከትለው ለደከሙ ሠራተኞች ለሐሳባቸው ድጋፍና የሚአጽናና ነገር በዚች መሬት ምን ያገኛሉ ።? ከመቃብርስ በላይ የሚሞተው ሲሞት አይሞትም እንደተባለው ሐሳባቸው በሚመጣው ትውልድ ላይ እንደተሳፈፈች ትኖራለች ።

የዕውቀትም ሚዳዋ ሰፊ ስለሆነች የሚፈልቁባትም ምንጮች እያሌ ናቸውና የዚህ ዓለም ሰው ሊወሰናት አይቻለውም ስለምን በዘመን የማይቻል ሥራ ነው ተብሎ የተፈረደው ደግሞ በዘመን ተችሎ የማይቻል የመሰለው የተቻለ ሆነ ።? እንደዚሁም የማይቻል የተባለው ሁሉ የሚቻል እየሆነ ሲአልፍ ሲተላለፍ ቆየ ፤ የሚመጣውም ትውልድ ለኛ የተወሰነውን አልፎ በሰፊዋ ሚዳ ላይ ከፈለቁት ምንጮች እየጠጣ በብርሃንና በሰላም መካከል ቀኖቹን ያሳልፋል ።

ገብረ እግዚአብሔር የአ ኦ ጉምሩክ ዲሬክተር ።

የኤውሮጳ ቋንቋ በተማሩ ኢትዮጵያውያን ላይ ለወጣው የጥርጥር ሐተታ ምላሽ ።

« … አባቶቻቸውን ብዙ ከሳራ አስከፍለው ኤውሮጳ ድረስ የሄዱ ልጆች ከትርጁማንነት በተቀር ሌላ ምን ይዘው ተምረው መጡ ? ትርጁማንነት ተምረው የሚመጡት ምናልባት ሀገራችንን ፈረንጆች የገዙት እንደሆነ እኛን ደንቆሮቹን ሊያስተረጁሙልን ይሆንን ? አይሆንም . . » የሚል የጥርጥር ሐተታ ፳፯ ኅዳር ፲፱፻፲፯ አእምሮ ቍጥር ፳፯ ላይ አንብበን እናዝናለን ።

የኢትዮጵያ ልጆች የሚበዙት ፤ እስከሁን ድረስ የኤውሮጳ ቋንቋ የተቻላቸውን ያህል አውቀው ኢትዮጵያውያንና ኤውሮጳውያን እያነጋገሩ ወይም ጽሕፈታቸውን ከንዱ ቋንቋ ወዳንዱ ቋንቋ እየተረጐሙ መንግሥትንና ሕዝብን በማገልገል የበቁት በገዛ መልክም ፈቃዳቸው ብርታትና በኤውሮጳውያን እርዳታ እንደሆነ እንጂ በዘመዶቻቸው ከሳራ እንዳልሆነ አስታዋይ የሆነ ሰው ሁሉ ያውቃል ።

ሠልጥነው የሚያሠለጥኑ ሕዝቦች ቋንቋ መማራቸውም ለቀረው ትምሕርት ሁሉ ዋና መክፈቻው አፍ ነውና ፤ በዚሁ አድርገን ጥበባቸውን ተምረን ስናበቃ ሀገራችንንና መንግሥታችንን እያገለገልን እንደነሱ ልክ ነጻነትና ጥቅም ክብር ከወንድሞቻችን ጋራ እናገኛለን ብለው ነው እንጂ ከላይ እንደተባለው የጥርጥር ሐተታ ባለቤት ሐሳብ የራሱ ብቻ ሳይሆን የሕዝቡም አገልጋይ አድርጎ ለሚገዛ ባዕድ መንግሥት ትርጁማኖች እየሆነ የሰው ቋንቋ ከማያውቁት ወንድሞቻችን በላይ እናድራለን ብለው አይደለም ።

እንደዚህ አለመሆኑም እጅግ በሰፋው ዕውቀትና እጅግ በበለጠው ኃይል ከፈጣሪያችን በታች የሚጠብቀን መንግሥታችን የኤውሮጳ ቋንቋ ትምሕርት ቤት በኢትዮጵያ እንዲከፈት በመፍቀዱና የኢትዮጵያ ልጆች ልዩ ልዩ ቋንቋና ጥበብ ዕውቀት እንዲማሩ ወደ ውጭ አገር በመስደዱ ይመሰክራል ።

የዚህ ሐተታ ባለቤት « መዠመሯ የኤውሮጳ ብልሃት የጅ ሆኖ የልብ ጥበብ ሁሉ በማርኛ ተገልብጦ ልጆቻችን ቢማሩት መቸም ቋንቋቸው ነውና በፍጥነት ይገባቸዋል ።

ይላሉ ። እዚህ ላይ ይልቅ የሚያስፈልግ ነገር ተናግሮዋል ። ነገር ግን የኤውሮጳ ቋንቋ ያወቁና ኢትዮጵያውንን ከጠረጠረና ከጠላ ይህ ደግ ሐሳቡ በማን ሊገለበጥ ያስበዋል ?

የኢትዮጵያ ልጆች ቋንቋ ብቻ እየተማሩ ወደ ሀገራቸው መመለሳቸውም ቀድሞ እንዳልነው በዘመዶቻቸው ከሳራ ሳይሆን በገዛ ፈቃዳቸው ብርታትና በፈረንጆች እርዳታ ነበርና ከቋንቋ ትምህርት ቤት ገብተው የነበሩት ወደ ጥበብና ዕውቀት ትምህርት ቀጽለን እንግባ ብለው ሲጣጣሩ ይህን ጊዜ የፈረንጆች እርዳታ የለምና የገንዘብ እጦት እንደ ክፉ አጋፋሪ ሆኖ ስለከለከላቸው ነው ።

የውጭ ቋንቋ ያወቅነውም ያላወቅነውም የኢትዮጵያ ልጆች ሐሳባችንና ምኞታችን ሁሉ ጠቅል ብሎ ባንድነት ለባለ ዘውዲቱ ሃገራችን ፍጹም አድልቶ ሳለ እንደዚህ ያለ ምቀኛ መከከድ በገዛ አገር ልጆች ላይ ባለማወቅ ታስቦ ተነግሮ ሲገኝ አስተውሎ ለማይመለከት የዋህ ለሆነ ሰው አገር ለመውደድና መንግሥት ለማገልገል ከሠለጠኑት ሕዝቦች እውቀት ብርሃን ርቆ ስንፍና ለብሶ በድንቁርና ጨለማ ውስጥ ተኝቶ መኖር ያስፈልጋል ማለት ይመስለው ይሆናል ።

ስለዚህ ይኸንን ክፉ ሐሳብ ለመከልከል እግዚአብሔር የጠላውና ሰውም የነቀፈው የሚጎዳውን ሐሜትና ክርክር ንቀፌታ በገዛ አገር ልጆች ላይ መናገር ትቶ የሚጠቅመውን ፍቅርና እምነት መተጋገዝ ባገር ልጆች መካከል ጸንቶ ለዘለዓለም እንዲኖርና የኤውሮጳውያን ሥልጥንና በኢትዮጵያ ሃገራችን እንዲገባ የሚያስፈልገውን ደግ ነገር ሁሉ እያሰቡ ቶሎ ቶሎ ብሎ ማስታወቅ ይገባል እንጂ ። «ምናልባት ፈረንጆች ሃገራችን የገዙት እንደሆነ ሊያስተረጁሙልን ይሆንን» የሚሉት የሰነፍ ክፉ ትንቢት በጋዜጣ አውጥቶ ማስታወቅ አይገባም ።

የግዕዝ ቋንቋ በሚያውቁ ኢትዮጵያውያን ላይ ለወጣው የንቀት ቃል ምላሽ ።

« … መቸም አእምሮ ማለት እውቀት ማለት እንደሆነ ጥቂቶች ሰዎች ሳያውቁት አይቀሩም እነዚሁም የግዕዝ ቋንቋ የሚያውቁ ሰዎች ናቸው ያውም የሚረባ የትምህርት ቤት በደምቡ የላቸውምና ከንዱ ወረዳ ወዳንዱ ወረዳ እየተባረሩ እየለመኑ ነው ይህሉ አእምሮ ያገኙት … » የሚል የንቀት ቃል ታትሞ አይተን ደግሞ እንደዚሁ እናዝናለን ።

ኢትዮጵያ ሃገራችን ከዳዊትና ከሰሎሞን ነገሥታት ጊዜ አያሌ ዘመን አስቀድማ ወዲህ ባለዘውድ መሆኑዋንና የነገሥታቷን የሕዝቦችዋን አኑዋወር እንዴት ሥልጡን እንደነበረ እየነገረን የምንመከበት ታሪክ የቆየልን ስለ ሃገራችን አድባራትንና ገዳማት ሊቃውንት ጥንቃቄ ነው ።

ኃይልና ሥልጣኔ ያላቸው ትልልቆች አገሮች ሃይማኖትና ሥርዓት ሕግ ፡ ኃይል የሌላቸውን ትንንሾች ሕዝቦች ሁሉ በያሉበት እየፈለጉ በብልሃት ኃይል ጠምደው በገዛ ሃገራቸው ሲጠቀሙባቸው ከአፍሪቃ ሙሉ ሕዝባችን ብቻውን የተረፈው ነገሥታቱ ሕግና ሥርዓት አውጥተው እየጠበቁ ሊቃውንቱም በግዕዝ ቋንቋ ጽፈው ሃይማኖት እየሰበኩ ስለቆዩና እነዚሁ ሃይማኖቱና ሕጉ ሥርዓቱ መዠመርያ የሚመክትበት ጥሩ ጋሻ ሁነውት ሁለተኛ በነጻነት እንደኖረ መኖር እንደሚገባው ምሥክር ሁነውት እግዚአብሔር ስለ ረዳው ነው ።

ወደፊትም ሕዝባችን የጦርና ፡ የንግድ የእርሻ የቀረውም ሥራና ጥበብ ሁሉ በያይነቱ መማሪያ እንደ ኤውሮጳውያን ባገሩ ሠርቶ የሚገባውን ሁሉ በትክክል እስቲያገኝ ድረስ ከባለጋራው የሚመክትበት አንዱ ጋሻው በግዕዝ ቋንቋ ተጽፎ የቆየው ሕጉና ታሪኩ ነው ።

እነዚህ ሕግና ታሪክ ተምረው ጽፈው በጥንቃቄ ያስተማሩና ያቆዩም የግዕዝ ቋንቋ አዋቂዎች ናቸውና የኤውሮጳውያንን አዲስ ትምህርት ባይኖራቸው ይህነን ደሞ መጨመር ያስፈልጋቸዋል ብሎ እንደማለት የሚረባ የትምህርት ቤት የላቸውም ከንዱ ወረዳ ወዳንዱ ወረዳ በረው እየለመኑ ተምረው ነው አእምሮን ያገኙ » ብሎ ሊሰድቡዋቸው ከቶ አይገባም ።

መንግሥታችን ራሱን ችዬ ሕዝቡን ዳኝቼ በትክክል የማሳድርበት ድልድል ሥርዓትና ትክክል ፍርድ ጥንክር ኃይል ፤ ሰፊ እውቀት ትጉኅ ትምህርት በኢትዮጵያ አገሬ አለኝ እያለ ከዓለም ሙሉ ነገሥታት ጋራ ስለ ነጻነታችንና ስለ ጥቅማችን ስለ ክብራችን ስለ የሚገባንም ሁሉ ያለ መታከት ሲሚገትልንና ሲከራከርልን « እኛን ደንቆሮችን የሚረባ የምህርት ቤት የላቸውም ። እንኳን አቡጀዲድና ክብሪት መስራት አልተማሩም እያሉ የሚያወሩት አንዳንድ ኢትዮጵያውያን ወንድሞቻችን በመንግሥታቸው ላይ እየመሰከሩ ማስረታታቸው መሆኑን አዙረው ገና አላዩትምና ነው ።

መንግሥታችን እንደ አንድ ጠበቃ ሁኖ ሲሚገትልን እኛ እንደምስክሮች ሁነን ያስረታነው እንደሆነ ከሺ ምስክር ዋና በከናፍር በሚሉት ምሳሌ ጠላታችን የሆነ ሁሉ ያስፈርድብናልና መንግሥታችን የሚለውን ሁሉ ሰምተን አክብረን በብዙ ጥንቃቄ ጠብቀን እግዚአብሔር ለኛ ኢትዮጵያውያን ፍጡሮቹ ሲል ሐብትና ዕውቀት ሥልጣን ደግነት አንድ ላይ አስማምቶ ሰጥቶ ላነገሠልን ለግርማዊት ንግሥታችን ዘውዲቱና ለልዑል ባለግርማ አልጋ ወራሻችን ራስ ተፈሪ ለኢትዮጵያ ሙሉ ሠራዊት ዕድሜ እየለመን መኖር ይገባናል ስንል ምላሹን እንጨርሳለን ።

መድኅኔ ገብሬ ።

የጃንሜዳ ሽቅድድም ማሕበር ።

የጃንሜዳ ሽቅድድም ማሕበር የዚህ ዓመት የበጋ ሽቅድድም መሰብሰብ ባ፫ፌብሬዩ አሙስ ዕለት እንደሚሆን በማክበር እናስታውቃለን ።

በላይ ለተነገረው የሽቅድም መሰብሰብ የሚሆነውን ፕሮግራም ዋና መሠረቱ እንደዓምና ፫ገርንብዩ ፩ሺ ፱፻፳፩ ፕሮግራም ታትሞ ሊወጣ ነው ።

ለማሕበረተኞቹ ።

ክምት ጀ ክሊ ።

በልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

መጀመሪያ ዓመት ፤ ቁጥር ፭ ።
1re ANNÉE № 5

ሐሙስ ጥር ፳፩ ቀን ፲፱፻፲፯ ዓ ምሕረት ።
JEUDI 29 JANVIER 1925

ብርሃንና ሰላም
LUMIÈRE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን በገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ ሲገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

የጋዜጣው ዲሬክተር ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የራሱን ጉዳይ የሚያሳትም ሰው ዋጋውን እየከፈለ እናትምለታለን ።



በተሰቀለውና በሞተው የሞትንም ሥልጣን ድል አድርጎ በተነሣው በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምኑ ቢሞቱም ሕያዋን ሁነው ይነሣሉ ።

እርሱ ራሱ እኔ ትንሣኤም ሕይወትም ነኝ ያመነበኝም ቢሞት እንኳ ይነሣል ብሏልና ። የ፡ሐ ፲፩ ፳፭ ።

ስለ ክብርት ወይዘሮ ተዋበች ሞት ።

ክብርት ወይዘሮ ተዋበች የንጉሥ ሚካኤል ልጅ የክብርት ወይዘሮ ስሒን እህት፤ የልዕልት ወይዘሮ መነን እኅት የክቡር ራስ ሥዩም ሚስት ናቸው ። በእናታቸውም የወይዘሮ ማናለብሽ ልጅ፤ የወይዘሮ ባፌና የልጅ ልጅ ናቸው ።

ነገር ግን ምንም ቢሆን ከሞት የሚቀር የለምና ሕመማቸው በጣም ሳይጎላ በተኚሽ በሽታ ጥር ፲፪ ቀን ማክሰኞ ለረቡዕ አጥቢያ ከሌሊቱ በ፫ ሰዓት በሞት አረፉ ። መሞታቸውም በተሰማ ጊዜ የሰው ሁሉ ልብና አዘነ፤ ይልቁንም ደግነታቸውንና ፍቅራቸውን በጣም የለመዱት ዘመዶቻቸው ኃዘኑን እንችልህም አሉት ።

ወዲያው ሌሊቱን አስከሬናቸውን ይዘው ወደ ደብረ ሊባኖስ ተጓዙ ። የተከተለውም ሠራዊት እጅግ ብዙ ነበር ።

ልዑል አልጋ ወራሽም የሰውን ድካም ለማቅለል አስከሬኑን በአውቶመቢል እንዲሄድ አደረጉ ። ሐዘንተኞቹንም እስከ ሱሉልታ ድረስ ሸኝተው ተመለሱ ። አስከሬኑም በሄደ ጊዜ አዘንተኞቹን ወይዘሮ ስሒንና ወይዘሮ መነንን ራስ ሥዩምን ለማረጋጋትና ለልቅሶ ተከትለው ወደ ደብረ ሊባኖስ ሔደው የነበሩት መኳንንትና ወይዛዝር በጣም ብዙ ናቸው ። ጥር ፲፫ ቀን ረቡዕ ሲሄዱ ውለው ቃሊም ሥላሴ ገብተው አደሩ ። ጥር ፲፬ ቀን ሐሙስ በ፪ ሰዓት ደብረ ሊባኖስ ገቡ ። ክብርት ወይዘሮ ተዋበችንም በያታቸው በወይዘሮ ባፌና መቃብር ቤት ውስጥ ቀበሩና ቀበሬ ተመለሰ ። ክቡር ራስ ካሣም ለመቃብሩ ደርሰው ኃዘንተኞቹንም አስተናግደው አጽናንተው ወደ ፍቼ ተመለሱ ።

የውሎ ቀን በጃን ሜዳ ።

ጥር ፲፯ ቀን የክብርት ወይዘሮ ተዋበች ውሎ በጃን ሜዳ ላይ ተደረገ ። የውሎውም ሥርዓት እጅግ የሚያሳዝን ነበረ ። መጀመሪያ በዚሁ ቀን ጧት ሜዳውን የሚያለብስ ፱ ትልልቅ ድንኳን በጃን ሜዳ ተተከለ ። በግራና በቀኝም መጠነኛ መጠነኛ ሰቀላ ድንኳን ተተከለ ። በድንኳኑም ውስጥ ያለውን ሜዳ ሥጋጃ አልብሶት ነበር ።

ሠራዊቱም ከጧት ጀምሮ ግማሹ ወደ ጃንሜዳ ግማሹ ወደ ልዑል አልጋ ወራሽ ግቢ ይጎርፍ ነበረ ። ሦስት ሰዓት ሲሆን ከልዑል አልጋ ወራሽ ግቢ ላዘንተኞቹ መቀበያ የሚሄደው ድግስ በየዓይነቱ ተቀጣጥሎ ተቀጣጥሎ ወደ ራስ ሥዩም ቤት ተጓዘ ። በ፬ ሰዓት ተ፴ ደቂቃ አቡታችን አቡነ ማቴዎስና ዕጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ወደ ጃንሜዳ መጡ መኳንንቱና ሊቃውንቱም በድንኳኑ ውስጥ ሆነው ቀባሪዎቹን ይጠብቁ ነበር

በ፭ ሰዓት ተሩብ ልዑል አልጋ ወራሽ በታላቅ አጀብ ወደ ጃን ሜዳ መጡ ። በዚህም ቀን በአዲስ አበባ ካሉ መኳንንትና ወይዛዝር ያልተሰበሰበ የለም ነበር ። በ፯ ሰዓት ተ፲ ደቂቃ ቀባሪዎች ደረሱ ። የመጣጣታቸውም ሁናቴ እንደዚህ ነው ።

መጀመሪያ ጥሩምባ ነፊዎችና መለከተኞች እምቢልተኞች በልቅሶ ዜማ ጥሩምባቸውን እየነፉ አለፉ ።

ቀጥሎም በወርቅ ዕቃ ያጌጡ ፫ በቅሎዎች መጡ ። በበቅሎዎቹም ላይ የወይዘሮ ተዋበችን ፎቶግራፍ አድርገው ባለወርቅ ዘርፍ የሐር ጥላ ተይዞላቸው መንሳንስም ተይዞላቸው ይጓዙ ነበር ። በሐር ዕቃ የተሸለሙ ሌሎችም በቅሎዎች አለፉ ። ቀጥሎም በወርቅ ዘቦ የተሸፈኑ በልዩ ልዩ ዓይነት ጌጥ የተጠለፉ መሰቦች አለፉ ከዚያም በኋላ ብዙ መሰቦች ተከትለው ነበር

ቀጥሎም በወርቅ ዘቦ የተሸፈኑ ፫ ወስከምቢያና ፪ የሐር መከዳ የወርቅ ዋንጫና የወርቅ ጫማ የወርቅ ድኮት ሌላውንም የጌጥ ዓይነት ሁሉ በየመሀረሙ ይዘው እያለቀሱ አለፉ ይኸን ሁሉ ማድረጋቸውም ወይዘሮ ተዋበች በሕይወት ሳሉ የነበረላቸውን ማዕርግ ለማሳሰብ ነው ። እኛም ዓይናችን የቻለልንን ያሀል ያየነውን ጻፍን እንጂ የጌጡንስ ነገር እያንዳንዱ ጽፈን ልንጨርሰው አልተቻለንም ።

ቀጥሎም ፴፩ ገምቦ እንደማዕርጉ ተሸፍኖ አለፈ ተሸካሚዎቹም ሁሉ በሚያሳዝን በሚያሳዝን ቃል ያለቅሱ ነበር ከዚህም በኋላ አዘንተኞቹ በታላቅ ልቅሶ እየተፋጁ መጡ ። እድንኳኑም ውስጥ በገቡ ጊዜ ዙሪያውን እየዞሩ ያለቅሱ ያስለቅሱ ነበረ ። በዚህ ጊዜ ሠራዊት እንባ ለእንባ ተራጩ ።

ከልቅሶውም ብርታት የተነሣ የልቅሶውና የመለከቱ ድምፅ ድብልቅልቅ እስኪል ድረስ ሆነ፤የትግሬ የወሎም የሸዋም ሴቶችም በየሀገራቸው ልማድ ሲያለቅሱ ያለፈቃድ ዕንባ ያስመጡ ነበር

በ፫ ሰዓት ተኩል ነጋሪት እየተመታ ልቅሰው ያለመጠን ጋለ ከዚህም በኋላ ሰውን በግድ አስቀመጡና አልቃሽ ቆማ ጥቂት እንደጀመረች ብፁዕ አባታችን አቡነ ማቴዎስ ተነሥተው ልብ የሚያረጋጋ ለሰውነት የሚስማማ ደስ የሚያሰኝ ምክር እንዲህ ብለው ተናገሩ ። እርሷ ወደመልክም ሥፍራዋ ነው የሄደቺው እናንተም ደግሞ ለሐዘን ጥቅም የለውምና ልቅሶውን ትታችሁ ልትጸናኑ ይገባችኋል ። ናዛዜ ኀዙናን ኢየሱስ ክርስቶስ ጽናቱን ይስጣችሁ ብለው አቡነ ዘበሰማያት ሰጡ ከዚህም በኋላ ጉባዔው በ፫ ሰዓት ተፈታ ።

ይሁን እንጂ የወይዘሮ ተዋበች ነገር ለዘለዓለም ከልብ የሚጠፋ አይደለም ። እንደዚህም ያለውን ኀዘን የሚወስነው ትዕግሥት ነውና ለክብርት ወይዘሮ ስሂንና ለልዕልት ወይዘሮ መነን ለክቡር ራስ ሥዩም ብርታቱን ይስጣቸው የሐዘን ዳርቻ ያድርግላቸው ብሎ ብርሃንና ሰላም ጋዜታ እግዚአብሔር ያጥናችሁ ይላል ።

በደብዳቤ የመጣ ቃል ።

የስፕሊን ጉዞ ከጀርማንያ ወደ አሜሪካ ።

ስፕሊን አንድ አይነት በአየር ላይ የሚሄድ እንደ ኤውሮፕላን ያለ ነው ፡ ኤውሮፕላን ክንፉን የዘረጋ ፕሮፔል በሚባል የሚዞር ከምድር ተነስቶ በዓየር ላይ ሊጫንና ሊሰፍ ይችላል ። የሚነዳበት ግን በሞቶር ነው ኤውሮፕላን ሁለት ዓይነት ነው ይኸውም ምኖፕላንና ስፕሊን ይባላል ምኖፕላን ክንፉ ሁለት ነው ስፕሊን ይግሞ ባለ አራት ክንፍ ነው ነገሩና አኳሆኑ ግን አንድ ነው ። ስፕሊን ግን አንድ ሞላላ ዱባ የሚመስል ጋን ወይም ከነፋስ የሚቀጥን ዓየር በውስጡ ተመልቶ የሚዘጋ ነው ያንን ነፋስ በውስጡ መልቶ ሲዘጋው የተነፋ ስልቻ በወሀ ሊሰጥም እንደማይችል እንዴሁ በምድር ላይ መቆም አይችልምና ከምድር ወደ ዓየር ይወጣል ወደፈቀዱት ቦታ ለማቅናትና ክፍ ዝቅ ለማድረግ ለማሳረፍ ግን በሞቶር ነው ። ይህ ሥራ ብጣም የገፋ በኤሮፓ ብርቱ ጦርነት ሁኖ ሳለ ነው ስለዚህ ጦርነቱ ሊያልቅ አቅራቢያ ጠንክረው በኤውሮፕላን ተዋጉ ዋና በዚህም ጦርነት እጅግ ቀንቶለት የነበረው ጀርመን ነው ። በሁለት ወር ውስጥ ጀርመን ፩ሺ ፫፻፷፭ ኤውሮፕላን ጣለባቸው እነሱ ግን ፪፻፺፩ ብቻ ጣሉበት ። መኪናው ስፕሊን የተባለበት ምክንያት የሰራው ሰው ስሙ ስፕሊን ስለሆነ ነው እርሱም የጀርማንያ ሰው ነው ። ኤውሮፕላኑን መጀመሪያ የሰራ ሰው ደግሞ አንድ ፋርማን የሚባል የፈረንሳይ ሰው ነው ።

እንግዴያስ ስፕሊን የሚሰራበት በጀርመን አገር ነው ስለዚህ አሜሪካዎች ከጀርማንያ ሁለተኛ ስለገዙ የጀርማንያ ሰዎች ፍሩድሪኮስሸሊን ከሚባል ከጀርመን አገር ውስጥ ተነስተው እየበረሩ ሰይቸርስት ወደሚባል የስቴት ኡኒቴ ማረፍያ በአሜሪካ ወዳለ ሲሄዱ በመንገድ ያገኛቸውን አኳኋን ብናነብ መልክም ነውና የበራሮቹ አለቃ ዮሐንስ ፎንሲለር የጻፈውን ቃላት በጭሩ ወደ አማርኛ እንተረጉማለን ።

ከፍርድሪክሳፋን ከጀርማንያ እስተሌይርስት አሜሪካ ርዝመቱ ፯ሺ፫፻ ኪሎ ሜትር ይሆናል፤ እንግዲያስ ለዚህ ኪሎ ሜትር ስፕሊን በ፹፩ ሰዓት ነው የሚገባው አለ ።

እንግዲያስ አለቀየው የጻፈው እንዲህ ነው ፤ መነሳታችን በ፲፩ ኅዳር በጥዋት ነበር ። ነገር ግን ከሙቀቱና ከጉሙ መክበድ የተነሳ ስፕሊን ለረጅም መንገድ የሚሆን ጭነትዋን ማንሳት አቃታት ስለዚህ ድሬክተር ኤክነር የመነሳትን ጊዜ ለሁደኋላ እንዲያደርጉት ግድ ሆነባቸው ።

በማግስቱ ጥዋትም እንዴሁ ጉም ነበር ነገር ግን ብዙ ሙቀት ስላልነበረ በራሪ በጥዋት በ፴፫ ደቂቃ ሊሰናበቱት የተሰበሰቡትን ሰላምታ ሰጥቶ ተነሳ በዚያ ከዋናው ከድሬክተር ኤክነር ጋራ የወጡ አራት የአሜሪካ አለቆችና ፳፰ የመኪና ሰራተኞች የጀርማንያ ሰዎች ነበሩ ።

ከዚያ ባሰን ወደሚባል ከፍታው ከጉም የበለጠ አቅንተን ተጓዝን ። ኋላ ወደ ደቡብ አድርገን መለስ አልንና ልፎርትን በግራ ትተን በፈረንሳይ አገር አለፍን ደምበሩ እኩል ሲቀረን በ፪ ሰዓት ምሳችንን በላን ። ምሳውም መልክም የሆነ ሹርባ ጥብስ እንዴሁም ሌላ ነበር።ድሬክተሩም ግራምፎን ዘመሩልንና በበራሪው ላይ ሁነን ሳለን ልክ ከቤታችን ያለን ይመስለን ነበር ።

ለዘጠኝ ሰዓት ሩብ ጉዳይ ሲሆን በራሪው ከነፋስ ብርታት የተነሳ ይገለባበጥ ጀመር ። ሰዎቹም በመርከብ ሳሉ እንደሚሆን መቅለስለስ ይመጣብናል እያሉ ይፈሩ ነበር ። ነገር ግን ጥቂት በጥቂት ስለተሻለ አንድም ሳይታመም በደህና አለፈልን ። በ፱ ሰዓት ተኩል ጃርንያስ አለፍንና ክኛክ ወደ ተባለ ከተማ ቀረብን። የሚጠጣ መጠጥ ግን ከወይን ጠጅና ለመድኀኒት የሚሆን ከጠርሙዝ እኩሌታ ኮኛክ በቀር ምንም አልነበረበትም ፤ ለይትናንት ግን ስለ ሙቀቱ ብዛት እንዴህ አለ፡ ኮታችንን ጥለን ሳለን እንዴት ሙቀት ይሰማል እንደዚህስ ከሆነ በጣም ስስ ልብስ ያስፈልጋል ።

ከዚያም ወደእስጳንያ ምዕራብ ሰሜን አድርገን ተጓዝን ጥሩና ልክ የሆነ ዓየርም ልናገኝ ጀመርን በእስጳንያ ደንበር ልንደርስ በቀረብን ጊዜ ግን ብዙ ነፋስና ወጨፎ ሆነ ከዚሁ የተነሣ በራሪው ሊዘልና ሊዘፍን ጀመረ ማታ በአምስት ሰዓት ግን ክፉውን አየር አለፍንና የተሻለ ሆነልን እንደዚሁ

ሁኖ አንድ ቀን አለፈ ። በማግስቱ ፲፫ ህዳር በምስት ሰዓት ተኩል ሳንሙባል የሚባል ደሴት በስጳንያ ምዕራብ ያለ አየን። የሆነ ሁኖ መንገዱን ልክ ቀንቶን መጣን ። በስድስት ሰዓት ተኩል ደህና ምሳ ተጋበዝን ። በተርሲራ አንድ ሺ ፬፻ ሚ ከፍ ብለን ስናልፍ አንበራ በተባለ ከተማ ጾስታ ጣልንላቸው ፡ ከዚያ በኋላ ደከም ያለ የደቡብ ነፋስ ነፈሰልን ። የጋዙ ጎተራ ከጥዋቱ ፀሐይ የተነሳ ነፋሱን የሚይዝ አንድ ተቀደደብን የራድዮ ተሌፎን ዋናና መሪ የሆነ አበጀው ። ደግሞም ሁለት ሞተር ቆመብንና ባራቱ ብቻ ኼድን ። ወደ ማታው ግን ነፋሱ ተሻለልን ። ማታ አንድ ሰዓት ሲሆን ነፋስ ከፊታችን ነበር ባንድ ሰዓት ፷ ኪሎ ሜትር ብቻ እንሄድ ነበር ። ያን ግዜ ደግሞ ከንዱ ፋውንድለን ድስባንክርና የጦር መርከብ ልንነጋገር ብለን ብንሞክር ራድዮዎችን እምቢ አለ ። እንደምንም ብለን ግን በሩቅ ወደ ሰሜን በኩል ካለው መርከብ ብርቱ ነፋስ ይመጣብችኋል የሚል ቃል ሰማን ቈየት ብሎ ግን በኛና በምንኼድበት መካከል ባለ ዓየር ነፋሱ አነስ ያለ መሆኑ በነፋሱ መስፈሪያ ልኩ ታወቀ አቅንተን ወደፊታችን ከመኼድ ግን ወደ ሰሜን ብንኼድ እንዲቀልልን አየንና ወደዚያ አቀናን በራሪውም ስለነፋሱ መመቸት ምቹነት በሰዓት ፻፵ ኪሎሜትር እስኪሄድ ድረስ ቀናለት ወደስድስት ሰዓት ሲሆን ጀምሮ የደቡብ ነፋስ ዝምአለና የምሥራቅ ነፋስ ተነሳ ። በሚከተለው ሌሊት ግን ከሙቀት የተነሣ አዛገሮች የሌሊቱን ቀጭን ልብስ ለስራ መልበስ እንደሚሻል መስሎ እስኪሰማቸው ድረስ ሆኑ ።ከተነሳን ሶስት ቀን በሆነን ጊዜ ግን አየሩ እየተሻለ ሄደ በራሪውም የሰሜን ነፋስ ሲነፍስ ሳለ ከንድ ትልቅ ቀስተ ደመና ያልፍ ነበር ስንኼድም አልፎ አልፎ ቀዳዳ ነበረበት እንጂ ጥቅጥቅ ያለ ጉም ነበር ነፋሱም ባንድ ሴኮንድ ፲፪ ፲፪ ሜትር ይኼድ ነበር ነገር ግን ነፋሱ እንደዚህ ብርቱ ሁኖ ሲቃወም ሞተሩም አራት ብቻ ሁኖ በጣም መፍጠኑ ግሩም ነበረ ። ደግሞ ከጉሙ ወጣን ያንጊዜ ሶስተኛ ሌሊታችን ነው ። ሙቀቱ ግን ሰውዬውን ትናንትና ጥዋት ስስ ልብስ ለብሰን ነበር አሁን ግን በብርድ እንደ ውሻ እንቀጠቀጣለን እስኪል ድረስ አሰነው ።ደግሞ ያለኝን ሁሉ ለበስሁ ማጆር እስኪቀናብኝ ድረስ አለ። በራሪው እንደ አሜሪካ ምሥራቅ ቍጥር በአራት ሰዓት ተኩል ከኩል ሌሊት በኋላ ወደቡስት ሲኼድ ነፋስ ወደሰሜን ምእራብ ይነፍስ ነበር ጥዋት ባንድ ሰዓት ተቀባዮችና ጋዜጠኞች መልተውበት ባሉ በኒዮርክ ላይ ሰፈፍን በራሪው በጎርማሳው ከተማ ላይ እየዞረ ይመላለስ ነበር፡ከዚያ ከ፱ ሰዓት ተሩብ ወደ፱ ሰዓት ተ፴፪ ደቂቃ ላክሁርት ወደሚባል ከተማ መጣንና በራሪው በዚያ ታየ ።ኋላ ፲ ሰዓት ተ፴፫ ደቂቃ ሲሆን በማረፊያ ደረስነና ገመዶቹን ወደታች ዘረጋን ወረድነም በዚያ ገብተን የነበርነውም ወጣንና ብዙ ደስ አለን ፡(ድሬክተር) ኤክነር በመንገዱ ሁሉ ሶስት ሰዓት ብቻ የተኛም እጅግ ደስአለው ፡በአውሮፕላኑ ውሥጥ የነበሩ በተቀባዮቹ በአመሪካ ሰዎች ደስ አላቸው የስፕሊኑ ጓዝ በዚህ አለቀ ።

ጋዜጣና ታሪክ የሚወድ ሳይታክትም የሚያነብና የሚመረምር ሰው ፊት ከነበሩ ሽማግሎች አሁንም ካሉቱ ሊቃውንትና ብልሆች ሰዎች ከሚመጡም ተጠባባቂ ምሉ ሰው ይባላል ።

ጋዜጣ የእግዚአብሔርን ስራና ትልቅነት የሰው አቅምና አኳኋን የሚገልጽልህ ነውና ጋዜጣ ለማንበብ ትጉ ሁን በኤውሮፓም ጋዜጣ ማንበብ የሚወዱና የማይወዱ የውቀታቸው ስፋት ልዩነት ብዙ ነው በማንበብህ ዓለምን ሁሉ አይ ነገርና ስራም መርምር ።

ተወልደ ብርሃን መድኅን።

ለኢትዮጵያ ልጆች አጭር ምክር።

ኢትዮጵያ ከቀድሞ ይልቅ ዛሬ የስልጣኔ ብርሃኑዋን እንደገለጸች በጣም እንረዳዋለን ።

መጀመሯ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ ምኒልክ የፊተኞቹ ነገሥታት ያላረጉትን የተማሪ ቤት አሠርተው በመተዋቸው ነው ።

ቀጥሎም የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ ልጆች እንዲማሩበትና ወደ እውቀት እንዲደርሱበት ብለው በገንዘባቸው የሠሩት ተማሪ ቤት እጅግ ደስ ያሰኛል ።ክቡር ራስ ኃይሉም እንደዚሁ ያደርጉ ይሆናል ።

፪ኛ ፡ ወደ ነገሥታት ወረቀት ብንጽፍ የሚያደርስልኝ የለ በሩ ጥብቅ ነው እየተባለ ብዙ ሰው ተቸግሮ ይኖር ነበር። ዛሬ ግን ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ተማክረው የሚነግርለት ላጣ ጉዳዩ በፍጥነት እንዲፈጸምለት ብለው ያደረጉት ሥራ እጅግ ድንቅ ነው ።ወረቀት ጽፈህ ረኮማንዲ አድርገህ በፖስታ ቤት ብታገባ ነገርህ ቀንቶ በፍጥነት ምላሹን ታገኛለህ።ይኸም ስለ ሕዝባቸው ጥቅም ያደረጉትን ርኅራኄያቸውን ይገልጻል።

፫ኛ፡ከሁን በፊት በኢትዮጵያ ያልተደረገውን ዛሬ ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን የማተሚያ ቤት አሠርተው ለኢትዮጵያ ልጆች ጥቅም ብዙ የሚሆኑ መጻሕፍትና ጋዜጣ ይታተሙበታል። በዚህም ኢትዮጵያ ከፍ ከፍ እያለች እንደሄደች ያስረዳናል። ይኸን የመሰለ ሌላም ሁሉ በያይነቱ ብዙ ተደርጓል።ለወደፊትም አውሮፓ የሔዱት ልጆች ተምረው ሲመለሱ ብዙ ረዳት እንዲሆኑዋቸው ተስፋ አለን። ኢትዮጵያ ቀድሞ በርታ በርታ ዘይቷና ፈትሏ አልቃለሁ ሲል እንደገና ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ዘይትና ፈትል አበጅተው ሊያበሯትና ሊያድሱዋት ይተጋሉና ስለዚህ እድሜና ጤናውን አብዝቶ ይስጣቸው ብለን ሁላችን እንለምን ።

ስለ ሕዝብ አሰለጣጠን ።

በማናቸውም አገር ሁሉ ስልጣኔ ገብቶታል የሚባለው በትምሕርት ነው እንጂ በጡብ በክርክር እርስበርስ በመጣላት ስልጣኔ ገባው ሲባል በወሬም ሆነ በመጽሐፍም ከቶ አልሰማንም። እንደምንሰማውስ የአውሮፓ ሰዎች ሃብታሞችም ሆኑ ድሆችም ሆኑ ልጆቻቸውን ሰባት ዓመት ከሆናቸው በኋላ ያላቸውን ገንዘባቸውን ከፍለው በሥርዓት ወደ ተማሪ ቤት ያገቡዋቸዋል ።

ከዚያም ሲማሩ ያድጋሉ ።ተምረውም ሲወጡ ከስተማሪያቸው የሚገባቸውን ወረቀት ይቀበላሉ ።ከዚያም በኋላ

በመንግሥት ቤት ሥራ ይይዛሉ ። ከስልጣኔ ወደ ስልጣኔ ከሐብት ወደ ሐብት ይደርሳሉ ይባላል ።

እንደዚህም ሁሉ መኳንንት ሆይ ይኸንን ጋዜጣ አንብባችሁ በሚቻላችሁ መጠን እንደዚሁ ልታደርጉ ይገባል ። ወንዶች ሴቶች ልጆቻችሁንም በሥርዓት ልታስተምሩዋቸው ይገባል ። ይልቁንም በአውሮፓ የበረታ የመንግሥት ሥራ እንደ ፖስታ ያለ ቴሌፎንም ቴሌግራምም ቢሆን ይኸን የመሰለውን አያሌ ነገር በየደነቱ ሴቶች ልጆች ናቸው የሚሠሩት ።

ባሕገራችንም ደግሞ በሥርዓት ተምረው ቢያድጉ ለመንግሥት እንዴት ያለ ትልቅ ጥቅም ይሆን ነበር ።

ሕዝብና መንግሥት ተደጋግፎ የሚጠቀመውን ካላደረገ መስማማትንም ካላገኘ ሥልጣኔ ባገር አይበረታም ። ሕዝቡም ደሀና የተዋረደ ሆኖ ከሰው በታች ይኖራል ።

ትምርትና መስማማት መተጋገዝ ያለው ሕዝብ ግን ከመት ወደዓመት ከፍ እያለ እየተሻሻለ ሥልጣኔው እየበረታ ሕዝቡም ከሰው በታች ከመሆን አርነት እየወጣ ራሱን እየቻለ ይሄዳል ።

ፍስሐ ወልደ ሚካኤል ።

(የዚሁ ተከታዩ በሚመጣው ጋዜጣ ይገባል ።)

የአውሮፓን ቋንቋ በተማሩ ኢትዮጵያውያን ላይ ያላግባብ ለተነገረው ቃል ምላሽ ፡

በዚህ ባለፈው ሳምንት በአእምሮ ጋዜጣ እንዳነበብነው የኢትዮጵያ ልጆች የፈረንጅ ቋንቋ የተማሩት አገሩን ፈረንጅ በገዛው ጊዜ ትርጁማን ሆነን እንበላለን ብለው ነው እንጂ ለሌላ ጉዳይ አይደለም ብሎ አንዱ አውርቷል ። የኢትዮጵያ ልጆች እንኳን ለሀገራቸውና ላንድ ጠንጠ መሬት ርስት ቢሆን ባዕድ ጉቦ ቢወስድባቸው ሲሆን በሥራት ሳይሆን በጉልበት መሬታቸውን ይወጡታል እንጂ እንዲያው በዋዛ ርስታቸውን አይለቁም እስቲ ተመልከቱ እነማናቸው እንዲህ ያለ ሃሳብ ያላቸው ። እንኳን በኢትዮጵያ ውስጥ ተወልደው አድገው የተማሩት ልጆች ይቅሩና በውጪያው አገር ተወልደው አድገው ተምረው ጣሙንና ጥበቡን የሚያውቁት ሰዎች እንዲህ ያለ ሃሳብ የላቸውም ። ከዚህ ቀደም ያየናቸው የጥንት ሰዎች ከውጭ አገር እንኳን ተምረው የሕጡት አገር መውደድን ሲያስተምሩና ሲያስረዱ ነበር ። ከዚያ ወዲህም ያሉት ልጆች ወደ ሰው አገር ሂደው በብዙ ልፋት እየተማሩ ራሳቸውን ሲችሉ አገራቸውን ለመርዳት አስበው መጥተው የሀገራቸውን መንግሥት ያገላግላሉ ። አገልግሎታቸውም ለበጣ የሌለበት እውነተኛ አገልግሎት ስለ ሆነ ጌቶቻቸው በየጊዜው ሁሉ ያመሰግኑዋቸዋል ። (ብርሃንና ሰላም ፳፱ቁጥር ተመልከት ።) በዚህ በአዲስ አበባም ግማሾቻቸው በመንግሥት ተማሪ ቤት ግማሾቻቸው በሌላ በሌላው ተማሪ ቤት እየተማሩ ለመንግሥታቸውና ለሀገራቸው በተቻላቸው ረገድ ሁሉ ያገለግላሉ ሌሎችም እጅግ ሳይታወቁ እየቀሩ ወደ ቤተ መንግሥት አገልግሎት አልደረሱም እንጂ በዚያው ባሉበት ቦታ ሆነው ለሃገራቸው ማሰብንና መተከዝን አልተዉም ። ግን ይህ ደፋሩ ሰውዬ እንዲህ ያለ የከፋ ስም ለወንድሞቹ መስጠቱ ብዙ ሰዎችን አሳዝኑዋቸዋል ። የሆነ ሁኖ ይህ በደል ለታሙት ብቻ አይደለም ዋና ሁለት ስህተት አለበት ። መጀመሪያ የኢትዮጵያ ከበርቴዎች አንዳንድ ልጅ እንኳ በገንዘባቸው እየረዱ ለማሰልጠን ያሰቡትን እንዳያደርጉ እንዲህ ያለ እንቅፋት በመንገድ ላይ አጋደመባቸው ። ሁለተኛ እነዚያ ሲገዙ ያላቸው ሰዎች ለካ እንዲህ ያለ ሐሳብ በኢትዮጵያ አለና ብለው እንዲገነግኑ አደረገ ።

አሁንም ከዚህ ቀደም የርሱን ወሬ አንብባችሁ ይህ ነገር ዕውነት የመሰላችሁ ሰዎች እንዳላችሁ እኛ ጥቂት ጥቂት የተማርነው ሰዎች ሐሳብ እርሱ ከወራበን ሐሳብ ልዩ ነውና እንዳትጠራጠሩ እንለምናችኋለን ። እኛስ ላገራችን ባስፈለገ ጊዜ ደማችንን አፍሰን ሥጋችንን ቆርሰን እናስከብራታለን እንጂ አንጥላትም ። ከዚህም ሁሉ በላይ ኢትዮጵያ እጅዋን ወደ እግዚአብሔር ዘርግታ የምትለምን አገር ናትና ይህ ሰውዬ ከወራበት መዓት እንዲሰውራት እናምናለን ። ሰውየውም ታላቅ በደል በድሏልና እንደገና ጀሮ አሳትሞ ከወንድሞቹና ከኢትዮጵያ ይቅርታ መለመን ይገባዋል ።

ተፈራ በልሁ ።

ስለ ብርሃንና ሰላም ምስጋና ለመጣልን ቃል ምላሽ ።

የአእምሮ ጋዜጣ ዲሬክተር ሙሴ አንድርያስ ከዋድያ ለጋዜጣችን ለብርሃንና ሰላም ። አእምሮ ፴፫ ቍጥር ። ምሥጋና ስላቀረበልን እጅግ ደስ ብሎናል ።

ልዑል አልጋ ወራሽም ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ ማድረጋቸው የኢትዮጵያውያንን አእምሮ ለማበርታት እንደሆነ የተረጋገጠ ነገር ነው ። አእምሮም በብርሃንና በሰላም እየኰለመሰ እንዲሔድ እንመኛለን ።

ብርሃንና ሰላም በመውጣቱም ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ሊመሰገኑበት ይገባል ።

ነገር ግን የአእምሮ ጋዜጣ ዲሬክተር ስለ ጻፈው የፍቅር ቃል ምሥጋናዬን በደስታ አቀርባለሁ ።

ብርሃንና ሰላምን እየተቀበሉ በደስታ ለሚያነቡትና ወደ ጋዜጣ የሚገባ ጥሩ ጥሩ ሐሳብ ለሚልኩልን ሰዎች ምሥጋና እናቀርብላቸዋለን ።

የቴሌግራም ቃል የኢጣልያ መንግሥት ሌጋሲዮን ።

አዲስ አበባ በ፳ ግንቦት ፲፱፻፲፯ ። የ፲፯ ግንቦት የሉት ወሬ ።

ሮማ ። የዲስቴፋኒ የገንዘብ ሚኒስትር ፓሪስ ላይ በተደረገው ጉባኤ የተባለውን ራፖር በኢጣልያ መንግሥት ምክር ቤት አቀረበ ይህንንም ያቀረበውን ራፖር የሚመረምሩ ብዙ መማክርቶች ነበሩ ። በኢጣልያን አገር የንግዱ አካሄድ በሺ፱፻፳፬ ዓ ም የዕቃው ወጭና ገቢ ቢታሰብ እያደር እየበዛ ሄደ ። የገቢውና የወጭው ዕቃ ዋጋ ድምር ሺ፬፻፳፱ ሚሊዮን ሊር ሆነ ። የገባው ዕቃ ብቻ ሺ፰፻፱ ሚሊዮን ሊር ካለፈው ዓመት በለጠ ። ወደ ውጭ አገር የወጣው ፫ሺ፩፻፱ ሚሊዮን ሊር ካለፈው ዓመት የሚበልጥ ሆነ ።

በልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

መጀመሪ ዓመት ፡ ቁጥር ፮ ።
1re ANNÉE № 6

ሐሙስ ጥር ፳፰ ቀን ፡ ፲፱፻፲፯ ዓ ምሕረት ።
JEUDI 5 FEVRIÉR 1925

ብርሃንና ሰላም
LUMIÈRE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ ሲገዛ ለፈለገ በ፬ መሐልቅ ይሸጣል ።

የጋዜጣው ዲሬክተር ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የራሱን ጉዳይ የሚያሳትም ሰው ዋጋውን እየከፈለ እናትምለታለን ።

እድኅን ሕዝበከ ወባርክ ርስተከ ።
ረአዮሙ ወአልዕሎሙ እስከ ለዓለም ።

ንዑ ወንትፌሣሕ ምስሌሁ ።
እስመ ርኢነ ብርሃነ ዚአሁ ።
እኔም ደረስሁበት አይቱ ሀሎ እያልሁ ።
በነቢያት ሁሉ እስከሁን ስለሰማሁ ።
ከንች ኢትዮጵያ የወጣ መኰንን ስላየሁ ።
ሰላምን ለማግኘት መጥቼ ሰገድሁ ።
መንበሩ ሣህሉ ።

ከዚህ ጀምሮ ስሙ እስከ ተጻፈበት ድረስ የፍሥሐ ነው ።

ስለ ወታደር ሥርዓት ።

የወታደር ሥርዓት በብዙ አገር እንደ ሰማሁት ። እስቀድሞ ወታደር ሥርዓት ይማራል ። በያይነቱ የተለየ ነገር አለ ።

መጀመሪያ እግራቸውን እንዴት አድርገው እንደሚያራምዱ ። ቀጥሎም ጌታቸው ሲመጣ እንዴት ያለ ሰላምታ እንደሚያቀርቡ ነው ።

ተጠንቀቅ የሚል ጥሩምባ ሲነፋም ድንቅ በሆነ ሥርዓት ብረታቸውን ይዘው ይቆማሉ ። ይኸን የመሰለውን ሥርዓት ከፈጸሙ በኋላ ስማቸው በቤተ መንግሥት መዝገብ ገብቶ ይጻፋል ። ልብስም በተለየ የወታደር ልብስ ወጥቶላቸው የሚሠሩትንም ሥራ ተቀብለው በሥርዓት ይኖራሉ ። አሁንም በዚሁ በአዲስ አበባ የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ጀምረውት ያሉ የወታደር ሥርዓት ዕፁብ ድንቅ ነው ። መንግሥት ያደረገውን ነገር ሁሉ ይከተለዋልና ለወደፊቱ ገና ገና ቢያደርጉት መኳንንት ሁሉ ሳያደርጉት አይቀሩም ። ወታደር በእንደዚህ ያለ ሥርዓት በመንግሥት መዝገብ ተጽፎ የሚሠራውንም ሥራ በተለየ ተቀብሎ ቢቀመጥ የተጻፈው ሥራውን በጥንቃቄ በፈጸመ ነበር ። ያልተጻፈውም በቶሎ ወደ እርሻው በገባ ነበር ።

እንግዲያ ላንድ ቀኛዝማች መቶ የሚያህሉ አሽከሮች ሥራቸውን ፈትተው በፊቱ ሲንጋጉ ቢውሉ ምን ይጠቅሙታል ። ከጩኸታቸውም ብዛት ያሰበው የልቡ ሐሳብ ይበተናል ።

ቀጥሎም ያከማቸውን ገንዘብ በልብሳቸውና በምግባቸው ይጨርሱታል ። ስለ ብዛታቸውም ምክንያት ከነሱ አሥር የሚያህሉት ከቀለብ ከደመወዝ ቢረሱ ብረታቸውን ይዘው ውድማ ይገባሉ ።

በሳምንቱ ተይዘው መጥተው ይሰቀላሉ ። በዚህ ትልቅ ጉዳት ይሆናል ። ይኸን የመሰለ ትልቅ ጉዳት የሚያመጣ ነገር በቶሎ ቢቀር ይሻል ነበር ።

ስለ ብርሃንና ሰላም ።

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ይኸንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ያሉበት ምክንያት ኢትዮጵያን ከስንፍና ጨለማ ወደ ዕውቀት ብርሃን ሊያደርሷት ታጥቀው ተሰናድተው ስለያዙዋት ይመስለናል ። ዳግመኛ ኢትዮጵያ እርስ በርሷ በመዋጋት እየደከመች ስትኖር መከፊ እስታራቂ ሁነው በመካከልዋ ብርሃንና ሰላም ሊያደርጉ ሙሉ ፈቃዳቸው ነውና ስለዚህ ይመስለናል ።

አስታዋይ አንባቢ ሆይ ብርሃን ከጨለማ እንዲበልጥ ዕውቀትም ከድንቁርና ይበልጣልና በኢትዮጵያ ብርሃንና ሰላም እንዲሰለጥን በሥራ ላይ መጠንከር ይገባሃል ።

ለኢትዮጵያ ልጆች አጭር ምክር ።

የኢትዮጵያ ልጆች ትንሽ ነገር ከፌ አድምጡ ።
አረቄ የሚሉት መጠጥ ይዘው ከሱቅ ተቀምጠው ሲሸጡ

የሚውሉ ብዙ የውጭ ሰዎች ናቸው ። እነዚህም በቤታቸው ከያይነቱ አረቄ ሞልቶ ሳለ ፩ድ መለኪያ እንኳ ወይም የመለኪያ እኩል አይቀምሱለትም ፡ ምክንያቱ ምንይሆን ብለህ ብትጠይቅ ስለዕውቀት ስለጥንቃቄ ነው ይሉሃል እንጂ ሌላ አይመልሱልህም ። ለኢትዮጵያ ሕዝብ ከሚሸጡት አረቄ እርሳቸው የሚጠጡለትስ ቢሆን ሰክረው የሸጡትን ገንዘብ ረስተው ወድቀው አእምሮዋቸው ጠፍቶ በተገኙ ነበር እንጂ የችንተገዢሚውን ከችንተገዢሚ የቤሳውን ከቤሳ ሲጽፉ ሲያገጣጥሙ ባልተገኙም ነበር ።

ደግም የንግዳቸውን ነገር ብናስበው ስቢርቶ የሚሉት እንደ እሳት የሚያቃጥል ነው ። እርሱንም ከሐገራቸው ሲያመጡ አሥር ኰንታል ያመጡ እንደሆነ ባሥር ኰንታል ሒሳብ ግብር ከፍለው ያገቡታል ። ከተከራዩት ቤት አግብተው ግን የሀገራችን ውሃ ተጨምሮ አሥሩን ኰንታል መቶ ኰንታል ያደርጉታል ። ዋና ንግዳቸውም የመቶውን ኰንታል ግብር በሥር ሒሳብ ሲሰጡ ነው ።

፪ኛ ። አረቄ አብዝቶ የጠጣ እንደሆነ ከመርዙ ብርታት የተነሣ አእምሮው ጠፍቶ ገንዘቡን እስከ ማጥፋት ይደርሳል ። ወደፊት ይህን የምታነቡ ሰዎች ልብ አድርጋችሁ ብታዩዋቸው አረቄ መጠጥ የሚያበዙ ሰዎች አእምሮዋቸው ጠፍቶ ተቅበዝብዘው የሚለብሱት አጥተው ታርዘው የሚበሉት አጥተው ተርበው ታገኙዋቸዋላችሁ እንጂ ደስ ብሏቸው አጊጠው አእምሮዋቸው ሰፍቶ አታገኙዋቸውም ። በዚህ ነገር ተወግተው የሚኖሩ ሰዎች ቀድሞ ከሞቱት የሚሻል ኑሮ የላቸውም ። ምሳሌ እንደሚል ወደመሸታ ቤት ከመሄድ ወደ ልቅሶ ቤት መሄድ ይሻላል እርሱ የሰዎች ፍጻሜ ነውና ይላል ። ወንድሞቼ ሆይ እንግዲያስ በእንደዚህ ያለ ሥራ ያሉትን ሰዎች አስቀድመን እንምከራቸው ። ባይመለሱ ግን የፍቅር መተባበራችንን ከነሱ እንለይ ። ክፉ ባልንጀራና ተናጋሪ ሴት ያሉት ሰው አእምሮው ይበታተናልና ።

ስለ ሥራና ስለ በዘንተኝነት ።

ኢትዮጵያ በእህል ከብዙ አገር ይልቅ የተሻለች ናት በአውሮፓ አገር ስለ እህል እንደ ሰማሁት ሁለት ጆንያ እህል ያለው ሰው ከታክልት ፍሬ ጋራ ከነቤተ ሰዎቹ ላመት ምግብ ይበቃቸዋል ይባላል ።

የአገራችን ግን ምግቡ እህል ብቻ ሲሆን ችግር አያገኘውምና እህሉ ብዙ መሆኑን በዚህ እንረዳዋለን ።

በመላዋ ኢትዮጵያ ከሌላው ይልቅ አራሹ ብዙ ይሆናል ለመነኰሴም ለወታደርም ቢሆን የሚመግብ አራሽ ነው ።

ከንዳንዱ ትልልቅ ደብር እንኳ ሰዓታት የሚቆሙ ፫፻ የሚያህሉ መነኮሳት ይገኛሉ እነዚህንም የሚመግባቸው ገበሬ ነው ።

ዳግመኛ ወታደር ብዙ ነው ። ወታደር የበዛበትም ምክንያት ይህ ነው ። አንድ ልጅ እያረሰ ግብሩን ለመንግሥት ሲሰጥ ኑሮ ባንድ ምክንያት ከንዱ ጋራ ቢጣላ ተነሥቶ ወደ አደባባይ ይመጣና ላንድ የሻለቃ አሽከርነት ያድራል ያም የሻለቃ ጠመንጃ ይሰጠዋል ። ሥራ አይሠራለትም በሄደበት ሥፍራ ሁሉ ብረቱን ይዞ በኋላ በኋላው ሲሮጥ ይኖራል ።

ለመንግሥት ግብር በሚሰጥበት ወራት ግን አባቱንና እናቱን ግብር አምጡ ይልዋቸዋል እነዚያም ፩ጠርሙዝ አረቄ ገዝተው ልጃቸው ወዳለበት ጌታ ይሔዳሉ ። እንዲህም ይሉታል ጌታችን ሆይ ልጃችን እርስዎን ያገለግላል እኛን ግን ግብር አምጡ እያሉ ያስቸግሩናል የቸርነትዎን ሥራ ይሥሩልን ይላሉ ። ጌትዮውም ያደረገ አድርጎ ወረቀት ይሰጣቸዋል ። ወረቀቱም እንዲህ የሚል ነው ። እነሱ ነፃ ይሁኑ ዕዳውን ግን ባገር ያሉ ገበሬዎች ይክፈሉት የሚል ነው ። ይኸን ወስደው ለጭቃ ሹሙ ይሰጡታል ። ጭቃ ሹሙም አስነብቦ እንደዚያው ያደርጋል ። ይኸንንም የመሰለ ሥራ የሚበረታ ባገራችን በትግሬ ነው ። በዚያ አገር ያሉ ገበሬዎችም ይህ ነገር ልባቸውን ያቃጥለዋልና የሚያርሱ ፰ ልጆች እንዳሉት በሬዎቹንና ማረሻውን ሽጠ ሂዱ እናንተም እየተከተላችሁ እንዲሁ አድርጉ ይላቸዋል ልጆቹም ሄደው አደባባይ ላደባባይ ሲሮጡ በዘንተኞች ሆነው ይቀራሉ ። ስለዚህም ምክንያት በዘንተኛ በዝቶ ሠራተኛ አንሶ ይገኛል ።

ፍሥሐ ወልደ ሚካኤል ዘብሔረ አክሱም ።

ከከንቱ ሐሳብ ስለ መጠበቅ ።

ባገር ቀድሞ ያልነበረ መሣሪያና ሥልጣኔ ሲመጣ የሕዝብ መቃወምና መጥላት በፊት የዓለም ሕዝብ ሳይሰለጥን በሁሉም አገር እንደነበረ እንሰማለን ። እንደኛ እንደዛሬ ሀሳባችን ሁሉ ሐዲስ መሣሪያ ሲወጣ ሕዝቡ የሚጎዳና ጥቅሙ የሚጠፋበት የሚጎልበት ይመስለው ነበረ ። ለምሳሌ ፡ በእንግሊዝ አገር ሳሙኤል ክሮምቶን የሚባል ፩ ሰው መጀመሪያ ፈትል የሚፈትል መኪና ቢያወጣ በደሞዝ ተቀጥረው ፈትል የሚፈትሉ ሰዎች ብዙ ጠሉት ለመግደል እስቲመኙት ደረስ ይባላል ። ደግሞም ፩ ሰው መጀመሪያ ባቡር ሲሰራ በእንግሊዝ አገር የሚሄድ ባቡር ቢያወጣ ሕዝቡ ሁሉ ጠላው ። ባቡሩ በደረሰበት አገር ዝናም አይዘንምም ለእህልም አይበጅም ከብቶችንም ያደነብራል ብለው ብዙ ነገር አወሩበት ይባላል ። ወሬው እንደዚህ ስለተወራ ሐሳባቸው ግን ይህ አልነበረም ። ነጋዴዎቹም ባቡሩ ከተሸከመ የምንጭነው ዕቃ እናጣለን ፡ አጋሰሶቻችን ሥራ ፈተው ገንዘብ እናጣለን መስሏቸው ነው ። ባላገሮችም ከብት ብናረባ አጋሠሥና የከርቻ ከብት ሰው አይገዛንም መስሏቸው ነው ። ለጊዜው ግን እንደዚህ አልሆነም ። በእንግሊዝ አገር የሚረባ ከብት ባይበቃ ከሌላው አገር ቁጥር የሌለው ከብት ይሄዳል ። ሄደ እንጂ ከብት አልረከሰም ።

ዳግመኛም በኛ አገር እንኳ የስፌት መኪና የወጣ ጊዜ በጅ ልብስ የሚሰፉ ሰዎች መኪና የሰፋው ልብስ ይበጣጠሳል ብለው ስላወሩ ብዙ ሰዎች ልብሳቸውን በመኪና ሳያሰፉ ቆይተው ነበር ። እነዚህም ልብስ ሰፊዎች ይህን ወሬ ማውራታቸው የስፌት መኪና ጥቅማቸውን ለማጥፋት የመጣ መስሏቸው ነው ። ነገር ግን የስፌት መኪና አመጣጥ የሰፊዎቹን ጥቅም ለማስፋት መሆኑን አስተውለው አለመረዳታቸው የሚገርም ነው ። ቀድሞ ለሰው ልብስ የሚሰፋ ሰው ሲሰፋ ውሎ የሚያገኘው ጥቅም መብልና ሁለት ብርሌ መጠጥ ነበረ

ግን በመኪና የሚሰሩ ስራ እቤቱ ኩርቶ ተቀምጦ በቀን ሁለት ከስት ብር አግኝቶ ይውላል ።

ባቡሩም ወደ አገራችን በመጀመሪያ ሲመጣ ብዙ ሰዎች አገር ያስርባል ዝናምም ያጠፋል ብለው ሲአወሩ ነበረ ። ምክንያቱም ሰውንም እቃውንም ባቡር ሲሸከመው ጊዜ ከብቶቻችን ስራ ፈተው የሚውሉ ጥቅማቸውም የሚጠፋ መስሏቸው ነው ። ነገር ግን እንደዚህ አልሆነም ባቡሩ በደረሰበት አገር ሁሉ ከብት ብዙ ስራ ያገኝ ጀመረ እንጂ ። አሁንም ከለጋር እስከ አራዳ እንኳ የአንድ ብቅሎ ክራይ አላድ ነው ከአፋሲ ወደ ባቡር ቡን የሚጭኑ ነጋዴዎች ዛሬ በሁለት ቀን መንገድ ሲሄዱ ቡን ጭነው ፳ብር ። ሲመለሱ ሸቀጥ ጭነው ፴ብር ያገኛሉ ሲሄዱና ሲመለሱ በ፩ በቅሎ ክራይ ፶ብር ማግኘታቸው ነው ባቡር በሌለበት አገር ግን ዛሬ በ፲፫ ቀን መንገድ ፯ብር እንኳ አያገኙም ፤ ባቡሩ ቢበዛ ግን የነጋዴ ጥቅም ብዙ ይሰፋል ። አሁንም ገበሬዎች የርሻ መኪና ሲያዩ እኛ ምን ሰርተን ልንኖር ነው ይላሉ ጸሐፊዎችም የማተሚያ መኪና ሲያዩ ይህ መኪና ጥቅማቸውን ሊያጠፋ የመጣ ይመስላቸዋል ግን የሱ አመጣጥ ጥቅማቸውን ሊያሰፋ እንደሆነ ጥርጥር የለውም ፤ ስራ ወዳጅ ንቁዎች ብልሆች ከሆኑ ያ መሳሪያ የነሱ መሳሪያ ሆኖ መጠቀሚያቸው ይሆናልና ፤ ከእጅ ስራ ይልቅ የመኪና ስራ እንዲያፋጥንና እንዲጠቅምም በስፋት መኪና አይተናል ። ደግሞ ልጆች የሚያሰለጥን የኤውሮፓን ትምሕርት ሲማሩ ቢያዩ እነዚህ ልጆች ተምረው ስራ ሲይዙ የእነሱን ስራ የሚወስዱባቸውና ጥቅማቸውን የሚያስቀሩባቸው የሚመስላቸው ሰዎች ምናልባት ይኖሩ ይሆናል ፤ ነገር ግን እንደዚህ አይደለም የሚማሩ ልጆች መማራቸው ከዚህ ቀደም የነበረውን የሰውን ጥቅም ለመውሰድ ለማጥፋት አይደለም በኢትዮጵያ ያልነበረውን ሐዲስ ጥቅም ላገሩ ለማውጣት ነው እንጂ ። ለምሳሌ አሁን ፩ልጅ ብር ወርቅ ከመሬት ማውጣት የመዓድናት (የመንርሎጅ)ስራ ተምሮ ቢመጣ የማንን ጥቅም ወሰደ ይባላል ከመሬት ተቀብሮ ከዚኅ በፊት ያልነበረውን ጥቅም አወጥቶ ሐዲስ ጥቅም ይጨምራል እንጂ ።

ደግሞ ሌሎች ከአበባ ሽቶ ማውጣትን ፣ ከሣር ከሮጌ ጨርቅ ፋብሪክ አቁሞ ወረቀት መሥራትን ወይም የብርጭቆ የሳሀን መስሪያ ፋብሪክ አቁሞ መስራትን ወይም ለመብራት የሚሆን ጋዝ ከምድር ማውጣትን ይህን የመሰለ ቁጥር የሌለውን ስራ ተምረው ሲሰሩ የማንን ጥቅም ወሰዱ ይባላል ? ጥቅም ጨመሩ ስንፍናን ችግርን ታግለው ባሉ ሐዲስ ጥቅም አወጡ ይባላል እንጂ ። የእውቀትንም ሥራ ሚልዮን ሰው ቢማር እንደዚሁ በየይነቱ ሚልዮን ሥራ እኛ ያላወቅነው አለና ወንድሞቼ ሆይ እናንተ በምትሠሩት ሥራ መኪና ቢወጣለት አትዘኑ ። ይልቅስ ያንን ሥራ በመኪናው መሥራትን እንድትለምዱ ትጉ ፤ ስንት ፲ ሺ ፋብሪክ መኪና በወጣበት በቆመበት አገር የሕዝብ ጥቅም ሚልዮን ጊዜ ከፍ ጥቅም እንዲሰፋ ጠይቁ ስሙ እንጂ መልክም መሣሪያ አዲስ ሥልጣኔ ስታዩ የናንተን ጥቅም ለማጥፋት የሆነ መስሏችሁ አትታገሉ ስል ለወንድሞቼ በትህትና አመለክታለሁ ።

ፊታውራሪ ዴሬሳ ።

በጥር ፳፫ ቀን ፲፱፻፲፯ ዓ ም ። ክፉ የሐሰት ወሬ ያወሩ ሰዎች በልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ችሎት ቀርበው ከተመረመሩና ነገሩን ከተናገሩ በኋላ የተነበበላቸው ቃል ከዚህ ቀጥሎ ያለው ነው ።

ለመጋባት እድሜአቸው ያልደረሰ ትንንሾች ኅፃናቶች ልጆች ባባትና በእናታቸው ፈቃድ ተዳሩ የሚሉ ወሬ ሰምተን ከቶ የነዚህ የኅፃናት ልጆች ጋብቻ የተደረገበት ምክንያቱ ምን ይሆን ብለን ብንጠይቅ ሀገር ለማጥፋት በሕዝብ ላይ ሁከት ለማስነሣት የፈለጉ ክፉ ሰዎች በየሀገሩ እየዞሩ ያልተጋቡትን ኅፃናቶች ልጆች መንግሥት እየመለመለ ሊወስድባችሁ ነው እያሉ ስለ አወሩላቸው ነው ። በቡልጋም እንዲሁ ተደርጓል ሲሉ ብንሰማ በሀገርና በሕዝብ ላይ ይህን ያህል የሐሰት ወሬ ሲወራ ሰምተን ዝም አንልም ብለን እድሜያቸው ሳይደርስ ልጆቻቸውን ያጋቡትን ሰዎች እየያዛችሁ አምጡ ብለን ሹማምቶችን አዘዝን ። እናንተም እየተያዛችሁ ከመጣችሁ በኋላ ብንጠይቃችሁ እድሜዋ ካንድ ዓመት እስከ ሁለት ዓመት የሆናት ልጅ ድራችሁ ተገኛችሁ ።

ቡልጋን የሚያህል የጥንት ክርስቲያን ሰዎች ሆናችሁ አዋጅ ሳይነገርባችሁ ሹም ሳያዛችሁ እንዲያው አንዳንድ ክፉ ሰዎች ባወሩት የሐሰት ወሬ ከክርስቲያን ሕግ ወጥታችሁ አገር አሸብራችሁ እንደዚህ ያለ መጥፎ ሥራ መሥራታችሁ እጅግ ያሳዝናል ።

በእገሌ አገር እንደዚህ ተደረገ የሚሉ ወሬ ብትሰሙ እንኳን ወደከተማ መጥታችሁ ከሹም ጠይቃችሁ ወደ ሀገራችሁ ተመልሳችሁ የሐሰት ወሬ ነው አይዞአችሁ ብላችሁ አገር አረጋግታችሁ ክፉ ወሬ አውሪዉን ይዛችሁ ላገሩ ሹም መስጠት ይገባችሁ ነበረ እንጂ የተወራውን የሐሰት ወሬ ሁሉ ማመንና መቀበል አይገባችሁም ነበረ ።

ወደፊትም እንደዚሁ ያለ የሐሰት ወሬ የሰማችሁ እንደሆነ በቶሎ ለሹም ነግራችሁ ወሬኛውን እጁን ይዛችሁ መስጠት ነው እንጂ የሐሰት ወሬ እየተከተላችሁ ከሥርአት የወጣ የማይገባ ሥራ ለመሥራት አታበሉ።

አሁንም እድሜያቸው ደርሶ በሚገባ በሥርዓት ከተጋቡት ልጆች በቀር እድሜያቸው ሳይደርስ በማይገባ የተጋቡትን ትንንሾች ኅፃናቶች ልጆች ወደ ቤታችሁ እየመለሳችሁ ቢቻላችሁ መጽሐፍ አስተምራችሁ ፤ ባይቻላችሁም እንደ ሀገሩ ልማድ ሥራ መሥራት እያስተማራችሁ አሣድጋችሁ አክለ መጠን ሲያደርሱ እንደ ክርስቲያን ሕግ አጋቧቸው ።

እነዚህም የሐሰት ወሬ እያወሩ ያስደነገጧችሁን ሀገር ለማጥፋት የክርስቲያንን ሕግ ለማፍረስ የተነሱትን ክፉ ሰዎች እየፈለግን እየያዝን እንቀጣቸዋለን ።

እናንተ ግን ጥፋታችሁ ገና መዠመሪያ ስለ ሆነና ባለማወቅ ስለ አደረጋችሁት የዛሬን ምረናችኋል ። ለወደፊቱ እንደዚህ ያለ የሐሰት ወሬ ስትሰሙ ያወራውን ሰው ይዛችሁ ለሹም ያልሰጣችሁ እንደሆነ ። የሐሰትም ወሬ ተከትላችሁ እንዳሁኑ የማይገባ ሥራ የሠራችሁ እንደ ሆነ ብርቱ ቅጣት ትቀጣላችሁ ። ጥር ፳፬ ቀን ፲፱፻፲፯ አዲስ አበባ ።

የጃን ሜዳ እሽቅድድም ።

ጥር ፳፰ ቀን ሐሙስ በጃንሜዳ የእሽቅድድም ማኅበር መሰብሰብ ሆኑዋልና ይኸንኑ በደስታ እናስታውቃችኋለን የእሽቅድድሙንም ሁናታ በሚመጣው ጋዜታችን እንጽፋለን ።

ከውጭ አገር የሚመጣ ልዩ ልዩ ወሬ ።

በሎስ አንጀልስ በካሊፎርኒያ ከአንድ የንግድ ቤት ሚዛኑ ፫፻ ኪሎ የሚያህል ገጹ ደግሞ ፬፻ የሆነ አንድ ትልቅ መጽሐፍ አሰናድቷል የሚል ጋዜጣ አነበብን ።

ጆባኒ ባቲስታ ቦታላ የተባለ የኢጣልያን ሰው ፡ ሚራፊዮር በሚባል ቦታ ፫፻፫ ኪሎ ግራም የተጫነች ኤውሮጵላን ይዞ ወደላይ ፬፻ ሜትር ያህል ከፍ ብሎ ፩ ሰዓትና ፶ደቂቃ ያህል ቆይቶ ደህና በመውረዱ አስደነቀ ። ወደላይም ከፍ ብለው ሳሉ ቅዝቃዜው ከዜሮ በታች ከ፴፫ እስከ ፵ግራድ ድረስ ሆኖ ነበር ።

በቴሌግራፍ የመጣ ቃል ፡
ከኢጣሊያ መንግሥት ሌጋሲዎን ።

አዲስ አበባ ጥር ፳ ፲፱፻፲፯ ዓም ።
የ፲፯ና የ፲፱ ጥር ፡ የለት ወሬ ።

ማድሪድ ። የስፓኝ ሚኒስትሮች ለጄኔራል ፕሪሞደሪቤራ በብዙ የሕዝብ ሸማግሎች ያገዛዙን ደግነት ለማስረዳት የተፈረመ ማስታወቂያቸውን ልከውለታል ምስጋናውንም አበርትተው ይናገራሉ ።

ሚሌላ ። የጄኔራል ግሮ ወታደሮች ያልታርን ተራራ ይዘው ከጠላቶቻቸው ፶ሰው ገድለው ብዙ ሰው አቆሰሉባቸው ፤

ሮማ ። የኢጣልያን ሚኒስትሮች ዛሬ ስለምግብ ውድነት ጉባኤ አድርገው ስለዚህ የሚሻል ለማድረግ ሲመክሩ ዋሉ ።

ሎንዶን ፤ በሚመጣው ሳምንት የየመንግሥቱ መልክተኞች የጀርመን አገር ስለመጠበቁና ኰሎኒያቸው ስለመያዙ ወታደሩም ወደ እያገሩ እንዲሄድ አገራቸውም እንዲለቀቅላቸው በፊርማቸው እንዲያስታውቁ ታዝዘዋል

ስቶኮልም ። ብራንድንግ ሙሉ ጤና ስለሌለው ጠቅላይ ሚኒስትርነቱን ሳንድሰር ለሚባል ሚኒስትር አስረከበ

ቤኤና ። የፊተኛው ጠቅላይ ሚኒስትር ሰይፐል እንደ መልክተኛ አለቃ ሆኖ ወደ ሮማ ይሄዳል ።

ቡካሬስት ። የሬማኒ ንጉሥ ከጥቂት ቀን ጀምሮ ቡአ ወርዶት ታሞ ነበር ነገር ። ግን ወፔራሲዮን ከደረጉለት (ከተበጣ) ወዲያ በጐ ሁኑዋል ።

ፓሪስ ። የኢታዝኢኒ ፕሬዚዳንት ኩልጅ መሣሪያ ስለመተው ነገር ፩ ጉባኤ ሊያደርግ ነው ተብሎ ስለተወራው ሙሴ ሔሪዮ እንዳላችሁ ይሁን ብሎ አስታወቃቸው ።

ሮማ ፤ ዛሬ በሴናተሮች ቤት አዲስ የወጣው የኢጣሊያ መንግሥት የጦር ደምብ ተመረመረ ።

ኔፕልዝ ፤ የአርጀንቲን በልዩ የተላኩ መልክተኞች በፔሬትዝ ፕሬዚዳንትነት ኔፕልዝ ገቡ ። የንግድ ማኅበሮች በክብር ተቀበሏቸው መልክተኞቹም የመጡት በኢጣልያና በአርጀንቲን መካከል ንግድ ለማስፋት የሚያስፈልገውን ምክር ለመማከር ነው ።

ፍሎሬዝን ፤ የዓለም መንግሥታት ከያገራቸው የሚገኘውን ነገር የሚያሳዩበት ከ፳፭ አብሪል (ማዚያ) እስከ ዡዋን (ሰኔ) መጨረሻ ይከፈታል ። ይኸውም የሚደረገው በሮፓና በአሜሪካን መንሥግታት መካከል ነው ።

ሎንዶን ፤ ንጉሡ ለሚስተር አስክዊት የኰንት ማእርግ ሰጧቸው ጋዜጣዎች ሁሉ ስለመሾማቸው የደስታቃል ጻፉላቸው

ቡካሬስት ፤ የሩማኒያ መንግሥት ለፓርላሜንት በሩማኒ አንድ ጳጳስ እንዲሾም ሐሳቡን አቀረበ ።

ሳንሬሞ ፤ ባለ ትልልቅ መርከብ ማኅበሮች በሳሬንሞ ስለሚደረገው የመርከብ ጉባኤ ወኪሎቻቸውን ላኩ ።

ቤርሊን ፤ አሊዮች መንግሥቶች ለጀርመን ጠቅላይ ሚኒስትር የኰሎኝን ወደፊት መለቀቅ የሚያስታውቅ ደብዳቤ ላኩለት የጀርመን ጠቅላይ ሚኒስቴርም እስካሁን አለመለቀቁ ስለምንድነው አሁንም በቶሎ እንዲለቀቅ ብሎ መለሰ ።

አዲስ አበባ ጥር፳፪ ፲፱፻፲፯።
የጥር ፳ቀን የለት ወሬ ።

ሮማ ። ትላንት የማቴዎቲ መሞት የተመረመረበት ወረቀት ሁሉ ከፍርድ ሚኒስትር ቤት ወደ ትልቁ ችሎት ተላከ ። የትልቁ ችሎት ፕሬዚዳን የምስክሮቹን ቃል መመርመር ጀመረ ።

በሴናተሮች ቤት እስቴፋኒ የገንዘብ ምኒስትሩ ስለ ሠራተኞች ደሞዝ ማሳደግ የተነሳ እንዲህ አለ ። ለሠራተኞች ደሞዝ ከማሳደግ አስቀድሞ የገህዘቡን ገቢ ማስተካከል ይሻላል ብሎ አመለከተ ።

ሊስቦና ። ፖርቶ አሌሳኖ የሚባል ትኒሽ ደሴት መቶ ያህል ዓሣ አጥማጅና ነጋዴዎች የነበሩበት የባሕር ሞገድ አጠፋው ። በዚያ የነበሩ ሰዎች ሁሉ ሞቱ አንዳንድ ዓሣ አጥማጆች በጀልባ ከሄዱት በተቀር ።

ቤርሊን ። የጀርመን መንግሥት ስለ ኰሎኝ መለቀቅ ነገር እንዲህ ብሎ መለሰ እኛ የታዘዝነውን ግዴታ ሁሉ ፈጽመናል እስካሁን ኰሎኝ አለመለቀቁ ስለምንድነው አሊዮች ከንግዴህ ወዲያ ኰሎኝን የሚይዙበት ምንም ምክንያት የላቸው ።

ሎንዶን ። ፪ቱ የንግሊዝና የግብፅ መንግሥት ደብዳቤ ይላላካሉ ። ይኸውም መልካም ወዳጅነታቸው እንደ ጥንት መመለሱን ያስረዳል ። የንግሊዝ መንግሥት ከቤ እስታክሞት ወዲህ የጠየቀውን ሁሉ የግብፅ መንግሥት ስለተቀበለ ። ሎርድ አሌንቢ የግብፅ ሐይ ኰሚሽነር ለግብፅ ጠቅላይ ሚኒስትር ደብዳቤ ላከበት ። ደብዳቤውም እንዲህ ይላል የንግሊዝ መንግሥት ለሱዳን ማጠጫ ብዙ ውሀ አይወስድም የግብፅን መንግሥት ለመጉዳት ይህኑም ወሀ ለሱዳንም ለግብፅም እንዲበቃ የሚመረምሩ ሰዎች ከ፲፭ ፌብሪዮ (የካቲት) ጀምረው እስከ ፴ ዡዋን (ሰኔ) ድረስ ሥራቸውን ያስታውቃሉ ።

በልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

መጀመሪያ ዓመት ፡ ቁጥር ፯ ።
1 re ANNÉE № 7

ሐሙስ የካቲት ፭ ቀን ፲፱፻፲፯ ዓ ም ።
JEUDI 12 FEVRIÉR 1925

ብርሃንና ሰላም
LUMIÈRE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፫ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፱ መሐልቅ ይሸጣል ።

የጋዜጣው ዲሬክተር ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የራሱን ጉዳይ የሚያሳትም ሰው ዋጋውን እየከፈለ እናትምለታለን ።

ብርሃንና ሰላም ።

ጥንታዊነቱን በሥራው ገለጠ ። ደግሞ ብርሃን በወልድ ፡ ሰላም በመንፈስ ቅዱስ እንዲመሰሉ በቅዱሳት መጻሕፍት ክብዙ አንቀጽ ላይ ይገኛል ። ይኸውም ፈኑ ብርሃነከ ፈኑ ሰላመከ ያለውን የመሰለ ሁሉ ነው ።

ስለዚህ ብርሃንና ሰላም ታስበ የነበረውን ጥንታዊ ሥራን ገለጠ እንጂ እንግዳ ሥራ (ስብከት) አይሰብክም ። እንዲህ ከሆነስ ያባቱን ገንዘብ ፡ ገንዘብ ያደረገ ልጅ ልዕልናን ገንዘብ ያደርጋል ብሎ ዮሐንስ አፈ ወርቅ እንደተናገረ አሁንም ስለ ሀገራችን ጥቅም የሚጥሩልንን ብርሃንና ሰላምን አመሥግነን ብንቀበል የኢትዮጵያ መንግሥት ብርሃናዊት ሰላማዊት ሆና ትኖራለች ። ብርሃንና ሰላም ለሆኑ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ለልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንንም የተጀመረው የዕውቀት ብርሃን በዘመናቸው እንዲሰለጥንና ፍጻሜው በሰላም እንዲሆን እንመኝላቸዋለን ።

ዳግመኛም ብርሃንና ሰላምን አመሥግነን ብንቀበል ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስም ምሳሌ አድርገው ፈኑ ብርሃነከ እግዚኦ አምላክነ ሰላመ ሀበነ ብለው የተናገሩ መጻሕፍትን ማመን ማመሥገን እንደሆነ አለጥርጥር የታወቀ ነው ።

የዘለዓለም ሕይወት የሚገኝባቸው መጻሕፍትን ሹ ፡ መርምሩ ብሎ ጌታ እንደተናገረ እናውቃለንና ።

ለዚህም አንድ ምሳሌ እናሳያለን ። ይህ በተፈጥሮ የተሰጠን የዓይናችን ብርሃን ከፀሐይ ብርሃን ጋራ በተዋሐደ ጊዜ ፡ ፀሐይ የደረሰበትን ሁሉ ያለድካም እንዲያሳየን ብርሃንና ሰላም ከልባችን ጋራ ተወሕዶ በዕረፍትና በጤና መልካሙን ነገር ሁሉ ያሳየናል እንጂ ፡ ጨለማ በሆነ ጊዜ ያይናችን ብርሃን ብቻ ምንም አይጠቅመንም ።

አሁንም ጨለማ የማይፈራረቀው ጠፈር የማይከለክለው እውነተኛው ብርሃንና ሰላምን ለማየት ያበቃን ፈጣሪያችንን ብርሃን ትዕዛዝከ በዲበ ምድር ። ሰላመከ ሀበነ እያልን እናመሥግነው ። የደጉና የታላቁ ንጉሥ የአፄ ምኒልክንም ስም አጠራር ወዝክርከኒ ለትውልደ ትውልድ ብለን በክብር እናነሣሣቸዋለን ።

አለቃ ዳኜ ።

እምይእዜሰ ይኩን ፍሥሐ ወሰላም ።

ብርሃንና ሰላም ሀገሩን ገባኝ ።
እንግዲህ ጨለማ ምንም አልተገኘ ።
ስብሐት ለከ ብርሃንና ሰላም ጋዜታ ።
አንተን ስላሳየን ደግሞ ወራሴ መ የሁሉ ጌታ ።
ንሴብሖ ወናሌዕሎ ለንጉሡ ስብሐት ጥዋት ማታ ።
[illegible]
አቤቱ ክለመፋቀር ክልለኝ በከመ ስሙር ወልታ ።
በብርሃንከ ንርዓይ ብርሃነ ።
ብርሃንና ሰላም ከልጋ ወራሽ በራ ።
ሠልጥና ነበረች ጭለማ አመንዝራ (መከራ)
እንግዲህስ ወዲያ ምንም አንፈራ ።
የተፈሪን ጥበብ አልበ ዘየአምራ ።
ዳዊት ይሴብሕ ወይዜምር ዕዝራ ።

ዘገየ ተገኘ ኃይሉ ።

ለኢትዮጵያ ልጆች ምክር ።

የኢትዮጵያ ልጆች ይህችን ባጭር የጻፍኳትን ምክሬን እንድታስተውሉልኝ እለምናለሁ ።

ይኸ ጊዜያችን መልካም እውቀት በየጊዜው ይወልድልናል እኛም ወንድማማቾች የሆን ሁሉ የኢትዮጵያ ልጆች በርትተን ይህነን ጊዜያችንን በልብ ንጽሕናና በበረታ እውቀት ብናግዘው እንዲሁ ጊዜያችን የወለደልንን ጥበብ እኛም በየ

ጊዜው እናገኘዋለንና ዋዛንና የሚያሰክር መጠጥን ስንፍናን ከኛ አርቀን እንበርታ ፡፡

በሰሎሞንም ምሳሌ እንዲህ ተጽፏል በ፳፪ ምዕ በ፲፩ ቊ የልብ ንጽሕና የሚወድ ጸጋ በከንፈሩ ላይ ትሆናለች ንጉሥም ወዳጁ ይሆናል ይላል ደግሞ በ፲፪ ቊ የእግዚአብሔር ዓይኖች እውቀት ይጠብቃሉ ፤ የወስላታውንም ነገር እርሱ ይገለብጣል ይላል ፤ ስለዚህ እውቀት ከተገኘ ሰው የሚታሰበውን ሁሉ ስለ መንግሥቱ እርዳታ ማናቸውንም ቢሆን ለማድረግ ቢጥር ሥፍራ በማጣትና በመቸገር ብዙ ነገር ይመክናልና የእውቀት ምልክት የታየበት ሁሉ ሥፍራና ሥራ ያገኘ እንደሆነ እውቀቱ እንኳ በጣም የተደላደለ ባይሆን ሰውነቱና የመሠረት አሳቡ የዕውቀት ስለሆነ ማናቸውም ሰው ቢሆን ሥፍራና ሥራ ሲይዝ በጐደለ እውቀቱ እየሞላበት በያዘው ሥራ ላይ ለሀገሩና ለመንግሥቱ የተደላደለ ጥቅም ያለው ሥራ እመስራት ይደርሳል ተብሏል ማለት እየሰማ የሀገራችን የኢትዮጵያ ልጅ በጣም ነቅቷል እንዲህ ረዳት ካገኘ ለሀገሩና ለመንግሥቱ ወደ ፊት የበለጠ ሥራ እንዲሰራ የታወቀ ነው ፡፡

በኢትዮጵያ ሀገራችን የብረት ሥራና የብር ፡፡ የወርቅ ፡፡ የሸማ ፡፡ የሥፌት በየይነቱ ፡፡ የእንጨት ፡፡ የደንጊያ ፡፡ የሸክላም ፡፡ የመጽሐፍ ፡፡ የጽሕፈት ፡፡ የምክርም ፤ ሌላም ሁሉ በየይነቱ ይህነን የመሰለውን አጥርተው የማየውቁ ብዙ ናቸው ፡፡ እነዚህንም በየይነቱ የተጻፉትን የሚያውቁ ሰራተኞች የሚችሉትን ሥራ ሁሉ እየሰሩ እንዲኖሩ መንግሥታችን በጣም ይቀበላቸዋል ፡፡ እንዲህ እንዲህ ያለው ሰራተኛ ወደ መንግሥት እየቀረበና ተመችቶት እየሰራ ቢኖር እውቀትም እየሰፋ ሌላውም ይህነን እያየ በርትቶ ለእውቀት ሥራ ይጣጣራል ደግሞ ስለዚህ እውቀታቸው የተደላደለ አጥርተው የሚሰሩትን ጥቂትም እውቀት የሚጐድላቸውን መንግሥት ለይቶ በመዝገቡ እንዲያውቃቸው እነዚሁም ሰራተኞች ወንድሞቻችን በጥበብ እንዲታወቁ ቢጥሩ የበለጠ መልካም ነገር በሆነ ነበር ፡፡ ያልታወቁትንም መንግሥት በመዝገቡ ጽፎ ካወቃቸው ሥራ የሚፈታበት ጊዜ ስላልሆነ የታወቁት ሠራተኞች በውስልትና በታ ሳይውሉ ለመንግሥታቸውም ረድተው ተመስግነው ለሀገራቸውና ለሰውነታቸውም መድኅኒት ይሆኑታል ፡፡ መንግሥትም በሀገሩ ውስጥ ያለውን ሰራተኛ በመላው ቢያውቀው የበለጠ ጥበብና ጥቅም ነው ፡፡

ደግሞ የኢትዮጵያ ልጆች የሆኑ ኢትዮጵያ ሀገራቸው ራስዋን ብትችልና ለምታ ብትጠና የሚወዱ ጥቂትም ጥበብ ያላቸው እስከሁን እንደዚህ በልዩ ፈቃድ ስላልነበራቸውና የትምሕርቱ ቤት ስላልጠና ፤ አገልግሎታቸው ለባዕድ መሆኑን ሳይወዱ እንደዛሬው እውቀት አልሰፋም ነበርና ለነሱ እንኳ እውቀት ማሳረፊያ በታ እያጡ አገራቸውን ሲወዱ ግድ እየሆነባቸው ጥበብ ለመጨመር እያሉ ባለፈው ጊዜ አየራቁ ቤታቸውን ትተው ለውጭ ጐረቤት እያገላገሉ የሀገራቸውን የኢትዮጵያን መንቃት የሚጠብቁ ብዙዎቹ መኖራቸውን ሁላችንም እንሰማለን ፤ በሀገር ውስጥም ያለን ወንድማማቾች በርትተን ተፋቅረን በመልካም መስማማት መጠቅ ከሚባል ባላጋራ ርቀን እናታችን ለሆነች ኢትዮጵያ ልማትና ስፋት ብንጥር የራቁንም ወንድሞቻችን እናት ወደ ሆነች ኢትዮጵያ ሀገራቸው ሊገቡ ያስባሉ ፡፡ ጥበብም የምትሰፋ ጥበበኛ ወንደ ሲበረክት ነው ፡፡

ይልቁን በሩቅ ሆነው ስለ ኢትዮጵያ ሀገራቸውና ስለ መንግሥታቸውም የሚያዝኑና የሚጸጸቱ ቢቀርቡ ኖሮ እናት ለሆነች መልካም ኢትዮጵያ ሀገራቸውና መንግሥታቸው እንዲህ ዕውቀት በሰፋና በተመቸ ጊዜ እንደምን አድርገው በተጠበቡላት ነበር ፡፡ ዳሩ ግን ባለፈው ጊዜ ትንሽ መራታቸው መሰብሰቢያ የትምሕርት ቤት እንዳሁኑ ጊዜ ስላልኖራቸው ነበር ፤ አሁን ግን ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን መልካም የትምህርት ቤት ደግሞ ይኸው አቁመዋል ፡፡ ብርሃንና ሰላምም ሆኖልናልና የራቁትም ወንድሞቻችን ሀገራቸውንና መንግሥታቸውን ለመርዳት ፤ የቀርቡቱም በትክክል መሰብሰባቸው አይቀርም የማለት ታላቅ ተስፋ አለን ፡፡

ኢትዮጵያ ብርሃንና ሰላም ወጣለት ፤ ዓይኑዋን ገልጣለች ለዚህች ለለምለም እናታችን ለኢትዮጵያ በፍቅርና በሰላም በአንድ ሐሳብ ከከንቱ ነገር ሁሉ ርቀን ይልቁንም መጠጥ ከሚባል ባለጋራ ተጠንቅቀን በርትተን ማገልገል ምንኛ መልካም ነው ፤ ብልህ አገልጋይ የሚሆን የኢትዮጵያ ልጅ አገልግሎትና ሥራ ሲያውቅ ብርታትም እያለው ከከንቱ ነገር ርቆ ፡፡ አንድ ሥራ ይዞ ተጠንቅቆ ለመንግሥቱና ለሀገሩ እንደ መርዳት አንዳንድ የኢትዮጵያ ልጆች የመጠጥን አመል ሳያውቁት ፡፡ መጠጥን በሚያህል ክፉ ባላጋራ ተይዘው እንዲያ ሲበላሹ እያዩ ፡፡ በእንዲህ ያለ ባለጋራ እጅ እየወደቁ ሥራ መፍታታቸው ያሳዝናል ፡፡ ከዚህ እንኳ መራቅ ታላቅ ዕውቀት ነው

ደግሞ የኢትዮጵያን ታላላቆች ጌቶችና መኳንንቶችም እንዲሁ እውቀት ያላቸውንና የእውቀትም ምልክትም ያዩበቸውን ትልቅ ነው ትንሽ ነው አማራ ነው ጋላ ነው ሳይሉ በየክፍላቸው እያወቁ በሥራ ጠምደው ከክፉ ነገር አርቀው በሐሳባቸውም እየሞሉ እያስጠነቀቁ አስጠግተው ለሥራ ቢያበቋቸው ጥቅሙ ለራሳቸው ነውና ብርሃንና ሰላም ያደረገልን ያበርታቸው ፡፡

እንግዲህ በአንድ ልብ ነዋሪ ፡፡ በአንድ ቃል ተናጋሪ ፡፡ ለሀገሩና ለመንግሥቱ ለጌታውም የሚመች የሚረዳዳ ባልንጀራ እግዚአብሔር ያበርክትልን ብርሃንና ሰላም ያደረገልን ይክበር ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን የዕውቀት ምንጭ ያደረገልን ይመስገን ፡፡ ኢትዮጵያን እናታችንን ዓይኑዋን ያስገለጸልን ስሙ ለዘለዓለም በኛ ላይ ይኑር ፡፡ በጽኑዕ ኃይሉና በታወቀ ርኅራኄው ወንድማማቾችን የሰላም እውቀት ተካፋዮች ስለ አደረገልን በግርማ ለሚፈራ ልዕልናው የእውነተኛ ጸሎት በልባችን ያሳድርብን ፡፡ አሜን ፡፡

ስለሺ በላይነህ ፡፡

ባለፈው ሳምንት ስለ ጃንሜዳ እሽቅድድም በሚመጣው ጋዜታ እንጽፋለን ብለን ተስፋ ሰጥተን ነበርና የእሽቅድድሙን ሁኔታ በዛሬው ጋዜታችን እናስታውቃለን ፡፡

የጃን ሜዳ እሽቅድድም

ጥር ፳፰ ቀን በጃንሜዳ ስለ እሽቅድድም መሰብሰብ ሁኖ ነበርና በዚህ ቀን የኢትዮጵያውያንና የውጭ አገር ሰዎችም ፈረሶች ሁሉ ተሰብስበው ነበር ፡፡

ጃንሜዳም በባንዲራና በሌላም መለዮ ዙሪያዋን ተከባ ነበር የእሽቅድድሙም ሥርዓት ቀድም ብሎ በማስታወቂያ ተነግሮ ነበር ።

በ፱ ሰዓት ተኩል ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ክቡራን መኳንንቶቻቸውንና ብዙ ሠራዊት አስከትለው ወደጃንሜዳ ወጡ ። እዚያም በደረሱ ጊዜ እሽቅድድሙን ለመመልከቻ ወደ ተዘጋጀው ስፍራ ገብተው ተቀመጡ ።

ሌጋሲዮኖችና ሌሎችም የውጭ አገር ሰዎች ወይዛዝሮችም ሁሉ በብዙ ተሰብስበው ነበር ።

በ፲ ሰዓት ተ፲፭ ደቂቃ እሽቅድድም ተጀመረ ።

፩ኛ እሽቅድድም ኖቢስ የተባለ ዋንጫ ።

የሜዳው ርዝመት ፰፻ ሜትር ነው ። መጀመሯ ያስቀደመውም ዋንጫውን ይወስዳል ።

በዚህም እሽቅድድም ውስጥ ፲፫ ፈረስ ገባ ነገር ግን አካሔዳቸውን ለማበላለጥ የሚያስቸግር ቢሆን እንደ ገና ይደገም ተባለ ።

እንደ ገና ግልቢያ በ፲ ሰዓት ተ፴፩ ደቂቃ ተጀመረ ልክ በ፪ ደቂቃ ቁራ የሚባለው የመሐመድ አሊ ማኅበር ፈረስ መጀመሯ ደረሰ ። ፪ኛ ብሊትስ የሚባለው የሙሴ ዋንጌር ፈረስ ፫ኛ የልዑል አልጋ ወራሽ ፈረስ ሆነ ። ለነዚህም ተጨባጨባላቸውና ፩ኛ እሽቅድድም ተፈጸመ ።

፪ኛ የዝላይ እሽቅድድም ።

የሜዳው ርዝመት ፫ሺ ፪፻ ሜትር ነው ። በዚህም ጊዜ የገቡት ፈረሶች የግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን። የሙሴ ጋሌብና የሙሴ ክንት ክሊ ፈረሶች ናቸው ።

ፒፖ (አሌአንስ ኑአሮ)የሚባለው የሙሴ ክንት ክሊ ፈረስ ፩፻ ሜትር ያህል እንደሔደ ጋላቢውን ወረወረውና ፈረሱ ብቻ ልክ እንደ ሌሎቹ እየጋለበና እየዘለለ ለሙሴ ጋሌብ ፈረስ ፪ኛ ሆኖ ሔደ። የዚህም ፈረስ ሁኔታ ሰውን ሁሉ አሳቀው ።የሙሴ ጋሊብ ፈረስ ምንም በለቀደመ ዘላይ የሚባለው የግርማዊት ንግሥተ ንግሥታት ዘውዲቱ ፈረስ አጥብቆ ይከታተለው ነበርና በግምት ፪ሺ ሜትር ያህል እንደ ጋለበ የሙሴ ጋሌብ ፈረስ ድድቁን ሳይዘል በጐን አልፎ በረረ።የቀሩት ግን ድድቁን እየዘለሉ ተከተሉት ። አሁንም ይህ የሙሴ ጋሊብ ፈረስ ምንም ስለቀደመ ዝላዩን ትቶ ነውና የእሽቅድድሙ ማኅበር ሹሞች ነገሩን መርምረው መጀመሯ ቀዳሚ በላይ የሚባለው የግርማዊት ንግሥተ ንግሥታት ዘውዲቱ ፈረስ ሆኖ ተጨበጨበ።የሆነ ሁኖ ሶስቱን ሺ ፪፻ሜትር በ፮ደቂቃ ጋለቡት ።

፫ኛ እሽቅድድም ።

በ፲ ሰዓት ተ፵፪ደቂቃ የኢትዮጵያ መኳንንት ፈረሶች እሽቅድድም ሆነ።የሚያደውም ርዝመት ሺ ፪፻ሜትር ነበረ ።

መጀመሯ የግርማዊት ንግሥተ ንግሥታት ዘውዲቱ ፈረስ ልክ በ፪ደቂቃ በደረሰ ጊዜ በታላቅ ጭብጨባ ተጨበጨበ።፪ተኛና ፫ተኛ የልዑል አልጋ ወራሽ ፈረሶች ናቸው።

፬ኛ እሽቅድድም ።

ይህ እሽቅድድም የተደረገ በኤውሮፓውያን ማኅበር ዋንጫ ነው።የሜዳው ርዝመት ሺ ፮፻ ሜትር ነው።መጀመሯው ቀዳሚ ዋንጫውን ይወስዳል።

በ፲፩ ሰዓት ተ፲፩ደቂቃ ተጀመረ በ፩ደቂቃ ተ፶፪ሲኮንድ ደረሱ።መጀመሯ ቀዳሚ ዙይት የሚባለው የሙሴ ጎስን ፈረስ።፪ኛ ሶሂይል የሚባል የሙሴ ጋሌብ ፈረስ።፫ኛ ቱርኳፓ የሚባል የሙሴ ጎስን ፈረስ ሆነና ተጨበጨበ።

፭ኛ እሽቅድድም።

በ፲፩ሰዓት ተ፴፪ደደቂቃ የከተማ እሽቅድድም ተጀመረ።

የሜዳው ርዝመት ሺ ፪፻ሜትር ነው።መጀመሯ ቀዳሚ ኤክሊብስ የሚባል የሙሴ በጉስያ ፈረስ። ፪ኛ፤የሙሴ ኤቤድ ፈረስ ፫ኛ፡የሙሴ ጐስን ፈረስ ሆነ።

እነዚህም በ፪ ደቂቃ ሜዳውን ቈረጡና በደረሱ ጊዜ ተጨበጨበ።

በዚህም ጊዜ የሚጋልቡት ፈረሶች ገና ሳያቋርጡ አንድ ሰው በመካከል አቋርጬ እሔዳለሁ ብሎ ሲያልፍ ከወደ ኋላ የሚመጣውን ፈረስ አሰነካከለውና ጋላቢው በግምባሩ ተደፋ። ለጊዜው ጥቂት እንኳ አልተንቀሳቀሰም ነበር ።ኋላ ግን ከዚያ እንሥተው እየደጋገፉ ይዘውት ሄዱ።

ያም ያሰነካከለው ሰው ተይዞ ወደ ዘበኞች እጅ አልፎ ነበር።ማናቸውም ሰው ሁሉ እንኳን በፈረስ መካከል ፤ነገርም መካከል ቢሆን ማቋረጥ አይገባምና ይህን ጋዜታ አንባቢ አካሔዱን በጥንቃቄ ሊያደርግ እንዲገባው ብርሃንና ሰላም ምክር ይሰጣል ።

፮ኛ እሽቅድድም ።

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ዋንጫ።የሜዳው ርዝመት ፪ሺ ሜትር ነው ።

መጀመሪያው ቀዳሚ ዋንጫውን ይወስዳል ።

የልዑል አልጋ ወራሽ ዋንጫ እሽቅድድም በ፲፪ሰዓት ተ፲፪ ደቂቃ ተጀመረ በ፪ደቂቃ ተ፵፮ሴኮንድ ሲምፕሊቻዩስ የሚባል የሙሴ ቡሎክ ፈረስ መጀመሯ ደረሰና ተጨበጨበ ፪ኛ ሲንዴርስ የሚባለው የሙሴ ተይለር ፈረስ።፫ኛ የሙሴ ጐሰን ፈረስ ሆነ።

፯ኛ እሽቅድድም።

በ፲፪ሰዓት ተ፳፭ደቂቃ የዕንጦጦ እሽቅድድም ተጀመረ የሜዳው ርዝመት ፪ሺ ሜትር ነው።በ፫ደቂቃ ደራቢ የሚባል የፊታውራሪ ደስታ ዳምጠው ፈረስ ጭራውን እየነሰነሰ ከተፍ አለ፤በዚህም ጊዜ በታላቅ ጭብጨባ ተጨበጨበና እሽቅድድሙ አለቀ ።

ከዚህም በኋላ ሶስቱን ዋንጫዎችና በየማዕርጉ ለቀደመ የሚሰጠውን ገንዘብ ይዘው ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ፊት አቀረቡ።ቀጥሎ ፈረሱ የቀደመለት ሁሉ እንደ ኤምፔሪያል ክለብ ሥርዓት የምሥጋና ቃል እየተቀበለ ዋንጫውንና ገንዘቡን ወሰደ።

በዚህም ጊዜ ጭብጨባው አሁንም አሁንም ይቀልጥ ነበር በመጨረሻውም ክቡር ፊታውራሪ ደስታ ዳምጠው የምሥጋና ቃል ተቀብለው ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ፊት እጅ ነሥተው ሲመለሱ በታላቅ ጭብጨባ ተጨበጨበና የእሽቅድድሙ ሥርዓት በ፲ሰዓት ተፈጸመ ።

ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ልዑል አልጋ ወራሽም ከዚያ ተነስተው ወደ ኤምፔሪያል ክለብ ቤት ገብ በ፲ሰዓት ተኳ፲ደቂቃ ከዚያ ወጥተው በአውቶሞቢል ሆነው ወደ ግቢ ተመለሱ ።

የከተማ ወሬ ።

በዚሁ ሰዓት ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ በታላቅ አጀብ ታጅበው ወደግቢ ሲመለሱ ፡ አራዳ በጣሊያን ስልክ ቤት አጠገብ ካለው መንደር እሳት ተነሳ የሚል የሚያስደነግጥ ወሬ ተሰማ ። ክቡር ከንቲባ ነሲቡም ይህን በሰሙ ጊዜ ከአጀቡ ተለይተው ይህ የእሳት አደጋ ወደወረደበት ሰፈር ገሠገሡ ። የመጥሪያ ጥሩምባ አስነፍተው ሠራዊት አስከትተው ወደዚያ ቦታ ደረሱ ። የሚቃጠለውንም ቤት ባዩ ጊዜ ከርኅራኄያቸው ብዛት የተነሣ እርሳቸው ራሳቸው የባሕር ዛፍ ቅጠል እየዘነጠፉ እሳቱን ያጠፉ ጀመረ ። የእሳቱን ኃይልና የነበልባሉን ወላፈን የጢሱንም ማፈን ጥቂት እንኳ አልተሰቀቁትም ነበር ።

ከዚህም በኋላ በእሳቱ ውስጥ ምናልባት ሰው ታፍኖ እንዳይሞት ብለው ያስፈልጉ ጀመር ።

አስፈልገውም በእሳቱ ውስጥ የሰው ጥፋት እንደሌለ ካወቁ በኋላ አሽከሮቻቸውን ውሀ እያመጡ በእሳቱ ላይ እንዲያፈስበትና ወደሌላም እንዳይተላለፍ እንዲጠብቁ አዘዙ

ክቡር ፊታውራሪ ደስታ ዳምጠውም ለመርዳት ብዙ ሠራዊት ይዘው ወደተቃጠለው ሰፈር በችኰላ ደረሱ ። እርሳቸውም የባሕር ዛፍ ቅጠል ይዘው የነበልባሉን ወላፈን ታግሠው እሳቱን ለማጥፋት ይጣጣሩ ነበር ።

በዚህም ሌላው ሁሉ እንዲተባበርና እንዲረዳ ለሕዝብ የበጎ አርአያ ሆኑ ።

የእሳቱ አደጋ ግን እየበረታ [illegible] አጥቶ አደረ ።

እነዚህም የተሰበሰቡት መኳንንትና ሠራዊት በቶሎ ደርሰው የእሳቱን ሥቃይ ታግሠው በመርዳታቸው ፍቅራቸውን ገልጠዋል ። ነገር ግን ይህ ብቻ አይበቃም የእሳት አደጋ በድንገት ቤታቸውንና ልብሳቸውን አቃጥሎባቸው ብርድ ሲያንቀጠቅጣቸው ላደሩት ሰዎች የከተማው ሰው የቸርነት እጁን ቢዘረጋላቸው ፍጹም ርኅራኄውን እንደገለጠ ያስረዳን ነበር ።

በቴሌግራም የመጣ ቃል ።
ከኢጣልያ መንግሥት ሌጋሲዮን

አዲስ አበባ ፳፫ ጥር ፲፱፻፲፰ ፳፮ ጥር የለት ወሬ ።

ሚላኖ ። ስለአንድ ዓይነት በሽታ (ካንሴር) ስለሚባል አንድ ልዩ የሐኪም ቤት ሊሰራ ነው ። ለዚሁም ሆፒታል መስሯ እርዳታ የሚላኖ ማዘጋጃ ቤት አንድ ሚሊዮን ሊሬ ሰጠ ።

ክሬሞና ። በክሬሞና የንግድ ማኅበር ቤት ነጋዶች ሁሉ ጉባዔ አደረጉ ። ከጉባዔውም በኋላ ነጋዶችና ባለፋብሪካዎች በተቻላቸው ነገር ሁሉ መንግሥትን እንዲረዱ ቁርጥ አደረጉ ።

ሎንዶን ። ብሪቴያና የሩማንያ ጠቅላይ ሚኒስትትር ከቸርችሂልና ከሌሎችም ትልልቅ ሰዎች ተገናኝቶ ወደሩማንያ ሊመለስ ነው ሞርኒንግ ፖስት የሚባለው ጋዜጣ ብሪቴያና በሎንዶን ከተማ ባየው ነገር ሁሉ በጣም ደስ ብሎታል ይላል ። የመንግሥት አማካሪዎች የአሊዮችን ብድር ነገር መረመሩ ።

ፓሪስ ። በፈረንሣዊ ፓርላሜንት የአሊዮች ብድር ነገር ሲመረመር አንዳንድ ዴፑቴዎች የፈረንሣዊ መንግሥት በጦርነት ጊዜ በጦሩ ምክንያት የተበደረውን ገንዘብ የጀርመን መንግሥት ካልከፈለ የፈረንሣዊ መንግሥት ለመክፈል አይችልም ብለው አስታወቁ ።

ሞስኮ ። ክራሲን በበሽታው ምክንያት ተሥራው ተሰናብቶ ሊሄድ ነው ኤርኔስቶ የሚባል የኢጣልያ መርከብ በባቱም መርከብ መቋሚያ አጠገብ ጋዝ ተጭኖ ሰጠመ ነገር ግን ሰው አልሞተም ሁሉም ዳነ ።

ኮፐንሐግን ። የዳንማርክ ሚኒስትር በቱርክ አገር ያለው በዳንማርክና በቱርክ መንግሥት መካከል ያለው የወዳጅነት ውል ተፈረመ ብሎ አስታወቀ ።

የጥር ፳፫ ቀን የለት ወሬ።

ኮንስታንቲኖፕል ። የቱርክ መንግሥት የክርስቲያን ጳጳስ ከቱርክ አገር ውስጥ እንዲወጣ አዘዘ ።

ቤልግራድ ። በቤኔትዚያ ከተማ ከዚህ ቀደም በኢጣሊያ መንግሥትና በዩጐስላቢያ መንግሥት መካከል ተጀምሮ የነበረው ክርክር በዚህ ወር በፌብሪዬ ውስጥ እንደገና ይከፈታል ።

ሎንዶን ። የንግሊዝ ባንክ አዛገ ወደ ኒዩ ዮርክ ሂዶ የነበረው ተመለሰ ። በኒዩ ዮርክ በየትልልቁ ባንክ በደረሰበት ሁሉ ለጀርመን መንግሥት የንግሊዝና የአሜሪካ መንግሥት ገንዘብ እንዲያበድሩ ለመማከር ነው ይባላል ።

ፓሪስ ። የፈረንሣዊ ጋዜጣዎች ሁሉ እንዲህ ይላሉ ። አዲስ የተሾመው የጀርመን መንግሥት ጠቅላይ ሚኒስትር ሉተር የሚባለው በፈረንሣዊና በጀርመን መንግሥት መካከል ላለው ወዳጅነት በጣም ደስ የሚያሰኝ ነው ሰውነቱ ከፊተኛው ጠቅላይ ሚኒስትር ከእሽትሬዜማን በጣም ትክክለኛ ስለሆነ ።

ሎንዶን ። የዱሮው የንግሊዝ አምባሳደር ሮድ በሮማ የነበረው በኢጣሊያና በንግሊዝ መንግሥት መካከል ላለው የወዳጅነት ማኅበር ፕሬዚዳን ሆነ ። የንግሊዝ ጋዜጣዎች በኢጣሊያ አገር የሚሆነውን ነገር ሁሉ በትክክል ስላልጻፉ ከሉ ጋዜጣ ጸሐፊዎች ዴይሊ ቴሌግራፍ ከሚባሉት የኢጣሊያን ፖለቲክ ሁሉ አስተካክለው እንዲጽፉ አንድ (ኰሬስፖንዴንት) ተጻፊ ወደ ሮማ ለመስደድ ቁርጥ አደረገ ።

በልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

መጀመሪያ ዓመት ፩ ቁጥር ፰ ።
1re ANNÉE № 8

ሐሙስ የካቲት ፲፪ ቀን ፲፱፻፲፯ ዓ ም ።
JEUDI 19 FEVRIÉR 1925

ብርሃንና ሰላም

LUMIÈRE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገሬቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

የጋዜጣው ዲሬክተር ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የራሱን ጉዳይ የሚያሳትም ሰው ዋጋውን እየከፈለ [illegible] ።

ቅበላ ።

ጥሉላት የሚበላበትና የሚጠጣበት ጊዜ ተፈጽሞ ቅጠላ ቅጠልና የተክል ዓይነት የሚበላበት ጊዜ ሲገባ በሀገራችን በኢትዮጵያ ቅበላ ይባላል ።

ዛሬም በዚህ ዘመን የቅበላ በዓል በየካቲት ፲፭ ቀን ሁኑዋል ። ከቅበላም በኋላ ያለው ጊዜ ጾመ ዓርባ ይባላል ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዓርባ ቀን ጾሞ የዲያብሎስን ፈተና ያሸነፈበት ጊዜ ነው ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እኛን ለማዳን ብሎ መጾሙንና መከራ መቀበሉን ለማሰብ እንደአባቶቻችን ትእዛዝ ከጥሉላት ወገን የሆነውን ምግብ ሁሉ ከመብላት እንከለከላለን ። ጥሉላት የሚባሉት ሥጋ ወተት ቅቤ እንቁላል አሣም ናቸው ። እነዚህን ከመብላት ተከልክለው ቅጠላቅጠሉን ወይም ያታክልት ምግብ በጊዜያቱ የሚበሉ ሰዎች ጾመኞች ይባላሉ ።

በዚህ ወራት የሚጾሙትም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለኛ መጾሙን እያሰቡ ይሁን እንጂ በመጾማቸው ሊመኩበትና ውዳሴ ከንቱ ሊቀበሉበት አይገባም ። ከክፉ ነገር ተለይተው በንጽሕ ተጠብቀው ጭቅጭቅና መከሰስን መሰደብንም ትተው የጾሙን ወራት ቢፈጽሙት መልክም ነው ።

ነገር ግን ጾመኞች ሁነን ከሥጋና ከቅቤ ከወተትና ከእንቁላል ብንጠበቅ ፡ ከ፱ ሰዓት በኋላ ግን የሚያሰክር መጠጥ ያለመጠን ጠጥተን ወደ ፍጅት ወደ ጭቅጭቅ ወደ መከሰስ ወደመሳደብ ብንሄድ ፈቃደ ሥጋችንን ብንፈጽም መጾማችን ከንቱ ይሆንብናል ።

በጾም ጊዜ የሚያሰክር መጠጥ ጠጥተው አምባጓሮ ያነሡ ሰዎች አይተናል ። ይህም ያሳዝናል ።

በጾም ወራት ከሥጋና ከቅቤ ከወተትና ከእንቁላል እንደምንከለከል መጠን ከሚያሰክርም መጠጥ ሁሉ ብንከለከል ራሳችንን መግታት ሰውነታችንን ከክፉ ነገር መጠበቅ በተቻለን ነበር ።

የባሰ ጉዳት ደግሞ አንድ ነገር አለ ። ጥሉላት በሚበላበት ወራት አረቄን የመሰለ ማናቸውንም የሚያቃጥል መጠጥ ቢጠጡ መጉዳቱ እንኳ ባይቀር ጉዳቱ በደረቅ ሆድ እንደሚሆነው አይጸናም ። ከጥሉላት ተከልክለው የሚያሰክር መጠጥ የሚጠጡ ሰዎች የመጠጡ ብርታት አንጀታቸውን አቃጥሎት ዝለው ይወድቁና በድንገት ቢሞቱ አባ ሰንጋ ገደለው ይባላል ።

አባ ሰንጋ የሚባለው ግን በአንድ አሳብ በኩል አረቄ ሳይሆን አይቀርም ፡ ፈረስ ረጅሙን ሜዳ በፍጥነት እንዲጨርሰው ፡ አረቄም የሰውን ዕድሜ ባጭር ያስቀረዋልና ።

አሁንም በጾም ጊዜ የሚያሰክር ብዙ መጠጥ የሚጠጣ ሰው እጥፍ ጉዳት ያገኘዋል ።

መጀመሪያ መጠጥ የሚያበዛ ሰው ሰውነቱን ወስኖ ገትቶ ማኖር አይቻለውምና ኃጢአት ወደመሥራት ይሳበል ለጽድቅ ያሰበውም ጾሙ ለከንቱ ይሆንበታል ።

ሁለተኛ ፡ በጾም ምክንያት ቅባት አጥቶ የለ ሰውነቱን እንደ እሳት በሆነ በሚያሰክር መጠጥ ቢያቃጥለው ጤና ያጣል ባይሞትም እንኳ ሳይታመም አይቀርም ። እንግዲህ ለመጾምና ለመጸለይ ከፈተናም ለመዳን ሥጋችንን መግዛት እንዲቻለን መጀመሪያ ነገር በጾም ጊዜ ከሚያሰክር መጠጥ ልንጠበቅ ይገባናል ። በፍትሐ ነገሥትም በአንቀጸ ጾም የታዘዘ ነው ።

ጾሙንም ከሥጋና ከቅቤ ከወተትና ከእንቁላል በመከልከል ብቻ ሳይሆን ከሚያሰክር መጠጥና ከክፉ ነገር ሁሉ ርቀን መጾም እንዲገባን አውቀን ጾመ ዓርባን እንድንቀበለው ብርሃንና ሰላም ያስጠነቅቀናል ።

መከባበር ።

ባገባብ ዕውቀት ማደግ የነፍስን ኃይል ያሸልና ያበረታል የክፉትንም ቡቃያ ያርማል ። ዝናም የጠጣ እርሻ በረከት ለሚያመጣ ሕይወት እንደሚሆን እንዲሁ ደግሞ ገልቱ ወይም እንደበሬ የሆነ ባገባብ ተቀጥቶ በማደግ ደግ ሆኖ በኑሮው

ታዛጋርና ስምም ይሆናል ። በደምብ ባገባብ ማደግ ሰውን ተወዳጅና ተፈላጊ ያደርገዋል ።

የጥንት ግሪክውያን ባገባብ በሕግና ወግም ያላደገ ሰው የነከውን ከሚወጋ ከጃርት ይሸክራል ይላሉ ።

ትንሽ ዕውቀት ያለው ሰው አገባብ ከማያውቅና ከሚገፋጭ ከማይስማማ ሰው የቀረበ እንደሆን ፤ አገባብ ካለማወቁ የተነሣ ያማዝነኛል በማለት ሊጠጋው ወይም ሊያስጠጋው አይወድም ። ስለዚህ ተንዳጆችና ኩሩዎች ለበላያቸውም የሚገባውን ከበሬታ የማይሰጡ ስምም የሌላቸው ሰዎች ሥራና እንጀራ እንደ ፈለጉ ሊያገኙ አይችሉም ። ወይም ጨርሰው ያጣሉ ።

እንደሚገባ ባልንጀራን አለማክበር ፤ የሚያሳዝንና የሚቈረቍር ቃል መናገርና ከሚገባው ማለፍ ሊታገሡት የማይቻል ክፉ አመል ነው ።

ባገባብ ያደጉና የማይጓደዱ ሰዎችን እውቀት እንኳ ቢያንሳቸው ሁሉ ይቀበላቸዋል ይወዳቸዋል ።

መተባበርና የመስማማት ባሕሪ የሌለው ግን ምንም ዕውቀቱ ቢበዛ [illegible] [illegible] በሁሉ ዘንድ የከበደ ነው ። ክሁሉ የበለጠ በሥርዓት የማደግ ጥቅም አረብ በርሱ በመከባበርና በመቻቻል ይገለጣል ።

እንዲህ ቢሆን ጕድለት በተገኘ ጊዜ ይቅር ለመባባል የተመቸ ነው ። ፍጹም ንጹሕ የለምና ። አያሌ ጊዜ እየራሳችን ሊታገሡንና ሊራሩልን እንደሚያስፈልገን እያሰብን በሌሎች ላይ ፍርድ አክብደን ልንጭን አይገባንም ።

ባንድ ወገን ደግሞ የሰው አእምሮ ልዩ ልዩ እንደሆነ ባሕሪውና አመሉም የተለያየ ነው ። ግን ለይተን አውቀን በሐሳባችን እንደመሰለን አስረግጠን እንዲህ ነው ለማለትም ችግር ነው ። ስለዚህ የባልንጀራውን ሐሳብ ደግሞ አክብሮ ማየት በአገባብ በሕግና ወግ ማወቅም አንድ መሠረት ነገር ነው ።

በደብዳቤ የመጣ ቃል ።

ስለ ሥራ ስልጣኔና ስፋት ።

ሥራ የሚሰፋበትንና የሚሰለጥንበትን ምክንያት ብናስብና ብናስተውል ሳንርቅ በቅርቡ ፤ ሳናበዛ በጥቂቱ ብዙ ድካም ሳያገኘን ፤ ከሀገራችን ላይ የልዑል አልጋ ወራሽ ማተሚያ ቤት ሥራ በመጠኑ እንዴት እንደ ሰፋና እንደ ሰለጠነ ፤ ሥራ አሰፋለኹና አሰለጥናለኹ ስንፍናንና በዝንተኝነትን እርቃለሁ በማለት ሀሳብ ብንመረምርና ብንመለከት ለምንሠራው ሥራ ሁሉ የሚስማማና የሚጠቅም የዕውቀትና የጥበብ ምክር እናገኝበታለን ።

ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ አንድ ቁጥር እንዳነበብነው ማተሚያ ቤቱ የቆመበትና ሥራው የተጀመረበት ቀኑ ቅርብ ሲሆን ከዚሁ ማተሚያ ቤት እየታተሙ የወጡ ። ሰውን ካለማወቅ ወደ ማወቅ የሚመልሱ ፤ ሥጋዊና መንፈሳዊ ምክርን የሚሰጡ ቅዱሳት መጻሕፍት በኢትዮጵያ ውስጥ ጥቅም ሊሆኑና ደኅንነትን ሊሰጡ እንደ ተዘረጉ እንሰማለን እናያለን በሥራው ውስጥ ካሉ ሠራተኞች የማኅተሙን ሥራ ተምሮና አውቆ የገባ አንድ ሠራተኛ እንኳ አልነበረም ። ነገር ግን እነዚህ የማኅተም ሥራ የማያውቁ ልጆች ተምረን እንሠራለን በማለት ወደ ሥራው ለመግባት ልዑል አልጋ ወራሽን ፈቃድ ለመኑ ። ልዑል አልጋ ወራሽም የሀገራቸውን ልጆች በትምርትና ልዩ ልዩ በሆነ ሥራ ለማሰልጠን ፍጹም ሐሳባቸውና ፈቃዳቸው ስለሆነ ወደ ማተሚያ ቤት ገብተው ተምረው እንዲሠሩ በሙሉ ፈቃድ ቀላጤ ሰጥተው ወደ ማተሚያ ቤቱ አለቃ በላኳቸው ጊዜ የማተሚያ ቤቱ አለቃ አቶ ገብረ ክርስቶስም ያለ ረዳት ብቻዬን አስተምሬ ሠርቼ እንዴት ይቻለኛል ሥራውስ እንዴት ይሰፋል ሳይሉ በሙሉ ደስታ ተቀብለው እንደ አለቃ ሳይቆጡ የተወደደ አባት የተወደዱ ልጆቹን እንዲመክር መክረው ጊዜ በከንቱ እንዳያጠፉ የሚገቡበትና የሚወጡበት ሰዓት ወስነው የሚያርፉበት በዓል ሳይበዛ በልክ አድርገው ለሥራ የሚያስፈልገውን በትምርት በብዙ ትጋት አስተምረው ሥራውን ባወቁ ጊዜ ለልዑል አልጋ ወራሽ ነግረው ቀለባቸውን እንደሚገባ አስቆርጠው በ በየደንባቸው የሰጡዋቸውን ሥራ በፍጥነትና በጥንቃቄ እንዲሠሩ በየጊዜው እየፈተሹ አብረውም እየሠሩ የጎደለውን እየሞሉ የዘበውን እያቀኑ እያጸኑና እያበረታቱ ያሠሯቸዋል ። ሠራተኞቹም አለቃቸውን በመፍራትና በማክበር ምክራቸውን በመስማት ጸንተው ለሥራ በሚያስተምሯቸው ትምርት በርትተው የተወሰነላቸውን ሰዓት ሳያጠፉ ጠብቀው ሥራቸውን በትጋት ተምረው ካወቁ በኋላ የተቆረጠላቸውን ቀለብ በወር በወሩ እየተቀበሉ አለቃቸው የሰጡዋቸውን የሥራ ደንብና ሥራት በመጠበቅ ሥራቸው እየሰፋና እየሰለጠነ ሄደ ።

አንዱ ደግሞ ሥራቸው የሰፋበትና ወደፊት በፍጥነት እየገፋ የሔደበት ምክንያት የሥራውን ዓይነት ለሠራተኞች ሁሉ አለቃው በማስተማራቸው ነው ። አንዱ ሠራተኛ ታሞ ወይም ችግር አግኝቶት ቢቀር ፤ ሌላው ሠራተኛ የቀረውን ሰው ሥራ ሲሠራ ስለዋለ ሥራው እሱን ሲጠብቅ አይቆየውም ።

አንድ አንድ የሥራ አለቆች ግን በማተሚያ ቤት ሥራ ቢሆን በሌላ ልዩ ልዩ በሆነ ሥራም ቢሆን ለሠራተኞቻቸው አንድ ዓይነት ሥራ ላንዱ አንድ ዓይነት ሥራ ላንዱ ስለ አስተማሯቸው አንዱ ሠራተኛ ድንገት ችግሮት ቢቀር ሥራው በዝዮ ስለ ዋለ ወደፊት ሳይገፋ በጅምር ይቀራል ።

ሥራቸውም እንደሰፋና እንደ ሰለጠነ አለቃውም ተመሥግነው ሠራተኞችን እንዳስመሰገኑዋቸው ያራቱ ወንጌላውያን ንባብና ትርጓሜ አትመው በጨረሱ ጊዜ ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ወደ ማተሚያ ቤት ገብተው ለሠራተኞች በብዙ ደስታ በተናገሩት ምሥጋና ለወደፊትም ባደረጉት ቃል እንረዳዋለን ።

በልዩ ልዩ ሥራ የምትቆሙ አለቆችና ሠራተኞች ባንድ ሰው ትጋት እንደዚህ ያለ የሥራ ስልጣኔና ስፋት ከተገኘ ሥራ ያልተማሩ ያገራችሁን ልጆች ወደ ሥራ እያገባችሁ በትክክል ሥራትና ትጋት ብታስተምሯቸው ለሀገራችሁና ለመንግሥታችሁ መልካም እርዳታ ነው ። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በከንቱ የወሰዳችሁትን በከንቱ ስጡ ያለ ሐዋርያትን ወይም መምራንን ብቻ አይደለም ። ሰው ሁሉ ከአምላኩ የተቀበለውን የጸጋ ስጦታ ሁሉ በትሕትና

እንዲያከፍል ነው እንጂ አንድ የተማረ ሰው ትምርቱን ለወንድሞቹና ላገሮቹ ልጆች ሳያከፍል እኔው እራሴ ከብሬበትና ተመሥግኜበት እኖራለሁ ሲል ባላሰበበት ጊዜ ድንገት የሞተ እንደሆነ ባያስተምርና ለወንድሞቹ ባያከፍል ሕያው ሁኖ የሚኖር ትምርቱ አብሮት ይሞታል ። አንዱ ግን እርሱ ሲሞት የተማረውን ትምርት ቀሪነትና የራሱን ኃላፊነት አውቆ ላገሩ ልጆችና ለወንድሞቹ ቢያከፍል፣ እንኳን ከንዱ ወዳንዱ በመተላለፍ ሕያው ሁኖ የሚኖር ትምርቱ ይቀርና እርሱም ቢሞት ከሞተ አይቆጠርም ። ሥራ የማናውቅ ሰዎችም ይህንን ሰው ከመሰሉ የያዙትን በደስታ ከሚያከፍሉ ወደ ሥራቸው ገብተን ትእዛዛቸውን ጠብቀን በሥራታቸው ጸንተን ጊዜ ሳናጠፋ ከተማርን በኋላ የያዝነውን ሥራ በጥንቃቄና በትጋት የሠራን እንደሆን ሥራችን እየሰፋና እየሰለጠነ ይሄዳል እኛ ከብረን ተመሥግነን ሀገራችንንና መንግሥታችንን እናስከብራለን ። ለሁሉም ነገር ብርሃንን አስፍተው ሰላምን አብዝተው የኢትዮጵያን ልጆች በጥበብና በዕውቀት እንዲያድጉና እንዲሰለጥኑ የሚያስቡ ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንንን ሁሉ የሚቻለው እግዚአብሔር ያሰንብትልን ኢትዮጵያን ይጠብቅልን አሜን ።

ሰሎሞን የኔነህ ።

በደብዳቤ የመጣ ቃል ።

በ፲፱፻፲፯ ዓመተ ምሕረት ታኅሣሥ ፴ቀን የታተመውን ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ ሳነብ ስለ አረቂና የሚያሰክር መጠጥ የተጻፈውን በየው ይኸው ቃል እውነተኛ የጉዳትን ምልክት የሚያስረዳ መሆኑን ተረዳሁት ። ማንም ሰው ቢሆን መንግሥቱንና ሕዝቡን እንደራሱ አድርጎ መውደድ የሚገባው መሆኑን አስበው ይህንን የመንግሥትንና የሕዝብን ጉዳት የማስረጃ ምልክት ለጻፉልን እኔም አንድ ምስኪኑ ኢትዮጵያዊ ምስጋና አቀርባለሁ ።

እውነትም የዚህ የአረቂ ነገር እጅግ ይገርማል እንኳን ይኸ ጉዳይ የማይሰራው አረቂ የሚባለው ነገርና ሌላውንም ከሩቅ አገር የሚመጣውን የሚለበሰውን ጉዳይ የሚሞላውን ዕቃ ሁሉ ለመግዛት አለገቢያችን ወጭ እያበዛን ገንዘባችንን እንዳንጨርስና እንዳንደኸይ እውቀት ተምረን ከመሬታችን ውስጥ እየወጣን ብንሰራው ከጉዳት የምንድን መሆናችንን የመንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር በሚለው በብልሁ በነጋድራስ ገብረ ሕይወት (ባይከዳኝ) መጽሐፍ ውስጥ አስረድቶ የሚናገር መሆኑን አነበብሁት ይህንኑም መጽሐፍ መርምሮ የሚያነብ ሁሉ ያገሩን የኢትዮጵያን ፍቅር አስተውሎ ሳያውቅና ለትምሕርትም ሳይጣጣር አይቀርም የሚል ተሥፋ አለን ።

ስለመንግሥታቸውና ስለሕዝባቸው ፍቅር ደስ ብሎአቸው ይህነን የትጋት መሪ የሚሆን መጽሐፍ ላሳተሙት ለልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ምስጋና ይገባቸዋል።

ይኸንን ከጨረስን ወዳአረቂው እንመለስ ።

ይልቁንም አንድ ጥቅም የሌለው ያረቂ ጉዳት በኢትዮጵያ ውስጥ መሰልጠኑ በጣም ያሳዝናል ባረቂ ምክንያት ከሚገኘው የመንግሥት ቀረጥ ገንዘብ ሕዝባችን ላረቂ የሚሰጠው ገንዘብ ቢታሰብ እንደኔ ግምት ላረቂ የምንሰጠው መቶ ጊዜ የሚበልጥ ይመስለኛል ።

በኢትዮጵያ ውስጥ ነጋዶች ለዘር ከሚያመጡት ብር በቀር እኛ እየሰራን አልተከንበትም ዘርም ማለት አስር ዘርቶ መቶ ለማግኘት ነው ። ያንኑም ብር በቀን ብዛት ለዘሪዎቹ መመለሳችን አይቀርም ። ገበሬ ትርፍ ለማግኘት እህሉን አመሬት አፍሶ በዝናምና በፀሐይ እንደሚደክም የነጋዴም ድካም ለትርፍ መሆኑ አለጥርጥር የታወቀ ነው ።

ይህኑ ጥቂቱን ገንዘባችንን እውቀት ተምረን ፋብሪካ አቁመን እሩቅ መስሎ የሚታየንን ዕቃ አገራችን እስትንሰራ ድረስ ይቅር ለማይባል ከሩቅ አገር ለሚመጣ ለልብስና ለዕቃ መግዣ እንዳይሆነን ከጉዳት በቀር ጥቅም ለሌለበት ላረቂ መጨረሳችን በጣም የሚያስገርም ነው ። እነሆ አንድ አጭር ምሳሌ እናገራለሁ ። ማናቸውም ከብት እረኛው ጠብቆ አውሎ በጊዜም ካላስገባው አውሬ ይበላዋል ። አውሬ ቢበላው ግን ጉዳቱ ለተበላው ከብትና ለረኛውም ጭምር ነው ። እንደዚሁ ለሕዝቡ ጠባቂው ንጉሡ ነው ። ያረቂም ጉዳት ከሁሉ የበለጠ ጥፋትን የሚያፋጥን መሆኑን ሁሉም የጠቀወልና የሚያበረደውንም የጠለተውን የምክር ቃል ታኅሣሥ ፴ቀን በታተመው በብርሃንና ሰላም ጋዜጣ ላይ አንብቦታል ።

ስለዚህ ባጭሩ ነገር ቀጥሎ ያለው የሚያስፈልግ ስለሆነ ደፍሬ እናገራለሁ ንጉሡ በገሩ ያለነውን ሕዝብ ሁሉ አረቂ እንዳንጠጣ በልዩ ልዩ ቅጣት ወስኖ ቢከለክለን ብዙ ጥቅም እንዲሆን የታወቀ ነው ። አረቂ ጭራሽ እንዳይጠጣ ቢከለከል በዚህ የተነሣ ትንሽ እንኳን ጉዳት የሚያገኝን አለመሆኑ የታወቀ ነውና ሕዝቡ አረቂ እንዳይጠጣ ለመከልከል እስኪመከር እንኳን የሚያዘገይ ነገር ያለበት አይመስለኝም ።

ምናልባት መንግሥቱ በረቂ ስለሚያገኘው ቀረጥ እንጐዳለን የሚል አሳብ እንዳለበት ከሕዝቡ በወር በወር ካያንዳንዱ ሰው አንድ ፩ መሐለቅ ግብር ቢቀበል የሚሻል ይመስለኛል ።

ተፈሪ ይፍሩ ።

የከተማ ወሬ ።

ከዚህ በፊት ያቃጠለው ሰው ሳይታወቅ በአዲስ አበባ አያሌ ቤት በእሳት ሲቃጠል እሳት ከሰማይ ወርዶ ቤቱን ያቃጥል እንደነበር ይወራ ነበር።

ዘንድሮም ደግሞ ባለፈው ሳምንት እሳት ቢነሣ ከሰማይ እየወረደ ነው እንጂ ከወዴት እንደመጣ አይታወቅም ሲባል ሰነበተ

አሁን ግን እሳቱን በየቤቱ ላይ የሚጥለው የሰይጣን ታዛገር የሆነ ሰው እንደሆነ ታወቀ ። ባለፈው ሳምንት በአዲስ አበባ አያሌ ቤቶችን በእሳት ካቃጠሉ ሰዎች ውስጥ ተይዘዋል ። ከነዚህም አንዱ ኃጢአቱን በርግጥ አምኑዋል የቀሩትንም የከተማው ሹሞች በብዙ ትጋት ይፈልጋሉና ጨርሰው እንዲይዟቸው ተስፋ እናደርጋለን ።

እንደዚህ የመሰለውን አጥፊ ሁሉ በቶሎ የሚገልጡት ሹሞች ከተገኙ ቀጣፊ ሁሉ ይሰጋል እንጂ አይገንም።

ስለ አውቶ ሞቢል ።

አንድ ጊዜ በአውስትራሊያ ብዙ ቤንዚን ሳይጨርስ የፈጠነ አቶሞቢል ለማየት ውርርድ ተደርጎ ነበርና ፲፱፻፩ኛ

ፊያት አውቶሞቢል ከ፹፬ ኪሎ ሜትር የሚበልጥ መንገድ ሒዶ ፲ ሊትርና ፶፭ ሳንቲ ሊትር ቤንዚን ጨረሰ ተብሏል ።

አውስትራልያ አዲስ ዓለም ነው ። ነገር ግን በዚያ አገር ማለፊያ ሆኖ የተሰናዳ ብዙ መንገድ አለ ። ስለዚህም የዚያ አገር ሰዎች ለእርሻም ቢሆን ለሌላም ሥራ ቢሆን ለመሔድ ባሰቡ ጊዜ ይህ የተሰናዳው መንገድ ሐሳባቸውን በፍጥነት ያቀልላቸዋል ። በዚህም ቢሆን መንገዱ ይህና ሁኖ ቢሰናዳና ፬ ሰው የሚይዝ አውቶሞቢል በአንድ ኪሎ ሜትር ዋጋው ፩ መሐለቅ ቢሆን ያለ ብዙ ኪሣራ በፍጥነት ወዳሰቡት ቦታ በተደረሰ ። መንገዱም በምኞት በተፈጸመ ነበር ።

ለምሳሌ ፤ ከዚህ በጡዋት ተነሥቶ ወደ አዲስ ዓለም ደርሶ በእኩለ ቀን ለምሳ ወደዚህ ለመመለስ በተቻለ ነበር ።

ነገር ግን ይህ መንገድ በከብት ወይም በእግር ደርሶ ለመመለስ ብዙ የሚያደክም ነገር ነው ።

ሜ ላ ኖ ።

የውጭ አገር ወሬ ።

በያፋ አጠገብ በሙሴ ኤትሽዝክ ገልድቤርግ ኦታክልት ከክርስቶስ ልደት በፊት እስከ ሁለት ሺ ዓመት ያህል የነበረ ሁለት መቃብርና የከነአናውያን የሸክላ ዕቃ ተገኝተዋል

የኢጣልያ መንግሥት ሌጋሲዮን ።

አዲስ አበባ ። ፳፱ ጥር ሺ ፱፻፳፩ የ፳፱ና የ፴ ጥር የለት ወሬ ።

ናፖል ። ሞንዚ የትሪፖሊቱን ገዥ ዛሬ ሞተ ።

አቴን ። በግሪክ አገር በያውራጃው ሁሉ ከኰንስታንቲኖፕል የቱርክ መንግሥት አቡናቸውን ስላስወጣባቸው ሕዝቡ ክርክር ጀምሯል ። ይህንንም ነገር ወደ መንግሥታት ማኅበር ያቀርባሉ ይባላል ።

ቤርሊን ። የጀርመን የንግድ ሥራ መልክተኛ አለቃ ትረንደለንቡርግ የሚባለው በፈረንሳዊና በጀርመን መካከል ስለሚደረገው የንግድ ሥራ የተስማሙትን ለጉባኤው ሚኒስትር አመለከተ ። የጉባኤው ሚኒስትርም በፈረንሳዊና በጀርመን መካከል የሚሠራው ንግድ በየጊዜው እየተመከረ ይደረጋል በማለት ተነጋግረዋል ።

አቴን ። የግሪክ ጋዜጣ ሁሉ ከኰንስታንቲኖፕል አቡነቸው በወጣበት ነገር የቱርክ መንግሥት ያለ ሥርዓት አደረገ በማለት ያወራሉ ። ያቴን ጳጳስ ይህነን ነገር ለያገሩ ቤተ ክርስቲያናት አስታውቃለሁ ብሎ ተናገረ ።

ባርሴሎና ። ማርሻል ፕሪምዶሪቤራና ጀኔራል አኒዶ ዛሬ ገቡ ።

ቲራና ። አሕመድ ዞጉ የልባኒ ሬፑብሊክ ጠቅላይ ገዢነት ለ፯ ዓመት ድረስ ተመረጠ ። ለዋና ከተማ ቲራናን መረጠ ።

የ፳፮ ጥር የለት ወሬ ።

ፓሪስ ። የግሪክ ሚኒስትር አቡኑን ከኰንስታንቲኖፕል የቱርክ መንግሥት ስላስወጣው ያለ ሥርዓት ተደርጓልና ይህነን ነገር እመንግሥታት ማኅበር ላይ አቀርባለሁ ብሎ ለፈረንሣዊ መንግሥት ጠቅላይ ገዢ አመለከተ ።

ሎንዶን ። የኰንስታንቲኖፕል ጋዜጣ አቡኑ ከኰንስታንቲኖፕል ስለ ወጣ ክርስቲያኖች ተንስተውበት ነበርና የቱርክ ጋዜጣ ለዚሁ ነገር በሚገባ ነው ያስወጣሁት ብሎ ይላል

ፓሪስ ። የሩማኒ ሚኒስቴር ብሬቲያና የሚባለው የመስኰብ ጦር ማሰናዳት ለአርመን አገር የሚያስፈራት ነው ፤ ስለዚህ እሷም መሰናዳት ያስፈልጋታል ይላል ።

የ፳፯ ጥር የለት ወሬ ።

ሮማ ። ሙሶሊኒ ዛሬ ከአንድ አሜሪካን ሰው በጦርነት ጊዜ ዘመዶቻቸው ለሞቱባቸው እንዲሰጥ ፻፳፭ሺ ሊር ተቀበለ

ፓሪስ ። የጀርመን የንግድ ሥራ መልክተኛ አለቃ ዛሬ ከቤርሊን ፓሪስ ገባ ፤ የፈሰንሳዊ መንግሥት ላለው ነገር የጀርመን መንግሥት የሰጠውን ምላሽ ነገ አቀርባለሁ ብሏል ። የቱርክ አምባሳደር ዛሬ ወደ ፈረንሳዊ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር መጥቶ በግሪክና በቱርክ መካከል ስላለው ነገር ለመነጋገር ፤ ባሰጣውም ይገባኛል በገዛ አገሬ መከልከል አልችልም ወይ ። ደግሞስ በኛ መካከል ማን ይገባብናል ብሎ ማንም እንዳይገባ አስታወቀ ።

የ፳፰ ጥር የለት ወሬ።

ኰስታንቲኖፕል ። የቱርክ ጠቅላይ ሚኒስትር በጉባኤው ላይ ስለ ግሪክ አቡን ከገር መውጣት ነገር እንዲህ አለ ። በገዛ አገራችን የሚፈልገን ቢሆን አስወጥተነዋልና ስለዚህ በግሪክና በኛ መካከ ሌሎች መንግሥታት አይገቡብንም ብሎ ተናገረ ።

ሎንዶን ። የንግሊዝ መንግሥት ከፈረንሣዊ መንግሥት ላይ የሚፈልገውን ያበደረውን ገንዘብ የመክፈያውን ጊዜ ቆርጦ አመለከተ ።

ፓሪስ ። የፈረንሣዊ ሚኒስትር በአሜሪካን አገር የነበረው ወደ ፓሪስ ተመልሶ ያሜሪካን መንግሥት ለፈረንሣዊ መንግሥት ያበደረውን ገንዘብ እንደሚቻላችሁ ይኸን ያህል በወር እንችላለን እንዳላችሁ ክፈሉ ብለዋል ሲል ተናገረ ።

የ፳፱ ጥር የለት ወሬ ።

ሮማ ። የኢጣሊያ ንጉሥ ለሺሌ ጠቅላይ ሚኒስትር አሌክሳንድር የሚባለው እጅግ የሚመሰገን ምሳ ጋበዘው ። በዚህም ጊዜ ንግሥቲቱም የቤተ መንግሥቱ ሰው ሁሉ የዚሁም የተጋበዘው ሚኒስትር ተከታዮች ነበሩ ።

ፊሬንዝ ። የሺሌ ጠቅላይ ሚኒስትር ከቤቱ ሰዎቹ ጋራ ፊሬንዜ በገባ ጊዜ መልካም አቀባበል ተቀበሉት ።

አቴን ። የግሪክ መንግሥት የቱርክ መንግሥት አቡኑን ያስወጣበት ምክንያት ወረቀቱ ደርሶታል ። ግን የግሪክ መንግሥት ምንም ቢሆን አቡናችንን ማስወጣት አይገባውም ነበርና ስለዚህም ይህን ነገር ለዓለሙ ማኅበር አሳያለሁ ብሏል ።

ሞስኰብ ። በመስኰብ መንግሥት ያለው የኢጣልያን መንግሥት ሚኒስትር በመስኰብና በኢጣሊያ መካከል ያለ ንግድ እያደረ ማለፊያ ሆነ ብሎ ተናገረ ይልቁንም የጋዙ ንግድ እያደረ ስለበዛ በዚያው ነገር አንድ ባንክ ለንግዱ የሚያስፈልግ ለማቆም ተስማምተዋል ።

በልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

መጀመሪያ ዓመት ፣ ቁጥር 9 ።
1re ANNÉE №. ፱

ሐሙስ የካቲት ፲፱ ቀን ፤ ፲፱፻፲፯ ዓ ም።
JEUDI 26 FÉVRIER 1925

ብርሃንና ሰላም
LUMIÈRE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ ሲገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

የጋዜጣው ዲሬክተር ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የራሱን ጉዳይ የሚያሳትም ሰው ዋጋውን እየከፈለ እናትምለታለን ።

ወረታ መመለስ ።

ወረታ ማለት በጎ ነገር ከተደረገለት ልብ የሚነሣ በጎ ነገር ቢቻል አብልጦ መክፈል ማለት ነው ። ይኸንንም ሕፃን ወተት የምትሰጠው እናቱን በመውደዱ በመጀመሪያ ሕይወት በሕፃንነት ይገልጻል ።

መሬት ፍግ ለሚያፈስበትና ለሚያለሰልሰው ገበሬ በተስፋ ትንሽ ዘርቶ ፍሬውን አበርክቶ በመስጠቱ ወረታውን ይመልሳል ።

ውሻ እንኳ በቤቱ የሚያኖረውንና የሚያበላውን ጌታውን ይወዳል ፤ ይከተለውማል ። ቤቱንም ይጠብቅለታል ።

ነገር ግን ሰያፍ ሰዎች ከእንስሳና ከሌላም ፍጥረት ሰንፈው በጎ ነገር ለሚያደርጉላቸውና ለሚያስቡላቸው ሁሉ የተገባ ውለታ ማመስገን በመመለስ ፈንታ የጠላሚዎቻቸው ተቃራኒዎች ሆነው ይገኛሉ ።

ይህም የሚገርም ነገር ነው ። በጎ ነገር እያደረጉ የሚተበሉት ወረታ ክፉ ቢሆን በጎ ሠሪዎቹ በሠሩት በጎ ሥራ ጸጸት ሳይገባቸው አይቀርም ። ግን በዚህ ዓለም በጎ የሚያደርግ ሁሉ ወረታው ክፉ እንደሆነ ከጥንት የተነገረ ነውና በኔ የደረሰብኝ ይህ ሥራ ከሁንም በፊት በጎ በሚሠሩ ሰዎች የደረሰ ነው በማለት ይጽናኑ ይሆናል ።

ወረታ አለመመለስ የክፋት መሠረት ነው ፤ በጎ ለሚያስብለትና ለሚያደርግለት በጎ ሊመልስ የማያስብ ልብ የማይጠቅም ጠማማ ልብ ነው ። ደግ ሥራን ሠሪው ቢዘነጋው የተሠራለት ሊያስበው ይገባል ።

ግን በጎ የሠራ ሰው ደግሞ የበጎ ሥራዬን ወረታ እቀበላለሁ ብሎ ሊያደርግና ሊጠባበቅ ከቶ አይገባውም ። በበጎ ክፉ የሚመልስ ግን ሕሊናው ሲወቅሰው ይኖራልና ውስጣዊ ዕረፍት አያገኝም ። እንግዲህ እኛ ኢትዮጵያውያን በጎ ለማያደርጉልን ለሀገራችን ልጆች ለትልልቆች ለትንሾችም በሚቻለን ወረታ ልንመልስላቸውና ልንረዳቸው እንጂ ልናበሳጫቸው አይገባም ። እንደ አቅማቸው በጎ እንሠራለን ብለው የሚያስቡ ሰዎች ደግሞ በበጎ ሥራችንና ሐሳባችን ከሰው ምስጋና አግኝተን ወረታ እንቀበላለን በማለት እንዳይሠሩ ፤ በበጎ ፈንታ ክፉ ቢያገኛቸውም እየታገሡ በጎነታቸውን ሳያቋርጡ እንዲሠሩ እናሳስባቸዋለን ።

የጀመረውን በጎ ሥራ እስከ መጨረሻ ለጠበቀው የድል አድራጊ አክሊል ይሰጠዋል ።

በደብዳቤ የመጣ ቃል።

እንበርታ ።

ተስፋ መቍረጥ ኃጢአት ነው ። ትጉህ አለመሆንም ሞት ነው ፤ እነዚህ ሁለቱ በሀገራችን እንዳይሠለጥኑ በእግዚአብሔር ኃይል እንቃወማቸው ፤

የኢትዮጵያን ሥልጣኔ በሚናፍቅ ልብ ውስጥ ሁሉ የኢትዮጵያ ሥልጣኔዋ ቀርቦ ይሆን ወይስ ገና ነው የሚል ጥያቄ ፤ ሲወጣ ሲገባ እንዲኖር ያለጥርጥር እንረዳለን ።

ከነዚህም ከልናቸው ልቦች ሌሎች አገሮች የደረሱበትን ሥልጣኔና የራቁበትን መንገድ አይተው ተመልሰው ልትሠለጥን የሚመኙላት አገራቸው የቀረችበትን መንገድ አይተው ተስፋ የሚቈርጡ ፤ ተናደው ተቃጥለው ከዕውቀት ሙቀታቸው የሚቀዘቅዙ ፤ የሚያረክ ውሃ ከሆነ ባሕርያቸውም ተመልሰው እንደ ውርጭ ባንድ ቦታ ድርቅ ብለው ይቀራሉ ።

እንደዚህ ያሉት ልቦች ባሕርያቸው መልካም ነበር ። ነገር ግን ከሁሉ በፊት ሊይዙት የሚገባቸውን ስንቅ ትተዋልና አሁን እንዳልነው በመንገድ ደክመው ፍዝዝ ብለው ይቀራሉ ስንቃቸው መተውም ያለፈውን ዘመን አኳኋን አለመመርመርና አሁን ያለውን አኳኋን አለመመልከት ነው ። ማን ሰው ነው ፤ ከአንድ አገር ወደ አንድ አገር ሲሄድ ባንድ ጊዜ ዘሎ (የሚገባ) የሚደርስ ፤ አገሩንስ በስንት እርምጃ ይደርሰዋል ።

ዳግመኛ እንዴት ያለ ሰው ነው ዛሬ ተወልዶ ዕለቱን የጉልማስነት ሥራ ለመፈጸም የሚችል በፊት ከእናቱ የሚያገኘውን ኃይል ተመግቦ ቀጥሎም የአባቱን ድካም ከጨረሰ በኋላ አይደለምን ።

እንዴትስ ያለ ሰው ነው ፤ ወደ ደርብ ሲወጣ አስቀድሞ ታችኛውን ደረጃ ቀጥሎም ሁለተኛውን እያለ ሳይረግጥ በቅጽበተ ዓይን ከደርቡ ላይ ወጥቶ የሚገኝ ።

እንዴትስ ያለ ገበሬ ነው ዛሬ ዘርቶ ነገ እሸት የሚመኝ ባጭሩ የሚበር መኪናና ዖፍ እንኳን ከፈቀዱበት ቦታ ለመድረስ ጊዜ ያስፈልጋቸዋል እስቲ መቍጠር እንዳይበዛብን ምሳሌ ልናደርጋቸው የሚገባንን ፍጥረታት ሁሉ ፊሳችን እንመልከት ።

አሁን ሠልጥነው ያሉትን ሕዝብ በታሪካቸው ብንሰማ በስንት ትግል ነው ። እንዲያውም በመጀመሪያ ጊዜስ በቀስታ ነው የተጓዙበት ።

ዋና ልንቈረቈርበት የሚገባን ግን እለ መትጋት ነው ። ስለ ምን ብትሉ ፤ ብዙ ልቦች ናቸው አንድ ሰው ስለ ሥልጣኔ ሲነጋገር የሰሙ እንደሆነ ማለት ስለ ትልቅም ስለ ትንሽም የተናገረ እንደሆነ ። ምን ያለ ነገር ነው ይህ አቡጀዲድ መድፍ ባሩድ የሚሠራ ፋብሪካ ነውን፤እንደዚህ ያለ ጥቃቅን ምን ይጠቅማል የሚሉ ።ነገር ግን ልናደርገው የሚቻለንና ልንዘልቀው የምንችለውን ነገር ሁሉ በፍጥነት ልናደርገው ይገባናል።ሥልጣኔ ማለት በጉልሁ ትልልቅ ነገር ብቻ አይደለም።የሚበዛውስ እኛ ልናደርገው የምንችለው ጥቃቅን ነገር ነው።ማለት ቤትን በያይነቱ በሆነ ነገር ማሳመርና በቤት ያለውን ነገር ሁሉ ጥሩ ማድረግ።ልብስም ቢሆን ዕቃም ቢሆን የቤትም ወለል ቢሆን ያጥር ግቢም ቢሆን ንጹሕ እንዲሆን ማድረግ።በቤትም ያለውን ሰው ሁሉ በገባብና በሥርዓት በትክክል ማስኬድ።የቤትን ሰዎች ሥራ አለማስፈታት።ሰዓትና ጊዜ ክቡር መሆኑን በቤት ላሉ ሰዎች መስበክ

በአንዋወር ሁሉ የነቃን መሆን።ልናደርገው ያሰብነውን ይለምድብንልና ጀምረን አለመተው።ይልቁንም በዚህ ዓለም እስካለን ድረስ ደስታ የምናደርግበት ቤታችን ነውና በማናቸውም ሁሉ የተሰናዳ ይሁን።አንድ ደርዘን አረቄ በመግዛት ፈንታ አንድ ወምበር መግዛት ዋና መሠልጠን ነው።የቤትንም ክፍል ብዙ ማድረግ ነው።ማየቱ ደስ የሚያሰኘውን ዕቃ ሁሉ ወደማይታይበት ሥፍራ መክተት ነው።ብዙ መኳንንት ቤታቸውን ስላሳመሩና ደህና አድርገውም ስላከናወኑት በጣም ደስ ያሰኛሉ።እነዚህንም ልናመሠግናቸው ይገባናል።የዲያብሎስ ምንጭ የሆነ አረቄ መግዛትን ትተው ገንዘባቸውን ለቁም ነገር ስላደረጉት።ገንዘባቸውን ለእንደዚህ ያለ ቁም ነገር ስላደረጉት በእግዚአብሔርና በመንግሥት በሕዝባቸውም ዘንድ የተመሰገኑ እንዲሆኑ ቁም ነገራቸውም እየተገለጠ እንዲሄድ ተስፋ እናደርጋለን።እንደዚህ ያሉት ሰዎች ከሁን በፊትም ከዚህም በኋላ ለሚኖሩበት አገርና ለሚገዙት ሕዝብ መልካም አርአያ የሥልጣኔ መሪዎች እንዲሆኑ ተስፋ እናደርጋለን ። ቅዱስ ጳውሎስም ቤቱን አስተካክሎ ማሳደር የማይችል እንዴት አድርጎ ማኅበረ እግዚአብሔርን ማስተዳደር ይችላል ይላል ፩ ጢሞ ም ፫ ቁ ፭።እንግዲያስ ለሰው መመዘኛው ቤቱ ነው ።

እስቲ ከከተማው ውስጥ ወጣ ብለን እንይ ። ቤታቸውን ሰርተውበት ባለ ቦታ ላይ በቀላል ነገር ጥሩ ቤት የሚያሰራ ድንጋይና ዕንጨት ሳርም መልቶ ሥራ ፈትቶ ሳለ በእንዴት ያለ ቤት ተቀምጠው ይኖራሉ ። ለዚህ ነገር የከበሩ መኳንንቶቻችን እንዲያስቡበትና ሳይሰለቹ እንዲደክሙበት እግዚአብሔር ይርዳቸው ። እንዴትስ ያሉ የተመሰገኑ ደጎች ጌቶች ናቸው አስቀድመው ቤታቸውን ቀጥሎም የሚገዙትን አገር እንዲሰለጥንና ወደ ፊት እየገፋ እንዲሔድ የሚያደርጉ ። እንዴትስ የተመሠገኑ ናቸው የምትቀመጥበትን ቤት አሳምረህ ስራ ብለው በግድ አስጀምረው ከሌላው አገር ይልቅ ግዛታቸውን የተሻለ የሚያደርጉ ። እንዴት ያለ አባት ለልጁ የሚያስበው ያሀል በረከት ያላቸው ናቸው ። ያቅምን ያሀል ወደ ፊት መግፋት ነው እንጂ ይህ ቁም ነገር የለበትም አለማለት ነው ። ስለዚህ ነገር ለመርዳት ሌሎች ናቸው እንጂ እኔ አገርን ማሰልጠን ምን ቸገረኝ ማለት ሞት ነው። እነዚያ ሊያደርጉት የምንመኛቸው አገራቸውን ለማሰልጠን የበለጠና የከበደ አሳብ አስጨንቆ ይዞ ተጭኖባቸዋልና ከዚህ ሸክም ያቅማችንን ያሀል በሙሉ ፈቃድና በሙሉ አሳብ ለመሸከም እንትጋ ። እውነት ስለ ኢትዮጵያ ሥልጣኔ የምንመኝ ከሆንን እኛ በተቻለን ነገር ሁሉ እርዳታን መግለጽ ነው ። ብዙ የተመሰገኑ ሰዎች በእውነተኛ ፍቅር እንደሚቃጠሉም የተቃጠልን እንሁን እግዚአብሔርን በመፍራት የሚታሰብ በጎ ፈቃድ ሳይፈጸም አይቀርምና ልንፈጽመው የሚቻለንን ነገር ለማድረግ ፈጣን እንሁን።እዘልቀዋለሁ ይሆንልኛል ማለት ሕይወት ነው።አልዘልቀውም አይሆንልኝም ማለት ግን ቁሞ ሳለ ሞት ማለት ነው።ብርቱ ፈቃድና ትጋት ካለን ከተማርንም የማይቻለን ነገር የለም።ለመፈጸሙ ኃይል የሚሰጥም እግዚአብሔር ነውና በቅማችን እንመገነው ይልቅ ዛሬ የኢትዮጵያ ጧት መሆኑ ምሉ ተስፋችንን ጽፈን እንዲያትምልን ለእግዚአብሔር ለአምላካችን በጸሎት እንስጠው ።

ተወልደ ብርሃን መድኅን ።

ስለ ሌባሽ ምክር ።

በሃገራችን በኢትዮጵያ ስለሚደረገው ሌባሽ ነገር በትንሹ እውቀቴ ያየሁትን እጽፋለሁ፤ከኛ በፊት በነበረው ዘመን ሰው ከንዱ አገር ወደንዱ አገር ሲሄድ ውሎ በመሸበት ጊዜ ከመንደር ሂዶ አሳድሩኝ ብሎ በለመነ ጊዜ እነዚያም ባለቤቶች በደስታ ተቀብለውት ከቤታቸው አግብተው እግሩን አሳጥበው እራቱን አብልተው ከደኅና መኝታ አሳድረው ሲነጋ ይሸኙት ነበር፤እሱም እነሱን መርቆ ፈጣሪውን አመስግኖ መንገዱን ይሄድ ነበር፤አሁን ግን በኛው ዘመን አንድ ድኃ ሰው ከንድ አገር ወደንዱ አገር ሲሄድ ውሎ ቀኑ በመሸበት ጊዜ መንደር ወዳለበት ሄዶ አሳድሩኝ የእግዚአብሔር እንግዳ ነኝ ብሎ ቢለምን እኛ ሌባሽይ እንፈራለን አናሳድርም ብለው ይመልሱታል፤ያም ሰው ጊዜው መሽቶበታልና እንግዴህ ወዴት እሄዳለሁ ብሎ እያዘነ ካጥራቸው ውጭ ከጉድፍ መጣያቸው ላይ ሲጨነቅ አድሮ ሲነጋለት ተነስቶ መንገዱን ይሄዳል፤ይህ ሁሉ ክፋት መደረጉ ምክንያቱ

ባሻይ ሆነ፡ ሕዝቡም የሚመጣበትን መከራ ፈርቶ እንግዳ ላሳድርም ቢል ከፈራው ነገር አላመለጠም፤ የሰረቀው ሌባ በደኅናው ተቀምጦ ያልሰረቀውን ይይዘው ጀመረ፤ ይኸንኑም እኔ ባይኔ አይቻለሁ፤ ከደጃዝማች ብሩ አገር ወለጋ አንድ ሰው ጠመንጃ ተሰርቆበት ሌባሻይ ቢአጠጣ ያልሰረቀውን ሰው ይዟለት የጠመንዣውን ግምት አስር ተቀበለው ያሰውም ገንዘብ የሌለው ድኻ ነበርና እየተረጠበ ከፈለ፤ እንደዚሁ ሰው የሚደረገው በየገሩ ብዙ ነው፤ ይህ ሰው ተረጥቦ ተከፈለ በኋላ በሃገሩ እጅግ ሌባ ቢበዛ ክቡር ደጃዝማች ብሩ ራሳቸው ወጥተው ከሰፊ ሜዳ ድንኳን አስተክለው በሃገር ሰው እንዳይቀር አስከትተው በተሰበሰበ ጊዜ በየጐረቤትህ ያለውን ሌባ አውጣ አውጥተህ ሳትነግረኝ ከቤትህ አትገባም ብለው ሕዝቡን ቢይዙት እንኳን በቅርብ ቀን የተሰረቀው ይቅርና ብዙ ዘመን የቆየውን እያወጣ የገሌን ከብት እገሌ ነው የሰረቀው እያለ ባገር የተደረገው ነገር ሁሉ አንድም ሳይቀር አውጥቶ ነገራቸው፤ የተነገረበትም ሰው እየተያዘ ቢጠየቅ አዎን እያለ አመነ፤ ከዚሁ ውስጥ ከዚህ በላይ ተሰርቆበት ያልኩት ሰው ጠመንጃውን የሰረቀው ዋናው ሌባ ተይዞ ቢመረመር አዎን እኔ ነኝ የሰረቅሁት ብሎ ተናገረ። እንግዲህ ያ ሳይሰርቅ ተይዞ የከፈለ ድኻ ሰው እንባ በማን ላይ ያርፍ ይሆን ።

ደግሞም ከሩቅ ሳንሄድ አሁን በቅርቡ የመድኃኔ ዓለም ዕቃ ከቤተ መቅደሱ ውስጥ ጠፍቶ ያ ሁሉ ሌባሻይ ሲጠጣ ክርሞ ያንድ ዕቃ ምልክት እንኳ ሳያገኝ ቀረ። የመንግሥት ዕቃ ጠፍቶ ያላገኘ የድኻውንማ ገንዘብ በምን ያግኝለት ። አሁን የኢትዮጵያ መንግሥት የድኻውን መበደልና መጐዳቱን አይወድምና የዚህን የሌባሻይ ነገር አስቦ አንድ ብልሃት ቢያደርግለት ከሕዝቡ መጠን የሌለው ምስጋና ባገኘ ነበር ። ሕዝቡም ዕዳ ፈርቶ እንግዳ አላሳድርም ብሎ በኋለኛው ቀን በወንጌል ቃል ከመወቀስ ይድን ነበር ስል አመለክታለሁ ።

ወልደ ሰማዕት ወልደ ትንሣኤ ።



ስለ አባ ደስታ ዕረፍት ከደብረ ሊባኖስ የመጣልን ቃል ።

አባ ደስታ ከተወለዱ ከ፲ ዓመት ጀምሮ እስከ ፳፭ ዓመታቸው የንባብና የጽሕፈት፤ የዜማና የቅኔ ትምሕርት እየተማሩ አደጉ ። ደግሞ ከዚህ በኋላ በወታደርነት ኑሮ ለመኖር አሳብ ከተነሳባቸው በኋላ ይህን አሳባቸውን ትተው የመጻሕፍትን ትርጓሜ ለመማር ጀመሩ ። በ፴ ዓመታቸው ግን በሙሉ አካላታቸው እየተዛወረ የሚያም ደዌ አደረባቸው ። በዚሁም ምክንያት ለጠበል ሲሉ ደብረ ሊባኖስ ገቡ ። በዚያም ሥጋ ወደሙ እየተቀበሉና ጠበሉን እየጠጡ ብዙ ወራት ከቆዩ በኋላ ጥቂት ጤና ስላገኙ ከእንግዲህ ወዲህ እስከ ዘመኔ ፍጻሜ ከደብረ ሊባኖስ አልወጣም ብለው ለእግዚአብሔር ብፅዓት አድርገው መነኰሱና በዚያው ተቀመጡ ።

አባ ደስታ በደብረ ሊባኖስ እንደ ገድል አድርገው ይዘውት የነበረ ሥራ ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈው ነው ።

፩ኛ ፡ ከጧት እስከ ፫ ሰዓት ያልተማሩትን መጽሐፍ ከመምሕሩን እየተማሩ፤ የተማሩትን መጽሐፍ ላልተማሩት እያስተማሩ ይውሉ ነበረ ። ከ፫ ሰዓት እስከ ፮ ሰዓት ወደ ቤተ ክርስቲያን ሒደው ቅዳሴ አስቀድሰው ቢመቻቸው ሥጋ ወደሙ ተቀብለው ይመለሱ ነበረ ። ከ፮ ሰዓት እስከ ፲ ሰዓት ወደ ጠበል ሒደው ጠበል ጠጥተው በ፲፩ ሰዓት ወደቤታቸው ተመልሰው እህል ይቀምሱ ነበረ ። የባሰ ነገር ካላገኛቸው በቀር የዘወትር ሥራቸው ይህ ነበረ ።

፪ኛ፡ በደብረ ሊባኖስ ያሉትን በሽተኞች በሽታቸው ተስቦም፤ ቁስልም፡ ሌላም የሚጋባ በሽታ ቢሆን ሳይፈሩ እየሔዱ ይጠይቁ ነበረ ለቁስለኞቹም ሳይጠየፉ ቁስሉን እያጠቡ የተለመደ የሀገር መድኃኒት እያደረጉ ይረዱ ነበረ ።

፫ኛ ፡ ዶማ ፡ አካፋ ፡ ይህን የመሰለውን የመሬት መቈፈሪያ በቤታቸው አሰናድተው አስቀምጠው በደብረ ሊባኖስ ቀባሪ የሌለው ድኻ የሞተ እንደሆነ ወይም ከሩቅ አገር ሬሳ ሲመጣ ያዩ እንደሆነ ዶማና አካፋቸውን ይዘው ሂደው ሌሎችንም ሰዎች እርዱኝ እያሉ መቃብር እየቆፈሩ ይቀብሩ ነበረ ።

፬ኛ ፡ ከአባታቸውም ቤት፤ ከሌላም ከዘመድና ከወዳጅ የሚመጣላቸውን የእለት ምግብ እየወሰዱ ለተቸገሩ ድኖች ያክፍሉ ነበረ ።

፭ኛ ፡ የመጻሕፍትን ትርጓሜ ከግዕዝ ቋንቋ ወደ አማርኛ ቋንቋ እየተረጐሙ ይጽፉ ነበረ። ከግዕዝ ቋንቋ ወደ አማርኛ ቋንቋ እየተረጐሙ የጻፉዋቸው መጻሕፍት ቍጥራቸው ከዚህ እንደሚከተለው ነው ።

፩ኛ ። መዝሙረ ዳዊት ።
፪ኛ ። አርባዕት ወንጌል ።
፫ኛ ። መጽሐፈ ኪዳን ።
፬ኛ ። ማር ይስሐቅ ።
፭ኛ ። ቅዳሴ ማርያም ።
፮ኛ ። ውዳሴ ማርያም ።
፯ኛ ። ውዳሴ አምላክ ።

ሌሎችም ለሕፃናት መማሪያና ለጸሎት የሚሆኑ ትንንሾች መጻሕፍት እየተረጐሙ ጽፈዋል ።

በዚሁ በጭሩ ኑሮዋቸው አንዳንድ ጊዜ ጤና ባገኙ ወራት ከዚህ በላይ የተጻፈውን ሥራ ሲሠሩ አንዳንድ ጊዜም በሽታቸው በጠነከረባቸው ወራት በቤታቸው ሲውሉ በተወለዱ በ፸፯ ዓመት፤ ደብረ ሊባኖስ ገብተው መንኵሰው በተቀመጡ በ፲፰ ዓመት በየካቲት ፰ ቀን እሁድ በ፲፱፻፲፯ ዓመተ ምሕረት ከዚህ ዓለም ድካም አርፈው በተስፋው በኖሩበት በዚያው በደብረ ሊባኖስ ገዳም ተቀበሩ ።

በዚህ ቀን የአባ ደስታ ወዳጅ የሆነ ሰው ከዚህ ቀጥሎ ያለውን የልቅሶ ግጥም ተናገረ ።

እጽፋለሁ ብዬ ወንጌል ትርጕሙን ።
ወዴት ወሰደው ጣሉት የቀለም ቀንዱን ።

ይህንንም መጻፋችን የአባ ደስታን ሥራና ዕረፍት ለመናገር ብቻ አይደለም ። ነገር ግን በገዳም የሚኖሩ መነኰሳት ሁሉ በሚቻላቸው ነገር ለተቸገሩ ሰዎች ቢረዱ በወዲያኛው ዓለም የበለጠ ክብር እንዲያገኙ እርግጥ መሆኑን ለማሳሰብና ለማስረዳት ብለን ነው ።

ሁለት ፍየሎች ።

ገደል ባለበት ባንድ ተራራ ላይ ሁለት ፍየሎች ሣር ይግጡ ነበር ። የገደሉም መተላለፊያ ሁለቱ ባንድ ጊዜ ሊተላለፉበት ወይም አንዱ ወደኋላው ዞሮ ሊመለስበት እስኪማይችል ድረስ እጅግ ጠባብ ነበረ ። ከበታቻቸውም ያለው ደግሞ እልም ያለ ገደል ነበረ ። ሁለቱ ፍየሎች እንዴት እደረጉ ይመስላችኋል ። አንደኛው ፍየል በዚህ በጠባቡ ገደል መተላለፊያ ላይ ቀስ ብሎ ተጋደመ አንደኛው ደግሞ በባልንጀራው ላይ ተረግጦ ሳይጐዳው ቀስ ብሎ አልፎ ሔደ የተጋደመው ፍየልም ከተኛበት ቦታ ተነሥቶ በደኅና ተሻግሮ ክንዱ ወዳንዱ እየዘለለ በተራራው ላይ ደስ ብሎት ሣሩን ሲግጥ ዋለ ።

ደግሞ ሁለት ሌሎች ፍየሎች ከንድ ወንዝ ተነሥተው ወዳንድ ተራራ ወጡ ። በመጨረሻም ብዙ ጐርፍ ከጐረፈበት ግደል ደረሱ ። ስለጐርፉ መሻገሪያም አንድ ትልቅ ግንድ በዚያ ተጥሎ ነበር ።

ፍየሎቹም እያንዳንዳቸው ያዩት ነበርና እያንዳንዳቸውም በፊት ለማለፍ ይፈልጉ ነበር ።

ሁለቱም ባንዳንድ እግራቸው ግንዱን ረግጠው እርሱ ይመለሳል ያም እርሱ ይመለሳል በማለት ሁለቱም ይጠባበቁ ነበር ።

ከነሱም አንዱ እንኳ መንገዱን ሊለቅ የወደደ አልነበረም ኋላ ግን ሁለቱንም ስለ መሻገሪያ ከተጋደመው ግንድ መካከል ደረሱ ።

የዚያን ጊዜም እየተጋፉ በቀንዳቸው ይዋጉ ጀመረ ሁለቱም ተንሸራተው ከበታቻቸው ባለው ጐርፍ ውስጥ ወደቁ ጐርፉም ይዟቸው ሄደ ።

ትምክሕት ረሌኅ ተየየዘ ገደል ከመግባት በፍቅር ተቻችሎ ተስማምቶ አብሮ መኖር ይበልጣል ።

ተጋድሞ ያሳለፈችውን ፍየል ምሳሌ ብንከተል ለራሳችን ድኅነ ወንድሞቻችንንም ማዳን በተቻለን ።

ማስታወቂያ ።

የካቲት ፳፫ ቀን ሰኞ በቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን የዓድዋ ጦርነት መታሰቢያ በዓል በታላቅ ክብር ይከበራል የበዓሉንም ሁኔታ በሚመጣው ጋዜጣ እንጽፋለን ።

ይኸውም መታሰቢያ በ፲፰፻፹፰ ዓ ም የካቲት ፳፫ ቀን በዓድዋ ላይ በተደረገው ጦርነት ውስጥ ስለ ሀገራቸው ስለ ኢትዮጵያ ሰማዕታት ሁነው ያለቁትን ወንድሞቻችንን የምናስብበት ቀን ነው ።

ከኢጣልያ መንግሥት ሌጋሲዮን ።

በቴሌግራም የመጣ ቃል ።

የ፩ና የ፪ የካቲት የለት ወሬ ።

አቴን ። የቴሌግራም አጃንስ ፡ ስለ ፓትርያክ በሆነ ነገር የግሪክ መንግሥት አንድ ሌላ መንግሥት በመካከል እንዲገባ ለምኑዋል የሚለው ወሬ ሐሰት ነው ይላል ።

ፓሪ ። ስለ ኤንትርአለያንስ ዕዳ የእንግሊዝ ምላሽ መጥቶዋል ሙሴ ሄርዮትና ሙሴ ክሌማንቴል በቀጥታ እንዲነጋገሩ ወደ ሎንድራ ይሄዳሉ ።

የ፬ የካቲት የለት ወሬ ።

ፓሪ ። የኢጣልያ አምባሳደር ከሙሴ ሄርዮት ራጋ ተገናኘ ። ጋዜጦች የኢጣልያ መንግሥት ለእንግልጣር ስለሚከፍለው ዕዳ የፈረንሳዊ መንግሥት ሐሳቡን ሊያውቅ እንደሚወድ ይናገራሉ ።

እንጎራ ። ከቍስጥንጥንያ ፓትርያርኩን ስለ ማስወጣት የውጭ ምኒስትር በሕዝብ ጉባዔ ፡ ነገሩ በመንግሥት ውስጥ የሚታሰብ እንደሆነ ተናገረ ። በዴፑቴ መካከል ብርቱ መቃወም ተነሣ በሽጉጥም ተታኰሱ ። ጉባዔው ዴፑቴ ወደ ጉባዔ ጦር ይዘው እንዳይመጡ የሚከለክል ሥርዓት ሊያደርግ አቆመ ።

ያ፯ የካቲት የለት ወሬ ።

በርሊን ። የፓስት ምኒስትር የነበረው ሆየፍ ተያዘ ። ጋዜጦች ጉቦ በልቶ ስላደላ በፍትሐ ነገሥት ሊመረመር ቀርቧል ይላሉ ።

የ፰ የካቲት የለት ወሬ ።

ማድሪድ ። ወንበዴዎች ወደትልቅ ሆቴል ገብተው በዚያ የነበሩ እንግዶችንና አገልጋዮችን በሚያፈዝ መድኃኒት አፍዘው እጅግ የከበሩ ዕንቆቻቸውን ሰረቁዋቸው ብለው ጋዜጦች ይጽፋሉ ።

የ፲፩ የካቲት የለት ወሬ ።

ሮማ ። የሙሴ ሙሶሊኒ የጊዜው ጤና ማጣት ወደመሻል ብሷል ።

የ፲፪ የካቲት የለት ወሬ ።

ሶፊያ የቴሌግራፍ አጃንስ ወሬ የሕዝብ ደኅንነት አለቃ ፍላይትሮቢች እንደ ተዋጋ የሙኒሲፓሊቴ ጸሐፊ እንደተገደለ ይጽፋል ። የዋና ወታደሮች ሰፈር ዘበኛ ትናንትና ማታ በሰው እጅ ሞተ ። በዚያች ሰዓትም የኮሙረስት ዴፑቴ በልታወቀ ሰው እጅ ሞተ ። ሊከተሉት የቃጡ ሹማምንትንም ወግቶ አመለጠ ግጋርዎችም የሁከተኞቹን ሥራ ሊያግዱ ብርቱ ሥርዓት አድርገዋል ።

በልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

መጀመሪያ ዓመት ፤ ቁጥር ፲ ።
1re ANNÉE № 10

ሐሙስ የካቲት ፳፮ ቀን ፲፱፻፲፯ ዓ ም።
JEUDI 5 MARS 1925

ብርሃንና ሰላም
LUMIÈRE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን በአገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሲገዛ ሲፈለግ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

የጋዜጣው ዲሬክተር ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ይስታውቁ ።

የራሱን ጉዳይ የሚያሳትም ሰው ዋጋውን እየከፈለ እናትምለታለን ።

ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።

ስለ አድዋ ጦርነት የመታሰቢያ በዓል ።

የካቲት ፳፫ ቀን በአራዳ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ታላቅ በዓል ተደረገ ይኸውም በዓል የዛሬ ፳፱ ዓመት በአድዋ ላይ ስለ ተደረገው ጦርነት መታሰቢያ ነው።

በዚህም ቀን ካህናቱ መዘምራኑ ግና በመንፈቀ ሌሊት ደወል ደውለው መጥቅዕ መትተው ደስ በሚያሰኝ ዝማሬ ሲዘምሩ አደሩ ከጧቱ በ፪ሰዓት ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን በብዙ ሠራዊት ታጅበው በታላቅ ግርማ ሆነው ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ሄዱ አባታችን ብፁዕ አቡነ ማቴዎስና ዕጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስም ወደ ቤተ ክርስቲያኑ መጥተው ነበር። ሠራዊቱ ግን ከብዛቱ የተነሣ ባደባባዩ ካለው ሜዳ ጀምሮ እስከ ገበያው ድረስ ግጥም ብሎ እርስ በራሱ ይጋፋ ነበር ነጋሪቱም ሲጐሸም በመላው ከተማ ይሰማ ነበር ። ከዚህ በኋላ በ፬ ሰዓት ተሩብ ታቦት ወጣና ዑደት ተደረገ።በዑደቱም ውስጥ የታላቁ ንጉሥ የዳግማዊ ምኒልክ ፎቶግራፍ ተይዞ ነበር ። ፎቶግራፉንም ያየው ሰው ሁሉ የደግነታቸውንና የርኅራኄያቸውን ነገር በዚህም ቀን ሀገራቸውን ኢትዮጵያን ከጠላት እጅ እንዳዳኑዋት እያሰበ ሲያደንቅ ዋለ ።

ልዑል ራስ መኰንን ።

በዓድዋም ጦርነት ጊዜ የሠራዊት ዋና ጠቅላይ ሁነው የጀግንነት ሥራቸውን የፈጸሙ ልዑል ራስ መኰንን አባ ቃኘው ናቸው።ስለዚህ ስማቸውን በክብር ልናነሳው ይገባናል ።

ከዑደት በኋላም ልዑል አልጋ ወራሽ ባለወርቅ ዘርፍ ቀይ ጥላ ተይዞላቸው በክቡራን መኳንንቶቻቸው መካከል በወምበር በተቀመጡ ጊዜ ካህናቱ ልብ በሚመስጥ ጣዕመ ዜማ ወርበው ያስረግጡ ጀመር ።

በዚህም ጊዜ ፎቶግራፍ አንሺዎች ፎቶግራፍ ለማንሣት ይጣደፉ ነበር ። ወረቡም ከተፈጸመ በኋላ አባታችን ብፁዕ አቡነ ማቴዎስ ተነሥተው ደስ የሚያሰኝ ምክር መክረው አቡነ ዘበሰማያት ሰጡ ።

በዓሉም በ፩ሰዓት ተ፳ደቂቃ በታላቅ ደስታ ተፈጸመልን ስለ በዓሉም ክብር ፳፩መድፍ ተተኰሰ ይኸም ሲሆን የእምቢልታውና የመለከቱ ድምፅ እጅግ ደምቆ ነበር ።

ከዚህም በኋላ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን በብዙ ዓጀብ ታጅበው ከክቡራን መኳንንቶቻቸው ጋራ ወደቤተ መንግሥቱ ተመለሱ

ሥራ እንውደድ ።

ለሰው ሁሉ የሚገባው እግዚአብሔርን መፍራት ንጉሥን ማክበር አገርን መውደድ ነው ። አገርንም የመውደድ ፍጻሜ በሥራ ላይ መጠንከር ነውና ሥራ በመሥራት የሚገኘውን ጥቅም ማወቅ ይገባናል ። ምድር ከዘር በፊት ፍሬ እንዳታስገኝ ማናቸውም ሰው ሁሉ ከትምርትና ከሥራ አስቀድሞ ሥልጣኔን አያገኝም ። ሥልጣኔ ማለትም የነገርን ስልት አከናውኖ መመለስና ሥልጣኔን በአፍ መመኘት ብቻ አይደለም ። ይህም ሳይቀር የምንችለውን ሥራ ጠንክረን እየሠራን በቅንነት ጌቶቻችንን ልናገለግላቸው ይገባል ።

በሥራ ላይ ጠንክረው የሚገኙትንም ሰዎች የማዕርጋቸውን ማነስ ሳንመለከት ለሥራ በመትጋታቸው እናመሠግናቸዋለን እነሆ ጉራጌ ለሥራ ታጥቆ ተዘጋጅቶ በመዋሉ የሚመሠገን ነው ። ለሥራም በመትጋቱ ለሰነፎች ሁሉ የትጋት አርዓያ ሊሆን የተገባ ነው ። ነገር ግን በመመሥገን ፈንታ ሠራተኛ ሁሉ የሚቀበለው ነቀፌታ ብዙ ነው ።

ጉራጌ ለከተማው ሰው ሁሉ አገልጋይ ሁኖ ሥራ ሠርቶ ስለኖረ ያገሩ ስም ከነቀፋ ተቈጥሮበት ይህ ጉራጌ እየተባለ ይነቀፋል ። ጉራጌ ማለት ከትግሬ የተከፈለ ጥንተ ክርስቲያን እንደነበረ ባነጋገሩና በታሪክም እንመለከታለን ።

ዳግመኛም ብረት ሠሪውን ሸማኔውን ቁርበት አልፊውን ሸክላ ሠሪውን ይኸን የመሰለውን ሠራተኛ ሁሉ ጠቢብ እያሉ የምስጋናውን ቃል ወደ ነቀፌታ መልሰው ይሳደቡበታል ይህም ምንም ለተናጋሪው ስድብ ቢመስለው በተመልካቹ ዘንድ ምስጋና ነውና እነዚህ ከላይ የቆጠርናቸው ሰዎች ጠቢብ ስለ ተባሉ ብዙ አያስቈረቍራቸውም ።

አሁንም ሥራውን ወደ ሠሪውን መንቀፍ አይቻልምና [illegible] ናቸው አይገባም ።

ጉራጌዎች ሥራ ከመውደዳቸውና ለሥራ ቀመጣጣራቸው የተነሣ አያሌ ጥበብ ለምደዋል ። ግምብ መገምባት አናጢነት ሸማ መሥራት በመኪና መስፋት ሌላም ልዩ ልዩ የሆነውን ሥራ ሁሉ ለምደዋል ።

ሥራ አይጸየፉም ንግድም በየዓይነቱ ለምደዋል የኢትዮጵያ ሰው ሁሉ እንደነሱ ለሥራ ቢተጋ ሀብታም እንደሚሆን ጥርጥር የለውም ።

እንግዲህ ጉራጌዎች ሥራ የሚወዱ ወንድሞቻችን ናቸውና እንውደዳቸው እንጂ አንናቃቸው ።

ተሸካሚም ለመጥራት በፈለግን ጊዜ ጉራጌ ጉራጌ ብለን በመጥራት ፈንታ ተሸካሚ ተሸካሚ ማለት ይገባል ።

ተሸካሚ ባንድ ሕዝባችን ወገን ስም ልንጠራው አይገባንም ከሁላችን የደኸየ ተሸክሞም የተዋረደ ሥራ ሠርቶም ቢሆን እንጀራ እንደሚበላ እናድርገው ። በመናቃችንና በመሳደባችን ሲሳይ ከሚያገኝበት ሥራ እንከልክለው ። ሥራ የሚወድና የሚሠራ አንድ ወገን ከሆነ ፤ የቀረው ወገን እየሰነፈ ፤ ሥራ የሚወድና የሚሠራ ወገን ግን እየበረታ እየበለጠገ እንዲሄድ የተገለጠ ነገር ነው ።

እንግዲህ ሁላችን ሥራ እንደሚወዱ ወንድሞቻችን ሁነን ሥራ ብንወድና ለሥራ ብንጣጣር ብንማርም የሰውን እጅ እያየን ከመሰቀቅ እንድናለን ።

ቅንዓትና መፎካከር ።

ሌሎች ሰዎችን ስለተመቻቸውና ደስ ስላላቸው ሥራቸውም ስለቀናላቸው ፤ የሚያስጠላ የቅንዓት ሐሳብ ፤ ወሰን የሌለው ስንፍና ከመላበት ልብ ይነሣል ።

ቀናተኛ ግን ልቡናው ሁል ጊዜ በእሳተ ቅንዓት ሲቃጠል ይኖራልና ማንም ደስ ብሎት ሊኖር አይወድም ። ስለዚህ ሃብታሞች እንዲደኸዩ፤ደስ ያላቸውም እንዲያዝኑ በብርሃን የሚመላለሱም በጨለማ ላይ እንዲወድቁ ብቻ ይፈልጋል በዚህችም ስስታም በሆነች ኑሮው ይህን ለማድረግ ብቻ ይጣጣራል።

ለበጎ ነገር የመፎካከር ሐሳብ ከቅንዓት የተለየ ነው ። የሌሎችን ሙያ አይቶ አደራረጋቸውንም ተመልክቶ እንዳየው አደራረግ ለማድረግ በሙሉ ብርታት መጣጣር ። ማለት ፤ ሌሎች የደረሱበትን ብርቱ ሥራ አይቶ እነሱን በሥራ ለመተካከል ወይም ለመብለጥ ያለምቀኝነት በሙሉ ኃይሉ መበረታታት ነው

ባንድ አገር በሚኖሩ በመኳንንቱና በሠራተኞቹ መካከል ቅንዓት ቢገባ መተማማትንና ጠብን ያመጣል ።

በሥራ እንብለጥ ብለው ቢቀዳደሙ ግን ሁሉም እያንዳንዱ የተሻለ እንዲሆንና በሌሎቹም ፊት ሊመሰገን ያስባል እንጂ ሌላውን ለመጉዳት አያስብም ።

በሥራ በልጦ የተመሰገነውም ደግሞ ለቀሩቱ አርአያ ይሆናል ማለት እርሱ እንደ ተመሰገነ እንመሰገናለን እያሉ ለመብለጥ እንዲጣጣሩ መነሳሻ ይሆናል ።

በሥራ የበለጠ በሚመሰገንበት አገር ድንገት አደጋ በሆን ጊዜ እበልጣለሁ እበልጣለሁ የሚል ሐሳብ ይነሣና የሰው [illegible] ይበረታል ። ሁሉም እያንዳንዱ ወደኋላ እንደማይቀር ይፈልጋልና ስለዚህ ጉብዝና ጉብዝናን ትወልዳለች ።

ከደጋውም ብዙዎችን በማዳናቸው እንደ ተአምራት የሆነ ነገር ያደርጋሉ ።

ቅንዓት ግን የስስት ፍሬ ናትና ሌላውን በበጎ ሥራ በመርዳት ፈንታ አስጠልታ ሌላውን በመከራ ላይ ለመጣል ታስመኛለች ። መልካሙንም ነገር መልካም ነው ለማለት ይቸግራታል ። ይህች ክፉ ሐሳብ በሁላችንም ሹልክ ብላ ገብታ የምትገኝ ናትና የዕገሌ ናት ብለን ልንወስናት አንችልም ነገር ግን በእግዚአብሔር ኃይል ከየልባችን ልንነቅላት ይቻለናል ቅንዓት በሌለበት መስማማት ይነግሣል ። መስማማትም ካለ ዘንድ ሁሉ ነገር ይተካከላል ።

እንግዲህ ቀናተኛ መሆን በቅኖች ፊት ነውረኛ የሚያደርገን ሐሳብ ነውና ፈጽመን ከሱ እንራቅ ።

ልብለጥ በማለት በሐሣብም በሥራም መጣጣርና ወደ ፊት መግፋት ግን ወደ መመሥገን የሚያደርሰን ነገር ነውና ልንፈጽመው ይገባናል ።

በመንፈሳዊም በሥጋዊም ሥርዓት ሁሉ ፡፡ ቅንዓት የማይገባ ነገር ነው ፡፡ በጎ ሥራ ለመሥራት መቀዳደም ግን የተገባ ነው ፡፡

ቅዱስ ጳውሎስም በጎ ሥራ ለመሥራት ተቀዳደሙ ብሏል ፡፡

አቶ ወልደ ሰማዕት ወልደ ትንሣኤ ።

በብርሃንና ሰላም በ፴ነኛ ቁጥር ለሌባሻይ ስለ ጻፍከው ቃል እጅግ አመሰግንሃለሁ ይኸውም እንዲፈጸም ተስፋ አደርጋለሁ ።

ከውጪ አገር የመጣ ልዩ ልዩ ወሬ ።

የእንግሊዝ ንጉሥ አዲሱን ሙዚቃ ለመመረቅ ወደ ቤተ መንግሥቱ ቤተ ጸሎት እንደሔዱ ።

የእንግሊዝ ንጉሥና ንግሥት ወደ ቤተ መንግሥቱ ቤተ ጸሎት ወደ ቅዱስ ያዕቆብ አዳራሽ በሰንበት ቀን ገብተው ነበርና ንጉሥ ለቤተ ጸሎቱ የሰጡትን ሙዚቃ ለመመረቅ የቤተ መንግሥቱ ቤተ ጸሎት አለቃ የሎንዶን ኤጲስ ቆጶስ መጡ ።

ከጡዋቱ በ፬ ሰዓት ተኩል ቅዳሴውና ስብከቱ ተጀመረ የማኅበሩ ሰዎችና የሚዘምሩ ልጆችም ሞልተው ነበርና መዝሙሩ በጣም ደምቆ ነበር ።

ኤጲስቆጶሱም በጉባኤው ውስጥ ስብከት አደረጉ ። የተሰበከውም አንቀጽ (፩ቆሮ ፲፬ ፲፭) ።

"እንግዲህ ምን ይደረግ ፡ በመንፈስ እጸልያለሁ በልቡናዬም እለምናለሁ ፤ በመንፈስ እዘምራለሁ ዳግመኛም በልቡናዬ እዘምራለሁ" የሚለው ቃል ነበረ ።

በሙዚቃውም ላይ የሚከተለው ቃል ተጽፎበት ነበር ። ከፍ ላለው ለእግዚአብሔር ክብርና በዚህ በቤተ መንግሥቱ ቤተ ጸሎት አንድነት ላላቸው ለሙዚቀኞች መታሰቢያ ከግርማዊ ንጉሥ ከ፭ኛ ጆርጅ የቆመ ይላል ።

የእሳት መነሣት በፓሪስ ።

በሬ ሮመር በሚባለው ልብስ በሚሠራበት ፋብሪካ እሳት ተነሣና ብዙ ጉዳት ጐዳ ሠራተኞቹ ግን ወጥተሙ ስለነበረ አንድ ሰውም አልሞተም ።

የተቃጠለውም ኪሣራ ከመቶ ሺ ጅኒ በላይ ነው ።

የእንግሊዝ ንግሥት ።

የእንግሊዝ ንግሥት የእጅ ጥበብ በመርፌ ከሚሠራበት የቤተ መንግሥት ተማሪ ቤት ሔደው አዩ ።

ስለ ሰር ሊ ስታክ በሰው እጅ መሞት ።

ስለ ሰር ሊ ስታ በሰው እጅ መሞት አያሌ ሰዎች ተይዘዋል ሹማምንትም ዓይናቸውን በሁለት ተማሪዎች ላይ ጥለዋል ።

እርሳቸውም በነገሩ የተባበሩ እንደሆኑ ከብዙ ጊዜ ጀምሮ ተጠርጥረዋል ። ነገር ግን እስካሁን ድረስ ምልክት ሊገኝባቸው አልተቻለም ነበር ።

መሐመድ ኤፌንዲ ኢስማዒልን በመያዝ የተገኘው ነገር ጥርጣሪያቸውን ወደማጽደቅ ብሏል ።

የተማሪዎቹን ቤቶች ሊፈትሹ ቄረጡ ።

ረቡዕ ዕለት ተፈተሸና ተማሪዎቹ ፈርተው ይሆናል ጠፉ እንደ በደዊን ለብሰው በባቡር ገብተው ወደ ሐማም ተሣፈሩ ። መልእክተኞቹም እንደ በደዊን ለብሰው በባቡሩ ውስጥ ገብተው ሸፍቶቹም ሳይጠረጥሩዋቸው ከርሳቸው ጋራ ተቀመጡ በቴሌግራም መልእክት እያሳለፉም ባቡሩ ሓማም ሳይገባ ባቡሩን አቁመው ዘበኞች ከብበው ተማሪዎቹ ተያዙ የተገኘባቸውንም ሽጉጥና ጥይት እንዲመረመር ወደካይሮ ሰደዱት ።

በደብዳቤ የመጣ ቃል ።

እንፋቀር ።

እግዚአብሔር አምላካችን አስቀድሞ በነቢያት ፤ ኋላም በሐዋርያት አድሮ ያጻፋቸውን መጻሕፍት ብሉያትና ሐዲሳትን ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ተመልክተን ብንመረምራቸው የበጎ ነገር ሁሉ መጀመሪያና መጨረሻ ፤ ፍቅር እንደሆነች ሲያመለክቱን እናያለን እንጂ እርስ በርሳችሁ ተቀያየሙ ፍቅር አትጠቅማችሁም የሚል ቃል አናገኝባቸውም ።

ከብዙ በጥቂቱ ደግሞ በየክፍላቸው ሊመለከት የሚወድ ሰው ቢኖር ፤ በኦሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ ፲፱ ቁጥር ፲፯ እስከ ፲፰ ። ፩ኛ ዮሐንስ ምዕራፍ ፬ ቁጥር ፯ እስከ ፲፩ ። ዳግም ቁ ፳ ቢመለከት የእግዚአብሔር ትእዛዝ ፍቅር እንደሆነች ያውቃል ።

እንግዴህ ምስክርነታቸው የታመነና የማይለወጥ የሆነ (ሉቃ ፤ ምዕ ፤ ፲፯ ቁ ፯ ።) ከየክፍላቸው [illegible] እነዚህን ቃላት ልብ አድርገን ከተመለከትን በኋላ ፤ እያንዳንዳችን ልባችንን ብንመረምረው ምን ዓይነት ፍሬ እናገኝበት ይሆን ። ያ አባታችን አዳምን ከእግዚአብሔር አምላካችን የለየ ፤ የስሕተት መጀመሪያ የሚሆን ምኞት የሚባል የራስን ጥቅም ብቻ መፈለግ አይደለምን ።

ይህም ቃል ከሐሰት የራቀ የታመነም መሆኑን ለመረዳት በኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ ፫ ቁጥር ፭ ፡ ብንመለከት ። እግዚአብሔር ያውቃልና ከእርስዋ በበላችሁ ቀን ዓይናችሁ እንድትከፈት እንደ አምላክም ትሆናላችሁ ። መልካምንና ክፉን ታውቃላችሁ የሚል የዲያብሎስን ቃል በሰሙ ጊዜ ፤ አዳምና ሔዋን ፤ የዘለዓለም ሕይወት የሚሆን ፍቅረ እግዚአብሔርን በመዘንጋት ዕፀ በለስን በልተው ፤ በሕይወት ፈንታ ሞትን ፤ በበረከት ፈንታ እርግማንን እንደ ተቀበሉ ። እግዚአብሔር አምላክም በማይመረመር ጥበቡ ያዘጋጀላቸውን ተድላ ደስታ አጥተው ፤

የዲያብሎስ ባሮች ሆነው ከገነት እንደ ተሰደዱ የሚያስረዳ ቃል እናገኛለን ።

እንግዲያስ እነዚህ ቃላት የተጻፉበት ምክንያት ለተግሣጽና ለትምህርት እንደሆነ አውቀን ፡ ይኸን ዲያብሎስ የሚባል ከአባት የቆየ ባላጋራ ደግሞ በኛ ዘመን ሠልጥኖ እንዳለ ዘወትር ማሰብ የግድ ያስፈልገናል ።

ከዚህም ቀጥለን ፡ የገነት ምሳሌ የምትሆን ፡ እንደ ሌሎች መንግሥታት እንኳ ከዚህ በፊት የሰው ጥበብ ረዳት ያላገኘች በጥበበ እግዚአብሔር ተዘጋጅታ ተድላ ደስታን የምትሰጥ ሀገራችን ኢትዮጵያን የምንጠብቃት፡ እርስበርሳችን በመፈቃቀር እንደሆነ እንወቅ ።

ከፍቅር ተለይተን ፀብ ክርክርን ብንወድ ግን ምን እንደሚያገኘን ሕሊናችንን መመርመር ይገባናል ። ለዚሁም ደግሞ እግዚአብሔር አምላካችን ኃይልና ብርታትን እንዲሰጠን በፍጹም ተስፋ እንለምናለን ።

ወልደ ጊዮርጊስ ደለለኝ ።

የታይምስ ጋዜጣ እንዲህ ብሎ ይጽፋል ።

አቴን ። አሁን መንግሥት የፓትሪያርክ ነገር ወደሄግ (የመንግሥታት ዳኝነት ቤት ያለበት ከተማ) ሊቀርብ ይገባዋል ሲሚል ለትናንትና ማመልከቻ የቱርክን ምላሽ ይጠብቃል ።

ምንም እንኳን ያገሩ ማኅተም ወደ ጦርነት ቢያደላ ባገሩም ሁሉ ንዴት ቢሠለጥን መንግሥት ነገሩን በቀስታ ይመረምረዋል ።

የዲፕሎማቲክ ዝምድናው ሳይፈርስ ክርክሩን የሚያሳፍር ሊያገኝ ተስፋ አለ ።

ብፁዕ ፓትሪያርክ ፲፰ ከንስታንቲን ትናንትና ወደሳሎኒክ ገቡ በባቡር ማረፊያም በሚሊቴር ክብር ተቀበሏቸው ።

ሊገናኙዋቸው ለፈቀዱላቸው ለግሪክ ማኅተም ወኪሎች ብፁዕ ፓትሪያርክ ስለርሳቸው ከተላኩ ከግሪክ መልዕክተኞች የሚመጣ ነገርንና የላውዛንን ውል አክብረው የፈረሙ መንግሥታት በመካከል መግባትን [illegible]

ከኢጣልያ መንግሥት ሌጋሲዮን ።

በቴሌግራም የመጣ ቃል ።

የ፲፯ የካቲት የለት ወሬ ።

ሮማ በሕዝብ ማኅበር ምክር የኢጣያን መንግሥት መልክተኛ እንዲሆን ሰናቶረ ቢቶርዮ ሳሎያ ተመርጥዋል ። ሴብቴምበር በጄኔብ በሚሆን ጉባዔም ከሰናቶር በኒኒ ሎንጋሬና ፍራንቸስኮ ከፖላ ጋራ ሆነው የኢጣልያ ወኪል ይሆናሉ ።

አንጎራ ። የመግሥታት ማኅበር የቱርክን መንግሥት የጦር መሣሪያ ለመወሰን በሚሆነው ጉባዔ በዲንበሩ እንዲውል ጠርቶታል እርሱም እዚያ እንዲውል ቈርጧል ።

ከስታንቲኖፕል ። የኮንሲይ ፕረሲዳን በቢላየት ክፍል አምባ ጓሮ ስለሆነ መግንሥት በቢላየት ሁሉ የማርሽ ያልን ሕግ ረጋፐም ላንድ ወር ያህል ሊያደርግ እንዲቈረጠ ለሕዝብ ጉባዔ አስታወቀ ።

ጋዜጦች በኩርድያ የተገለጸውን የሕዝብ መነሣት ያሳጣሉና የመነሣቱን ኃይል ለመወሰን ችግር ነው ይላሉ የግርግሩ መሪ ሼኽ ሳይድ ባሁኑ መንግሥት ሕዝብ እንዲነሣ የሃይማኖት ስብከት እንዳደረገ ሐሳቡም የኩርድን መንግሥት አቁሞ ካሊፍን ለመሾም እንደሆነ አስረግጠው ይናገራሉ ።

የ፲፰ የካቲት የለት ወሬ፡

ሮማ ። ፖፖሎ ኢጣልያ የተባለው ጋዜታ የሙሴ ሙሶሊኒ የጤናው ሁኔታ እየተሻለ ይሔዳል ይላል ። ስለ መንግሥት ነገር በበለጠ ኃይል ሊሠራና በጣም ከሚቀርቡት ሥራ ጓደኞቹ ጋራ አብሮ ለመቆየት ይችላል ።

ስቶክልማ ። የኮንሲይ ፕሬሲዳን ብራኒንግ ሙቶዋል ።

ሎንድር ። ንጉሥ ጆዮርጅ እየተሻላቸው ሒደዋል ወደ መካከለኛ ባሕር ሽርሽር በሚሉት ጊዜ ንግሥቲቱ እንደሚሸኙዋቸው ተቈርጥዋል ። ወደ ባሕር ሽርሽር የሚሉበትም ቀን ንጉሥ በተሻላቸው ጊዜ ይወሰናል ። የቤተ መንግሥት የተለየ መርከብ ሊበጅ ወደ ፖርትስማውት ወደብ ሔዷልና የመሰናዳቱን ጊዜ ይዘገያል ።

የየካቲት ፲፱ ቀን የእለት ወሬ ።

ሮማ ። ሙሶሊኒ በን ሆኑዋል ። እንዲያርፍ ሐኪም መውጣት ከልክሎታል ።

ቤርሊን ። ኤቤርት ሐኪሞች በሽታው ጠንክሮበታል ይላሉ

ቢዬና ። የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሆዱን ታሞ ኦፔራሲዮን ከደረጉለት በኋላ ተሻለው ።

ሎንድራ ። ጋዜጦች ከአንጎራ ዋና ሚኒስትር ኵርዶችን ለመውጋት በየወገኑ ወታደር ሰደደና ሽፍቶቹ ድል ሆኑ ። ግን የኵርድ ወገኖች ስለ በዙ ሽፍታው የንጉሡን ሠራዊት ወደ ፊት ለመግፋት አስቸግሮታል ።

የየካቲት የ፳ና የ፳፩ ቀን የእለት ወሬ ።

ፓሪስ ። የ፲፱፻፲፯ ዓመተ ምሕረት የፈረንሳይ ወታደር፡ሰባት መቶ ሺ. ተራ ወታደር ። ፸፪ ሺ. አምስት መቶ አለቆች ። ሠላሳ ሁለት ሺ. መኳንንቶች ። አምሳ ሺ. የባሕር ወታደር ፬ ሺ. ፪፻ የባሕር ወታደር መኳንንቶች ናቸው

ሎንዶን ። በማኒካ ካናል ከድንገተኛ ክፉ መናወጽ የተነሣ መርከብ የሚቆምበት ቦታና መርከቦች ተጎዱ ።

ሮማ ። ቦይስካውትስ የተባሉ ፻፵ አውስትራልያውያን ላልታወቀ ወታደር እጅ ነስተው አክሊል አስቀመጡ ወደ ፓንቴዎን ሔደውም በንጉሥታቱ መቃብር ላይ አክሊል አስቀመጡ ።

ዮጂኒይሮ ። (እንደ ቤንዚን ያለ) የሚቃጠል ነገር በተቀመጠበት ዕቃ ቤት እሳት ተነሣና በጠገቡ ከነበረው ከተማ ብዙ መቶ ሰዎች ሞቱ ስድስት መቶ የሚያሁሉት ቈሰሉ ሶስት ሺ. ቤት ተቃጥሎ ወና ሆነ ።

በልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ።

መጀመሪያ ዓመት ፡ ቁጥር ፲፩ ።
1re ANNÉE №. 11

ሐሙስ መጋቢት ፫ ቀን ፡ ፲፱፻፲፯ ዓ ም ።
JEUDI 12 MARS 1925

ብርሃንና ሰላም

LUMIÈRE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፮ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

የጋዜጣው ዲሬክተር ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት
ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የራሱን ጉዳይ የሚያሳትም ሰው ዋጋውን እየከፈለ
እናትምለታለን ።

የደብዳቤ ቃል ።

ክቡር ዲሬክተር ።

አንድ እውነተኛ የኢትዮጵያ ወዳጅ በክበረ ጋዜጣዎ የተገበና ግልጥ ጥቅም የሆነ ሁለት ነገርን ለኢትዮጵያ ሹማምት ለማመልከት ይለምናል ።

፩ኛ የብር ምንዛሬ በመሐለቅ ።

ለአንድ ብር የሚገባ ምንዛሬው አሥራ ስድስት ሲሆን በገባያ ከስምንት እስከ አሥር መሐለቅ ሲመነዘር ጊዜ ቀለባቸውን በብር ተቀብለው ለሚያስፈልጋቸው ለዕለት ኑሮዋቸው በመሐለቅ መንዝረው ለሚገዙ ምስኪኖች ሠራተኞች በእውነት ትልቅ ጉዳት ነው ። አንዱን ወደ ብዙ ለመክፈል በሚሆን የገንዘብ ምንዛሬ ከሚገባው አልፎ በመቶው አምሳ በልጠ የተገኘ እንደሆነ ያለቅጥ ከሚገባ ማለፍ እንደሆነ እርግጥ ነው ።

በዚሁ ምንዛሬ ላይ ደግሞ መጻተኛ ሰው ያገሩን ገንዘብ ሰጥቶ ብር አገኛለሁ ብሎ ቢለውጥ ገንዘቡን ወደ ብር መለወጡ ብርቱ ጉዳት ይሆንበታል ።

የተገቡ ሹማምት ይህንን ነገር በጥንቱ መሠረው እንደሚቻላቸው የተሻለ መንገድ ቢያደርጉለት ሁሉ ባመሠገናቸው ። ይልቁንም እየሠሩ በቀን በቀን የሥራቸውን ደመወዝ ብር የሚቀበሉ ሰዎች ።

፪ተኛ በእርሻ ፊተኛ ከሆኑ ከሌሎች ብዙ አገሮች ጋራ ብምትቈጠር እንደ ኢትዮጵያ ባለች አገር አንድ ኪሎ እንጀራ ከአራት ፍራንክ በላይ ቢያወጣ ፍትሕ ነውን ።? ይህ ስለ ምንድር ነው ።?

የት አገር ላንድ ኪሎ እንጀራ ከአራት ፍራንክ የበለጠ ይከፈላል?።

የተወደዱና ትጉሕ ከንቲባ ይህንን ስለምንድር የሚለውን ጥያቄ መርምረው በትጋትና በትልቅ ፍቅር የሚፈጽሙት እርስዎ ነዎት ።

ክቡር ዲሬክተር ለደግነትዎ ደስ የሚያሰኝ ሊሆን እለምናለሁ ።

ስለ ስለሺ ይገዙ ሞት ።

በ፲፱፻፲፯ ዓ ም ባለፈው ወር በታሕሣሥ ስላሺ ይገዙ በፈረንሳይ አገር በምንፖልዬ ተማሪ ቤት የመሞቱን መርዶ ሰምተን እጅግ አዘንን ። ደግመኛም በክሌር ተብሎ በተሰየመው በሥለጠነው በፈረንሣይ አገር ጋዜጣ እንደምናይ ፡ በምንፖልዬ ተማሪ ቤት ያሉት የኢትዮጵያ ልጆችና ታላላቆች መኳንንቶች የልዩ የልዩ ሥራ አለቆችም ሁነው በታላቅ ማዕርግ ሬሳውን ተከትለው ለርሱ የሚገባውን ቃላት ተናግረው እንደ ቀበሩት ሰማን ።

ተሰብስበው ከቀበሩት መኳንንትም የተነገረው ቃልና የተናገሩትም ሰዎች እነዚህ ናቸው ።

(፩) ፡ ፕሮፌሶር በለሪ የምንፖልዬ ተማሪ ቤት አለቃ [illegible] ይጠይቀው የነበረ ። ከሞተም በኋላ ለሚቹና ለወላጆቹ የሚገባ ቃል ተናገረ ።

(፪) ፡ የግብፆች ተማሪዎች ፕሬሲዳንትም በብዙ ኀዘን እንዲህ ሲል ተናገረ ። ኢትዮጵያውያንና ግብፆችን የሚያገናኝ የሀገራችን አንድነት ብቻ አይደለም ። ሐሣባችንም የሚሔድበት መንገድ አንድ ነው ። እርሱም ወደዚህ ለመድረስ መጥቶ ወዳጃችን ስለሺ ይገዙ ስለ ደግ ሐሳቡ ስለ ሞተ የዚህ ኀዘኑ ተካፋዮች መሆናችንን እንገልጣለን ብሎ ተናገረ ።

እነዚያ መኳንንቶች ፡ በዚያ ያሉት ወንድሞቻችንን እያጽናኑ ሬሳችንን ስለ አከበሩልን እኛም የኢትዮጵያ ልጆች ልናመሠግናቸው የሚገባን ስለ ሆነ ለየማዕርጋቸው የሚገባ ምስጋና እናቀርባለን ።

መጀመሪያ ስለሺና ወንድሙ ማህሌ በ፲፱፻፲፬ ዓ ም ወደ ፈረንሳይ አገር ሔደው ሁለት ዓመት ያህል ከተማሩ በኋላ ማህሌ

በድንገት በሽታ ታሞ በሞት አረፈ ። ስለሺም ወንድሙ ማህሌ ከረፈ በኋላ ከድንጋጤና ከብስጭት የተነሣ ሁለት ወር ያህል በሕሊናው እረፍት አላገኘም ነበር ። ወዲያውም የሳንባ በሽታ ስለተከተለው ለጤንነቱ የተወለደበትን አገር የሚያስፈልግ ስለሆነ በ፲፱፻፲፭ ዓ ም ወደ አገሩ ተመለሰ ።

ነገር ግን ሐሣቡን ለመፈጸም ብርቱ ፈቃድ ስለ ነበረው በ፲፱፻፲፮ ዓ ም መጋቢት ፳፩ ቀን ተመልሶ ወደ ፈረንሳይ አገር ተሻገረ ። በሔደም ጊዜ በጭራሽ የመሰናበቻችን ቀን መሆኑን ሳናውቀው ወላጆቹና ዘመዶቹ እኛም ባልንጀሮቹና ወዳጆቹ ሐሣብህን ይፈጽምልህ ወደአገርህም በደህና ለመመለስ ያብቃህ እያልን ተሰነባበትነው ።

እንግዴህም የብርሃንና ሰላም ወዳጆች ሆይ የነዚህ የሁለቱ ወንድሞቻችን ሞት የትምርትን ፍቅር ያሳስበናል ።

እነሱ ከዚህ ሁሉ የደረሱት ባባታቸው ቤት ለኑሮዋቸው የሚበቃቸው አጥተው አይደለም ነገር ግን በብዙ አይነት ትምርት እንደምናይ ያገር ፍቅር የፍጥረት ባሕርይ ናትና አብሮ አደግ ለሆነች ለዚች ባሕርይ ዋና ሰራተኞቹ ለመሆን የሚያስፈልጋት መሳሪያና ጋሻ ትምርት ስለሆነ ሐሣባቸውን ለመፈጸም እስከ እለተ ሞታቸው ድረስ ታገሉ ።

እንግዴህ እነዚህ ልጆች ዋና ሰራተኞች ተብለን ልንጠራበት በሚገባ ሐሣብ ከሞቱ ሐሣቡ አይሞትምና በዓለም ሁሉ ድል እንዳደረገ ባገራችንም ድል የሚያደርግ ከሆነ እንደ ሰማዕታት ልንቈጥራቸው ይገባናል ፡ እግዚአብሔር በምሕረቱ በአለም ሳሉ እውነተኛ ሐሣብ ተከትለው እንደነበር እንዲሁ ደግሞ በእውነተኛ ሰማያዊ መንግሥቱ ተካፋዮች እንዲያደርጋቸው እየተመኘን ለእቶ ይገዙ የኢዮብን ኀዘን ያድርግላቸው እያልን ኀዘናችንን እንገልጣለን ።

እነዚህና ሌሎቹም ወንድሞቻችን ሁሉ በሀገራቸው ሁነው በጣም ተምረው ለአንድ ዓመት ወይም ለሁለት ዓመት ያህል ትምርታቸውን ለመፈጸም ወደ አውሮፓ ቢሔዱ ክብድ አልነበረም ። ነገር ግን ያልተወለዱበት አየር ስለሆነ በቀን ብዛት ከሚመቀኙቸው ይልቅ የመመላለሻቸውና ለቀለባቸው በየወሩ የሚወጣው ወጭ ገንዘብ በሀገራችን ለሚቆመው ተማሪ ቤት ወጭውን ችሎ ጥቅም የሚገኝበት በሆነ ነበር ።

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ [illegible] ምሮ ዳግማዊ ምኒልክ ከቆሙት ተማሪ ቤት ጋራ በመተጋገዝ ሥራውን እንዲፈጸምና ፍሬውን እንድናይ እንመኛለን ።

አራዶም ዕቅቡ ።

ከታይምስ ጋዜጣ የተገኘ ወሬ ።

ባለፈው ጋዜጣችን ስለ ሰር ሊ ስታክ መግደል ሁለት ተማሪዎች ተይዘዋል ብለን ጽፈን ነበር ፤ አሁን በመጣልን ታይምስ እንዲህ እናነባለን ፡ ዛሬ ታሄር ቤ ኑር የተባሉ ሹም ከተያዙት ተማሪዎች አንዱን የሕግ የትምርት ተማሪ አብደል ፋታህ ሊንያትን መረመሩት ሰር ሊ ስታክን ከገደሉት ሰዎች ጋራ እርሱም በመግደል ተባብሮ እንደነበረ አመነ ሌሎች ሰዎች እንደነበሩና ወንድሙ አብደል ሐሚድም ከርሳቸው ጋራ እንደነበረ በቃሉ ውስጥ ተሠውሮ ተገኘ ።

የዮርክ ዱክ ግዳይ ።

የእንግሊዝ ንጉሥ ልጅ ዮርክ ዱክ ከሚስታቸው ከዱኬስ ጋራ ወደ ኬንያ (አፍሪቃ) አደን ለማደን ሔደው ነበርና የዮርክ ዱክ ግዳይ የሚከተለው ነው ። አንድ አንበሳና አንዲት አንበሳ አጋዘን ፈቆ ፤ ድኩላ ፤ ሰሳ ፤ የበረኻ አህያ ፤ አሪያ ፤ ጅብ ። ሁለት አውራሪስ ሁለት ጎሽ (እያንዳንዳቸው የገደሉዋቸው ።)

ዋዞ ኒሮ ከሚባል ወንዝ ጀምሮ እስከ ቻንድለረስ ፏፏቴ ድረስ ጉማሬ ፈለጉ ግን አላገኙም ከአርቸርስ ፓስት አጠገብ አንድ የተወጋ ጉማሬ ከማንደር ብሩክን ነጥቆ ሊወስዳቸው ነበር ለጥቂት አመለጡ ።

ወደ ሲዮሎ ሲመለሱ የዮርክ ዱኬስ(ማለት የዱኩሚስት) ተኵሰው አንድ አውራሪስ ገደሉ ዱኬስ ከማይድንበት አካሉ ላይ ተኵሰው ስለመቱት ባንድ ተኵስ ብቻ ሞተ ወይዘሮ አናሊም አንድ አውራሪስ ገደሉ ዘሆን ለማግኘት ግን አልተቻለም ።

ኩሎኝን ስለ መልቀቅ የእንግሊዝ ሐሣብ ።

በአውሮፓ ያለውን ወቅሣ ተመልክተን የእንግሊዝ መንግሥት የኩሎኝን መልቀቅ ይቈይ ያለባት ምክንያት በተገባ ሥርዓት ምክንያት ብቻ ተመርቶ እንደሆነ እንደገና ማስታወቅ እንደሚያስፈልግ ይመስላል ።

የጀርመን መንግሥት ።

የጦር ዕቃ ስለ መተው በውሉ ያለውን ክፍል ፤ (ክሎዝ) የሚገባውን ነገር እንዳልፈጸመ የሚገልጥ ምክንያት አለ ።

የኩሎኝ መልቀቅ ይቈይ የተባለ የጦር ዕቃ ስለ መተው የተደረገው ክፍል እስኪፈጸም ድረስ በዚሁ ምክንያት ብቻ ነው ።

በእንግሊዝ መንግሥት ሐሣብ ፤ ምክንያቱ ይህ ብቻ ነው እንጂ ስለ ኩሎኝ መልቀቅ ሐተታ ወደሌላ የሚያደርስ ነገር የለውም ።

ስለ ግሪክ ፓትሪያሪክ ታይምስ የሚለው ። የእንግሊዝ አገር የካንተርበሪ ሊቀ ጳጳስ ስለ ግሪክ ፖትሪያሪክ ሁነታ በሎርድስ ሸንጎ አመለከቱ ።

ሎርድ ኩርዞን ነገሩን መረመሩና ሁለቱ ባላጋራዎች ተነጋግረው በስምም ሊጨርሱት እንደሚገባ አስታወቁ ጦርነት የሚባለው ቃል የሚጠቀስበት ወይም በስውር የሚመለከትበት አኳኋን እንዲመጣ ቢተውት በሕዝብ መካከል ትልቅ ነውር በሆን ።

ቱርኮች የዚህ የነገሩ መጨረስ በመን ግሥታቸው ውስጥ ብቻ ሊደረግ እንደሚገባው አድርገው የሚያዩትን ነገር ለማሳረፍ የእንግሊዝ መንግሥት ሊያደርገው የሚችለውን የሚጠቅም ነገር በርግጥ ባደረገው አሉ ።

ፊጋሮ ከተባለ ከስመ ጥሩው ከፈረንሳዊ ጋዜጣ እንዲህ የሚል አነበብን ።

አብደል ከሪም የተራሮች ነገድ እንደገቡለት የሚገልጥ እጅ ለመንሣት የመጡትን መላክተኞች ተቀበላቸው ። የሪፍ (የማሮክ ተራሮች) ሰዎች ይሰበሰባሉ በቶሎ ጦርነት እንደሚደረግ ይታሰባል ።



PHOTO BY VANDYCK.

የዮርክ ዱክ።
የእንግሊዝ ንጉሥ ልጅ።



PHOTO BY VANDYCK

ዱኪስ።

የዮርክ ዱክ ሚስት።

ጀኔራል ፐሪሞ ዴ ሪቬራ የስፓኛ መንግሥት ዋና ሚኒስትር በየካቲት ፳ቀን ወደ ማሮክ እንደ ገና ይመጣሉ ።

ያለፈው የታይምስ ጋዜጣ ራይሱሊ የተባለ የማሮክ ደጃዝማች ከስፓኛ ጋራ ተባብሮ በአብዶል ከሪም ጭፍራ እንደ ተያዘ የራይሱሊ መውደቅም ለስፓኛ መንግሥት ትልቅ ጉዳት እንደሆነ አመልክቶ ነበር ።

የራይሱሊ ሁለት አሽከሮች አብዶል ከሪምን በምክር በጦር ዕቃ በገንዘብ የሚረዳው የእንግሊዝ መንግሥት እንደሆነ በንዴት ይናገራሉ ፤ የመርዳታቸውም ምክንያት የእንግሊዝ ኀብታሞች ሐሣባቸው በዚያ ያለውን ኀብታም የብረት ቦታ ሊይዙ እንደሆነ ይላሉ ፤ ነገር ግን ታይምስ ይህንን ታሪክ ውሸት ነው ብሎ ይክደዋል እንዲህም ብሎ ይቀጥላል ስለ ነፃነታቸው ለሚታገሉት ያዘኑ ሰዎች ከኢንግላንድ ወደ ማሮክ ኃዘናቸውን የሚገልጽ ወረቀት እንደጻፉ እውነት ነው ፤ የመንግሥት ሹመት የሌላቸው ሰዎች የእንግሊዝ የፖሊቲክ እርዳታ የሪፍ ሰዎች ለተባሉቱ (ማሮኮች) ተስፋ ሰጥተው አንድ ጊዜ ነፃነታቸውን ያገኙ እንደሆነ የእንግሊዝ መንግሥት እንደሚያልፍለት አስረገጡላቸው ይላል ።

አሁን የመጣልን የታይምስ ጋዜጣ፡ የውጭ ጉዳይ ስክሬቴር፡ ሪፊዎችን ከስፓኛ ጋራ ሲዋጉ የግርማቸው መንግሥት እንደረዳቸው የተወራውን ወሬ ፈጽሞ ይክደዋል ። የስፓኛ መንግሥት በማሮክ ስላገኘው ችግር ያዝንለታል ። በእንግሊዝ ዜጎችና በአብዶል ከሪም መካከል ያለ ዝምድናንና መጻጻፍንም ለማጽደቅ ዘወትር እምቢ ብሎዋል ። ቀጥሎም እምቢ ይላል አለ ።

የፈላስፎች ቃል ።

እችላለሁ ብሎ ማሰብ ለማድረግ እንደሚቻል ይቆጠራል
ቡክስቶን ።

እጅግ ካላስፈለገ በቀር ልጆችን የሚያሰቅቅ የጭካኔና የኃይል ነገር አታሳዩዋቸው ። ልባቸውን ዘማታችሁ እምነታቸውንም ታጠፋታላችሁ ፤ አለዚህ አብሯቸው ከሚያድገው ትምህርት የሚገኘውን ፍሬ አለኝታ ማድረግ አይሆንምና ።
ሬኑሎን

አለመጠንቀቅ ። ስንፍና ፤ የልስላሴ ኑሮን መውደድ ይልቁንም የምታንቀጠቅጠውን ፍርሃትን መፍራት የብዙ ሰዎችን ደካማ ሕሊና የሚያሳውርና የሚያበላሽ ይህ ሁሉ ነው ። ላመኔ ።

ፍርሃትን ይዛ የምትሄድ ነፍስ ዘወትር እየደከመች ትሄዳለች
ሮሊን ።

መፍራት የሚገባን አንድ ነገር ብቻ ነው ። ይኸውም ፍርሃትን ነው ።
ሞንቴኝ ።

ሰው አጽናፍ ስለ ጠማው ምስጢርም ጠምቶታል ። ታላላቅ ነፍሳትን ፍጻሜ ወደሌለው መንገድ የሚገፋ ይህ የአጽናፍ ጥማት ነው ። ሁሉን ማወቅ አይቻልም የሚባለውን ትልቁን ንጉሥ ተሸክመው ሁሉን ነገር ገልጾ ወደማወቅ ይጓዛሉ መመራመር ፍጻሜ ስለሌለው በተገለጸው ነገር ላይ ሁሉ ይንሳፈፋል ። ጥምን እያበረደ ወዲያውም ያብሳል ። አ ሄሎ ።

ትክዜ አሳቦችንን የሚነድፍና የሚስል ቀለምም የሚያገባ ኃይል ነው በሐሳብና በምኞት በፍጻሜም መካከል ዋና ማዕከላዊ ነውና እንግዲህ ሥራው የታወቀ ጥቅም ያለው ነው ።
ረናን ።

ሁሉን ነገር አለችግር ይፈጽማል ብለው ከሰቡበት እንደዚሁ ይሆናል ።
ሸኒንግ ።

አለችግር መፈጸሙን አሳንሶ ካሰቡት ብዙ የሚበልጥ ነገር ይደረጋል ።
ማሴሸርብ ።

የአምልኮት እውነተኛው ፍቅር ለሰው ነጻና የተከበረ መሆኑን የማወቂያ ሕሊና በመስጠቱ ይታወቃል ። እንግዴህ ስግደት ማለት አጐንብሶ መውደቅ አይደለም መቅናትና መነሳት እንጂ ።
ጉዮ ።

ብዙ ነገር ለመፈጸም የሚያስቸግረው ። እንደሚያስቸግር መቍጠር ስለ ተለመደ ነው ።
ዱክሎስ ።

እንደመቻል ማሰብ መቻል ነው ።
ቢርገርሊ ።

ራሳችሁን አቀርቅራችሁ አትሂዱ መንገዱን ለማየት ዓይኖችን ማንሳት ያስፈልጋል ።
ላመኔ ።

ኃያላን ሰዎች ፈቅደው ይነቃሉ ።
አኖሬ ደባልዛክ ።

ለመግለጽ አለመቻል ከዕውቀት በላይ ነው ዕውቀተኛ አለመሆን ግን የበታች ነው ።
አ ሄሎ ።

ከቂምና ከንዴት የሚቀዳው ኃይል ከቶ ድካም ብቻ ነው
ማዳም ሰዊቹን ።

የብርታታችን መንፈስ ኃይላችንን ይጨምርልናል ።
ቦቦናርግ ።

አለመድከም ። አለመቀዝቀዝ ። ትእግሥተኛና ተወዳጅ ደግሞ መሆን ። የሚወለደውን አበባና የሚከፈተውን ልብ መመርመር ። ዘወትር አለኝታ ማድረግና ዘወትር መውደድ ይህ ነው ግብራችን ።
አሚዬል ።

ጭንቅ የተፈጠረው ለማበርታት ነው እንጂ ለማስነፍ አይደለም የሰውነታችን መንፈስ በክርክር ጊዜ መበርታት ያገባዋል ።
ሻኒንግ ።

ነፍስ ያለው ፍጥረት ሁሉ የኃይል ማደሪያ ሥፍራ ነው
ጹሑብም ራሱ ኃይል ያለው ሥራ ነው ።

ከማይ ፍላማሪዮን ።

ከሰውነቱ ውጭ የሚያልፍ በራሱ ሰውነትና ባለው ገንዘብ ደስ የሚለው ነው ። ከሰውነት ውጭ ያለፈ የጸና ደስታ አይገኝም ደስታችን ከነፍሳችን ውስጥ መውጣቱ በተሰማን ጊዜ መከራ የማይደርስብን አይምሰለን ።
~~ማዳም ደ ላምቤርት ።~~

እንደ ምኞቴ ይሁን የሚል ፈቃድ እጅግ ኃያል የሆነ ነው
አዝኒ ደጌገሪን ።

አንዱን ነገር በሚፈጸም መንገድ ለማድረግ የአካልና የመንፈስ ብርታት እጅግ የሚያስፈልግ ነው ።
ጐት ።

ከሰው ነፍስ የበለጠ ረቂቅ የለም ። ሁሉ ተደርጎ መመነት ብቻ አለ ።
ኤፒክቴት ።

ከምኞት ይልቅ የሚበልጥ ኃይል አለኝ ። ይህ ነገር

የማይሆን ነው ብለን በኋላ ትክዜ የሚገባን ተመልሰን ራሳችንን ማረን ለማለት መሆኑ ይታያል ። ላሮሽፉኮልድ ።

አጥብቆ ከመመኘት በቀር በዚህ ዓለም ላይ ምን ትልቅ ነገር አለ ። ? ሚሽሌ ፡

አሳብ ረቂቅ ነው ። የሚደረስበት በብዙ ድካም ነው ። ምንም መልካም ቢሆን ለሰው ልብ አይበቃም ። ባሬስ ።

እኛን የሚያሰንፈን የምኞታችን ለስታኑት ብቻ ነው ፡ አጥብቀን የተመኘነውን ግን ሁልጊዜ በርትተን እናደርጋለን ። ሩስ ።

ንቦች አለጭለማ አይሰሩም ፡ አሳብም አለዝምታ አይሰራም ደግነትም አለምሥጢር ። ማቴርልንክ ።

ድልን የሚሰጥ የድል ምኞት ነው፡ዓለምን በሚያናውጥ በታላላቅ ክርክር ጊዜ እውነተኛ የሆነ በልዩ ልዩ ዘመን በሚነሳው ስውርና ጭለማ በሆነ ክርክር ጊዜም እውነተኛ ነው ። ሀንረ ፔሬዮብ ።

የመብት ሁሉ ምሥጢር ምኞት ነው ። ሮበርስቶን ።

ብርቱ ምኞት ጥቂቱን ብዙ ያደርጋል።ሲደክማ መዣሪያ ኃይል ይሰጣል ። ችግርን ያስቀራል ፤ ብዙ ጊዜም እንኳ ረዳት ይሆናል ። ሻኒንግ ።

በምኞት ብቻ ከምንም እንደርስም ለምኞትም እርሾ ያስፈልገዋል ከነፍሳችን ኃይል ሁሉ ሥራ ያልተሠራበት እንደሆነ በቶሎ የሚዝግ ምኞት ነው ። ላቡላዬ ።

ኑሮን የሚያበራ አሳብ እግዚአብሔር ለሰው ለመስጠት የሚችለው መልካም ጸጋ ነው ። ኤድጋር ክኒት ።

ቁርጥ ምኞት ጊዜ ያገኛል ወይም ያደርጋል ። ሻኒንግ።

ባንድ አሳብ ውስጥ የሞኝነት ትጋት መያዝ የትንንሽ መንፈስ ስሕተት ነው ። ታላቅ ነፍስ በዚህ ጊዜ እርፊት አያጣም የግምብ ላይ ጥላውን እያየ ማሰብ ይችላል።ዛሬ የምታስበውን በጥንካሬ ተናገር ከነድ ቀን አንድ ልታፈርሰው ሳትችል አትቀርምና ነገም ይህንኑ አድርግ ። ኤማርሰን ።

ለሚተጋ ልብ የሚያውከው ነገር የለም ። ገተከር ።

ከኢጣልያን መንግሥት ሌጋሲዮን በቴሌግራም የመጣ ቃል ።

የየካቲት የ፳ና የ፳፩ ቀን የእለት ወሬ ።

ሮማ ። ለሙሴ ሙሶሊኒ የኢጣልያን ወገን ሁሉና የውጭ አገሮች የመዳን ምኞታቸውን ገለጹላቸው ። ንጉሥና እቴጌዪቱ የንጉሡም እናት በጀነራል ፒታዲኒና በኮምኘት ኮሲላ በኩል ስለ ጤናቸው መመለስ ለፕሬዚዳንቱ የሰላምታ ቃላቸውን ላኩላቸው ።

ኮስታንቲኖፕል ። ድጋርስን ሑሪዩን በኩርዲስታን የመነሣት ግር ግር ይዘረጋ እንዳለና የበታው ጭፍራ ከፍሎች ከተነሡቱ ጋራ እንዳበሩ ያስታውቃል ። የመንግሥትም ጭፍሮች የተነሡትን ለማገድ ገና አልጀመሩም ።

ሎንድር ። የንጉሥ በሽታ በጣም እየተሻለ ሔዷል ። ወደ መካከለኛው ባሕር ለመሔድ የሚነሡበት ቀን ገና አልተቈረጠም ። ግን የንጉሥ መርከብ ከፖርትስማውት መጋቢት ፳፯ ቀን ። እንዲነሣ ሊሰናዳ ታኅዟል ።

የየካቲት የ፳፪ና የ፳፫ ቀን የእለት ወሬ ።

ሮማ ። ሙሶሊኒ ዛሬ ጥዋት የውስጥ ምኒስትርን ፤ የሥራ ምኒስትርን የኮሙኒ ካስዮን ምኒስትርን የፕረዚዳን ሱሴክረቴርን በቤታቸው ተቀበሉ ፌደርዞኒ ያገር ውስጥ አኋሆን በመላው መንግሥት ሰላም እንደሆነ አስታወቀ ፡ ዲዩርያቲ ወደ ኢጣልያ ደቡብ ስለ መጐብኘትና በዚያ አገር ክፍል የሆነውን የሕዝብ ሥራ አሠለጣጠን ነገረ ፡ ሙሶሊኒ መንገድ የማበጀት ሥራ ቤቶች የመሥራት ሥራ መሬትንም ለእርሻ የሚመች የማድረግ ሥራ ሁሉ በትልቅ የትጋት ፈቃድ ተይዞ እንዳለ በደስታ ሰሙት ።

ቺያኖ በሕዝብ የባሕር አገልግሎት (ሰርቢስ ማርቲም ፑብሊክ) አኋሆን በሁሉ ነገር ማለፊያ ሁኖ እንዳለ ሥርዓትነቱና ንግዱም እንደሰፋ ለፕረዚዳንቱ ነገረ። ከዚያ ወዲያ ሙሶሊኒ ከሚቀርቡዋቸው የሥራ ጓደኞቻቸው ጋራ ስለሚያስቸኩል ፖሊቲክ ነገር ያስቡ ጀመሩ ።

በርሊን ። የኤበርት ሞት ሕዝብን በጣም አሳዝኑዋል በተያዮሮን በሕዝብ መገናኛ ሥፍራም የሐዘን ባንዲራ ሰቀሉ ቀብር ለሮብ እንደሚሆን ይመስላል ።

ፓሪ ። የአምባሳደሮች ጉባኤ የኮንትሮል መላክተኞች ራፖርና የኢንተርአለያንስ የሚሉቱር ሸማግሌ ስለዚያው ነገር የላኩት ያመልክቻ ማክሰኞ እለት ይመረምራል ።

ስቶኮልም ። የብረቲንግ የቀብር ሥርዓት ልብ በሚነካ አገባብ ተደረገ በቤተ ክርስቲያን ካህናትና የዲፕሎማቲክ መላክተኞች ነበሩ ፤ ቃሬዛውን እስከ መቃብር የሸኙ ሰዎች ወደ አምሳ ሺ ይሆናሉ ከዚያም ብዙ ንግግር ተደረገ ።

ኒዮዮርክ ። የቡዌኖስ አይሬስ ቴሌግራም የአርጀንቲን ግማሽ መኳንንት ወረሩ ይነግራል ወረራውም በመናገሻው ከተማ መንግሥትን የሚቃወም ግርግርታ አስነሣ በጠቡም አንድ ወታደር ሞተ አያሌ ሰዎችም ቈሰሉ ።

የየካቲት የ፳፬ ቀን የእለት ወሬ ።

ሮማ፡ ኮሌጅ ሮማኖ ከንጉሥ፤ከባሕር ምኒስትር ከኮሎኒ ምኒስትር ፤ ከሴናተሮችና ከዴፑቴ ከሹማምትና ከሌሎች ፊት የካሞዌውስና የባስኮጋማ መታሰቢያ ተደረገ ኦኖራብል ኦርላንዶና የጄኖባ ኡኒቬርሲቴ ፕሮፌሰር ቢታሊት ስለ ባስኮ ጋማ ሥራ ስለ ካሞዊውስ የግጥም ሥራም ተናገሩና ተጨበጨበላቸው ።

ዋሺንግቶን ፤ የኢጣልያን አዲሱ አምባሳደር ዴ ማርቲኖ የምሥክር ወረቀቱን ለፕረዚዳን ኩሊድጅ አቀረበ።

አንጎራ ፤ ከቢኒ ስንብቱን አቀረበ ።

ቶኪዮ ፤ ታችኛው ሸምብር የያፓንን ሱፍራጅ ኡኒቬርሴል ማለት(ዜጋ ሁሉ ያገሩን ገዢ እንዲመርጥ ሥልጣን የሚሰጠው አኋሆን) ተቀብሎታል ። አሁን ሸምብር እንዲቀበለው ይጠብቃሉ ።

በልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ።

መጀመርያ ዓመት ፣ ቍጥር ፲፪ ።
1re ANNÉE № 12

ሐሙስ መጋቢት ፲ ቀን ፣ ፲፱፻፲፯ ዓ ም ።
JEUDI 19 MARS 1925

ብርሃንና ሰላም
LUMIÈRE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፫ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

የጋዜጣው ደሬክተር ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ደሬክተሩ ያስታውቁ ።

የራሱን ጉዳይ የሚያሳትም ሰው ዋጋውን እየከፈለ እናትምለታለን ።

ስለ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ በዓል ።

ባለፈው ሳምንት መጋቢት ፬ ቀን ልዕልት ወይዘሮ መነን የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስን በዓል ለማክበር ወደ ዝቋላ ወርደው ነበር ። ይኸውም በዓል መጋቢት ፭ ቀን በየመቱ የሚደረግ የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ የዕረፍታቸው መታሰቢያ ቀን ነው ። አቡ ማለት ግን አባ በማለት ፈንታ የገባ ያልታረመ ቃል ወይም ጋሎች ስለ ከበሬታ አቦ ብለው ያወጡት ስም ነው እንጂ የሚገባ ስማቸውስ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ገብረ ሕይወት ወይም ገብረ አብ ነው ። ዛሬም በዚያን ቀን የመታሰቢያቸው በዓል በዝቋላ ተራራ ላይ እጅግ አምሮ እንደነበረ ሰማን ። ይኸውም ጻድቁ ብዙ ትሩፋት የሠሩበት ብዙ ገድል የተጋደሉበት ቦታ ስለሆነ ከሩቅ አገር ድረስ ብዙ ሰው እየተሰበሰበ የመታሰቢያቸውን በዓል በዝቋላ ተራራ ላይ ያከብራል ።

ልዕልት ወይዘሮ መነንም በዓሉን አክብረው መጋቢት ፰ ቀን ወደ አዲስ አበባ በደስታ ተመለሱ ።

የዚሁ ቀን በዓል አከባበር በአዲስ አበባ መጋቢት ፭ ቀን የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስን የዕረፍታቸውን በዓል መታሰቢያ ቀን ለማክበር ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ። አዲስ አበባ ላይ በጻድቁ ስም ወደታነጸው ቤተ ክርስቲያን ሔደው ነበር ።

ስለ በዓሉም ከበሬታ አላማ ሰንደቅ ተተክሎ ነጋሪት ሲመታ ዋለ ። ይኸውም በዓል ቀዳሚት ቀን ነበርና ከቅዳሴ ውጭ ታቦት ወጥቶ ዑደት ሆነ ። ከዑደት በኋላ ብፁዕ ዕጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ከልብ የሚጠልቅ ምክር መክረው አቡነ ዘበሰማያት ሰጡ ። በውነትም በዚያን ጊዜ የሰበኩት ስብከት ሕዝባችንን በጣም የሚጠቅም ስለሆነ ከዚህ ቀጥለን እንጽፋለን ።

ከሁሉ አስቀድሞ ፈጣሪያችንን እግዚአብሔርን እንውደደው እንፍራው ። እግዚአብሔርንም ከወደድነው ዘንድ እርስ በርሳችን እንድንፋቀር መንፈሱን ይሰጠናል ። የቀደሙት አባቶቻችን ነቢያት ፣ ሐዋርያት ፡ ጻድቃን ፡ ሰማዕታትም ፡ ይኸንን ክብር ያገኙት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በሥራ ቢከተሉት ነው ። እኛም አባቶቻችን እንዳደረጉት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በሥራ ብንከተል ነው እንጂ ባፍ ብቻ ክርስቲያን ተብለን የምናገኘው ጥቅም የለም ።

ለዚሁም ሁሉ የትሩፋት መሪዎች እናንተ ካህናትና ለሕዝብ ሁሉ የበጎ አርአያ ልትሆኑ ይገባል ። ትሩፋት ማለትም ወንድም በተቸገረ ጊዜ የተቻለውን ያህል መርዳት ወደ ቤተ ክርስቲያንም በመጡ ጊዜ እንደ ተቻለ ያህል ትኒሽ መባ ይዞ መምጣት ነው ። ወደ ቤተ ክርስቲያንም መጥቶ በተሰጠው አእምሮ እግዚአብሔርን ማመስገን ነው እንጂ ቧልት ጨዋታ መናገር አይገባም ። እንዲህ እያደረጉ ቤተክርስቲያን ስመን መጥተናልና በዚህ ብቻ እንጠቀማለን ማለት ግን ከንቱ ሐሣብ ነው ። አሁንም ሁላችን በፍቅር ተባብረን እግዚአብሔርን በመውደድ ጸንተን እንኑር ። ጊዜያችንንም በከንቱ አናሳልፈው ።

ሞት የሚመጣበትን ሰዓት አናውቀውምና ተዘጋጅተን እንኑር እንጂ ወደፊት ጊዜ አለን በዚህ ጊዜ እናደርገዋለን ማለት ከንቱ ልማድና ከንቱ ሐሣብ ነው ። ጊዜ የለም ። ሰው በተወለደ ጊዜ ሞት ባጠገቡ ነው ። በተሾመም ጊዜ መሻሩ በጎኑ ነው የሚኖረው ። እኛም ለእግዚአብሔር ከዚህ ዓለም የምንወስድለት አንዳች ነገር የለም ። ነገር ግን በዚህ ዓለም ሕጉን ጠብቀን በፍቅር ተባብረን ጊዜያችንን በበጎ ሥራ ብንፈጽመው ኋላም በወዲያኛው ዓለም መልካሙን በታ አዘጋጅቶ ይቆየናል ። ይኸን ሁሉ የምትመለከቱበት አስተዋይ አእምሮ ይስጣችሁ ብለው ምክራቸውን ፈጸሙ ።

ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንንም በክቡራን መኳንንቶቻቸውን ታጅበው ወደ ግቢ ተመለሱ ።

እንደዚህ ያለውን ስብከት የሚያዘወትሩት ቢሆን ቤተ ክርስቲያን እስማለሁ ብሎ ለጸሎት የሚመጣ ሰው ሁሉ ሲጋፋ

ባዶውን ከሚመለስ ለነፍሱ ጥቅም የሚሆነውን ምክር አግኝቶ ወደ መንፈሳዊ ጎዳና ተመርቶ በተመለሰ ነበር።ከቀን ብዛትም የሕዝብ ሁሉ ልቡና ክፉ ነገር ከማሰብ በጎ ነገርን ወደማሰብ ባደላ ነበር። አሁንም ብፁዕ ዕጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ለመምሕራኑ አብነት ሆነዋልና እንግዴህ መነኮሳቱና ቀሳውስቱ ሊቃውንቱና ካህናቱ እርሳቸውን አብነት አድርገው ሁል ጊዜ ለሕዝቡ በጉባዔ እንዲሰብኩ ተስፋ እናደርጋለን።

ከዚህ ቀጥለን ለዚሁ በአል የደብሩ ሹም አለቃ ኃይለ ሥላሴ የተቀኙትን ቅኔ እንጽፋለን።ይኸንንም መጻፋችን በፊት እንደተናገርነው ብፁዕ ዕጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ልብ የሚያረካ ስብከታቸውን ለሕዝቡ ቢገልጹለት የሰው ሁሉ ውሣጣዊ ልቡናው በትምርት እንደ ለመለመ ጽፈናል።

ይኸም የሚከተለው ቅኔ ሕዝቡ በማያውቀው በግዕዝ ስለሆነ ነው እንጂ መላው ሕዝብ በሚሰማውስ ባማርኛ ቢነገር ልክ እንደ ስብከት ነው፤ማናቸውም የተማረ ሊቅ ሰው ሁሉ በብሉይ በሐዲስ የተመሠረተ መንፈሳዊ ተግሣፅ የሚሰጥ ቅኔ ቢቀኝ ትርጓሜውን ጨምረን ልንጽፈው እንወዳለን።

(ዕጣን ሙገር በግዕዝ ቋንቋ)

በአልባሰ በግዕ ቅድው እመ ገብረ ሕይወት መጽአ።
በስመ አቡሁ ብንያም ኢተጸውዐ።
ከመ ተጸውዐ ብንያም፡ እንተ ይመሥጥ በግዐ።
እምጣነ በውስጥ ወበአፍአ።
ገብረ መንፈስ ቅዱስ በግዕ፡ እንቅጸ አባግዕ ዘበአ።
ከመ ያእትት ጽእለተ አቡሁ ወያሰስል ፀብአ።

አሠረ ንጉሥ ።

አንቀጸ ብፁዓን ማቴዎስ ወምኒልክ፡ አስካለ ማርያም ዘሰምአ ።
ኃይለ ሥላሴ ብፁዕ ብእሲ ፡ ዘምስለ ብፁዓን ተበፅዐ ።
እስመ ምስለ ሱቱኤል ተጋብዐ ።
ብሔረ ብፁዓን ይበእ፡ ነሚአ ጽዋዐ ።
ለአእምሮ ፡ ዘሱቱኤል ነሥአ ።

የዚህ ንባብና ትርጓሜ ባማርኛ።

(የዕጣን ማሳረጊያ)። «ባማረ በበግ ልብሶት ገብረ መንፈስ ቅዱስ ቢመጣ ባባቱ በብንያም ስም አልተጠራም ፡» ማለት ገብረ መንፈስ ቅዱስ ጠጉር ቢለብስ እንደ ብንያም ነጣቂ አይደለም « ብንያም በግን የሚነጥቅ ተኩላ ተብሎ እንደተጠራ »ማለት ብንያም ነጣቂ ተኩላ ማለዳ የበዘበዘውን ይበላል ተብሎ ነበርና ዘፍ ፵፱ ፳፯። «ገብረ መንፈስ ቅዱስ በውስጥም በውጭም ወደ በጎች በር የገባ በግ ነውና »ማለት በሥጋውም በነፍሱም ሐዋርያትን የመሰለ ማለት ነው በዮሐንስ ፲ ፩ የተጻፈውን ቃል ያሳስባል በሥጋው አሕዛብን ሲያስተምር መከራ እየተቀበለ ነውና ሲያስተምራቸው በልቡ እየጸለየ እያዘነ ነውና።

«ያባቱን ስድብ ፈጽሞ ያርቅ ዘንድ »ማለት መምሕራን እየተባሉ የሰውን ገንዘብ እየበሉ ወደማይገባ መንገድ ሰውን እየመሩ እንደሚያታልሉ አይደለም ማለት ነው። ፪ጴጥ ፪ ፲፯ —፳፪ ።

(የንጉሥ መታሰቢያ)።«የተመሠገኑ የማቴዎስና የምኒልክ በር እስካለ ማርያምን የሰማ የተመሠገነ ሰው ኃይለ ሥላሴ ከተመሠገኑ ሰዎች ጋራ ተመሠገነ »ማለት፤በምኒልክና በማቴዎስ ፈቃድና ትእዛዝ እስካለ ማርያምን የሚጠብቅ ፈቃዳቸውን የሚፈጽም ደግ ሰው ኃይለ ሥላሴ ከደጋግ ሰዎች(ከዳዊት ከሰሎሞን) ያባቶቻቸውን ፈቃድ ከፈጸሙ ጋራ ተቆጠረ ማለት ነው።በር መግቢያ መውጫ ጠባቂም እንደሆነ መንግሥትም የሕዝብ ጠባቂ መውጫ መግቢያ ነውና «ሱቱኤል የያዘውን ለማወቅ ጽዋን ይዞ ከደጋግ ሰዎች አገር ይገባ ዘንድ ከሱቱኤል ጋራ አንድ ሆኑዋልና» ማለት ሱቱኤል ያወቀውን ለማወቅ ምሥጢር ተገልጾለታልና ማለት ነው ሱቱኤል (ዕዝራ) መጻሕፍትን ከጠፉ በኋላ ጽፏል ።

ልዑል አልጋ ወራሽም መጻሕፍትን ከግዕዝ ወደ አማርኛ መልሰዋልና ።

ጨዋታ ።

ከድሬዳዋ በባቡር ተሣፍሬ ወደ አዲስ አበባ ስመጣ አንድ ሰው አጠገቤ ተቀምጦ ነበረና እየተጫወትን ስንሄድ አረቄ በኮዳ ይዞ ኑሮ አስቀድሞ እሱ ቀድቶ ጠጥቶ ደግሞ ለኔ እንካ ጠጣ አለኝ እኔም አልጠጣም የማልጠጣበትም ምክንያት አንድ ጊዜ ታምሜ ነበረና ሐኪም ስለከለከለኝ ከዚያ ወዲህ ከቶ አረቄ ጠጥቼ አላውቅም ብዬ መለስሁለት ።

ሰውየውም ይልቅ ብትጠጣ ይሻልህ ነበረ የሚያድን ክርስቶስ ሆኖ የዛሬ ዘመን ልጆች ጥቂት ሲያማችሁ ወደ ሐኪም ትሮጣላችሁ፡እንዲያውስ ፈረንጆች ከመጡልን አንድ ዋና ነገር ይህ አረቄ አይደለምን ብሎ ጠየቀኝ ።

እኔም አዎን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዘመኑ ብዙ አመምተኞችን ሃይማኖታቸውን አይቶ በቃሉ እንደዳናቸው በዚያውም ዘመን መድኃኒተኞች እንደነበሩ ማቴ ም ፱ና ፬ እናነባለን ፈረንጆችም ወዳገራችን ጥቅም ያለው ብዙ ነገር አምጥተውልናል ።

መጀመሪያ፤ ይህ አንተንና እኔን ይዞ በሩጫ የሚሔድ ዱሮ በእግር ከሐረር አዲስ አበባ ፳፭ ወይም ፴ቀን ያስጉዝ የነበረውን ጎዳና ቈርጦ በ፪ቀን የሚያደርስ የምድር ባቡር ነው ።

፪ተኛ ዱሮ ጌታ ወደሎሌው ወረቀት ጽፎ መልክተኛው በስንጥር እንጨት አጣብቆ ይዞ ሲሔድ መልክተኛው በመንገድ አደጋ ቢያገኘው ወረቀቱ የትም ወድቆ ምሥጢሩ ባክኖ ጉዳዩም ተጓጉሎ ይቀር ነበረ ። ዛሬ ግን የቸኰለ በስልክ ቃል ለቃል ተነጋግሮ፡ያልቸኰለ ደብዳቤ ጽፎ ከፖስታ ቤት እየገባ ደብዳቤው ለተጻፈለት ሰው በእምነት ደርሶ ጉዳዩ በቶሎ የሚፈጸም ሆነ ።

፫ተኛ በሱቅ ተደርድሮ የምታየው ዕቃና መሣሪያ ሁሉ ከፈረንጅ አገር የመጣ ነው፡ገና ወደፊት እኔ ባየኹ ያላየሁት አንተ ስሙን በጆሮህ ያልሰማኸው ብዙ ዕቃና መሣሪያ ይመጣል ይህ ሁሉ ዱሮ መች ነበረ ብዬ መለስሁለት ።

ሰውየውም እባክህን ተወኝ ዱሮማ ከልዑል ራስ መኰንን ጋራ ከሐረር ወደ አዲስ አበባ ስንሄድ መጀመሪያ ስንቅህን ደግስ ሎሌና ገረድህን አልብስ፤ ከብትህን አጠጥር ተብሎ አዋጅ ይነገርና ጉዞውም ሲጀመር አሽከር ተራዳና እርኩቱን ተሸክሞ እለፍ ጓዴ እያለ አጋሠሡን ሲነዳ ገረድ ገንቦዋን አዝላ ዘፈንና እልልታዋን እያቀለጠች ስትሄድ ። በኋላ አባ ታነው መልእክ

መስሎ በሰጋጊ በቅሎ ተቀምጦ በቀኝ በግራው ባለሟሎቹ እያሳሳቁት እምቢልታ መለከቱ እሬቱ ዋይ ዋይ እያለ በአልፍ ሠራዊት ታጅቦ ጥቂት እንደተጓዘን ገና በሩቁ ያባ ታኘው ድንኳን ጥላ እንደ ጣለ ደመና ረቦ በዙሪያው የመኳንንቱና የሠራዊቱ ድንኳን የመስከረምን አበባ (ወይም የኅዳርን ከዋክብት) መስሎ ይታያል፤ አሽከር ድንኳን ተክሎ ከብት አሠምርቶ ሣርና ገለባ ዘርሮ፤ ገረድ ቂጣ ጋግራ፤ ቡና አፍልታ እንደርሳለን፤ ትጥቃችንን ፈትተን እግራችንን ታጥበን ቋንጣው ዳቦ ቆሎው፤ ይቀርባል ቡና ይጠጣል፤ ቂጣ በተልባ እንበላለን ያለው ጠጁን፤ የሌለው ተልባውን ይጠጣና ከየባላገሩ ቤት መጥኑ፤ ድልቡ፤ በዙሪያ ገበው እንደ ጕርፍ ይጕርፋል ወዲያው ግብር ይገባል በጠጅና በጮማ እየተቀማጠልን በድንኳን እያደርን ድሀ ወታደርም እየቁጥቋጠው ሥር አርፎ በሶውን፤ ድርቆሹን፤ በልቶ የቅምጫና ወሀውን ጠጥቶ እኩሉ ሲያቅራራ እኩሉ የት ጎንበስ ጎንበስ ሲል እያደረ በንዲህ ያለ ውበት ፴ ቀን ብንጓዝ ምን አለበት ። እስኪ ዛሬ ከኪሣራ በቀር ከባቡር ምን ጥቅም አግኝተናል ብሎ ጠየቀኝ።

እኔም ከባቡር ያገኘነው ጥቅም መጀመሪያ ሰውና እንስሳው የሚደክመው ድካም መቅረቱ ከየወረዳው ሹማምት ይልቁን ከተገዢዎቻቸው የሚመጣው ኪሣራ ላመት ይበቃናል ብለው የቈለሉትን ሣርና ገለባ ሌላውንም ሁሉ ወታደር እየዘረፈ የሚሠራው ግፍ ሁሉ ቀርቶ ዛሬ በገልግል እንጀራ ስንቅ አዲስ አበባ በ፪ ቀን ይደረስ ጀመረ፤ የዚያን ጊዜውን ድካም ዋጋና የዛሬውን የባቡር ኪሣራ ብናመዛዝነው የዛሬው ባቡር ዋጋ ፲ ጊዜ ያንሳል ።

ሁለተኛ የብረት መንገድ ከተዘረጋ ወዲህ ከሮጳ የሚመጣ ዕቃ ሁሉ ከቀድሞ ዋጋው እኩሌታውን ነቅሰዋል (እንሰአል) ሶስተኛ ከባለጸጋይቱ ሀገራችን የሚገኝ ነገር ሁሉ ዱሮ በየጋላው አገር የዝሆን ጥርሱን እንደ እንጨት አወናክረው እያቆሙ ጎጆ ይሠሩት ነበረ ቡናው ጥቅም እንደ ሌለው ዛፍ ፍሬ እየረገፈ ይቀር ነበረ ማለትን እንሰማለን ። ቆዳም ባገራችን ምን እንደነበረ ታውቃለህ፡ዛሬ ግን ይህ ሁሉ ገንዘብነቱ ታውቆ ዋጋ የሚያወጣ ሆነ፤ ይልቁንም የምድር ባቡር ከመጣ ወዲህ የቀድሞ ዋጋውን ያህል ጨምሯል የሀገራችንም አራሾች እህሉን እየሸጡ ብዙ ጥቅም አግኝተዋል ፤ ነገር ግን አራሹ ስላነሰና ሸምቶ የሚበላው ስለበዛ በገበያ እህል ተወደደ ይባላል አገራችን ጠባብ አይደለችም ብዙ ጠፍ መሬት አለና ስለዚህ መንግሥታችን የጠፉን መሬት ለሥራ ፈቱ እየሰጠ ቢያሳርሰው እህል ይበዛል፤ እህልም እተወደደበት አገር እየተሸመተ ሕዝብና መንግሥት ይበለጽጋል፡ነገር ግን እኔ አላርስም ሌሎች እርሰው ያመረቱትን እህል በግድ በርካሽ እየሸመትሁ እበላለሁ ማለት መልክም አይመስልም ብዬ መለስሁለት ።

ሰውየውም ይህን ስትዘበዝብ የዋልከውን ነገር ሁሉ ከጉዳይ አልቈጥረውም ነገር ግን የሀገራችን እህል ዓይናችን ሲንከራተት አፈረንጅ አገር ከሚሄድ እዚሁ ነቅዞ ቢበላው ይሻላል ብሎ መለሰልኝ ።

ከዚህ በኋላ ከመጨቃጨቅ በቀር ለነገራችን የረባ ፍጻሜ ስላጣሁበትና ነገሬ የማይገባው ስለ ሆነ ጨዋታውን ተውሁት ።

አስታጥቄ ወልደ አማኑኤል ።

የደብዳቤ ቃል ።

እንደምናየው ኢትዮጵያ የልጆቿ ዕውቀት ቀድሞ በጥበብ ከቆዩ አባቶች ሲወርድ ሲዋረድ የመልክም መሠረት ቡቃያ ሕይወት ሆንዋቸው የሥልጣኔ አገባብ በመጀመሪያቸው ደስታዋ እየጸና ለጕረቤቶችዋ ውበቷን ባለማቋረጥ እስከፍጻሜ ድረስ ዕለት ዕለት ትገልጻለች ።

በዘንተኝነትንም እንደማዕበል በያለበት ከበው መግቢያ አሳጥተዋታልና እነሆ በሀገራችን የትምሕርት ቤት መስፋት የሠራተኛው መተባበርና ትጋት ለመንግሥታችን እንደማይደርቅ ምንጭ መፍለቅ የሕዝቡ ከትልቁ እስከ ታናሹ ድንቁርና መሸሽ ልባቸውን እየመሰጣቸው የጐደለውን የትምሕርት ቤት ለማቆም ያስቡ ይሆናል ። ዕርዳታቸውም በድኖቻቸው ሁሉ ላይ ነው ስለሆነ የተለመደ ጠባይ ቢኖር ለተበዳዮች በመራራት የሕዝብ አነዋወር ጠባቂዎች ጉዳት የሆነውን ነገር ማረም ይገባቸዋል ክብረት በመተዛዘንና በመፈቃቀር ሥራ ይመጣል፤ ዳሩ ግን መንግሥት ከልከበረ አእምሮን ለማግኘት መመኘታችን ከንቱ ነው ። የኢትዮጵያ ልጆች በየዋና ሥራ ላይ የታመኑና ያሉ ለመንግሥት የሚገባውን ባለማጕደል በትክክል ቢሰሩ የሐገራችን ልምላሜ አይመረመርምና እያንዳንዳችን የሚገባ ስጦታችን አይሰናከልብንም፤ ሰማያዊ መዝገብ የመሰብሰብምሳሌ ይሆንልንና መታመንም በዙሪያችን እንደ ድባብ ታጠላን ነበር ። በባላገርና በዳር አገር የሚሠራውን ሁነታ ባጭር አሳስባለሁ በሚከተለው ጋዜታ ለይቼ እጽፈዋለሁ ። የተመሰገነችው አገራችን ደም ግባት የቤትዋም ማማር በልዑል ተፈሪ መኰንን መብራቷ መልክም እንደሆነ ይታያል ። ወደ ጥበብም እንደ ጥንቁቅ እንዝሬ አመልማሎ ሐሊናዋን ትዘረጋለች መታሰቢያዋም ለሚከተሉት ሰዎች ፍሬ ሁና ትኖራለች፤ የልዑል አልጋ ወራሽ ሐሣብ ስለ እናታችን ኢትዮጵያ ትምሕርት ማስፋት ከፀሐይ በታች የፍጥረት ልብ ሊወስነውና አስተውሎ ይቈጥረው ዘንድ አይችልም ። ያለመቋረጥ ምኞታቸውን ብንቀበል ብልሀነትን በመውደድ እንደመስታወት የጸራች የውቀት አውድማ በሠራን ነበር ። ለዚሁም የሠራዊት ጌታ ጠብና ክርክርን እንዲያስወግድልን ፈጥነን ወደሱ እንጸልያለን ። ምን እናገራለሁ ብሎኛልና ይህነንም እሱ ሰርቶዋልና በዘመኔ ሁሉ ቀስ ብዬ እሄዳለሁ ።

[illegible] [illegible] እንደተባለ ልዑል በገንዘብዎ [illegible] ማክናወኛ ብለው ከልብዎ ፈልቅቀው በሕይወታችን ዘመን ከፍታው በበዛ ችሎትዎ ያሠሩልን የተማሪ ቤት በፍጹም ተዘጋጅቶ ሳለ ሥራው ባለመጀመሩ እናዝናለን ። አቤቱ አስብ በፊትህ በውነት እንደሄድሁ የሚል ጸሎትዎን ታምኑ ተስፋችንን እናበረታለን ። ያስጀመረዎን ያስፈጽምዎ እያልን ከውነተኛው ንጉሥ መድኀኔ ዓለም ቸርነቱን እንለምናለን ። በዚህ ዘመን ያሉ ኢትዮጵያውያን አዲስ ጊዜ እንዲወጣላቸው ወደ ዕውቀት ምሥራቅ ልባቸውን በመጣደፍ ያዘነብላሉ ። መመኘታቸውንም እንከተል ይላሉ ።በትዕግሥት የተሠወረችውን የጥበብ መዝገብ ትገልጽልናለች በማለት ያደክማሉ ። በማይታክት ልብ በሚቃጠል መንፈስ በጎ ነገር እናደርጋለን ሲሉ የድኅነት ቅጥር ሥቃይና ሞት ደመወዛቸው ሆና ትታገላለች ስለዚህም መምሕራኖች በመንፈሳዊና በሥጋዊ ነገር ልብ ለማጽናት ሲያስተምሩ እንደሚገባቸው የታዘዙትን ከሁሉ የሚበልጥ

የጥበብ ስጥወታ ለመግለጽ ግዴታቸው ይሆናል ። የእጅ ብልሃት በመምሕራን መልካም ፈቃድ በየገሩ እንደዳበረ እንመለከታለን እኛም የዕረፍት ዘመን የጠበቀ ግሥገሣ እስኪመጣልን የውቀት መከፈቻ እንዲሰጠን እጅግ አብዝቶ የወደድነን አለመሰልቸት አስቀድመን መድኀኒታችንን ሰላም ስጠን ስንል እንለምናለን

አየለ ገዳ ። ዘብሔረ ወግዳ ።

* * *

ባንድ ያለፈ የብርሃንና ሰላም ጋዜጣ ኑሚሮ ብርሃን ፫፻ሺ ኪሎ ሜትር ባንድ ሰንንድ የሚወረወር ሲሆን ፡ በዚያች የምድር ነጥብ ሳይደርስ እስከሁን በመቆየቱ የተወቀሰበትን ክፍል አይተን ፡ የነገሩን እውነትነት ለማወቁ እጅግ የመረረ ሆኖብናል በዚያች ቦታ ሳይገለጽ መዘግየቱን የሚያጸድቅ አንዳች የሚያሳርፍ ምክንያት በማጣታችን ከብዶን እንቈረቈራለን ። ምን ስለጉደለበት ይሆን በምሉ ፍጥነቱ ያልደረሰበት? ወይስ «ያች ቦታ ከፈጣር» እንዴት ያለች ብትሆን ይሆን ? ወይስ ብርሃን በምሉ ፍጥነቱ የማያሳልፍ አንዳች የሸፈናት ነገር አላት ይሆን ? እነዚህና እሱን የመሰሉ ጥያቄ ከልባችን ጋራ በመመራመር እንቈረቈራለን

ብርሃን በአየር ሲያልፍ ባንድ ሰንንድ ፫፻ሺ ኪሎሜትር እንደሚወረወር የፍጥረት ባሕርይ መርማሪዎች ብለዋል ። በውሀ ውስጥ ሲያልፍ ግን ባ፩ ሰንንድ ፪፻፳፭ሺ ኪሎ ሜ ብቻእንደሚወረወር ብለዋል። ይህ ሲሆንም በምሉ መድመቁ አይዘልቅበትም። ደግሞም በውኃ ውስጥ ያለ አንዳች ነገርን የሚያዩ ሰዎች ካለበቱ ስፍራ የቀረበ ሆኖ ይታያቸዋል ። የዚህም ምክንያት ውሀ የብርሃን ፍጥነትን የሚያዘገይ መሆኑ ነው ተብለዋል በእንደዚህ አሊያ ሰዎች በትክክል ሳያዩ በትክክል የሚያዩ እንዳሉ ሲመስላቸው የነገሩን ሁሉ አኳሆን ያወቀ መሐንዲሱ አሊያ ሰዎች በትክክል እንዲያዩ ብሎ ሲያስብ ፡ እኒህ የፍጥረት ባሕርይ ሕጋት የማይለወጡ የማይገለበጡ ዘላለም የቆሙ ስለ ሆኑ ብርሃን በዚያች ቦታ በቀጥታ እንዲደርስ በእውቀቱ ኀይልና በፈቃዱ ብርታት ፡ የብርሃኑን ፍጥነት የሚያዘይገን ነገር ለማስወገድ ሲታጠቅ ጊዜ ከሰራተኞቹ ጋራ ሆኖ ሳለ ፡ ልክ በሌለው ልፋታቸውና ወሰን በሌለ ትጋታቸው ኀይል «በዘመን የማይቻል የመሰለውን የሚቻል ሆኖ ሲገኝ» ባንዳች የቦታው የማይዘለቅ ባሕርይ ምክንያት ከስራቸው የታገዱ እንደሆን ለዚያች ቦታ የሚሆን ምን ተስፋ አለ? የሚወጣው ፀሐይ ፊተኛ ጮራን ለመሳለም ዓይኑን ወደ ምሥራቅ የሚመልስ ትውልድ ቡሩክ ነው።ለሚከተሉት ትውልዶችም ብርሃኑ እየደመቀላቸው ይሄዳልና እውነተኛ ብርሃንና ሰላምን ያወርሰዋቸዋል ።

ኤፍሬም ተወልደ መድኅን ።

ከኢጣልያ መንግሥት ሌጋሲዮን ።

በቴሌግራም የመጣ ቃል ።

የየካቲት የ፳፰ቀን የእለት ወሬ ።

ሮማ በየካቲት የመንግሥት ዋና ገቢ ሺ ፲፻፲ - መሊዮን ሊሬ ሆነ ። በ፲፱፻፲፯ ዓ ም በየካቲት ከነበረውም ገቢ ፳፬ መሊዮን ሊሬ በለጠ ።

ሙሴ ሙሶሊኒ በፕሬዚዳንት ኤበርት ሞት የጀርመንን ኀዘን ስለ ተካፈሉ ከጀርመን መንግሥት ቻንስለዩ የምስጋና ቴሌግራም ተቀበሉ ።

ፓሪስ በታንጀሬ በሚሊቴር ሰፈር አብደል ከሪም ሙተዋል የሚል ከማድሪድ የመጣውን ወሬ አያምኑትም ።

አንጎራ በትልቁ የሕዝብ ጉባዔ የፈትሒ ቤ ሻምብር ስንብቻና የኢስሜት ፓሻ ሻምብር መቆም የተጻፈበት የሬፑብሊኩ ፕሬዚዳንት ደብዳቤ ተነበበ ።

ዋሽንግቶን ሙሴ ኩሊድጅ ባዲሱ ያራት ዓመት ሹመታቸው እንደ የሬፑብሊኩ ፕሬዚዳንት ለመንግሥት ለመታመን መሐላቸውን ከቀረቡ ወዲያ የምርቃን ንግግር አደረጉና ፡ ዩናይትድ ስቴትስ (የተባበሩ ያሜሪክ አውራጆች ።) ከሕዝብ ሁሉ ጋራ በሰላም ለመኖር ፈቃዱ ሲሆን ለመታፈሩና ለደኅንነቱ የሚገባ የሚሊቴር ሠራዊት ማድረግ እንደሚያስፈልገው ተናገሩ ። ስለ ሕዝቦች ጉባዔ ይህ ፖሊቲክ እንዲቀጥል ፈቃዳቸው እንደ ሆነ ተናገሩ ዩናይትድ ስቴትስ ኑዋሪ በሆነ በመንግሥታት ማኅበር መጋቢያ እንዲገባ ፈቃዳቸውን አስታወቁ ። ደግሞም አሜሪክ በኤውሮፓ ፖሊቲክ ሊገባ ወይም ከአሮጌው ዓለም አሮጌ ፖሊቲክ ሊታወም ተስፋ እንደማይሰጥ፤ ግን ታላቁ ገቢው ችግርን ለማቅለል የፈረሰውን የሕዝብ አኳኋን እንደገና ለማቆም ሊረዳ እንደሚገባው ተናገሩ ኑዋሪ ሰላም የሚገኝበትን መንገድ ብዙ ጊዜ እንደ ፈለጉት አስታወቁና የዚህን ነገር ድል መንሣት የሚያስረግጠው የሰው መንፈሳዊ ባሕርይ ብቻ እንደ ሆነ ተናገሩ ። የአሜሪክ ፖሊቲክ ለመርዳት እንጂ ከቶ ለመጨቈን እንደማይሆን ብለው ንግግራቸውን ጨረሱ የካቲት የ፳፱ቀንና የመጋቢት የ፩ የ፪ቀን የዕለት ወሬ ።

ሎንድር ቻምበርሌን በፓሪስ አድርገው ወደ ጄኔብር ለመሔድ ተነሥተዋል ።

ፓሪስ ሙሴ ሄርዮትና የቤልጅክ የውጭ ጉዳይ ምኒስትር ሂምናስ በጄኔብር ስለሚነጋገሩበት ነገርና አሁን ከሁለቱ መንግሥታት መካከል የንግድ ጉዳይ ሁኖ ስላለ ስለ ኤኮኖሚ ነገር ተገናኝተው ነበር ።

በርሊን ፡ በፓርላሜንት ሰፈር የጀርመን መንግሥት አውራዎች የጀርመን ሬፑብሊክ ለዲስ ፕሬዚዳንት እስኪመረጥ ድረስ የውጭ ጉዳይ ምኒስትር የነበረ ሙሴ ሲሞንስን በሕግ አድርገው የመንግሥት ፕሬዚዳን እንዲሆን ሊመርጡት ይስማማሉ እየተባለ ይወራል ።

ፓሪስ ። ሙሴ ሄርዮት ቻምበርሌንን በታላቅ ክብረት ተቀበሏቸው ። በዚያም የኢጣልያ የቤልጂክ የያጰን አምባሳደሮች ነበሩ ።መጋበዙ ሲያልቅ ሙሴ ሄርዮትና ቻምበርሌን እርስ በርሳቸው ምኞታቸውን እያቀረቡ ጽዋቸውን አነሡ ።

ማስታወቂያ ።

ብርሃንና ሰላምን የም ትቀበሉ ሁሉ የዓመት ዋጋውን እስከ ሚያዝያ ድረስ እንድታገቡልን በማክበር እናመለክታችኋለን ።

በልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ።

መጀመሪያ ዓመት ፤ ቁጥር ፲፫ ።
1 re ANNÉE № 13

ሐሙስ መጋቢት ፲፯ ቀን ፤ ፲፱፻፲፯ ዓ ም ።
JEUDI 26 MARS 1925

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፫ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፩ መሐልቅ ይሸጣል ።

የጋዜጣው ዲረክተር ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲረክተሩ ያስታውቁ ።

የራሱን ጉዳይ የሚያሳትም ሰው ዋጋውን እየከፈለ እናትምለታለን ።

የልዑል ራስ መኰንን መታሰቢያ ።

በየመቱ ።

በሐረር ባሉ አድባራትና አብያተ ክርስቲያናት በሌላውም በታ ሁሉ ፤ ስሙ የማይሞተው የደጉ የስመ ጥሩው የራስ መኰንን መታሰቢያ ግሩም በሆነ ፍትሐት እየተፈታ መጋቢት ፲፫ ቀን በየመቱ የመታሰቢያቸው በዓል ይደረጋል ።

ይኸውም ቀን በ፲፰፻፺፰ ዓ ም መጋቢት ፲፫ ቀን ከዚህ ዓለም ድካም ተለይተው ወደዘለዓለማዊ ዕረፍታቸው የተመሩበት ስለሆነ ለይተን ጻፍነው እንጂ ስማቸውስ ሁልጊዜ በየአድባራቱ በየገዳማቱ ሲጠራ እንዲኖር የታወቀ ነው ።

በመላው ኢትዮጵያ ካሉ አድባራትና ገዳማት ሁሉ የራስ መኰንን ገንዘብ ያላለፈበት፥እጃቸው ያልተዘረጋበት ወዴት ነው?

በራስ መኰንን ስም የተቀረጸ መስቀል ፤ በስማቸው የተጻፈ መጽሐፍ የሌለበት ደብር ወዴት ነው ? ። ስለዚህ የርኅራኄ እጃቸው በተዘረጋበት አገር ሁሉ ስማቸው ሕያው ሆኖ በጸሎት ሲነሣ ይኖራል ።

ዛሬም ፲፱፻፲፯ ዓ ም መጋቢት ፲፫ ቀን እሁድ በሐረርና በሌላውም በታ ሁሉ የመታሰቢያቸው ቀን በጣም ክብሮ ዋለ ያልቁንም ለነዳያን የእረፍት በዓል ሆኖላቸው ከረሃብ ድካም አርፈውበት ዋሉ ።

ከዚህም ቀጥሎ የዛሬ ፲፱ ዓመት የልዑል ራስ መኰንን መሞት አዲስ አበባ ላይ በተሰማ ጊዜ አንድ ወዳጃቸው እያለቀሰ የተናገረውን የልቅሶ ግጥም ብርሃንና ሰላምን ለሚያነቡ ሰዎች እንጽፍላቸዋለን ።

ልዑል ራስ መኰንን የሞቱበት ቀን ዓርብ ነበርና ምሥጢር አጋጥሞት በግጥሙ ውስጥ ስለተናገረው ቃል የመጻሕፍትን ምሥጢር ለመጠራጠር እንዳይደለ ተመልከት ።

፩ የሸዋ መኳንንት እግዚአብሔር ያጥናችሁ ።
በየበሩ ቋሚ ከልካይ ሞተባችሁ ።
፪ እንግዲህ ትንግሡን ደቅር ማመናችን ።
ዓረብ ጠፍቶ ለሁድ ክቀረ ጌታችን
፫ ብዙ ንጭ ጥሎ ብዙ ንጭ አስጥሎ እንዲህ ሳይቀምስለት ።
አሳፍሮት ሄደ የሐበሻን መንግሥት
፬ ሰገባውን ደገፎ ገገዞ ዓረቡን ።
መሬተኛው ጠሩ ሰፊ ብለምን ።
ወደ አንተ ደገሰው ራስ መኰንን
፭ በማሩ መች ደሄዳል የንጋሚ ልጅ
በቅሎ የሚያወቀው መኰንን ነው እንጂ ።
፮ ከቁልቢ ጠፍቶ ሲሄድ ወደማታ ።
ከተማሰው መሳቢት አደፈራሞደ ጌታ ።
፯ ድንገት ሳናስበው ዝናብ ዘነበብን
የዘንድሮ አዝመራ ረግሮ ቀረብን
አዳራሽ ማብላቱን እየተወ ሰው
ዕዳስ ማብላቱ ነው የሚያስለቅሰው
፰ ገበታ ዘርግቶ ሲያሳልፍ ለቶቹ ።
ድንገት ሳያስቡት ነክቶባቸው ጣቱ
አልቅሰውበት ነው ዓደናቸው ውጥፋቱ ።
፱ ፈረስ በቅሎ ሰጠኝ ብዬ እንዳለምንህ ።
እኔን ሲፈልግ ነው አንተን ያገኘህ
፲ የንጉሡ ባለሟል ውሸት የት ለመድ
ፈረሱን አስጭኖ ሳያስበው ሄደ ።
፲፩ ቢያሳስት ነው እንጂ ሲያረዳ ስልክኛው ።
መኰንን አይደለም የሞተው ደሀ ነው ።
፲፪ መኰንንነቱን አናውቀውም እኛ
ለድሀ ብር አፍሳሽ ደሀን እንጥረኛ
፲፫ መኰንን መጻፊያህ ቀስተንቻ ይሁን
መቃብር ክፉ ነው ያጠፋል ቀለምህን ።

በዚህ በልቅሶ [illegible] እየገጠመ በለዋበ ጊዜ የዋናተኛ ወዳጆቻቸው ሁሉ እንባቸውን ሲያንርፉት ውለው ነበር ። ግጥሙም ይኸ ብቻ አልነበረም ፤ ላንባቢ እንዳይሰለች ብለን ለመታሰቢያ ያሀል ከፍለን ጻፍነው እንጂ ፤ በዓረብ አገርና በሐረር በዓዱዋ ላይና በሌላውም በሰልፍ በታ ሁሉ መጀመሪያ እየተገኙ የጀግንነት ሥራ እየሠሩ የኢትዮጵያን ዝና የደገፉ ራስ መኰንን ናቸውና ለሀገራችን የዋሉላት ውለታ ሁሉ ትዝ ስላለን የመታሰቢያቸውን ታሪክ ለብርሃንና ሰላም ወዳጆች ጽፈንላቸዋል ።

የደብዳቤ ቃል ።

ይድረስ ለክቡር አቶ ገብረ ክርስቶስ የልዑል ኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ማተሚያ ቤት ዲረክተር ። የፍቅር ሰላምታዬን በትሕትና አቀርብልሃለሁ።የላክህልኝ ጋዜጦች

ደረሱኝ በጣምም ደስ አለኝ አስበህና አክብረህ ስለላክህልኝ እግዚአብሔር ያስብልህ እግዚአብሔር ያክብርህ ።)

ሰማህን ክቡር ወንድሜ ሆይ እስከ ዛሬ ድረስ ሐገራችን ልታፈራ የሚገባትን አለማፍራቷ ደማችን ሊከበር የሚገባው ንብረታችን የተሟላ ሊሆን የሚቻለው ሲሆን ጎደሎ ሆኖ መቅረቱ እርስ በርሳችን ባለመረዳዳታችን ሁላችንም የኢትዮጵያ ልጆች ተባብረን ዕውቀትን በመካከላችን ለማኖር ባለማሰባችን ነው ። ለእኛ እንደሚመስለን ሰው ከእንስሳ የሚለየው በመልኩ ነው ፤ ነገር ግን ይህ እውነት አይመስለኝም ። መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ሰውን በመልኩ ፈጠረው ይለናልና የሰው ልጅ ክብረቱ በመልኩ እግዚአብሔርን ስለ መሰለ ነው ።ይህም ትልቅ ስህተት ነው ። የሰው ልጅ ምን ጊዜም ከስህተት ወጥቶ አያውቅምና ሁልጊዜ በሁሉ ቦታ እየተሳሳትን እንኖራለን ። አሁንም አምነንና ክርተን የምንቀመጥበት አሳብ ግዙፉን ወይም መሸፈኛውን ቆዳ እንጂ በውነትስ ረቂቁንና በቆዳው ውስጥ ያለውን ፍሬ አናውቅም ።

ሰው ከእንስሳ የሚለየው በመልኩ ብቻ አይደለም ፤ ብአእምሮውና በሥራውም ነው እንጂ ።ይህም እርግጥ መሆኑን በመጽሐፍ ብንፈልግ በፈቅድነው ነገር ልንረዳው እንችላለን ሰው እርግጥ ከእንስሳ በመልኩ ብቻ ቢሆን የሚለየየው ፈረስ እንደ ዘሆን ፤ ይኸኛውም እንዳይጥ እኩል እንስሶች ተብለው ባልተጠሩ ነበር ።

ሁለተኛ ጠሩ የሚሉት ቃል በሁለት ይፈታል ፡ ጠሩ (ሰው ጠሩ) ጠፉ (ንጹሕ ሆነ የደፈረሰው ጠሩ) አንዱ ቃል በድምጥም በፊደልም ሳይለዋወጥ በሥራው ልውጥነት ክሁለት ተከፈለ ።

መ ቅ ኦሪት ዘፍ ፩ ፳፮ ።ወይቤ እግዚአብሔር ንግበር ሰብአ በአርአያነ ወበአምሳሊነ ወይኰንን ዓሣተ ባሕር ወአራዊተ ምድር ወአዕዋፈ ሰማይ ወእንስሳሂ ወኵሎ ምድረ ወአራዊተ ዘይትሐወስ ዲበ ምድር ።

ቁ ፳፯ ወገብሮ እግዚአብሔር ለእጓለ እመሕያው በአምሳሊሁ ተባዕተ ወአንስተ ይላል ። ይህስ መልክም ነው ። ግን የእግዚአብሔር መልኩ እንደምንድነው ። የእግዚአብሔር መልኩ እንደ መልክም ሥራ ደስ የሚል ጽዱ የቀና መንገድ ነው ። የእግዚአብሔርን መልክ በደግ ሥራ እንጂ ሌላ በምን ነገር እንምስለው ይሆን እግዚአብሔርን ልንመስል የሚገባን በደግ ሥራ ነው ። የእግዚአብሔር ሁለንተናው ደግ ሥራ ነው ። ደግ የሚሠራም ሁሉ እግዚአብሔርን ይመስላል ፤ ደግ የማይሠራ እግዚአብሔርን አይመስልም ። ደግ የሚሠራ ግን በእግዚአብሔር መልክ ተፈጥሬአለሁ የኢየሱስ ክርስቶስ ወዳጅ ነኝ ብሎ በልቡ ደስ ሊለው ይችላል ፤ ከዚች ዓለም ሕይወት ወሰን ሲደርስም ወደ ወዳጁ ጌታ ሊገናኝ በመሔዱ ተስፋ ያደርጋል ክፉ የሚሠራ ግን በእግዚአብሔር መልክ ያልተፈጠረ (በግዙፍ መንገድ እንስሶች ከሰው በመልካቸው እንደሚለዩ) እሱም ልክ እንደዚሁ ከሰው በሥራው የተለየ ነው ። ለሱም ሞት መፈራ ነች ተስፋም የሚያደርግበት ነገር የለም ።ሞትም ይዞት ሲሔድ የሚያደባልቀው ከኃጥአኖች ጋራ ነው ። ይህን የመሰለ ሰው ፤ ሰው ነኝ ብሎ በልቡ አይኩራ ልኩራ ቢል ሕሊናው ትንቀዋለች ።

በልዑል ኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ማተሚያ ቤት የሚወጣ ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም መልክም ስም ተሰይሞለታል ብርሃንና ሰላም ብርሃን ዕውቀት ሰላም ዳኝነት ። ብርሃንና ሰላም ማለት ዕውቀትና ዳኝነት ለመልክሙ ሀገራችን ለኢትዮጵያ ለኛም ለኢትዮጵያ ሕዝቦች በጣም ያስፈልገናል ።

በድሮ ዘመን ሰው ከእንስሳ አይሻልም ነበር ፤ አመሉም ኑሮውም እንደ እንስሶች ሁሉ ነበር ። ግን እግዚአብሔር የሰውን ልጅ የሚወድ ስለሆነ ኢየሱስ ክርስቶስን ለዓለም ቤዛ አድርጎ ላከልን ። ኢየሱስም ፴፫ ዓመት በማህላችን ተቀምጦ የደግን ሥራ ምንጭ ብርሃንና ሰላም የመላበትን መንገድ በሐዋርያቶቹ ልብ ቅዱስ ወንጌልን ትቶልን ወደ አባቱ ተመለሰ ።

ይህ በልዑል ጌታችን ማህተም ቤት የሚወጣ ጋዜጣ እውቀት ላለው ወንድማችን ጉልበት ይሆነዋል ፤ እውቀት ላነሰውም እውቀት ይጨምርለታል ። ተራ ቀጋ ከሌላው ከመልካሙ ሲከትቡት ስሙ ደስ ያለ አበባው ያማረ ጽጌ ረዳ ይሆናል እንደዚሁም ሁሉ አመሉ ለስላሳው ሕዝባችን ብርሃንና ሰላም በሚያመጣ ነገር የተከተበ እንደሆነ ሁሉም ክርስቶስን ሊመስል ይችላል ። ስለዚህ የኢትዮጵያ ልጆች ሁሉ ለንደዚህ ያለው መልክም ነገር እየተረዳዳን ይህ የተጀመረ ሥራ እየሰፋ እንዲሔድ እና ድርግ ። ይህን የመሰለ አሳብ ያለን ሰዎች ሁሉ ፍርኃት አይደርብን ሀገር የሚያጠፋ ሕዝብ የሚበድል መንግሥት የሚያናውጥ ሥራ አይደለም የምንሠራው ። ይልቅ ይህን የመሰለ ሥራ ሀገር ያለማል ሕዝብ ይጠቅማል መንግሥት ያጠነክራል ። ነገር ግን በክፉት መንገድ የሰለጠኑ የሀገር የሕዝብ የመንግሥት ጠላቶች እየተነሱ ክፉ ሊሠሩብን ቢያስቡ ኃሳባቸውን ቢፈጽሙም ባይፈጽሙም እኛ አንበሳጭ ተስፋም አንቈረጥ ። ወንጌል በድፍን ዓለም የተሰበከው የስንትና የስንት ጻድቅ ደም ፈስሶ ነው ። ክፉ ቢሠሩብን ፍሬው እራሳቸውን ይጎዳል እንጂ እኛን እምብዛም አይጎዳን ። ግፍ ቢሠሩብን ፍሬው ጉልበት መልክ ዕውቀት ይሆነናል የሕዝብ ጸሎት ተኛ ጋራ ነውና ።

አሁንም ክቡር ወንድሜ ሆይ በብርሃንና በሰላም ስይመውና መሥርተው ለሀገራችን መልሚያ ለሕዝባችን መጠቀሚያ ለመንግሥታችን ማጠንከሻ የሚያስፈልገንን ጋዜጣ አስበው ላወጡልን ጌታችን ለልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ የሙሴን ክብር የሰሎሞንን ጥበብ ክርስቲያን የተባለ ሁሉ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደሚያፈቅር ኢትዮጵያዊ የተባለ ሁሉ ደግሞ እሳቸውን አፍቅሮ እንደ ጀመሩት በሳቸው ረዳትነት ቃሁኑ ችግራችን የምንወጣ እንድንሆን የዚህን ሁሉ ክብር አስተባብሮ ይስጣቸው የኢትዮጵያ አምላክ ስል እየተመኘሁ ላንተም ለምስጉኑ ወንድሜ ስለ ሀገራችን ስለ ኢትዮጵያ ስለ ተጎዳው ሕዝባችን ስለ መንግሥታችን ለሚለፉልን ልዑል አባትና ጌታ ስትል እንደ ሐዋርያት የታመንክና መከራ ቻይ አገልጋይ እንድትሆንላቸው እመኛለሁ ይህን የመሰለ ምኞቱም የዕውቀት ጨረር ላረፈበትና ገና ላላረፈበት ድፍን ኢትዮጵያ ልጅ ሁሉ ነው ።

የካቲት ፬ ቀን ፲፱፻፲፯ ዓመተ ምሕረት አስመራ ተጻፈ ።

በሕይወት ይግጠመን ።

ተወሰን ሥ ሚካኤል ።

ስለ ብርሃንና ሰላም።

ብርሃንና ሰላም ምንኛ ደግናቸው
ሪትና ወንጌል የታወቁባቸው ።
ብርሃንና ሰላም ምንኛ ደግናቸው ።
ሰው ልጅ በልቡ የሚኮራባቸው ።
ብርሃንና ሰላም ምንኛ ደግናቸው ።
መልክሙን ከመጥፎ የምንመርጥባቸው
ብርሃንና ሰላም ምንኛ ደግናቸው ።
አፍቅረን እንሁን በልብ እናርጋቸው ።
ብርሃንና ሰላም አጥተን ባገራችን
መከራ በዛብን አወደ እድላችን ።
ብርሃንና ሰላም መፈለግ አቅቶን ።
ኖርን እስከ ዛሬ ተሸክመን ለቅሶን ።
ባናውቅበት ማግኘት ሰላምና ብርሃን ።
ተናቅንበት እንጂ መች እስከሁን ኮራን።
እደስ ፀሐይ ወጣ የሚሞቅ ሁላችን ።
ብርሃንና ሰላም ደህ በፊታችን ።
ብርሃንና ሰላም መጣ በፊታችን ።
እስቲ እናጊጥበት ለብሰነው ሁላችን ።
ብርሃንና ሰላም ደህኛ ዘመን ልብስ
ያምራል ያስመጠን ልብ አርጎ ላየውስ ።
ዳሩ ግና ቢሆን ሥራው ያስቸግራል።
ቀዳጁና ሰፊው ከወዴት ይገኛል ።
ብርሃንና ሰላም እኒህ የሰው ልብሶች ።
መቼ ጠፉ እስከሁን ጠሉ የሰው ልጆች
ያለባበሳቸው ቅጡ ስለጠፋ ።
ሁሉን ብርድ መታው ወደቀ ተዳፋ ።
ያስነው እንቃን ተየወደቅንበት ።
ሠርቶ አልባሽ ታገኘን ተራብ መኮንን ቤት
እግዚአብሔር ይመስገን እስቲ ደስ
ይበለን ።
ብርሃንና ሰላም አልባሽ ጌታ አገኘን ።
ሐዘናችን ቅለል እንባችንም አቁም ።
ሽማግሌም ይጦር ይደጉ ልጆቹም ።
መንግሥታችን ይጥና ሮማችን ይከበር ።
ሕዝባችን ተጠቅሞ ደስ ብሎት ይደር ።
ሐገራችን ትሰፋ ትልማ ሁሉን ታፍራ ።
ንጋዴም ይነግድ በህግ እየኮራ ።
ሕዝብ አርንት ያግኝ ዳኝነት ይፈራ ።
ጠቅል ባንተ ጊዜ ቀርቶ የግፍ ሥራ ።
ተመስሥ ሚካኤል ።

ይድረስ ከክቡር አቶ ሰይፉ ።

ብርሃንና ሰላምን በመቀበልህ ደስ እንዳለህ በደብዳቤህ አነበብኩ ። ይልቁንም ወደብርሃንና ሰላም ሊገባልህ የሰደድኸውን የመልክም ሐሳብህ መግለጫ የሚሆን ቃሉን ባነበብሁት ጊዜ ብዙ ደስ አለኝ ። በዚያም ባለህበት አገር ብርሃንና ሰላምን ሊቀበሉ የሚፈልጉትን እየጠያየቅህ ማኅበረተኞቻችን እንደሚበዙና ብርሃንና ሰላም በዚያ አገር በሚኖሩ ዘንድ የተወደደ እንደሚሆን ለማድረግ በመጣጣርህ እንድትረዳን እለምንሃለሁ

በዚያ አገር የሚኖሩ የተማሩ ሰዎች ምንም በትግርኛ ቢናገሩ አማርኛም ቋንቋቸው ነውና ይወዱታል ያውቁታልም ትግርኛና አማርኛ ያንድ የግዕዝ ልጆች ናቸውና መተባበር አላቸው ።

ብርሃንና ሰላምን ቢያገኙ ለቋንቋም ቢሆን ለሌላም ምክር ቢሆን ይጠቅማቸዋል ። በዚያ አገር ደግሞ እንደብርሃንና ሰላም ያለ ሌላ የሚያነቡት ጋዜጣ የላቸውም ። በአገራቸው ቋንቋ ብርሃንና ሰላምን ሲያገኙ በጣም ደስ እንዲላቸው እርግጥ ነው

በዚያ ባለህበት አገር የኢትዮጵያ ልጆችም ፡ ፈረንጆችም አማርኛ የሚያውቁ ሞልተዋል ። ስለዚህ ብርሃንና ሰላምን ለመቀበል ብትጠይቃቸው ሳይወዱ አይቀሩምና አንተ ያምታገኛቸውን በቃልህ ፡ ለማታገኛቸውም ሰው እየላክህ እንድታስታውቃቸው በማክበር እለምናሃለሁ ። ብዙ ሰዎች ብርሃንና ሰላምን ለራሳቸው ብቻ ስለፈለጉት ብርሃኑ ሳይደምቅ ይቀራል ። ሰላሙም ወደሁከት ይለወጥባቸዋል ። አንተ ግን ብርሃንና ሰላም ለወንድሞችህ ሁሉ እንደሚሆን ነው እንጂ ለራስህ ብቻ ሊሆን እንደማትፈልገው አምናለሁ

በዚያ ያሉ የኢትዮጵያ ልጆች በሚማሩበት ተማሪ ቤትም አማርኛ ይማራሉና ብርሃንና ሰላምን ብንሰድላቸው ለተማሪዎቹ ትልቅ ጥቅም ይሆንላቸዋልና ብትጠይቅልንና አድራሻቸውን ብትልክልን መልካም ነው ።

አንተ በአስመራ ሁነህ እንደምትጽፍልንም ሌሎች ወንድሞቻችን የሚጽፉትን በጋዜጣው አይተኸዋል ፤ ስለዚህ ብርሃንና ሰላምን የሚወዱ ብዙ ናቸው እየበዙም ይሄዳሉ ። አሁን እንዳደረግኸው መልካም መልካም ቃል ጽፈህ ብትልክም ብርሃንና ሰላም በደስታ ይቀበለዋል ።

ላንተና በዚያ ላሉ የብርሃንና ሰላም ወዳጆች ሁሉ የማክበር ሰላምታዬን በብርሃንና ሰላም አቀርብላችኋለሁ አዲስ አበባ
መጋቢት ፲፯ ቀን ፲፱፻፲፯ ዓ ም ።

የሚያከብርህ
ገብረ ክርስቶስ ።

ከኢትዮጵያ ወደ ውጭ ስለሚወጣ ነገር ።

ባለፈው ወራት ሰንጋ፡እህል፡በግ፡ወደ ውጭ ስለ መውጣቱና መሸጡ የከተማው ሕዝብ ሸመታ ተወደደብን ሲል እንሰማለን ፤

ደግሞም ባ፩ ጐን ከቅርብ ከባላገር የሚመጡ ድሆች የእህሉና የከብቱ መወደድ ደስ ሲላቸው እንሰማለን። ልብስ ለብሰው ሲሄዱ እናያለን መቼውንም ላንዱ ጥቅም የሚሆን ነገር የግድ ላንዱ ጉዳት ይሆናል የሚጠቀመውና የሚጐዳው ግን በስራቸው ቢሰማሙበት ለሁለቱም ጥቅም ይሆናል እንደምን ቢሉ (ቢባል) አሁን እህልና ሰንጋ ወደ ውጭ ሲወጣ በእውነት ለባላገሩ ጥቅም ነው ለከተማው ሰው ግን ጉዳት ነው። እህልና ሰንጋ መውጣቱና መሸጡ ሲቀር ግን ለከተማው ጥቅም ነው ለባላገር ደሃ ግን ትልቅ ጉዳት መሆኑ የታወቀ ነው ። ስለዚህ የሁለቱም ወገን ሕዝቦች እንዳንጐዳ ብንስማማበት ለሁሉም ጥቅም ነው ያልሁት አሁን እህል በከተማው ውድ ሆኖ በጣም ችግር ሲሆን ወደ በቾ ወይም ወደ አቢቹ ወይም አሩሲ ከከተማው የ፪ት ቀን መንገድ ብንሄድ እህል ርክስ አመት ሙሉ የታረሰው እህል ቢሸምቱት ለባልና ለሚስት ልብስ የማይበቃ ሆኖ እራቁት ሲሄዱ ይገኛሉ ወደ ከተማ እንዳያመጡም ለጭነቱ ይርቃልና አይቻልም ስለዚህ እህል ተወደደ የሚባለው ከዚህ ከከተማው ብቻ ነው ለዚህ ነገር የሚያስፈልገው ከተማውንና ባላገሩን የሚያስማማው መንገድ መስራት ብቻ ነው ።

ይኸውም መንገድ የተባለው ባቡር አይደለም። ዛሬ ድካምና ኪሳራ እንዳይበዛ ለትልልቅ አውቶሞቢል የሚሆን ቀጭን መንገድ ሐዲድ የማያስፈልግ በያለንበት አውራጃ ሁሉም ሰው ከባላገር ወደ ከተማ የሚገባውን ጥጥ ጥጥ መንገድ ፩ ሰው ፩ ሜትር ፩ ሰው ፩ ሜትር ብንሰራው በ፩ ወር በተጨረሰ ነበር። መንገዱን የሚሰራውም ከመንገዱ በስተቀኝ ያለው ሕዝብ ከመንገዱ እንስቶ እስከ ፪ ቀን መንገድ ያለው ሕዝብ ነው ከመንገዱ በስተግራ ያለውም አገር እስከ ፪ ቀን መንገድ ያለነው ሕዝብ ተካፍለን ብንሰራ ቶሎ ያልቃል ከዚያ በኋላም በዚሁም መንገድ ላይ እህልና ሰው ከብትም የሚያመላልስ ትልልቅ አውቶሞቢል ፲ ፲ ቶን የሚጭን መንግሥት ወይም ኩባንያ ቢያመጣልን አስሩ ሞቶሞቢል በቀን ፲ ቶን አግብቶ ይውላል ይኸውም ፲ ቶን ማለት ሁለት ሺ ወይም ፩ሺ ፭፻ ዳውላ ይሆናል እንግዲህ በእንደዚህ ያለ ሁናቴ ቢሆን የከተማውን ሰው የእህል ችግር አያገኘውም ባላገሩም ነቀዝ እየበላው ወደ መሬት ይፈስ የነበረው እህሉ በመልካም ዋጋ ሲሸመትለት ደስ እያለው እኩሉን ለመሬቱ ግብር ይሰጣል

እኩሉን ልብስ ይለብስበታል የዚህን ጥቅሙን ሲያውቀው ደግሞ ለሚመጣው ዓመት እጥፍ አድርጎ ያርሳል ብርም ብዙ ወደ አገር ይገባል ባለ አውቶሞቢሉም ብዙ ብር ያገኛል ለመንገደኛም መንገድ ያጥራል ለመንግሥትም ብዙ ቀረጥ ይገባል ለዚህ ምሳሌ እኔ በወር የማገኘው ገንዘብ ፯ ብር ቢሆን እህል ተወዶ ፫ ፫ ቁና በብር ብሸምት ድሙሩ ፳፩ ቁና ነው ደግሞም ብር ከገር ጠፍቶ የማገኘው ገንዘብ በወር ፫ ብር ቢሆን እህል ረክሶ በብር ፯ ፯ ቁና ብሸምት ድሙሩ ያው ፳፩ ቁና ነው እንጂ የተረፍሁት ነገር ፩ም የለም ስለዚህ ብርም እንዳይቸግር እህልም እንዳይወደድ የሚያከናውንልን መንገድ መሆኑን ሕዝቡ ማሰብ ይገባናል ። አሁን ይኸን መንገድ ከኢትዮጵያ የትኛው አውራጃ ነው ከመንገድ ግራና ቀኝ ያለው አገር ባገሩ አኳያ መስራት የማይችል ? ሁሉም ይችላል ። እግዚአብሔር ይኸን ለማድረግ ኃይሉን ይስጠን ።

ፊ ዶሬሳ ።

ጥ ያ ቄ ።

ኢትዮጵያ በተፈጥሮዋ ሃብታም ናት ። ከተፈጥሮዋ ባሕርይ በሚገኘውም እኛን ልጆቿን ትመግበናለች። ግን እኛ ከተፈጥሮዋ የሚገኘውን ሀብት አለማበርታታችንና አለማብዛታችን ፤ የሀብትዋንም ሙላት ከኛ አልፎ እስከውጭ ድረስ እንደሚገፋ አለማድረጋችን ስለምንድር ነው ?

በሀብታም አገር ውስጥ ተቀምጠን ድሆች መሆናችን ስለምንድር ነው ?

በኢትዮጵያ ተሾመው ከገበር ላይ ከሚሰበስቡ መኳንንቶች በቀር ፤ በሥራቸው ወይም በንግዳቸው ሀብታሞች የሆኑ ጥቂቶች ናቸው ። ከሕዝባችን ነግዶ ወይም ሠርቶ እንደ ፈረንጆች ከብሂያ አቁሞ ትልልቅ ነገር ቀርቶ ትንኒሽ ነገር አለመጀመሩ በምን ምክንያት ነው? ።

ለዚህ ትኒሽ ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት የሚችሉ ብዙ ዕውቀት ያላቸው ሰዎች አሉና እየሐሳቡቸው ምላሽ እንዲሰጡና በጋዜጣ እንድንጽፍላቸው እንወዳለን ።

የተቀበልነውን ዕውቀት ለወንድሞቻችን ብናካፍላቸው ወይም ብዙ ወይም ጥቂት ፍሬ ሳያፈራ አይቀርም ። ዕውቀታችንን ለራሳችን ብቻ ይብቀነው ዝም ብንል ግን አፈር መሆናችን ኢይቀርምና የዚያን ጊዜ መታሰቢያ የለንም ።

እመክራለሁ የቀና መንገድ አሳያለሁ የሚል ሰው እንደ ሚገባ ሊመክርና መልክም አሳቡን ሊገልጽ ቢፈልግ በደስታ ተቀብለን በብርሃንና ሰላም እናትምለታለን ።

ስለ ጤፍ ውቂያ ።

በመጋቢት ፲፬ ቀን ልዑል አልጋ ወራሽ ጤፍ የሚወቁትን ሠራተኞች ለማበርታትና ሥራውን ለማየት ጤፉ ወደ ሚወቃበት ስፍራ ሔደው ነበርና ጤፍ ወቂዎች ደስ ደስ እያላቸው ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል እየገጠሙ ይጫወቱ ነበር ።

እንዴት ነው ተፈሪ ያባ ቃኘው ልጁ ።
የማይጠረጠር ለስለወዳጁ ።
፶ሺ ብር ሰጥ የማይከብደው እጁ ።
ድኻን እየበላ ሲያማው በየደጁ ።
መላክ ጠባቂ አለው ተፈሪ አባ ጠቅል ደጥለዋል እጁ ።
ጤፍ ውቂያ ነው ሲሉ ብትሰማ ወሬ ።
ሚስቱም ብላቴኖች ደስጦናል በሬ ።
እኔም መጥቻለሁ በረቱን አጥሬ ።
አደራህ ተፈሪ እንዳይቀር በወሬ ።
እምዬ ተፈሪ ደታደ ጉዳታችን ።
ዘጥ እምበፍ በንል አለቀ ልብሳችን ።
እኔ የፈራሁት የሚስቱን መላስ ነው ።
ምንጊዜ ጨረስከው ማለቷ ማለት ፡፡
ተፈሪ አባ ጠቅል የብረት ምሰሶ
የፈረሰውን ቤቱን አቀናው መ

ከዚህም በኋላ በ፫ ሰዓት ተመለሱና በያይነቱ የሞት ፍርድ ተፈርዶበት እንደ ኃጢአቱ ብዛት የሚሰቀለው ሲሰቀል የሚደበደበውም በጠመንጃ ሲደበደብ እጅግ ግፅር ይበዛበት የነበረውን የሰውን ሥቃይ ለማቅለል ልክ እንደ ኤውሮፓ መስቀያና መደብደቢያ የሠሩትን አይተው ተመለሱ ።

ይኸውም ዓርብ ይጀመራልና ሂዳችሁ ለማየት ትችላላችሁ ።

የውጭ አገር ወሬ።

የታይምስ ጋዜጣ ። የእንግሊዝ ቅኝ ገዥባላንድን ፤ የእንግሊዝ መንግሥት ለኢጣልያን መንግሥት ሊሰጠው ነገሩን በሎንዶን ፓርላሜንት እንደ ተነጋገሩበት ይናገራል።

ባለፈው በ፲፩ኛው ኑሜሮ ብርሃንና ሰላም ፤ ጀርማንያ የጦር ዕዳን ፈጽማ እስክትተው ድረስ ከሎኝን መልቀቅ ይቆይ ተብሏል ብሎ አመልክቶ እንደነበረ ከቡራን አንባቢዎቻችን ያስታውሱት ይሆናል ።

በዛሬው የታይምስ ጋዜጣ ፤ ስለ ጀርመን መንግሥት የጦር ዕዳ መወሰን ፤ የአሊያንስ የሚሉቱር ሽማግሎች በቤርሳይ ሆነው በማርሻል ፎሽ ፕሬዚዳንትነት የጀርመን መንግሥት የጦር ዕዳን ሊተው የዕርቁን ውል በጭራሽ እንደ ፈጸመው ሊታይ፤ እርሱ ሊቀበለው የሚገባውን ማመልከቻ አሰናድተው ወደ ፓሪስ እንዳቀረቡትና ለአሊያንስ መንግሥቶች ሁሉ ግልባጭ እንደ ተሰጠ እናነባለን ።

የፈላስፎች ቃል።

የተመኙትን ያላገኙ ሁሉ ከሞቱ እንግዲህ በዓለም ላይ ማ ይኖር ይሆን ። ፒሲጐር ።

የሚፈጸም ጠበብ ነው።የሚቻል ግን ሰፊ ነው በነዚህ ላይ ነፍስ ከነምኞቶቿ መኖሯ ቤት ሠራች ለዘላለም ጥበብና ፍቅር የሚመነጭበት የውበትና የብርሃን ውቅያኖስ ከለበት ውስጥ የተጠማ ሰው በየጊዜው ዘላለም ከዚሁ ምንጭ ጥሙን ያበርዳል እንቅልፍን የሚያጫጭኑ መልክም ሕልሞች ሁሉ ተንቅልፍ በመንቃት ጊዜ ይታወቃሉ ። ላ ማርቲን ።

ከኢጣልያን መንግሥት ሌጋሲዮን በቴሌግራም የመጣ ቃል ።

የመጋቢት ፯ ቀንና የ፯ ቀን የእለት ወሬ ።

ዎሺንግቶን የጃኔብ የቅርብ ጊዜ ሁኔታዎች ።

የሕዝብ ማኅበር የጦር ዕዳ መወሰን ጉባዔ በዎሺንግቶን ጉባዔ ለማድረግ የሚያስበውት አኳኋን የመጣ ይመስላል የጦር ዕዳ ስለመተው ሙሴ ኩሊድጅ አንዳች ነገር ሊደረግ ምኞታቸው እንደሆነ ይባላል ። ይህንን ነገር በሚኒክ ለሕዝቦች ማኅበር ላሁን አንዳች አሳብ ሊያቀርቡ እንደማይችሉ ይባላል ። ነገር ግን ዩናይትድ ስቴትስ ከሮፓ መንግሥቶች ጋራ ሊያደርገው የሚፈልገውን መልክም ዝምድና የሚያበላሽ አንዳች የኃይል ሥራ ለማድረግ እሺ አይልም ።

በልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ።

መጀመሪያ ዓመት ፤ ቁጥር 14 ።
1 re ANNÉE № ፲፬

ሐሙስ መጋቢት ፳፬ ቀን ፲፱፻፲፯ ዓ ም ።
JEUDI 2 AVRIL 1925

ብርሃንና ሰላም

LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፫ መሐልቅ ይሸጣል ።

የጋዜጣው ዲሬክተር ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የራሱን ጉዳይ የሚያሳትም ሰው ዋጋውን እየከፈለ እናትምለታለን ።

በብርሃን እንገለጽ ።

ብርሃን ማለት ሰው ሁሉ በሕይወት የሚመላለስበት የሕይወት ክንፍ ነው ። ብርሃን በሚያሰጥም ባሕር ላይ ክንዱ ዓለም ወደ አንዱ ዓለም የሚያሻግር በስንፍና የማይጠረጠር የታመነ መርከብ ነው ። ብርሃን የፍጥረት ሁሉ ሕይወት ነው ፤ ብርሃን ሕይወት ላለው ሁሉ ምግብ ነው ። ብርሃን ሰው ሁሉ በጤና የሚሮጥበት ዕንቅፋትነት የሌለው ሰተት ያለ ሜዳ ነው ብርሃን ዕውርን የሚመራ መሰናከል የማያገኘው ጎበዝ ነው የብርሃንን ጥቅም ሁሉ ብንናገርስ አንድ መጽሐፍ እንኳ አይበቃውም ።

ጨለማም ደግሞ የርሱ ተቃዋሚ ነውና ልዩ ልዩ የሆነ ቅጣትና ውርደትን ሞትንም የሚያመጣ የፍጥረት ሁሉ ባላጋራ ነው ።

እነዚህም ሁለቱ አንድ አንድ ጌቶች ልጆች ወልደዋል እነዚሁም የብርሃን ልጅ ጥበብ ፤ የጨለማ ልጅ ድንቁርና ናቸው የነዚህንም መጠናቸውን የመረመረ ሰሎሞን የሥራቸውን ልዩነትና የሚሰማሙትም ከማን ጋራ እንደሆነ እንዲህ ሲል ይገልጻል «ብርሃን ከጨለማ እንዲበልጥ እንዲሁም ጥበብ ከድንቁርና እንድትበልጥ ለይቼ አወቅሁ» ይላል

እንኪያ በኛ ላይ ነግሦ ያለው ማናቸው ይሆን ። ቍስሉን የደበቀ መድኃኒቱን ይደብቃል የሚባለው ተረት እንዳይደርስብን ቍስላችንን ገልጠን እንናገረው ። ቍስሉን ገልጦ ለሚያሳይ ሰው መድኃኒቱ የተሰናዳበት ዘመን ነውና ። ቂጥኝ ቢደብቁት እንደ ተደበቀ አይቀርም ። ይልቁንም ስለ ተደበቀ አጥንት ሰብሮ ጅማት በጥሶ እንደማይለይ ርስተኛ በሰውነት ተጣብቆ ይኖራል ። መደበቅ ቀርቶ መድኃኒቱን ፈልገውለት ኖሮ ቢሆን ግን የውጭ ገላውን ብቻ አቍስሎ ይሔድ ነበር ።

አሁንም እውነትን እንግለጽ ካልንስ ጠላታችን ጨለማ ነው ። ቅንዓት ምቀኝነት የሚባል ባንዲራውን አቁሞ ፤ ዙፋኑን በመካከላችን ዘርግቶ ተቀምጦ ወንድሞቻችንና ረዳቶቻችንን እንደ ጠላት አስመስሎ እርስ በርሳችን ሲያጋጨን የሚኖር ይኸው ጨለማ ነው ።

ሥራ እየሠሩ አገራችንን በሚረዱ በነዚያ ብልሆች ሠራተኞች (በጠቢባን) ላይ የሚወርደውን መከራ በኛ ላይ እንደ ደረሰብን አድርገን እስኪ እንመልከተው ።

ሲሆን ሥራቸው ታይቶ ከነሱ በሥራው የበለጠ እንደ አውቀቱ መጠን የሚገባ ምሥጋናና ከፍ ያለ ማዕርግ ቢያገኝ የቀረውም ሁሉ እንደዚያ ለመሆን ሥራውን እያሰፋ ይሔድ ነበር ።

ይኸውም ሁኖ ምሥጋና በማግኘት ፈንታ ስድብና ዱላ ሲመገቡ ይኖራሉ ። እንዴት ያለ ግፍ ነው ። ይህ ግፍ ፍጹም የግፍ ግፍ ነው ። ይህን የምናየውን መሬት አርሰን ቆፍረን የምንበላበት እንኳ ከነሱ በተገኘው መሳሪያ ነው እንጂ ጥርሳችንን መሳሪያ አድርገን እንዳች ሥራ ለመሥራት እንደማንችል የታወቀ ነገር ነው ።

ያደረጉልንን እርዳታቸውንና ሙያቸውን አይተን በሙሉ ልቡናችን እንዳንወዳቸው የሚጋርደን ያ ክፉ መንፈስ ጥርጣሬን አሳድሮ ወንድሞቻችንን እንደ ባላጋራ አስመስሎ የሚያሳይ ጨለማ መሆኑን ልብ እናድርገው ።

እስቲ በብርሃን እየተመለከትህ ጥቂት እይ ። ሰው ጅብ ይሆናል ማለት እንዴት ያለ ጨለማ ይመስልሃል ። አንድ አንዶቹስ ሰዎች ደንጊያ እንቅፋት ሆኖ የመታቸው እንደሆነ ቡዳ ነው እያሉ ተመልሰው ደንጊያውን ይደበድቡታል ። እስቲ የጨለማውን ኃይል እይ ። ዓይን ያለው ሰው ደንጊያው ደንጊያ እንደሆነ መለየት ያቅተውን ። እንደዚህ ያለውንስ ነገር ማድረግ ፈጣሪውን እንደ መሳደብ ያለ ነው ።

እግዚአብሔርም ፍጥረት ሁሉ እንደተፈጠረበት ሊኖር አድርጎ ፈጠረው እንጂ እንደፈቀደው ወደ ብዙ ባሕርያት ሊለወጥ ሥልጣን አልሰጠውም ። አያሌ ደፋሮች ግን ጅብ ሙቶ አግኝተን ቀለበት በጆሮው ላይ አየንበት ብለው ውሸታቸውን ይለቃሉ ። ምናልባት የሚኖረው በጫካ ነውና ከወንድሞቹ ጋራ

እየተጣላ እንደውሻ ዦሮው ተበስቶ ይሆናል ። ቀለበት አድርጎ ትንሽልማቱ አገኘነው ማለት ግን በውነት ፊት ሊቆም የማይችል ቅሰኑፍ ውሸት ነውና የዕውቀትን መብራት አብርተህ እየው እንጂ ይሆናል ብለህ አትመነው ።

ይኸንንም ለመመርመር ብዙ ድካም አያስፈልግም፤በሲሶ ዓይን የሚታይ ቀላል ነገር ነው ። ነገር ግን አንድ የሚከብድ ነገር አለ ይኸውም ክፉ መንፈስ ሥራው ሰውን ለመጉዳት ነውና የጨለማ ንጉሥ ስለሆነ ተደብቆ መጥቶ የሰውን ስም እየጠራ እኔ እገሌ ነኝ እያለ ሰውን ከሰው ያጣላል ። ሰውም ይኸንን ነገር ሲሰማ እውነት ይመስለዋል ። ይልቁንም መንፈስ ነውና በየአገሩ የሚደረገውን የሚጠረጠረውንና የማይጠረጠረውን ያውቃልና እገሌን የገደልሁ እኔ ነኝ፤እገሌንም ያሳመምሁ እኔ እገሌ ነኝ እያለ የሚጠረጠሩትን ምስኪኖች ብልሆች የሕዝብ ረዳቶች የሆኑ የሠራተኞችን ስም ይጠራል ። መቼም የክፉ መንፈስ ፈቃዱ ሰውን እርስ በርሱ ለማፋጀት ነውና አንዱ ወንድሜን ገደለብኝ አንዱም ዘመዴን በላብኝ እያለ ጥርጣሬውን በመግደል እንዲገልጠው ያደርገዋል ። እንደዚህ እየሆኑ የሚያልቁ የኢትዮጵያ ሰዎች ስንትና ስንት ናቸው እዩ ፍጹም ዕውር የሆነ አንድ ሰው በክፉ መንፈስ ጠብ ክርክር ነፍስ መግደል በሆነ ሥራ ተመርቶ ዓይን ያላቸውን እነዚህን ማጥፋቱ እንዴት ያሳዝናል።እነዚህን ሰዎች የጎዳ የኢትዮጵያን ዓይን እንደጎዳ አድርጎ ማየት ነው።እነርሱ ግን ዕውቀት በሌላቸው በነዚህ እጅ በጭንቅ ተይዘው ሳሉ የብርሃን ተስፋ ብቅ እስኪልላቸው ድረስ እስካሁን መገኘታቸው ይገርማል ልናመሰግናቸውም ይገባናል ።

አሁንም መንግሥታችን የጥበብ ሥራ ሲሠሩ ያያቸውን ሰዎች ሊያቀርባቸውና ሊረዳቸው በመጀመሩ ትልቅ ተስፋ ነው ጥቅማቸው ታውቆ በግፍ ፈንታ በሥራቸው ክፍ የሚሉበት ጊዜ በቶሎ እንዲደርስላቸው አምላክ ይርዳቸው እኛም እንደሚገባ እንድናከብራቸው ዓይናችንን ይግለጽልን ። አሜን ።

ተወልደ ብርሃን መድኅን ።

በ፲፫ኛው ቍጥር ብርሃንና ሰላም የሕዝቡን አዋቆች አእምሮ ለማንቀሳቀስ አንድ ጥያቄ ጠይቆ ነበረ ፤ ጥያቄውንም [illegible] ማድረጉን አመልክቶ ነበረና ለዚሁ ምላሽ አያሌ ሰዎች ጽፈው ሰጥተውናል ። ከመጣልንም ቃል ላሁኑ የሚበቃ ያህል እናትማለን የቀረውንም ደግሞ በየተራው እናትምላችኋለን ።

የጥያቄ ምላሽ ።

ይድረስ ለብርሃንና ለሰላም ማተሚያ ቤት ። መጋቢት ፲፯ ቀን ፲፱፻፲፯ ዓመት የተጻፈ የብርሃንና ሰላም ጥያቄ ። በሀብታም አገር ውስጥ ስንኖር ድኆች መሆናችን ስለምንድነው የሚለው ጥያቄ ያስደንቃል ። ጠያቂው ምክንያቱን እያወቀው ጠይቋል ። እኔም ለዚሁ ቃል ምላሽ ከዚህ ቀጥሎ ጽፌአለሁ ።

፩ኛምሳሌ ። በሾላ ፍሬ ውስጥ የሚኖሩ ትንኞች በውጭ ታላቅ ብርሃን መኖሩን አያውቁም። በሾላው ውስጥ ያለው ጭላንጭል ብቻ የሚበቃ ይመስላቸዋል ። እኛም የኢትዮጵያ ልጆች በውጭ ታላቅ ሀብት መኖሩን አላሰብንም ይህ ያለንበት ንብረታችን የሌሎችን ንብረት የሚበልጥ መስሎ ይታየናል ባውሮፓ ያለውን ሀብት ከሀብታችን ጋራ ብንመዝነው ምንም እሚዛን የሚገባ አንድ ነገር አናገኝም።

፪ኛ ። የሐገር ፍቅር ያለበት ሰው ሁሉ እውነት ይወዳልና ስለዚህ የውነተኛውን ነገር በግልጽ እጽፋለሁ ። የሀገሬ ልጆች በአእምሮአቸው የሚያውቁትን ባንደበታቸው መናገር በጆቻቸው መጻፍ ይቸግራቸዋል ። አንድ አንድም ሰው በአንደበቱ የሚናገር በጁ የሚጽፍ ቢኖር ሰሚና አድራጊ አለ መኖሩን አውቆ በሕሊናው ውስጥ ሲቃጠል ይኖራል የኢትዮጵያ ልጆች አገራችንን እንደ አውሮፓ ሀብታም ለማድረግ የማይቻል ይመስላቸዋል ነገር ግን ሰው ለመሥራት የማይችለው ነገር የለም። ባውሮፓ ያለው የሚያስደንቅ ሥራ ሁሉ በሰው አሳብ የተሠራ ነው ።

፫ኛ ። ብርሃንና ሰላም የኢትዮጵያን አስተዳደር ኑሮዋን ተመልክቶ ይህንን ጥያቄ መጠየቁ ኢትዮጵያ በዚሁ ኑሮዋ ብትዘገይ ከድህነቷ ይልቅ ሕይወቷም አይታመን ብሎ ያሰበ ይመስላል ።

፬ኛ ። የኢትዮጵያ ልጆች ድሆች የሆንበት ምክንያት ከዚህ ቀጥሎ በተጻፉ በጠላቶች ምክንያት ነው ። ጥበብ ፍቅር አንድነት ። ምክር ። መልካም ሥራ ። እነዚህ የቀኙ ሰልፈኞች ናቸው ። ደግም የግራው ሰልፈኞች ። ድንቁርና ። ምቀኝነት ። መለያየት ። አለመስማማት።ስንፍና ። ባንድ ወገን ሁነው። ውጊው እጅግ ብርቱ ሆነ ። ኢትዮጵያም በነዚህ በሁለቱ ሰልፎች በኃይላቸው ባመጋጨታቸውም መከከል ተጨቁና ከሁለት ኃይል መከከል የተቀመጠች ይመስላል ።

፭ኛ ምሳሌ ። በምቀኝነት ሀረግ ተተብትበ የወደቀ ሰው ሀረጉን በጣጥሶ ከልተነሳ ከፀላቶቹ ለማምለጥ አይቻልም በወጥመድም የተያዘ ወጥመዱን ካልበጠሰ ሕይወቱ ተስፋ የላትም።

፮ኛ ። ግብዝነትን ልማድን የሚያስፈራ ጉዳት እንዲከተላቸው እርግጥ ነው ። ጌታም ተጠበቁ ከፈሪሳውያን እርሾ እርሱም ግብዝነት ። ብሎ አስተምሮአል ።

፯ኛ ። የሰልፉ ። ድል ገና ለማንም እንደሆነ አልታወቀም ነገር ግን የጥቅም ወገኖች ቆስለዋል ። ጥበብን ድንቁርና ወጋት። ፍቅርን ምቀኝነት አደከማት አንድነትን። መለያየት አቆሰላት። [illegible] ጨቆናት ። እኛም ለጥቅማችን ባንረዳ በድህነት ለመኖር የሚገባን ሆነ ።

፰ኛ ምሳሌ ። ዝንጀሮ መጫር መቆፈር ያውቃል ። እንደመቆፈሩ ዘር መዝራት ያውቅ ቢሆን እጅግ ባለፀጋ ይሆን ነበር ። እኛም የኢትዮጵያ ልጆች ልማድ እንዳይለወጥብን እንደመትጋታችን ለትምህርትና ለሥራ እንደዚሁ የምንጣጣር ቢሆን ሃብታሞች አዋቂዎች የሚባል ታላቁን ስም እንጠራበት ነበር ።

ለዝንጀሮ ሁለት የሚያስደንቁ ብልሃቶች አሉት መዠመሪያው ብልሃቱ ሰው የሚዘራውን መልቀም ። ነዶ መምዘዝ ነው ። ሁለተኛው ብልሃቱ በገደል በዋሻ ተጠግቶ ጨለማ በሆነ ጊዜ ገደሉ በራሴ ላይ ይወድቅብኛል ብሎ ፈርቶ ገደሉን በጭንቅላቱ ደግፎ ያድራል ይህንን ልማዱን ብልሃቱን እንደቁም ነገር እንደ ሃይማኖት አጥንቶት ይኖራል ። በማይጠቅም ልማድና በጥርጣሬ የሚኖር ሰው ለሀገሩ እንቅፋት ነው ። ያለጥቅም ይቀራል ።

፱ኛ ። አገሩን ወደተሻለው አነዋወር እየመራ እያሻሻለ እገለግላለሁ የሚል ሰው አይታጣም ነበር ። ከከፉ ልማድ አንዱን እንኳ የሚለውጥ ሰው ቢገኝ በቶሎ ይከሰሳል ። ይሽነን የሚመስል ሁሉ ድህነት ያደረጃል ።

፲ኛ፣ ግብዝን ሁለት ጊዜ እባብ ነከሰው ይባላል ። መጀመሯ ከጉድፍ ላይ ጋፊሮ ሲጋፍፍ፣ ሁለተኛ እዚሁ ቦታ ነከሰኝ እያለ ለዘመዶቹ ሲያሳይ ደገመው ።

፲፩ኛ፣ ኢትዮጵያ ግብዝነትንና ልማድን ከልናቀች ወደ ሀብት ከፍ ማለት ያቅታታል ።

፲፪ኛ ፤—ምሳሌ ፤ ልማድ ብርቱ ኃይለኛ እንደሆነ በድመት ላይ ይታያል ። አንድ ሰው ድመቱን አሠልጥኖ እሱ ሲጽፍ መብራት ይዛ ትቆም ነበር ። አንድ ተንኰለኛ ሰው አይጥ በወጥመድ ይዞ አመጣ ባለቤቱ ሲጽፍ ድመቷ መብራት ይዛ ቆማ ስታበራ አይጡን በመከከላቸው ለቀቀው ድመቷም መብራቱን ወርውራ አይጡን ልታሳድድ ሔደች ይባላል ። እኛም የኢትዮጵያ ሰዎች ምንም እጅግ ብንሠለጥን ለከፉ ልማዳችን እናደላለን ። ከዚህ የተነሳ ድህነት አይለቀንም ።

፲፫ኛ፤ ሀብትን ለመሻት ። እርሻን ንግድን ። ትምህርትን ። መከተል ይጠቅመን ነበር ። ትምህርትን እንዳንከተል ክርክር መንገዱን ዘግቶብናል ። እርሻን እንዳንከተል የምድራችን ፍሬ ለሆዳችን ብቻ ነው እንጂ ተሸጦ ገንዘብ እንዳይሆን ልማድና ስስት ይልቁኑ የማያርሱ ሰዎች ይከራከራሉ ። በዳር አገር ያሉት ሕዝቦችን አርሰው የምድራቸውን ፍሬ የሚሸጡበት አጥተው ቁረንጮና ቅጠል ተሸፍነው ይኖራሉ ። ላገሬ ገጋሮውም የሚሰጡት ግብር እያጡ ልጄ ዋሴ ሚስቴ ዋሴ ይላሉ ። እኛ በከተማ ውስጥ የምንኖረው ሕዝቦች ግን ነጭ ጨርቅ ለብሰን ሐር ለመደረብ እንችላለን ። ሥጋውን ቅቤውን ማሩን እህሉን ሁሉንም ከወንድሞቻችን ላይ በርካሽ ዋጋ እንድንወስድ ብለን በብርቱ ኃይል ተነሣንባቸው ። ንግድን እንዳንከተል በያውራጃው ያሉ አገረ ገጋሮች ንግድን ባይረዱት ወይም መንገድ ባይሠራ ንግድ ጥቅሙን አልሰጠም ። ገቢ የሌለበት ቤት ባዶ እንዲሆን የታወቀ ነው ።

፲፬ኛ ። እርሻ በየመቱ ጥቅሙን ይሰጣል ። በየጊዜው እየታረሰ ለሚገኝ እህል ተግቶ በማረስ ፋንታ እህል ሔደበት [illegible] መጀመሪያው ጉዳት ይህንን ሐሳባችንን በአዋቂዎች ሚዛን አስመዝነን ከሚዛኑ ቢጐል ያሳፍረናል ። ሁለተኛ አጼ ምኒልክ ለዚሁ ጥቅም ብለው ያሰሩልንን የምድር ባቡር ከመክሰስ ይልቅ ወደ ጅማ ወደ ሲዳሞ ወደ ጐጃም ወደ ሌቃ ወደ ወሎ ። ይህንኑ የመሰለ መንገድ መሥራት ያስፈልግ ነበረ ። የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድ ሥራ ለመሥራት ፋብሪካ የለውም የሚያስፈልገውን ዕቃ በየይነቱ ከውጭ ከውጭ የመጣውን ይገዛል ። ከመግዛት በቀር ፣ የሚሸጠው ሳይኖረው ጊዜ በግድ ድሀ ይሆናል ።

፲፭ኛ፣ ምሳሌ ተኩላ ጉሮሮዋን አጥንት ወጋትና ወደ ብልሐተኛ ስትሄድ አሞራ በመንገድ አገኛት ወዴት ትሄጃለሽ ብሎ ጠየቃት ጉሮሮየን አጥንት ወግቶኝ የሚአወጣልኝ ብልሐተኛ እሻለሁ አለችው ። እኔ ባወጣልሽ ምን ትሰጭኛለሽ አላት ወርቅ እሰጥሃለሁ አለችው ። በዋጋ ተስማሙና በይ አፍሽን ክፈቺው አላት አፉዋን በከፈተች ጊዜ እራሱን እስከ ጉሮሮዋ አግብቶ አጥንቱን መንጥቆ አወጣላት ። በይ ዋጋየን ስጭኝ ቢላት አንተ ስንጣሪ አወጣህልኝ እኔም ያንተን እራስ አፌን አልፎ እጉሮሮዬ ከደረሰ በኋላ አወጣሁልህ ዋጋ የለህም አለችው

እኛም የኢትዮጵያ ልጆች አዋቂ የሆነ አገሩን የሚወድ ይህንን ነገር ይመዝነዋል ። ለውጭ አገሮች የኢትዮጵያ ንግድ ቢቀር ጉዳታቸው ትንሽ ነው ። ከንድ ቤርሚል ወሀ አንድ መለኪያ ቢቀዱለት አንድ ግራም አይጐልም ። አንድ መለኪያም ቢጨምሩበት አንድ ግራም አይሞላም ። ኢትዮጵያ ግን የምድሯን ፍሬ ሸጣ የሚያስፈልጋትን ካልገዛች ከድህነት እርነት ለመውጣት እንደምን ይቻላታል ። እኛ እህል አንሸጥም እንደምንለው የውጭ ሰዎች ዕቃችንን ለናንተ አንሸጥም ቢሉን ጉዳታችን የታወቀ ነው ። አሁን እንኳን ዕቃቸውን ስለ አስወደዱ በግድ እጥፍ ዋጋ እንከፍላለን ። ይህነን አለማወቅ እጅግ ይገርማል ። ኢትዮጵያ ከሁሉ በፊት የቆየች መንግሥት በረማመዷ ሕፃን ትመስላለች ።

፲፮ኛ የኢትዮጵያ ሰዎች አገራቸውን እንደ ቀድሞው ዘመን ። ልማድ እንድትኖር የሚወዱ አይታጡም ። የቀድሞ ልማድ የማይጠቅም መሆኑን እንኳን አእምሮ ያለው የሰው ልጅ ። ተኩላ እንኳን ልማዷን አሻሽላለች ። የቀድሞ ዘመን ተኩላ የጣዝማ ጉድጓድ ባገኘች ጊዜ ከደስታዋ የተነሣ ግራና ቀኝ ስትቦርቅ የጣዝማው ጉድጓድ ይጠፋባት ነበር ፤ ባሁኑ ዘመን ግን ተኩላ የጣዝማ ጉድጓድ ባገኘች ጊዜ ። አፉዋን ተጉድጓዱ ተክላ በፊት እግሯ ረግጣ መቦረቁም እንዳይቀርባት በኋላ እግሯ ፊናጥ ፊናጥ እያለች ደስታዋን በጨረሰች ጊዜ ማሩን አውጥታ ትበላለች ።

፲፯ኛ ። ግርማዊት መጀመሪያይቱ ዘውዲቱ ሥዩምተ እግዚአብሔር ንግሥተ ነገሥታት ዘኢትዮጵያ ። ንግሥተ አዜብ የሰሎሞንን ጥበብ ለመረዳት ብላ እንደሄደች ሰምተዋል ። ወደ አውሮፓ ሄደው ጥበብን ለማየት እንዳይሹ እድላቸው ጥበብን እስከ ቤታቸው ድረስ አመጣላቸው ለኢትዮጵያ እንግዳ የሆነችውን ጥበብን ተቀብለው ልማዳችንን አሻሽለው በልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን መሪነት ኢትዮጵያን ከብርሃንና ከሰላም አገናኝተው ከድህነት ባርነት ወደ ነፃነት ይስቧታል [illegible] ነፃነት የወጣ የከበረ መንግሥት ማነው ። የኛ ድህነት በንሠራ በንነግድ ። በንማር ይመስለኛል ። በዚሁ በቀድሞው ልማዳችን ከዘገየን ከድህነት የበለጠ ጉዳት እንዲከተለን አውቀነዋል ።

ነጋድራስ ደስታ ምትኬ ።

የዕውቀት መዘርጋት ።

እስከሁን ድረስ ያገራችን ሕዝብ ወደ ቤተ ክርስቲያን ለጸሎት በሔደ ጊዜ ከቅዱሳት መጻሕፍት ቃል አንዲት ቊጥር እንኳ በቋንቋው በአማርኛ የሚያሰማው እያጣ እንዲያው መመለሱ በጣም ያሳዝን ነበረ ። ይኸም ሲሆን ካህናቱ ጸሎት ማድረጋቸውና ከቅዱሳት መጻሕፍት ብዙ ንባብ ማንበባቸው አልቀረም ፤ ነገር ግን የሚጸልዩትና የሚያነቡት ሕዝብ በማያውቀው ቋንቋ በግዕዝ ነው እንጂ ያንን ወደ አማርኛ መልሰው በቋንቋው አይነግሩትምና ስለዚህ የቃላቸውንመጐ—

ረምረም ብቻ ሰምቶ ይመለስ ነበረ ። አሁን ለአንድ ሰው በማይሰማው ቋንቋ ቢነግሩት የፍቅርና የጠብ የርግማንና የምርቃን እንደ ሆነ መለየቱ ያቅተዋል ። እንደዚሁም ሁሉ ግዕዝ በሚያውቁት ሰዎች ዘንድ እጅግ የተከናወነ የተዘጋጀ ቋንቋ ነው ። ነገር ግን ላልተማረውና ላላወቀው ሰው በግዕዝ ቢነግሩት ጨለማ መስሎ ይታየዋል።

አሁንም የምሥራች የዕውቀት ብርሃን እንደተዘረጋ ምልክት አየን። ባለፈው ሰሞን ክቡር መልአከ ገነት ወልደ ሐና በአራዳ ጊዮርጊስ ደብር ላይ እሁድ ቀን ከቅዳሴ በኋላ ሕዝቡን ሰብስበው ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ያሳተሙትን ባለ ንባብና ባለ ትርጓሜ ቅዱስ ወንጌል አስመጥተው እያስነበቡ ለሕዝቡ ሲያሰሙት አረፈዱ ፤ ለወደፊትም በየሳምንቱ እንደ አንድ ምዕራፍ እንደሚያስነብቡ በጎ ፈቃዳቸውን አስታወቁ ። ሕዝቡም በሚያውቀው ቋንቋ የእግዚአብሔርን ቃል በመስማቱ ደስ ብሎት እያመሰገነ ወደ ቤቱ ተመለሰ

እንግዲህ የክህናቱና ያለቆቹ ሁሉ ዋና ሽም ክቡር መልአከ ገነት ወልደ ሐና የበጎ አብነት ከሆኑ የቀሩትም አለቆች ሁሉ እርሳቸውን አብነት አድርገው ሕዝባቸውን በመንፈሳዊ ጥቅም እንዲጠቅሙት እንመኛለን ተከተል አለቃህን ተመልከት አላማህን የሚባለውንም ተረት እንዳይዘነጉት እናሳስባቸዋለን ።

ከታይምስ ጋዜጣ ።

የጀርመን ሬፑብሊክ መጀመሪያ ፕሬዚዳንት ሙሴ ኤበርት የመሞቱን ነገር በተሌግራም ከመጣልን ወሬ አንድ ጊዜ አመልክተን ነበር። አሁን ከመጣልን ከታይምስ ጋዜጣ ያገኘነውን አዋጥተን ትንሽ አሰፋፍተን እንጽፋለን ።

የጀርመን መንግሥት በጣም በምታስፈራው ሰዓት ውስጥ ከፖሊቲክ ሰዎችዋ መካከል በብዙ መታመንና ብልህነት የሚያገለግላት ቻይ ሰው በማግኘቱዋ በጣም የታደለች ሁና ነበር የጀርመን መንግሥት በብርቱ ማዕበል ወዲህና ወዲያ ስትጋፋ በውስጧ ኤክስትሬሚስት የተባሉ ወገን ወደ ቦልሸቢዝም ሊያዘነብሏት ሲሉ ከመፈላለስ መካከል ያወጣት ሙሴ ኤበርት ነው

ፍሬድሪክ ኤበርት ዝቅ ካሉ ሰዎች በሃይድልቤርግ ከተማ እንደ ኤውሮፓ ቍጥር የካቲት ፬ ቀን በ፲፰፻፸፩ ዓ ም ተወልዶ በልደገቹ በዚያ አገር ባለው ተማሪ ቤት ቢማር አደገ ፲፬ ዓመት ሲሞላው ካንድ ኮርቻ ሰፊ ዘንድ የእጅ ጥበብ ሥራ ይማር ጀመረ ። ጥበቡን ከለመደ በኋላ ኮርቻ ሰፊ ሆኖ አገሩን ሲዞር ወደ ብሬሚን ደረሰ። በዚያ የሶስያሊስቶች ወገን ማኅበረተኛ ሆነና ሚስት አግብቶ ከዚያ ተቀመጠ ። ቈይቶም ያንድ ወገን አስተዳዳሪ ሆነ ። በ፲፰፻፺፬ ዓ ም የሶሲያሊስት ጋዜጣ ዋና ሠራተኛ ሆነና በዚያ ስድስት ዓመት ሠራ ከዚያ ወዲያ የብሬሚን የሶሲያሊስቶች ክፍል የምሥጢር ጸሐፊ (ሰክሬቴር) ሆነ ። በዚህ ጊዜ ሉካንዳ ከፈተና ከወገኑ ብዙ ሰዎች ይመጡለት ነበሩ ።

በ፲፱፻፲፫ ዓ ም ሶሲያሊስቶች የሙሴ ቤበልን አገልግሎት ስላጡት ኤበርት ቤበልን ወርሶ የሶሲያሊስቶች ፕሬዚዳንት ሆኖ ተመረጠ የኤውሮፓም ጦርነት በተነሣ ጊዜ ይህንን ሹመት ይዞ ነበር በጦርነቱም ውስጥ የተቻለውን ሁሉ ለማድረግ ተጣጣረ አንድ ልጁ ቢሞትበት ሁለተኛውን ልጁን ወደሚዋጉት ጭፍሮች ተመልሶ ጠንክሮ እንዲዋጋ መከረው ።

ፕሪንስ ማክስ አብ ባይን የግዛት ልጓምን በእጁ ከጨበጠ በኋላ ሶሲያሊስቶችን ከሥልጣን መከልከል እንደማይቻል ባየ ጊዜ ወደ ሸንጎው (ሻምብር) ሊገባ የጠራው ፊተኛ ሶሲያሊስት ኤበርት ነው ። እርሱ ግን ለራሱ እምቢ ብሎ ሙሴ ሺይድማንን ሌሎችንም ከወገኑ አቀረበ። ነገር ግን በጦርነቱ መጨረሻ የጀርመን መንግሥት ድል በሆነ ጊዜ ከጀርመን መንግሥት ውስጥ እኩሌታው ወደ ቦልሸቢዝም ሲያደሉ ዝም ብሎ ለማየት አልተቻለው ም ። የመንግሥትን አካሔድ ሊለውጡ የሚያስቡ (ሬቮሉሲዮኔር) ወገን ሐሳባቸውን ወደ ተገባ በሕግ ወደ ሚሔድ መስኖ ሊያቃናው አስቦ ከርሳቸው ጋራ ኪዳን ገባ። ወደ ሐሳቡ በሚያደርሰው መንገድ ላይ ግን ልዩ ልዩ የሆኑ ወገኖች ማንም ሊናገረው የማይችል ስንት መሰናክልና ስንት እንቅፋት ስንት ማገጃ ያደርጉበት ነበር። ስንት ጉባኤዎች እየተሰበሰቡ ይማከሩበትና ይከራከሩበት ነበር። በዚያች በምታስጨንቅ ሰዓት ኤበርት ካማካሮቹ ጋራ ሁኖ በኃይል ድል ሊያደርጋቸው ቈርጦ አደረገና ኖስክ የተባለ የርሱ ሰው መሪ ሆኖ ሶስት ሺ ሠራዊት ጠበንጃቸውን እየያዙ ተሰልፈው በበርሊን አደባባይ አለፉ።

ክርክሩ በቶሎ ቆመና ኤበርት የኋለኛ ሐሳቡን በፍጥነት ፈጸመ (ማለት) ሕዝቡን የጦር መሣሪያቸውን ነሣቸው ።

ተከራካሪዎቹም ሥልጣን ከእጃቸው እንዳመለጠ በተሰማቸው ጊዜ ኤበርትን ተሟገቱት ። በዌይማር ጉባኤ ሰብስበው ምላሽ እንዲሰጡዋቸው ጮሁ ። ኤበርትን ግን ከዚህ ወዲህ ለዋናው ጉባኤ እንጂ ለየቦታው ሰብሳቢዎች ምላሽ እንደማይሰጥ ተናገረ ። ይህች ቃል ሁናታቸውን ቈረጠች ።

ዋናው ጉባኤ በዌይማር ተሰብስቦና የካቲት ፲ ቀን የፕሬዚዳንት ማዕርግ ተጀመረና በመራጮች ብዛት ኤበርት ፕሬዚዳንት ሆኖ ተሾመ ። ሥራውንም ሲረከብ የድፍን ጀርመን ሕዝብ ወኪል እንጂ የወገኖቹ ብቻ መሪ እንደማይሆን ተናገረ ። ስለሆነ ግን በሶሲያሊስቶች መካከል ያደግሁ ነኝና እምነቴን ምንም ቢሆን አልደብቅም አለ ።

ከዚህ ወዲህ በሬፑብሊክ ውስጥ ምንም እንኳን በየጊዜው አምባጓሮ ቢነሣ ኤበርትና ማኅበረተኞቹ አሸነፉ ።

የሙሴ ኤበርትን ሥራ ሁሉ ከልክ ያለፈ ስጦታ ያለው ሰው ካልሆነ የሚፈጽመው የለም ሙሴ ኤበርት ሥራቸውን ሲጀምሩ ታውክ የነበረ የሕዝቡም አሳብ ጭምር ነው እንጂ መንግሥቱ ብቻ አይደለም እርሳቸው ግን ትእግሥት በሚያስፈልገው ጊዜ በትዕግሥት ፤ ኃይልና ጽኑ ፈቃድ በምታስፈልግ ሰዓት በዚያው እያደረጉ በብዙ ብልህነት አገራቸውን ከመፍለስ ስለ አዳኑዋት ስማቸው ሲታሰብ ይኖራል።

ክቡራን አንባቢዎቻችን ሆይ ፡ ሙሴ ኤበርት በሥራቸውና ለመንግሥታቸው በመርዳታቸው ዋና አብነት ሆነው በማናቸውም ጊዜ የማይፈርስ ሐውልት ለስማቸው አቁመው አለፉ። ለስማቸውም መታሰቢያ የሆነ ያገራቸውን መንግሥት በብዙ ትጋት በመርዳታቸውና ለሕዝቡም የሚጠቅም ሥራ በመስራታቸው ነው እንጂ ተሾመው ሲገዙ ስለመኖራቸው አይደለም ። ስላገሩ እየደከመ የሞተ ሰው ከድካሙ አረፈ እንጂ አልሞተም ።

በልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ።

መጀመሪያ ዓመት ፡ ቍጥር ፲፭ ።
1re ANNÉE № 15

ሐሙስ ሚያዝያ ፩ ቀን ፲፱፻፲፯ ዓ ም ።
JEUDI 9 AVRIL 1925

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን በገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

የጋዜጣው ዲሬክተር ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የራሱን ጉዳይ የሚያሳትም ሰው ዋጋውን እየከፈለ እናትምለታለን ።

ማመልከቻ ።

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ስላቆሙት ተማሪ ቤት መከፈት ከብዙ ጊዜ ጀምሮ እንናፍቅ ነበር ። አሁን ግን እንዲከፈት በመሆኑ እጅግ ደስ ብሎናል ።

ዳግመኛም ከተማሪ ቤቱ የሚገኘውን ፍሬ አይተን እንደዚሁ ደስ እንዲለን ተስፋ እናደርጋለን ።

አዲሱ ተማሪ ቤት የበለጠ ፍሬ እንዲያፈራ ፡ እርዳታንና ማነቃቃትን እንዲሰጥ ፍጹም ምኞት አለን ።

በየአውራጃውም ባለ በትልልቅ ከተማ ሁሉ ይህን የመሰለ ተማሪ ቤት ለማቆም እንዲጣጣሩ በየገሩ ላሉ አገረ ገዦዎች ሁሉ እናሳስባቸዋለን ።

ወደ ተማሪ ቤት የሚገቡ ልጆች በመብዛታቸው ልክ ወደ ግዞት ቤት የሚገቡ ዓመፀኞችና ቀጣፊዎች እያነሱ እንዲሔዱ እርግጥ ነው ።

ላገረ ገዦዎች የተማረ ሰው ቢበዛ ለመግዛት ይመቻቸዋል ያልተማረ ሕዝብ ከመግዛት የተማረ ሕዝብ መግዛት ይሻላልና

ስለ ተማሪ ቤቱም አኳኋን ። የሚከተለውን ማስታወቂያ መመልከት ነው ።

ማስታወቂያ ።

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ለኢትዮጵያ ልጆች ማሳደጊያና መማሪ እንዲሆን ማለፊያ ተማሪ ቤት ከሚያስፈልገው መሣሪ ጋራ እንደ ተሰናዳ ፯ን ሜዳ አጠገብ ሰርተዋል ፡ ይኸውም ተማሪ ቤት በሚያዝያ ፲፱ ቀን ይከፈትና ሥራው ይጀመራል ፡ ግን ከሁን ጀምሮ ተማሪ ቤቱን ለመክፈት እስከ ተቆረጠበት ቀን ድረስ ልጆቻቸውን በዚህ ተማሪ ቤት ለማግባት የሚፈልጉ የተማሪዎች አባት ወይም ሞግዚት ከእሁድና ከትልቅ በዓል ቀን በቀር ዘወትር ከጧቱ በ፩ ሰዓት እስከ ፫ ሰዓት በዚሁ ተማሪ ቤት ወደ እኔ እየመጡ ወይም ወረቀት እየጻፉ ለተማሪ ቤት የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ ቢጠይቁ እኔ ለተማሪ ቤት መግቢያ የሚያስፈልገውን ሁሉ አስታውቃለሁ ። ደግሞ ለዚህ ተማሪ ቤት ጥቂት ማስረጃ ብጽፍላችሁ ደግ ይመስለኛል ።

ልዑል አልጋ ወራሽ ይህን ተማሪ ቤት የከፈቱበት ምክንያት መገመሪ ለኢትዮጵያ ልጆች ሁሉ መማሪያ የሚሆን የሚበቃ ተማሪቤት ስለሌለ ነው ፡ ሁለተኛ ተማሪዎች ሌት ተቀን በዚሁ ተማሪ ቤት ኑዋሪ ሆነው በሥራቸው በምግባቸው ባካሄዳቸውም ሁሉ በሥራት ተጠብቀው ካልተማሩ ለጤናቸውም ለባሕርያቸውም ልክ አድርጎ ለማሳደግና ለማስተማር የማ ይቻል ስለ ሆነ ነው ፡ ግን እንደዚህ ባለ መንገድ ልጆችን ለማሳደግና ለማስተማር ብዙ ገንዘብ እንዲፈጅ የታወቀ ነው ፡ ነገር ግን ምንም ከማራው ቢበዛ ልዑል አልጋ ወራሽ ስለ ሀገራቸው ልጆች ጥቅም ሲሉ ለዚህ ሥራ የሚያስፈልገውን ገንዘብ ለመስጠት አልነፈጉም ፡ የገራችንን ልጆች ለጤናቸውና ለባሕርያቸው ለትምህርታቸውም [illegible] [illegible] እንደሌለ የታወቀ ነው ፡ አባት እናቶቻቸውም ስለራሳቸው ጉዳይና ደጅ ጥናት ሲሉ ልጆቻቸውን ባልሰለጠኑና አእምሮ በሌላቸው አሽከሮቻቸው እጅ እንዲጠበቁ በግድ ይሆንባቸዋል ስለዚህ ብዙ ጊዜ ልጆች ስለ ጤናቸው ይጎዳሉ ፡ አስተዳደጋቸውም ክፉ ስለሆነ ባለጌ ይሆናሉ ባሕሪያቸውም ክፉ ይሆናል መጠጥ ይለምዳሉ ክፉ ስድብ ይማራሉ ፡ ይዋሻሉ ቅጥፈት ይማራሉ ፡ ከዚህ በላይ ደግሞ ክፉ የዝሙት ሥራ በገርጌቻቸው እየሰሙ ዝሙት ይማራሉና በሕፃንነት እድሜያቸው እየተበላሹ ይቀራሉ ፡ ስለዚህ ልጆቻችን ጤና የሌላቸውና ባሕሪያቸው ክፉ ሁኖ በድንቁርና እንዳያድጉ ብለው ልዑል አልጋ ወራሽ ልጆች ኑዋሪ ተማሪ ሆነው የሚማሩበት ተማሪ ቤት ከፍተዋል በዚሁ ተማሪ ቤት ዘወትር የልጆችን ጤናና አካሔድ እየጠበቁ የሚያስተምሩ የተመረጡ አስተማሪዎች አድርገዋል ይኸ መቸም ዋና ትልቅ ነገር ነው ። ወደዚያውም ደግሞ የአውሮፓን ደህና ትምህርት እንዲማሩ ሁሉ ነገር ተሰናድቷል ፡

ስለዚህ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ልጆቻችን ደህና ትምርት እያገኙ ግማሻቸው መሐንዲስ ግማሻቸው ሐኪሞች እየሆኑ ሌላም ልዩ ልዩ የጥበብ ሥራ እየተማሩ ዛሬ የውጭ አገር ሰዎች በሀገራችን የሚሠሩልንን ሥራ ሁሉ ያገራችን ልጆች እንዲሠሩልን ተስፋ እናደርጋለን ።

ደግሞ ሌላ አንድ ነገር ላመልክታችሁ ። ምናልባት ያላስተዋሉ ሰዎች በዚህ ተማሪ ቤት የሚማሩ ልጆች ከሀገራችን የተለየ ሌላ ሃይማኖት ይማራሉ ብለው ያስቡ ይሆናል ፡ ግን በዚህ ተማሪ ቤት ያሉ የውጭ ሀገር አስተማሪዎች እንደ ደምባቸው ያንኑ የታዘዙትን የቋንቋና የሒሳብ ትምርት ብቻ ሊያስተምሩ እንጂ ፈጽመው የሃይማኖት ነገር እንዳያስተምሩ በጣም ተከልክለዋል ። ደግሞ በዚሁ ትምህርት ቤት ልጆችን ዘወትር ዳዊትና የሃይማኖት ትምህርት እንዲያስተምሩ ያገራችን መምሕራን ተሰናድተዋል ። ይኸንን እኔ በላይ የጻፍሁትን ነገር ሁሉ ከጥቂት ቀን በኋላ ተማሪ ቤቱ ሲከፈትና ሥራው ሲጀመር እናንተው ራሳችሁ ባይናችሁ አይታችሁ ነገሩን በጣም ትረዱታላችሁ በከንቱ ሌላ ሐሠተኞች ሰዎች የሚያወሩትን የሐሰት ወሬ ሰምታችሁ ነገሩን ሳታስረግጡ እውነት ነው ብላችሁ እንዳታምኑ ተስፋ አደርጋለሁ ።

በ፲፱፻፲፯ ዓመተ ምሕረት መጋቢት ፳፫ ቀን ።
ኃኪም ወርቅነህ ።

በ፲፬ ቁጥር ብርሃንና ሰላም ፡ የቀረውን የጥያቄ ምላሽ በሚመጣው ቁጥር እናትማለን ብለን ተስፋ ሰጥተን ነበርና የጥያቄው ምላሽ የሚከተለው ነው ።በትጋትና በቅንነት እንደ ተሰማቸው ልክ የዕውቀት ምላሽ የሰጡንን ሰዎች እናመሰግናቸዋለን ።

በጎ ሀሳባቸውን በብርሃንና ሰላም እንደዚህ የሚያስታውቁ ዕውቀት ያላቸው ሰዎች እየበዙ ስለሔዱ እጅግ ደስ ብሎናል ።

ዕውቀታቸውን በብርሃንና ሰላም ሊገልጹ የሚችሉ ብዙ ናቸውና ሀሳባቸውን በብርሃን ገልጸው ለሕዝባችን እንዲያስረዱት እንጂ ዝም ብለው ደብቀውት እንዳይቀሩ ተስፋ እናደርጋለን ።

ሰው በተቻለውና በተሰጠው መጠን በቃልም በሥራም መንግሥቱን ከገለገለ ሕዝቡን ከረዳ ዕዳ የለበትም ነፃ ነው ። እውነተ ፈሪሐ እግዚአብሔር ያላቸው በሥተም የተቀበሉትን (መክሊት) አይደብቁም ።

የጥያቄ ምላሽ።

ይድረስ ከአቶ ገብረ ክርስቶስ የልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ማተሚያ ቤት ዲሬክተር ።የፍቅር ሰላምታዬን አቀርባለሁ ። በ፲፫ኛ ቁጥር ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ ጥያቄ ፡ በኢትዮጵያ ተሸመው ከገበር ከሚሰበሰቡ መኳንንቶች በቀር በሥራቸው ወይም በንግዳቸው ሀብታሞች የሆኑ ጥቂቶች ናቸው ከሕዝባችን ነጋዴ ወይም ሠርቶ እንደ ፈረንጆች ኩባንያ አቁሞ ትልልቅ ነገር ቀርቶ ትኒኒሽ ነገር አለመጀመሩ በምን ምክንያት ነው የሚለውን ቃል ብመለከተው ጥልቅ የሆነ አሳቤ በዚህ ላይ ወደቀ ።ትልልቁ ነገር ቀርቶ አንዱ አንዱ ዋና የሆኑ ምክንያቶች እነዚህ ናቸው ። በኢትዮጵያ ክሉ ሕዝብ ይልቁንም መኳንንቱ ሁሉ ሊነግዱና ሊሰሩ ሳያስቡት አልቀሩም ነበር።ነገር ግን አንድነትና ፍቅር ጠፍተው ምቀኝነትና ተንኰል ስለ ሠለጠኑብን አንዱ ተነሥቶ የንግድን ነገር አስበ እሠራለሁ እነግዳለሁ ብሎ ሲጀምር እነዚሁ ምቀኝነትና ተንኰል ባንድነት ሆነው የመጡበት ሳይታወቅ በድንገት ይኸን የመሰለ መልካም አሳቡን ያጠፉብታል ፡ እሱም በዚሁ ነገር ተበሳጭቶ ይተወዋል ። ሲቸገረው ተቀምጦ ምንም ሳይሠራ በሰው ትከሻ ለመብላት ይመኛል ፡ ሌላውም ባልንጀራው ለከሌ ምን ሲበጀው አየሁት ማንስ ረዳው ከማሰናከል በቀር እያለ ምኞቱ እንደዚያው እንደ ወንድሙ ሆነ ።ስለዚህ የሚታወቁት ዋና ምክንያቶች እነዚህ ናቸው ፤ በስተቀረማ ተገበር አንቆ አስጨንቆ ከሚገኝ ብዙ ጌትነት ፤ ነግዶና ሠርቶ የሚገኘው ትኒሹም ቢሆን እንዲበልጥ የታወቀ አይደለምን ። ለምሳሌ በአውሮፓም ቢሆን በአሜሪካንም ቢሆን ብዙ ብዙ ኀብታሞች ባለ ብዙ ሚሊዮር አሉ ሲሉ የምንሰማው በንግድ ወይም በእርሻ ሌላም ፋብሪካ ይኸን የመሰለ ነገር ሁሉ እያቆሙ ነው እንጂ ኀብታቸው ከገበር ላይ በሚገኝ ገንዘብ ይኸን ያህል ለመክበር ይቻላልን ከንቱ ነው ። ያልሠራና ያልነገደ አለመክበሩን ይኸው ብቻ ያስረዳናል ። ግን ቢሆን ይህንን የምንሰማውን ሁሉ ለማድረግ ፍቅርና አንድነት ከሉ ብዙ ጊዜ ሳንቆይ እንደርስበታለን ። ይህንን ሁሉ ለመፈጸም ሙሉ የማይነቃነቅ ፈቃድ ካለ ይሆናል እርስ በርሳችን መስማማትና መፋቀር መንግሥታችንን መውደድና መርዳት ያስፈልገናል ። ይኸንን ካደረግን ዘንድ እግዚአብሔር ይረዳናል ለልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ይህንን ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ የዕውቀትና የሥልጣኔ ጎዳና የሚመሩንን ለኛ ለኢትዮጵያ ሕዝቦቻቸው ስለ አወጡልንና ስሙንም ብርሃንና ሰላም ብለው ስለ ሰየሙት ሙሉ የኢትዮጵያ ሕዝብ ባንድነት ሆኖ መጨረሻ የሌለው ምስጋና ሊያቀርብላቸው የተገባ ነው ። ብርሃንና ሰላምም እየሰፋና እየለመለመ ፍሬው እንዲያጠግበን ስል እመኛለሁ ።መጋቢት ፳፪ ቀን ፲፱፻፲፯ ዓመተ ምሕረት ።

ሊቀ መኳስ መኰንን ዋልቱ ።

፲፱፻፲፯ ዓ ም መጋቢት ፲ቀን በ፲፫ ቁጥር በ፶፪ ገጽ በብርሃንና ሰላም ስለ ተጻፈው ጥያቄ። ኢትዮጵያ በተፈጥሮዋ ሀብት ትመግበናለች እኛ ስለምን ሀብቱዋ ከኛ ተርፎ ወደ ውጭ እንዲገፋ አናደርግም በሀብታሚቱ አገር ውስጥ ተቀምጠንስ ድሆች መሆናችን ስለ ምንድር ነው ስለ ተባለው ምላሽ ። መጀመሪያ ለኛ እንደሚመስለን ሀብታችን ከሌላው ሕዝብ ሀብት የሚበልጥ ይመስለናል እንጂ በሀብት የሚበልጠን ሕዝብ ያለ አይመስለንም እዚሁ በጐረቤታችን እንኳ በምስር ጅግራፊያ እንደሚወራው ምስር በዓመት በዓመት ጥጥ ወደ ውጭ ሸጣ የምታገኘው ገንዘብ ፲፫ ሚልዮን ፮፲ ነው ፡ በብር ፶፩ ሚሊዮን ብር ነው ይላሉ ፤ ለኛ ግን ለዘወትርም ባገራችን ይህን ያህል ብር የለም ይባላል ። ያመት ገቢያችንም ከ፭ ሚሊዮን ብር አይበልጥም የኢትዮጵያ ሕዝብ ብንከፈል አላድ አላድ እንኳ አይደርሰንም የነአሜሪካ የነርፓማ ምን ይወራል ለምሳሌ በአንድ የእንግሊዝ ቅኝ አውስትራልያ በሚባል አገር ከአመት ገቢ ፪ ፫ ነገር ለምሳሌ እጽፋለሁ። የጠጕር ሸያጭ

ከ፺፰ ሚሊዮን ተኩል ጅኒ ይበልጣል በብር ፫፻፹፰ ሚሊዮን ብር ያብልጣል የስንዴ ሽያጭ ፳፪ ሚሊዮን ጅኒ ነው፤ በብር ፪፻፳ ሚሊዮን ነው፤ የትንባሆ ሽያጭ እንኳ ከ፩ ሚሊዮን ፳፻፺ ሺ ጅኒ ይበልጣል፤በብር ፲፰ ሚሊዮን ፱፻ ሺ ብር ነው ይኸን ይኸን ስንሰማው ገረመን የቀረው ወጭያቸውን ልክና ቁጥር የለውም በጋዜጣ ላይ ልንጽፈውም ይበዛል፤ ይህም ወሬ አይደለም ደረክቶሬ ከሚባለው ከንግድ መጽሐፍ የተጻፈ ነው እንጂ ትንንሹን ነገር ባመት ይህን በሚያህል ገንዘብ ባመት ባመት ይሸጣሉ ማለትን አሁን ብንሰማው ድህነታችን ታወቀን እንጂ ቀድሞስ ከሕዝብ ሁሉ የኛ ሀብት የበለጠ ይመስለን ነበረ፤ ይህም አውስትሬልያ የሚባል አገር አገሩ እንኳ ቢሰፋ ሕዝቡ የኢትዮጵያን ሕዝብ ግማሽ ይሆናል ይኸ ሁሉ ገንዘብ በነዚህ በጥቂቶች ሰዎች እጅ በተሠራ ሥራ ወደ አገራቸው ይገባል።ሁለተኛም ባገር እርሻና ንግድ ከብት ማርባት ሰፍቶ ያለልክ ከኛ ተርፎ ወደ ውጭ ወጥቶ አለመግፋቱ ስለ ምንድር ነው ስለተባለው ምላሽ፡ይህም ለኛ ጥቅም መሆኑን እስከ አሁን ገና አላወቅነውም ወጭ ነገር ለኛ ጉዳት የሆነን ይመስለናል እንጂ ። ግን ፩ ፩ ዕውቀት ያላቸው ሰዎች ከገር የሚወጣ ያገር ወጭ ላገር ጉዳት ከሆነ የውጭ አገር ሰዎች ባገራችን የሚገኘውን ሁሉ ገመድ ሲባን ሳይቀር አምጥተው የሚሸጡልን ለምንድር ነው እኛ እንድንጠቀም ለኛ ብለው ነዎይ? ሲሉን ብቻ ትክክል የሆነ ምላሽ እናጣለን ።

ከዛሬ ፳ዓመት በፊት ባቡር ገና በድሬዳዋ ሳለ ባቡር በመጣ ጊዜ ያገራችንን ሰንጋና እህል እየወሰደ ያስወድድብናል ተብሎ ይወራ ነበረ በዚህም ነገር ፩ቀን ከደጃዝማች ገብረ እግዚአብሔር ቤት ግብር ገብተን ስንበላ አንድ መኰንን በጨዋታ እንሥቶ ባቡር ሊመጣ ነው ይባላል በመጣም ጊዜ ሁሉን ነገር ያስወድዳል አሉ ክፉ ነገር መጣብን አላቸው፤እሳቸውም ባቡር ክፉ አይደለም መልክም መሻሪያ ነው አሉት፤እሱም መለሰና ባቡር በመጣ ጊዜ ፩ብሬ ፬ብር ወይም ፭ብር ያወጣል እህልም ፩ዳውላ ዋጋው ፲ብር ይሆናል ይባላል አላቸው ። እሳቸውም ይኸን እህልና በሬ አምጥተው የሚሸጡልን የውጭ አገር ሰዎች ናቸውን ወይስ እኛ ነን የምንሸጥላቸው ብለው ቢጠይቁት የሚሸጥማ የአገራችን ሕዝብ ነው ግን እኛ ለራሳችን ስንገዛው ዋጋው ይወደድብናል እንጂ አላቸው።እሳቸውም ለራስህ ብቻ ነው የምታስበው ይህ ድሀ ባይኖር ፬ብር ቢሆንስ ከየት አምጥተን እንገዛ ነበረ ግድ የለም ያገር ድሀ ፩ብሬ ፭ብር ተሸጦለት ገንዘብ ያግኝ እንጂ ለኛም እንደዚሁ እንደ ሀብቱ መጠን ይገብራል፤እኛም እንደ ዚሁ ብር እናገኛለን ይኸ ብዙ ይጠቅመናል እንጂ አይጐዳንም አሉ ። እኛም ለጊዜው ነገሩ አልመሰለንም ነበረ ዕውቀት ያላቸው ሰዎች ግን ከዛሬ ፳ዓመት በፊት ባቡር ገና ሳይመጣ ውጭ ነገር ጥቅም እንደ ሆነ ያውቁ ነበረ ለኛ ከገራችን የሚወጣ ነገር ድንጋይ እንኳ ቢሆን መውጣቱ የሚጐዳ ይመስለናል እንጂ በያመቱ የሚታረሰው የሚጠፋው እህል በያመቱ የሚወለደው የሚሞተው ከብት ተሸጦ ሄዶ ለዘላለም ኑዋሪ የሚሆነውን ገንዘብ ብር አምጥቶ እንዲጠቅመን አላወቅንም

ሶስተኛም ከኢትዮጵያ ሰዎች ምነው እንደ ሌላ ሕዝብ ነግደው አርሰው ወይም ኩፓኒያ አቁመው ሃብታም ያለመሆናቸው ስለተባለው ጥያቄ ምላሽ ባገራችን የስልጣኔ (ማለት) የሥራ መማርያ የትምሕርት ቤት ኮሌጅ ባለመኖሩ ነው ሰው ሳያውቅና ሳይማር እንዴት አድርጎ ሊሠራ ይችላል ኢትዮጵን በሚያህል በሌላ አገር ከትምሕርትና ከንባብ መማሪያ ተማሬ ቤት ሌላ ኮሌጅ ዩኒበርስቲ የሚባለው የሥራ የዕውቀት መማሪያ ተማሪ ቤቶች የሚቆጠሩ በሽህ ነው ይባላል።ለኛ ገና አንድ አንድ ኮሌጅ እንኳ የለንም የት በተማርነው እውቀትና ሥራ ኩፓኒያ አቁመን ሠርተን ሀብት እናግኝ የቀረው ለዚህ ነገር ምላሽ ብዙ ነው በሌላ ቀን እጽፋለሁ ።

ፊ ዴሬሳ ።

ስለ ሕዝብ ልማትና ጥፋት ።

አንድ ሕዝብ ቢለማም ቢጠፋም በገዛ ፈቃዱ ነው እንጂ ባንድ ሰው ፈቃድ ለመዳን ወይም ለመጥፋት አይችልም ስለዚህ ለሚመጣው ጥፋት ሁሉ አላፊውን አንድ ሰው ለማድረግ የማይገባ መሆኑን ብርሃን ይመሰክራል ።

ዕውቀት እውነትን ስትፈልግ በብዙ ጎዳና ላይ ትገኛለች ነገሩ ሳይገባት ቢቀር ድንቁርና ነው ። በነገሩ ላይ ብታወላውል ጥርጣሬ ነው ። ነገሩን በትክክል ሳትረዳ ብትሰራ የሐሳቧን አደረገች ። ከምትከደው ነገር የምታምንበት ወገን ነገር ያየለ እንደሆነ ምንአልባት ይሆናል በማለት ትኖራለች ነገሩ እየገባት አልቀበልም ብትል በጥፋት መንገድ ላይ ትገኛለች ። ነገሩ በትክክል ገብቷት እውነትን ብትከተል በብርሃን ጎዳና ላይ ትሄዳለች ስለዚህ መሳሳት በሰው ባሕርይ ያለ ነው የስሕተትን ጎዳና እየተረዱ በዚያው ላይ መጠንከር የጋኔን ሥራ ነው ።

በብርሃን የሚኖሩ ሕዝቦች እንደተቻላቸው ያህል ከስሕተት ለማምለጥ ዕውቀት የምትታዘዝበትን የቀናውን መንገድ ፈልገው ከመጨረሻ መደባቸው እውነት ከምትባል ላይ ይደርሳሉ ። በተቀረ የመሪዎቻቸውን መልክም ምክር የጣሱ የስሕተትን ጎዳና እየተረዱ በጥንት ልማዳቸው ላይ የጠነከሩ ሕዝቦች ካንድ ቀን ቅጣት አያመልጡም፤ የእስራኤልን ሕዝብ መመልከት ነው ከክርስቶስ የሚበልጥ ዓለምን ለማዳን የመጣ የለም ነበር፤ የእስራኤል ሕዝብ ግን ለመዳን ፈቃድ ስለ አልነበረው ጠፋ ። ኢየሩሳሌም ኢየሩሳሌም ዶሮ ጫጩቷን በክንፏ ውስጥ እንደምትሰበስብ ልጆችሽን ለመሰብሰብ ፈልጌ ነበር ነገር ግን ፈቃድሽ አልሆነም አለ፤ ክርስቶስ በተናገረ በ፵ኛው ዓመት የሮማ ንጉሥ ልጅ በኀይለኛው ሠራዊት ከተማዋን ከበ ድንጋይ በድንጋይ ላይ እስኪጠፋ የሕዝቡ ደም በመንገድ ላይ እንደ ጎርፍ እስኪፈስ ድረስ አረዳቸው በገዛ ጥቅሙ የሚቀና በገዛ ጥቅሙ ላይ ተንኰል የሚአስብ ሕዝብ ምን ይመስላችኋል ይህ የገበሬ ጥቅም ነው ስለ ዚህ ወታደር ተመቀኝ ይህ የወታደር ጥቅም ነው ስለዚህ ገበሬ ተመቀኝ እንዳይባል የሕዝብ ጥቅም ሁሉ የተሣሠረ ነው ባላገሩ ካልበለጠገ የወታደሩ ትዳር መጥፋቱ ነው ኑሮው በባላገሩ ላይ ስለሆነ የመንግሥቱም ኃይልና ብልጥግና የሕዝቡ ኃብት ሲበዛ ነው ።

ወደ ውጭ አገር ብዙ እህል በመውጣቱ ምክንያት የተነሳ በገቢያው እህል ጠፋ እያሉ ሰዎች ያወራሉ በትክክል

መሠረት የሌለው ነገር ከማውራት አስቀድሞ ነገሩን መርምሮ የታሰበውን ነገር መናገር ለተናጋሪውም ለሰሚውም እጅግ ደስ ያሰኛል ። በተቀረ በአንድ ሥራ ምክንያት የተገኘውን ጥፋት ፤ ለሌላው ጥፋት ላልተገኘበት ሥራ ያለምክንያቱ ምክንያት ቢሰጡት መሠረቱ ይፋለሳል ።

በብርሃንም ያሉ ሰዎች ነገሩን ታላቅ ስሕተት በመሆኑ ይረዱታል ። ቢበዛ ቢበዛ ባመት ከሁለትና ከሶስት ሺ. ዳውላ የበለጠ እህል ከሐዋሽ ወዲህ ማዶ ካለው አገር ውስጥ ወጥቶ አያውቅም ። እንደዚህ ከሆነ በአዲስ አበባ ገበያ እህል ምን አስወደደው? ብሎ መልከሙ ጠያቂ ቢጠይቅ ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ የአረቂ መሥዋዕት ስለሆነ ነው ብዬ እመልስለታለሁ ለምላሼም የሚያስረዳ መሠረት የሆነ ነገር እሰጠዋለሁ ።

በአዲስ አበባ ዙሪያ ፲፪ ቁጥር የአረቂ ማውጫ መኪኖች አሉ ከነዚህም ፫ቱ ትልልቆች ፬ቱ አንስተኞች ናቸው ። እነዚህም አሥራ ሁለቱ ድስት የተሰጣቸው ኃይል ቀጥሎ እንደተጻፈው ነው

ከትልልቆቹ አንዱ መኪና በቀን ፮ሺ. ኪሎ እህል ያነጥራል ከ፬ቱ አነስተኞች አንዱ በቀን ሺ.፭፻ ኪሎ እህል ያነጥራል ።

፫×፮ሺ.=፲፰ሺ.×በ፫፻=፭ሚ.፬፻ሺ.
፬×ሺ.፭፻=፮ሺ.×በ፫፻=፩ሚ.፰፻ሺ.
ድምር ፯ሚ.፪፻ሺ.

በንግድ መንገድ ደንብ ስለ ዕሁድና ስለቀሩትም በዓላት በዓመት ፫፻ ቀን ብቻ ይታሰባል ።

ማለት ፯ሚ.፪፻ሺ. ኪሎ ፸፪ሺ. ዳውላ ነው ከመቶ አስር ፯፻፳ሺ. ኪሎ አልኮል ይሰጣል ይልቁንም ለዚህ ሥራ ጤፍ ይፈለጋል ሌላው እህል ሁሉ ከመቶ ስምንት ሲወጣው ጤፍ እስከ ፲፪ ከመቶ ይወጣዋል ይህም ፰፻፷፬ሺ. ኪሎ አልኮል በሩብ የሚሸጥ አረቂ አንዱ ኪሎ ሶስት ጠርሙስ ሲወጣው ፪ሚ. ፭፻፺፪ሺ. ጠርሙስ ይሆናል ።

እንግዴህ ተመልከት የአገሬ ሰው ፸፪ሺ. ዳውላውን በ፪ ብ ፫ ሂሳብ ለ፻፵፬ሺ. ብር ይሸጥና ፪ሚ.፭፻፺፪ሺ.ውን ጠርሙስ አረቂ ጠርሙስ በአንድ ሩብ ሂሳብ በ፮፻፵፰ሺ. ብር ይገዛና ማለት የሸጠው እህል ሳይበቃው ቀርቶ ከቤቱ እንደገና በሬውን ፍየሉን በቅሎውን ፈረሱን አህያውን ሸጦ የቀረበትን ፭፻ ፬ሺ. ብር ዕዳ ይከፍልና የበሽታና የኃጢአት ምንጩን ተሸክሞ ደስ እያለው ወደ ጎጆው ይመለሳል ።

ይልቁንም የሚገርመው ባላገሩ ከቤቱ ሲነሣ አስቦ እህልም እንጨትም ሌላም ነገር ቢጭን ለአረቂ መግዣ ክፍንቱ በላይ ሳይለጥፍ አይመጣም የያዘውን ሸጦ ወደ አረቂ ቤት ገብቶ መጠጥ ከጀመረ በኋላ ጨዋታ ሲደራ የዚያ ክፍንት በላይ ለጥፎ ያመጣው ነገር ሺያጭ ገንዘብ ያልቅና በደስታ መኻከል ሳያውቀው አልነከም ብሎ ምሎ ያስቀመጠውን ገንዘብ መሐላውን አፍርሶ ይጠጣበታል። ፸፪ሺ. ዳውላ መርገዝ ሆኖ ከሚቃጠልበት አሥሩ ወይም ፳ሺ. ዳውላ ለንግድ ቢሔድ ለአገሩ ጥቅም ነበር ።

በሬ ሔደብን እያለ ይጮኻል ነገር ግን በአሥር ብር የሚሸጠውን በ፳ ብር ሸጦ ልብሱን ገዝቶ የተረፈውን ገንዘብ ወደ ቤቱ ይዞ ሲመለስ ደስ ይለዋል ። በዓመት ስንት በሬ ይወጣ ይመስላችኋል ፤ ሁለት ወይም ሶስት ሺህ በሬ ቢወጣ ነው ። ነገር ግን የሚወጣው ቆዳ ስንት ነው በዓመት ከኢትዮጵያ የሚወጣው ቆዳ ከ፭ ሚሊዮን ፯፻ሺ. ቁጥር አያንስም ።

ደግሞ ቅሪላና ማስ ጭልጌ ምንጣፍ ለሌላውም ሥራ ሁሉ የሚቀረው ሲታሰብ እስከ ፬፻ ሺ. ይሆናል ። እንደዚሁ ሲሆን የቆዳው ቁጥር ፮ ሚሊዮን ይደርሳል ፤ ይህንንም ቁጥር ሲመለከቱት ይህ ሁሉ ከብት በበሽታ ያለቀ ነው ወይስ ለምግብ ታርዶ ነው ብሎ ያስጠይቃል ። ደግሞ በምግብ ወይም በበሽታ ምክንያት መሆኑን ይህንን ያህል ከብት የሚያልቀው የሚያስረዳ መንገድ ይገኛል በዓመት በአዲስ አበባ ቄራ ላይ የሚታረደው ፲፬ሺ. በሬ ነው በቤተ መንግሥትና በየመኳንንቱ ቤት ለሠርግም ለተስካርም በማናቸውም ምክንያት የሚታረደው ፳፪ ሺ. በሬ ይሆናል በድምሩ ፀቄራና በከተማው የሚታረደው ዓርባ ሺህ በሬ ቢሆን ነው ። ደግሞ በአዲስ አበባ ከተማ ሂሳብ በኢትዮጵያ በዓመት የሚታረደው ከብት ቢታሰብ ከ፯፻ ሺ. አይበልጥም ይሁንና አንድ ሚሊዮን እንበል ፤ አንዱ ሚሊዮን በበሽታ ማለቁ ነው ። አንድ ሚሊዮን ቆዳ አንዱ በ፬ ብር ሂሳብ ፬ ሚሊዮን ብር ይሸጣል ። አንድ ሚሊዮን በሬ አንዱ በ፲፰ ብር ሂሳብ ፲፰ሚሊዮን ብር ይሸጣል የሕዝቡ ትርፍ ፲፬ ሚሊዮን ብር በከንቱ ጠፋ ፤ አንድ ሚሊዮን ቆዳ ፬፻ ሺ. ፈረሲላ ይወጣዋል ። በአምስት ብር ሂሳብ እንደ ጉምሩክ ደንብ ዋጋው ሁለት ሚሊዮን ብር ይሆናል ቀረጡ ፪፻ ሺ. ብር ግን አንድ ሚሊዮን በሬ በ፳ ብር ሂሳብ ቀረጡ አምስት ሚሊዮን ብር ነው ፤ ፬ ሚሊዮን ፰፻ ሺ. ብር ለመንግሥቱ ጥፋት ነው ሁሉም ይቅርና ከመቶ አንድ አሥር ሺህ በሬ ብቻ ስለንግድ በዓመት ይውጣ ፱፻፺ውን ሺ. በሽታ ይፍጀው። እንግዴህ የሚጠቅመንንና የሚጎዳንን ነገር ልብ እናድርግ ።

የአዲስ አበባ ጉምሩክ ዲሬክተር
ገብረ እግዚአብሔር ።

ስለ ብርሃንና ሰላም የምሥጋና ቃል ለምትጽፉልን ለኛም ሰላምታ ለምትልኩልን ሰዎች ለሁሉም እያንዳንዳችሁ ለመጻፍ ጊዜ አናገኝምና ለሁሉም ባንድነት የማክበር ምሥጋናችንንና ሰላምታችንን በብርሃንና ሰላም ልከንላችኋል ።

ከኢጣሊያ መንግሥት ሌጋሲዮን በቴሌግራም የመጣ ቃል ።

የመጋቢት ፲ ቀን የለት ወሬ

ሎንድር ሎርድ ኩርዞን ሙተዋል ።

አስመራ የኮሎኒ ምኒስቴር ስጦታ የሆነው ያዲሱ ቤተ ክርስቲያን ምርቃን በትልቅ አገባብ ደወሎች እየተደወሉ ተፈጸመ።

ዲኖባ በንጉሥ ባቡር የእንግሊዝ ንጉሥና ንግሥት ከተከታዮቻቸው ጋራ ትናንትና መጡ ።

የመጋቢት ፲፱ቀን የለት ወሬ።

ናፖሊ የእንግሊዝ ንጉሥና ንግሥት ሙሴዎ ናሲዮናሌ (የሚታይ ነገር የተሰበሰበበት) የተባለውን ሥፍራ ሔደው አዩ ።

የመጋቢት ፳፫ቀን የለት ወሬ ።

ክርዚታ የእንግሊዝ ንግሥት ፤ የቤተ መንግሥትን ሬጂዮ ፓርክ ሔደው አዩ ።

የመጋቢት ፳፬ ቀን የለት ወሬ

ናፖሊ የእንግሊዝ ንጉሥና ንግሥት ወደ ሚሲና ለመሔድ ተነሡ ።

በልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ።

መጀመሪያ ዓመት ፡ ቁጥር ፲፮ ።
1re ANNÉE № 16

ሐሙስ ሚያዝያ ፰ ቀን ፡ ፲፱፻፲፯ ዓ ም ።
JEUDI 16 AVRIL 1925

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፫ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፬ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ ሲገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

የጋዜጣው ዲሬክተር ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የራሱን ጉዳይ የሚያሳትም ሰው ዋጋውን እየከፈለ እናትምለታለን ።

ስለ ሆሣዕና በዓል ።

ማዚያ ፬ቀን ግርማዊት ንግሥት ነገሥታት ዘውዲቱ ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን በብዙ ሠራዊት ታጅበው አራዳ ላይ ወደታነጸው ወደ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ሔደው ነበር።በዚህም ቤተ ክርስቲያን ስለ ሆሣዕና ክብር የሚደረገውን የተዕዱኖ ሥርዓት አኳኋን አይተው ተመለሱ ። ብፁዕ ዕጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስም ለበዓሉ የሚገባ ስብከት ሰበኩ ።

መንፈሳዊ መታሰቢያ በያመቱ ።

በገራችን በኢትዮጵያ ከሆሣዕና ማግሥት ከሰኞ ጀምሮ እስከ ፋሲካ ያለው የጌታችንን ሕማም ሞት የምናስብበት የሕማማት በዓል ይባላል ። በዚሁም ሰሞን ክህናቱ ሕዝቡ አፍአዊ ሥራን ትተው እየሰገዱና እየጸለዩ በውሳጣዊ ሥራ ወደ እግበማድረግ የፈጣሪዋን መታሰቢያ ሳታጠፋ ትኖራለች ።

ጸሎተ ሐሙስ ።

፩ኛ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያት የትሕትናን ሥራ ማስተማሩን የምናስብበት ቀን ነው ።

፪ኛ ። ቅዱስ ቍርባንን ለሐዲስ ኪዳን እንግዳ ሥርዓት አድርጎ ለሐዋርያት የሰጠበት ቀኗ ነው ።

፫ኛ ። የሚያሲዘው ይሁዳ ከመምጣቱ አስቀድሞ ወደ አባቱ ጸሎት የጸለየበት ቀን ነው ።ጸሎተ ሐሙስ የተባለውም በዚሁ ምክንያት ይመስላል።

የዚህ ሁሉ መታሰቢያ በገራችን ዛሬ ይደረጋል ።ትሕትናን ለማስተማር ጌታ የደቀ መዛሙርቱን እግር እንዳጠበ ዛሬ አባታችን አቡነ ማቴዎስ ወይም ቀሳውስቱ የሕዝቡን እግር እያጠቡ ትሕትናን ያስተምራሉ ። ቅዱስ ቍርባንንም ለማሳሰብ በዚህ ቀን ቍርባን ይደረጋል ። ጸሎትም ከጧት እስከ ማታ ድረስ ሲጸለይ እንዲውል በየቤተ ክርስቲያኑ ይታያል ።

የጾሙም ሰዓት በደረሰ ጊዜ ጉልባን የሚባል የንፍሮ ዓይነት ምግብ ይበላል።የዚህንም ምክንያት ያገራችን ሽማግሎች እንዲህ ብለው ይተርካሉ ።በቅዱስ ወንጌል እንደ ተጻፈ በጉን እንበላ ዘንድ አሰናዱ ብሎ ጌታ ሐዋርያትን አዝዞ ነበርና እንዳዘዛቸው አድርገው ሲበሉ ከናንተ አንዱ ባለጋራዬ ነው ብሎ ስለ ነገራቸው ቍርጥ የኃዘን ነገር ሰምተው ደንገጡ በልተውም ከጨረሱ በኋላ ነገ ስናንተ የሚሰጥ (የሚሰቀል) ሥጋዬ የሚፈስ ደሜ ይኸ ነው ብሎ ከሚበሉት ዳቦ ከሚጠጡት ወይን እንሥቶ ቅዱስ ቍርባንን ሰጣቸው ሐዋርያትም የጌታ ሞት ቍርጥ መሆኑን አውቀው በጣም አዝነው ነበር ።

የጸሎተ ሐሙስ ጉልባን (ንፍሮ) መበላቱም የኃዘን ምልክት ነው ይኸውም የአዝን ንፍሮ እንደማለት ነው ።በአገራችን ልማድ ሰው የሞተ እንደሆነ ቀብረው ሲመለሱ ንፍሮ በልተው እንዲሰነብቱ በዚህም ቀን የሚቀቀል ጉልባን በዚህ ልማድ የኃዘን ቀን መሆኑን ለማሳሰብ ነው ብለው [illegible] በጸሎት በስግደት ይዋላል ከዚህም ቀን ጀምሮ እስከ እሁድ ድረስ አክፍለት ያከፍላሉ ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሚያይ ዓይን ያለው ይይ ብሎናል።

አንድ ጊዜ በብርሃንና ሰላም የአገራችንን ሀብት እንደሚገፋ አለማድረጋችን ስለምንድር ነው የሚል ጥያቄ አግኝተናል።ይህ ጥያቄ ዕውቀት ያለው ሰው ሁሉ ሊመለከተው የሚገባ ኃይል ያለው የሚቀሰቅስ ጥያቄ ነው ።

አገራችን ወደፊት እንድትገፋ የሚመኙ ሰዎች ብዙ ስለሆኑ ይህች ጥያቄ የብዙዎችን ልብ እንድታነቃ ተስፋ እናደርጋለን ።

ለዚህ የሚሆን ምላሽ በጣም ብዙ ነው ። አንዱ እንዲህ ቢሆን ይሻል ነበር ብሎ መልካም አሳቡን ሲናገር፡አንዱ ደግሞ እንደዚህ ነው እንጂ ብሎ ያንን መልካም አሳብ ለማጥፋት የሚጣጣር ስለሆነ እንዳንቀሳቀስ የሚያደርገን የሚያፈዝ መርዝ

በያይነቱ ሞልቷል ። የዚህም መርገዝ ምንጩ፡ ያ በኢትዮጵያ ላይ በብርቱ ኃይል ሠልጥኖ ያለ ልማድ የሚባል አውሬ ነው ።

በላያችን ተጠምጥሞ አለቅም ያለን እንዴት ባለ አያይዝ ቢይዘን ነው ። እንዴት ያለ ሰው ነው፤ በእጅህ ያለውን ደንጊያ ጣልና ወርቅ እንስጥህ ቢሉት ፊት የያዝሁትን አለቅም ብሎ እምቢ የሚል ። እምቢ ሲል ያየነውሳ እንደሆን የዚህን ሰው ስሙን ማን ብለን እንጠራው ይሆን ።

ክፉ ልማድ ድል ሆነ የሚባልበትስ ቀን መቼ ይደርስ ይሆን ብልሁ የኢትዮጵያ ልጅ ዘሆን ገድሎ ከላይዋ ወጥቶ እንደሚፎክር ክፉ ልማድን ጥሎ ከላይዋ ወጥቶ የሚዘልባትና ጠላቶቹም ለመንጠቅ የተዘጋጀ ዓይናቸውን የሚያሹባት እለት መቼ ትሆን በለመዱት መንገድ ብቻ ለመሔድ የሚያስፈልገውስ ለዕውር ብቻ ነው እንጂ ዓይን ያላቸው ሰዎችስ ክፉና በጎውን ለይተው በተሻለው መንገድ ሊጓዙ ተፈቅዶላቸዋል ።

ነገርን ሁሉ መርምረን የተሻለውን እንፈልግ እንጅ ቀድሞ ባባቶቻችን እኮ አልነበረም አንበል ። አሁን ብንመለከት ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ በፊት ያልቆያቸውን ነገር ይጠቅማል ብለው ተማሪ ቤት ሆቴታል ሌላም በያይነቱ ባይጀምሩ ይሻል ኖሮአልን ። አሁን ያሉትስ ሥልጣን ያላቸው ሰዎች ፩ የነበረውን ሁለት፡ ሁለት የነበረውን አሥር ፡ ፲ የነበረውን መቶ ለማድረግ ካልተጣጣሩበት ሥልጣኔ እንዴት አድርጎ ይሰፋል ። የመጀመሪያ ሥራስ በሚያሰፉት ብልሆች ሰዎች ካልተገለጠ እንዴት አድርጎ ይሰፋል ። እስቲ በዓለም ሁሉ ያለውን እንመልከት በክፉ ልማድ ናጠከረ ሕዝብ ምንም ቢሆን ዕውቀቱን ያሰፋል ተብሎ አይጠረጠርም ልማድን እንግዛው እንጂ አይግዛን ። ሌላውስ ይቅርና በክፉ ልማድ ቀምበር ተጠምደው ከንቱነትን ሲሠሩ የሚውሉ ሰዎች ስንት ናቸው ሥራ መፍታትን ከኔጥ ቆጥረዉት እየለመኑ ሲበሉ የሚኖሩ ስንት ናቸው እሁንም ክፉ ልማድን የምናርቅበትን ኃይል ይስጠን ። በጎውንም ልማድ የምንመለከትበት ዓይናችንን ይክፈትልን ። ግርማዊት ንግሥታችንና ልዑል አልጋ ወራሻችን ከክቡሩ መኳንንቶቻቸው ጋራ በተባረከ አንድነት ሁነው ኢትዮጵያን ጋርደው የሚኖረውን ክፉ ልማድ የሚባለውን መጋረጃ በማጥሰው ጥለው አዲሱን ብርሃን እንዲያበሩልት እግዚአብሔር መሪያቸውና ብርሃናቸው ሁኖ ይርዳቸው አሜን ።

ተወልደ ብርሃን መድኅን ።

የጥያቄ ምላሽ ።

ኢትዮጵያ በተፈጥሮዋ ኃብታም ናት ከተፈጥሮዋ ባሕርይ በሚገኘው እኛን ልጆቹዋን ትመግበናለች እኛ ግን ከተፈጥሮዋ የሚገኘውን ሀብት አለማበርታታችንና አለ ማብዛታችን ከኛም ተርፎ ለውጭዎች እንደሚተርፍ አለ ማድረጋችን ስለምንድነው ብሎ የብርሃንና ሰላም ጋዜጣ ባለፈው ሳምንት ስለ ጠየቀው ጥያቄ ምላሹን በጭሩ ከዚህ በታች በተጻፉት ቃሎች በማክበር አመለክታለሁ ።

፩ኛ፡ ኢትዮጵያ ከሁሉ አስቀድማ ጥንታዊ እንደ ነበረች ታሪክ ይነግረናል ። ለሀብታምነቷም ቁጥርና ስፍር የለውም ። የውጭ ሰዎች እንኳ ጥቅሟንና ሀብቷን የመረመሩ በኢትዮጵያ ውስጥ ፴ ሚሊዮን የሚሆኑ ማዕድኖች (ሚኒራልስ) አሉባት ብለው ይመሰክሩላታል ።

፪ኛ፤ እኛ የኢትዮጵያ ልጆች የኢትዮጵያን ሀብትና ጥቅም የምናገኝበትና የምንመረምርበት የሚበቃ የትምሕርት ቤት ስለሌለን ከነዚህ ፴ ሚሊዮን ከሚሆኑ ማዕድኖች ከሺ አንድ እንኳ አይሆኑምና የምናውቃቸው ስለዚህ በኢትዮጵያ ከተፈጥሮዋ የሚገኘውን ሀብት ለማበርታትና ለማብዛት ይሳነናል

፫ኛ፤ በኢትዮጵያ ወንድም ከወንድሙ አንድነት ለማድረግና ለመስማማት ከተስማማም በኋላ የተስማማበትን ሥራ ሁሉ በትክክል ለመፈጸም ዕውቀትና ድፍረት ስለ አነሰ ሌላ የውጭ ሰው እየመጣ በኢትዮጵያ ሀብትና በረከት ጥቅም ካገኙ ወንድሞቹ ገንዘብ ይበደር ይነግድና ደሀው በልጥን በጥቂት ወራት ባለ ብዙ ሺ ብር ይሆንና ራሱን ረድቶ በሀገሩ ላሉት ደሆች ዘመዶቹ በሃዋላ ገንዘብ እየላከ ይረዳቸዋል ። እነዚያም የኢትዮጵያን ሀብትና የወድማቻቸውን ቸርነት እያደነቁ በተላከላቸው ገንዘብ ችግራቸውን ይወጡታል ። ይኸን ማለቴ ሰው የተቸገረውን ዘመዱን መርዳት አይገባም ለማለት አይደለም ለምሳሌ ማድረጌ ነው እንጂ ።

፬ኛ፤ በኢትዮጵያ አንዳንድ የተማረና የንግድም ሆነ የሌላ ሥራ የሚያውቅ ሰው ቢኖር በድህነት ምክንያት የተነሳ ያለውን ዕውቀቱን የሚያሰፋበት መንገድ የለውም ከነዚያም ከነበር ወይም በሌላ መንገድ ገንዘብ ያጠራቀሙትን ሰዎች እባካችሁ ገንዘብ ስጡኝና ለናንተም አትርፌ ለኔም የለት እራት እንዲሆነኝ አብረን እንነግድ እኔ ዕውቀት ልሁናችሁ ፤ እናንተ ጉልበት ረዳት ሁኑኝ ቢላቸው ድህነቱን አይተው ከለማመናቸው የተነሳ ይስቁበታል ይከለክሉታል እንጂ እስቲ ፲ሺ ብር አለኝ ከሥሩ ሺ አንድ ሺ ብር ላበድረውና ሥራውንም የሚመለከትልኝ አንድ የታመነ ሰው ከርሱ ጋራ ላድርግና ለጊዜው ልፈትነው ከንድ ሺ ብር ቢጠፋ ሁሉም አይጠፋምና አልጐዳበትም ጥቅምም ጉዳትም ቢኖረው በጥቂት ወራት እረዳዋለሁ ብሎ አያስብምና እውቀት ያለው ደሀ ኢትዮጵያዊ ሥራ ሊሠራ አይችልም ። ደግሞ ሰው ምንም እውቀት ቢኖረው ገንዘብ ከልኖረውና ወይም በገንዘብ የሚረዳው ሰው ካላገኘ በዚህ ዓለም ሥራ መስራት እንደማይችል በሁላችን ዘንድ የታወቀ ሳይሆን አይቀርምና ገንዘብ ከማጣት የተነሳ ብዙ ያገር ጥቅም ከገር ልጅ አልፎ ለሌ

፭ኛ፤ እርሻ አርሰን ከብት አርብተን ራሳችንን ረድተን ለሌላ እንዲያልፍ ለማድረግ ብናስብ ብዙ እንቅፋት የሚሆኑ እስቸጋሪ ነገሮች ባገር አሉና በቶሎ ተስፋ አስቆርጠው ወታደር ለመሆን ወይም የመንግሥት አገልጋይ ለመሆንና ታላቅ ሹመት ለማግኘት ወይም ለፈረንጅ ለመቀጠር ያስመኛሉ ። አንዳንድ ጊዜም ለሌብነትና ለዳንዴነት ያሳስቡና ከክፉ ቅጣት ያደርሳሉ ከነዚህ አስቸጋሪ ከልኋቸው ነገሮችም አንዱ በዚያ በሚታረስበት አገር ውስጥ ያለ የሹማምንት ግፍ በሕዝቡ ላይ የሚደረገው ነው ። አርሼ አርብቼ ለራሴ ተጠቅሜ ለመንግሥት እገብራለሁ ያለ እንደሆነ ደሀው በሆነ ባልሆነ በጭቃ ሹም በምስለኔ በመልከኛ በሻለቃ ዋስ ጥራ ታሰር ተወረስ ። በስርሀስ ፍታ ነው እንጅ ተቀጣ የለብኝ እየተባለ ነገሩ በቶሎ ሳያልቅለት እየተጉላላ በከንቱ ጊዜውን ያበላሹበታል ። ይኸን ያልለመደ

ሰው እዳር ሆኖ በተመለከተ ጊዜ እጅግ አድርጎ ይፈራል እንጂ የኢትዮጵያን ሀብት ለማግኘት ከመከከላቸው ገብቶ ለማረስ ይቅርና ባገራቸው ውስጥ እንኳ ለመኖር አይመኙም ። ሁለተኛው ችግር በየገጠሩ ከብትና እርሻ ያለው ለራሱ ወተት ጠጥቶ እንጀራ ጠግቦ ያድር ይሆናል እንጂ ገበያ አውጥቶ ለብር ሸጦ ለራሱ ተጠቅሞ ለመንግሥቱ ግብር አያበረክትም አንዳንዱ ጋላ ወይም አማራ መቶ ፡ ሁለት መቶ ቁም እያንጋጋ አንድ ድልብ ሰንጋ ወይም አንድ ሽህር ሳምስት ሳሥር ብር ብሸጠው ምን ጥቅም አለኝ ይኸን ያህል ዓመት ለፍቼ ቀልቤ አርብቼ ሲል ሚስቱና ልጆቹ እሱው ራሱ እየተራቆቱ ይኖራሉ እህሳቸውም እንዲሁ ዋጋ የለሽ ሆኖ ይነቅዛል ባይነቅዝም ያመት ቀለባቸውን አርሰው መቸም አንሸጥ ብለው መሬታቸው እዳሪ እየሆነ ይቀራል ። እነዚህም ሰዎች እውነት አሳቸው ሰው በለፋበት ልፋት ትርፍና ጥቅም ካላገኘ ለማን ጥቅም ብሎ ያስባል ። መጀመሪያ ራሱን ረድቶ በኋላ ለቀሩት ያስባል ። በኢትዮጵያም እህል ቢወደድ መጀመሪያው ምክንያት ከዚህ በላይ ያልሁት ይሆናል ። ደግሞም ከሸማቹ አራሹ ይበዛልና ለጥቂቶች ተብሎ የብዙዎች ጥቅም ቢቀር በሀብታም አገር ውስጥ ተቀምጠን ደሀ የመሆናችን ምክንያት ይህ ይሆናል ።

፫ኛ ፡ እንግዲያውማ በቶሎ የሚደርሰውና የሚያከብረው ያገራችን ጥጡ እንኳ ዋጋ ቢኖረው እንደ ጐረቤቶቻችን ወደ ውጭ ቢላክ ብዙ ብር ቢያመጣ ሌላው ማዳድን እውቀት ተገኝቶለት እስኪታወቅ ድረስ በየበረሃው ገብተን እርሻውን ብናሳብደው ብዙ ጥቅም አግኝተን በከበርን ነበር ። ዛሬ እንዳናደርገው ለሚስቶቻችን ፈትል ብቻ ነውና የሚያስፈልገው ከባላገር ባንድ ብር ፯ አሞሌ መጎ እናስመዝናለን ። ያ እስቲፈተልና እስቲጨረስ ድረስ ብዙ ጊዜ ያስፈልጋል ። አለዚያም እርስ በርሱ የተባለውን ድርና ማግ ብንገዛው ያሉብሰናል ዋጋውም ከሁለት ብር አይበልጥምና በየጊዜው ገንዘባችን ለውጭ ሰው ይሆናል ። እኛም በረሃ ገብቶ ማረስ አያስፈልገንም መሬታችንም ሁሉጊዜ ጠፍ ይባላል ለመንግሥትም ሆነ ለሕዝብ ምንም ጥቅም አያመጣም ። ስለዚህ ሕዝባችን ነግዶ ወይም ሰርቶ አይጠቀምም ።

፬ኛ ፡ እህል ወደ ውጭ የሄደ እንደሆነ ሸማቹ ይራባል ይባላል ይልቅስ ለከተማው ሸማች እህሉ እንዳረከሰለት ተቱሰበ አንዳንዱ ቸርቻሪ ከገበሬ ተሻምቶ እየገዛ በቁልቢጥ ለተሙን ሲሸነሽነው እየታየ ዝም መባሉ ስለምንድነው ። ገበሬው እንዳመጣ ለከተማው ሰው በትክክሉ ቢሸጥ ምንም ችግር ባልነበረ ። ግን ድኃ አዳሪ በምን ትኑር ይባል ይሆናል ። ለድኃው ሲታሰብ በማያስፈልግ መንገድ ብዙ ከበርቴዎች በሸመታ ምክንያት ጥቂቶች ድሆች ሲያከስሯቸው ከበርቴዎቹ ድኃ ይሆኑ የለምን ። እነሱም በዚህ ሥራ የገቡ እንደሆነ ድኃው እየበዛ ይሄዳል ። ምናልባት እነዚህም ድኃ የሚመስሉ እህል የሚቸረችሩ ሰዎች ሁሉ ድሆች አይምሰሏችሁ እንዱ ሲጠቀም እያዩ እያምልጠን ነው እንጂ ባሎቻቸውና ልጆቻቸው በከተማው ልዩ ልዩ የሆነ ሥራ ገንዘብ የሚገኝበት አላቸው ። ሁሉ ደሆች አይደሉም ብዙም ብር በቤታቸው እንዲኖር የታወቀ ነው ። እህሉን ትተው በቅመማት ብቻ እንኳ ቢነግዱ ይበቃቸው ነበር ደግሞም ድኃ የሚኖርበት ይኸ ብቻ አይደለም ብዙ ሌላ መንገድ አለ ። ደግሞ ከዚህ በላይ እንዳልሁት መንግሥት የብዙ ሰው ጥቃት ነው እንጂ የሚጠብቀው የጥቂቶችን ጥቅም ብቻ አይደለም ። የጥቂቶቹን ጥቅም ብቻ የጠበቀ እንደሆነ ብዙዎች ይጐዱበታል ። ብዙዎችም ከተጐዱ ዘንዳ ለመንግሥትም ጉዳት ይሆናል ። መጋቢት ፳፩ ቀን ፲፱፻፲፯ ዓመተ ምሕረት ተጻፈ አዲስ አበባ ።

ተፈራ በልሁ ።

ስለ ብር ምንዛሪ ።

በብርሃንና ሰላም በቁጥር ፲፩ እንዳነበብነው ስለ ብር ምንዛሬ በመሐልቅ ሹሞቹ እንዲተጉበት የተጻፈ ማለፊያ ሐሳብ ቢፈጸም ስንት ድኃ ሕዝብ በአውራጃ ሁሉ በተጠቀመ ነበር ፤ ጥሬ ብርና መሐልቅ ያው አንድ ናቸው (ማለት ብር ነው) እንግዲያውስ አንድ ብር በመሐልቆች ስትመዘን (፳) ሽያ መሐልቅ ትመዘናለች በምን ምክንያት ነው ብር መርከሱ? መሐልቅስ መወደዱ ምናልባት ከመሐልቅ ማነስ እንደሆነ ብርን በመጠን መሐልቅ ቢያደርጉት በግድ ይመዘዘናል ወይም መሐልቅን የመሰለ በሌላ ነገር መንግሥት ቢያሰራ ሕዝቡ ጥቅሙን ነውና የሚፈልግ በቶሎ ይለምዳል መሐልቅ ይረሳል ይረክሳልም ። አሁን በቅርብ ቀን በሐረር ክፍል በጨርጨር አውራጃ የብር ምንዛሬ በመሐልቅ ሰባት ተኑስ ፤ ስምንት ተኑስ ፤ ዘጠኝ ተኑስ ፡ ኑሱም በጨው ነበር ፤ ባለ አንድ ብር ምስኪኖች ሁሉ ገበያ ውለው ወደየቤታቸው ሲመለሱ በልብሳቸው ጫፍ ጨውን እየቋጠሩ ይሄዳሉ ፤ ይህንን ጨው ለመሸከም የማይፈልጉ አንድ ብር ለመመንዘር ሲፈልጉ በግድ አለውዷታቸው ሁለት ብር መመንዘር ይሆንባቸዋል ወይም ሳይወዱ መሸታ ቤት ገብተው የኑሱን መጠጥ ይጠጣሉ (በዚሁ ምክንያት ይጨርሷት ይሆናል) ባለጨውም መሸቶበት በችኮላ ሲሄድ የቋጠረው ጨው ፈስቦት ከነ አፈሩ ሲያፍስ አይተናል ። አሁን ግን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ለድኃው ጉዳት አስበው ብዙ ቤሳ አስመጥተው ከአስበ ተፈሪ ግምጃ ቤት ለሕዝቡ በ፲፮ ሸረፍ ፡ ባንድ ብር (፴፪) ሰላሳ ሁለት ቤሳ እንዲሸረፍ አደረጉ [illegible] ነበር አሁን ግን እግምጃ ቤትም ቤሳውን ስለ መሐልቅ በ፲፮ ሸረፍ ከገንዘብ አግቢው መልሰው የሚቀበሉ ስለ ሆነ ሰው ሁሉ ለመደው ። ዛሬ የሚበልጠው የድኃው ጉዳይ በቤሳ ይፈጸማል ስለ ኑስ ጨው መቋጠር ቀረ ፤ ቤሳውን እኪስ መክተት ሆነ ፡ መሐልቅም እየረከሰ ቤሳው እየተወደደ ይሄድ ጀመረ እድሜ ለልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ።

እንድርያስ ። አስበ ተፈሪ ።

የከተማ አጠባበቅ ።

የአዲስ አበባ ከተማ ጠባቂዎች ክቡር ከንቲባ ነሲቡና ነጋድራስ አስታጥቄ ለከተማው ጽዳትና ለሕዝቡ ጤንነት ስለ አሰቡ ባለ ጤና ውሻ ያላችሁ ሰዎች ከጥራችሁ ግቢ እውሩና ቤታችሁን ይጠብቅ ፤ ወይም ባንገቱ ላይ በስማችሁ ምልክት

እድርጉለትና ጤና በሌላቸው ውሾች ከታዘዘው አደጋ እንዲሠወሩ አስበናል ። ከዚህ የተረፉ በየ መንገዱና በየ አደባባዩ የሚገኙ በሽተኞች ውሾች ግን ወደ አደጋ ይወድቃሉ ማለትን በማስታወቂያ ቢያስታውቁ እውነቱን በሐሰት መልክሙን በጥፋት እንደ ንግድ አድርገውት የሚለውጡ አንድ አንድ ሰዎች በከተማው ውስጥ አይታጡምና ይህንኑ ለሕዝብ ጤንነት የታሰበውን ወደ ጥፋት ቆጥረውት ከሌላም ነገር ጋራ እያይዘው ዛሬስ ሌባና ወምበዴ ይሰልጥንብችኑ ብለው ውሾችሁን አጥፉ ይሉን ጀመር እያሉ ያላዋቂዎችን ልብ ለማሻከር ብዙ ሰው ከተሰበሰበበት እየዞሩ ያወራሉ ያስወራሉ ይባላል ። ግን አንድ አንድ እውነትን የሚፈልጉ አይጠፉምና እስቲ ውሾችሁን ከቤታችሁ አስገቡቱባችሁ?ወይስ እንደ ማስታወቂያው ቃል ለውሾችሁ ከንገቱ ምልክት አድርጋችሁለት ሲከተላችሁ ቀምተው አስገቡቱባችሁን እያሉ ቢጠዩቋቸው ጊዜ ምላሽ ያጣሉ እንግዲያ በየመንገዱና በየአደባባዩ እየተቁማመጠ ለወደቀው እያበደ ሰው ለሚያበላሸው ውሻ ነውን የምትጨነቁት እያሉ ነገራቸውን ያቃልሉባቸዋል ። ይህንንም ዛሬ እነሱ አልጀመሩትም።ተናክሽ ውሻህን ተዋጊ በሬህን እሰር እየተባለ ሲነገር ከጥንት የቆየ ነው ምቀኛ አላዋቂ ግን እነሱን ሲከተል ከቆረሩት ጉድጓድ ተያይዘው ይወርዳሉ እስቲ ይህንን ነገር በየራሳችን ብንመለከተው ከበሽተኛ ውሻ በእርእያ ሥላሴ የተገኘው ሰው አይበልጥምን ። ከበሽተኛ ውሻ ላይ ብዙ ዝምብ መቀመጡን እንስተዋለን ያስ ዝምብ ተነስቶ ማረፊያው ከሰው ላይና ሰው ከሚመገበው ላይ አይደለምን ያንንስ የተመገበ ሰው ሕይወት ያገኛልን ይህንን ሁሉ መርምረው የሰውን ሕይወት ሲፈልጉ ነው እንጂ የውሻ በለደም መባል አይገባቸውም ። ይህ ሁሉ ምን ይሆናል እኛስ በምናገኘው በእግዚአብሔር እጅ ባለው ሹመትና ማግኘት ብንመቀኝ የዲያብሎስ ዜጋ ለመሆንና ያለጊዜያችን ለመቀሠፍ ነው እንጂ እግዚአብሔር የቀባውንና የሾመውን ለሐገርና ለሕዝብ ጥቅም የሚያስበውን ንጹሕ ሰው በከንቱ ሐሰት ወሬ እናጠፋለን ማለት ይህ ለኛ የተሰናዳ ጥፋት ይሆንብናል እንጂ ንጹሕ ሰው በከንቱ ሐሰት ወሬ እንዳይጠፋ በጣም ከልባችን እንረዳው ።

ተገኝ [illegible]

ተፈሪ አባ ጠቅል የዕቡዩ ሞረዱና

ደጃች በየነ ።

በ፯ ማዚያ እጅግ የሚደንቅ ነገር ተደረገ።ደጃች በየነ ዕገሌ አባቱ የማይል ሰው ከትንሽነት ወደትልቅነት በጌቶቹ ፈቃድ መውጣቱን ሁላችሁ የምታውቁት ነው።የተሾመውንና የተከበረውን ክብረት የባሕሪው አድርጎት ሁከትንና ሴረኝነትን ግንዘብ አድርጎ ሰላምን የማይፈልግ ሰው ስለሆነ የብዙ ጊዜ ኃጢአቱን እግዚአብሔር ተመራምሮ ባደባባይ ጣለው።ከዚህም ብፊት አገር እንዲያስተዳድር የወላሞ አገረ ገዥ ቢያደርጉት የወላሞ እሥር ቤት ሲቃጠል ሔዶ እንደ ማጥፋትና እንደ መርዳት ይልቁንም በማግሥቱ ሬሳውን ማስቀበርን ትቶ ግብር እግብቶ ነጋሪት ሲያስመታ በመዋሉ ተከሶ አዎን አለ፡ ተከሶ የቆመበትንም ሰው በጅራፍ ገርፎ በገደለበት ተቆራኝቶ ተፈርዶበት ወደ እንኮበር እሥር ቤት ሔዶ እንደነበረ ሁላችሁም ሰምታችሁታል ። ዛሬም ባደባባይ እንደሰማነው ግርማዊት ንግሥትም አልጋ ወራሽም ፤ ከደመኞቹ አስታርቁ ብለው ወደርስት በታውሔዶ ቆይቶ ደጅ እንዲጠና ቢሰዱት ጋሻ ለሰጠ ጦር ፤ እንደሚባለው ከዚያ ሆኖ ወደ ክቡር ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ አልጋ ወራሽ የፈረንጅ ደንብ በገራችን ሊያገቡብን ነውና ሳያገቡብን ፤ ከትላላቆች ሽማግሌዎች እርስዎ ብቻ ነዎና የተረፉት ሴቲም በዘነዘና ትረዳዎታለች ።

እኔም ልምጣና ልርዳዎ ሰዌን ያስመልሱልኝ ብሎ ሌላም ልዩ ልዩ የሴራ ቃል ጽፎ ኖሮ ወሬው ተሰምቶ ተይዞ የጻፈው ደብዳቤ ረቂቅ ከአልጋ ወራሽ ችሎት ቀርቦ ይኸ ቃልህ አይደለምን ተብሎ በትሕትና ቢጠየቅ አዎን ቃሉ የኔ ነው ብሎ ትርፍ ትርፍ ቃል ስለ ተናገረ ቅዱስ ዳዊት ወመጠውከኒ ዘበኖሙ ለዐርየ እንዳለው አስፈርደው እንደ ሚገባው ተገርፎ በደጃች አባ ሻውል እጅ ሊታሰር ሔደ ።ኢትቅትል ጻድቀ ወኢታሕዩ ኃጥአ ተብሎ ታዟልና ይኸን በማድረጋቸው የቆመውም የተቀመጠውም ሰው ሁሉ የሚገባ ፍርድ በመሥራታቸው እጅግ ደስ አለው ።

ክቡር ቢትወደድ ኃይለ ጊዮርጊስ ድሮ የንግድ ሚኒስትር የነበሩት በሚያዝያ ፯ ቀን ፲፱፻፳፯ ሙተው አዲስ አበባ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ተቀበሩ ፡፡

[illegible]ዶቻቸው እግዚአብሔር ያጥናችሁ እንላለን።

በኢጣልያ መንግሥት ሌጋሲዮን የመጣልን።

የሚያዝያ ፳፫ቀን የለት ወሬ ።

ታኦርሚና ፤ የእንግሊዝ ንጉሥና ንግሥት ከግሪክ ቴአትሮ ገብተው አይተው አድንቀው ላጭር ጊዜ በከተማው ሽርሽር ብለው ወደ ሚሲና ለመሔድ ተነሡ ።

ሳንሬሞ ፤ ሞሐመድ ዓሊ የዱሮ የፋርስ ሻህ (ንጉሥ) ያሁኑ ንጉሥ አባት ሙቷል ሬሳውም ወደ ቴሄራን ይጓዛል ።

ሲራኩዛ፤ የእንግሊዝ ንጉሥና ንግሥት የተቀመጡበት የቤተ መንግሥት መርከብ (ያክ) ከሚሲና ተነሥቶ ወደ ሲራኩዛ መጥቶ ቆመ ጥቂት ቈይቶም ንግሥቲቱ ከተከታዮቻቸው ጋራ ቅርብ ከተማውን በመላው በእግር ዞሩት።

በልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ።

መጀመሪያ ዓመት ፡ ቁጥር ፲፯ ።
1re ANNÉE № 17

ሐሙስ ሚያዝያ ፲፭ ቀን ፲፱፻፲፯ ዓ ም ።
JEUDI 23 AVRIL 1925

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፰ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፲ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፱ መሐልቅ ይሸጣል ።

የጋዜጣው ዲሬክተር ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የራሱን ጉዳይ የሚያሳትም ሰው ዋጋውን እየከፈለ እናትምለታለን ።

ስለ ፋሲካ በዓል ።

ፋሲካ ማለት እንደ እብራይስጡ ቃል ማለፍ ማለት ነው የዚህም ጥንቱ ነገሩ እንዲህ ነው ፡ እስራኤል በግብፅ ሳሉ እግዚአብሔር በግብፃውያን ሞተ በኵር (መቅሠፍት)አምጥቶ ክሰውም ከእንስሳውም ሁሉ የግብፃውያንን በኵር በኵራቸውን ሁሉ ባጠፋበቸው ጊዜ ፤ የእስራኤል በኵር እንዳይጠፋ ዓመት የሆነው ጠቦት በግ አርደችኍ ደሙን በመቃንና በመድረኩ ላይ እርጩት ያንን ደም እየየ መቅሠፍቱ ያልፍላችኋል ብሏቸዋል ። እርሳቸውም እንዳላቸው በጉን አርደው ደሙን በመቃን በመድረኩ ላይ ቢረጩት የበጉን ደም እየየ አልፏቸው ስለ ሔደ አለፈን ሲሉ ፋሲካ ብለውታል ፤ ይኸንንም ሁሉ ዘፀ ፲፪ ፩–፶፩ ተመልከት ።

በዚህ ምክንያት ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በየመቱ እንደዚሁ ያከብሩት ነበር ።

ደግሞ በዚ የዱ ሐኀ ክመስር [illegible] እግዚአብሔር ነውና በባዕድ እጅ ከመገዛት በኋ ከመሆን እግዚአብሔር ከጠላት እድኖ በብርቱ ክንዱ ነፃ እንዳወጣቸው የሚያስቡበት ቀን ስለ ሆነ እንዲሁ በየመቱ የበግ ጠቦት እያረዱ ደሙን እየረጩ የወጡበትን ቀን መታሰቢያ ያከብሩ ነበር ። ዘፀ ፲፪ ፴፩ ፵፪

በዘመን ሐዲስ ያለን እኛ ክርስቲያኖች ደግሞ ፋሲካን እናከብራለን አከባበራችን ግን ከእስራኤል አከባበር የተለየ ነው ። እነሱ የሚያከብሩት ሥጋዊ ድኅነታቸውን(ድኅነተ ሥጋን) በማሰብ ነው እኛ ግን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሞት ነፍሳዊ ድኅነትን(ድኅነተ ነፍስ) እንዳገኘን እያሰብን ነው ። እነሱ ይሠዉት የነበረው መሥዋዕታቸው የበግ ጠቦት ነበር ፤ የኛ ግን መሥዋዕታችን ነዋ በግዑ ለእግዚአብሔር ዘያአትት ኃጢአተ ዓለም ተብሎ የተነገረለት የዓለምን ኃጢአት የሚያስተሠርይ የእግዚአብሔር በግ ክርስቶስ ነው ። ዮሐ ፩ ፳፱ ።

ቀድሞ የበጉን ደም እየየ መቅሠፍቱ አልፏቸው እንደ ነበረ ዛሬም በክርስቶስ የሚያምኑ ምዕመናን ። የክርስቶስ ሥጋውና ደሙ የድኅነት ምልክታቸው ነውና ነፍሳዊ መከራ አያገኛቸውም ።

እግዚአብሔር እስራኤልን ከግብፅ ባርነት ነፃ እንዳወጣቸው በክርስቶስ አምነው የሚታዘዙ ምዕመናንንም ከሰይጣን ሥልጣንና ከባርነት ነፃ ያወጣቸዋል ። ያ ብርቱ ጠላታቸውም ሊበረታታባቸው ቢፈልግ በክርስቶስ ትንሣኤ ድል ሆኑዋልና በእውነተኞች ምዕመናን ላይ ኃይል አያገኝም ።

ስለዚህ በዓለ ፋሲካን ስናከብር የሞትን ኃይል ድል ነሥቶ ከሙታን እንደ ተነሣ እናስባለን ።

ይህ ድል ማድረግም ለክርስቲያን ሁሉ የማሸነፍ ተስፋ የሚሰጥ ኃይል ነው ።

በዚህ በዓል አገራችን ባመት ባመቱ ትልቅ ደስታ ያደርጋልች ፤ ዘንድሮም በየቤቱ ክርስቲያኑ ታላቅ ደስታ ተደርጓል ። ሕዝቡም በእልልታ በደስታ ተቀብለውታል ።

በአዲስ አበባ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያንም የጌታችን ርኛና በትርጓሜ ሲነገር አደረል ።

በዚህ ነገር አለቅየውና ሊቃውንቱ ካህናቱም ተባብረው ለሕዝቡ ስላሰቡለት እናመሠግናቸዋለን ። ሌሎቹም እንዲህ እንዲያደርጉ ተስፋ እናደርጋለን ።

በትንሣኤም ቀን ከኪዳን በኋላ ቀሳውስቱና ሕዝቡ እየተቀባበሉ የሚናገሩት የምሥራች ቃል ይህ ነው ።

(በግዕዝ) ክርስቶስ ተንሥአ እሙታን በዓቢይ ኃይል ወሥልጣን ፤ አሠሮ ለሰይጣን አግዓዘ ለአዳም ሰላም እምይእዜሰ ኮነ ፍሥሐ ወሰላም ፤ (ባማርኛ) ክርስቶስ በፍጹም ኃይልና ሥልጣን ከሙታን ተነሣ ፤ ሰይጣንን አጋዘው ፤ አዳምን (ሰውን) ነፃ አወጣው ፤ እንግዲህስ ወዲህ ደስታና ሰላም ሆነ ማለት ነው ።

የደስታ የምሥራች በሆነ በዚህ ቃል ብርሃንና ሰላም ለወዳጆቹ ሁሉ እንኳን ብርሃነ ትንሣኤውን ለማየት አበቃችሁ ይላል ።

ይድረስ ለብርሃንና ሰላም ዲሬክተር
ሰላምና ደህንነት ለርስዎ ይሁን ።

ለብርሃንና ለሰላም በየጊዜው እንድጽፍ አሳቤ ተነሣስቶ ሳላቋርጥ በየጊዜው መጻፌን ፈቃድዎ ሳይሆን አይቀርም ብዬ ጽፌልዎታለሁ ።

ይድረስ ለኢትዮጵያ ልጆች ሰላምና ደህንነት ለኔና ለናንተ ይሁን ። መስታወት የሚባል ደብዳቤ ከዚህ በታች ጻፍኩላችሁ ለማንበብ እንዳትታክቱ እለምናችኋለሁ ። መስታወት ማለት መልክን የሚያሣይ ነው ፤ ደግሞ ደግ ወዳጅ የሆነ መከረ የሰውን ባሕሪ አመሉን ገልጾ ይመክራል ወደ መስታዎቱ ቀረቡ መልካችሁን አስተውሉ ውበት እንዳለበት ወይም ጉስቁልና ገልጾ ያሳያችኋል ። ጉስቁልና ቢኖርባችሁ እድፋችሁን ፀርጋችሁ መልካችሁን ልታስጌጹበት ይገባል ።

፩ኛ ፡ (ምሳሌ) እኛ መልኩን በመስታወት ውስጥ ያየ እንደሆን መስታወቱን ይሰብራል ምን ክፉ መልክ አየሁ ብሎ ይቀየማል እኛ እንዴት ግብዝ ነው መልኩን ስለ አየ መስታወትን የሚሰብር ። የኢትዮጵያ ልጆች ግን መልካቸውን ሲያዩ ጊዜ በቶሎ ያስጌጻሉ ብዬ ተመኝሁላችሁ ።

፪ኛ ፡ ሰነፍ የራሱ ገዳይ ነው ማንም ሳይገድለው ይሞታል ። የመስኩብ መንግሥት ምንም የውጭ ኃይል ሣይነካው ከሴራና ከድማ የተነሣ ራሱን ገደለ ማለት ሰምታችኋል ከዚህ የበለጠ ሐተት የለም ። ራሱን መግደል እጅግ ክፉ ለዘላለም የማይረሣ የስድብ ስም ነው ። የሰነፍ አማቡ ይገለጣል ተብሎ ከብዙህ ዘመን ጀምሮ ይነገራል ።

፫ኛ ፡ (ተረት) አንድ ሰነፍ ሰው ነበረ ይላሉ ከቶ ስራ የማይወድ ሥራ ይጠላል መብል ይወዳል እያሉ ዘመዶቹ ጠሉት ምግብ አጥቶ በራብ ተጨነቀ እንዳይሰርቅ እንዳይቀማ ቅጣት ፈራ ዘመዶቹን ጠራና ኑ ኑ እባካችሁ ከነፍሴ ቀብሩኝ ብሎ ለመነ ምንም ቢሆን ከሞት አልድንም ሥራም አልወድ ምግብ አላገኝም ከረኃብ ሞት ይሻላል ብሎ ወተወተ ። ዘመዶቹም ተስፋ የሌለው ሰነፍ መሆኑን ያውቃሉና ከነፍሱ ሊቀብሩ ተሸክመው ሲሔዱ አንዲት ሴት ወይዘሮ በመንገድ አገኟቸው የምን ሰው ተሸክማችኋል ብላ ጠየቀች ፤ ይህ ወንድ— [illegible] አትቀብሩ እኔ እንጀራ እያበላሁ እቤቴ አስቀምጠዋለሁ አለች ያም ሰነፍ ይህንን ሰማና እመቤቴ ሆይ የሚሰጡኝ እንጀራ ደረቅ እንደሆነ በምን ውሀ እያራሰሁ አበላዋለሁ ብሎ መለሰ እጅግ ተደነቀች ። አንተ ከነፍስህ ካልተቀበርክ መቃብር ለማን ይሆናል ለመቃብር የተገባ ሰነፍ ነው ወስዳችሁ ቀብሩት ብላ ተጓዘች ይላሉ ። ወንድሞቼ ሆይ ስንፍና እንዲህ ክፉ ከሆነ በሀገራችን እንዳይኖር ማስወገድ ነው ።

፬ኛ ፡ የሀገሬ ሰው በባልንጀራው እጅ ያየውን ለመውሰድ ይመኛል እንጅ ባልንጀራው ጥሮ ግሮ አግኝቶ እንደሆነ ባልንጀራው ባገኘበት መንገድ ተከትሎ በድካሜ አገኛለሁ አይመስለውም ለዚህም ትጋት የለውም ትጋቱ አቅም ቢኖረው በማማለጃ በመተያያ ለማግኘት ይሻል ። አቅም ባይኖረው በልመና በደጅ ጥናት ለማግኘት ይሻል ። ባልንጀራው የደከመበትን ቢወስድ የሚጠላ የለም ። ለሥጋ የጐመጀ ሰው ከፍንጫው ቆርጦ ቢአጐርሱት ሥጋ አገኘሁ ብሎ ቢበላው እርሙን መብላቱ ይሆናል አፍንጫውም ሲቆረጥ ፎናና ነውረኛ ይሆናል ጉቦ መብላትም እንደዚሁ ሁለት ጉዳት አለበት ። መጀመሪያ ጉቦ ሰጭው የሚሰጥበት ምክንያት አንድ የራሱን ጥቅም ለማግኘት ነው ። ይህ ከሆነ ምንም ቢሆን የጉቦ ተቀባዩና የመንግሥት ወይም የሕዝብ ሣይጐድል ለጉቦ ሰጭው ጥቅም አይገኝም ።

፭ኛ ፡ ባሁኑ ዘመን ለኢትዮጵያ ልጆች ታላቅ ደስታ የምስራች ሆነ የሁላችንን ልብ በደስታ መላው የቀድሞ ዘመን ዳኛ በባዶ ሆዱ ሊፈርድ አይችልም ነበረ ። ያልበላ ዳኛ ብስጩ ነው ያዘው እወህኒ አግባው እያለ ሣይፈርድ እያሰረ ብዙ ሰው በወህኒ በሽታ ይሞት ነበረ ። አሁን ግን ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ዳኛ የሆነ ሳይበላ በባዶ ሆዱ እንዲፈርድ ብልሃት አገኙ ። ሕዝቦችን የሚታሰሩበት ምክንያት ኃጢአታቸው ሣይፈረድ አትሰሩ ብለው ከልክለዋል ። ዳኞቹንም ደመወዛችሁ ይብቃችሁ ብለዋል ። ይህም የመጽሐፍ ቃል መሆኑን በሉቃስ ወንጌል ፫ምዕራፍ ፲፫ና ፲፬ ቁጥር እሱም አላቸው ከታዘዘላችሁ አብልጣችሁ አትውሰዱ በማንም ግፍ አትስሩ ማንንም በሐሰት አትክሰሱ ደመወዛችሁ ይብቃችሁ ይላል ። ደግሞ በኦሪት ዘፀአት ፳፫ ምዕራፍ ፰ቁጥር ማማለጃ አትውሰዱ ማማለጃ የብልሐተኞችን ዓይን ያሳውራልና የጻድቃንንም ነገር ያጣምማል ብሎ ሙሴ ተናግሯል ። ድሐውም በከንቱ አላመታሰሩን አወቀና ማማለጃ ለመስጠት የግድ የለበትም ይህንን የሰማ ሁሉ ልዑል አልጋ ወራሽን እንደምን ያመሰግን ይሆን ። ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ሆይ እኔም አመሰግንዎታለሁ የሐገር ፍቅር አነሣሥቶ የከበሩ አያቶችዎ ወደ ማስተዋል ተገልፀው ኢትዮጵያን ወደፊት ለመምራት ወደ ደህንነት መንገድ አቅንተው ይዟሉ ። የጥበብና የማስተዋል መንፈስ በፍቅር ያናድድዎታል ደንግዝግዝ ባለው ጨለማ ውስጥ ብርሃንን ብልጭልጭ አደረጉልን ። ሁላችንን በአንድነት ሰብስበው በመከከላችን አብርተው የውስጣችንን ጨለማ ያጠፉልን ዘንድ መጣርዎን እመሰክራለሁ ለጥቅማችን ማሰናዳትና ማበጃጀት ከእግዚአብሔር የተሰጡን ቸር ጠባቂነትዎን ለዘላለም ያኑርልን አሜን ።

[illegible] የሚመጣበትን መንገድ ከልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን [illegible] በጥር የሚከፈተው አለመኖሩን አውቀነዋል ነገር ግን ክፉ ልጅ ቢአዝሉት ያለቅሣል ቢአጠቡት ጡት ይነክሣል እንደሚሉት ተረት መለያየትን ፀብን ቅናትን መከራከርን ሁከትን ለሥራ መስነፍን እያረገዙ የሚወልዱ ወላጆች በኢትዮጵያ ውስጥ ሊኖሩ አይችሉም ። ከዛሬ ጀምረው በአእምሮ በብርሃንና ሰላም ጋዜታ እንደ እሳት ቅናታቸው እየለበለባቸው ተቃጥለው ይጠፋሉ በር ጠባቂውም የታመነ ነው በረኝነቱ ከበቱ የቆየው ነው ። የምስክሩ ቃል ከቡር ራስ መኰንን የሞቱ ለት የሸዋ መኳንንት እግዚአብሔር ያጥናችሁ በየበር የሚቆም ከልካይ ሞተባችሁ ብሎ አንድ ሰው አለቀሰ ይባላል እኔም የራስ መኰንን ሥራ የመቀሌን ያድዋን የአረብ አገርን እመሰክራለሁ

፮ኛ ፡ መጣላትን በላምና በጥጃ ስናየው እንደምን ይከፋል ላም ጥጃዋን ብትጠላ ጥጃም እናቷን ብትጠላ የሁለቱም ጉዳት

እርግጥ ነው ለጥጃም ወተትን ያህል ጥቅምና ማደግ ይቀርብታል ላምም ወልዳ ካላጠባች ወደ መሲና ትቆጠራለች ። የመሲና መጨረሻ መታረድ ይታሰብላታል ።

፱ኛ ፤ በሰው ቤት ሊከብርና ጨዋ ሊሆን የሚወድ ሰው እንደ ምን የቤቱን ሥራት ያሳምር ይሆን ። የቤቱን ሥራት ሣያሣምር በሰው ቤት ሊከብር ቢወድ የንብረቱ ማነስ ክብር ይከለክልበታል ። ወደ ጎረቤቱ ሔዶ የነበረ ሰው በዚያ ታላቅ ክብር ተቀብሎ ቢመለስ ደግሞ ጎረቤቱ ብድር ለመክፈል እንግድነት ቢመጣበት የቤቱ ሥራት እጅግ ያላማረለት እንደ ሆነ እንደ ምን ያፍር ይሆን ። ይህነን ቃል የጻፍኩት ላዋቂዎች ብቻ ይመስላል በውስጤ ያለውን በመላሴ ለመናገር እስኪቻለኝ ድረስ ይህነን ክብ የሆነ ቃል እጽፋለኍ ።

፲ኛ ፤ የኢትዮጵያ ልጆች ወደ ተሻለው መንገድ አቃንተው ጒዞ ጀምረዋል ጒብ ታገር ሊጠፋ ነው ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ደምብ በሚባል ሰይፍ ቆራርጠው ቆራርጠው ጒቡን ጒንድሽ ብቻ አድርገውታል ። አሁን ዛሬ ጒብ ሰጭው እባካችኍ ተቀበሉኝ ይላል ተቀባዩ ግን ለምን አመጣብኝ አልቀበልም እያለ ይመልሳል ። እኔም ለዘመዶቼ ጒዳይ ስል ወደ ክቡር አፈ ንጉሥ ከተማ ገንዘብ ይዤ ብሄድ አሽከራቸው ይጣሉኻል ቢሉኝ ገንዘቡን ሳላሳይ ጒዳዬን ተናግሬ ተመለስኩ ። ቀኛዝማች ሞላም ወሬውን ሲያነሡበት ይጣላል ማለትን ሰምቼ ነበር ባነሣበት ገላመጠኝ ። የልዑል አልጋ ወራሽ አሽከር ግራዝማች ክልክሉም ላንዲት ድሃ ብዬ ገንዘብ ይዤለት ብሔድ ገላምጦ መለሰኝ ። ይህንን የምሥራች መደበቅ አይገባም ባገራችን ጒብ መናቁን ሰምቶ ደስ የማይለው የለም ።

፲፩ኛ ፤ ጒቡን የሚሰጥ ሰው ተቀበሉኝ እያለ ማስጨነቅ ስለ ልማድ ይመስላል ጒብ ካልሰጡኍ ጒዳይ አይቀናልኝም ቢመስለው ልማድ አስጨንቆታል ። እኛ ግን እንግዲህ ጒቡን ከቁም ነገር አንቆጥረውም ።

፲፪ኛ ፤ እኛ የኢትዮጵያ ልጆች በፈሳሽ ውሀ እህል መዝራትን አልለመድነውም ዝናምን ጠብቀን እንዘራለን ዝናም ባጣን ዘመን መራባችን እርግጥ ነው ። ሽመታ ብናጣ እስከ ሞት እንደርሳለን ። ከዚህ ቀደም የተመሰገኑ ራስ መኰንን የሐረር ሰው ቢራብ ከውጭ አገር ማሽላ በባቡር አስመጥተው ሕዝባቸውን ክፉ ቀን [illegible] እህላችንን እንሸምትም ማለታችን እኛን የራበን ጊዜ ወዴት ልንሸምት ይሆን ? ።

ዓለም ከተፈጠረ ዘመን ከተቆጠረ እስከ አሁን ድረስ በየዘመናቸው የነበሩ የሰው ልጆች ዓለምን በተሻለው መንገድ ለመምራት ሲሉ ከወንድሞቻቸው ጋራ ሲጋጩ እንደነበረ የቀድሞ ዘመን ታሪክ ይነግረናል ። ይልቁንም በመጀመሪያው ጊዜ የአዳም ልጆች አቤልና ቃየል ተጋደሉ ። የምቀኝነት ኃይል ያለችግር ሞትን ሲወልድ እናያለን ሁለቱ የአዳም ልጆች የተጋደሉበት ምክንያት አንዱ መልካም ሥራ ሲሰራ ጊዜ ። ሁለተኛው ደግ ሥራ ለመስራት አቃተው ። መልካም ሥራ ለመሥራት የማልችል ከሆነ ወንድሜን መግደል እችላለሁ ብሎ የገደለው ይመስላል ። ለሁለቱ ወንድማማች የማይበቃ መስሎ ያጋደለ ዓለም አሁን ለብዙ ሚሊዮን ሕዝብ የሚበቃ ሆነ የዳር አገር አገረ ገዦዎች በተወሰነ ደንብ ላይ ተሾመው እንደሆነ ደምቡን ሁሉ ማሻሻል የሚያስፈልግ ይመስላል ። ባልተወሰነ ደንብ ላይ ተሾመው እንደሆነም የተወሰነ ደንብ ሊቀበሉ ይታሰባል ። ነገር ግን የዳራገር አገረ ገዦዎችና የሕዝቡ አነዋወር ከሕግ የተለየ ነው ። ዓለም ከተፈጠረ እስካሁን ድረስ በየዘመኑ የነበሩ አዋቂዎች ዓለም ደህና አካሔድ እንድትራመድ ለማሻሻል ብዙህ ፈልገው ነበሩ ። ነገር ግን ከሁለቱ ብልሐቶች በቀር ሌላ አላገኙም ። ሁለቱ ብልሐቶች ሰርቶ መብላትና መፋቀር ብቻ ተገኙ ። ለነዚህ ማጥኛ ሌላ መንገድ የለም ከትምህርትና ከመተዛዘን በቀር ።

ነጋድራስ ደስታ ምትኬ ።

መጋቢት ፫ ቀን ፲፱፻፲፯ ዓመተ ምህረት በተጻፈው በ፲፩ኛው ቍጥር ጋዜጣ ላይ የኢትዮጵያ ወዳጅ ቀጥለው ያሉትን ነገሮች ጽፎ አሳይቶናል ።

ስለ ብር ምንዛሬ በመሐልቅ ።

ለኢትዮጵያው ወዳጅ ምላሽ ፤ ስለ መሐልቁ ምንዛሬ ነገር እንደ ተቻለው መጠን ከንቲባው ብዙ ጊዜ አስበበታል ይህንኑም የከተማው አዋጅ ጥበቃ ሥራውን የሚዘጋጅለት ለማድረግ ለመንግሥት ማስታወሱን አልዘነጋም ፤ መንግሥትም ደግሞ ይህንኑ ለሕዝቡ ጥቅም የሚሆነውን ያመነዛዘር ስራ የተቃና ለማድረግ እንደሚጥርበት የታወቀለት ነው ።

ስለ እንጀራ ሽያጭ ።

መጀመሪያ በእርሻ ፊተኛ ከሆኑ ከሌሎች ብዙ አገሮች ጋራ በምትቈጠረው እንደ ኢትዮጵያ ባለች አገር አንድ ኪሎ እንጀራ ከ፬ ፍራንክ በላይ ቢያወጣ ፍትሕ ነውን ? ሲል ምክንያቱን ይጠይቃል ። ፪ኛ ደግሞ የት አገር ለአንድ ኪሎ እንጀራ ከ፬ፍራንክ የበለጠ ይከፍላል ? ይላል ። የዚህንም ነገር ጥያቄ የሚመራመሩትና የሚፈጽሙትም ከንቲባ ናቸው ሲል የጥያቄ አንቀጹን ይጨርሳል ። የኢትዮጵያ ወዳጅ በጋዜጣ ቃል ጽፎ ከጠየቀ ዘንዳ ከንቲባውም ለጥያቄው በተጻፉት ቃሎች ምላሽን ያስረዳል ።

መጋቢት ፫ ቀን ፲፱፻፲፯ ዓመተ ምሕረት አዲስ አበባ ገበያ ውስጥ ሰው ሁሉ በ፩ መሐለቅ ሂሳብ ፲እንጀራ ገዝቷል ግራም ወይም ተኩል ይሆናል ። እንግዲህ በዚያው ቀን ፩ቱ ኪሎ ተኩል እንጀራ በ፩ መሐልቅ ሂሳብ መገዛቱ ነው ። የዚህኑ እንጀራ ግጋር ኪሎው ከ፬ፍራንክ አለመብለጡን አስረዳለሁ ። የኢትዮጵያ ወዳጅ በዚሁም ቀን መጋቢት ፫ ቀን አሙስ እለት ባዲስ አበባ ገበያ ውስጥ ፩ብር በ፱መሐልቅ ሂሳብ ተመንዝሯል ። በዚያውስ ቀን በፍራንክ ሂሳብ አንዱ መሐለቅ ምንዛሬው ምን ያህል ኍሯል ? መጋቢት ፫ ቀን ፲፯ንም አሙስ እለት ፩ብር በ፲፪ ፍራንክ ከ፷ሳንቲም ሂሳብ የኢትዮጵያ ባንክ ገዝቷል በፍራንክ ሂሳብ የ፩ መሐለቅ ምንዛሬ የ፲፪ ፍራንክ ከ፷ ሳንቲም ዘጠኝኛው እጅ ሲሆን ፩ ፍራንክ ከ፵ሳንቲም መሆኑ ነው ያ፩ዱ መሐለቅ ምንዛሬው ፩ ፍራንክ ከ፵ ሳንቲም ሲሆን ከአዲስ አበባ ገበያ ውስጥ ፩ኪሎ ተኩል እንጀራ በ፩ ተሙን መግዛቱ ይታወቃል ። ፩ን ኪሎ እንጀራ በ፬ፍራንክ

በላይ ይበልጣል ብሎ የኢትዮጵያ ወዳጅ በጋዜጣ ውስጥ ከጻፈው ቃል ውድነቱ ፯ ጊዜ ያነሰ መሆኑን ያንዱ ኪሎ እንጀራ ዋጋ ፶፯ ሳንቲም በመሸጡ እንረዳዋለን እንግዲህ ከዚህ በላይ የጻፍነው ቃል በአዲስ አበባ የእንጀራ ግዢ ሁኔታ ነውና ለፊተኛው ጥያቄ ምላሽ ከጨረስን ወደ ፪ኛው ጥያቄ አንቀጽ መለስ እንበልና ባለ ሆቴሎችና ጥሩ ዳቦ ጋጋሪዎችም ለገዢቻቸው በሚሸጡላቸው ዋጋ የግጋሮው አኳኋን እንደምን መሆኑን እስቲ እንመልከተው ።

ጥሩ ዳቦ ጋጋሪዎች የሚባሉ ሁሉ ረዘም ያለውን ዳቦ ባ፩ ብር ሂሳብ አምሳውን ዳቦ ይሸጡታል ። ይህንኑ አምሳውንም ዳቦ የእያንዳንዱን ክብደት ብንመዝነው ከ፻፸ ግራም ወደ ፻፹፭ ግራም ይሆናል እስቲ ይሁንና በ፻፸ ግራም ሂሳብ እንደምራቸውና የ፶ውን ክብደት አኳኋኑን አጥርተን እንወቀው ።? ይህ ሲሆን ባዲስ አበባ ውስጥ የጥሩ ዳቦ ዋጋ ባ፩ ብር ፶ ጊዜ ፻፸ ግራም ማለት ስምንት ኪሎ ከ፭፻ ግራም ወይም ተኩል ይሆናል ። በፍራንክ ረገድ የብር ምንዛሪ ፲፪ ፍራንክ ከ፳ ሳንቲም ከሆነ ጥሩ ያንዱ ኪሎ ዳቦ ዋጋ ፩ ፍራንክ ከ፵፬ ሳንቲም መሆኑ ነው ስለዚህ ባለፈው ጋዜጣ የኢትዮጵያ ወዳጅ ስለ ጻፈው ስለ ፬ቱ ፍራንክ ሂሳብ ነገር በጣም የተራራቅን ነን ።

እፈረንሳዊ አገር በዛሬው ጊዜ ያንዱ ኪሎ ዳቦ ግጋር ከ፩ ፍራንክ ፶ሳንቲም እስከ ፩ ፍራንክ ከ፷፭ሳንቲም ይሆናልና በዚህ ሂሳብ የዚህ አገር ያንዱ ኪሎ እንጀራ ዋጋ ፶፯ ሳንቲም ሲሆን ከፈረንሳዊ አገር ዋጋ ፫ት ጊዜ ማነሱን ስናስታውቅ የኢትዮጵያ ወዳጅ በጋዜጣ ከጻፈው ቃል ፯ ጊዜ የቀነሰ መሆኑ ነው ።

ጥሩ ዳቦ ደግሞ ያንዱን ኪሎ ዋጋ ፩ ፍራንክ ከ፵፬ ሳንቲም እንደሆነ በርግጥ ስናስበው ከፈረንሳዊ አገር ግጋርም ያነሰና የኢትዮጵያ ወዳጅ ከጻፈው ቃል ፫ት ጊዜ ያህል የቀነሰ መሆኑን ለማወቅ አያሰጋም ።

የኢትዮጵያ ወዳጅ የሕዝቡ ጉዳት አሳዝኖት ጽፎ ስላስታወሰን ደስ ይለናል ፡ ግን ይህንን መጻፉ ዳቦውን በማታለል ሸጠውለት ይሆናል ፡ ለእንግዲሁ ግን የዳቦው ዋጋ በላይ እንደ ተጻፈው መሆኑን አስቦ ይግዛ ።

እንዲህ አድርጎ የሚያስፈልገንን ነገር በጽሕፈት ወይም በቃል የሚያስታውቀን ቢገኝ ደስ ብሎን እንቀበለዋለን የጐደለውን ለመምላት የጠመመ የመሰለውንም ለማቅናት በጣም እንጥራለን።በምክር የሚረዱ ወዳጆች በማግኘታችን ደስ ይለናል።

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ነሲቡ ዛማኔል።

ከነጋገርህ የተነሣ ትጸድቃለህ ።ከነጋገርህም የተነሣ
ይፈረድብሃል ማቴ ፲፪ ፴፯ ።
ከሞት ታደርሳለች ያላረፈች መላስ ።
ነክክተውት ነበር የረጋውን ራስ ።
አንስቶ መሔድ ነው የወደቀን ዕዳ ።
ዳኛ እንዲህ ያረጋል ተበየነ ወዲያ ።
በአእምሮ ሳንቃ እንደበትን ዝጉት ።
ያጠፉል ይገላል አፍን ቃልጠበቁት ።
አሁን ለምንድነው እንዲህ መሞላቀቅ ።
ደሀን ታሳደገው የገደለው ይጽደቅ ።
አምላክ ግፍ አይችልም ፍዳን አያስቀርም ።
የእግዚአብሔር ፍርድ ነው አያስቈረቍርም ።
በሰፈሩት ቁና መሠፈር አይቀርም ።
ይኖር የነበረ ጾምን እንደናቀ ፤
ዓርብ ሮብ ነነዌን እያደባለቀ ።
በየነ ሁዳዴን ሕማሙን አወቀ ።
እንደከራ አልሔደም እንደተጀነነ ።
ጠጅ ጠጣ ቢሉት ውሀ እየለመነ።
የመሬት ዝምድናን አወቀ በየነ ።

ለውሀ ብነግረው ይዞት እየሔደ ።
ለእንጨትም ብነግረው እየተማገደ ።
ለድንጋይ አልነግረው አይሰማ ደንቆሮ ።
ባመሉ ቀለለ በየነ ዘንድሮ ።

ማስታወቂያ ።

ቢትወደድ ኃይለ ጊዮርጊስ በነጋድራስ ፋላስ ላይ ስለ ሚፈልጉት ገንዘብ ሙሴ ካሎስ የተከራየው በሸማ ተራ በታች ያለው የነጋድራስ ፋላስ ሱቅ በሐራጅ ተሸጦ እዳው ይከፈል ስለተባለ በማዘጋጃ ቤት ፊቃድ ይሸጣልና የሚገዛ ሰው ሁሉ ሚያዝያ ፳፪ ቀን ሐሙስ ከጧቱ በ፫ ሰዓት ወደ ማዘጋጃ ቤት ድረስ መጥቶ ሊገዛ ይችላል ። የቦታውም ስፋት አምስት ሺ ዘጠና ሚትር ካሬ ነው ። በላዩም ያለው ቤት አንድ ትልቅ አራት ክፍል የሆነ፡ ሁለተኛው ቤት ሰባት ክፍል የሆነ ፤ ሶስተኛው ቤት ሶስት ክፍል የሆነ ፤ ያንዱ ክፍል ስፋቱ አሥራሰባት ሚትር የሁለቱ ስልሳ ስምንት ሚትር ፤ አንድ ቤት የሰም ማንጠሪያ አንድ ሰቀላ የማር ቤት አንድ ትንሽ የማር ቤት ነው ፡ ክራዩም በወር በወሩ መቶ ሠላሳ አምስት ብር ነው ። ሚያዝያ ፳ ቀን ፲፱፻፲፯

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ነሲቡ ዛማኔል ።

ከታይምስ የተገለበጠ ።

በሉክሶር የአንቲኪቲ ነገር መቈፈር ሥራ ከዶክተር ሞንድ አለቅነት በታች ሆኖ የነበረ የረበርፑል አርኪዮሎጂስት በንጉሥታት ሸለቆ ከንጉሥታት መቃብር ለብቻ የሆነ ከስመ ጥሩው ከቴበስ ራሜሴዩም መቃብር አጠገብ መካከል ሁለት አዲሶች ነገሮች አግኝተዋል ።

ሚስተር ኤሜሬ ባሁኑ ቅርብ ጊዜ ሥራቸው በፊት ያልተፈለጉ የፈርዖኖች ዋና ሚኒስትሮች መቃብር በማግኘት እድላም ሆነዋል ። እጅግ ጥሩ በጣም ሃሳብ የሚያነሳቡ ናቸው ጕዝቤቸል ብዙ ክቡር የሆነ የተቀባ ምስልና ሌላም ምስሎች አለባቸው ነገሩን ገና በዝርዝር አላወቅነውም ። ግን የሚስተር ኤሜሬ ደብዳቤዎች እንደሚሉን ያገኘውን ነገር በሉክሶር ሃሳብ ብዙ ቀስቅሶዋል ። ሚስተር ኤሜሬ ይዘውት ያሉ የመቈፈር ሥራ ከሊበርፑር ዩኒቨርሲቲ ጠባቂነት በታች ይፈጸማል ።

በቴሌግራም የመጣ የሚያዝያ ፩ ቀን የለት ወሬ ።

ሎንድራ ፤ሜሲክ የተባለች ከተማ በምድር መናወጽና በእሳተ ገሞራ ጠፉች ተብሎ ይወራል ።

የሚያዝያ ፰ ቀን የለት ወሬ ።

ፓሌርሞ ፤ የእንግሊዝ ንጉሥና ንግሥት የተራቢያ አዳራሽ አይተው ሞንቴ ፔሌግሪኖ ወደ ተባለ ተራራ ደረሱ ፤ ፕሪንስ ጆርጅ ወደ እንግሊዝ አገር ለመሔድ ተነሡ።

በልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ።

መጀመሪያ ዓመት ፤ ቁጥር ፲፰ ።
1^re^ ANNÉE № 18

ሐሙስ ሚያዝያ ፳፪ ቀን ፤ ፲፱፻፲፯ ዓ ም ።
JEUDI 30 AVRIL 1925

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን በአገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፬ መሐልቅ ይሸጣል ።

የጋዜጣው ዲሬክተር ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የራሱን ጉዳይ የሚያሳትም ሰው ዋጋውን እየከፈለ እናትምለታለን ።

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያን ልጆች ለማሰልጠን ያቆሙት ተማሪ ቤት መከፈት።

ባለፈው ጋዜጣችን ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ያቆሙት ተማሪ ቤት ይከፈታል ብለን በደስታ ጽፈንላችሁ ነበር ፤ አሁንም በሚያዝያ ፲፱ ቀን ተከፈተ በመከፈቱም እጅግ ደስ አለን ። በዚህም ቀን ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን በ፬ ሰዓት ወደ ተማሪ ቤቱ ሔደው ተማሪ ቤቱንና የተማሪዎቹንም አኳሆን አዩ ፤ ክቡር ራስ ሥዩምም በዚህ ጊዜ አብረው ነበሩ ። የተማሪ ቤቱንም ሥርዓት ያሰዩ የተማሪ ቤቱ ሹም ሐኪም ወርቅነህ ናቸው ። የፈረንሳዊ ቋንቋ አስተማሪዎችም ሙሴ ጃን ጉዮና ሙሴ ፓል ላቡርዳሪ ፤ የእንግሊዝ ቋንቋ አስተማሪ አቶ ኤፍሬም ናቸው

የተጀመረውን ሥራ እግዚአብሔር ለጥቅምና ላገራችን በረከት እንዲያደርግልን እንመኛለን ።

የተማሪ ቤቱንም ሁኔታ ሌላ ቀን በብዙ እንድንጽፍላችሁ ተስፋ እናደርጋለን ።

ተስፋ ።

ብርሃንና ሰላምን የሚቀበሉ ሰዎች እያደሩ ይበዛሉ ። ይህም ሕዝባችን ዕውቀትና ትምህርት የመፈለጉ ጊዜ መሆኑን ያስረዳል ብዙ ሰዎች ደግሞ የሥራቸውን ጉድለት ቢያስታውቋቸው ሳይከፋ ኑሮዋቸውና ሥራቸውን ለማረም ፈቃድ እንዳላቸው በቃላቸው ይናገራሉ ። ይህም ዕውቀት ለመፈለግ ትልቅ የምስራች ነው ። አሁን እኛ ሥራ በምንፈታበት ጊዜ ብንማር መልካም ነበር ፤ በደረስን ይሆን ? ብለው የጠየቁ ትልልቅ መኳንንት ሰምተናል ፤ ይህ ብቻ አይደለም ሽበት ወረር ያደረጉ ሰዎች ጥበብ እንድናገኝ በማለት የውጭ አገርን ቋንቋ መማር ጀምረው የሚያነቡ ሰዎችም እናውቃለን ። ይህ ሁሉ ኢትዮጵያውያን ትምህርትና ዕውቀት ስልጣኔም ለማግኘት የአእምሮዋቸውን በር እንደከፈቱ ብርሃንና ሰላም ተረድቶታል የዕውቀት ብልጭታ ሊያሽበርቅላቸው የጀመረ ብርሃንና ሰላም በማግኘታቸውም በቃላቸውም ያመሰገኑ ጽፈውም የምሥጋና ቃል በማሕተማቸው አትመው የላኩልን መኳንንቶች ብዙ ናቸው ። ይህም ብርሃንና ሰላም ወደ ፊት ይግፋ ማለታቸው ስለሆነ ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ለጀመሩት በጎ ሥራ ተስፋ የሚሰጥ ነገር ነው ። ብርሃንና ሰላም በዚህ ምክንያት ሥራውን ለመፈጸም ድፍረት አግኝቷል ።

ብርሃንና ሰላም እስከሁን ድረስ በፈለግነው ጊዜ ያላደረስንላቸው በዳር አገር ያሉ ሰዎችም የጶስጣ ሥራ ከሁኑ የበለጠ በተከናወነ ጊዜ ብርሃንና ሰላም ለመዘርጋት የተመቸ እንዲሆንልን ተስፋ እናደርጋለን ።

ይህንን ለማድረግ ደግሞ እጅግ ከባድ ነገር አይደለም የጋሪ መንገድ እስኪበጅ ድረስ አያሌ ወታደር ለዚሁ ሥራ ትጥሮ በያውራጃው መንገድ ማረፊያ ቤት ሠርቶ ከጎዲ ማረፊያ ወደንዲ ማረፊያ እየተቀባበሉ ሊፈጽሙት ይቻላል ።

ይህንን ሥራ ለማከናወን ሊጣጣሩበት የሚገባቸውም ክቡር የጶስጣ ሚኒስትር ናቸው ። እንደሚያስቡበትም እናምናለን

በዳር አገር ሁሉ ጋዜጣና ደብዳቤ ለመላክ የተመቸ ከሆነ አውራጃው ሁሉ በዚህ መንገድ ከዋና ከተማው ጋራ ቢገናኝ አንድ ወገን ችግር ይሞላልና ይህ በቶሎ እንዲፈጸም ተስፋ እናደርጋለን ።

ስለ እውቀትና ስለ ስራ ስለንግድም አሰፋፍ ።

ምድረ ገነት ክብርት ቅድስት ኢትዮጵያ ሀገራችን ከጥንት ከዳዊት ከሰሎሞን ጀምሮ እስከኛ ቀን ድረስ ምንም በእውቀትና በስልጣኔ ወደ ኋላ ስለቀረችና ይልቁንም

አይኖችዋ የብርሃንን መንገድ ማየት ስለ አልለመዱ የጥንት ኃይሏ ሳያንሳት ከስፋቷ ተቀንሳ ስለ አገኘናት የልጆችዋ ሁሉ ትልቅ ጉዳታችንና ኃዘናችን ስለሆነ ዋናውን ነገር ነጻነቷን ሳታወላውል በእግዚአብሔር ጥበቃና ለሀገራቸው በደስታ ደማቸውን አፍሰው ሥጋቸውን ቆርሰው ስለ ሀገራቸው ትልቅነት ና ክብር ተሰይፈውና ኅይወታቸውን አሳልፈው በሰጡት ሰማዕታት ለልጆችዋ ብርታት አቆይታ ከሰችን ። ትልቁ ዋናው ነገር ነጻነት እያለን የእውቀት አይን ብርሃን በጣም የሚያስፈልገን ጕድሎናልና ከሁሉ በፊት ክብርት ሀገራችን ልጆችዋን ማስተማርና ማሰልጠን እርሻና ንግድን ማስፋት በጣም ያስፈልጋታል እውቀት ለሰው መጀመሪያ የሚያስፈልገው የሚዓይ ዓይን የሚሰማ ጆሮ የሚአስብ ህሊና የዚህን ዓለም መከራና ስቃይ የሚአቀል ድኅነትንና ኃጢአትን የሚአርቅ ብርሃን ፍቅር ህብረት ትልቅነት ጤና የነፍስና የሥጋ ጸጋ ማለት ነው ። እንደዚሁም ስለ ድንቁርና ዲዩጋርን የግሪክ ፈላስፋ አንድ ቀን ወዳጆቹ መሬት ከተሸከመችው ሁሉ በጣም ክበድና አጉል ጭነቷ ምንድርነው ብለው ቢጠይቁት ደንቆሮ ሰው ነው ብሎ መለሰላቸው ። እንዳለውም ሁሉ ድንቁርና የእውቀት ተጻራሪ የኃጢአት ምንጭ የድህነት የምቀኝነት ያለመስማማት የበሽታ እናት ፡ ስራ ትምህርት ንግድ ስልጣኔ የምትቀፍ የሀገርና የሕዝብ በልዩም የሰው ሁሉ ጠላት ናት ። ስራ ማለትም የፍጡራን ሁሉ ሕግና የሚገባ ደንብ መማር ማስተማር ማረስ መነገድ ማነጽ መገንባት ብረትን ወርቅን ብርን ማንጠርና መስራት ነው ስራም መንግሥትንና ሕዝብን የሚአከብር የሚአሰለጥን ከሰው ሁሉም ችግርንና ኃጢአትን የሚአርቅ ትልቅ ትእዛዛችን ነው የእግዚአብሔር ፍጡራን በሙሉ ልብ አድርገን ብንመለከትና ብንመረምር በሰማይ ፀሐይ ጨረቃ ከዋክብት ምድርን ሲአበሩና ሲአሞቁ እናያለን ፡ በምድርም እንሳስት ዕፀዋት ውኃ እሳት ትልቅ አእምሮ ስንኳን እንደኛ ያልተሰጣቸው ነፍሳት እንንብና እንጉንዳን በትጋት ሲሰሩ እናያለን ፤ በሰለጠነም አገሮች ከ፫ አመት ልጅ ጀምሮእስከ ፸ አመት ሽማግሌ በኛ ወይም በራሱ እየሰራ በክብረት ላይ ክብረት በእውቀት ላይ እውቀት በኃይል ላዩ ኃይል ሲጨምር እናያለን ።

የኔ ወንድም ግን ብርና ወርቅ ከንግሥታትና ከመኳንንት ግምጃ ቤት እየፈላቁ የሚአድር ይመስለዋል እንጅ እሰው ሁሉ እጅ ውስጥ ተቀብሮ ሲሰራ የሚአበላው የሚአከብረውም ሲሰንፍም ጠም የሚአሳድረው ስራ (ማለት) እርሻና ንግድ ሙያውን ቢአውቅ ሁሉም ነጋዴና አራሽ ሰራተኛ ሆኖ በስርአትና በደስታ በኖረ ነበር ። ኢትዮጵያም ክብርት ሀገራችን ልጆቿዋን ብታስተምር ለምለምና ሰፊ መሬቷን በጣም ብታርስና የቀንድ ከብትም ብታረባ በነዚህም ፍሬ (ማለት) በእህል በጥጥ በቡና በማር በቅቤ በቀንድ ከብት በቆዳ ይህንንም በሚመስሉ ሁሉ ትልቅ ንግድ ብታቆም እንደነገሯን ሁሉ በቶሎ እንድትከበርና ወደ ስልጣኔም ደረጃ እንድትደርስ ጥርጥር የለውም ነበር ።

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና እንደራሴ ተፈሪ መኰንን ባለፈው ያውሮፓ መንገዳቸው የትግሬ መስፍን ክቡር ራስ ስዩምን ። የጐጃም መስፍን ክቡር ራስ ኃይሉን ፡ ያድዋ ገዥ ክቡር ደጃዝማች ገብረ ሥላሴን ፤ የባሌ ገዥ ክቡር ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴን ፤ እንዲሁም የልዩ ልዩ አውራጃዎች ገዥ ክቡራን መኳንንት ያውሮፓን ሥልጣኔ ባጭር የልዩ ልዩ መንግሥታትን ህብረትና ስርአት የትምሕርትን የውቀትን የንግድን በጣም ስፋት የሕዝብን በትልቅ ሥልጣኔና ስርአት አስተዳደር (በዝርዝር ቢጻፍ አንድ መጽሐፍ የማይችለው የሥልጣኔና የእውቀት የሚአስገርም ስራ) ስለአሳይዋቸውና የኃገራቸውን ሕዝብም ለማስተማር ለማሰልጠን እርሻን ንግድን ለማስፋት ኢትዮጵያንም ወደተሻለ አንዋንዋርና ወደ ስልጣኔም ደረጃ ለማድረስ የሁልቀን ሃሳባቸውና ልፋታቸው ስለሆነ እግዚአብሔርን ማመስገንና እድሜ እንዲሰጥልን መለመን ይገባናል።

ያውሮፓን ስልጣኔና ስርአት ያዩ ክቡራን መኳንንት ለሀገራቸው የውቀት የብርሃን የስልጣኔም ሐዋርያት ሆነው የኢትዮጵያን ሕዝብ እንዲአስተምሩ እንዲሰብኩ ልጆችም እንደሚቻላቸው እውቀት ባለበት ስፍራ እየላኩ እንዲአስተምሩ በሚገዙበትም አገር ላይ ሰው ከፈቀደ የሚአውከው የለምና ትምሕርት ቤት እንዲከፍቱና ለሙሉ ኢትዮጵያ ምሳሌ ሆነው ብርሃን በሀገራቸው ለማግባት እንዲጣጣሩ እርሻን ንግድን ትምሕርትን እንዲአስፉ ሀገራቸውን ወደስልጣኔና ወደሚሻል አኗዋዋር ለማድረስ እንዲበቁ በኢትዮጵያ ታሪክም ላይ ምስጋናና ክብር ለዘላለሙ እንዲአገኙ ይልፉ ፤ ይህንንም ለማድረግ ከእግዚአብሔር ኃይል እንዲሰጣቸውና እንዲቀናቸውም የኢትዮጵያ ልጆች ሁሉ ምኞትና ሙሉ ተስፋችን ነው ።

ቁሬና ከተማ ። ፊለቀ ወልደ ሐና ።

ምድርን ምልዋት ግዚትም (ዘፍ ፩ ፳፰)።

ሁሉን የሚችል እግዚአብሔር ፍጥረታትን ሁሉ በ፮ ዕለታት ፈጥሮ ጨረሰ ሲፈጥርም ሁን ያለው ነገር ሁሉ ሆኖ ይገኛል እንጂ በሥራው ሁሉ ድካም አልነበረበትም ለአሳቡም ተቃራኒ ወይም መሰናክል የለውም ።

እንግዲህ ያልነበረውን አንዳች ነገር ባንድ ደቂቃ አጉልቶ ለማሳየት የሚችል እግዚአብሔር ብቻ ከሆነ ጉጋርዎቻችን የሮጳን ሥልጣኔ በፍጥነት ባገራችን ለማቆም መቻላቸውን በፍጹም እንረዳለን ። ነገር ግን ሰውም ቢሆን ባሳቡና በሥራው ሁሉ ተቀዋሚና መሠናክል የሌለበት ሰው እጅግ የታደለ ነው ።

ለኢትዮጵያ በኵር የሆኑ ታላቁ ንጉሣችን ዳግማዊ ምኒልክ ብዙ ዘመን ተለያይታ የኖረችውን አገር በብዙ ድካም አገናኝተው አንድ ኢትዮጵያ ስላሰኙዋት መታሰቢያቸው ለዘለዓለም አይረሳም ። ከአድዋም ጦርነት በኋላ ያበዳኛው ስም በዓለም ሁሉ ታወቀ ፤ ከአድዋም ጦርነት ጀምሮ አጼ ምኒልክ እቤት እስከ ዋሉበት ቀን ድረስ በሰሎሞን ዘመን እንደ ነበረው ሁሉ ዘመነ መንግሥታቸው የእረፍትና የሰላም ዘመን ነበረ ፤ አሳባቸውም ኢትዮጵያ እንደ ጐረቤቶችዋ እንድትሠለጥን ይባላል ። ያሰቡትን ለማድረግ ኃይልና ሥልጣን ችሎትና ሙሉ ፈቃድ እንዲያስፈልግ የታወቀ ነገር ነው ፤ ነገር ግን ወደ ኋላ የቀረንበትን ምክንያት አላወቅነውም ከዘመኑ አልደረስንምና ዳሩ ግን ያለፈውን ትተን የሚመጣውን እናስብ ፡፡

ቸሩ አምላክ ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱን በገናናው አባታቸው ዙፋን ስላስቀመጠልን ልክ የሌለው ምሥጋና

እናቀርብለታለን፤ ልዕልት ንግሥታችንም አባታቸው የመሠረቱትን አሳብ ለመፈጸም ፈቃዳቸው ሆኖ ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ከመሳፍንቶቻቸው ጋራ ሂደው አውሮፓን ጎብኝተው በመምጣታቸው የኢትዮጵያ ልጆች ለደስታችን ፍጻሜ የለውም፤ ልዑል አልጋ ወራሽ የትምሕርትና የሥራን የፍቅርና ያንድነትን መመላለሻ ጎዳና ጠርገውልን መጡ እንግዲህ የብርሃንና ሰላም ደጅ ተከፈተ። የጥበብ ጮራ በአገራችን ተነዛ። እስከ ዛሬ ድረስ የኢትዮጵያ ልጆች ምድራችን የተሸከመችውን ብልጽግና ሳናውቅ ወርቁንና ብሩን ነሐሱንና ብረቱን ክቡሩን ዕቃና ደንጊያ ሁሉ በእግራችን እየረመረምን በላዩ ያገዳና የሰንበሌጥ ጎጆ እየሠራን በድኅነትና በብልጽግና መካከል እንኖራለን እንግዲህ ግን የምድራችንን ሀብት ለማየት ዓይናችንን እንዲከፍቱልን በልዑል ተፈሪ መኰንን ላይ ሕሊናችንን ሰቅለናል፤ የዕውቀት መሪያችን ልዑል ተፈሪ መኰንን ዋና አሳብና ጥረታቸው ኢትዮጵያ እንድትለማና እንድትሰለጥን መሆኑን በፍጹም አውቀነዋል፤ ይህንም ካወቅን እኛ የኢትዮጵያ ልጆች ይህን መልክም አሳባቸውን በደስታ ለመቀበል ልባችንን ጥሩ አድርገን እናሰናዳው። ጆሮአችን እውነተኛውን ነገር ለመስማት የተከፈተ ይሁን። እጃችን ለሥራ ይንቀሳቀስ የአሳቢዎቻችንን ተቀዋሚና መሠናክል መሆንን ትተን ፈቃደኞች እንሁን ዳተኝነትንና ቸልተኝነትን ትተን ወደተሻለው ዕውቀት ለመድረስ እንሽቀዳደም ምድር ለናንተ ነች ተብሎ ለቀደሙ አባቶቻችን የተነገረው ተስፋ ሁል ጊዜ በፊታችን ይሁን።

ነገር ግን ያለኔ አንዳች ነገር ልታደርጉ አትችሉም ያለውን ቃል አስበን ፈቃድህ ይሁን እያልን ወደሰማይ አባታችን በጸሎት እንትጋ።

አስታጥቄ ወልደ አማኑኤል።

የሀገር ፍቅር።

ትምርት ማለት እንደ ትርጓሜው እውቀት ማግኘት ነው ዕውር ሰው ብርሃኑንና ጨለማውን መለየት እንዳይችል እንዲሁም ያልተማረ ሕዝብ የሚያለማውንና የሚጎዳውን ነገር ለይቶ ማወቅ አይችልምና ፍጻሜው ጥፋት እንደሆነ ጥርጥር የለውም። እስቲ ኤውሮጶችን ቀድሞ በትምርት ሳይሠለጥኑና አሁን በትምርት ከሠለጠኑ በኋላ የሚኖሩትን አኗዋር እንመልከት ቀድሞ ዘመን ዓይናቸው በትምርት ሳይከፈት አንዱ መንደር ካንዱ መንደር ጋራ እርስ በርሳቸው እየተፋጁ የገዛ አገራቸውን እንኳ ጠቅልለው መግዛት ያቅታቸው ነበር አሁን ግን ትምርት የሚባለውን መነጸር ይዘው ለመንግሥታቸው የሚያሠለጥነውንና የሚያጎሰቍለውን መመልከት ከጀመሩ በኋላ አገራቸውን ጸጥ አድርገው አስማምተው የሰው አገርን ይገዙ ጀመር፤ ደግሞ ጃፓንን ከ፶፮ ዓመት በፊት በጨለማ እንዴት እንደነበረና ኋላ ጐልቍ የሌላቸው ልጆች ወደ ኤውሮጳ እየላከ ቢያስተምራቸው እንዴት እንደሠለጠነ አገሩንም አስፍቶ እንደ ኤውሮጳ መንግሥታት ከፍ ያለ ለመሆን እንደቻለ እንመልከት፤ ይህን ትምርት የሚባለውን መነጸር ይዘን ግራና ቀኝ ብንመለከት እኛም እንደነዚህ ሠልጥነን አገራችንን ጠቅልለን ለመያዝ እንድንችል የታወቀ ነገር ነው መንግሥታችንም ይህን አስተውሎ ልጆቹን በትምርት እንዲሠለጥኑ በማድረጉ እምላክን እናመሰግናለን። አገሩ በባዕድ ሰው የተገዛ ሕዝብ ሥሩ ሊወድቅ እንደ ቀረበ ዛፍ ነው። የቅጠሉ ልምላሜና መልኩን ሲያሳምረው የነበረ ኃይሉም ይጠፋል በብዙ ጭንቀትና ሐዘን ከመሬት ለመውደቅ ደርሶ ተጐናብሶ ግርማው እየጠፋ ኃይሉም እየደከመ ይሄዳል ጥቂት ነፋስ ነፍሶ የነካው እንደሆንም ፍሬው ሁሉ ያረግፋል ቀጥሎም ከስሩ ተነቅሎ ይወድቃል። አገሩን የቀማት ሰው በታመመ ወይም ጭንቅ ባገኘው ጊዜ የሚረዳው ጐረቤትና ወዳጅ የለውምና ከገሩ ርቆ ያለመጸናናትና ያለ ረድኤት ይሞታል። በሞተም ጊዜ የሚቀብረውና የሚያለቅስለት ጠፍቶ እንደ እንስሳ ሁሉ ለሰው የሚገባው ክብረት ይቀርበታል፤ስለዚህ ሰው ሁሉ ስላገሩ አንገቱን አሳልፎ መስጠት ይገባዋል።ከሉልና ከዘውድ አብልጦ ለሚወዳት ለአገሩ አንገቱን በመስጠቱም እንዳንድ ሰማዕት ሁኖ ጽድቁን ፈጸመ ይባላል።የተማረ ሰው ይህን ሁሉ እንዲሆን ያውቃልና ያች አንዲቱ አንገቱስ ይቅርና ብዙ አንገትም ቢኖሩት ሁሉንም አሳልፎ ለመስጠት የታመነ ነው ያልተማረ ሰው ግን ሕይወቱን አሳልፎ መስጠት ቀርቶ ባለቤቱ ይኸውላችሁ ኑ ውሰዱ ብሎ ይጠራቸዋል ለዚህ ነገርም ምስክር ትምርት ያልነበራቸውን ኢትዮጵያን ከበዋት ያሉትን ሕዝብ እንመልከት በመልክና በባህርይ የማይስማማቸው ባዕድ ሕዝብ እነሱን ለመግዛት መጀመሪያ ወዳገራቸው በገቡ ጊዜ እንግዶች ስለ ሆኑ ሽቅበቱን መውጣት ቍልቍለቱንም መውረድ ያቅታቸው ነበርና ባላገሮቹ እየተሸከሙ ያወጡዋቸው ነበር ይባላል።እነዚህ ሕዝብ አሁን ከላይ የተናገርነው ምሳሌ ስለ ደረሰባቸው እጅን በጅ ቈረጥሁት እያሉ ያለቅሳሉ ታላቁ ንጉሥ አጤ ምኒልክ ይህ ሁሉ ስለ ተሰማቸው የትምርት ቤት አቁመው ትተውልናል ይህን ማድረጋቸውም ከኔ በኋላ የሚነግሡት ነገሥታት ይህን የተውኩላቸውን ምሳሌ ይዘው ከኔ ይልቅ ትምርትን ያሰፋሉ ስለ ማለት እንደሆን እርግጥ ነው።ስለዚህ ግርማዊት ንግሥታችን አባታቸው የጀመሩትን ነገር ለመፈጸም እምላክ ይገዛቸው የተወደዳችሁ የኢትዮጵያ ልጆች ሆይ ከባርነት ነጻነትን ከድንቍርና እውቀትን ብንወድ ከሁሉ በፊት ትምርት የሚባለውን መክፈቻ መያዝ ያስፈልገናል ለዚሁም ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ያሰሩትን ተማሪ ቤት አይተን እምላክን እያመሰገንን ለትምርት እንድንጣጣር እግዚአብሔር ይርዳን።

ኪዳነ ማርያም አበራ።

ስለ አስበ ተፈሪ አኳኋን።

ጨርጨር ቀድሞ የአረማዊ አገር ነበር ከቀድሞ ጀምሮ እስከሁን ድረስ ክፋትና ስንፍና ጠብና ድንቁርና ይልቁንም የሰው ገንዘብ መቀማትና ያለፍርድ የሰው ደም ማፍሰስ ያለልክ ሰልጥኖበት ይኖር ነበር። አሁን ግን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ጨርጨርን ሊያሰለጥኑ ስለ አሰቡ ፊታውራሪ ተክለ ሐዋርያት በአውሮፓ አገር ብዙ ዘመን ተቀምጠው ዕውቀትን ሁሉ በያይነቱ መርምረው የመጡ ስለሆኑ ጨርጨርን እንዲያሰለጥኑ አዘዟቸው።(የጨርጨርም ዋና

ከተማዋ ቁኒ ንፋስና ብርድ ውርጭ የሰለጠነበት ቦታ ነበር።) እሱን ትተው መጀመሪ ለከተማ የምትሆን መልካም ቦታ አዩና ስሚንም እሰበ ተፈሪ ብለው ሰየሙዋት ። ከተማዪቱም እጅግ መልካም ሁና የተዘጋጀች ቦታ ናት ቅያሱም ካሁን በፊት ማንም ሰው እንዲህ ለመቀየስ አልቻለም ። አሁን ግን ለጊዜው የተሠራው የግንብና የጣራ ቤት የሥራው ማማርና የቅያሱ መተከክል የከተማው አጀማመር ምንኛ የሚያምርና የሚያስደንቅ ነው።በማናቸውም ቦታ እንዲህ ሆኖ የተሰራ ቅያስ አይገኝም ።(ለሚመጣው ዓመት ግን እንኳን ለማየትና ለመስማት እንኳ የሚያስደንቅ ከተማ ሳይሆን አይቀርም ።)እዚሁ እከተማው ውስጥ እንድ ታላቅ ውኃ አለ በውስጡም ብዙ ልዩ ልዩ አታክልት ይገኝበታል ። አታክልቱም ወይን ፣ ብርቱካን ፣ ቡን ሎሚ ትርንጎ ሙዝ ሮማን ይልቁንም የጌሾው አታክልት ተቈርጦ የሚያልቅ አይመስልም ። ይኸን የመሰለ ሌላም ሁሉ ይገኝበታል ።

ድንቁርና ስንፍና ምቀኝነት ያለባቸው ሰዎች ግን እንዲህ ይላሉ ። የጥንቱ ከተማ ቁኒ ምን አለና እዚህ እቈላ ውስጥ ውሀ በሌለበት ቦታ ከተማ ይሰራሉ ሥራቱም ሁሉ እንደአውሮፓ አገር በልክ በልክ ነው ። ለሥራም በሰዓት ግቡ በሰዓት ውጡ ይሉናል ሙቀቱም አያስቀምጥ ውሀም የለ እያሉ ይተማማሉ የአውሮፓ ሰዎች እንደምንሰማውና እንደምናየው ሁሉን ነገር በልክ በልክ ቢያደርጉ ክብረዋል እንጂ አልተዋረዱም ።

ታኅሣሥ ፴ ቀን ፲፱፻፲፯ ዓ ም በታተመ ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ በ፪ኛው አንድ ሠራተኛ ሥራ አስተካክሎ የሚያውቅ ቢገኝ ሥራውን መሥራት አይችልም እንዳለው በታዘዙት ትእዛዝ የእውቀት ሥራቸውን በየዓይነቱ ሲያሰሩና ሲሠሩ ሥራውም እየተቃና እያማረ ቢሔድ በብዙ ውዝግብና ጭቅጭቅ ሥራቸውን ሊያስፈቷቸው ቢነሱ የኢ መ አ ወ ተፈሪ መ ሙሉ ሥልጣን ሰጥተዋቸው ነበረና የዕውቀታቸውን ብርሃን ወደፊት እያበሩ አስኬዱት እንጂ የሰነፎች ሐሳብና ምክር አልተፈጸመላቸውም። እነሱም ምክራቸው ተፈጽሞላቸው ቢሆን በዚህች አገር የሥልጥንና ትምህርት እንዳይቆም መከልከላቸው መሆኑን አላወቁትም።አሁን ወደ ፊት ግን የከተማውን ማማርና የሰውን ሥልጥንና በተመለከቱት ጊዜ በራሳቸው ጥፋት ራሳቸው ሳይፈርዱ አይቀሩም ።

ቢተው ጽጌ ።

በቴሌግራም የመጣ ቃል ።

አዲስ አበባ ፳ ሚያዝያ ፲፱፻፳፭ የ ፱ ሚያዝያ ፲፱፻፲፯ የለት ወሬ ።

ሮማ ።የጃራቡብን ነገር በስምም ለመጨረስ የኢጣልያና የምስር መንግሥት ውል ሊያደርግ ነው ተብሎ ከውጭ አገር ጋዜጠኞች እንደተወራው የኢጣልያ ሕዝብ ያስታውቃል ። የጃራቡብን በረሃ ለኢጣልያ መስጠት ስለተከለከለ በሁለቱ መንግሥታት መከከል የታሰበውን ውል መዋዋል እስከጊዜው ድረስ ተተውታል ።

ከታኒያ ።ስላንድ አገር ዋኖች ሹማምንት ለመሾም የተሰበሰቡበት መንግሥትና ሚኒስትሮች ዴፑታ ሁሉ አቡኑም ስለ ቢክቶሪዮ አማኑኤል ፳፭ኛውን ዓመት ግዛቱን በዓል አድርገው በማክበር ሳልን የመሳሰለ በሽታ ለያዛቸው ልጆች መታከሚያ ትኒሽ ሆፒታል በቢክቶሪዮ አማኑኤል ስም የተጠራ ለማቆም ቆረጡ።

ፓሌርሞ ። ከየፓሌርሞ ክፍሎች ጋራ ከዚያች ያሉ የእንግሊዝ መንግሥት ወገኖች ቶልሻ ገጠሙና የፓሌርሞ ክፍሎች አሸነፉ ። ስለዚህ የእንግሊዝ ወገኖች ከዜሮ በታች ሶስት ጊዜ ዝቅ አሉ ።

ፓኒሪ።ፔንለበ ያቆመው አዲሱ የምስጢር ቤት በጦር ጊዜ የሆነውን ነገር ሁሉ መዝገብ ያጋር ብሪያን የገንዘብ ክፍን የትምሕርት ቤት ዱሞንድን እኒህን ስስቱን ሾሙ ፐቲ ፓሪዚዬን እንደሚያስታውቀው አዲሱ የምስጢር ቤት ተተክሏል ከመተከሉ በፊት ብሪያንና ከዩ ይመካከሩ ነበርና እንዳልተስማሙ አመለከቱ ክርክሩ በጣም በርትቶ እንደነበረና የስምምን ነገር ሁሉ ለመበታተን ቀርቦ እንደነበረ ጋዜጣ ያስታውቃል ግን በፍጥነት አገራቸውን የሚጠቅመውን ነገር ስላሰቡ በመጨረሻው ሙሉ መስማማት ተገኘ ስለዚህ አዲሱ የምስጢር ቤት ተተክሎ እሚኖር ነው ።

ሶፊያ። ስለ አንድ ዴፑቴ ቀብር ከቤተ ክርስቲያን ከተሰበሰቡት ሰዎች የቤተ ክርስቲያኑ ግድግዳ ልስኑ ተቀርፎ ወድቆ ስስት ታላላቅ ሚኒስትሮች አቆሰለ ። ስላስተዳደር የወጣውን አዲስ ትእዛዝ አገሮች ሁሉ በጸጥታ ተቀበሉት ከቤተ ክርስስቲያኑ ውስጥ በሆነው ድንገተኛ አዲስ ከሞቱት ሰዎች የዘበኞች አለቆችና መኳንንቶች ዴፑቴም አሏቸው ።

የሚያዝያ ፳ ቀን ምንዛሬ ።
ፓሪስ ፻፳፱ ፹፯ ።
ሎንዶን ፻፲፮ ፫፻፶፬ ።
ኒዩ ዮርክ ፳፬ ፫፻፳፫
ወርቅ ፩፻፲፱ ፵፪ ።

አዲስ አበባ ፳፩ ሚያዝያ ፲፱፻፳፭ የ፲፫ ፲፱፻፲፯ የለት ወሬ

ሮማ፤ስለ ሁለተኛው የሕዝቡ ሁሉ ምክር ዛሬ በእኩል ቀን ከበኔጽያ በታላቁ አዳራሽ ተሰብስበው ነበር ። ብዙ እንደራሴዎች መጡ፤በመጀመሪያው ምክር ስለ እርሻ ማኅበር የሚመጣውን ገንዘብ ነገር ተከራከሩ ። በሁለተኛው ምክር ስለ ምንዛሬ ማቆም ብርቱ ክርክር ሆነ የሆነውን ነገርና የምክሩን ፍጻሜ አለቆች ነገ ለሕዝቡ ያስታውቃሉ ። ከዚህ በኋላም የኢጣሊያ የምክር ቤት ከውጭ አገር ለመጡት እማከሮች መዓርግ ከትልቁ አዳራሽ ቅጥር ከታክልቱ መከከል ቻይ አቀረበላቸው ሙሶሊኒና የምክሩ ፕሬዚዳንቶችም ወደ ቻዩ መጡ የውጭ መንግሥታት እንደራሴዎች ሙሶሊኒን አክብረውት አብረው ይነጋገሩ ነበር፤የምክር ቤቱ በትልቁ አዳራሽ አማከሮቹን ሁሉ በክብረት ተቀበላቸው ።በምክሩም ሚኒስትሮች ሁሉና ፕሬዚዳንቶች ታላላቅ ሰዎች የምክሩ አለቆች፤ማኅበረተኞች ሁሉ ተሰብስበው ነበር ።

ሞጋዲሺዮ ፡ከዱካ አብሩሲ አገር ቤት ስለ ተተከለው የጥጥና የሌላም በያይነቱ የሆነ ዘር ዘይት ማውጫ መኪና ከፕሬንሱና የቅኚ አገር አለቃ ፊት ትልቅ በዓል ተደረገ ። ይኸውም መኪና በ፩ ሰዓት ፲፻ ኪሎ ዘይት የሚያነጥር ነው ሥራውም ከሁለት ተጠባባቂዎች ነጮች በተቀር ባገር ልጆች ብቻ ይሠራል ።

በልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ።

መጀመሪያ ዓመት ፤ ቍጥር ፲፱ ።
1re ANNÉE № 19

ሐሙስ ሚያዝያ ፳፱ ቀን ፤ ፲፱፻፲፯ ዓ ም ።
JEUDI 7 MAI 1925

ብርሃንና ሰላም

LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

የጋዜጣው ዲረክተር ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲረክተሩ ያስታውቁ ።

የራሱን ጉዳይ የሚያሳትም ሰው ዋጋውን እየከፈለ እናትምለታለን ።



ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያን ልጆች ለማስልጠን ያቆሙት ተማሪ ቤት ።

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ለኢትዮጵያ ይሆን የተማሪ ቤት በገንዘባቸው ሠርተው በረከት ሲያቀርቡ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን በጉባኤ ተናገሩ ።

የተወሰነ ቦታ የሌለህ በሁሉ የመላህ አምላካችን ሆይ በፈቃድህ
ያስገመርከኝን ያስፈጸምከኝ ይህንንም እንድናገር
የፈቀድክልኝ ምሥጋና ላንተ ይሁን ።

ስለኢትዮጵያ ታላቅነትና ቀደምትነት ይልቁንም በአረመኔ ተከባ ስለሃይማኖቷና ስለነፃነቷ እየተጋደለች የቆየች መሆንዋን እንኳን እኛ ገንዘባችን ገንዘቧና የውጭ አገር የዓለም ሕዝብ ሁሉ ያገኙን መልክምነት የታሪኳን ታላቅነት በመጽሐፍም በቃልም ሲናገሩት የምንሰማው ነው ። ነገር ግን ለኢትዮጵያ ሆነች ነው እንጂ ነበር ምን ይጠቅማታል ።

በመንግሥታቸው ጽናት ባኗኗርዋቸው ሥርዓት ፍጹም ተስፋ እንዳላቸው የዓለም ሕዝቦች ሁሉ በአፍሪቃ ነፃነቷን ይዞ ለቆየችው ለኢትዮጵያ የምትደረጅበት ለመንግሥቷ ጽናት ፣ ለሕዝቧ ድሎት የሚሆናት ዕውቀትን ፈልጎ አግኝቶ ሥራ መሥራት ነው ። ሥራም ለመሥራት አስቀድሞ መማሯን ማበጀት ነው ።

ለኢትዮጵያ ነፃነትና ጽናት ወሰንዋን ጠብቆ አሳፍሮ አስከብሮ ለማኩራትና የሕዝቧ ልብ የታመነ ኃይል እንዲኖረው ለማድረግ መማሯ ትምሕርት መማር ነው ። ከዚህም ቀደም ሕዝባቸው በዕውቀት እንዲሠለጥን ዳግማዊ አጼ ምኒልክ የተማሪ ቤት እንዳቆሙ ሰው ሁሉ የሚያውቀው ነው ። ለመማርም ትጋትና ቅን ልቡና ያስፈልጋል ።

ተማሪ ቤት ለማቆምና ልጆቻቸው ያልሆኑ ተማሪዎችን መርዳት ልጆቻቸውንም እንዲማሩ ማድረግ ኢትዮጵያን ለሚወዱ ሁሉ ይገባል ። ነገር ግን አሁን ማንም ሰው ሲጠይቁት አገሬን ኢትዮጵያን እወዳለሁ የማይል ሰው የለም ። ይህ እስካሁን ያፍ ልማድ ብቻ ነው እንጂ ወዳጅ የሚሉትን ሰው በችግሩ ከል- ረዱት በተጨነቀ ጊዜ ካላደረሱለት የወዳጅነቱ ምልክት እምን ላይ ነው ።

አሁንም ለሀገሬ ለኢትዮጵያ ወዳጅ ነኝ የሚል ሰው ሁሉ የወዳጅነቱን ምልክት ለማሳየት ለተማሪ ቤት መርዳትና የሚቻለውም ተማሪ ቤት በመሥራት ልጁን ማስተማር የሚገባ ነገር ነው ። ይህነንም የሚያደርጉ ሁሉ የውነት የሀገራቸውን ፍቅር ገለጹ ማለት ነው ።

የልጆቹንና የወገኑን መማር የሚወድና ለተማሪ ቤትም የሚረዳ ሰው መጀመሪያ ራሱ ይጠቀምበታል ። ሁለተኛም በልጁ በወገኑ ጥፋት ሳይጸጸት ደስ ብሎት ይኖራል ሶስተኛም ለሀገሩ የውነተኛ ፍቅር እንዳለው ይገልጽበታል ።

የእግዚአብሔርን ትእዛዝ የማይፈጽምበት ከሰው ፍርድ የማያመልጥበት የእውነተኛ ባርነት እግዚአብሔር ሳያዳላ የፈጠረውን አእምሮ ሥራ ማስፈታትና ለድንቁርና መገዛት ነው ።

እናንተም በዚህ በተማሪ ቤቱ ዛሬ የሰበሰባችሁ ልጆች ወደ ፊትም በተማሪ ቤቱ የምትገቡ ሁሉ የምነግራችሁ ዕውቀት ለሰው የምትጠቅም እንደ ሆነች በብዙ መጽሐፍ እንደ ተጻፈ ታውቃላችሁ ወደ ፊትም የምትማሩት ነው ። ዕውቀት የተጨበጠች ማንም የማይወርሳት ገንዘብ ናት የሰማያዊንም የምድራዊንም አዋጅ የማታስፈርስ ፣ ከጥፋትም የማታደርስ ሚዛን የሌላት አልማዝ ናት ። በሰው ልብ ያልታሰበ የእግዚ- አብሔርን መንግሥት የምታስወርስ፤በመከራም ጊዜ ጠበቃናትና እግዚአብሔር እንዲህ ለተባለች ጥበብና ዕውቀት ያብቃችሁ ።

ይህችንም የዕውቀት ምግብ ሰጥታ የምታሳድጋችሁን ተማሪ ቤት በጥበብ አድጋችሁ በአእምሮ በምትጐለምሱበት ጊዜ እግዚአብሔር እንደ እየእድላችሁ በሚሰጣችሁ ዕውቀት የሀገራችን መማሯ ናትና እንዳትጠብ እንድትሰፋ ። እንዳትወድቅ እንድትበረታ እንድትረዷዋት እለምናችኋለሁ ።

ይህቺ ዕለት ዛሬ ለኔ ምን ያህል የደስታ ቀን እንደሆነች ልቤና ፈጣሪዬ ነን የምናውቀው እግዚአብሔርም ቢያድለኝ ይህች ተማሪ ቤት መከፈቷን ዓይቼ ደስ እንዳለኝ ተምራችሁ ለሀገራችሁ መርዳትን ፣ በኢትዮጵያ ትምህርት መስፋቱንና የተማሪ ቤት መብዛቱን እንዲያሳየኝ እመኛለሁ ።

በአውሮፓ አገር በታላላቅ ተማሪ ቤት ብዙ ብዙ ተማሪዎች የሚማሩበት የሚያድሩበት እንደተሠራ ዓይቻለሁ ። ይኸውም በዕውቀት መማሪያነት ገንዘብ አግኝተው አሰፋትና ሠሩት እንጂ ምንም ሀሳቡና ምኞቱ ታላላቅ ሥራ ለመሥራት ቢሆን ባንድ ጊዜ ለመፈጸም የሚቻለው የለም ።

እንደዚሁ በትንሽ በትንሽ እየተጀመረ ከታላላቅ ሥራና አገር ከመጥቀም ይደርሳልና መቶ ሺ ተማሪ ለመባል ቁጥር ከ፩ እንዲጋርምር ። ኃያ ሺ ተማሪ ቤት ለመባል ቁጥር ከ፩ እንዲገምር ። በኢትዮጵያ ላሉ ተማሪዎችና የትምህርት ቤቶች በቁጥሩ ተራ ውስጥ የምትገቡ እንደሆናችሁ የተረገጠ ነው ።

አሁንም ይህች ተማሪ ቤት ምሳሌ ናትና በኢትዮጵያ ከዚህ በላይ ተናግሬ እንደተመኘሁት እንድትሆን ጥርጥር የለበትም ።

የተማሪ ቤት የመረረችውን ያህል ትጣፍጣለችና ያላችሁትም የምትመጡትም ምክሬን ሰምታችሁ ለተማሪ ቤቱ ያቆምሁትን ደንብ እንድትፈጽሙ እለምናችኋለሁ ።

በዚችም ተማሪ ቤት ያቆምሁት የውጭ ቋንቋና ጥበብ ብቻ አይደለም ፤ የሀገራችንም ቅዱሳት መጻሕፍት ወልድ ዋህድ ሃይማኖት የሚነገርበት ናት ።

የሀገሩንም ትምህርት ጽሕፈት ቋንቋ እንደሚገባው የማያውቅ የውጭውን እማራለሁ የሚል ምሳሌው ቀዛፊ እንደሌለው ታንኳ ነው ። የሀገራችንን ዕውቀትና ትምህርት ተግታችሁ ተማሩ ።

መጨረሻ የምነግራችሁ ቅዱስ ዳዊት እግዚአብሔር የአምር ሒሊናሆሙ ለጠቢባን ከመ ከንቱ ውእቱ ያለው በተማረው መጠን አሳቡንና ዕውቀቱን ወደ ተንኰል የሚመራውን ነውና እውነተኛውንም ጥበብ ለሚፈልግ ሰው ጌታ በወንጌል ፭ ወርቅ የሰጠው ባሪያ አስር አድርጎ ቢመልስ እንደተመሰገነና በብዙ አህጉር ላይ እንደተሾመ እንድትሆኑ ።

፩ወርቅ የሰጠው ባሪያ ቀብሮ አስቀምጦ ያንኑ ቢመልስ እንደ ረገመውና በስቃይ እንዲኖር እንደ ተፈረደበት እንዳትሆኑ እለምናችኋለሁ ።



ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ።

አሁንም የልበናችሁ መሠረት እግዚአብሔርን በመፍራት አገርን በመውደድ የተጠመደ እንዲሆን እግዚአብሔር የሁላችንንም የልባችንን መሠረት በዚህ ያድርገው ብዬ ርህሩህ ፈቃዱን እለምናለሁ ።

እግዚአብሔር ንግሥተ ነገሥታትን ይጠብቅ ።
ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር ።ኢትዮጵያ ሕያው ትሁን ።

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ስለ ተማሪ ቤቱ ተናግረው ሲጨርሱ ዳር እስከዳር ተጨበጨበ በዚያ የነበርን ሁላችንም ደስታችን እጅግ ታላቅ ሆነ

በሚመጣውም ጋዜጣችን የተማሪ ቤቱ ሹም የኃኪም ወርቅነህን ንግግርና ሌላ ቃል በሰፊው እናትምላችኋለን ።

ኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ፡

Discours prononcé, le 2 mai 1925, par Son Altesse Imperiale Teferi Makonnen, Héritier du Trône d'Ethiopie et Régent de l'Empire, à la cérémonie de la remise solennelle á la Nation Ethiopienne de l'Ecole qu'Elle a fait construire á ses propres frais.

O notre Dieu, dont le royaume n'a pas de limite et qui est partout.

Je rends grâce à Toi pour m'avoir permis par Ta volonté d'accomplir ce que j'ai commencé et de prononcer ce qui suit :

Pour la grandeur et l'ancienneté de l'Ethiopie et notamment pour les luttes qu'elle a soutenues contre les païens, qui l'entouraient pour conserver sa religion et son indépendance, non seulement nous qui sommes ses biens et elle le nôtre, mais nous avons entendu tous les peuples de l'univers proclamer verbalement et par écrit la grandeur de son histoire et la prospérité du pays. Mais il serait plus raisonnable pour l'Ethiopie de dire qu'elle est, au lieu de dire qu'elle a été. Pour arriver au même degré intellectuel que les autres peuples de l'univers qui vivent dans la confiance de la puissance de leurs gouvernements et sous l'ègide des lois de leurs pays, il est nècessaire d'acquèrir l'instruction pour travailler à la puissance de l'Ethiopie, qui, en Afrique, a conservé son indépendance, et à la prospérité de son peuple. Pour pouvoir travailler, il faut préparer avant tout les armes nécessaires. L'instruction est indispensable pour sauvegarder l'indépendance de l'Ethiopie, pour faire respécter ses frontiéres et les rendre inviolables, pour la nimber d'une auréole de fiertè et pour rendre le peuple conscient de sa force.

Tout le monde sait que c'est pour dèvelopper l'intelligence de son peuple que Sa Majesté l'Empereur Menelick II a fondé une école.

pour s'instruire, il faut avoir la bonne volonté et la persévérance C'est un devoir pour tous ceux qui aiment l,Ethiopie de fonder des écoles d'aider les enfants des autres et de forcer les leurs à s'instruire .Pourtant si on interroge n'importe qui il ne se trouvera personne pour dire qu'il n'aime pas l'Ethiopie; ce sentiment n'a été jusqu' aujourd' hui qu' une habitude irréfléchie. Où serait la preuve d' amitié si on ne vient pas en aide à celui que l'on dit ami? quand il est dans

il ne suffit pas de proclamer son amour pour l'Ethiopie; il faut lui en donner la preuve ; c' est une obligation sacrée surtout pour ceux qui en ont les moyens de fonder des écoles, de les doter des subventions et ainsi donner de l'insctruction à leurs enfants. Ce sont ces actions qui constituent un témoignage éclatant du patriotisme. Celui qui aimerait à faire donner l'instruction á ses enfants et á ses compatriotes et à encourager les écoles il sera le premier à en profiter Deuxièmement il vivra heureux parce qu'il n' aura pas à craindre la perdition de ses enfants et de ses compatriotes par manque d' instruction. Troisiémement, il fera preuve du plus ardent amour pour la patrie.

L' homme qui ne développera pas son intelligence, dont Dieu l'a gratifié, et obéira à la voix de l' ignorance n'est pas à même d'observer la loi de Dieu ni d'échapper à la justice humaine ; c'est une véritable servitude dans laquelle son ignorance l'aura plongé.

Vous, enfants, que j'ai réunis aujourd' hui dans cette école et tous ceux qui y entreraient à l'avenir, vous savez qu' il est écrit dans plusieurs livres que l'instruction, dont Je vous parle, est profitable a l'homme qui la possède. La science est un bien personnel que nul ne peut hériter L' instruction est un diamant précieux et inéstimable qui préserve du mal, empêche la violation des lois du ciel et de la terre et ce que le coeur humain est incapable de concevoir fait hériter le royaume de Dieu ; dans les difficultés de la vie, elle est le bouclier protecteur et Je souhaite que le bon Dieu vous fasse acquérir cette science.

Lorsque grandis dans la sagesse vous aurez atteint la mûre intelligence que Dieu vous a accordée snivant votre chance et qni est l' arme de notre pays, Je vous prie d'aider au développement et au rayonnement de cette école qui vous a élevés en vous nourrissant de la science,

Dieu et mon cœur seuls savent l' intensité de la joie que j' éprouve aujourdhui. C' est un grand bonheur pour moi d' assister à l' ouverture de cette école et je souhaite vivement de vous voir instruits pour aider votre pays et contribuer au développement de l' instruction et à la creation de nombreuses ècoles en Ethiopie.

j' ai vu en Europe de nombreuses écoles fréquentées par de nombreux élèves externes et internes Ces écoles ont été fondées et développées dans les cours des siècles grâce à l' argent acquis par l' arme de l' intelligence. Il est impossible à l'homme qulle que soit sa puisanec d'esprit d'accomplir de grandes choses en un court espace de temps. C'est en procédant petit à petit que l'on arrive à de grands résultats et ainsi à servir sa patrie.

Pour dire 100000 élèves il faut commencer á compter par un ; pour dire 200000 écoles il faut commencer à compter par une ; il est indiscutable qu 'il en sera de même en Ethiopie en ce qui concerne vous autres élèves et les écoles.

Je vous donne cette école en exemple, et je ne doute pas qu' il n' en soit pas ainsi en Ethiopie comme je l' ai dit et souhaité plus haut L' ècole deviendra douce autant qu' elle a été amère Je prie, vous qui êtes présents et ceux qui viendront, de vous conformer aux réglements que j'ai établis pour Mon école.

Ce n' est pas seulement pour enseigner les sciences étrangères que j' ai fondé cette école mais aussi pour enseigner les livres saints de notre pays et la foi du fils unique de dieu.

Celui qui veut apprendre les sciences étrangères avant [illegible] et la langue de son pays, ressèmble à une barque qui n' a pas de rameur Appliquez—vous avec ardeur à apprendre les sciences de votre pays.

Je vous adresse un dernier mot. comme l' a dit saint David "Le Seigneur connait que les pensées de l'homme sage ne sont que vanité." Ces paroles ont èté dites pour chaque élève qui dirige sa pensée et son intelligence vers le mal

Celui qui cherche la véritable sagesse n' a qu'à sen rapporter à ces paroles de l' Evangile ; " le serviteur qui a reçu de son maitre 5 pièces d' or lui ayant rendu 10, il en a été remercié et nommé à gouverner plusieurs pays ; le serviteur qui a reçu 1 pièce d or l' ayant enterrée, il a étè maudit et condamné à vivre dans les tortures. Je vous prie de suivre l'exemple du bon serviteur et non du mauvais.

Je prie la miséricorde de Dieu afin que la base de votre conscience ainsi que de nous tous soit la crainte de Dieu et l'amour de le patrie

Que Dieu protége le gouvernement royal
Que *l*'Ethiopie soit éternelle
Que' l' Ethiopie soit immortelle

መጀመርያ ዓመት ፤ ቍጥር ፳ ።
1re ANNÉE № 20

ሐሙስ ግንቦት ፮ ቀን ፲፱፻፲፯ ዓ ም ።
JEUDI 14 MAI 1925

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ ቢገዛ ለፈለገ በ፬ መሐልቅ ይሸጣል ።

የጋዜጣው ዲሬክተር ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወ ፤ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የራሱን ጉዳይ የሚያሳትም ሰው ዋጋውን እየከፈለ እናትምለታለን ።

የሰላም ብዛትና የብርሃን መድመቅ ።

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ ሰው ጥቅም እንዲያገኝ ብለው ተማሪ ቤት ስለ ከፈቱለትና ከአእምሮው እንቅልፍ በብርሃንና ስላም ስለ ቀሰቀሱት ደስ ብሎታል ። ስለ ደስታውም ብዛት በቃል የተነገረውን በጽሕፈትም የተጻፈውን ከብዙ ደብዳቤ ላይ አግኝተነዋል ።

ይህ ስለሆነልን ኢትዮጵያን በእውቀትና በትምሕርት ሥልጣኔ ወደፊት እንዳትገፋ ይጋርዳት የነበረው ክብ አሮጌ የስንፍና ግድግዳ በንድ ወገኑ ፈረሰና ኢትዮጵያውያን ወደ ሥልጣኔ የሚያደርሰውን መንገድ አግኝተው በፍጥነት እንዲራመዱ ተስፋ እናደርጋለን ። ግን መንገዱ እንዳይጠብ ኢትዮጵያውያን ሁላችን የበሰበሰውን ክብ ግድግዳ እስተጣራው እጅ በእጅ ተጋግዘን ብንነቅለው እርሱ ከልሎ ያስቀበረንን [illegible]

እንግዲህ ለጥቅማችን የተገኘውን መንገድ በየመዐዝኑ እንዲዘረጋ የሚያግደውንም መመንጠር የሚቻላችሁ የየአውራጃው ገዦዎች ሕዝባችሁን የሚከልለውን አሮጌ የስንፍና ግድግዳ ከዙሪያው እንዲያስለቅቅና በትምሕርት ብርሃን በቀና ጎዳና እንዲመላለስ ወደ ሚያስፈልገው የዘመኑ ሥልጣኔ ደረጃም እንዲደርስ አፋጥኑት እርዱት ።

እንዲህ ብታደርጉ በጎ ነገር ለጀመሩላችሁ ወደፊትም የኢትዮጵያውያንን ጥቅም ለሚያስቡ ለልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ትልቅ ደስታና እርዳታ ፤ አገራችሁንም የመውደዳችሁ መግለጫ ነው ። አገሩን የሚወድ የመላውን ሕዝብ ጥቅም እንጂ የራሱን ጥቅም ብቻ አያስብም ። የማያልፈውንም ሹመት ያዙ ማለት ከሞታችሁ በኋላ ሲጠራ የሚኖረውን ስም ፈልጉ ።

ላገራችን የሚያስፈልጋት የሚጠቅማትም ትምሕርት ነው በኢትዮጵያ ትምሕርት ከገነነ ፤ ስንፍና ከበነነ ሁሉም ይቀናል እንድንሸነፍ የሚዋጋን ረቂቅ ጠላታችን ኢሸነፍ ጀምሮአልና ጨርሰን ድል እናድርገው ።

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ያቆሙት ተማሪ ቤት በተመረቀ ጊዜ ሐኪም ወርቅነህ የተማሪቤቱ ሹም የሚከተለውን ቃል ተናገሩ ።

ያገራችን ልጆች በትምርትና በመልካም አስተዳደግ እንዲያድጉ አስበው ይህንን ተማሪቤት በትልቅ ቸርነትና ለጋስነት ባቆሙ በልዑል አልጋ ወራሻችን ስም ለዚሁ ተማሪ ቤት ተማሪዎች እንኳን በደኅና መጣችሁ ብዬ ምርቃን ላቀርብላችሁ እንዲፈቀድልኝ እለምናለሁ ። ወዳጆቼ ሆይ ፤ ትምርት ለሕዝባችን ዋና የሚያስፈልገው ነገር ነው ። ስለዚህ አስራ ሁለት ወይም አስራምስት ሚሊዮን ለሚሆኑ ላገራችን ሰዎች አንድ ፤ ወይም ሁለት ትምርት ቤት ምንም አይበቃቸውም ። ግን ኃብታሞችና [illegible] [illegible] [illegible] ክፍል ለልጆችና ለሴት ልጆች የሚሆኑ ብዙ ተማሪ ቤቶች እንዲከፈቱልንና ከገራችን ልጆች ቢያንስ ቢያንስ ጥቂት ሺ ልጆች የትምሕርት እድል እንዲያገኙልን ተስፋ እናደርግ ። ባገሩ ስፋትና ቁመት ሙሉ በንዲያውም የሚማሩበትን ተማሪቤት ማቆምና ማኖር ልጆችና ሴት ልጆች ሁሉ ትምርት እንዲያገኙ ማሰብ ፤ በውነት የመንግሥት ሥራ ነበር ግን ይኸ ሥራ ለመንግሥታችን የሚገባ ሥራ መሆኑ ስላልተገለጠላቸው እጅግ አዝናለሁ ። ከአያሌ ዘመን በፊት የኢትዮጵያ ሕዝብ በዘመኑ በነበረው ብልሃትና አውቀት የሰለጠኑ ነበሩ ግን ልዩ ልዩ በሆነ አኳኋን እየተበላሸን ሄድንና ዛሬ ጭራሽ ወደኋላ ከሉቱ ሕዝቦች ጋራ ነን ። ወደኋላ መሆን ማለት ዕውቀት ትምርት ኃብትና ሥልጣን ማጣት ማለት ነው ። ስለዚህ በሌላ ሕዝብ ፊት ከዘሬታ አናገኝም ለራሳችንም ዓርነት ኑሮ ያስፈራናል የዓለም ታሪክ ለማያውቁ የፍጥረትንም ሕገጋት ላላስተዋሉ ሕዝባችን ባሁኑ ኑሮዋችንና ባለፉት ሶስት መቶ ዓመት አነዋወር መኖር መልካም እንደሆነና የውጭ አገሮች በነገሩ መካከል ሳይገቡ

የነገሩንም አኳኋን ልብ ሳያደርጉት ሊቀር እንደሚቻል ሁኖ ይታያቸዋል ። ይህ ግን የኛ ትልቅ ስሕተት እንደሆነ አስረግጥላችኋለሁ ። እንዴት ብትሉ ፤ ጸንቶ የቆመ የፍጥረት ሕግ ነውና ማናቸው ሰው ወይም ሕዝብ ባለው አኳኋን ብዙ ጊዜ ሊቆይ አይችልም ። ወይ ወደ ፊት ይገፋል ወይም ወደ ኋላ ይቀራል ። ወደኋላ የቀረ እንደሆነ ግን ከርሱ የበለጠ ሥልጣን ባለባቸው ሰዎች ይሰጥማል ሩቅ ወዳለ ምሳሌ እንዳንሄድ የጋሎች የወላሞች ባዙሪያችን ያሉ የሌሎችንም ጥቁሮች ምሳሌ እስቲ እንመልከት ። በምን ምክንያት ነው ልንገዛቸው የተቻለን የኛን ያህል ብልሆች የኛን ያህል ኃይለኞች የኛን ያህል የሠለጠኑ ባለመሆናቸው ብቻ ነው ። ይኸ ሕግ በዓለም ሙሉ የጸና ነው ወይም በፍጥነት ወይም በመዘግየት ከኛ የበለጠ ብልሀትና ዕውቀት ካላቸው ሕዝብ ጋራ ስንቃረብ ይህ ሕግ በኛ ዘንድም እንዲሠራ እንዲቀጻ ባይመስለን ግን ፤ ሃሳባችን ትክክል እንዳልሆነ እርግጥ ነው ። የበለጠው ብቻ ይኖራል የሚለውን ሕግ ሰው እኖራለሁ ብሎ ይታገላል እንደሚል ሕግ ያህል የማይነወጥ ጥና ነገር ነው ። በዚህ ዓለም ከሆነ ። እንደሌሎችም ሰዎች ከሆን እኛም ከዚህ ሕግ እንደማናመልጥ እርግጥ ነው ። እናመልጥበታለን ብለን እስከ ማሰብ ደርሰን ብንሞኝ ግን ውለን አድረን የሚያሳዝንና የሚያሳጽት መንቃት እንነቃለን እንግዲህ ወዳጆቼ ሆይ አሁን ጊዜ ሳለን እንንቃ ፤ ጊዜ ሳያልፍም እንታጠቅና እንስራ ። ምኞት የሞላበትን ፊታችሁ ብርሃንና ትምርትን ሲናፍቅ ማየቴ እናትና አባቶቻችሁ የትምሕርት ጥቅም እንደሚያስፈልግን ማወቃችሁን ይመሠክርልኛል ደስ ያሰኘኛል በተወደደችው አገራችን ለሚሆን ጊዜ እንደሚመጣም ተስፋ ያስደርገኛል የያፓን ሰዎች የሕዝባቸውን ሕይወትና ነፃነት ከጥፋት ያዳኑ ይህንን ዋና የሚያሻቸው ነገር በጊዜ ስላወቁት ነው ።

ስለ ኑሮዋቸውም ታግለው ድል ለማድረግ ቢፈልጉ የኤውሮጳችን እውቀት ማወቅ እሱም በቶሎ ማወቁ ግድ እንደሆነ ተረድተው በትጋት መስራት ጀመሩና በዓለም ታሪክ ሌሎቹን ሕዝብ ለመድረስ ብዙ ዘመን ወዳስፈለጋቸው ደረጃ እርሳቸው በስልሳ ዓመት ውስጥ ደረሱበት ዛሬ ያፓኖች እንደማናቸው የኤውሮጳ ሕዝብ ያህል ወደ ፊት ያሉ ኃይለኞች የሠለጠኑ ናቸው ። ይህንን የሚያስደንቅና የሚያስመሰግን የድፍን ሕዝብ ወደፊት ማየት ጥበብና የሀሳብን መቁረጥ አርአያ እንከተል የሚያብብ የተማረ ኃይለኛ ሕዝብ እንድንሆንና የጥንት ነፃነታችንን ለመጠበቅ እንድንችል ጉድለታችንንና ድንቁርናችንን በፍጥነት እንምላው ። ከሕዝባችን አንዳንድ ሰዎች እግዚአብሔር አሳልፎ አይሰጠንም እሱ ይጠብቀናል ይሉዋችኋል ግን እግዚአብሔር ራሳቸውን የሚረዱን ብቻ እንዲረዳ እውቀትን የሚንቁም የሚገባውን መጠንቀቅ እንደማይጠነቀቁና ጥፋትና መቸነፍ የተፈረደባቸው እንደሆኑ እነግራችኋለሁ ። እንግዲህ ልጆቼ ሆይ እኔ የምመክራችሁ በውነት የተማሩ ማለት በቋንቋ በታሪክ በጂዮግራፊ በሒሳብ በዕውቀት መልካም መሠረት ያላቸሁ እንድትሆኑ ሌትና ቀን እንድትጣጣሩ ነው እንጂ ያንድ የውጭ አገር ቋንቋ አፍአዊ እውቀት ይዛችሁ እንደ አነጋገሬ ለኑሮዋችሁ የሚበቃ ለማግኘት እንዳታስቡ ነው ይልቁንም ከፍ ያለ የመልካም አካሔድና የሃይማኖት ትምህርት ያዙ ። በዚህ ካላችሁ ልጆች ብዙዎች በጣም ትልልቅ ሆነዋልና አሁን ከመጀመሯ ልትጀምሩ ግድ ተሆነ ከፍ ወዳለ ትምህርት ቤት መዓርግ አትደርሱም ይሆናል ብዬ እፈራለሁ ። ግን ቢያንስ ግማሻችሁ ከትንሾቹ የትምርት ጓደኞቻችሁ የበለጠ በመጣጣር በከንቱ ያሳለፋችሁትን ጊዜ እንድትተኩት ተስፋ አደርጋለሁ ።

እንግዲህ ነገሬን ስጨርስ እናንተ ትልልቆች በነገራችሁና በካሔዳችሁ ልትጠነቀቁ እለምናችኋለሁ ። ይህ ደግሞ በምግባራቸው እናንተ አላፊዎች ስለ ሆናችሁላቸው ስለ ትንንሾቹ የትምህርት ጓደኞቻችሁ መልካም አርአያ እንድትሆኑዋቸው ነው እንጂ ስለ ራሳችሁ ብቻ አይደለም ። ትምህርት የሚያስፈልግ መሆኑን ከንድ ትልቅ ሰው ጋራ ስንጫወት የውጭ አገር ቋንቋ ያወቁና የተማሩ ናቸው የሚባሉቱ ሐበሾች ልክ እንዳልተማሩቱ ያህል ቀጣፊዎችና የማይታመኑ ከሆኑ ለሐበሻ ትምህርት አይጠቅማቸውም አሉኝ ።

ይህንን ስሰማ እጅግ አዘንኩ ግን ለዚያ ሰው ትምህርት ማለት አንድ የውጭ አገር ቋንቋ ማወቅ ብቻ እንዳልሆነ ነገርሁት ዛሬ ድረስ ከልጆቻችን የሚበልጡት የተማሩት ይኸ ብቻ ነው ትምህርት ማለትም እስከ ውስጥ የሚዘልቅ ጥንቃቄ ያካሔድና የአእምሮ ማስተማር ማለት እንደሆነ ነገርኩዋቸው ትንሽ ትምህርት የሚያስፈራ ነገር ነው ከፒሬያን ምንጭ ወይ አብዝተህ ጠጣ ወይም አትቅመስ የሚለውን የግሪክ ተረት በውነት የተረገጠ ነገር መሆኑን ገለጥኩላቸው (ፒሬያን ምንጭ የተረት ምንጭ ከርሱ ወኃ ጥቂት ብቻ የጠጡበት እንደ ሆነም ይገድላል ብዙ ቢጠጡለት ግን ጤና ጉልበት እውቀት ይሰጣል ይባላል) እንግዴህ ወዳጆቼ ሆይ ይህንን አስቡና ከእውቀት ምንጭ ብዙ ጠጡ ረጅም ጊዜ ጠጡለት የዘመናችሁንም ትምህርት የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ትምህርትና ትእዛዝ በጥንቃቄ በመከተል ቀድሱት ክርስቲያን ተብሎ መጠራት ብቻ አይበቃም በኑሮዋችሁ በምግባራችሁ በስራችሁም ክርስቲያን መሆናችሁን ልታሳዩ ይገባችኋል ደግሞ ጥቂት ያካሔድ ስርአታት እንድሰጣችሁ ፍቀዱልኝ እርዳታ እንዲሆኑዋችሁም ተስፋ አደርጋለሁ ።

፩ ፡ እውነተኛና ትክክለኛ ሰው ሁኑ ።
፪ ፡ በቃልህና በስራህ ንጹሕ ሁን ።
፫ ፡ ቅንና ክብረት የሚገባው ሁን ።
፬ ፡ ቸር ሁን በሕዝባችንም ከሰፈኑ የቅንዓት ኃጢአት ነፃ ሁን
፭ ፡ አገርህን የምትወድና ላገርህ ሕይወትህን አሳልፈህ ለመስጠት የተሰናዳህ ሁን ።
፮ ፡ አባትህንና እናትህን በእድሜ ካንተ የሚበልጡትንም አክብር ።
፯ ፡ በስራና በጨዋታ አጥብቀህ ቅን ሁን ።

ባጭሩ ሌሎች ላንተ ሊያደርጉልህ እንደምትፈልግ አንተም ለሌሎች እንዲሁ አድርግ ሁሉን ባንድ ቃል ብናስረው እውነተኛ ሰው ሁን ፤ አሁን እንግዴህ ስራችሁ እንዲከናወንላችሁ አጥብቄ እየተመኘሁላችሁ ላስተማሪዎቻችሁ አደራ አሳልፌ እሰጣቸዋለሁ ። እነርሱም ጤናማዎች የብርሃን ሰዎች ልጆች ሆናችሁ እንድታድጉ እንደሚያግዝዋችሁ አልጠራጠርም ።

ደጉ ቸሩ አልጋ ወራሻችን ብዙ ጊዜ የተመረቁ ይሁኑ እግዚአብሔር ጤና ጥበብ ኃይል ይስጣቸው እድሜ ላልጋ ወራሻችን ። ከዚህ በኋላ በደስታ ተጨበጨበ ።

ብፁዕ እጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ በግንቦት ፩ ቀን ፲፱፻፲፯ ዓ ም በራጉኤል ቤተ ክርስቲያን ለነበረ ሰው ሁሉ ንስሐ ገብቶ የኃጢአትን ሥርየት በኢየሱስ ክርስቶስ እንዲያገኝና ከነፍስ ደዌ እንዲድን ልብ በሚነካ ንግግር አሳሰቡት ከትሕትናቸው የተነሳም ራሳቸውን ጨምረው ነቅፈው ሕዝቡን አስተማሩ ።

ካህናት ሆይ የሕዝብ ጠባቂዎች ናችሁና እርሳቸውን አብነት አድርጋችሁ ሕዝቡን ወደዘለዓለም ሕይወት የሚያደርስ መንገድ እንድታሳዩት ብርሃንና ሰላም ያሳስባል ። ይህ ብቻ አይደለም ደግሞ ለማነቃቃት የሚሆን የምክር ቃል ብፁዕ እጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ የጻፉልን ቃል ከዚህ ይከተላል ።

የተላከ ከእጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ዘነበረ በመንበረ ተክለ ሃይማኖት ገብሩ ወሐዋርያሁ ለኢየሱስ ክርስቶስ ወልዱ ለቅዱስ ማርቆስ ወንጌላዊ ። ይድረስ ከኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ዲሬክተር ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት ከተለያየንበት ቀን ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ እንደምንድርነህ ።

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ራስ ተፈሪ በቀናው ሐሳባቸው አባቶቻችን በንባብ በትርጓሜ አቅንተው ወስነው ያስቀመጧቸው መጻሕፍት ለኢትዮጵያ ለልጅ ልጅ እንዳይጠፉ ሰው ሁሉ እንዳሰበ ጊዜ እንዲያገኛቸው በውነተኛ ገንዘባቸው ማተሚያውን አስመጥተው መጻሕፍቱን ሁሉ በመሰብሰባቸው ቅዱሳት አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ብዙ ደስ ብሏቸዋል ። አሁን ደግሞ ብርሃንና ሰላም ብለው ባወጡት ጋዜጣ የኢትዮጵያ ልጆች ዓይናቸውን ገልጠው ድምጥ ማሰማት ስለጀመሩ ብዙ ደስ ብሎናል ፤ በውነትም ይህ ብርሃን ከሰላም ተዋህዶ በፊታችን ተጋርዶ ያለውን ጨለማ እንዲያርቅልን ብዙ ተስፋ የሚሰጥ ነው ።

አስቀድሞ ጌታ ይህን ዓለም በፈጠረ ጊዜ በአርምሞ ሥራውን ሲፈጽም በቃሉ ማዘዝን ለይኩን ብርሃን ብሎ ገለጸው ፤ ብርሃኑንም ቀን ብሎ ጸራው ። ኋላም በነቢዩ በኢሳይያስ ምዕ ፷፪ ቍ፡፲፩ እነሆ ለአሕዛብ ብርሃን አድርጌ ሰጠሁህ መድኃኒትም እስከ ምድር ዳር ድረስ ትሆን ዘንድ ተብሎ ስለ ወልድ ተነግሯል ። ነቢያትም እንደዚሁ ስለ ብርሃን በብዙ ክፍል ተናግረዋል ። ዮሐንስ ወንጌላዊ ምዕ ፩ ቍ ፬ እስከ ፱ ፡ ምዕ ፫ ቍ ፲፱ እስከ ፳፩ ፡ ምዕ ፲፪ ቍ ፴፭ እስከ ፴፮ ቍ ፵፮ ፡ ምዕ ፲፬ ቍ ፱ እስከ ፲ በሐዲስም መጻሕፍት ለብርሃን በብዙ ክፍል ይናገራሉ ይህንም መጻፌ የሥራው አቀናንና አካሔዱ በጣም ደስ ቢለኝ ነው ይልቁንም ሚያዝያ ፳፪ ቀን ሐሙስ የመጣልኝ ብርሃንና ሰላም ስመለከተው አንድ የሚያስገርም ቃል ፈለቀ ወልደ ሐና የሚባል የኢትዮጵያ ልጅ በቶሪኖ ከተማ የጻፈውን የፈላስፋ ቃል መሬት ከተሸከመችው ሁሉ በጣም ከባድና አጉል ጭንቀ ምንድር ነው ብለው ቢጠይቁት ደንቆሮ ሰው ነው ብሎ መለሰላቸው ያለው ቃል በምችና በሌላ በሽታ ታሞ ሁለት ጆሮው የደነቆረ ሰው እንዳይደለ ደገኛዋን አእምሮን ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ያቆሙትን የውቀት መኪና የሚያስፈልጋትንም በትጋት እያቀረበ ሥራ ከመሥራት ተከልክሎ ከሌላ የተገኘውን ገንዘብ በመፈለግ የሚውል ሰው እንደሆነ አወቅሁትና ከሰሁብት በታ ከራሴ ጀምሬ በመላ ኢትዮጵያ ብመለከት ያገራችን መሬት ኢትዮጵያ ወደኋላ ማለቷ አለመንቀሳቀሱዋ ሸክም ቢከብዳት ይመስላል ። እናት እንኳ ልጇዋን በማኅፀን ዘጠኝ ወር ፤ ከተወለደ ሰሰት ዓመት አዝላ አጥብታ ታሳድገዋለች በሶስት ዓመቱ እንደ መጠኑ ማገልገል ይጀምራል ለአካለ መጠን ሲበቃ ወጥቶ ወርዶ ያባት የናቱን ጥቃታቸውን ያወጣል ስማቸውን ያድሳል። እኛም ደግሞ እንደዚሁ ሁሉ እንደ ባሕርያችን ተሸክማ ያቆየችንን ሀገራችን ከባሕርያችን ከዳግማዊ ምኒልክ በተገኘች አእምሮ ጠባይዕ ከኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን በተገኙ ብርሃንና ሰላም እየተሰበሰብን መንቃት ይገባናል።

ድንቁርና ይኸን ያህል ለምድር የሚከብድ ከሆነ አንድ ሰዓት እንኳ ዕረፍት ባላስፈለገንም ይመስለኛል ። በውነትም ይህ ሁለት ጆሮው የደነቆረ ሰው ባይኑ የሚያየውን እንጂ ከጐንና ከጐኑ ከኋላው የሚመጣበትን አያውቅም ከወደኋላው መጥቶ በሽማ ዓይኑን በሸፈነው ጊዜ በፊቱ የሚያየው ይቀራል ከባለጋራው እጅ ከገባ በኋላ ወዲህና ወዲህ ብሎ ለማምለጥ አይችልም ። የድንቁርና ጉዳቱ እስከዚህ ድረስ ሆኖ ስለ ታየኝ ይህን ጻፍኩልህ ።

እኔ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ተላዌ
ዓሡሩ ለተክለ ሃይማኖት ብርሃነ ዓለም ።

የሀገር ውስጥ ወሬ

በዚህ ሳምንት ከሚያዝያ ፳፫ ቀን ጀምሮ በአዲስ አበባ ላይ ዝናም ሲዘንም ሰነበተ ይልቁንም ሚያዝያ ፴ ቀን ከ፯ ሰዓት ተኩል በኋላ ብርቱ ዝናም ከበረዶ ጋራ ዘነመ ።

ሰው ሁሉ ድርቅ ሆነብን ብሎ ተጨንቆ ነበር ። ሁሉ የሚቻለው አምላክ በቸርነቱ ይኸው በጥቂት ጊዜ ምድሩን ለምለም አደረገው ። በየጊዜው ፀሐይና ዝናም ለሚሰጠን አምላክ ምስጋና ይግባው ።

የብርሃንና የሰላም ጋዜታ ዲሬክተር ሆይ ።

ኢትዮጵያ ባካሔዱ መንገዷ ወደ ጥበብ የፊት ልማዷን እያሻሻለች ለፍርድም በጎነት አደርጋለሁ በማለት የምሽቶቶርሞ ብሎ እንደሚጠብቁ አንድ ታመን አገልጋይ ጋሻ ጦር ለብሰው ለታዘገቻቸው ጉዳት የሚሆነውን ነገር በምሕረት ዓይኖቻቸውና በርህሩህ ልቡናቸው በውነተኝነት ተራራም የፍርድን ሚዛን ለማስተካከል በመድከማቸው ለሕይወታችን የሚያጸግብ ፍሬ ይሰጣሉ ። እስከ ዛሬስ ከተማና ባላገር አለ፩ድ መሰናክል የሚገባውን ሕግ መደንገግ ሲቻል ፊትና ጀርባ ሆነው መኖራቸው ምን ይሆን ምክንያቱ ? እንደሚመስለውማ ገበሬ የፈላስፎች በኵር ሊሆን ይገባዋል ማናቸውም ሰው ቢሆን አለ እህል ሊኖር አይችልምና ምሰሶና መሸጋገሪ መሠረትና መቋሚያ የሚሆን ሁሉ ከመሬት መገኘቱን የሚጠራጠር ፩ም አይገኝም ። ገበሬ ሥራውን በነጻነት እንዲሠራ ሀገር እንዲበለጽግ ቢፈለግ ባለማስተዋል ያለውን ልዩነትና ጉዳት አስቦ የቤትን ውስጥ ግዛት ማስጌጥና እድፉን መወልወል የዕውቀትን እርከብ ፈጥኖ የሚቆነጠጥበትን እርከን ማዘጋጀት የገበሬን በደል

ጠንቅቆ ማስተዋል ይገባል በከንቱ ትእዛዝና ሸክም ቢያኰበዱበት ባጠመዱት ወጥመድ መያዝ ነውና ችግረኛ መባል በኢትዮጵያ ርስት ሆና ትኖራለች ። የባላገርንና ዳር አገርን እርነት መውጣት ፤ የጥበብን መስፋት ፤ የመንግሥቱን መክበር የማያስብ ልብ ለሀገሩ ልማት የማይጥር ሰው በከንቱ የተሰበሰበ በከንቱ ይበተናልና በውጪ አዋቂ መስሎ በዘመኑ ሙሉ ተርቦ በባዶ ቤት ተከናንቦ የሚኖር ሰነፍ ሰውን ሥራ የማይወድ ጉልማሳን ያሳስባል ከሱ በኋላ የሚሆነውን አያውቀውምና ስለዚህ ተባብሮ መኖር የደመቀ አበባና እንደ ፀሐይ ብርሃን በየጊዜው የጥበብን አዝመራ የሚሰጥ ፈጥነው ለሚሰለጥኑም የሚያበረታ ላልሰለጠኑትም ከሚገባቸው ማዕረግ እስኪደርሱና የዕውቀት ዕጣ ክፍላቸውን ለማግኘት ለሚናፍቁ ማስተማሰሻ ሆኖ የሚያበረታ የታመነ ረዳትና አቀነባባሪ መሆኑ በሁሉ ዘንድ የተገለጸ ነው ከተማና ባላገር ከስምምነት መንገድ ወጥተው መኖራቸው ያስደንቃል ። በኢትዮጵያም መሬቷ ጠፍ ሆኖ የሚኖርበት ምክንያት ስንፍናን ተገን አድርጎ ገበሬ የሆንኩ እንደ ሆነ ግብር ይበዛብኛል ጥቃትም ይከበኛል ፤ ወገን የሚባል ልክ የሌለው ጉዳና አሰና የተበደልኩ እንደ ሆነ ከመንግሥት የሚያደርሰኝ የለም የሚል ሐሳብ ሰውነቱን አቦዝኖት ይኖራል ፤ ከዚህ ሁሉ እነዚህን የርሻን ጣም የሚያውቁትን ኢትዮጵያውያን በእረፍት በየረገዱ አትክልትና አዝርዕት የእንስሳ ማርባትም የቀረውንም የሚገባቸውን ሥርዓት አድርጎ አገር እንዲከብር በትክክል ወስኖ ቢያሰፈራቸው ያለመናናቅ ቢተጋ የድንቁርናን ደን ላጭቶ ከብልህነት እርምጃ ይደርስ ነበር ። የሰይጣን ዕንቅፋት የሆነ ሐሰትንና ተንኰልን ለማጥፋት አለ ውልውል ጸንቶ የሚዋጋ ሕዝብ የሰይጣን ድል ነሺና የክርስቶስ ዋና ገንዘብ መሆኑ አይፋቅበትም የሐኬት ምንጭ የሆነ ኩራት ከነ ጭፍሮቹ ፈልሶ በተሰደደ ጊዜ የኢትዮጵያ ልጆች በኩራት ኃጢአት ሁሉ እንደ ተሸፈነ አውቀው በከንቱ ዓለም ሁሉ ብልሐት ሲያገኙ ወደ ኋላ የሄዱበትንና የድህነት ጉርፍ አጥልቋቸው ከውስጡ ለመውጣት የተሳናቸውን ሁኔታ መርምረው ካገኙት ወዲያ ከእንቅልፋ እንደ ተነሣ አርበኛ ይሆኑ ነበር ። ክበረትና ዕውቀትም ጥቂት ገላጣ ቦታ ለድንኳናቸው መትከያ ያህል ካገኙ ኢትዮጵያ ስለ ልጆቿ የስንፍናን መድኃኒት ጥበብን ናፍቃለችና እንደ ማንም ቢሆን እንደ ወደደ የልቡን ሐሳብ ለመፈጸም አይችልምና በለዘብታ የጐረቤቶችዋን ክብር ለማግኘት ሠራዊቷን እያነቃቃች በነገርህ ችኩል አትሁን የተባለውን በማስታወስ ሕያው አምላክን ረዳት አድርጋ የውቀት ግብርናዋን ወደ ፊት እየገፋች ትሄዳለች ። ምክሯም ልብኝ በኃጢአተኞች አይቆና ነገር ግን እግዚአብሔርን በመፍራት ይሁን በውነት ፍጻሜኽ መልካም ይሆናልና ተስፋኽም አይጠፋም እያለች ነው ፤ ነገር ግን ክፉ ልማድን በማሻሻል ፈንታ የሕዝብን ልብ ማስነፍ ነውር የማይመስላቸው ሰዎች ዕንኳን ቢኖሩ ከንግዲህስ ወዲያ አባትየው በለማወቅ ይኖር እንደ ሆነ ልጁ እንዲማር የሚመጣውም ትውልድ መልካም ስም እንዲያገኝ ይጣጣራል አባቶቻችን ሕይወታቸውን ያላንድ ብልሀት አሳለፉት እያለ የሀገሩን ጥቅም በያገባቡ እያከናወነ የትምሕርት በያለበት መፍለቅ የሚመኛትና የሚፈጽማትስ እንዴት የታደለ ነው። አሁንም ባለወርቅ አትክልቷ ኢትዮጵያ ከ፫ት ሺ ዘመን በፊት ታላቅነቷ ሲሸጋገር የመጣው ከክብር ማለፊያ ከፍታዋ ሳትዋረድ የወንጌልን ቃል እንድትፈጽም የጅ ሥራና የመንፈሳዊ ልመናቸውን አበርትተው ሥጋዊ መበደላቸውን የሚያሳይ የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ ተቀብለው እንደነሱ ሰው ሆነው የተመሰገኑት ሰዎችን እድል እንዲያገኙ የአእምሮ መክፈቻ የሆነ የትምሕርት ብርሃንና ሰላምን ይስጣቸው ስንል እንመኛለን ። ሚያዝያ ፳፫ ቀን ፲፱፻፲፯ ዓመተ ምሕረት ።

እያለ ገዳ ዘብሔረ ወግዳ ።

ከኢጣሊያ መንግሥት ለጋሲዮን የመጣ ቴሌግራም

የ፳ ሚያዚያ ፲፱፻፲፯ የለት ወሬ ።

ማልታ ። ሚኒስትር ዲ ሳከሌያን የያዘች ያኸት ጁሊያና የምትባል መርከብ ገባች ምኒስትሩም ወርደው ሁሉን እየዞሩ ሲያዩ ሕዝቡ በደስታ ተቀበላቸው ።

ቤኔጽያ ። ዱክ ቤርጋሞና ፡ የንጉሡ እንደራሴ ፡ የትምሕርት ነገር አማካሪ ሮማኖ ፡ ብዙ መኳንንቶችም በተሰበሰቡበት ስሌ የቤኔጽያ ጆግኖች ጥበብ ሥራ በዓል ተደረገ የትምሕርት ነገር አማካሪ ሮማና ደስ የሚያሰኝ ነገር ስለተናገረ ተጨበጨበለት ።

ጀኖባ ። አሚራልዮ ካኘ ከዱክ አብሩሲ ጋራ ወደ ስሜን አገር የሄደበትን ፳፭ተኛውን ዓመት ለማክበር በቅዱስ ጂዎርጂ ግቢ ትልቅ በዓል ተደረገ ። አሚራልዮ ካኘም በወርቅና በብር የተጌጠች የወታደር ምሳርና አንድ ብዙ ፊርማ ያለበት የስዕል መጽሐፍ ተቀበለ ።

ናፖሊ ። ኰንቴኖሴላ የተባለች ትንሽ የጦር መርከብ ፓቴዕን ከሚባል መርከቦች ከሚሠሩበት ሰፈር በደኅና ተነስታ ትዋኝ ጀመር ።

እሌሳንድሬታ ፤ ኰማንዳንት ዴ ፒነዶ ወደ ባግዳድ ለመሄድ ዛሬ ጧት ተነሳ ።

ሬጂዮ ከላብሪያ ። ዱክ ፒስቶያ ሲገባ በደስታ ከተቀበሉት ሕዝብ ሁሉ ጋራ ሁኖ በፈቃዳቸው አጦር ሄደው የነበሩትን ማኅበሮች በንዲራ መረቀ ።

ሮማ ። ከጦር የምክር ቤት ዛሬ ጧት በሙሶሊኒ ሥልጣን [illegible] ሊፈጽም ነው ። የመንግሥት በአየር የሚሄዱ መርከብ ሥራው ሁሉ በሕብረት እንዲሆንና ይልቁንም የመሬት ሥራ እንዲያሻሽል ይሆናል ይባላል ። ከርሱ ጋራም የመንግሥት የአየር መርከብ ወታደሮች ፤ ከባሕር አለቃ በታች ያሉ የአየር መርከብ ወታደሮችና የቅኝ አገር ወታደሮች ሁሉ ናቸው ከነዚህ ያንዳንዱ ክፍሎችም እየተመረጠ እላይ የተባለውን ነገር ሊፈጽም ነው ። አማካሮቹ ሁሉ የተባበሩትን አዲሱን ትእዛዝ ንጉሡ ሊፈርም ነው ።

ባግዳድ ። ኰማንዳንት ዴ ፒነዶ ወደ ቡሺር ለመሄድ ዛሬ ጧት ተነሳ ።

ቡሺር(ፔርሲያ) ። የአየር መርከብ መሪ ኢጣልያዊ ኰማንዳንት ዴ ፒነዶ ደረሰ ።

በልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ።

መጀመሯ ዓመት ፡ ቁጥር ፳፩ ።
1re ANNÉE № 21

ሐሙስ ግንቦት ፲፫ ቀን ፲፱፻፲፯ ዓ ም ።
JEUDI 21 MAI 1925

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

የጋዜጣው ዲረክተር ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲረክተሩ ያስታውቁ ።

የራሱን ጉዳይ የሚያሳትም ሰው ዋጋውን እየከፈለ እናትምለታለን ።

ከጌጥ በፊት ለኑሮ የሚያስፈልግ ነገር ማድረግ እንደሚገባ ።

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ለኢትዮጵያና ለልጆቿ ጥቅም የሚሆን ሥራ አስጠው የጽሕፈት መኪና አስመጥተው ብዙ ቅዱሳት መጻሕፍትና አንዳንድ የሀገራችን ብልሆች ለሀገር ጥቅምና ምክር የሚሆን ሐሳብ የጻፉትን ታሪክ ስለ አሳተሙልን የቅንነትና የቸርነት ሐሳባቸውን ይፈጽምልን እያልን እናመሠግናለን ።

ለድሀ ቸርነት የሚያደርግና ለሀገሩ የሚያስብ ለእግዚአብሔር ያበድራል ፡ በጐነቱንም ይከፍለዋል ። ጥበብ እንደ ርስት ያለች መልካም ነገር ናት ። ጥቅሟም ፀሐይን ለሚያዩ ሰዎች ይረባል ። የጥበብ ጥላ ሕይወትን ትሰጣለችና ። እንደዚሁ አእምሮና ቅንነት ያለው ሀገሩንና ሕዝቡን በቸርነቱ እየጐበኘ የዘለዓለም ሕይወትና ምሥጋና ያገኛል ። በሰነፍ እጅ ግን የጥበብ መግዣ ገንዘብ ቢኖር ጥበብን ይገዛ ዘንድ አእምሮ የለውምና ምን [illegible]

የጥበብ መጀመሯ እግዚአብሔርን መፍራት ፡ የሕግ ፍጻሜ ፍቅር ነው ። ይኸውም የሚገኘው መጻሕፍትንና ያለፈን ታሪክ መመልከት ነውና ልዑልም በፍጹም ቸርነታቸው በገንዘባቸው መጻሕፍትን ከነትርጓሜው የዓለምን ታሪክ ከነምክንያቱ ስላሳተሙልን መልካምና ክፉውን ለመለየት አደረሱን ።

ከሁን ቀደም መጠን በሌለው ድካም የተማሩ የሀገራችን ሊቃውንቶች ጥቂቶች ፡ ያልተማርነው ብዙዎች ስለሆን አንዳንድ ቀን ወደቤተ ክርስቲያን የተሰበሰብን እንደሆነ የእግዚአብሔር አገልጋዮች የሆኑ የሚነግሩንን ሁሉ ትእዛዝ ስላልሰማነው የእግዚአብሔርን ፍቅር በልባችን ሳናሳድር የቤታችንን ጉዳይ ተነጋግረን ወይም ተጣልተን እንመለሳለን ። ቅዱስ ጳውሎስ በየቋንቋቸው ሲያስተምር እንዲህ አለ ፤

አሁንም ወንድሞቼ ሆይ ወደላንተ ብመጣ በብዙ ቋንቋስ በማታስተውሉት ብነግራችሁ ምንድነው የምጠቅማችሁ ገልጬ ካልነገርኳችሁ ብሏል ።

ደግሞ ያለፈ ታሪክ ማወቅና ማንበብ አንድነትንና ጥበብን ይሰጣል ማንም ሰው ከሱ በፊት የነበረውን ታሪክ ሲመለከት ያንጊዜ እንደ ነበረ ሁሉ ሆኖ የመልካምና የክፉውን ጊዜ ታሪክ ያገኛል ። ይኸውም መልካሙ ጊዜ የሚሆነው በጥበብና ባንድነት በብርታትና በቸርነት መሆኑን ፤ ክፉውም ጊዜ በስንፍናና አንድ ላይ ባለመከናወን እግዚአብሔርን ባለመፍራት መሆኑን ሁሉንም ከመጀመሯው እስከ መጨረሻው ድረስ እየመረመረ ያገኘዋልና ደጋጉን እየተከተለ መጥፎውን እየነቀፈ ለእግዚአብሔርና ለመንግሥት የሚበጀውን ለራሱም ኑሮ የሚስማማውን ይይዛል ይረዳልም ።

ከሁን ቀደም የነበሩ ሽማግሌዎቻችን ያለፈ ነገር የጠየቅናቸው እንደሆነ የተጻፈ ነገር ስላላገኙ ስንኳን ታሪክ ሊነግሩን የገዛ እድሜያቸውን [illegible] ለፈረስ ደርሼ ነበር እያሉ ይመልሱልን ነበር እንጂ ጥቅም ያለው ነገር አይሰጡንም ነበር ።

ያለፈ ነገር አለመመልከት ግን በጨለማ እንደ መኖር ያህል ነውና የዛሬውንም ያለፈውንም አኳኋን በብርሃንና ሰላም ስለ ገለጹልን እኛም የኢትዮጵያ ልጆች ለዕድሜያቸውና ለጤንነታቸው እግዚአብሔርን እየለመንን በተቻለን አገልግሎት ወረታቸውን እየመለስን መንግሥታችንን ብንረዳ የሕይወት ጥላ እናገኛለን ። ክፉውን እየጣልን መልካሙን እየተከተልን የፍቅር መክፈቻ ይዘን የጥበብን ደጅ እየከፈትን መንግሥታችን ብንረዳ መንግሥታችንንም የችግር ድካማችንን እያሰበ ልዩ ልዩ ሥራ የሚሠሩ ፋብሪካዎች ያመጣልናል ።

የሰውም ዋና ችግሩ ልብስና ምግብ ይህንንም የሚለዋውጥ ገንዘብ ነው ። ችግር የሚመጣ በጉልበት ማነስ ነው

ጉልበትም የሚያንሰው ረዳት የሌለው ሰው ነውና አንድ ሰው ለራሱና ለቤተ ሰዎቹ ምግብ ሲል ብቻውን በርሻ ይደክማል ይኸንንም ሀሳቡን ሳይጨርስና በቅብቅቡ ላይ የዘራውን ዘር አርሶ ሳያደርስ ያገሩ ጭቃሹም መጥቶ በሬውን አስፈትቶ እጁን አንጠልጥሎ ወስዶ አስሮ አሰንብቶ ወይም የራሱን ሥራ አሥርቶ ሲጨርስ ይለቀዋል ። በብዙ ቀኑ ሲመለስ ዘሩን ወፍ በልቶት ያገኘዋል ። እንደገናም እንዳይዘራ ጊዜው ያልፍበትና ከዚህ የተነሣ አዝመራው ስለተሳሳተበት ለምግቡ ሲጨነቅ የልጆቹና የራሱ ልብስ ሲያልቅበት ትኂሽ ከሚሻል ጉረቤቱ በወለድ ገንዘብ ተበድሮ ለጊዜው ይገዛና ይህንን ገንዘብ ከነወለዱ የሚከፍልበት አቅም ስላጣ ልጆቹንና ርስቱን ጥሎ ከዚያ ጭንቅ ኑሮው ተመርሮ ይሰደዳል ። ከዚህ በኋላ ልጆቹ ጠባቂ ስለሌላቸው በየዱሩ እየተበታተኑ መንግሥትና ባላገር ያውካሉ ።

ወይም ወደ ከተማ እየተሰበሰቡ ላንዱ ሹም እያደሩ እነሱም ጭቃሹምነት እየተሾሙ በባላገር የቀሩትን አራሾች ያውካሉ ፡ ወይም በከተማ ያለሥራ እየተቀመጡ ግብር ገባወይ ከገሌ ጋር አልበላም እያሉ ጌቶቻቸውንና አጋፋሪ በመሰብ ሲያውኩ ይኖራሉ ።

በዚህም ተመርረው ወዳባታቸው ርስት እንዳይመለሱ የአባታቸውን ያበረረ ጭቃሹም ለባለዳ አሳልፎ ሰጥቶታል ፤ ሠርተውም እንዳይበሉ ከዚህ በላይ ከተጻፈው በተቀር የተማሩት ነገር የለምና እንደገና የመንግሥት አስቸጋሪ ይሆናሉ ።

መንግሥታችን ግን ይህንን የባላገር በጭቃሹም ምክንያት መሰደድን አይቶ መሬቱን በቁርጥ ግብር ቢያደርግለት ከነልጆቹ የሚሠራው የእህልና ያታክልት አሥራትና የመሬቱ ግብር አሁን በጭቃሹም እጅ ከሚገባለት ገቢ ይልቅ አሥር እጅ እጥፍ ያገኝ ነበር ።

መንግሥትም ለሚያስፈልገው ነገር ሁሉ ከምስለኔና ከጭቃሹም ጋራ ከመጸከም ወፍጮውንም ሌላውንም የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ በመኪና ቢያሠራ ጭቃሹም በ፬ ዓመት የሚያሠራውን ፡ መኪናው በ፩ ቀን ያሠራለታል ። የሥራው መከናወንና የባለገሩ ነጻነት ፡ የመንግሥትና ያገር ሕይወት ይሆናል ። ከመሬቱም የሚገኘው ግብርና አሥራት ስንኳን ለራሱ ከዚህ በኋላ የዚያ የባላገር ልጆች አገርንና መንግሥታቸውን እየረዱ ባለመበታተን አደገዋልና ከመንግሥትሮቻ ማደሪያቸውን እንደሚገባቸው እየተቀበሉ ጠፍ መሬት እያቀኑ ከብረው ያስከብራሉ ፤ ልብስ እንዳይቸግራቸው የሥራ ጊዜ አግኝተዋልና ለግብራቸውና ለልብሳቸው ሲሉ ቡን እየተከሉ ጥጥ እየዘሩ ይኖራሉ ።

ይኸ ባላገር አንድ ዋና ችግር ቀረው ፤ የሰው ኃይሉና መልኩ ገንዘቡ ነውና ይህንን ከዚህ በላይ የተጻፈውን የርሻ ሥራ ሁሉ ብቻውን ሠርቶ የማይከናወንለት ስለሆነ ረዳት ሙያተኛ የሚያስፈልገው ሆነና ከሚሻል ጉረቤቱ ልብሴ ሲደርስ እከፍልሃለሁ ብሎ አንድ ብር ተበድሮ ባ፲፮ መሃልቅ ምንዛሬ ሂሳብ ፳ ሙያተኛ ሊገዛ ወደ ገበያ ይሄዳል ነገር ግን ባ፩ ብር ፳መሃልቅ ስለሆነ ለ፳ ሙያተኛ የማይበቃው ነውና እንደገና ፩ብር የሚያስጨምረው ስለሆነበት ብቻዬን ሠርቼ ዕዳዬንና ግብሬን ለመክፈል አልችልም ከመታሠር ከገር መብረር ይሻለኛል ብሎ ይሰደዳል ።

ልጆቹም ወደከተማ እየተሰበሰቡ ከነእገሌ እንወለዳለን ያባታችን መሬት ጠፎ ያጠጣል እያሉ የሰነፍ ወሬ እያወሩ ያባታቸውን መሬት ፡ መሸታ ቤት እያስማሙ ቢሠሩት ብዙ ዘመን ጠፎ የሚያጠጣውን መሬት ለትንሽ ቀን መጠጥ ይለውጡታል ። መጠጥ እስከ ብዙ ክህደት ያደርሳልና የመሬቱ ዋጋ ከለቀባቸው በኋላ ነጋዴና ባላገር እየቀሙ የመንግሥት አስቸጋሪ ይሆናሉ ።

ይህንን ባላገር ከስደት ያደረሰ የገንዘብ ማነስ ነው ፤ ሀገራችን ኢትዮጵያ በለምነቷ የምትሰብልን ገንዘብ እጅግ ብዙ ነው መንግሥታችንም የገንዘብ ጌታ ነው እንጂ የገንዘብ ድህነት አግኝቶት አያውቅም ፤ ነገር ግን ባላገሮቹ ሳይሠሩ ማፍረስ የሚባል መኪና አቁመን አንድ አንድ ብርቱዎች ባላገሮች በንግድና በርሻ ያመጡትን ገንዘብ ፤ ቢቀር ለማያገኙዳ ከማን አንሼ ለሚባል ጌጥ እያስቀጠቀጥን የባላገር ማስደንበሪያ ስላደረግነው ነው እንጂ አንሰን አይደለም ።

ጌጥ የሚገባ ለዋና ዋና መኳንንትና ወይዛዝር ደግሞ ላገሩና ለመንግሥቱ አልፎ ደሙን ለሚያፈስ ጅግናና ለብልህ ሠራተኛ ነው እንጂ ለነ ከማን አንሼ ፈረስ መጣምርና ለበቅሎ ዶቃ ለድኩት ይህንን ለመሰለ ማድረግ የሚገባ አይደለም አንዳንድ ሰዎችማ መንግሥት ሳይሰጣቸው በፈቃዳቸው እያስቀጠቀጡ የማይበቃቸውም ቢሆን እንደገና ከባንክ እየተበደሩ ለራሳቸውም ለሚስቶቻቸውም የማይገባውን ጌጥ ባደባባይ ላያጌጡት ለመለቀሻ ይሆነናል እያሉ ያሠራሉ (እውነትም ይኸ ጥፋት ያስለቅሳል) ሰው ሁሉ የሚለቀስለት በደግነቱ ነው እንጂ በጥፋቱ አይደለም ።

ይልቅ ሰው የሰራውን ሥራ ቀጥቅጦ ባገልግል ከማገር ጠፍ መሬት እየገዙ ማረሻ ቢያደርጉት ይሻላል ። ወይም ቢነግዱበት ፲ሩ ፳ ፤ ፳ው ፺ ፤ ፺ው መቶ ብር ይሆናልና ከዚህ በኋላ ቢያጌጡም ሥራው ነው ይገባዋል ይባላል እንጂ አያስነቅፍም ።

አሁን በሀገራችን የመንግሥትና የሕዝብ ገንዘብ ሆኖ የሚቀጠቀጠው ብር በትንሹ ፩፻ሺ ብር ይሆናል ፤ ከዚሁ ውስጥ ከ፻ው [illegible] ጋር እደጅ ይወድቃል ፫፻፳ሺ ብር ይተርፋል ፻ው ሽህ ብር ለጼረስ መጣምር ለበቅሎ ዶቃ ይሠራና ፈረሱ እንደልቡ እንዳይጋልብ መኄቻ ግምበር ግምባሩን እያወለቀው ባፍንጫው ደም እየዘነበ ጌታውን መራ ሳያስወጣ ሚዛኑ ስለከበደው በቶሎ ይደክማል መጣምሩም በየዱሩ እየተበታተነ ያልቃልና የመጣምሩ መርገፍ የፈረሱ መድከም ለባለቤቱ እጥፍ ጉዳት ይሆንበታል ።

ባግረ በተሰናዳ የጠፍር እቃ የሚጋልብ ፈረስ ግን የልቡን ሠርቶ ሳይደክም ይመለሳል ።

ደግሞ ፪፻፳ው ሺህ ብር ከነማን አንሼ በሚባል እግር ውስጥ ስለተሸፈነና ባገልግል ውስጥ ስለሆነ ዝርዝሩንና ስሙን ለማወቅ አይቻልምና እንዲያው አልበ ስም ነው ፤ በልብ አልባ ባይሸፈን ግን ይታወቅ ነበር ። ልብማ ያላትን ሴት ሰሎሞን በ፴፩ ምዕራፍ ላይ እርሻም አስባ ትገዛለች ከጅዋም ፍሬ

ወይን ትተክላለች እጅዋን ወዳመልማሎና ወደ እንዝርት ትዘረጋለች ጽንዓትና ደም ግባት ልብሷ ነው እግዚአብሔርን የምትፈራ ሴት ትመሰገናለች ብሏት የለምን ፡ አገልግል ውስጥ ከማገር ጥጥ እየገዙ ወይም እያዘሩ ቢፈትሉት ጌጥ ይሆን ነበር የሕዝብ ጌጡ ልብስና ምግብ የመንግሥት ጌጡ ሕዝብ የወታደር ጌጡ ሙሉ ልብ ነውና እንደዚሁ ብናጌጥ እንዴት ብማረብንና ለጐረቤትም ባስቀናን ነበር ።

የኢትዮጵያ ኃይልና ብርሃን የሆኑ ደጉ አጤ ምኒልክ የማይገባው ሰው ሁሉ በፈቃዱ የሚያስፈልገውን ጌጥ እንዳያሰራና እንዳያጌጥ ያስከለክሉ ነበር ፡፡ ይህንንም ማድረጋቸው ሳትሰሩ ብታጌጡ አያምርባችሁም ሰርታችሁ ብታጌጡ ያምርባችኋልና ሥራችንን ስንጨርስ እናስጌጣችኋለን ማለታቸው ነው እንጂ ከግር እስከ ራሳችን ብናጌጥላቸውና ቢያምርብን ብንወደድ ጠልተው አይደለም ።

ገበሬ በሬውን ጠምዶ ሲያርስ የዘራውን ዘር ከፈሩ ሳያደርስ በሬውን በመከከል አቁሞ ያጌጣልን ወይስ እህሉን ሲወቃ አምርቶ በጐተራው ሳያገባ ያጌጣልን አያጌጥም የሚያጌጠውስ ዘሩን ሲጨርስ ጭቃውን ታጥቦ ውቂያውን ሲጨርስ አባራውን አራግፎ እህሉን በጐተራ አግብቶ ያጌጣል እንጂ እደጅ ያለውን አገዝመራ በጁ ሳያደርግ ምንም ቢሆን አያጌጥም ።

አሁንም መንግሥታችን የችግር ድካማችንን የሚያስብልን ነውና ይህንን ሳንሠራ የምናፈርሰውን ፩፻ ሺ ብር ደግሞ በሁለተኛው ዓመት የሚቀጠቀጠውን ፩፻ ሺ ብር አንድ ላይ በ፪፻ ሺህ ብር የዚህኑ የብር መሥሪያና የልብስ ፋብሪካ ቢያመጣልን ። ይኸውም ባይሆን በዚሁ በ፪፻ ሺ ብር መሐልቅ ቢመጣ ያ ሙያተኛ መግገ መሐልቅ አጥቶ መሬቱን ጠፍ እያደረገ የበቅሎ ዶቃ ድምጽ እየሰማ ወደ ከተማ የተሰበሰበ ያትክልት ሠራተኛ ሁሉ እንደገና እየሠራና እያሠራ ከሚያገኘው አትክልት መንግሥትም የሚያገኘው አሥራትና ቀረጥ ከሁሉ ገቢ አሥር እጥፍ ያገኝ ነበር ።

በዓለም ሁሉ ለጐበዝና ለባለሙያ ልዩ ልዩ የሆነ ጌጥ አለ ። ነገር ግን ለማዕርግ እንደሚሆን ለሥራና ለሩጫ ቀልጣፋ የሚያደርግ ለባለሙያ እንደ ኒሻን ያለ ለጐበዝ በክንዱና በትከሻው ላይ ነው እንጂ ለሰውና ለከብት [illegible] አይደለም ።

ሸክም ጌጥ መሆኑን ጥቅም ቢያገኙበት ይልቅ እነሱ ደክመው የሚያወጡትን ብር እያስቀጠቀጡ እንደ ቀሚስ ለማጥለቅና ለማጌጥ ይችሉ ነበር ።

ብርን በሚዛን ለክተው የሠሩት ለሚያስፈልገን ነገር መለዋወጫ እንዲሆነን ነው እንጂ ለማያስፈልግ ጌጥ ማስቀጥቀጣችንን አውቀው ቢሆን እንደ ጠገራ ብረት እያድበለበሉ ይልኩልን ነበር ።

ቀድሞ ኃይላችንና ብርሃናችን ግርማዊ አጤ ምኒልክ ይኸውም በየጥቅማችን የምናገኘው ገንዘብ ለድሆቸው የማያዳርሳቸው ቢሆን በያቅሙ እንዲገበያይ ፡ አላድ ሩብ ፡ መሐልቅ ቤሳ አድርገው ይህነንም ውለታቸውን እንዳንረሳ በስማቸውና በመልካቸው አሳትመው ባ፩ድ ብር ከ፲፮መሐልቅ በታች እንዳይመነዘር ደንብተውልን ነበር ። ነገር ግን ያን ጊዜ የሚብልጠው ሀገራችን የሚገበያየው ባሞሌና በጠገራ ነበር ። ዛሬ ግን መላው ሀገራችን የሚገበያየው በመሐልቅ ብቻ ሆኖ መሐልቅ እጅግ ስለ ተወደደ ባላገሩ እጅግ አለመጠን ተቸገረ በዚህ በ፪፻ ሺ ብር መሐልቅ ቢመጣ ግን መንግሥትም ባለ አገርም ብዙ ጥቅም ያገኝ ነበር ከጥቅም በኋላ መጣምርና አልቦ መርገፍም ቢያጌጡ ያምራል ።

አሁንም መንግሥት በፈቃዱ ከሚያሠራው በተቀር በያለበት ብር ማስቀጥቀጥናመቅበር ትንሽ ቀን ቢቀር ባንድ ብር እስከ ፳ መሐልቅ ድረስ ይመነዘር ነበር ።

እኔ የምፈራ በጣም የማዝን ።
ከመርገፍ በኋላ አልቦ መባልን ።
ድህነት ያስበል ያገር ጠፍ መሆን ።
ድሃ ሳያለብስ ሳያበላ ወጥ ።
ቡና ሳያስተክል ሳያስዘራ ጥጥ ።
አወይ ጌታው ብሩ እንዲያው መቀጥቀጥ ።
እንዳሁን ሞያሌ እግር ላይ ማፍጠጥ ።
ሆድን እየራበው ካንገት በላይ ጌጥ ።
እንዴት በጠገብን ይኸ ቢለወጥ ።

እሸቴ የሐረር ጉምሩክ ዲሬክተር ።

አገራችንን በእውነተኛ ፍቅር እንውደዳት

ብፁዕ እጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ በመላ ኢትዮጵያ ብመለከት ወደ ኋላ ማለቷ የድንቁርና ሸክም ቢከብዳት ነው ያሉት ቃል እርግጥ ነው ይኸንንም ቃል የኢትዮጵያ ሕዝብ ከሊቅ እስከ ደቂቅ ተረድቶታል ከዓለም ሥልጣኔ ወደ ኋላ መቅረታችንን ካወቅነው ደግሞም ያለ ሥልጣኔ ከሌላው ዓለም ችለን አለመተካከላችንን ከተረዳነው ብፁዕ እጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ እንዳሉት ድንቁርና ይህን ያህል ለመሬት የሚከብድ ከሆነ ፩ ሰዓት እንኳ ልናርፍ በውነትም አይገባንም ። (አሁን) ለምሳሌ ብዙ ሚልዮን ብር የምታወጣ የምታበራ እንቍ የያዘ ነጋዴ ከየረር ላይ ተቀምጦ ማታ ጊዜ ልኮ አሁን ሌሊት ገስግሶ ለመጣ ሰው ይህችን ክብርት ዕንቍ በትንሽ ዋጋ እሸጣለሁ አለዚያ ግን ጡዋት በባቡር መሄዴ ነው ቢል ጊዜው ማታ የክረምት ጨለማ ቢሆን ያችን እንቍ ገስግሶ ለማግኘት ምን ጭንፍ ጅብርቶ ከመሄድ በቀር ሌላ ነገር የለም እንዲሉ የታወቀ ነው ። ያችም የምታበራ እንቍ እውቀትና ጥበብ ናት ወደርሷ ለመድረስና እሷን ለማግኘት የሚያዘው መብራት ፋኖስም በመላ ኢትዮጵያ በየወረዳው ሊቆም የሚገባው የሥልጣኔ ትምህርት ቤት ነው ። ይኸንንም የትምህርት ቤት የተባለውን የኢትዮጵያ ልጆች በትጋት ካላቆምነው አውቆ በገዛእጁ አይቆምም ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ያቆሙት የትምህርት ቤት በተከፈተቀን ልዑል የተናገሩትን ቃል የኢትዮጵያ ልጆች ለልጅ ልጅ ልንረሳው አይገባንም ይልቁንም አገሬን እወዳታለሁ ብሎ መናገር ከንቱ የአፍ ልማድ ነው ። የሚያስፈልጋት በጊዜው ካልተደረገላት ያሉትን ቃል ልንከተለው ይገባናል ።

የቀድሞ አባቶች በጊዜያቸው ለኢትዮጵያ የሚገባትን አድርገውላታል በስሐጤ በመተማ በአድዋ በሌላም በብዙ ስፍራ ደማቸውን አፈሰሱላት አንገታቸውን ሕይወታቸውንም ለሀገራቸው ሲሉ አሳልፈው ለሞት ሰጡ ።

ግማሾቹም ለሕይወታቸው ለሞት ሳያዝኑ ተዋግተው ቆስለው፣ሳይቆስሉም እግዚአብሔር ያወጣቸው እስከሁን አሉ ።

እኛ ግን ዛሬ ጦር ቢመጣ እንደነሱ ላገራችን እንሞታለን ብለን ብናወራ የአፍ ልማድ ነው ያለፈውን ወይም ገና በሌሎች ጊዜ የሚመጣውን ነው ለሀገራችን የምንረዳት ብንል አይረባም አገራችንን እንወዳታለን ብንልም እውነት አይመስልልንም በጊዜ የሚያስፈልጋትን ላገራችን ካላደረግንላት ፤ አሁን ለምሳሌ ውሀ ለጠማው ሰው እንጀራ ልስጥህ ቢሉት የተራበውን ሰው ልብስ ልስጥህ ቢሉት ለዚያ ሰውዬ ምንም መጥቀም አይደለም አሁንም ላገራችን እንሞትላታለን ማለት ሞት በሚያስፈልግ ጊዜ ይሆናል ። አሁን የሚያስፈልጋት የስልጣኔ ትምሕርት ቤት ማቆምና ማብዛት ብቻ ነው ጥቂት ገንዘብ ልንከስርላት ከልወደድን እንሞትላታለን ነፍስን ያህል ነገር ላገራችን አሳልፈን እንሰጣለን ማለት ለአፍ የከበደ ነው ። ተገንዘብ ነፍስ ክብርት ናትና ። እሁንም መንግሥታችን የትምሕርት ቤት አቁሞልናል ገናም ብዙ የሥልጣኔ የትምሕርት ቤት በየወረዳው እንዲያቆምልን ሙሉ ተስፋ አለን ልዑል የኢትዮጵያ አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንንም የሚያስደንቅ የትምሕርት ቤት አቁሙልን እኛ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ግን አገራችንን በውነት ከወደድናት አንድ የሥልጣኔ ትምሕርት ቤት ገንዘብ አዋጥተን እናቁም ስናቆምም ለትርፍ አይደለም ገንዘባችንን አውጥተን አጥፍተን ለገራችን ጥበብ ልንገዛላት ነው እንጂ የምናወጣውም ገንዘብ በየዓመቱ ነው ። እንደ አቅማችን ወይም እንደ ፈቃዳችን ይኸን ገንዘብ እሰጣለሁ የሚልም ሰው ከብርሃንና ሰላም ጋራ የታተመች ትንሽ ወረቀት ትመጣለችና በርስዋ ላይ ስሙን ስራውን አገሩን በየመቱ በእርግጥ ለትምሕርት ቤት ሊረዳ የሚችለውን ገንዘብ ጽፎ ፈርሞ መልሶ ወደ ብርሃንና ሰላም መላክ ነው፣ ብርሃንና ሰላም ፩ ላይ ሰብስቦ በጋዜታ ጽፎ ያትመዋል ያንጊዜ የገንዘቡን ልክ ስናውቅ አንድ ቀን ተሰብስበን ተማክረን ስራውን የሚያስኼድ ሰው እንመርጣለን ። እባክችሁ ይህቺን ፩ ነገር ላገራችን ስንል እናቁም ልጆቻችን እንኳ አባቶቻችን ላገራቸው ጥቅም በጊዜያቸው ምን ሠሩላት ብለው ይናገራሉ።እኔ ድኻው ከሁሉ ጀምሬ አስታውቃችኋለሁ አለ አቅሜ ላገሬ ፍቅር ስል በየመቱ ሁለት ሁለት መቶ ብር እረዳለሁ (በዚህ በሚቆመው የትምሕርት ቤትም ገንዘብ ያለው ለገጊያው ዘበንቱ ይማራል ከዚያ የሚገኘውንም ገንዘብ እኛ እንወስደውም ለትምሕርት ቤት ማስፊያ ይሆናል ይኸን ብናደርግ ላገራችን ትልቅ ጥቅም ማድረጋችን ነው ይኸን የትምሕርት ቤት የምናቆምም ሰዎች ለወደ ፊቱ ለስማችን ትልቅ ከበሬታ ያለው ስም እናገኛለን ትንሽ ዓመታት እንዲህ ከደረ ግን በኋላ የተማሪቤቱም ራሱን ይችላል።ልዑል አልጋ ወራሽ ሆ ይ ይኸን የእውቀት ኤሌክትሪክ(መብራት)አብርተው የብርሃንን መንገድ ስላሳዩን እውነተኛው ምስጋና ይገባዎታል፣ምስጋናውም ከንቱ ውዳሴ አሁን እኔ ብቻ አመስግኜዎ የሚቀር አይደለም ለልጅ ልጅ የኢትዮጵያ ልጆች ያመሰግኑዎታል እንጂ የትምሕርት ቤት በመክፈትዎ ትልቅ እርምጃ ወደ ብርሃን አቅንተው ተራምደዋልና ።

ፊታውራሪ ጀሬሳ ።

ስለ መንግሥት ደጅ ጠኞች ።

ከሁን ቀደም የደጅ ጠኝ ብዛት ለመንግሥት ምንድነው ጥቅሙ የሚል ጥያቄ ተነስቶ ነበር ። የደጅ ጠኝ ዓይነቱ ሶስት ነው ። አንደኛ ለሹመት ታጭቶ የተቀመጠ ደጅ ጠኝ አለ ሁለተኛ በወንጀል ተግዞ ተስፋ ሳይኖረው ብዙ ቀን በደጅ ጥናት የተቀመጠ አለ ። ሶስተኛ የጭዋ ልጅ ሠርቶ ነግዶ ለመብላት የማያውቅ በዘመን ብዛት እሾማለሁ አገኛለሁ እያለ ዕድሜውን የሚገፋ አለ ። ተሹሞ የተሻረ ከጦር ሲሰማራ የኖረ አርበኛ በደጅ ጥናት የተቀመጠ መንግሥት ከምክር ላይ ለንዲህ ያለ ጉዳይ ማን አለ ብሎ ሲጠይቅ ያን ጊዜ እነዕገሌ አሉ ተብሎ መንግሥት ላሰበው ጉዳይ ይገኛሉ ።የመንግሥትንም አሳብ ይፈጽማሉ ፡ የደጅ ጠኝ ለመንግሥት ይኸ ዋና አንዱ ጥቅሙ ነው ። ባለ ተሥፋ ደጅ ጠኝ የመንግሥቱን መጥናት የሠራዊቱን መስማማት ወደ እግዚአብሔር ይለምናል ። የግዞተኛ ደጅ ጠኝ ተስፋ የሌለው የጨዋ ልጅ የደጅ ጠኝ ብዛት ለመንግሥቱ አይበጅም ። ወደ እግዚአብሔርም ምነው ለኛ የሚል እታመጣልንም እያለ መንግሥቱን እየማ የሠራዊቱንም ልብ ያሸክራል ። ልጅነት ያለው የውስልትና መንገድ ያስባል በንዲህ ያለ ምክንያት የደጅ ጠኝ ብዛት ከሚጠቅመው የሚጎዳው ይበልጣል ። የሕዝብ እናት አባቱ መንግሥት ነው ሁሉም እንደባህሪው እንደመጠኑ ለጉልት የሚበቃውን ጉልት ደሞ ዝቅ ላለው ቀላድ እየሰጠ ሳይፈትነው አልቀረም የዓለም መሻት በቃኝ አይልምና አንድ አንዱ ሽፍቶ እንጀራዬን አወጣለሁ እያለ ብዙ የሠራዊት ደም ከማፍሰስ ይደርሳል ። ሌላውም ሲሰርቅና ሲወንበድ እየተያዘ ዕድሜው በቅጣት ያጥራል ። እግዚአብሔር አዳምን ፈጥሮ በኤዶም ገነት ሲያስቀምጠው የቀረውን ምድር ሁሉ እንደገነት ያበጀውና ይጠብቀው ዘንድ ሁሉን ሰጠው ። እንዲሁም ትምህርትና ሥራ የሚወደውን ሰው መንግሥትም በነፃነት የወደደውን ከሕግ ያልወጣ ሥራ ቢይዝና ቢከብር ይወዳል ። ደስ ይለዋልም ለደጅ ጠኙ በየወሩ የሚወጣው ገንዘብ ጥቂት አይደለም ። ግን በየማዕርጉ ሥራ ሳይዝ በመቀመጥ ከሐሜት ይደርሳል ። ሥራና ትምሕርት ያልተሰበከ ሆኖ ነው እንጂ ወታደሩም በወታደርነቱ ስልፍን እየተማረ ትእዛዝን ቢጠብቅ መኳንንቱም ባለቅነቱ ወታደርን ለማስተማርና ትእዛዝን ይጠብቅ ዘንድ ለማትጋት አገር የሚጠበቅበትን ድሀ የሚጠቀምበትን ቢያስብና ቢሰራ አገሩም ይለማል ሰውም

ከደጅ ጠኒዎች የሚበልጡት መኳንንትና ሊቃውንት ናቸው ። ወግ እያለቀበት የሚሠራው እያጣ ቀኑ ረዝሞበት ይውላል ከሁን ቀድሞ በኢትዮጵያ ያሉት መጻሕፍት ሁሉ ተሰብስበው ለደጅ ጠኙ ከማይርቀው ቦታ ላይ ለዚሁ ሥራ ብቻ ሁነኛ ቤት ቢቆም ባዋቂ ሰው እጅ እየተጠበቀ ደጅ ጠኝና ዕውቀት የሚሻው ሁሉ ከዚያ ሥፍራ እየሄደ መጻሕፍትን ቢመለከት ዕውቀትን እየቀዳ ጥበብ ይሰፋ ነበር ።

ከንቲባ ገብሩ ።

በሚያዝያ ፳፱ ቀን ፲፱፻፲፯ ዓ ም የእንግሊዝ ንጉሥና ንግሥት ወደመካከለኛ ባሕር ከሔዱበት መንገዳቸው በደህና ወዳገራቸው ወደለንዶን ተመልሰው ገቡ ።

ንጉሡ ጤንነታቸው ታድሶ በደህና ወዳገራቸው ስለ ተመለሱለት ሕዝቡም በትልቅ ደስታና ክብር ተቀበላቸው ።

በልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ።

መጀመሯ ዓመት ፡ ቁጥር ፳፪ ።
1re ANNÉE № 22

ሐሙስ ግንቦት ፳ ቀን ፤ ፲፱፻፲፯ ዓ ም ።
JEUDI 28 MAI 1925

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ ሲገዛ ለፈለገ በ፬ መሐልቅ ይሸጣል ።

የጋዜጣው ዲሬክተር ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የራሱን ጉዳይ የሚያሳትም ሰው ዋጋውን እየከፈለ እናትምለታለን ።

ደብዳቤ ወደ ክቡራን ወንድሞቼ ወደ ኢትዮጵያ ልጆች ብርሃንና ሰላምን ኢየሱስ ክርስቶስ ፴፫ ዘመን በመሐከላችን ተቀምጦ ለሰው ልጅ ያስተማረውን እይሰውርባችሁ እያልኩ የሚገባችሁን ሰላምታ አቀርባለሁ ።

ክቡራን አበቶቼ ሆይ በዚህ ሰሞን አስመራ ላይ ታላላቅ ሰዎች የጠየቁኝን ነገር ላውራላችሁ ።

ምድነው የሚመስልህ ፤ ዛሬ የሐገራችሁ ፖለቲክ ኢትዮጵያዎች እስከዛሬ ድረስ በውቀት መንገድ ተአውሮፖች ጋራ በጣም ተራርቃችሁ ነው የምትቀመጡት አጼ ምኒልክ የአውሮፓን እውቀት ሊከፍቱ ጀምረው ነበር ዘመናቸው በማጠሩ ሐሳባቸው ሳይፈጸም ቀረ ።

ተዚያም ወዲህ የሳቸውን መንገድ ይዞ የሚያሰፋ ይቅርና የከፈቱት በር እንዳይዘጋ ስንኳ አስቦ የጠበቀላቸው የለም ነበር አሁን ግን ልዑል ተፈሪ መኰንን አጼ ምኒልክ የከፈቱት እንዳይዘጋ ማሰባቸው ቀርቶ ሌላ ብዙ የውቀት በር መክፈትና [illegible] እንኳንስ የተማረና ያልተማረም ያውቀዋል ። ነገር ግን ማን በጅ ብሎ ይቀበላቸዋል ። ጥንት አውሮፓ አሁን የናንተን ዘመን በምትመስልበት ጊዜ ብዙ ነገሥታቶቻ እንደኑ ሉይ ክቶርዝ በሐገራቸው እውቀትን ለማግባት በማሰባቸው እንደምን ይለፉ ነበር ፡ ስንትስ በለጋራ ለክፉ ይመኙቸው ነበር አሉኝ ።

ቀጥለውም ዛሬ ኢትዮጵያዎች እርስ በርሳችሁ ወገን ለይታችኋል፤ይህንም የመሰለ ሥራ ዋና እውቀት አባራሪ ይመስለናል እያሉ ይህን የመሳሰለ ነገር ብዙ ጠየቁኝ ።

ተዚህ ቀደም በዚሁ በትግሬ ወረዳ አንድ የተማረ የባዕድ አገር ሰው ላንዱ ለሐገራችን ለተማረ ሰው ዛሬ ስለሐገራችሁ ነገር ሳስብ እንቅልፍ ሳይወስደኝ አደርኩ አለው ፤ ምነው በምን የተነሳ ቢለው ይኸኛው በሕልሜ ኢትዮጵያን አሰብኩና ኢትዮጵያ ተውቀት ብርሃን ተለያይታ ታርዛ ትኖራለች ይህን የእውቀት ብርሃን አግኝታ ተዚህ ተጭንቂ እንድትድን አስር ዓመት ያስፈልጋታል አስር አይበቃም ሐያ ይሁን አልኩ ይህም አይበቃም አምሳ ይሁን ይህም አይበቃም መቶ ይሁን ፤ አይበቃም አምስት መቶ ይሁን አይበቃም ሺህ ይሁን እያልኩ ሳልም የዚህን ጊዜ ደንግጬ ባንኩ ያለምኩትንም በውኔ ባስበው እውነትም ኢትዮጵያ የውቀት ብርሃን እንድታገኝ ሺህ ዓመት አይበቃትም ይህም ታልበቃት የውቀት ብርሃን በኢትዮጵያ ሳትገባ ልትቀር ነው ብዬ በንደዚህ ያለ ኃሳብ የተነሳ እንቅልፌን አጥቼ አደርኩ አለ ቢሉኝ ፤ ይህን የመሰለ ነገር በሐገራችን በኢትዮጵያ ላይ በኛ በልጆቿ ላይ መታሰቡ እጅግ አለመጠን ሲያሳዝነኝ በኢትዮጵያ የውቀት ብርሃን መግባቱ ዘበት ከሚመስላቸው ሰዎች ጋራ እኔው ራሴ ተሟገትኩ ።

በ ጊዜ ለኋላ ብኋል ሰሎሞን ማናቸውም ነገር ያለ ጊዜው ሊሆን አይችልም ። እኛ... ደጅ [illegible] የውቀት ብርሃን በሐገራችን ከተተከለች ምን ዘመን አለው የዮት የቅድማያቶቻችንን ነፍስ ይማር ደማቸውን አፍሰው አጽማቸውን ከስክሰው በቀኑዋት አገር ላይ ሁለት የሚደጋግፉ እንደ መልክም እህል የሚጣፍጡ እንደ መልክም ሽቱ የሚአውዱ እንደ ዕንቁ የሚያበሩ የሰው ልጅ ሊያውቃቸውና ሊወዳቸው የሚገባ የውቀት ፋናዎች ተተክለዋል መተከላቸውንም አሌ የሚል የለም አሁንም ቢሆን ቁመው እያበሩ ይመሰክራሉና እነዚህንም ፋናዎች የማያውቅ ቢኖር ተዛሬ ጀምሮ ይወቃቸው እነዚህም እውነተኛውን አምላክ እግዚአብሔርን የምናውቅበት የኢየሱስ ክርስቶስ ሃይማኖትና የየሐገራችን ፍቅር ናቸው ።

በነዚህ በሁለቱ ነገሮች ብቻ ኢትዮጵያ እራስዋን ቀና አድርጋ ልቡዋን አኩርታ ባፏ ሙሉ ባልበልጣችሁ አትበ-

ልጡኝም ብላ የውሸት ትንቢት በሚያወሩበት ላይ ልትናገር ትችላለች ።

እውነት ነው አውሮፖች ዛሬ ሁሉም እራሳቸውን ችለዋል እራሳቸውንም ተመቻል አልፈው ርቀው ሄደው ሰው ይጠቅማሉ ሰው ይጎዳሉ ።

ኢትዮጵያ በዘመኑዋ እንዲሁ እንዳሁን እንደነሱ ጊዜ ነበረች ተወሰኑዋ አልፋ ሄዳ ብዙ ሰው ትጠቅም ትጎዳ ነበር

እውነት ነው እስላም በአንድ አይቅር ክርስቲያን የተባለውን ሁሉ ለማጥፋት የተነሳ ዘመን ብዙ የአውሮፓ ነገሥታቶችም መከራቸውን እንዳዩ ሁሉ ፣ ኢትዮጵያ በቁም ነገሯ ጠንክራ ሃይማኖቷን አልለውጥም በማለት ብዙ ዘመን ሙሉ እንደ ቀበሮ በጉድጓድ ፣ እንደ ጅንጀሮ በገደል እየተሰቀለች ክብዙ ዘመን አንስታ የተጌጠችበት ጌጡዋ እንዳልነበረ ሁሉ ሆኖ እስኪጠፋ ድረስ ተስላም ጋራ ደም ተፋሳ የኢዮብን ጥንካሬና ትዕግሥት ሰጥቷት ያን ሁሉ መከራ ገፍታ እዚህ ለመድረስ በቃች ።

ንጽሕት ኢትዮጵያ ምን ፈጠረች ተጀምሮ እስኪጨረስ ድረስ ደግ እንጅ አንድም ክፉ አልሠራች ። ኢትዮጵያ ታረመኔ ተዋግታ ብትድን ክርስቲያኖቹ መች ትተዋት ነበር እግዚአብሔር ሳያግዛቸው ቀረ እንጅ ።

ዛሬም ቢሆን ኢትዮጵያን ቅኝ ለማድረግ የሚመኙ ባዕድ ነገሥታቶች እስሩን ቢያወሩ በዚህ የተነሳ መልክክሞቹ ልጆቿ የሰጡትን ስም የሚነሳት የለም ።

ግን እኛ የዛሬ ዘመን የኢትዮጵያ ልጆች ደም በርግጥ ተዋርዷል የቀረው ይቅርና ፈረንጆች ኢትዮጵያን ለማቅናት ትንሽ ትልቁ እስኪአውቀው ድረስ ማሰባቸው ለኛሞታችን ነው ምነው እኛ የፈረንጅን አገር ለማቅናት አለማሰባችን ።

ይህን አለማሰባችን ተነሡ የሰነፍን ብንሆን አይደለሞይ እንግዲያማ በሐገር ስፋት ቢሆን በፈር ብልጥግና ቢሆን ኢትዮጵያ በትበልጣቸው ተብዙዎቹ አታንሳቸውም ነበር ። ነገር ግን እኛም እራሳችን የማንመረመረው ፈረንጆችም እውነተኛውን ምክንያት ሳያውቁት እየቀሩ እኛ ኢትዮጵያውያኖች እንዲህ በአእምሮ ከተፈጠሩ ፍጥረቶች ሁሉ በታች የምንታይበት ምክንያት ምንድር ነው ።

እውነት ነው እስላም ባንድ አይቅር ክርስቲያን የተባለመከራዋን ያየች ብዙ አገር መከራቸውን የተቀበሉ ሞልተዋል በዚያን ጊዜ የተቀበሉት መከራ እስከሁን ድረስ ያልተለያቸውም አሉ ።

አፍሪካ በቆዳ ስፋት ታውሮፓ ብዙ ጊዜ ብትበልጥ አውሮፓ ደግሞ በሰው ብዛት ታፍሪካ ብዙህ ጊዜ ትበልጣለች ። በአፍሪካ እራሳቸውን የቻሉ ታላላቅ ነገሥታቶች ብዙም የሉ በአውሮፓ ግን ስንትና ስንት ታላላቅ ነገሥታቶች አሉ ።

እስላም አውሮፖችን ለማጥፋት በተነሳ ጊዜ በአውሮፓ እንደምን ያለ ጭንቅ ሆኖ ነበር የስፓኝ መንግሥት በዚያ ዘመን አንድ ትልቅ ተብሎ የሚጠራው ተጨርሶ ድል ተመቶ ነበር ። ተዚያም አልፎ እስከ ፈረንሳይ አገር ሄዶ ፑዊቲየ እሚባል አገር አጠገብ በ፯፻፴፪ ዓመተ ምሕረት ሻርል የሚባል (ዱክ) የንጉሡ ክንቲባ ድል ባይመታው አውሮፓ ባንድ አይቅር ልትጠፋ ነበር ። ለንዲህ ያለውም ጅግና ሻርል ማርቴል ብለው ስም አወጡለት ማርቴልም ማለት መዶሻ ማለት ነው ።

በንደዚህ ያለ ምክንያት የውነተኛው የውቀት መብራት ይህች የክርስቲያን ሃይማኖት በእስላም ረክሳ ተመጥፋት ዳነች

አውሮፓ ሕዝቡ በመብዛቱ ብዙህ የጠነከረ መንግሥት በመኖሩ እየተረዳዱ ተክፉ መከራ ዳኑ በተረፈማ እንደ ግብጽ እንደ ሶርያ ያሉት አገሮች መሠረታቸውን አጥተውት ይኖሩ የለምን ። ኢትዮጵያ ግን ታሪኳ ለድፍን ዓለም የሚደንቅ ነው ።

ቆዳዋ በሰፋ አፍሪካ በምትባል አገር ውስጥ ሺጉጥ ብላ እረዳት ሳትፈልግ እራሷን በራሷ ደግፋ ቢከፋም ቢበጅም እስከሁን ቆየች ። አሁን ግን በአውሮፓ የቆመ የውቀት መብራት በማንኛውም ረገድ በኢትዮጵያ ታለው ይበልጥ ደመቀ ይህም መሆኑ አውሮፖች በገዛ እራሳቸው በቆሙት መብራት ብቻ አይደለም እድሜ ለአሪያን አዋቂዎች የቱርክ ንጉሥ ፪ኛ ሞሐሚ በሺ ፲፬፻፶፫ ዓመተ ምሕረት የክርስቲያኑን መንግሥት ድል መቶ የውነተኛው የውቀት ፋና የተተከለበትን ከተማ ክንስታቲኖፕልን (እስጥምቡል) ቢቀማ በዚያች አገር የነበሩ መምህራንና ፈላስፎች በእስላም መንግሥት ተመገዛት እያሉ የክርስቲያን መንግሥት ወደሚገኝበት ሸሹ ።

እንደዚህም ያለው ምክንያት አውሮፓ ለቆመው የውቀት መብራት አጋጋር አድማቂ ሆነ ፊት ይነድ በነበረ እሳት ላይ እንጨት ሲጨምሩበት እሳቱ እየደመቀና እየበረታ እንደሚሄድ ሁሉ ይህም ነገር የሆነበት ዘመን በአውሮፓ ሕዝቦች ብዙህ ክብር አግኝቶ ሞአየን አጋር ተብሎ ይጠራል ። (ፍችውም መሐከለኛ ዘመን ።)

በኢትዮጵያ አገር ግን አንድም አጋጋር እስከሁን አላገኘን ቢከፋም ቢበጅም እኛው ራሳችን በፈለግነው ብልሃት ነው እስከሁን ያለነው ማለት ከባቶቻችን በወረስነው ።

ብዙሕ የአውሮፓ ሰዎች የኢትዮጵያ ሕዝብ አይሰለጥንም እያሉ ትንቢት የሚናገሩ እውነትስ የሕዝባችንን አንጎል በቀጡ መርምረው አውቀውት አለዚያም የነቢይ ዕውቀት ተሰጥቶአቸው ተነብየውት አይደለም ። የወደቀ ግንድ ምሳር ይበዛበታል እንደሚሉ እኛ የኢትዮጵያ ልጆች ተትምሕርት ስንገዝር ስለተራራቅን እንደሁ ሆነን እምንቀር መሰላቸው ። ወንጌል ዘማቴዎስ ወብዙኃን ቀደምት ይከውኑ ደኀርት ወደኃርት

በአውሮፓ በሁሉ በታ የተማሪ ቤት ከፍተው ልጆቻቸውን በተወለዱ በ፯ ዓመታቸው አስጀምረው እስከ ፲፫ ዓመት ዕድሚ ድረስ በግድ ያስተምሯቸዋል ። በፈረንሳይ አገር ሕግ አንድ ልጅ በ፯ ዓመቱ ትምሕርት ጀምሮ እስከ ፲፫ ዓመት ተምሮ በሕግ ሊአውቅ የግድ አለበት ወሰን ታልደረሰ ትክክል እንደ ወንድሞቹ ሥራ ሊአገኝ አይችልም በተወለደበት አገር ። እኛ የኢትዮጵያ ልጆች እንኳንስ እንዲህ በግድ ይዞ እሚአስተምረንና በገዛ እራሳችንም ፈቅደን ዕውቀት ብንፈልግ እሷን ለማግኘት ትምሕርት የምንማርበት በታ የለንም ።

ምክንያቱን ያላወቀ በመንግሥታችንና በበቶቻ ሊያዝን ይገባዋል ። ምክንያቱን ያወቀ ግን ታላቁ ንጉሥችን ሰሎሞን በ ጊዜ ለኵሉ ያለውን ያስባል እንጅ ሌላ በማንም አያዝን ።

ስለምን ቢሉም እስከ ዛሬ በሀገራችን መንግሥታችንም አባቶቻችንም የትምሕርትን ፍሬ በትምሕርት የሚገኘውን ጣም አያውቁትም ነበርና ነው እንጂ ይህን አውቀው ቢሆን ግን የትምሕርት ቤት በያለበት እየሰሩ የኢትዮጵያ ልጆች በመልከም እንዲማሩ የተቻላቸውን ያህል በለፉ ነበር ።በኢትዮጵያ መንግሥታችንም አባቶቻችንም ሃይማኖታችን ጠንታ ሀገራችን ተፈርታ ተከብራ እንድትኖር በሚያስፈልገው ነገር ሁሉ አስበውና ታጥቀው መቀመጣቸውን ሥራቸው ይመሰክርላቸዋል

(የተረው በሚከተለው ቁጥር ይታተማል ።)

ታዛገዥ ልጃችሁ ሰ ሥ ሚ ። አስመራ

ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያን ልጆች አይናቸውን ለመክፈትና ዕውቀት እንዲሰፋ አስበው የሠሩትን የትምሕርት ቤት ባየሁ ጊዜ ያሥር ዓመት ልጅ ለመሆን እንደተመኘሁ ኃሳቤን አምላክና ልቤ ያውቀዋል ።ለትልልቆቹም የተማሪ ቤት እንዲከፍቱልን ተስፋ አለን ። ይህን መልከም ሃሳባቸውን እድሚያቸው እረዝሞ እንዲፈጽሙልን እግዚአብሔርን እንለምናለን ፤ ሁለተኛ ልዑል ራስ መኰንን ለሀገራቸው ለኢትዮጵያ ጥቅም ይፈልጉ ነበርና ዓረብ ዘመቻ ሲሄዱ ወሊጋ ደርሰው ደጃዝማች ገብረ እግዚአብሔርን ጠሩና ፴ ዳውላ ቡን ለስንቅ አምጣልኝ አሏቸው ። ደጃዝማች ገብረ እግዚአብሔርም ራስ ሆይ ፴ ዳውላ በሀገሬ አይገኝም የተገኘውን ያህል ላምጣ እንጂ ቢሉ ልዑል ራስ መኰንንም ምነው በገርህ ቡን አልተከልክምወይ ብለው ጠየቋቸው ። እሳቸውም እረ አልተከልኩም እንደምን ይተከላል አላውቅም እኔስ አሉ ። ራስም አሁንሳ ከየት እያመጣህ ነው የምትጠጣ ብለው ጠየቋቸው ፤ ገበ ከሚባል አገር ኑጋዴ እያመጣልኝ ነው የምጠጣው ብለው መለሱ ። ልዑል ራስ መኰንንም እንዴት ተበደላችኋል ብለው ላገሩ በጣም አዝኑና የቡን ፍል ማፍላት የሚያውቅ ፩ ሰው ሰጧቸውና ይኸ ሰው እስከ ሁለት ዓመት ከንተ ዘንድ ቈይቶ ፍሉን አፍልቶ በተኖ አተክክሉን አሳይቶህ ይምጣልኝ ብለው ሰጥተዋቸው ሔዱ ። እሱም ሁለት ዓመት ከደጃዝማች ገብረ እግዚአብሔር ሀገር ተቀምጦ አፈላሉንና አተካከሉን አሳይቶ ሸኝተው ሰደዱት ። ከዚያ በኋላ ደጃዝማች ገብረ እግዚአብሔርም ትጉህ ነበሩና የሀገራቸውን ሰው ሁሉ [illegible] ልብሱን ለበሰ ። ወዲያው ላመት ግብር የሚቸገር ሰው የቡናውን ፍሬ ለቅሞ እየሸጠ ያለችጋር ከፈለ ። ያገሩ ሰው ዕድሜ ለመኰንን ይህን ያመጡልን ልጅ ይውጣልዎ እያለ እየመረቀ ሀብታም ሆኖ ሲኖር አሁን ከ፳ ከ፯ ዓመት ወዲህ ሶስት እጅ ደርቆ እሩብ ያለ ይመስለኛል በግምት ። ደጉ ልዑል ራስ መኰንን ላገር ጥቅም ብለው ያስተማሩትን ቡን አሁንም ደርቆ አልቆ ሀገሩ እንዳይደኸይ ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን መድኃኒቱን ከአውሮፓ አስፈልገው አምጥተው ምርቃኑን አሳልፈው እንዲቀበሉ ተስፋ አለን ። የሀገራቸው ጥቅም ነውና ።

ሶስተኛ በወለጋ ወረዳ ያለውን ሀገር የሻለቃው ባይበረታበት በየመንገዱ ባላገሩንም መንገደኛውንም ሽፍታ ይቀማ ጀመረ ። ጥንት ሽፍታ ሲጀምር በቶኬ በጨሊያ ተጀመረ ። አሁን ግን ይኸ ሁለቱ አገር የሻለቆች ስለበረቱበት አማን ሆን ። ከቅርብ ቀን ወዲህ ጨሊያ አገሩ በልዑል አልጋ ወራሽ እጅ ሁኖ ፊታውራሪ ወልዳማኔልን ከሾሙበት በጤና ተቀመጠና ሽቦከ ከሚባለው አገር ጀምሮ እስከ ደጃዝማች ገብረ እግዚአብሔር ሀገር ድምበር ድረስ መንገደኛም ባላገርም ይቀማ ጀመር ። ይህን ልዑል አልጋ ወራሽ በብሩህ ልቡናቸው አስበው ፩ ሥርዓት ታላቆሙለት ጠረፍ ጠረፉ ከጠፋ ለመንግሥት ብዙ ጉዳት ሳይሆን አይቀርም ።

ፊታውራሪ ኪዳነ ማርያም ።

ይህን ለጥቆ ያለ ቃል የጻፈ ሰው መርጠው ተውብኝ እንዳይልና ምላሽም የሚመልስለት አያጣም በማለት አትመንለታል

ይድረስ ከክቡር አቶ ገብረ ክርስቶስ አጅጉን ብዙውን እንደምን ሰንብተሃል እግዚአብሔር ይመስገን እኔ ደህና ነኝ ልዑል ጌታችን ብርሃንና ሰላምን አክብረው በማቆማቸው በሙሉ ኢትዮጵያ ሐሳባቸውን ሐገሬም ያለመታዎክ እንድትኖር እንዳሰቡላት ያስረዳናል ከሐሰት ነገር ለመራቅና ለሕዝብ ምክር ማከፈያ የተሻለውን መንገድ ለመያዝና ሕዝባቸውን እንዲመክሩብትና እንዲያጥናኑት በብርሃንና ሰላም በጣሙ እንረዳለን አንተንም ወንድማችንን ስለሀገርህ ድክምና ሐሳብ እንዳለብህ አውቀው ለሥራቸው ወሳኝና ምክር ፈጻሚ ማድረጋቸው ብዙህ ደስ ያሰኛል ፊታውራሪ ዴሬሳ ከሐገራችን ስለሚሄደው ሰንጋና እህል የሚለውን ቃል ስላዩሁ መልከም ነው እጅግ ድንቅ ነው ነገር ግን ለዚህ ነገር መጀመሪያ ሐገርን ሚዛንማግባት ያስፈልጋል ሚዛን ማለት እንዲህ ነው ፤ ኢትዮጵያ ሰው ከለበት ይልቅ አውሬ የሚረባበት ዱር ይበዛል ከብት ካለበት ይልቅ ከብት የሌለበት ይበልጣል ደግሞም ከብት ያለበት ሐገር ጥቂት እሩብ መሬትስ አትሆንም ይህን ሳይመዝኑ ሥራ ቢያደርጉ ላገር ጥፋት ለመንግሥት ጉዳት ለሕዝብ ድኅነት ማይሆን አይቀርም በሀገራችን በኢትዮጵያ እንደሌላው ሀገር ሁሉ አታክልትና የንጨት ፍሬ መብላት አልተለመደም እስከሁን ድረስ በኢትዮጵያ ላይ አንድ ዘመን ትልቅ ረሃብ ሆኖ ነበር የረሃቡም ምክንያት መጀመሪያ ከብት አለቀ ከዚያ በፊት የከብት በሽታ አልነበረም አንድ ዴ ቢመጣ ምጥጥ አድርጎ ጨረሰው ከዚህ በኋላ የሚታረስበት ከብት ስለታጣ አህያ ያለው አህያውን ፈረስና በቅሎ ሳይቀር እንዲያው አላገበብ ፫ ዓመት ይሆን አባት ልጁን ልጅ [illegible] እግዚአብሔር የተቀረጠ ነገር ስለሆነ ምንም ቢያደርጉት ሳይሆን ቀረና ፤ በረሀብ የሚያልቀው ሰው እጦርነት ውስጥ በመትረየስ ያለቀ ይመስል ነበር ። ስለዚህ መንግሥታችን ትክክለኛ ሚዛን ማቆም ያስፈልጋል ባህል በኩል ይህን ሚዛን ማግባት ያስፈልጋል ማንኛውን አገር ብላጊ ሰጥቶታል ማንኛውን አገር ከረምት አንሰታል በማንኛው በኩል ገበሬ ምርት አምርቷል ብሎ ይህን ሳያዩ ሚዛን ሳይሆን ሥራ ለመሥራት አገር ላገር አሳልፎ ቢሰጡት ይህም ደግሞ ላገር ጉዳት ለመንግሥትም ጥፋት ለሕዝብም ድኅነት ይሆናል ይህን መንግሥት አይቶ ታላደላደለው ላገሩ ጉዳቱ ለሕዝቡ ድኅነት ሳይሆን አይቀርም በሀገራችን የኢትዮጵያ ዋናው ፋብሪክ በሬ ተገበሬ ሲል ይገኛል ። ይህንኑም ማየትና ሚዛን ማግባት ያስፈልጋል ምን አንሰ እንደሆነ እያነሡ ስለሄዱ እኛ ስላነስን ነው

እንጂ ያሉትስ ለሀገራችን ለኛውም ይበቁን ነበር ለኛም ብድር ያስፈልገን ነበር ስንኳንስ ለሰው አሳልፈን እንሰጥና አገር ላገር መገበያየት እንጂ ምንም ያህል ትርፍ ያለው አይመስለኝ እሚዛን ቢያገቡት ስንኳንስ እንሰጥና እናበድር ዘንድ ምንም የሚቻለን አይመስል ለመንግሥታችን ጉዳት ለኛም ድህነት ነው ትርፍ ላገር የሚያጐድል ለሕዝብ ጤና ላገር ደህና መንግሥት ቢያይና ማንኛው ጠፍቷል ማንኛው ለምቷል ብሎ ትክክል ሚዛን ማቆም ያስፈልጋል ።

ይነሱ ደነቀ ።

ኢትዮጵያ የዕውቀት እርሻዋን ለማልማት በብርሃንና ሰላም ስለ ገለጸችልን አስቤ ጽፌአለኹና እንዲታተምልኝ እለምናለሁ ።

ክቡራን መኳንንቶች ሕዝባችሁን
ውደዱ ። መንግሥታችሁን እርዱ ።
በሀገራችኍ አውሬኛ ደግ እንዳይበደል
ፍርድ እንዳይጓደል አስቡ ።
ያባ ስጉድን ቤት አታዩትም ወደ ።
ያባ ሻንቆንስ ቤት አታዩትም ወደ ።
ያባ ቀማውን ቤት አታዩትም ወደ ።
ስንቱን ልቁጠራቸው አስተውሎ ለሚያደ
ስሙኝ ልንገራችኍ መኳንንቶች ሁሉ
በየ ማዛታችኍ ባውሬኛችሁ ሁሉ።
ድልድዩን ሠሩታችሁ መንገዱን ደልድሉ
ብርሃኑ ይከፈት ይታየው ለሁሉ ።
ገንዘብ አዋጥታችሁ ፋብሪካ ትክሉ ።
ጥበብ ሠርቶ ይልበስ የታረዘው ሁሉ ።
ሐኖንት ጥቅም ነው ለመንግሥትም ክብር
ሕዝቡም ይስለጥን ከዳር እስከ ዳር።
አገራችን መልካም በወርቅም በብር ።
ምቀኝነት ይጥፋ እንኹር በፍቅር ።
እክብራችሁ ያዙት የውቀቱን መምሕር
አውሮፓን አሻግሮ ጥበብ ከሳያችሁ ።
የልባችሁ ቁልፉ ይከፈትላችሁ ።
ስማችሁ ይጠራ እስከ ልጅ ልጃችሁ ።
ኢትዮጵያ ሆይ ።
የጸድቃን ማረፊያ ገነትን መሳይ ።
ባዕድ እንዳይነቅሽ ክፉም እንዳታይ ።
ዘውዱን ለዘውዷ ብለው ኖሯል ወደ
አስ ማወቃችን ዓለም አታሳይ ።
ደገርማል ደደንቃል አስተውሎ ለሚያደ
ምኒልክ ፈጽሞ ነበደ ኖርዋል ወደ ።
ተፈሪን ጨፈቃ ዘውዲቱን ፀሐይ ።
አምላክ አስተናብሮ እንዲህ ደስመንወደ
ከዚህ ወዲያስ ዓለም ደፈጠራል ወደ ።
እንዲህ ኛና ልብስ ምን ያደርግልናል
ተፈሪ ጥበቡን ሠርቶ ያለብሰናል ።
ድርብና ኛና ቀድሞስ መች ጠፋና ።
ወንድ አንተ ተገኘኽ ጥበብ ለበስከና ።
ባቡር ገመገስ ሽቀጡን ያዘና ።
ገበያው ተፈሪ ሆና ተገኘና ።
ጽፌም አልችለ. ፈጽሞ ባዋራ
ከንዲህስ ወዲያ ጠቅል ያንተን ሥራ

ኃይለ ሚካኤል አያልቅበት ።

ማ መ ል ከ ቻ ።

በ፳፩ ቊጥር ጋዜታ በኢትዮጵያውያን ማኅበር ለሚቆመው ተማሪ ቤት እንደአቅማችን ገንዘብ ልንሰጥ ተነግሮልን ነበር በዚሁም ብዙ ሰው ደስ ብሎታል ፤ ሁሉም በያቅሙ ከመስጠት እንዳይመለስ ተስፋ እናደርጋለን ። በልብ ቅንነት የተሰጠ ትኒሽም ቢሆን እግዚአብሔር ከባረከው ለብዙ ጥቅም ይሆናል እጅዋን ዘርግታለችና የሚቻለንን ያህል በልብ ቅንነት እንስጣት

ያገራቸውን ፍቅር ለመግለጽ የሚቻላቸውን ያህል እየረዱ ተማሪ ቤት እንዲቆም ፈቃዳቸው እንደሆነ በመት በመት የሚሰጡትን ገንዘብ ልክ በፊርማቸው ያስታወቁ ሰዎች በሚመጣው ብርሃንና ሰላም ስማቸውና ሊሰጡ ያስታወቁትን የገንዘብ ልክ በዝርዝር እናትምላችኋለን ።

የፈላስፎች ቃል ።

በትምህርት ማደግ የኑሮ ብልሃት ነው ።በደህና የመኖርያም ኆይ ነው ። ላቡላይ ።

ማስተዋል የሚያውቅ ሰው ጊዜው አይጠፋበትም ።ለሌላው ሥራ ፊት የሚሆን ለራሱ አስተዋይና አሳቢ ነው ።

አ ደ ቢኚ ።

መኖር መሥራት ነው በኑሮው ምንም የማይሠራ ሰው ኑሮው ከምንም አይቆጠር ፤ ማዳም ጉዞት ።

ኑሮ ፈሳሽ እንዲኖረው ያስፈልጋል ።ውሀም ቢሆን ፈሳሽ ከሌለው ይበላሻል ። ላማርቲን ።

ኑሮን ለመማር ሙሉ ንብረት ያስፈልጋል ።ሞትንም ለመማር የድንገት ነገር ያስፈልጋል ፤ ሴኔክ ።

ታላላቅ ነገርን ለመፈጸም ሞት እንደሌለብን አድርጎ እስበ መኖር ያስፈልጋል ፤ በበናርግ ።

እውነተኛ ሥልጣኔ በማደስ ይገኛል፤ አ ቢኒት ።

ኑሮ ዋጋ ያለው ወደፊት ለመቀደም የሚደረገውን እርምጃ ያህል ለብዙ ጊዜ ነው እንጻሩን ማስረዘም ራሱንም ማሳደግ ነው ። የሚገለበጥ ይጠፋል ።የማይታደስም ይሞታል ።

አ ኪኔት ።

በቴሌግራም የመጣ ቃል ።

ያ፲፫ ግንቦት ተከታይ ወሬ

ፓሪስ ።ሚኒስትር ክዩ ከገንዘብ መርማሪዎች ጋራ ተገናኘ እነሱም ነገሩን ሁሉ መርምረው ባዲሱ ሥራ የገንዘብን አኳኋን እንደተሻሻለ አስታወቁ ። ደግሞም የፈረንሣዊን መንግሥት ገንዘብ አኳኋን ለማሻሻል ስለ ተሰማሙ መንግሥቱ የሚቸግረውን ነገር ሁሉ በእምነት ለሕዝቡ እንዲሰጥ አሳባቸውን እየገለጹ ነገራቸውን ጨረሱ ከዩ መጠራቱን ለከንቱ እንደማይሆን ገልጸ የሚያስረዳ ነገር ተናገረ ።

አቴን ።የጦር ምኒስትሩ ጋኒራል ፒቲቴሮሩዎን የላይኛውን የጦር መዓርግ ልሽን ሰጠው የኢጣሊያ መላክተኞችና መርከቦች ለኢጣልያ ወታደር አጐበር ለማድረግ የሚሰበሰበውን ጉባኤ አብሮ ለመዋል ዛሬ በእኩል ቀን ወደ ሳሎኒክ ለመሄድ ተነሱ ።

ቢየና ።የቀድሞይቱ ንግሥት ዚታ ጉሮሮዋን ስለ ታመመችና የሳምባ በሽታም ስለ ያዛት ጋዜጣዎች ስለ ጤናንትዋ የሚያስፈራ ወሬ ያወራሉ ።

ሮማ ።ሚኒስትሮቹ ሁሉ ባዳልዮን የወታደሮች አለቆችን አዛጋ ግራጂዮሊም የሱ እንደ ራሴ ክባሴሮሞ የጦር ሚኒስትር እንደራሴ አሚራልዮ አክቶንም የባሕር ወታደሮች

ክንትራሚራልዮ ሲሪያኒ የባሕር ሚኒስትር እንደራሴ ጄኔራል ፒቺዮም የአየር መርከብ ወታደሮች አለቆችን አዛጋ ኰሎኔሎ ክሰኔ የሱ እንደራሴ ጄኔራል ቦንሶኒ፤ የአየር መርከቦች ሚኒስትር እንደራሴ እንደሆኑ ቆርጠዋል፤ ደግሞም የምክሩ ቤት ግራንዲ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር እንደራሴ ቱሩሲም ያገር ግዛት ሚኒስትር እንደራሴ እንዲሾሙ አሳቡን ገለጸ ።

ከፓሪስ የታተመ የአሜሪክ ደቡብ ሐሳብ(የፈረንሳዊ ራዲዮ ማኅበር)ማልቢ የተባለው ጋዜጣ ወደ ስፓኞል መንግሥት ትልልቅ ሰዎች መልክተኞች መስደድ እጅግ የሚያስፈልግ እንደሆነ ያመለክታል ።

ቤልግራድ የቡልጋሪ ወገን በኃይል የሴርብን ዳርቻ አልፈው፬ት ቤት አቃጠሉ በላገሮቹም ሽፍቶቹን አበረሯቸው ።

በልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ።

መጀመሪያ ዓመት ፡ ቁጥር ፳፫ ።
1^re ANNÉE №. 23

ሐሙስ ግንቦት ፳፯ ቀን ፲፱፻፲፯ ዓ ም ።
JEUDI 4 JUIN 1925

ብርሃንና ሰላም

LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፰ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፲ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

የጋዜጣው ዲረክተር ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲረክተሩ ያስታውቁ ።

የራሱን ጉዳይ የሚያሳትም ሰው ዋጋውን እየከፈለ እናትምለታለን ።

ከፊተኛው ቍጥር የቀረ ይህ ነው ።

እውነት ነው ዛሬ ኢትዮጵያን ያየ ሰው የሐገራችንም ሰው ሆነ የውጭ አገር ሰው ቢሆን ይህ የምለው ነገር ከንቱ መስሎ ሳይታየው አይቀርም ። ስለሆነ ግን የፈለገና የለፋ ነውና ጥቅም ያለውን መንገድ ማግኘት የሚችል አሁንም ይህን የምለውን ሁላችሁም በየወገናችሁ መርምሩት ።

ፈረንጆች በዚህም በዚያም ምክንያት በሀገራቸው የውቀት መገኛን መንገድ ቢአሠለጡኑዋት እኛ ደግሞ ለጊዜው በሚያስፈልገን መንገድ ሀገራችን ኢትዮጵያን መከላከያ መንገድ አሰልጥነን ነበር የምንቀመጥ ። ይህም ማለት መንግሥታችን አባቶቻችን ለኛ ለልጆቻቸው ዋና ትምሕርት ያስተምሩን የነበረው ፈረስ መጋለብ ፤ጦር መወርወር ፤ ውሀ መዋኘት ፤ ጦም ውሎ ጦም አድሮ መዋጋት ለጠላት ፊት አለመመለስ ይህን ይህን የመሰለ ለዘመኑ የሚያስፈልገውን ነበር ። በንደዚህ ያለውም መንገድ የኢትዮጵያ ልጆች ስማቸውን ከዓለም ዓለም ኗሯ [illegible]

የኛ ዘመን ግን የዚህ የጥንት የአባቶቻችን ትምህርት ዘመን አይደለም የኛ ዘመን ተጥንቱ ታባቶቻችን ዘመን በጣም ልውጥ ያለ ነው ። አሁን የኛ ዘመን የሚፈልገው የሥጋ ጉልበት አይደለም ። የኛ ዘመን የሚያስፈልገው ግን ያንጎል ብርታት ነው ያንጎል ብርታት በምን ይገኛል ቢሉ በትምህርት ነው ።

ኢትዮጵያ ከብዙህ ዘመን አንስታ በአውሮፓ ትልልቅ ነገሥታቶች መኖራቸውን ታውቃለች ግን እነዚህ ነገሥታቶች ተሷ የሚበልጡ ይሁን አይሁን አታውቅም ነበር ። አሁን እግዚአብሔር ይመስገን ታጤ ቴዎድሮስ በአጤ ዮሐንስ ጊዜ ታጤ ዮሐንስ ባጤ ምኒልክ ጊዜ አውሮፓ ስሟና ልጆቿ ይቀሩና እስከማድቤቷ ድረስ ታወቀ ፤ ተዚህ ይበልጥ ደግሞ አሁን እግዚአብሔር በነቢያቶች ትልቅነቱንና የሰማይም የምድርም ጌታ መሆኑን አስታውቆ አስታውቆ በማከያው ልጁን ወልድን ለዚች ተበላሽታ ፈርሳ ለነበረችው ዓለም አዳኝ ሠሪ እንደላከ ሁሉ ኢትዮጵያም የተመሰገነውን ልጇዋን ተቀሩት ተተወለዱት ወንድሞቿ ጋራ አድርጋ በቅጡ ሳታውቀው ወደምትኖረው አገር አውሮፓ ተፈሪ መኰንንን ላከችው ፤ በዚህም የተነሣ ዛሬ ክብርት ኢትዮጵያ አውሮፓን ምርምር አርጋ አወቀቻት ፤

እስከ ዛሬ ያለውቀት በኢትዮጵያ ሊሰራ የተገባው ሁሉ አልተሠራም እንግዴህ ወዲያ ግን ሊሠራ ተጀምሯል ። አሁን ግን ብዙ የተማሩ የአውሮፓ ሰዎች በኢትዮጵያ ሁለንተናው እያማረ ባለመሔዱ ስለምን ይነቅፉናል ። እንኳንስ ኢትዮጵያን የምታህል አገርና ያንድ ባለጠጋ ቤት ስንኳን ፊት የቆመውን ሥርዓት ለውጦ አዲስ ለማግባት ብዙ ልፋት አለበት ።

አሁን ልዑል አልጋ ወራሽ ተዚህ ቀደም ሀገራችንን የሚጎዳ ደማችንን የሚያቀርድ ባህል ሀገር በሚያለማ ደም በሚያስከብር ባህል ለመለወጥ ያስባሉ ያጣጣራሉ ። ግን ይህ በመልክም እንዲፈጸም ማነው የሚረዳቸው ። ሰው ሞኝ ነው ዛሬ [illegible]

ሰውን የሚረዳው እግዚአብሔር ነው ሰውን የሚረዳው ጊዜ ነው ።(በጊዜ ለኵሉ) ስለዚም ልዑል አልጋ ወራሽ የኢትዮጵያን ብርሃን እንደ አውሮፓ ለማድረግ የጀመሩት ሐሳባቸው የሚፈጸም ይመስልሃል ወይ ። እሰናክይስ ሐሳባቸውን ከንቱ እያደርገውም ወይ ብለው ለጠየቁኝ ሰዎች በሙሉ ሐሳቤ እሰናክይ ለራሱ ተሰናክሎ ይቀራል እንጅ የሳቸውን ሥራ ከንቱ አድርጎ ለማስቀረት የሚችል አይገኝም ።

ዛሬ በኢትዮጵያ የውቀት ብርሃን እንደናንተ አገር እንደ አውሮፓ እንዳትሆን የማያስብና የማይሠራ የሕዝባችን የሀገራችን የመንግሥታችን ባላጋራ ነው ተዚህ ይበልጥ ደግሞ የጊዜ የዘመን ደበኛ ነው ።

ተጊዜ ተዘመን ጋራ ሊጣላ የሚችል ማነው ቢጣላስ

ለመውደቅ እንጂ መቼ ሊጥል ነው ። ስለዚህ ሁሉ ዛሬ ልዑል ተፈሪ መኰንንን የሚጋፋ ቢኖር ጠቡ ከሳቸው አይደለም ተጊዜ ተዘመን እንጂ ብዬ መለስኩላቸው ።

ግን ይህን ምላሽ የሰጠኋችው የትንሽ ወስላቶች ወይም የደንቆሮች ሐሳብ እየተመለከቱ ድፍን ኢትዮጵያ ሐሳብ እንዲሁ መስሏቸው ኢትዮጵያ እንደዚሁ ሆና የምትቀር እንዳይመስላቸው ብዬ ነው በተረፈ ግን እግዚአብሔር ይመስገን ክቡራን አባቶቼን ሁሉን ባይሆን ብዙዎቹን በመካከላቸውም በማደግ እንዲጋጣሚም እየሆነ ተነሡ በመጫወት ተውጭ አገር ሰው ይበልጥ አውቃቸው ይመስለኛል ስለዚህም ያለውቀት በስህተት ተሚደረገው በስተቀር የኛ የኢትዮጵያ ልጆች አባቶች ሀገራቸውን የሚጎዳ ደማቸውን የሚያዋርድ ሥራ በውቀት የሚሠራት አንድም አይገኝም አንዳንድ ቢገኝም ይህ የሚያስገርምና ተስፋ የሚያስቆርጥ አይደለም ።

ኢየሱስን አሳልፎ የሰጠ በጁ የበላው የጠጣው የገዛ ደቀ መዝሙሩ ይሁዳ አይደለሞይ። ሲሆንማ ፲፪ ፍሬዎች ነበሩ የኢየሱስ ክርስቶስ ደግነቱ ሥራው የሚሰጣቸው ተስፋ ይቀርና የሱ ሰው ነኝ ተብሎ ማደሩ ብቻ ብዙ ያኮራ ነበር ነገር ግን ሰው ትልቅነቱም ትንሽነቱም በሥራው ነውና ይሁዳ በገዛ ውርደቱ ክፉ ሆነ ።

አሁን ይህን ያስጻፈኝ በሀገራችን የገባች የውቀት ብርሃን ትጠፋለች ገና ልትገባ የምታዘግመው ትቆማለች ትሸሻለች ብዬ አይምሰላችሁ ይህ እንዳይሆን በብዙ ነገር ተረድቼዋለሁ ይህን ያጻፈኝ ግን ክቡራን አባቶቼ በንዲህ ያለ በጸያፍ ሐሳብ ስማቸው መጠራቱን ይወቁት በማለትና ለክቡራን አባቶቼ እንዲህ ሞገስ የሌለው ስም ምነው ወጣላቸው ብዬ አዝኜ ነው።

ታዛዥ ልጃችሁ ሰ ሥ ሚ ።

በ፳፪ኛው ቁጥር ብርሃንና ሰላም ይነሱ ደነቀ የተባለ ሰው በገራችን ንግድ እንዲለማና እንዲሰፋ ድሀም በማረሱ ከብት በማርባቱ ትርፍ እንዲያገኝ የሚያነቃቃ ቃል የጻፉትን ሰዎች ሐሳባቸውን እየነቀፈ ጽፏል ።

በጻፈውም ውስጥ አገራችን ሰው ካለበት ይልቅ ሰው የሌለበት ፣ ከብት ከሚረባበት ይልቅ አውሬ የሚኖርበት ይበልጣል ይላል ። ክርሱ በፊት የጻፉት ሰዎች ደግሞ እንዲህ ነው ያሉት ፣ ሰው የሌለበት ጠፍ የሆነ ቢያርሱት ግን ፍሬ የሚሰጥ መሬት ብዙ ነውና የተገኘው እህል ብዙ የሚሸጥ ሲሆን ሰዉ እርሻን ያሰፋል በእንዲያው የሚቀመጠውም መሬት ሲታረስ ጊዜ እርሻ ስለበዛ እህል ይበዛልና እንደ ሸማቹ ብዛት ሸያጩም ይበዛል ብለው ነው የጻፉት ።

ደግሞ በከብት ማርባት ብዙ ጥቅም የማይገኝ ስለሆነ ከብት የሚያረባ አንሶ የአውሬ መኖሪያ ሆኖአል ስላለውም፤ ከብት በብዙ ተሸጦ ዋጋ የሚያወጣ ቢሆን ከብት የሚያረባው ይበዛና የዱር አውሬ መኖሪያ ሆኖ የነበረው ሰፊው መሬት በእንዲያው ከሚቀመጥ ከብት እየረባበት ብዙ ኢትዮጵያውያንን በጠቀመ ነበር ።

ይነሱ ደነቀ በሬና እህል በጣም ከመውደዱ የተነሣ በሬና እህል እንዳይኼድበት እንጂ የድሀው ጥቅም የመላው ሕዝብ ትርፍ ማግኘት አልተገለጠለትም ። ስለ ከብትና ስለ እህል ክርሱ በፊት የጻፉ ግን ጥቅሙን እያስረዱ ነው የጻፉት ። ግን ለብዙዎች ሳይገባቸው እንዲቀር ለይነሱ ደነቀ ሳይገባው ቀርቶ ይሆናል ። የልቡን በር ያልከፈተ ደግሞ ምንም ነገር እንደማይገባበት የታወቀ ነው ።

ኢትዮጵያውያን እንግዴህ ነጋላቸው፤ይነሱ ብለን ስንቀሰቅስ በርሚል ውሀ ተደፍቶባቸው ከእንቅልፋቸው ባነው የማይፈራገጡ የማይንቀሳቀሱ ሰዎችን መስለው ቢገኙ በጣም እናዝናለን፤ነገሩም ለሰማው ሁሉ የደነቀ ነው ። ግን ተቀስቅሰው የነቁ ደግሞም የሥራ ጊዜ መሆኑን አውቀው የሚጠቅም ሥራ ለመሥራት የተሰናዱ ብዙ ናቸውና እንጸናናለን ።

ይድረስ ለወዳጄ ላቶ ገብረ ክርስቶስ
ሰላም ላንተ ይሁን ፡

ብርሃን ወሰላም ተብሎ የተሠየመ ጋዜታ በመውጣቱ ብዙ ደስ ብሎናል። ስለምን ጋዜታ የስልጣኔ መምሕር ነው የጨለመውን ያበራል የተሰወረውን ይገልጣል። ከሁሉ ደስ ያለን ሰው ሁሉ የልቡን አሳብ ገልጦ እንዲናገርና እንዲጽፍ ልዑል አልጋ ወራሽ ስለፈቀዱ ነው ። ይህን ፈቃድ መፍቀዳቸው የኢትዮጵያን ሕዝብ አርነት የማውጣታቸው ምልክት ነው ። ይህን አርነት ሴት ወንዱ ትንሽ ትልቁ በልልታ በደስታ መቀበልና መመረቅ ይገባዋል የጋዜታ አርነት ግን ለሚገባ ለሚጠቅም ነገር ነው እንጂ ለማይገባ ሰው ለሚያዋርድ ወይም ለከንቱ ውዳሴ ለመጻፍ አይደለም አገሩን የሚወድ ሰው ቅን መሆን ያስፈልገዋል። ለዛሬ በረጅሙ መጻፍ አልተቻለኝም ቢቻለኝ ደስ ብሎኝ በጻፍሁልህ ነበረ ። ነገር ግን አሁን ጊዜው የርሻና የዘር ጊዜ ስለሆነ ወደቀላዶቼ አሳቤ ሁሉ ስለሆነ ቸግሮኝ ነው ።

አሁን ስለተማሪ ቤት ኢትዮጵያን የሚወድ ሰው ሁሉ እንዳቅሙና እንደችሎቱ ገንዘብ ይስጥ ስለተባለ እኔም እንዳቅሜ በድሜ እስካለሁ ድረስ በያመቱ ሶስት ሶስት መቶ ብር እሰጣለሁ ባዘዝኸኝ ጊዜ መስጠቱን እጀምራለሁ። ይኸ ጥቂት ስጦታዬ ግን ተዘርቶ የሚያበቅለውና የሚያፈራው ፍሬ ብዙ ይሆን ዘንድ ተስፋ አለኝ ፡፡ ስጦታዬ ትንሽ ቢሆን ያገሬ ፍቅር ትልቅ ነው ። የተማሪ ቤቱን አጀማመሩን ካየሁ በኋላ ሌላ ገንዘብ እጨምራለሁ። ስለምን እንዲህ ላለው ነገር ገንዘብ መስጠት ማበደር ይባላል እንጂ መስጠት አይደለም ። ስለምን ስለ አገር ጥቅም የተሰጠ ነገር ዋናው አንድ ሲሆን አንዱ ሺህ ይሆናል ኢትዮጵያን በቅን ልብ የሚያስቡላትን ሰዎች እግዚአብሔር ይደግፋቸው ዘራቸውን ለዘላለሙ ይበርከው ያለምልመው ።

አቶ ፈቃዱ ።

እኔ ከሰው ሁሉ ያነስሁ ተክለ ሃይማኖት ብሩ ሥራዬ በዳግማዊ ምኒልክ ትምሕርት ቤት መማር ነው ።

ሌላ ገንዘብ ስለ አልኖረኝ ብዙ አድርጌ አዝናለሁ፤ምነው እንደ ርግብ የዋሃን ሁኑ ፣ እንደ እባብ ብልህ ሁኑ የሚለው ቃል ትዝ አለኝና አሁንስ እባብ ራሱን ከተመታ ወድያ ከመውደቅ ሌላ ምን ሊሰራ ይችላል ደግሞም ለሰው ራሱ ክርስቶስና አገሩ መሆኑን ካወቅሁ በኋላ ላገሬ የምረዳበት ገንዘብ በማጣቴ እጅግ አዝናለሁ ነገር ግን ከልብ ካለቀሱ እንባ አይጠፋም የሚሉት እውነት ነውና ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ

መኰንን መንግሥታቸው ይስፋ በወር በወሩ ሶስት ብር ያወጡልኝ ቀለብ አለችኝና ለዕለት ምግብ ላመት ልብስ ካገኘሁ ይበቃኛል ለሰው ሁሉም የታዘዘለት ይህ ነውና ሳገኝ እስከ ጨምር ድረስ ክቡር ፊታውራሪ ዴሬሣ ላወጡት አሣብ በገራችን በኢትዮጵያ የተማሪ ቤት ስለ ማቆም ለመርዳት ያለውን ቢወረውር ፈሪ አይባልምና በብዙ ድፍረት ባመት ባመት ሶስት ብር ከጉልበቴ ጭምር እረዳለሁ ይህን ትልቅ ቀጥርና ጥቅም ላሰበልን ሰው በምድር አሣቡ ይጽና በሰማይም ልዕልና የምትባል መንግሥት ያውርስልን አሜን ።

ክቡራን አንባቢዎች ሆይ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ካለመሰልቸት እንድትመለከቱት እለምናችኋለሁ

ግንቦት ፳ቀን ፲፱፻፲፯ ዓመት በብርሃንና ሰላም ይነሡ ጁነቀ የሚባለው ስለእህልና ከብት መሄድ ነገር መጀመሪያ ኢትዮጵያን መመዘን ያስፈልጋል ስላለው እጅግ መልካም ነው ልሣን ሚዛን አስፈልጎ እየቀደመ ወደፊት እየተመዘነ ሥልጣኔ እየገባ ጥቅሙ ሲታወቅ ጠፉ መሬት ለም ይሆናል እያደር የባልንጀራውን ጥቅም ባልንጀራው ሲያውቀው በመቀዳደም አሁን ሥራ ፈት የሆነው ሁሉም ሠራተኛ ይሆናል ፤

በማናቸውም አገር ቢሆን ጥቂት በጥቂት እያለ እየተሻሻለ እየሠለጠነ ሄደ እንጂ እንዴሁ ኤውሮፓም አሁን እንደሚታየውና እንደሚወራው ሆኖ አለመገኘቱን ኤሮፓውያን በቃላቸውም በታሪካቸውም ይናገሩታል ። ነገር ግን በትጋት ሥራና መንግሥታቸውን በመውደድ ስንፍናንና ምቀኝነትን ትዕቢትን በመናቅ እዚህ አሁን አሉበት ደረጃ ደረሱ ።

እኛም አስቀድመን በሥልጣኔ ከዓለም በፊት የነበርነውን እያደር ባባያ በሬ ጠምደው መሠረት ሆነው በጠንካራው እንደማይነቃነቅ ተመሥርተው ያሉትን አራት ነገሮች ምቀኝነት ሥንፍና ትዕቢት አለመስማማትን እነዚህን እንደ አውጫጭኝ አውጥተን ብንጥላቸው በፍጹም ኢትዮጵያ መራዋን ተወጣች ማለት ነበር ። አሁን ግን አለ ሥራ ተቀምጠን በስንፍና አንዱ ባላገር ዓመት ሙሉ ከጭቃ ሹምና ከምስለኔ እየተከላከለ አንዲት ማሳ ቢያርስ ሁለት ዳውላ ቢወጣት እኔ አለሥራ ተቀምጬ እሱ ዓመት የደከመበትን ሁለት ዳውላ እህል ባንድ ብር ልሸምትህ ማለቴ [illegible] የነበረውን ድካም ቀጥሎም በዘር ፤ ኋላም ባረም ፤ በጨዳ ፤ በመሰብሰብ ፤ በውቂያ ፤ በማዝራት ፤ በማግባት ዓመት ሙሉ ያለእረፍት ሌት በውርጭ ቀን በፀሐይ የደከመበትን ዓመት ሙሉ ያላንድ ሥራ የተቀመጠ ሰው ሁለቱን ዳውላ እህል ባንድ ብር ሲሸምተው ጊዜ ፈጽሞ የዘላለም ተስፋውን ለመቍረጥ ይደርሳል ያም ሰው ባለመሬት አይደለም ከብት አለው ሣር ይገዛል ልጅ ንብረት አለው ልብስ ቀለብ ያስፈልገዋል ያች ብር እስንት ቦታ ትደርስለታለች የጣጣውን ብዛት የብሯን አንድነት ባስተዋሉ ጊዜ ኑሮው መሮት እመሰደድ ይደርሳል ።

ሁሉ አረሶ ግን ይሸምት እንደሚሉት ሁሉ ገበሬን ብን ጉዳው ሁላችን ሸማች ግን ይረስ ። ይልቅስ አስቀድመን እሱ ሳይነቃብን እኛ ሸማቾች ተማክረን ስለገበሬ ጉዳት ያመቱን ልፋት ብንመለከትለት አጥብቆ የሚያስፈልግ ነው ።

ይህንንም የብላሽ የሰው ድካም እንውሰድ የምንለው በዚህ በከተማ ያለነው ነን እንጂ ባላገሩማ እንባውን እያፈሰሰ በመራቆቱ እያዘነ ተቀምጧል አገልጋዮች ባዋጅ ነጻ ይውጡ ሲባል የገበሬ ነጻ አለመውጣት ምክንያቱ ምን ይሆን ገበሬ አልማዝ እንቍ ነው እንቍና አልማዝ በነገሥታት በመኳንንት ፊት እንዲከበሩ ገበሬም እንዲሁ በነገሥታት በመኳንንት በሕዝብ ፊት ሊከበር የተገባው ነው ገበሬ በመልካም ስፍራ የተተከለ ፋኖስ ነው ፋኖስም ለሕዝብ ሁሉ እንደሚያበራ እንዲሁ ገበሬም የሕዝብ የሕይወት ብርሃን ነው ፋኖሱን በመልካም ስፍራ አኑሮ የሚያስፈልገውን እስፒርቶ ወይም ላምባ በመጠኑ ቢሰጡትና ቢጠብቁት ለዘወትር ያበራል እንዲሁ ገበሬንም ሳናበሳጭ እሱ እንደጠየቀን ዋጋውን ብንከፍለው ለፈቀደውም ቢሸጥ ባንከለክለው ካመቱ ዛሬ ትንሽ ትርፍ ቢያገኝ ከባልንጀራው እየተወያየ አራሹ ሲበዛ ካሁን ይልቅ ሶስት አራት ጊዜ የረከሰ ይሆን ነበር ዛሬ እንደሚባለው ወደ ፈረንጅ አገር እህል እየሄደ ተወደደ ይባላል ይህ የሰነፍ ወሬ ነው ይልቅስ መቶ ጋሻ አምስት መቶ ጋሻ ሺህ ጋሻ መሬት አለኝ ብሎ አፈታሪክ ከማውራትና በዚህ በምስኪኑ ገበሬ እጅ የታረሰውን እስር ሆኖ አንድ እንጀራ እየተባጨቁ ያለሥራ ተቀምጦ ወዲያና ወዲህ እያሉ መንግሥትና ገበሬን ከማማት አሞትን ቆርጦ ቢያርሱት ሚሊዮኔር ለመባል ያደርሳል ።

የሐገራችን ሕዝብ እንጀራውን ገበሬን ያላመሰገነ ውለታም ለሱ ያልመለሰ ዘበት ነው የተፈጥሮ ማማት ልምድ ነው ። አሁንስ ቢሆን ከዚህ የበለጠ እንዴት እህል ይርከስ በእግዚአብሔር ይስጥልኝ ለመውሰድ ይመስለኛል ። አገራችን ኢትዮጵያ አጥብቃ ለም ናት ብዙህም መስኖ አላት ፍሬዋንም ባመት ሁለት ሶስት ጊዜ ትሰጠናለች እኛ ስለምን ይህን ያህል ቀን ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ እስከ አሁን ዘመን ድረስ የሥልጣኔ አበባዋን ከዙኛ ጐረቤቷ አሻግራ እያየች ስትናፍቅ በመኖሯ እያዘነች ከጐረቤቷ ስትወያይ ። ስለምን ይሆን የኔ እንዲህ መሆን ወላድ አይሉኝ መሐን ። እንደ ባልንጀሮቼ መውለድ አሳምራለሁ የኔ ልጆች ባህሪ ትጋት አንድነት በማጣታቸው መልኬንና ስሜን ለምን ያጠፉታል እያለች ስትጸጸት ብትሰማት እውነት ነው ልጆችሽ አርበኞች ናቸው ዳሩ ግን [illegible] ምንናምን ናቸው ስትል ጠየቀቻት ፤ ምቀኝነት ስንፍና ትዕቢት አለመስማማት እነዚህ ናቸው ስትላት ። ወየው እኔ እነዚህማ ባለ ብዙህ ወገኖች አይደሉምን እንደምን ተችሎኝ እንዴትስ ያለ ልጅ ብወልድ ይህን የሚያጠፉና መልኬን ከነስሜ የሚያድሱኝ ዘመንና ልጅ አገኛለሁ እያለች ስትጨነቅ አይዞሽ አሁንማ ጊዜሽ ቀርቧል አስቀድሞ ቢሆን በዙሮሽ ያለነው አጭተንሽ ነበር አሁን ግን ከዳዊት ከሰሎሞን በሺ ፰፻፴፮ ዓመተ ምህረት ተወልዶ ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ተብሎ በተማሪ ቤት ሕግ ይመሰርትሻል ። ቀጥሎም ንግሥተ ነገሥታት ዘውዴቱ ወለቱ ለዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ፤ ልዑል ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ባንድ ቃል ተናጋሪ ሆነው እንደ ገና በተማሪ ቤት ያድሱሻል

ጌታ በአምልኮቱ ንጉሥ በመንግሥቱ ጉልማሳ በሚስቱ ቢገቡበት ቀናኢ እንደ ሆነ የተወሰነልንን በታ አልፈን አል ተወሰነ በታ መገኘት ትልቅ ኃጢአት ነው ይከለክለናል በኛም ዘሯ አሻግረሽ ያየሽው የተመኘሽው እንዴ ሳይቀር በነሱ ጊዜ አበባሽን ታያለሽ ስላለቻት አጥብቃ ጊዜውን ስትጠብቅ ልጆቿም ትንቢቱን ነግሯ ስለተፈጸመላት ኢትዮጵያ ምስጋናዋን ወደ እግዚአብሔር ታቀርባለች የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ስለ ሐገራቸው ፍቅር የዋሉትን ውለታ አስበው በገንዘባቸው የነዚህን ፆራቱን የባህርይ ረቂቅ ምስጢር ምቀኝነት ስንፍና ትዕቢት አለመስማማት የሚሏቸውን ፈንቅለን ባንድነት እንድንጥላቸው ያሰሩልንን የትምርትን ድጅኖ አጥብቀን ይዘን እንዳይዛበ አድርገን መፈንቀሉን ብንማረው መልካም ነው ።

ይነሱ ደነቀም ስለሐገሩ አስበ ኢትዮጵያን በሚዛን ማግባት ያስፈልጋል ስላለው እውነቱ ነው ያሰኘዋል ኢትዮጵያ የሥልጣኔ አፍራሽ እንቅፋቷ ብዙ ስለሆነ ሚዛኑ እጅግ ይከብዳታል ። ልጆችዋ ጨለኞች ማንስ ይቀልላታል አፈ ታሪክ አይውሉ ተዋውዬ ፥ ከባሯ ጡት ተጣብቼ ፤ አየው ብሄድ ታስሮ እስፈታው ብሄድ ተሸጦ እንደሚሉት ባለአዕምሮው ንጉሦቻችን ስለሕዝባቸው ጥቅም ነፃነት እውቀትን ሥልጣኔን በሀገራቸው እንዲገባ ሲደክሙልን ለመልካም ውለታ ክፋ መመለስ እንቅፋት እየሆንን እብዙህ ብስጭት በማድረሳችን የሞት ሞት ይፈረድብናል ። መዝሙር ፺፱ ተቀነዩ ለእግዚአብሔር በትፍሥሕት ። ተፈሥሐ ጻድቃን በእግዚአብሔር ልባችንን ንጹሕ አድርገን መንግሥታችንንና ሐገራችንን ብንወድ እንደ ዋጋችን እንቀበላለን እግዚአብሔር በኪኑ ጥበቡ አንግሦ አስጀምሮ የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ሐገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን አስበው የልብ ዋግምት የሆን ብርሃንና ሰላምን ስላሳዩን ሐገርዎ ኢትዮጵያ ዋጋዎን ትክፈልዎ ስንል ባንድነት የኢትዮጵያ ሕዝብ ምስጋናችንን እናቀርባለን

በመስኛ ሠራተኛ ይገኛል ፥ የምንቆጥባቸው ሶስት ነገር አሉ ጊዜ ፥ ገንዘብ ፤ ድካም ፥ የትኛው አባት ማናቸው ልጅ ያንድነትን ጉልበት የሚፈልግ፡ግን መለየት የቤተ ሰብ ችግር ነው ፥ ለመልካም ጌታ መልካም አገልጋይ ፤ የሰነፍ መሬት [illegible] አይገኝም ማናቸውንም ነገር በጊዜ አድርግ ። ለመልካም ተማሪ መልካሙን በታ ስጥ ። ምንም ቢሆን የድኩላ ቆዳ ሳይሞት አይሸጥም ። መርከበኛ የሚታወቀው ማዕበል በተነሣ ጊዜ ነው። በሽተኞች በከብት መጥተው በእግራቸው ይሄዳሉ ። ለትልቅ በሽታ ትልቅ መድኃኒት ። ለሐገሩ በመልካም የሚያገለግል አጉት አክስት አያስፈልገውም ። እርስ በርሳችሁ ተፋቀሩ ይህ ነውና በዓለሙ ሁሉ የሚያስፈልገው ።

ብርሃን ሥላሴ አባ የሬ ።

በኢትዮጵያውያን ማህበር ለሚቆመው ተማሪ ቤት በየዓመቱ የሚሰጡትን ገንዘብ ልክ በፊርማቸው ያስታወቁትን ሰዎች በዝርዝር አትመን እናወጣለን ብለን ነበር ። እስካሁን ድረስ እየፈረሙ የላኩልን ሰዎች ቀጥሎ የተጻፉት ናቸው ።

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋወራሽ

ልዑል ተፈሪ መኰንን ።	፭፻	ብር
ልዕልት ወይዘሮ መነን ።	፫፻	ብር
ፊታውራሪ ደሬሳ ።	፪፻	ብር
አቶ አስፋው አንዳርጌ ።	፭	ብር
አቶ ሰሎሞን የኔነህ ።	፭	ብር
አቶ በላቸው ወልደ ሩፋኤል ።	፭	ብር
ነጋድራስ ደስታ ። መጀመሪያ ፩ ባመት ባመት	፳	ብር
ገብረ መድኅን ጐሳ ።	፭	ብር
ልጅ አበበ ወልዴ ።	፭	ብር
ፊታውራሪ ኪዳነ ማርያም ።	፳	ብር
አቶ ገብረ ኢየሱስ ተስፋዬ ።	፲	ብር
አቶ ኪዳነ ማርያም አበራ ።	፲	ብር
አቶ ማህሌ ወልደ ሰማዕት ።	፲	ብር
ቄስ ባድማ ያለው ።	፫	ብር
አቶ መርስዔ ኀዘን ።	፫	ብር
አንዳርጌ ዳምጤ ።	፫	ብር
አለቃ ዳኜ ።	፮	ብር
ሥዩም ኃይለ ማርያም ።	፬	ብር
አቶ ወርቁ ይታጠቁ ።	፲	ብር
አቶ ተክለ ጊዮርጊስ ።	፫	ብር
ግራዝማች እያና ።	፲	ብር
ሙሴ አብርሃም ።	፶	ብር
ግራዝማች ገብረ ዮሐንስ ።	፲	ብር
በጅሮንድ ሰብስቤ ።	፲	ብር
አቶ ተፈራ ለወጠኝ ።	፬	ብር
አቶ ታደሰ መሸሻ ።	፲	ብር
ከንቲባ ነሲቡ ዛማኤል ። መጀመሪያ ፪፻ ባመት ባመት	፪	ብር
አቶ ተፈራ በልሁ	፲	ብር
አቶ ፈቃዱ ።	፫፻	ብር
ሊቀ መኳስ መንገሻ ውቤ ።	፳	ብር
አቶ ዮሐንስ ማርቆስ ።	፭	ብር
ተክለ ሃይማኖት ብሩ ።	፫	ብር
አቶ ይብሳ ።	፭	ብር
እየለ ገዳ ።	፬	ብር
[illegible]	[illegible]	ብር
አቶ ወልደ ጊዮርጊስ ደለለኝ ።	፭	ብር
መምህር ወልደ ማርያም ።	፲	ብር
አቶ ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት ።	፴	ብር
ድምር	፬ ሺ ፲	ብር

አቶ ፈቃዱ እንዳሉትም ልጆቻችሁንና ያገራችሁን ልጆች ለማስተማር የምታወጡትን ገንዘብ ማበደር እንጂ ማውጣት አይባልም ። አገሩንና ሕዝቡን መውደድ በአፍ ብቻ መናገር አይበቃም የተባለውን ቃል ሁለ ጊዜ እያሰብን ያገራችንና የሕዝባችንን መውደድ በማድረግ ልንገልጸው የሚገባን ነው ።

የሚሰጡትንም እርዳታ ጽፈው ያስታወቁንን ሰዎች እጅግ እናመሰግናቸዋለን ፤ ከዚህ በፊት ያላስታወቁን ደግሞ ጽፈው እንዲያስታውቁንና እንደዚሁ በሚከተለው ቊጥር አትመን እንድናስታውቃችሁ ተስፋ እናደርጋለን ።

በልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

መጀመሪ ዓመት ፡ ቁጥር ፳፬ ።
1re ANNÉE № 24

ሐሙስ ሰኔ ፬ ቀን ፲፱፻፲፯ ዓ ም ።
JEUDI 11 JUIN 1925

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

የጋዜጣው ጸሐፊ ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ጸሐፊው ያስታውቁ ።

የራሱን ጉዳይ የሚያሳትም ሰው ዋጋውን እየከፈለ እናትምለታለን ።

ስለ በዓለ ጰራቅሊጦስ

በዓለ ጰራቅሊጦስ ወይም በዓለ መንፈስ ቅዱስ በግንቦት ሠላሳ ቀን ዋለ ፡፡ በክርስቶስ ማኅበር ላይ እርሱ ተስፋ እንደ ሰጠ ወደ ሰማይ ከወጣ በኋላ ባርባ ቀን መንፈስ ቅዱስ የእሳት ልሳን መስሎ በመውረዱ ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችበት ትልቅ መታሰቢያ ያለው ቀን ነው ። በክርስቲያኖችም ሁሉ አንድ ዋና በዓል ነው ፡ የእግዚአብሔር መንፈስ በሐዋርያት ዘመን በግልጥ እንደ ወረደ ምእመናንንም እንዳበረታቸው ፤ ድፍረትንና እውነተኛውን ኃይል እንደሰጣቸው የክርስቲያን (የክርስቶሳውያን) ትምርትም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እየተዘረጋ እንደሔደ በግብረ ሐዋርያት ከ፪ምዕራፍ ጀምረህ ተመልከት ።

እኛም መንፈሳዊ ዓይናችን እንዲበራ ፤ እውነተኛ ድፍረትንና ኃይልን መስማማትንና ፍቅርን እንድናገኝ ፤ የምናደርገውም ሁሉ ለበረከት እንዲሆን መንፈስ ቅዱስን መቀበል ያስፈልገናል ፤ እግዚአብሔር ለሚለምኑትና ለሚታዘዙለት መንፈሱን ይሰጣቸዋል ብሎ ቅዱስ መጽሐፍ ነግሮናል ። ስለዚህ መንፈስ ቅዱስን እንድናገኝ አምላክን መለመንና እንደ ቅዱስ ቃሉ መታዘዝ ያስፈልገናል ። ይህች ሕይወታችን ቶሎ ታልፋለች ባላሰብነው ቀን ወደዘላለማዊ ኑሮአችን በሞት እንሻገራለን። መንፈስ ቅዱስን ብንቀበል በእግዚአብሔር መንፈስም ተመርተን ሥራችንን ሁሉ ብንሠራ ሞት አያሰጋንም ። ሰማያዊ ቤት እንዳለን እርሱም ከምድራዊ ቤታችን እንደሚበልጥና እንደምናገኘውም የእግዚአብሔር መንፈስ ያስረዳንና በሞታችን ጊዜ በደስታ እናርፋለን ። የእግዚአብሔርን መንፈስ የምትፈልግ ሆይ እርሱን በጸሎት ደጅ ጥናው ታዘዘውም። እመን ብቻ ይሰጥሃልም ።

እውነተኛ ፍቅር ።

የተወደዳችሁ የኢትዮጵያ ልጆች በኢትዮጵያ በእናታችሁ እቅፍ ሙቋችሁ የምትኖሩ ። ከእናታችሁ እቅፍ ነጥቆ የሰሜን ብርድ ያልነካችሁና የሰሜንም ውርጭ ከገላችሁ እስከ አጥንታችሁ ጠልቆ ገብቶ ደዌ ያላሳደረባችሁም ። ፍቅር በሶስት መከፈሉን እንመልከት በዚህ ጊዜ አገሬ የከበረች እናቴ ኢትዮጵያን አፈቅራለሁ እንጂ እጠላታለሁ ማለት አይገኝም እንግዲያ ፍቅርህ እውነተኛ ነውን ። የመንግሥትንና ያገርን ፍቅር የሚመስሏት ወይም የምትመስላቸው ሶስት ናቸው ።

፩ኛ ፤ በእግዚአብሔርና በሰው መኻከል ።
፪ኛ ፤ በባት በእናትም በልጆች መኻከል ።
፫ኛ ፡ በባልና በሚስት መካከል ።

በነዚህ ውስጥ ፍቅር ሊገባ ሊኖር ሊጠና ሊታገሥ ሊጠበቅ ሊያሸንፍ እንደሚገባ ። ያንተና የመንግሥትኽም ፍቅር እንዲሁ ሊሆን ይገባዋል ።

በኃጢአት ተከሶ ሞት በተፈረደበት ጊዜ ዝም ብሎ ቢተወው ለክፉ ጠላት ለዲያብሎስም አሳልፎ ቢሰጠው ስለ እርሱም ባይሞት ኃጢአቱን ተሸክሞም በመስቀል ባይሰቀል በማቴዎስ ወንጌል በ፳፰ ምዕራፍ በ፲፰ ቁጥር ሥልጣን ሁሉ ተሰጠኝ በሰማይና በምድር ባላንለም ነበር ። ስለምን እንዲሁ ባያደርግ ሰው ሁሉ የሰይጣን ባርያ ሁኖ በቀረ ነበር እንጂ አንድ ስንኳ በእግዚአብሔር መንግሥት ባልተገኘም ፤ የበደሉትንና ያልበደሉትን ሞት ገዛቸው እንዲለን መጽሐፍ ። ዳዊትም እግዚአብሔር ከሰማይ ዘቅዝቆ ወደ ምድር ተመለከተ የዚያን ጊዜ ሰው ባንድ ሁኖ አንድ ሳይቀር ኃጢአት ሲሠራ አምላኩን ሲያሳዝን ተገኘ ይለናል ። እንግዲያስ ከሰማያዊ መንግሥቱ ምን አወረደው እንበል ። ወርዶስ በድህነት በመከራ ኑሮ በዓለም መኖሩ ምን ይሆን ። በመጨረሻስ በሰው እጅ ተይዞ በመስቀል

የሚሰቀል ርጉም ነው እንደሚል መጽሐፍ በዚህ መስቀል ምን አሰቀለው ፤ ለዚህ ሁሉ ያደረሰውስ ምን ይሆን ፤ መጽሐፍ ቅዱስና ሊቃውንቶቻችን እንዳሉ ። ፍቅር ሰሐቦ ለወልድ ኃያል ወይም በወንጌል እንደሚል እግዚአብሔር ዓለምን ወዷልና ፩ዱ ልጁን ቤዛ እስኪሰጥ ድረስ በርሱ ያመነ እንዲድን እንጂ እንዳይጠፋ ። ስለዚህ ፍቅር የሚያመለክተንን ሁሉ አሁን ልንቈጥረው አንችልም ። ይህ እስኪያደርግልን ድረስ የሚያፈቅረን በምን ምክንያት ይሆን እስቲ በራስህ መዝነው አንተ ራስህ አላንድ ምክንያት ስንኳን ይህንን የሚያህል ጥቂትም ልትወድ አትችልም እንግዲያስ የወደደን ቸሮች በጎች ስለ ሆን ነውን ፤ አይደለም ሐዋርያ እንደሚነግረን እግዚአብሔር ገና ጠላቶቹ ስንሆን በልጁ ሞት ታረቀን ብሎ ሐዋርያ ጳውሎስም ይህነን ፍቅር ባየ ጊዜ ማለት ገና ኃጢአተኛ ሳለ ስለ ወደደው ስለ እርሱም ስለ ሞተለት አይደለምን ከክርስቶስ ፍቅር የሚለየኝ ማነው የሚል ስደት ነውን ራብ ነውን ወይስ ሰይፍ ምንም ሞትም እንኳ ቢሆን ከክርስቶስ ፍቅር የሚለየኝ የለም ይላል ይህ በእግዚአብሔርና በእውነተኛ ሰው ያለ ፍቅር ባንተ ላይ መኖሩን እንግዲያስ ሰውነትህን መርምር ።

በእግዚአብሔርና በመንግሥትህ ይኸን የሚያህል ወይም ይኸን የሚመስል ፍቅር እንዳለህ እይና አስተውል ። ወይም እንዴት ሁና ሳለች ነህ ኢትዮጵያን የምትወዳት በራሷ ስታድር ትክክል እንደሚገባት ስትሄድ ከንተም አንዳች ነገር ሳትፈልግ ነህን የምታጨበጭብላት ይህነንንስ እንድታደርግ እውቃለሁ ደግሞ እውነትህ ነው ። ግን በተሞኘች በተቸገረች ለሚረዳት የማትጠቅም ሰነፍ ተስፋ የሌላት ላንተም ምክርህንና ስራህን የማትቀበል ስትሆንሳ እንዴት ነህ ፤ አያሌ ሰዎች ሲሉ እንደሰማሁ የሚረዳት አይጠቀምባትምና ለዚች አገር መልፋት ከንቱ ነው ። አንተም እንደዚሁ ታስብ ይሆን ። እንግዲያስ ሐሳብህ እንደዚህ ከሆነስ ፍቅርህ ለርሷ እንዳልሆነ ነገርህ ይመሰክርብሃል ። ብታከብርህ ብትሸልምህ ብትሾምህ ግን ልትከተላት መልክም ነው ። ስለዚህስ ወይም ይህነን እንዲያገኙስ ከምድር ዳርቻ መጥተው እንኳ ባገለገሏት በዚህም ፍቅርህ ለራስህ መሆኑን አሣብህ መሰከረብህ ። እንግዲያስ እንደዚህ ከሆነ ፍቅርህ ኢትዮጵያን እወዳለሁ አትበል ። ውሸት ኃጢአትም ነው ። ራሴን እወዳለሁ ብትል ግን እውነት አልክ ። እንግዲያስ ከዚህ ከልነው የመሰልነው እውነተኛ ፍቅር የመጣ ። አይደለም ። ባለቤቱ እንደሚል በጌቴ ሴማኒ ሲጸልይ ላለ ። የሚቻል እንደሆነ ይህች ጽዋ ከኔ ትለፍ ። ተመልሶ እኔ ግን ስለዚሁ መጣሁ ይላል ስለምን ሙቶ ዓለምን ሊያድን ። ይኸ ነው እውነተኛ ፍቅር ። አንተም ስለ ሕዝብህ ስለ አገርህ በሞትህ እንኳ መርዳት የሚሆንልህ ከሆነ እውነተኛ ፍቅር ካልህ ግፉ ግን ምናልባት እርሱ አምላክ ሁኖ ነው የሞተ እንጂ በሰው እንዴት ይቻላል ትል እንደሆነ ግን ስለ ሀገራቸው ፍቅር የሚሞቱ ቁጥርም የላቸውም ። እንግዲያስ በጭሩ እውነተኛ ፍቅር እስከ ችግር እስከ መከራ እስከ ሞትም እንጂ አምሮህ ስትገዛ ስታጌጥ እስከለህ ብቻ አይምሰልህ ።

ተወልደ ብርሃን መድኅን ።

(ከዚህ የቀረው በሚከተለው ቍጥር ይታተማል ።)

የብርሃንና ሰላም ምክር እንደሚሰማ ምስክር ።

የብርሃንና ሰላም ጋዜጣ የጠለቀው ምክሩ ሁሉ ወደሰው ልብ እየገባ የሚሄድ መሆኑን የሚያስረዳ ምስክር ከዚህ ቀጥሎ እንደተጻፈው እንገልጻለን ።

ይኸውም የብርሃንና ሰላም ጋዜጣ መታተም ከጀመረ ወዲህ ከየሌላው ምክሩ ጋራ ደግሞ ሕዝቡም ካረቄ እንዲከለከል ልዩ ልዩ የሆነውን እውነተኛውን ምክር ከነማስረጃው ተግቶ መከረ ። እነሆ ለክቡር ቢትወደድ ኃይለጊዮርጊስ ተዝካር ላስራሁለታቸው የቅዱስ ጊዮርጊስና የቅዱስ ሩፋኤል ካህናት ላርባቸው ያስር አድባራት ካህናት እቤታቸው ተጠርተው ሲበሉ ከጠጅና ከጠላ በቀር አረቄ አልተጠጣም ። በዚሁም ተዝካር ላይ አረቄ እንዳይጠጣ ለሙተው ልጆቻቸውና አሽከሮቻቸው ቁርጥ አድርገው ተማከሩ ። ለዚሁም ላርባቸው ወዳጆቻቸው ሁሉ ከተሰበሰቡ በኋላ አረቄ ለምን ሳትገዙ ቀራችሁ ብለው ጠየቁአቸው እነሱም አረቄ በማናቸውም ወገን ከጉዳት በቀር ጥቅም እንደሌለበት አስበን ተውነው አሏቸው እነሱም አረቄ የተለመደ ስለሆነ የተጠሩት ካህናት ቅር ይላቸው እንደሆነ ብለን ነው እንጂ እውነትም አረቄ ከጉዳት በቀር ጥቅም እንደሌለበት ተረድተነዋል አሏቸው በዚሁ ቀረ ። ልዩ ልዩ ከሆነው ከብዙው ጉዳቱ ሌላ ደግሞ ለዚያን ቀን ላረቄ መግዣ ይሆን የነበረው ፫፻ ብር ያህል ከጥፋት ዳነ ።

ካህናቱም በብዙ ድካም የተደገሰላቸውን ተመግበው አረቄ ቢጨምሩበት ኖሮ የበሉትም ሳይስማማቸው ብዙ አንባሮና ጉዳትም የነበረ አረቄ ቢቀር የተመገቡት ተስማምቶላቸው ጠብና ጉዳትም ሳያገኛቸው በደህና ወደየቤታቸው ሄዱ ።

የደግሱ አሰናጂዎችም ምናልባት ስላረቄው መቅረት ቅር ብሏቸው ይሆን ብለው የካህናቱን አጋፋሪዎች ቢጠይቋቸው አረቄ በመቅረቱ ደስ ብሎናል እንጂ ቅርም አላለን በየድግሱም ቤት አረቄ መጠጣታችን ባለቤቱ ገንዘቡን ከስሮ ገዝቶ ሲያቀርብልን እንጠጣም ያልነው እንደሆነ ያዝንብናል እያልን ነው እንጂ ከጉዳት በቀር ትርፍ እንደሌለው አጥተነው አይደለም አሉ ።

እንግዴህ አረቄን ከጥፋት በቀር ጥቅም እንደሌለው ሰው ሁሉ ካወቀው በይሉኝታ እያለ እንዳይጠጣውም ደጋሹ ማቅረቡን ከተወው ሕዝቡ ከጥፋት ደህንነትን ለማግኘት የሚጣጣር መሆኑን ያስረዳል በዚሁም ላይ የተማረ ቤቱ እየጠነከረ ሲሄድ ትልቅ ጥቅም ይሆናል ።

ብርሃን ከጨለማ ሰላምም ከጠብ እንደሚሻሉ አስበው እንደዚሁ የብርሃንና ሰላምን ምክር ለሚከተሉ ሁሉ ትልቅ ምስጋና ይገባቸዋል ።

ደግሞ ማናቸውም ሰው ቢሆን ወዳጁን መምከሩ ለተመካሪው ጥቅም ብሎ ነው እንጂ ለራሱ ጥቅም ብሎ አይደለም ነገርግን ወዳጁ በምክሩ ሲመለስ መካሪው ደግሞ ደስ ይለዋል እንደተባለ ሰውን የሚገስጽ ኋላ ጸጋ ያገኛል ፤ ምሳሌ ምዕራፍ ፳፰ ቍጥር ፳፫ ።

ተመካሪው ግን እውነተኛውን ምክር ባይቀበል ጉዳቱ ለራሱ ይሆናል እንጂ ለመካሪው አይደለም በዘለፋ ላይ አንገቱን ያደነደነ ሰው ጥፋት ድንገት ይመጣበታል ፤ ምሳሌ ምዕራፍ ፳፱ ቍጥር ፩ ።

የብርሃንና ሰላም ወዳጅ።

ስለ ፊታውራሪ ዴሬሳ አሳብ ይነሱ ደነቀ የሚባል ሰው ከሀገራችን ስለሚሄደው ሠንጋና እህል የሚለውን ቃል ስለ እየሁ መልከም ነው እጅግ ድንቅ ነው ነገር ግን ለዚህ ነገር መጀመሪያ አገርን ሚዛን ማግባት ያስፈልጋል ሚዛን ማለት እንዲህ ነው ኢትዮጵያ ሰው ታለበት ይልቅ አውሬ የሚረበበት ይበዛል ማለቱ ለሥራ አእምሮውን ከሚአነቃቃ ይልቅ ሰነፉ ይበዛል ፤ ከብት ታለበት ይልቅ ከብት የሌለበት ይበልጣል ማለቱ ሠራተኞች ታሉበት አገር ሰነፎች ያሉበት አገር ይበልጣል ማለቱ ይሆናል እንጂ እውነት የሀገራችን መንግሥት የሕዝቡን ጥቅም ሳይመዝን እንዲያው አላሰበውም ይኸውም ሊታወቅ ይህ ሰው በብልሁ በነጋድራስ ገብረ ሕይወት መጽሐፍ የተባለውን ቃል ሳያነብ ለመንቀፍ ብቻ የቸኰለና የገባያን ነገር መርምሮ የማያውቅ ይመስላል።ይኸ ሁሉ ሰው እገበያ መሰብሰቡ ለከንቱ አይደለም ሊመለዋወጥ ነው እንጂ ባለሸማው ለባለበርኖስ ፤ ባለበርኖሱም ለባለሸማ ፤ ባለቅቤውም ለባለበርበሬ፤ ባለበርበሬው ለባለቅቤ እንዲሁም ብዙ መለዋወጥ በያይነቱ አለ ተለዋዋጩ ሰው ግን ለራሱ የሚበቃውን ያህል እቤቱ ሳያስቀር ጨርሶ አይላውጥም እንደዚሁም ሁሉ የኛም መንግሥት ለሕዝቡ የሚበቃውን ሳያስቀር ይኸንን እንዳያደርግ ለተጠራጣሪው ሰው እርግጥ ይሁነው ፤ ይልቅስ አንድ ሰው ብቻ እሚጠቀምበትን ነገር ትተን ብርሃን አልጋ ወራሻችን የውቀት ፋኖሳቸውን ከበሩልን ቀን ከአረቄ ተለይተን ሌሊት ከእንቅልፍ ነቅተን አገራችን የምትጠቀምበትን መሥራትና መረዳዳት ነው።የሮፓ ሰዎች የበረቱበትና የሠለጠኑበት ስለ ስንፍና ብለው መቀመጥና ምቀኝነትን አልተከተሉም ። እስከ ሞት ድረስ አገራቸውን ረዱ እንጂ ። ይኸውም ሊታወቅ አንድ የሮፓ ሰው ውል ሲዋዋል እስከ ዘጠና ዓመት ወይም የበለጠ ይዋዋላል ። እውነት አንዱ ሰው ይኸንን ያህል ዕድሜ በርግጥ አገኛለሁ ብሎ አይደለም ጥቅሙ አለ ድረስ ለራሱ ከሞተም በኋላ ለዘመዶቹና ለሃገሩ እንዲሆን ነው እንደዚህ ያለው ሥራ መሽቀዳደም ነበር ሰውየውስ ግን እንኳንስ ለሚሰራና ገና ለታሰበው ለፊታውራሪ ዴሬሳ አሳብ መሰናከያ አበጀበት እሱም ይህነን መጻፉ እኔ ተሞትሁ ሠርዶ አይብቀል የተባለው የእንስሳ ተረት አጥንቶ ነውና ይልቅስ ልዑል ጌታችን የዘረጉልንን የውቀት ገበታ አብረን እንድንፋተት ወደ እግዚአብሔር እንለምናለን ።

አበበ ወልዴ ።

ምቀኝነትን ስለመጥላት ፤

በ፲፰ተኛው ቁጥር በብርሃንና ሰላም ጋዜጣ ከቡር ሊቀ መኳስ መኰንን ዋልቴ አንድነትና ፍቅር ጠፍተው ምቀኝነትና ተንኰል ስለ ሰለጠኑብን ብለው ያሉት ለተመለከተው ሰው በትክክል እውነት ነው ለሐገር አሳቢ መባልና ምስጋና ይገባቸዋል ።

እጅግ የሚገርመው ላሁኑ ለግዜው የምቀኝነት ሃይል ነው እንደምን ቢሉ ጥቅሙንና ጉዳቱን አለ መለየቱ ቀጥሎ የተጻፈው ነው አሁን በቅርቡ የድሃውን ችግር አይቶ እግዜር ጥቅም የሚሆነውን የደከመበት ነገር ዋጋ እንዲያገኝ ምክንያት ቢያመጣ እህል በሬ ወደ ውጭ አገር ሄደብን አገር ተራበ እህል አለቀ ይላሉ ግን ይኸ ሁሉ የድሃ ችግር ልማድ ስለ ሆነን ይኸ ስራ የማይሰራ ከንቱ ልማድ እንዳይለየን ነው እንጂ ጥቅም ላለው ነገር አልሆነም ድካማችን እህል ቢሄድ ብር ይመጣል ሃገራችን ተመስገናለች ሃገራችንን ማነው የሚያመሰግናት ቢሉ በእህል ረገድ ብልጽግና የሌላቸው የውጭ አገር ሰዎች ናቸው እነዚህም ሰዎች እውቀት የላቸውም ስራም አይሰሩ እንደሚሉን ለሁላችንም ተሰምቶናል ስለዚህ በሌላው ቢቀር እንደዚህ ባለው በሐገራችን ብልጽግና ብንከራከራቸው ክፉ ይመስላችኋልን፤ ደግሞስ ደሃው አርሶ ብር ከሚያገኝ ነቀዝ ይብላበት ደባላል ገበሬ ብር ቢያገኝ ጠፉን መሬት ገዝቶ ወይም ተመርቶ ሳር ያለበትን ከብት ያረባበታል ደግሞ ከዚያው ከገዛው መሬት አንዱን ጫካ መንጥሮ እህል ይዘራል ፤ እንደዚህ ከሆነ ገንዘብ በማግኘት የተነሣ ፊት ከነበረው እህሉና ከብቱ የኋላው ከብቱ የበዛ ይሆናል የመሬቱንም ግብር ሳይጨነቅ ሳይታሰር በልኩ ይሰጣል በሬም ቢሸጥ ከዚህ በላይ እንዳልኩት ንዋይ ከለ ሳር ያለውን መሬት ከገዛ ከዚያ ያረባል መሬት ከበዛ ከብቱን በሽታ አያጠቃውም ካንዱ መሬት በሽታ ቢገባ ካንዱ መሬት ይዛወራል ይኸንን ብናደርግና ገንዘባሞች ከሆንን ከብቶቻችንን በሽታ እንዳይቃወማቸው እናውቃለን ። ስለዚህ በሽታ የሚፈጀውን ከብትና ነቀዝ የሚበላውን እህል በገንዘብ ብንለውጠው ክፉ አይደለም ። አቶ ገብረ እግዚአብሔር ባለፈው ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ እንዳስታወቁን እውነት መታረድ ብቻ አይደለም ከብቱን የሚጨርሰው በሽታም ጭምር ነው የሚፈጀው የታረደው ግን ስለተበላ ለሰው ትርፍ አለው በሽታ የሚፈጀው ግን የሚበልጠው ቆዳው እንኳን ዋጋ የለውም እህሉም እንደዚሁ ነቀዝ የሚያስቀረው ብዙ ነው ከቡራኖች ሆይ ይኸን ዋና የድሃ ጉዳት አስቡና ደሃው ብራም ሆኖ መሬት እየገዛ ጠፉን እያለማ ከብቱ እንዳያልቅበት እህሉ እንዳይነቅዝበት አስቡለት ። ላም እንዳይሸጥ ቢከለከል ክፉ አይደለም ስለምን ላም ከሌለ ዋና ጉዳታችን ነው ላም ከሌለ በሬ የለም በሬ ከሌለ እርሻ የለም ይልቁንም ደግሞ መሲና ሁነው የማይወልዱ አያሌ ናቸው ስለዚህ እንዲህ ያለ ጉዳት ካገኘንእኳን ብራም መባልና ያው ቀድሞ የምንጠራበት የእህልና የከብት ባለጸጎች [illegible] መባል ይወገድብናል ቢሆን የላም ነገር ማጉዳቱ ይታወቀን እንጂ ሌላው ከዚህ በላይ እንደ ተጻፈ የሕዝብ ክብረት ላገር ጉዳት አይሆንም ይልቁንም እነዚህ የብር እንጅ የእህል ብልጽግና ላልተከፈላቸው የውጭ አገር ሰዎች እነሱ በአንድ በገንዘባምነት ነው የሚጠሩት እኛ ግን በህል ብልጽግና በገንዘባምነት የተጠራን እንደሆነ ክብራችን ይተካከላል ይታወቃቸዋል እኛ እህል ብንሸጥ ብር ይመጣል ትርፋችን የእህልና የገንዘብ ባለጸጎች እንባላለን ክብራችንም በእንደዚህ ያለ በ፪ ነገር ይጠራል ።

ጉዳት የድሀ አላገባብ መታሰር መፈታት ነው እንኳን ንቅይ አግኝቶ ሳይኖረው ተበድሮ ካንዱ ሃብታም በሬ ግዝቶ አርሶ ግማሹን ለሆዱ ግማሹን ለመሬቱ ግብር እየሰጠ ልብስ መግዣ እያጣ እራቁቱን ይኖራል ይህ ግን በገንዘብ ችግር የተነሣ በሬው

ለባነሰ እርሻው ስለቀለለ ነው ልብስ ማጣቱ እሁንማ እህል ብር መሆኑ ከተወገደ በ፪ ጥማድ ያረሰ ያም በ፭ ጥማድ ያረሰ ጉዳታቸው ይገዳደር ይመስለኛል እህሉ ካልተሸጠ ለነቀዝ ቀለብ ከሆነ ያ በብዙ ካረሰው ይኸው ባንድ በሬ እርሱ ግማሹን ለሆዱ ግማሹን ለግብሩ አድርጎ በተረፈው የሚታሰረው ተሻለ አሁን ግን ለልብሱ መግገፍ የሚሆነው ነገር እግዚአብሔር ምክንያት ቢያመጣለት ራቁቱን ሆኖ ከመሔድ ልብስ ለብሶ መታየቱ የሚጎዳ ነገር መስሎ የምቀኝነት ኃይላችንን እንዴት እናብዛበት ደግሞስ የለፋህበትስ ከመሬት እንደወጣች ነቀዝ በልቷት ወደዚያው ወደመሬት ተመለሰ ልፋትህ ዋጋ ይጣ እንለዋለን ። እንግዲህ ጌታም ድኃም ያው ልማዳችን እንዳይለወጥ ሊሆን ነው ልማዱ ደግሞ የሚጠቅም አይደለም ለገጋርም ለተገጋርም ጥፋት ነው ። ማለት ፩ ድሃ በዳኝነት ወይም ለመሬቱ ግብር የሚሰጠው ብር ስላጣ ልጆቹ ሚስቱ ሲያለቅሱ መጥፎ ይታሰራል ጢት ማታ ሲጮህ ታስሮ ቀለቡ የልጆቹና የሚስቱ መቸገርና የሱ ልቅሶ ለገጋርው ባይሰማው ጢት ማታ ሲጮህ የሰሙ ሰዎች ምን ያለ ጨካኝ ነው ይሉታል ይልቁንም ወደ ፈጣሪው የደረሰ እንደሆነ መጨረሻ የሌለው ጥፋት ያገኘው ይመስለኛል አሁን ግን ድሀንም አስሮ ከመቀለብ ላንድ አሽከር ቢያበላው ትርፍ ነበረው ደሀም እንደዚህ ያለ ነገር ከሚያገኘውና ከገጋርው ቤት ታስሮ ጠጅና ጮማ ከመመገብ ከሚስቱ ከልጆቹ ጋራ ጎመኑን መብላት ይሻለዋል ። በዚህ ነገር ገጋርም በደህው ጩኸት ከመጸጸትና ርኅሩሆች የምንባልበት ደሀም ገንዘብ እያጣ እድሉ እስራት ሆኖ የሡንሡለት ፊት ከማራ ጨምሮ ከመሄድ የገጋርም የተገጋርም ትርፍ የሚገኝበት መልካም የጊዜ ጸጥታና መልካም ንግሥትና መልካም አረኛ አልጋ ወራሽን ብልጽግናን ያገኘንበት ዘመን ነው ይህ ሁሉ የነዚህ የሁለቱ ጠበቂዎቻችን ከእግዚአብሔር የተሰጣቸው እድል ቢሆንና ጸሎታቸው ለፈጣሪያቸው ቢደርስ ነውና የሀገራቸውና የሕዝባቸው ብልጽግና የተሰማን ። ይህ መልካም እድላቸው ለሁላችን ተገልጾልናልና የነሱን ዕድሜ በጣሙ ለአያሌ ዘመን እንዲያደርግልን ባንድነት ቸር መሐሪ ርኅሩህ አምላክን እንለምን

ሳሙኤል ዘውገ ።

ተረት ።

[illegible]
የተንጠለጠለ ቀጭን ገመድ ተጠምጥሞባት ተያዘች ላታመልጥ እየጮኸች ትንፈራገጥ ነበረች።ትንሽ ቆይቶ ጩኸቷን ሰምተው የሌት ወፎች ከየትም ከየትም ተጠራቅመው ብዙ ሁነው ተሰበሰቡና በተያዘችው ላይ ሲያንዣብቡ እንደ ደመና ሆኑ።

ከዚህ በኋላ ሁሉም ተስማምተው በቀጭኑ ገመድ ላይ አንድ ቦታ በየተራ ባፋቸው ይነጩ ጀመር ፤ ከጥቂት ጊዜ በኋላም ገመዱ ተበጠሰ ፤ የታሠረችውም ተለቀቀች ይባላል ።

ይህ ተረት ምን ያስተምረናል ? ።

ግንቦት ፳፪ ቀን ሐሙስ እለት ወዳጃችን አቶ ተስፋ ጊዮርጊስ መንግሥትን ስለማገልገላቸው ለሙያቸው የተገባ ኒሻን ከኢትዮጵያ መንግሥት ስለተሸለሙ እንኳን ደስ አለዎ እያልን የደስታቸው ተካፋዮች መሆናችንን እናስታውቃለን።

በኢትዮጵያውያን ማኅበር ለሚቆመው ተማሪ ቤት በዓመት የሚሰጡትን ገንዘብ ስለ መልካሙ ሐሳብ አስቀድሜ አመሰግን ዘንድ ፍቀዱልኝ ።

በመጀመሪያው ለኢትዮጵያ የሚያስፈልጋት ትምህርት እንደሆነ ሕዝቡ አውቆ ለዚሁ ስጦታ የሚመሰክረው ሕዝቡ በደስታ ገንዘቡን ሲሰጥ ነው ። የጀርመን ፍልሶፋዊ ፊኽት «Ficht» እንዲህ አለ ፤ የሕዝቡ ሁሉ እድል መደላደሉ ወይም መዋረዱ ለልጆች ትምህርት ከሚሰጡት የተነሣ ነው ። ነገር ግን እንዲህ ያለ ረቂቅ ንግግር ፍሎሶፎችና ዕውቀተኞች ቢናገሩ ፈጻሚ ሰው ካልተገኘ ምን ጥቅም አለው ።

ለኢትዮጵያ ግን የፍሎሶፎችን ቃል የሚፈጽምና ኢትዮጵያ እንዳትዋረድና ልጆቿን የሚያስተምሩ ብልሁ ረቂቁ ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ናቸው። እርሳቸውም የትምህርት ዘር ዘርተዋል ዘሮቹም በለመለመችዋ መሬት ላይ አርፈዋል። ለታላቁ አስተማሪ ለልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ታላቅ ክብርና ምስጋና ለዘለዓለም ይሁን እንደዚሁም የእውቀት ትምህርት ለማጽናት የሚጥሩት ተከለ ትምህርት ይሆናሉ ደግሞ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ቃላቸውን ስለ ሰማ ምስጋና ይገባዋል ። በብርሃንና ሰላም የሕዝቡ ስም በተርታው የታተመው በኢትዮጵያ ብዙ ደህና ተማሪ ቤት እንዲያቆሙ ተስፋ ናቸው ። ይልቁንም የአቶ ፊቃዱ መልካም ንግግር በደስታ የሚቀበሉት ቃል ነው ልጆቻችሁን ለማስተማር የምታወጡትን ገንዘብ ማበደር እንጂ ማውጣት አይባልም አሉ በውነትም ታላቅ ጥቅም ያለው ብድር ነው ። ላንድ ሰው ፩ሺ ብር ብታበድሩ ፻ ወይም ፪፻ ብር ወለዱን ታገኛላችሁ ደስታውም ይህ ነው ። ዳሩ ግን ለተማሪ ቤት ፩ሺ ብር ብታወጡ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ፻ ወይም ፪፻ ለሕዝቡና ለሀገሩ ጥቅም የሚሆኑ ጉልማሳ ልጆች ወለዱን ታገኛላችሁ ዋና ከዚህ የሚበልጥ ተድላ የለም አሁንም ፲ ብር ለዚሁ ተማሪ ቤት እርዳታ ልኬያለሁ ሐሳቤ ብዙ ነበረ ነገር ግን ለሚመጣው ዓመት እንድንጨምር እግዚአብሔር ያብቃን ይህ ስጦታ እንዲሰፋ ብዙ እምነትና ተስፋ እናደርጋለን ።

እንድርያስ ካዋድያ።

በኢትዮጵያውያን ማኅበር ለሚቆመው ተማሪ ቤት እርዳታ እንሰጣለን ብለው ፊርማቸውን የሰጡ ሰዎች ።

ከ፳፫ ቁጥር ጋዜጣ የመጣ ድምር	፪ሺ፲	ብር
አቶ ኃይሌ መኰንን ።	፫	ብር
ከቶ ሣህሉ ጽጌ ።	፭	ብር
አቶ አማረ ጉሹ ።	፮	ብር
ሙሴ ሚናስ ሄርቤግያን ።	፳፩	ብር
ግራዝማች ሽመልስ ።	፲	ብር
ፊታውራሪ ተፈሪ ቸርነት ።	፲፭	ብር
አቶ ይግዛው ጉሹ ።	፲	ብር
አቶ ብሩ እዝነህ ።	፲	ብር
አቶ ተክለ ማርያም ካሣሁን ።	፭	ብር
አቶ ይልማ ነከሬ ።	፲	ብር
ሙሴ እንድርያስ ካዋዲያ ።	፲	ብር
ድምር	፪ሺ፻፲፭	ብር

በልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

መጀመሪያ ዓመት ፡ ቁጥር ፳፭ ።
1re ANNÉE №. 25

ሐሙስ ሰኔ ፲፩ ቀን ፡ ፲፱፻፲፯ ዓ ም ።
JEUDI 18 JUIN 1925

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፮ መሐልቅ ይሸጣል ።

የጋዜጣው ዲረክተር ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲረክተሩ ያስታውቁ ።

የራሱን ጉዳይ የሚያሳትም ሰው ዋጋውን እየከፈለ እናትምለታለን ።

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ።

የኢትዮጵያ ብርሃን ፤ ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን። በዚህ ባለፈው ሰሞን እቤት ስለዋሉ በጣም አዝነን ተጨንቀን ነበር ፤ ግን እግዚአብሔር በቶሎ አዳነልን ። ኢትዮጵያም በመዳንዎ እጅግ ደስ ብሏታል ስለ መዳንዎ ደስ እያለን ለእንግዲሁ ዕንቅፋት የሌለበት ጤንነትና ረጅም ዕድሜ አግኝተው ላገርዎ ለሕዝብዎም ለኢትዮጵያውያን የሚያስቡትንና የጀመሩትን ደግ ሥራዎን አምላክ እንዲያስፈጽምዎ እንመኛለን ።

(ካለፈው ቍጥር የቀረ ።)

እውነተኛ ፍቅር።

ሁለተኛ ፍቅር መግለጫ ፤ በባትና በልጆች ያለ ፍቅር የጸና ነው አባቶች ልጆቻቸው ባሳዘኑዋቸው ልክ ከነዚህስ ጋራ ከመኖር ቤቱ ይጥፋ ኑሮም ይቅርብን ብለው ሁሉን ቢበትኑ ልጆቻቸው ለጥፋት እነርሱ ለኀዘን በሆኑ ነበር ። ሰውም ሁሉ ሲያላግጥባቸው በኖረ ነበር ዘመናቸውም በኀዘንና ተስፋ በሌለበት መጸጸት እየቈሰሉ እየተናቁ እየተሰደቡ እየተዋረዱ ባለፈ ነበር ስለዚህም ምንም እንኳ አለልክ ጥፋት ቢገኝባቸው ራሳቸው ይቀጡዋቸዋል እንጂ አድብቶ ለሚጠብቅ ጠላት አሳልፈው መስጠትስ አይጠረጠርም በታሪክም አልተሰማም ። እንኪያ እስቲ ራስህን መርምርና በዘውድህ በክብረትህ በኢትዮጵያ ያባቶችን ፍቅር ያህል እንዳለህ እይ።ወይም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴዎስ ወንጌል በ፯ም በ፱ ቁጥር ስለ አባትና ስለ ልጆች ፍቅር የሚለንን ተመልከት ። ማነው ከናንተ ወገን ልጁ እንጀራ ቢለምነው ደንጊያ የሚሰጠው ። አሣ ቢለምነውስ እባብ የሚሰጠው ። ወይም እንቍላል ቢለምነው ጊንጥን የሚሰጠው እናንተ እንኳ ክፎች ስትሆኑ መልካም ስጦታ ለልጆቻችሁ መስጠት ካወቃችሁ የሰማይ አባታችሁማ ለሚለምኑት መልካም ነገርን እንዴት የማይሰጣችሁ ይመስላችኋል የሚለውን እይ ።

የሶስተኛ ፍቅር መግለጫ ባልና ሚስትን መጀመሪያ እግዚአብሔር አንድ አካል አድርጎ ፈጠራቸው ሁለቱን ብቻ ፈጠረ እንጂ ሁለት ወንድ ላንድ ሴት ወይም ሁለት ሴት ላንድ ወንድ አይደለም ። እነዚህም ሁለቱ ቍጥራቸው እንኳ ሁለት ሊባሉ አይፈቀድላቸውም ። ነገር ግን ሁለቱ አንድ ሥጋ ሆኑ ይላል ። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ መለያየትም በጠየቁት ጊዜ እግዚአብሔር ያጋጠመውን ሰው አይለየው ይላል ። እንግዲያ ሰው ሚስቱን ምንግዜ ሊወዳት ነው የሚገባው እኔ የሚመስለኝ ለዚህ ምላሹ እንዲህ ይሆናል ። አምራ ሳለች በመልኳ በልብሷ በዕውቀቷ በጉልበቷ በስራዋ ባጭሩ በሁሉ ደስ ስታሰኝ ሳለች እወዳታለሁ የሚል ቃል ነው የሚባለውና የሚነገረው ግን ታማ ደክማ አድፋ ሞኝ ሁና ደንቁራ ከስታ ባጭሩ ስታስጸይፍ ተበላሽታና ተጎሳቍላ ስትታይ ሳለችሳ እንደዜች ያለች መች ለኔ የምትሆን ናት እርስዋን ስጠብቅ ልኖር ነኝን ሌላ አምጡልኝ የምትል አይደለምን ወይም እንግዲያስ እስከ ስንት ዓመት ልኰነን ነው እያልኽ ታማክኛ የለምን ወይም እርስዋስ እንኳ ደህና ናት ነገር ግን አባቷ እናቷ ወንድሞችዋ ዘመዶችዋ ክፉዎች ናቸውና አይስማሙኝም እንዲህ ከሆነ ትሂድልኝ እንጂ እርስዋን እወዳት ነበር የሚልሳ ብዙ አይደለምን ። እንደዚህ ያለ ፍቅር እንግዲያስ የጋለሞታ ፍቅር ነው እንጂ እውነተኛ ፍቅር ሊባል አይችልም አንተሳ ገበሬ ነጋዴ መኰንን ጌታ ስልጡን የኢትዮጵያ ዘር የሆንኽ ፍቅርህ እስከዚህ ብቻ ነውን ወይስ ከዚሁ ያለፈና የበረታ ነውን ኢትዮጵያን የምንወዳት ምንጊዜ ነው ስትሰጥህ ስትሾምህ ሰው ሁሉ ሲያመሰግናት ስታምር ጌቶችዋ ሲወዱህ ሲያመሰግኑህ ሲያከብሩህ ባጭሩ ደስ የሚያሰኝህንና የሚያምርህን ስታገኝባት ነውን የምትወዳት ከንደዚህ ያለ ነገር የሚነሣ ፍቅርስ ለጊዜው ሊጠቀሙበት የሚፈልጉ ጋለሞቶች እንኳ ለጊዜው በወደዱዋት ከምድር ዳርቻ መጥተውም ደግሞ በሰገዱላት ። ነገር ግን እንግዲያስ በምን ልውደዳት የማይከብርባት የማይረዳባት ባጭሩ ሁሉ ጕድሎባት ሳለ እንዴት አድርጌ ልውደዳት ብለህ ታስብ ይሆን ። የተክሊል ሚስትህ ናት ከሞት በቀር አንድ መከራ በማይለየው ኪዳን ተይዘሃልና ስለዚህ ብቻ ውደዳት እንደዚህ ያለ የታመነ ፍቅር ያላቸው የታመኑ በእግዚአብሔርና በውነተኞች ሰዎችም የተመሰገኑ ናቸው ።

ሰው እስኪሞት ድረስ በስሙ እንዲጠራ እንዲሁም ኢትዮጵያ የማዕርግ ስምህ ናትና ከሞትህ በኋላ እንኳ ልጆችህ እስከ ዓለም መጨረሻ ለልጅ ልጆቻቸው ሁሉ እንዲጠሩባትና እንዲከብሩባት የከበረች ስማቸው ናት እንዲሁም ኢትዮጵያና ልጆችዋ ባንድ ሰው ይመሰላሉ በምሉ ልብህ በምሉ ፈቃድህ ባንድ ሰው ላይ ያለ አንድነትን መርምር ከራሱ እስከ ጣቱ ያለ መስማማትንም ተመልከት እስቲ ማናቸው አካል ነው ከነዚህ ሁሉ ተለይቶ ለሌላ ሰው የሚያገለግል ወይስ ከነሱ ማናቸው ነው አንዱ አንዱን የሚጐዳ ሁሉ ግን ከእግዚአብሔር የተቀበለው እየ ማዕርጉና እየስራው አለበት ግን በዚሁ ያ ከፍ ያለ ዓይን በዚያ ዝቅ ባለ አካል ላይ አይቀናም አይጸየፈውም ትንሹም አካል ከፍ ባለው አካል አይቀናበትም ራስም እኔ በሁሉ ላይ ነኝና እንደሌሎች መቼ ሆንሁ አይልም ስለዚህም ለእግር የሚጐዳ መሰናክያ እሾኽ ወጽመድ ምንተብሎ ይቈጠራል እግርን የሚያገኘው ነገር ሁሉ ሌላም ብዙ ነገር ባወቀ ጊዜ ከዚሁ እንዲያመልጥና እንዲድን ያደርገዋል እንጂ ለጥፋት አሣልፎ አይሰጠውም ወይስ እንዴት ያለ እግርና እጅ ነው ራስን የሚቀጠቅጥ አንገትንስ የሚቆርጥ ጨከኝ የማይራራ እየቀማ የሚኖር መግደልና መንጠቅ የለመደ ሲመጣ ሲያዩ እኔ ራስ ቢፈጠፈጥና ቢቈረጥ እርሱን ለማዳን ብዬ የምደክምና የምዋረድ ምን ቸገረኝ የሚል እግር ምንም የለም እንዲሁም ደግሞ እግር ራስ ከኔ ተቈርጦ ቢጣል ከውርደቴ ምን የሚከፋ ይመጣብኛል ወይስ እርሱን ተሸክሜ ብኖር ምን አገኘሁ የሚል እግር ይገኛል ተብሎ አይጠረጠርም በዚህ ፈንታስ ራስን የሚጐዳ ነገርን በየ ጊዜ የማይደፈር በቋ ጽኑ አምባ እስኪያገኝ ድረስ ራሱን ተሸክሞ ይሮጣልና ያድነዋል እንጂ ራስን በመጉዳት የሚደርሰውና የሚከተለውን መከራ ያውቃልና እስከዚህ ድረስ አይሰንፍም ወይስ ምን እጅ ናት ከዚህ በላይ ያልነው መከራ ሲመጣ እኔ

ሁሉን ለማገልገል የምደክምና ውርደተኛ ሁኜ የምኖር ምንቸገረኝ ብላ ዝም የምትል እጅ ትገኛለችን ፤ ራስ ፈጽሞ እስኪደክምና ፈጽሞ እስኪቆስል ድረስስ ዝም ብላ የምታይ እለችን ፤ ዝም በማለት ያንተ ጋሻ ለመከልከያ መሳሪያ ለጸላት መውጊያ ይዛ የምትቸኩል እርስዋ አይደለችምን በየአካላታችን ያለ መስማማት አንድነት መረዳዳት ፍቅር እንዴት ወይስ ምንብለን እንቍጠረው እንደዚህ ያለ መስማማት ሊያገኙ የሚረዳቸውም ያንዱን ጉዳትና ጥቅም ባንዱ ላይ ሳይደርስ ከቶ እንደማይቀር ስላወቁ ነው አንዲትን አካል ይኸን ያኽል ማዕረግ ክብረት ሐብት እንሰጥሻለንና አንዱን አካልሽን ቈርጠሽ ስጭን ብለው ቢያባብሏት ያልዋትን ነገር አገኛለሁ ብላ የምትሰጥ ትገኝ ይሆንን የለም አይታሰብም አይጠረጠርም እንግዲያስ በእንደዚህ ያለ እውነተኛ የጠነከረ የወርቅ ሰንሰለት ታስረው የሚኖሩ ስለ ሆኑ ምንም እንኳ ያንዱ አካላቸውን ዋጋ በመቀበል ባይበለጥጉ ስለብርታታቸውና ስለ መታመናቸው ሲመሠገኑና ሕሊናቸው ደስ ሲለው ይኖራሉ ።

ተወልደ ብርሃን መድኅን ።

(ከዚህ የቀረው በሚከተለው ቍጥር ይታተማል ።)

የአንድ ሽማግሌ ተረት ።

ብልሆች ምክርን በምሳሌ ለመስጠት ሲያምሩቸው ተረት ነው እያሉ ያወራሉ ። እንዲሁም በጣም ትንሽ ልጅ ሳለሁ አንድ አስተማሪዬ ባባቱ ቤት የነበሩ ይኸን ቀጥሎ የተጻፈውን ምሳሌ ሲተርቱልን ልብ አደርግ ነበር ።

ቋጥኝና መንገደኞች ።

አንድ ዛፍ ብቻውን የበቀለ እንደሆነ በነፋስ ይወዘወዛል ይደበደባልም ቅጠሉም ሁሉ ይረግፍና ያለ ጥላ ይቆማል ። ቅጥዮቹና ቅርንጫፎቹ ሁሉ ወደላይ እንደማደግ ወደ ታች እየተጐነበሱ መሬትን ይፈልጋሉ ። አንድ ዛፍ ያለ ክንፎቹ ክንፎቹም ያለ ቅጠል ምንም ቀልብ ያለው ጥላ የላቸውም እንደዚሁም ደግሞ አንድ ችግኝ ከቆሩና ከጠራራ ፀሐይ መከለያ ያላገኘች እንደሆነ መጀመሪያ ትጠወልጋለች (መጠንከር ይኸን ጊዜ ነው) ሁለተኛም በግማሽ ትደርቃለች ።(ይህም ፃዕረ ሞቱ ነው) ። ሶስተኛም ጨርሳ ትሞታለች ።(ተሞቱ ሁሉ ከንቱ ነው) ። አንድ ሰውም ብቻውን ሲሆን የብዙዎች ሰዎች ያደርጉታል [illegible]

በልባቸውም ያለ እረመጥ ነበልባሉን ባፋቸው እየላከ ያቃጥላቸዋል ። ከዚህም ወዲያ ነፋስ እንደመታው ስንዴ እሸት ሊጀምር ሲል ብዕሩ አልችል ብሎት እንደሚጐነበስና ገርጥቶ እንደ ሚታይ ሁሉ ይኸም ሰው የዚያን ያህል ማለት ነው ።

ወንድሞቼ ሆይ እኅቶቼ አባቶቼ እናቶቼ ሆይ ሁላችሁም ስሙኝ እላችኋለሁ ። እንደዚህ ዛፍና እንደዚህ ችግኝ ብቻቸውን እንደበቀሉት አትሁኑ ። ተስማሙ ። እንዳችሁ ባንዱ ላይ ተደራርባችሁ በፍቅር እርስ በራሳችሁ ተሳሰሩ ።

እንዳችሁ ካንዱ በተለያያችሁ ጊዜ ፤ ፍቅርም ይቅርና ፤ ሁላችሁም ሐሳባችሁ ለራሴ ለራሴ ሲሆን ሐዘንና መከራ በራሴ እሸከመኝ ብሎ የመለመን ያህል ነው እንጂ ሌላ ትርፍ የለበትም

አንድ ቀን ብዙ ድንቢጦች ተሰብስበው አውድማ ውስጥ ሲጭሩ አየሁ ። አሞራም አንዷን ይዞ ለመሄድ በመካከላቸው አረፈ ። ሁሉም አንድ ጊዜ ቢያወኩበት ደንግጦ ከመካከላቸው አንድም ሳይዝ በረረ ። ምንም አቅም ባይኖራቸው ብዛታቸው በጃቸው ። እኔም ከዚያ ወዲህ ድንቢጦች ሺ ሁነው የሚጓዙት ለምን እንደሆነ ተረዳሁ ።

ይኸውላችሁ ወንድሞቼ ፍቅር እንደዚህ መልካም ነው ምሳሌያቸውን ተመልከቱት ውሰዱትም ። ስንት ናችሁ ብሎ ለሚጠይቃችሁ አንድ ነን ብላችሁ መልሱለት ። ይኸን ማለት እኛ ወንድሞቻችንን ነን ፤ ወንድሞቻችን እኛን ናቸው ማለት ነው

ነገር ግን ከወንድሞቹ የሚነጠል ሰው በሔደበት ስፍራ ሁሉ ፍርሐት ይከተለዋል ። ባረፈም ጊዜ ፍርሐቱ በጐኑ ይቀመጣል በተኛ ጊዜ እንኳ አይለየውም ።

የተረቱ መጀመሪያ እዚህ ነው ።

አንድ ሰው ብቻውን ወደ አህያ ፈጅ ይጓዝ ነበር (ሁላችሁም ያህያ ፈጅን ዳገት ታውቃላችሁ ። ተነስሙም አህያ ፈጅ ነው) ። ወንጭትን ተሻግሮ ያን ዳገት በጋሠስ ጊዜ ትልቅ ቋጥኝ ታፋፍ ተንከባሎ መንገዱን ገጥሞ ይዘበት አገኘው ። በግራም በቀኝም ለማለፍ ቢፈልግ የማይቻለው ሆነ ። ባለው ኃይል ሁሉ ደንጊያውን መግፋት ጀመረ ነገር ግን ውዳሴ ከንቱ ሆነበት ። ወደኋላውም ተመልሶ ዶብ እንዳያድር ጅረቱ በደራሽ ውሀ ሞልቶ አየው ። ጭንቀትና ፍርሃት በልቡም ውስጥ ነገሡ እንዲህም ሲል አሰበ ። ምግብ አልያዝሁ ምን በልቼ እድራለሁ ? እዚህ አጉል ቦታ ተገን የለኝ በጁ መሣሪያ የለኝ ፤ እርቧቸው የዋሉ አውሬዎች ከየዋሻቸው እየወጡ የደከመ አህያ የሚፈልጉበት ጊዜ ሊደርስ ነው ። ምን ይወጠኛል አለና ባንድ ዛፍ ስር ተቀመጠ ። ሌላ ደግሞ ከኋላው የለጠቀው አንድ ሰው ኑሮ በተራው ደረሰና እንደ ፊተኛው ያቅሙን ያህል ለፋና የማይሆንለት ቢሆን ዘወር ብሎ ለብቻው ቁጭ አለ ። ሶስተኛው መንገደኛ ደረሰ ። ይኸም ባዲስ ጉልበት በቅጡ ተረግጦ ቋጥኙን ይገፋ ጀመር ። ነገር ግን አላነቃነቀውም በደከመውም ጊዜ ሄዶ እንደሌሎቹ በጐናቸው ተቀመጠ ። ሶስቱም መንገደኞች ጭንቀትና ፍርሐት አደረባቸው ። ይተክዙም ጀመሩ ። አንዱ ተመካከላቸው ተነስቶ እንዲህ አላቸው ። በመካከላቸው ሰላምን ለሚያነግሡ እኔም በልባቸው ውስጥ ደስታን አነግሥላቸዋለሁ ብሏል እግዚአብሔር ።

አሁንም ይኸ ቋጥኝ የደፈነብን መንገድ የጋራችን ሁኖ [illegible]

በሉ አሁንም እግዚአብሔር የጋራ ጥቅማችንን አሳቢ ያደረገን ሥላሴዎችም በኛ በሶስታችን ተመስለው ኃይላቸውን ያውሱን ኑ አንድነት እንግፋ አላቸው ። አንድነትም ገፉት ተጐዳናቸውም አውጥተው ጣሉት ። አያችሁ ብልሃቱ ጥቂት ኑሯል ። ፍቅር ታለ ምን ይቸግራል ተባብለው በደህና ሁሉም በየስፍራቸው ሔዱ ።

ይኸውላችሁ ወንድሞቼ መንገድ ማለት ሕይወት ነው ። መንገደኛውም ሰው ነው ቋጥኙም በሕይወታችን ሙሉ ተጋድሞ በየጊዜው የሚያሰናክለን መከራ ነው ።

እግዚአብሔር በሚዛኑ መዝኖ አንድነት የሚሔዱን ሰዎች እውከት እንዳያገኛቸው የሚበቃቸውን ጉልበት ይሰጣቸዋል አሁንም የብቻችሁን ጥቅም አታስቡ ። ያንዱን መከራ አብራችሁ ግፉ ለመጣባችሁ ጠላት አብራችሁ መክቱ ። ሰላምም በመ—

ሻከላችሁ ይንገሥ እንዲህም ከሆናችሁ ጠላታችሁን ድል እንድታደርጉት በእግዚአብሔር የተነገረ ቃል ነው ።

እንዳርጋቸው መሰይ ።

ስለ ትምህርት ጥቅም ።

ብርሃንና ጨለማ ጠርነት ለማድረግ ቊርጥ ያደረጉ ይመስላል በኢትዮጵያ በየአውራጃውና በየወረዳው የትምሕርት ቤት ለማቆም ገንዘብ የሚያስፈልግ ስለሆነ ሁላችንም በፈቃዳችን እንዳቅማችን ገንዘብ አዋጥተን የማኅበር ቤት እናቁም ብሎ ብርሃንና ሰላም ጋዜታ ይናገራል ። በፈቃዳቸው የማይሰጡና ይልቁንም ይህነኑ በዝርዝራቸው ያልፎሙ ያለጥርጥር በ፲ ፺ና ይሆናሉ ይኸውም ሲያንሱ ነው።ምሳሌ፤፩ ከፉ ጠላት ብዙ ዘመን የሚቀመጥ ከክፋት ወደ ደግነት የማይለውጥ ዘወትር ጠብና ክርክር አንድ ጊዜ እረፍትና ሰላምን ለጐረቤቶቹየ ማይሰጥ ቢኖር ሁለጊዜ በመለማመጥና ዳር ዳር በማለት ቢቀመጡ እሱ ከልሞተ ወይም ጨክኖ ካላጠፉት ለመቸም ሰላምን እንዳያገኙ የታወቀ ነው ። እንግዴህ የትምሕርትን ብርሃንና ሰላም ወደ ኢትዮጵያ ለማግባት ጨለማንና ድንቊርናን ለማውጣት መንግሥት በኃይሉና በፈቃዱ የሥልጥንናን ሥራ በቶሎ ለማግባት ቊርጥ ከደረገ የሚያስፈልገውም ዋና መሳርያው ገንዘብ ከሆነ ሕዝቡ ምንም ሳይጐዳ ከመንግሥቱም ግምጃ ቤት ገንዘቡ ሳይወጣ የሚያስፈልገውን ያህል ገንዘብ ባመት ባመቱ ማግኘት ይችላል በመላ ኢትዮጵያ የመንግሥቱን ሥራ ይዞ ከረድኤቱ ማደሪያውን የብር ደሞዝ ድርጎ እህል ገባር በየወሩና በየአመቱ ከሚቀበል ወይም ከተቀበለ (ማለት እንደገባር) ከባለ ገባሩም አንዱ ገባር አንድ ብር በወር እንደሚሰጥ ታስቦ ከአዲስ ገቢ ወታደር ሰራተኛም አንስቶ እስከ ተጧሬ ሽማግሌ ከመኳንንት ሹሞችም ከባላምባራስ እስከ ራስ ከመንግሥት በቁጥር ከሚወጣላቸው ከአስር አንድ ከመቶ አስር በወር በወሩ እንዲሰጥ በአራቱ ማዕዘን ትእዛዝ ቢያልፍ እንዲፈጸም የታወቀ ነው ። በዚህ ሕዝቡ አይከፋውም አይጐዳምም ገንዘቡ ተመልሶ ለልጆቻቸው የሚሰጥ ነውና ። አሁን ባለገባር ገባሩ ከሚያገኘውና ጉልበቱ ቢታሰብ የሚቀበለው በመቶ አምሳ ይሆናል ከዚህ በመቶ አስር ቢሰጥ ምን ይጐዳል ? ነጋዴዎችና አራሾች ከሚያገኙት ሁሉ ከአስር አንድ ያወጡ የለምን ? መንግሥት በፈቃዱ ቢሆን ለዚህ ሥራ [illegible] በየዓመቱ ከሶስትና አራት ሚሊዮን ብር ይበልጥ ይገኛል ። ያውም ገንዘባቸውን ከፍሎ ልጆቻቸውን ማስተማር ከሚችሉት በቀር ። ይኸ ገንዘብ ላንድም ለሌላ ሥራ ለትምሕርትና ለትምሕርት ሥራ በቀር እንዳይወጣ ከሆነ መቶ ሁለት መቶ የትምሕርት ቤት በየአይነቱ ሊያቆሙበት ይቻላል ። ተመልከት ካንድ ትምሕርት ቤት በአራትና በአምስት ዓመት በጥቂቱ እናስብና አምሳ ልጆች ተምረው ቢወጡ ከሁለቱ መቶ ትምሕርት ቤት አስር ሽህ ልጆች መማራቸው ነው ። በእግዚአብሔር ፈቃድ ለንደዚህ ቢፈጸም በእኛው እድሜ ሥልጥንናን ብርሃንና ሰላምን ለማየት ተስፋ እናደርጋለን ።ቸሩ አምላክ ለዚህ በጎነት ሥራ ለሚጣጣሩ ልዑል አልጋ ወራሻችንን ይርዳልን እድሜ ለንግሥታችን ።

እንድርያስ ።

ስለ መልካም አሳብ የተማሪ ቤት እንዲቆም አስበው ወንድማችን ክቡር ፊታውራሪ ዱሬሣ ላመለከቱን እርዳታ ይኸውም ያቅሜን ፭ ብር ልረዳ ፈርማዬን በላኩልኝ ማስታወቂያ ልኬአለሁ እግዚአብሔር ልዑል ጌታችንን በረጅም እድሜ ያሰንብትልን ጥበብም ያስፋልን እንጂ ደግሞ ወደፊት የሚቻለኝ ሲሆን አምሳ ብር ልረዳ ተስፋዬ ታላቅ ነው ። ይህነንም አሳብ እግዚአብሔር ያስፋልን ።

ስለሺ በላይነህ ።

በኢትዮጵያውያን ማኅበር ለሚቆመው ተማሪ ቤት እርዳታ እንሰጣለን ብለው ፈርማቸውን የሰጡ ሰዎች ።

ከ፷፬ ቊጥር የመጣ ድምር ።	፪ሺ ፻፲፭ ብር
አቶ ዮሐንስ ገብረ ማርያም ።	፭ ብር
አቶ ኤፍሬም ፤ መግቢያ ፱ ብር ። ባመት ባመት	፳፭ ብር
አቶ ስለሺ በላይነህ ።	፭ ብር
አቶ አርዐዶም ዕቊቡ ።	፳ ብር
አቶ ወልዴ ሰማዕት ወልዴ ትንሣኤ	፫ ብር
ሙሴ ዋሀራም ።	፶ ብር
አቶ ይርጉ ተክለ ማርያም ።	፲ ብር
አቶ ብርሃን ሥላሴ አባ የሬ ።	፲ ብር
አቶ ተገኘ ።	፲ ብር
አለቃ ሠርፀ ድንግል ።	፫ ብር
ድምር	፪ሺ ፪፻፶፮ ብር

ለተማሪ ቤቱ እርዳታ ማስፈረሚያ ወረቀት የሚፈልግ ሰው ከልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት እየመጣ ሊወስድ ይችላል ።

የፈላስፎች ቃል ።

ነፍሳችን ተለዋጭ ናት በሥልጣኔም ታዳጊ መሆኗ በዚሁ ምክንያት ነው ። ኤምሊዮ ካስቴላር ።

በትምህርት ከማደግ የሚገኘው ትርፍ ሰው ለመስራትም ነው እንጂ መኪና ብቻ ለመስራት አይደለም ፤ ፖል ዠኔ

የውስጣችን ክብር ሥራ ሁል ጊዜ በሥልጣኔያችን እድገት ሥራ ነው ። ማዳም ስዊቼ ።

ከልክ ማለፍ የኩራት መሸፈኛ እንዳይሆን መፍራት ነው ለስላስነትም የስንፍና ምክንያት እንዳይሆን መፍራት ነው ። ዡል ሲሞን ።

[illegible] በሁሉ ነገር ራስን መቻል ነው ። ሞንቴኝ ።

ከኢጣልያ መንግሥት ሌጋሲዮን የመጣ የቴሌግራም ቃል ።

የግንቦት ፴ቀን የለት ወሬ ።

ሮማ ። የኢጣልያ ንጉሥ ቢቶሪዮ አማኑኤል መንግሥት ከጀመሩ እስከሁን ፳፭ ዓመት ስለሆናቸው የሮማ ሕዝብ ተሰብስቦ በዓሉን በታላቅ ሰልፍና ድንቅ በሆነ አከባበር አከበረ ፤ ብዙ ሠራዊትም ተሰልፎ በንጉሡና በንግሥቲቱ በመኳንንቱም ፊት ሰልፉን አሳየ ።

የሰኔ ፩ ቀን የለት ወሬ ።

ሞስኮ ። (የመስኮብ ከተማ) ፯ አሬዎፕላኖች ሰዎች እንደያዙ ወደ ቴኪዮ ለመሄድ በረሩ ። ቢሆንላቸው የሩስያውያንና የቺና ማኅበር አቁሞ በኤውሮጳና በቺና መካከል የተከከለ የንግድ ሥራ ለማቆም ይታሰባል ።

በልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

መጀመሪያ ዓመት ፡ ቁጥር ፳፮ ።
1re ANNÉE № 26

ሐሙስ ሰኔ ፲፰ ቀን፡፲፱፻፲፯ ዓ ም ።
JEUDI 25 JUIN 1925

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumiére et paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

የጋዜጣው ዲሬክተር ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ይስታውቁ ።
Gabré Christo Taklé Haymanot
Diréctеur

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሲገዛ ስፈልግ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie
Un an 5 Thalers
Etranger
Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

(ካለፈው ቍጥር የቀረ ።)

እውነተኛ ፍቅር።

አንተ የኢትዮጵያ ልጅ ሁሉን የሚመረምር አምላክ ፊት ሰውነትህን መርምር።አዎን በእንደዚህ ያለ ፍቅር ተይገርሰሁ ብለህ ልትመሰክር የምትችል እንደሆን ወይም የማትችል እንደሆን ፡ እንደዚህ ያለ ፍቅር ከሌለህ ግን ከእግዚአብሔርና ከህሊናህ ከኢትዮጵያም ፊት ይቅርና በጸላቶችህ ፊትና በጸላቶችህ ሕሊና እንኳ የተናቅህ እንደ እርኩስ እንስሳም የተጸየፍህ የምትሆን በግዜውም ያ የታለለህን ነገር እንደ ይሁዳ ከመጸጸትህ የተነሣ ጥልኸው መታነቅህ አይቀርም ከራሱና ከገሩ አብልጦ ገንዘብንና ውዳሴ ከንቱን የሚወድ ሁሉ ባለቤቱ ራሱ የተዋረደ ነውና ለውርደቱ ዳርቻ የለበትም ተጨነቅ ።

ነገር ግን ተስፋ አትቁረጥ የሙሴንም ውርደትንና እድልን አትርሣ የንጉሥ ልጅ እየተባለ ጥቂት ዘመን ደስ ከሚለው ይልቅ ከሕዝበ እግዚአብሔር ከወገኖቹ ከወንድሞቹ ጋራ መዋረድን ወደደ ይለናል አንተማ ሕዝብህንና አገርህን ለመውደድ በእንደዚህ ያለ ፍቅር ተይዘሐልን ወይስ በትንሽ ነገር ትታለላለህን እንድ ትልቅ ሰው በእንደዚህ ያለ ፍቅር ንግግር የተነሣ ስንጫወት ማለን ምድር በኋላዬ ሣር አይብቀልበት አለ አህያና፤ በኋላዬ የሚሆን ነገር ምን ቸገረኝ ብሎ መለሰልኝ እንደዚህ ያለ ነገርም ደግሞ ከያሌ ሌሎች ሰዎች ሰማሁ እኔም ራስህንስ በተናቀውና በተጸየፈው እንስሳ ካስተካከልከው ምን ልበልህ እስከል ድረስ ሆንሁ፡ አሁንም እንዲሁ ያለ አሣብ ላለህ ሰውነትህም ምንቸገረኝ በሚል ድንዛዜ ተይዘህ ሳለህ ወንድሜ ይህቺን ምላሽ እንጂ ሌላ ልልህ አልችልም ማለት ሰውነትህን እንደ እንስሳ ስለቈጠርኸት የቀኈጭቱ ብርታት እስኪሣቅይህ ድረስና ሰው መሆንህን እስክትረዳ ድረስ ነው እናንት መኳንንቶች እጅና እግር የሆነ ሕዝባችሁን ትወዳላችሁን የማን እራስ ነው በላያቸው ተቀምጦሚለሁና ልክራ ይገበኛል ብሎ በሌሎች አካላት ቢጠፉም ይጥፉ ብሎ የሚጣላቸውና የሚጓደድ ፡ወይስ እንዴት ያለ እግር ነው ራስን እኮ እኔ ባልሸከመው ወድቆ የሚቀር ነበር ብሎ የሚኰራበትና የሚሣቀይበት ይኖር ይሆን ።

ምናልባት እነዚህማ እግዚአብሔር እንዲሁ አድርጎ ቢፈጥራቸው ነዋ ትል ይሆንን ። አዎን፡አሁንማ ያ ስላንዲት የራስ ጸጉር የሚያስብ ከልሸመው የሚሾም ይኖር ይሆን ለሁሉ መቼም ባለቤቱ እንደፈቀደለት ነው የሚሰጠው ፡ የከበርክ የኢትዮጵያ ልጅ ለምና ከሚበላ ጀምረህ ንግሥ እስከለ ድረስ እንዲባል፤፩ ሰው ባንድ ጆማት የተያዝኸ ባንድ አጥንት የምትቆም ላንዲትም ሆድ ምግብ ሰውነትህ ኃይል የምታገኝ ነህና ይህን አትርሳ ፡ አንድ ቀን ከአንድ ተራራ ወዳንድ ተራራ ልሻገር ብዬ ስገሠግሥ ሳለሁ አንዲት በሕልምና በሐሳብ ክልቤ ልትለይ የማትችል ፍሬዋ ከሌላ አገር ወይን የሚጣፍጠኝ ወርክ በወንዝ ዳር ቁማ አገኘኋት በዙሯዋም ብዙ ሰው ከበዋት አየሁ፤የሰዎቹም አሰጣ ጠንዴት እንደሆነ የሚያውቅ አልነበረም፡ስለዚህም ለጠባቆችዋ ብዙ ቸገራቸው ። ብቻቸውን እንዳይከተኰቷትና እንዳያጠጧት የዛፏ ግንድና ስር ሰፋብቸሁ፡ደግሞ እርሱን ሲሰሩ ሳሉ አያሌ ሌሎችስ ከነ አቶ አመጻኞች የተባሉ ትልልቆች ሰዎች የተቀበሉት ስለታም መጥረቢያ ይዘው ብትወድቅ በላያቸውና በልጆቻቸው ላይ መሆንዋን ፊጽማም ዘራቸውን እንዳች ሳይቀር እንድታደቃቸው ሳያውቁ ስሯን ሊበጥሱ ይጠባበቁ ነበር ፡ ዋና ጠባቂ አድርጎ የዛፊቱ ጌታ የሾመው ተስፋ ያለው የተመረጠ ሹሚም ብዙ በጉዳቷ የሚያዝን ስለሆነ ስለችግሯ ይጨነቅ ነበር ጊዜውም የደረቀ በጋ ስለነበረ ዛፊቱ የምትጠጣበት ውሀ እውቀት ብርቱ፤ያሸንፋል፤ጠላቱ ከሚባል ወንዝ በበይ መጥቶ ነው የሚያረካት እንጂ ምንም የቆመችበት ያለችበትም ቦታ እንኳ ወንዝ ቢሆን የሚበቃት ውሀ የለበትም በዚያ የነበሩ ሰዎች ግማሻቸው ምነው ውሀ ብናመጣላት ብትጠጣና ስሯ ቢበረታ

ኋላ ነፋስ ገፍቶ እንዳይጥላት ይሉ ነበር ። ግማሾቻቸው ግን የፀሐዩንና የነፋሱን ብርታት አያውቁምና እንዴት ያለ ነፋስ ነው ይኸነን ገፍቶ የሚጥል ብለው ከጽላው በታች አርፈው ይጓደዱና ይንቀባረሩ ነበሩ ፤ እኩሌታቸውም በላይዋ ተቀምጠው ፍሬዋን እየለቀሙ ይበሉ ነበሩ እኩሌታቸውም ከፍሬዋ ወስደው የዲያብሎስ ወንዝ ከሚባለው ምንጭ የተቀዳ የሞት ውሀ የሆነ በፍሬዋ እየገዙ ጠጥተው ሰክረው በመርዙ ደንዝዘው ከጽላዋ በታች ወድቀው ተበላሽተው ተጥለው ነበሩ ፤ በጠገብዋ በነበረ መንገድ የሚያልፉ የነበሩ ሰዎችም ግማሾቻቸው ይስቁባቸው ግማሾቻቸውም ይሳለቁባቸው ግማሾቻቸውም ያለቅሱባቸው ነበሩ የፀሐዩ ትኩሳት እንዳይነካቸው ግን የዛፊቱ ቅጠል ብርቱ ስለ ሆነ ይረዳቸው ነበር እንጂ እርሱ ባይኖር እንደዚህ የመሰሉ ሰዎች በሕይወታቸው ይኖራሉ ተብሎ አይጠረጠርም ።

በዚሁ ተጸጽተው እንዳይተውትም በጥፋታቸው የሚያመሠግኑዋቸው እነ አቶ አታላይ የሚባሉ ፍሬውን በመርዝ ለውጠው እንዲወስዱት ያባብሏቸው ነበሩ ። ዛፊቱም ከንደዚህ ያሉ ሰዎች ረድኤት እንድታገኝ ተስፋ የላትም ። ፍሬዋን ለቀመው ለመርዝ መለወጥ እንጂ የስርዋን ነገርና የውሀ ማጣትዋን ነገር አይማቅያቸውም ነበር ። እንደዚህ ሁኖ ሳለ በዛፊቱ ላይ ተሹሞ ያለ ሰው በዩ እያበጀ ። እውቀት–ብርቱ–ያስሸንፋል ጠላቱ ። ከሚባል ወንዝ አምጥቶ ዛፊቱን ሊያጠጡ የሚችሉና ታምነው በፀሐይ ትኩሳት በሌት ጨለማና ውርጭ በጠላት ብርታት እየተሳቀዩ ታምነው የሚረዱ ሊያይ ብሎ በዙሯዋ ቆሞ ባለ ሰው ላይ ይመለከት ነበረ ። ሰዎቹ ግን ሁላቸው በሙሉ ልባቸው የሚያገዙላትና የሚደክሙላት ይመስሉ ነበሩና መለየታቸው ቸግሮት አለእረፍት ይተነፍስና ይቃትት ነበር ነገር ግን አያሌ ከነሱስ ከንድ ስር የሚጎዳ ውሀ ቀድተው ሊያጠጡዋትና ከጎጂው ውሀ ጌታ ጥቂት እናገኝ ይሆን ብለው ከዚሁ ሊያጠጧት ቸኵለው ነበሩ ። ይኸንን ማድረጋቸው ግን ምክንያቱ ለወደፊቱ ፍሬዋን ለቀመው ሕይወታቸውን እንደሚጎዳ ስላላወቁ ነው ። ነገር ግን በዚያም በውነት የሚያገዙላትና ሕይወታቸውን ሊያማልፉላት የሚወዱም ብዙ ነበሩ ፤ እንደዚሁ ሁኖ ሰዎቹን መለየት ስለቸገረውም የዛፊቱ ሹም ሲጨነቅ ሳለ በዚሁ ገብቼ ስላልተመለከትኩትና ስላላየሁት እኔ ብሆን እንዲህ ባደረግሁ እንዲህም በጨመርሁ ። እንደነዚህ ያሉ ሰዎችም በዚሁ ሊገቡ አይገባቸውም ብዬ ብዙ ዓመት እመክ ነበርሁ ። ስለዛፊቱ ያዘንኩበት ዘመን ሁሉ ፤ በላዩ ፈረድኩ ኋላ ግን አንድ እውነተኛ አሳብ የሚባል ሰው መጥቶ በል ይህን ሁሉ ሥራ ቢፈቀድልህ እዚያ እርሱ ተቀምጦበት ያለ ሁነህ ብታስተካክለው እኔ ብሰጥህማ ብሎ አስጨንቆ ያዘኝ ። ስለዚህ እኔ ሳይደርሰኝ ተጨነቅሁና መልሼ ለሰውዬው በዛፊቱ ላይ የሾመው የዛፊቱ ጌታ ሁሉን ያውቅ ነበር ለሰዎችም ለያንዳንዱ ልባቸውንና ኩላሊታቸውን ስለሚመረምረው እንዲረዳውና አሣቡን እንዲያበራለት ብዬ ለመንኩ ። ስለ ሰውዬው ብርታትና እውቀትም እጅግ ተደነቅሁ ። ሰው ሁሉ ፈዛ ስላየሁ ብዙ አዘንሁ ፤ ነገርግን በምሊዮን ጭነት ወርቅ እንኳ የማይታለሉና ዛፊቱን አሣልፈው የማይሰጡ ሰዎች ዓይቼ ተጽናናሁ ። ይልቁንም እንዲረዳት ብሎ እግዚአብሔር የሾመውን ፈቃድንና ያያሌ ሹማምንቶችን የልጆችዋን ፈቃድ ምን መሆኑን በተረዳሁ ጊዜ ብዙ ጊዜ ደክሞ የነበረ የተስፋ አሳቤ ታደሰ በመጣሁ ጊዜ ደግሞ ከወንዙ ስመላለስ ዛፊቱን እመለከት ነበርሁና ያ እግዚአብሔር ቀብቶ በዛፍዋ ላይ የሾመው ሰው በጣም የሚያጠጣትንና የሚያረካትን ክረምት እንዲመጣ ሙሉ ተስፋ እያደረገ እስከዚያ ድረስ ከእውቀት–ብርቱ–ያሸንፋል–ጠላቱ በበይና በመቅዳት ሲያጠጣት አገኘው ነበርኹ ውሐ የሚመጣበት መንገድ ግን ውሀውን ተሸክሞ ማለፍ የሚያስቸግሩ ብዙ ደንጎች ነበሩበት ስለዚህ ይህን ያህል መከራ ሳለው ሳይሰለች ወደፊት መግፋቱን አይቶ የዛፊቱን አለቃ ሙሉ ፈቃድና ሙሉ አስተዋይ አእምሮ ያለው ብዙ ሰው ያመሰግነው ነበር ። ብዙዎቹ ግን የዛፊቱ ችግር ያልገባቸው የደህንነትዋን መንገድም የማያውቁ ይህንን ድካም በስንፍና ቀጭቱ ያዩት ነበር ነገር ግን የተወደድህ አንባቢ ሆይ በውጭ የሚታይና የሚባልን ነገር ትተህ ይኸን ያህል ድካም ለምን እንደሆነና ወደ ንዴት ያለ በረከት እንዲያደርስህ አጥልቀህ መርምር ። እግዚአብሔር ለኢትዮጵያ ያሰበላትን ነገርሃም አስተውለው ነገሩን ሳትመረምርም የሰውን አሣብ አትንቀፍ ብርቱ ጠላት ያለው ሰው ጠላቱን ለመቃወም ብዙ መሳሯ ያስፈልገዋልና መሳሯም የብረት ነገር ብቻ አይምሰልህ ። ከጦረኛ ጦር ። ከባለጠበንጃ ጠበንጃ ። ከባለ መድፍ መድፍ ። ከባለ ወርቅ ወርቅ ። ከባለ ብር ብር ። ከባለ ትምሕርት ትምሕርት ። ከባለ ሙግት ሙግት ። ከተለማማጭ ተለማማጭ ከቁጡና አስፈሪ ቁጡ መሆንን ። ደግሞ ምንብለን እንቍጠረው በቍጥሩ ልክ እንዳመጡ መቃወም ያሥፈልጋል ብዙ ሰዎች ግን ደግሞ እንደዚህ ያለ ነገር ምንድር ነው በዚህ ወይም እንደዚህ ነው እንጂ የሚሉ አሉ ።

ግን በበጋ ጥላ ፤ በክረምት የዝናም ልብስ በሙቀት ስስ ልብስ በብርድ በርኖስ (የሚጎዳህን) የሚቃወምን እንዲያስፈልግህ አትርሳ ።

ተወልደ ብርሃን መድኅን።

ስለ አገር ፍቅርና የትምሕርት ቤት ማስታወሻ ።

ክቡራን ወንድሞቼ በኻያ አንድ ቍጥር በብርሃንና ሰላም ለአገራችን ጥቅምና ብርሃን የምትሆን የትምሕርት ቤት እንድናቆም ጽፌላችሁ ነበረ ይህም የጻፍኩት ቃል ክቡር ፈቃዳችሁ ሁኖ እንድታደርጉ ሙሉ ተስፋ አለኝ ። ነገር ግን አንድ አንድ ሀሳብ ሰባሪ ሰነፍ ሰው ልብ የሚያሻክር አይጠፉምና ወይም አታላይ ትምርት ምን ያደርጋል የተማሩትስ ሰዎች የቃለ የሮፓችን ሥራ የሚሠሩ ይሏችሁ ይሆናል ይኸን የሰነፍ አሳብ ከንቱ መሆኑን አስረዳችኋለሁ ልብ አርጋችሁ አንብቡ የሥልጣኔ ትምርት ቤት ማለት ይኸ ዛሬ እኛ ከገራችን ቆሞ ያየነው ብቻ አይደለም የሥልጣኔ ትምርት ቤት ማለት ደረጃ ፤ ደረጃና ስም ስም አለው ይኸ ዛሬ ባገራችን ያለው የትምርት ቤት እስኩል ይባላል ያውም ሙሉ አይደለም ፤ ልጅ ከዚያ ፭ ፯ ዓመት ተምሮ መጨረሱን የምስክር ወረቀት ተቀብሎ ይወጣል ከዚያ ወጥቶ ኮሌጅ ከሚባለው የሥልጣኔ ትምሕርት ቤት ገብቶ ፬ ዓመት ተምሮ አሁንም ለትምሕርቱ የምስክር ወረቀት (ሰርትፊኬት) ተቀብሎ ይወጣል እውቀት የጐደለው ገንዘብ የቸገረው ከኮሌጅ ሲወጣ እሱም የሚበቃ ዕውቀት ያለው ትምሕርት ነውና በሱው ሥራ ይይዛል ። ግን ዋና ዋና ብልሆች የምስክር ወረቀታቸውን ይዘው ዩንበርሲቲ ከሚባለው ዋና

የውቀት መማሯ የትምሕርት ቤት ገብተው ከዚያ እንደሚማሩ ስራ ብዛት ፭ ዓመት ወይም ፫ ዓመትም ተምረው ከዚያ ሐኪም ወይም የብረት የባቡር የመኪና ኤንጅኔር ማለት (ማሐንዲስ) ወይም የቤት የድልድይ ኤንጅኔር ወይም አቡካቶ የጥብቅና ስራ አዋቂ ወይም የኮማርሻን ስራ የኩፓንያ የባንክ አቋቋምና አሰራር ተምረው ይወጣሉ ይባላል ።የሚማሩትን የሥራውን ስም ስሙን ሁሉን ለመጻፍ ግን ለቁጥር ይበዛል ብለን ትትነዋል ። ትልልቅ ሥራ የሚሰሩ አዲስ ብልሃት የሚያወጡ በዚህ አካሄድ የትማሩት ናቸው ። የዚህ ዓይነት የትምሕርት ቤት በመታጣቱ ነው እንጂ ሰነፎች እንደሚያወሩት ትምሕርት የማይጠቅም ሆኖ አይደለም ወይም የኢትዮጵያ ልጆች እንደሌላው አገር ሰልጥነው የጥበብ የውቀት ስራ መሥራት የማይችሉ ሆኖ አይደለም ስለዚህ ልባችሁ አይስነፍ እኛ ከበረታንበት ወደፊት ይኸ ኮሌጅ የሚባለው የሥልጣኔ የትምርት ቤትም በቅርብ ቀን እዚሁ ይቆማል ዘሃ ተጋግዛ ዘሆን ታስራለችና ደግሞ አንዳንድ ሰዎች ነገር የማይመረምሩና የማይገምቱ አሉ እንደ አባቶቻችን አንቀመጥም ወይ አዲስ ጥበብ ለምን እንማራለን የሚሉ ።

ግን ይኸም ከንቱ የሰነፍ ጨዋታ ነው ሰውን እንዳባቱ ማን ያኖረዋል እንደ ጊዜ ይኖራል እንጂ የድሃን ልጅ ደሃ ሁነህ ቅር ቢሉት በጀ ይላልን ወይስ የጌታን ልጅ አትደኸይ ቢሉት ይችላልን ። እስቲ ማነው እንዳባቱ ሊኖር የቻለ ሁሉንም አስተውሉት የአያቶቻችን መሳሪያ ጦር ነበር ነገር ግን አባቶቻችን በዚያው በጦሩ እንቆይ አላሉም የጠበንጃን መሳሪያነት መረጡ እንጂ ደግሞስ ምናልባት ጠላት ቢነሣብን የአባቱን መሳሪያ ይዞ ይመጣል ወይ በጣቱም አይነካው በዓለም ሁሉ አባቱ መጣቀሻ የቋድ ጠበንጃ ይሠራ የነበረው ሕዝብ ከምሱር ያለው ሁለት አፍ በቂቱ ሠራ ። አባቱ በቂቱ ይሰራ የነበረው ሲናድር ውጅግራ ሠራ አባቱ ሲናድር ይሰራ የነበረውም ዛሬ ማውዜር መትረየስ ይሠራል አባቱ በጋሪ ሲሄድ የነበረው ባቡር ሰራ ደግሞ አባቱ ባቡር ይሰራ የነበረው ዛሬ በኤሮፕላን በአየር ላይ ይሄዳል ስለዚህ እኛም ከዓለም ተለይተን ለብቻችን እንዳባቶቻችን እንኑር ማለት አይመቸንም እንደ ሌላው ዓለም ተምረን ሠልጥነን እንስራ እንጂ ወንድሞቼ ሆይ ይኸ ሁሉ የከበደ የማይሆን የማንችለው እሩቅ መስሎ እንዳይታየን ከተጋንበት ትንሽ ነው ~~ይኸ ሁሉ የምናየው የዓለም ጥበብ ከዚች~~ ከትንሽቱ የሥልጣኔ ትምሕርት ቤት ነው የሚነሳው እንጂ ከሰማይ አይወርድም እኛም ሙሉ ሰዎች ነን ጉድለታችን ከዓለም ወደ ኋላ ያስቀረን የሥልጣኔ ትምሕርት ማጣታችን ነው በሷ እንትጋ ከዚህ ቀጥሎ ስለዚሁ ጉዳይ የተጻፈውን ቃል አስተውላችሁ እንድታነቡት በትሕትና እለምናችኋለሁ ዛሬ በዓለም ካሉት ሕዝቦች በከፍታ ደረጃ ያሉት አሜሪካና አውሮፓ ናቸው ደግሞ እነሱን ተከትሎ የደረሰባቸው ጃፓን ነው እነዚህም ከዓለም የሚበልጡ ብልሆችና ጌቶች የሆኑበት ምክንያት አንድ አንድ ሰው ለየራሱ ትዳር ለራሱ ጥቅም ብቻ እስቦ ገንዘብ ሰብስቦ በማኖር አይደለም ሕዝብ ሁሉ አንድነትን አጠንክሮ ላገሩ ከማሰብ የተነሣ ነው እንጂ ላገር ማሰብ ማለትም መጀመሪያው የሥልጣኔ ትምሕርትን ማስፋት ነው ።ሁለተኛው መተባበር ነው ። የአንዱን ሐሳብ አንዱ አለመቃወም የአንዱን ሰው ሐሳብ በመቃወም ፈንታ ሌላ ሐሳብ አስቦ መስራት ነው ዓለም ሁሉ ከባለጋራው ይታገላል እኛ ግን ካለማወቅ የተነሣ እኛ በኛ እንታገላለን አገሬ አገር ትሁን የሚል ሰው የሥልጣኔ ትምርት መተባበር እንዲሰፋና እንዲለማ መጠንከር ነው

ጃፓን በብዙ ዓመት የሰለጠኑትን መንግሥታት ተከታትሎ በ፵ ዓመት መድረሱ ያለ ኃይሉን ሁሉ በሥልጣኔ ትምሕርት ላይ በማድረጉና በመተባበሩ ነው ።መተባበራቸውም ለየራሳቸው ጥቅም አይደለምም ላገራቸው ሥልጣኔ ስፋት ላገራቸው ነፃነት ነው እንጂ ።ሂሶፒ በምሳሌ እንዲህ ይላል አንድ ሀብታም ሰው ከብቱን ሁሉ ሽጦ ወርቅ ገዝቶ ትልቅ እንክብል ወርቅ አድርጎ ቀበረውና ጧት ጧት ሂዶ ተሸሽጎ ሲያየው አሽከሩ ሰልሎ አይቶ ሰርቆበት ይዞ ጠፋ እሱም ጧት ሂዶ ወርቁን አይቶ አጥቶ ሲያለቅስ አንድ ብልህ ሰው ምን ሆንህ ብሎ ቢጠይቀው አጫወተው ያም ብልህ ሰውዬ ናና ተስፋ የሚሆንህን ነገር እንግርሃለሁ ብሎ በዚያ ወርቅ ስፍራ ትልቅ ድንጋይ ወስዶ ቀብሮ ጧት ጧት መጥተህ ይህንን እይ ያም ወርቅህ ቢሆን ዱሮም ከዚህ በቀር ሌላ ሥራ የለውምና የገንዘብ ጥቅሙ ስራ መስራቱ ነው እንጂ መኖሩ መቀመጡ አይደለም ይላል ሂሶፒ እሁንም ገንዘብ ማግኘትን ብቻ ብናውቅ ለዚያ ገንዘብ የሚገባውን ስራ ባናውቅ ይኸን ያህል ነው።አሁን ብዙ እናውቃለን የሚሉ ሰዎች በቤት ስራ ውል የውጭ አገር ሰዎች አከሡሩን ወይም አንድ ውል ተጻጽፈን በማይሆን ውል ገንዘባችንን ወሰዱብን ብለው ሲያዝኑ ከብዙ ሰዎች እንሰማለን ይኸ መሆኑ እነዚያ እንደዚህ የሚያደርጉ ሰዎች በጌትነት በገንዘብ በልጠው የሎሌ ብዛት ማእርግ ወይም በግድ በኃይል አይደለም ቢማሩ በእውቀት ቢበልጡ ነው ስለዚህ ልጆቻችን (ማለት) ያገር ልጆች ቢማሩ ከዚህ ይጠብቁናል ለራሳቸውም ይጠበቃሉ በቀረ ይወረሳሉ ያገር ልጆች ቢማሩ መሐንዲስ ቢሆኑ በቤት ሥራም እንደዚህ አንጉዳም በሁሉም በሌላ እንደዚሁ ነው ። ስለዚህ ለሥልጣኔን ትምርት መረዳዳት ትልቅ ጥቅም መሆኑን እወቁ ።

ስለ አገር ፍቅር ስለ ነፃነት ብ
ስምናችሁ ።
ጣማሮች ወንድሞቼ ለምን ረሳችሁ ።
የሚረሳ ቃል ነወይ የጻፍሁላችሁ ።
ትምሕርት ብርሃን መሪ ነው ለልጅ
ልጆቻችሁ ።
ደግሞም ደጋፊ ሀበኛ ነው ለወርቅ
አገራችሁ ።
ወደ ፊትም ትልቅ ማዕርግ ነው ለ
ክቡር ስማችሁ።
ስለ አገር ነፃነት ስለ ማዕርጋችሁ ።
ስለ ኢትዮጵያ ወላጅ እናታችሁ ።
ልመናዬን ስሙኝ ጌቶቼ እባካችሁ ።
የትምሕርት ቤት እናቁም ነጻነት ማለት
እውቀት ነው የማያሳፍራችሁ ።
ባለም ሕዝብ ፊት የሚያስከብራችሁ ።
ሠልጥነዋል ተብሎ መጠራት እሱ ነው
ጣርማችሁ ።
እያልሁ እለምናለሁ ትጊሽ ወንድማችሁ
በቀረስ ከንቱ ነው ሕዝብ መባ
ላችን ።
[illegible]
ልጆቻችን ።
ከልብ አስተውሉ ወንድሞቻችን ።
ልብ ዳኛ ነው አይቀርምና ታሪክ መ
ጻፋችን ።
ለሚመጣው ትውልድ ለወገኖቻችን ።
መጻፉ አይቀርም በዝርዝር ስማችን ።

ምንም ቢሆን በስልጣኔ ትምህርት እየተባበርን በ፩ነት ካላሰፋነውና ስልጣኔ ካልሰፋ ለየራሳችን ጥቅም በማሰብ የዓለምን ፖለቲክ አንዘልቀውም እኔ ብቻ ባገኝ ብጠቀም አይበቃም ምንም ቢሆን ሰው ከነወገኑ ከነአገሩ ካልቆመ የራሱን ጥቅም ብቻ ቢፈልግ ስሩ እንደ ተቈረጠ ዛፍ ይሆናል ያንዳንድ ሰው ጥቅም በጥቂት ቀን ሊጠፋ ይችላልና የአገር ጥቅም ኑዋሪ ነው ።

ፊታውራሪ ዴሬሳ

ሰኔ ፲፫ ቀን ሰኞ ማለዳ ወደልዑል አልጋ ወራሽ ቤት ስወጣ ድንገት ብዙ አጀብ አየሁ።ያጀቡ ሰው ሁሉ ፊቱ ብርሃን ሆኖዋል ብጠጋ ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ደስ በሚያሰኘው ጸዳላቸው በምሕረት ዓይናቸው ግራ ቀኝ እያዩ አጥቂቸው የሰነበቱ ተቻጋሪ ደሀቸውን እያስቀረቡ እንደሚገባ ጉዳዩን ሲፈጽሙለት ደርሼ ጠመንጃዬን ይገፍ መሬት ስሜ ደስታውን ተካፈልኩ ፤ ኢትዮጵያ ተጨንቃ ኀዘኑዋን ወደ ደስታ የለወጠው አምላክ ይክበር ይመስገን ። የልጁዋን መልክም ሐሳብና እርዳታዋን ያስፈጽምላት ደስታዋን ያሰነብትላት ለልዕልት ንግሥተ ነገሥታትም እንኳን ደግ አሳቡ ፈቃደኛ ልጁዎን ዓይንዎን ባይንዎ ያሳየዎ ብዬ ይህን ዝማሬ ጻፍኩ ። ተፈሪ ቸርነት

ጥያቄ ።

ክቡር ነጋድራስ አስታጥቄ ባገራችን እየተጀመረ የቀረ ሥራ ብዙ ነው ብለው በሰስተኛ ቍጥር ብርሃንና ሰላም ጽፈው ነበር።አሁን ወደ እርሳቸው መልሰን እንጠይቃለን ።

ባገራችን ብዙ ሥራ እየተጀመረ መቅረቱ በምን ምክንያት ነው ? ደግሞ ባገራችን ደግ ሥራ እየተጀመረ ወደ ፊት ሊገፋ እንጂ ተጀምሮ እንዳይቀር ምን ማድረግ ያስፈልገናል ? ።

የሚጠቅመንን ነገር ለማድረግ የተሰናዳን እንሁን።

ኢትዮጵያ እናታችንን ከድንቍርና ፈርዖን እጅ ለማውጣት ከንዳንድ ወር ጕልበታችን ክፍለን ብንሰጥ ሙሴያችን ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን እጃቸውን እንስተው ኤርትራ መለያየትን ምቀኝነትን መትተው ኢትዮጵያ እናታችንን ከልጆቿ ጋራ ለማሳለፍ እንዴት ቀላል ነገር በሆን ይመስላችኋል፡አሁን ጊዜ የለንም፡እንዲህ ይሁን አይሁን እስክንል ድረስ መቀሠፍት የሆነ ምስጥ ፡ በሥር ሀሳባችንን እንዳያጠፉ እስራኤል በተነሱበት ቀን በተራቸውን በእጃቸው ይዘው መጪሚያቸውንም በእግራቸው አግብተው የሚገባቸውን ነገር አደረጉ ። በዚያን ጊዜ ያ የተሰጣቸው መሪ ያላቸውን ቃል ባያደርጉ ከባርነት ነፃ በወጡ ይመስላችኋልን።ምንም ቢሆን ነፃ ባልወጡም ነበር፡እንዲሁም እኛ አገራችንን አገራችን የምንል አንዳንድ አገር ማለት ምን እንዲሆን የማያውቁትን ለማስታወቅ አብነት እንዲሆንባቸው ያ የምንወደው ገንዘባችንን በመጀመሪያ ክንዳጋዱ ወር ጉልበታችን ክፍለን ብንሰጥ ዓይናችንን የዕውቀት ብርሃንን ከማየት ሸፍኖን ያለ የድንቁርና ጨለማ ጠላታችን ፈጥኖ በጠፋ።ባንዳንድ ልኳንዳ የሚጠፋው የኢትዮጵያ ገንዘብ ብናስበው እጅግ ብዙ ነው ። እንዴት ብሎ ይጠፋ እንዳለ ብናስበውም ይገርማል።መጀመሪያ በልኳንዳው የሚገባ ሰው ርቦት ሊበላ ነው የሚገባ።ኋላ ግን ያልታሰበ እነ አቶ እገሌ በዚያ ሲቆዩ ያ ሰው ባላሰበው እነሱ ከኛ አብልጦ ይበላል ይጠጣልም እንዳሉኝ ብሎ ውስኪ በሶዳ ምንትስ በምንትስ አምጣ ልዩ ልዩ የሆነውንም መብል አምጣ ብሎ ከትዕቢት የተነሳ ላንድ ወር የሚበቃው የነበረ ገንዘቡን ባንድ ሰዓት ጥሎት ይሄዳል ይህ ሁሉም እውቀት ከማጣት የተነሳ ነው ።

የኢትዮጵያ ገንዘብ የሚጠፋ ክብርህ ለሌላ እንዳትሰጥ ዕድሜህንም ለቄራጥ ሰው ።ሌሎች ከኃይልኽ እንዳይጸግቡ ድካምኽን ለሌላ ሰው ቤት እንዳይሆን የተባለውን ባለማወቅ ነው

እንግዲህ እኛ የኢትዮጵያ ልጆች ምኞታችን ስለደረሰልን የኢትዮጵያ አገሩን ወዳጅ የሆነ ሁሉ ሹምም ቢሆን ሎሌም ቢሆን እሥራኤል ከግብፅ ባርነት ነፃ በወጡበት ቀን እያንዳንዱ ነውር የሌለበት በግ እንዳረደ እኛም በሙሉ ፈቃድ ለአገራችን ጥቅም የሚሆነውን የትምህርት እርዳታ መስጠት የተገባን ነውና ነገሩን ስለወደድሁ የሚገባኝም ስለሆነ እንደ አቅሜ መግቢያ ፶ብር ባመት ባመት ፴ብር እሰጣለሁ መንገሻ ካፈላ።

በኢትዮጵያውያን ማኅበር ለሚቆመው ተማሪ ቤት እርዳታ እንሰጣለን ብለው ፈርማቸውን የሰጡ ሰዎች ።

ከ፳፫ኛ ቍጥር የመጣ ድምር	፪ሺ፪፻፺፮	ብር
ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ	፩ሺ	ብር
ደጃዝማች ገሡሡ ።	፶	ብር
ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ።	፴	ብር
ደጃዝማች እምሩ ኃይለ ሥላሴ ።	፳፰	ብር
ደጃዝማች ወልደ ሥላሴ ።	፳	ብር
ደጃዝማች ከበደ ጓንጉል ።	፳	ብር
ደጃዝማች ኃይሉ ከበደ ።	፳	ብር
ፊታውራሪ ደስታ ዳምጠው ።	፲፪	ብር
ቀኛዝማች ዓምዴ ።	፳	ብር
አዛዥ ፍቅረ ማርያም ።	፳	ብር
ቀኛዝማች ታደሰ ገነሜ ።	፳	ብር
አቶ ተክለ ማርቆስ ።	፲	ብር
ባላንባራስ ዘውዴ ።	፲	ብር
ባላንባራስ ለማ ይብሉ ።	፲	ብር
ባላንባራስ ኃይለ ማርያም ።	፲	ብር
አቶ ሀብተ ሥላሴ ሀብተ እንድርያስ	፲	ብር
አቶ በቀለ ደስታ ።	፭	ብር
ግራዝማች ክልክሉ ።	፲	ብር
አዛዥ ወልደ መድኅን ።	፭	ብር
መንገሻ ካፈላ መግቢያ ፶ ባመት ባመት	፴	ብር
አቶ እሸቱ ክንፌ ።	፫	ብር
የሻቃ መዘምር ኃይሉ ።	፲፭	ብር
ድምር	፫ሺ፮፻፶፬	ብር

የቴሌግራም ቃል።የሰኔ ፲፩ ቀን ፲፱፻፲፯ የለት ወሬ።

ሎንዶን፡ጃዋና ዋና የሽን መንግሥት ሥራ ፊፕሬዘንታንቶች ሺን በእንግሊዝ ላይ ጦርነት መፈለጓን አስታውቀዋል ብለው የጦር ሚኒስትሩን ለመኑት የሚል ከፐኪን የመጣ ቴሌግራም ከሻንጋይ ረውተር ተቀብሏል ። ምኒስትሩም ይህን ሲሆን የሽን በቅንነት አኑዋዋር ውጮች እንዲረዱ የባላባቶችን ለሸላምነትን መነሣሣት ቢሆን ነው የሚበልጥ እንጂ ፡ መንግሥት የሕዝቡን አንድነት ፈቃድ ባደረገ ነበር ።

የሰኔ ፲፪ ቀን የለት ወሬ ።

ኒዩ ዮርክ።(አሜሪክ) ሚሊዮኔር ዳኔሊ ጉጀንሄም በአየር ባቡር የሚሔዱ ተማሮች የሚማሩበትን ተማሪ ቤት በኒዩ ዮርክ ለማቆም አምስት መቶ ሺ ዶላር (ያሜሪክ ብር) ሰጠ ።

ሞስኮ፡(በመስኮብ) በአልታይ አገር ክፍል ብርቱ አውሎ ነፋስ ተነሥቶ ጉዳት ከደረሰበት አገር እስከሁን ድረስ ያገኘነው ወሬ ፳፰ ሙተዋል፤ብዙ ቈስለዋል ፪፴ ቤቶች ፈርሰዋል ፤ የባቡርና የቴሌግራም መመላለስ በዝነዋል ይላል ።

በልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

መጀመሯ ዓመት ፤ ቁጥር ፳፯ ።
1^re^ ANNÉE № 27

ሐሙስ ሰኔ ፳፭ ቀን ፲፱፻፲፯ ዓ ም ።
JEUDI 2 JUILLET 1925

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumiére et paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

የጋዜጣው ዲሬክተር ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ይስታወቁ ።
Gabré Christo Taklé Haymanot
Dirécteur

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የሰው ዋና ባላጋራው የሐኬት ኑሮ ነው ።

እንስሳ ሁሉ ሕይወታቸውን ለመጠበቅ ምግብ ለማግኘት ይጣጣራሉ ፤ ሰው ደግሞ ከእንስሶች ከፍ ያለ አእምሮና የበለጠ የእጅ ሥራ ስጦታ አለውና በበለጠ ለኑሮው ይጣጣራል የሥራውን መበላለጥና የአእምሮውን ከፍታ የሚመሰክሩልንም በየከተማው የቆሙ ትልልቅ ሕንፃና በያይነቱ፤የምድር ባቡር መርከብ የማያቋርጥ የትምርት እውቀትና ብልሃት ፤ የንግድ ሥራም ናቸው ። ሰው እውነተኛ ሰው ከሆነ የባልንጀራውን ደግ ኑሮ ያስባል እንጂ ለገዛ ራሱ ጥቅም ብቻ አያስብምና ። ትጉ የታመነ ብልህ ሰው የውሳጣዊ ሐሳቡ ፍሬ በልቡ ደግነት ያገኘውን ዕውቀትና መቻል ለጥቅም በማድረጉ ይገለጣል ።

ግን የማይሠሩ ሰዎች ስለሚገኙ የሚያሳዝን፤ነው ሐኬትና በዘንተኝነት ባሕርያቸውን አደፍርሶባቸዋል።ኃይላቸውንም አሽንፎ ሥራ እንደማይችሉና ይሉኝታ የሌላቸው አድርጓቸዋል ። ስለዚህ ከተ [illegible]

እንስሳት ሁሉ ምግባቸውን በልፋታቸው ያገኙታል በተለየም በትጋት ሥራቸው ለሰው አብነት መሆን የሚቻላቸው እንስሳት አሉ ። ባንድነት ይሄዳሉ ፤ ደግሞ ከገኙትም ምግብ ያስቀምጣሉ፡ ልጆቻቸውንም ሊነጥቅባቸው ከመጣው ይመከታሉ ልጆቻቸውንም በጥንቃቄ ያሳድጋሉ ። ልጆቻቸውን ከልክ ባለፈ ፍቅር ያፈቅራሉ ራሳቸውንም ከልቻሉ አይለዩዋቸውም ።

ብዙ ለኛ አብነት የሚሆኑና ትምርት የሚገኝባቸው ደግ ባሕሪ ያላቸው እንስሳት አሉ የብርታትና የሥራ አለማቋረጥ የትጋት ጥቅም በብዙ መንገድ ይገለጣል ግን የበለጠ በሰው ይገኛል ።

ሀኬተኞች የሆኑ ሁሉ ለኑሯቸውም የሚሆን ነገር ለመሥራት የማይጣጣሩ ይሉኝታቸው የሞተ ሰዎች ቢገኙ ከእንስሳ ዝቅ ያሉ ያሉ ይመስላሉ ።

እንተ ታከች ወደ ገብረ ጉንዳን ሒድ መንገዷን ተመልከት ጠቢብም ሁን ምሳሌ ፮ ቍ ፮ ።

የሀኬት ጉዳት የሚታወቅ የሥራም ጥቅም የሚገለጥ በትምርት ነው። እኛ ኢትዮጵያውያን ሀኬት የተባለ ዋና ባለጋራ እንዳይሰለጥንብን ያስፈራልና ፤ ይህንን ባለጋራችንን ተረዳድተን በትጋት የትምርት ጦር መሣሯ አበጅተን ድል ልናደርገው ይቻለናል ።

ሀኬት እስታለ ድረስ ምንም ነገር ሊቀና አይቻልም ። በሥጋዊም በመንፈሳዊም ሀኬት ወደጥፋት የሚጐትት ነውና ከሁን ጀምረን ብንቃወመውና ለሥራ ብንተጋ የምንፈልገውን ለማግኘት እግዚአብሔር ይረዳናል ።

ቀዳሚሃ ለጥበብ ፈሪሃ እግዚአብሔር ።

ለመንፈሳዊ ሀብትና ለሥጋዊ ሀብት እድል የሚሆን ራስ [illegible] ለሁ ብዬ ጀመርሁ ። እቤተ መንግሥት ገብቼ እንድሾምና እንድሸለም ብሎ ከስማተኛ ዘንድ ሄዶ ግርማ ሞገስና መስተፋቅር ስለሚፈልግ ሰው ። ሁለተኛም ጠላት ተንሥቶብኛልና ብሎ መድፍን ፀር ሴላም በያይነቱ ክታብ ስለሚፈልግ ሁሉ ረብህ ጥቅም እንደሌለው ይህ መጽሐፍ ይናገራል ። ግርማ ሞገስ ዓቃቤ ርእስ መስተፋቅር ማለት እግዚአብሔርን መውደድና የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መፈጸም ነው ። ትእዛዙም በይፈጸም ወይኩን ፈቃድከ እያሉ ማዘንና ጾም ጸሎት መያዝ ነው ። በዚሁም እግዚአብሔርን ከመውደዳቸው የተነሣ ከእግዚአብሔር ዘንድ ግርማና ፍቅር አግኝተው የተጠቀሙ ብዙ ሰዎች ናቸው ። እግዚአብሔርን በሚወድ ሰው ከፉ መከራ አይመጣበትም ቢመጣበትም ለመፈተን ነው እንጂ ለታገሠው ሰው ጥቅም አለበትና የቀቢጸ ተስፋ ኀዘን እንዳያገኘው ይሁን ። ብንጓጓም

ለማታልፈው ዓለም ይሁን እንጂ ለሐላፊው ዓለም አንጓጓ ። በሰዎቹ ሲያልፍ አይተናልና ። የዚህን ዓለም ብዕል ጌታችን ሳንለምነው ይሠጠናል ። ይህን ዓለም የፈጠረ ለኛ ነውና ። ሰው ሁሉ ሥራ ከያዘ እግዚአብሔር እንዲያስብለት ይወቅ ። ከዚህም ቀጥሎ የተጻፈው ራስ መጠበቂያ ትርጓሜው ይህ ነው እርምሞ ። ትእግሥት ። አነጋገር ። አካሄድ ። አስተያየት ። ሳይጠይቁት አለመመለስ ። በልክ መብላት መጠጣት ነው ። ከዚህ ውስጥ ቢመረምሩት ለነፍስና ለሥጋ የሚሆን ጥቅም ይገኝበታል ። በዚህም መጻሕፍት ተባብረውበታል ። ዘሰ ርእያ ለብእሲት ወፈተዋ ወድአ ዘመወ ባቲ በልቡ ይላል ። እስመ እምቃልከ ትጸድቅ ወእምቃልከ ትትኴነን ይላል ። ብፁዕ ብእሲ ዘኢሖረ በምክረ ረሲዓን ወዘኢቆመ ውስተ ፍኖተ ኃጥአን ይላል በአነጋገርህ የተነሣ ትከብራለህና ። በአነጋገርህ የተነሣ ይፈረድብሀልና ነው ። በአነጋገር የተነሣ ከብረው የሚኖሩ ብዙ ሰዎች አሉ ። ደግሞ በክፉ አነጋገር የተነሣ ባደባባይ ቅጣት እየተፈረደባቸው ተዋርደው የሚኖሩ ብዙ ሰዎች አሉ ። ከካሄድም የተነሣ ብዙ የተዋረዱ ሰዎች አሉ ። ከሌባ ከወንበዴ ጋራ አብረው ሄደው ። ደግሞም እመሸታ ቤትና እሸርሙጣ ቤት ገብተው አንባጓሮ አንሥተው ተጋድለው ባደባባይ ሞት የተፈረደባቸው ናቸው ። ደግሞ በጎ አካሄድ ማለት ቤተ እግዚአብሔር እጅ ለመንሣት ከመምረ ንስሐ ዘንድ ሂዶ የተሠራ ኃጢአት ተናግሮ ይፍቱኝ ብሎ ሥርዓት ለመቀበል ቃለ እግዚአብሔር ከሚነገርበት ቦታ መስማት ቤተ መንግሥት ደጅ ጥናት አደባባይ ሂዶ የሚፈርደውን ፍርድ መስማት የመንግሥት አዋጅ መጠበቅ ነው የመንግሥትም አዋጅ መጠበቅ ራስን መጠበቅ ነው መንግሥት በየጊዜው አዋጅ መንገሩ ለደህውና ለሕዝቡ ሲል ነውና ። ደግሞ ከመኝታህ ተነሥተህ ለመብላትና ለመጠጣት አትዘጋጅ በሰላም ያዋለህንና በሰላም ያሳደረህን እግዚአብሔርን አመስግነህ ቤተ እግዚአብሔር እጅ ነሥተህ ይሁን እንጅ ። ነገር ግን ያለንበት ቦታ እገደል አፋፍ ነውና ለዚህ ለገደሉ ድልድይ እንሥራለት ድልድይም ማለት ንስሐ መግባትና ሥጋው ደሙን መቀበል ነው በድንገት እንዳንወድቅ በዚህ ዓለም ክፉ ሞትና በጎ ሞት አለ ። ክፉ ሞት በኃጢአት ሳሉ በድንገት መሞት ነው ። በጎ ሞት ንስሐ ገብቶ ሥጋው ደሙን ተቀብሎ መሞት ነው ። ደግሞ ምንም ቢሆን ከመሸታና ከሻርሙጣ ቤት ቤትግል ያገባህ ያልሆንክ እንደሆነ ግን በመሸታ ፍቅርና በሸርሙጣዋ ፍቅር ይቆራኙሃና እሷን እሷን እያሰኙ የኋላ ኋላ ከጥፋት ያደርሱሀል ። ገንዘብህም በማይረባ ጠፍቶ አንተም ደህይተህ ያስፈርዱብሀል ልቀቁኝም ብትላቸው በጅ አይሉህም የመሸታ ቤት አጋንንት ሰውን ሁሉ ተቆራኝተው መሸታና ሸርሙጣ ስለማስወደድ መክንያት ብዙ አጥፍተዋልና ነው ። ሰዎቹም ወደሞት ስንቱ እየተፈረደባቸው ሄዱ ። አንተ ግን ከዕለታት አንድ ቀን መጠጥ ቢአምርህ አቤትህ ሁነህ የማያሰክር መጠጥ ጠጣ ። ሁለተኛ ቀን ግን እንደዚሁ ላድርግ ብትል ከገንቦው ጋራ አጋንንት ተቆራኝተው መጥተው ነውና ሚስትህ ትቆጣህ አጋንንትም ደንግጠው ይበሩልሀል አንተም ባለ አእምሮ ትሆናለህ ። ባለፈውም ኃጢአታችን ሰማያዊ አባታችን ይቅር ይበለን ወይሥረይ ለነ ኃጣውኢነ ።

ቀለመ ወርቅ ስመኝ።

ስለ ብርሃንና ሰላም ።

አንዱ ወንድሜ ስለእንግድነቴ ተቀብሎኝ ተቀምጠን ስንጨዋወት ልዑል አልጋ ወራሽ በተመሰገነ ሐሳባቸው አሁን ለኢትዮጵያ ጥቅም ብርሃንና ሰላም ብለው ስም ያወጡለትን በስምንት በስምንት ቀን እየታተመ የሚወጣውን ጋዜጣ ላንብብልህ ብሎ ባነበበልኝ ጊዜ በጣሙ ደስ አለኝ ።

አንደኛው ደስታዬ እግዚአብሔር ለኢትዮጵያ በቸርነቱ አስበ ተፈሪ መኰንንን ትክክል የወርቅ ሚዛን ዳኛ ስለሰጠን ነው ። ሁለተኛው ደስታዬ የኢትዮጵያ ልጆች በልባቸው ውስጥ የብርሃን ጉርፍ የውቀት ምንጭ ሲፈላ ኖሮ አሁን ፈልቆ ለየወንድሞቻቸው የውቀት መክፈቻ ስለሆነ ነው ።

ደግሞ በጨለማ ከመኖር በብርሃን መኖር ማለት ከገጠር በከተማ ትርጓሜው ። ከድንቁርና ዕውቀት ከስንፍና ትጋት እመርጣለሁ ፣ ስለሆነ ይህ የሁሉም ሐሳብ ነው እንግዴህ ደስታዬ ተፈጸመ ። አሁንም እግዚአብሔር ይመስገን ብርሃንና ሰላም የሚያመጣውን ጥዑም ቃል እያየሁ ወደፊት ለመጻፍ ተስፋ አለኝ፡፡ደግሞ በኢትዮጵያ ማኅበር ስለሚቆመው ተማሪ ቤት እርዳታ፡፡በሐገራችን በኢትዮጵያ አንድ ነገር አለ እንደምን ማለት ። አንዲት እመበለት በግዕዝ ቋንቋ ዕቤርት እጓለ ማውታ ይላታል ሴትኛ አዳሪ ችግረኛ ማለት ነው ። ቢሳሳተኝም ብርሃንና ሰላም ያቃናልኝ ። ላንድ ጻድቅ ወይም ለመላእክት ባመት ባመቱ ለምኜ እዘክርሃለሁ ብላ ትሳላለች እስከ ጊዜ ሞቷ አትለቅም ። ስእታዋን ይዛ ዘንጓን ተመርኩዛ ፤ ባመት ባመቱ እየለመነች ስታዘክር ትኖራለች ። ስለቷን አታስታጉልም ከብቱ በጋጣ ብሩ በሳጥን እህሉ በጎተራ ቢሞላ ምንም ቢተርፋት ለዝክሩ ጊዜ ልመናዋ አይቀርም ። ምነው ገንዘብ ሞልቶሽ ትለምኛለሽ ያሏት እንደሆነ ። ገንዘብስ ሞልቶኛል ነገር ግን እኔ የተሳልኩት ባመት ባመቱ ለምኜ ልዘክር ነው ከቤቴ አውጥቼ የደገስሁ እንደሆነ ስለኩራት ያደርግብኝና ጻድቁ ወይም መልአኩ ዝክሩን አይቀበለውም ብዬ ነው ትላለች ። እስቲ እባካችሁ ይህን ርቀት እንመልከተው ያች እመበለት በልቧ አስባ ምንም ሳታፍር እንደዚህ ያለድካም ስትደክምይህማ ኢትዮጵያ ስትቀደስ ባይኑ እያየ በልቡ እየተረዳ እየለመነስ ቢሆን ለማኅበሩ ደምብ የማይከፍል ሰው ይገኝ አይመስለኝም፡አሁንም እኔ መንግሥተ ሰማያትን ለማግኘት ተስፋ [illegible] ዘኢትዮጵያ የሚከፈተውን የተማሪ ቤት ብርሃን ለማየት ተስፋ አለኝና ፤ እንዳቅሜ አምስት ብር እሰጣለሁ ። እግዚአብሔር በጀመረው ምሕረት ኢትዮጵያን ይቀድስልን።ብርሃንንና ሰላምን ማውጣቱ የመቀደሷ ወራት ቢሆን ነው ፤

መክብብ ደስታ ።

የጥያቄ ምላሽ ።

ብርሃንና ሰላምን ለመቀበል ወደ ክቡር አቶ ገብረ ክርስቶስ በጻፍኩ ጊዜ በሀገራችን እየተጀመረ የቀረው ሥራ ብዙ ነውና የብርሃንና ሰላም መታተም ተጀምሮ እንዳይቀር ይበርቱበት ብዬ ቲንሽ ምክር ቃል ጽፌ ነበረ። አሁን ፳፮ተኛው ቀጥር ነጋድራስ አስታጥቄ በሀገራችን እየተጀመረ የቀረው ሥራ ብዙ ነው ብለው በሶስትያ ቁጥር ብርሃንና ሰላም ጽፈው ነበር አሁን ወደርሳቸው መልሰን እንጠይቃለን ባገራችን ብዙ ሥራ

እየተጀመረ መቅረቱ በምን ምክንያት ነው።ደግሞ በሀገራችን ደግ ሥራ እየተጀመረ ወደ ፊት ሊገፋ እንጂ ተጀምሮ እንዳይቀር ምን ማድረግ ያስፈልገናል የሚል ቃል ተጽፎ አየሁ ይህም እጅግ የሚያስደንቅ ጥያቄ ነው።ነገር ግን ሰው በተጠየቀ ጊዜ የሚመስለውን መናገር ይገባዋል።ስለዚሁም ጥያቄ እንደኔ ሀሳብ ሥራ ሁሉ እየተጀመረ መቅረቱ እንደሚገባ ሳይጀመር እየቀረ ይሆናል ይመስለኛል ። እንደሚገባ ሳይጀመር ማለት ሰው ያልተማረውንና ያለመደውን ሥራ ጀምሮ መጨረስ አይቻለውም ማለት ነው ። ሰው ማናቸውን ሥራ ሳይማረው ሊሰራው ይችላል ወይስ ያለትምህርት ምን ሥራ ለመሥራት ይቻላል ። ሥራ ሁሉ የለመደውንና የተማረውን ይፈልጋል ።በሀገራችን እየተጀመረ የቀረው ሥራ ሁሉ በትምህርት የሚገኘው የሥራ መውደድ ዕውቀት ስላነሰ ይመስላል።ደግሞ በሀገራችን ደግ ሥራ እየተጀመረ ወደ ፊት ሊገፋ እንጂ ተጀምሮ እንዳይቀር ምን ማድረግ ያስፈልጋል ለተባለውም ጥያቄ ፤ በሀገራችን ብዙ ተማሪ ቤት መክፈትና ልጅ ልጁ ሁሉ እንዲማር ማድረግ ነው የሚያስፈልገው ሁሉ የተማረ ሲሆን የሀገራችን ሥራ የተጀመረውም እየተፈጸመ ፍጻሜውም እያማረ ወደፊት የሚገፋ ይሆናል ። በኤውሮጳ እንደምናየው ስንኳን የተጀመረው ሥራ ሳይፈጸም ሊቀር ሥራው ሁሉ ተይዞ ለሕዝቡ ሳይበቃ እየቀረ ብዙ ትምሕርት ያላቸው ሰዎች ሥራ እያጡ ይቸገራሉ።ነገር ግን ትምሕርታቸው ይረዳቸዋልና አዲስ የበለጠ ሥራ እየመረመሩ እያወጡ እራሳቸውንም ሀገራቸውንም ያከብራሉ ይረዳሉ ይህም የሚገኘው በትምሕርት ነው ።

የተማሪ ቤትም መከፈት ለሀገራችን የሚያስፈልግ መሆኑን አስበው ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ለቋንቋ ለሒሳብ ለጅግራፊ ለዓለም ታሪክ ለእጅም ሥራ ሁሉ መማሪ የሚበቃ ማለት መጋርመሻ ለሕዝብ ትምሕርት የሚያስፈልገውን ተማሪ ቤት በሐረርጌ በአዲስ አበባ በአንኮበር በደሴ አቆሙ።ደግሞ እንዲሁ በየአውራጃው ሁሉ ተማሪ ቤት ሊከፈት ሳለ ጃንሆይ ከቤት ቢውሉ ሁሉም ቀረ ።

አሁንም ልዑል አልጋ ወራሽ ይህን ጃንሆይ የጀመሩትን ለመፈጸም እስከ ዘለዓለም በብዙ ምስጋና ስም የሚያስጠራ ሥራ በራሳቸው ገንዘብ ትልቅ ተማሪ ቤት አሰርተው አቆሙ። ይህም ሥራ ለሀገር መቅናትና ለሕዝብ መሰልጠን ዋነኛው መሠረት ነው ። ኢየሱስ ክርስቶስ ዓለምን ለማዳን መከራ መቀበሉ መሰቀሉ መሞቱ ለአርአያ ለቤዛ ነው ። በሥራችሁም ሁሉ እኔን ምሰሉ ሲል ነው ። ልዑል አልጋ ወራሽም ይህን ተማሪ ቤት ስላቆሙ በሀገራችን በየአውራጃው ላሉ መሣፍንት መኳንንት አርአያ ቤዛ ሁነዋልና ሀገር እንዲቀና ሕዝብ እንዲሰለጥን እንደዚሁ ልዑል አልጋ ወራሽ እንደሚሰሩት ። ጌታ በሥራችሁ ሁሉ እኔን ምሰሉ እንዳለ መሣፍንቱ መኳንንቱ በሥራቸው ሁሉ ልዑል አልጋ ወራሽን መስለው በየግዛታቸው እንደሚበቃ ተማሪ ቤት ማቆም ይገባቸዋል ። ይህም ሥራ ለሀገራችን መኳንንትና መሣፍንት በወዲህኛውም በወዲያኛውም ዓለም ክብር የሚያሰጥ ሥራ ነው ። በሀገራችን ያለ ጋላ ሻንቅላ ጊሚራ ወደአምልኮተ እግዚአብሔር ተመልሶ መንፈሳዊ ሥጋዊ ትምርት ቢማር በነፍሱም በሥጋውም ተጠቅሞ ሀገሩንም ራሱንም የሚረዳ ነውና እንደዚህ ያለውን ሕዝብ እንዲማር ለሚያደርጉ ጌቶች እግዚአብሔር የክብር ክብር እንዲሰጣቸው አውቀው ይበርቱበት ። በመጻሕፍትም ካሉት ትእዛዛት መጀመሪያው ኢታምልክ ባዕደ ነው ። ሁለተኛውም አፍቅር ቢጸከ ከመ ነፍስከ ነው የቀሩት ትእዛዛት ሁሉ እነዚህን ሁለቱን በመፈጸም ይገኛሉ ። የሀገራችንም መቅናትና ወደፊት መቅደም ሥራ ከዚህ ቀጥሎ በተጻፉት በሁለቱ ሥራዎች አገባብ ይገኛል አሁን በመጀመሪያ በመላው ኢትዮጵያ ያለ የባላገር ግብር ልክ ባለው ነገር ተወስኖ ይህንኑ የተወሰነውን ግብር ባመት ከሚከፍል በቀር በዚሁ ግብር ምክንያት ጧትና ማታ ከመታሰር ሕዝቡ ነፃነት እንዲያገኝ ማድረግ እንደኢታምልክ ባዕደ እንደ መጀመሪያው ትእዛዝ ያለ ነው ።

ሁለትያ የስድስት ዓመት ልጅ ሁሉ ሴትም ወንድም ማንበብ መጻፍ ሒሳብም የዓለም ታሪክ የእጅም ሥራ ማለት የሕዝብ የመጀመሪያ ትምሕርት እንዲማር የጠበቀ አዋጅ ተደርጎ የግድ ተማሪቤት ማቆምና ለዚሁ ተማሪቤት የሚያስፈልጉትን መጻሕፍት ባማርኛ አሳትሞ በየአውራጃው ላሉ ሹማምንት ተልከላቸው ይህ ሥራ በቶሎ ቢጀመር አፍቅር ቢጸከ እንደሚለው እንደሁለትያው ትእዛዝ ያለ ነው ፡፡ በነዚህ በሁለቱ ሥራዎች የሃገራችን መቅናትና መሰልጠን በፍጥነት ይገኛል ። አስተምሃሪም እንዳይቸግር በብርታታቸው እራሳቸውን እየረዱ ብዙ ትምሕርት ብዙ ዕውቀት ብዙ ምርምር ያተረፉ የሃገራችን ሰዎች ለሃገራቸው ለማገልገልና ለመርዳት ፈቃድ ያላቸው ብዙ ይገኛሉ በየአውራጃው እየተላኩ ቢያስተምሩ ይህ በቋንቋ የተለያየ የሃገራችን ሕዝብ በማንበብ በመጻፍ ሰልጥኖ የሃገራችን ቋንቋ አንድ አማርኛ ብቻ ሆኖ ሕዝቡም አንድ ልብ ሆኖ ተስማምቶ ሃገሩን እየጠበቀና እየረዳ ለመኖር የሚበቃ ይሆናል ። እነዚህም አስተማሮች ሥጋዊውን ትምሕርት ያስተምራሉ እንጂ መንፈሳዊውን ትምሕርት ባውራጃው ያለ የመቅደሱ አለቃ ወይም መሬጌታው ማስተማር አለበት ። የመቅደስም አለቃ መሆን ለማስተማር ነው።ለዚሁም ተማሪቤት የሚያስፈልገውን ገንዘብ ሕዝቡ ለማውጣት አይሰንፍም ። ይህ ልጅ ልጁ ሕዝብ ሁሉ ይህን መጀመሪያ የሚያስፈልገውን ትምሕርት ከተማረ በኋላ ከፍ ላለው ትምሕርት ከፍ ያለ ተማሪቤት (ኡንቤረዚቲ) መንግሥት ቢያቆም ከዚያ እየመጣ ይማራል ።

ነገር ግን የኢትዮጵያን ሕዝብ የመበለ ትምሕርት የሚገባውና የሚስማማው እውቀቱን የሚገልጽለት ተማሪ ቤት ቢያገኝ በእውቀት መሰልጠንን በፍጥነት ገንዘብ አድርጎ መገኘቱ የማይጠረጠር ነው ። እግዚአብሔር ጌቶቻችንን በሕይወት ያኑርልን እንጂ እንዲህ እንዳሁኑ እንደመንግሥቱ ሥራ በመልካም አካሄድ ሃገራችን በፍጥነት ለመሰልጠኑ ሙሉ ተስፋ አለን ። ደግሞ ስለሃገር መክበር ዋነኛው ሥራ የአትክልትና የማዕድን ሥራ ነው ። በሃገራችን አትክልትም ይሆናል ። ማዕድንም በብዙ ይገኛል ወርቅ ብር ጋዝ ባዜቃ መዳብ ብረት ሚካ እርሳስ ይህን የመሰለ ሁሉ በብዙ ይገኛል ። ይህን የመሰለ ኃብት ጌትነት ከመሬት ወጥቶ ሥራ ቢሠራበት ነው እንጂ ተቀብሮ ቢቀር ጥቅማችን ምንድር ነው በዚሁ ሥራ መንግሥት ያቆመው ሰራተኛ ይህን የማዕድን ሥራ አነቃቅቶ ከመሬት እንዲወጣ ማድረግ ይገባዋል ።

ነገሥታቱ የመንግሥቱ ሥራ ሁሉ በትክክል እንዲሰራላቸው ይሾማሉ ይሸልማሉ፤እነሱም እራሳቸው አሁን እንደምናየው ስለ ሕዝባቸውና ስለ ሀገራቸው ጥቅም በብዙ ትጋትና ብርታት የሚሠሩት ሥራ እጅግ የሚያስደንቅ ነው የመንግሥቱ ሥራ ሁሉ በብዙ ጥንቃቄና በብዙ ትጋት መስራት ተይዟል ነገር ግን በማእድኑ ክፍል ሥራ በድሬዳዋ አውራጃ አንድ የሚካ ሥራ ተዠምሯል ሲሉ እንሰማለን እንጂ በሌላ ስፍራ የማእድን ሥራ ይሠራል የሚሉ አልሰማንም በዚህ ሥራ መጉደል የሀገር ኃብትና ጌትነት ተቀብሮ መቅረቱ ነው ። ይህም የማዕድን ሥራ በብዙ ሊታሰብበት ይገባል ።

ደግሞ ዋና የሀገር መከበር ጥጥ መዝራት ቡን መትከል ሸንከራ አገዳ መትከል ሱፍና ተልባ መዝራት ተልባው ለዘይቱ ብቻ አይደለም ጭረቱ ለልብስ ያማረ ይሆናል፤ ወይራ ስለዘይቱ መትከል ወይም በሀገራችን ያለውን ወይራ ከኤሮጳ መልካሙን የወይራ ዠሮ አስመጥቶ መከተብ ወይን መትከል የዝባድ ድመት ማርባት ንብ ማርባት የሃር ትል ማርባት ላስቲክ ማውጣት ይህ ሁሉ በሀገራችን ለመሥራት የሚቻል ነው ለዚህ ሁሉ ለየአንድአንዱ ሥራ አንድ አንድ ሠራተኛ መንግሥት የሥራውን አካሄድ ደምብ ሰጥቶ ቢያቆምበት የሀገራችን መከበር በቶሎ ይገኝ ነበር ሀገር የሚከብረው ከሀገር እየወጣ የሚሸጥ እቃ እየበዛና ከውጭ ወደ ሀገር የሚገባው እቃ ሲያንስ ነው ። በሀገራችን ቡን ቆዳ ዝባድ የዝሆን ጥርስ ሰም እየወጣ ወደውጭ አገር ይሸጣል ግን በዚህ በሀገራችን እቃ ሽያጭ ያገኘነው ገንዘብ ከውጭ ወደሀገራችን በሚገባው ባቡገዲ በቆጫ በድር በማናቸውም ይህን በመሰለ በባሕር እቃ ዋጋ ተመልሶ ይወጣል

ስለዚህ በሀገራችን ጥጥ በብዙ ተዘርቶ በልብስ ራሳችንን ችለን ከውጭ የሚመጣው ልብስ የማያስፈልገን ቢሆን ገንዘባችን ተመልሶ ወደ ውጭ አይወጣምና ሀገራችን በቶሎ ይከብራል ። ከማዕድኑ ሥራ በቀር ከዚህ በላይ እንደ ተጻፈው ያትክልቱ ሥራ በጥቂት በጥቂት መሠራቱ አልቀረም ። ነገር ግን ድካሙ ላልቀረ ጥቅሙ ብዙ አይደለም ። ምክንያቱም ጥቅም እንደሚገኝበት የሚያሳይና የሚያስተምር ሠራተኛ በዚሁ ሥራ ላይ ስላልቆመበት ነው ። በዓለም ላይ ሁሉ የአትክልትም የሌላም ሥራ ሆነ ብዙ የፍልስፍናና የጥበብ ሥራ እየተጨመረበት ጥቅሙም እጥፍ እየሆነ ይሠራል እንጂ የብልሃት ሥራ ሳይጨመርበት በባሕርዩ እንደሚገኘው ብቻ ብዙ ጥቅም የሚሰጥ አትክልትም ሌላም ሥራ ሆነ አይገኝም ለዚሁም አትክልት ሥራ ትምርት ያለው ኤሮጳዊ አስመጥቶ ተማሪ ቤት እንዲቆምና የሀገራችን ሰዎች ተምረው እነዚሁ የተማሩት በያውራጃው እየሄዱ እንዲያስተምሩ ማድረግ የሚያስፈልግ ነው ። ለነገሩ ሁሉ ፍጻሜ ተማሪ ቤት ትምሕርት ነውና ለዚሁ ለሀገራችን ለመልካሙ ሥራ ሁሉ መፈጸምና መከናወን እግዚአብሔር ፈቃዱ ይሁን ። አሁንም ለሚቆም የኢትዮጵያውያን ማኅበር ተማሪ ቤት እርዳታ አምሳ ብር እሰጣለሁ ። ነጋድራስ እስታጥቄ ሀብተ ወልድ ።

ለተማሪ ቤቱ እርዳታ ማስፈረሚያ ወረቀት የሚፈልግ ሰው ከልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት እየመጣ ሊወስድ ይችላል ።

በኢትዮጵያውያን ማኅበር ለሚቆመው ተማሪ ቤት እርዳታ እንሰጣለን ብለው ፈርማቸውን የሰጡ ሰዎች ።

ከ፳፯ኛ ቍጥር የመጣ ድምር	፩ሺ፻፷፬	ብር
አቶ ማህሌ ፀዳሉ ።	፻	ብር
ነጋድራስ እስታጥቄ	፶	ብር
አቶ ሚካኤል ብሩ ።	፻	ብር
ግራዝማች ወልደ ዮሐንስ ወልደአብ ።	፲	ብር
አቶ መክብብ ደስታ ።	፭	ብር
ግራዝማች ተስፋዬ ።	፲	ብር
አቶ ተአውቀ ሃብተወልድ ።	፳	ብር
እንድርያስ ክለሜንት ።	፲	ብር
አቶ ኃይለ ጊዮርጊስ ።	፲	ብር
አቶ ተክለ ሚካኤል ።	፴	ብር
ድምር	፩ሺ፭፻፱	ብር

ቴሌግራም ። ሰኔ ፲፯ ቀን ፲፱፻፲፯ የለት ወሬ።

ፕራጋ ። ቾኮስሎቫክ በአሪዮናውቲክ በሆነ ነገር አስቀድሞ ከኢጣልያ ጋራ ለመከራከር ተሰናድቶ እንዳለ ያስታውቃል ።

በልግራድ ። ፓስኪን ይሻሉዋል ።

ፒሳ (ኢጣልያ ፤) ንጉሥና ፕሪንስስ ማፋልዳም ጆባናም ወዲህ ደርሰው ባውቶሞቢል ሳን ሮሰሬ ወደሚባል አልፈዋል

ፓሪስ ። መሊከ ከሚባል የከፍቱን አገር ክፍል አንዳንድ የሚና ሠራተኞች ከ፫ ሜትር እስከ ፫ ሜትር ከ፳ ሳንቲመትር የሚያህል ርዝመታቸው የረጅሞች ሰዎች አስከሬን አግኝተዋል ብለው ያወራሉ ።

ክስታንቲኖፖሊ ። የኮስትናባል ፕሬፌት የማህበርተኞች መርከቦች ነጆዎችን በዝሮሮ ከሚባል ትልቅ ሆቴል እራት ጋበዛቸው ።

ሪጋ ። በሰኔ ፲፰ የኢጣልያ መርከቦች አንድ ክፍል ከሰቤት (መስከፍ) ውሆች ይቈያሉ ።

ፌዝ ። ከሊፋ ሱልጣን የሚባል የፌዝ መንዚፍ (ሹመኛ) ያሁኑ ሱልጣን ወንድም ጤናን ባለማግኘቱ ምክንያት ሹመቱን ባለቤቱ ለቆዋልና ፤ ሱልጣን ሞላይ ማህሙድ የሚባል ወንድም ተተክቶዋል ።

ፓሪስ ። ፪የሚያህሉ የቺና ሰዎች ኮምኒስቲ ነን አሰኝተው የቺናው ሌጋሲዮንን ዘምተው የሻንጋይ ሽፍቶች የሚል ባለቤታቸው የጻፉትን ብዙ ወረቀት በሞት እያስፈራሩ የቺናውን ምኒስቴር በግድ አስፈረሙት ። ፈታኞቹ ነገሩን ደረሳቸውና ብቻ ሽፍቶቹ ከሸሹ ወዲያ ባጠገብ የነበሩቱ መጡ ። አንድ ሰው ብቻ ይዘዋል ። ምርማሪ ተጀምሮዋል ።

ሮማ ። ዛሬ አውግሥትዮ ከሚባል ሥፍራ በደቦኪዳኝነት ሁለት የፋሺስቲ ጉባዔ ተደርገዋል ፤

ፌዝ ፤ ኤውታን በሚባል በሰሜኑ እኵል ሁነው የሚዋጉ ያሉ ጭፍራ ፤ ራውነስ ከሚባል የነበሩት ጠላቶች በጭራሽ አባረሩዋቸው ። ጠላቱ በኒ መስኩልዳ ከሚባል መሬት በጣም ወደ ኋላ አፈግፍጎ ሲያበቃ ያደረጉት ቁም ነገር የለም እንጂ ባጠገብ ያሉቱ ያገር ሹማምቶች ይሰበሰባሉ ።

በልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

መጀመሪያ ዓመት ፡ ቁጥር ፳፰ ።
1 re ANNÉE № 28

ሐሙስ ሐምሌ ፪ ቀን ፲፱፻፲፯ ዓ ም ።
JEUDI 9 JUILLET 1925

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

የጋዜጣው ዲሬክተር ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።
Gabré Christo Taklé Haymanot
Dirécteur

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሲገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

መልካም አሳብን ስለመከተል ።

ኢትዮጵያ አገራችን በቀኝና በግራ ካሉት አገሮች ይልቅ በጣም ያመረችና የዘሩባትን ሁሉ የምታበቅል ለስላሳ መሬት እንደሆነች የታወቀ ነው ። የፊተኞች አባቶቻችን ለስላሳ መሆንዋን አይተው ብዙ የሚአስቸግር አረም እንድታበቅል ሳያስተውሉ ዘራቸውን ዘሩ ፤ ከነሱ በኋላ የተነሱት ግን ብዙ እሾህና አረም ቢያዩባት እንነቅላለን ብለው ታገሉ ። ስራው በጥቂት ሰዎች ተሰርቶ የማይፈጸም ስለሆነ ደክመው ተውት ፤ ከነሱ በኋላም የተነሱ ሰዎች እሾህና አረም መንገዱን በጣም አልደፈኑውምና እኛን በደህና ካሳለፉን ለሌሎች ምን ያደክመናል ብለው ትተውት አለፉ ፤ ቀጥለውም የተነሱ ይህን ክፉ እሾህ ነቅለን እንጥላለን ብለው በኃይል ጀመሩት ፤ እሾህ ግን ያለ ብዙ ጥበብ በኃይል ብቻ አይነቀልምና አሸንፎ ቀረ ፤ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት አጤ ምኒልክ ግን ምንም እንኳ ብቻቸውን ቢሆኑ እንደተቻላቸው እሾሁን ነቅለው መልካም አድርገው መስርተው መንገዱን በትክክል አዘጋጅተው ሠራዊቱ በተደለደለው መንገድ እንዲሔድ አደረጉ ፤ ልዑል አልጋ ወራሽም በቀኝና በግራ ያሉ ጕረቤቶቹ ባንድ አሳብና ባንድ ልብ ተጋግዘው ላገራቸውና ለሕዝባቸው የሚጠቅም ሥራ እንዳዘጋጁ አይተው እንደጕረቤቶቹ ለማድረግ በሙሉ ኃይላቸው ሥራቸውን ጀምረዋል እኛም ለሀገራቸው የሚያስቡትን ፍጹም አሳባቸውን ተከትለን ባንድ ልብ ያለመጠራጠርና ያለ መለያየት ተግተን መሥራት ይገባናል ። ጊዜውና ሰዓቱ ሳያልፍብን ፡ ምሳሌ ፤ አንድ ሃብታም ሰው ከደባባይ ወጥቶ ዛሬ በዚህ ሰዓት ወደኔ ቤት የሚመጣ ብር በከንቱ እሰጣለሁ ብሎ ድምፁን ከፍ አድርጎ ለሁሉ አሰምቶ ተናግሮ ወደቤቱ ሄደ ። ከሰሙት ሰዎች እኵሌቶቹ ሰዓቱን ጠብቀው ሔደው ደጅ መቱ ፤ ባለቤቱ በቀጠረው ሰዓት ለመጡ ሰዎች ከገንዘቡ እንደ ሚያስፈልጋቸውና እንደሚገባቸው ሰጣቸውና ወደቤታቸው ሲመለሱ ጕረቤቶቻቸው ወዴት ሄዳችሁ ነበር አሏቸው ፤ ቀድሞ ከተናገረው ሰው ዘንድ ሒደን ብር ይዘን መጣን አሉ ። እነሱም ሊቀልድ ነው ገንዘቡን በከንቱ አይሰጥም ብለን ተጠራጥረን ነው እንጂ መች እንቀር ነበር አሉና ድንገት ብናገኝ እንሂድ ብለው ሔደው ሳንቃ ይመቱ ጀመረ ፤ ባለቤቱም ከቤት ብቅ ብሎ ምን ሰዎች ናችሁ አላቸው ሰዎቹም ብር ፍለጋ የመጣን ነን አሉት ባለቤቱም ምነው ሰዓቱን አልሰማችሁምን ? አላቸው ሰዎቹም መስማትስ ሰምተናል ገንዘብህን በከንቱ አትሰጥም ብለን ተጠራጥረን ነው እንጂ አሉት ባለቤቱም ገንዘብስ መልቷል ግን ተጠራጣሮች ምንም አያገኙምና ልሰጣችሁ አልወድም ደግሞ ሰዓቱ ካለፈ ደጅ ለመክፈት አይመቸኝም ብሎ ሳንቃውን አጥብቆ ዘግቶ እቤቱ ገባ ፤ ሰዎችም ያላንዳች ተስፋ በውጭ ቆመው ቀሩ ። ስለ [illegible] ለሕዝቡ ጥቅም ለሚደክም ሁሉ ያ ጻድቅ ፈራጅ ዋጋውን እንዲሰጠው የታወቀ ነው ።

ስለ ብርሃንና ሰላም ።

ብናገኝ መልካም ነው የውቀት ጥበብን ።
ርምጃ ማሳመር ማቅናት መንገድን
ሃይለኛ ሳይመጣ ጥቃት ሳይዘን ።
ንሯል እንዳንሆን የቀልገ ሳይ ጉንፋን ።
ናዕውቀትን ቅረባት ትስጥህ ሕይወትን ።
ሰውን ሰው ቢመክረው ተግቶ በየለት
ላገሩ ጥቅም ነው ለሕዝቡም ብልሃት ።
ምሕረትም ይገኛል ባምላክ ቸርነት ።

ቄስ ባድማ ያለው ።

ስለ ተማሪ ቤት ።

ክቡር ኢትዮጵያዊ ሆይ በእግዚአብሔር ረዳትና በልዑል አልጋ ወራሻችን ብርታት በዚህ ዓመት ለዚያ በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ ምኒልክ ላቆሙት ተማሪ ቤት ሁለተኛ ተማሪ ቤት ባገራችን እንደቆመልን ስላየን እጅግ ደስ ሊለን ይገባናል፤እግዚአብሔርን በሙሉ ልባችን እናመሰግነዋለን

እንዲሁም አገራችን እየሠለጠነና እየበረታ እንዲሄድልን አብረን ዕድሜ ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታታችንና ለልዑል አልጋ ወራሻችን እንበል ። ደግሞ እነሱ የጀመሩልንን ምሳሌ ልንከተል ይገባናል ። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከቅድስት ማርያም ድንግል ተወልዶ ኃጢአት ሳይሠራ ስለኛ መከራና ሞት እንደ ወረደበት እንዲሁም እነሱ ስለ ኢትዮጵያና ስለልጆችዋ ብዙ ሸክምና መከራ እንዳላቸው አንርሳ ። እንግድያስ ክቡር ኢትዮጵያዊ ሆይ እኛ ደግሞ እያንዳንዳችን እንደ አቅማችን አገራችንን ለመርዳት እንንቃ፤አሁን የመኝታ ጊዜ አይደለም እናታችን የልጆችዋን ብርታትና ፍቅር ለማየት ትናፈቃለችና አሁን ቶሎ እናሳያት ።

ከዚህ ቀድሞ ብዙ የኢትዮጵያ ልጆች አገራቸውን ለመርዳት ምሉ ፈቃድ እንደነበራቸው እርግጥ ነው ። በሩ ስላልተከፈተላቸው ግን እስከሁን ያደረጉት ነገር የላቸውም አሁን ግን ያ በር በልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ከተከፈተ ሁላቸው የኢትዮጵያ ልጆች በዚህ በር ለመግባት እንደሚገሠግሡ እርግጥ ነው ።ይህም በር ባገርህ ተማሪ ቤት ማቆም ነው ከመጀመሪያ ዘመን ጀምረን እስከ ዘመናችን የዓለም ታሪክ ብንመለከት ያለትምሕርት የሠለጠነና የበረታ መንግሥት አናገኝም ። ስለዚህ ልዑል አልጋ ወራሽ አገር የሚያሠለጥንና የሚያበረታ ትምሕርት እንደሆነ ስላወቁ ተሁሉ በፊት ተማሪ ቤት አቆሙልን ። እርሳቸው የግርማዊ ንጉሠ ነገሥታታችንን የዳግማዊ ምኒልክን መንገድ ተከትለው ሁለተኛ ተማሪ ቤት እንዳቆሙ እንዲሁም የኢትዮጵያ ልጆች የሳቸውን መንገድ ተከትለን ሶስተኛ ተማሪ ቤት ለማቆም ሙሉ ፈቃዳችን ሊሆን ይገባናል።ይህን አሳብ አንድ ወንድማችን በብርሃንና ሰላም ጽፈው ስላስታወሱ የሳቸው ሐሳብ ብቻ እንደሆነ የሚመስላቸው [illegible] የብዙ ወንድሞቻቸው ሀሳብ መሆኑን አውቀው በብርሃንና ሰላም ጽፈው ስላስታወሱ ብዙ እናመሰግናቸዋለን ። ይህ መጻፋቸው ደግሞ የወንድሞቻቸውን አሳብ አውቀው ብርቱ የማይነቃነቅ ተስፋ ስላላቸው ነው የጻፉት እንጂ በሌላ ነገር አይምሰለን ።

እንግዲያስ ክቡር የኢትዮጵያ ልጅ እኔ ድኻ ነኝ ስለዚህ የኔ ስጦታ የሚረባ አይደለምና ዝም ማለት ይሻለኛል እንዳትል ሁላችን እያንዳንዳችን እንዳቅማችን ላገራችን ብንሰጥ በጉዳት ፈንታ ደስታና በረከት ነው የሚሆንልን ንብረታችንም ሁል ጊዜ እየበለጠ እንደሚሔድ እርግጥ ነው ።

የሰው ሐሳብ ጕደሎና ሰነፍ ነውና ስለዚህ ይህ ታስቦ ያለሐሳብ እግዚአሔር ለመዝራቱ ኃይል ሰጥቶ ፍሬውን ለመብላት ያብቃን ።

ተክለ ሚካኤል ዕቍባ ጋብር ።

ስለ ሚካ።

አሁን በሐገራችን አዲስ የተገኘው ሚካ የሚባል ማዕድን (ሚኔሮ)በጣም ያልታወቀ ስለሆነ በብርሃንና ሰላም የታወቀ እንዲያደርጉት ተስፋ አለኝ። ኢትዮጵያ በተፈጥሮዋ ሐብታም ናት ሐብቷም ልክ የሌለው ነው ። እኛ እንኳ ከምናውቀው በስተቀር ብዙ የአውሮፓ ልዩ ልዩ የሆኑ መሐንዲሶች ዞረው ያዩት የብልጽግናዋን ብዛት ያደንቃሉ ከሐገራችን ከኢትዮጵያ መሬት በሌላ በሌላ አገር ከቶ የማይገኝ ነገር ሁሉ ይገኝበታል ዕንቁ ፤ ወርቅ፤ብር፤ሚካ፤ናስ፤ መዳብ ፤ ከስልና ፤ ኒኬል ፤ ሌላም ብዙ ብዙ ዓይነቶች ስማቸው የረቀቀ ዋጋቸው የከበረ የሚገኙባቸው ድንጋዮች ሞልተዋል ብዙ የውጭ አገር ሰዎች ዕውቀት የመላቸው ይህንኑ ሲናገሩ ከሐገራችን የበለጠ የተፈጥሮ ሐብት አላት እያሉ እውነተኞች ይናገራሉ ።

አንድ አንድ ሰዎችም በኢትዮጵያ ብዙ ዓይነት ማዕድን አለ ፤ ነገር ግን ብዛት የለውም እያሉ የሚሉ ነበሩ፤አሁን ግን በኢትዮጵያ ያለ ማዕድን ሁሉ ብዛት እንዳለው አንድ አንዱ የተመረመረው ማዕድን ያስረዳናል፤አሁን በቅርብ ጊዜ ከሁለት ዓመት ቀደም ብሎ ሙሴ አናስታሲ ቤ ሱኒዮስ የሚባሉ የግሪክ አገር ሰው በሐረር አውራጃ ሚካ ቢያገኙ ብዙ ሰዎች ምንም የሚረባ አይደለም እያሉ ያወሩ ነበር ፤ አሁን በቅርብ ቀን መሐንዲስ ዞሮ ዓይቶ ብዛቱ ልክና መጠን የለውም ብሎ በራፖሩ ጽፎአል ፤ ዓይነቱም እነምሳና አመሪክን አገር ተልኮ ዓይነቱ ተመርምሮ ከኢትዮጵያ የሚወጣ ሚካ መጀመሯ ዓይነት ብለው ጽፈውልናል ፤ ነገር ግን አንድ አንድ ሰዎች ሚካም የለ ዓይነቱም መጥፎ ነው የሚሉ ቢኖሩ እነሱ በኢትዮጵያ አንድ አንድ ሥራ እንዳይቆም የሚመኙ ናቸው ፤ ዛሬ ሚካ በዓለም በመልክም ዋጋ አጥብቆ ይፈለጋል ፤ በኤሌክትሪክ ሐይል የሚሄድ መኪና ሁሉ ሚካ ከሌለው በፍጥነት ይቆማል ሚካ የሚገባበት ሥራ በጣም ብዙ ነው እንደዚህ አጥብቆ የሚፈለገው ሚካ በሀገራችን በመገኘቱና ዓይነቱ ተመርምሮ ከሁሉ የሚበልጥ በመሆኑ በጣም ደስ ይለናል ፤ ይህም በሀገራችን መጀመሩ ለመንግሥታትንና ለሕዝቡ ታላቅ ጥቅም ያለው ነገር ነው ይልቁንም ይህንን የሚመስል ሥራ ለማቆም ምሳሌ ይሆናል በማለት ታላቅ ተስፋ አለን።

ከዚህ ቀደም ክቡር ሊቀ መኳስ መኰንን ዋልቴ ፍቅርና አንድነት ጠፍተው ምቀኝነትና ክፋት በመሐከላችን ሰለጠነብን ብለው እንደተናገሩት ቃል እነዚህን ሁለት ክፉ ነገሮችን ትተን ፍቅርና አንድነትን ብናከብራቸውና ብንወዳቸው ያከብሩናል እናታችን ኢትዮጵያም ትመርቀናለች እንደዚህም ከሆነ ዘንድ በየተቻለን ጉልበት ባንድነት ከልባችን መንግሥታችንን ለመርዳት የምንችል እንሆናለን ስል በሙሉ ተስፋ ነኝ፡ ብርሃንና ሰላምም እየሰፋና እየበዛ የዕውቀትና የስልጣኔ ምንጭ ሆኖ እንዲፈውሰን ስል እመኛለሁ ።

አየለ ደገፉ ።

የሀገር ፍቅር ።

ለሰሚው ግራ ልብ አድርጎ በሚያይ ያለውዴታ የሚያስቅ ዘመን ነው ዘመናችን።ግን ይህን ያልኩበትን ነገር ገልጬ ለመናገር በጣም ደስ ባለኝ ነበር ስለሆነ እግዚአብሔር በኃይሉ አገለጠው ድረስ እኔ ባልናገረውም ግድ የለም ።ወንጌል የተጠ-

መቀ ይዳን ያልተጠመቀ አይዳን ይላል። ከሌላ ቦታ ደግሞ መልካም ሥራ የሌላት ሃይማኖት የሞተች ናት ይላል ። ኢትዮጵያ ነኝ ለማለት ከኢትዮጵያ መወለድ ይበቃል ኢትዮጵያ አገሬ ነች ለማለት ከሷ መወለድ ብቻ አይበቃም የተገባውን የልጅነቱን ሥራ ካልሠራ ።

ወላጁን የበደለ ልጅ በወላጁ ባይረገምም በመጥፎ ሥራው በእግዚአብሔር ዳኝነት የተረገመ ነው ። ዛሬ በኢትዮጵያ የተወለዱ ሁሉ ግን ለኢትዮጵያ ጥፋት እንጂ ልማት የማይሠሩ ደመ ነፍስ ቢሆኑ እንጂ እሷን አያጠፉም እራሳቸውን ካልሆነ በቀር ። ቆቅ ወጥመድ ተዘርግቶ እያየች እምትበላውን እንጂ የምትጠፋበትን ልብ ሳትል ከመከሩ ትወድቃለች ። ቆቅ ደመ ነፍስ ነች የሰው ልጅ ግን አእምሮ ያለው ፍጥረት ሆኖ ይህን አለማወቁ የእግዚአብሔር ቁጣ እንጂ የሌላ አይመስለኝም ።

በዘመናችን ብዙ ወንድሞቻችን በሚሠሩት ሥራ እንኳን የማይሠሩት የሚሠሩትም እየተመለሱ ይቆጫቸዋል ፤ ብቻ ምን እረብ አለው ይሁዳ በመጸጸቱ ሕይወቱን በገዛ እጁ አሳለፈ እንጂ ሌላ ያደረገውን አናውቅም ። የእግዚአብሔር ጸጋ ያልተለየው ግን ንስሐ መግቢያ ጊዜ ያጣ አይመስለኝም ።

በመጥፎ ዘመን ተወለድኹ ታንድ አምሳ ዓመት በፊት ወይ በኋላ ተወልጄ በነበር እያልኩ ስቆጭ እድሜ ለልዑል ተፈሪ መኰንን እንደገና የተወለድኩብትን ዘመን ያስመሰግነኝ ጀመር ። መልካምንና መጥፎን ዛፍ በፍሬያቸው ትለዩዋቸዋላችሁ ይላል ። ደግ ማለት ሰው የሚጠቅም ክፉ ደግሞ ሰው የሚጎዳ ሁሉ ነው ። ይህንም አሌ አንል ኢየሱስ ለሰው ልጅ ሲል ሞተ ። እንደዚሁም ሁሉ ተፈሪ መኰንን በኛው በግማሽ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክፉት ተድከማቸው ሁሉ ባንጠቀም ጥቅም እንጂ አንድም ክፉት አይገኝበት ። አሁንም ወደፊት የልዑል ጌታችን እድሜ ይርዘም ዘር ይበረክ ሀገር እንደምን እንደሚወደድና እንደሚረዳ ብልሐቱን አስተምረውናልና ። ባባቶቻችን ጊዜ የሀገር ፍቅር ተበጥሮ ተወስኖ አይታወቅም ነበር ማለት ስለ ዘመቻና ስለ ጌታ ፍቅር እንጂ ስለ ሀገሬ ብሎ የሚሞት ብዙ ይገኝ አይመስለኝም ነበር ። ሀገር በክፋትና በውሸት መንገድ አይረዳም በውነተኛ መንገድና በሙሉ ልብ በሆነ ፍቅር ካልሆነ በቀር ። ብዙ ወንድሞቻችን የዚህን ነገር በቅጡ አድርገው ጽፈውታል አሁንም እነሱ ያሉትን እኔ ልድገመው ። ሀገር ለመጥቀማ የገንዘብ ማውጣት የሃይማኖታችን የውነተኛዋን ሕይወታችንን መሠረት ኢየሱስን መከተል ነው ። ሥጋዬንና ነፍሴን ከማቃጥልበት የዓመፃ ንዋይ ቀንሼ በፈጣሪዬ ፊት ሞገስ የማገኝበትን ጸጋ እግዚአብሔር ከሰጠኝ ወሰን የሌለውን ደግነቱን እያመሰገንሁ ደግሞ ይህን የመሰለ ጸጋውን ለወደፊት እንዳይሰውርብኝ በግምባሬ ተደፍቼ እየለመንሁ ክቡር ፊታውራሪ ዶሪሳ ገንዘብ አዋጥተን በማኀበር ትምህርት ቤት እናቁም ላሉት በያመቱ ጉልበቱ እስነፈ ድረስ መቶ መቶ ብር እሰጣለሁ ። ሰ ሥ ሚ

ቅንዑ ለእንተ ተዓቢ ጸጋ ።

አለቃ ሠርፀ የሩፋኤል ደብር አለቃ እሁድ እሁድ ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ካሳተሙት ቅዱስ ወንጌል ለዕለቱ የሚያስፈልገውን ክፍል ንባቡን እስከ ትርጓሜው ለሕዝቡ በማሰማታቸው ደስ ብሎናል ሌሎችም ደግሞ በየደብሩ እንዲሁ ቢያደርጉ ሕዝቡ ጥቅም ያገኛል ለሳቸውና እንዲሁ በማድረጋቸው ለሕዝቡ የአምላክን ቃል ለሚመግቡ ሊቃውንት ሁሉ እናመሰግናቸዋለን ።

የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ የተመሰለው ትርጓሜ ።

ሰኔ ፳፯ ቀን ፲፱፻፲፯ ዓመት በተጻፈው በአእምሮ ጋዜታ ክቡር ማህሉ ጽጌ የትጋት ማስታወሻ ብለው በጻፉት ቃል ውስጥ የኢትዮጵያ ባንዴራ በምን እንደተመሰለ ማወቅ እንዲያስፈልግ ብለው ጽፈዋል ። መትጋታቸውንና መሻታቸውን አመስግኜ ሰንደቅ ዓላማ ሳይሉ ባንዴራ ማለታቸውን ሰንደቅ ዓላማ ብለው በማርኛ እንዲገልጹት ይረዳቸዋል ቢመስለኝ ከዚህ በታች የሚከተለውን የሰንደቅ ዓላማችንን ነገር ትርጓሜ ፤ ምሳሌውን ከብሉይና ከሐዲስ የተስማማውን እጽፋለሁ ። ባማርኛ ቋንቋ ሰንደቅ ዓላማ ማለት ሁለት ቃል ነው ። ሰንደቅ ማለት የምድርን ክብነት የሚያስረዳ ነው ። ዓላማ ማለት ሶስት በተራ የተሰፉ በሶስት ቀለም የተለዩ ጨርቆች ናቸው ። ከሰንደቁ በላይ መስቀል አለ ። ወበቀራንዮ ተተክለ መድኃኒት መስቀል እንዲል የሰንደቅ ዓላማችንን ትርጓሜ የፊቱን እየመረመርኹ ያሁኑን እያየሁ ላንባቢዎች ጽፌ አቀርባለሁ ። የመስቀሉ ትርጓሜ ለጸላዮች አሸናፊ ለወዳጆች መድኃኒት ነው ። በመስቀሉ መድኃኒት እንደተሰቀለበት ላመኑ ከነፍስና ከሥጋ ጻላት ያድናል ። አዳምን ከሞት ዓለምን ከጥፋት ለማዳን ዲያብሎስን ድል ለመንሣት ኢየሱስ ክርስቶስ መጣና ሙሴ እባብን እንደሰቀለ በምድረ በዳ እንዲሁም የሰው ልጅ ይሰቀል ዘንድ የተገባው ሆነ ። የተሰቀለውም ሰንደቅ በምንሳት በምድር ምሳሌ ነው ። የሰንደቁና የመስቀሉ ትርጓሜ ከዚህ በላይ እንደተጻፈው ነው ። የአረንጓዴው ትርጓሜ ይከተላል ። መጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ፈጠረ ። ምድርም ባዶ ነበረች ። አንዳችም አልነበረባት (ዘፍጥረት ፩ ፡ ፩) በሶስተኛው ቀን በዚህች ምድር ላይ በመጥረቢያ የሚቆረጡ በማጭድ የሚታጨዱ አትክልትን አዝርእትን ለዓይን ደስ የሚያሰኙን ተስፋ የሚሆኑን ልምላሜ አበቀለባት ዘፍ ፩ ፲፩ ፲፪ የኢትዮጵያም ሰንደቅ ዓላማ በዚህ ልምላሜ ምሳሌ ፍሬን እንድታገኝ ተስፋ አያደረገች የአላማዋን ምልክት ቅጠልያውን በላይ ሰፋች ። ይህነን ልምላሜ እያየች ፍሬዋን እስክታገኝ ድረስ አምላኳን ደጅ ትጠናለች ። እነሆ ገበሬ የከበረች ምድርን ፍሬ እስኪያገኝ እንዲታገስ ኢትዮጵያም በቅጠልያው ምሳሌ ተስፋ አድርጋ ትኖራለች ያዕቆብ ፭ ፯ የጥፋት ውሀ በምድር ላይ በወረደ ጊዜ የኖኅ ርግብ የወይራ ጫፍ የለመለመ ቅጠል ይዛ የምስራች ጥፋት አለፈ ምሕረት ደረሰ ለማለት ለኖኅ ይህንን ልምላሜ አሳየች ። በሆሣዕናም የለመለመ ቅጠል እየያዙ ሆሣዕና ለዳዊት ልጅ እያሉ ለአይነተኛው ንጉሥ ምስጋና አቀረቡለት ። እኛም ቅጠልና አበባን አስቀድመን ሳናይ ፍሬን ከመሬት እንዳናገኝ በሁላችን ዘንድ የታወቀ ነው ። የብጫው ትርጓሜ ከዚህ ይከተላል ። ቅጠል ከወጣ በኋላ አበባ እንዲከተል ኢትዮጵያም ደህንነትን ታስከትላለች ብጫ የደህንነት ምሳሌ ነው ።

ሕዝቧም ክረምት አለፈ ፍሬ ደረሰ ሲሉ በአደይ አበባ እንቁጣጣሽ ይላሉ ፤ የዚህም ምሳሌ የለምለሚቱ የመቤታችን በዓል በዓለ ቍስቋምን ጽጌ ይሉታል እመቤታችንን ከልምላሜ

ወደ ጽጌ ከጽጌ ወደ እውነተኛው ፍሬ ደርሳለችና ይህንን ምሳሌ ተከትላ ኢትዮጵያ ከቅጠልያው በኋላ ብጫውን አላማ ሰፋች የቅጠል ተከታይ አበባ ነውና ፤ እብጫው ውስጥ አንበሳ አለ ይህ ዓንበሳ ከይሁዳ ወገን ያሸነፈ ማለት ነው ። የቀዩ ትርጓሜ ከዚህ ይከተላል ይህ ቀይ በደም በእሳት በፍሬ ይመሰላል ። ኢትዮጵያም ከብጫው በኋላ ቀዩን ታስከትላለች ፤ ደም በመሆኑ ደም የነበረው ፍሬ ሆኖ እንዲወለድ አስባ ኢትዮጵያም የፍሬዋን ምሳሌ ቀዩን አላማ አደረገች ። ያለደም ፍሬ የለምና ። ጌታችንም ኢየሱስ ክርስቶስ ከ፴፫ ዓመት በኋላ ሥጋውን ቆርሶ ደሙን አፍሶ ፍሬ መንግሥተ ሰማያትን ሰጠን ለዘላለም ደህንነት እንድናገኝ ። የደሙን ምሳሌ የወይን ፍሬን አደረገልን ። ቀዩ ወደታች መሆኑ ምንጊዜም የደም መንገድ ወደ ታች ፈሳሽ ነው ስትል የደሙን ምሳሌ ቀዩን በታች አደረገች ። እናት እስክትወልድ ድረስ ብዙ ትጨነቃለች የሆዷን ፍሬ ልጅዋን ባገኘች ጊዜ እጅግ ደስ ይላታል ። ደም የነበረውን ፍሬ አገኘታለችና ። ቀይ ደም መሆኑን ሲመሰክር ማነው እሱ ከኤዶምያስ የሚመጣ ልብሱ ቀይ ደም የሚመስል ነው ። ይህም በልብሱ ያማረ በጉልበቱ ብዛት የሚሔድ እኔን በቅን የሚናገር እኔን ለማዳን የሚበረታ እንዳለ ኢሳኢያስ ፷፫ ፩ ። በዚህ ምሳሌ የኢትዮጵያ ልጆች ደማቸውን እያፈሰሱ ሲዋጉ ሲላጉ ሲነዳደሉ የዘውዳቸውንና የዙፋናቸውን ፍሬ አገኙ ።

እሳት በመሆኑ እሳት በላዒ ለዓማፅያን ወእሳት ማኅየዊ ለእለ ይገብሩ ፈቃዶ ። እሳት ፀላቱን የሚያቃጥል ወዳጁን የሚያሞቅ ነው ። ሠለስቱ ደቂቅም ከነልብሳቸው ወደ እሳት ገብተው ዳኑ የጣሏቸውን ፀላቶቻቸውን ግን የእሳቱ ወላፈን ገደላቸው ። ዳንኤል ፫ ፳ ፤ ሰዶሞችንም በእሳት ገሞራ አጠፋቸው ፤ ዘፍጥ ፲፱ ፳፬፤ ለሐዋርያትም በእሳት ምሳሌ መንፈስ ቅዱስ ወረደላቸው የሐዋርያት ሥራ ፪ ፫ ፤ ኢትዮጵያም ይህንን ሁሉ አምና በተረዳው አስተካክላ ተርጉማ ለሚፈሩህ ሰንደቅ አላማ ሰጠኻቸው ፷ ፬ መዝሙር ። በመድኀኒትህ ደስ ይለናል በአምላካችንም ስም ሰንደቅ አላማ እናነሳለን ፳፭ መዝሙር ። እግዚአብሔር አላማዬ ነው እንዲህ ሲል እጁን በእግዚአብሔር ዙፋን ጫነ ዘፀአት ፲፯ ፲፭ ፲፯ ። የሚለውን ተቀብላ ሕዝቧን በዚህ ሰንደቅ አላማ አሠልጥና ትጠብቃለች ። በመላው ዓለም ሰንደነቅ አላማና ዘውድ ትእምርተ መንግሥት (አርማ) የሌለው መንግሥት የለም አንዱ ያንዱን ምልክት ምንም ቢሆን አይተላለፉም ። በኃይልና በጦርነት አሸንፈው ካልሆነ በቀር ። የኢትዮጵያም ልጆች ይህ በላይ የተጻፈው የመንግሥት ምልክት እንዳይጠፋባቸው የጦር ሰንደቅ አላማቸውን ይዘው የመድፉን መንጓጓት የመርውጡን መንዷዷት የጠበንጃውን መንጣጣት የሰይፉን አቆራረጥ የጦሩን አሸረካከት የውጊያውን መፋፋም የውካታውን መሟሟቅ የፈረሰኛውን መጋፈጥ የእግረኛውን መጋፋት ሳይፈሩ አገራቸውን ከፀላት አድነው ሰንደቅ አላማቸውን አክብረው መንግሥታቸው ከተመሰረተ እስከ አሁን ጥቃት ውርደት አላገኛቸውም ። ስለ ኢትዮጵያ ነፃነት ፍሬ ደማቸውን እያፈሰሱ መንግሥታቸውን አቁመው ጠንክረው መጠበቃቸው የባዕድ አገር ሰንደቅ አላማ እንዳይተከል የመንግሥታቸው ክብር እንዳይዋረድ ነው ። አጼ ገላውዴዎስ ከግራኝ ሙሐመድ፤አጼ ዮሐንስ ከቱርክ፤አጼ ምኒልክ ከኢጣልያ ሲዋጉ ይህች ሰንደቅ አላማ ነበረች ። የኢትዮጵያ ነገሥታት ፀላት በተነሳባቸው ጊዜ ጫን ነጋሪት ፤ ክተት ሠራዊት ፤ ተከተል አለቃህን ፤ ተመልከት አላማህን እያሉ በአላፊውና በመጭው ይሰለፉበታል ። የኢትዮጵያ ሰንደቅ አላማ በልምላሜ በአበባ በፍሬ ትመሰላለች ። በአረንጓዴ የተመሰለችው አረንጓዴው ልምላሜዋን ያሳስባል ። ይህም ልምላሜ የተስፋ የሰላም ምልክት ነው ። ኢትዮጵያም ለምለሚቱ አበባዩቱ ፍሬያማዩቱ የተስፋና የሰላም መንግሥት ነኝ ጦር ሳይጀምር እርቅና ሰላም እወዳለሁ ስትል አረንጓዴውን ባላይ ታሳያለች ። ደግሞ ፀላት እየገፋ እርቅ አፍርሶ ድንበር ጥሶ ቢመጣ አምላክ በሰጠኝ ነበልባለ እሳት አቃጥዬ እፈጀዋለሁ በደም አጠምቀዋለሁ ልጆቼም ደም አፍሳሽ እሳት ጎራሽ ናቸው ፤ መንግሥቴን በእሳትና በደም አጥሬዋለሁ እያለች ቀዩን ምልክት አድርጋለች ። የኢትዮጵያ መንግሥት ሲቆም ሲመሠረት ነገሥታትና ሊቃውንት ተስማምተው ይህንን ምሳሌ ተርጒመው በሶስት አይነት ቀለም ሰንደቅ አላማ ሰፍተው አቁመዋል ። ሶስት መሆኑ እግዚአብሔር ምድርን ሁለተኛ በወሀ አላጠፋትም ሲል የምሕረት ኪዳን በሶስት አይነት ቀለም በቀስተ ደመና ምልክት ሰጥቶናል ። እኔም ኢትዮጵያዊ ደስታ ላስተዋዮች አንባቢዎች የሰንደቅ አላማችንን ትርጓሜ ጽፌ አቀርባለሁ ።

ነጋድራስ ደስታ ምትኬ ።

ትንሽ ስጦታዬን አትናቁ ።

ለተማሪ ቤት እርዳታ በየመቱ ፪ ሩብ እረዳለሁ ይኸንንም እንዳትንቁብኝ በማክበር እለምናችኋለሁ እኔም አንድ ደሃ ነጋዴ ነኝ የምነግድበትም ገንዘቤ ከወለጋ ወደ አዲስ አበባ ንግድ የምመላለስበት ፳ ብር ናት ስለዚህ ገንዘብም ባይኖረኝ ደሃም ብሆን መጀመሪያ በኢትዮጵያ ልጆች ስም በሚቆመው የትምሕርት ቤት ማህበር ስሜ እንዳይለይ ብየ ለማሰብ ነው ይችን ትንሽ ገንዘብ ደፍሬ መስጠቴ ፤ ድህነቴን አይታችሁ አትናቁ ማሰቤንና ያገሬ ፍቅር እንዳለኝ ብቻ አስቡ እንጂ ፤ ብዙ ቢኖረኝ ብዙ እሰጥ ነበረ ። አሁንም እግዚአብሔር ከዚህ የበለጠ ትዳር በሰጠኝ ጊዜ ከዚህ የሚበልጥ እሰጣለሁ ። ምን ማድረግ ይቻላል አእምሮና ገንዘብ ፩ ላይ ሁለጊዜ አይገኙምና ። መቸም አገርን መውደድ ላገር ማሰብ በጌትነትና በድህነት አይደለም ፤ ከፍጥረት ነው እንጂ ። ይህችን የኢትዮጵያ ልጆች መሪ የምትሆን የትምሕርት ቤት በቶሎ ቁማ ለማየት ቸሩ እግዚአብሔር ያብቃን

ጨዋቃ ጎሹ ።

በኢትዮጵያውያን ማኅበር ለሚቆመው ተማሪ ቤት እርዳታ እንሰጣለን ብለው ፈርማቸውን የሰጡ ሰዎች ።

ከ፳፯ኛ ቍጥር የመጣ ድምር	፬ሺ፫፻፱	ብር
አቶ ሰይፉ ሚካኤል ።	፻	ብር
እሸቱ ተከተለው ።	፲፫	ብር
ክብረት አስታጥቄ ።	፫	ብር
በላቸው ገብረ መድኅን ።	፪	ብር
ጨዋቃ ጎሹ ።	፪	ሩብ
ቀኛዝማች አጋ ለሚ ።	፫	ብር
ድምር	፬ሺ፬፻፴፫	ብር ተ፪ ሩብ

በልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ። –

መጀመሪያ ዓመት ፡ ቁጥር ፳፱ ።
1re ANNÉE № 29

ሐሙስ ሐምሌ ፱ ቀን፲፱፻፲፯ ዓ ም ።
JEUDI 16 JUILLET 1925

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን በገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

የጋዜጣው ዲሬክተር ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።
Gabré Christo Taklé Haymanot
Dirécteur

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሲገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ያጼ ቴዎድሮስ ዘውድ

ለኢትዮጵያ መንግሥት ሲመለስ የተደረገ የክብር አቀባበል

የአገባቡ አኳኋን (ፕሮግራም) ።

ለታላቅ ብሪታኒያ መንግሥት ባለ ሙሉ ሥልጣን ሚኒስቴር ለክቡር ሻርል።ቤንቲግ በሐምሌ ፱ ቀን ፲፱፻፲፯ ዓመተ ምሕረት ቀዳሚት በ፭ት ሰዓት የግቢ ምኒስትር ደጃዝማች ወልደ ገብርኤል ከሌጋሲዮን በሚገባ ታጅበው ይዘዋቸው እንዲመጡ መታዘዙን አቶ ሣህሉ ፀዳሉ አስታወቁ ።

በታላቁ ቤተ መንግሥት ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ልዑል አልጋ ወራሽ ከምኒስትሮችና ከመኳንንቶች ጋራ ወታደሮችና የጦር አለቆችም በጦር ልብስ ተሰልፈው ይጠብቋቸው ነበር የእንግሊዙም ሚኒስትር ዘውዱን ባራት ፈረስ በሚሳብ ሠረገላ እማኽል አድርገው በህንድ ዘበኞች አስከብበው ይዘው መጡ ዘውዱን በተሰናዳላቸው ሰደቃ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ፊት አስቀምጠው ከዚህ የሚቀጥለውን ቃል ተናገሩ ።

ግርማዊት ሆይ ፤

በንግሥት ቪክቶሪያ መንግሥት በ፲፰፻፷፰ ዓመተ ምሕረት ከመቅደላ የተወሰደውን የአጼ ቴዎድሮስን ዘውድ የታላቂቱ ብሪታንያና የአይርላንድ ከባሕርም ማዶ ያሉት ግዛቶች ንጉሥ፣የህንድ ንጉሠ ነገሥት በሆኑት በግርማዊ ጌታዬ በንጉሡ ትእዛዝ ለግርማዊት ንግሥት በማክበር እመልሳለሁ።

ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ።

የዚሁ ዘውድ ታሪክ ባጭሩ ለግርማዊት ንግሥት ሳያስደንቅዎ እንደማይቀር እርግጥ ነው።መቅደላ ከተያዘ በኋላ ይህ የንጉሡ ነገሥት ዘውድ ሮልፍስ በሚባል ባንድ የፕረሽያ ሰው እጅ ገብቶ ነበር፤ይህ ሰውዬ ከሎርድ ናፒየር በታች ይታዘዝ ከነበረው ዘመቻ ጋራ አንድነት ለመሄድ የተፈቀደለት ሰው ነበረ። ከዚህ በኋላ ይህንኑ ዘውድ ሱኤዝ ላይ ይቀመጥ የነበረው የፕረሽያ ዋይስ ቆንስል ቤርሊን ውስጥ ባለው የነገሥታት ዕቃ መሰብሰቢያ ቤት እንዲቀመጥ ብሎ ለከንት በኋላ ግን ፕሪንስ ቢስማርክ ለተባሉት ላከላቸው።የእንግሊዝ መንግሥት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ይህነን ነገር በሰሙ ጊዜ ዘውዱ እንዲመለስልን እያሉ ከፕረሽያ መንግሥት ጋራ መጻ–

ጻፍና መላላክ ጀመሩ ከዚያ በኋላ ይኸው ዘውድ በፕሪሽያ ንጉሥ በኋላም የጀርመን ንጉሠ ነገሥት በሆኑት ትእዛዝ የንግሥት ቢክቶሪያ መንግሥት እንደፈቃዱ እንዲያዝበት ሁኖ ተመለሰ ። በተመለሰም ጊዜ ኮንት ቢስማርክ በዘውዱ ጫፍ ላይ የሚሆነው መስቀል ጐድሏል፤ ስለሆነ ግን እኛም እንደዚሁ ሁኖ ነውና የደረሰን እንዲሁ እንዳለ ይኸው መልሰናል የሚል ደብዳቤ ጽፈው ላኩ ።

ከዚህ በኋላ የእንግሊዝ መንግሥት ይህንኑ ዘውድ ከመጋቢት ፴ ቀን ሺ፰፻፷፱ ዓመተ ምሕረት አንስቶ ሃምሳ ስድስት ዓመት ድረስ በቢክቶሪያና በአልቤርት ሙዚዩም አስቀምጦት ሲኖር በሚያዝያ ፳፱ ቀን ሺ፱፻፳፭ ዓመተ ምሕረት እኔ ወደ ኢትዮጵያ ይገባው እንድመልስ ተብሎ ከተቀመጠበት ስፍራ ወጣ ። የዚህም ዘውድ አኳኋን በሺ፰፻፷፱ዓመት በሙዚዩም ሲገባ ልክ እንደዚሁ እንደነበረ አሁንም እንደዚያው መሆኑን ለግርማዊት ንግሥት አረጋግጥ ዘንድ ሥልጣን ተቀብያለሁ ።

የኢትዮጵያ መንግሥት ልዑል አልጋ ወራሽ ባለፈው ዓመት የእንግሊዝን አገር ሄደው ማየታቸው ለግርማዊው ንጉሥና ለግርማዊት ንግሥት እጅግ ደስ አሰኝቷቸዋል ። ግርማዊ ንጉሥ ጆርጅ ደግሞ የኢትዮጵያንና የታላቂቱን ብሪታንያን ቤት መንግሥቶች እንዲህ በደስታ ያስተሳሰራቸውን የወዳጅነት ማሰሪያ ወደፊት እያጸኑና እያጠበቁ ለመሔድ ምኞታቸው ስለሆነ በዚሁ ምክንያት የአጼ ቴዎድሮስን ዘውድ ለግርማዊት ንግሥት እመልስላቸዋለሁ ብለው ቃላቸውን ለልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ሰጡ ።

አሁንም እንዲህ በመሰለውና ታሪክም ሆኖ በሚቆየው ነገር የንጉሤን ትእዛዝ በመፈጸሜና ይህንንም የንጉሠ ነገሥት ዘውድ ለግርማዊት ንግሥት በማስረከቤ ለኔ የተለየ ክብር በመሆኑ ያኰራኛል ይህም የንጉሥ ስጦታ ለግርማዊት ንግሥት ደስ እንዲያሰኛዎና ይህኑም ስጦታ ለግርማዊ ንጉሥ ጆርጅ በተለየ የወዳጅነታቸውና የአክብሮታቸው ምልክት ሆኖ እንዲቀበሉላቸው ተስፋ ያደርጋሉ ።

አሁንም እንደዚሁ የንጉሡን ትእዛዝ እየፈጸምሁ እግዚአብሔር ግርማዊት ንግሥትን እንዲባርክና እንደታላቂቱ ንግሥታችን በረከት ለመላበት ነገር ሁሉ መታሰቢያ እንደሆኑትና የልጅ ልጃቸውም ይህነን የወዳጅነት ምልክት እንደለኩልዎ እንደ ንግሥት ቢክቶርያ ያለ ረጅም ዕድሜና የደህንነትም መንግሥት እንዲያደርግልዎ እግዚአብሔርን እለምናለሁ ። ደግሞም ለልዑል አልጋ ወራሽና ለኢትዮጵያም መንግሥት ሕዝብ ሁሉ ልዑል እግዚአብሔር በከረቱን ይስጣቸው ።

የኢትዮጵያ መንግሥት ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን የተናገሩት ቃል ።

ክቡር ሚኒስትር ሆይ ።

ከሮፓ መንገዴ በተመለስኩ ጊዜ ግርማዊ ንጉሥ ዤዎርጆ ያጼ ቴዎድሮስን ዘውድ እመልሳለሁ ብለው ስሰናበታቸው የነገሩኝን ቃል ለግርማዊት ንግሥት ባመለከታቸው ታላቅ ደስታ አድርገው ነበር ።



የኢትዮጵያ መንግሥት ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ።

አሁንም የግርማዊ ንጉሥ ዤዎርጆ ቃላቸው ስለተፈጸመ ግርማዊት ንግሥትና የኢትዮጵያ ሕዝብ በመላው እግዚአብሔርን በቸርነቱ እናመሰግነዋለን ። ይህ ዘውድ ከ፶፮ ዓመት በኋላ እኔ ወደ ሮፓ በመሄዴ ምክንያት በግርማዊት ንግሥት በመንግሥታቸው ዘመን ተመልሶ ወደ ኢትዮጵያ ስለመጣልን በጣም ደስ አለን ።

ክቡር ሚኒስትር ሆይ እዚህ ላይ የማስታውስዎ ይህ ያጼ ቴዎድሮስ ዘውድ ተመልሶ ስለመጣልን ከትልቅ መታሰቢያ እንቆጥረዋለን ። ነገር ግን የኢትዮጵያ ዘውድ ከቀዳማዊ ዘመን ዠምሮ ክብሮ የኖረና አሁንም ወደ ፊት እስከ ፍጻሜ ዘመን ባለተስፋ መሆኑ ከእውቀትዎ እንዳይሰወርዎ በፍጹም አምናለሁና ለዚህ ታሪኩን አስረዝሜ ልነግርዎ የሚያስፈልግ መስሎ አልታየኝም ።

ይኸውም የዘውድ ነገር ከኢትዮጵያ ታሪክ ክፍል የተገናኘ በመሆኑ ግርማዊት ንግሥት በታላቅ ደስታና ክብር ይቀበሉዎታል ።

ክቡር ሚኒስትር ሆይ ይህ የግርማዊ ንጉሥ ዤዎርጆ ስጦታ የሚደነቅ የወዳጅነት ምልክት ስለሆነ ግርማዊት ንግሥት በፍጹም ልባቸው ምስጋናቸውን ለግርማዊ ንጉሥ ያቀርባሉና ይህንኑም ምስጋናቸውን ገልጸው እንዲያስታውቁላቸው በብዙ ይለምኑዎታል ።

እኔም ራሴ ግርማዊ ንጉሥ ዤዎርጆን ለማየት ሂጄ በታላቁ ከተማቸው ሳለሁ ይኸንን ታላቅ ቸርነታቸውን ስላሳዩኝ

ይህ ስራ ለዘለዓለም ከልቤ ተጽፎ መታሰቢያ ሁኖኝ ይኖራል በዚሁም ምክንያት ከፍ ያለ ምስጋናዬን ለግርማዊ ንጉሥ አቀርብላቸዋለሁ። ቸርነቱ የማያልቅበት እግዚአብሔር ለግርማዊ ንጉሥ ዜዎርጊስና ለግርማዊት ንግሥት ማሬ እንደዚሁም ለቤተ ዘመዶቻቸው ሁሉ ሰላምና ጤና ክብርና ደስታ ለዘወትር እንዲሰጣቸው በታላቅ ተስፋ እንለምናለን ።

ስለ ጉባዔ ሐዋርያት በዓል መታሰቢያ ።

በሐምሌ ፫ ቀን እሁድ የሐዋርያት ጉባዔ መታሰቢያ በዓል ነበረና ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን በዓሉን ለማክበር በሚያስገርም አጀብ ወደ ጴጥሮስና ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያን በጥዋት ሔደው በዓሉን በደስታ አክብረው በሶስት ሰዓት ከዚያ ተነስተው በአጀብ ወደ ቤተ መንግሥቱ ተመልሰው ሠራዊታቸውን ሁሉ በደስታ ግብር አበሉ ።

የበዓሉም አከባበር ምክንያትና ጉቡዓን የተባለበት እንዴህ ነው ። በአንጾኪያና በሶርያ ያሉ ምዕመናን በወንጌል ካመኑ በኋላ ከፈሪሳውያን ወገን ገብተው የኦሪትን ሥርዓት ካልፈጸማችሁና ካልተገዘራችሁ መዳን አይቻላችሁም ስለ አሏቸው ሕዝቡ ተጨንቁ ታወኩ ። ከዚህ በኋላ በኢየሩሳሌም ወደ ነበሩ ሐዋርያት ሽማግሎች ላኩባቸው ። ሐዋርያትም ይኸን ሰምተው አንድነት ተሰብስበው ሥርዓት ጽፈው ልከውላቸዋል ግብረ ሐዋርያት ም ፲፭ ቁ ፩—፴፫ መመልከት ነው። በዚህ ምክንያት ጉባዔ ሐዋርያት ተብሏል ።

ሁለተኛም ። በገራችን በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መጽሐፈ ሥንክሳር የሁለቱ ሐዋርያት የሞታቸው መታሰቢያ እንደሆነ ይናገራል ።

ስለ ብርሃንና ሰላም ።

ከዚህ ቀድሞ በሀገራችን ለመንግሥቱና ለሕዝቡ ጥቅም የሚያስቡ እጅግ ሰዎች ነበሩ፡ነገር ግን የጓደኞቻቸውን ሐሳብ ባለማወቅ ሁሉም በየልባቸው እንዳሰቡ እንዲሁ ይቀር ነበር እንዲህም መሆኑ በቀድሞው ጊዜ ፩ዱ ላንዱ ሰው ለሐገራችን ጥቅም እንዲህ ያለ ምክር አስቤ ነበር ግን ከንጉሥ ማን ያገናኘናል ብሎ ሲያማክረው ምክሩንና ሃሣቡን ተቀብሎ ሄዶ በዚያ በብልሀ ሰው ሃሣብ ይሸለምበት ነበርና ስለዚህ ሰው ሁሉ ለሀገሩ ማሰቡ ሳይቀር የሚናገርበትና ለሕዝቡ የሚያስረዳበት ብልሀት እያጣ ተፋፍሮ ይኖር ነበረ፤አሁን ግን እግዚአብሔር ለሕዝቡ ቸር ነውና ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንንን ለኢትዮጵያና ለሕዝብዋ ጠባቂ ሰጠን ። ልዑል አልጋ ወራሽም ለኢትዮጵያ አልጋ ወራሽነት ከተቀቡ ጀምሮ እስከ ዛሬ እንዲሁ እንደምናየው ሁሉ ድካማቸው ለኢትዮጵያና ለኛ ለሕዝብዋ ነው ። ደግሞ ዛፍ ከፍሬው እንዲታወቅ በገንዘባቸው ያቆሙት ተማሪ ቤት ና ሆፒታል ሌላም ያቆሙት ሥርዓት በየክፍሉ ሁሉ ይገኛል፡ደግሞ አሁን እላይ እንደጻፍኩት ሰው ሁሉ ለሀገሩ ጥቅም ያሰበውን እንዲናገርና የሰው ሁሉ ልብ እንዲከፈት በገንዘባቸው ማተሚያ ቤት አቁመው ጋዜታ ከነስሙ አሳምረው ብርሃንና ሰላም ብለው ሰይመው የሰው ሁሉ ልብ መክፈቻ አደረጉ፤አሁን ሰው ሁሉ ለሀገሩ አንዳች ጥቅም ቢያስብ ወደ ዲሬክተሩ አቶ ገ ብረ ክርስቶስ ዘንድ ጽፎ በነሃሣቡን በጋዜታ ሊገልጽ ይችላል፡ስለዚህ ሁሉ የልዑል አልጋ ወራሽን ሐሳባቸውና ድካማቸውን ሁሉ ስላየሁ እግዚአብሔር ሐሳባቸውን ሁሉ ያከናውንላቸው ይርዳቸው ስል በሙሉ ልቤ የተካከለ ምኞቴን አቀርባለሁ፡ቀጥዬም ትንሽ ግጥም ጽፌአለሁ ።

እስኪ በጽሕፈት ላስታውቅ የልቤን ።
ጨለማው ካለፈ ከሆነ ብርሃን ።
የሰጠን ተፈሪን አልጋ ወራሽን ።
እስከ ዘለዓለም አምላክ ይመስገን ።
እድሜ ለምኑ እንጅ ላልጋ ወራሻችን ።
የሸማ መኪና ልናይ ነው ባይናችን ።
ሕይወት ለተፈሪ ላልጋ ወራሻችን ።
ብርሃንና ሰላም ገባ በገራችን፡
ልዑል አልጋ ወራሽ ልብ አድርጎ ላየው ።
ብርሃንና ሰላም አለ ከፊትዎ ፡
ብርሃንና ሰላም ብሎ የሰየመ ማነው ጋዜታዎን ።
ብርሃንና ሰላም ማለትስ እርስዎን ።

ውድነህ ይነሡ ።

የጥያቄ ምላሽ ።

ብርሃንና ሰላም የኢትዮጵያ መብራት ስለ ሆነ የኢትዮጵያን ዓይን የሚከፍተውን ጥያቄ እያየ ይጠይቃል ። ስለዚህ በ፳፬ኛው ቁጥር አንዲት የሌት ወፍ ባንድ ቤት ከፈፍ የተንጠለጠለ ቀጭን ገመድ ተጠምጥማበት ተያዘች ላታመልጥ እየጮኸች ትንፈራገጥ ነበረች ትንሽ ቈይቶ ጩኸቷን ሰምተው የሌት ወፎች ከየትም ከየትም ተጠራቅመው ብዙ ሁነው ተሰበሰቡና በተያዘችው ላይ ሲያንዣብቡ እንደ ደመና ሆኑ ከዚህ በኋላ ሁሉም ተሰማምተው በቀጭኑ ገመድ ላይ አንድ ቦታ በየተራ ባፋቸው ይነጩ ጀመር ከጥቂት ጊዜ በኋላም ገመዱ ተበጠሰ። የታሰረችው ተለቀቀች ይባላል ይህ ተረት ምን ያስተምረናል ሲል ጠየቀ ።

ይህ ተረት አገርን የሚያሰለጥኑና የሚያበረቱ ፪ ዋና ዋና ትምርት ያስተምረናል ። ፩ኛ መስማማትና መተጋገዝ ነው ። የመስማማትና የመተጋገዝ ጥቅምም የሚከተለው ነው ፤ ይህች በገመዱ ታስራ ተንጠልጥላ ስትጮህ የነበረች ወፍ እህቶችዋ ተሰብስበው ባይረዷት ከሞት አመልጣለሁ የሚባል አሳብ አልነበረባትም እህቶችዋ ጩኸቷን ሰምተው ከግራና ቀኝ መጥተው ሁሉም ባንድ ሁነው በሉ አይዟችሁ ብንሰማማ እህታችንን ከሞት እናድናለን እያሉ ባንድነት እየተጋገዙ ስለ ሠሩ በወፍ አፍ ይቈረጣል ተብሎ የማይጠረጠረውን ጠንካራ ገመድ በጣጥሰው እህታቸውን ከሞት አዳኑ ምሉ እውቀት የሌላቸው ትንንሽ ዎፎች እህታቸውን ለማዳን እንዲሁ ተሰማምተው ሲሰሩ እኛ በአርአያ ሥላሴ በምሉ እውቀት የተፈጠርን የኢትዮጵያ ሕዝብሳ አሳባችን ከነዚህ እንስሶች ጐድሎ እንሰ ቢገኝ የመርገም መርገም የጥፋት ጥፋት መሆኑ አይታወቀንምን ? ይህን ለይተን ካወቅን ያገራችን ክብርና መዓርግ ነን ይህን ካላወቅን ግን ላገራችን ክብደናት የምንኖር

የተከመረ ድንጋይ መሆናችንን እንወቀው ። እንስሶች እንዲህ ተስማምተው ሲሰሩ እኛ ሰዎች እንዴት ልናደርግ እንደሚገባን እናስብ ።

፫ኛ ትምርቱም መፈለግ ነው ። ማለት አንድ ነገር እደርጋለሁ ብሎ ማሰብና መጨነቅ ነው ። ልታደርገው የምትፈልገውን ነገር የማይቻል የማይታሰብ ከባድ ሁኖ ቢታይህ እንኳ ይህ መፈለግ የሚባል ሥልጣን ሁለ ጊዜ ከልባችን ካለ ቸጋሪውን ነገር ለመገለቁ እንደምንችል ጥርጥር የለውም። ሳይደረግ ቸጋሪ የማይመስል ከተደረገ በኋላም ቀላል ሁኖ የማይታይ ነገር የለምና ተስፋ ሳንቈርጥ መፈለግ የተባለውን መሳሪያ ይዘን እንጣጣር ። ይህን ከደረግን ከሁን በፊት በዚህ ዓለም የተሰራው ጥበብስ ይቅርና ሌላ ያልታየና ያልታሰበ ጥበብ ለማውጣት እንደምንችል እርግጥ ነገር ነው ። ቅዱስ ወንጌል ኅሡ ወትረክቡ ጐድጕዱ ወይትረኀው ለከሙ ይላል ። እንደ ፈሎሶፍም መፈለግን መቻል ይከተለዋል ያላል ። ስለዚህ ጸሐይ ሳለች ሩጥ አባት ሳለ አጊጥ እንደሚባለው ምሳሌ ልዑል አልጋ ወራሽ ሳሉልን እኒህን ቃሎች እየተከተልን እንድንማርና እንድንሰራ አምላክ ይርዳን ።

ኪዳነ ማርያም አበራ

ስለ ተማሪ ቤት እርዳታ።

ልዑል አልጋ ወራሽ ያገሬችንን ልጆች በፈረንሳዊ በእንግሊዝ፤በኢጣልያ፤በአሜሪካ፤እንዲሁም ዕውቀት ባለበት አገር ሁሉ እየላኩ በምድር ላይ ሲሄዱ ለባቡሩ ዋጋ፤ በባሕር ላይ ሲሄዱ ለመርከቡ ዋጋ፤ ከፍለው ከሚማሩበትም አገር ከደረሱ በኋላ ምግባቸውንና ልብሳቸውን ሌላም ለተማሪ ቤት የሚያስፈልገውን ሁሉ በገንዘባቸው ችለው ማስተማራቸው ዕውቀት የናፈቃት ኢትዮጵያን ከየ ሀገሩ በትምሕርት የቀዳትን ዕውቀት እየመገቧት ለማደስና ለማሠልጠን ነው እንጂ እነዚህ በየ ሀገሩ በብዙ ገንዘብ ያስተማሯቸው ልጆች ሳረጅ ይጦሩኛል ሳጣ ይሰጡኛል ብለው አይደለም፤ ጡረታውም ስጦታውም በውነት ለሀገራቸው ለኢትዮጵያ እንዲሆን ነው እንደዚህም ከሆነ አገር የንጉሥ ብቻ አይደለም የሕዝብም ነውና እንደዚህ መሆኑን ከተረዳነው ይኸንን ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ያበጁትን የቀና ጐዳና ተከትለን ልንሄድ ይገባናል ። ስለዚሁም ለተማሪ ቤቱ እርዳታ አሁን ለጊዜው መቶ ብር ።ባመት ባመት ኀምሳ ብር እሰጣለሁ ። ደግሞ ቸርነቱ የማያልቅበት አምላክ ለልዑል አልጋ ወራሽ ረጅሙን ዕድሜ ሰጥቶልን እኛንም ከቆየን ትምሕርት እየሰፋ ዕውቀት እየበዛ እንዲሄድ ተስፋ አለኝና ቀጥሎም ለመርዳት የተዘጋጀሁ ነኝ። ሐምሌ ፫ቀን ፲፱፻፲፯ ዓ ም

ፊታውራሪ ገብረ ማርያም

ስለ መረዳዳት ።

ስለ ትምህርት ቤት እርዳታ ከዕለት ምግብና ልብስ የሚተርፍ ገንዘብ የለኝም ብሰጥም የሚጠቅም አይሆን ብዬ ዝም እንዳልል አንድ ሴት የተናገረችው ይታሰበኛል ።

አንድ ሰው ከሚስቱና ከእህቱ ጋራ በበረሃ ተከታትሎ ሲሔድ ሁለት ወምበዴዎች አገኙት።ያንን ሰው ይዘው ሲተናነቁ ሚስቱ ትጮህ ጀመር ። እህቱ ግን አሁን እዚህ እበረሃ ማን ሊመጣልሽ ነው ቁ ቁ የምትይው፤ ይልቅ ነይ በድንጋይም በምንም እንርዳው አለችና ሰውዬውም ብርቱ ስለሆነ ረድተውት ጠላቶቹን አሸንፎ ሔደ ይባላል ። ድር ቢያብር አንበሳ ያስር ነውና እኔም ባቅሜ ክፉን ነገር ተረዳድቶ ማስወጣት መልካምን ነገር ተረዳድቶ ማስቀረት የሚገባ ስለሆነ መልካምን ለሚያስገኝ ክፉን ለሚያጠፋ የትምህርት ቤት እርዳታ ሶስት ብር እንድሰጥ ፈቃዴ ነው ።

ይህም መልካም ተክል ሥሩን እንዲዘረጋ፤ ፍሬው እንዲጠረን ለአሳዳጊዎቹ ለግርማዊት ንግሥትና ለልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ዕድሜ እንዲሰጥልን ታላቅ ምኞቴ ነው ። ወንድም አገኘሁ በዛብህ ።

በኢትዮጵያውያን ማኅበር ለሚቆመው ተማሪ ቤት እርዳታ እንሰጣለን ብለው ፊርማቸውን የሰጡ ሰዎች ።

ከ፳፫ኛ ቊጥር የመጣ ድምር ፬ሺ፯፻፴፭ ብር ተ፪ ሩብ

ፊታውራሪ ገብረ ማርያም መግቢያ ፩ ብር ባመት	፶	ብር
ፊውታራሪ ኃይሌ መግቢያ ፶ ብር ባመት	፲	ብር
ቀኛዝማች አጥናፍ ሰገድ፤	፴	ብር
ግራዝማች ዘገየ ቈለጭ፤	፲፭	ብር
ሙሴ ኒኅስ ጆዴጳን በመጀመሯ ፳፭ ብር ባመት	፲፭	ብር
አቶ በልሁ ዘረፋ፤	፭	ብር
አቶ ወንድም አገኘሁ በዛብህ፤	፫	ብር

ድምር ፬ሺ፰፻፴፰ ብር ተ፪ ሩብ

ከኢጣልያ መንግሥት ሌጋሲዮን በቴሌግራም የመጣ ቃል።

ሰኔ ፳፯ ቀን የለተወሬ ።

ፕሬስ ደ ፖዝ (ቤርሊን ።)

የንግሊዝ ወታደሮች ሻሚን በሚባል የውጭ አገር ኰሎኒ ዙሯ ምሽግ ለመሥራት ብዙ እሾሃም ሽቦና ላሸዋ መክተቻ ጆንያ ተቀበሉ፤(ጆንያው አሸዋ እየተሞላ ላይ በላይ ተነባብሮ ድድቅ የሚሆን ነው)ለውጭ አገር ሰዎች ስንቅ ለማቀበል በካንቶን መርከብ መቆሚያ አለች ሰለቱን መርከበኞች ይገባሉ የዲፕሎማት ዝምድና ጠንከረ ሰስት የቺና ኰሚሰሮች በውጭ አገር መንግሥት መልክተኞች ለሽምግልና ከተመረጡ።የቺናን ፲፫ ጥያቄ የውጭ አገር መንግሥት ስላልተቀበለ ተሸፉ ።

የጀርመን ካቢኔት የውጭ አገር ፖለቲካውን በሬክስታግ አያማክርም አያስታውቅም የመተማመን ውል ማስታቂያው ምላሽ ካልመጣለት ከፓሪስ እንደመጣው ወሬ አዲሱ የሪፍ ጦር የፈረንሳዊን ጦር በስተቀኝ በኩል ተጭኖታል።በመከከል በኩል ፈረንሣዊ ወደ ፊት ገፍቷል፤ ስለሆነ ግን በሁሉ በኩል አልቀናውም ።

የአሜሪካ የጥርስ ሀኪሞች መልክተኞች የጥርስ ህክምናን ነገር ከሮፓ ለመመርመር የሮፓን ከተማ ዞረው ቤስሊን ገቡ።

ከዮ ስለ ፈረንሣዊ እዳ ሂሳብ አሁን በቅርብ ወደ ዋሽንግቶን የሚሄዱትን አለቃ ይመርጣል ።

የንግሊዝ መንግሥት ሹማምንቶች ኰሎኙን የሚለቁበትን ቀን አልቈረጡም ።

በልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

መጀመሪያ ዓመት ፡ ቁጥር ፴ ።
1re ANNÉE № 30

ሐሙስ ሐምሌ ፲፮ ቀን ፲፱፻፲፯ ዓ ም።
JEUDI 23 JUILLET 1925

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

የጋዜጣው ዲሬክተር ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት
ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።
Gabré Christo Taklé Haymanot
Dirécteur

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ፡ ሲገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ስለ መንፈሳዊ አገልግሎት ።

ለሃይማኖት ማስረጃ አስቀድሜ የጻፍኋት ይህቺ ናት ትእዛዙን ብንሰማ ሕጉን ብንጠብቅ በውነት የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት እንሆናለን።

የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራትና መውደድ ነው እግዚአብሔርን የሚወድ ሃይማኖቱ አይለወጥም ክሕደት ኑፋቄ ትዕቢት በልቡናው አይገባምና እግዚአብሔርን መውደድ ማለት የሚወደውን መልካም ሥራ ሁሉ ማድረግ ነው ።ፈጣሪህ እግዚአብሔርን በፍጹም ልብህ በፍጹም ሰውነትህ በፍጹም ኃይልህ በፍጹም አሳብህ ውደደው። ሉቃ ፲ ፳፯

ሁለተኛ እኛ ካህናቶች ትእግሥትን ይዘን በፍጹም ልቡና ፈጣሪያችንን ብንለምነው የጸለይነው ጸሎት የሠዋነው መሥዋዕት ያርግልናል ። በምቀኝነት ሰንሰለት የታሠረ ሰው ምቀኝነት ሰንሰለት ከእግረ ልቡናው ወልቆ ካልወደቀለት የሕይወቱ ሐሣብ አይተካከልለትምና እንደዚህ ቻምሮ ያለ ሰው ማማለድ አይችልም።እንደ ሙሴ እንደ ዳዊት ራስን አሳልፎ መስጠት ይገባል።በመታገሣችሁ ነፍሳችሁን ትወዷታላችሁ መከራውንም ታግሦ የተቀበለ እሱ ይድናል። ልቡናቸው ንጹሕ የሆነ ሰዎች ንዑዳን ክቡራን ናቸው እነሱ እግዚአብሔርን ያዩታልና ማቴ ፭ ፰ ። በጸሎታችን ዘወትር እናስባችኋለን ተሰሎ ፩ ፪ ።

አምኖ የሚጸልዩት ጸሎት ሕመምተኛውን ያድነዋል እግዚአብሔርም ከመኝታው ያስነሳዋል ኃጢአትም ቢኖርበት ይሰረይለታል ። ኃጢአታችሁን እስበሳችሁ ተነጋገሩ ለወንድሞቻችሁ ጸልዩ ፤ ከፍዳ ትድኑ ዘንድ ፤ የጻድቅ ጸሎት ፈጽማ ታድናለች ። ያዕ ም ፭ ፲፮ ለእግዚአብሔር የምሥጋና መሥዋዕት አቅርብ የከበረች መሥዋዕት ታከብረኛለች ። በዚችው በከበረች መሥዋዕት እግዚአብሔር ማዳኑን ገለጠ ። ራስን አሳልፎ ስለመስጠት ሙሴ እሊህን ሕዝብ ከምታጠፋ እኔን ከሕይወት ደብዳቤህ ፋቀኝ ብሏል ።

እኔን ቀጣ እንጂ እሊህ በጎች ምን አደረጉ ሳሙኤል ካልዕ ም ፳፬ ቍጥር ፲፯ ። ሶስተኛ ካህናቶች ነን ብለን በስማችን ተመክተን ሕጉን ትዕዛዙን አፍርሰን እንኖራለን ስለዚህ ልቡና የሚረዳው ስድስት ነገር አለና የዚህን ልማድ መተው ይገባናል ። መጀመሪያ ካህን ተብሎ እየተጸራ የስሙን ትርጓሜ ስንኳን አለማወቅ ። ሁለተኛ በውጭ ካሉት ምዕመናን አንሶ ሥጋውን ደሙን ሳይቀበሉ መኖር ። ሶስተኛ ከቤተ ክርስቲያን ሲያገለግሉ አድሮ በቅዳሴ ጊዜ መሰሥ ብሎ መውጣት ያገልግሎታችንን አስብ መበለት በነግህ መጥታ እፏ ተቀብላው መሄድ ። አራተኛ ከቤተ ክርስቲያን ገብቶ ጸሎትና የታዘዘውን ቃለ እግዚአብሔር መቀበል ቀርቶ ያልታዘዘውን ጨዋታና ነገር መያዝ እንደ ዝግባ ረዝሞ የቀረ ግንድ እድሜያችንን በትዕቢት መጋዝ መቁረጥ ነው።አምስተኛ ዘሕጻናት በምንዲ የተደረገውን መዋሠፍት እየሰማን ግዕዛችን ከሕፃናት ግዕዝ በማነሱ እጅግ ያስደንቃል ።ስድስተኛ አባቶቻችን መምሕራን በፍልሰታና በወርሀ ጾም መጻሕፍት እንስማ ብለው በጀመሩ ጊዜ ምዕመናን ሲሰሙ ካህናት አንድቃል አለመስማት ይህ ሁሉ መቅረቱ ምልአተ ኃጢአት እንዳይመለስብን ማሰብና ማዘን ንስሀ መግባት ይገባል ውሻ ወደ ጥጥ ሚዳቋ ወደ ሊጥ እንዲሉ የእግዚአብሔር ምግቡ ንስሀ ሀዘን ነው።

አንደኛ ። ሕጌንና ትእዛዜን ብትጠብቁና ሰንበታቴን ብታከብሩ ድልባችሁን ትበላላችሁ ። የወይናችሁም መጥመቂያ ይመላል እንዳለ። ሁለተኛ፡በቤተ ክርስቲያን ላይ ቀሳውስትን ሹሙ እንዳለ ። ፫ተኛ እውነት እላችኋለሁ የሰውን ልጅ ሥጋ ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ በላንት ሕይወት የላችሁም ሥጋዬን የበላ ደሜንም የጠጣ ለርሱ የዘላለም ሕይወት አለው

እኔም በኋለኛው ቀን አስነሣዋለሁ ። ሥጋዬ በውነት መብል ነውና ደሜም በውነት መጠጥ ነውና ። ሥጋዬን የበላ ደሜንም የጠጣ በኔ ይኖራል እኔም በርሱ እኖራለሁ ። ዮሐ ፮ ፶፫ —፶፬

አራተኛ ። የቄሱ ቡራኬና ማሰናበት የቁርባንም መመለስ ሳይፈጸም ቅዱስ ወንጌል ከተነበበ በኋላ ጭንቅ ነገር ካላገኘው በቀር ከቤተ ክርስቲያን አንድም ሰው አይውጣ ። ፍትሐ ነገ አን ቀጽ ፲፪ በስ ፺፪ ። ደግመኛም የእግዚአብሔር ቤትስ ከፍርሃት ጋራ የጸሎት ቦታ ነው እንጂ የጨዋታ ቦታ አይደለምና በቤተ ክርስቲያን ማንም ፈጽሞ አይናገር ። በቤተ ክርስቲያንም የሚናገር ይለይ እንዳለ ። ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፲፪ በደስ ፲፯ ።

አምስተኛ ። ጠቢብ ይህችን ይሰማል ጥበቡንም ያበዛል መምር ያለው ሰው የተሠወረ ነገርንና ምሳሌን ያውቃል ምሳ ፩፫፡፲፯ና መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሓ ግቡ ማቴ ፫፪ እስ በሳችሁ ኃጢአታችሁን ተማመኑ ያዕ ም ፭ ቁ ፲፯። በግፍ ሲበደል ኀዘንን በበጎ ሥራ ለሚታገሣት ሰው የእግዚአብሔር ጸጋ ትሰጣለችና ፩ ጴጥ ም ፪ ቁ ፲፱፣

አራተኛ። ደግና መንፈሳዊ ትእዛዝ በመጻሕፍት ላይ ተጽፈው ሳሉ እኛ ካህናቶች ለህዝብ እንደ ማስተማር የሐገራችን ሕዝብ መጻሕፍት ባለመመርመር በኀዘን ዓይሀ ሰጥመው ፊታቸውን እየነጩ ደረታቸውን እየጸፉ እርቃናቸውን ጥለው ሲወድቁ ሲነሱ እያየን ዝም ማለታችን ይገርማል የሐመር ምስል የሆነ የመጽሐፍን ቃል ብናስተምራቸው እንዲያደናቸው ስናውቅ እንደዚሁ አድርገው ማዘን እንዳይገባ መጻሕፍት ተበብረውብታል ። መላእክትም ሴቲቱን አሏት አንቺ ምን ያስለቅስሻል ማንንስ ትፈልጊያለሽ ዮሐንስ ም ፳ ቁጥር ፲፫ ።ለስ እግዚአብሔር ብሎ የሚያዝኑት ኃዘን ሕይወትን ያመጣል ለዓለሙ ብሎ የሚያዝኑት ኃዘን ግን ሞትን ያመጣል ፪ ቆሮ ምዕ ፯ ቁ ፲ ። ወለካህን ለእመ ሞተ አሀዱ ይትከዝ እምአዝማዲሁ ኢይትከዝ ላዕሌሁ ከመ ተረፈ አህዛብ ወኢይስጥጥ አልባሲሁ ወኢያዝልፍ ብከየ ወኢይንጺ ስዕርተ ርዕሱ አላ ያዕኩዮ ለእግዚአብሔር ብዙሀ ወይኩን ተአጋሢ በመከራሁ ከመ ኢዮብ ጻድቅ እንዳለ ፍትሀ ነገሥት አንቀጽ ፳፪ በስ ፶፫ መጽን ፲ ።

ከዘመዶቹ ወገን አንዱ ቢሞት ካህን እንደ አሕዛብ አይዘን ልብሱን አይቅደድ አዘውትሮ አያልቅስ ራሱንም አይላጭ ለእግዚአብሔር ያመሰግን እንጂ [illegible] ሁሉ [illegible] ታጋሽ ይሁን ፍ ነ አን ፳፪

ወኢይደልወነ ከመ ንሕዝን በእንተ እለ ኖሙ ከመ ከሎሙ አህዛብ እለ አልቦሙ ተስፋ ተሰሎንቄ ፲፭ አ ።

ስለሞቱ ሰዎች ተስፋ ትንሣኤ እንደሌላቸው እንዳሕዛብ ልናዝን አይገባም ይላል ጳውሎስ

በአፊ ወርቅም ካራተኛው እስከምስተኛው ክፍል ንባቡን ከነትርጓሜው ለተመለከተው ይገኛል ።

አምስተኛ ። ሲያውቁ ከመበደል በድንቁርና ደንጊያ ላይ ቁሞ የሚለምኑት ልመና እንዲሻል ምሳሌ ያለው ነቢይ ያስረዳል ። ፪ኛ።ይህ ሁሉ ጉድፍ ዓይነ ልቡናችን ውስጥ ገብቶ ሳለ ከሰው ዓይነ ልቡና ሃይማኖት ጉድፍን ለማውጣት እጃችንን እንዘረጋንለን ። በወንድምኅ ዓይን ያለውን ጉድፍ ለምን ላውጣልህ ትለዋለህ ባንተ ዓይን ያለውን ጉድፍ ሳታይ ማቴ ም፯ ቁ፫

ሰባተኛ። ባንድ ቤት ሁለት ወደን ለእግዚአብሔርና ለገንዘብ መገዛት እንችላለን ብለን በሁለት ልቡና ሀረግ ተስበን ሰውነታችን በቅናት ቀስት ተነድፎ ይኖራል ።፩ ባሻ ለሁለት ጌታ መገዛት አይችልም ማቴ ም ፮ ቁ ፳፬ ።

ስምንተኛ ፤ የወለደችን ቤተክርስቲያን እንደመርዳት እንደ ማገልገል ሁሉ የንጀራ እናት ገባያ ትሻላለች ብለን ሳትወልደን እሷን መውደድ ነው። የጌታችንን ሥጋውን ደሙን ይዘን ወደ መቅደስ በምንገባበት ጊዜ ብዙ መወደድ አለን ዕብ ምዕ ፲ ፲፱

የናቴ ልጆች ስለኔ ተጣሉ የራሴን የወይን ቦታ ያልጠበቅሁ የወይን ቦታ ጠባቂ አደረጉኝ መሐ ም፩ ቁ፮ ።

ዘጠኘኛ ፤ እግዚአብሔር አባታችንን የወሳድ መካን አርገነው ስንኖር እግዚአብሔር እውነተኛው ዳኛ ፍርዱ መጥቶ የበየነውን እንዲሆን ያባት ደሀ መሆናችንን እናስብ ታሪክ እንዳባ መቃርዮስ ኪዳን አምላክ ብርሃንን ተመልከት።

ሰማይ ስማ ምድርም አድምጭ እግዚአብሔር እንዲህ ብሎ ተናግሯልና ልጅ ወለድኩ አሳደኩም እነኛ ግን ወነጀሉኝ ላም እንኳ ጌታውን ያውቃል አህያም ገለባ የሚበላበትን የጌታው ቤት ያውቃል እስራኤል ግን ወገኖቹ አላወቁኝም አልተረዱኝም ኢሳ ም፩ ቁ፪ ።

ጌታ መላእክትን አስከትሎ በጌትነት በመጣ ጊዜ በጌትነቱ ዙፋን ይቀመጣል አሕዛብ ሁሉ በፊቱ ይሰበሰባሉ እረኛ በጎችን ከፍየሎች እየራሳቸው እንዲለይ አባግዕን ከፍየሎች ለይቶ በቀኝ ያቆማቸዋል ማቴ ም ፳፭ ቁ ፴፬።

አቤቱ በጥላህ ማን ያድራል በተቀደሰው ተራራህ ማን ይኖራል በቅንነት የሚሔድ ጽድቅንም የሚያደርግ በልቡም እውነት የሚኖር በመላሱም የማያማ በባልንጀራውም ክፉ ያላደረገ ባልንጀራውንም ያልሰደበ ቸልተኛውን በፊቱ የናቀ ።

አስረኛ፡ይህንን ሁሉ ነገረ ይቅር ብሎ እንዲታረቀን አድልዎ ወደሌለበት በዚህ ሁሉ ላይ ንጉሠ ነገሥት ተብሎ ወደነገሠ ንጉሥ ፍቅር ዘንድ ሂደን የርቅ ስልፋ እናድርግ ።

ወእመኒ አእመርኩ ነገረ ኵሉ ሰብእ ወነገረ ኵሉ መላእክት ወተፋቅሮ አልብየ ኮንኩ ከመ ድምፀ ብርት ዘይነቁ ወእመ አኮ ከመ ከበሮ ዘይጠብጥ ወእመኒ ተነበይኩ ወአእመርኩ ኵሎ ዘኀቡዕ ወኵሎ ጥበበ ወእመኒ ብየ ሃይማኖት እስከ አፈልስ ደብረ ወተፋቅሮ አልብየ ወአልቦ ዘረባህኩ ተፋቅሮ ያሥተዔግሥ ተፋቅሮ ያስተምሕር ተፋቅሮ ያስተቃንዕ ወኢያስተኃፍር ወኢያስተኤቢ ልበ ወኢየኃሥሥ ተድላ ለበሕቲቱ ወኢያስተማዕእ ወኢይሄሊ እኩየ ወኢያስተፌሥሕ በግፍዕ ወያስተፌሥሕ በጽድቅ ። ቆሮ ም ፲፫ ቁ ፩ ጴጥ ቀዳ ም ፬ ቁ ፰

የሰውን ሁሉ ቋንቋ ባውቅ የመላእክትንም ቋንቋ ፤ ፍቅር ከሌለኝ እንደሚመታ ደወል ሆንኩ ወይም እንደሚመታ ከበሮ ሆንኩ ኃላፍያትን መጻእያትን ብናገር የተሰወረውን ሁሉ ባውቅ እውቀትንም ሃይማኖት ቢኖረኝ ተራራ እስከማፍለስ ደርሼ ፍቅር ከሌለኝ የጠቀምሁት የለም ፍቅር ያስታግሣል ፍቅር ያስተዛዝናል ፍቅር ለበጎ ያቀናል አያሳፍርም አያስተፋፍርም ልብ አያኰራም ለብቻየ ደስታ ላድርግ አያሰኝም አያስተዛዝንም ክፉውን ነገር አያሳስብም በማይገባ በግፍ ደስ አይለውም በውነት ደስ ይለዋል እንጂ ።

አለቃ ሠርፀ ዘደብረ ሩፋኤል።

የሥልጣኔ ትምርት መልካም እንደሆነ የሚያመለክት ምሳሌ ።

አሁን እንስሳን ሁሉ ስናያቸው መልካም አእምሮ እንዳላቸው እናያለን የንብ ጥበብና ሥራ ደግሞ ይልቁንም አድማቸውን አንድነትን አበርትተው መሥራታቸው ባንድ መንገድም አውራቸውን ተከትለው መሄዳቸው እንዴት ይገርማል ።

በዚህ አንድነታቸውንና ሥራቸው በትጋታቸው ብዙት መልካም ከሁሉ የጣፈጠ ምግብ ማርን ተመግበው ይኖራሉ ለራሳቸውም ብቻ አይደለም እኛንም ጭምር ይመግቡናል እንጂ ።

ደግሞም ማናቸውም እንስሳ ቢሆን ትልቆች ዝሆኖችም ቢሆኑ ትንሾች ዎፎችም ቢሆኑ ሁላችውም ተኝተው ሳሉ ከመከከላቸው አንዱ የሚጎዳቸው አውሬ በሩቅ አይቶ ወይም ሽታ ሰምቶ ከተኛበት ብድግ ብሎ ከሚጎዳቸው ለመዳን ሲነቃ ቢያዩት የቀሩትም ትንንሾችም ቢሆኑ ትልልቆችም ቢሆኑ ዝም ብለው ጥቂቶቹ የነቁት ያስቡበት እኛ ምን ቸገረን ብለው ንቀው አይተኙም ሁሉም ብድግ ብለው መዳኛቸውን ያስባሉ እንጂ ዝሆኖችም ኃይለኞች እንኳ ቢሆኑ አይተኙም ይነቃሉ ፤ ደግሞም ከአንበሳ ጉበዝ ልበ ሙሉ ትዕቢተኛ የሆነ የለም ፤ እሱ እንኳ ነቅቶ ካልተሰናዳ ዘንግቶ ከተኛ አንድ ትንሽ ልጅ በተኛበት መቀነቻውን ሰብሮ ያበላሸዋል አንበሳ ከነቃ ግን የሚያስፈራ ነው ሰውን ግን እግዚአብሔር ከሁሉ ለይቶ ሙሉ አእምሮ ሰጥቶት በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው ስለዚህ መንቃትና ማስተዋል ይገባዋል በማለት ላገራችን ለኢትዮጵያ የሥልጣኔ ትምሕርት እንመኝላት ይኸንኑ መመኘትና መሥራት የሚገባቸው ለጥቂቶች ሰዎች አይደለም ወይም ትልልቆች ብቻቸውን መሥራት ወይም ትንንሾች ለብቻቸው ማሰብ አይደለም ከኢትዮጵያ እወለዳለሁ ላገሬ እሞታለሁ የሚል ሁሉ የሥልጣኔ ትምርት መመኘትና ማቆም ይገባዋል፤ ለምን ቢባል የጦር መሣሪያ ተሰርቶ የሚሰናዳ በሥልጣኔ ትምርት ነው ። የጠላትን ፖሊቲክ መጠባበቅ የሚቻል በስልጣኔ ነው ። አንድነት መተባበር የሚገኘው በስልጣኔ ትምርት ነው ። ገንዘብ የሚጠራቀምና አገር ባለጸጋ የሚሆነው በሥልጣኔ ትምርት ነው ። ያገር ነፃነትና ማዕረግ እንዳለ የሚኖር በሥልጣኔ ትምርት ነው ።

ነገር ግን አንዳንድ ሰነፍ ሰዎች አሉ የሥልጣኔ ትምርት ማለት የፈረንሣይ ቋንቋ ወይም የእንግሊዝ ወይም የኢጣልያን የጀርመንን ቋንቋ ማወቅ ብቻ የሚመስላቸው ፤ ለሕዝብም ይህኑ የሚሰብኩ ፤ ይህ መቸም የሰነፍ ወሬ ነው ። የሥልጣኔ ትምርት ማለት ተምሮ ኤንጂኒሩ ሆኖ ፋብሪክ አቁሞ መድፍ መትረየስ ማውዘር ጥይት መሥራት ።

ወይም ተምሮ ምኒሮሎጂ ሆኖ ወርቅን ብርን ነሃስን ብረትን እርሳስን ከምድር ማውጣት ይኸ ሥራ ሲሠራ ስንት ድሆች በደመወዝ ይጠቀማሉ ስንትስ ኩባኒዮች ሀነው ይህን ገንዘብ ከመሬት ውስጥ አውጥተው ጌታ ይሆኑበታል ይመስልሃል ። ወይም ተምሮ ጂኦሎጂስት ሆኖ በማኪና ጋሻ መሬት አርሶ በምርቱ መጠቀም በብር አቅንቶ ባለ መቶ ሺ መሆን በስልጣኔ የሚሰራውን ለመቁጠር አይቻልም ይበዛል እንዳለፈው ግን የስልጣኔ ትምሕርት ማለት ይኸ ይኸና ይኸን የመሰለ ሁሉ ነው ።

ደግሞም ይኸንን የተቈጠረውን ሁሉ ለመስራት ከሰማይ የራቀ አስመስሎ የማይሆን የማይቻል ነው ብሎ በገዛ ሐሳብ ሰንፎ ድል አለመሆን በስልጣኔ ትምሕርት ነው የሚገኘው ነገር ግን የሆነ ሆኖ ይኸን የስልጣኔ ትምሕርት ለመማር በየስራው ክፍል ትልልቅ መጻሕፍት ስንክሳር የሚያክሉ የስራ መጻሕፍት አሉ እነዚህን መጻሕፍት ሳይማሩ መስራት አይቻልም እነዚህም መጻሕፍት በኛ ቋንቋ አልተጻፉም ተርጉሞ ለመጻፍም ይኸን ትልልቅ ሥራ የተማረ ሰው የለንምና አይቻለንም ። የተማረ ሰው እንኳ ቢኖር ለመተርጐሙ ባማርኛ ቋንቋ አይገኝለትም ይባላል ።

ለምሳሌ አሁን ባንድ ሞቶር የሚዞር ማኪና ውስጥ ማግኔቶ ስሊንደር ቱሊ የሚባል ስም አለ ፤ እንግዴህ እንደዚህ ያለው ስም ባማርኛ ትርጉም የሌለው በአንድ የስራ መጽሐፍ ውስጥ አምስት ሺ አስር ሺ ይገኛል ፤ ስለዚህ የውሮፓን የስልጣኔ ስራ ለማግኘት በግድ በፊት አንድ የአውሮፓን ቋንቋ መማር ያስፈልገናል ። የአውሮፓን ቋንቋ መማር መፈለጉ ለዚህ ነው እንጂ ለማስተርጐም ብቻ አይደለምና ስለዚህ ሆነ ብለን ለልጆቻችን እናስብ ለልጆቻችን ማለትም ለየራሳችን ልጆች ብቻ አይደለም ላገር ልጅ ሁሉ ነው እንጂ እኔ ሁልጊዜ ይኸን ቃል መላልሼ መጻፌ ጌቶቼን ወንድሞቼን በስራ በጉዳይ ብዙት እንዳይረሱት ለማስታወስ ወይም የማይረባ መስሏቸው እንዳይንቁት ለማመልከት ነው ።

ፊታውራሪ ደሬሳ ።

ስለ ሀገር ፍቅር ።

ለሰው ሁሉ አባትና እናቱ ሀገሩ ነው ፤ ለዚህ የሚመሰክር በዓለም ያለ የሰው ሁሉ ፍጥረት ፤ አባቱና እናቱም ከመሰረት አንድ ሁኖ ሳለ በዚህ በሚኖርበት በዘመናዊ አገር ስለተለያየ እኔ ኢትዮጵያዊ ነኝ ለኢትዮጵያ ደሜን አፈሳለሁ ፤ እኔ ፈረንሳዊ ነኝ ለፈረንሳዊ አገር እሞታለሁ ብሎ ይላል ። እኔ ዘረ አዳም ነኝ ለዘረ አዳም እረዳለሁ ቢል ኖሮ ጥል ቂም በቀል በዓለም በጠፋና ትግልና ጦርነት ሁሉ ከሰው ተቀዋሚ ፍጥረት ጋራ ብቻ በሆን ነበር ፤ ነገር ግን ከጥንት ጀምሮ ሰው ባገር ፍቅር ተለያየ አውሮፓ ባለፈው ጦርነት ጊዜ አባት እናቴን ሳይል ያገር ፍቅር በልጠበት ዘመዶቹን ሁሉ እያጣ እጦርነት ውስጥ ለሀገሩ ደሙን እያፈሰሰ ወድቆ የቀረ ሕዝብ ቁጥር የለውም ፤ ይህም አዲስ ነገር አይደለም እኛም አባትና እናታችን ሀገራችን ስለሆነች ክፉ ሀሳብና ምቀኝነትን ሳንቀላቅል በሰላም ጊዜ የሚገባንን ሥራ ልንፈጽምላትና በሚያስፈልጋትም ሰዓት ደማችንን ልናፈስላት የተገባ ነው፤ በሁኑ ዘመን አንዳንዶች በታች ሆነው የሚገዙ ነጻነት የሌላቸው ፤ ነገር ግን ያገር ፍቅር ምን እንደሆነ የተረዱ የቅኝ አገር ሕዝቦች ደማቸውን እስከማፍሰስ እየተጋበዙ ሀገራቸውን ነጻ አወጡ ። ቀድሞም ሕጻናቶቻቸውን በማስተማር በጥቂት ዘመን ከታላላቅ መንግሥት በሥልጣኔና በብልሀት እኩዮች ሆነው ኃይላቸውን የገለጹ መንግሥቶች አሉ ለዚህ ሁሉ የሚያገለግል ትምሕርት ነው ።

እግዚአብሔርን የሚወድ ሰው የእግዚአብሔን ትእዛዝ የሚፈጽም ነው ። ትእዛዙንም ለመፈጸም አስቀድሞ ትእዛዙን

ማወቅ ያስፈልጋል ። ለማወቅም መማር የግድ የሚያሻ ነገር ሆኖ ተገኘ ። ከዚህ በፊት ብዙ ጊዜ እንደተባለ ሀገሩን የሚወድ ሰው ፍቅሩን በሚገባው ሥራ መግለጽ ያስፈልገዋል ። ነገር ግን ይህ ስላገር ፍቅር የሚሠራ የሚገባ ሥራ የተባለ ለሠሪው እንዴት ሊገለጽለት ይችላል ፤ የትምሕርት ቤት ባይኖርና ባይማር ለዚህ ሁሉ አስተዋይና ቸር የነበሩ ታላቁ ንጉሠ ነገሥት አጼ ምኒልክ ላገራቸው ልማት ለሕዝባቸው ንቃት ዋና ነገር አድርገው ካሰቡት ሥራ መጀመፘ የትምሕርት ቤትን አቆሙ ፤ ያለጥርጥር ሀሳባቸው በየሀገሩ አውራጃ ሁሉ ሌሎችም የትምሕርት ቤት ለመመስረት ነበረ እንጂ ባንድና በሁለት ትምሕርት ቤት ተወስኖ ለመቅረት አልነበረም ፤ ይህም ያቆሙት የዳግማዊ ምኒልክ ተማሪ ቤት ለኢትዮጵያ መንግሥት የሚያገለግሉ በጽኑ ቅጣትና በመልካም ትምሕርት ያደጉ ልዩ ልዩ የአውሮፓ ቋንቋ ያወቁ የውቀትን ጣዕም የቀመሱና ከፍ ላለ ብልሀት ትምሕርት የደረሱ ልጆች ሰጥቷል ። እስካሁንም ያለማቋረጥ ሥራውን እየሠራ መንግሥትን መጥቀም አልተወም ። ባባታቸው ዙፋን የተቀመጡ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱም እግዚአብሔር በፈቃዱ የደጉ አባታቸውን ውጥን ለመፈጸም ያስነሳቸው ስለሆኑ ለኢትዮጵያ ታላቅ መመኪያ የነበሩ ግርማዊ አባታቸው የጀመሩትን የሥልጣኔ ሥራ ከልዑል አልጋ ወራሻቸው ጋራ እየተረዳዱ ለማከናወን ቸል አላሉምና እግዚአብሔር ለዘለዓለም ይጠብቅልን፡እነሆ ዛሬ ደግሞ በትጋት ለሀገራቸው የሚያስቡ ጌታችን ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ስለሀገራቸው ጥቅም በገዛ ገንዘባቸው የትምሕርት ቤት አቆሙ። አዲሱን ሥልጣኔ ስለሚከተል ሀሳባቸውና ስለብዙ ድካማቸው ምስጋናችንን የምንገልጽበት ቃል አናገኝም ።

መንግሥት ያለሕዝብ ሕዝብ ያለመንግሥት አይሆንም ተባለ ይህም በሥራ ሁሉ በመረዳዳት ነው እንጂ በመግዛትና በመገዛት ብቻ አይደለም ። ስለዚህ ይህንን የደጉ ጌታችንን መልካም ሥራ ልብ አድርጎ በመመልከት ለኢትዮጵያ በማኅበር የትምሕርት ቤት ለማቆም ነገሩን ለወጠኑ ለመንግሥትና ለሀገር እርዳታ ስለሆነ መጀመፘ ምሥጋናዬን አቀርብላቸው ዘንድ የተገባኝ መስሎ ይታየኛል ።

ሁለተኛ ይህች ትንሽ የሆነች በሙሉ ልብና ደስታ የማቀርባት ከኢምንት የምትቆጠር ስጦታዬ ለዚህ መልካም ምኞትና ሀሳብ ሥራ መከናወኛ ከብዙ ጓደኞቼ ጋራ ሆና ትረዳለች በማለት በተሰጠኝ አቅም ከጉልበቴ ፍሬ ባመት ባመቱ ፭ ፭ ብር ለተማሪ ቤት እሰጣለሁ ስል ደስታዬን እገልጻለሁ ።

እንደዜሁ ቅሬ ሲሉ ጸላቶችሽ ።
በጨለማ ኑሪ ፀሐይ አይውጣልሽ ።
ሰው ሳይሰማ ሌሊት ሁሉም ሲዝቱብሽ
በብርሃን ተፈሪ ተገለጸ ኃይልሽ ።
እንቺም ባለድል ነሽ ደግ አባቢ አገኘሽ
ክበሪ በጠቅል ስጋትም አደግባሽ ።
ሰላም ላንቺ ይሁን ነውና ገንዘብሽ
መንግሥት እንዲታፈር ሥራት
እንዳደላላ ።
ቀን ሌት ስትደክም በጸሎት ሳትዛላ።
እስባ ዘውዲቱ ላማራ ስጋላ ።
ትጠብቀዋለች እንደራሴ ብላ ።

ክብርና ምስጋና በጣም ላንተ ይሁን
ብርሃን ለሰጠኸን ድል አርገኸ
ጨለማን ።
አምላክ ይጠብቅኸ እስከ ብዙ ዘመን ።
በሰላም ለመኖር ለማየት ከበታን ።
በኃይለ ሥላሴ እዜህ ከደረስን ።
ዕንቅፋት መጐላላት ሌት እንዳያገኘን
እንኑር በሰላም እንሂድ በብርሃን ።
ሐኪም ታፈቅራለች በጸና በብርቱ ።
ትጠብቀዋለች ራስዋን ዘውዲቱ ።
ብርሃን ተወለደ ለዓለም ሰው ሁሉ።
በሰላም ሁናችሁ ሥራውን አስተውሉ

ወልደጊዮርጊስ ወልደዮሐንስ

የትምሕርት ቤት ለማቆም ስለሚሰጠው የእርዳታ ገንዘብ ።

እግዚአብሔር በቸርነቱ ብዛት ይህንን መልካም አሳቡ ከአሰማኝ ለእንደዚህ ያለው ለመልካሙ አሳብ ሁሉ ተግቶ መርዳት የሚገባኝ ነውና የሚቻለኝን ያህል በየመቱ አስር አስር ብር እንድረዳ ፈቃዴ ነው ። ደግሞ እግዚአብሔር በቸርነቱ ይኸ የታሰበው የትምሕርት ቤት ቆሞ ፍሬውን ለማየት ያብቃኝ የዚህንም የትምሕርት ቤት ዋና ረዳትና አስተናባሪ የሚሆኑ ጌታችንን ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንንን በሰላም አኑሮ የሕፃናቶቻችን በጐ መሪ እንዲያደርግልን መከራና ውርደትን ባንድነት በትእግሥት ወደ ቻለው ሁሉን ለማድረግም ወደ ሚቻለው አምላክ እለምናለሁ ።

ክቡር ዲሬክተር ወዳጄ ሆይ ለዜህ ለተማሪ ቤት ማናቸውም እንዲዘጋጅና እንደሚቀና የምትጨነቁበት እናንተ ናችሁ ለነገሩ ግን እኔም ፍጻሜውን ለማየት በመጨነቅ እስባለሁ ። ይኸውም አሳቤ ለሀገሬ ለኢትዮጵያ የበጐ ሥራ መውደዴን ይገልጣል ።

ግራዝማች ይፍሩ

ብርሃንና ሰላምን በዕውቀታቸው ለመሰረቱ ዕድሜ ለልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ። ለኢትዮጵያ ልጆች ጥቅም የሚሆን ተስፋ ተገኝቶበታልና ይኸውም ዋና ተስፋ ስለ ኢትዮጵያውያን ልጆች የሚቆመው ተማሪ ቤት ነው ለሀገራችን ደሃ ታላቅ ጥቅም ነው ። እነሆ እኔ ድኃ ነኝና የድኃ ጥቅም በመሆኑ ደስ አለኝ ከደስታዬ በኋላ በብዙኀ ገንዘብ እንዳልረዳ አቅም ባለማግኘቴ አዝናለሁ ። ስለሆነ ያቅሜን ያህል ላገሬ መርዳት የሚያስፈልገኝ ነውና አቅሜ አነሰ ብሎ ይኸንን የሚመስል ያገር ጥቅም አለመረዳት ከስንፍና ይቆጠራል ። አሁንም ይኸችን ትንሽ እርዳታዬ ታላቅ ፍሬ እንድታፈራ እግዚአብሔርን ተስፋ አድርጌ አቅሜ እደከመ ድረስ ባመት ባመቱ አስር አስር ብር እሰጣለሁ ።

ደጀን ወልደ አረጋዊ ።

በኢትዮጵያውያን ማኅበር ለሚቆመው ተማሪ ቤት እርዳታ እንሰጣለን ብለው ፊርማቸውን የሰጡ ሰዎች ።

ከ፳፱ና ቍጥር የመጣ ድምር	፬ሺ፱፻፴፱	ብር ተ፪ ሩብ
አቶ ኃይለ ሚካኤል ገብረ ሥላሴ ።	፫	ብር
ወይዘሮ ወለቸ በሻሕ ።	፫	ብር
አቶ ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ ።	፭	ብር
ግራዝማች ይፍሩ ።	፲	ብር
አቶ ደጀን ወልደ አረጋዊ ።	፲	ብር
ወልደ ጻድቅ ወልደ ማርያም ።	፭	ብር
ድምር	፬ሺ፱፻፸፭	ብር ተ፪ሩብ

ከኢጣልያ መንግሥት ሌጋሲዮን በቴሌግራም የመጣ ቃል

የስምንተኛው ቀን ሐምሌ የለት ወሬ ።

ሞስኮ ፤ ሊሞቱ የተፈረደባቸው የጀርመን ተማሪዎች (ወታደሮች?)ቤተ ሰቦች እናንተ ባለቤታችሁ እስከትመረምሩልን ድረስ አይሙቱብን ብለው ለኮሚታት ጀነራል (ሽማግሌዎች) ስለ ለመኑ ፤ ነገሩ ኮሚታት ጀነራል እስቲፈርዱት ድረስ ፍርዱን ሳይፈጸም ቈይቷል ።

በልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

መጀመሪያ ዓመት ፥ ቁጥር ፴፩።
1re ANNÉE № 31

ሐሙስ ሐምሌ ፳፫ ቀን ፲፱፻፲፯ ዓ ም።
JEUDI 30 JUILLET 1925

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን በገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Son Altesse Impériale Teferi Makonnen , Héritier du trône d' Ethiopi , eprofondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix , a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

የጋዜጣው ዲሬክተር ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ይስታውቁ ።
Gabré Christo Taklé Haymanot
Diréсteur

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ ሲገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን የተወለዱበት ቀን መታሰቢያ በዓል ።

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን በሐምሌ አሥራ ሰባት ቀን ፲፰፻፹፬ ተወለዱ። ዘንድሮ ፴፫ ዓመታቸው በሐምሌ ፲፮ ቀን ፲፱፻፲፯ ዓመት ሞላ ።

ልዑል ተፈሪ መኰንን የተወለዱበት ቀን መታሰቢያ በዓል ሲከበር ኢትዮጵያ ልምላሜ ለብሳ ትታያለች። ልምላሜ አበባና ፍሬ እንዲገኝበት በተስፋ የሚጠበቅ ነገር ነው። ይኸም የልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ዘመን ለኢትዮጵያ የልምላሜና የሥልጣኔ አበባ የሰው ልብ የሚያጠግብ የትምርት ፍሬ ወደሚገኝበት ጊዜ የሚያደርስ ተስፋ ያለው ዘመን ነውና የሚስማማ አብነት አግኝቷል ።

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ረጅም ዕድሜ አግኝተው በዘመናቸው ኢትዮጵያ እንድትለማና እንደሚገባት እንድታድግ ተስፋችንና ምኞታችን ነው። ዕድሜ የሚያበዛ ሁሉንም እንደሚከናወን ማድረግ የሚቻለው እግዚአብሔር አምላክ ነውና የኢትዮጵያ ተስፋ የሆኑ አልጋ ወራሻችንን ለኢትዮጵያ ልማትና ጸናት የሚሆን ዕድሜ ያጥግብልን ብለን አምላካችንን እንለምናለን ።

ሐምሌ ፲፮ ቀን ዋና ክረምት ነው ። ግን የሰውን ደስታ የሚወድ አምላክ ደስታችን እንዳይደፈርስ ብራ አድርጎት ዋለ። በዚሁ ቀን ፫ ሰዓት ተኩል ሲሆን የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ተማሪ ቤት ተማሪዎችን የተማሪ ቤቱ ሹምና አስተማሪዎቻቸው አሠልፈው ወደ ልዑል አልጋ ወራሽ ግቢ ይዘዋቸው መጡ። በፊት በፊታቸው ፩ ትልቅ ባለ አንበሳ ሰንደቅ አላማ ሁለት ሰዎች ይዘውት ይሔዱ ነበር። በሰንደቅ አላማውም ላይ «የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት» የሚል ቃል በወርቅ ቀለም ተጽፎበት ነበር ።

ከዚያ ቀጥሎ ሙዚቀኞች አምረው ተሠልፈው ተከተሉ ከነሱ በኋላም ተማሪዎቹ ሁሉ ትንንሽ ሰንደቅ አላማ ይዘው ተሠርተው ልዑል አልጋ ወራሽ ወዳሉበት ቤት በር ሲደርሱ ቆሙና ሙዚቀኞቹ በሙዚቃ የሚያምር ዜማ አዜሙ ።

ከዚያ በኋላ ተማሪዎቹ ልዑል አልጋ ወራሽ ወዳሉበት እንዲገቡ ተፈቀደላቸውና አስተማሪዎቹም ተማሪዎቹም በልዑል አልጋ ወራሽ ፊት ተሠርተው ቆሙ ።

የተማሪ ቤቱ ሹም ክቡር ሐኪም ወርቅነህ ካስተማሪዎቹና በተማሪዎቹ ስም የምሥራች ቃል ከተናገሩ በኋላ ሙዚቀኞች ሙዚቃ እየመቱ ተማሪዎቹም በቃላቸው ደስ በሚያሰኝ ድምፅ በስምም ሁነው አቶ ኤፍሬም የተማሪ ቤቱ ፪ና ሹም እንደራሴ የገጠሙትን መዝሙር ዘመሩ ።

(መዝሙሩም የሚከተለው ነው ።)

፩ የኢትዮጵያን ብርሃን
ዘላለም ያኑርልን
የነፃነት አምባችንን
አምላክ ይጠብቅልን ።
ለሶስት ቀለሞች ፅናት
ላገር ለሕዝባችን ልማት።
ዕውቀት እውነት ሊነግሡብን
ተፈሪን ያኑርልን ።

፪ የተ መ ት ቤ ተማሮች
ለሠራታችን ሶስት ቀለሞች
ክብር መሆን በሕይወትበሞት
ነው ዋናው የኛ ምኞት
ለሶስት ቀለሞች ጽናት
ላገር ለሕዝባችን ልማት ።
ዕውቀት ዕውነት ሊነግሡብን
ተፈሪን ያኑርልን ።

ይህ መዝሙር ከተዘመረ በኋላ ዳር እስከ ዳር ተጨበጨበ ። ወዲያውም አቶ ኤፍሬም ቀጥሎ የተጻፈውን ቃል ተናገሩ ።

ልዑል ሆይ ።

በነህ ተማሮች ስም ሁኜ አንዲት የምስጋና ቃል ለመናገር የልዕልናዎን ፈቃድ እለምናለሁ ።

ይህች ፲፯ኛ ቀን ሐምሌ አዲስ ብርሃን የገለጸችልን ቀን ናትና ለኛ በልዩ የከበረች የተወደደች ቀን ናት ፤ ሆናም ትኖራለች ። በታላቁ ቸርነትዎ ከባት ከናት የበለጠ ሥራ ስለሠሩልን የምስጋናችንና የደስታችንን ወሰን አናውቀውም ። ሙሴ ዓለትን መቶ ውሃ አውጥቶ ሊጠሙቱ የእስራኤል ልጆች እንደ አጠጣ ባገራችን ከፉኛ ተዘግቶ የነበረውን የትምሕርትና የጥበብ በር በታላቅ ኃይል ከፍተው ገቡና ከጥበብ ጥማታችሁ እርኩ ስላሉን የምስጋና ሐሳባችንን የምንገልጽበት ቃል አናገኝም ። ይህንን የሐምሌ ቀን የዘርን መዝሪያ ያደረገ አምላክ የጥበብም ዘር የሚዘራበት ወራት ስላደረገልን የዚህች የሐምሌ ፲፯ኛ ቀን በዓል መታሰቢያነቱ የማይሞት ሆኖ በማይፋቅ ቀለም በልባችን ውስጥ ተጽፎ እንደሚኖር ለልዕልናዎ እንድናስታውስ እንለምናለን ። ለልዑል ጌታችን ለልዕልት እመቤታችን ለወይዘሮ መነን ለክቡራን ልጆችዎ ስለዚሁ ቀን ደስታ ከልባችን ውስጥ የመነጨ የደስታ ምኞታችንን እያቀረብን ዕድሜና ክብር ከደስታ ጋራ እንመኝልዎታለን ።

ልዑል ሆይ ቀጥየም በማክበራቸው የሥራ ጓደኞቼ (አስተማሪዎች) ስም ሁኜ ክብርና መከናወን ከደስታ ጋራ የሞላው ረጅም ዕድሜ እግዚአብሔር ይስጥልን ብዬ ምኞታችንን አቀርባለሁ ። ከንግግሩ በኋላ ጭብጨባ ሆነ ።

ከዚህ በኋላ ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ደስ የሚያሰኝ ቃልመለሱ፡ቃሉም የሚከተለው ነው ።

የተወለድሁባትን ዕለት ለማክበር መጥታችሁ አስተማሪዎቼንና ተማሪዎቼን በማየቴ ስለ መልካም ሐሳባችሁም አመሰግናችኋለሁ ። ይልቁንም የ፣ ቤ ደስታ የማይገኘው በ፴፫ ዘመኖች ውስጥ ከሠራኋቸው ሥራዎች ሁሉ እናንተን የተከልኩባትን ዕለት እንደ ተወለድኩባት ቀን አቈጥራታለሁና የዚችኑም የተማሪ ቤት ውጋጋን ይኸው ማየት ጀመርሁ ፈጽሞ ብርሃኑዋ ተገልጾ የኢትዮጵያ ቀኝ እጅ መልካም ሠሪዋ እንድትሆኑ እየተመኘሁ ደስታዬን እየገለጥሁ በትምሕርታችሁም እንድትበረቱ አደራ እላችኋለሁ ።

ይህነን ያየንና የሰማነም አጥብቆ ደስ አለን ። ከዚያም የነበሩ ሰዎች ደስታቸው ከልቡናቸው ተርፎ ግምባራቸው ብርሃን ተሥሎበት ሲያሸበርቅ ይታይ ነበር ።

ይህ ሁሉ ሲደረግ የነበሩ መኳንንቶች
ክቡር ደጃዝማች ወልደ ሥላሴ
ክቡር ደጃዝማች ጌታቸው ያገር ግዛት ሚኒስትር
ክቡር ደጃዝማች ሃብተ ሚካኤል
ክቡር ከንቲባ ነሲቡ
ክቡር ልጅ መኰንን እንዳልካቸው ናቸው ።

የአርመን ልጆች ሙዚቀኞችም የሚከተለውን ቃል ተናገሩ ።

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ሆይ እጅግ ክብር የመላበትና በዓለም ታሪክ ዓመትታ ውስጥ የማይረሳና ሊሞት የማይቻለው የዛሬ ቀን የሰጠን የደስታ ሰዓቶች ያስታወሱንን የከበረ መታሰቢያ ምክንያት አድርገን ፤ የተማሪ ቤትዎ ልጆች ምስጋናቸውን ሲያቀርቡልዎ ፤ እኛም የነሱ ተከፋይ ሆነን ጥልቅ የሆነ ምሥጋናችንን ደፍረን እናቀርብልዎ ዘንድ እራሳችንን አደፋፈርን ።

በልዑል ሰውነትዎ እውነተኛ ለክርስቲያን የተገባ ወሰን የሌለው ርህራኄ ተዋህዶ ድፍርስ የሌለበት ማንም ቀድቶ የማይጨርሰውና የማይጠፋ የፍቅር ምንጭ አደረገዎ ፤ ስለዚህ በራስዎና በተወደደ አገርዎ ውስጥ ባለመታከትና ባለማቋረጥ የሚያደርጉት መልካም ሥራ የማይበቃኝ ነው ብለው ፤ ይህን መልካም ሥራዎን ከባሕር ወዲያ ማዶ ለመዘርጋት ፈቃድዎ ሆነ ። ይህንንም ማድረግዎ በጊዜያችን በተደረገው ሰልጥነናል በሚሉም ሕዝቦች ሕሊና ክብዶ ባለው የክፋት ሥራ ምክንያት መከራና ሥቃይ የተቀበሉን የሰው ዘሮች አጽናናለሁ በማለት ነው ።

ልዑል ሆይ ፤ ከወንድሞቻችን ከተፈሪ መኰንን ተማሪ ቤት ልጆች ጋራ ሁነን ትሁትና እውነተኛ የሆነ የምስጋና ቃላችንን እያሰማን ፤ እግዚአብሔር ለልዑልነትዎና ለከበረ ቤተ ሰብዎም ተድላ የመላበት እረጃጅም እድሜ እንዲሰጥልንና ፡ ቀን ለሆነ ለብርቱዋ ለኢትዮጵያ ሕዝብም ልማትን እንዲሰጠው እየለመንን ።

ተፈሪ መኰንን ያኑርልን ።
ኢትዮጵያን ያኑርልን ።
እያልን እንናገር ዘንድ ይፍቀዱልን።

Altesse Impériale

Nous profitons de l' occasion heureuse offérte par les heures radieuses de cette journée solennelle , immortelle dans les annales de l' histoire des peuples , pour nous permettre d' oser de mêler le tribut de notre profonde reconnaissance à celle exprimée par les élèves de votre école .

Votre Altesse qui est l' incarnation même de la plus pure bonté chretienne qui n' a ni borne ni limite , que rien ne peut épuiser pour avoir comme source limpide et intarissable la charité infinie , non contente d' etendre ses oeuvres bienfaitrices sur son propre et cher pays , a voulue aussi d' étendre le champ d' action de ses immenses et merveilleuses vértus , au delà des mers lointaines, dans la pensée éminemment pieuse de consoler les peines et les victimes de l' humanité meurtie par la pérpétration des grands crimes des temps modernes accumulés sur la conscience des peuples dits civilisés .

Permettez nous Altesse ; de mêler notre faible mais loyale voix, à celle plus autorisée de nos fréres de l, école Teferi Makonnen et de souhaiter du fond de notre coeur que Dieu veuille bien accorder à votre Altesse Impériale ,, ainsi qu , à votre noble et Impériale famille , une longévité pleine de bonheur , une prospérité parfaite au brave peuple de la vaillante Ethiopie et de crier

Vive Teferi Makonnen
Vive l' Ethiopie .

ከዚህ በኋላ ለተማሪዎቹ ሱክር ሻይም ተሰጠ ተማሪዎቹም ከደስታቸው ብዛት የተነሣ እንደገና መዝሙሩን ደገሙት ፡፡

ይህ ሁሉ ከሆነ በኋላ ከልዑል አልጋ ወራሽ ጋራ ፎቶግራፍ ተነሡና ተሰናብተው ሙዚቃ እየተነፋ በአጀብ ከግቢ ወጥተው ወደቤታቸው ሄዱ ።

ለዚህ ዓለም እንግድነትና ባለተራ መሆናችንን የሚያስረዳ ምክር

ወንድሞቼ ሆይ ።

ወደዚህ ዓለም የመጣንበት ጉዳይ እንደ የጉዞ መንገድ መሆኑ ለሁላችንም የታወቀ ነው ፤ ያሁኑ ባለተራ መንገደኞች በዚህ ዓለም ጉዞ የሚገኘውን ሁሉ ለማግኘት ተራው የኛ ነው ቀደም ብለው ያለፉት አባቶቻችን በዚህ መንገድ ሲያልፉ አንድ አንድ ጊዜ ችግርና መከራም አግኝተው ይሆናል አንድ አንድ ጊዜም ጥቂት ደስታ አግኝተው ይሆናል ተራቸውን እንደ ትጋታቸውና እንደ እድላቸው ጨርሰውት አልፈዋል ወንድሞቼ ሆይ አስተውሉ እኛም አሁን ለመጣንበት ተራችን ያለፉት አባቶቻችን መጥተው አይጋፉልንም ወደኋላ የሚከተሉም አለ ጊዜያቸው አይደርሱልንም ለሞትም ለሕይወትም ለመልካምና ለክፉም የኛው ተራ ነው በዚሁ ጉዟችን እያማረብን እንድናልፍ ባነፉት ታላላቆች ላይ ያየነውን ማአረግ እንድንቀበል ። እለምናችኋለሁ ፡፡ ሁለት የብረት መጋዝ ቢኖር አንዱ ቢሠራበት እየሠራ እያማረ እየተወለወለ ያልቃል ያ ሥራ የማይሠራው ብረት እየዛገ እያደፈ እረገድ እየበላው ያልቃል ፤ እንዲህ ከሆነ የማናቸው እድል ይሻላል ከሚሠራና ከማይሠራው ፡፡ እኛም እንዲያምርብን እየሠራን ብናልፍ መታሰቢያም እናጣም ነበረ ሥራ የሚያሰናክሉት ሰዎች የዓለም እንቅፋቶች እንደሆኑ ጥርጥር የለውም መሰናከያ የሚሆነን ሰው አሳቡ ይከሰሰው ይህቺ ዓለም በሚበልጥ ስም ዓለም ተብላ ትጠራለች ነገር ግን አነዋወርዋን ሲመለከቱት የውጊያና የመከራ ኑሮ ሞልቶባታል ዓለም ስትባል አንዳች ችግር የሌለባት ዓለም ትመስላለች ነገርግን ስሟና ግብሯ የተለያየ ነው በስሟ ዓለም ስትሆን፡ በአነዋወሯ ዓለምነት የላትም ዓለምነቷ እንደምኞት ሆኖ ይኖራል ፡ ዓለም ስለምን ዓለም መሆን አቃታት የሰው ልጆች በመስማማትና በመልካም ሥርዓት አንድ መሆን ቢያቅታቸው ዓለምም ዓለም መሆን አቃታት ፤ አንድ ሽማግሌ ጊዜ ሞቱ ሲደርስ በአልጋው ዙሪያ ልጆቹን በተርታ አቁሞ በትሮችሁን ሁሉ አምጡና በገመድ እሰሩት አለ ። ሁሉም ሰብስበው ባንድነት አሥሩት ከዚህ በኋላ አንዳንዳችሁ ስበሩት ብሎ አዘዘ ልጆቹም ለመስ በርአቃታቸው ። ደግሞ እስራቱን ፍቱና አንዳንዱን ስበሩት ብሎ አዘዘ ፈቱና ነጣጥለው አንዳንዱን ሰባብረው ጣሉት ፤ ከዚህ በኋላ ሽማግሌው ምሳሌውን ተረጐመ አንድ ብትሆኑ በምንም አትሸነፉ ። ብትነጣጠሉ ምንም ኀይልና ደስታ አታገኙም ብሎ ተርጕሞ ሞተ ። አሁንም ዓለም ለስሟ መልካም እድል አግኝታ ለአነዋወርዋ ፍጹም ደስታ አላገኘችም የሰው ልጆች ቢስማሙና ባንድ ሥርዓት ቢተዛዘኑ እውነተኛ ዓለም ማለት የዚያን ጊዜ ይገኛል ያለሥርዓት መንግሥት ይጠፋል ። ሠራዊትም ይፈታል ስለ ቋንቋ መስማማትና በመልካም ሥራት አንድ ለመሆ– የሚረዳ ቋንቋ መማር ነው ቅዱስ ጳውሎስ ወደቆሮንቶስ ሰዎች ጻፈው ፩ ቆሮንቶ ፲፬ ምዕራፍ በሙሉ ማንበብ የቋንቋን ጥቅም ያስረዳል ። የሰው ልጆች ከእንስሳ የሚበልጡበት በእእምሮና በቋንቋ ነው ።

ምድርም ሁሉዋ ያንድ ቋንቋ ያንድ ነገርም ነበረች እግዚአብሔር አለ እነሆ እርሳቸው አንድ ወገን ናቸው ለሁሉም አንድ ቋንቋ ነው ለመስራት የፈለጉትን አይከለከልባቸውም ። ኦሪት ዘፍጥረት ፲፩ ም ፩ቁ እስከ ፱ቁ ተመልከት የባቢሎንም ሰዎች ቋንቋቸው ሲጠፋ ለግንቡ ሥራ የተስማሙበት አሣብ አብሮ ጠፋባቸው እኛም የኢትዮጵያ ሰዎች ለትምርት ባልተጋነበት ምክንያት በልዩ ልዩ ቋንቋ የተጻፉ ቃላት ለማንበብ አንችልም ጥቅምን ሁሉ የሚአመለክቱና ወደሁበት የሚመሩ ቃሎችን አንብበን ባንሰማ ማናቸውንም የሚሻለውን ሥራ ለመሥራት አሳባችን አልተነሳሳም የትምሕርት መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው ተብሏልና የትህምርት ሁለተኛ ቋንቋ ማወቅ ይሆናል አንድ ትልቅ ሰው እንዲህ ብሎ ጠየቀኝ በሐገራችሁ የሹመት ስም አረብ ባሻ ቱርክ ባሻ ሚኒስቴር ማለት ምን ማለት ነው ብሎ ቢጠይቀኝ እንደተቻለኝ ተረጐምኩለት ለትርጓሜዬ ተከራክሮ ባይነሳበት ድንገተኛ ቃል መልሼ አመለጥሁት የውጭ አገር ቋንቋ ከግዕዝና ከአማሪኛ ቢተርፍ ወደ አማሪኛ ለመተርጎም አማሪኛ የታጣ እንደሆን ሳዲሱ ነገር አዲስ ቋንቋ ለመውለድ የሚችሉ መልከም ወላዶች በኢትዮጵያ ይገኛሉ ነገር ግን ምቀኝነት በመከከላችን ተጋርጦ አያጠያይቀንም የምቀኝነት ኀይል በቀድሞ ዘመን አንድ ምቀኛ ደሐ እወሕኒ ታስሮ ንጉሡ ወደ ወሕኒ ቤት ገብና ምጽዋት ሊመጸውት ትክክል ስጥወታ ሲጀምር እየ ያም ምቀኛ ደሐ ንጉሥ ሆይ ከነዚህ ሰዎች ትክክል ምጽዋት ከሚሰጡኝ አንድ አይኔን አውጥተው ይውሰዱት ብሎ ተናገረ ይላሉ ወንድሞቼ ሆይ መንግሥታችን ሰፊ ናት ለሁላችን ማደጊያ ትበቃለች እርስበርሳችን ምን ያጨቃጭቀናል በየሀኩላችን አገልግለን በየማያችን ልናድግ ይቻላል መከሩ እጅግ ነው ሰራተኞቹ ጥቂት ናቸው ሉቃስ ፲ ፪፥ የኢትዮጵያ እድል እንደበረታ፡ የኢትዮጵያ እድል በልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ትጋት ። ይህ እድል ኢትዮጵያን ከቀድሞ ኑሮዋ ወደሚሻል ኑሮ መሻሻል ነው ። የቀድሞ ነገሥታት በጌትነት ሲያስተዳድሯት እንደነበረ የታወቀ ነው ። አሁን ግን ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን እንደ አንዱ አገልጋይ በማስተዋልና በትጋት እኛን ያገለግላሉ ይህም የወንጌል ቃል ነው ፡፡ ከናንተ በላይ አለቃ መሆን የሚወድ ያገልግላችሁ ማርቆስ ፵፫ ፲፩ ምዕራፍ በገንዘባቸውና በጉልበታቸው አገ–

ራቸውን በትክክል ያገለግላሉ ። ወደ አውሮፓ ለሔዱት ተማሪዎችና እዚህ ላቆሙት ትምህርት ቤት የሚከፍሉት ገንዘብ ብዙህ ነው ከዚህ የበለጠ እድል የለም ። አስተዳዳሪያችን ጌታችን አገልጋያችን ሆነዋል ።

ወንድሞቼ ሆይ ተጠንቀቁ በማያሣልፈው በጠማማው መንገድ አትሒዱ ። ኢትዮጵያ ያገኘችው እድል ደግሞ ባለፈው ዓመት ልዑል አልጋ ወራሽ ወደ አውሮፓ በመሄዳቸው ክብራችን ተገልፃ በታላቅ አገር ሁሉ ውበታችን ተፈሪው ግርማችን ሲታይ ኢትዮጵያ በሁሉም አፍ ተመስግና የመንግሥቶች ሁሉ ጓደኛና ያንድነት ጥቅም ተከፋይ ሆንናልና ጉዳትን ሁሉ ተግተን እንሸሽለን ከሚከተለው ጉዳት መሸሽ የማያውቅ ሰው አቅሙን አያውቅ ጥቅሙን አያውቅ ። ዕወቁኝ ብሎ ደብቁኝ የግርግርታ ቤት ድልምታ የሚሉት ስድቦች ይፈጸሙብታል።ማነው ማረሻ በጁ ይዞ ወደ ኋላው የሚመለከት

ክቡር ነጋድራስ አስታጥቄ በሀገራችን መልካም ሥራ እየተጀመረ ይቀራል ብለው የተናገሩት እውነት ነው የጥቅም ሥራ በአዋቂዎች ታስቦ የተጀመረው በባለሟሎችና ይልቁንም በአማላጆች ማስተገር ጥቅም ሁሉ ምኞቱን ለመፈጸም ያቀተዋል አሁን በአዲስ አበባ በከተማው ውስጥ አንድ ለከተማው የሚጠቅም መንገድ ለመክፈት ቢታሰብ ያንዱ ባለሟል ዘመድ ቦታ ጥቂት የሚነካ ቢሆን ባለሟሉ አማልዶ ትልቁን ጥቅም በትንሹ ጥቅም እንዲለውጠው የታወቀ ነው ለመብዛትና ለመስማማት የሚናፍቁ ሕዝብ ቢኖሩ ዓለም ለነሱ ናት ። ቅኖች ይህነን ምክሬንና ልመናየን ይሰሙታል ብዬ ተመኝቼ እጽፋለሁ ነጋድራስ ደስታ ምትኬ ።

ተስፋ ።

ባለፈው ሳምንት ወይዘሮ ወለቨ በሻህ ጠላትን ለማባረር ሴት ተልጅ እንደ ዓቅሙ መዋጋት እንደሚገባው ስለ ተረዱት ድንቁርና ጠላታችንን ለማባረር ለትምርት ቤቱ እርዳታ እንደሰጡ ባነብ ወሰን የሌለው ደስታ ደስ አለኝ ። እንዲሁም የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሉ ደስ እንደሚለው ጥርጥር የለውም የደስታው ዋና ተስፋውም ይህ ነው በ፲፰፻፺፯ ጃፖን ከመስኮብ ጋራ ጦርነት ገጥሞ እንደነበር እናውቃለን የጃፖን መንግሥት ወደዚሁ ጦርነት ሽማግሌ ወላጆች ያሉዋቸውን ጉበዛዝት እንዳይሄዱ ከልክሎ ነበር ከዚሕ መሃከል አንድ ልጅ የነበራት አሮጌ ሴት ልጇዋን እጦርነቱ ሂድ እያለች ብትወተውተው ለመሄድ ተነሳ ተመልሶ የወታደሮች አለቆች አንተ ሽማግሌ እናትህን ትተህ ልትሄድ አይሆንልህም ብለው እንደከለከሉት ቢነግራትም ስለታም ቢላዋ አንስታ ከእንግዲህ ወዲህ እጦርነቱ በነጻነት ትሄዳለህ ብላ በቢላዋው ሆዷን ቀዳ ሞተች በዚሁ የሴቲቱ ሥራ የተነሳ የጃፖን ሕዝብ ከሴቱ ጀምሮ እስከ ሽማግሌው ድረስ በብርታት ተዋግተው ጠላታቸውን ድል ነሱ እንዲሁም የኢትዮጵያ ሴቶችና ሽማግሌው ሁሉ ወይዘሮ ወለቨ በሻህን እንዲከተሉ ተስፋ እናደርጋለን ሴቶቻችን እንደዚሁ ከመሰለ ደግ ሥራ ስለ ደረሱልንም እምላካችንን እናመሰግናለን ። እዚህ ድረስ ያስደረሰንም ብርሃንና ሰላም ነውና እሱን ላቆሙልን ልዑል አልጋ ወራሻችን እምላክ ስለ ኢትዮጵያ ብሎ ዕድሜና ጤና ብርታትም እንዲሰጥልን ሳናቋርጥ ልንለምነው ይገባናል ። ኪዳነ ማርያም አበራ።

ስለ ተማሪ ቤት እርዳታ ።

ለተከበረችና ለተወደደች ሀገሬ የተሰጠኝን ኃሳብ እገልጻለሁ ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን በሰየሙት ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ ስመለከት በኢትዮጵያ ስለ እሚቆመው ተማሪ ቤት እርዳታ እንሰጣለን ያሉ ብዙህ የክቡራኖች ስም ስማቸው ተጽፎ አየሁ ተመግበውት ሁለተኛ የማይርቡ ትምሕርት ብቻ ነው ፤ እንጀራ የሆነ እንደሆነ ግን አሁን ተመግበነው በሰዓት በሰዓቱ እንደሚያስቸግረን ታውቃላችሁ ለዚህ ላስቸጋሪ ጋሻው ትምሕርት ነው ብዬ የተቻለኝን በመት በመቱ ፫ ፫ ብር እረዳለሁ ይኸነንም ፫ ፫ ብር ብሰጥ ምንም ቢሆን በነዚህ በሚማሩት ልጆች መቅናቴን አልተውም እግዚአብሔር የልቤን ኃሳብ እስኪፈጽምልኝ ቀናተኛ ነኝ ለመቅናትም ያደረሰኝ የኔ ታናሾች የሆኑ ሁለት ወንድሞች ነበሩኝ በተቻለኝ እየረዳኋቸው ጥቂት ቀን ተምረው ነበረና ደግሞ ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን አንድ ጊዜ በብዙ ተመግበውት የሚያጠግብ ሁለተኛ የማያስርብ የተማሪ ቤታቸው በተከፈተ ጊዜ ፈቅደውላቸው ሁለት ወር ያህል እንደተማሩ የትምሕርት ፍቅር እንዳለባቸውና ትምሕርታቸው ደስ ስለ አሰኛቸው የተማሪ ቤቱ አለቃ ኃኪም ወርቅነህ የፈረሙበትንና የተማሪ ቤቱ ማህተም ያለበትን የምስክር ወረቀት አምጥተው ሰጡኝ ያን ጊዜ ደስታም ያዘኝ ቅናትም ታሰበኝ መቅናቴም ከኔ በኋላ የተገኙት ይኸነን ሁለተኛ የማያስርብ እንጀራ በልተው ስለ አየሁ ነው ነገር ግን እነሱም ሆዳቸው ሰፊ ነው መሰለኝ ገና አልጠገቡም ።

በልዑል ኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ትምሕርት ቤት ያላችሁ ክቡራን ወንድሞቼ ሆይ ወንድሞቼን አመስግኖ እኛን ከነሱ በላይ ያለነውን ሳያመሰግነን ቀረ ብላችሁ እንዳትሉኝ የምስክራችሁን ወረቀት ስለአላየሁ ነውና ይቅርታችሁን እለምናለሁ ከጻፍኩትም ውስጥ መርምራችሁ የተገደፈና የተሳተ ቢገኝበት የኔ አለማማር ነውና እንድትአርሙት እንጂ እንዳትነቅፉት እንባቢዎቹን ሁሉ እለምናችኋለሁ ። በልሁ ደገፉ ።

በኢትዮጵያውያን ማኅበር ለሚቆመው ተማሪ ቤት እርዳታ እንሰጣለን ብለው ፈርማቸውን የሰጡ ሰዎች ።

ከ፴ ጥቅር የመጣ ድምር	፩ሺ፱፻፸፫	ብር ተ፪ ሩብ
አቶ ተክለ ጽዮን ።	፲	ብር
አቶ በልሁ ደገፉ ።	፫	ብር
ባላምባራስ በቀለ እየለ ።	፲	ብር
አቶ ኃይሌ መረኑ ።	፭	ብር
ወይዘሮ እዳነች ዛማኔል ።	፭	ብር
ልጅ በቀለ ጉሹ።	፭	ብር
ድምር	፪ሺ ፲፩	ብር ተ፪ ሩብ

የቴሌግራም ቃል ሐምሌ ፲፩ ቀን የለት ወሬ ።

ካዛብላንክ ። ሡልጣን ሕዝቡ የፖለቲክ ሥራ እንዳይሰሩ ደግሞ ከረፋኖች ጋራ መስማማትን እንዲተው የጻፈውን ደብዳቤ ብዙ ሕዝብ በተሰበሰበበት መስጊድ ውስጥ በቃዲው አስነበበው ቀጥሎም በተራራው አገር ያሉት አብደልከሪምን የሚከተሉት በፍጥነት እንደሚቀጡ ተናገረ ።

በልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

መጀመሪያ ዓመት ፤ ቁጥር ፴፪።
1re ANNÉE № 32

ሐሙስ ሐምሌ ፴ ቀን ፲፱፻፲፯ ዓ ም።
JEUDI 6 AOUT 1925

ብርሃንና ሰላም

LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopi, eprofondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

የጋዜጣው ዲሬክተር ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።
Gabré Christo Taklé Haymanot
Diréctour

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ጥበብ ።

አንድ ንጉሥ የሚሸጠውንና የሚለወጠውን ነገር እያለሁ በማለት ወደ ገበያ ወጣ ።

በነጋዶች መካከልም አንድ ሊቅ አስተማሪ እየና ምን ፈልገህ ተቀምጠኻል ? ብሎ ጠየቀው ። ሊቁም በዚህ የተቀመጥሁት ጥበብ ለመሸጥ ነው ብሎ መለሰለት ። ንጉሡም ዋጋው ስንት ነው ? ብሎ ጠየቀው። ስስት መቶ ብር ነው ዋጋው አለው ። ንጉሡም የጥበቡን ዋጋ ስስት መቶ ብር ሰጠው ።

አስተማሪውም « ልታደርገው የምታስበውን ማናቸውንም ጉዳይ ሁሉ በፊት ተጠንቅቀህ አስበህ አድርገው መጨረሻውንም መርምር » ብሎ ምክር ሰጠው። ንጉሡም ይህችን ብዙ ዋጋ የሰጠላትን የሊቁን ምክር ብዙ ጊዜ ይደግማት ነበር ። አንድ ጊዜ ሰዎች ንጉሡን ለመግደል መክረው ተማማሉና የሚላጨውን ሰው ንጉሡን እንዲያርድላቸው በገንዘብ ገዙት። ላጭውም ንጉሡን ለመላጨት በቀረበ ጊዜ ንጉሡ እንደ ልማዱ የሊቁን ቃል (ልታደርገው የምታስበውን ማናቸውንም ጉዳይ ሁሉ በፊት ተጠንቅቀህ አስበህ አድርገው መጨረሻውንም መርምር የሚለውን ቃል) ቀስ ብሎ ደገመው ላጭው ይህነን በሰማ ጊዜ ንጉሡ አሳቡን ያወቀበት መስሎት ብዙ ፈራ ከመደንገጡና ከመንቀጥቀጡ የተነሣ ንጉሡን የሚላጭበት ምላጭ ከእጁ ወደቀ ከዚህ በኋላ ከንጉሡ እግር ወድቆ አስቦት የነበረውን ሁሉ ተናገረና ይማሩኝ ብሎ ለመነ ይባላል።

ንጉሡ የገዛት ጥበብ ሕይወቱን ከሞት አድናለችና ዋጋዋም ቢበዛ ጥቅም ነው እንጂ ጉዳት አይደለም ።

ንጉሡ የገዛት ጥበብ በልቡ ስለያዛትና አዘውትሮ ስለደገማት ከሞት አዳነችው ። እኛ ደግሞ ዘወትር በቃል በምክር መጽሐፍም ከማንበብ ብዙ ጥበብ እናገኛለን ። ግን ለጊዜው እየገረመን ጉድነው እያልን ተቀብለን እንረሳዋለን በልባችን ስላላኖርነውም ጥቅም አናገኝበትም፤ከብዙ መጻሕፍትና ሊቃውንት የሚጠቅም ምክር እናገኛለንና ማን ያውቃል ከሞት የሚያድነን ጊዜ ይደርስ ይሆናል ፤ ስለዚህ የጥበብን ቃል በልባችን ማኖር በአፋችንም መድገም እንልመድ ።

በየሳምንቱ የሚወጣው ብርሃንና ሰላም እንኳ ዋጋው በርካሽ ቢሆን እየመላለስን ብናነበው ምክሩንም ብንጠብቀው ከሞት የምንድንበት ጥበብ አናጣበትም ።

ልታደርገው የምታስበውን ማናቸውንም ጉዳይ ሁሉ በፊት ተጠንቅቀህ አስበህ አድርገው መጨረሻውንም መርምር ሕይወትህም ትጠበቃለች ።

ለስኢትዮጵያ ልጆች ማኅበር ለሚከፈተው የስልጣኔ ትምሕርት ቤት ማስታወሻ ።

አሁን የኢትዮጵያ ሰዎች የ፳ ዓመት ልጅ ባይኖር አገራችሁን ትወዳላችሁ ብለው ቢጠይቋቸው እንኳን አዋቂው የ፳ ዓመት ልጅ ሳይቀር ከሁሉም ሰው አገሬን እኔ እወዳታለሁ ሲል ይገኛል ። ነገር ግን ሐኪሞች በሮፓ በትልቅ መነጠር የሰውን አንጀት ኩላሊት ያያሉ እንደሚባል ሁሉ አገርህን እርዳት ለስልጣኔ የሚሆን የትምሕርት ቤት ይቁም ቢባል አገራቸውን በውነት የሚወዱ ሁሉ ገንዘብ እንደ አካሳት ትወደዳለችና ከዚያች ቆርሰው መስጠት በመጀመራቸው ከአንጀት አገራቸውን መውደዳቸውን ገልጸው ያሳዩ ጀመሩ ። የቀሩት ወንድሞቼም እንደዚሁ ሁሉ ገና ይረዳሉ በማለት ሙሉ ተስፋ አለኝ።ይኸን የትምሕርት ቤት እንድናቆም ስጽፍ ለዚህ እርዳታ የሚገኘው ገንዘብ ፲ የትምሕርት ቤቶች የሚያቆም መስሎኝ ነበረ አሁንም ደግሞ በገንዘብ መውደድ የቆየ አይመስለኝም በሥራ ብዛትና በመዘንጋት ዛሬ ነገ በሚለት ወይም ነገሩን

በማስቲዋል ነው ገና ይሆናል እላለሁ እንጂ ለአገር ጥቅም መሆኑን እያወቀ እኔ አገሬን ልከብርበት ላጌጥበት እወዳታለሁ እንጂ እንድትሰለጥን ስልጣኔዋ እንዲሰፋ ለመርዳት ትንሽ ገንዘብ ልከፍልላት አልወድም የሚል ፩ ሰው እንኳ ይገኛል አልልም ። ቢኖርም ትልቅ ስህተት ነው ሰው ለራሱ ጥቅም ብቻ ገንዘብ መሰብሰብን ለራሱ ብቻ ማሰብን ቢከተል ምንም አይጠቅምም ለጊዜው እንኳ ገንዘብ ያጠራቀምሁና ጌታ የሆንኩ ቢመስለው ያገር ሁናቴ እየታደሰ ስልጣኔ እየሰፋ ከልሄደ ያ ገንዘብና ጌትነት ለ፩ ለበረታ ሰው ይሆናል ያንን ሰው ፩ ስህተት ቢያገኘው ወይም ቢያረጅ ወይም እሱ ሲሞት ከልጅም ቢሆን በ፩ ነገር ይሄድበታል ወይም ሰውየው በጌትነቱ በማእረጉ ሳለ ይኸን አሁን የምነጋገረውን የስልጣኔ ትምሕርት የተማረ በአድ ከየትም መጥቶ በእውቀት ይወርሰዋል ለዚህም ማስረጃ ያለፉትን ሰዎች እናስተውል ስለዚህም አንድ ምሳሌ እጽፋለሁ ፩ ትልቅ ግንድ ፲ ወይም ፳ ሰዎች ተሸክመውት ሲሄዱ ከነሱ ፩ ሰው እኔ እንዳልሸከም ቀስ ብየ ዝቅ ብየ ልሂድ ብሎ ከተሸከሙት መሐከል ዝቅ ቢል የቀሩትም ሁሉ እንደዚያው ሰውየ በየልባቸው ቢያስቡ በሁላቸውም ላይ ወድቆ እንዲያደቃቸው አይጠረጠርም ።

ደግሞ ሁለተኛ ምሳሌ ለጦር ከተሰለፈ ወታደር መሐከል አንዱ ሰው የቀሩት ይዋጉ እኔ ለምን እሞታለሁ ብሎ ቢያስብ የቀሩትም ሁሉ እንደሱ ቢያስቡ መዋጋቱ ቀርቶ ሁሉም ድል ሆነው ያልቃሉ።ቢተጋገዙ ግን ድል ያደርጋሉ ስለዚህ ለማናቸውም ነገር የራስን ጥቅም ብቻ መከተል ሕዝብን ይጐዳዋል እንጂ አይጠቅመውም ደግሞ ከልባችን ብናስተውልና ብንመለከት የገንዘብ ስራው ምን ምን ይሆን ገንዘብን ማግኘት ለመብላትና ለመጠጣት ለመልበስ ብቻ ይሆን ሰዎች በዓለም ላይ ሳሉ ብዙ ገንዘብ የሚያጠራቅሙ ብቻ ለዚህ አይደለም ለመብላትና ለመልበስስ ማንም ሰራተኛ ደሃ ያገኛል ወይም ገንዘብ መሰብሰብ ለመቅበር ይሆን አይመስለኝም ጥንቱንም ከመሬት ውስጥ ተፈጥሮ ሲኖር ብልሐተኞች ቆፍረው አውጥተው ስራ ይሰሩበታል መጀመሪያ የስራ መሳሪያቸውም የስልጣኔ ትምሕርት ነው አሁንም ከመሬት ብልሆች ቆፍረው ያከመውያወጡትን መልሶ መቅበር ኃጢአት ነው ደግሞም እንደ አበቶቻችንና እንደ አገራችን ልማድ ብር መሰብሰብ ብዙ ገንዘብ ማከማቸት አልነበረም እንደ ሌላው ዓለም አካሄድ ደግሞ ገንዘብ መሰብሰብ ላገር ጥቅም ለስም ለስራ ነው ለስም ማለትም ገንዘብን በማጠራቀም ስም አያስጠራም የሰለጠነ ሕዝብ ብዙ ገንዘብ ሲያገኝ ላገሩ ጥቅምና ለስሙ መታሰቢያ የሚሆን ስራ ይሰራበታል ለበሽተኞች መታሰቢያ የሚሆን ሆስፒታል ወይ ላገሩ ልጆች የስልጣኔ ትምህርት መማሪያ የሚሆን የትምሕርት ቤት ያቆምበታል ። እንኳን ላገራቸው ለኛ እንኳ ከምድር ዳርቻ አስበው አሜሪኮች በዶክቶር ላንቤ እጅ ያቆሙትን ሆስፒታል እናያለን ዶክቶር ላንቤ አሜሪክ በሄዱኩ ጊዜ መስተር ጆርጅ ሚሞሪያል ወደኔ መጡና ለኢትዮጵያ ምን ያስባሉ ብለው ጠየቁኝ እኔም አንድ ሆስፒታል ለማቆም አስባለሁ ግን እኔ ለዚህ የሚበቃ ገንዘብ የለኝምና ለዚሁ ስራ እግዚአብሔርን እለምናለሁ ብየ አጫወትኳቸው ።

እሳቸውም ለእናቱ መታሰቢያ ይሁን ብለው ለሆስፒታሉ መስሪያ አንድ መቶ አርባ ሺ ብር ሰጡ ብለው ዶክቶር ላንቤ አጫወቱኝ እኔም መስተር ጆርጅ ሚሞሪያል ከዚህ ሆስፒታል የሚያገኙት ትርፍና ጥቅም አላቸው ወይ ብየ ብጠይቃቸው እንደ መርፌ ከዚህ አይወስዱም ላገሩ የበሽተኞች ማስታመሚያ ይሁን ብለው ሰጡ ብለው ነገሩኝ ይኸን ጥቅም ለኢትዮጵያ ያደረጉላት ምስተር ጆርጅ ሚሞሪያል ዘንድሮ ሞቱ።ግን ሰው ከሞት አይቀርም ደግሞም መልካም ሥራ የሠራ ሰው እሱ ቢሞት ስሙ አይሞትምና ይኸውና የምስተር ጆርጅ ሚሞሪያል ስም እንኳን በገራቸው ይቅርና እዚህ በኢትዮጵያ በሠሩት ሆስፒታል ለዘላለም እንዲጠራና እንዲመሰገን እናያለን ። የሰለጠኑ ሕዝቦች እንደዚህ ያለውን ሥራ መስራታቸው አንድ ሰው ለሰው አገር መቶ አርባ ሺ ብር ማጥፋቱ የገንዘብ ጥቅም ከዚያ አገር ባይታወቅ ይሆን ፥አይደለም የገንዘብ ሥራው ዋናው ይኸ ቢሆን ነው ።

እንደዚህ ያለውን ያገር ጥቅም የሆነ ሥራ የሚያቆሙ ሰዎች ለሁል ጊዜ የእገሌ ሆስፒታል የእገሌ ኮሌጅ ተብሎ ስሙ ለዘላለም በዚህ ይጠራል ለነፍሱም ትልቅ ጥቅም ነው ። ጌታ በወንጌል አስተምሩ ዋጋችሁን ታገኛላችሁ ። የታመመ ጠይቁ አስታምሙትም ብሎ አዘናልና ።

ግን በኛ አገር ይኸ ትልቅ ስም ትልቅ ማዕርግ ትልቅ ያገር ጥቅም የሚሰጥ ሥራ ገና አልተለመደም ። አሁን በንአጼ ቴዎድሮስ በነአጼ ዮሐንስ ጊዜ የነበሩ ትልልቅ መኳንንት ድሮ ስማቸው ተረስቷል ።

እንደዚህ መሆኑም ስማቸው ለዘወትሩ የሚጠራበት ትልልቅ ሥራ በገንዘባቸው ባያሠሩ ነው ። በልጆቻቸው እንዳይጠሩም እንደ አባቱ የሚሆን ልጅ ከመቶ አንድ አይገኝም ስለዚህ ገንዘብ በብዙ መፈለጉ ስም ለማቆምና ላገር ጥቅም ነው እንጂ ሊበላ ብቻ አይደለም ። ደግሞ በሌላ ዓለም ሁሉ ወሬውን እንደሰማነው የስልጣኔ ትምሕርት ቤትን በሰፊው በየወረዳው የሚዘረጋ መንግሥት ነው ይባላል ይኸንን በሌላ ቀን እንጽፋለን ። መንግሥትም ስለዘረጋው ደግሞ ሕዝብና ያገር ታላላቆች ፥ መንግሥት ይሥራ ብለው ዝም ብለው አይመለከቱም ። ሁሉም ላገሩና ለስሙ መታሰቢያ ይጥራል፥አንባቢ ሆይ ከአሜሪክ ሆኖ ባዕድ ላገራችን እንደዚህ ሲያስብላት እኛ ዝም በማለታችን ልብ ይታዘብልና ይኸን ጋዜታ በማንበብህ ትጠጣት ይሆናል ። ፊታውራሪ ዱሬሳ ።

ማስታወቂያ ።

በዚህ ዓለም ላይ ተቀምጬ በጣም ስጨነቅ ዕውቀት የሚባል ያረጀ ሰው መጥቶ እንዴት አደርክ አለኝ እኔም ቶሎ ተግቸ የዚህን ዓለም ነገር ፈጽሞ መርምሮ የሚመክረኝ ሰው አጥቸ ነበርና እግዚአብሔር ይመስገን አልሁት እሱም በጁ ብዙን መጻሕፍትና ብርዕ ሌላም ይኸንን የመሰለ የጽሕፈት መሳሪያ ይዞ አየሁት እኔም አባቴ ሆይ ምነው በዚህ ዓለም ከልጠፋ ነገር መጽሐፍና ብርዕ በጅዎ ይዘው ይሄዳሉ አልሁት ። ልጄ ሆይ አስቀድሞ የሰው ዕውቀት መክፈቻ መጽሐፍ እንደሆነ አልሰማህም እንደምን ዕውቀት

ዕውቀት ይለያል አለኝ ። ይኸስ መልካም ነው አሁን እርስዎ ብዩት አገር ይኖራሉ አልሁት ፤ ለደንቆሮችና ብልሃት ላነማቸውም ሰዎች የምኖርበት አገር ሩቅ ነው ለብልሆችም በጣም ቅርባቸው ነኝ አለ አሁን ግን ይኸች ኢትዮጵያ የምትባል አገር ሕፃናቶች ዕውቀት ዕውቀት እያሉ ስሜን ማንሣት ስለጀመሩ በንደዚህ ያለ ሐሳብ ተነስቼ መጣሁ አለ ። እንደምን አልሁት እንግዲያውስ የኔን ምክር ለመስማት ከፈለግህ በል ና ላጫውትህ አለኝ እኔም እሺ ብዬ ተከተልሁት እሱም ዕውቀት መልካም በምትባል ጠረጴዛ ላይ ወስዶ አስቀመጠኝ እሱም ምክር መሰረት በምትባል ወንበሩ ላይ ተቀምጦ ማጫወት ጀመረ ።

ልጄ ሆይ የመጣሁበት ምክንያት እንደዚህ ነው አለኝ ጥንት የኢትዮጵያ ሕፃናት አባት ሁሉ እርስ በርሳቸው ባለመስማማት አንድነትና ፍቅር በማጣት ተበታትነው አገራቸውን አስጠቅተው እኔን መልካሙን አባታቸውን አብረው ከአገር አስወጥተው ይኖሩ ነበረ ፤ አንድ ብልህ ሰው ከመካከላቸው ተነስቶ ተው እንመከር እርስ በርሳችንም እንስማማ እውቀትንም ከጠፋበት አገር ፈልገን እናምጣው ብሎ ባመከራቸው ጊዜ ከውቀት ይልቅ ድንቁርናን ከመታገሥ ይልቅ ቁጣን መንገድ እያለ በጠማማ መሔድን ይወዳሉና ሰይፋቸውን መዘው ዓይናቸውን አፍጥጠው በጣም መጮህ በምትወድ አፋቸው መጮህ ይነሱበታል ። እሱም ብዙ ነገር አስቦ ሳለ በፍርሃት ብዛት ተነስቶ ይሸሻል ያሰበውም ዕውቀት ተመልሶ ይርቀዋል እሱም ከነኛው መስሎ ይኖራል የንደዚህች ያለች እውቀት ያጠራት ከሁሉ በታች ሆና የምትኖር አገር ነች አሁን የዛሬዎቹም የኢትዮጵያ ልጆች ሁሉ ዘር ከልጓም ይጠቅሳልና የነዚያው ያባቶቻቸው ትዕቢትና አለመስማማት እስከሁን አልተለያቸውምና ምንም ቢሆን አይስማሙም አሁን ግን ምንም ትዕቢት ቢኖርባቸው ሌላ ባዕዶች በሀገራቸው ላይ እየመጡ ሲስማሙና በፍቅር ተጋግምደው ሲኖሩ እያዩ ጸጸት ይዟቸው ልዑል እግዚአብሔር አንድ ቢያደርጋቸውና ቢያፋቅራቸው ነው እኮ እኛም እንደነሱ እርስ በርሳችን ተስማምተን ዕውቀትን ፈልገን ጥበብን ተምረን ከንዱ ወደ አንዱ መዞርን ትተን ተንኮል ምቀኝነት የሚባሉትን ሌቦች ከአገር አጥፍተን ብንኖር ለኛስ መልካም ጤና ነገር አይደለም እያሉ ሲማከሩና ሲጫወቱ ሰማኋቸው እውቀትን የሚፈልግን እያሉ የኢትዮጵያን ልጆች ሲፈልጉህ ሰማኋቸው ይልቁንም ጥቂት ጥቂቱ ወንድሞቻቸው ስለተለዩዋቸውና እምክራቸው ውስጥ ስላልተጨመሩላቸው ነው እንጂ እነሱስ አጥብቀው ይፈልጉሃል አላኝ እሱም አቶ መሰንበት ይባላል አሁንም ልጄ ሆይ እነኛ የዱሮ ትእቢተኞች ትንሽ ትንሽ ቀርተው እንደሆነ ሳያበሩኝ አይቀርም አለኝ አየ የታለ አባቴ ሆይ ምንስ ቢሆን ከንድ ብርቱ ሁለት መድኃኒቱ የሚባል ተረት አለ ዛሬ የኢትዮጵያ ልጆች ሁሉ አንተን ፈላጊዎች ነን ወገንህም ብዙ እንደሆነ እወቅ አልሁት እሱም እግዚአብሔርን አድሜ ስጠኝ ብለህ ለምነው እኛን እውቀትን አጥፍተው አገሬን አበላሽተው የሚኖሩ የነበሩትን ሐሳብ አስትተህ ወዳሁኖቹ ወንድሞቹ ምክር መልሰኝ ብለህ ለምን ከተወለድህ አንስቶ እስቴ አስብ እድሜህስ እንዴት እጅግ አጭር ነው በዚያችም በትንሽ እድሜህ የእግዚአብሔርን ምሕረትና ደግነት ክፉውንም ደጉንም ሁሉን ታግሶ መኖሩን አታይምን አንተም በሥላሴ አምሳል ተፈጥረህ ጊዜ እስቲወጣ እንደምን ረሃብ ጥማት አትችልም አንተን የሚያስቆጭህና የሚያሳዝንህ የለም ነፍስ ተፈጥራ ሥጋ ከመልበስ ከመብል የምትለይ አይደለችም ደግሞስ ቅዱስ ማቴዎስ ያለውን አልሰማህምን ወደሰማይ ዎፎች ተመልከት እንዳይዘሩም እንዳያጭዱም በጐታም እንዳይከቱ እሱ የሰማይ አባታቸው ይመግባቸዋል እናንተ ይልቅ ከነሱ አትበልጧቸውምን ለነገም አታስቡ ነገ ለራሱ ያስባልና የቀኑስ ክፋቱ ይበቃዋል ።

ዓለሙ ወልዴ ።

ስለ ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ተማሪ ቤት ።

ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ሐምሌ ፳፰ ቀን በአሥር ሰዓት ተማሪ ቤታቸውን ለማየት ሄዱ። በዚያን ጊዜም ሰ አ ኢ ግራን ዱክ አሌክሳንድር ዲሩስ መጥተው ነበረ ። ልዑል አልጋ ወራሽም ከመኳንንቶቻቸውና ሰ አ ኢ ግራን ዱክ አሌክሳንድር ዲሩስ አብረው ከነበሩ የውጭ አገር ሰዎችም ጋራ በተማሪ ቤቱ በየክፍሉ እየዞሩ ተማሪዎቹን አዩ አስተማሪዎቹም በልዑል አልጋ ወራሽንና በሰዎች ሁሉ ፊት ተማሪዎቻቸውን ጠየቁ ። ተማሪዎቹም በማንበባቸውና ምላሽ በመመለሳቸው ልዑል አልጋ ወራሽና በዚያ የነበሩትንም ሰዎች ደስ አሰኙዋቸው ከዚያ በኋላ ልዑል አልጋ ወራሽና ሰ አ ኢ ግራን ዱክ አሌክሳንድር ዲሩስ መኳንንቱና በዚያ የነበሩ የውጭ አገር ሰዎች ሻይ ወደ ተሰናዳበት ቤት ሄዱና በዚያን ጊዜ ሐኪም ወርቅነህ በእንግሊዝ ተናገሩ ንግግሩም በሚመጣው ጋዜታ ይታተማል

ተማሪዎቹም ባማርኛ መዝሙር ዘመሩ ስለመዝሙሩ በ፴፩ ቍጥር ብርሃንና ሰላም ተመልከት ሙዚቀኞችም ደስ የሚያሰኝ ዜማ በሙዚቃ ያዜሙ ነበር በመጨረሻ ሰ አ ኢ ግራን ዱክ አሌክሳንድር ዲሩስ ለተማሪዎቹ ደስ የሚያሰኝ ቃል ተናገሩ ።

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ሥራቸው ብዙ ሲሆን በየጊዜው ሥራ በሚሠራበትና ተማሪዎቹ በሚማሩበት እየዞሩ ማየታቸው ሕዝባቸው ለሥራና ለትምህርት እንዲበረታና እንዲፈጥን ሥራ የሚያሠሩና የሚያስተምሩ በትጋት እንዲያሰሩና እንዲያስተምሩ [illegible] ተማሪዎቹም በሥራቸውና በትምርታቸው እንዲበረቱ ለማነቃቃት ነው ። የኢትዮጵያ ሕዝብ በሥራና በትምርት ወደፊት ቢገፋ ከፍ ወዳለ የሕዝብ ሥልጣኔ ለመድረስ ተስፋ እንዳለው የታወቀ ነው ።

ስለ ሴቶች ተማሪ ቤት ማህበር ።

በምሕረትና በትዕግሥት ይዘው ለሀገራቸው ልማት ለሕዝባቸው ፍቅርና ሰላም እንዲሆን ብለው አስበው አዲስ የተማሪ ቤት ማኅበር በመጀመራቸው ለልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ዕድሜና ጤና እንዳይለይብን ብለን እንለምናለን ። አሁንም ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ልዕልት ወይዘሮ መነንም ስለ ሴት ተማሪ ቤት የሚያስታውሳቸው ሰው ስለ ጠፋ ነው እንጂ

ለወገኖቻቸው ለሴቶች ተማሪ ቤት ቤወጣ እንዳይጠሉ እርግጥ ነው እኔ እስታሁን ሳልማር ባለፈው ጊዜዬ እጅግ እዝናለሁ አሁን ግን የትምሕርት ጥቅሙን ስላገኘሁ እምላክ ይመስገን ። ስለዚህ የሴት ተማሪ ቤት ማህበር እንዲያቆሙልን ወገኖቻችን ከድንቁርና ጨለማ ወደ ብርሃን ዕውቀት እንዲያደርሱን ተስፋ አደርጋለሁ ። የሴት ተማሪ ቤት ማህበር በቆመ ጊዜ በዚህ ባለችው አቅሜ ስለ እርዳታ ባመት ባመቱ ፳፭ ብር እሰጣለሁ ።

አሰገደች ሚካኤል ብሩ ።

ከኢየሩሳሌም ተመጣሁ ባለፈው ጋዜታ የወንዶች ማህበር ተማሪ ቤት መጀመሩን ብሰማ በጣም ደስ አለኝ ። ግን ወንዱ ተምሮ ስለ ጓደኛው ደግሞ የተማረች ሴት ታላገኘ እንደ አንድ አይን ሰው መሆኑ ነውና ስለዚህ እንደኔ ሃሳብ ደግሞ አንድ የተማሪ ቤት ለህቶቻችን ብንአቆም በጣም ደስ የሚያሰኝ ነገር የሚሆን ይመስለኛል ። ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ለልዕልት ወይዘሮ መነን እለምናለሁ የሴት ማህበር ተማሪ ቤት እዲያቆሙልን ተስፋ አደርጋለሁ እኔም ባለች አቅሚ ስለ ሴቶች ተማሪቤት እርዳታ ባመት ባመት ፳፭ ብር እሰጣለሁ

የህቶችዋን መማር የምትወድ የውብ ዳር ሚካኤል ብሩ ።

በኢትዮጵያ ተማሪ ቤት እንደ ገና ስለ ተከፈተ የደስታ ቃል

ከገሩ ወጥቶ ባዕድ አገር ሒዶ ልማደ ሀገር ማየትን የመሰለ መስተያት የለም መስተያት ባይንህ የማይታይ በገዛ ፊት ላይ ያለውን ነገር እንዲያሳይ እንዲሁም ሰው ባዕድ አገር ሒዶ የዚያ አገር ሥልጣኔ የሕዝቡ አነዋወርና ሥራውን ሲመለከት የገዛ አገሩ ጐደሎነትንና መጥፎነቱን በጣም ይታየዋል ። እኔም አገሬን ትቼ በምናኔ ኢየሩሳሌም ተመጣሁ ይኸው ፲፱ ዓመት ሆነኝ ኢየሩሳለም ላይ ክርስቲያኑም እስላሙም አይሁድም ተርፎበታል እነሆም ሁሉ ለየሕዝባቸው የሚያደርጉትን ተመልክቼ ከገሬ ሕዝብ ባጣጥረው በጣም ይገርመኛል ከገሬ ጭምር እራሴን እንቀዋለሁ ተልቤም ጋራ አገሬ የጐደለበት ነገር ከቶ ምን ይሆን ብየ ብመራመር ሕዝቡ በትምሕርት በጥበብ አለማደግ በስተቀር ሌላ የቀረበት ነገር አልታየኝም መንግሥታችን ከተተከለ ያልተነቀለ ነው የውነት ብርሃን ክርስትና ከድሮ የገባበት ሕዝብ ነው እላለሁ እስላምና አይሁድ እረመኔ ስንኳ ሳይቀር በገንዘብ በጥበብ እኛን መብለጣቸውም ወንድ ልጅና ሴት ልጅ ለይተው የድኃና አባት እናት የሌለው ልጅ ሰብስበው ተማሪ ቤት ከፍተው በትምርት ቢያሳድጓቸው ነው እንጂ በሌላ እንዳይደለ ተረዳኝ። አገራችንም ትምሕርት ከማጣት የተነሣ የድንቍርና ጭጋግ እያደረ ሲሸፍነው ሕዝብ የምያስተዳድር መንግሥት እየጠና የሚሔድበት ጥበብን ሁሉ ትቶ እስተመጸየፉ ደረሰ በትምርት ያሳደጓቸው በሀብት በሞያ ከርሱ በላይ ሁነው ለእለት ምግብ የነሱ እሽከር ሆኖ መኖሩ በዚያ ብናቀውና በተጸየፈው ጥበብ መሆኑን ገና ልብ አላደረገውም ይህም ሁሉ ባይማርና በትምርት ባያድግ ነው ። ይህን ሁሉ እያሰብሁ ሲቈጨኝ ይኖር ነበር ኢየሩሳሌም ቅድስት ለመሳም ከመጣው ወንድ መኰንን ሴት ወይዘሮ ይህነኑን ያላጫወትኩት የለም ይነቃቁበታል ስል። ሚያዝያ ፳፪ ቀን ፲፱፻፲፯ ዓ ም ብርሃንና ሰላም አዲስ አበባ ላይ ተማሪ ቤት በሚያዝያ ፲፱ ቀን ተከፈተ ብሎ ሲያወራ ልቤ ውስጥ የተሰማኝ ደስታ የደስታ ደስታ ነው የይስሐቅ ልጅ ያዕቆብ ልጆቹ ከምስር ተመልሰው ልጅህ ዮሴፍ አልሞተም አለ ብለው የነገሩት ጊዜ ደስ ያለውን ደስታ ያህል ነው ። በኔ ዕድሜ ይህን መስማቴ ለኔ የኢትዮጵያ ትንሣኤ ማየት ያህል ነው ። ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ የተማሪ ቤትን ለኢትዮጵያ በረከት ሲያቀስቡ በጉባዔ እንደ ተናገሩት ለኢትዮጵያ ነፃነት ጽናት ወሰንዋን ጠብቆ አሳፍሮ አስከብሮ ለማኰራትና የሕዝብዋ ሃብ የታመነ ኃይል እንዲኖረው ለማድረግ መሣሪያው ትምርት መማር ነው ።

ልጅ ሲወለድ እማማ ማለትን እንደሚማር እኔም ታገሬ በምናና እንደወጣሁ ምኞቴ ኢትዮጵያ ብትማር ነበር ። እምና ልዑል አልጋ ወራሽ ወደ ኤውሮጳ ሲሄዱ ያዩትን የለማ አበባ ፍሬ ሁሉ ወስደው በኢትዮጵያ መዝራት እንዲጀምሩ ተስፋ ነበረኝ ። የተማሪ ቤት ማቆምን ነገር ዓለም ከተፈጠረ እስከዛሬ ስለ ሁለተኛ እናት እንጂ በዕንቍ ተመዝና ይህን ያህል ታወጣለች የሚል የለም ። ስለዚህ ተማሩ የኢትዮጵያ ልጆች የናታችሁን ጸጸትና ያባቶቻችሁን ድካም መልሱ አገራችሁ በሞላ ተግቶ ተነስቷልና እናንተን ብቻ ለማሳደግ በርቱ ስለምን አገሩን የሚያስከብር የተቀጣና የተማረ አዋቂ ነው የኤውሮጳ ነገሥታት እንዲህ ያለ ስምና ክብር የሚሰጣቸው ሕዝባቸው ሁሉ ብቻ አይደለም ግን እውቀታቸው ዓለምን የሚጠቅም ስለሆነ ነው እናንተም ኢትዮጵያን በውቀታችሁና በብርቱ ትጋት ተነሱም ይበልጥ ልታደርጓት ይቻላችኋል ።

ማን እናቱ ብትዋረድ ይወዳል? እንበሳ ጥጃ ተናቱ መለየት እንደሚጠላ ሐበሻ ሁኖ ተኢትዮጵያ መውጣትን ማን ይወዳል? ለእምላክ ቀራንዮ ባይሆን እኔም ታገሬ አልወጣም ነበር ጥቂት ቀን ልቅሶ ይሻላል ተዚህ ዓለም ደስታ፤ እግዚአብሔር ደግሞ በቸርነቱ ክንፍ አቅፎ ለኢትዮጵያ ብርሃንና ሰላም ግርማዊት ንግሥትና ልዑል አልጋ ወራሽን ሌት ተቀን እንደሚደክሙባት አይቶ የተከሉትን የኰተኰቱትን ዘር ፍሬና መዓዛ ለብዙ ዘመን ያሳያቸው ብየ ፈጣሪየን እለምነዋለሁ ።

አሁንም ባለኝ አቅሜ ለተማሪ ቤት እርዳታ የሚሆን መግቢያ ፭ ወርቅ የምስር ባመት ባመቱ ፴ ብር እሰጣለሁ ።

ወይዘሮ ደስታ

በኢትዮጵያውያን ማኅበር ለሚቆመው ተማሪ ቤት እርዳታ እንሰጣለ ብለው ፊርማቸው የሰጡ ሰዎች ።

ከ፴፮ ቍጥር የመጣ ድምር ፭ሺ ፯፻ ብር ተ፱ ሩብ ።

ወይዘሮ ደስታ መግቢያ ፭ የምስር ወርቅ ባመት ባመት	፴ ብር
ራስ ናደው ።	፫፪ ብር
ደጃዝማች ጌታቸው ።	፳፪ ብር
ጸሐፌ ትእዛዝ ወልደ መስቀል ።	፬ ብር
አቶ ኃይሌ ሮበ ።	፫ ብር
አቶ ያግሉ አበ ወሎ ።–	፭ ብር

ድምር ፭ የምስር ወርቅ ፤ ፭ሺ ፯፻፺፮ ብር ተ፱ ሩብ

በልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

መጀመሪያ ዓመት ፤ ቁጥር ፴፫።
1re ANNÉE № 33

ሐሙስ ነሐሴ ፯ ቀን ፲፱፻፲፯ ዓ.ም።
JEUDI 13 AOUT 1925

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን በገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen , Héritier du trône d' Ethiopi , eprofondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix , a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les jeudis

Direction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

የጋዜጣው ዲሬክተር ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።
Gabré Christo Taklé Haymanot
Dirécteur

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ስለ ፍልሰታ ጾምና ጸሎት ።

የፍልሰታ ጾም የተጀመረበት ምክንያት በነገረ ማርያምና በስንክሳር እንደተጻፈው እንዲህ ነው፤አባቶቻችን የእመቤታችን የሞቷና የእርገቷ ነገር ባይረዳቸው ነሐሴ ፩ቀን ጀምረው እስከ ፲፬ ቀን ጾመዋል በ፲፮ ኛው ቀን መልአክ አምጥቶ ሰጥታቸው ቀብረዋት በሦስተኛው ቀን ተነሥታለች ስለዚህ የኢትዮጵያ ሊቃውንት ለእመቤታችን መታሰቢያ ብለው ከሰባቱ አጽዋማት ጨምረው አዘውናል ። ያባቶቻችንን ትእዛዝ አክብረን የእመቤታችንን መታሰቢያ ባመት ባመት ከነሐሴ አንድ ቀን ጀምረን እስከ አሥራስድስት ቀን ንጽሕናዋን ቅድስናዋን እያሰብን ኋላም ከሞት ወደ ሕይወት ከመቃብር ወደ ክብር መሄዷን እያሰብን እንጾማለን በዚሁ ጾም ጊዜ በኢትዮጵያ ያሉ ክርስቲያን ከመኳንንቲም ከወይዛዝሩም ከካህናቱም ከመነኰሳቱም ወገን ሁሉ ከሰው ተለይተው ጥሬ በልተው ውሃ ጠጥተው የሚጾሙ አሉ ። ጾምና ጸሎት በልብ ቅንነት ከእግዚአብሔር ጋራ ለመታረቅና የኃጢአትን ሥርየት ለማግኘት ቢያደርጉት ከእግዚአብሔር ምሕረትና ይቅርታ ያሰጣል ሙሉ ታሪኩን በልዑል አልጋ ወራሽ ማተሚያ ቤት በታተመው በሰንበት ውዳሴ ማርያም ትርጓሜ ፻፸ ገጽ ተመልከት ።

ይድረስ ለብርሃንና ሰላም ዲሬክተር ።

በአዲስ አበባ በልዑል አልጋ ወራሽ ማተሚያ ቤት ብርሃንና ሰላም የሚባል ጋዜጣ በተጀመረ ጊዜ እንዲህ በቶሎ በያገሩ የሚደርስ አልመሰለኝም ነበረ አሁን ግን ከኢትዮጵያ በጣም ሩቅ ወደሚሆን ወደ አውሮጳ ድረስ በመምጣቱና ለኢትዮጵያ ልጆች ያገራቸውን ወሬ በማስታወቁ ብዙ ደስ አለኝ፤ እኔ ራሴ በገኔብ ሳለሁ ፫ ጊዜ ደረሰልኝ።በፊት ያልሰማሁትን አዲስ ወሬ አገኘሁበት ስለዚህ ዲሬክተሩንና ሠራተኞቹን ሁሉ በጣም አመሰግናለሁ ደግሞ ወደፊት ሥራው እየበዛና እየሰፋ እንዲሔድ የልቤን ምኞት አቀርባለሁ በአውሮጳ በየትምሕርት ቤት የሚኖሩ የኢ

ብላታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ።

ትዮጵያ ልጆች ሁሉ በዚህ ነገር በጣም ደስ ብሏቸዋል በየሳምንቱም ብርሃንና ሰላምን ለማግኘት በፍጹም ልባቸው ይመኛሉ ።

አሁንም ለመንግሥታችን ጉዳይ ተልከን ወደ ገኔብ መጥተን ሳለን ያየሁትና የሰማሁት ነገር ለዓለም ብርሃንና ሰላምን የሚያመጣ ነውና ከዚህ በታች የተጻፉትን ጥቂቶች ቃሎች በብርሃንና ሰላም ውስጥ ገብተው እንዲታተሙልኝ ዲሬክተሩን እለምናለሁ ። ቃሎቹም ከዚህ ቀጥሎ ያሉት ናቸው ።

ከሰባት ዓመት አስቀድሞ በሙሉ አውሮጳ የተደረገው ትልቁ ጦርነት በዓለም ላይ ትልቅ ጉዳት እንዳመጣ መንግሥቶቹና ሕዝቡ ሁሉ ተረድተው በነገሩ በጣም እንዳዘኑበት ዛሬ ተመሰከረ ። ጉዳት መሆኑንም መረዳታቸው ትምሕርታቸውና እውቀታቸው ስለበዛ ነው ።

ደግሞ ዛፍ በፍሬው እንዲታወቅ እውቀትም የምትገለጠው በስራ ነውና እውቀታቸውን በስራ ለመግለጥ ስለ ሰውብ በዓለም ላይ የማይገባ የጦርነት መሣሪያ ንግድና የመርዝና የተቀመመ መድኃኒት በጦርነት ጊዜ እንዳይደረግ ብለው ይህን ለመወሰንና ውል ተዋውለው ደንብ ለማቆም በስዊስ አገር በመንግሥቶች ማህበር ስፍራ በገኔብ ጉባኤ እንዲሆን ተማከሩ ። ይህንም አሳባቸውን ለየመንግሥቱ ሁሉ አስታወቁ ኢትዮጵያም ከዓለም መንግሥቶች ጋራ ማህበር ገብታለችና ለዚሁ ጉባኤ ስለ ተጠራች መላክተኞች ላከች ።

ጉባኤውም የተጀመረው እንደ ኢትዮጵያ ቍጥር በሚያዚያ ፳፯ ፲፱፻፲፯ ነበረ ለዚህም ጉባኤ መላክተኞች የላኩ መንግሥቶች ፵፬ ናቸው ስማቸውም በውሉ እንደ ተጻፈው ተራ ከዚህ ቀጥሎ ያለው ነው ።

ጀርመን ፡	መላክተኞቹ ፡	፯ሰዎች ፡
አሜሪካ ፡	መላክተኞቹ ፡	፱ሰዎች ፡
አውስትርያ ፡	መላክተኞቹ ፡	፪ሰዎች ፡
ቤልጅክ ፡	መላክተኞቹ ፡	፫ሰዎች ፡
ብራዚል ፡	መላክተኞቹ ፡	፪ሰዎች ፡
እንግሊዝ ፡	መላክተኞቹ ፡	፱ሰዎች ፡
ቡልጋርያ ፡	መላክተኛው ፡	፩ሰው ፡
ካናዳ ፡	መላክተኛው ፡	፩ሰው ፡
ሺሊ ፡	መላክተኞቹ ፡	፫ሰዎች ፡
ቺን ፡	መላክተኛው ፡	፩ሰው ፡
ኮሎምበ ፡	መላክተኛው ፡	፩ሰው ፡
ዐኄማርክ ፡	መላክተኞቹ ፡	፪ሰዎች ፡
ምስር ፡	መላክተኞቹ ፡	፫ሰዎች ፡
እስጳንያ ፡	መላክተኞቹ ፡	፬ሰዎች ፡
ኢስቶኒ ፡	መላክተኛው ፡	፩ሰው ፡
ኢትዮጵያ ፡	መላክተኞቹ ፡	፫ሰዎች ፡
ፊንላንድ ፡	መላክተኛው ፡	፩ሰው ፡
ፈረንሳዊ ፡	መላክተኞቹ ፡	፲፩ሰዎች ፡
ግሪክ ፡	መላክተኞቹ ፡	፪ሰዎች ፡
ሁን ጋሬያ ፡	መላክተኛው ፡	፩ሰው ፡
ህንድ ፡	መላክተኞቹ ፡	፬ሰዎች ፡
አይርላንድ ፡	መላክተኛው ፡	፩ሰው ፡
ኢጣልያ ፡	መላክተኞቹ ፡	፰ሰዎች ፡
ጃፓን ፡	መላክተኞቹ ፡	፭ሰዎች
ሌቶኒ ፡	መላክተኛው ፡	፩ሰው ፡
ሊቶአኒ ፡	መላክተኞቹ ፡	፪ሰዎች ፡
ሉክሳምቡርግ ፡	መላክተኛው ፡	፩ሰው ፡
ኒካራጉዋ ፡	መላክተኛው ፡	፩ሰው ፡
ኖርዌ ፡	መላክተኛው ፡	፩ሰው ፡
ፓናማ ፡	መላክተኛው ፡	፩ሰው ፡
ሆላንድ ፡	መላክተኞቹ ፡	፪ሰዎች ፡
ፋርስ ፡	መላክተኞቹ ፡	፪ሰዎች ፡
ፖሎኝ ፡	መላክተኞቹ ፡	፯ሰዎች ፡
ፖርቱጋል ፡	መላክተኞቹ ፡	፪ሰዎች ፡
ሩማኒያ ፡	መላክተኞቹ ፡	፪ሰዎች ፡
ሳልባዶር ፡	መላክተኛው ፡	፩ሰው ፡
ሰርብያ ፡	መላክተኞቹ ፡	፫ሰዎች ፡
ሲያም ፡	መላክተኞቹ ፡	፪ሰዎች ፡
ስዊድን ፡	መላክተኞቹ ፡	፫ሰዎች ፡
ቸኮስላባኪያ ፡	መላክተኞቹ ፡	፪ሰዎች ፡
ቱርክ ፡	መላክተኞቹ ፡	፪ሰዎች ፡
ኡርጉዋይ ፡	መላክተኛው ፡	፩ሰው ፡
ቬኔዚዌላ ፡	መላክተኛው ፡	፩ሰው ፡
አርጀንቲን ፡	መላክተኞቹ ፡	፫ሰዎች ፡

ድምር ፵፬ መንግሥቶች ፻፳፩ መላክተኞች ናቸው ።

በዚህም በጦርነት መሣሪያ ንግድና በተቀመመ የመድኃኒት ጦርነት እንዳያደርጉ አንድ ወር ከ፲፫ ቀን ተከራከሩ ክርክሩም እጅግ የበረታ ነበረ አንዱ መንግሥት የወደደውን ሌላው መንግሥት አልወድም ይላል ። ሌላው አልወድም ያለውን አንዱ እወዳለሁ ይላል ። ነገር ግን ትምህርትና እውቀት ያላቸው ሰዎች ናቸውና በየቀኑ ባንዳንድ ነገር እየተሰማሙ ይድሩ ነበረ ፤ በመጨረሻውም በጦርነት መሳሪያ መነገድ እንዲቀር መንግሥቱ ብቻ የሚያስፈልገውን መሳሪያ እንዲያገኝ በመድኃኒት የተቀመመ የመርዝ ጦርነት በጭራሽ እንዲቀር ተስማምተው ጨረሱ ። በጣም ያልሰለጠኑና ዕውቀት የሌላቸው መንግሥቶች ይህን ደምብና ሕግ ለመጠበቅ አይችሉም ብለው ከአፍሪቃና ከእስያ ክፍል በብዙ አገሮች የጦርነት መሳሪያ በጭራሽ እንዳይገባ አገሩን ወስነው ከለከሉ በካርታም ለይተው ጻፉ ።

ኢትዮጵያ ከዳዊት ከሰሎሞን አስቀድሞ በነጻነቷ ጸንታ ስለ ክርስትናዋ ከእስላምና ከአረመኔ ጋራ ስትጋደል የኖረች መንግሥት እንደ ምን አድርጋ የጦርነት መሣሪያ ትከለከላለች ከዓለም መንግሥቶችስ ጋራ ማህበር መግባቷ የዓለም መንግሥቶች ከሚያገኙት ጥቅም ተካፋይ እንድትሆን አይደለምን ብለን ለጉባኤው ነገራችንን አመለከትን ።

የኢትዮጵያንም ነገር በጣም የሚያውቁት በዙሪያዋ የቅኝ አገር ያላቸው እንግሊዝና ፈረንሳዊ ፣ ኢጣልያ ናቸውና በወሰን የምንገናኝ ስለ ሆነ በጠመንጃና በጥይት እየተነገደ በወሰን ላይ ሁከት እንዳይሆን ብለን ነው እንጂ የኢትዮጵያን ነጻነት ለመንካትና የሚገባትን የጦርነት መሣሪያ ለመከልከል ብለን አይደለም አሁንም በጠመንጃና በጥይት ንግድ እንዳይነገድ ከጠበቃችሁ ለኢትዮጵያ መንግሥት ለራሱ የሚያስፈልገውን የጦርነት መሣሪያ አትከለክልም ። ይህንንም በሰማን ጊዜ የኢትዮጵያ መንግሥት በጠመንጃና በጥይት መነገድ የማይገባ መሆኑን ራሱ አውቆ ይህንኑ ለማስቀረት ገና አስቀድሞ አዋጅ ነግሮ በፈቃዱ ደንብ አቍሟል ይህንኑም አስቀድሞ ያቆመውን ደንብ ባለፈው ዓመት ለመንግሥታት ማህበር ጽሕፈት ቤት ልኳል ብለን መለስንላቸው ።

ከዚህም በኋላ በኢትዮጵያ ዙሪያ በቅኝ አገሮች ያሏቸው እንግሊዝና ፈረንሳዊ፤ ኢጣልያም የኢትዮጵያ መንግሥት መላክተኞች የፍቅርና የወዳጅነት ቃል እንጂ የክርክር ቃል አለመፈለጋችንን ስለተረዱት ነገሩ በፍቅርና በወዳጅነት እንዲጨረስ ለየመንግሥታችን አመልክተን ምላሹን እንነግራችኋለን ብለው ነገሩን እስከ ስምንት ቀን አቆዩት በስምንተኛውም ቀን ሁሉም ባንድነት የኢትዮጵያ መንግሥት ለራሱ የጦርነት መሣሪያ ማግኘቱንና በጦርነት መሣሪያ ንግድ ማስቀረቱን ወደናል ብለው ተቀበሉ ።

ስለ ጦርነት መሣሪያ ንግድና ስለ ተቀመመ የመድኃኒት መርዝ ማስቀረት አርባ አራት መንግሥቶች ተስማምተው ውሉ በተፈረመበት ቀን ለኢትዮጵያ መንግሥት የተደረገውን ክብር ከዚህ ቀጥሎ እንደ ተጻፈው አመለክታለሁ ።

አምና ሐምሌ በ፲፱፻፲፮ ዓመ ምሕ የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና እንደራሴ ልዑል ተፈሪ መኰንን ወደ አውሮጳ መጥተው ከነገሥታቱና ከመሳፍንቱ ከሚኒንንቱም ተገናኝተው የኢትዮጵያን መንግሥት ቀደምትነትና የሚያስፈልጋትንም ሁሉ ካስታወቁ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ በሚመለሱበት ጊዜ የዓለም መንግሥቶች ማህበር ያቆሙበትን ገኔብን ሳላይ አልሔድም ብለው ከፓሪስ ወደ ገኔብ መጥተው ነበረና ወደ መንግሥታት ማህበር ጽሕፈት ቤት ደረሱ ። በዚያም የተደረገላቸውን የክብር አቀባበል በአውሮጳ የመንገድ ታሪካቸው ተጽፏልና አሁን ለመጻፍ አያስፈልግም።

የመንግሥታትንም ማህበር ቤት ካዩ በኋላ በዋናው የጽሕፈት ቤት ተቀምጦ ለኢትዮጵያ መንግሥት መታሰቢያ ሆኖ እንዲኖር ብለው በአዲስ አበባ ከጥሩ ወርቅና ከአውራሪስ ቀንድ፤ ከዝሆን ጥርስም በብዙ ብልሃት የተሠራ የጽሕፈት ዕቃ ሰጥተው ነበረ ።

ይህም የዛሬው ጉባኤ የተሰበሰበበት የጦርነት መሣሪያ ንግድ ነገር በስምምነት ካለቀ በኋላ ውሉ ተጽፎ የየመንግሥቱ መላክተኞች እንዲፈርሙበት ቀረበ ። በዚያም ጊዜ የዋናው ጽሕፈት ጸሐፊ ልዑል አልጋ ወራሽ አምና ለዚሁ የመንግሥታት ማህበር ጽሕፈት ቤት ስለ ኢትዮጵያ መንግሥት መታሰቢያ ብለው የሰጡትን የጽሕፈት ዕቃ አምጥቶ በጉባኤው መካከል በታላቅ ጠረጴዛ ላይ አኖረው ።

የዚህንም የጽሕፈት ዕቃ የስራውን ማማር በሙሉ ለመጻፍ ባይቻለኝ እንኳ በትንሹ ከዚህ ቀጥሎ እንደተጻፈው ነው ።

ታቹ መቋሚያው ከዝሆን ጥርስ የተሰራ ነው ። ወደ ላይ በቀኝና በግራ በሁለት የአውራሪስ ቀንድ እንደ ቅስት ሆኖ ተገናኝቷል በቅስቱ ላይ የቅዱስ ጊዮርጊስ ሥዕል በፈረስ ተቀምጦ ደራጎንን እንደገደለ ሆኖ የተቀረጸበት የኢትዮጵያ ዘውድ ከጥሩ ወርቅ ተሠርቶ ይታያል ። ዘውዱና ሁለቱ የአውራሪስ ቀንዶች በወርቅ የእርባን ሥራ ተጋጥመዋል ፦

ከዘውዱ በታች አሥር ሳንቲም ያህል ዝቅ ብሎ ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ የተባለው የኢትዮጵያ ትዕምርተ መንግሥት (አርማ) አንበሳው ለክርስቲያንነታችን ምልክት የሚሆነንን መስቀሉን ተሸክሞ የነገሥታቶቻችንን ምልክት የሚሆን ዘውዱን ጭኖ በእርባን ሥራ ተሠርቶ በወርቅ ሰንሰለት በመካከል ተንጠልጥሎ ይታያል ።

ባንደኛው አውራሪስ ቀንድ በመካከሉ ላይ ዘውዲቱ ንግሥተ ነገሥታት ዘኢትዮጵያ ተብሎ የግርማዊት ንግሥታችን ስም በወርቅ እርባን ሥራ ተቀርጾ ይታያል ።

በሁለተኛው የአውራሪስ ቀንድ በመካከሉ ላይ የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና እንደራሴ ተፈሪ መኰንን ተብሎ የልዑል ጌታችን ስም በወርቅ እርባን ሥራ ተቀርጾ ይታያል ሁለቱ የአውራሪስ ቀንዶች በዝሆን ጥርሲ ላይ ቆመው በወርቅ የእርባን ሥራ ተያይዘዋል ።

ይህም የጽሕፈት ዕቃ ከታችኛው ከዝሆን ጥርሱ ጀምሮ እስከ ዘውዱ ጫፍ ቁመቱ ሥልሳ ሳንቲም ይሆናል ካንድ ክንድ ጥቂት ይረዝማል ።

የቀለሙ መያዣ አራት ሆኖ ከዝሆን ጥርስ እየተፈለፈለ ጫፍ ጫፉ በወርቅ የተከፈፈ ነው ለዚሁም የሚያስፈልገው አራት ብርዕ ከዝሆን ጥርስ ተሠርቶ ብዕር ማግቢያው የወርቅ ነው ብርዕ ማስቀመጫውም እንደ ደረጃ እንደ እርከን እየሆነ ከጥሩ ወርቅ የተሠራ ነው ብርዑም ሲያድፍ የሚጠረግበት የሰፍነግ ማስቀመጫው ከዝሆን ጥርስ የተፈለፈለ ሆኖ በጫፉ ወርቅ የተከፈፈ ነው ሌላውም ይህን የመሰለው ለጽሕፈት ዕቃ የሚያስፈልገው ሁሉ አንድ ሳይቀር ከዝሆን ጥርስና ከወርቅ የተሰራ ነው ።

ይህም የኢትዮጵያ መንግሥት መታሰቢያ የሚሆን የጽሕፈት ዕቃ መጥቶ በጉባኤው መካከል በታላቅ ጠረጴዛ ላይ በተቀመጠ ጊዜ በጉባኤው የተቀመጡት የየመንግሥቱ መላክተኞች ሁሉ እየተነሱ ለማየት መጋፋት ብቻ ሆነ በሀገራችን በመቅ በዓል ቀን ለዑደት ታቦት በወጣ ጊዜ ሕዝቡ ለማየት እንዲሽቀዳደሙ ይህንም የጽሕፈት ዕቃ ለማየት ሁሉም ይሽቀዳደሙ ጀመሩ ።

ነገር ግን ጽሕፈቱ በኢትዮጵያ ቋንቋና ፊደል ስለ ሆነ ለማንበብ የሚቻገሩ ቢሆኑ ክቡር ደጃዝማች ጌታቸው አቶ ተስፋዬ ተገኝ እዚያው ቆሞ በፈረንሣዊ ቋንቋ እየተረጐመ እንዲያስረዳቸው ነገሩት አቶ ተስፋዬም እየተረጐመ አስረዳቸው በስራውም ማማርና ለመንግሥታት ማህበር በመስጠቱ ብዙ ደስ አላቸው

ከዚህም በኋላ ውሉ ቀረበና የየመንግሥቱ መላክተኞች በዚሁ በኢትዮጵያ መንግሥት መታሰቢያ ብርዕ ፈረሙ ።

እኛም ደስታችን ከልክ ያለፈ ሆነ ከደስታችንም ብዛት የተነሣ ክቡር ደጃዝማች ጌታቸው የዛሬ ደስታ ግርማዊት ንግሥትና ልዑል አልጋ ወራሽ ዛሬ በገኔብ በነበሩ ይህ ቀን የታላቅ በዓል ቀን ሆኖ ይቆጠር ነበረ ብለው ተናገሩ ።

ከዚህም በኋላ በመጀመሪያ የጉባኤውን ፕሬዚዳን (አለቃ) ቀጥሎም ፯ ትልቆች ሰዎች እየተነሡ የተሰበሰቡበት ነገር በመልካም መስማማት ስለ መፈጸሙ የደስታ ዲስኩር አድርገው ተለያዩ ።

ደግሞ ከዚህ ቀጥሎ ስለ ቋንቋ ነገር ትንሽ አመለክታለሁ ስለ ጦር መሣሪያ ንግድና ስለ ተቀመመ የመድኃኒት መርዝ ነገር የተሰበሰቡ ያርባ አራት መንግሥቶች መላክተኞች ሁሉ ከእንግሊዝና ከአሜሪካ መላክተኞች በቀር ሁሉም በፈረንሳዊ ቋንቋ ይናገራሉ እንግሊዝና አሜሪካም

ቋንቋቸውን ስለ ማክበር ብለው በእንግሊዝ ቋንቋ ይናገራሉ እንጂ የፈረንሳዊ ቋንቋ አጥርተው ያውቃሉ ።

በእንግሊዝ ቋንቋ የተነገረው በፈረንሳዊ ይተረጐማል ከፈረንሳዊም የተነገረው በእንግሊዝ ይተረጐማል ፤ ከእንግሊዝና ከፈረንሳዊ በቀር በጉባዔው ቀርቦ በገሩ ቋንቋ የሚናገር የለም ክቡር ደጃዝማች ጌታቸው ብቻ የኢትዮጵያን ጉዳይ ባማርኛ ቋንቋ እየተናገሩ በፈረንሳዊ ተተረጐመ እንዲህም ማለቴ ወደ ውጭ አገር የሚላክ ሰው በግድ አንድ የውጭ አገር ቋንቋ ማወቅ ያስፈልገዋል ማለቴ ነው እንጂ የእኛ ያማርኛ ቋንቋ በ፵፬ መንግሥቶች መላክተኞች ፊት በመነገሩ ማመስገኔ አይደለም ። ክቡር ደጃዝማች ጌታቸው ጥቂት ጥቂት የፈረንሳዊ ቋንቋ ያውቃሉ እኔም ጥቂት ጥቂት የእንግሊዝ ቋንቋ አውቃለሁ አቶ ተስፋዬ ተገኝም ደህና አድርጎ የፈረንሳዊ ቋንቋ ያውቃል ። ነገር ግን በተለየ የእኛ ጉዳይ ካልሆነ በቀር ሲከራከሩና ሲነጋገሩ በቶሎ ፍሬ ነገሩን ለይተው ለማወቅ ይቸግረን ነበረ ፤ በኋላ ግን የተነገረው ቃል ሁሉ አንዲት ነጥብ ሳይጐል በማተሚያ እየታተመ ለመላክተኛው ሁሉ ይላክ ነበረና ነገሩን በዚያ እናገኘዋለን በዚያ በገርጌብ ጉባዔ ክርክር አንዳንደ በየተራ እየተነሡ የፖለቲካውን ነገር እያቃኑ ሲናገሩ ያየ ሰው ቋንቋ ባለማወቁ በጣም ሳያዝን አይቀርም ፤ ወንድ ልጅም ያለው ሰው ዕለቱን ወደ ትምህርት ቤት ሳያገባው አያድርም ወደ ፊት ግን ግርማዊት ንግሥትና ልዑል አልጋ ወራሽ በኢትዮጵያ በየአውራጃው የትምህርት ቤት እንዲሠራ እያደረጉ የኢትዮጵያን ልጆች ከጨለማ ወደ ብርሃን ፤ ከድንቁርና ወደ ዕውቀት ያደርሱዋቸዋል ብለን ሙሉ ተስፋ እናደርጋለን ።

ብላታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ።

የክረምት ወሬ ።

ከሐምሌ ፳፮ ቀን ጀምሮ እስከ ነሐሴ ፫ ቀን ዝናብ አቋርጦ ነበር በዚሁ ምክንያት ጭቃው ደርቆ የአዲስ አበባ መንገድ ሁሉ ለሽርሽር የተመቸ ነበር ። ወደሥራ ስንሄድና ስንመለስ መንገዱ ጭቃ ስላልነበረው አያሰቅቀንም ነበር ። ግን ዝናብ ያነሰ እንደሆነ እህል ይጠፋል የሚል ሐሳብ ገባንና ክረምት በመላው ዝናብና ጭቃ ሆኖ ክረምት ሲያልፍ ሲሳይ ማግኘት ይሻለናልና ጌታችን ሆይ የክረምቱን ዝናብ አትንሳን ብለን አምላካችንን ወደመለመን ገባን ። የማለምኑትን የማይነሳ አምላካችንም ዝናመ ምሕረቱን ነሐሴ ፫ ቀን አዘነመና የእህሉ ቡቃያ አታክልቱ ሁሉ ዝናብ ጠግቦ በልምላሜ አወለወለና ቅባት የተቀባ መስሎ ቢታይ የሕዝቡ ልብ በደስታ ተንቀሳቀሰ ፈጣሪውንም አመሰገነ አዲስ አበባም ከዱሮው የበለጠ የተሰናዳ መንገድ ስላለው ጭቃው የሚያሰቅቅ የተበጀ መንገድ በሌለበት ነው እንጂ በሥራት በተበጀው መንገድ ላይ ቢሄዱ የሚያሰቅቅ ጭቃ የለበትም ።

የፈላስፎች ቃል ።

ልጅ ጉልበት ስለሌለው ለዘመዶቹ መታዘዝ ያስፈልገዋል መታዘዙ ጉልበት በማጣቱ አይሁን የልጅ ነፃነትን ጉልበት በማጣቱ መወሰን አይገባም ።

ዡሩሶ።

ሥራ ለመሥራት እዚህ እታች ነን እያንዳንዳችን አእምሮዋችንና ዕውቀታችንን ይዘናል እነዚህን የተቀበልነው ለራሳችንም ለባልንጀሮቻችንም የደኅንነት ሥራ ለመሥራት ነው እንጂ መቅበር አይገባንም

ዡል ሲሞን ።

የእግዚአብሔር እዳ ያለብን እሱን ብቻ መውደድ ነው

ላኮርዲል።

የልባችን ትዝብት ወደ ሙሉ ሰውነታችን የተላከ የአምላክ ቃል ነው

ሲክረቲፍ ።

የያዝነውን ሥራ አሳምሮ መሥራት መጀመሪያ ግብራችን ነው እውቀት ያለው ጉንዳን እንኳ ከጕሬው አልፎ ዓለምን ሁሉ ቢያይ ያሁኑንም ጊዜ ትቶ ዘላለምነትን ቢያስብ ምንም ቢሆን ከዚያው ትል አጕድሎ ወደ ጕሬው አይወስድም

ጉዮ ።

ፈንጠዝያህን ሳትመለከት አስቀድመህ ሳጥንህን መርምር

ፍራንክሊን፡

በኢትዮጵያውያን ማኅበር ለሚቆመው ተማሪ ቤት እርዳታ እንሰጣለን ብለው ፊርማቸውን የሰጡ ሰዎች ።

ከ፻፴፪ ቍጥር የመጣ ድምር ፰የምስር ወርቅ ፰ሺ፭፻፸፮ብር ተ፪ሩብ

አፈ ንጉሥ ከተማ ።	፷	ብር
ቤተማርያም በዛብህ ።	፪	ብር
ገብረኪዳን ጋሻው ።	፪	ብር

በርሻና በመሥሪያ ምኒስትር ሥራ ውስጥ ያሉ ሰዎች በኢትዮጵያውያን ማኅበር ለሚቆመው የትምህርት ቤት የሚሰጡትን እርዳታ ልክ የሚያስታውቅ

አቶ መኰንን ሀብተ ወልድ ።	፲	ብር
መምሬ ብሥራት ።	፰	ብር
ሙሴ ሐናፊ ።	፷	ብር
አቶ ቀጸላ ።	፫	ብር
ልጅ በድሉ ዮሴፍ ።	፫	ብር
አቶ አፈ ወርቅ ወልደ ጻድቅ ።	፫	ብር
አቶ ወንድማገኘሁ አፈሩ ።	፫	ብር
አቶ አስፋው ገብረ ዮሐንስ ።	፪	ብር
በሺ ወርቅ ኃይለ ድንግል ።	፭	ብር
እሼቴ ተክለ ወልድ ።	፭	ብር
መኰሪያ ወልዴ ።	፭	ብር
ዘውዴ ወልደ ሚካኤል ።	፭	ብር
ገብረ አምላክ ዘማርያም ።	፪	ብር
መንገሻ ሻረው ።	፭	ብር
መኰንኔ ።	፭	ብር
ተሰማ ወንድማገኘሁ ።	፭	ብር
ገብረ ማርያም ወልደ ገብርኤል ።	፭	ብር
አብተ ማርያም ሰልፋቆ ።	፭	ብር
ኃይለ ማርያም ።	፭	ብር
ኢርበሮ ።	፭	ብር
ወልደ ሐዋርያት ።	፭	ብር
መንገሻ ሀብተ ገብርኤል ።	፪	ሩብ
ተክለ ሥላሴ ወልደ ተክሌ ።	፪	ሩብ
ፈለቀ ።	፭	ብር

ድምር ፰ የምስር ወርቅ ፤ ፰ሺ፯፻፺፱ ብር ተ፪ ሩብ

በልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

መጀመሪያ ዓመት ፤ ቁጥር ፴፬።
1^re^ ANNÉE № 34

ሐሙስ ነሐሴ ፲፬ ቀን ፲፱፻፲፯ ዓ ም።
JEUDI 20 AOUT 1925

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d'Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

የጋዜጣው ዲሬክተር ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።
Gabré Christo Taklé Haymanot
Diréсteur

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ ሲገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ስለ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ ምኒልክ ልደት ።

ስለ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ዳግማዊ አጼ ምኒልክ ልደት ነሐሴ ፲፪ ባመት ባመቱ ኢትዮጵያ በደስታ ታከብረዋለች ። በ፲፰፻፴፱ ዓመተ ምሕረት ተወለዱ ። በ፲፰፻፹፩ ከጎንደር ተመለሱ ፳፭ ዓመት ከነገሡ በኋላ ፲፱፻፮ ዓመተ ምሕረት ዓረፉ ። ካረፉም ወዲህ ፲፩ ዓመት ይሆናል ። ምንም ቢሞቱ ልደታቸው በነሐሴ ፲፪ ቀን ሲታሰብ ይኖራል ከሌሊቱ በ፲፪ ሰዓት ፤ ዘንድሮም ነሐሴ ፲፪ ቀን የልደታቸው መታሰቢያ ፳፩ መድፍ ተተኰሰ ።

ስለ ቡሄ ።

ነሐሴ ፲፫ ቀን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የክብሩን መገለጥ እናከብራለን ።

ይልቁንም በበለጠ ሕፃናት ቡሄ ቡሄ እያሉ ይጫወታሉ ቡሄ የተባለበትንም ምክንያት ከቀድሞ የነበሩ አባቶቻችን እንዲህ ብለው ይተርካሉ ። ጌታ በደብረ ታቦር ብርሃነ መለኮቱን ለደቀ መዛሙርቱ በገለጠ ጊዜ በተራራው ዙሪያ ብርሃን ሁኑዋል ስለዚህ በተራራው ዙሪያ የነበሩ እረኞች ጊዜው አልመሽም መስሏቸው እስከ ጨለማ ከብቶቻቸውን ሲያበሉ ቆይተዋል አባቶቻቸውም ልጆቻችን ምን ሆኑ ወይስ ምን አግኝቷቸው ይሆን ብለው መብራት አብርተው ዳቦ ይዘውላቸው ቢሄዱም ከብቶቻቸውን እያበሉ ጋራፍ እያጮሁ ሲጫወቱ አገኙዋቸው ምነው እንዲህ እስቲጨልም ቆያችሁ ብለው ቢጠይቋቸው ቡ ሔ ብለዋል ይባላል ቡ ሔ ማለትም አምላክ አለ ማለት ነው ዛሬም ሕፃናት ይህን ቃል ለቃል ሲያያዝ የመጣውን ልማድ ይዘው ትልልቆቹ ቡሄ ቡሄ እያሉ መብራት እያበሩ በጎረቤት ክሊ ዘመድ ወዳጅ ዳቦ ይቀበላሉ ለትንንሾች ልጆችም ከቤታቸው ይልኩላቸዋል ።

በቀድሞ ዘመንም በዚሁ ቀን በጋራፍ እየተጋረፉ ብዙ ጫዋታ ይጨዋወቱ ነበር ዛሬ ዘመን ግን የጠበንጃና የሽጉጥ ተኵስ ስለ ተከለከለ የጋራፉ ድምጥ ከጠበንጃውና ከሽጉጡ ድምጥ ጋራ እንዳያሳስት ተብሎ በከተማ ተከልክሏል የቡሄንና የጭራሮውን መብራት ሽማግሎች ሲያወሩት እንደሰማን ተረክን

ስለ ውርስ ገንዘብ ።

ብዙ ሀብታሞች ጌቶችና መኳንንቶች ለልጆቻቸው ብዙ የሚወርሱት ርስትና ከብት ወርቅና ብር ሊተውላቸው ይጥራሉ ያከማቻሉ ። አባት ሲሞት ልጅ የሚወርሰው ነገር ቢያገኝና ከብቱ በኋላ ባይቸገር ባባቱም ዕዳ ባይያዝ መልካም ነው ። ከዚህ በፊት ብዙ ልጆች ከባቶቻቸው በኋላ ያባቶቻቸውን ወይም የናቶቻቸውን ሀብት ወርሰው ሲያበቁ ሳይጠቀሙ የቀሩና የተጎዱ ብዙ ናቸው ። የጎዳቸውም ገንዘብ መውረስ ሀብት ማግኘት አይደለም ። ግን ከገንዘብና ከከብት በፊት ሊወርሱት የሚገባ ከትምርት የሚገኘውን የዕውቀትን ሀብት አባቶቻቸው ኢላወረስዋቸውምና እንኳን የወረሱትን ሀብት ራሳቸውን ቅሉ መጠበቅ ባይችሉ ነው ። ለልጅ ብዙ ርስትና ከብት ወርቅና ብር ከማውረስ የትምርት ዕውቀት አውርሶ መሞት እጅግ የበለጠ ነው ፤ በፊት ዕውቀትን ወርሶ በኋላ ገንዘብ ቢያገኝ ገንዘብንና የገንዘብን ሞያ ያውቃልና በገንዘቡ እንደሚጠቅምበትና እንደሚጠቀምበት የታወቀ ነው ።

እንግዲህ ለልጆቻችሁ ከሌላ ሀብት ይልቅ በትምርት የሚገኘውን ዕውቀት እንድታወርሱዋቸው በጣም ተጣጣሩ በደስታም ታርፋላችሁ ፤ ልጆቻችሁ የተማሩ ከሆኑ ከናንተ በኋላ የሚቀረው ርስታችሁና ከብታችሁ ለጥቅም ይሆናል እንጂ እንዳልሆን ሆኖ አይባክንም ።

የእግዚአብሔር ፍርሐት የበለጠ ጥበብ የዘለዓለም ሕይወት የሚያስገኝና ላገሩና ለመንግሥቱ የታመነ ወንድ መሆን ንጹሕ ሕሊናና የተከናወነ ኑሮ በትምሕርት ይገኛል ያድጋልም ።

ልዑል የኢ መ አ ወ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ ልጆች የትምርት ዕውቀት ቢወርሱ ለራሳቸው ተጠብቀው ሀገራቸውን ይጠብቃሉ ብለው ስላሰቡ ገንዘባቸውን ብቻ አይደለም የሚሠው የኢትዮጵያ ልጆች ዕውቀት እንዲወርሱ በጣም ይደክማሉ እንጂ

እኛም የኢትዮጵያ ሰዎች ይኸን ትልቅ ሐሳብ ለጥቅማችንና ለደስታችን እንደሆነ አውቀናልና ለልጆቻችን የትምርት ዕውቀት እንድናወርሳቸው ገንዘባችንና ጒልበታችንን በመሠዋት ሙሉ ፈቃድ አድርገን ክፍ ወዳለ የሥልጣኔ መዓርግ የሚያደርስና ብርሃንና ሰላም የሚሰጥየል አወ ተፈሪ መኰንንን ሐሳብ፡እንከተል

ያልተማረ ልጅ ብዙ ገንዘብ በመውረሱ እንዳይጠቀም ባያሌ ሰዎች ተገልጧል ። ብዙ ገንዘብ አለድክም ያገኘ እንደ ሆነ ያ እስኪያልቅ ድረስ ሲቀማጠል ሲበላ ሲጠጣ ይቈያል ሥራም አይሠራ ወደጥፋት የሚጐትተውን የሐኬት ኑሮ ይማራል

ገንዘቡን ሁሉ አባክኖ ሲጨርስም ሠርቶ እንዳይበላ የለመደው ሀኬት ነውና እጁና እግሩ በሐኬት ኑሮ መንምነዋል ስለዚህ ገና በሕይወቱ ምውት ነው የዘመዶቹ ሐዘን ሆኖ ይኖራል

ትርፉም ዛሬ ሆን ነውና እንጂ የእገሌ ልጅ እኮ ነው እንደዛሬ አይምሰላችሁ የሚል የስንፍና ትምክህት ብቻ መስማት ነው ።

የተመቸ ጊዜ ሳለን ለልጆቻችን ከሁሉ አስቀድመን የትምርት ዕውቀት እናውርሳቸው ስንሞትም ሕያዋን ሰዎች ተክተን ስለምንሞት ፀፀት የለብንም ።

የሚታሰብና የሚነገር በማድረግ በጎ ሥራን መግለጥ እንዲገባ።

ለኢትዮጵያ ልጆች ጥቅም የሚያስቡ ብዙ ብልሆች ሰዎች በብርሃንና ሰላም ምክራቸውንና የሐሳባቸውን ዕውቀት በግልጥ ማስታወቅ ከጀመሩ ብዙ ጊዜ ሆነ ብርሃንና ሰላም በቅንነት የተሠራና የቆመ ለኢትዮጵያ ልጆች ዕውቀቱንና ጥቅሙን ያፈሳል ያዘንማል በዝናሙ የበቀለው የዕውቀት ዘር አብቦ እናየዋለን ፤ ደግሞ በትክክል አፍርቶ ፍሬውን ለመብላት እንዲያበቃን የተስፋ ባለቤት እግዚአብሔርን እንለምናለን ፤ ግን በብርሃንና ሰላም እጅ የተዘራ ከወፍራም ምድር የወደቀ ፈጥኖ ፡ ፴ ፷ ፻ ፍሬ አፍርቷልና ይህን ተሰብስቦ ለመብላት ጊዜ እንድናገኝ ተስፋ እናደርጋለን ። ግን ተርበን ሳለን የጠገብን መስለን መኖራችን ርኅሩኅ ልብ ላለው ሰው እጅግ ያሳዝናል እነዚያም የውትትና የርኅራኄ ዘርን ዘርተው ፍሬውን ለመሰብሰብ ያልተጉና ያልቸኰሉ ሰዎች ለሌላ ሰው እንጂ ለራሳቸው ጥቅም ያላሰቡ ይመስላሉ እንደዚህ ያሉ ሰዎችም የገንዳና የፋና ምሳሌ ሳይሆኑ አይቀሩም የመከረውን የማያደርግና የማይፈጽም በኋር ቆመው ለሚያዩት ሰዎች መዘበቻ እንዲሆን የታወቀ ነገር ነውና ይህን በብርሃንና ሰላም የለሰለሰ ቅብቅብ ምክርና ሀሳብ በትጋት ማድረግ እንዲገባን ብርሃንና ሰላም ለፍቅር ማበረተኞቹ ያመለክታል ።

ሐዋርያ ያዕቆብም ም ፬ ቁ ፲፯ ደግ ነገርን የሚያውቃት አውቆም የማይሠራት እሷ ኃጢአት ዕዳ ትሆንበታለች ብሏል በዚያች ባሥረኛዪቱ ኢትዮጵያ በተባለች ወጥመድ ሰው ሁሉ እንደተያዘባት በጎውንም ነገር ማድረግ ወዶ ሲቻለው አለመሥራት አሥራንደኛ ሳትሆን አትቀርም ። ደግሞ በቃላቸውም በጋዜጣም በጎ ሥራ የሚያመለክቱ ሰዎች አስቀድመው ራሳቸው እንዲጀምሩና ለሌላው መሪ መሆን ይገባቸዋል ።

ይህ ካልሆነ በጎውን ሥራ አመልክቶ መተው።ሕግ ጠባቂዎችነን እንደሚሉ ከቡድ ሸክም አሥረው እንሥታችሁ ተሸከሙ ብለው እሳቸው ግን በጣታቸው እንደማይነኩት እንደ ጸሐፍት ፈሪሳውያን መሆን ነውና ። የበለጠ የግብዝና ምንጭ መሆን ነው ወይስ በዮሐንስ ም ፰ ቁ ፫ በሴሰኝነት ተገኘች ብለው ባቀረቡለት ጊዜ እሷ የሠራችውን ከናንተ ወገን ያልሠራ በደንጊያ ይግደላት ያለውን ባናስብ ይሆን ? ኋላም ወቃሾቻችን መጻሕፍት ናቸው እንጂ ሌላ አዋቂ ነኝ ባይ አይወቅሰንምና ብርሃንና ሰላም ጠበቃ ሆኖ እንዳይሞግተን ዛሬ አስቀድመን እጃችንን እንስጥ ።

አሐዱ. ኢትዮጵያዊ ።

ክብ ወይም ከባቢ የሆን ቃል ።

ክብ ማለት በዙሪያው የተከበበ ነው ። ከባቢ ማለት በፀላታቸው ላይ አደጋ በዙሪያው ከበው ድል ለማድረግ የሚቸኩሉ ጀግኖች ናቸው ። የኢትዮጵያ ጀግኖችና አዋቂዎች አሁን ፀላቶቻቸውን ከበው የሚያስጨንቁት ይመስላል ። ብርሃንና ሰላም በሚጽፍልን ቃል ሁሉ የመታደሳችንን የምስራች እንሰማለን በብርሃንና ሰላም ጋዜታ የሚጽፉ ወንድሞቼና እኔም በየጊዜው ከባቢ ከባቢ ቃል ጽፈናል ነገር ግን ደስ ይለኛል የውስጣችን ጨለማ በጥቂት ብርሃን ስለ ተከበበ ለመከበባችን ይልቁንም ለሙብዛታችን ከዚህ ቀጥሎ ስማቸው የተጻፈው ወይዘሮዎች እረድተዋል ። እንግዲህ ሴቶች ሣይቀሩ ወደሰልፉ ውጊያ ሲገቡ ጀግኖችማ እንደምን ለድሉ አይቸኩሉም ወይዘሮ አሰገዶች ሚካኤል ብሩ ወይዘሮ የውብዳር ሚካኤል ብሩ ወይዘሮ ደስታንም ወደ ሰልፉ እንደገቡ በብርሃንና በሰላም ጋዜታ አንብባችኋል ከእንግዲህ ወዲህ ከጨለማ ክድንቁርና ከምቀኝነት ከስንፍና ከብልግና እንፈራም ። እኔም ታናሽ ወንድማችሁ አሁን ብልግናን ለማቁሰል የቃል ፍላፃ እወረውራለሁ ። ብልግና በመልክም ሥራት አለመወሰን ነው በኢትዮጵያ የጋብቻ ሥራት እንደ ክርስቲያን ሥራ ለመፈጸም ያቃታቸው ይመስላል ። የብልግና መታሰቢያ ይህ ቀጥሎ ስማቸው የተጻፈው ቃሎች ናቸው ። የጭን ገረድ የከንፈር ወዳጅ የስርቆሽ በር እነዚህ ሥራትን የሚአፈርሱ የብልግና ስሞች በዚህ አገር ነፃነት ያላቸው ይመስላል በየክርስቲያኖቹ ቤት እንደምን ደፍረው ይገባሉ ። ስለ ጭን ገረድ ባንድ ሰው ቤት ሚስትና ገረድ ቢኖር ይህንን ምሥጢር ቄሱም ቢአውቅ ለሁለቱም የንስሐ አባት ቢሆን ብልግና ይመስላል ። ስለ ከንፈር ወዳጅ ልጅ አገረድ የከንፈር ወዳጅ ያዘች ተብሎ ከነውር ያልተቆጠረ እንደሆነ ከሕፃንነቷ ጀምሮ ለብልግናዋ እንደ ጉመጀች ታድጋለች ። ስለ ስርቆሽ፡በር፡ሰው ሁሉ በየቤቱ ሁለት በር እያበጀ ስርቆሽ በር የሚባል ስም የሚአወጣለት ስለምን ይሆን?። ይህንን የሚአውቅ የኢትዮጵያ ወዳጅ ቢኖር ትርጉሙን እንዲጽፍልኝ እለምነዋለሁ ። ስለ ጋብቻ ምኒልክ ይሙት አገባሁ ማለታችን ምኒልክ ይሙት ፈታሁ ለማለት እንዲቻል ይመስላል የጋብቻ ሥራት እንኳን ለክርስቲያኖች ለእስላሞችም ኒከ አላቸው ክርስቲያን የሆነ በእግዚአብሔር ቃል በቃል ኪዳን በመሐላ መጋባት የሚገባው ይመስላል ። ስለ ሴቶች ተማሪ ቤት እነዚያ

ሶስቱ ወይዘሮዎች እንደለመኑ ልመናቸውን ያገራቸው መንግሥትና ሕዝብ ሳይፈጽምላቸው አይቀርም የታመነ ተስፋ አላቸው ከዚህ ቀድሞ የነበረው የሴቶች ትምሕርት ከናቶቻቸው ነበረ እንጂ ከመምሕር ትምሕርት አላገኙም በእናቶቻቸው ላይ ሲደረግ ያዩትን ጉዳይ ሁሉ እንደቱም ነገር ተቀብለውት ይኖሩ ነበረ በእናቶቻቸው ላይ የሚአገኙት ትምሕርት ለባሎቻቸው እረዳት ማበጀት ባል ወደ መንገድ ሲሄድ ሥራ እንዳይፈታ ወዳጅን ማገልገል ። ከዚያ ከባላቸው የሚሻልም ሰው ቢገኝ ገንዘቤን አከፍለኝ ብለው ባላቸውን ከሰው መፋታት ። ከዚህም በኋላ ብዙህ ነፃነት ማግኘትን በእናቶቻቸው ላይ አይተዋልና ከዚህ የሚበልጥ ጥቅም መኖሩን አላወቁም የሚበልጠውን ጥቅም ለማግኘት ከትምሕርት በቀር መንገድ የለም ። ኢሳይያስ የሚለውን ስሙ አቤቱ ከእሊያ ሰዎች ጋራ አትቁጠረኝ የእንቅልፍ መንፈስ የፈሰሰባቸው ዓይናቸውን የሚጨፍን ማወቅ የሚገባኝን ምስጢር ባላስተውል በኢሳይያስ የተናገርከውን ትንቢት ፈጽምልኝ በዚያን ቀን ደንቆሮው የመጽሐፍን ነገር ይሰማል የእውር ዓይንም ከጨለማና ከጽጋግ ወጥቶ በመንፈስም የጥፋት ማስተዋልን ያውቃሉ ። እንቢተኞች ሕግን ይማራሉ አቤቱ በሕዝቅኤል የሰጠኸኝን ተስፋ ፈጽምልኝ ። አዲስ ልብ እሰጣችኋለሁ አዲስ መንፈስ በውስጣችሁ አኖራለሁ ። ከሥጋችሁም የድንጋዩን ልብ አወጣለሁ የሥጋንም ልብ እሰጣችኋለሁ የሚለው ትንቢት ለኢትዮጵያ ባሁኑ ጊዜ የሚፈጸምላት ይመስላል ። ስለ እህል ወደውጭ አገር መሸጥ ባለፈው ወራት ሕዝቡ እህላችን ተሸጠ እያለ ብዙህ ይወተውት ነበረ ነገሩን ብንመረምረው በብዙህ እርሱ እህሉን ሸጦ ሌላውን ጥቅምና ሐብት ቢአገኝ ምንቸገረው ብለን ቃልን ሁሉ ጽፈናል ። አሁን ግን ሕዝቡ ሁሉ የጠላው እህል ወደውጭ አገር መሸጡን አይደለም ። በተለየ ላ፩ ፩ ሰው ፈቃድ መስጠቱን ጠልቶ እህል ወደውጭ መሸጡን ወዶታል ነፃነቱና ፈቃዱ ለሞላዋ ኢትዮጵያ ቢሆን ሁሉም ያረሰውን ለቀለበ አስቀርቶ የተረፈውን ወደ ውጭ ቢሸጥ አልጠላም ።

ነጋድራስ ደስታ ።

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ልዑል ግራንድ ዱዩክ የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ተማሪቤት ለማየት በሔዱ ጊዜ ሐኪም ወርቅነህ የተናገሩት ቃል

ልዑል ግራንድ ዱዩክና ክቡራን ወይዛዝሮች መኳንንቶችም በዛሬ ቀን ሁላችንም ስለ ፍቅር ብላችሁ መጥታችሁ ስለጐበኛችሁን ስለ አስተማሪዎችና ተማሪዎች ሆኜ ፤ብዙ ደስታ አመሰግናለሁ ። ይኸ ተማሪ ቤት በሚያዝያ ፲፱ ቀን ተከፈተ የዚያን ጊዜ የተማሪዎች ቍጥራቸው ፴፪ ነበር ፣ ግን ዛሬ ድረስ ፹፩ ሆነዋል ብዬ በደስታ አስታውቃለሁ ። ደግሞ ብዙዎች ወደ ተማሪ ቤት አግቡን እያሉ ይለምናሉ ነገር ግን አያሌዎች ስለ እድሜያቸው ብዛትና ስለሌላም ምክንያት መግባት አልሆነላቸውም ። እላንት ክቡራን ወይዛዝሮችና መኳንንቶች የኛን ተማሪ ቤት ሥራ አለማለቁን እንደምታዩት ነው ። ይልቁንም ለኑዋሪ ተማሪዎች የሚሆነው ቤት ገና ፈጽሞ አላለቀም ። ነገር ግን አሳቢያችን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ይህ ሁሉ ሥራ ሳያልቅ የተማሪ ቤቱን በፍጥነት ከፈቱት ይህንም ያደረጉበት ምክንያት ለተማሪ ቤቱ በቶሎ መከፈትና ትምሕርት ለመጀመር ሲቸኩሉና ሲጨነቁ ለነበሩት ተማሪዎች መልካም ጊዜያቸው በከንቱ እንዳያልፍባቸው ሲሉ ነው ።

ለነዋሪ ተማሪዎች የሚሆነው ቤት በቶሎ አለማለቁ ለአያሌዎች ተማሪዎች ስለክረምትነቱ እጅግ ያስቸግራቸዋል ይልቁንም ለህጻናቶችና ቤታቸው ለራቀባቸው ተማሪዎች ግን እነዚህ ተማሪዎች ይኸን ችግራቸውን ሁሉ ጉዳይ ሳይሉት በጣም ደስ ብሏቸው ዘወትር ወደተማሪ ቤት ይመጣሉ ስል በደስታ አስታውቃለሁ ። በዚህ በመልካም አድርጎታቸው እግዚአብሔርም ዛሬ ድረስ ረድታቸው የዘንድሮን ክረምት በጣም አቅሎላቸዋል ።

ክረምቱ እንዳለቀ አንድ ትልቅ የትምህርት ማጥኛ አንድ በየ አይነቱ የተሰበሰበ መጻሕፍቶች ማኖሪያና ማንበቢያ ቤት አንድ የጅምናስቲክ መማሪያና አንድ የአናጢ ስራ መማሪያ ቤት አራት ክፍል ተማሪዎች የሚማሩበት ለሶስት ወይም ለአራት አስተማሪዎችና ለተማሪ ቤት አገልጋዮች የሚሆኑ ቤቶች በወዳጃችን እርዳታ ይሰራል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ ።

ተማሪ ቤቱ ፈጽሞ እስቲአልቅ ድረስ ገና ብዙ የሚሰራ ሥራ አለ ። ግን ትልቁ መሰረት አቋሚአችን በልግስና ከሚሠጡ እርዳታ በላይ ሌሎች ትምሕርት የሚወዱና ለኛ የሚአስቡ ሰዎች በኢትዮጵያ ህጻናቶችን በደህና ትምሕርትና በመልካም አስተዳደግ እንዲአድጉ የሚአስፈልገውን እርዳታ ደህና አድርገው እንዲረዱን ተስፋ አደርጋለሁ ። ይህን ተማሪ ቤት የሚወድ አንድ ቸር ወዳጃችን ትልቅ እርዳታ እረድቶናል እርዳታውም ሁለቱ መቶ ወቄት ወርቅ በመስጠቱ ነው ለዚህ ለታላቅ ለጋስነቱ ዛሬ በጉባኤ በጣም አመሰግነዋለሁ ።

ልዑል ግራንድ ዱዩክ ሆይ የእርስዎ ወደ አዲስ አበባ መምጣትና እኛን አክብረው ለመጐብኘትዎ ለሀገራችንና ለሕዝባችን ደስ የሚአሰኝ ወዳጅነትዎን ያሳያል ነገር ግን ይህ ነገር አዲስ አይደለም ። ማለት የታላቁ የመስኮብ ሕዝቦች ለኛ የዋላችሁልን እጅግ ደስ የሚአሰኝ የወዳጅነት ውለታችሁን ዛሬ ድረስ አረሳንም ውለታውም እጅግ በተቸገርንና በተጨነቅንበት ጊዜ ብዙ የሚጠቅምና የሚአስፈልግ እርዳታ ስለ ላካችሁልን ነው

የኢትዮጵያ ወታደሮች በአድዋ ጦርነት የቆሰሉና የታመሙትን በጣም እውቀትና ቸርነት ባላቸው በመስኮብ ሐኪሞች እየታከሙ ብዙ ሽ ወታደሮች ነፍሳቸው ድኑዋል የዚያን ጊዜ የመጡት ሐኪሞች በመስኮብ መንግሥት ኪሳራ አያሌ ዓመት ድረስ ሲያክሙና ሲያገለግሉ ኖሩ ታላቁ ብልሁ አጤ ምኒልክ ሕክምና ለሀገራችን ትልቅ ጥቅም መሆኑን አይተው በወዳጆቻችን በፈረንሳዊዎች እርዳታ አንድ ሆስፒታል ለራሳቸው ከፈቱ በዚህ በሆስፒታል ውሥጥ ፈረንሳይ ሐኪሞች አሁን ድረስ እጅግ የሚያስመሰግን የሕክምና ሥራ ይሠራሉ ። ደግሞ እላንተ ክቡራኖች መጥታችሁ ስለጐበኛችሁን እንደገና አመሰግናችኋለሁ በዚህ አሁን ልዑል አልጋ ወራሽ በብዙ ሀሳባቸውና ብልህነታቸው ያቆሙትን የትምህርት ቤት ስለአያችሁ ደስ ብሏችኋል ብዬ ተስፋአደርጋለሁ ።

እኛ ምንም በትምህርት ወደ ኋላ ብንሆን ማንም መንግሥት ወይም ህዝብ የዋሉልንን ውለታና የፍቅር ስራ የማንረሳ መሆናችንን አይጠረጠርም ።

የተፈሪ መኰንን ተማሪ ቤት ተማሪዎች ልዑል ግራንድ ዱዩክና ክቡራን ወይዛዝሮች መኳንንቶችም በቸርነታችሁ ዛሬ መጥታችሁ ስለጐበኛችኋቸው እጅግ ደስ ብሏቸው ስለ ክበሬታው ያመሰግናሉ ። ክቡራኖችም እነሱንና የተማሪ ቤቱን ዘወትር ታስባላችሁ ብለው ተስፋ ያደርጋሉ ሐምሌ ።

ኃኪም ወርቅነህ ።

በኢትዮጵያውያን ማኅበር ስለሚቆመው ተማሪ ቤት እርዳታ።

የኢትዮጵያን ልጆች ልቡና ለማነቃቃት ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ብርሃንና ሰላም የተባለ ጋዜታ አሳትመው ድንቅ የሆነ ተማሪ ቤት ሠርተው የዕውቀት የመልካም ሥራ ሁሉ አበጋዝ ፊታውራሪና ደጀን በመሆናቸው ሰውን ሁሉ ከስንፍና እንቅልፍ ስለቀሰቀሱት ረጅም ዕድሜ ታላቅ እድልና ጤና ሰጥቶ ያሰቡትን ሁሉ ወደፍጻሜ እንዲያደርስላቸው በሁሉ ነገር ከሀሊ የሆነ ቅዱስ አምላክን እናመሰግነዋለን ። ከሁን ቀደም ታላቁ ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ ምኒልክ የትምሕርትና የዕውቀት ዘር አብቅለውልን ሄዱ ። አይብዛ እንጂ ይኸውም ቢሆን በየጊዜው ጥቂት ጥቂት ፍሬ መስጠቱ አልቀረም ነገር ግን ምንም በሥጋ መዋቱ ቢሆኑ በመንፈስ ሕያው ናቸው ተጨንቀው ያስቡበት የነበረ ሥራ እየሰፋ ሄደ እንጂ አልቀረም

ስለዚህ የታላቁ ንጉሠ ነገሥት መልካሙ ሀሳባቸው አልሞተም ሀብታቸው ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ላይ አድሮ ለኢትዮጵያ ለዘላለም ጥቅምና ደስታ የሚሆን የበለጠ ታላላቅ ሥራ ያሠራል ሆነ ፤ ወደፊትም አሁን ከተጀመረውና ከየነውም የሚበልጥ ሥራ ለኢትዮጵያ ነፃነት ለዘላለም ጥቅም የሚሆን መታሰቢያ ግርማዊት ንግሥታችንና ልዑል አልጋ ወራሻችን እንደሁለት ዓይን በስምም ሁነው ስለ ሀገራቸው የሚያስቡት መልካም ሥራ ሁሉ እንዲከናወንላቸው ምሉ ተስፋ እናደርጋለን (ዓይን ሁለትነቱ ሳይቀር ለየብቻው አያይም ። ቀኝ ወደተመለከተበት ግራው፤ግራው ወደተመለከተበት ቀኝ ይህ የኔ ነው ይህ ያንተ ነው ሳይባባሉ ባንድነት አይተው ከእግዚአብሔር የታዘዙትን የሰውን መፍቅድ ፈጽመው ደስ ብሏቸው ደስ አሰኝተው ሥራቸውን በትክክል ሲፈጽሙ ይኖራሉ ። (ማኅቶቱ ለሥጋከ ዓይንከ ውእቱ) አሁንም እኛ የኢትዮጵያ ልጆች ለነዚህ ለሁለቱ ዓይኖቻችን ለሕይወታችን መብራቶች በፍጹም ልባችን በየተሰጠን ሀብትና ክፍል ልናገለግላቸውና በፍቅር ባንድነት እንደ ሁለት ዓይን ሆነን ያለዕረፍት ልንረዳቸው ይገባናል) ስለዚህም ወንድማችን ፊታውራሪ ዱፌሳ እንዳሳሰበን ሁሉ ወደፊት ለሚቆመው የትምሕርት ቤት እርዳታ ይህችን ታናሽ ስጦታ መግቢያ ፳ ብር ሰጥቻለሁ) ባመት ባመቱ ፲ አሥር ብር እንድሰጥ ፍጹም ደስታዬ ነው ። የዚህንም የታሰበውን የትምሕርት ተክል ልምላሜውንና አበባውን እንዲያዩ በፍሬውም ደስ ብሏቸው በመልካሙ ሀሳባቸው ለልጆቻቸው እያከፋፈሉ እንዲመግቡን ለግርምት ንግሥታችንና ለልዑል አልጋ ወራሻችን ታላቅ ጤና ረጅም ዕድሜ ጥበብና ማስተዋልን አብዝቶ እንዲጨምርላቸው ቸርና መሐሪውን አምላክ በፍጹም ልባችን እንለምንላቸው ።

አለቃ ደስታ ። (ሐረር)

ብርሃንና ሰላም የሚባል እስከስሙ ደስ የሚያሰኝ አገራችን እናታችን ለምለሟ አበባዋ ኢትዮጵያ የምትጠጣው የእውቀት ምንጭ በየሳምንቱ የሚፈልቅበት ቦታ ጌታችን አሳቢያችን ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን አስበው ስለ ሰሩልን በጣም ደስ ብሎኛል እጅግም አመሰግናቸዋለሁ ይልቁንም ደግ የሰራ እድሜው እንዲረዝም የታወቀ ስለሆነ በአሪት ጊዜ እስከ ፱፻፷፱ ዓመት ድረስ ተቀምጠው እንደነበሩት (አሪት ዘፍጥረት ምዕ ፭ ቊ ፳፯) እንደ ደጎቹ ሰዎች የጌታችንን የልዑል አልጋ ወራሽን እድሜ እ||ደነሱ እንዲያረዝምልን እግዚአብሔርን እለምናለሁ ። እኛም የኢትዮጵያ ልጆች ይኸንን ያፈለቁልንን የእውቀት ምንጭ ዘወትር እየጠጣን ከባልንጀሮቻችን ከአውሮፓ ልጆች ጋራ ትክክል እንድንሆን እመኛለሁ ደግሞ ይኸውም ብርሃንና ሰላም የሚባል የእውቀት ምንጭ አንድ ላይ ተጠራቅሞ የጠማው ሰው ሁሉ እንደፈቃዱ እየሄደ እንዲጠጣ ስለ ሚሰራው የትምርት ቤት እርዳታዬን ባመት ባመቱ አምስት ብር ልሰጥ ፈቃዴ ነው ። ለገሰ ቸሩ ።

በኢትዮጵያውያን ማኅበር ለሚቆመው ተማሪ ቤት በዓመት የሚሰጠውን ገንዘብ በብርሃንና ሰላም ሲጻፍ አይቶን ደስ ቢለን እኛም በዓመት ፲፭ ብር ለመርዳት ፈቃድ አለን ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ለኢትዮጵያ ዕውቀትንና ትምርትን ለመጨመር ተማሪ ቤት ማቆማቸው የውጭ አገር መንግሥቶች እንደ ሚሠሩት ልክ ሁኖ ብናየው እርሳቸውን እጅግ እናመሰግን ዘንድ ይገባናል ለምትበልጠው ዕውቀት ቅኑ ብሎ ጳውሎስ የተናገረውን ስለፈጸሙ ።

ዘርቦስ ኩፓኒያ ።

በኢትዮጵያውያን ማኅበር ለሚቆመው ተማሪ ቤት
እርዳታ እንሰጣለን ብለው ፊርማቸውን የሰጡ ሰዎች ።

ከ፴፫ ቊጥር የመጣ ድምር ፭የምስር ወርቅ፡፭ሽ፪፻፵፪ ብር ተ፱ሩብ

አለቃ ደስታ መግቢያ	፳	ብር
ባመት ባመት ።	፲	ብር
ለገሠ ቸሩ ።	፭	ብር
ዘርቦስ ኩባኒያ ።	፲፭	ብር
ኢያሱ ዳንኤል ።	፲	ብር

ድምር ፭ የምስር ወርቅ ፤ ፭ሽ፫፻፪ ብር ተ፱ ሩብ

በትምሕርት የማደጋችን ትርፍ በራሳቸው ለመገዛት የሚችሉ ፍጥረቶች ለማቆም ነው እንጂ ሌሎች እንዲገዟቸው አይደለም ። ሐርቤር እስፔንሴር ።

ማስታወቂያ ።

ለራሶችና ለደጃዝማቾች ለሴት ወይዘሮች የሚገባ በያይነቱ ጥሩ ካባ ከኤሮፓ መጥቶልኛል። ቤቱም ባንክ ኦፍ አቢሲንያ ከእንግሊዞች ባንክ አጠገብ ነውና ይህንን ካባ መግዛት ለሚፈልጉ ሰዎች መጥተው እንዲገዙ አስታውቃለሁ ። ኢያሱ ዳንኤል ።

በልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

መጀመሪያ ዓመት ፤ ቁጥር ፴፭ ።
1re ANNÉE № 35

ሐሙስ ነሐሴ ፳፩ ቀን ፲፱፻፲፯ ዓ ም።
JEUDI 27 AOUT 1925

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d'Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

የጋዜጣው ዲሬክተር ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።
Gabré Christo Taklé Haymanot
Diréсteur

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ፍርድ ።

አንድ ሰውዬ እንጨት ሊቆርጥ ወደ ዱር ሔዶ በዱሩ መካከል ሲዞር አንድ አውሬ ተጨንቆ ሲጮህ ሰማ ቀርቦ ቢመለከትም አውሬው ከጉድጓድ ውስጥ ገብቶ በላዩ ትልቅ ድንጋይ ወድቆ ጉድጓዱን ዘግቶበት አየ፤ሰውዬው ይህን በማየቱ አዝኖለት ደንጊያውን አነሣለት ። አውሬው ደግሞ ዘሎ ወጥቶ እውጥሃለሁ አለው ፤ ሰውዬውም ከሞት አድኜህ እንዴት ትውጠኛለህ ብሎ ለመነው ። አውሬውም ከራበኝ ብዙ ጊዜ ነውና የዚህ ሐሳብ የለኝም አለው ። የዚያን ጊዜ ሰውዬው ከሩቅ መንገድ ፈረስ እየተሳበ ሲመጣ አየና እባክህ ይኸ የሚመጣ ፈረስ እስኪደርስና እርሱ እስኪፈርድ አቈየኝ አለው ፤ እሺ አለ ። ፈረሱ ደረሰና ሰውዬው ነገሩን በነገረው ጊዜ ፈረሱ እንዲህ ብሎ መለሰ ምን ትፈልጋለህ ታዲያ ፤ እኔ እንኳ ስራሴ ይኸው ለጌታዬ ብዙ ዘመን አገልግዬ ስለ አረጀሁና ስለደከምሁ በጠበንጃ ሊገድለኝ ስቦኝ ይሄዳል ። ስለዚህ በዚህ ዓለም በጎ የሠራ ፍዳው ይህ ነው ብሎት አለፈ ። የዚያን ጊዜ አውሬው አሁንሳ ምን ትላለህ ልዋጥህ አለው።ሰውዬውም ውሻ ሲመጣ አየና ይህን ውሻ እስኪጠይቅ እንኳ አቈየኝ አለው ። አውሬውም ይሁን አለ ። ውሻውም ቢጠይቀው ተወኝ እባክህ በዚህ ዓለም ምንም ቢሆን በጎ የሠራ የሚቀበለው ብድራት ክፉ ነውና እኔ እንኳ ቀን ቀን ጌታዬን ወደ አደን ሲሄድ እየተከተልኩ በሌሊትም ቤት እየጠበቅሁ ስኖር አሁን ስላረጀሁና ዓይኔ ስለደከመ ሊገለኝ እንደምታየኝ እየተሳብሁ ወደ በረሃ እሔዳለሁ ብሎት አልፎት ሄደ ።

እንዲሁ አያሌ መንገድ አላፊዎች ሲጠይቅ ይኸኑ የመሰለ ይነግሩት ነበር አውሬውም አንዱ ንግግሩን በጨረሰ ልክ ልዋጥህ እያለ ይቃጣው ነበር፤በመጨረሻ ቀበሮ ስትመጣ አየና ይች ቀበሮ እስክትናገር እባክህ አቈየኝ አለውና ፈቀደለት፤ቀበሮዪቱ በደረሰች ጊዜ ሰውዬው ነገሩን ሁሉ ነገራት ቀበሮዪቱም ወደ ሰውዬው ጠጋ አለችና ባድንህ ምን ትሰጠኛለህ? አለችው ሰውዬውም በሳምንት አንድ ቀን በኔ ግቢ እየገባሽ እንደ ፈቀድሽ ዶሮ ብይ አላት ። ከዚያ በኋላ ቀበሮዪቱ ወደ አውሬው ቀረበችና እንዴት ነው ነገሩ? የት ነው የነበርኸው? እንዴትስ ሁነህ ነበር? አለችው፤አውሬው ደግሞ የነበረበትንና አሁኑን አሳያለሁ ብሎ በነበረበት ጉድጓድ ቍጭ አለና እንዲህ ሁኜ ነበርኹ አለ ። የዚያን ጊዜ ጐበዚቱ በላዩ የነበረውን ድንጋይ መልሳ ገጠመችበትና «አንተ ለዚህ በጎ ሳደረገልህ ከሞትም ላዳነህ የማትራራ ክፉ አውሬ ከዚያው ከነበርክበት በቃ ለዘለዓለም ተዘጋ» ብላው መንገዷን ሔደች ሰውዬውም በደሕና ወደ ሥራው ሔደ ይባላል ።

በጎ ሥራ ለሚሠሩልን በበጎ ሥራ ፈንታ ክፉ ልንመልስ ብንጣጣር ባላሰብነው ለዘለዓለም ዘግቶ የሚያስቀር ቅጣት ይፈረድብናል ክፉውን እንኳ በበጎ ማቸነፍ ነው የታዘዝነው በጎ ያደረጉልንን ሁሉ ማመሥገን ክፉ ስለ ሚሠሩም ከክፋታቸው እንዲመለሱ መጸለይ ይገባናል ።

ስለ አረቄ ።

በአዲስ አበባ አያሌ ትልልቆች ሰዎች ድግሥና ግብር ባደረጉ ጊዜ አረቄ መጠጣትና ማጠጣት እንደቀረ በመስማታችን እጅግ ደስ ብሎናል ። ከኢትዮጵያ መኳንንት ያረቄን ጉዳት ተረድተውት አረቄ መጠጣትን ከብዙ ጊዜ ጀምረው የተዉት ብዙ ናቸው ። አሁን ግን አስተዋይ የሆነ ሁሉ አረቄ ጉዳት እንጂ ጥቅም እንደሌለው ተረድቶት ጠልቶታል ። አረቄ ታልጠፋ ምንም ሕይወት የለን እያሉ የሚናደዱም ብዙ ናቸው ።

ከዚህ በፊት በብርሃንና ሰላም ፱ ቍጥር ስለ አረቄና እሱን የመሰለ መጠጥ መጠጣት የሚገኘውን ጉዳት አመልክተናል ። ክቡር አቶ ገብረ እግዚአብሔርም በብርሃንና ሰላም ፲፰

ቊጥር በአረቄ ምክንያት የሚገኘውን ኪሳራና ጉዳት በሚያስረዳ ቃል ጽፈዋል ። እንዲህ የመሰለውን የሚያስጠነቅቅ ምክር ሕዝባችን በቶሎ ስለሚቀበል ሕዝባችን ክፉውና በጎውን ለመለየት እስኪችል ድረስ ዓይኑ ሊበራ እንደ ጀመረ የሚያስረዳ ነገር ነው።

በኤታት ኡኒ አሜሪካ ያረቄ ዓይነት መጠጥ ጨርሶ እንዳይገባ እንደተከለከለ ባገራችንም ያለው አረቄ እንዲጠፋ ሌላውም እንዳይገባ ጨርሶ ቢከለከል ሕዝባችን ጤናውን ከማበላሸትና የአእምሮውን ብርታት ከማጉደል በዳን ፡ ይህነን ሹሞቻችንና ሕዝባችን ላገራችን ከዋና ጉዳዮቹ አንዱ አረቄ መሆኑን አውቀውት በጣም ተቀይመውታል በቶሎ እንዲበቀሉትም ተስፋ እናደርጋለን ።

ባረቄ ትርፍ የሚያገኙ ነጋዶችም ብዙ ሰው ጉድቶ ብዙ የገንዘብ ትርፍ ከማግኘት ሰው ድኖ የሚበቃቸውን ትርፍ በሌላ ሥራ ማግኘት እንዲያስቡ እንጂ አረቄ ቀረ ሰው ከጉዳት ዳነ ብለው እንዳይቀየሙ ተስፋ እናደርጋለን ።

ስለ ትምርት ።

ይድረስ ጀግኖች ወደሆናችሁ ወንድሞቼ ጥበብንም በፍጥነት ወደምትቀበሉ የኢትዮጵያ ልጆች እንኳን ኢየሱስ ክርስቶስ በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ዘኢትዮጵያ ሀብት በልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ትጋት ወደጥበብ ሥልጣኔ መንቀሳቀስ ዘመን ያደረሳችሁ ። ደግሞ ፍጽምት ወደምትሆን ሥልጣኔ ዘመን የነገሩትን የማይረሳ የለመኑትን የማይነሣ ሰማያዊ አባታችን ክርስቶስ በብርሃን መርቶ በሰላም አቆይቶ እንዲያደርሰን ተስፋ አለን የቀድሞ ወሬ በቀድሞ ዘመን በኢትዮጵያ የንድግና የሒሳብ ሥራ የሚያውቁ ብዙዎች አልነበሩም ይባላል። እንደዛሬ የንግድና የሒሳብ ሥራ አልሰፋም ነበርና ቊጥር ከለማወቃቸው የተነሣ ስለገቢውም ስለወጭው ገንዘብ ቢሆን እንጨት እየከረከሩ ገመድ እየቋጠሩ በምልክትና በመላ እየሠሩ ይኖሩ ነበር ዛሬ ግን የሒሳብ ሥራ ማብዛት ማጉደል ማካፈል መደመር ይህን የመሰለ የሒሳብ ረገድ ሥራ ሁሉ የኢትዮጵያ ልጆች የእውቀት ሥልጣኔን በመመርመራቸው ግብጦ መጣል ባቄላ መቍጠር ሳያስፈልጋቸው በቃልም ቢሆን በጽሕፈት አስበው በፍጥነት ይሠሩታል ። ይኸውም የሒሳብ ሥራ ለጊዜው እንደሚያስፈልግ በጥንቃቄ መሠረቱ ዳግማዊ ምኒልክ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት እንደ ቀዳማዊ አባታቸው እንደ ሰሎሞን ጥበብን ይፈልጉ ነበርና ላገራቸው ልጆች ጥቅም እንዲሆን ብለው የሒሳብና የቋንቋ ትምህርት ቤት ስላቆሙልን በዕውቀትና በትምህርት በመመርመር ነው እንጂ እንዲያው በልብ ወለድ ሀሳብ ሥራ ገመድ ቋጥሮ እንጨት ከርክሮ ሳይማርና ሳይመራመር እንደ ቀድሞ ዘመን በምልክት ለመሥራት አይሆንለትም ሰነፎች ግን ለልጆቻቸው ዕውቀት መሰናከያ ሁነው የቋንቋ ትምህርት ማወቅ ሃይማኖት መለወጥ ነው እያሉ ሊናገሩ ሞኝ ሲናገር ብልህ አድምጥ እንደሚባል ይህንን የስህተት ወሬ ሲያወሩ እንሰማለን ልጆቻቸውም ቃላቸውን ሰምተው ከሥራ ተከልክለው ከዕውቀት ሥልጣኔምርምር ርቀው ለሃገር ጥቅም ከሚሆን ሀሳብ ተለይተው ያባት ዕዳ ለልጅ ያፍንጫ ዕድፍ ለእጅ ይሆናልና ድቁርናን የዕውቀት ትምህርት አድርገው በሌብነት በመቀማት ይኖራሉ በኋላ ወደሞት ወጥመድ ይገባሉ ማለት ሥራ ፈት የሆነ ሰው ያባቱንና የናቱን ገንዘብ ከጨረሰ በኋላ ዕውቀት ከማጣቱ የተነሣ ሥራ አይሠጠውምና ደም ወደማፍሰስ ቤት ወደማቃጠል ማዕርግ ደርሶ እንዲሞት ያለጥርጥር እርግጥ ነው ። ይህነንም ማስታወቄ ለሀገር ጥቅም የሚሆነውን ጥበብና ልዩ ልዩ የሆነን ቋንቋ ከማወቅ ከአታላዮችና ከሰነፎች በሰማው ነገር የኢትዮጵያ ልጅ ጥበብን ከመከተል እንዳይሰንፍ ነው እንጂ እኔስ ከተወለድኩባት ከማርኛ ቋንቋ በቀር ሌላ የማውቀው ቋንቋ የለም ፤ ኢትዮጵያዊ ሆይ አታላዮችንና ሰነፎችን አትከተል እግረ ሕሊናህ በድንቁርና እንቅፋት እንዳይሰናከል ቋንቋ መማርና ማወቅ ያንዱን ሀገር ቋንቋ አንዱ የማያውቀው ስለሆነ ለመነጋገር ባስፈለገው ጊዜ አስተርጓሚ እንዳያሻውና ሀሳቡን ለመፈጸም እንዳይቸገር ነው እንጂ ሃይማኖት የሚነካ አገር የሚጐዳ አንዳች የለበትም አንድ ምሳሌ በዓይን የታየና የተደረገ በቀድሞ ዘመን በመንዝ አገር በየጁ አገር የሚኖሩ ሰዎች መንግሥት ሳያዝዛቸው የውጭ አገር ጠላት ሳይመጣባቸው እርስ በራሳቸው ይዋጉ ነበሩ ደማቸው እንደ ክረምት ዝናም ጐርፍ እስኪወርድ ድረስ ። ዳግማዊ ምኒልክ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ይህ የሕዝብ ማለቅ በከንቱ እንደሆነ አስበው በነጋሪት አዋጅ አድርገው በቀሳውስት አስገዝተው ውጊቱን ቢከለክሏቸው የዚያ አገር ሰዎች የቀድሞ ልማዳችን መዋጋትና ደም ማፍሰስ ካልሆነ የተዘራው እህል አይሰምርም የተወለደው ጥጃ አያድግም እያሉ ሲያወሩ እንሰማ ነበር፤ ይህነንም የቀድሞ ታሪክ ከብዙ በጥቂቱ ለማስረዳት ያህል የተጻፈው የመንዝና የየጁ ሰዎች እርስ በርሳቸው በለመዋጋታቸውና ደማቸውን ባለማፍሰሳቸው ለሀገራቸው ጉዳት የሆነ መስሏቸው ሊያሲዙ እንደነበሩ ዛሬም ለሀገራችን ጥቅም የሚሆነውን ነገር እንግዳውን ጥበብና የቋንቋ ትምህርት ከንቱ ስም የሚያወጡለት አሉና፤ ለኢትዮጵያና ለልጆቻቸው ጥቅም መሆኑን እንዲረዱት ብለን ነው ፤ ዘበ ዕዝን ሰሚዓ ለይስማዕ ።

ያባታችን አጋፋሪ በቀለ አበዬ ።

ምክር ፤

ብርሃንና ሰላም ጋዜታ ከወጣ የብልሆች ሥራና የዕውቀት ነገራቸው ለብዙ ሰው ጥልቅ የሚሆን ምክርና ዕውቀትን ገለጠ

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ለሕዝባቸው የብርሃንና የሰላም የጥበብ መሪ ለመሆን የመንፈሳዊ ሥራ እየሠሩ ያስረዳሉ ። ሥራቸውም ቤተ ክርስቲያን ማሠራት መጻሕፍትን ማሳተም የትምሕርት ቤትና የመታከሚያ ቤት ማቆም ድልድይ ማሠራት ብዙ ገንዘብም እያወጡ በየገዳሙ ለደከሙ ለተቸገሩም ድኆች ይሰጣሉ ። ባንድ ብልህ ሰው አገር ትፀናለች በክፉዎችም ብዛት አገር ትጠፋለች ይላል ሲራክ ምዕራፍ ፲፮ ቁጥር ፬

ልዑል ጌታችን አገራችንና ሕዝባችን በብርሃንና ሰላም እንዲኖር በፍቅርና በትዕግሥት የመንፈሳዊ ሥራ እየሠሩ

እንደሚኖሩ ሁሉ ። እኛም ሕዝባቸውና አሽከሮቻቸው ሁሉ በፍቅርና በትሕትና መንፈሳዊ ሥራ እየሠራን በሥራችን ሁሉ በውነት ብንረዳቸው እግዚአብሔርም ደስ ይለዋል የምንኖርበትን ዓመታትና ጊዜያችንን በሕይወትና ሰላም ያስፈጽመናል ።

በማየ አይኅ የዚህን ዓለም ፍጥረት ካጠፋ በኋላ ሁለተኛ በማየ አይኅ እንዳይጠፋ ለኖኅ ቃል ኪዳን ሰጠው ከዚያ ወዲህ የሰው ኃጢአት በምድር ላይ በበዛ ጊዜ ለዓለም ፍጥረት መቅጫ ከዛዘው ከ፫ት አይነት መቅሠፍት ከረኃብ ከጦርነት ከመቅሠፍት በሽታ ከዚህ ሁሉ እግዚአብሔር አገራችንን ይጠብቃት ነበር ። እስ በራሳችን ባለመፋቀራችን እግዚአብሔርንም በሙሉ ልባችንና አሳባችን ባለመውደድና ባለመፍራታችን ሁልጊዜ በጦርነት በበሽታ በረኃብ ሲገሥፀን ይኖራል ። ሰውም ከክፉ ሥራው አይመለስም ።

ሰውም ሁሉ ከክፉ ሥራው እንዲመለስ ። ወደኔ ተመለሱ እኔም ወደናንተ እመለሳለሁ ይላል እግዚአብሔር የሠራዊት ጌታ ዘከርያስ ም፩ ቊ፫ ።

የኃጢአተኛን ሞት አልሻም ኃጢአተኛ ከኃጢአቱ እንዲመለስ እንዲድንም እንጂ ተመለሱ ከክፉ ሥራችሁ ንስሐ ግቡታችሁ ተመለሱ ከክፉ መንገዳችሁ ስለምን በኃጢአታችሁ ሳላችሁ ትሞታላችሁ እናንተ የእስራኤል ወገኖች ። ሕዝቅ ፴፫ ፲፩

አእምሮ የሌላቸው እንስሳ ። አህያ ጅብን ፍየል ነብርን ዶሮ መጠማጥን አይከተሉም ጠላታቸውን ያውቃሉና ሰው ሁሉ ምነው ሰይጣንን ይከተላል ክፉ ሥራን መሥራት ሰይጣንን መከተል እንደሆነ እያወቀው ። እግዚአብሔርን የምትወዱ ክፉ ሥራ መሥራትን ጥሉ ። ክፉ ሥራን የሚሠራ ነፍሱን የጠላ ነው

ይህም ክፉ ሥራ ሁሉ በሰው ላይ የሰለጠነ በየሀገሩ የተማሪ ቤት ባለመቆሙ መጻሕፍትና መምሕራን በማነሳቸው ነው አሁን ግን በየሀገሩ የተማሪ ቤት ለማቆም መጻሕፍትንም እያሳተሙ ለማብዛት መምሕራንም እንዲበዙ አስተማሪ በየጋላው አገር ልከው አረመኔዎችን ሁሉ ወደ አምልኮተ እግዚአብሔር ለመመለስ ጅምራቸውና አሳባቸው ሁሉ ለዚህ ነውና እግዚአብሔር ዕድሜ እንዲሰጣቸው በሙሉ አሳባችን እግዚአብሔርን እንለምናለን ። መሳፍንቱና መኳንንቱም በየሀገራቸው ቢረዱ መልካም ነው ።

ቤተ ክርስቲያን የተማሪ ቤትም እየቆሙ ልጆቻቸውን ቢያስተምሩ ጥቂት በጥቂት ሲል ከብዙ ዘመን በኋላ ብዙ ሕዝብ ከአምልኮ ጣዖት ወደ አምልኮተ እግዚአብሔር ይመለስ ነበር ።

አሁን አረመኔዎች በየዳር አገሩ ብዙ አሉና በመሾም በመሸለም በገንዘብ መስጠት በማስተማር በምክርና በውቀት ተረዳድተን ወደ ክርስትና ብንመልሳቸው እግዚአብሔር ደስ ይለዋል ። መቶ በግ ያለው ከመቶ አንዱ ቢጠፋ ዘጠና ዘጠኙን ትቶ ያን የጠፋበትን ይፈልግ ይሄዳል ባገኘውም ጊዜ በብዙ ደስ ይለዋል ጐረቤቶችንና ወዳጆቹን ጠርቶ የጠፋውን በግ አገኘሁ ደስ ብሎኛል ደስ ይበላችሁ ይላል ማቴ ፲፰ ፲፪ ከሚቆጠሩ አረመኔ አንዱ ቢጠመቅ ወደ እግዚአብሔር ቢመለስ ደስ ይለዋል ፊታውራሪ ዴሬሳ መክረው ገንዘብ አዋጥቶ የተማሪ ቤት ለማቆም ስለ ጀመሩ ደስ ብሎኝ እኔም የተቻለኝን ፳ ብር እንድረዳ ፈቃዴ ነው

ዕውቀትን ለመግለጥ ገንዘብ የሰጣችሁ ።
አገርን ለመርዳት የተፋጠናችሁ ።
ብርሃንና ሰላም ሕይወት ይድረሳችሁ ።

ገብረ ጻድቅ ።

ምሳሌ ።

አንድ ሰው ምሉ ሳለ የሚያገባ ጐደሎ ሳለ ግን የማያገባ እወቅልኝ ብሎ ጠየቀኝ ። እኔ ደግሞ የጠየቀኝን ጥያቄ በተቻለኝ ምላሽ ሰጠሁት ። ሌላም ሰው ደግሞ የተሻለ ምላሽ ጽፎ ቢያስታውቅ ደስ ይለኛል። ምላሹም እንዲህ ነው ያምሉ ሳለ የሚያገባ ልበኛና እውቀተኛ ሳለ ጥበቤ ይበቃኛል ብሎ የሰውን ጥበብ የማይንቅ ነው። ጐደሎ ሳለ የማያገባ ግን ጥበብ የሌለው ሰው ጥበብ ያለው ይመስለውና የሌላውን ጥበብ ለመመርመር አይሆንለትም እለ እሱ እውቀት ሌላ እውቀት ያለ አይመስለውም ስለዚህ ሁለጊዜ በጐደሎው ይኖራል ብየ መለስሁለት። እኛም ደግሞ የኛ እውቀት የሚበቃን መስሎን እንዳንታለል ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን በብሩህ ልባቸው አስበው ብርሃንና ሰላም ብለው በሰየሙት ጋዜጣቸው የሚገኘውን ምክር አለዕረፍት እንመርምር እግዚአብሔር አሳቡን ለእስራኤል በነቢያት ይገልጽላቸው ነበር ለኛም ከልባችን ልብ ለመጨመር ከማስተዋላችንም ማስተዋል ለመጨመር አቶ እውቀት ኃሳቡን በብርሃንና ሰላም አድርጎ ይገልጽልናል። ይህነን ልዑል አልጋ ወራሻችን ብርሃንና ሰላም ብለው ያደረጉት የእውቀት ምንጭ የሆነ ጋዜጣ በመትጋትና በማስተዋል ናፍቆትም ባለው ልብ ብናነበው ከርሱ ብዙ ጥቅም ያለበት ምክር እንማራለን ፤ ለዚህ ወሰን የሌለው ቸርነት ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ የሚያደርጉት በጐነታቸው እንደኔ አሳብ ለኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን የሚበቃ ምሥጋና ያለ አይመስለኝም ። ነገር ግን ኢትዮጵያም እጅዋን ወደ እግዚአብሔር ዘርግታ ትደግፋቸው። እኛም የኢትዮጵያ ልጆች ከትልቅ እስከ ትንሽ በምሉ ልባችን እድሜያቸውን እንደማቱሳላ አድርጎ የልባቸውን ኃሳብ ሁሉ ያስፈጽማቸው ብለን አለእረፍት ሁለጊዜ እንለምን ፤ እኛም በርስዎ እውቀት ተመርተን ላገራችን ጥቅም እንድንሆን ተስፋ እናደርጋለን።

ብርሃነ መስቀል

ስለ ስጦታ ።

የሕዝብ ተማሪ ቤት ለማቆም ስለታሰበ የትምሕርትን ነገር የወደደ ሰው ሁሉ ለተማሪ ቤቱ እርዳታ ይህነን ያህል ገንዘብ እሰጣለሁ እያለ ያስታውቃል ብሎ ብርሃንና ሰላም ጋዜታ ያነበበ ሰው ወሬ ነገረኝ ፤ በማርቆስ ወንጌል ም ፲፪ ቍ ፵፩ እስከ ፵፬ የሱስም በመዝገብ ማዕኑ አጠገብ ፊትለፊት ተቀመጠ ሰዎች ምጽዋት በማዕኑ እንዴት እንደ ጣሉም ያይ ነበረ ። እጅግም ባለጠጎች እጅግ ነበር ድኃ ሴትም ባልቴት መጣች ፪ ጅጅድም ጣለች ድረም የሚያህሉ ፤ ደቀ መዛሙርቱንም ጸራቸው አላቸው እውነት እላችኋለሁ ይህቺ ድኃ ባልቴት አብዝታ እንደጣለች በማዕን ከጣሉት ሁሉ ። ከከብታቸው የተረፈውን ጥለዋልና ይህቺ ግን

ከድኅነትዋ ያላትን ሁሉ ራቷን ሁሉ ጣለች እንዳለ እኔም ያቅሜን ያህል አምስት ብር እረዳለሁ ፤ ይህም ለሕዝብ ተማሪ ቤት እንዲቆም መታሰቡ እጅግ መልካም ነው ፤ ነገር ግን እንደሰማሁት ለርዳታ የተጻፈው ገንዘብ እስካሁን ስድስት ሺ ብር እንኳ አልሞላም አሉ እንዲህም መሆኑ (ሚሊዮም) ባለ ሺዎች (ባለ ሳንቲን) ባለመቶዎች ጣል ጣል ካላደረጉበት ባለ (ዲዚን ባለ አስሮች ያወጣነው የማይጠራቀም ስለሆነ ነው ። ትምርትን በጣም የምንወደው ድኆች ነን ። ካሁን ፊት ሃብታምና ገንዘብ ያለው ሰውማ እኔ እግዜር የሰጠኝ ሞልቶኛል ለልጆቼም ርስቴ ይበቃቸዋል ለሌላ ሰው ትምርትና ማግኘት እኔን ማን አሳቢ አደረገኝ ይል ይመስለኛል ። ለዚሁም ምሳሌ ጥንት እንደተረተ ሆኖ የሚነገር አንድ ቃል እሰማ ነበር ። ቃሉም እንዲህ ነው አንድ ጥቂት ጌትነት ያለው ሰው ከዕለታት አንድ ቀን ምሳውን በልቶ ጠጅ ጠጥቶ ጥሙን ተረክና ሰውነቱን ደስ ቢለው ጠጅ ያገኘሽ አይጣሽ ያጣሽ አያግኝሽ አለ ይባላል ። ይህም ንግግር የምቀኝነት መሆኑ የታወቀ ነው ፤ ስለዚህ እግዚአብሔር ምቀኝነትን አጥፍቶ እውቀትን ፈሪሃ እግዚአብሔርን ፍቅርን ያስፋልን ሃብታሞችንም ለድኃ እንዲራሩ ያድርግልን ብዬ እመኛለሁ ደሃን የሚያስጨንቅ ፈጣሪውን ይሰድባል ፤ ለድኃ ቸርነት የሚያደርግ ግን ያከብረዋል እንዳለ ምሳሌ ። ም ፲፬ ቍ ፴፩

፪ኛ ፤ ለድኃ ቸርነት የሚያደርግ ለእግዚአብሔር ያበድራል በጎነቱንም ይከፍለዋል ። ምሳሌ ም ፲፱ ቍ ፲፯

ይኸም ሁሉ የሚገኘው በትምሕርት ነውና ለትምሕርት ገንዘብ ያለው በገንዘቡ እውቀት ያለው በምክሩና ባገልግሎት የሚረዳውን ሰው ክርስቶስ በሥጋውም በነፍሱም ዋጋውን አያስቀርበት ። ደግሞ ቸሩ አምላክ ፈቃዱ ሁኖ ይህ የታሰበው የትምሕርት ቤት ሲከፈት ወይም ትምሕርት ሲጀመር የትምሕርቱን አኳሆን ምኞቴን ቀጥሎ ያለውን ቃል ማስታወሻ እጽፋለሁ መጀመሯ ስለ ቤተ ክህነት የካህን ልጅ ወይም የካህን ወገን የሆነ ሁሉ ለቤተ ክርስቲያን ሥራ እንደ ቀድሞው በግዕዝ መጽሐፍ ይማር ። ሌላው ሕዝብ ግን ባማሪኛ በታተመ መጽሐፍ ቢማር ትምሕርቱ በቶሎ ይገባውና ባማርኛ የታተሙትን መጻሕፍት ቅዱሳትን ለማንበብ ይደርስና ትዕግሥት አግኝቶ ከክፉ ነገር ሁሉ ርቆ ለነፍሱና ለሥጋው የሚጠቅም ቃል ያገኝበታል ሁለተኛ የታሪክ መጽሐፍና ጋዜታ ያነበበ እንደሆነ አገር መውደድና ለመንግሥት ማገልገል ይችላል ። ፫ተኛ ወደ ብልሃት ተማሪ ቤት ገብቶ ይማራል ለራሱ እንጀራ መብያና ለመንግሥት መርጃ የሚሆን ታላቅ እውቀት ያገኛል ሰው ሁሉ በግዕዝ መጽሐፍ የሚማር የሆነ እንደሆነ ግን በቶሎ የንባብና የጽሕፈት ትምሕርት አይገባውም ለዚሁም ላማርኛ መማሪያ መጀመሯ የሚሆን ፊደል ያለበት አቶ በቀለ ሀብተ ሚካኤል የጻፈው ትንሽ መጽሐፍ ታትሟል ባዲስ አበባም በሌላውም አገር በየከተማው ሁሉ እየላኩ ቢያስተምሩበት መልካም ይመስለኛል ። ይህነን ሁሉ ለማድረግ መልካም አሳብና ምኞት ሁሉ ለማስፈጸም የእግዚአብሔር የተቀደሰ ፈቃዱ ይሁንልን ለግርማዊት ንግሥታችንና ለልዑል አልጋ ወራሻችን እረጅም ዘመን ይስጥልን ቅድስት አገራችንን ኢትዮጵያን ከነሕዝቧ ይጠብቅልን አሜን ።

ወልደ ጻድቅ ወልደ ማርያም

ልዑል ግራንድ ዱክ አሌክሳንድር ዲሩስ አገራችን ኢትዮጵያን አይተው በአዲስ አበባ ሰንብተው በነሐሴ ፳ ቀን ወደ ኤውሮጳ ለመሔድ ተነሡ ልዑል ግራንድ ዱክን ለመሸኘት ደግሞ ልዑል የኢ. መ አ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ካያሌ መኳንንቶቻቸው ጋራ እስከ ባቡር ማረፊያ ድረስ ወርደው ነበር

በኢትዮጵያውያን ማኅበር ለሚቆመው ተማሪ ቤት እርዳታ እንሰጣለን ብለው ፊርማቸውን የሰጡ ሰዎች ።

ከ፴፬ ቍጥር የመጣ ድምር ፩ የምስር ወርቅ፡፩ሺ፫፻፱ ብር ተ፱ ሩብ

ታፈሰ ገዛኸኝ።	፲	ብር
አቶ ገብረ ጻድቅ ።	፩	ብር

ድምር ፩ የምስር ወርቅ ፤ ፩ሺ፫፻፲፩ ብር ተ፱ ሩብ

የፈላስፎች ቃል።

ለኛ ደግ ላልሆኑትም እንኳ ቢሆን እኛ ደግ እንሁናቸው ። ካስፓሬ

መጀመሪያ ራሳችን ደግ ከሆንን ቀጥሎ ደስ ይለናል ድልን ሳናገኝ አስቀድመን ዋጋችንን አንበል ፤ ሥራም ሳንሠራ አስቀድመን ደመወዝ አንጠይቅ ። ዠሩሶ

ከሰውነቱ የሚማሩት ነገር የማይገኝበት ሰው በዘመኔ ሁሉ አላገኘሁም ። አ ዶ ቢኔ

በዚህ ምድር ላይ በድንቅ የሚታይ መልካም ነገር ግልፍተኛነትን ከሚችል ፍቅርና ከሌላ ሰው ዘንድ የጐደለውን ደግነት ከሚሸፍን ደግነት በቀር ሌላ ነገር የለም። ሮቦርስቶን

እኛ ለሰው ለመታዘዝ ደስ የማይለን ከሆንን ሌላም ሰው ለኛ አልታዘዝም ብሎ እልህ ሲይዘው ደስ ይለን እንደሆን እስቲ እናስብ ። ሴኔክ

እጅግ የበዛ የመገሥት ኃይል ያደረበት አሳብ አለ ይኸውም እንደ እቶን እሳት ያበራል ወደ ዕውቀት ለማያት ይወስዳችኋል ብርሃን ያለበትን ዘለዓለምነት ይከፍትላችኋል ንግግር እንኳ አንድ አንድ ጊዜ አርበኛ ነው የተቀበሩ ነፍሳትን የሚያስነሳ ኃይል አለው ። ኤድጋር ኪኒት

ከጥቂቶቹ በቀር ሁሉም የማይታዩትን ጠላቶች የልብ ገርነት ያሸንፋቸዋል ። ለባታር

ታላላቅ ብርሃናት መውጫቸው ከደግነት ነው ።

ሀንሪ ፒሬዶብ።

ከጣሊያን መንግሥት ሊጋሲዮን የመጣ የቴሌግራም ቃል ።

የነሐሴ ፲፰ ቀን የለት ወሬ

ፓሪ። አንድ የፈረንሳዊ ወኪልና አንድ የእስጳኒያ ወኪል ካያሌ ሳምንት ጀምሮ በማሊላ ታንጀሬ ሰንብተዋል በዚህ የሰነበቱበትም አብደልክሪም ከላካቸው መልክተኞች ለመገናኘት ኑርዋል፤ግን እነሱ ሳይመጡ ስለቀሩ የሁለቱ መንግሥት ሰዎች በየስፍራቸው እንዲመለሱ ትእዛዝ ተቀበሉ ።

ስቶክልም። የስዌድ መንግሥት ስለ ኢንቴርናሲዮናል የአየር መርከብ ምክር ለማድረግ አስራ አምስት መንግሥታት ጠርቷል ምክሩም ለሴብታምብር (መስከረም) ፳፰ ቀን ነው

ሬባ። (ማሮክ) የመጨረሻው ወሬ ፈረንሳዊ በተዞል አውራጃ ድል እንዳደረገ ያስረግጣል ።

በልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

መጀመሪያ ዓመት ፡ ቁጥር ፴፮ ።
1re ANNÉE № 36

ሐሙስ ነሐሴ ፳፰ ቀን ፲፱፻፲፯ ዓ ም።
JEUDI 3 SePtembre 1925

ብርሃንና ሰላም

LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d'Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraissant tous les jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

የጋዜጣው ዲሬክተር ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።
Gabré Christo Taklé Haymanot
Diré́cteur

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie
Un an 5 Thalers
Etranger
Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres



የክቡር ደጃዝማች ማሞ ሞት ።

የክቡር አቶ በዛብህ ልጅ የልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን አጐት ፡ ክቡር ደጃዝማች ማሞ በነሐሴ ፱ ቀን ገሙ ከሚባል አገር ከሚያልፈው ዓለም ወደማያልፈው ዓለም እንዳለፉ በስልክ ተሰምቶ የመቤታችን በዓል ስለ ሆነ ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን አልተረዱም ነበረና ሰኞ በነሐሴ ፳፭ በምቢልታ በመለከት በሚገባ ማዕርግ ተረዱ ። ክቡር ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስም ወዳጃቸው ነበሩና እያለቀሱ ገቡ ።

ከሸዋ ያለ ታላላቅ ወይዛዝርና መኳንንት በልዑል አልጋ ወራሽ ግቢ መጥቶ ታላቅ ኀዘን ሆኖ ዋለ ፤ በዚሁም ቀን እንደ ወትሮው ልማድ አታሞ ሊመታ ነው ፤ አልቃሽ ሊቆም ነው እያልን ስንጠባበቅ ከቶ እንደዚህ ያለው ልማድ አልተደረገም

፲ ሰዓት ሲሆን ለኀዘንተኛውም ግብር ተደርጎ በፀጥታ ተበልቶ ካለቀ በኋላ የማዕድ መጨረሻ ጸሎት በሚደረግበት ጊዜ መምሕርነት ከምንኩስና ባንድነት የያዙ ታላቁ መምሕር ደስታ ከዚህ የሚከተለውን ቃል ተናገሩ ።

እግዚአብሔር የኀዘን ዳርቻ ያድርገው ። ከዚህም ቀጥዬ የማመለክታችሁ የበጎ መምሕር የሆኑትን የልዑል አልጋ ወራሽን አሳብ እንድትከተሏቸው እለምናችኋለሁ ።

ለመለቀስም የሚገባቸው ታላቁ አጎታቸው ደጃዝማች ማሞ ሲሆኑ እንደ ሀገሩ ልማድ ለማስለቀስ የሚገባቸውን ልዑል አልጋ ወራሽ ሆነው የበጎ አብነት ለመሆን አታሞ ከመመታት አልቃሽ ከማቆም ከልክለው በመጽሐፉ እንደታዘዘው በሚገባ እንደ ፍቅሩ መጠን ሲለቀስ ዋለ ይህ ለሟቹስ ለቋሚውስ ምን ጎደለበት ። ትእዛዝ በማክበሩ ክብሩ የመላ ይሆናል እንጂ ።

አሁንም ይህን ጉዳና ሁላችሁም እንድትከተሉት እለምናችኋለሁ ብለው አቡነ ዘበሰማያት ሰጥተው ጨረሱ ።

አሁንም ወንድሞቻችን ሆይ ይህችን ቃል ስለ ሰው ሳይሆን ስለ እግዚአብሔር ብላችሁ ልትፈጽሙት የልዑል አልጋ ወራሽ መምህርነት የእግዚአብሔር በረከት ያድርባችኋል ብሎ ብርሃንና ሰላም ይለምናችኋል ። ለልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ለክቡር ራስ ናደው ለክብርት ወይዘሮ ማሚት ከነልጆቻቸው ለልጅ ግርማ ማሞ ለወይዘሮ ወለተ ኪዳን እግዚአብሔር ያጥናችሁ የኀዘን ዳርቻ ያርግላችሁ ብሎ ብርሃንና ሰላም ምኞቱን ያቀርባል ።

ማመልከቻ ።

በነሐሴ ፳ቀን ፲፱፻፲፯ ዓመተ ምሕረት በልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ትጋት በምስጢር ሰላዮች ዕውቀትና ብርታት ። ከትልቅ ተወልደው በአእምሮ ያነሱ የወይዘሮ ፀሐየወርቅ ዳርጌና የተከታዮቻቸው የረቂቅ ተንኰል ምስጢራቸው ተገለጠ ። ይኸኑም ፍርዱ በሚፈጸምበት ጊዜ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ልንጽፍላችሁ ተስፋ እናደርጋለን ።

ስለ አዲስ አበባ ከተማ ዘበኞች የሥልጣኔ ሥራ አቋቋም ።

በከተማ ካሁን ቀደም የነበረው የከተማው ዘበኛ ጥቂት ስለነበረ አሁን ወደፊት ከተማው በመላው እንዲጠበቅ ተብሎ ለጊዜው የሚረዱ ዘበኞች ተጨምረዋል ነገር ግን የተጨመሩት ዘበኞች ያሉበት ስፍራ እሩቅ እሩቅ አገር ስለሆነ ባሁኑ ወር ፈጽመው አልከተቱም ። ለሥራውም አካሄድና ለዘበኛውም አቋቋም አሰልጣኝ ተደርጓል፡ከተማውም አሁን መጀመሪያ ለአሥር ኮሚሣርያ ተከፍሏል ። ኮሚሣሪያ ማለት የሚሾመው ያንድ ክፍል የዘበኛ ሹም ትእዛዝ የሚሰጥበትና የሚቀበልበት አስተካክሎ የሚሠራበት ማለት ነው።ከዚሁም የመጀመሪያው ኮሚሳሪያ ነሐሴ ፲፬ ቀን ተከፈተ ።

ይኸውም ዋናው ኮሚሳሪያ በተከፈተበት ቀን የከተማው ዋና የዘበኛው ጠቅላይ አለቃ ግራዝማች ሣህሌና የሥራው አዘጋጅ ኮርቴን ባቢኪያን የሥራውን አዠማመር ለማሣየትና ይኸውም ሥራ የቆመበትን ቤት ለማስመረቅ ክቡር ከንቲባ ነሲቡና ክቡር ነጋድራስ አስታጥቄን ደግሞ የማዘጋጃ ቤቱን አማካሪ ክቡር ሙሴ ሻኑዋን ጠርተው ነበረና ወደዚሁ ቤት በመጡ ጊዜ የከተማው ዘበኛ አንድ ሳይቀር የሰልፍ ልብሱን ለብሶ ከሾላው በታች ባለው መንገድ ግራና ቀኝ ተሰልፎ ተቀበላቸው ክቡር ከንቲባ ነሲቡም በመካከላቸው አልፈው ወደ አዲሱ ኮሚሳሪያ ቤት ቀረቡ ። ይኸውም አዲሱ የኮሚሳሪያ ቤት በባንዴራና በልዩ ልዩ ጌጥ ተጊጦ አምሮ ነበረ ።

ክቡር ከንቲባም ይህ በጊዜያቸው በመከፈቱ ደስ ብሏቸው ወደዚሁ ቤት እንደገቡ ለባንዴራ መስቀያ በተዘጋጀው ደርብ ላይ ወጥተው ባንዴራውን ከፍ አድርገው ሰቀሉ ።

በዚያን ጊዜ በዚሁ ኮሚሳሪያ ቤት ላይ ባንዴራውን ከፍ አድርገው ስለሰቀሉላቸው የዘበኛው ዋና ጠቅላይ አለቃና ኮርቴን ባቢኪያን የደስታ ምስጋና አቀረቡ ። ጥሩምባ ነፊዎቹም በጥሩንባ ድምጽ እያዜሙ ምሥጋና ሰጡ ። ከዚህም በኋላ የከተማ ዘበኞችና የፈረስ ሠልፈኞች ሠልፋቸውን ለማሳየት በማማር እየተሰለፉ ክቡር ከንቲባ ነሲቡ ወዳሉበት መጡ ። መጀመሪያ የፈረስ ሰልፈኞች ከአለቃቸው ጋራ በፈረስ በፈረስ ሰይፋቸውን እየመዘዙ በሚያምር ድምጽ ጥሩምባ እያስነፉ ሰላምታ ሰጥተው አለፉ ። ሁለተኛም የግራዝማች አማረ ባልደረቦች በጠመንጃ ተሰልፈው ጥሩምባ እያስነፉ ሰላምታ ሰጥተው አለፉ ። ሶስተኛም እንደዚሁ የባሻ ደነቀ ባልደረቦች ተሰልፈው ሰላምታ እየሰጡ አለፉ አራተኛ የባሻ ወልዴ ጊዮርጊስም ባልደረቦች ሰላምታ ሰጥተው አለፉ ። ይህም ሁሉ ሲሆን ሁለት ያህል ፍቶግራፍ አንሺዎች እየዞሩ ያነሱ ነበሩ፡ከዚህ በኋላ ክቡር ከንቲባ ነሲቡ ይህ አዲስ ቤት በመቆሙና ዘበኞቹም በሰልፋቸው ደስ ስለ አሰኙዋቸው ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈውን የቃል ምስጋና ስብከት አደረጉ ።

የአዲስ አበባ ከንቲባ ነሲቡ ዛማኔል ።

የኢትዮጵያ ዋና ከተማ ከፒታሊ ከመቶ ሺ የሚበልጡት ሕዝቦች ሰፍረውበት ባለችው ስፍራ ዋናነቷን ከመንግሥት በተቀበልሁት ኃላፊነት ለሥልጣኔዋ አካሔድ ሙሉ ፈቃድ እንዳለኝ ለማስረዳት ስልና የዚሁኑም ሥራ በማከናወን የሚረዱኝን አዋቂዎች በየክፍላቸው በማስጠጋቴ ለደስታዬ ፍጻሜ የላትም ።

ይህ የአዲስ አበባ ከተማ የሕግ አቋቋም ሥራ ቀድሞም ተጀምሮ እንደነበረ አሁንም ባለው ዘመን በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ባልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ፈቃድ ለጊዜው በኔም አገልጋይነት የተነሳ እያደር እየተሻለና ሥራው እየጠነከረም በመሄዱ የከተማ ነዋሪ ሕዝቦችን ደስ ሳይላቸው አይቀርም ። ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ ወይም ለሚከተለው ስብከት ማድረጊያ በጣም ጊዜ ስላላገኘሁ ላሁኑ ደስታዬ የሚያስፈልጉኝን ምረቃዎች ብቻ መጀመሪያ ለፖሊሱ ዋና አለቃና ለዋናውም የፖሊሱን ሥራ አዘጋጁ ሁለተኛም በበታቻቸው ላላችሁ ዋና ዋና ሹማምንቶችና ለፈረሰኛው አለቃ ቀጥሎም እንደዚህ ለበታቾቻቸው ተከታይ አለቆች ሶስተኛም ለታመኑት ለአዲስ አበባ ከተማ የፖሊስ ወታደሮችና ለፈረስ ሰልፍ ተማሪዎች ጭምር ከዲሬክተሩ ጋራ በማዘጋጃ ቤቱ ስም ሁኜ ጥልቅ የሆነ ምሥጋናዬን በሚገባ ላቀርብላችሁ በጣም ደስ ይለኛል

አስቀድሞም እንደኖረች አሁንም ለወደፊቱ ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር መንግሥታችንንም ለዘለዓለም ያኑርልን አሜን ብለው በጨረሱ ጊዜ ሕዝቡ ዳር እስከ ዳር በደስታ አጨበጨቡ፡

ደግሞ ለዚሁ ሥራ የተመረጠው የፖሊሱ አስልጣኝ ቀጥሎ የተጻፈውን ቃል ተናገረ ። ክቡር ክንቲባ ነሲቡ ሆይ በኢትዮጵያ መንግሥት በታላቁ ከተማ ውስጥ የፖሊስ የሥራ ሕግ ለማቆም ታምኜ ስለ ታዘዝሁና ለዚሁም በዛሬ ቀን የመጀመሪያውን የፖሊስ ከሚሳሪያ በመክፈታችን እጅግ ደስ ብሎኛል ።

እኔ መጀመሪያ የፖሊስ ሥራ የሠራሁትና ያገለገልሁት በአርመን አገር በግሪክ አገርና በፈረንሳዊ አገር ነው ። ደግሞ አሁን በእግዚአብሔር ቸርነትና በኢትዮጵያ መንግሥት ፈቃድ የፖሊስ ሥራ ለማቅናት ስለ ታመንኩ እጅግ ደስ ብሎኛል ።

አሁንም እናንተ እንደምታውቁት የኢትዮጵያ መንግሥት ከብዙህ ሺህ ዘመን በፊት ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ በሃይማኖቱና በነጻነቱ ስለ ቆየች ዛሬም ለዚሁ ምስክር የዓለሙን ታሪክ ብንመረምርና ብንመለከት ዮልያኖስ የሚባል የቢዛንትንዩ ንጉሥ በየመን አገር ያሉት ክርስቲያኖች ስለ ተገላሉ አይሁዶችን እንዲያጠፋ ኢትዮጵያን ለመነ ።

ስለዚህ ኢትዮጵያ ድል አድርጋ የየመንን አገር ሰባ ስድስት ዓመት ገዝታ የጨረቃና የኮከብን አምልኮ አስጥላ በኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል ሰላምን ሰጠች ።

ዛሬም ለኢትዮጵያ ተስፋና ብርሃን ለሆኑት ለልዕልት ግርማዊት ንግሥትና ለልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን በብሩህ ልቡናቸው አስበው አገራቸው ሰልጥኖ እንዲነቃና እንደውጭ አገር መንግሥት ትክክል እንዲሆን የሚገባውን የፖሊስ ሥራ በመጀመሪያ እንዲቆም ስላደረጉ የከበረ ምስጋናዬን በትሕትና አቀርባለሁ ።

ስለ ዚህም የኢትዮጵያ ልጆች በሀገራቸው ውስጥ ሥልጣኔ እንዲገባና የሀገሩ ሕዝብ እንደውጭ አገር እንዲነቃ ላሰቡትና ለወደዱት ሰዎች የማክበር ምሥጋናዬን አቀርብላቸዋለሁ ይኸውም በታሪክ ተጽፎ ከሕይወታቸው በኋላ ለመታሰቢያቸው ሁኖ በልጆቻቸውና የኢትዮጵያን ጥቅም በሚወድ ሰው ሁሉ አፍ እንዲነገር ፍጹም ተስፋ አደርጋለሁ ።

አሁንም ይህ ሥራ ለሥልጣኔ እንደተጀመረ ፍጻሜው አምሮ ሌላውም ሁሉ እንደሚገባው የሥራ ሕግ እንዲሰራና ኢትዮጵያ ነቅታ ትክክል ከአውሮፓ እንደ አንዱ መንግሥት እንድትሆን በሙሉ ልቤ እመኛለሁ ።

ማናቸውም መንግሥት ቢሆን ቀዋሚ ሆኖ የኖረውን ታላቅነት ለማሳየት የፈለገ እንደሆነ የተከከለውን የሥራ ሕግ መከተል ያስፈልገዋል በማናቸውም መንግሥት የፖሊስ ሥራ ዋና ስለ ሆነ የመንግሥትን ትእዛዝ በቶሎ ፈጽሞ የሕዝብን ጤንነትና ሰላም እየጠበቀ አገሩን አስመስግኖ ወደ ከፍታ ያደርሳል።ስለዚሁም ነገር በሙሉ ሐሳባቸው ስለ ጣሩና በሥራውም ረገድ ላገራቸው ስለ ሚሆነው ጥቅም ሌትና ቀን ስለ ረዱን ለክቡር ክንቲባ ነሲቡ የማክበር ምስጋናዬን አቀርባለሁ ይኸውም በታሪክ ተጽፎ ለመታሰቢያቸው ሁኖ እንዲነገር እመኛለሁ ከዚህ ቀጥለን ያለ እረፍት እየደከሙና ለመንግሥታቸው ጥቅም እየጣሩ የሀገራቸውን ሰላም ስለ ጠበቁ ነጋድራስ አስታጥቄንና ግራዝማች ሣህሌን እናመሰግናለን ።

ስለ ኢትዮጵያ ጥቅምና ሥልጣኔ ለተጀመረው ሥራ እንደ ጽጌ ረዳ አብቦ እንዳይረግፍ ከዚህ ቀደም እንደተሰጠኝ እርዳታቸው አሁንም ላወደፊት እርዳታቸውን ከቀድሞ የበለጠ እንዲሆንልኝ በማክበር እለምናለሁ ።

ስለ ዚህ ምክንያት ይህ ሥራችን አንዱም ሳይጐድል ነዋሪ ሁኖ እንደ አበባ እያማረ እንዲሄድ ሀገር መውደድን ጨምረን ያለ ስንፍና በትጋት እየሰራን ሥራው እየተቃና እንዲከናወንና እንዲሰለጥን እንመኛለን ብለው በጨረሱ ጊዜ የደስታ ጭብጨባ ተጨበጨበላቸው ።

ይህም ካለቀ በኋላ ክቡር ክንቲባ ነሲቡ ለሻምፓኝ ወደ ተዘጋጀው ክፍል ገብተው ክቡር ዲሬክተርንና ክቡር ሙሴ ሻኑዋን በቀኝ ክቡር ግራዝማች ሣህሌንና ካፒቴን ባቢኪያንን በግራ ደግሞ ሻምበሎች ግራዝማች አማረና ባሻ ደነቀ የፈረስ ሰልፈኞች አለቃ አቃ ኢዮብና አቶ ሚካኤል ካሣ ልጅ ወርቁ ይታጠቁና እኔም በዚሁ በፊታቸው ነበርንና ሻምፓኝ ተከፍቶ መርቀን ከጠጣን በኋላ ኢትዮጵያ ወደ ፊት የብርሃንና የሰላም የሥልጣኔና የደስታ ጊዜ በልዕልት ግርማዊት ንግሥትና በልዑል ብርሃን ተፈሪ መኰንን ዘመን በማግኘቷ እግዚአብሔርን ምሥጋና ይድረሰው ብለን በሙሉ ልባችን አመሰገን ።

ተክለ ማርያም ካሣሁን ።

ክቡር ክንቲባ ነሲቡ ከተሾሙ ጀምሮ የማዘጋጃ ቤት ሥራ የዋና ከተማችን ያዲስ አበባን አስተዳደር እየተሻሻለና ወደ ፊት እየገፋ በመሄዱ እጅግ ደስ ብሎናል ። ወደ ፊት ደግሞ በክቡር ክንቲባ ነሲቡና በክቡር ነጋድራስ አስታጥቄ በዲሬክተሩ በማዘጋጃ ሹማምትና ሠራተኞች የሚታሰበውን ሥራ በተፈጸመበት ጊዜ በብርሃንና ሰላም ገልጠን እንድናስታውቃችሁ ተስፋ እናደርጋለን ።

የጥያቄ ምላሽ ።

ነሐሴ ፲፬ ቀን ፲፱፻፲፯ ዓ ም የተጻፈ የብርሃንና ሰላም ጋዜታ ፤ ክቡር ነጋድራስ ደስታ ሰስት ያህል ጥያቄ ከወድሞቻቸው እንደ ጠየቁ ምላሹንም የሚያገኝ ሰው ቢኖር እንዲያስታውቃቸው ልመና ጭምር ጽፈዋል ። ክቡር ነጋድራስ ደስታ በውነት በሀገራችን ስልጥንና እንዲገባ መጥፎ ጠባይና ብልግናም እንዲቀር ይህን የመሰለ ሁሉ ቀርቶ ሌላ ደህና እንዲተከበት ተጊ መሆናቸው እርግጥ ነው ። እኔም ይህ የጠየቁት ጥያቄ በጣም ደስ አሰኝቶኛል ፤ ነገር ግን ከጥያቄዎቹ መሃል «ስርቆሽ በር» የሚባለውን ጥያቄ ብቻ ትንሽ የሚመስለውን ከነማስረጃው ጽፌአለሁና የሚሰማማ ቢሆን እንዲቀበሉት ፤ የማይሆን ቢሆን ግን አንባቢ እንዳይነቅፈኝ አጥብቄ እለምናለሁ ።

በኢትዮጵያ ያለን ቋንቋ መሠረታዊነቱ ከግዕዝ ነው ። በንግግራችንም ሁሉ አልፎ አልፎ ፍጹም ግዕዝ እየሆነ ይገኝበታል እነሆ በግዕዝ « ሠረቀ » ማለት ወጣ ተብሎ ይተረጐማል ። ለዚሁም በብዙ መጻሕፍት ክፍል የሚያስረዳ ይገኛል ። እንደዚሁ እንዳልሁት ሠረቀ ከሚለው ተያይዞ የመጣ ቋንቋ የስርቆሽ በር መባሉን ያመለክታል ፤ ይኸውም የመውጫ በር ማለት ይመስላል ።

ደግሞ እንደዚሁ በግዕዝ (ፍትሕ) ማለት ፍርድ ተብሎ ይተረጐማል ፤ ይኸውም የፍትሕ በር ማለት የፊት በር ይመስላል ለቀረው ጥያቄ ግን እኔም ከክቡር ነጋድራስ ደስታ ጋር መልስ ጠባቂ ነኝ ። ይህነንስ በዚህ እናቁመውና ያየነውን ልጻፍ የልዑል አልጋ ወራሽ ሐሣብ ሁልጊዜ ለኢትዮጵያ ጥቅም መሆኑን በሥራቸውና በሐሣባቸው ግልጥ እንደሆነ ብዙ ጊዜ የታወቀ ነው ። እነሆ ልዑል አልጋ ወራሽ ያሠሩት አዲስ የግቢ በር ስሙን የሰላም በር ብለውታል ። ይኸውም በኢትዮጵያ ሰላም እንዲሆን ማሰባቸውን ያስረዳል ፤ ትንሽ ግጥም እናንብብ ።

ልዑል አልጋ ወራሽ የድኆ ገዳም ።
በሠሩት ጐዳና ይግቡ በሰላም ።
በእርስዎ ጐዳና በቀናው መንገድ ።
የሚከተልዎ በሰላም ይሂድ ።
መሄድ ይሻለናል በርስዎ ጐዳና ።
መንገድዎ መልከም የቀና ነውና ። ውድነህ ይነሡ ።

ስለ ተማሪ ቤት እርዳታ፤

በኢትዮጵያ ማኅበር ለሚቆመው ተማሪ ቤት እርዳታዬን ፯ ብር ሰጥቻለሁ ።

ደግሞ የብርሃንና ሰላምን ምክር እንደተከተሉ አንዳንዶች ሰዎች የሕዝቡ ባሕሬ ሁሉ ተገሥጾ ገንዘባችንን ሕይወታችንን ለሚጐዳ ላረቄ ከመስጠት ለጥበብ መግዣ መስጠት ይሻለናል ብሎ አረቄ መግዛትን የተወው እንደሆነ እኔም ከሁኑ እንኳ ትዳሬ በጣም የማንስ ብሆን እንደምንም ብዬ ባመት ባመት ፫ ፰ ብር ለዚሁ ተማሪ ቤት እርዳታ እሰጣለሁ እግዚአብሔር ግን ተስፋ ቢሰጠኝ እንደሚቻለኝ መጠን እሰጣለሁ

ይኸውም ለማቆም የታሰበው ተማሪ ቤት በእግዚአብሔር ቸርነት ለመልከም ፍሬ እንዲበቃና እንደመከር አዝመራ የሰውን ልብ ሁሉ ደስ ለማሰኘት ያብቃልን ፤ እግዚአብሔር የዚህን ተማሪ ቤት መስራቾች ትጋት በብርታትና ባለመሰልቸት ያስጨርስልን። በክፉ ልማድ ምክንያት ከለመማርና ሥራ ከመፍታት ብዙ ሰዎች ለስንፍና ሥራ ይተባበራሉ ለንደዚህ ያለው መልከም ሐሳብ ግን መተባበርና ገንዘብን መስጠት እንዴት ያለ ትልቅ እድል ነው። ደግሞ ይኸንን ፩ አጭር ምሳሌ እናገራለሁ የጣር መሬት ያለው ሰው ላም ገዝቶ ቢያረባ በሬ ያገኛል ቅቤ ይበላል በዶውም ለረኛውና ለልጆቹ ለሌሊቱ ቤት ጠባቂው ለውሻውም ጭምር ምግብ ይሆናል ለማገዶ ኩበት ያገኛል። ላሚ እንኳን ብትሞት ከወለደቻቸው ሌላ የራስዋን ሰውነት ለባለቤቱ በያይነቱ ብዙውን ጥቅሟን ትታለት ትሄዳለች ። (ማለት ሥጋዋ ቆዳዋ ቀንዷ ጭራዋ) ፤ የጣር አገር ሰው ግን ጣር እያለው በላምዋ ዋጋ ቅቤ እየገዛ ቢበላው ጣሩም በከንቱ ደርቆ ይቀራል ገንዘቡም በቅቤው ግዢ ቶሎ ያልቃል አደራረጉም ከስንፍና ይቆጠራል ራሱም ይጐዳል እንደዚሁ እኛም ዕውቀት ስለሌለን ከባለጸጐች እስከድኆች ከመሬታችን ውስጥ ብዙ ጥቅም እያለን በብዙ ድካም የምናገኘውን ገንዘባችንን በጥቂት ድካም ብልሆች የሚያመጡልንን ዕቃ ስንገዛ እንኖራለን የብልሆች ጥቂቱ ድካም ብልሃት የሌላቸውን ሰዎች ብዙውን ድካም እንዲገዛ አስረድቶ በሚመክረን የመንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር በሚለው በብልሁ ፀነጋድራስ ገብረ ሕይወት መጽሐፍ አንብበነዋል ።

እኛም ደስ የሚያሰኙንን የብልሆችን ዕቃ ሁሉ ለመግዛት በያመቱ ብዙ ገንዘብ ለማውጣት የማንነፍግ ሰዎች እውቀትን እራሷን ለመግዛት ብንነፍግ ግን እንዴት የሚያስገርም ይሆንብናል እንደተባለ ጥበብን የሚያገኝ ሰው ምስጉን ነው ማስተዋልንም የሚገዛ ምሳ ፫ ም ቍ ፲፫

በቀደም ለት ፊታውራሪ ዴሬሳ እግኝተውኝ ሲያጫውቱኝ እውቀትን ለመግዛት መንገዱ የሚያሰናክልና ቅን መሆኑን በታሪክ እንዳገኙት የጃፓኖችን አሰለጣጠን ጀማሪና አሁን ያሉበትን የማዕርጋቸውን አኳኋን ቢነግሩኝ እኔም ስለ ሐገሬ ልቤ በመቸከልና በተስፋም ተመሰጠ ። ይህቺን በብዙ ድካም ከየደመወዜ ላይ በየወሩ አንድም ሁለትም ብር እያስቀረሁ ያጠራቀምኳትን ገንዘብ ሩብን ሃምሳዋን ብር ለመስጠት ልቤ መሐላ አደረገ ። እኔ ጌታዬ የሞቱብኝ እንደራሴ ሀሳብ እውቀትና ተስፋ የሌለኝ ምስኪኑ ድሃ ካለችኝ ከፍዬ ስሰጥ ብልሆቹ ባለጸጐቹ ያገሬ ጌቶች ሁሉ በያንዳንዳቸው ገንዘብ አንድ አንድ ተማሪ ቤት ለማቆም ዝቅተኞችም እንደመጠናቸው ብዙ ገንዘብ ለማውጣት እንዴት ይነፍጉ ይመስላችኋል ።

ደግሞ እንደትጉሁ እንደፊታውራሪ ዴሬሳ ምኞት በኢትዮጵያ ማህበር ለሚቆመው ተማሪ ቤት እርዳታ መንግሥት ከማዘጋጃ ቤቱና ከጉምሩክ ገቢ በወር በወሩ ከመቶው አስር ለመስጠት የግርማዊት ንግሥት ዘውዲቱና የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ደስታቸው ሳይሆን ይቀር አይመስለኝም ።

ተፈራ ይፍሩ ።

በኢትዮጵያውያን ማኅበር ለሚቆመው ተማሪ ቤት እርዳታ እንሰጣለን ብለው ፊርማቸውን የሰጡ ሰዎች ።

ከ፴፰ ቍጥር የመጣ ድምር ፰ የምስር ወርቅ ፰ሺ፫፻፲፰ ብር ተ፪ ሩብ

ሊቀ መኳስ መኰንን ዋልቴ ባመት ባመት ።	፪	ብር
ፊታውራሪ መንገሻ ይልማ መግቢያ	፲፰	ብር
ባመት ባመት	፬	ብር
አቶ ተፈራ ይፍሩ መግቢያ ፯ ብር ባመት ባመት	፰	ብር

ድምር ፰ የምስር ወርቅ ፯ሽ፴፰ ብር ተ፪ ሩብ

የፈላስፎች ቃል

እግዚአብሔርን ወደህ የፈቀድከውን አድርግ ።

ሰን አጐተን ።

ንሮዋችንን ለራሳች ብቻ የማድረግ ልማድ ሁል ጊዜ ለሌሎች መኖር እንዳንችል ያደርገናል ። ቢኒት ።

ወየጉድ ። ይህ ለራሱ ብቻ የሚኖር ክፉ አንዋዋር ኖረ።

አልፍ ዶሙሴት ።

ለሌሎቹም ደስታ ካላሰቡ ለራስም ደስታ አይገኝም ።

ቤርናርደን ደስን ፒዬር ።

መኰትኰት ወዳጆችን ብቻ አይደለም ። ወዳጅነትንም ነው እንጂ ። በጥንቃቄ ጠብቆ ተመልክቶ ውሀም ማጠጣት ነው

ዡበር ።

ላንተው በራስህ እመን ልብ ሁሉ በዚህ በብረት ሽቦ ይንቀጠቀጣል አምላክ ላንተ ያገኘልህን ቦታ ተቀባል ። በዘመንህ ካሉ ሰዎች ጋራ መተባበርን የሥራ እንደ ሰንሰለት መያያዝን ታላላቅ ሰዎች ይህነን አድርገዋል ። በዘመናቸው በተሰጣቸው ዕውቀት እንደ ልጆች እየተማመኑ ። ኤሜርሰን ።

በልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ

መጀመሪያ ዓመት ፤ ቁጥር ፴፯ ።
1re ANNÉE № 37

ሐሙስ ጳጉሜ ፭ ቀን ፲፱፻፲፯ ዓ ም።
JEUDI 10 SePtembre 1925

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraissant tous les jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

የጋዜጣው ዲሬክተር ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።
Gabré Christo Taklé Haymanot
Diréecteur

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በሳምንት ሊገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ስለ ርእሰ ዓውደ ዓመት ።

ርእሰ ዓውደ ዓመት ማለት የዓመት በዓላት አጽዋማት ሁሉ መሰብሰቢያ አውድማ ማለት ነው በአውድማ የሥጋዊ ምግብ የዘር ወገን ሁሉ እንዲሰበሰብበት በዚህም ቀን የነፍስ ምግብ የሚሆን በዓላትን ማክበር አጽዋማትን መገመሪያና መጨረሻ የምንረዳበት ቀን ነው ። ይኸውም ቀን ዕንቊጣጣሽ ይባላል ።

የኢትዮጵያ ሰዎች ለምለም ሣር ከራሳቸው ላይ እያሰሩ አበባ በእጃቸው እየጨበጡ በዓሉን ያከብሩታል ለምለም ሣርና አበባ መያዛቸው በኖኅ ጊዜ ማየ አይኅ ጎደለ ስትል ርግብ ለምለም ቅጠል ባፏ ይዛ ታይታ ነበርና ምንም የኖኅ ውሃ የጥፋት ቢሆን ክረምት የወሀ ዘመን ስለ ሆነ ወሀ ጎደለ ክረምት አለፈ ለማለት ይመስላል ።

የዕንቊጣጣሽም ታሪክ ንግሥተ አዜብ ለሰሎሞን ተንከራ የሚባል ዕንቊ ወስዳ ገጸ በረከት ብትሰጠው ዕንቊ ለጣጣሽ ይሁን ብሏታል ይባላል በኢትዮጵያ ሕግ የተሰበከው በንግሥተ አዜብ በምኒልክ እናት ጊዜ ነውና በዚህ ምክንያት ይህ ሲታሰብ ይኖራል ባዚሁም ቀን የቅዱስ ዮሐንስ መጥምቅ በዓል ይከብራል ።

እንደኛ መስከረም የኢትዮጵያችን የአዲስ ዓመት መጀመሪያ ነውና እኛ ደግሞ በዋዜማው ለብርሃንና ሰላም ወዳጆች ሁሉ እንኳን ከ፲፱፻፲፯ ዓ ም ዘመነ ማቴዎስ ወንጌላዊ እስከ ፲፱፻፲፰ ዓ ም ዘመነ ማርቆስ ዜናዊ በደሕና አደረሳችሁ እያልን በብርሃንና ሰላም በአዲስ አበባ የደስታ ምሥራች እናቀርባለን ።

ይድረስ ለክብርት እናታችን ለኢትዮጵያ ።
የማክበር ሰላምታዬ ላንቺ ለናታችን ይሁን ።

እስከ አሁን ድረስ ወረቀት ሳልጽፍልሽ የቆየሁት ።
ወረቀትና ቀለም የለኝም ነበር ከጥንት ።
ዕድሜ ለልዑል ተፈሪ መኰንን አገኙልኝ ከተሰወረበት ።
ቀለሙንም አዘውልኛል ወዳንቺ እምጽፍበት ።
በምጽፍልሽ ቃል ጸያፍ ቢገኝብኝ ።
አልተማርኩምና ይቅርታ አድርጊልኝ ።

ክብርት እናታችን ሆይ እስከ አሁን ድረስ የቀደሙት አያቶቻችን ባንቺ በናታቸው እጅ የሚገኘውን መልካም ምግብና ለሰውነት ደስ የሚያሰኘውን ነገር ሁሉ ሳያገኙት ስለ ቀሩ እንደጐረቤቶቻቸው አምሮባቸው አልኖሩም ነበር አንቺም እናታቸው ባንቺ እጅ የሚገኘውን መልካም ምግብ ሳይበሉት ስለቀሩ ማዘንሽ አልቀረም ለዚሁም ምሳሌ እናት ለልጅዋ ምግብ አሰናድታ ሳይበላላት የቀረ እንደሆነ መናደድዋ እንደ ማይቀር አንቺም ስትናደጅ ትኖሪ ነበር ።

አሁን ግን እኛ የዛሬዎቹ ልጆችሽ ባንቺ በናታችን እጅ የሚገኘውን መልካም ምግብሽን ሁሉ እየበላን እንደ ጐረቤቶቻችን በደስታ እንድንኖር ብርሃን በልዑል ተፈሪመኰንን ተገለጸልን

እንግዴህ በብርሃን እያየን በሰላም እየሄድን አሳብና አሳባችን ከተገናኘ ባንቺ በናታችን እጅ የተዘጋጀውን ምግብ በፍቅር ሆነን እንበላዋለን ብለን ልጆችሽ ሙሉ ተስፋ አድርገናል አንቺም እናታችን በጣም ደስ ይበልሽ ፤ ልጆችሽ ይኸንን አሳብ

ስለአሰቡልሽ ፤ ነገር ግን በፊት ማሰብ ። ከማሰብ በኋላ መሥራት ከመሥራት በኋላ መብላት ነውና ይህንን ልጆችሽ የሚያስቡትን እንዲሰሩት ከሰሩትም በኋላ እንዲበሉት ብለሽ እንቺም እናታችን ወደእግዚአብሔር ለምኝልን ። ቀድሞም ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር የተባልሽ ነሽና ይላል ልጅሽ

ይድረስ ከክቡራን ልጆቼ ።

ብርሃንና ሰላም ለናንተ ለልጆቼ ይሁን ።
ክቡር ወረቀታችሁ ደረሰኝ ።

ለቀደሙትም አያቶቻችሁ በኔ በናታቸው የሚገኘውን ያዘጋጀሁላቸውን ምግብ ሁሉ ብርሃን ሳይኖራቸው ቀርቶ በለ መብላታቸው እጅግ ስናደድ መኖሬ እርግጥ ነው።አሁንም ልጆቼ ሆይ ብርሃንና ሰላም መርምሮ አውጥቶ በኔ በናታችሁ እጅ ተዘጋጅቶ የተቀመጠውን ምግብ በፍቅር አንድነት ሆናችሁ እንድትበሉት የምታውቁበት የተማሪ ቤት የምታውቡበት ብርሃንና ሰላም አስበ ላወጣላችሁ ክብር ምስጋና ይግባው ።

እናንተም ይህንኑ አሳባችሁን ሁሉ በፍቅር ባንድነት አድርጉት፤ደግሞ አንድ ትልቅ ነገር አስታውቃችኋለሁ ምቀኝነት ተንኮል ሐሰት የሚባሉ እነዚህንም የመሰሉ ሌሎችም ጓደኞቻቸው አሉና እስካሁንም አውከው የሚኖሩ እነሱ ናቸውና እነሱ ከቤታችሁ እንዳይገቡ በመንገድም እንዳታነጋግሯቸው ከልተጠነቀቃችሁ የምታስቡት መልካም ሐሳብ ሁሉ ከንቱ ሁኖ መቅረቱ ነው ከመናደድ በቀር ደስ የሚል ነገር አለመገኘቱን እወቁት ። እኔ ግን ባይሰሙኝ ነው እንጂ ለቀደሙትም አያቶቻችሁ መምከሬ አልቀረምና ለናንተም ውርድ ከራሴ ነው ። እውነትን ከቅንነት ጋራ ባልደረባ አድርጋችሁ ሥራችሁን ብትሠሩ ሐሳባችሁ ሁሉ እንዲፈጸም ደስታም በሕይወታችሁ ሁሉ አብሯችሁ እንዲኖር በርግጥ አመለክታችኋለሁ ። አሁንም ሥራውን በትክክል የሚሠራ ለሚሠራም ሰው እንቅፋት የማይሆን ሰው ቢኖር በእግዚአብሔርም በሰውም የተመሰገነ ይሁን አሜን ።

ትላለች እናታችሁ ኢትዮጵያ ።

ሁሉም ነገር የሚገኘው በትምሕርት ነውና ከድንቁርና ወደ እውቀት፣ ከተንኮል ወደቅንነት ሐሳብ በፍቅርም የሚገኘውን ትርፍ እውቀን እንድንሰሪበት ። እውቀትን ከተሰወረበት መርምሮ ለማግኘት የሚያስፈልገው በየስፍራው የተማሪ ቤት ነበር፤ ለዚሁም ተማሪ ቤት በሐገራችን በኢትዮጵያ አስራምስት ሚሊዮን ሕዝብ አይጠፋምና አስራአምስቱ ሚሊዮን ሕዝብ አስራ ሁለቱ ሚሊዮን በሰው ፈቃድ የሚያድር ቢሆን ሶስቱ ሚሊዮን ሕዝብ በፈቃዱ የሚያድር ሳይሆን አይቀርም ይኸ ሶስቱ ሚሊዮን ለሐገሩ ልጆች አስበ የተማሪ ቤት ማቆሚያ አምስት ፭ ብር ቢረዳ ፲፭ ሚሊዮን ብር ይገኝ ነበር ። ይኸውም ፲፭ ሚሊዮን ብር ብዙ የተማሪ ቤት እንዲያቆም አይጠረጠርም ።

ይኸንን ሐሳብ ለሕዝቡ በልቡ ጽላት እንዲጽፍለት ልዑል እግዚአብሔርን እለምናለሁ ።

እኔም ሐሳቤን አመልክቼ እንዳልቀር እንዳቅሜ አዲስ እንዲቆም ለታሰበው ተማሪ ቤት አስር ፲ ብር ባመት ባመቱ እሰጣለሁ። ከዚህ በላይ ያለውን ደብዳቤ የጻፈ ታፈሰ ገዛኸኝ።

ስለየኢትዮጵያ ቸርነትና የልጆቿ ለትምህርት መንቃት ።

ብርሃንና ሰላም ገቡ ባገራችን ። እየሰሩ ይሂድ የውቀቱ ቤታችን ። ትምህርትን ጡደዱ ሁሉም ልጆቻችን ። እውቀትን ናፈቀ አብዣኛው ሕዝባችን ። እግዚአብሔር ይመስገን ፈጣሪ አምላካችን ። ለዘላለም ትቁም ሰንደቅ አላማችን ። ለልጆቿ ትሁን ኢትዮጵያ አገራችን ። ትሰንብት ዘውዲቱ ካልጋ ወራሻችን ።

ለማን እናት አለው እንዳገሬ እናት ። እሸት የምትሰጥ በጋ ተክረምት ። ተራራና ወንዟን ዛላዋን ላያት ። ምንም ያህል አታንስ ከምድረ ገነት ። ታፈሳለችና ማርና ወተት ።

አልረሳሁም ነበርኩ ሳለሁ በስደቴ ። ምንም አቅም ባጣ ቢደክም ጉልበቴ ። በጋሜዬ ሂጄ መጣሁ በሽበቴ ። ዓይኔ ከፈዘዘ ካለቀ ጉልበቴ ። እንግዲህ ጠውሪኝ ኢትዮጵያ እናቴ፤

እንኳንና ለኔ ለበኽር ልጅሽ ። ምስርና ሱዳን ትመግቢያለሽ ፤

ከርበ አራቱ መንግሥት ተስማማ ተፈሪ፤ ተጋ ተጋ ብለሽ አገሬ ተማሪ ፤

እንግዲህ እንማር ከውል እንዳንወጣ ፤ ያ ፳፭ ዓመት ገሥግሦ ሳይመጣ ፤

ሕፃን አይደለምወይ የበቀደም ልጅ ። ከፍ ከፍ ያረገችው ዘውዲቱ ናት እንጂ ።

ምንጊዜ ተወልዶ ዋነተኛ ሆነ ። ታናሹን ታላቁን ይዞት ተሻገረ ።

ወራሽ አለኝ ብለሽ አጥብቀሽ ስትከሪ ። እሱስ ቃብጣን ሆነ ሰው አሸጋጋሪ ። ትህትና ያቡቱ አይከራም ተፈሪ ። ደግሮ አሻገረው ያን ሁሉ ተማሪ ። ጨራሼ ነህ እያልሽ ስታጠናክሪ ፤ ይኸው ሊቅ ሆነልን አገር አስተማሪ ።

በሎንዶን ከተማ ተመስክሮለት ። ማዕርግ ተቀበለ የሊቆች ዕውቀት ።

ኢትዮጵያ ውለጅ እንግዲህ አትፍሪ ። ሊቁ እሱ ከሆነ ልጆች አስተማሪ ።

ውለዱ ተባዙ ስለ ደኸያችሁ ሴቶች አትታክቱ ። የልጅ ማሳደጊያ ወርቅናት ዘውዲቱ ፤

እኔ ግን አልፈራም ሚስቴ ብትወልድልኝ መስከረም ሲነጋ። እስተምረዋለሁ በዘውዲቱ ዋጋ ።

ባባት በቅድም አያት ንጉሥ ስንለው ። እዋቆች ፊስገ ምን አስበ ነው ።

አደገ አባ ጠቅል ጉለበተባችሁ ። ትታገሉትና ትሰበራላችሁ ምንም ቢጉለብት ኃይል ተሰምቶት ። እሱ ታግሎ አይጥልም ካላነቀፉት ። የሸዋ መንገዱ ክፉ ነው ቢሉት ። ነቅሎ ነቅሎ ጣለው ያንሁሉ ዕንቅፋት ።

ንግሥት ዘውዲቱ ምንጊዜ ገበሬ መቸስ አራሽ ሆኑ ። የሰውን ዘር ሁሉ ትክክል ነው ያሉ ።

ቆንጆይቱ አገሬ ተይኝ ተመከሪ ። ሌላም ጮኛ የለሽ እርጊ በተፈሪ ። ተፈተሻልና መክነሽ እንዳትቀሪ ።

ራስ ውጥንዎን ይጨማምሩበት ። ልግሥናዎም ይብዛ ለተማሪ ቤት ። ጠመንጃ ተጣለ ተረሳ ጥይት ። ገፍቶ መጣብዎ የውቀት ጦርነት ። ለጋ ለጋ ጉበዝ ያሰናዱለት ።

መርምረው አገኙት በኤውሮጳ አገር ። ግዛት በውቀት
እንጂ አይለማም በጦር ።
እባክዎ ንግሥት ልጅዎን ይርዱት ። በምክር በገንዘብ
ለተማሪ ቤት ፤ የጀመረው ሀሳብ እንዲሳላለት ። ድንበር እንዲጠና
እንዲረጋ ርስት ፡ አባት ቅድም አያቶች ከጥንት ያቆዩት
አብረን እንነሳ እንርዳ ሁላችን በልግም አይደለም
በሙሉ ልባችን ። በጉልበት በምክር ባለ ገንዘባችን ። ለነሱ
ዘውድ ነው ለኛም አገራችን ። የተቀበረበት የንግዴ ልጃችን
ራስ አገር ማየት ዙረት ከለመዱ ። ድልድዩ ይሠራ
ይጠረግ መንገዱ ። ሕዝቡም ደስ ይበለው ይንሰራፋ ንግዱ
ያበሻ መኳንንት አትውደዱ ባዳ ። ከደስታው አብሮን
በችግር አይረዳ ። ሰብስቦ ይሄዳል በታላቅ አቁማዳ ። ምስጢር
ብንሰጠው ያገባናል ዕዳ ።
ምን እንኳን ቢከፋ ይብሉት ልጆቻችሁ ። ፈጥነው የሚ–
ደርሱት ለመቃብራችሁ ።
ኢትዮጵያ አገሬ ለጋ ቆንጆ ናት ። ታናሹ ታላቁ አሻግሮ
ሲያጫት ፤ መልከም መራጭ አገር መልምሎ ዳራት ። ከሣህለ
ሥላሴ ከምኒልክ ቤት ።
ባገራችን ሰማይ ያለህ አምላካችን ። እንለምንሃለን ባን–
ድነት ሁላችን ። እስላም ክርስቲያኑ ፈላሻው ጋላችን ። ቅማንትና
ወይጦው ጥቁሩ ሻንቅላችን ። ኢትዮጵያ ትክበር የጋራ እናታችን
ትሰንብት ዘውዷ ፥ ያደራ ልጃችን ። መንግሥቲቱም ትጥና
የጥንት ርስታችን ። እንድናዎርሳት ለኋላ ልጃችን ። አሜን ።
አህመድ ይማም ። ምዕራብ ወለጋ ሰዮ ከተማ

ስለ ተማሪ ቤት እርዳታ ።

ሰው ሁሉ ሐሳቡን ለማስታወቅ ፈቃድ ሳደረጉለት የጥበብን ወሬ ለመስማት የሰውን አእምሮ ለማበርታት ለሚጣጣሩ ለግርማዊት ንግሥታችንና ለልዑል አልጋ ወራሻችን እድሜና ጤና ክብርና ምስጋና ያድላቸው ስንል በዚች በተባረከች ዓውደ ዓመት እለት እግዚአብሔርን እንለምናለን ። እኔም አንድ ኢትዮጵያዊ ድሀ ዝናም በዘነመ ጊዜ ሀብታምና ድሀ አንድነት ያርሳሉና ምንም ችግሬን አገር ያወቀው ፀሐይ የሞቀው ቢሆን ዝናመ ምሕረት ለሆነች ለጥበብ ትምሕርት ቤት እርዳታ በየዓመቱ በታህሣሥ ወር ሁለት ሁለት ብር እረዳለሁ ፤ ነገር ግን በየሳምንቱ ብርሃንና ሰላም ስመለከት ስለ ተማሪ ቤት እርዳታ ስጦታ ድሆች በዝተው ሀብታሞች አንሰው አገሁና ሳዝን ስተክዝ አንድ ሰው መጣ ልብ ካዘነ ዘንድ ፊት ይጠቍራል እንደ ተባለ ምን ሆንሃል አለኝ እኔም በኢትዮጵያውያን ማህበር ስለሚቆመው ለሐገራችን ጥቅም እንዲሆን የጥበብ ትምሕርት ቤት በገንዘብ እርዳታ ድሆች በዝተው ሀብታሞች አንሰው ስለ አየሁ ነው ብዬ መለስኩለት ነገሬን ገለጽሁለት እርሱም እንዲህ ብሎ መለሰልኝ ፡ ድሆች ቢፈጥኑም ቢዘገዩም ስጦታቸው ከማጣታቸው የተነሣ ጥቂት ነውና ቶሎ ይረዳሉ ። ሐብታሞች ግን ሀሳባቸው በብዙ ለመርዳት ነው ገንዘባቸው በሃገር ግዛትና በሰው ላይ ስለሆነ አሁን ለጊዜው በፍጥነት ለመርዳት ባይዘጋጅላቸው ነው እንጂ ። ከቶ ከኢትዮጵያ ያተወለደ ስንኳን ሀብታምና ችግረኛ እንኳ ቢሆን እንደማግኘቱ መጠን ለገንዘብ እርዳታ የሚሰንፍ የለም ብሎ ከሰማሁት እንጂ በትሁት ቃል ነገረኝ ። እኔም እንደ ዘካርያስ ሳልጠራጠር እንደ ኒቆዲሞስ ሳልከራከር የኢትዮጵያ ልጆች ሁሉ ብርሃንና ሰላምን ለመከተል ባጭር እንደታጠቁ የጥበበን ዓይን ለማየት እንደናፈቁ አስቤ ቃሉን ተረዳሁት ልዑል እግዚአብሔር መንግሥታችንን ለመርዳት ጥበብን ለማጥናት አሁን የምናየውን የዕውቀት ፍሬ ደርሶልን ለመብላት እንዲያበቃን በፍጹም ልቤ ተስፋውን እታመናለሁ ።

በርሀ ሠረቀ ለጻድቃን ወለርቱዓነ ልብ ትፍሥሕት እላለሁ ።
የአቡን አጋፋሪ በቀለ አበዬ ።

የከተማ ወሬ ።

ስለ በዓለ ሩፋኤል አከባበር ።

በጳጐሜ ፫ ቀን ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን በነግህ ወጥተው የቅዱስ ሩፋኤልን ቤተ ክርስቲያን ስመው ጸሎታቸውን አድርሰው በፍጥነት ተመለሱ ። በዚሁ ቀን ልዑል አልጋ ወራሽ የየአድባራቱን ካህናትና ድሆችን ሁሉ ሰብስበው ትልቅ ግብር አድርገው የሚያበሉበት ቀን ነው ዘንድሮም ለዚሁ ግብር የሚሆን ምግብና መጠጥ በሚገባ ተሰናድቶ በትልቁ አዳራሽ ቀረበ ።

አምስት ሰዓት ከሶስት ሩብ ሲሆን ልዑል አልጋ ወራሽ ከእልፍኝ ተነሥተው ወደትልቁ አዳራሽ ሲወርዱ ካዳራሹ በር እስከ ውጭ በር ድረስ ሰው ከብዛቱ የተነሣ እንደ ሮማን ፍሬ ተጨናንቆ ነበር ፡ ካዳራሹም ገብተው በተቀመጡ ጊዜ ከቡራን መኳንንቶቻቸው ሁሉ ግራና ቀኝ ከበዋቸው በየመዓርጋቸው ተቀመጡ ። ልክ በ፮ ሰዓት ሙሉ ግብር ሆነና ሰው ይገባ ጀመረ የካህናቱም አበዛዝ በማየት እንጂ በመስማት አይጠገብም ፡ የምግቡም ዓይነት ሁሉ በየመዕቡና በያውራጃው እንደሚገባ ተሠርቶ ነበርና ካህናቱ በየማዕርጋቸው እየተቀመጡ ተጋበዙ ። የካህናቱ ዋና ጋባዥም መምሕር ወልደ ማርያም ነበሩ ሲሳዩም እጅግ ብዙ ነበር ።

ከሁሉም ይልቅ ደስ የሚል ደግሞ የተጠጣው የማር ጠጅና የወይን ጠጅ ነው አረቄ የሚሉት ለሽታ እንኳን አልነበረም ካህኑም በልቶ ከጠገበ በኋላ በ፰ ሰዓት አጋፋሪዎቹ ማስወጣት ጀመሩ ። በልቶ የሚወጣና ለመብላት የሚገባ እንዳይገፋ የበሉት የሚወጡበት በር ለብቻው ነበር ፤ ካህኑ ሁሉ በልቶ ጠጥቶ እግዚአብሔርን እያመሰገነ ልዑል አልጋ ወራሽን እየመረቀ ለዘጠኝ ሰዓት ሩብ ጉዳይ ጨርሶ ወጣ ። የካህናቱ ግብር ካለቀ በኋላ በከተማው ያለ ድኃ ሁሉ በ፱ ሰዓት ወደ አዳራሽ ግብር ገባ ከሁሉ ይልቅ ድንቅ ነገር ሁኖ ይታይ የነበረ ደግሞ ድሀው በልቶ ከጠገበ በኋላ በማዕዱ የተረፈውን ብዙ እንጀራና ሥጋ እንደቻለ እየተሸከመ ሄደ ። ይኸም የጌቶቹ የቸርነት ፈቃዳቸው ስለሆነ ነው ። ድሆቹም ተመግበው ከጠገቡ በኋላ እጃቸውን ወደሰማይ እየዘረጉ ያመሰገኑት ምስጋናና የመረቁት ምርቃት ከብዛቱ የተነሣ ለመጻፍ አልተቻለም ፡ ግብሩም ከተፈጸመ በኋላ አሥር ሰዓት ሲሆን ልዑል አልጋ ወራሽ በብዙ መኳንንቶቻቸው ታጅበው ካዳራሽ ተነሥተው ወደእልፍኝ ገቡ ።

ይኸነኑ በዓል ከብዙ ጊዜ ጀምረው በዓመት በዓመቱ ደስ እያላቸው በልግስና ያከብሩታል ደግሞ ለሚመጣውም ዘመን ሁሉ እንደዚሁ በደስታና በልግስና እንዲያከብሩት

እድሜና በረከት ስጥልን እያልን ልዑል እግዚአብሔርን እንለምናለን ።

ጳጉሜ ፩ቀን ያዲስ አበባ ድሆች ልዑል አልጋ ወራሽ ከግምጃ ቤታቸው ያዘዙላቸውን ብዙ ገንዘብና ልብስ ሲቀበሉ ዋሉ ። «ለድኃ የሚሰጥ ለእግዚአብሔር ያበድራል ። »

ያገር ውስጥ ወሬ ።

ዘንድሮ በኢትዮጵያ ዝናቡና ፀሐዩ በልክ ለእህልና ለተክል እንደሚያስፈልግ ሁኖ ስለ ከረመ አዝመራውና ተክሉ ሣሩም በየገሩ እጅግ አምሯል ፤ በደጋ ያለ ገብስ ዘርዝሯል ባቄላ ፍሬ መያዝ ጀምሯል ። የቈላ እህል የቀደመው በስኋል ጤፉ ይታረማል ። እግዚአብሔር አምሮ የታየውን አዝመራ ፍሬውን በደኅና ተሰብስቦ ለማየት ያብቃን ፤

የውጭ አገር ወሬ ።

ከታይምስ ጋዜጣ የተተረጐመ ።

በሶስት ቀን ኤውሮጳን መዞር ።

ካፒቴን አራሻርና ሙሴ ክሮል ፈረንሳውያን በአየር መርከብ መብረር የሚችሉ ሰዎች ኤውሮጳን በሶስት ቀን መብረር እንጨርሳለን ብለው ተነሥተው በሶስት ቀን በኤውሮጳ ዙርያ በረው ተመለሱ ። ከፓሪ ተነስተው ክስታንቲ ኖፕልና (ቍስጥንጥንያ)ሞስኮ ደርሰው በጀርመን ሰንጥቀው በኮፐንሀገን ስለ ተመለሱ እጅግ ተመስግነዋል ።

የቤልጅክ ንጉሥና ንግሥት ።

ንጉሥ አልቤርትና ንግሥት ኤልሳቤጥ ወደ ህንድ ደርሰው ለመመለስ እንደ ማንም ሁነው ከብሩክሴል ተነሡ ።

ንጉሡ ራሳቸውም የመንገዳቸውን ነገር ያበጃጁ ነበር ፤ የሚያስፈልጋቸውም በእንግሊዝ መርከብ ተሰናድቶላቸው ነበር ፤ ንጉሥና ንግሥት ወደ ማርሴይ እመርከብ ይገባሉ ወደ ብሩክሴል የሚመለሱበትም በኦክቶብር (ጥቅምት) መጨረሻ ነው

የቦርኮሎ ከተማ አደጋ ።

በሆላንድ አገር በቦርኮሎ ከተማ ብርቱ ጎርፍ ጎረፈና ብዙ ጉዳት ጎዳ አራት ሰዎች ሞቱ ሁለት መቶ ቈሰሉ ፤

ርህሩህ የሆኑ የሆላንድ ንግሥት ውልሄልሚናና ፕሪንሴስ ጁሊያና ጉዳት ወደ ደረሰበት ቦታ ሂደው የቈሰሉ በተሰበሰቡበት ሆፒታል ገብተው ከንዳንድ ቍስለኞች ጋራ ተነጋገሩ የከተማው ሰዎች አምስት ሺ ናቸው ከነሱ ቤታቸውን ያጡ ሁለት ሺ ናቸው ። የከተማው ጉዳት ኪሳራው ሶስት መቶ ሺ ጊኒ ያህላል ባዚያ የነበሩ አንድ የፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያንና አንድ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ባጣም ተጎዱ አንድ ክፍ ያለ ታወር (ሰገነት)ደግሞ ጭራሽ ፈረሰ ።

በኢትዮጵያውያን ማኅበር ለሚቆመው ተማሪ ቤት እርዳታ እንሰጣለን ብለው ፊርማቸውን የሰጡ ሰዎች ። ከ፴፯ ቍጥር የመጣ ድምር ፭ የምስር ወርቅ ፯ሺ፯፻፸፭ ብር ተ፪ሩብ

ጣሰው አየለ ።	፪	ብር
ታፈሰ ገዛኸኝ ።	፲	ብር
መታፈሪያ አውግቸው ።	፪	ብር
ሞገስ ደስታ ።	፭	ብር
ተድላ አበበየሁ ።	፭	ብር
በቀለ አበየ ።	፪	ብር

ድምር ፭ የምስር ወርቅ ፯ሺ፰፻፩ ብር ተ፪ ሩብ

የፈላስፎች ቃል ።

በደስታ ለመኖር የሚፈለግ አንድ ነገር ብቻ አለ መልካምንና እውነትን መፈለግ ነው ሥራኅን ካሳመርክ በኑሮህም ደስ ይልሃል ። ረናን ።

መርሳት የምናውቅበት መጠን ልክ ያህል ደስ ይለናል ሴክሬታን

በሰውነት ታሪክ ውስጥ ያሉት ፲፪ቱ ሐዋርያቶች ብቻ አይደሉም ጉልማሳና ኃይለኛ ተወዳጅ ሆኖ የኖረውን ልብ ያህል አሁንም ይቆጠራል ወደፊትም ይቆጠራል ። ጉዮ

ባልንጀራህን ደስ ማሰኘትን የመሰለ ፍሥሐ የለም ማዳም ዴጊኔይ

ደስታ መልካም ከማድረግ ይገኛል ። አሪስቶት

በእድሜህ ሁሉ የውነተኛ ደስታህ ጊዜ የትኛው ነው? ለሌሎች ብለህ ራስህን የረሳህበት ጊዜ አይደለምን? ። አሌክሳንደር ቢኔት ።

ከሁሉ ይልቅ ደስታ የሚገኘው ከእድል በመስማማትና ሰው መሆንን በመውደድ ነው ። ኤራስም ።

ደስ የማለት ትልቁ ሞያ በመልካም የመኖር ሞያ ብቻ ነው ። ዱሲስ

ኀዘን የነፍስ ሞት ነው ደስታ ግን ሕይወት ነው ። ቢኒች

ከሰውነትህ ውስጥ የውነተኛ ደስታ ምንጭ ካላገኘህ ማለት የሕሊና ሰላምና የልብ ንጽሕና ። ከውጭ አገኛለሁ ብሎ መፈለግ ከንቱ ነው ። ማሲዮን

ደስታ ከማናቸውም ነገር ውስጥ ቢሆን ይገኛል ። ፈልጎ ማውጣት ግን የያንዳንዳችን ሥራ ነው ። ማርክ ኦሬል

ማስታወቂያ

ለራሶችና ለደጃዝማቾች ለሴት ወይዘሮች የሚገባ በያይነቱ ጥሩ ካባ ከኤሮፓ መጥቶልኛል ቤቱም (ባንክ ኦፍ አቢሲንያ) ከእንግሊዞች ባንክ አጠገብ ነውና ይህን ካባ መግዛት ለሚፈልጉ ሰዎች መጥታው እዲገዙ አስታውቃለሁ ። ኢያሱ ዳንኤል

በልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ

መጀመሪያ ዓመት ፤ ቁጥር ፴፰ ።
1re ANNÉE № 38

ሐሙስ መስከረም ፯ ቀን ፲፱፻፲፰ ዓ ም።
JEUDI 17 SePtembre 1925

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ፡ ይታተማል።
Hébdomadaire paraissant tous les jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

የጋዜጣው ዲሬክተር ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።
Gabré Christo Taklé Haymanot
Diréсteur

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ስለ ልዑል አልጋ ወራሽ ተማሪ ቤት ።

መስከረም ፩ቀን ልዑል አልጋ ወራሽ ከቤተ መንግሥት፡ ወደ ቤታቸው በተመለሱ ጊዜ የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ተማሪ ቤት አስተማሪዎችና ተማሪዎች ሰንደቅ አላማቸውንና የተጌጠ አበባ ይዘው በፊት በፊታቸው መዚቃ እየተመታ ተሰልፈው በ፲ሰዓት ተኩል ወደ ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ግቢ ገቡ ልዑል አልጋ ወራሽና ልዕልት ወይዘሮ መነን ካሉበት ቦታ እንዲገቡ ተፈቅዶላቸው ገብተው እጅ ነሡና አበባቸውን አበረከቱ፡ እንዲህ በማድረጋቸውም ልዑል አልጋ ወራሽንና ልዕልት ወይዘሮ መነንን እጅግ ደስ አሰኙዋቸው ። የዚያን ጊዜ ክቡር ሐኪም ወርቅነህ በእንግሊዝ ቋንቋ ተናገሩና አቶ ኤፍሬም ተረጐሙት ቃሉም ቀጥሎ እንደ ተጻፈው ነው ።

ለተወደዱ ደግ ሠሪያችን አልጋ ወራሽ ።

ልዑል ሆይ ።

እኛ የልዕልናዎ ተማሪ ቤት አስተማሪዎችና ተማሪዎች ፍቅርና ማክበር በተሞላው ልብ እውነተኛ ምርቃታችንን እንድናቀርብልዎና ደስታ መከናወንም የሞላው አዲስ ዓመት እንድንመኝልዎ ዛሬ ቀን መጥተናል ። ሁሉ የሚቻለው አምላክ ባለፈው ዓመት ከልዕልናዎና ከኛ ጠላቶች የተንኰልና የሰይጣን ምክር በደህና ጠብቆ እንዳሻገረዎ ዘወትር ይጠብቅዎ ። ያለፈው ዓመት ተማሪ ቤታችን ስለተከፈተበት መታሰቢያነቱ ጸንቶ ይኖራል ፡ ይኸም ተማሪ ቤት እንደ ክርስቲያንና ቅን ሰዎች ሆነን ኑሮዎችንና ባሕርያችንን የምናሳምርበት ነው እንጂ ትምሕርት ብቻ የምናገኝበት አይደለም ። የኛ የትሑታን አመስጋኞችዎና ያገልጋዮችዎ እውነተኛው ጸሎታችን ሁሉን የሚችል አምላክ ለተማሪ ቤታችን መስራች ከቤተ ሰባቸው ጋራ ረጅም ዕድሜና ደስታ ይስጥልን እያልን ነው ።

እግዚአብሔር ለኢትዮጵያ ነፃነትን ለንግሥታችን ሕይወትን ይስጥልን ብለው በጨረሱ ጊዜ ዳር እስከ ዳር በደስታ ከተጨበጨበ በኋላ መስፍን ቀለመ ወርቅ የተባለ ተማሪ ስለተማሪዎቹ ቀጥሎ የተጻፈውን ተናገረ ።

ልዑል ሆይ ።

እንኳን ዘመኑን በዘመን አደሰልዎ ርግብ ለምለም ቅጠል ይዛ መጥታ ለኖኅ የድኅንነት ወሬ እንዳወራችለት እንቍጣጣሽ ብለን በምናቀርበው አበባ የኢትዮጵያ የድኅንነት ዋና የምሥራች እንድናወራ እንለምናለን ። ፲፱፻፲፰ኛ ዓመተ ምሕረት የትምርት ቤትዎን መቆምና ሥራውን መጀመር አይታለችና የዓይነተኛው አዲስ ዘመን መጀመሪያ ሆና በኢትዮጵያ ታሪክ ዓመቶች ትቈጠራለች በርስዋ ውስጥ የዘሩትን የደግ ሥራ ዘር ፍሬ ወደ ሚለቅሙበት የመከር ጊዜ እንዲደርሱም ረጅም ዕድሜ እንመኝልዎታለን ደግሞም ይኸን ብርሃን ባገራችን የሚያሰፋ ሥራን ያስጀመረዎ ኃይሉ የማይወሰነው አምላክ ብርሃኑ እየሰፋ እንዲሔድና ኢትዮጵያን ወደፍጹም ሥልጣኔ ደረጃ እንዲያደርሱዋት ልዕልናዎን እንዲጠብቅልን እየተማለልነው ከክቡራን ቤተ ሰዎችዎ ሁሉ ጋራ በረከትና ደስታ ሰላምም እንዲያድልልን እንለምነዋለን ብዬ የተማሮቹን ምኞት ለማቅረብ ልዑል ፈቃድዎን እለምናለሁ ብሎ በጨረሰ ጊዜ ተጨበጨበ።

ተማሪዎቹም በሙዚቃ እየተመሩ በቃላቸው ባማረ ድምጽና በተስማማ ዜማ ዘመሩ።።መዝሙሩም ከአቶ ኤፍሬም ተወልደ መድኅን የተገጠመ ቀጥሎ የተጻፈው ነው ።

፭ ለኢትዮጵያ እናታችን ፡፡
ለነፃነት ትምክሕታችን ፡፡
ለሰንደቅ ዓላማ ኵራታችን ፡፡
እንምላለን መታመናችን ፡፡
፮ ንግሥተ ነገሥታት ግርማዊት
ጠብቅ አምላክ ዳዊት ፡፡
ልዑል የኢ መ አ ወ ተፈሪ ፡፡
ጠብቅ የዓለም ፈጣሪ ፡፡
፯ ፋከራችን ብርሃን እርነት ፡፡
ዓላማችን ፍርድ ቅንነት ፡፡
መማሪያችን ጥበብ ትምሕርት ብልሃት ፡፡
ምሽጋችን የግዜርን ፍርሃት ፡፡

መዝሙሩንም ሲጨርሱ ተጨበጨበላቸው ቀጥሎም ለተማሪዎቹ ሱካር ተሰጠ አስተማሪዎቹም ሻይ ተጋበዙ ፡፡ ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንንም ከዚህ በታች የተጻፈውን ያማረ ቃል ተናገሩ ፡፡

የተከልሁትን ተክል ዕውቀትን በማጠጣት የምትደክሙ መምሕሩን ክቡር ሐኪም ወርቅነህ ዋጋዎን የኢትዮጵያን ፍቅር ያደረጉትን በዚህ ዘመን መለወጫ የሚያብቡ ተማሪዎቹን መጽደቃቸውን ስላሳያችሁኝ አመሰግናችኋለሁ ፡፡

የተወደዳችሁ ልጆቼ ሕይወታችሁ ከመቃብር በላይ አለ ድረስ እናንተ እንዳመጣችሁልኝ ያይደለ አበባ ፍሬው የሚያጠግብ ዕውቀትን ነውና አበባ አድርጌ ያቀረብሁላችሁ እንዳይደርቅ ተግታችሁ ተምራችሁ ለሚመጣው ዓመት ፍሬያችሁን ለማየት አብሮ እንዲያደርሰን ምኞቴን አቀርብላችኋለሁ ብለው ከተናገሩ በኋላ ረጅም ጭብጨባ ተጨበጨበ አስተማሪዎቹና ተማሪዎቹ በዚያ የነበረ ሰው ሁሉም እጥብቆ ደስ አለው ፡፡

ከዚህ በኋላ ተማሪዎቹ መዝሙሩን ደገሙና ክስተማሪዎቻቸው ጋራ እንደ ቀድሞው ሙዚቃ እየተመታ በአጀብ ደስ ብሏቸው ወደ ቤታቸው ሄዱ ፡፡

ስለ ኢትዮጵያ ጥቅም ፡፡

መክበር መክበር ጌታ መሆን የማይፈልግ የማይወድ ሰው ምንም ቢሆን ሰው ሊያከብረው ክብረት በኃይሏ ልታከብረው ሰው ጌታ ሊያደርገው ወይም ጌትነት በግድ ጌታ ሁን ልትለው ምንም የማይስማማ ነገር ነው ፡፡

አስቀድሞ ሰውን ሰው እያከብረውም ሰውን ሰው ትልቅ እያደርገውም ይህም እርግጥ መሆኑን አንባቢ ከቅዱስና ከሊቃውንቶች መጽሐፍ ልብ እርጎ አስተዋይ ከወንድሞቹ እኑዋኑዋር ላይ ሊረዳው ይችላል ፡፡

የሰው ልጅ ክብረቱም ጌትነቱም አስቀድሞ ከእግዚአብሔር ቀጥሎም ከራሱ ዘንድ ነው የሚመጡለት ፤ ስለዚህ ማነው እግዚአብሔርን አዝዞ ዕገሌን ጌታ አድርግ ወይም ድኃ አድርግ ለማለት የሚችል? እንደዚሁም ሁሉ ማነው ወንድሙን በግድ ያለ ፈቃዱ ወይ ጌታ ወይ ድኃ ሁን ብሎ ለመያዝ መብት ያለው ይህን የመሰለ ሰው ቢገኝም እብድ ወይም አዕምሮ የጐደለው ሞኝ ይባላል እንጂ ትክክለኛ ሰው ሊባል አይቻልም ፡፡

በዚች ዓለም ያልተወሰኑ ክብረትና ጌትነት ለሰው ልጅ እንጂ ለሌላ ከቶ ላንዳች ፍጥረት ሰንኳ አልተሰጡም ሁሉን ባንድ አይቀር የፈጠረ አምላክ መሬትን እስከ ያዘችው ነገር ሁሉ ፈጥሮ ለሰው ልጅ መጠቀሚያ ሁኚ ብሎ ሰጣት እግዚአብሔር ሰው የተባለን ሁሉ በመሰሉ ፈጥሮ በደሙ አክብሮ የሥራዬ ክብር ሁኑ ብሎ ጠራቸው ፡፡

የሰው ልጆች ግን የፍጥረታችንን መሠረት ስናየው ደስ ሊለን ይገባናል ፤ ግን የሥራችንን ፍሬ ስናየው ከማህላችን ብዙዎች የመረረ እንባ ስናለቅስ ተገድደናል ፡፡ ከማህላችን ጥቂቶች ደግሞ በደስታ ላይ ደስታ ልንጨምር የተዘጋጀን በመሆናችን እድለኞች ነን ፡፡

ማነው በደስታ ላይ ደስታ ለመጨመር የታደለው ማነው ደስታውን ወደመከራ ለመለወጥ መጥፎ እድል የታደለው? የዚህ ምላሹ አጭር ነው ሁላችንም ያለአእምሮ የተፈጠርን የለንምና ሕሊናችንን ብንጠይቃት ያለኃፍረት በውነት ለየሁላችንም አይነታችንን ትነግረናለች ፡፡

የሀገራችን የብዙ ወንድሞቼን ሐሳብ ብመለከተው የክብረትንና የጌትነትን ዓይነት ምን እንደሆነ የማያውቁ መኖራቸውን አይቼ እጅግ አዘንኩ ላንዳንዶቹ ወንድሞቻችን ክብረት ከመኳንንት ተመንግሥት መቅረብ መተዋወቅ መሾም መሸለም ይመስላቸዋል ጌትነት ደግሞ የምድር የዐመፃ ንዋይ መሰብሰቡ ይመስላቸዋል ፤ ይህ ግን ትልቅ ስህተት ነው ስሕተት መሆኑንም እያወቀ ይህን በመሰለ ሐስብ የሚቆም በልቡ ትልቅነት የሌለው ነው ፡፡

መኳንንት ንጉሥ በቅብአ ሹመት አድገው ቢታዩ በባሕርያቸው ልክ እንደ ወንድሞቻቸው ሁሉ ናቸው እንጂ ክፉና በጎ የሚለዩበት ከንወድሞቻቸው የተለየ አዲስ አይነት ባህሬ እንደሌላቸው ለማወቅ ማንም ይሳነው አይመስለኝም ፡፡

መኳንንትና ንጉሥ እውነት ክፉና በጎ መለያ ልውጥ ባህሬ ቢኖራቸው መቸ አልሚና አጥፊአቸውን ሰው ቁም ነገሬምና ወሬዳ መለየት ያቅታቸው ነበር ፡፡ ሰው ገንዘብ በሰበሰበሽ ጌታ ይሆን ቢሆን መቶ ብር የሌለው ሰው መልከም በልቶ መልከም ለብሶ ነፍስና ሥጋውን ደስ አሰኝቶ ከመሰሉ ተፋቅሮ ሲቀመጥ ተሸህ ብር ይበልጥ ያለው ደግሞ መጥፎ በልቶ መጥፎ ለብሶ ተመሰሉ ሁሉ ተጣልቶ መች ይቀመጥ ነበር ፡፡

እንግዴህስ እንደኔ ሐሳብ ሞገስና ጌትነት ቀጥዬ እንደ ምጽፈው ይመስለኛል ፡፡ የሰው ሞገሱ ሀሊናው ያልናቀችው እንደሆነ ነው ፡፡ የሰው ጌትነቱ ሰው የተባለበትን እድል ጸጋ በስንፍናው ሳያጠፋ የተቀመጠ እንደሆነ ነው ፡፡ አለዚያ በከንቱ ብንኮራና ጌታ ብንመስል ባለቤቱ ያቀለለውን አሞሌ ባለዳ አይቀበለውም እንደሚባል ሁሉ በኅሊናችን የተናቅን በሥራችን የደኸየን በሰው ፊት ብንግደረደር ፍሬ የለውም ፡፡

ሕሊናችን እንደምን ትንቀናለች ጸጋችንንስ እንደምን እናጠፋታለን ? ሕሊናችን የምትንቀን በሰው ልጅ የማይገባ ሥራ ስንሠራ ነው ጸጋችንንም የምናጠፋ የምንሰራውን ሁሉ በሕግ በገባቡ ያልሠራን እንደሆን ነው ፡፡ ፍጻሜውን ወደፊት ተመልከት

ለሰው ልጅ የተገባ ሥራ ምንድነው ሕግ አገባብ ማለትስ እንዴት ነው ? ለሰው ልጅ የተገባ ሥራ ሀገር የሚአለማ ሕዝቧ የሚጠቅም በጠቅላላው ከፍርድ ያልተዛነፈ ሥራ መሥራት ነው

ሰው ሀገሩ እንድትለማ ሕዝብ እንዲጠቀም ፍርድ እንዳይጓደል አስቦ ከሠራ በሕሊናው ከመወቀስ በትክክል ይድናል ይህን የመሰለ ሥራ ሲሠራ እራሱን በመንፈሳዊና በሥጋዊ መንገድ አሳምሮ ይጠቅማል ። ማለት ለሀገሩ ሲሠራ ሀገሩ እንደሥራው ሚዛን ብትለማ ትርፉ ጥቅሙ ዞሮ ለሱ ነው እሱ ለወንድሞቹ ቢአስብ በተራቸው ወንድሞቹ ደግሞ ለሱ ያስባሉ ፍርድ እንዳይጓደል ቢጠብቅ የቀሩት ሁሉ ደግሞ እንደሱው ቢአደርጉ ጥቅሙ ዞሮ ለነሱው ነው ።

ለሰው ልጅ የተገባ ከባታችን የወረስነው ሥራ በግምብራችን ላብ ለፍተን መብላትን ነው ። በተፈጥሮአችን ልንጠብቅ የተገባን ዳኝነትን ነው ። እነኝህን ሁለት ነገሮች ደስ ቢለንም ባይለንም ልንጠብቃቸው የግድ አለብን (ኢትኩን ከመ ፈረስ ወበቅል እለ አልበሙ ልብ) ።

ሕግ አንባብ ። አገባብ መልካሙን ክፉ ክፉውን መልክም የሚአደርግ ነገር ነውና እሱን በርትተን ማወቅ መማር ያስፈልገናል ፤ ሁሉን ብንሰራ ሁሉን ብንሰበስብ አገባብ ካላወቅን ጥቅማችን ሁሉ በከንቱ ይቀራል ። ሰውነት ልብ ካላለ ዓይን አያይም እንደዚሁም አትአኑራችንን ልብ ብለን ካልተመለከትነው በደምብ መሄድ አለመሄዳችንን ለማወቅ አንችልም መሬት ብዙኅ ነገር ተሸክማለች ። ግን ሁሉ ላንድ ነገር አልተፈጠረም ሁሉም በየበኩሉ የሚአገለግልበት ነገር አለ በሰማይ ብዙሀ ነገር እናያለን ሁሉ ላንድ ዓይነት ሥራ አልተዘጋጀም ሁሉም በየበኩሉ የሚገባበት ቦታ አለ፡ምልክት ፀሐይ ጨረቃ ከዋክብት ። በንስሳም እረገድ እንደዚሁ ነው ለሚሳይ ለሥራ ሳራዊትነት የተፈጠሩ አሉ ሁሉም በየ በኩላቸው ለየተፈጠሩበት ነገር ይበጃሉ ። የሰው ልጅ ጐደሎ ፍጥረት ነው ግን ይህን ጐደሎነቱን በእውቀቱ የተሟላ እንዲያደርገው የእውቀት ኃይል ተሰጥቶታል ። የሰው እውቀት በእግዚአብሔር እውቀት ፊት ከለች አትቆጠርምና ሰው እተቻለው ድረስ እግዚአብሔርን እየፈራና እያመሰገነ በደምብ እየኄደ ጐዶሎነቱን መሙላት አለበት ። የሰው ልጅ ጎደሎነቱን መሙላት የሚችለው የእግዚአብሔርን ፈቃድ እየፈጸመ እግዚአብሔርን ሲከተል ነው ።

ሰው እንደምን አድርጎ ነው የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም የሚችል ቢባል፡ያንን የታዘዘበትን ሥራ ሲፈጽም ነው፡አለዚያም ከንቱ ነው ። ኢየሱስም « እግዚአ እግዚአ የሚለኝ አይደለም መንግሥተ ሰማያት የሚገባ ያባቴን ፈቃድ የሚፈጽም ካልሆነ በቀር» ብሏል።

ከኢትዮጵያችን ሁላችንም ባንድ አይነት ሥራ ላይ አልተቀመጥንም ሁላችንም እንደ እድላችንና እንደ ግምባራችን ብዙሀ አይነት ሥራ ይዘናል በየያዝነው ሥራ ላይ እተቀመጥን ድረስ ያን የያዝነውን ሥራ በርትተን ካልሰራነው ይህን ይዘን ሥራውን ሳንሠራ ወይ ዝም ብለን ብንቀመጥ ወይም ደግሞ ሌላ ሥራ ብንፈልግ ምንም እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት ልንሰራ የተገባንን ለመሥራት የተገባን አልሆንም።

ለመፍረድ እንዲመቻችሁ ባይኔም ያየሁትን በጆሮዬም የሰማሁትን ልንገራችሁ ። ብዙኅ ሕዝብ አሳዳሪዎች ሹማምቶች አሉ የተሾሙበትን ሥራ ትተው መጽሐፍ ሲደግሙ ከቀሳውስቶች ጋራ የሃይማኖትን ነገር ሲያወጡ ሲያወርዱ የሚውሉ ደግሞ ብዙ ቀሳውስቶች አሉ የቤተ እግዚአብሔርን ነገር እርግፍ አርገው ትተው የቤተ መንግሥትን ነገር እሚሠሩ ይህን የመሰለ ነገር ሀገርና ሕዝብን የሚጐዳ ለእግዚአብሔርም ደስ የማይል ነው ። መቼ መጽሐፍ በደገምሽና ጸሎት ባበዛሽ ነው የእግዚአብሔር ፈቃድ የሚፈጸም።የእግዚአብሔር ፈቃድ የሚፈጸም በዋሉበት ቦታ ጠብቆና የያዙትን ሥራ ሲፈጽሙ ነው ። ብዙ የሀገራችን መኳንንቶች ከጧት እስከ ማታ ዳዊት ሲደግሙና ጸሎት ሲያደርጉ ይውላሉ ። ልብ ብለው ቢመለከቱት ጌቶቻችን ዳዊትን ጸሎት ብለው ሊያዘወትሩ አይገባቸውም ነበረ ስለምን ማለት ዳዊትን እንደጸሎት አዘውትሮ ለመያዝ በትክክል የእግዚአብሔርን ሕግ ተከታይ መሆን ያስፈልጋል ። አለዚያ ዳዊት ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ደግ የሚሠራውን ሲመርቅ ክፉ የሚሠራውን ደግሞ ሲረግም ነው እሚታየው ። ደግሞ የሚረግም በሱ ላይ ክፉ የሚሠሩትን አይደለም ከውነት መንገድ የወጡትን ነው እንጂ፤ስለዜህ ምክንያት መኳንንቶቻችን በሁለት ፊት ተውነት መንገድ ተሳስተው ይገኛሉ ። መጀመሪያ የሕዝብ አሳዳሪ ሁነው ሳሉ የሕዝቡን በደል ሲያዩና ሕዝብ የሚጠቀምበትን መንገድ እንደ መፈለግ ያለሥራቸው ገብተው ከጧት እስከ ማታ የሃይማኖት ነገር ሲሠሩ ይውላሉ ።ይህ ተሆነ ሐሳባቸው ለምን ቄስ መነኵሴ ሆነውየቤተ ክህነት ነገር አይሰሩም? እንደነሱ አካሄድ ግን የጠጣ መነኵሴ መሆን ነው ማለት ሁለቱም እንዳይቀርባቸው በሁለቱም ወገን ሰውነታቸውን ደስ ለማሰኘት ይፈልጋሉ ። ግን ቢሆን እግዚአብሔር በጥበብ አይበለጥምና የሱን በላይነት ተረድቶ እሱን ደስ እንዲለው ማሰብ ይሻላል

ሁለተኛ ለእግዚአብሔር አሥር ጊዜ ዳዊት ከመድገም አንድ መልክም ሥራ ስለ እግዚአብሔር ብሎ ቢሠሩለት ይበልጥ ነበረ ። ጌቶቻችን በጸሎት እየተጠመዱ እየዋሉ በውስጣቸው ብዙ ግፍ ሲአሰሩ ይውላሉ ።እግዚአብሔር የግፍ ሠሪ አምላክ አይደለም የደግ ሠሪ እንጂ ።

እኛ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ሃይማኖታችን ከቡሉይና ከሐዲስ።መንግሥታችን ከሰሎሞን የተመሠረተ የመከበሪአና እራሱን የቻለ ጌታ መሆኛን መንገድ አጥተን ብንደናበር ብዙሀ ሰው ሳቀብን፤ብዙሀ ትንንሽ ሰዎች አዋረዱን ።

አሁንም ሁልጊዜ እንደተዋረድንና እንደተሳቀብን እንዳንቀመጥ ሁላችንም የኢትዮጵያ ልጆች ሁሉ እየተረዳዳንና ወደ ትምርሀት ፤ ወደ ሥራ እየተጋን የመከበሪአችንና የመጠቀሚያችንን መንገድ እንፈልግ ። ፍጻሜውን ወደፊት ተመልከት።የሰው ልጅ ምንም ባለ አእምሮ ሆኖ ቢፈጠር የተፈጥሮ ባህርዩን በትምህርት ካላራቀቀው ካላቃናው ሞገስና ብልጥግና የሚአገኝበትን ነገር ፈልጎ አግኚ ሊሆን የተገባ አይሆንም ። የትምህርትን ጣም የማያውቅ ዛሬ ከመሐከላችን ብዙኅ ሰው ይገኝ አይመስለኝም ። ቢገኙም ከቁጥር አይገቡ ። ከሽህ ባለጤና አስር በሽተኛ ቢገኝ አልቂት መጣ ተብሎ እንደማያስፈራ ሁሉ አይነት ነው ። ትምህርት ሁላችሁም እንደምታውቁት የሰው ልጅ ጉልበት ። የሰው ልጅ ጌጥ ነች ስለዚህ የሰው ልጆች ነንና ይህችን ትምህርት እንውደዳት እንፈልጋት ። እንደምን እንፈልጋት ብትሉ ሁላችንም እየተረዳዳን በኢትዮጵያ የትምህርት ቤት በማስፋት ነው ።

ሰማችሁ ኢትዮጵያዎች እንዴት ለልጅ ልጆቻችሁ የዘለዓም እፍረት ታቆዩአቸው ? ሁላችሁ የነገሥታት የመኳንንት የድኃ ዘሮች ሁሉ ባንድነት ሁናችሁ ስማችሁን ስታጠፉ፡ የሰሎሞን ዘር የማህለ ሥላሴ ልጅ የቃኘው እምበሳ ተፈሪ አባ ጠቅል ብቻውን ያላንድ እረዳት ለድፍን ኢትዮጵያ ልማትና ለድፍን ኢትዮጵያ ሕዝብ ጥቅም አስቦ የሁላችሁንም የመንፈሳዊና የሥጋዊ እውነተኛውን ምርቃትና በረከት ይውሰድባችሁ ።?

ለልጆቻችን በምናቆያቸው ታሪክ ተፈሪ መኰንን የነበሩበት ዘመን የምን ዘመን ነበር ይሉን አይምሰላችሁምን ? ሰማችሁ፡ ልብ ባንለው ነው እንጅ ብንመለከተውክ ተፈሪ መኰንንን በቁማቸው አጽድቀናቸዋል ። እኛ ሀገራችንን አለማገልገል ደማችንን አለማስከበር ። እራሳችንን አለመጥቀም ለተፈሪ መኰንን ሚዛን የሌለው የጻድቃኖች ዋጋ ሆኑአቸዋል፡

እበላ ባይ ይቀላምድ ይሆናል፤ያፍ ኩራት ባይሆንብኝ እኔ ግን እውነቱን እንደተቻለኝ እነግራችኋለሁ ። ሰው ዓለም በቃኝ አይልም እንጂ እንደ እውነቱ ቢሆን ለተፈሪ መኰንን ከእንግዲህ ወዲያ ያለው ዓለም ትርፍ ዓለም ነው እንጂ እውነተኛውን ዓለማቸውን ግን እስካሁን በደረጉት ሥራ ሁሉ ፈጽመውታል ። እድሜ ለብዙህ ሞኞች ወንድሞቻችን የልዑል ተፈሪ መኰንን ስም ግን ለሀገራችን የመልካም ታሪክ መጀመሻ ለውጭም አገር ሕዝብ ታሪክ የመልካም ነገር ምሳሌ መስጫ ሁኑዋል

እድል አይቀማ፤እድል አይገዛ። አሁንም ወደፊት እድሜ ለብዙህ ሞኞች ወንድሞቻችን የልዑል ጌታችን ወሮታ ስለ ኢትዮጵያና ስለ ኢትዮጵያ ሕዝብ ገና እንደ ጋራ እያደገ ይሄዳል።ለታሪክም ጸሐፊ ያጠግብ ይመስለኛል ።

የልዑል ጌታችን መልካም ሥራ ዋጋ በብዙህ ወንድሞቻችን ሞኝነት ነው ያደገው ፡ ማለቱ ፍችው እንዳይጠፋችሁ ትንሽ ላስረዳችሁ ። በጸሐይ ላይ መብራት ቢያበሩ ምንም አይጠቅም ጨረቃ በቀን ስትወጣ እንኳንስ ልታበራ መኖሯም አይታወቅ ለመብራትና ለጨረቃ ዋጋ የሚሰጥ ጨለማ ነው ስለሆነ ጨረቃና መብራት በፀሐይ ባይጠቅሙ በጨለመ ጊዜ መጥቀማቸው በግልጽ የታወቀ ነው ። እንደዚሁም ሁሉ ተፈሪ መኰንን በሠለጠነ አገር ላይ ተሰይመው ቢሆን ይህን ያህል ስማቸው አይጠራም ነበር በሰለጠነ አገር ላይም ንግሠው ሀገር የሚያለማ ሕዝብ የሚጠቅም ሥራ ባይሠሩ መንግሥታቸውን መያዝ ቀርቶ ዘራቸውን አስደበው ይቀሩ ነበር፡

ተፈሪ መኰንን የማህለ ሥላሴ ልጅ በኃይላቸው ወይም በመጥፎ መንገድ መንግሥት ልያዝ ብለው አልመጡም።በሐገራችን ተደርጎ የማይታወቀውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ለምኖና ትጠቅመናለህ ሀገራችንን ታለማለህ ደማችንን ታስከብራለህ ብሎ እንደ ነቢያቶች ተነብዮ አምጥቶ በኢትዮጵያ እናት ላይ ቁጭ አረጋቸው ። የዚህንም እርግጥነት ያወቅነው ደጃች በየነ የተቀጡ ለት ልዑል አልጋ ወራሽ ደጃች በየነ ባናደዱዋቸው ነገር የተነሣ ክቡር ፊታውራሪ ሃብተ ጊዮርጊስን አልጋ ወራሽነቱን እንደራሴነቱን ይያዙልን ብላችሁ ብትለምኑኝ አልፈልግም ብላችሁ አጥብቃችሁ ብትለምኑኝ ለጊዜው እሺ ለወደፊቱ ይታሰባል ብልም ለዛሬው እሺ ካሉን ለወደፊቱ አይሆንም ቢሉ እረዳለሁ ብለው አልማሉልኝም?ቢሏቸው ባደባባይ አዎን ብለው መሰከሩ ። የኢትዮጵያም ሕዝብ አሳብ በከንቱ አልቀረም ገና ታሁኑ ለኢትዮጵያ በሰሎሞን ጊዜ የተደረገላትን ክብር ባባዳኛው ጊዜ የተጀመረላትን ማዕርግ ተፈሬ መኰንን በብርታትና በትጋት ወጠኑትም ሰሩትም ።እንግዲህ ወዲህ የኢትዮጵያ ሰዎች ሁሉ ለእግዚአብሔር የተገባውን ምስጋና አቅርበን የማህለ ሥላሴ ዘር ይባረክ የልዑል ተፈሬ ዕድሜ ይርዘም እያልን ስለሐገራችን ልማትና ስለ ሰውነታችን ጥቅም ተባብረን ብንሠራ ነው እንጂ ጥቅማችን።እንዲያው በከንቱ ደመ ነፍስ ይመስል ሕይወታችንን በከንቱ ብናሳልፋት ምንድነው ጥቅማችን። ?

ከዚኽ የቀረ ቃል በሚከተለው ቍጥር ይታተማል ።

ሰ ሥ ሚ።

የከተማ ወሬ ።

ጳጉሜ ፫ ቀን ማታ ስለ አዲስ ዓመት መቀበያ ደስታ ያዲስ አበባ ሰው ሁሉ ችቦ እያበራ ሆሆ እያለ የደስታ ግጥም እየገጠመ ሲጫወት አመሸ። ከተገጠመውም ግጥም ጥቂት እናመለክታለን አበባሽ ላበባ፡አበባ እልል ብዬ ልግባ ።ኢዮሃ አበባዬ መስከረም ጠባዬ።አበቦች መስከረም ጠባች።አይዞሽ ነፍሴ ደረሰልሽ ገብሴ።

ጋሎች ደግሞ እንደ ቋንቋቸው እየገጠሙ ይጫወቱ ነበር በዚሁ ዕለት ቀድሞ ዘመን ልክ የሌለው ተኵስ ይተኰስ ነበር ። ዛሬ ግን አዋጅ ስለ ከለከለው ከተማው ሁሉ ፀጥ ብሎ ከጨዋታ በቀር ሌላ ነገር አልተሰማም ፡ ጨዋታውም በየቤቱ ነው እንጂ በሜዳና በጎዳና አልነበረም ። ነገር ግን ባንድ ሸለቃ ሰፈር ውስጥ የቀድሞውን ልማድ ይዘው አያሌ የጠመንጃ ተኵስ ሰማን ይኸንንም ዘበኞቹ የተኰሱትን ሰዎች በትጋትና በፍጥነት መርምረው ልኩን ሲያስታውቁን እንጽፋለን ።

ስለ አዲስ አበባ ዘበኞች

ባለፈው ሰሞን የግራዝማች አማረ ጭፍሮች የፊታውራሪ ደስታ ዳምጠውን በምባ የሠረቁትን ሌቦች ይዘው አሠሯቸው ።

ደግሞ ሌቦች ያንድ ነጋዴ ቤት ቁልፉን ሰብረው ከሰረቁ በኋላ እስከ እቃው ያዟቸው።

የደጃዝማች ወልደ ገብርኤል የልጃቸው አሽከር የደጃዝማች ወልደ ገብርኤልን ባለ ቀለህ ሸጉጥ ሰርቆ ሊሸጥ ይዞ ሲሄድ ዘበኞቹ ሌባ እንደሆነ አውቀው መርምረው ይዘው አሥረውታል ።ይኸነን የመሰለ ትንንሽ ነገርም ብዙ አግኝተዋል ።

ግራዝማች አማረም ለራሱ ተግቶ ጭፍሮቹን ስላተጋ ከንቲባው እጅግ አመስግነውታል ። እኛም እናመሰግነዋለን

የዘበኛው አለቆችና ዘበኞቹ እንዲህ ከጠነከሩ ሌባና ቀማኛ እንዲጠፋ የታወቀ ነው ።

ሌሎችም ሻምበሎች ደግሞ እንደዚሁ በትጋት የሠሩትን የሚያስታውቀን ስናገኝ እንጽፋለን ።

በልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ

መጀመሪያ ዓመት ፥ ቁጥር ፴፱ ።
1re ANNÉE №. 39

ሐሙስ መስከረም ፲፬ ቀን ፲፱፻፲፰ ዓ ም ።
JEUDI 24 SePtembre 1925

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን በገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d'Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraissant tous les jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

የጋዜጣው ዲሬክተር ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።
Gabré Christo Taklé Haymanot
Diréctéur

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ ሲገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements

Ethiopie	Etranger
Un an 5 Thalers	Un an 7 Thalers

le numero 2 piastres

ካለፈው ቁጥር የቀረ ።

ሰማችሁ።ግድ ባይዘኝ ይህን ሁሉ ባልጻፍኩላችሁ ፡ ግን ጭንቅ ከፉ ነውና የሀገራችን መጥፋት የሕዝባችን መበደል ይህን ሁሉ ነገር አጻፈኝ ። ብዙ ፈረንጆች ድኅነት እየስመረረቸው ሀገራቸውን እየጣሉ በሀገራችን ይመጣሉ እነኝህ የመጡ ፈረንጆች በሀገራችን ብዙ ጊዜ ሳይቀመጡ ባለ ብዙህ ሺህ ብርና ባለብዙ አሽከር ሆነው ሀገራችንን እንደመውደድ ሕዝባችንን እንደማመስገን ዞረው እንደውሽ ይንቁታል፤ ይህም እያለን በሞኝነታችን እንደሌለን መስለን ከነሱ በመገዛታችን የነሱን እጅ በማየታችን ነው ። እያለን ሠርቶ መብላት ሲአቅተን ጊዜ ልንሰደብ የተገባን ነንና አሁንም የሰው እጅና የሰው ስድብ መሮን አመላችንን ብንለውጥ በጣም መልካም ነው።ፍጻሜውን ወደፊት ተመልከት ።

በሰማይ ነፍሳቸው ይማርና ክቡር ነጋድራስ ገብረ ሕይወት መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር በሚባለው መጽሐፍ ላይ የተማረን ሕዝብ ባህልና ያልተማረን ሕዝብ ባህል አሳምረው ጥቅሙንና ጉዳቱን ሁሉ ጽፈውታል ትንሽ አእምሮ እንዳለን ከሱ ላይ ብቻ ብዙ ትምሕርት ልናገኝ እንችላለን ። እሳቸው እንደሚሉት ሁሉ የመንግሥት ጥቅሙ የሚገዛው ሕዝብ ስልጡን የተማረ ሲሆን ነው ። ጉዳቱም የሚገዛው ሕዝብ ትምሕርት የሌለው ሲሆን ነው ።

የኢትዮጵያ መንግሥት ይህን እስካሁን አሳምሮ ሳይረዳው አይቀርም ። እንኪያስ ስለምንድነው።ሕዝቡ የተማረ እንዲሆን አለማሰቡ ። አጼ ምኒልክ ይህን ነገር አሳምረው ተረድተውት በፈረንሣይ በእንግሊዝ በኢጣልያ ባረብ የተማሬ ቤት ከፍተው መኳንንቱም ልጁን እንዲያስተምር ማድረግ ጀምረው ነበር እሳቸው እቤት ቢውሉ በረጋም ሐሳብ የጀመሩት ሥራ ሁሉ በፍጥነት ተዘጋ ። እሳቸው እቤት ከዋሉ አንስቶ እፍረታሙ ቀን ድረስ የኢትዮጵያ የማደጊያና የመጠቀሚያ በር ሁሉ ተዘግቶ ሳለ የኢትዮጵያ አምላክ እንደገና የተዘጋውን በር ከፍቶ በሩ ሁሉ በመዘጋቱ የተነሳ ቂም በቀል የሚያደርገውን አጥፍቶ ድፍን ኢትዮጵያን አንድ አካል አንድ አምሳል ትንሽ ትልቁን ወንድማማች አድርጎ ሁሉን በደህና መንገድ አገባው ይህም አጼ ምኒልክ ምን ያህል ከብታም ። ንግሥት ዘውዲቱ ምን ያህል ባለ መልካም እድለኛ መሆናቸውን ያስረዳል ።

የሆነው ሆኖ ዛሬ በኢትዮጵያ የተማሬ ቤት እየበዛ እየሄደ የኢትዮጵያ ሕዝብ በትምሕርት እየሰለጠነ እየሄደ አጼ ምኒልክ የጀመሩት ሥራ ሁሉ እየሰፋና እየሰለጠነ እንዲሄድ ለማድረግ በጣም ሊተጉ የሚገባው ይልቁንም ለግርማዊት ንግሥት ነገሥታት ዘውዲቱ ምኒልክ ነበር ።

መንግሥታቸው ለሕዝቡ ሁሉ መማርያ የበቃ ተማሬ ቤት እንዳላወጣላቸው አይተው የኢትዮጵያ ልጆች በማህበር የትምሕርት ቤት ለማቆም አስበው እስከሆን ቢለፉ ይኸው የሚበቃ ገንዘብ ለመሰብሰብ አልቻሉም የኢትዮጵያ መንግሥት በገንዘብ አልደኸየ እንደምን ቢሆን ነው ሕዝቡ ይህን ያህል በትምሕርት ማጣት ተርቦ ሲአየው አይኑን ጨፍኖ እማያይ መስሎ መቀመጡ

ይህስ ለግርማዊት ንግሥታችንና ለልዑል አልጋ ወራሻችን ነገሩን ገልጾ እሚአመለክት ቢጠፉ እንደሆን ነው እንጂ እነሱስ ሰምተውት በህዝባቸው ጨክነው ዝም ይሉ አይመስለኝም ኢትዮጵያ እንኳንስ ለልጆቿ ለባዕድ አልፋ ትጠቅማለች እንደምን ቢሆንነው ለልጆቿ መማሪያ ተማሬቤት ማቆሚያ ገንዘብ እምታጣ

ይህን የመሰለ የፍረት ሥራ ለኛ ለዘመኑ ልጆችምንም አይቆጨንም ግን ባባቶቻችን ጊዜ ቢሆን በንደዚህ ያለ ነገር ጨክኖ ዝም የሚል ይገኝ አይመስለኝም ። እውነትስ አባቶቻችን የኢትዮጵያን ለዘለዓለም ለኢትዮጵያ ልጆች መሆኗ አይፈልጉ

ቢሆን በርግጥ ኢትዮጵያ እስከሁን ከባቶቻችን የወረስናት እርስታችን ባልሆነችም ነበር ።

አሁንም የኢትዮጵያ ልጆች ሁሉ በብሉይና በሐዲስ የተመሰረተ ሃይማኖት ይዘን ከብዙህ ሺህ ዘመን አንስተን በራሳችን ደም መገዛት የለመድን አእምሮ እንደሌለው ሕዝብና በራሳችን መገዛት እንዳለመድን መስለን መታየት ቀርቶ ያባቶቻችንን አመል ይዘን በሞገስ ላይ ሞገስ በጌትነት ላይ ጌትነት እያከልን እንድንሄድ ይሁን ሥራችን ሁሉ ።

ብናገር ብናገር መች ትሰማላችሁ። እርም ብየ እንዳልተው ወንድሞቼ ናችሁ ።

ሐገራችን መልካም እኛ ባለጤኖች ። ንግግር እንወቅ እንሁን ሠራተኞች ። ናሙስ የላቸውም የዘበኑ ሰዎች ። ሠርተን መና እንዳንቀር ነቃ በሉ ጌቶች ።

ሳለፈው እንቆጭ እንሞኝ ወደፊት ። ምን እንፈራለን እንሥራ ፊት ለፊት ።

ኢየሱስ ክርስቶስ ሞተ ለሰው ልጅ ሲል ። ትርፉም ለኛ በጅን ደሙ ሆነን እክሊል ።

ዮናታን ከባቱ ለዳዊት አደላ ። ጵርስቅላም ሠርታ ጴጋ አገኘች ተድላ ። ያገሮቼ ልጆች ተጴጋ እንዳንለይ ጠቅልን እንጥላ

አዲስ ብሑል ወጥቶ ሁሉ ተደነቀ ። ዲናም ታገር ጠፋ ፍርድም ረቀቀ ።

ሥራህን አትተው አትስነፍ ግድ የለም ። አጋጋርህ ብዙህ ነው ግፍ የሚወድ የለም ።

በዘርህ የታወቅህ በሥራህ ተወደድክ ። ባንተ ሁሉ ቀና እንኳን የተወለድክ ።

መንግሥታችን ይጥና ይጠንክር በጣሙ ። ነገራችን ይመር ይጎክ እንዳቅሙ ። ንብን ይወዳደር የሥራችን ጣሙ ።

ተጀምሮ እንዳይቀር የውበቱ ሥራ ። ፈጣሪ መርጦሻል ፋናው ላንቺ በራ ። ሪም ጉልት ስጭን እሮይ ቤት እንስራ ።

ተመልከች ኢትዮጵያ ክፉች አይኖችሽን ። ፈርመሽ ደግፈው በርግጥ ደጋፊሽን ።

ሬ ብሎ ይቅር በክፉ እሚመኝሽ ። መንገድ አስጠርጊ ለወጣት ልጆችሽ ። ኰፊያ እያስጣሉ እዚህ ያደረሱሽ ። ንቀው አይተውሽም ሁሉም ቢገዙብሽ ። ንቆሽም የመጣ ይወድቃል ከፊትሽ ።

ዘውዳችን አማረ ሰው ሁሉ ቀናበት ። ውሉን የማይረሳ ንጉሥ ምን አለበት ።

ዲና ሲሆን አገር ተፈሪ ሲታጣ ። ቱስህት ይሆንና እርፌትም አይመጣ ። ምንም አትዘግዩ ይንገሥ ከልጋ ይውጣ ። ኒቆዲሞስ ብርግጥ ለኛ ሲል የመጣ ።

ልክ የለው ጥበቡ ደግነት ያበዛ ። ክፍል ለሱ ሆኑአል ጠቅል እንዲገዛ ።

ሰ ሥ ሚ ።

ስለ አጼ መስቀል በዓል አከባበር ።

አጼ መስቀል መቼም ሲያያዝ እንደመጣው ታሪክ ባአጼ ዳዊት ዘመን አባይን መመለሻ መንገድ ፈልገው የማይገዙትን አንዳንድ ክፍል አገር አሸንፈው የመታረቂያውንም ዋጋ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከተሰቀለበት ከግማደ መስቀሉ አንዳንድ ወደሀገራችን ያመጡበት ቀን ስለ ሆነ ያጼ መስቀል ተባለ ።

ይኸውም በዓል ለኢትዮጵያ ነገሥታት ስለ ጌታችን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅር የሚያከብሩበት መታሰቢያ ቀን ሆኖ ጸንቶ ይኖራል ። ዛሬም በ፲፱፻፲፰ ዓመተ ምሕረት ያጼ መስቀል ዕለት ግርማዊቷ ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ብፁዕ እጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ሌላውም መኳንንቱ ሁሉ አዲስ በተሰራው ሰገነት ላይ ተቀምጠው የሥራው አኳሆን) ሁሉ እጅግ አምሮ ይታይ ነበረ ።

የአውሮጳ መንግሥት መላክተኞችም በልዑል አልጋ ወራሽ በስተ ቀኝ በኵል በተከበረ ቦታ ተቀምጠው ነበረ ሰው እረግቶ በየማዕርጉ ከተቀመጠ በኋላ የክህናቱ ሥራ ሲጀመር የቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ዲያቆን ስብከቱን እንዲህ ብሎ ጀመረ ።

ውእቱ አሚረ ይጠፍዕ ኩሉ ምክሮሙ ። ብፁዕ ብእሲ ዘአምላከ ያዕቆብ ረዳኢሁ ፡ ወትውክልቱኒ ላዕለ እግዚአብሔር አምላኩ ዝሉ ሰበከ ።

ከዚህም በኋላ ቄሱ ባማረ ድምጽ የሚገባውን ከተናገረ በኋላ በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ ፲ ፡ ቍጥር ፲፮ እላንተን የሰማ እኔን የሰማ ነው ፡ እላንተንም የናቀ እኔን የናቀ ነው ። እኔንም የናቀ የላከኝን የናቀ ነው ። እሊያም የተላኩ ሰዎች ደስ ብሏቸው ተመለሱ እንዲህም እያሉ አቤቱ ጌታችን አጋንንት በስምህ ተገዙልን።ጌታም ሰይጣን ከሰማይ እንደ መብረቅ ሲወድቅ አየሁ አላቸው እነሆ ሥልጣን ሰጥቻችኋለሁ እባቡንም ጊንጡንም ትረግጡ ዘንድ የጸላትንም ኃይል ታደክሙ ዘንድ ምንም የሚጐዳችሁ የለም ነገር ግን አጋንንት ቢገዙላችሁ ብቻ ደስ አይበላችሁ ። ስማችሁ በልበ እግዚአብሔር ስለታወቀ ደስ ይበላችሁ እንጂ።

በዚያችም ሰዓት ጌታችን እንዲህ አለ ። ሰማይን ምድርን የፈጠርክ አባቱ አመሰግንሃለሁ ይህቺን ምሥጢር አዋቂዎች ነን ከሚሉ ሰውረሃልና አላዋቂዎች ነን ለሚሉ ለሕፃናት ገልጸህላቸዋልና አባቱ ሆይ ፈቃድህ ሆናለችና ሁሉ ከንተ ተሰጠኝ እኔም ለወደድሁት እገልጽለታለሁ ወልድንም ያለ አብ አብንም ያለ ወልድ የሚያውቀው የለም ከዚኅ በኋላ ወደ ደቀ መዛሙርቱ ተመልሶ እላንተ ያያችሁትን የሚያዩ ዓይኖች ንዑዳን ክቡራን ናቸው እላችኋለሁ ። ብዙ ነቢያት ነገሥታት እላንተ ያያችሁትን ሊያዩ የሰማችሁትን ሊሰሙ ወደው ነበር ። ነገር ግን አላዩም አልሰሙም ።

በዚህ ዓለም የተሾሙ በእግዚአብሔር ፊት የሚያበሩ ሁለቱንም ዘይቶች ሊያጠፉቸው የሚወድ ሰው ቢኖር ከፉቸው እሳት ትወጣለች ጸላቶቻቸውን ታቃጥላለች እሳትም የተባለ ፍትሐ እግዚአብሔር ነው ደግሞ ማንም ሊበድላቸው ቢወድ ሞት ይፈረድበታል ። ራዕየ ዮሐንስ ም ፲፩ ቍ ፬ ።

እስመ ለዓለም ።

ነገሥት ክቡራን ደቂቀ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት እሉ ሰመዮሙ መድኅን አዕማደ ቤተ ክርስቲያን ነሰቱ አስዋኪ ረሲዓን ሜጡ ነፍሳተ ውስተ ዘበአማን መድኅን በኃይለ መስቀሉ አድከሙ ኵሎ ዘያስተቃርን ።

ከዚህም በኋላ ክህናቱ እጅግ ባማረ ድምጽና በተባበረ ቃል ሥራቸውን ሠርተው ሲጨርሱ አበባ ለመኳንንቱና ለሊቃውንቱ ለውጭም አገር መኳንንቶች ከተሰጠ በኋላ ግርማዊት ንግሥት ልዑል አልጋ ወራሽም ግብር ለማብላት ወደትልቁ አዳራሽ ገቡ ። አንባቢ ሆይ ከዚህ በላይ ያለውን ምስማክና ወንጌል ስታነብ ቃሉ ካለፈው ሥራ የተስማማ መሆኑን አስብ ባለፈው ዓርብ በመስከረም ፲ ቀን የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላቶች የልዑል አልጋ ወራሽ አስቀያሚዎች የሞት ፍርድ ስለተፈረደባቸው ፈጣሪያቸውን ለሚያምኑ ጌታችን ደህንነት ፣ ስለነዚያ ጥፋት አስበው አጣርተው ያወጡት ቃል መሆኑ ነው ከዚህም ቀጥሎ ስለ ታላቁ ስለ መስቀል በዓል እንድንጽፍላችሁ ተስፋ አለን ።

በልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ችሎት ላይ የተፈረደ የውነት ፍርድ ። ይኸውም የውነትን ፍርድ ለሚፈልግ ሁሉ ተስፋ የሚሆን ።

መስከረም ፯ቀን የወይዘሮ አልታየ ተነጋጋሪዎች ቀኛዝማች አምዴና ግራዝማች ወልዴ ዮሐንስ ፊታውራሪ ዘርፉ ደጃዝማች ስዩምን ከሰው ቀርበው የኑዛዜው ቃልና መነኮሴው የተጠየቁበት ቃል ይነበብ ብለው በመጀመሪያ የተነበበው የኑዛዜው ቃል ይህ ነው ፣ የወይዘሮ ዓፀደ ወይን ቃል በነፍስ አባታቸው ሲናዘዙ ። ለወይዘሮ አበበች ሺ ብር ለወይዘሮ ሮማን ወርቅ ሺ ብር ለምጽዋት ሺ ብር ለቀኛዝማች ወልደ ማርያም ልጆች ለወንዱ ልጅ አምስት መቶ ብር ለሴቷ ልጅ አምስት መቶ ብር ከዚህ የተረፈ ገንዘቤን በኮንትራት ተዋውለው የደንዲ ማርያምን ፣ አባባ የደበሩልኝን አሰርተው ከዚህ የተረፈ እንደሆነ ለታቦቷ አልባሳትና መጻሕፍት ይግዙበት ። የኔ ገንዘብ ያነሰ እንደሆነ አባባ ከፊሳቸው ጨምረው ይደብሩልኝ ለታቦቷ ዘበኛ ከኰንታ ከመጡ ሎሌዎች ከግሚራ ከመጧቸው አሥር በሮች ደኅና ደኅና መርጠው ከብረቱ አሥር ብረት አሲዘው ለታቦቷ ዘበኛ ሰጥቻለሁ ፣ ግራዝማች ወልደ ጻድቅ አንድ ጋሻ ግራዝማች አያኔ አንድ ጋሻ ባላምባራስ ሰጲሳ አንድ ጋሻ ባላምባራስ በላይነህ አንድ ጋሻ እነዚህን ከነመሚሪያቸው መርቄላቸዋለሁ መሬቱንም ደንዲ ማርያም ያግቡ ርስት አድርጌላቸዋለሁ ይኸንን ልጅ ያለው እንደሆነ ለልጁ ልጅ የሌለው እንደሆነ ለታቦቷ ይስጥ ከነዚህ የተረፈ አባባ የተከሉኝን ርስቴን ሁሉ ለደንዲ ማርያም ሰጥቻለሁ ክህናቱ ይተክሉበት ለነዚህ ለሥሩ ዘበኞች እንደ ክህናት አድርገው ርስት ይትከሉልኝ ። ደግሞ ክህናቱ እንደገቡ እንዳይቸግራቸው ለዘበኞቹም ጭምር ተከብቶቹ ውስጥ አንድ አንድ በሬ ይስጡልኝ እኔ ያልሁት ይህንን ነው ከዚህ ወዲያ አባባ ያውቃሉ ደጃዝማች ስዩም የሰጧችሁን ተቀበሉ ይኸንን እምጡ ይኸንን እምጡ አትበሏቸው ፣ ፈትል ድርና ማግ ያልተሠራ መርቄላቸዋለሁ ስጧቸው ። የሴት መሣሪያዬን ወይዘሮ አበበችና ወይዘሮ ሮማን ወርቅ ይክፈሉ ስዳር ተከትለው የሄዱት እሽከሮቼ ሙት አመቴን አውጥተው አወደዱበት ይኑሩ አሰናብቻቸዋለሁ ። ተኰንታ ከግሚራ ያመጧቸውን ሎሌዎች ልባት ዓመቴን አውጥተው እፈቀዱበት ይኑሩ አሰናብቻቸዋለሁ ለአባ መኰንን አንድ ጋሻ ይኸንን እርስት አድርጌ ሰጥቻቸዋለሁ ።

ቢሸጡትም ቢለውጡትም ግብሩን የወደዱትን ያድርጉ ጥንድ በሬ አንድ ላም አስር ዳውላ እህል የጡጢን ቤቴን የደንዲን መሬቱን አሉ ድረስ አትንኩባቸው የደንዲን ማርያምን አሉ ድረስ ስለኔ ሆነው ይኸ ከፋ ይኸ ለማ እያሉ ዋና ሆነው ይጠብቁልኝ ። አንድ ዳዊት አንድ ድርሳነ ሚካኤል አንድ ሰይፈ ሥላሴ አንድ ማኅሌተ ጽጌ ይኸንን ለነፍስ አባቴ ላባ መኰንን ሰጥቻለሁ ፣ ሲሞቱ ለደንዲ ማርያም ይስጡልኝ የቀረ ገንዘቤን ትልቁንም ትንሹንም ለደንዲ ማርያም አውርሻለሁ ይኸ የተናገርኩት ቃል ሚያዝያ በገባ ባምስት ቀን ያበለት ባ፲፱፻፲፫ ዓመተ ምሕረት የሚል ። ሁለተኛ ባላምባራስ ቸርነት አቶ መርሻ ግራዝማች ቆርቾ ቀኛዝማች ኃይሌ ሚካኤል ቀኛዝማች ሞላ ቀኛዝማች ኃይሉ ሊጋባ ወዳጆ ቀኛዝማች ክፈለው ፊታውራሪ አረጋይ አሉበት አባ መኰንን የተጠየቁት ቃል ከዚህ በታች እንደ ተጻፈው ነው ።

ወይዘሮ ዓፀደ ወይን እንደምን ተናዘዙ ቢሏቸው ሚያዝያ ፭ ቀን ረቡ እኔ እንኳን ተናዘዝ አላልኳትም ያን ዕለት ቆርባ ነበር ። ምነው አባቴ ተናዘጊ አትሉኝም አለችኝ እኔ ትሞቻለሽ ብዬ ተናዘዢ እላለሁ አልኳት ወዲያው የኑዛዜው ቃል ይጻፍ ብትል ። እኔም ሽማግሌ ተሰብስበ ነው እንጂ እኔ ብቻዬን አንድ ሰው እንደምን አድርጎ ያናዝዛል አልኳት ግድ የለም ኋላ ሲገለበጥ ሽማግሌ ይሰማዋል አሁን በረቂቅ ይጻፍ ብላ እኔም እሺ ብዬ በረቂቅ ጻፍን ። በማግሥቱ ሐሙስ ሐኪም መጥቶ አከማት ሰውነቷም ደከመ ። ደግሞ ዕሁድ ቆረበች እኔም ያንን ረቂቅ ይገፉ ሳለቅ ቆየሁ ሰውነቷ ሲሰጋ ሰንበተ ምነው ይህ ነገር እንደምን ይሁን ሰው ሰምቶት ተገልብጦ አልታተመ እንደምን ይሁን ብላት ። አሁን በጐ የሆንኩ እንደሆነ ተገልብጦ ይታተማል አለዚያም ይኸን የነገርኩዎትን ኑዛዜ ላባት ለናቴ ይንገሩ አያስተሩብኝ ቢወዱ ይያዙት ባይወዱት ይተውት አለችኝ ።

እስዋም በስድስት ሰዓት ጠፋች እኔም ያንን ያለችኝን ቃል አልተውም ብዬ እስዋም እኔም የጻፍነውን ባንድ ወረቀት በቀለም ገልብጬ ያንኑ ያርባ ዕለት ወስጄ አፈሰስኩላቸው እነሱም ሰምተው ዝም ብለው ሄዱ ብለው ተናገሩ ። እርስዎና እስዋ ረቂቅ የጻፋችሁ ጊዜ ሌላ ሰው የለምን ቢሏቸው ሌላ ሰው የለም እኔና እስዋ ነን አሉ ።

አሁን ደግሞ እንደምን ይሁን ብለው ቢጠይቋት ያቀርቶ ሌላ ተጽፎ ይታተማል አለች ያንኑ እረቡለት የጻፍኩት ተገልብጦ ይታተማል አለች ቢሏቸው ያንኑ እረቡለት እኔና እሷ በረቂቅ የጻፍነው ተገልብጦ ይታተማል አለች እንጂ ሌላም እጨምራለሁ ከዚያም እቀንሳለሁ አላለችም አሉ ፣ ያርባለት የኑዛዜውን ወረቀት በሁሉም መካከል አይደለምን ያነበቡት ቢሏቸው ወይዘሮ አልታዬም ደጃዝማች ሥዩምም ተቀምጠው በሁሉም መካከል ነው ያነበብኩት አሉ ፣ ቃሌ ነው ብለው ሄዱ ፣ ወይስ ቃሌ አይደለም ብለው ተዋውሰው ሄዱ ቢሏቸው ሁሉም ሰምተው ቃሉን ሰምተው ዝም ብለው ሄዱ እንጂ ቃሉ አይደለም ብለው መዋዋስም የለም አሉ ፣ ለርስዎስ ተናዛ የለም ቢሏቸው ጥንድ በሬ አንድ ላም አንድ ጋሻ መሬት ቀድሞም ይገፎው ነበር እሱን

እርስት አድርጋ ደግሞ አንድ ጋሻ መሬት አለሁ ድረስ ልበላ ሰጥታኛለች ብለው ከተናገሩ በኋላ ፊታውራሪ ዘርፉ ደጃዝማችን እንዳንከሳቸው ለማታለያ እንኳን ገንዘቡን ታከላቴም ብቆርጥላት አይቆጨኝም እያሉ ሁለት ሶስት ጊዜ ያተሙት ማህተማቸው አለ ብለው አቅርበው የተነበበው ቃል ከዚህ ቀጥሎ እንደተጻፈው ነው፤ ይድረስ ከመቤቴ ከናቴ ከወይዘሮ አልታዬ ለጤናዎስ እንደምን ሰንብተዋል እኔ በርስዎ ሐዘን በሥላሴ ቸርነት እግዚአብሔር ይመስገን ደህና ነኝ ለፊታውራሪ ገድል በቃል የላኩብኝ ደረሰኝ ይኸ ሁሉ የኔና የርስዎ አልነበረም እኔም በችግርና በሐሳብ መቀመጤን እመዬቴም ያውቁታል ለሁሉም ነገር የሚቻለኝን ነገር በጥቢው ለሁነኛ ሰው እልክለሁ የቀረውን ነገር እግዚአብሔር ባገናኘን ጊዜ እንነጋገራለን የሚል በነሐሴ ፳ ቀን በ፲፱፻፲፫ ዓመተ ምሕረት በቴሌግራም ወረቀት የተጻፈ በደጃዝማች ሥዩም ማህተም የታተመ ወረቀት ከተነበበ በኋላ ግራዝማች ወልደ ዮሐንስ እንደዚሁ ደጃዝማች ሥዩምና ወይዘሮ አፀደ ወይን ባልና ሚስት ሆነው ሲኖሩ ወይዘሮ ዓፀደ ታመው ቢሞቱ ያርባለት እመዬቴ ወይዘሮ አልታዬ ደጃዝማችም ቁጭ እንዳሉ እኝህ የንስሐ አባት ነኝ የሚሉት መነኩሴ ። የኑዛዜ ቃል አለ እኔና ደጃዝማች ሥዩም የጻፍነው ብለው ይኸን ማህተም የሌለበትን ወረቀት ቢያነቡ እመዬቴ ይኸስ ምንም አይደል ይልቅ እሷ በእጇዋ ጽፋ የሰጠችኝ ቅፈፍ መሳይ አለ ብለው ሰቀው ሄዱ

ከዚያም በኋላ ምነው ዝም አልከኝ ብለው እመዬቴ የላኩብቸው እንደሆነ ለገንዘቡ ነገር ግድ የለዎትም እንኳን ገንዘቡን ታከላቴ ብቆርጥላት አይቆጨኝም እያሉ ይኸው አሁን የተነበበውን ማህተም ሁሉ በማታለል እያተሙ ቆይተው ባልጋ ወራሽ ቃል ቢጠሩ ሶስት ሺህ ብር ላሸከራቸው ለፊታውራሪ ገድል ማህተም ጨምረው ይኸ ለቸገረ ጉዳይ ይሁንዎ በተረፈ እኔ ስመጣ ይሆናል ብለው ቢልኩ ያንኑም ሶስት ሺህ ብር ሌላ እንፈልግም ብላችሁ ተፈጠሙና ልስጣችሁ እንጂ እንዲህ ብላችሁ ካልተፈጠማችሁ አልሰጣችሁም ቢለን አፈ ንጉሥ ላይ ተቃርበን በብይን ሰጠን ደግሞ በኋላ እግልግል በሽማግሌ ገብተን አምስት ሺህ ብር በቁርጥ ትወስዱ እንደ ሆነ ውሰዱ አለዚያ ሌላ የምሰጠው የለኝም ብለው አፈረሱ አሁን እየጀመርከልኝ አድርሃልና ጨርስና የባልና ሚስት ገንዘቤን አከፍለኝ ቢል ከደጃዝማች ሥዩም ጋር አብሮ የቆመው ፊታውራሪ አስፋው ወይዘሮ አጸደ ወይንና ደጃች ሥዩም ባልና ሚስት ሆነው መኖራቸው እርግጥ ነው በመጀመሪያ ደጃዝማች ሥዩም ታመው ወይዘሮ አጸደ ወይን እናቴን አያለሁ ብለው ሂደው ወዲያው ቀሩ ደጃዝማች ታመው ሲድኑ እመይቴን አሟቸዋል ብለው ቢነግሯቸው እኔ እንደሷ አልጨክንም ብለው የሰሙለት እለቱኑ ድንኳናቸውን አስይዘው ሂደው እዚያው አጥር ግቢ ተክለው ተቀመጡ እሳቸውንም ግብቼ ልጠይቅ ያሉ እንደሆነ ሰውም አይገባም እያሉ ይከለክሏቸዋል ትንሽ ቆይተው ሞቱ።የርባለት ዳስ ሲፈርስ ዋንጫ ሲመለስ እመዬቴም እተቀመጡበት እመዬቴ ወይዘሮ አልታየ ኑዛዜ በቅፈፍ መሳይ ጽፋ ሰጥታን ነበር ፈልጉት ብለው ቢፈለግ ጠፋ ወዲያው እኝህ የንስሐ አባትየው አባ መኰንን እሱዋም በጇዋ ጽፋ እኔንም ያጻፈችኝ ወረቀት አለ ብለው አነበቡ ያን ጊዜ የልጇ ቃሏም አይደለም ብለው መዋዋስ የለ ።

ዛሬ ባምስት ዓመቱ የሰጡችሁን ተቀበሉ የሚል ኑዛዜ ነበርና ፫ ሺብር በፈቃዴ ለችግርዎ ጉዳይ ይሁንዎ ብዬ ብልከላቸው አፈንጉሥ ላይ ከሰው ተቀበሉኝ አገርም ስንገዛ የሷም አገር ለብቻዋ ተለይቶ ግምጃቤቷም ለብቻዋ ሆኖ ምስለኔ ግምጃቤት እሷው ሾማ እንደዚሁ ተለይቶ ይኖር ነበርና ያርባው ለት ግምጃቤቱን ከፍተው ያለውን እቃ ልቅም አድርገው በቅሎ ማይቀራቸው አስራ ሁለት ማለፊያ በቅሎ ለኔ የተናዘዘችልኝን የመቶ ሸማ ድርና ማግ፤ የዘጠኙን ሸማ ብቻ አሰርተው ሲሰጡኝ የቀረውን ገንዘብ ሁሉ ልቅም አድርገው ወሰዱ ያርባው ለት ኑዛዜ ሲፈስ ዝም ብላችሁ ሄዳችሁ እንጂ አልተዋዋሳችሁኝ በመንፈቅ ባመት አልተዋዋሳችሁኝ ዛሬ ባምስት ዓመቱ ተነጣጥሬ ገንዘብ ልከፈል ትለኛለህ አልገባም አላከፍልም ቢል ግራዝማች ወልደዮሐንስ እጥይቅ አግብቶ ። ተጠየቅ ደጃዝማች ሥዩምና ወይዘሮ ዓፀደ ወይን ባልና ሚስት ፍትና መንግሥት ሆነው አብረው ኖሩ ቢለው ፊታውራሪ አስፋው ባልና ሚስት መሆናቸውም እውነት ነው አለ ። ተጠየቅ ወይዘሮ ዓፀደ ሲሞቱ በደንቡ ጨዋ ተሰብስቦ አልተናዘዙም ቢለው ፤ መነኩሴው ያርባው ለት ኑዛዜ አለ ብለው አፈሰሱ እንጂ በማኝ በዳኛ አልተናዘዙም ሰው አይግባ ብላችሁ ከልክላችኋል አለ ፣ ተጠየቅ ይኸውም ኑዛዜ የምትለው ወረቀት ያርባ ለት ቢነበብ ወይዘሮ አልታዬ ወርቅ ዝም ብለው ሄዱ እንጂ የልጄ ቃሏ ነው ደረሰኝ ብለው አልተፈጠሙም ቢለው፤መነኩሴው ኑዛዜ አለ ብለው አንብበው ቃሏም ነው ቃሏም አይደለም አላሉም እንዲያው ዝም ብለው ሄዱ አለ ። ተጠየቅ ከዚያ ወዲህ ደግሞ ሁለት ሶስት ጊዜ በማታለል ለስዋ እንኳን ገንዘቧን ከካሌም ብቆርጥላት አይቆጨኝም እያልክ ማህተምህን ሁለት ሶስት ጊዜ አተምህ ቢሉት እመዬቴ አይቆጡብኝ እኔ በመጣሁ ጊዜ ይሆናል እያልኩ አትሚአለሁ አሉ እንጂ ገንዘብ አከፍላለሁ አላልኩም ደግሞ አንድ ጊዜ ሁለት ሺ ሁለት መቶ ብር አንድ ጊዜ ሶስት ሺብር እየላክህ ዝምረህ ቆየህ ቢለው ወይዘሮ ዓፀደ ወይንም ሲናዘዙ ደጃዝማች ሥዩም የሰጧችሁን ተቀበሉ የሚል ነውና በኑዛዜው የሙት ቃል እንዳያልፍብኝ ብዬ በፈቃዴ ሰጥቻለሁ አሉ።ከዚህ በኋላ ፊታውራሪ ዘርፉ ኑዛዜ የምትለው ባንድ መነኩሴ የተጻፈውን ወረቀት ነው እንደደንቡ እማኝ ዳኛ ተጨምሮ የተናዘዙችው ቃል የለም ያውም የኑዛዜው ወረቀት የምትለው ማኅተም የሌለበት ሌጣ ወረቀት ነው አንድ መነኩሴ ለራሱም ከመሬቱም ደጉን ከከብቱም ደጉን አድርጎ በናዘዘው ቃል አይረጋብኝም ያርባውም ለት ያንኑ ቃሌ ነው ብለው አልሄዱ ዝም ብለው ሰቀው ነው የሄዱት አልተዋዋሱኝም የምትለውም እንዳንዋዋስኸም እንኳን ገንዘቡን ታከላቴም ብቆርጥላት አይቆጨኝም እያልክ በማታለል ሁለት ሶስት ጊዜ ማኅተምኽን እያተምህ ነው ያቆየኸኝ በጨዋ በሽማግሌ አልተናዘዘችም ቃልክ ያንድ መነኩሴ ቃልና ያልታተመ ወረቀት እንዴት ይረጋብናል አንድ ጊዜ ሁለት ሺ አንድ ጊዜ ሶስት ሺ እየጀመርኸልን ከቆየኽ በተለሙ ያርሷል በጀመሩ ይጨርሱዋል ነውና የባልና የሚስት ገንዘባችንን ዘልቀህ አከፍል እንዲሉህ ዳለቻ ፈረስ እሰጥ አለ።ፊታውራሪ አስፋው ጥይቅ እዞሮ ሲጠይቅ።ተጠየቅ ያርባ ለት ዳስ ሲፈርስ ዋንጫ

ሲመለስ እመዬቴ ወይዘሮ አልታየ እተቀመጡበት ይኸው የኑዛዜ ወረቀት ተነበበ ቢለው ግራዝማች ወልደ የሐንስ መነበቡን ተነቧል አለ። ያን ጊዜ የልጇም ቃሏ አይደለም ብላችሁ መዋዋስ የለም ቢለው አልተዋዋስንም አለ ።

ተጠየቅ በመንፈቁም በዓመቱም አልተዋዋሳችሁም ቢለው በማኅተምህ እያሞኘኸን ቆዩህ አልተዋዋስንም አለ ደግሞ እመዬቴ ወይዘሮ አልታዬ ግምጃ ቤቱን ከፍተው ዕቃውንም አስራ ሁለት ማለፊያ በቅሎ ከጋጥ ወሰዱ ቢለው መውሰዱን ወስደዋል ደግሞ የቀረን አለን አለ ፤ ከዚሁ በኋላ ፊታውራሪ አስፋው ጨዋ አላናዘዘም ትላለህ ሰው እንዳይገባ ከልክላችኋል የመዬቴ የገዛ የንስሐ አባታቸው አናዘው ያውም ኑዛዜ ያርባ ለት ፈሰሰ ብልህ አምን ፈሱዋል አልክ ያን ጊዜ ኑዛዜው ሲፈስ የልጇ ቃሏ ይኸ አይደለም ብሎ መዋዋስ የለ ዝም ብላችሁ ሄዳችሁ ከተናዘዙልን እንኳን ከመቶ ሸማ ድርና ማግ ዘጠኝ ሸማ ነው የሰጣችሁን ግምጃ ቤቱን ከፍታችሁ እቃውንም በቅሎውንም ከጋጥ ወሰዳችሁ ብላችሁ ወስደናል አላችሁ አሁን የኑዛዜውን ቃል አፍርሳችሁ ከመጣችሁ ከልብሱም የቀረኝን በፈቃዴም የሰጠኋችሁን ገንዘቤንም መልሳችሁ ኑዛዜው በፈሰሰ ባ፭ ዓመቱ ለምን ትነጣጠረኝና ለኔ እንዲረጋልኝ ሰጋር በቅሎ አስጥ ብሎ ወድሮ ከዚህ በኋላ ለፈራጁ ግባቸውን ሲያሳዩ አስፋው ወስኔ የሚባለው ለደጃዝማች ሥዩም የቆመው ተሟጋች እንዲህ ሲል ውርድ ነዛ ወረቀቱ እንደቃሉ አይደምቅም እንጂ እጅግ ያስደንቅ ነበረ ።

በላ ልበልሃ መሠረቱን ። ያጤ ሥራቱን ። ያብርሃም ሕራቱን ፤ አልናገርም ሐሰቱን ፤ አልደብቅህም እውነቱን ፤

አለተፈሪ ንጉሥ ፤ አለከባ ልብስ ፤ አለጠቅል ፈረስ ።

አለ መኰንን ማን ወልዶ ፤ መድፉ ያደርጋልነዶ ። ሰገሌ እፋፋ ወርዶ ።

ሕዝቅያስ ነው አባቱ ፤ ሰናክሬም ነው ጠላቱ ። አይታገድም ክብቱ ለወዳጅ ለጠላቱ ።(አልኩሐ) እንዝርት የሌላት ሴት ፤ ጥፍር የሌላት ድመት ፤

ዝናር የሌለው ባሻ ፤ ድንበር የሌለው እርሻ ፤ የወሎዬ እናት ልንገርሽ ፤ እንዲህ አረጉልሽ ፤ ልጅሽ አበሻን ሲሻ ።(አልኩሐ)

አለዳዊት ጸሎት ፤ ከመንን ወዲያ ሴት ። አለሸዋ መንግሥት አለውጋርግሬ ብረት ፤ አለቢላም ሙክት አለ ዳኛ ሙግት ልፋት ነው መታከት (አልኩሐ) ። አስፋው ወስኔን የጠላ ዳኛ ፤ ዱላ የሌለው ቀማኛ ፤ በቅሎ የሌለው መልከኛ ፤ አሳዘነኛ አሳዘነኛ ።

አለተፈሪ መንግሥት ፤ አለአቡን ክህነት ፤ እሳት የገባ ጅማት ዝናብ የመታው ድብኝት ፤ ወልድን ፍጡር ማለት ፤ ሥጋ ትገባለች ከመሬት ፤ ነፍስም ትገባለች ገሃነመ እሳት ። እስመ ኰሉ ኃላፊ ፍጥረት ፤ (አልኩሐ) ። አስፋው ወስኔ ።

ከዚህ በኋላ ፍርድ ተጀመረ ከቋሚውና ከተቀማጩም ሁለት እጅ የሚሆነው ታክፍላለህ እያለ ፈረደ አንድ እጅ የሚሆነው አያክፍልም ኑዛዜው ይረጋለታል እያለ ከፈረደ በኋላ ከወምበሮቹ ባላምባራስ ቸርነትና ፤ አቶ መርሻ ፤ ባላምባራስ ኃይሌ ግራዝማች መንገሻ ። ግራዝማች ቆርቾ ባንድ ቃል ኑዛዜው የፈሰሰ ለት ካልተዋዋሉኝ አላክፍልም የምትሉት ለመዋዋሉስ ላለመዋዋሉስ በፊት በሽማግሌ በዳኛ በጸሐፊ እንደደንቡ ሁኖ የተክከለ ኑዛዜ መቼ ተገኘና ነው ።

እኚህ መነኩሴ ደጉን መሬት ደጉን በሬ የደንዲ ማርያምን እልቅና ለራሳቸው አርገው ነው አናዘገኩ የሚሉት ያውም የኑዛዜው ወረቀት እንኳን ማህተም የሌለው ደረቅ ወረቀት ነው ያርባም ለት ቢፈስ ዝም ብለው ሄዱ እንጂ የልጇ ቃሏ ደረሰኝ ብለው አልሄዱም ኑዛዜውም አባት እናቴ ቢወዱት ይያዙት ባይወዱ ይተውት የሚል ነው ይኸው እነሱ ቢጠሉት ነው መያዛቸው ደግሞም ሁለት ሶስት ጊዜ እንኳን ገንዘቡን ከካላቴም ብቆርጥላት አይቆጨኝም እያሉ አትመዋል ከብሩም እየዠመሩ ቆይተዋል የሚያስከለክል ኑዛዜ አልተገኘም ያክፍላሉ ብለው ፈረዱ ። ቀኛዝማች ኃይለ ሚካኤል ቀኛዝማች ሞላ ፤ ቀኛዝማች ኃይሌ ፤ ቀኛዝማች ከፈለው ፤ ፊታውራሪ አረጋይ ፤ ባንድ ቃል በሕይወቷ ያለች ሴት እንኳን ተባሏ ተጣልታ ስትሄድ ሳትዋዋስ ሄዳ በኋላ ቆይታ መጥታ ገንዘብ አክፍለኝ ብትል ለማክፈል አይሆንም እነኝህም ለደምቡማ የንስሐ አባትም ቢሆን ጨዋ ጨምሮ ይናዝዛል እንጂ ብቻውን ለማናዘዝ አይሆንም ይሁንና እኚህ መነኩሴ ያርባ ለት ኑዛዜ አለ ብለው ያፈሰሱ ጊዜ ሰምታችሁ ዝም ብላችሁ ከመሄድ የልጇ ቃሏም አይደል አንድ መነኩሴ ባናዘዘ አይረጋም ወረቀቱም ማህተም የለበትም ብላችሁ መዋዋስ ነበር መነኩሴውም ብቻቸውን ማናዘዛቸውን እያወቃችሁ ወረቀቱም ማህተም የሌለበት እንደሆነ ስታውት ዝም ብላችሁ ሳትዋዋሱ ሄዳችሁ ይሁንና በመንፈቁ አልተዋዋሳችሁ ባመቱ አልተዋዋሳችሁ ዛሬ ኑዛዜ በፈሰሰ በአምስት ዓመት አክፍሉን ትላላችሁ አያክፍሉም ብለው ከፈረዱ በኋላ ።

ልዑል አልጋ ወራሽ ።

ይኸነን ነገር የሚያስቀረውና የሚያስደርገውም ይሉኝታ ነበር የተሰጠም ለታቦት የተሰጠው አብራ ለኖረችው ባሏ ተብሎ ቢተውት በሆነ ነበር እንጂ አባትና እናቷ ይኸን ኑዛዜ እናፍርስ ሲሉ ልባቸውም የሚአውቅ እንደሆነ እርስዎ ወደ ሄደችበት ቦታ የሚሄዱናቸው እያወቁ እንኳ ከደጃዝማች ስዩም ወስደን ለማርያም እንሰጣለን ብለው ቢያስቡ እግዚአብሔር የማይታለል ዳኛ ነው ፤ ስለሆነም የተሰወረውን እግዚአብሔር ይግለጠው እንጂ በተገለጸው ነገር ቢሆን እግዚአብሔር ያፋታቸውን ባልና ሚስት ገንዘቧ ይቅርባት ለማለት ክፍንት ወገን የመጣው ምክንያት ኑዛዜ ሲነበብ ቃሏም አይደል ካላሉ ፡ ኑዛዜውን ቢያምኑ ነው ለምትሉት ፡ ይኸንን ባትል ታክፍል የነበረውን ፡ አንተስ ደጃዝማች ሥዩም ይቅርልህ ስትል ጊዜ ቃሏ ነው ብለህ አለ መፈጣጠምህ በሁለታችሁም ወገን ነገሩ እኩል መሆኑ ነው ልባችሁ ሌላ አፋችሁ ሌላ ሆኖአል ፤ በዚሁም ላይ ልጅቷ የጻፈችው ረቂቅ እንኳ ቢገኝ ይረዳ የነበረው አልተገኘ በመጨረሻም ልጅቷ ይኸንን ኑዛዜ አባት እናቴ ቢወዱ ይቀበሉት ባይወዱ ይተውት ብላለች ብለው ተናዛለች ባሉበት አፋቸው ቄሱ ከመሰከሩ ቄሱ ለራሳቸው የሚደርሳቸውን እንኳ ባይናገሩ ኖሮ በጠራጠረ ነበር መጽሐፉም ባንድ ምስክር ነገር አትቁረጡ ብሎ ከልክሎናል አንተም እስዋ ከሞተች ወዲህ ለቤተ ክርስቲያን ሥራና ለወይዘሮ አልታዬ ወርቅ በየጊዜው ሰጠሁ የምትለውን ገንዘብ እስዋም

በተለየ ግምጃ ቤት አሰርታ ገንዘቧ ለብቻዋ ነበር የሚኖረው ያተለየውን ሁሉንም የሚለየው የናንተው መዝገብ ነውና በዚያው ተሳስባችሁ ማካፈል ነው ተብሎ ፍርዱ በዚህ ተፈጸመ ።

ስለ ብርሃንና ሰላም ።

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ለሐገራቸው ልጆች እውቀት የሚመሩና ፍቅር የሚሰጥ ብርሃንና ሰላም የሚባል ጋዜጣ አውጥተዋል የሚሉ ወሬ ሰምቼ የእሥራኤል አምላክ አቆይቶኝ ምን ጊዜ አየው ይሆን እያልሁ ልቤ ብዙ ተስፋ አድርጎ ሳለ አቶ ወልደ ሰማዕት የሚባል ወንድሜ የሆነ ከወለጋ አዲስ አበባ ወጥቶ ነበርና የብርሃንና ሰላምን ታሪክ ለሰው ፍቅር የሚሰጥ መሆኑን አይቶ በወር በሁለት ወር ቢሆን በእግር ካልሄዱ በስተቀር ያዲስ አበባ ወሬ ተሰምቶበት ከማያውቀው አገር ወለጋ ድረስ የብርሃንና ሰላም ውጋጋኑ ይድረስህ ብሎ ጋዜጣውን በቦስጣ ልኰልኝ አየሁ ። ይኸውም ጋዜጣ ወለጋ ድረስ መምጣቱ ኢትዮጵያ እውቀት እንደተገለጸላት ሲያስረዳን ይመስለኛል ። የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪን እግዚአን ኢየሱስ በሰላም አቆይቶ ዘረው እንዳዩት እንደ አውሮፓ አገራቸውን ለማሰልጠን ያበቃልን ለማተሚያ ቤት ሠራተኞች ሁሉ ምስጋናየን አቀርባለሁ።አሁን የት ይገኛል እንዳት ያለ ተድላ፥ተፈሪ መኰንን የሐገሬ ባላ። ብርሃንን በፊትህ ሰላምን በኋላ። ለሚጨልመውም እንዲታየው ፋና፥ቂም ለማይዝም ሰው የሚያኖር በጤና ፥ እንዲህ ያለ ታሪክ አምጥተሃልና ፥ እድሜሓን ያርዝመው ተፈሪ በጠና ።

ወለጋ ሰዮ ደምሴ ወልደ ሥላሴ ።

ስለ ፍቅር ።

በብርሃንና ሰላም ብዙ ዕውቀት ያላቸው ሰዎች የጻፉትን ቃል ባየሁ ጊዜ ምሥጢሩን ተረድቼ ክቡሩን ወንድሞቼን ብዙ አመሰገንሁ ለነዚህም ለከበሩት ወንድሞቼ የዕውቀት ዝናም ሲዘንም እኔንም ፍጥረቱን ሁሉ በሚያጠላው ብርሃንና ሰላም በሚባለው በታላቁ ዛፍ ስር ተጠልዬ ሳለሁ ጠፈጠፉ ነክቶኝ ልጽፍ አሰብሁ ዳሩ ግን የጻፍሁት የፍርሃት ብርድ እያንቀጠቀጠኝ ነውና የጽሕፈት እጅ እግር ምሥጢሩ ረቂቅ አደለም ጉልህም አይባል ። ይልቁንም ብርሃንና ሰላምን ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻው አልተመለከትሁትምና ምናልባት ከኔ አስቀድመው የጻፉ ሰዎች የተናገሩትን ቃል ጽፌ እንደሆን ብዬ ነው ። ቢገኝም ብርሃንና ሰላም መርምሮ የነሱን ቃል ትቶ የኔን ብቻ እንዲጽፍልኝ በፍርሃት እለምናለሁ።በብርሃንና ሰላም የጻፉ ሰዎች ሁሉ የፍቅርን ነገር አምልተው አስፍተው ጽፈዋል ። እውነትም ፍቅርን የጠበቀ ምውታንን ከሚያነሡ ይበልጣል ብሎ እንደተነገረ የፍቅር ሥራ እጅግ ታላቅ ነው ሲሰሩት ከሥራ ሁሉ ያንሳል የመጣላት ሥራ ግን ብዙና ድካምና ችግር አለበት ድኅነትንም የሚያመጣ እሱ ነው ። እስኪ አሁን አንድ ሰው ከወንድሙ ጋራ ቢጣላ ቢሰድበውም ወደ ዳኛ ሂዶ ዕገሌ ሰድቦኛልና አስመጣልኝ ይለው የለምን ዳኛውም ቀላጤ የሚሆንህ ሰው አምጣ ይለዋል እሱም ሌላ ዘመድ እንዳለው ሂዶ ዕገሌን እከሳለሁ ብዬ ለዳኛ ብነግረው ቀላጤ የሚሆንህ ሰው አምጣ ብሎኛልና እባክህ ቀላጤ ሁነኝ ብሎ ሥራውን አስፈትቶ ይወስደዋል ፤ከዳኛውም ቤት ወይ አልተመቸም ይሉትና ሲመላለስ የሱ ሥራ መፍታት አንሶ የሚሠራውን ሰው ሥራ ያስፈታዋል ደክሞ ደክሞ ቀረቡ ብለውሃል የሚል ቃል ይዞ ሲሄድ ያ የሚከሰው ሰው ይደበቅና እሱን ሲፈልግ ብዙ ቀን ሥራ ይፈታል ።

ከገናውም ወዲያ ከዳኛው ዘንድ ተቋቁመው ሰደበኸኛል አልሰደብሁም እሰጥ ሲለው አፌን ይገዙ ይላል ። በሶስተኛው ቀን ከጠበቃዬ ይላል ። በስምንተኛው ቀን ጠበቃውን ይዞ ይቀርባል ከሳሹ ግን እውነት ይገርለሁ ብሎ ብቻውን ይቀርብና እንደመጀመሪያው ቀን እሰጥ አገባ ተባብለው ምስክር ይቆጥራል ብዬ አለኝ የለህም ሲባባሉ ያ ጠበቃ ያንን ከሳሽ ብዙ ዕዳ ያገባዋል የረታውም እንደሆነ ልሰራህ ሲለው አልገባም ይልና እሰጥ ተባብለው ወደ አፈ ንጉሥ ይመጣሉ የዳኝነትም ነገር ይኸው ዛሬ በልዑል ትጋት ቷንሽ ዓይን ሊያወጣ ጀምሯል እንጂ ቀድሞ ቢሆን እንደምታውቁት ያንድ ሰው ነገር በሰባት በስምንት ዓመት አይቈረጥም ነበረና ይህንን ያህል ቀን ጥቅም የሚያገኙበትን ስራ ትቶ ጥቅም ለማያገኙበት ነገር ለዳኛ ለጸሐፊ ለከልካይ ጉቦ ሲሰጥ ገና የሰው ገንዘብ አገኛለሁ ብሎ ገንዘቡን ይጨርሳል ወይም መጨረሻውን ካሳም የለህ ተብሎ ይመሰክርበታል በከንቱ ደክሞ ይቀራል። ቢከስ እንኳ ከባለጋራው ጋራ ሲሟገት ስራ ፈትቶ የበላውን ገንዘብ ለመክፈል የሚችል ገንዘብ አያገኝም በዚህም ላይ ዕገሌማ ካማ በልቶኝ እያለ ቢታሠር አያስፈታው ቢታመም አይጠይቀው ቢሞት አይቀብረው በዚህ ዓለም እንዲህ ሁኖ ኑሮ ኋላም ይህን ቃል ባፈረሰበት ተፈርዶበት ገሃነመ እሳት ይገባልና ይህ እስከመጨረሻው ብዙ ድካም ያለበት ነው ። ፍቅር ግን ከዚህ ከተናገርነው ነገር ሁሉ አንዳች የሚያደክም ነገር የለበትም ፍቅር ካለ ድኃና ባለጸጋ እኩል ናቸው ሰው ይውደድህ ደንጊያ ይጫንህ እንደሚሉ ሁሉ ገንዘብም ባይኖረው ድኃውን ባለጸጋው ያበላዋል ፍቅርን የያዘ ሰው አይሰስት አይቀና የራሱን ከመስጠት በቀር የሰው ገንዘብ አይመኝም ስለዚህ ብዙ ድካም ያለበት ፀብን ትተን ሳይደክሙ የሚገኝ ፍቅርን ገንዘብ እናድርግ ከዳኛ ብንሄድ እንኳ በርስታችን በሚስታችን ይሁን እንጂ በስድብማ ምን ያስሄደናል ። ወይ ስድቡ አንተ ጠቢብ አንተ ሠራተኛ ብሎ ይሆናል ይህ የሰዳቢውም የተሰዳቢውም ነገር ድንቅ ነው መጀመሪያ ሰው ሸክላም ሆነ ብረትም ሆነ ሸማም ሆነ በየዓይነቱ ሥራ ቢሠራ ማመስገን ትቶ መስደብ ይህ ከድንቁርና ይቈጠራል ። ዳግመኛ ይህ ሠራተኛ ማደሯዬ ብሎ የያዘውን ሥራ ቢነግሩት ሰደቡኝ ብሎ ከዳኛ መሄድ ድንቁርና ይመስላል (ይባላል) ይህን በስድብ የምንከሰሰውን ሥራ ትተን ተፋቅረን ሠርተን ብንበላ መልካም ይመስለኛል ።

እስካሁንስ ድረስ የሃገራችን ሰው ይህን ሥራ መሥራቱ አዋቂው አንሶ አላዋቂው በዝቶ ይመስለኛል ። አሁንማ በልዑል አልጋ ወራሽ መሠረትነት ላይ የማይናወጽ የትምሕርት ቤት ተሠርቶልን ብርሃንና ሰላም ተገልጾልን እንዴት ይኸን ክፉ ግዕዝ እንተውም ። ይህም ብርሃንና ሰላም ተብሎ የተጠራ ስም ከግብሩ የተለየ የበተከ አይደለም ። በመቅረዝ ላይ ያለች ፋና ከቤት

ላለው ሁሉ እንድታበራ እርሱም በሰው ልቡና ያለውን ምሥጢር ገልጾ የሚያሳይ ስለሆነ ስሙ ከግብሩ የተባበረ ነው እንጂ ። ማቴ ፬ ፲፮ ዳግመኛም ሕዝብ ዘይነብር ውስተ ጽልመት ርእየ ብርሃነ ዐቢየ ወለእለሂ ይነብሩ ውስተ ጽልመት ወጽላሎተ ሞት ሠረቀ ሎሙ ብርሃን ብሎ ነቢዩ ኢሳይያስ የተናገረው ትንቢት የተፈጸመበት ነው ።

እኔም ወሠረቀ ከመ ያርእዮሙ ብርሃኖ ፤ ለእለ ይነብሩ ውስተ ጽልመት ወጽላሎተ ሞት ፤ ከመ ያርትዕ ዕገሪነ ውስተ ፍኖተ ሰላም ። እያልሁ የምሥራች የምልበትን ቃል ከዚህ አ-ስከትዬ እጽፋለሁ ።

ብ | ርሃንና ሰላም ሰ | ለጠኑ በዓለም ።
ር | ሴት ተከሏቸው ለ | ሁለታቸውም ።
ሃ | ገሩን ተፈሪ ጠ | ቅልሎ ሁሉንም ።
ን | ግሥት መኳንንቱ ኑ | ረዋል በሰላም ።
ና | ሁ ሠናይ ጸንቶ በ | ናሁ አዳም ።
ሰ | ምተነው ስንኖር ዓ | የው ዓይናችንም ፤
ላ | ንት ይሁን ተፈሪ ለ | ክብር ስምህም ።
ም | ስጋና ልዕልና ም | ክርና ኃይልም ፤

እኔም ምንም እንግዴህ ተምሬ ሥራ ለመሥራት ባላደርስ ለወንድሞቼ በተደረገው ጥቅም ብዙን ደስ ብሎኛል።ወይሬእዩ ሠናያተ ዘትከውን ለከልአን ከመ ዚአሆሙ ይእቲ እንዲል። ስለዚህ የቅሜን ያህል በኢትዮጵያውያን ማኅበር ለሚቆመው የትምርት ቤት በመት በመቱ አምስት አምስት ብር ለመስጠት ፈቃዴ ነው ።

ሞገስ ዓምደ ሚካኤል ።

ማስታወሻ ።

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን በፊተኛው ዓመት የኢትዮጵያን ነጻነት ለመግለጽ ወደ አውሮፓ መሄዳቸው ዋና ጥቅማችን መሆኑን ተረድተነዋልና በየጊዜው ለመጻፍ አያስፈልግም ፤ ልዑል አልጋ ወራሽም ከአውሮፓ እንደ ተመለሱ ሌላውን ሁሉ በንጽፈው ሁለት ዋና ዋና ሥራ ሠሩልን መጀመሪያ ቀድሞ የኢትዮጵያን ፖለቲክ ፲፪ ሰዎች ብቻ ከንጉሡ ጋራ የሚደክሙበትን ዛሬ ማንም አገሩን የወደደ ኢትዮጵያዊ አሳቡን በብርሃንና ሰላም እንዲገልጽና አገሩን እንዲረዳ የጋዜጣ ቤት ከፈቱልን ። ሁለተኛ ለሥልጣኔ መከናወኛ የትምርት ቤት አቆሙልን ። ልዑለ ልዑላን ተፈሪ መኰንን የጥበብ መሪ የፍቅር መገኛ የደስታ ምንጭ የኃይል መታደሻ የክብር መመኪያ የምሕረት አባት የትእግሥት መሰብሰቢያ ምንም የሰይጣን ልጆች የኢትዮጵያ ጠላቶች ከቀና ሥራቸው ለማስተጓጐል ሁለጊዜ ቢጣጣሩ በእግዚአብሔር ኃይል ደገፋነት እውነተኛ ሥራቸው ያለመሠናከልና ያለማቋረጥ ወደፊት እየገፋ ይሄዳል ይሁንና ልዑል አልጋ ወራሻችን አውሮፓን ለመጎብኘት የኢትዮጵያን ባላባቶችና መሣፍንቶች ይዘው መሄዳቸው አገራችንን ተጋግዘን እንሥራ ማለታቸውን ያስረዳል ። ግርማዊት ንግሥታችንም ልዑል አልጋ ወራሽና መሣፍንቱ ከውሮፓ መንገዳቸው አዲስ አበባ በክብር የገቡ ለት በተናገሩት ዲስኩር ቸርነቱ የማያልቀው አምላክ እንዳያችሁት አገር ለሕዝባችን ጥቅምና ለሀገር ልማት በሚሆነው ነገር ሁሉ እንድታስቡበትና እንድትተጉ ያድርጋችሁ ማለታቸው መተጋገዝን ያረጋግጥልናል እኛም ከዚያ ወዲህ የትኛው አገረ ገገር ተማሪ ቤት ይከፍት ይሆን በየትኛውስ አውራጃ የሥራ መኪና (ፋብሪካ) ይቆም ይሆን ማንስ የልዑል ተፈሪ መኰንንን ፍለጋ ተከትሎ ሁለተኛ ይባል ይሆን እያልን በማሰብ ሐሊናችን ይወጣል ይወርዳል፡ወደፊትም እንደዚሁ ነው፡ነገር ግን ይህ መዘግየት በመጠባበቅና በመሮክከር ይመስላል መፈከከርና መዘግየት በኔም (በጸሐፊው ደርሶብኛል) በኢትዮ-ጵያውያን ማኅበር ለሚቆመው ተማሪ ቤት ለሚሰጠው እርዳታ ምናልባት ሺህ ብር መቶና ሐምሳ ብር የሚሰጡ ይኖራሉ በማለት እስከሁን ቆየሁ አሁን ግን እተቻለኝ ድረስ በያመቱ ፲፲ ብር ለመስጠት ቈረጥሁ እስከሁንም በመዘግየቱ የወንጌልን ቃል አቃለልሁ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዳመሠገናት ሴት የተቻለን ያህል ቶሎ ሰጥቶ መመስገንን ረሣሁ ስለዚህም ስሜ ከብዙ መሥመሮች በታች ሊጻፍ የግድ ሊሆን ነው ። ይህንም ስጽፍ አንድ ምሳሌን አስባለሁ በክፉ ቀን ሰውዮ የሙክት ስልቻውን ይዞ እህል ሊሠርቅ በጨለማ ሄደ።ሚስቱ ባሌ ሠርቆ የሚያመጣው ጤፍን ይሆን ዘንጋዳ ። ስንዴን ይሆን ገብስ አተርን ይሆን ባቄላ እያለች ስታስብ ባሏን የባለጠጋ ሎሌዎች ነቅተው ቂጡን በጨሬ ወግተውት ሲሮጥ መጥቶ እቤቱ ገብቶ እድው ብሎ ወደቀ፡ሚስቱም የሠረቀው እህል ከብዶት የጣለው መስሏት አንቱ ምን እህል ነው ያመጡት ብላ ብትጠይቀው እበክሽን ተዪኝ አንች የደላሽ እኔ ለራሴ ተወግቼ ነው የመጣሁት አላት እሷም ምን እበላ ብለሁ ነው ተወግተሁ የመጣሁት ብላ ተቈጣችው ይባላል የተወደደህ አንባቢ ሆይ ይህን ምሳሌ በኔ በራሴ ነው እንጂ በሌሎች የጻፍሁት አይምሰልህ (ማለት) ለተማሪ ቤት እርዳታ ያለ ገንዘቤን ለመስጠት ፈቃዴ ነበረ ነገር ግን ቤተ ሰዎቼን እንደፈራሁ አስብ ። አስታጥቄ ወልደ አማኑኤል ።

ስለ ሃገር ጥቅም ።

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ላገራቸው ሕዝብ ትልቅ ጥቅም የሚገልጹበት የጽፈት መኪና እንደሆነ በረቂቅ እውቀትዎ ስላሰቡ መኪናውን በፍጥነት አስ መጥተው በትጋትና በጥንቃቄ የሚያትሙ ሠራተኞች አቁመው መንፈሳዊና ሥጋዊን እውቀት ብርሃን የሚገልጹ ብዙ መጻ-ሕፍት አሳተሙ ። እኛም ኢትዮጵያውያን ባልጋ ወራሽ ማተሚያ ቤት የታተሙትን መጻሕፍትና ጋዜጣ ስናነብ ገና ይታተማሉን ስንሰማ ለማንበብና እውቀታችንንም በነሱ ለማስፋት ብዙ ናፍቆት ስለነበረን ጆሮቻችን ሰምቶ ዓይናችን ስላየው ልዑል ጌታችን ለኢትዮጵያ ሊገልጹት ያላቸውን ብርሃንና ሰላም እግዚአብሔር እንዲያስፈጽማቸው ብርቱ ተስፋ ስላለን ልባችን በደስታ ሞላ

ጋዜጣ ብዙ ዕውቀትና ጥበብ የሚገልጽ አብነት ነው ብዙ ያልታዩና ያልተሰማም ብልሃትና ሥራም ያስተምራል ስለ ዚህ የማይሰለች የኢትዮጵያ ልጅ በቋንቋውና በሌላ ቋንቋ የተጻፉትን ጋዜጣና ታሪክ ይልቁንም በቅዱሳት መጻሕፍት ያሉትን ታሪክ ዘወትር ቢያነብ እግዚአብሔር አምላኩን በፍጹም ልቡ በምሉ ኃይሉ እንዲያከብርና ንጉሡንና አገሩን እንዲወድ ያስተምሩታል ።

እግዚአብሔርን በመፍራት ንጉሡንና ሕዝቡን አጥብቆ የሚወድ ፍጹም ሰው ይባላል ። እኛም ኢትዮጵያውያን በጥበቡ

ወደተሠራ ደረጃ ለመውጣት ብንፈልግ አንድ ሕዝብ አንዲት አገር አንዲት ሃይማኖት አንድ ልብ ሆነን ልዑል እግዚአብሔር አምላካችን ጥቃታችንና ውርደታችንን ብናመለክተው ቶሎ እንዲሰማን አውቀን ልብ ሳንከፍል ወገን ሳንለይ በፍቅር አንድነት ሆነን ልንለምነው ይገባናል ። ፍቅር የዕውቀት ሁሉ ማሰሪያ ናትና በፍቅርና በማስተዋል የሚገዛ ንጉሥ በሚገዛው አገር ተወዳጅ ስለ ሆነ ሕዝቡ በፍቅር ይገዛለታልና ብዙ ኃይልና ሀብት እውቀትም ይበዛለታል በፍቅር ተስማምቶ የሚኖር ሕዝብ በዕውቀትና በኃይል እየጐለመሰ ሊያድግና ሊበረታ ኃይልም ሊያገኝ ይችላል ልዑል እግዚአብሔርም በፍጹም ልቡ በምሉ ኃይሉ የሚያመልከውንና እርሱ በርሱ በፍቅር የሚኖር ሕዝብን ሲያይ ብዙ ኃይልና ጥበብ ይጨምርለታል ።

ይግዛው ጎሹ



ስለ አለቃ ገብረ መድኅን ሞት መታሰቢያ ።

ያለቃ ገብረ መድኅን ሞት ለሞቱት አረፍት ለወዳጆቻቸውና በትምህርት ለወለዷቸው ጸጸት የሆነ ሐዘን ነው ። እኚህም አለቃ ገብረ መድኅን ትውልዳቸው ትግሬ የትልቅ ወገን ናቸው ።

ትምሕርት ለመማር ያልሄዱበት ሐገር ያልቀጸሉት መጻሕፍት አይገኝም፤ተምረውም አሳባቸውን ለማስተማር ከሰማሩት በኋላ ተማሪ የበዛላቸው ጉባዔ የሰፋላቸው መምህር ሆኑ ከማስተማራቸውም በሚተርፈው ሰዓት መጻሕፍትን ከግዕዝ ወዳማርኛ ይገለብጡ ነበር ከዚሁም የምናውቀው ቄርሎስ አረጋዊ መንፈሳዊ የገለመሩት ሃይማኖተ አበው ነው ሌላም ይኖራል ።

ከከተማ ውጭ ሆነው የወልድዋህድ ሃይማኖት መሠረት ግብረ ገብ ያራቱ ጉባዔ መጻሕፍት ምስክር መሆናቸውን ዳግማዊ አፄ ምኒልክ በሰሙ ጊዜ ካሉበት ደብዳቤ ልከው አስጠርተው ባዲስ አበባ ካሉት አድባራት አብልጠው ያሰሩትን የቅዱስ ጊዮርጊስን ቤተ ክርስቲያን አልቅና እንደ መምሕራን አክብረው ሾሙዋቸው እሺ ብለው ለጊዜው ፈቃድዎን ፈጽመው በሰባት ዓመቱ ሹመቱ ይብቃኝ ጉባዔ አይፈታብኝ ብለው ለቀቁ። ብዙ ጊዜ ሲያስተምሩ ቆይተው ፲፱፻ ዓመተ ምሕረት ኢየሩሳሌም ተሻገሩ።እግዚአብሔር ፈቃዱ ሁኖ እሳቸው ከኢየሩሳሌም ሲመጡ ጌታችን ልዑል አልጋ ወራሽ ደጃዝማች ተፈሪ ተብለው ሐረር ሲገቡ ተጋጠሙ ፍቅር የማይስበው የለምና በፍቅር ምክንያት ቆይተው ሳሉ ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ሐረር መካነ ሥላሴን ቈረቈሩ አለቃ ገብረ መድኅንን ሹመት ስንኳን ይኸን አዲስአበባ ጊዮርጊስን ለቀው እንደ መጡ ሰምቻለሁ ቤተክርስቲያኑን ያሰሩልኝ ካህናቱን ስርአተ ቤተክርስቲያኑን ያደላድሉልኝ ብለው ለመኑዋቸው።ከተደላደለበኋላ ሌላ ሰው እሾምበታለሁ ካሉኝ ቃልዎን አምናለሁ እሺ ብለው ሥራውን ተጀመረ ቤተ ክርስቲያኑ ሲሰራ ካህናቱ ሲሰበሰቡ የደከሙትንና የጣሩትን ድፍን የሐረር ሰው የሚያውቀው ነው ። ከልዑል አልጋ ወራሽም ጋር አባትና ልጅነታቸው የተማመነ ነውና መካነ ሥላሴን እንደሚገባ አደላድለው ጨርሰው አለቃ ገብረ ክርስቶስን አሹመው እሳቸው ትምርት እያስተማሩ እዚሁ አዲስ አበባ ለቸገረው ጉዳይ ሁሉ ሳይለዩ ከልዑል አልጋ ወራሽ ጋር ሲኖሩ ።ዘወትርም ሐሳባቸው ለትልቅ ሥራ ነውና ተድላ ሥጋቸውን ትተው ያባታችን ያቡነ ሳሙኤል መቃብር ያለበትን አሰቦትን ገዳም ለማቅናት ሄዱ አገሩን ማቅናት መነኮሳቱን መሰብሰብ ቤተ ክርስቲያኑን ማሠራት ጀምረው በመስከረም ፱ ቀን አረፉ ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን በመስከረም ፲፫ ቀን ተረዱ መኳንንቱም ካህናቱም ወይዛዝሩም ለለቅሶ ሲደርሱ ዋሉ ፤ ታላቅ ለቅሶና ኃዘን ሆኖ ዋለ ።

ብርሃንና ሰላም ልዑል አልጋ ወራሻችንን እግዚአብሔር ያጥናዎ ይላል ።

ማስታወቂያ

ለራሶችና ለደጃዝማቾች ለሴት ወይዘሮች የሚገባ በያይነቱ ጥሩ ካባ ከኤሮፓ መጥቶልኛል ቤቱም (ባንክ ኦፍ አቢሲንያ) ከእንግሊዞች ባንክ አጠገብ ነውና ይህን ካባ መግዛት ለሚፈልጉ ሰዎች መጥተው እንዲገዙ አስታውቃለሁ ። ኢያሱ ዳንኤል

አ ፔ ማርሲያኖ

የፊያት ኩምፓንያ የአቶሞቢልና የርሻ መኪና በኢትዮጵያ ዋና ወኪል ።



A . P . Marciano

Concessionnaire Ex . pour l'Ethiopie des automobiles et tracteurs Fiat .

በልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ

መጀመሪያ ዓመት ፤ ቁጥር ፵ ።
1re ANNÉE № 40

ሐሙስ መስከረም ፳፩ ቀን ፲፱፻፲፰ ዓ ም።
JEUDI 1 OCTOBRE 1925

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraissant tous les jeudis

Direction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

የጋዜጣው ዲሬክተር ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።
Gabré Christo Taklé Haymanot
Diréсteur

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ያከፍላል ። በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ስለ መስቀል በዓል አከባበር ።

የመስቀል በዓል አከባበር መስከረም ፲፯ ቀን በዋዜማው ደመራ ይተከልና የከተማው ሰው ሁሉ በአንድነት ተሰብስቦ ለበዓሉ ደስታውን ይገልጣል ። ይኸም ሥራት ከቀድሞ ሲያያዝ የመጣና በዓመት በዓመት የሚደረግ ሥርዓት ነው ።

ዘንድሮም በዚሁ ቀን ያዲስ አበባ ከተማ ሰው ሁሉ ይህን ከበዓል ለማክበር ብርሃን መስቀሉን ለማየት ከጧት ጀምሮ ጌጡንና ሕበባውን አሰናዳ መኳንንቱና ካህናቱ ወታደሩና ሕዝቡ ሁሉም ለማየት በየልቡ ይጓጓ ነበር እውነትም የዘንድሮ በዓል አከባበር እንኳን እዚሁ ሁኖ ባይን ለሚያየውና ከሩቅ ሁኖ በጆሮ ለሚሰማው ሁሉ እጅግ የሚያጓጓና የሚያስገርም ሆን ።

ስፍራውም ከቀድሞው ይልቅ ሰተት ባለ ባማረ መስክ በፍል ውሃ ሜዳ ነበረ ፤ ከሜዳውም መካከል ዕፁብ ድንቅ የሚባል ዓምድ ድንኳን ተተክሎ ነበር ፤ በውስጡ ደረጃ ደረጃ ተሠርቶ በላዩ ላይ የተዋበ የተዋበ ምንጣፍ ተነጥፎበት ነበር በድንኳኑ በር ግራና ቀኝ ሰንደቅ ዓላማ የሚሰቀልበት እንጨት ተተክሎ የሰንደቅ ዓላማችን ቀለም መልክ ባለው ሐር ተጠምጥሞ ነበር ። በድንኳኑ ፊት ለፊትም የደመራው እንጨት በወርቅ መጐናጸፊያ ተሸልሞ ቆሞ ነበር ።

ከ፮ት ሰዓት ጀምሮ የከተማው ሰው ሁሉ ወደ ፍልውሃ ለመሔድ በየመንገዱ ይንቄረቄር ነበረ ከሰዉም ብዛት የተነሣ መንገዱ አልበቃ ብሎት እየተጨነቀና እየተጋፋ በጎዳናው ሁሉ እንደ ውሃ ምላት ይጎርፍ ነበር ። ለ፯ት ሰዓት ሩብ ጉዳይ ሊጋባ ወዳጆ ከነጭፍሮቻቸው መጡና ሰውን ከሜዳው ሙልጭ አድርገው ከዳር ቆሞ እንዲያይ አደረጉት ። ፯ት ሰዓት ተኩል ሲሆን ሁለቱ ሰንደቅ ዓላማ ተሰቀለና እየተውለበለበ ሲያሸበርቅ ልባችን ትንቀሳቀስ ፤ ወዲያው ብፁዕ ዕጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ በአቶምቦል ከተፍ አሉ ። ከዚያ በኋላ የእያድባራቱ ሊቃውንቱና ካህናቱ የማእርግ ልብሳቸውን እየለበሱ ቀሳውስቱና ዲያቆናቱም መስቀልና ጥና እየያዙ መጡ ።

፰ት ሰዓት ሲሞላ ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ከዋናው ቤተ መንግሥት ወጡና በብዙ አጀብ ለደመራ ወደ ተሰናዳው ቦታ መጓዝ ጀመሩ የአጀቡ ብዛትና የጌጡ ማማር አበባ መስሎ ሲታይ እንደ ህልም ልብ ያበክን ነበር ልዑል አልጋ ወራሽም በወርቅ መረሻትና በወርቅ ዕቃ በተጨነቀች በቅሎ ተቀምጠው ወርቅ ጥላ ተይዞላቸው በከዋክብት መካከል እንዳለች የምላት ጨረቃ መስለው ደምቀው ይታዩ ነበር ።

በ፰ት ሰዓት ተ፳ት ሩብ ከሜዳው ደርሰው በድንኳኑ ውስጥ በተሰናዳው ከፍ ባለው ቦታ ከመካከል ላይ ተቀመጡ በቀኝ በኩል የውጭ አገር መኳንንቶች በየማዕርጋቸው ተቀመጡ ። በግራ በኩል ብፁዕ ዕጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስና ክቡራን የሀገራችን መኳንንቶች በየማዕርጋቸው ተቀመጡ ።

የየደብሩ ሊቃውንትና ካህናት ደመራውን ከበው ቆሙና የሚገባውን ሥርዓት አድርሰው ወንጌል ተነበበ መጨረሻውም «በወልድ የሚያምን የዘለዓለም ሕይወት አለው» የሚል ነው ቀጥለው ፵፩ እግዚኦታ አድርሰው ደመራውን ፫ት ጊዜ ዞረው ገለል ሲሉ ልዑል አልጋ ወራሽ ከነመኳንንቶቻቸው ሶስት ጊዜ ዞሩና ተመልሰው ከነበሩበት ቦታ ተቀመጡ ፤ ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ደመራውን ሲዞሩ ልዩ የሆነች ሰንደቅ ዓላማ እፊት እፊታቸው ተይዛ ትዞር ነበር ይህ ሁሉ ሲደረግ ፍቶግራፍ አንሺዎች ቶሎ ቶሎ ለማንሳት ያተፈትፉ ነበር ።

በ፱ ሰዓት ተሩብ ማህል ሰፋሪ (የንጉሥ ሠራዊት) የመስቀል አበባ የተጐነጐነበት የደመራ እንጨት ይዞ ሆ እያለ ሰልፉን እያሳየ ያልፍ ጀመር ።

ቀጥሎ የፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ሠራዊት ተሰልፎ ዞረ ከዚህ በኋላ ሁሉም በያለቃ በያለቃው እየተሰለፈ ዞረ ። በዚህ ሁሉ ሰልፍ መከከል የግቢ ሚንስትር ደጃዝማች ወልዱ ገብርኤል ባማረች በቅሎ ሁለት ጦር ይዘው አረንጓዴ ቡቅዳዴ አስረው አምረው ታጅበው ይሄዱ ነበር ።

ከዚህ ቀጥሎ ፊታውራሪ ደስታ ዳምጠው ፈረስ ዘበኞች አሰልፈው እሳቸው በመከከል ሁነው ባማረ ጌኔራሎች በሚቀመጡበት የወርቅ ኰርቻ ተቀምጠው አለፉ ።

ቀጥሎ ጸሐፊ ትእዛዝ ወልደ መስቀል ጭፍራቸውን ይዘው አለፉ ፤ በዚያ ውስጥ የኢትዮጵያ መንግሥት ማተሚያ ቤት ሠራተኞች ነጭ ለብሰው ሰይፍ ይዘው አምረው ታዩ ።

ቀጥሎ ፖስጣ ቤቶች እንደ ወትሮ ልማድ ተሰልፈው ዞሩ

ይህ ሁሉ ካለፈ በኋላ ያዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ነሲቡ ዛማኤል ሰልፍ ጥሩምባ እያስነፋ ብቅ ባለ ጊዜ የሰውን ሁሉ ዓይን ያቅበዘብዝ ጀመር በፊት የፈረስ ሰልፈኛ ነጭ ከት ለብሶ ፈረሱን በደንብ እያስሄደ ጡሩምባ እየነፋና ሰላምታ እየሰጠ ግሩም እየተባለ አለፈ ። የማዘጋጃ ቤት ሙዚቃ መቾምችም ሠራዊቱ እስኪያልፍ ድረስ ሙዚቃ ይመቱ ነበር ። ቀጥሎ ካኪ የለበሰ ወታደር በደንብ ሰልፉን እያሳየ ሰላምታ ሰጥቶ ካለፈ በኋላ ብዙ ልጆች እንደ ዘበኛ ለብሰው ልዩ አይነት ባርኔጣ አድርገው እንደጠመንጃ ሁኖ የተሠራ እንጨት ይዘው ሰልፋቸውን ባሳዩ ጊዜ ጉድ ተባለላቸው ። ቀጥሎ የማዘጋጃ ቤት ጸሐፊ ሁሉ ነጭ ለብሶ ነጭ ባርኔጣ አድርጎ እየተብለጨለጨ በየማዕርጉ ተሠርቶ በከንቲባውና በድረክተሩ ፊት ፊት ብቅ አለ ።

ክቡር ከንቲባ ነሲቡና ክቡር ነጋድራስ አስታጥቄም ለየመዓርጋቸው እንደሚገባ እንደ አውሮጳ ሹማምት አለባበስ ነጭ ልብስ ለብሰው በፈረስ በፈረስ ተቀምጠው ሰይፋቸውን መዘው እንደሚገባ ሰላምታ በሰጡ ጊዜ መላው ሕዝብ ተደንቀ እጅግ አድርጎ ውበትና ማማርም ተሰጥቷቸው ነበር ። ይልቁንም ለኢትዮጵያ መኳንንት እንደዚህ ያለውን መልከም ሥራ ስላሳዩና አብነት ስለሆኑ መኳንንቱና ሕዝቡ እጅግ አድርጎ አመሰገናቸው ።

ሰልፍ የተማረ የከንቲባ ጭፍራም ፫ ሺ ያህል ነው ።

ከዚህ ቀጥሎ የሥራ ሚንስትር ጭፍራ ተሰልፎ አለፈ ። ቀጥሎ የቀኛዝማች በየነ ሀብተ ማርያም ጭፍራ ተሠልፎ አለፈ ።

ቀጥሎ ያራ ንጉሥ ከተማ ጭፍራ ተሰልፎ አለፈ ።

ቀጥሎ የሊጋባ ወዳጆ ጭፍራ ተሰልፎ አለፈ ።

ቀጥሎ የእጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ጭፍራ ተሰልፎ አለፈ.

፲፩ ሰዓት ሩብ ጉዳይ ሲሆን የልዑል አልጋ ወራሽ ሠራዊት ቀረበና ወርዋሪ የተባለ የፊታውራሪ መንገሻ ይልማ ጭፍራ ዝግ ብሎ አምሮበት አለፈ ።

ቀጥሎ የባላምባራስ ገብረ ሥላሴ ጭፍራ እንደዚሁ አለፈ ።

ቀጥሎ የበጅሮንድ ሰብስቤ ጭፍራ ተሰልፎ አለፈ ።

ቀጥሎ የፊታውራሪ ኃይሌ ጭፍራ ተሰልፎ አለፈ ።

ቀጥሎ የልዕልት ወይዘሮ መነን ሠራዊት በቀኛዝማች ሀብተ ጊዮርጊስ እግር አለፈ ።

ቀጥሎ የቀኛዝማች ታደሰ (በጅሮንዱ) ጭፍራ ተሰልፎ አለፈ

ቀጥሎ የግራዝማች ሽመልስና የባላምባራስ ለጥ ይበሉ ጭፍራ ተሰልፎ አለፈ ።

ቀጥሎ የባልደራሶች ጭፍራ ተሰልፎ አለፈ ።

በመከከል ፊታውራሪ ገብረ ማርያም የወርቅ ጦር እንደያዙ እምቢልታና መለከት እየተነፋ አለፉ ።

ቀጥሎ ሰልፍ የተማረ የግራዝማች ገብረ ዮሐንስ ጭፍራ በፊቱ ሙዚቃ እየተነፋ የሥልጣኔ አካሄዱን ያሳይ ጀመር ። አረማመዱም በጣም የተስማማ ነበር ፤ ይህ ሁሉ ሲሆን ሙዚቀኞቹ ከመከከል ቁመው ሙዚቃ ይመቱ በዚህ መከከል ያልጋ ወራሽ ተማሪ ቤት ተማሪዎች ልዩ ሰንደቅ አላማ በፊታቸው አሲዘው በፊት በፊታቸው ሙዚቃ እየተነፋ አንድ አይነት ልብስ ለብሰው የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ ተማሪ ቤት ተማሪ የሚል ጽሬት ያለበት ባርኔጣ አድርገው ቀርበው ሰላምታ ሰጡ ። ከተማሪዎቹ በኋላ የልዑል አልጋ ወራሽ መትረየስ አንጋች ዘበኛ ነጭ ነጭ ሱሪ ታጥቆ ሰማያዊ ከት ደርቦ መትረየሱን አንግቶ በጠገበ በጠገበ ፈረስ እያናጠረ ብቅ ብሎ ሰይፉን መዞ ሰላምታ በሰጠ ጊዜ ሰውን ሁሉ ከሰማይ እንደ ወረደ መብረቅ ዓይኑን እንጸበረቀው ። አቶ መኰንንም በጥቂት ቀን እንዲህ አድርጎ ስላሰለጠነ ሕዝቡ ሁሉ አመሰገነው ።

በኋላቸው እግረኞቹ ዘበኞች ሰልፋቸውን አሳይተው አለፉ ። በኋላ ፊታውራሪ ወልደ አማኑኤል እጅግ አምረው ታጅበው አለፉ ። ቀጥሎ የግራዝማች ከልክሌ ጭፍሮች የተማሩ ዘበኞች አምረው ተሰልፈው አለፉ ። ከዚህ በኋላ እነዚያ እንግት መትረየስ የያዙ ፈረሰኞች አልጋ ወራሽ ወደአሉበት በቀረቡ ጊዜ ሰልፍ የተማረ ዘበኛ ከባቢ ሆኖ ከሜዳው ላይ ከድንኳኑ ፊት ለፊት ተሰልፎ ሲታይ ወታደሩ ለምለም ቅጠል ፤ በሰው እጅ ተይዞ የነበረ ሰንደቅ አላማ ሁሉ ያማረ የመስቀል አበባ መስሎ ነበርና ማየቱ ለዓይን የሚያስጐመጅ ስለሆነ በዚያ የነበረ ሰው ሁሉ አንድ ጊዜ ቢያጨበጭብ ፈረሱ ሁሉ ይጨፍር ጀመር ። ከተጨበጨበ በኋላም ሙዚቀኞቹም ያማረ ዜማ በሙዚቃ አዜሙ ።

፲፩ ሰዓት ተሩብ ሲሆን የውጭ አገር መኳንንቶች እየተሰናበቱ ሄዱ ።

ከዚያ በኋላ ያልጋ ወራሽ ዘበኞችና ተማሪዎች ወደ ልዑል አልጋ ወራሽ ቀረቡ ፤ ልዑል ከበቅሎ እስኪወጡ ድረስ ሙዚቀኞቹ ያማረ ዜማ ያዜሙ ነበር ።

ልዑልም ከዚያ ወደ ቤተ መንግሥት ሲመለሱ በፊታቸው ተማሪዎች ግራና ቀኝ መትረየስ ዘበኞች ከክቡራን መኳንቶቻቸው ጋራ ሁነው በሚያስደንቅ አጀብ በፊት በፊታቸው ሙዚቃ እየተነፋ ወደ ታላቁ ቤተ መንግሥት ገቡ እንደዚህ ሁኖ የበዓሉ አከባበር በደስታ ተፈጸመ ።

ምንም ወደፊት የምናስበውና ተስፋ የምናደርገው ከዚህ የበለጠ ቢሆን ዘንድሮ ትልቅ ነገር አየን ለማለት እንችላለን ።

ብርሃንና ሰላም ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ለልዑል አልጋ ወራሽ ለወዳጆቹም ሁሉ ለሚከተሉት ዘመናት የበለጠ ብርሃን እየተመኘላቸው እንኳን ብርሃነ መስቀሉን አሳያችሁ ይላል ።

መስከረም ፲፯ ቀን ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ከቤተ መንግሥቱ ወደ ቤታቸው በገቡ ጊዜ አሥር ሰአት ተኩል ሲሆን የልዑል አልጋ ወራሽ ተማሪ ቤት ተማሪዎች በሥርዓት ለብሰው በሚገባ ሠልፍ ሁነው ሰንደቅ አላማቸውን ይዘው ክቡሩ ሐኪም ወርቅነህና አስተማሪዎቻቸው ይዘዋቸው ወደ ልዑል አልጋ ወራሽ ግቢ ገቡ ልዑል አልጋ ወራሽና ልዕልት ወይዘሮ መነን ከመኳንንቶቻቸው ጋራ ወደ ነበሩበት ቤት ገብተው እጅ ከነሡ በኋላ መስፍን ቀለመ ወርቅ የተባለ ተማሪ ስለ ተማሪዎቹ የሚከተለውን ቃል ተናገረ ።

ልዑል ሆይ ።

እለኒ ንግሥት የክርስቶስን መስቀል ከተቀበረበት ቦታ በዚህ ቀን ስላገኘች ይህ የመስቀል ቀን እንደተከበረ እንዲሁ እኛም ብዙ ዘመን ተቀብሮ የነበረውን የዕውቀት ብርሃን ለኛ ለባሮችዎ ያበሩልንን ቀን እንደዚች እንደ መስቀል ቀን ልናከብራት ተስፋ አለን ።

፪ተኛ ። ያዕቆብ ወደ አጎቱ ወደ ላባን ሲሄድ የካራንን ምንጭ ያገሩ ሰው ሁሉ ካልተሰበሰበ ሊከፈት የማይቻለውን ደንጊያ ብቻውን ከፍቶ የሐገሩን መንጋ ሁሉ እንዳጠጣ እንደሁም ዳግማዊ ምኒልክና ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንንም ፲፫ ሚልዮን የኢትዮጵያ ሕዝብ ተሰብስቦ ሊከፍተው ያልቻለውን የድንቁርና ደንጊያ ፈንቅላችሁ ያለ አንድ አሳብና ረዳት የትምርትን ቤት ከፍታችሁ ያገራችሁን ልጆች ሁሉ ስለ አስተማራችሁን የያዕቆብ ምሳሌ ሁናችኋልና ያዕቆብ ለእስራኤል አባት እንደ ተባለ እናንተንም ይህ መልካም ሥራችሁ የኢትዮጵያ አባቶች እንዲያሰኛችሁ አይጠረጠርም ።

፫ተኛ ። አባት ሁሉ ለልጁ ገንዘቡን የሚያወርሰው ሲሞት ነው እንጂ በሕይወቱ ምንም አያደርግለትም ። ልዑል ግን ክቡር ዳዊት በሕይወቱ ሳለ ልጁን ሰሎሞንን እንዳነገሠ ፤ እርስዎም በጉልማስነትዎ ወራት እኛን በመትከልዎ ያባትዎ የዳዊት ምሳሌ ሁነዋልና ፤ እስመ እምፍሬ ከርሥከ አነብር ዲበ መንበርከ ብሎ ላባትዎ ለዳዊት የሰጠውን ቃል ኪዳን ይፈጽምልዎ ።

፬ተኛ።ልዑል ሆይ ከግርማዊት ንግሥት እናትዎና ከልዕልት ወይዘሮ መነን ከክቡራን ልጆችዎ ከኢትዮጵያም ሀገርዎ ጋራ ረዥም የደስታ ዘመን ያስጥልን እንላለን ።

፭ተኛ።መልካሙን ዛፍ በመልካም ፍሬው ታውቁታላችሁ እንዳለ ወንጌል ፤ የበጎነት አርአያ ሆነው መልካም ፍሬ የሚሰጡን ቅንነትና ጥበብ የመላባቸው አለቆችን ክቡር ሐኪም ወርቅነህ ከነቤተ ሰባቸው ዕድሜ ይስጥልን መምሕሮቻችንንም ይባርክልን ብለን ክርስቶስን እንለምናለን።

፮ተኛ ልዑል ሆይ በሌሀ በወንድሞቼ ስም ሆኜ ካቀረብሁት ቃልና መዝሙር የተሳሳተ ቢኖር እንዳልነቀፍ ሁለት ምክንያት አመለክታለሁ ።

፩ኛ ። ተማሪ ነኝና ስሕተቴን ወደ ፊት በትምርት አርመዋለሁ ።

፪ተኛም ፤ ብዙኅ ዘመን በጨለማ ኑሬ ዛሬ በድንገት ብርሃን ሳገኝ ጊዜ የብርሃኑ ጨረር ዓይኔን እያንጸበረቀኝ ነውና ምንም እንኳ ከልዕልናዎ ፊት ሊነበብና ሊዘመር የሚበቃ ቃል ባይሆን በከሃሊነትዎ ይታገሡኝ ስል ልዕልናዎን እለምናለሁ ። ብሎ በጨረሰ ጊዜ ዳር እስከዳር ተጨበጨበ ።

ወዲያውም ልጆቹ ከመስፍን ቀለመ ወርቅ የተገጠመውን የመስቀል መዝሙር ዘመሩ ። መዝሙሩም ቀጥሎ የተጻፈው ነው።

መዝሙር ዘመስቀል ።

፩ መስቀሉ የጌታችን ።
መታሰቢያው ያምላካችን ።
የቤተ ክርስቲያን ኒሻናችን ።
መድኃኒትዋ ለነፍሳችን ።

፪ እንድናገኝ ከበሬታ ።
ትምርታችን እናበርታ ።
እንታለል በጨዋታ ።
ጥበብ ወዷል የኛ ጌታ ።

፫ እንዳሬቀርህ ጥበብን ።
ያርዝምልን እድሜህን ።
ከዓለምህ ጋራ ከመነን ።
ይባርክልን ዘርህን ።

፬ እንድንኖር በትዕግሥት ።
ሰብስቦናል በንድነት ።
ፍቅርይስጠን መለኮት ።
እንድንረዳ ለመንግሥት ።

ከመዝሙሩ በኋላ ለተማሪዎቹ ሱክር ተሰጠ ። አስተማሪዎችም ሻይ ተጋበዙ ።

ልዕልት ወይዘሮ መነን ስለ ተማሮቹ የጻፉት ቃል ።

ይድረስ ከክቡር ሃኪም ወርቅነህ ሰላም ለርሰዎ ይሁን

የልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሬ መኰንን ተማሪ ቤት ተማሪዎች ምንም ልጆቼ ቢሆኑ እናት ለልጆቿ የቡሄ ዳቦ ባለፈው ዘመን እንድትሰጥ ለሚጠቀማቸው ጉዳይ መሙሊያ የሃያ ሺ ፍራንክ ቼክ ልኬልዎታለሁና የናት መታሰቢያ መሆኑን አስበው እንዲቀበሉላቸው

ደጃዝማች ጌታቸውም የሚከተለውን ቃል ተናገሩ ።

ልዑል ሆይ

እነኚህን የትምህርት ምንጮች እንደተወደደ ፈሳሽ ወሃ በፊትዎ ሲመነጩ ሳይ ዛሬ ሶስተኛ ቀኔ ነው ይኸውም እስመ እምፍሬ ከርሥከ አነብር ዲበ መንበርከ የተባለውን ትንቢቱን ባወቀ አናግሮ ባወቀ አስፈጽሞታል ልዑልና ልዕልት ወይዘሮ መነን የድካማችሁን ዋጋ ጀምሮታል ይፈጽመዋልም ክርስቶስ በጎ ስራ መጀመርን እንጂ የመፈጸሚያ ሥልጣኑ በሱ እጅ ናትና ይፈጽምልዎ ብዬ ከልቤ እመኝልዎታለሁ ለነኚህም ለተማሪዎች እርዳታ አምስት ሺ ፍራንክ እንቁጣጣሽ ብያቸዋለሁ ።

ደግሞ ተማሪዎቹ ሁላችሁም ወንድሞቹ ሆይ አሁን የያዛችሁት ስራ ቀድሞ እኔም እራሴ ሌሎችም ትልልቆች የነገሥታት ልጆች ጀምረውት ነበር የተማሩት ተማሩ ያልተማሩት ቀሩ ይህችንም ቃል ለትንንሾቹ ትልልቆቹ ተርጉሙ ። ለትልቆቹም መምሕራኖቹ በየጊዜው አስታውሱዋቸው ። እግዚአብሔር ረድኤቱን በተወደደ መንፈሱ ይላክላችሁ ብለው ነገራቸውን በጨረሱ ጊዜ ተጨበጨበ ።

ልዑል አልጋ ወራሽም ለተማሮቹ ተስፋ የሚሰጥና የሚያበረታ ቃል ነገሩዋቸው ። ንግግሩም ቀጥሎ እንደ ተጻፈው ነው ።

የክርስቶስ መስቀል ለክርስቲያን ሁሉ ተስፋ ነው በተለየም ኢትዮጵያ የክርስቲያን መንግሥት መባሏ በነፃነት ነው

ነፃነትም በእውቀትና በትምሕርት ነው የሚገኝ ከኢትዮጵያ ከ፲፰ ሚሊዮን መካከል የቍጥር መጀመሪያ እንደሆናችሁ የውቀትም መጀመሪያ እንድትሆኑና ዮሴፍ ስለ ሃገሩ

ጠውቀቱ እንደ ተሰደደበት አገር ለንጉሡ እንደራሴ እንደሆነ እናንተም ለያንዳንዱ አውራጃ ትምሕርትን ለሚወዱ ሁሉ ምሳሌ እንድትሆኑ እመኝላችኋለሁ ።

ወደፊት ለምታደርጉትም የምመክራችሁ ትምሕርትን ሳይማሩ ጊዜያቸው ለተላለፈባቸው ታላላቅ ሰዎች የሚጸጸቱትን መጠን ብታውቁት እንኳን ቀን ሌሊት ለትምሕርት አታርፉም ነበር። አሁንም ጥበብን ለመፈለግ ጊዜው ያለፈብን ነንና የመክርናችሁ ጥቅማችሁን ወደፊት እንድታገኙ አውቃችሁ በርቱ፤ ለትምርትም የተጋችሁ ሁኑ ። ጌታ በወንጌል የተናገረው ለናንተ ነው የተፈጸመላችሁ ። ብዙ ነገሥታት ሊያዩ ሊሰሙ የፈለጉትን አላዩም አልሰሙም ። እናንተ ግን የፈለጋችሁትን እያችሁ ሰማችሁ ተብሎ የተነገረውን ታደላችሁ፤ እድሉ ግን የናንተ ብቻ አይደለም ግርማዊት ንግሥትም እኔም ከኢትዮጵያ ሕዝብና ከወይዘሮ መነንና ከልጆቼ ጋር የታደልን ነን ያለፉት የሚመኙትን አይተናልና አሁንም ቸሩ እግዚአብሔር የጀመራችሁትን ለመፈጸም እንዲያበቃችሁና በመስቀሉ እንዲባርካችሁ ፈቃዱ ይሁን ብለው በጨረሱ ጊዜ አብረው የነበሩ ክቡራን መኳንንት በደስታ እንባ እየታነቁ በጭብጨባ ተፈጸመ ከዚያ በኋላ ተማሪዎቹ በውጭ ያማረ ሰልፍ አሳይተው እየዘመሩ በደስታ ወደ ቤታቸው ሔዱ ።

ስለ ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ስለ ተማሪ ቤት እርዳታ ስለ ኃገራችን መጀመሪያ መሰረት ስላንድ ድንጋይ ወይም ስለኰረት ትሆንልኝ እንደሆነ ብየ አራት ሺ ፍራንክ እርዳታ ሰጥቻለሁ ። ተሰማ እሸቴ ።

ባለፈው ሰሞን ስለ ክቡር አለቃ ገብረ መድኅን ሞት ሐዘን ጽፈን ነበር ።

ደግሞ ዓርብ መንከረም ፲፫ ቀን ከደከሙበት ደብር ክቅዱስ ጊዮርጊስ ልዑል አልጋ ወራሽ ሔደው የአዲስ አበባ አድባራት ካህናት ሁሉ መጥተው የጉዛ ፍታት እየተፈታ እንደ ሚገባው ሀዘንተኞቹ እያለቀሱ ለክርስቲያን በሚገባ ሥርዓት ክብራቸውን የሚገልጽ ውሎ ተዋለ። የዚያን ዕለት መምሕራኑ የተቀኙት ቅኔ ።

ሚበዝኁ

ሊቀ ሊቃውንት ባእል ባዕሲያ ንበር
ወቅትስኒ ደቢሎ ።
ልወአሊሁ ሕማሃ እስመ ተቃውሞ
ኢተክህሎ ።
ዘምስለ ኃያል ሞት ኒመ አሐዱ
ኒቢደ ወኒመ ያበዝኁ ተማህሎ ።
ርእሰ ደብር ገብረ ሥላሴ ።

ሥላሴ

ኃያላኒ ድኅረ ሞዑ እንዘ ኢደፈ
ርዎ ብዙኃን ክልዔቱ አሐው ዘሰደፈ
ሃይማኖት ቀነተ ።
ሕምግባሰ ወኢትዮጵያ ዝንጉጊ ያዕትቱ።
ወይቴ ኃሰፉ ቅንታን ለደፍን መንቱ
እንዘ ብዙኃን በበፍኖቱ ።
እኮኑ ሞቶሙ ለክልዔቱ ።
እመ በጽሐ ለዋህድ ሞቱ።
ዘንኑ አለቃ መርሻ

ሥላሴ ።

ለፍሥሐ ገብረ መድኅን ሰቆቃወ
ኤርምያስ ኢደደሉ ሕንባ ንጎሚን
ትንቢት ድኅረ ተፈጸመ ሎቱ ።
መቃብረ አምጣን ረሰየ በገዳም ሰርሱ።
ባሕቱ ደዩሉ ለወልደ ማርያም ባሕቲቱ።
ሰቆቃወ ድንግል ለሰዐለቱ ።
አምጣን በአፍኦ ተቀብረ እምትእደንቱ
ወውእቱ እንግዳ በቤቱ ።
መምሕር ወልደ ጊዮርጊስ ዘራጉኤል

ሥላሴ ።

ደቤለን በመልእክቱ መተርጉም ጳው
ሎስ ገብረ መድኅን ከመ ምስለ ክርስቶስ
አሐሉ ደእዚ በመዓዘ ገነት ጸም ።
እፊቱ ተፈልጠ እምዝንቱ ዓለም ።
ወምስለ ወልደ አብ ለወልድ አክሉ
ዘገብረ መድኅን ሕማም ።
ከመ ቃለ ቄርሎስ መተርጉም ።
በተዋህደ ሞት ክብረ ወልደ ማርያም ።
እስመ ገንቱ ሃይማኖት ፍጹም ።
ዘአለቃ ወልደ ተክሌ ።

ሥላሴ ።

አርመመ ገብረ መድኅን ማዕበሰ
ንባብ ወትርጓሜ ወንምንሁ ቀደመ
ተንሥኦ ወልደ ማርያም በቍር።
በሞት እስመ ተአተተ ሕይወቱ እምድር።
በምንት ደበቀል ባሕቱ ዘምስለ ሐመ
ልማል ማዕር።
እምከመ ተኃጥአ ማየ ባሕር ።
እስመ ጊሠ ሞት ሐንከሰ አእጋር ።
በክልኤቱ ሊቃውንት አብትር ።
ዘአለቃ ወልደ ሚካኤል ዘቂርቆስ ።

በሌላው ነገር ከለው ይልቅ የሐዘን ብዛት መሠረት በኛ ላይ አድሯል ። ፕል ቡርገርት

አዎን ኑሮ መልካም ነው ። ደስታ ግን ስከር ነው አለ ፍርሃትና አለ ትካዜ ይህንኑ መሥራት ማፋጭ ነው ።

አልፍ ደ ሙሲት

ማስታወቂያ ።

ስለ ኢትዮጵያ ፍቅር በኢትዮጵያ ለሚቆመው ተማሪ ቤት በፈቃዳችሁ እንሰጣለን ያላችሁትን ቃላችሁን ለማስከበር ገንዘቡም ወለድ እንዲገኝበት በኢትዮጵያ የንግድና የርሻ ማስፋፊያ ማህበር ዲሬክተር እጅ ላቶ ይቴታ ጠብታስረክቡ የደረሰኙን እሱ ይሰጣል ። ይኸውም ሲደረግ ገንዘቡን ያስረከቡ ሰዎች ስም በየሳምንቱ በብርሃንና ሰላም ይጻፋል ። ለመስጠት አሳቢዎችንም ያተጋል የናንተንም ቃል ያስከብራል ።

ገብረ-ክርስቶስ ተክለ-ሃይማኖት
የብርሃንና ሰላም ዲሬክተር ።

ማስታወቂያ

ለራሶችና ለደጃዝማቾች ለሴት ወይዘሮች የሚገባ በያይነቱ ጥሩ ካባ ከኤሮፓ መጥቶልኛል ቤቱም (ባንክ ኦፍ አቢሲንያ) ከእንግሊዞች ባንክ አጠገብ ነውና ይህን ካባ መግዛት ለሚፈልጉ ሰዎች መጥተው እንዲገዙ አስታውቃለሁ። ኢያሱ ዳንኤል

አ ፒ ማርሲያኖ

የፊያት ኩምፓኒያ የኦቶሞቢልና የርሻ መኪና በኢትዮጵያ ዋና ወኪል ።



A.P. MARCIANO

Concessionnaire Ex. pour l'Ethiopie des automobiles et tracteurs Fiat.

በልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ

መጀመሪያ ዓመት ፤ ቁጥር ፵፩ ።
1re ANNÉE №. 41

ሐሙስ መስከረም ፳፰ ቀን ፤ ፲፱፻፲፰ ዓ ም ።
JEUDI 8 OCTOBRE 1925

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን በግዛታቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህነን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

የጋዜጣው ዲሬክተር ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ይስታውቁ ።
Gabré Christo Taklé Haymanot
Diréceteur

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ ሲገዛ ስፈልገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie
Un an 5 Thalers
Etranger
Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የብዙኃን ማርያም በዓል አከባበር ።

በመስከረም ፳፩ ቀን የብዙኃን ማርያምን በዓል ለማክበር ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን በክቡራን መኳንንቶቻቸውና በሠራዊቶቻቸው ታጅበው በአውቶሞቢል ከሌሊቱ በ፲፩ ሰዓት ወደ እንጦጦ ማርያም ወጡ ። ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ልዑል አልጋ ወራሽ በደረሱ ጊዜ ቅዳሴ ገቡ ። ከቅዳሴው በኋላ ፪ ሰዓት ተኩል ሲሆን ታቦት ወጥቶ ዑደቱ ባለቀ ጊዜ ካህናቱ በ፫ ሰዓት በልዑል አልጋ ወራሽና በብፁዕ ዕጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ በመኳንንቱና በሕዝቡ ፊት «ወእንቲኒ ታቦት እምነበኒ መጸእከ ወነበኒ ተሐውረ መድኃኒተ ኩኒ ለምኒልክ ንጉሠ ነገሥት» እያሉ ወረቡ ። አስረጋጮችም እንደ ማዕርጋቸው ያማረ ያማረ ሸልማታቸውን ለብሰው ሲያስረግጡ የድምጻቸውን መስማማትና የእግራቸውን አረማመድ የጸናጽል አጣጣላቸውንና አነሳስ ያየ ሰው ሁሉ በዓይን ደስ የሚያሰኝ ድንቅ ነገር መስሎ ይታይ ነበርና በጣም አደነቀላቸው

ከዚህ በኋላ ዕጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ዘመኑን ዘመነ ማህል መንግሥታችንን የፍቅር የሰላም መንግሥት ያደረገልን አምላክ ይክበር ይመስገን ብለው ስብከት ጀመሩ ። የእግዚአብሔርን ፍቅር መከተል ነው ። ፍቅሩንም የምንከተለው አባታችንን አዳምን ከፍጥረታት ሁሉ በላይ ከፍ አድርጎ ከፈጠረው በኋላ አትብላ ያለውን ዕፀ በለስ በልቶ መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ ቢያገኘው ሰማይ ዙፋኔ ነው ምድርም የእግሬ መመላለሻ ነው ያለ አምላክ ሰውን ከማፍቀሩ የተነሣ በትሕትና ዝቅ ብሎ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከቅድስት ድንግል ተወልዶ ከኃጢአት በተቀር እኛን መስሎ ቤዛ ሁኖበሞቱና በመነሳቱ አዳነን ዛሬ በዚህ የተሰበሰብንበትምክንያት የመቤታችንን በዓል ለማክበር ነው ። እመቤታችንን ሰውን ከወደደ ከልጇዋ ትእዛዝ ወጥተን እንወዳታለን ብንል ሐሰተኞች እንሆናለን እግዚአብሔር እንዳፈቀረን እርስ በርሳችን እየተፋቀርን ሥጋውና ደሙን በተጸጸተ ልብ ብንቀበል የእግዚአብሔር ፍቅር ከኛ ላይ ይፈጸማል እንዲሁ የመሰለም ብዙ ምክር መክረው ከሕጉና ከሃይማኖቱ እየውጣን የርሱን ፍቅር ከመሸሽ ያድነን ላገራችን ልማት ለመንግሥታችን ጽናት ይስጠን ። ዝናመ ምሕረት ፣ አክለ በረከት አይንሳን ብለው አቡነ ዘበሰማያት ሰጡ ፣ ፫ት ሰዓት ተሩብ ሲሆን ታቦት ገባ ።

ብፁዕ ዕጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ በተሰጣቸው አባትነት የሚያስፈልገውን መንፈሳዊ ምግብና የሕይወት ውሃ የሆነ የእግዚአብሔርን ቃል እንደሚረዳው አድርገው በየዕለቱ ስለሚመገቡት ይህነን አባትነት የሰጣቸው አምላክ ውለታቸውን እንዲሰጣቸውና በጀመሩት ሥራ እንዲያተጋቸው እንዲያበረታቸውም እንመኝላቸዋለን ።

ሶስት ሰዓት ተኩል ሲሆን ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ከቤተ ክርስቲያኑ ተመልሰው ወደ ልዑል አልጋ ወራሽ ግቢ በትልቅ አጀብ ሁነው ባራት ሰዓት ገቡ ።

የልዑል አልጋ ወራሽ ግቢ በአበባና በሰንደቅ ዓላማ አጊጦ ነበር ፡ ትልቁ አዳራሽም ከደረጃው ጀምሮ እስከ ውስጡ ያማረ ያማረ ምንጣፍ ተነጥፎ በሰንደቅ ዓላማና በአበባ አጊጦ ነበር ንግሥተ ነገሥታትና ልዑል አልጋ ወራሽ ተቀምጠው መኳንንቱና ሕዝቡን ሁሉ በየማዕርጉና በየደንቡ ግብር ሲያበሉ ዋሉ

ትልቁም ግብር በ፲ ሰዓት በደስታ ተፈጸመና ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ልዑል አልጋ ወራሽ በመኳንንቶቻቸው ታጅበው ወደ እልፍኝ ገቡ ።

ይድረስ ።
ክቡር አቶ ገብረ ክርስቶስ የብርሃንና ሰላም ዲሬክተር
ከማክበር ጋራ ሰላምታየን አቀርባለሁ ።

ለሃገራቸው ለደህንነትና ለልማቱ የሚያስቡ የኢትዮጵያ ልጆች ትምሕርት የጥበብና የብልጥግና መክፈቻ ቁልፍ መሆኑን አውቀው የትምሕርት ቤት ቢቆም መውደዳቸውንና ይኸንኑ በብርሃንና ሰላም እየጻፉ በየጊዜው ማስታወቃቸውን አይቼ እጅግ ደስ አለኝ ። እኔም ለዚሁ ለትምሕርት ቤት ማቆሚያ የሚሆን አንድ መቶ ብር እርዳታ እሰጣለሁ ። ነገር ግን ይህንን ለማስታወቅ ስጽፍልዎ ሌላ ጥቂት ቃል ጨምሬ እንድጽፍልዎ ደፍሬያለሁና እንዲቀበሉት ፈቃድዎ ይሁን ባንድ ምክንያት ፓሪስ ከተማ መጥቼ በዚሁ ከተማ በተቀመጥሁበት ወራት ውስጥ ያየሁትንና የተመለከትሁትን ሁሉ እንድጽፍልዎና እርስዎም በብርሃንና ሰላም እንዲጽፉት ለማድረግ አስቤ ለአንባቢ ይረዝማል ብዬ የሚበዛውን ትቼ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ብቻ ባጭሩ ብጽፍልዎ ትንሽ ጥቅም የሚሆን መስሎ ስለታየኝ ጽፌልዎታለሁና ፡ እርስዎም ዓይተው ምናልባት ጥቂት ሰዎች ይልቁንም የማዘጋጃ ቤት ሹሞችና ዘበኞች አንብበው ሥራቸውን እያጠኑ ለመሄድ የሚረዳ ነገር ቢያገኙበት በብርሃንና ሰላም እንዲያትሙት እለምንዎታለሁ ።

በፓሪስ የሚኖር ሕዝብ ነባሩም እንግዳውም ቍጥሩ ሶስት እስከ አራት ሚልዮን ይሆናል ። ይኸም ሁሉ ሰው በተቀመጠበት ከተማ አምሥት ወር ሙሉ ስቀመጥ በዚህ ባምሥት ወር ውስጥ ። ያየሁት የሬሳ ቁጥር በአራዳ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በአንድ ወር የሚቀበረውን የሬሣ ቁጥር አላየሁም ፤ ዳሩ ግን ይህንን የሚያህል ብዙ ሕዝብ የተሰበሰበበት ከተማ ሲሆን እጅግ ቢያንስ ከአሥር እስከ ሐያ ሺ ሰው በቀን ቢሞትበት እንኳን አያስደንቅም ነበር ይኸም መሆኑ ስለ ከተማው ጥዳት ነው ።

የጥዳቱም ነገር እጅግ ያማረ ነው ። ከተማንም የማያሳድፍና በመጥፎ ሽታው በሽታ የሚያመጣ የሰው ኩስና በከተማው ውስጥ እየሞተ የሚወድቅ የማናቸውም ዓይነት እንሥሣ ሬሣና ጥንብ እንደሆነ ማንም ያውቀዋል በፓሪስ ከተማ ግን ወኃው በመዘውር በየቤቱ እየገባ ኩሱ መሬት ሣይነካ እየተቀበለ በየ መንገዱ የወደቀውን ትንንሽ ጉድፍ እየጠረገ በመሬት ውስጥ ለውስጥ እየወሰደ ከከተማው ውጭ አውጥቶ ለዚሁ ተብሎ በተበጀ በታላቅ ዘባጣ ሜዳ ጥሎ እርሱ በተበጀለት መንገድ እየጠለለ ወደ መሬት ገብቶ ወደጥሩ ጥሩ ውኃነቱ ይመለሣል ። የጉድፉም አተላ የመሬት ማፋጊያ ይሆናል ። የእንሥሣ ሬሳ ወይም ጥንብ ግን እንኳንስ በከተማ በማናቸውም ቦታ ቢሆን በመሬት ለማየት አይቻልም ። ከተማውም እንደዚህ ሆኖ ስለ ጠዳ ደዌ የሚባል በአገሩና በከተማውም ለመግባት አይችልም ። በቀን ብዛትም ቢገባ ስለ ሐኪም ብዛት በቶሎ ብሎ ከአገር ይሰደዳል ። ስለዚህ ሰውም ቢሞት በተወሰነለት እድሜው ይሞታል ። በሌላም መንግሥትና አገር የሚከብረውና የሚታፈረው የሚወለደው ሕፃን እያደገ የሕዝቡ ቁጥር እየበዛ ሲሄድ ነው ሕዝቡም ቁጥሩ እየበዛ የሚሄደው ተወልዶ ያደገው እየቆየ የሸመገለው ብቻ ሲሞት ነው ። ይኸም ቢቀር የሚወለደውና የሚያድገው ቁጥር እየበዛ የሚሞተው ቁጥር እያነሰ ሲሄድ ይሻላል ። እንጂ የሚወለደውና የሚሞተው ቍጥር የተካከለ እንደሆነ አገሩ ኃይል እየጨመረ ይሄዳል አይባልም ከሚወለደውና ከሚያድገው ቁጥር የሚሞተው ቁጥር የበዛ እንደሆን ግን አገሩን ያስፈራዋል በኛም ሀገር ከኅዳር በሽታ ወዲህ በከተማው ጤና ጠፍቶ ተወልዶ ከሚያድገው ሕፃንና በሕይወቱ ከሚኖረው ሰው የሚሞተው ቍጥር እንደበዛ ለሰው ሁሉ የሚታይ ነው ። እንግዴህ ቍጥራችን እየጐደለና እያነሰን እንሄዳለን ማለት ነው ። ይህነንም ሁሉ መናገሬ ሰው በተወሰነለት ዕድሜው እስኪሞት ድረስ ጤናውንና ሕይወቱን የሚጠብቅለትና የሚደግፍለት አንዱ የሕይወት ምሰሶ የአየር ጥሬትና የከተማ ጥዳት ሆኖ በፓሪስ ከተማ የሚኖረውን የሕዝብ ብዛትና በዚሁ ሁሉ ብዛቱ በሽታ ገብቶ አለመፍጀቱ በከተማው ጥዳት የተነሣ መሆኑን ስለ ተረዳሁ የከተማው ጥዳት የሕዝብ ጤና መሆኑን ለኛም ከተማ መዘጋጃ ቤት ለማሳሰብና ልቡን ለማነሣሣት ስለ ተመኘሁ ላመልከት ብዬ ነው እንጂ የሰው እድሜ ባለቤት አምላክ መሆኑን ለመቃወምና ወሬ ለማውራት ብዬ አይደለም ። እንግዴህ የሕዝብ ጤናና ሕይወት ደጋፊው ጠባቂው የአየር ጥሬትና የከተማ ጥዳት ከሆነ ከተማንም የሚያጠዳ ወኃ ከሆነ የኛም ከተማ ማዘጋጃ ቤት የሌላው አገር ማዘጋጃ ቤት የሚሠራበትን ደንብና ሕግ ተከትሎ በአዲስ አበባ ዙሪያ ያለውን የምንጭና የወንዝ ውሀ ሁሉ በመልካም መሐንድስ ሰብስቦ በከተማው አግብቶ ቀብሮ ሕዝቡም ጥሩ ወሃ እየጠጣ ከተስቦ በሽታ እንዲያመልጥ ከተማውንም እያጠበ በመጥፎ ሽታ በከተማው ደዌ እንዳይገባ በቶሎ ያዘጋጅልናል እያልን በብዙ ትዕግሥት ተስፋ ማድረግ ይገባናል ።

ደግሞ በአዲስ አበባ ከተማ የዘበኛ ሥራና በፓሪስ ከተማ የዘበኛ ሥራ መካከል ታላቅ ልዩነት አይቼ ሁሉን ባይሆን አንዳንዱን እንኳን ልጽፈው አሰብሁ ። የፓሪስ ከተማ የዘበኛ አለቃ ጥዋትና ማታ ዘበኛ በሚለዋወጥበት ጊዜ ዘበኞቹን በገላጣ ቦታ እየሰበሰበ እንዲህ እያለ ሲመክራቸው ሰማሁ ።

ምንም ሥራችንና ትእዛዛችን ተዘርዝሮ በደንባችን የተጻፈ ቢሆን እንዳትዘነጉትና እንዳትሣሳቱ አስገነዝባችሁ ዘንድ የግድ አለብኝ ። አሁንም እኛ በመልክም ሥራችንና በሥልጣናችን ሕዝብን ወደ ሕግና ወደ በጐ ሥራ ሁሉ ለመምራትና መልክም አብነት ለመሆን ብርቱ ግዴታ አለብን ። እናንተም ይህነን መሠረት አድርጋችሁ ማንም ሰው መንገድ ወይም ቤት ተሣስቶት ቢጠይቃችሁ ወይም ግራ ገብቶት ተቸግሮ ብታዩት በቶሎ ብላችሁ በትሕትና ቃል የተቸገረበትን ነገር ጠይቁት የተሣሣተውንም አመልክቱት ። ሰውም ቢወድቅ ወይም በድንገት ጋሪ ቢመጣበትና ቢደናገረው በቶሎ ወደርሱ ቀርባችሁ እርዱት አበራቱት ወስላታና ክፉ ሠሪም ብታገኙ ወደ ዳኛ ወይም ወደ እሥር ቤት እንዲሄድ በቃላችሁ ንገሩት እንደ ትእዛዛችሁም ባያደርግ ይዛችሁ ውሰዱት እንጂ ሊመታችሁ ከአልፈተነ በቀር አትምቱ አታጉላሉ ። የሰውም አገር ሰው እንግዳ በማናቸውም ነገር እንዳይጠቃ እንዳይታለል ጠብቁት ። እያለ ሲሰብካቸው ዘበኞቹም

ራሳቸውን ደፍተው ቃሉን ሁሉ በመጠንቀቅና በትሕትና ሰምተው ትእዛዙን ተቀብለው ወደ ሥራቸው ይሄዳሉ፤ሽጉጣቸውን ታጥቀው ስንገዘር ዱላቸውን ይዘው በየሥፍራቸው ቆመው እየተንጐራደዱ የተሰጣቸውን ትእዛዝ ፈጽመው ሰዓታቸውን አድርሰው ለባለ ተራው ያስረክባሉ ። የተሠጣቸውን ትእዛዝ ግን ተላልፈው በመንገድ የሚተላለፈውን ሰው ከሥራት ማይወጣ ሲያሩናብዱ ግራ ሲያገቡ የተገኙ እንደሆነ ተንኮልም ለማድረግ ወይም ክፉ ሠርቶ የተያዘውን ተራርቀው ለመስደድ ሲመክሩ የተገኙ እንደሆነ በዘባቸውም ሰዓት ተቀምጠው ወይም ተኝተው የተገኙ እንደሆነ ከወንበዴና ከሌባ ቅጣት የበለጠ ቅጣት ያገኛቸዋል ። ለሥራቸው መጠንቀቃቸው ግን እንሆ ከአዲስ አበባ ለትምሕርት የሄዱ ያገራችን ልጆች ፓሪስ ደርሰው አንድ ቀን በከተማ ሲተላለፉ አንድ የአሥር ዓመት ልጅ የሚሸጥ ሥዕል ይዞ ሲዞር አግኝተውት ሽጥልን ብለው ቢጠይቁት አንድ ፍራንክ ተኩል የሚሸጠውን በሁለት ፍራንክ ሲሸጥላቸው ዘበኛ በሩቅ አይቶ ይኸንን ልጅ ጠርቶ በምን ያህል ሸጥህላቸው ብሎ ቢጠይቀው ። በሁለት ፍራንክ ሸጥሁላቸው ብሎ መለሰለት ዘበኛውም እንግዶች ናቸው ብለህ ልታታልል ስለምን እራስህን አሰለጠንህ ብሎ ወደ እሥር ቤት ወሰደው ። ደግሞ በሀገራችን የሚኖር ሙሴ ገርዎርገር የሚባል የግሪክ ሰው ከአዲስ አበባ መጥቶ ፓሪስ የገባለት ማታውን እራቱን በልቶ እንዳይተኛ ሰዓቱ ጊዜ ስለሆነ በመንገድ ዳር ዳር እየተመላለሰ ሲናፈስ አንድ ሰው ከአንድ ቤት ወጥቶ በፍጥነት እየተራመደ መጥቶ ወደ ሙሴ ገርዎርገር ቀርቦ ምነው ጌታው ብቻዎን እዚህ አጉል ቦታ ይተክዛሉ እንግዳ ነዎ መሰለኝ፤ እኔ እንግዳ ሰው አገር ማልመድ ሥራዬ ነው አሁንም ይምጡ ወደ ቡና ቤት ሂደን ትንሽ እንጫወትና በኋላም ወደሆቴል እሸኝዎታለሁ ። እያለ ሲነግረው ንግግሩንም ሳይጨርስ ዘበኛ በሩቅ ሁኖ አይቶት ኖሮ ወደነርሱ ሲገሰግስ ያ ሊያታልል የዠመረ ሰው በቅጽበት እሮጦ ጠፋ ዘበኛውም ወደ እንግዳው ቀርቦ ጌታው እንግዳ ነዎን? ገንዘብስ ይዘዋልን? ብሎ ጠየቀው።ሙሴ ገርዎርገርም አዎን ጌታዬ እንግዳ ነኝ አሁን ከባቡር ወርጄ እራቴን በሆቴል በልቼ ቀኑ ጊዜ ስለሆነ ትንሽ ለመናፈስና የከተማውን ድንቅነት ለማየት ብዬ እዛወራለሁ ገንዘብም በኪሴ ይዤአለሁ ብሎ መለሰለት ዘበኛውም መልሶ መንገደኛ ሁኖ ገንዘብ ይዞ በአሁን ሰዓት በፓሪስ ከተማ ለመናፈስ አይመችም ለገንዘብዎ ሲሉ መልክም ነገር አሣይተው ለሰውነትዎ የሚያስፈራ ሊያደርጉብዎ የማይመለሱ ብዙ ወስላቶች ሰዎች አሉ።አሁንም ወደ ሆቴልዎ ገብተው ይተኙ ለወደፊቱም ይጠንቀቁ ብሎ መከረው ።

እንግዳውም ስለምክሩና ከክፉ ነገር ስለ አዳነው ለሚጋራ መግዥ ትንሽ ገንዘብ ሊሰጥ ተኪሱ ኮረጆውን ቢያወጣ ዘበኛው ተቈጥቶ ምክር መስጠቴ የግድ ሥራዬ ሆኖብኝ ነው እንጂ እርሰዎን አገልግዬ ገንዘብ ለመቀበል አይደለም ብሎ ገስጾ ሸኝቶ ሰደደው ። የኛም አገር ዘበኞች ይኸንን ሁሉ ሥራው ከሆነ ከአዋቂ ሰው ባይማሩትና ጨርሰው ባይለምዱት መጥፎው ሁሉ ይወራባቸዋል ። ነገር ግን መልካም አስተማሪ አስተምሯቸው ሥራውን ከለመዱት በኋላ የዘበኝነቱን ሥራ አስተካክለው እየሠሩ እራሳቸውን አስመስግነው መንግሥቱንም ሳያስመሰግኑት ይቀራሉ ተብሎ አይጠረጠርም ።

ለዚሁም ሁሉ አለቆቻቸው የዘበኝነት ሥራ ሥራቸው የሆነ የተመሠከረላቸው አዋቆች ሠራተኞች ፈልገው እያገቡ እነዚያም መልካሙን ደንብ ሁሉ እያቆሙ አሁን በዘበኞቹ ውስጥ የሚወራባቸውን መጥፎ ሥራና ልማድ ሁሉ አርመው እያስወገዱ የዘበኛውን ሥራ በትክክል እንዲያስኬዱት ያደርጓቸዋል ብለን ቡብዙ ትእግሥት ተስፋ እናደርጋለን ።

ሹሞቹ ግን እኛው እናውቃለን እያሉ የዘበኛ ሥራ የሚያውቅ ሠራተኛ ገብቶ ደንቡን አዘጋጅቶ ዘበኞቹን እንዳያስለምድ እንቅፋት የሚሆነውን ነገር ሁሉ እያደረጉ ቢያሰናክሉ መጥፎውም ሥራና ልማድ እየሰፋ ይሄዳል ። የዘበኛውም ሥራ ጥቅም መሆኑ ቀርቶ ፍሬው የሕዝብ ጉዳት ይሆናል ።

ደግሞ የሀገራችን ልጆች ተምረው ሥራ እስኪይዙ ጊዜው እሩቅ ነው መንግሥቱ ግን አገሩን በቶሎ አዘጋጅቶ ዓለሙ ሁሉ የሚኖርበትን አዲስ የጥበብ ደንብ አንዳንዱን እንኳ አግብቶ ለማቆም የሚያስቸኩለው ምክንያት አለውና በማናቸውም ሥራ ቢሆን የታመኑና እውቀታቸው የተመሠከረላቸው ሠራተኞች እየተፈለጉ ገብተው ካላዘጋጁት በቀር ሥራውን ያልተማረ ያገር ሰው ምንም ብልህ ቢሆን ለመንግሥቱና ለሀገሩ ለዛሬ የሚያስፈልገውን ሥራ አስተካክሎ ያስኬደዋል ማለት የኢትዮጵያ ሰው ማይድህ ይሮጣል ማለ ትይሆናል ።

እናውቃለን እንችላለን የሚሉም ሹሞች ቢኖሩ ከልክ አልፈው ይሣሳታሉ ። በኋላም ትርፋቸው ሐሜትና ሐላፊነት ይሆንባቸዋል ።

ደግሞም ሥራውን የሚያዘጋጅ ሠራተኛ ይግባ ስለተባለ ሥራው እንዲተካከል ነው እንጂ የሹሙ በላይነትና አዛጋርነቱ እንዲቀርበት አይደለም ።

ከዚህ በኋላ ትንሽ ነገር ለአንባቢዎች ለማስገንዘብ ደፍሬያለሁና ይፍቀዱልኝ ።

እነሆ በዓለም ሁሉ ላይ ያለ ልዩ ልዩ መንግሥትና ሕዝብ የሚኖርበትን በየሐገሩ በሰው እጅ የተሠራ የጥበብ ሥራ ሁሉ ባንዳንድ ቦታ በየጊዜው እየተሰበሰበ ሕዝብም ሁሉ ከያገሩ እየመጣ ይህነኑ የተሰበሰበውን ለማየት እንዲችል መንግሥታት ሁሉ በንድነት መክረው ኤክስጰዚሲዮን የሚባል ደንብ ስለአቆሙ የዚህ የዛሬው ዓመት በ፲፱፻፳፫ በግንቦት ወር ፓሪስ ይተሰብስቦ እስከ ጥቅምት ወር ድረስ ሰው ሁሉ እየመጣ እንዲያይ ተመክሮ ተቆርጦ ኖሮ፤እኔንም በድንገት እግሬአደርሶኝ ከኢትዮጵያ በቀር በዓለም ያለ መንግሥት የሚገዛው አገር ሁሉ በውስጡ በሰው እጅ የሚሠራ የጥበብ ሥራ ሁሉ ከየአገሩ መጥቶ ፓሪስ ላይ እየራሱ ባንድ ቦታ ቤት እየተከራየ የያገሩን እቃ እያገባ ዘርግቶ ከያገሩ ለተሰበሰበው ሕዝብ በየበኩሉ በሚያሣይበት ጊዜ ደርሼ ከዚህ ሁሉ መንግሥትና ሕዝብ አገሬ ኢትዮጵያ ብቻ በቦታዋ ሣትገኝ ተለይታ በመቅረቷና ከቁጥር የጐደለችበትን ምክንያት ለጠየቁኝ ሰዎች የሰጠሁት ምላሽ መሠረት የሌለውና አንካሣ ስለ ሆነብኝና ለአገሬም እፍረት ስለመሆኑ አጥብቄ አዘንሁ ።

ከዚህም ይልቅ የሚያሣዝነው የኢትዮጵያ መንግሥትና ቀድሞም ለእግዚአብሔር እርስትነት ከተመረጠ ከእስራኤል ሕዝብና የእግዚአብሔር ባርያ ከተባለው ከዳዊት ዘር ሆኖ የወረደ በኋላም የይሁዳ እርግማን እንዳይደርስበት በወንጌል ተሰብኮ

በክርስቶስ ስም ተጠምቆ ለክርስቲያን ሃይማኖት ደሙን ሲያፈስ የኖረ ስመጥሩ መንግሥትና ሕዝብ ሆኖ ሣለ ዛሬ ዓለም ሁሉ የሚያድርበትን ጥበብና ደንብ ተቀብሎ ከሌሎቹ መንግሥትና ሕዝብ እንዳይተካከል ። ጣዖት ከሚያመልኩ መንግሥትና ሕዝብ ሠንፎ ተለይቶ ወደ ኋላ በመቅረቱ ነው ።

ይህም ሁሉ የሆነበት ምክንያት የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት በአንድ ልብና አንድ አሣብ ሆኖ ትምርትን ለማቆም ጥበብን በሀገሩ ለማግባት እንዳይተጋ በብዙ ምክንያት ስለ ተሰናከለ ነው ይመስለኛል። ታላቁ ጌታችን ጃንሆይ አጼ ምኒልክ ግን ያለ ትምሕርት መንግሥትም አገርም እንዳይቆም አስተውለው ተረድተው (አገሬ በትምሕርት ትጠናለች) ብለው አስተማሪውን ከምሥር አስመጥተው ለትምሕርቱ የሙሴ ኢልግን ቤት መርጠው የመኳንንቱን ልጆች አግብተው ትምርቱን አቆሙ።ከርሳቸውም በኋላ ትምርቱ እየሰፋ እንዲሄድ ነበር እንጂ በከንቱ እንዲቀር አልነበረም መኳንንቱና ሕዝቡ ግን ይህነን ብርቱ ቃል ፈጽሞ መዘንጋቱ በጣም የሚያዝናል ለትምርቱ የቆመው ቤት ቆሞ መቆየቱ ስንኳ ጥቅም ሆኖ ታይቷቸው ደግፈው ያቆዩትን ሰዎች ማመስገን ይገባል ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ግን ምንም በብዙ እንቅፋት ቢሰናከሉ አባታቸው ታላቁ ንጉሠ ነገሥት አስበው የጀመሩትን የትምሕርት ሥራ እልኩ ለማድረስ ያለ እረፍት እንዲጣጣሩና እንዲታገሉ እናያቸዋለን የሐገራቸውም ልጆች እንዲማሩላቸው ያለ አድልዎ ለሁሉም መትጋታቸውን እኔም እመሰክራለሁ በ፲፱፻፲፩ የአገራችን ልጆች በፈቃዳቸው ፓሪስ ሄደው የሚማሩበት ገንዘብ አጥተው ተቸግረዋል ብዬ እኔው ብነግራቸው ከንዳቸው የሚበቃ ገንዘብ ሰጥተውኝ ለነዚያ ልጆች ላክሁላቸው ልጆቹም ተምረው አሁን በየሥራው አግብተዋቸዋል ለትምሕርቱም የኢትዮጵያ ልጅ ከሆነ የአማራ ልጅ የጋላ ልጅ የዘመድ ወይም የባዕድ ልጅ ነው ብሎ ማማረጥ የለባቸውም እንደዚሁም ደግሞ በአዲስ አበባም በሮፓም በአሜሪካም በምሥርም በየሥፍራው የራሳቸውን ገንዘብ እየከፈሉ የሚያስተምሩዋቸው ልጆች ብዙ ናቸው በዚህም ላይ የአገራቸው የተማረና የታመነ ልጅ በውጭ አገር ሥራ ውስጥ አለ ማለትን የሰሙ እንደሆነ ከአለበት ቤት አስወጥተው የመንግሥታቸውን ሥራ ያስይዙታል።ይህም ሁሉ ለመንግሥታቸውና ለሐገራቸው ልማት መጣራቸውን ያሳይላቸዋል ፤ እኔም ይህነን መናገሬ እውቀታቸው ያልተደላደለ ወይም በመጥፎ አሳብ የሆነ አንዳንድ ሰዎች ልባቸው እያወቀ የመንግሥቱንና የአገሩን ጥቅም ወደ ጐድን ትተው ለየራሳቸው ጥቅም ሲሉ እርግጡን እየተው በየጊዜው የሚያወሩባቸውን ውሸት ይኸነን ጋዜታ ያነበበ ሰው ትንሽ እንዲረዳውና የርሳቸውን ፋና ተከትሎ ለአገሩና ለራሱ የሚሆነውን ጥቅም ይፈልግ እንደሆነ በማለት ነው እንጂ እኔ እርሳቸውን አመስግኜ ክብር እንዲጨመርላቸው በማለት ብጽፈው ግብዝነት መጨመር እንዲሆንብኝ አውቃለሁ እርሳቸውም በራሳቸው ገንዘብ እያስተማሩ መንግሥቱን ለማጠንከርና አገሩን ለማልማት ምንም ቢጥሩ ባንድ ሰው ገንዘብ ያንድ መንግሥት አገር ሕዝብ ተምሮ በጥበብ መንገድ ይገባል ወይም እነዚህ በርሳቸው ገንዘብ የተማሩት ልጆች ትምሕርት አገሩን በጥበብ መንገድ አግብቶ ያቀናዋል ለማለት አጅግ ይቸግራል ። አሁን ግን በታሰበውና በተጀመረው መንገድ መንግሥቱም መኳንንቱም ሕዝቡም ባንድ ልብና ባንድ ፈቃድ ሆኖ ተባብሮ ለትምርት የሚያስፈልገውን ገንዘብ አውጥቶ በአገርም የትምርት ቤት አቁሞ ብዙ ልጅ እንዲማር ወደ ሮፓም እየሄዱ ብዙ ልጆች ትልቅ እውቀት እንዲማሩ ማድረግ ያስፈልጋል።ሕፃናትንም ማስተማር በብዙ ከሁለት እስከ አምስት መቶ የሚሆኑ ሰብስቦ በየሃገሩና በየሥራው እየላኩ ነው እንጂ አምሳና ስልሣ ሰው ተምሮ አገር ለማቅናት አይሆንም እነሆ ከሽንና ከአፍጋኒስታን አገር መጥቶ ፓሪስ ላይ የሚማረው ተማሪ ያንዳንዱ አገር ከአምስት መቶ እስከ አንድ ሺ እስከ ሁለት ሺ ተማሪ ነው ።የሚማርበትንም ገንዘብ የሚያወጣው መንግሥቱና አገሩ ነው የትምርቱን ፍሬ ለመንግሥቱ ማጠንከርያና ለአገሩ ማልሚያ እንዲሆን ማንም አይስተውም ።

አሁንም የአገራችን ሰዎች ትምርት የተባለችውን የእውቀትና የብልጥግና መክፈቻ ቁልፍ ለዓለም ሁሉ ለማብራት እሮጳ ላይ በተቀጣጠለችው ጥበብ መብራት አይተዋት ለዚችው ለትምርት ማቆሚያ የሚሆን ገንዘብ ከማጠራቀም በቀር አገራቸውንና መንግሥታቸውን አደላድሉ ለማቆም ሌላ መድኃኒት አለ መኖሩን ስለ ተረዱት በየመጠናቸውና በየችሎታቸው ገንዘብ ለማውጣት በፍጹም ልባቸው የተዘጋጁ መሆናቸውን በብርሃንና ሰላም እያስጻፉ ማሳየታቸው ርብርቱ ደስ የሚያሰኝና ብዙ ተስፋ የሚያስደርግ ነገር ነው ።

ነገር ግን ይህ መልካም አሳብ ከተገለጠላቸው በኋላ ገንዘቡን ለማውጣት ከተሽቀዳደሙት ሰዎች የሚበዙት ታላላቆቹ ጌቶችና መኳንንቱ አለመሆናቸውን ላስተዋለው ሰው ትንሽ ቅር ያሰኛል ፤ አንባቢም ስለምን ቅር ያሰኛል ጊዜውስ ገና አይደለምን ? ይለኝ ይሆናል ጊዜውስ ገና መሆኑ እርግጥ ነው ቢሆንም ስለ ብዙ ምክንያት ጌቶቹ ከተርታው ሰው ትምርቱን ለማቆም መቅደም የግድ ያስፈልጋል።ምክንያቱም የሚከተለው ነው ።

እነዚህ መኳንንት የመንግሥቱን ጌትነት ተካፋዮች ስለ ሆኑ በምክርም ቢሆን በሥራም ቢሆን መንግሥቱን ለማጠንከርና አገሩን ለማልማት የሚሆነውን ነገር ሁሉ ለማድረግ መንግሥቱን ለመርዳት ሲሉ ከሕዝብ በፊት መሆን ይገባቸዋል

፪ተኛ።በቀኝም ቢሆን ወይም በግራ ጊዜው ይቆይ እንጂ በኢትዮጵያ ጥበብ መግባቱ የማይቀር ነው፤ጥበብም በአገር ከገባ ከንጉሡ በቀር ሰው ሁሉ በማዕርግ ከፍና ዝቅ የሚለው በትምርትና በሥራ በውቀት መሆኑ መቼም የታወቀ ነው ሰውም ሆኖ ለልጁ የማያስብ የለምና መኳንንቱም ልጆቻቸው ስፍራቸውንና ማዕርጋቸውን እንዳያጡ ቢማሩላቸው ጥቅማቸው ነውና የትምርቱን መሠረት ለማቆም መሽቀዳደም የሚገባቸው ለመኳንንቱ ነው ። ደግሞ ድሃ ሰው የድህነቱን ኑሮ የለመደው ስለ ሆነ ጌትነት ካልፈለገና የባዕድ ገዢ ካልመጣበት በቀር የገዛ ቢገዛ ለገዛው በትሕትና መገዛትና ታዞ መኖር ነው እንጂ ወደ ፊት ለሚመጣው ነገር ማሰብና ወደ ትምርት ለመሽቀዳደም የግድ የሚሆንበት ነገር የለበትም ። ጌታ ወይም የጌታ ልጅ የሆነ ሰው ግን የጌትነት ሥፍራውንና ማዕርጉን ለመጠበቅና

ለልጁ ለማሳለፍ ሲል መንግሥቱ ጸንቶ አገሩ ለምቶ ነጻነቱ ተደላድሎ ተጠብቆ የሚኖርበትን ነገር ሁሉ ለመፈለግና ለማቆም መሮጥና መሽቀዳደም የግድ ይሆንበት ይመስለኛል ።

፫ተኛ ፡ መንግሥቱ ተደላድሎ የሚቆምበት አገሩ የሚለማበት በትምርት ብቻ መሆኑን ተርታው ሕዝብ ተረድቶት ገንዘብ ለማውጣት ሲሽቀዳደም መኳንንቱ ቢያዘግሙ ጥበብ አገሩ ቢገባበት አይወዱም ተብለው ይታማሉ ፡ ጥበብንም ጠልተው በኢትዮጵያ አትገባም እያሉ በዚህ ተስፋ ቢቀመጡ ዓለሙ ሁሉ በብርሃን ሲኖር ኢትዮጵያ ብቻ በጨለማ ውስጥ ተቀምጣ የሌላው አገር ሕዝብ ባቡሩን በመሬት ውስጥ አግብቶ እንደ ሜዳ ሲሮጥበት ሰማዩን በነፋስ መርከብ እንዳሞራ እየ ቀደደው ሲሄድ ታደምጣለች ማለት ይሆናል ፤ ጥበብንም በሀገራችን እንዳትገባ እናሰናክላለን ብለው ቢያስቡ ስሕተት ይሆንባቸዋል ። ስለምን ቢሉ ጥበብ ማለት ከረጅም ገደል አፋፍ ተፈንቅሎ መገላበጥ የጀመረን ቋጥኝ ደንጊያ ይመስላል ይህም ቋጥኝ መንከባለል ከጀመረ በኋላ ደግሞ አቆመዋለሁ ወይም እመልሰዋለሁ ማለት ተድጬ ልረፍ ማለት ይሆናል ይህንን ሁሉ መጻፌ ቅናቱ ውጋት ሆኖ እንቅልፍ ቢነሣኝ ነው።

የሮጳን ሥራ ያላየ ሰው በጎ ሄደ ። ስለምን ቢሉ የሮጳን መዘጋጀትና ሥራዋን ያየ የአገራችን ሰው ኢትዮጵያ እስከ መቶ ዓመት ድረስ የሮጳን ሲሰውን ሥራ አታቆምም ብሎ ተስፋ ይቆርጣል ።

እኔም ምኞቴና ይህንን ለመጻፍ ልቤ የተነሣሣበት ምክንያት ኢትዮጵያ ሥራ ፈታች ተብሎ ሰበብ እንዳይፈለግባት ነጻነቷን የሚያጸና አንዳንድ እንኳን ነገር እንድታቆም ነው ይህም የመጀመሪያውና የመጨረሻው አሳቤና ምኞቴ መሆኑን ሰው ሁሉእንዲያውቅልኝ እመኛለሁ ።

ወልደ ማርያም አየለ ።

(ፓሪስ)

ከልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ከፍ ያለ ተማሪ ቤት ።

የደስታ ቃል

ከልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን የተማሪ ቤት ያለን ተማሮች የደስታችን ብዛት ወሰን የለበትም ደስታችን የበዛበት ምክንያትም የሰውተምረን አዋቂዎች እንሆናለን በዚያውም እንከብርበታለን ብለን ብቻ አይደለም ። ባንድ መንገዱ እርግጥ ነው ትምህርት የሚማር ሰው ተምሮ መጥፎውንና መልካሙን ከለየ በኋላ ሥራ ይይዛል በያዘው ሥራም አስቀድሞ ራሱን ይጠቅምበታል ቀጥሎም መንግሥቱንና አገሩን ይጠቅምበታል ነገር ግን በተለየ የኛ ደስታ እንዲህ ነው ። የልጅና የተክል የሁለቱ ምሳሌያቸው አንድ ነውና ተክል የሚያሳድግ ሰው ብዙ ድካምና ብዙ ጥበብ መጠበብ ያስፈልገዋል ። አንዳንዱ ሰዎች ሲያደርጉ እንደምናይ ሳይረዝም ባጭሩ እንጽፋለን አንድ ብዙ ፍሬ የሚያፈራ ተክል ቢኖር ፍሬው ግን መፃፃ የማይጣፍጥ ቢሆን ከንድ ጣፋጭ ፍሬ ከሚያፈራ ተክል ቈርጠው ወደዚያ መፃፃ ፍሬ ወደሚያፈራ በጥተው ያገቡበታል እንደ ጥበባቸውም መጠን አድርገው ያስሩታል ከዚያ ወዲያም አንድ አካል ሆኖ ተስማምቶ ያድጋል የቀድሞ መፃፃ ፍሬ ቀርቶ ጣፋጭ ፍሬ ያፈራል ። እንዲሁም እኛ በመከከላችን አንድ ትእግሥት የሌለው ሁከተኛ ቢሆን ያስተማሮቹንና ያንዳንድ ትእግሥት ያላቸው የቀለም ጓደኞቹን አካሄድ እያየ የርሱን ሁከት እየተወ የሌሎቹን ትእግሥት እየተከፈለ ጭምት እየሆነ ይሄዳል ስለዚህም እኛ የቀለም ጓደኞቹ ብዙ ደስታ ደስ ይለናል ።

ሁለተኛም ፤ ክፉ የሰውን ሕይወት ሊያጠፋ የተዘጋጀ መጠጥ የሚባል መርዝ አለ እርሱን በጠጣህ ጊዜ ልትሰራው ያለህን ትተህ ያላሰብኸውን ሥራ ትሰራለህ ያልተሰለፍህበት ዘመቻም ትዘምታለህ እነሱም አሁን ስማቸውን ልንቈጥራቸው አያስፈልግም ስለ ምን በመጠጥ ሰውነትህ በተቃጠለ ጊዜ የምታስበው አሳብና የምትቈጥረው ጕዳና የታወቀ ነው እኛ ግን ይኸንን ከመሰለ ነገር ሁሉ ሰውነታችንን ነፃ አድርገዋታል ስለዚህም የደስታችን ብዛት ወሰን የለውም።

ሶስተኛም የፊተኞች ጓደኞቻችን አይቴ ብሔሩ ለጥበብ ወአይቴ ማኅደሩ ወበአይቴ ተረክበ አሠረ ፍኖታ እያሉ ሲያነቡት ሳሉ ግዕዝ ቋንቋ ምንም እንኳን ያባቶቻችን ቋንቋ ቢሆን የሚነጋገርበት ሰው ስለሌለ ላንዳንዱ ሊቃውንት በቀርእኛን ለመሰሉ ተማሮች አሳቡ ሳይገባቸው እንዲያው ይቀር ነበር ፤ ዛሬ ግን ለቀደመው አባታችን በግዕዝ ሐዕዋ ለህንደኬ ንግሥት ኢትዮጵያ ብለን የምንጠራው (ማለት ጃንደረባ) ትርጕሙን በማያውቀው ቋንቋ እያነበበ ሲሄድ ሳለ ከኢየሩሳሌም ጋዛ ወደሚባል ቦታ በሚያወርድ ምድረ በዳ እግዚአብሔር በመንፈስ አድርጎ ፊልጶስን ትርጕሙን ገልጾ ሊነግረው እንደላከለት እንዲሁ ለኛም ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ሐከከ በሌለው ልብ የጥበብ ጕዳና ጸራጊ ሁነው የኢትዮጵያን ልጆች ከውቀት ለያደርሱን ንባቡን ስናውቀው ትርጕሙ የሚያቅተን የነበረ ግዕዝንም ወዳማሪኛ አስተርጕመው ግልጽ ሊያደርጉልን ሌላም በያይነቱ ለሆነ ጥበብ መሪ ሊሆኑን እግዚአብሔር ባርኮ ሰጥቶናል ስለዚህም የደስታችን ብዛት ወሰን የለውም ።

አራተኛም ፤ ይህንንም የውቀት ምንጭ የሚመነጭበትን የተማሪ ቤት ገንዘባቸውን ፍጹም የነሐሴ ዝናም ይመስል ዕለት ዕለት እያፈሰሱ ስላቆሙልን ደግሞ ከዚያው ገብተን እንድንማር የሚማር ሰው ለምግቡና ለልብሱ በተማሪ ቤት ለሚያስፈልገውም ሁሉ ገንዘብ ሊኖረው ያስፈልገዋል እኛ ግን ይኸን ሁሉ አጥተን ልንቀር የነበር በምሉ ቸርነታቸው ስለሚሰጡን የደስታችን ብዛት ወሰን የለውም ።

አምስተኛም ፤ የቀለም ጓደኞቻችንን ከዚሁ እውቀት ተካፋዮች እንዲሆኑ ብለው የላኩዋቸው አባትና እናት የልጆቻቸውን ፍቅር እያየን የጥበብ ትምሕርትም ከሁሉ የሚበልጥ እንደሆነ ተረድተው በማድረጋቸው ከልጆቻቸው ጋር ባንድ ሁነን እጅግ ደስ ይለናል ።

አጫጭር ግጥም እጽፋለሁ ።

ኦ ክብርት ሀገርነ ኢትዮጵያ ።

በመኑ ወበአምሳለ መኑ አስተማስሎ ለሠናይ ላሀይኪ ። በጽጌ ገዳምኑ ዘጥቅምት ወበልምላሜ ማዕርኑ ዘክረምት ኢረከብኩ አንሰ ዘይትማሰለኪ ። ባሕቱ እጽሕፍ ዕበየ ክብርኪ ። ሐለይኩ አንሰ በዕመቀ ልብየ ። ዕንቍ ወወርቅ ሀቡረ ክልኤሆሙ ሠናየ ።

ለእመ ኮነ ሠናየ ርእየቶሙ ለወርቅ ወለዕንቍ ። እስመ ሃየለ ሠናይታ ለሀገርነ ዘውገ ማዕነቅ ።

ብሀለኑ ሰሎሞን «ጥበብ ተዓቢ እምኑ ኵሉ»። ጽድቅ ውእቱ ኢኮነ ሀሠመ ነገረ ቃሉ ።

ኦ ደቂቀ ኢትዮጵያ ።

ጸሐፍኩ ለክሙ ነገረ ጥበብ በክብር ። ይቤ ዳዊት «አጽንዕዋ ለጥበብ ከመ ኢይትመዓዕ እግዚአብሔር»። መኑ የዓቢ ጥበብኑ ፍቅረ ሀገር።? ለእመ ኢሀሎ ጥበብ ፍቅረ ሀገርኒ ኢይትአመር ተሠርዓወ ሞጣሕተ ጥበብ ደቂቀ ኢትዮጵያ አሕማር ። አምጣነ ዓደወ ባሕረ በምልዓተ እግር ።

ረኪበሙ ሐመረ ዘኢይረከበ ሞገድ ። ወሐመሮሙኒ ውእቱ ተፈሪ ዘኢትዮጵያ ዓምድ ።

ሠናይ ውእቱ ፍካሬሁ ለልሳንከ ጥዑም ። ወአልበ ዘይዌስዮ ለነገረ ቃልከ በዓቅም ። ለአቅርቦ ስብሐተ ኀቤከ እንዘ ጽንዓ ኃይልየ አደክም ።ዓረገ አድባረ አሕምሮ በሰዋስዊከ ግሩም።

«ብጹዕ አንተ ወሠናይ ለከ።» «ብእሲትከ ከመ ወይን ሥሙር ውስተ ጽርሐ ቤትከ ።» «ወውሉድከ ከመ ተክለ ዘይት ሐዲስ ዓውደ ማዕድከ ።»

ዘውእቱ ብሂል ወራሴ መንግሥት ዘኢትዮጵያ ተፈሪ መኰንን
ብሂልየ ፈጸምኩ ፍሥሐ ወልደ ሚካኤል ዘብሔረ አክሱም

ይድረስ ክቶ ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት
የብርሃንና ሰላም ዲሬክተር

እንደምን ሰንብተሃል እኔ ግን እግዚአብሔር ይመስገን ደህና ነኝ ።

ከዚህ ቀደም ልዑል ጌታዬ የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን የጽሕፈቱን ማተሚያ ቤት ሥራው እንደተጀመረ አሳዩኝ።ስለ ሥራው እርቀትና ብዛት በቶሎ ይሠራ አልመሰለኝም ነበር ። አሁን ባለፈው ዘመን ግን በፈቃዳቸው ለመንግሥታቸው ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሉ እርዳታና እውቀት ትምሕርትና ሃይማኖቱን እንዲያጸናላቸው ብለው በግዕዝ ተጽፎ እንዳልተጻፈ ሁሉ ምሥጢሩና ትእዛዙ የምንጠቀምበት ሁሉ ሳይገለጽልን ይኖር ነበር፤ይልቁንም በግዕዝ የሚያስተምሩ ከህናቶች እገሌን እገሌ ጠየቀው እንዳንባባል ብለው ። ያላወቁትም እንዳወቁት መሰለው ይኖሩ ነበር ። አሁን ግን የማቴዎስ ወንጌል ሕዝብ ዘይነብር ውስተ ጽልመት ርእየ ብርሃነ ዓቢየ ወለእለሂ ይነብሩ ውስተ ጽልመት ወጽላሎተ ሞት ብርሃን ሠረቀ ሎሙ እንዳለ ። ጌታችን የኢትዮጵያ አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን እውነተኛው የኢትዮጵያ የብርሃንና የእውቀት የነጻነት መክፈቻ አስተርጉመው ለትልቁ ለትንሹ ለሴቱ ለልጁ እንዲገለጽለት ብለው ለጆሮው መክፈቻ ለዓይኑ ብርሃን ለልቡ መሠረት ለሆኑልን ጌታችን እስከ ዘለዓለሙ ምሥጋናቸው ለልጅ ልጅ አይጥፋ ብዬ እመርቃለሁ ። ደግሞ አንተም ወገናችን የሃገራችን የኢትዮጵያ ልጅ ለብርሃንና ሰላም ጀማሪዋና አሰናጂ ሆነህ ተመርጠህ ዲረክተር ስለ ሆንክ እንኳን ደስ ያለህ እኔም በእውቀትህ ደስ ብሎኛል ልዑል አልጋ ወራሽ ብርሃንና ሰላም ተፈሪ መኰንን ለሀገራቸውና ለድሃቸው ማሠልጠኛና መርጃ ላቆሙት ተማሪ ቤት አሁን ለዕለቱ ያሰበኩትን እርዳታ አስር ወቄት ጥሩ የኢትዮጵያ ወርቅ ሰድጃለሁና ይኸንን አጭር እርዳታ ተቀብለህ እንድታስገባልኝ እለምንሃለሁ። ወርቁንም ተግራዝማች ዘውዴ ነው የምትቀበለው ደግሞ የኢትዮጵያን ታላቂቱን አገሩን የሚወድ አቶ ጨዋቃ ጎሹ የሚባል ሰው ወንድሞቼና ወገኖቹ ቢያውቁለትና ቢከብሩለት የሚወድ ከወለጋ አዲስ አበባ የምንግድባት የምመላለስባት ሐያ ብር ናት ስለዚህም ገንዘብ ባይኖረኝ ድሃም ብሆን መጀመሪያ በኢትዮጵያ ልጆች ስም በሚቆመው የትምሕርት ቤት ማኅበር እንዳልለይ ብዬ ስለ ድህነቴ ብዛት የምሰጠው ባጣ ነው ብሎ እንዳቀመ ሁለት እሩብ ለረዳው እርዳታ ትንሽ ትልቅ ብሎ በማያበላልጠው በታላቁ መሪ ብርሃንና ሰላም የተጻፈውን ቃሉን ባነበው እጅግ ደስ የሚያሰኝ ነው እኔም በጣም ደስ አለኝ አሁንም ልዑል ብርሃኑ ብርሃነ ሰላም ብለው ካወጡለት ከታመነው ጋዜጣ ማኅበር ገብቻለሁና እንደ ደንቡ እንዲመጣልኝ እንደተጻፈው ዋጋውን ሰድጃለሁ ለወደፊቱም ከብርሃነ ሰላም ማህበር የሚገቡትን መኳንንቶቼን በሁለተኛው ወረቀቴ ስማቸውን እስከ ገንዘቡ እሰዳለሁ ።

የወለጋና የዓቢጋር የዓረብ አውራጃ ገጋር ደጃዝማች ብሩ ።

ስለ ሀገር ጥቅም ።

ለክቡራን አባቶቼና ወንድሞቼ ባጭሩ በተቻለኝ ሃሳቤ ለማመልከት ተስፋ አደርጋለሁ የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ብርሃንና ሰላምን ከሉበት ስፍራ ደክመውና ፈልገው ባገራቸው ማግባታቸው ባይኖችን ለማየትና በጆሯችን ለመስማት ብቻ አይደለም በፍጹም ልባችን አግብተን አገራችን ኢትዮጵያ እንድትሰፋና እንድትስለጥን እራሷንም አጥብቃ እንድትችል ብለው ነው እኛም ልጆቿ ብርሃንና ሰላምን መሰረት አድርገን እንድንረዳትና ተስማምተን ተፋቅረን እንድናስከብራት እስዋም ልጆችዋን እንድታከብረን ነው መጽሐፍ ቅዱስ እንደ ሚያስረዳን ሰሎሞን አምላኩን ሲለምን አስተዋይ ልቡና መልክምን መፍረድ ስጠኝ አለው ነገሥት ቀ ምዕ ፫ ቍ ፱ የለመነውን አስተዋይ ልብና ዕውቀት ያለመነውን ጨምሮ ክብርንና ባለጠግነትን ሰጠው ቍ ፲፪ (፲፫) እንዲሁም ዛሬ ኢትዮጵያ አምላኳን ለምና ኖሯል ከጭለማ ወደብርሃን ከፀብም ወደሰላም ከግብዝነትም ወደ እውቀት መድረሻዋን እግዚአብሔር የፈቀደበት ጊዜ ሲደርስ ልዑል ራስ ተፈሪን አልጋ ወራሽ አደረገላት ። እሳቸውም አገራቸውን ለማስፋትና የልጆችን ዓይን ለመክፈት ታጥቀዋል ይልቁንም በጣም ናፍቆታቸው ነው ። ሰነፍ አባት ልጁን ሳያስተምርና ሳይቀጣ በከንቱ ያሳደገው እንደሆነ ልጁ አባቱንም በቁመ-

ሳያገለግል ለራሱም ሳይጠቀም ላገሩና ለመንግሥቱም ሳያገለግል በከንቱ ጊዜው ታልፋለች ፤ ደግና ብርቱ አባት ግን ልጁን አስተምሮ አሰልጥኖ ቀጥቶ ያሳድጋል ፤ ልጁም ላባቱና ለመንግሥቱ ላገሩ እያገለገለ ስሙ ታውቆ ከታላቁ ደረጃ ደርሶ በክብር ይኖራል ።

አሁንም ብርቱው ጌታችንና የዕውቀት አባታችን ልዑል አልጋ ወራሽ እጃቸውን ዘርግተው ልጆችን ለማስተማርና አገር ለማሰልጠን ከጭለማ ወደ ብርሃን ከፀብም ወደ ሰላም ለመምራት ሲደክሙና ሲናፍቁ እኛም ተፋቅረንና ተባብረን ሀሳባቸውን ብንፈጽምና ተምረን ብንረዳቸው ጥቅማችን ለራሳችንና ላገራችን መሆኑን ምንም በዕድሜዬ ልጅ ብሆን በፍጹም እረዳዋለሁ ። ያለፈ ነገር አይቆጭህ እንደሚሉ ሁሉ ከኔ ጀምሮ ሳንማር ጊዜያችን ያለፈብን ሁሉ ብንናደድና ብንቆጭ ያ ያሥር ዓመት ልጅነት ተመልሶ አይገኝም ፡ ይልቁንም ደግሞ ለኛ በጣም የሚያስፈልጉን ከሁሉ የበለጡ ትምርቶች አሉ ። እነሱም ጌታንና አገርን በፍጹም መውደድ መፋቀርንና መተባበርን ማስፋት ነው ። መክብብ ይላል ለሁሉ ጊዜ አለው ም ፫ ቁ ፩ እነሆ የዕውቀት መጀመሪያና የትምርት ጊዜው ልዑል አልጋ ወራሽ ናቸው ፡ ንግሥተ አዜብ እንኳ በሰሎሞን ጊዜ ኢየሩሳሌም ሄዳ ነበር ቢባል ለሀገሯና ለሕዝቧ ጥቅም ፍለጋ ሄደች የሚል ታሪክ አላገኘንም ከዚህ በፊት እንደ ልዑል አልጋ ወራሽ ያለ የልጆችን ዓይን ለመክፈትና ብርሃንና ሰላምን አገሩ ለማግባት የሚጥር አላየንም ።

ብርሃንና ሰላም ተገቡ አገራችን ።
እድሜ ለተፈሪ ሰፋች መንግሥታችን ።
የሰው ደጅ ተመርገጥ ዳነልን እግራችን ።
ተጨፍኖ ሲኖር ተከፈተ ዓይናችን ።
ደስታቸው ይብዛ ለወዳጆቻችን ።

የሺ ጥላ ማሬ ።

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ሎንዶንን በመጎብኘታቸው የተነሣ የእንግሊዝ ንጉሥ የህንድ ንጉሠ ነገሥት የመንግሥታቸውን ማሳሰቢያ ለኢትዮጵያ መንግሥት ፩ መንበር እንሰጣለን ብለው ነበርና በክቡር ሚኒስትራቸው በሙሴ ሺርል ቤንቲግ እጅ በመስከረም ፳፯ ረቡዕ ባ፲፩ ሰዓት ይኸንን ስጦታ ሲያቀርቡ የተናገሩት ምርቃን ።

ግርማዊት ሆይ ።

ከእንግሊዝ መንግሥት የመጣልኝን ትእዛዝ ተቀብዬ ልዑል ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ አምና የእንግሊዝን አገር ሄደው ማየታቸው ለግርማዊ ንጉሤ ለእንግሊዝ መንግሥትና ለእንግሊዝም ሕዝብ ለሰጣቸው ደስታ መታሰቢያ እንዲሆን መንግሥቱ ወደኢትዮጵያ እሰዳለሁ ያለውን ዙፋን ለግርማዊ መንግሥት በማክበር አቀርባለሁ ።

በዙፋኑ ጐን ከእንግሊዝ መንግሥት ለኢትዮጵያ መንግሥት የተሰጠ ስጦታ ነው የሚል ጽፈት እናያለን የንጉሠ ነገሥት ዘውድ በላዩ ላይ ያለበት ዙፋን የግርማ ምልክት ነው ብቅርጽ ሁኖ የምናየው ጽጌ ረዳ ደግሞ ለታላቂቱ ኢትዮጵያ መንግሥት ምሳሌ ከሆነው አንበሳ ጋራ የተያያዘው የእንግሊዝን አገር ውበትና ክብር የሚያሳይ ሕዝብ ሁሉ የሚወደው አበባ ነው ። እነዚህ ምሳሌዎች የታላቂቱ ብሪታንያንና የኢትዮጵያንና መንግሥት በደስታ ላስተሳሰራቸው ወዳጅነት የዘላለም መታሰቢያ እንዲሆኑና በሁለቱ ዋና ገዦች በመንግሥታቸውና በሕዝባቸው መካከል ለዘላለም የቀረበ ወዳጅነት መመራረቂያ እንዲሆኑ እመኛለሁ ።

አሁንም ልዑል እግዚአብሔር በዚህ ዙፋን ላይ በመንግሥቱ ተቀማጭ የሚሆነውን ለዘላለም እንዲባርክና ለግርማዊት ንግሥትና ላልጋ ወራሹም ረጅም ዕድሜና ደህንነት እንዲሰጣቸው የእግዚአብሔርም ሞገስ በኢትዮጵያ መንግሥትና ሕዝብ ላይ እንዲያርፍ ምድሪቱም ፍሬዋን እንድትሰጥና ሕዝቡም መንፈሳዊ ሥራቸውን በዚህ ዓለም እንዲፈጽሙ እለምናለሁ ።

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ የተናገሩት ቃል

ክቡር ሚኒስትር ሆይ ።

በዚህ ቀን ከእንግሊዝ መንግሥት ለኢትዮጵያ መንግሥት የተሰጠውን መንበር በደስታ እንቀበልዎታለን ።

ግርማዊት ንግሥትም ባባታቸው ዙፋን ተቀምጠው የእንግሊዝ መንግሥትና የኢትዮጵያ መንግሥት ፍቅር እንዲጸና መውደዳቸውን ክቡር ሚኒስትር የሚያውቁት ነውና ደስታቸውን ከምስጋናቸው ጋራ እንዲያቀርቡላቸው ይለምኑዎታል ።

ይኸውም የግርማዊ ንጉሥ ፭ኛ ጕርጋ የእንግሊዝ መንግሥትና ሕዝብ የእንግሊዝን አገር ለማየቴ መታሰቢያ የሁለቱን መንግሥት ፍቅር መተሳሰር የማያረሳሳው ምልክት እንዲገለጽ ይህ የወዳጅነት ሀውልት በኔ ምክንያት የተተከለ በመሆኑ ደስታዬ ከልክ ያለፈ ነው ።

ሁለቱም መንግሥቶች የንጉሠ ነገሥት ዘውድ በጃቸው መኖሩን የሚያስረዳና ይህ የምንቀበለውም የጽጌ ረዳ አበባ የተቀረጸበት መንበር የማይደርቅ የጽጌ ረዳ አበባ የሁለቱም መንግሥት አገርና ሕዝብ እንደ ለመለመ የሚኖር የማይረግፍ ፍቅራቸውን ያሳየናልና ይህ መታሰቢያ በመንግስታችንና በሕዝባችን ፊት የማያቋርጥ ደስታ እንዳለው ልንገልጽልዎ ፈቃዳችን ነው ።

እርሰዎም ስመጡበት በዚህ በቅርብ ጊዜያት ሁለት ጊዜ የደስታ ምልክት አቅራቢ በመሆንዎ የታደሉና የምናመሰግንዎ መሆኑን ልንናገረው የግድ ሆነብን ።

አሁንም ይህን ምክንያት ይዘን ለግርማዊ ንጉሥ ፭ኛ ጕርጕርና ለቤተ ዘመዶቻቸውም ሁሉ ረጅም እድሜና መልካም ጤና እንዲሰጣቸው እግዚአቡሔርን እንለምናለን ።

አዲስ የትምርት ቤት ለማቆም ስለታሰበው እርዳታ

ሰው መጀመሪያ ሲፈጠር ሕሊናው ለትምርት የሚስማማና አዕምሮው በትምርት የሚሰፋ ሁኖ ተፈጥሯል ትምርትም ዓይን ይከፍታል ልብ ያነጻል የሀገርን ፍቅር በልብ ያሳድራል ነጻነትን ይሰጣል ይህንንም የመሰለውን የትምርትን ጥቅም የተመለከቱ የኢትዮጵያ ወዳጆች ብዙ ሰዎች አዲሱን የትምርት ቤት ስለ

ማቆም እርዳታቸውን በደስታ እንዳስታወቁ እኛም የውጭ ጉዳይ ምኒስቴር ሠራተኞች ለዚሁ አሳብ ተካፋዮች መሆናችንን ለመግለጽ እንዳቅማችን ይህንኑ አዲሱን ተማሪ ቤት ለማገዝ በያመቱ የምንሰጠውን የእርዳታ ገንዘብ ቀጥሎ እንደተጻፈው በየፊርማችን እናስታውቃለን ።

በኢትዮጵያውያን ማኅበር ለሚቆመው ተማሪ ቤት እርዳታ እንሰጣለን ብለው ፊርማቸውን የሰጡ ሰዎች ። ከ፴፺ቍጥር የመጣ ድምር ፭የምስር ወርቅ ፺ሺ፴፩ ብር ተ፱ ሩብ

አቶ አስታጥቄ ወልደ አማኑኤል ።	፲ ብር
አቶ ይነሡ መግቢያ ፲ ብር ባመት ባመት	፭ ብር
ግራዝማች ማህሌ ።	፲ ብር
ሙሴ ኤድዋርድ ፖጎሪያ ።	፷ ብር
አቶ ሮዩም ወልደ ገብርኤል ።	፩ ብር
አቶ ሞገስ ዓምደ ሚካኤል ።	፭ ብር
አቶ መንገሻ ደጀኔ ።	፫ ብር
አቶ በቀለ ወልደ ማርያም ።	፫ ብር
አቶ ደምሴ ድባቡ።መጀመሪያ	፬ ብር ተ፫ ሩብ
ባመት ባመት።	፭ ብር
ወልደ ማርያም አየለ ።	፻ ብር

የውጭ ጉዳይ ሠራተኞች ።

አቶ ደስ አለኝ ሀብተ ማርያም ።	፲ ብር
አቶ ዘውዴ ታደሰ ።	፲ ብር
ብላታ ኃይለ ማርያም ።	፲ ብር
አቶ በየነ ሽረው።	፲ ብር
አቶ ገብረ ሚካኤል ።	፫ ብር
አቶ ተሰማ ።	፫ ብር
አቶ ምሩጽ ።	፫ ብር
አቶ በላቸው ወልደ አብ ።	፫ ብር

ድምር ፭ የምስር ወርቅ ፺ሸ፱፻፲ ብር ተ፩ሩብ

ማስታወቂያ ።

ስለ ኢትዮጵያ ፍቅር በኢትዮጵያ ለሚቆመው ተማሪ ቤት በፈቃዳችሁ እንሰጣለን ያላችሁትን ቃላችሁን ለማስከበር ገንዘቡም ወለድ እንዲገኝበት በኢትዮጵያ የንግድና የርሻ ማስፊያ ማህበር ዲሬክተር እጅ ላቶ ይታጠቁ ብታስረክቡ የደረሰኙን እርሳቸው ይሰጣሉ ። ይኸውም ሲደረግ ገንዘቡን ያስረከቡ ሰዎች ስም በየሳምንቱ በብርሃንና ሰላም ይታተማል።ለመስጠት አሳቢዎችንም ያተጋል የናንተንም ቃል ያስከብራል።

ገብረ–ክርስቶስ ተክለ-ሃይማኖት
የብርሃንና ሰላም ዲሬክተር ።

ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ስላቆሙት ተማሪ ቤት እርዳታ ። በርሻና በንግድ ማስፊያ በኢትዮጵያ ማኅበር ቤት አደራ ያስቀመጡ ሰዎች ።

አቶ ተሰማ እሼቴ ።	፫፻፲	ብር
አቶ ይታጠቁ ጋረደው ።	፸	ብር
ድምር	፫፻፹	ብር

በኢትዮጵያውያን ማኅበር ለሚቆመው ተማሪ ቤት እርዳታ በርሻና በንግድ ማስፊያ በኢትዮጵያ ማኅበር ቤት አደራ ያስቀመጡ ሰዎች ።

ልጅ አበበ ወልዴ ።	፭	ብር
አቶ ይታጠቁ ጋረደው ።	፲፭	ብር
አቶ ተፈራ በልሁ ።	፲	ብር
ድምር	፴	ብር

የፈላስፎች ቃል ።

ደስታ የሥራ ልጅ ነች ። ሲር ገርን ሉቦክ

የደስታና የክብረት ረዳቶቻቸው እኩል ናቸው ። ሾፔንሆዌር

እድሏን ለማጽናትና ለመፈጸም በምታስብበት ነገር ለተወለዱበት አገር ታዛጋርና ጉልበት ከመሆን በቀር ምን ትልቅ ነገር አለ፡ የሥራችን በዘመናት ሥራ ታሪክ ውስጥ መግቢትጠፊው ፍጥረታችን የማይቀበለው የሚመስል ክብርና ጽናት ያገኛል ። ቡትሩ

ለጨዋታ ብለህ ልጆች እንደሚያነቡት አታንብ ፡ ለመማርም ብለህ ኩሩዎች እንደሚያነቡት አታንብ ። እንዲህ አይደለም ለመናገር ብለህ አንብ ለነፍስህ ከታላላቅ መናፍስት ነጥሮ የወጣ የዕውቀት መጐናጸፊያ አድርግ ። ፍሎበር

ማስታወቂያ

ለራሶችና ለደጃዝማቾች ለሴት ወይዘሮች የሚገባ በያይነቱ ጥሩ ካባ ከኤሮፓ መጥቶልኛል ቤቴም (ባንክ ኦፍ አቢሲንያ) ከእንግሊዞች ባንክ አጠገብ ነውና ይህን ካባ መግዛት ለሚፈልጉ ሰዎች መጥተው እንዲገዙ አስታውቃለሁ። ኢያሱ ዳንኤል

አ ፔ ማርሲያኖ

የፊያት ኩምፓንያ የኦቶሞቢልና የርሻ መኪና በኢትዮጵያ ዋና ወኪል ።



A.P. MARCIANO

Concessionnaire Exclusif pour l'Ethiopie
des automobiles et tracteurs Fiat.

በልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ

መጀመሪያ ዓመት ፡ ቁጥር ፵፪ ።
1re ANNÉE № 42

ሐሙስ ጥቅምት ፭ ቀን ፲፱፻፲፰ ዓ ም።
JEUDI 15 OCTOBRE 1925

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d'Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraissant tous les jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

የጋዜጣው ዲሬክተር ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።
Gabré Christo Taklé Haymanot
Dirécteur

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ፡፡
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ስለ ሰልፍ ማየት ።

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ለሥልጣኔ የቀደመውንና የኋላውን የጦር ሠራዊት ለማበራታት ልቡ ወዶ በመሥራት ወደ ኋላ የቀረውን ወደ ሥልጣኔና አገራችሁን ወደ መርዳት ቶሎ ኑ ተፋጠኑ ለማለት መስከረም ፴ ቀን ቅዳሚት ትልቅ ሰልፍ ተደርጎ ነበር።

ሰልፉንም ሲያዩ የነበሩ መኳንንቶች ክቡር ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ የጦር ምንስትር ።

ክቡር ደጃዝማች ወልደ ገብርኤል የግቢ ሚንስትር
ክቡር ደጃዝማች ጌታቸው ያገር ግዛት ሚንስትር ።
ክቡር ደጃዝማች ሙሉጌታ የገንዘብ ሚንስትር ።
ክቡር ጸሐፊ ትእዛዝ ወልደ መስቀል የጽሕፈት ምኒስትር ።
ክቡር ደጃዝማች ወልደ ሥላሴ
ክቡር ቀኛዝማች ዓምዴ ናቸው ።

ሁለት ሰዓት ተኩል ሲሆን ፍልውሃ ሜዳ በተሰናዳው ድንኳን ልዑል አልጋ ወራሽ በተቀመጡ ጊዜ ሰልፉ እንዲገባ ታዘዘ።የዚያን ጊዜ በአራዳ በትልቁ መንገድ የመጣ የማዘጋጃ ቤት ሠራዊት ያዲስ አበባ ዘበኛ ፤ ደግሞ በቤተ መንግሥቱ በታላቁ በር መንገድ የመጣ የልዑል አልጋ ወራሽ ሠራዊት ሙዚቃ እየተነፋ ወደ ሰልፉ ቦታ ሲሄድ ለጆሮ ድንቅ ለዓይን ብርቅ ሆኖ ነበር ።

፫ ሰዓት ሲሆን የከንቲባ ሠራዊት አስቀድሞ ሰልፉን እንዲያሳይ ተፈቀደለትና ከሜዳው መግባት ጀመረ በፊት በፊት ግራዝማች ማህሌ የሠራዊቱ ጠቅላይ አለቃና አቶ ኢዮብ የፈረሰኞች ወታደር አለቃ እየመሩና ሙዚቃ እያስነፉ መጡና ልዑል አልጋ ወራሽና መኳንንቶቻቸው ባሉበት ድንኳን ፊት ሰላምታ ሰጥተው አለፉ።ግራዝማች ማህሌ ግን ሠራዊቱ በመላው እስኪያልፍ ድረስ ከመካከል በፈረስ እንዳሉ ቁመው ቀጥ ብለው ሰላምታቸውን እንደሰጡ ይመለከቱ ነበር ። ሠራዊቱም ባለቃ ባለቃው ሰልፉን እያሳየ አለፈ

ልጅ በረሄም የአቶ ገብሩ ልጅ ማለፊያ ፈረስ ተቀምጠ ቀርቦ ሰላምታ ሰጥቶ ቁሞ ጭፍራውን ሲያሳልፍ እጅግ አምሮ ይታይ ነበር ። ይህ ሁሉ ሲሆን የመዘጋጃ ቤት ሙዚቃ ነፊዎች ከሜዳው ላይ ሁነው ሙዚቃ ይመቱ ነበር ።

ተከኪ ለባሽ ወታደር በኋላ ሰልፍ የሚማሩ ትንንሽ ልጆች » አዲስ አበባ ያብባል ገና » እያሉ ሰልፋቸውን እያሳዩ አምረው አለፉ ፡፡

ቀጥሎም የማዘጋጃ ቤት ጸሐፊዎች ነጭ ለብሰው ሰልፋቸውን አሳይተው አለፉ ። የልብሳቸውም ጽዳት እጅግ ግሩም ነበር ።ጸሐፊዎችን አስቀድመው ክቡር ከንቲባ ነሲቡና ክቡር ነጋድራስ አስታጥቄ ካፒቴን ባቢኪያንም በፈረስ በፈረስ ተቀምጠው ቀርበው ሰላምታ ሰጡ ። ክቡር ከንቲባ ነሲቡና ክቡር ነጋድራስ አስታጥቄ።ለሥልጣኔ መጓጓታቸውን የሚገልጥ የለበሱት ልብስና የወርቅ ጌጥ ለሥልጣኔ የሚያነቃቃ ስለሆነ በወርቅ ላይ የተደረበ ወርቅ መስሎ ይታይ ነበር ።

በ፫ሰዓት ተ፳ ደቂቃ የልዑል አልጋ ወራሽ ሠራዊት በፊት በፊቱ ሙዚቃ እየተነፋ ግሩም ሆኖ አምሮ ሳያቋርጥ ገጥሞ የተስማማ አካሄዱን እያሳየ ቀረበ።አ ካሄዱም በሙዚቃ እየተመራ አረማመዱ ከሙዚቃው ድምፅ የተስማማ ነበር ። ግራዝማች ገብረ ዮሐንስ በፈረስ ተቀምጠው በልዑል አልጋ ወራሽ ፊት ሰላምታ ሰጥተው ባለፉ ጊዜ ወታደሩም በያለቃው ሰላምታ እየሰጠ አለፈ ።

ቀጥሎ የአርመን ልጆች ያማረ ዜማ በሙዚቃ እያዜሙ ዓየሩን እያነዋወጡት በመትረየስ አንጋች ፈረሰኛ ፊት ፊት ሁነው መጡ ፤ መትረየስ አንጋች ፈረሰኛም ፈረሱን

ክርክም እያስረገጠ ሰማያዊ ልብስ ለብሶ ከሜዳው ጥልቅ ባለ ጊዜ በሰልፉ መካከል ልዩ ሆኖ ታየ። ፈረሰኞቹንም አቶ መኰንንና ልጅ በዛብህ እየመሩ ቀርበው ሰላምታ ሰጥተው አለፉ ፤፤

ከዚህ በኋላ የማዘጋጃ ቤት ፈረሰኞችና የልዑል አልጋ ወራሽ ፈረሰኞች ግራና ቀኝ ሆነው ልዑል አልጋ ወራሽ ባሉበት ድንኳን ፊት ለፊት ቆሙ፡ የዚያን ጊዜ እግረኛ ወታደር እሜዳው ላይ የጦር ሰልፍ ሥራ እየሮጠ ኰብ ኰብ እያለ መሄድ፥ ቁሞ ተንበርክኮ ተኝቶ መተኮስ አሳየ። ግራዝማች ገብረ ዮሐንስም የጦሩን ሰልፍ ትእዛዝ ሲሰጡ እንደ አንበሳ ድምፅ ድምፃቸው ሞገስ ነበረው ። እንደዚሁም ደግሞ የማዘጋጃ ቤት ወታደር የሰልፍ ሥራውን አሳየ ።

፬ት ሰዓት ሲሆን ሠራዊቱ ሁሉ ድንኳኑን ከቦ ቆመ። ከዚህ በኋላ በየማዕርጉ ሽልማት ተጀመረ። የተሸለሙ ሰዎችም ቀጥሎ የተጻፉት ናቸው ።

የማዘጋጃ ቤት ከንቲባና ሹማምት ሽልማት ።

ከንቲባ ነሲቡ	ሁለተኛ የክብር ኒሻን ።
ነጋድራስ አስታጥቄ ።	ሶስተኛ ኒሻን (ባላምበል)
ግራዝማች ማህሌ ።	ሶስተኛ ኒሻን (አምበል የሌለው)

ሻምበሎች

ልጅ በርሄ ።	ባላንበሳ	ወርቅ ።
ግራዝማች አማረ ።	ባላንበሳ	ወርቅ ።
ባሻ ደነቀ ።	ባላንበሳ	ወርቅ ።
ባላምባራስ ማዘው ።	ባላንበሳ	ወርቅ ።
ባሻ ተሰማ ።	ባላንበሳ	ወርቅ ።
ባላምባራስ ዘለቀ ።	ባላንበሳ	ወርቅ ።
ባሻ ደፋሩ ።	ባላንበሳ	ወርቅ ።
ፊታውራሪ ረዳው ።	ባላንበሳ	ወርቅ ።
ባሻ ገሠሠ ።	ባላንበሳ	ወርቅ ።
ባሻ ወልደ ጊዮርጊስ ።	ባላንበሳ	ወርቅ ።
ባላምባራስ ደጀኔ ።	ባላንበሳ	ወርቅ ።
ባሻ ካሣ ።	ባላንበሳ	ወርቅ ።
ባሻ ጣሰው ።	ባላንበሳ	ወርቅ።

የገንዘብ ሹም ።

አቶ ከበረ ።	ባላንበሳ	ወርቅ ።

የፈረሰኞች ሹም ።

ዓቃ ኢዮብ ።	ባላንበሳ	ወርቅ ።

የተሸለሙ ፈረንጆች ።

ካፒቴን ባቢኪያን ።	ባላንበሳ	ወርቅ ።
ሙሴ ሚናስ መሐንዲስ ።	ባላንበሳ	ወርቅ ።

የማዘጋጃ ቤት ሠራተኛ።

ሙሴ አርስቲዲሞስ ።	ባላንበሳ	ወርቅ ።

የመቶዎች

ባሻ ወልደ ሰማያት ።	ባላንበሳ	ብር
ባሻ አብጤ ።	ባላንበሳ	ብር
ባሻ ወልደ ማርያም ።	ባላንበሳ	ብር
ባሻ ወልዳረጋይ ።	ባላንበሳ	ብር
ባሻ ገብርነህ ።	ባላንበሳ	ብር
ባሻ ወልደ ጊዮርጊስ ።	ባላንበሳ	ብር
ባሻ አሉላ ።	ባላንበሳ	ብር
ባሻ ጋረደው ።	ባላንበሳ	ብር
ባሻ አየለ ።	ባላንበሳ	ብር
ባሻ ቸኰለ ።	ባላንበሳ	ብር
ባሻ አባደራድ ።	ባላንበሳ	ብር
ባሻ ኪዳኔ ።	ባላንበሳ	ብር
ባሻ ተፈሪ	ባላንበሳ	ብር
ባሻ ወልደ ጊዮርጊስ ።	ባላንበሳ	ብር
ባሻ መኰንን ።	ባላንበሳ	ብር
ባሻ በቀለ ።	ባላንበሳ	ብር
ባሻ ወልደ ትንሣኤ ።	ባላንበሳ	ብር
ባሻ የምሩ ።	ባላንበሳ	ብር
ባሻ ጥላዬ ።	ባላንበሳ	ብር
ባሻ በላይነህ ።	ባላንበሳ	ብር
ባሻ መኰንን ።	ባላንበሳ	ብር
ባሻ አጐናፍር ።	ባላንበሳ	ብር
ባሻ ዘለቀ ።	ባላንበሳ	ብር
ባሻ እንዳለ ።	ባላንበሳ	ብር
ባሻ ወልደ አረጋይ ።	ባላንባሳ	ብር
ባሻ ወልደ ዮሐንስ ።	ባላንበሳ	ብር
ባሻ አበበ ።	ባላንበሳ	ብር

ከልዑል ኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ዘበኞች የተሸለሙ ሹማምት።

ግራዝማች ገብረ ዮሐንስ ሶስተኛ ኒሻን (አምበል የሌለው)።

አቶ እጅጉ ኃይሉ ።	ባላንበሳ	ብር ።
አቶ ገብረ ሚካኤል በላይነህ ።	ባላንበሳ	ብር ።
አቶ መብራቱ ጓንጉል ።	ባላንበሳ	ብር ።
አቶ ጣሹ ተሰማ ።	ባላንበሳ	ብር ።
አቶ በላቸው ሉሜ ።	ባላንበሳ	ብር ።
አቶ ማዘው ወደሬ ።	ባላንበሳ	ብር ።
አቶ ሀብተ ሥላሴ እጅጉ	ባላንበሳ	ብር ።
አቶ የዱ ስንበቱ ።	ባላንበሳ	ብር ።
አቶ ዓለሙ ማዘው ።	ባላንበሳ	ብር ።
አቶ ገብረ መድኅን በላቸው	ባላንበሳ	ብር ።
አቶ ጨርቆስ እሬቦ ።	ባላንበሳ	ብር ።
አቶ ጉተማ ገቾ ።	ባላንበሳ	ብር ።
አቶ ገብረ ማርያም ተሰማ	ባላንበሳ	ብር ።
አቶ ዓለሙ ወልደ ጻድቅ	ባላንበሳ	ብር ።
አቶ ደማም ወልደ ጻድቅ ።	ባላንበሳ	ብር ።
አቶ አረጋ ገንበሬ ።	ባላንበሳ	ብር ።
አቶ ተሰማ ዘርፉ ።	ባላንበሳ	ብር ።
አቶ አየለ ወልደየስ ።	ባላንበሳ	ብር።
አቶ መሾሬያ ባሌጎ ።	ባላንበሳ	ብር።
አቶ ሙሐመድ ስሌ ።	ባላንበሳ	ብር።
አቶ አበበ መርን ።	ባላንበሳ	ብር።
አቶ ደማ ጅቦ ።	ባላንበሳ	ብር።
አቶ ደና አጋ ።	ባላንበሳ	ብር።
አቶ ደሬስ መሐመድ ።	ባላንበሳ	ብር።

የሙዚቃ ሹም ።

ሙሴ ኬወርክ ናልባንዲያን	ባላንበሳ	ወርቅ።

የመትረየስ ዘበኞች ሹሞች ።

አቶ መኰንን ።	ባላንበሳ	ወርቅ።
ልጅ በዛብህ።	ባላንበሳ	ወርቅ።

ከሽልማት በኋላ ከንቲባ ነሲቡ ዘማኔል የሚከተለውን ቃል ተናገሩ ።

ልዑል ሆይ ።

፩ኛ የአዲስ አበባ ዋና ከተማዎን በጥሩ ልቤ እንዳገለግላት በኢትዮጵያ ንግሥትና በራስዎ ስም ሁነው ስላዘዙኝ በከተማይቱ ላይ የዘበኝነት ሥራ ሥልጣኔ እንዲነግሥባት በማድረግ በበታቼ ካስጠጉልኝ ሹማምንቶችዎም ጋራ ሁኜ በማበርና በመረዳዳትም ጭምር በጥቂት በጥቂት እያሻሻልሁ

የሄድሁ ይመስለኛል ዳሩ ግን የልዕልና ዕውቀትዎ በርግጥነት ያልመዘነውን ነገር አደረግሁ በሚል ሃሳቤ መንቃቃትና መተንፈስም አይገባኝም ።

፪ኛ አሁንም እነሆ በኛ አንደበት ብቻ ለመናገር የማንችለውን የሥልጣኔ መሪነትዎን ሥራ በየጊዜያቱ እያደሱት መሄድዎን ለመግለጽ የመጀመሪያ ዋና ከተማዎን የሚጎበኙ ታማኝ ዘበኞችዎን አስተካክለው እንዳቆሟቸው ያውቃሉና ስለዚህም ያሰለጣጠናቸውን ደረጃ ለመቀጸል ፈቃድዎ እንደሆነ እንዲያውቁ ሲሉ የቀኝ ዓይኖችዎ ብርሃን በፊት ለፊት እያደነቁ ይመኟቸዋል ስለዚሁም ባስረኛው ምዕራፍ ከ፩ እስከ ፪ ቁጥር ሲራክ ያለውን ቃል እንጠቅሳለን ። ንጉሥ ጠቢብ ይኄሥጽ ሕዘቢሁ ወመኰንን ለባዊ ይገብር ሥርዓተ እንዳለ ።

ትርጉሙ ብልህ ንጉሥ ሠራዊቱን ስርቶ ቀጽቶ ያሳድራል አዋቂም መኰንን የገሌ ዶብቃ የሚል ሥርዓትን ይሰራል አለ

ሁለተኛ ከመ መልአከ አሕዛብ ከማሁ ወአሊሁ ወከመ መኰንና ለሃገር ይገብሩ እለ ውስቴታ እንዳለ ።

ትርጉሙ ሠራዊቱ እንደንጉሣቸው አኳሆን ይሆናሉ ባገርም ያሉት እንዳገረ ገዢዋ ያደርጋሉ ብሏልና ።

፫ኛ ካለፈው ዓመት በሚበልጥ አኳሆን የማዘጋጃ ቤት ዘበኞችዎን እርምጃ አሁን በቅርብ ቀን እንደተመለከቷቸው ደስ ያልዎ ይመስለናልና ብለን ለማስረገጥ እንዲመቸን ሲሉ በቅንነት ሃሳብና በደግነት ፍፋቶትዎ ዛሬም ደግመው በተለየ ስፍራ ይኸው ጐበኙዋቸው ።

፬ኛ ይኸውም የከተማዪቱና የኢትዮጵያ ያገሪቱም አውራጃዎች ሁሉ በመላቸው የስልጣኔን መሠረት እያጸኑና እያጠኑም ለመሄድ መዘጋጀታቸውን ጊዜው ያስረዳናልና ሳንሰንፍ ሳንዘነጋ በጌታችን ጥላ ጥቂት በጥቂት አረፍት በማድረግ እየተነፈስን ሕግና ስልጣኔን አስተካክለን ለማጋነንና ለማቋቋም ስንል እንዲሁም ወደፊት በሰውነታችን ሥራ አረጋግጠን እንድንገፋ ሙሉ ተስፋ ይኖረናል ።

መጨረሻ የልመና ሃሳቤን በሚጠብቅ አርአያ ለዕውቀት መሪ ጌታዬ በቀጥታ ስነግርዎ ሳለሁ ወደፊት የምንራመድበትን ያጋዠነትዎን ሥልጣን በዘበኞችዎ ላይ እንዲያደርጉት የተሰናዱ መሆንዎን የአያያዝዎ ሁኔታ በጣም ያስረዳኛልና ስለዚህ ይህቺን የዛሬዋን ሙሉ ዠንበር ማለት ስለ ዘበኞችዎ ፍቅር ሲሉ ሥራ ያፈቱበትን ቀን ምክንያት አድርጌ በኔም በራሴና በከተማይቱም ስም ሁኜ እንደዚሁም ደግሞ በታመኑ ዘበኞችዎና በሹማምንቶቻቸውም ምሳሌ ጭምር በመሆን ቁሚያለሁና ስለዚህ ያንድነት ቃላችንን ከፍ አድርገን ለመዘመር ለኢትዮጵያ ንግሥታችንና ለልዑልነትዎም ከበሬታ ምሥጋናን ስናቀርብ በፊጣሪያችን ፊት በጣም ደስ ይለናል ።

ከዚህ ሌላ ደግሞ ለመጠቅለያው ምኞት እስካሁንም ድረስ በነጻነት እንደኖረች እንግዴህም ለወደፊት አገራችን ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር ደግሞም መንግሥታችን አይናወጽብን ብዬ እጨርሳለሁ ።

ልዑል አልጋ ወራሽም ላለቆቹና ለሠራዊቱ የሚያበረታ ቃል ቀጥሎ እንደ ተጻፈው ተናገሩ ።

ሰው በሠራው የራሱ ባልሆነው በሚያምር ነገር ከመቅናት የራሱን መጥፎ ወደ ማለፊያ እንዲሄድ መጣጣርና ማሳመር ይበልጣል። ምንም ክፉ ቢሆን መጥፎው ልማድ ለጊዜው ማለፊያ መስሎ ይታያልና ስንፍናም መጥፎውን ማለፊያ ነው ብሎ ለመናገር አጋጋር ይሆነዋል ።

አሁን ለምሳሌ ከዛሬ አርባ ዓመት በፊት የነበራችሁት ባይናችሁ ፡ ከዛሬ አሥራምስት ዓመት ወዲህ ያላችሁት በጆሯችሁ እንዳያችሁትና እንደምትሰሙት ብዙው ደግ መስሎ ይታይ የነበረው ልማድ ከተሰራ ወዲያ መጥፎነቱ እየተመሰከረበት የቀረ ሊቆጠር አይቻልም ። ለዘመዱ ፡ ለወዳጁ ፡ ለጉዳዩ ብራና ተፈልጎ ጸሐፊ ተለምኖ ተጽፎ በወር ሐረርጌ ድረስ ተልኮ ጉዳይ ይጨረስ የነበረው በ፩ቀን እንዲደርስ ባቡሩ የተሰናዳ ሲሆን አባቱ አለዚያ ልጁ እንዲጽፍ የጊዜው አኳሁን ስለ ፈቀደለት እንደዚሁም ሁሉ የጊዜው ጉዳይ ባጭሩ ይፈጸማል። መልከም ነገር ሁሉ ይሰራል የልብ መፍቅድ ሁሉ ይፈጸማል። ስለዚህም ቀድሞ በሀገራችን ባቡር የለም ነበረና በበቅሎ እንሄዳለን ወረቀት የለም ነበረና በብራና እንጽፋለን ጉዳያችንም በቶሎ አይፈጸምልን የሚል ሰው አይገኝም ። በስልኩም በባቡሩም ሳያቋርጥ ይሰራበታል ።

ሁለተኛም ፡ ቱርኮች ከፈረንጆች የሐረርጌ እስላሞች ከቱርኮች ተምረው ዶርያ የሚባል ዘበኛ በሐረር እንዳቆሙ ልዑል ራስ መኰንን ለጃንሆይ አጼ ምኒልክ ቢያሜውቷቸው ወደ እዚህም ስደድልኝ ብለዋቸው እነዚህ ዶርያ የሚባሉ ዘበኞች በአዲስ አበባ በመጡ ጊዜ እንደዚህ ያለው የዘበኛ አኳሁን ቢቆም ሰው ሁሉ በጣም እንደ ተደነቀ እንሰማለን ። ምንም ለመጀመሪያው ቢያስደንቅ እስካሁን የነበረውን በከተማ ውስጥ ተኩሱን ሌብነቱን ማንም ያውቀዋል የፊተኛውንና ያሁኑን አኳሁን ለማመሳሰል እንኳ አይቻልም ።

አሁንም ሰው በየጊዜው የሚሻል ነገር ለማድረግ መጣጣር መሥራት ይገባዋልና የከተማውን ጥበቃ እምነት በናንተ ላይ መጣላችን ከናንተ አዲስ ከገባችሁት በፊት የዛሬ ፬ ፭ ዓመት የገቡት ሠራተኞቻችን ስለ ጠቀሙን በጥቅማችን ላይ ጥቅም ለመጨመር ነውና የመረጥናችሁ ። ጠባቂነት የተሾመ ሰው ትሕትና መታመን ሰው አያውቅብኝም ብሎ ሠርቶ ልብ እንዳይወቅሰው መሆን ይገባልና ለዚህ የታመናችሁ እንድትሆኑ እንለምናችኋለን ።

ደግሞ ምናልባት ከናንተ ውሥጥ አንዳንድ ሰው ኮት በመልበሱ ሰልፍ በመማሩ የሚያፍር እንዳለ ከንቱ አሳብ መሆኑን ተረዱት ። ይልቅ ለወታደር የሚገባውን በሚገባ ሠርቷልና ይመሰገናል እንጂ የኢትዮጵያ ሰው ወደናንተው ኑሮ ይመጣል እንጂ ለወታደርነት የሚገባው ለሥራ የሚቀለጥፈው ልብስ ቀርቶ ለወታደርነት የማይገባ የኖረው ልማድ አይመጣባችሁም ።

ሰው አንድ ሰው እንኳ እንዲያምነው ብዙ ይጥራል ። እናንተ ግን የምትታመኑበትን ሥራ ሰርታችሁ በከተማ

ነዋሪው ሕዝብና ከውጪ የሚገባውና የሚወጣው ሰው ሲያምናችሁ ክብራችሁ እንደምን ትልቅ ይሆን፤ሊገመት የማይቻል ነው።ከዚህ ቀደም እንዲህ ሳትበዙ መጀመሪያ ጀማሪ የሆናችሁት ግራዝማች ሣህሌም ለዚህ ሥልጣኔ ሥራ መጀመሪያ ለዘበኛ አለቃ ሆናችሁ ስለጀመራችሁት አመሠግናችኋለሁ ።

ይኸው አሁን ዛሬ ሳለፈው መስቀል አለቃችሁ ከንቲባ ነሲቡ የመልካም ምሳሌ መሪ ለመሆን ያደረገው መልካም የሥልጣኔ መግለጫ አለባበሱን ባየን ጊዜ ደስታችን ከልክ ያለፈ ሆን ።

እነ ግራዝማች ገብረ ዮሐንስ የዛሬ ፲፰ ዓመት ከሀገራቸው ወጥተው እሰው አገር ሔደው አገልግለው ቢመለሱ ጓደኛ በማጣት እንሰው የሚያገለግሉት እንደማያገለግሉ ሆነው ተረስተው የነበሩትን ትንሾቹን ሰብስቤ የመትረየስ ዘበኞች ባደርጋቸው እናንተን የመሰለ ጓደኛ አግኝተው ይኸው እንደምታዩት በዙ እንጅ አላነሱም ፡፡

እናንተም የዛሬ ዓመት በየአውራጃው ሰፍቶ በዝቶ የሚመስላችሁ ጓደኞችሁ እንዲታይ የታመነ ነገር ነው በርቱ ፡፡

አሁንም የመከርኋችሁን ቃል ማሳሰቢያ በመጀመሪያው ክብር ይህን በማግኘታችሁ ለሚመጣው ዓመት መልካም ሥራ ሰርታችሁ ከፍ ወዳለው ማዕርግ እንድትደርሱ ማበራታ ይህን ኒሻን በደረታችሁ ላይ ሳደርግላችሁ ከልቤ እጅግ ደስ እያለኝ ነው ፡፡ እግዚአብሔር ለንግሥታችን ረጅም እድሜ ። ለኢትዮጵያ ሀብትና ልማት እንዲሰጥ እንለምናለን ብለው በጨረሱ ጊዜ ረጅም ጭብጨባ ተጨበጨበ ።

በ፰ ሰዓት የሰልፉ ሥራ ተጨረሰና ልዑል ከነመኳንንቶቻቸው በኦቶሞቢል ሁነው ወደቤተ መንግሥቱ ገቡ ።

ከዚህ በፊት እንዲህ ያለ ነገር በሀገራችን ስላልተደረገና መጀመሪያ ስለሆነ ድንቅ ነገር ሆኖ ታይቶናል።አጀማመሩ እንደኛ እንደኛ እጅግ መልካም ነው ። በሌሎች ዓይን ግን ገና የወጣኒም ያህል አይደለን።ስለዚህ የየአውራጃው አገረ ገዢዎች መኳንንቶች ገና መሆናችንን ከወቃችሁ የሰለጠነና ሰልፍ የተማረ ወታደር እንዲያስፈልግ ከተረዳችሁ፡ከተማረውና ከሰለጠነው ወታደር አስተማሪ እየተቀበላችሁ ለየሠራዊታችሁ የሥልጣኔ ሰልፍ እንድታስተምሩ ብርሃንና ሰላም ይማልዳችኋል ።

የኢትዮጵያ ያገራችን ሰውም ከባሕርዩ ፈጣንና ጀግና ስለሆነ የሚያሳየው ካገኘ እንኳን የወታደር ትምርት ምንም እንዳያቅተውና እንዳያቆየው የታወቀ ነው ።

ይድረስ ከክቡር አቶ ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ሹም ።

ሰላም ለርሰዎ ይሁን ስንል የከበረ ሰላምታ እናቀርባለን በልጅ ሲራክ ኅሩይ በኩል የመጣልን ጋዜጣ (ብርሃንና ሰላም) ደረሰን እግዚአብሔር ይስጥልን ብለን እናመሰግናለን ። ያጼ ቴዎድሮስ ዘውድ እንግሊዞች ዘንድ የነበረው በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በልዑል አልጋ ወራሽ እጅ ገባ የሚል አንበንበት እጅግ ደስ አለን ። ለኢትዮጵያም ውጭ አገር ሄደው ከዓለሙ ሁሉ በፍቅር ላስተሳሰሯት ጌታችን እድሜ ይስጥላት ብለን እግዚአብሔርን እንለምናለን ለወደፊቱም በብርሃንና ሰላም እንደዚሁ ያለ የደስታ ነገር እንድንሰማ ተስፋ እናደርጋለን ብርሃንና ሰላምም የኢትዮጵያን ልጆች በፍቅር አስተሳሳሪና ብርሃኑም የማይጠፋ እያብረቀረቀ የሚሄድ እንዲሆን ምኞታችን ነው በውስጥዎ በማተሚያ ቤት ለሚሰሩ ሁሉ ምስጋና እናቀርባለን ለወደፊቱም ለጌታቸው አገልግሎትና ለሐገራቸው ጥቅም የሆነ የጀመሩትን ስራ እያሰሩን እንዲሄዱ እንመኛለን ። በሕይወት ያገናኘን ።

ፈረንሳዊ ትምሕርት ቤት ያሉ የኢትዮጵያ ልጆች ።

ስለ ክቡር ብላታ ኅሩይ መምጣት ።

ክቡር ብላታ ኅሩይ ከኢትዮጵያ መንግሥት ተልከው ወደ አውሮጳ ሔደው መልክታቸውን ፈጽመው በመስከረም ፳፱ ቀን በ፲፩ ሰዓት አዲስ አበባ ሲገቡ።ክቡር ከንቲባ ነሲቡ ዘበኛውን አሰልፈው ብዙ ሌሎች መኳንንቶችና ብዙ ወዳጅቻቸውም አክብረው በደስታ ተቀበሉዋቸው ። ብርሃንና ሰላምም እንኳን በደኅና ገቡ ይላል ።

የሰርግ በዓል ።

በጥቅምት ፩ ቀን ክቡር ከንቲባ ነሲቡ የፊታውራሪ ባብቹና ልጅ ማዳሙዋዜል ማሩሲያን አገቡ።የተክሊሉ ሥርዓት በቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ተደረገ ሰርጉም አምሮ ተከናውኖ በደስታ ተፈጸመ ፡፡ መጋባታቸውን እግዚአብሔር እንዲባርከው ብርሃንና ሰላም ይመኝላቸዋል ።

ማስታወቂያ

ለራሶችና ለደጃዝማቾች ለሴት ወይዘሮች የሚገባ በያይነቱ ጥሩ ካባ ከኤሮፓ መጥቶልኛል ቤቴም (ባንክ ኦፍ አቢሲንያ) ከእንግሊዞች ባንክ አጠገብ ነውና ይህን ካባ መግዛት ለሚፈልጉ ሰዎች መጥተው እንዲገዙ እስታውቃለሁ ። ኢያሱ ዳንኤል

አ ፔ ማርሲያኖ

የፊያት ኩምፓንያ የኦቶሞቢልና የርሻ መኪና በኢትዮጵያ ዋና ወኪል ።



A.P. MARCIANO

Concessionnaire Exclusif pour l'Ethiopie des automobiles et tracteurs Fiat.

በልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ

መጀመሪያ ዓመት ፡ ቁጥር ፵፫ ።
1re ANNÉE № 43

ሐሙስ ጥቅምት ፲፪ ቀን ፲፱፻፲፰ ዓ ም።
JEUDI 22 OCTOBRE 1925

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraissant tous les jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

የጋዜጣው ዲሬክተር ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።
Gabré Christo Taklé Haymanot
Diréctcur

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሲገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ በዓል አከባበር ።

ጥቅምት ፭ ቀን ያቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስን በዓል ለማክበር ግርማዊት ንግሥትና ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ከመኳንቶቻቸው ጋራ በብዙ ሠራዊት ታጅበው ሁለት ሰዓት ሲሆን በቤተ ክርስቲያን ገቡ፤ ሁለት ሰዓት ከሥራምስት ደቂቃ ሲሆን ቅዳሴ ገቡ ፡ ሶስት ሰዓት ተኩል ከቅዳሴ ወጡ በአራት ሰዓት ታቦት ወጣና ዑደት ሆነ ደብተሮቹም ያማረ ያማረ ሸልማታቸውን ለብሰው ሲያስረግጡ ድንቅ ሆነው ይታዩ ነበር ከዑደት በኋላ እጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ደስ የሚያሰኝ ምክር መከሩ ቃሉም ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈው ነው ።

ወንድሞቼ ሆይ በዛሬ ቀን በከንቱ የተሰበሰብን አይምሰላችሁ በዚህ ቀን አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ አገራቸውን ትተው ክብር የተቀበሉበት ቀን ነው፤አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ደግ ሥራ በመሥራታቸው ሃይማኖታቸውን በማጽናታቸው ክብር አገኙ እኛም እግዚአብሔርን በምሉ ልባችን እንውደደው ሃይማኖታችሁ የጸና ይሁን።አባቶቻችን ሃይማኖትን መሰረት ምግባርን ሕንፃ አድርገው ያቆዩንን ሃይማኖት ብንከተል የነሱን ክብር እንድናገኝ የታወቀ ነው ። እነሱማ ብዙ ትሩፋት ሰርተዋል ፤ እኛም ደግ ሥራ የሰራን እንደሆነ ለየራሳችን ብዙ ክብር እናገኛለን ። አባቶቻችን ሃይማኖታቸውን አጽንተው ኢስፍተው ቢኖሩ ክብር አገኙ ።

ደግሞ ከዚህ በኋላ አንድ ነገር አመለክታችኋለሁ ። ሰማችሁ ሰው ሥራ ሳይሠራ ተቀምጦ ከዋለ ኃጢአት ሊሠራ ግድ ይሆንበታል ። ሥራን አትጥሉ ሥራ መልካም ነው አትስነፉ ደግሞ ጊዜው የሥራ ጊዜ እንደሆነ ታውቁታላችሁ ። ሥራ ፈትቶ እየተንጓለሉ ቢውሉ ምን ጥቅም ይገኛል ። ሰዎች የሠሩትንና ያሰናዱትን ሥራ እያየን ከመቅናትና ከመመቅኘት ይልቅ እኛ ብንሠራ ምን ይቸግረናል አገራችን ለምለም ናት ዘወትር ፍሬዋን ትሰጠናለች ለምን እንሰንፋለን ሥራ እንውደድ ሥራ ያልሠራ ሰው ዘወትር እጁን ወደ ልመና እንደዘረጋ ይኖራል ።

እናንተም ከህናቶች መምህራን የሆናችሁት አስተምሩ ። ልጆቹም ተማሩ ጠንክሩ ።

ከዚህ ያላችሁ ሕዝብ ሁሉ በሥራችሁ ላይ አትስነፉ እንኳን በያዛችሁት ሥራ ላይ ይቅርና ጧትና ማታ በደጃችሁ በጓሯችሁ አትክልትም ማናቸውንም ሥራ ለመሥራት አትስነፉ እንዲያው ሲጎላሉና ሲንጓለሉ ቢውሉት ምን ይገኛል ምንድነው ጥቅሙ እስቲ ተመልከቱት ሥራ ብንፈታ ምን እንጠቀማለን ? ተሰብስበን አንድ ቤት ከማየት መሥራት ይሻላል ጌቶቹ የሰጧችሁ ደስ ሲላችሁ ያልሰጧችሁ ሲከፋችሁ ጊዜ እንደምን ይሁን ።

ከዚህ ሁሉ ለየራሳችን ብንሠራ ራሳችንን እንኳ ባንችል እናግዛቸዋለን ። ተቀምጦ መዋል ኃጢአት ነው ደዌውም የሚጸናብን ሰንፈን ተቀምጠን ስለዋልን ነው ፤ ይኸ ጉልበታችሁ ብታከብቱት አፈር ይበላዋል ታዩታላችሁ ወንድሞቻችሁን ከፊታችሁ እየነጠለ ሲወስዳቸው ። እናንተም መኳንንቶቹ አጀብ አነሰን አትበሉ ጥቂት ሰዎች አስከትላችሁ የቀሩትን ሥራ ብታሲዟቸው መልካም ነው ። እንዲያው ሲንጓለሉ ቢውሉ ምን ትጠቀማላችሁ ሥራ ብንሠራ እንድንጠቀም ታውቃላችሁ ለምን እንድንጎዳ ታበባላችሁ።እኔ ደግሞ ይኸን ሁሉ ሐተታ መናገሬ የኔ ዕውቀት ከናንተ ዕውቀት ይበልጣል ማለቴ አይምሰላችሁ ፤ የታየኝን ሐሳቤን አመለክታችሁ ብዬ ነው ።

እግዚአን ኢየሱስ ክርስቶስ ክቡር ሥጋውንና ደሙን ለመቀበል ያብቃን ። ይቅርታውን ይዘዝልን መንግሥታችንን ጽኑዕ ሰላም ያድርግልን ግርማዊት ንግሥታችን ይጠብቅልን

ፍቅረ ሰላም ያውርድልን ብለው አቡን ዘበሰማያት ሰጡ ። አምስት ሰዓት ሲሆን ታቦት ገባ ወዲያው ግርማዊት ንግሥትና ልዑል አልጋ ወራሽ ከመኳንንቶቻቸው ጋራ ሁነው እንደፊተኛው በብዙ ሠራዊት ታጅበው ወደ ቤተ መንግሥት ሄዱ ።

የደጃዝማች ሀብተ ማርያም መልክተኛ ፊታውራሪ ኪዳነማርያም የተናገሩት ንግግር ። ልዑል ሆይ ።

ደጃዝማች ሀብተ ማርያም ፡ እኔ ሐሳቤ ሃምሳ ስልሳ ተማሪ ለመላክ ነበር መቼም በያገሩ የጥንት ልማድ እንጅ ስልጣኔ እንዳይገባ የሚወዱ ስላሉ ቸገረኝ ለወደ ፊቱ ልጨምር ሙሉ ተስፋ አለኝና አሁን የልዑል ጌታዬን ፈቃድ ለመፈጸም እኒህ ፳፫ ተማሪዎች በግሥጋሴ አድርስላቸው ብለው በላኩኝ ጊዜ በ፺ ቀን ከዚህ ገባሁ ። እነዚህም ሕፃናቶች ከደስታቸው ብዛት የተነሳ ፩ ጊዜ ሳይደክማቸው ከኔው ጋር ገስግሰው ገቡ፣ ከኮቱ ላይ የቅጠልያ ምልክት ካለው ልጅ በመለስ ያሉት ልጆች የፈረንሳዊ ትምሕርት ከዚያው ከደጃዝማች ሀብተ ማርያም ተማሪ ቤት የተማሩ ናቸው ። ምልክታቸውንም ቅጠልያ ማድረጌ ኢትዮጵያ ቅጠሏ ደርቆ ሥሯ ሊደርቅ ሳለ በእግዚአብሔር ፈቃድ ተከትለው ደርሰውባት ቅጠሏን ስላለመለሙላት ስለዚህ ምሳሌ ነው ። ፪ተኛ በኮቱ ላይ የብቁዳዳ አበባ ካለበት ልጅ በመለስ ያሉት ሕፃናቶች የእንግሊዝ ፊደል በ፪ኛና በ፫ተኛ ፊደል የሚማሩ ናቸው ።

የነሱም በብቁዳዳ አበባ መመሰሉ ልዑል አልጋ ወራሽ የኢትዮጵያን ልጆች በትምሕርት እንዲያብቡላቸው እርገጥልና ያበበውን እድሚያየው ረዝሞ ከፍሬው እንዲበሉ ሙሉ ተስፋ አለን ። ሶስተኛ ቀይ ከፈይ ከኮቱ ምልክት ካለው ልጅ በመለስ ያሉት ሕፃናት ያማሪኛ ትምርት ጨርሰዋል የቀዩም ከፈይ ምሳሌ የኢትዮጵያ ልጆች ምንም በትምሕርት ከዚህ ቀደም ባይሰለጥኑ ከጥንት ጀምረው ለሐገራቸው ደማቸውን ያፈሳሉ አሁንም ልዑል ሆይ ይህነን ደጉን ሃሳብዎን አምላክ እንዲፈጽምልን በየቤታችን ጸሎት ማድረግ ይገባናል ። ይልቁንም ለኛ ለባሮችዎ ጸሎት እንጂ ዕረፍት አይገባንም ብለው ፊታውራሪ ኪዳነ ማርያም ከመለከቱ በኋላ ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ሕፃናቱን ወደፊታቸው አቅርበው ካገራችን ወጣን ከዘመድ ተለየን የማለት አሳብ አይግባችሁ በሚቻለን ሁሉ እናት አባት ሆነን እንጠብቃችኋለን ብለው ደስ አሰኙዋቸው ። በደጃዝማች ሀብተ ማርያም ገብረ እግዚአብሔር ብልህነትና ትምርት ማስጀመር ወዲያው ፈጥነው እነዚህን ተማሪዎች ወደሡሩት ተማሪ ቤት በመላካቸው አመሰግነው ከተማሪ ቤቱ ነዋሪ እንዲሆኑ በምግብም በልብስም እንደ ደንቡ እንዲደረግላቸው ወደ ክቡር ሃኪም ወርቅነህ እንዲጋጠሙ አዘዙ ።

ወደ ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ ዲሬክተር ክቡር አቶ ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት የተወደዱ ወዳጄ ሆይ በማክበር ሰላምታ አቀርባለሁ ።

በማዚያ ፴ ቀን በጻፉልኝ ደብዳቤዎ ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ በየሳምንቱ እንልክላችኋለን ብለው ያልታሰበ ሙሉ ተስፋ ሕላስታወቁን ምስጋናችንን ጥበብ አዳይ ለሆኑን ለልዑል አልጋ ወራሽ አቅርበን ደግሞም አሰናጂ ለሆኑዋቸው ለርስዎ የሚገባዎን ምስጋና እንዲቀበሉን እለምንዎታለሁ ።

በየሐገሩ ለትምሕርት በልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ገንዘብና በሌላም ነገር ሁሉ እርዳታ ተበታትነን ያለን የኢትዮጵያ ልጆች በሰው አገር ያገራችንን የእየለቱን የእየሳምንቱን የእየወሩን ከነአከታቴውም የዓመቱን መለዋወጥና ወሬ እንደ ዕለት ምግብ ያህል ተርበን ተጠምተን ሳለን በእንደዚህ ያለ ብርሃንና ሰላም በሚባል ለሙሉ ኢትዮጵያ ጥቅም በሚሆን ጋዜጣ በየሳምንቱ እንድንቀበል መዳረጋችን በእውነት መጠን የሌለው ከፍተኛ ደስታ ሆነን ።

እንግዲህ ወደፊት ይኸን ጋዜጣ በየሳምንቱ ከደረሰን ወሬ ጻፉልን እያልን በማባበል የምናደክማቸው የምንጽፍላቸው የማይረባ ማባበያ እረኛጅም ቃል ከየወዳጆቻችን ይቋረጣል ለዚህም ለማይረባ ቃል ወረቀት መጻፊያ የምናጠፋው ሰዓት የፖስታው ገንዘብ ትርፋችን ነው እንደዚሁም ወዳጆቻችንም ያተርፋሉ ።

ምናልባት ለወዳጆቻችን አንዳንድ ጥቂት የምናውቀው ምክር እንኳ ለመጻፍ ብናስብ እኛ የተለየ የወዳጅ ምክር ባለንበት አገር ለሌሉለን ላገራችን ሰው ሁሉ የሚሆን ስለ ሆነ በዚሁ ጋዜጣ ላይ አየጻፍን በጥቂት ሰዎች ይቀር የነበረው ይልቁንም በሙሉ አገራችንን መርዳት እንዲሆንና እነሱም በዚሁ ጋዜጣ ሐሳባችንን እንዲያገኙት ተስፋ አደርጋለሁ።እኛም እንደዚሁ የነሱን ሃሳብ በጋዜጣው እናገኘዋለን ብለን ተስፋ አድርገናል ።

አሁንም ክቡር አቶ ገብረ ክርስቶስ በዚህ በጻፍኩልዎ ወረቀት ላይ ጥቂት ሐሳቤን ቀቅዬ ስለምጽፍ በጻፍኩልዎ ወረቀቱ ላይ የጋዜጣን ትንሽ የጥቅሙን ነገር የተቻለኝን ያህል ወደ ጋዜጣ አንባቢዎቻችን ልጽፍ እወዳለሁና ድርቤ በመጻፌ ይቅር እንዲሉኝ አምናለሁ ።

አሁንም ይህን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላምን ወይም ሌላ ጋዜጣ የምታነቡና የማታነቡ ሰዎች በዚህ በጋዜጣ ዲረክተር በጻፍኩት ወረቀት ላይ ፈቃዳቸውን ለምኜ ጥቅሙን ትንሽ የተቻለኝ ያህል በጭሩ እንደተባለ አመለክታችሁ ዘንድ እለምናለሁ ።

ከብዙኅ ዘመን ጀምሮ ጥቅሙን ፈጽመው ያገኙት ሕዝቦች አገር ጋዜጣ እንዲህ ተብሎ ተመስግኑዋል ሥራውም ተቆጥሯል

የጋዜጣ ማተሚያ ሁሉ ብዙህ ጋዜጣ እያተመ እያወጣ በየለቱ ከተማሪ ቤት ውጭ ሕዝቡን ለማስተማርና ለማሰልጠን እጅግ እርዳታና ምኞት ሰጥቷል ይህን ሁሉ ሕዝብ በውነት የሚበቃ አስተማሪ ተገኝቶ ጋዜጣ ባይኖር ማስተማርና ማሰልጠን በጣም ያስቸግር ነበረ ይባላል፡እንዲህ መባሉ ሕዝቡ ለጉዳዉሲል ሶስት አራት ጋዜጣ በለት በያይነቱ ስለሚያነብ ያለፈውን ታሪክ ባመጣጥና በጥቅስ የለቱንም በየለቱ በጋዜጣው ላይ ስለሚያገኘው ወደፊት እተማሪ ቤት ገብቶ በሚማርበት ጊዜ እንደ መከለስ ያህል ይሆንለታል ስለዚህ ለብዙ ተማሪዎች አንድ አስተማሪ ማስረዳት ምቹ ይሆንለታል ።

ደግሞ ሁለተኛ አንዳንድ ሰዎች ልጆቻቸውን እቤታቸው ማንበብና ለመጻፍ ያህል ያስተማሩዋቸው እንደሆን ፈጽመው እተማሪ ቤት ሳይሄዱ ዘወትር ጋዜጣ በማንበብ ማንበብና ታሪክ ያውቃሉ ሥራም በጋዜጣ ላይ ማስታወቂያ የተጻፈውን እንበው-

የወደዱትን ሥራ እያዘወተሩ በመሥራት እጅግ የረቀቁ አዋቂዎችና ከበርቴዎች ይሆናሉ ። ደግሞም ቀጥሎ እንዲህ ተብሏል ፡

የዛሬ ዘመን ጋዜጣ ማሕበር ሁሉ እጅግ ድንቅ የሆነ ነው ታላላቁ የጋዜጣ ማተሚያ ሁሉ እልፍ አዕላፍ የሚሆን ጋዜጣ ፀየለቱ እያተመ እያወጣ ይሸጣል ምንም አደጋ እሳት ወይም ጦርነት ይኸን የመሰለ ሁሉ ቢመጣ ጋዜጣው መታተሙ አይቆምም እንዲያውም አንዳንድ ጊዜማ ከዘወትሩ የሚበልጥ ሕዝቡ እያሻውና ጋዜጣው እያነሰ ይኸ የጋዜጣ ማተሚያ የሚሠራው ሥራ መጠን የለውም ይባላል ። ለዚህም የጋዜጣ ማተሚያ ብዛቱ በዓለሙ ሁሉ ከአምሳ ስድስት ሺህ ይበልጣል ። ከዚሁም ከሐያ አራት ሺህ የሚበልጠው በአሜሪካ ነው ። በያንዳንዱ ጋዜጣ ማተሚያ በየቀኑ እስከ መቶ ሺህ ድረስ ይታተም ይሆናል ። በዚህ ላይ በወር በሳምንት በመንፈቅ ወይም በዓመት አንድ ጊዜ የሚታተሙ መጻሕፍቶች አሉ ከነዚህም ብዙህ የትምሕርት እርዳታ እንደጋዜጣው ይመጣል ።

የጋዜጣ ሥራዎች ቀድሞ እንደተባሉና እንደተቆጠሩ መጀመሪያ ወሬ መሰብሰብ ። ፪ተኛ ወሬ መንዛት (ማከፈል) ፫ተኛ ሐሳብን መግለጽና ፬ተኛ ሐሳብ ለመፍጠር (ለመጸነስ ።) ደግሞም ሁለተኛ እንዲህ ተብሏል ። የጋዜጣ ሥራዎች ሶስት ሽረቦች ናቸው ። መጀመሪያ ታሪክ መንገር እንደምን እንደተደረገ ። ፪ተኛ ክርክርን ወደፊት በሚሆነው ነገር ማስቀደም ፫ተኛ ወደፊት የሚሆነውን ማሰማት እንዲህ ጋዜጣ ታሪከኛ ትንቢተኛ ተወራራጅ (ተሟጋችና) የጊዜ መለኪያ አውራዶሮ ነው ። ደግሞም ፈጽሞ የዛሬ ዘመን ጋዜጣ ከዚኅ ከተወሰነው ወሰን ይልቅ አልፎ እሩቅ ይሄዳል ።

ከልጆች እስከ ሽማግሌዎች ቤተሰቦች እንዳመል እንዳመላቸው እንደሚአሻቸው እንደትርፍ ምንጭ መልካም ምክር ተረት እንቆቅልሽ ግጥም ስዕል የሚገዛ እቃ ስዕል ሁሉ ልዩ ልዩ አይነት ክፍል ገጽ ምዕራፍ ያገኙበታል ።

ስለዚህ ጋዜጣና የጋዜጣ ማተሚያ ጥቅሙ በብዙህ ወገን ስለሆነ አለጥርጥር ይኸን የተባለውን ጥቅም ከሰጠን በኋላ ደግሞ ላገር ንግድ የርሻ ሥራ ስልጣኔ ለሕዝብ እርቅ እውቀት መተጋገዝ ለማስፋትና የሕዝቡን ነገር ችግር የሕዝቡን ትዳር ችግር ለማጥፋትና መልካሙን ለማሻሻል ። ጉዳዉን አለመዘግየት ለመከራከርና በፍጥነት ለመፈጸም የሕዝቡን ልብ አንድ ልብ አንድ ሐሳብና አንድ ጉልበት ለማድረግ በጣም የሚያሻ ነው

ስለዚህ ስለተባለው ጥቅም ሁሉ ብርሃንና ሰላም እየሰፋና እየበዛ ሕዝቡም ጥቅሙን እያወቁ በብዙ እንዲገዙ በተቀባዎቹም ሰዎች ሁሉ በሚሰጣቸው ጥቅሙ የተወደደና የተመሰገነ እውነተኛ የጥበብ መምሕርና የኢትዮጵያ ሕዝብ የፍቅር ማስተሳሰሪያ ሰንሰለት እንዲሆን ፍጹም ተስፋ አድርጉ እኔም እንደዚሁ ፍጹም ተስፋዬ ነው ።

በሻህ ውረድ ሀብተ ወልድ ።

ከዚህ ቃል የቀረው በሚመጣው ቍጥር ይታተማል ።

ስለ ሐረር ዘብጥያ ወይም ወሕኒ ፡፡

ሰው በተቻለውና ባለው እውቀቱ ላገሩ መርዳት ይገበዋል ነገር ግን እኔ አውቃለሁ ብዬ አይደለም የተዘነጋ ነገር እስታውስ ብዬ ነው እንጂ ።ደግሞ ከዋቂ ሰው ዝንጋታ እንዳይጠፋ ከዚህ አስከትዬ ጽፌዋለሁ ።ይኸም ባንድ ፈላስፋና ባንድ ትንሽ ሴት ልጅ የደረሰ ነው ።አንድ ቀን አንድ ፈላስፋ በጽሬት ቤቱ ሲሠራ ሳለ መዝጊያው ተመታ እርሱም በድንጋጤ ግባ ብሎ ጮኸ ባየም ጊዜ አንዲቱ ልጅ ከጎረቤቱ ናት ።እርስዋም በትሕትና እንዲህ ብላ ጠየቀችው ጌታዬ ሆይ እንዴት አደሩ እናቴ ከርስዎ ዘንድ እሳት እንድወስድላት ላከችኝ ። ልጄ ሆይ እጅግ መልካም ነበር ነገር ግን እሳቱን የምትወስጂበት ምንም እቃ አልያዝሽም ቆይ ለእሳቱ መውሰጃ እንዳችነገር ልስጥሽ አላት

ልጅቱ ግን እንዲህ ስትል በድፍረት ተናገረችው አዬ ለዚህስ ግድም ባልነበረ እኔ እስከዚህ ድረስ ያልተማርኩ አይደለሁም እሳቱን ይፍቀዱልኝ እንጂ ለዚቹን ታህል እውቀት የምጨነቅ አይደለሁም አለቺና እሳቱን ከፈቀደላት በኋላ ወደ ማንደጃው ቀርባ ከበረደው አመድ በግራ እጅዋ አድርጋ ፍሙን በመዳፏ ላይ አስቀምጣ እየሳቀች ሄደች ፈላስፋው በዚህ ነገር ተገረመና በራሱ እንዲህ አለ ከዚህ ሁሉ እውቀቴ እስከ ዛሬ ይህቺን እውቀት አላገኘኋትም አለ ይላሉ ። ነገር ግን ይህቺን ታህል እውቀት አጥቶ አይደለም ልብ ያለማድረግ ነው እንጂ እኔም እንደዚች እንደ ትንሽ ልጅ ሆኜ ለሕዝባቸው የሚጠቅም ያልታሰበ ነገር ለልዑል ጌታዬ አስታውሳለሁ ።

የሐረር ዘብጥያ እጅግ ጠባብና ወሰክ ስለሆነ ተጋቢ በሽታ ገብቶ ሕዝቡን በተቅማጥ ይፈጅዋል ሰው በብዙ ጥፋት እወህኒ ይገባል ከጥፋትም እንዳንዶቹን ስማቸውን እጠራለሁ ።

(በሌብነት በወንበዴነት በዳኝነት ባደብ) በእንደዚህ ያለ ነገር ብዙ ሰው ወሕኒ ይገባል ከነዚህም ጥቂቶች ይድናሉ እንጂ ብዙዎች ይታመማሉ ከታመሙትም ግማሹ ይሞታሉ ታመውም የዳኑት የጥንት ጤናቸውን አያገኙም በሽተኛ ሆነው ይኖራሉ በደህና በደህና ቦታ የሚሆኑ ሰዎች ስለ ብር ተኩል ዳኛነት እየታሰሩ በማለቃቸው በጣም አዝናለሁ ሌባስ ቢሆን ያለ ፍርድ በተቅማጥ ቢሞት ለመንግሥታችን ምን ጥቅም ይገኛል ።ነፍስ ገዳይስ ቢሆን ያለ ፍርድ ተቅማጥ ቢገለው ለሕዝቡስ ምን ቅጣት ሆን ላባላጋሮቹስ ምን ጥቅም ። እኔ ስንኳን በማውቀው በዜች ባንድ ወር ስድስት ወይም ሰባት ሰዎች ይሆናሉ የሞቱት፡እኔም ይህን ብጠይቅ አንዱ ሰው ሰድቦ ዋስ ስላጣ ነበር የታሰረው በታሰረ በሶስት ቀን ሞተ ሶስቱ ባባሪ ተይዘው ሳይረቱ ሁለቱ በሌብነት አንዱ በዳኝነት ነው አሉኝ ። ምናልባት ባንድ ወር ሶስት ቢሞቱ ባመት ምን ያህል እንደሚሞቱ ማሰብ ነው፤ምናልባት ሰላሳ ስድስት ሰው መሆኑ ይመስለኛል ። በኢትዮጵያችን ይኸን ያህል ሕዝብ ማለቁ ባጣም ያሳዝናል ።

የውጭ አገር ሰዎችእማ ወሕኒን በክፍል በክፍል አድርገው ፩ኛ ፪ኛ እያሉ ሰውንም እንደ ኃጢአት እንደ ኃጢአቱ ያስሩታል በ፳ በ፳ ቀን ሐኪም እስረኞቹን ይፈትሻቸዋል ። እነሱ ለሕዝባቸው በጣም ይሳሳሉ በዳኝነታቸው አንዱ ስንኳን ቢሞት ብዙ ጭቅጭቅ አለበት። እንደ ውጭ አገር ሰዎች ስንኳ ባይሆን ሌባ ከጨዋ ጋራ ትንሽ ጥፋት ያለው ብዙ ጥፋት ካለው ጋራ መታሰሩ ቀርቶ ከሐረር ግምብ ውጭ አንድ ትልቅ ወሕኒ ተሰርቶ ለቤቱም ክፍል ክፍል አድርጎ እንደ ኃጢአት እንደ ኃጢአቱ ቢታሰር እጅግ መልካም ይመስለኛል ።

ከዚህ አስከትዬ ፈጣሪዬ በመልክም አመሰግንለዋሁ ።
እግዚአብሔር ይመስገን ክብሩ ይስፋልን ።
ግርግዳው ተፈሪ ጣራዋ መነን ።
እግዚአብሔር ይመስገን ይባረክ መንግሥቱ ።
ግርግዳው ተፈሪ ጣራዋ መነን ናቸ ጉልላቱ ዘውዲቱ ።
እግዚአብሔር ይመስገን እንበል ሁላችን ።
ተፈሪ ከሰጠን ሰላም ተብርሃን ።
መንግሥቱ ይስፋልን ለመድኃኔ ዓለም ።
ተፈሪ ከሳየን ብርሃንና ሰላም ።

አስፋው አበጀ ።

ጥቅምት አሥራንድ ቀን በልዑል አልጋ ወራሽ ችሎት የተፈረደ ፍርድ ።

ጥቅምት ፱ ቀን በሺ ፱፻፲፰ ዓመት በአዲስ አበባ ከተማ ማዘጋጃ ቤት በኩል ባለው ዘብጥያ (ግለት) የእስር ቤት ውስጥ ያሉ እስረኞች ቀን በቀን ሰብረን እናመልጣለን ብለው ጡብ እንስተው የዘብጥያውን አጥር ሰብረው ሊሄዱ ሳለ የዘብጥያው ዘበኛ በምኒልክ በዘውዲቱ በተፈሪ አምላክ ተመለሱና ወደ እስር ቤታችሁ ግቡ ቢሏቸው እምቢ ብለው ሊያመልጡ ሲሉ የዘብጥያው ዘበኞችም ምን ስንሆን እናያለን እስሩስ ሰብሮ ማምለጡ እኛስ መታሰራችን አይደለምወይ ባልጋ በመንግሥት ስንለው እምቢ ካለ በለው ብለው ቢተኩሱ ከነዚሁ ከስረኞቹ ውስጥ የነበሩትን ዋና ዋናዎቹን ሰብሮ ለመሄድ ጡብ ያነሱትን ሶስቱን እስረኞች በጥይት ገደልዋቸው ሁለቱን አቆሰልዋቸውና ከስረኞቹ ጡብ አንሺዎች ወገንና በስረኞቹም ላይ ተኩሰው የገደሉ ዘበኞች ተይዘው በጥቅምት ፲፩ ቀን ወደልዑል አልጋ ወራሽ ዋና ችሎት ቢቀርቡ የስረኞቹ ጥጋብና ሰብረውም ለመሄድ ሲሉ ዘበኛውን ደርበህ በለው ብለው በመንግሥት አምላክ ሲላቸውም እንቢ ብለው ዘበኛውን ጥሰው ሊወጡ በመተባበራቸው ከዘብጥያው እስረኛ ወገን እስራ ስድስት ምስክሮች ከውጭ የነበረ የመንገደኛ አላፊ አምስት ምስክሮች በስረኞቹ ላይ መስክረውባቸው ያደራረጋቸውም የጥፋታቸው መዝገቡ ከተነበበ በኋላ የመንግሥቱ የዘብጥያ ዘበኞች በእስረኛው ተጠባባቂነት የተነሣ እስሩ እንዳያመልጥባቸው ሲሉ የሚገባ የዘበኝነታቸውን ሥራ ስለሠሩ ተመስግነው በዚሁ ምክንያት ከተያዙበት እስራታቸው ተፈተው ወደዘበኝነት ሥራቸው ተመለሱ ።

ግን ከነዚሁም የዘብጥያ እሥረኞች ውስጥ የሞቱትና የቈሰሉት ሰዎች ዘብጥያ የታሠሩበት ኃጢአታቸው አራቱ በባሯ ፈንጋይነት ገብተው አሥራምስት አሥራምስት ዓመት እንዲታሰሩ የተፈረደባቸው ነበሩ ። ሶስቱ ሞቱ አንዱ ቆስሎ አለ አምስተኛው አሁንም የመንግሥት ዘበኛ ደብድቦ የታሰረና አስቀድሞም በብዙ ኃጢአት እየተገኘ እየደበደበና እየቀማም አስቸግሮ የኖረ ነበር ይኸውም ቆስሎ አለ ፤ አሁን ሁለቱም ቈስለኞች እማዘጋጃ ሐኪም ቤት ገብተው ይታከማሉ ።

የፈላስፎች ቃል።

በምትፈግና በምትራራ ፍቅር ላደገ ልጅ እድሜው ሁሉ የሚከተለውና በያለበት የሚያገኘው የፍሥሐ ገንዘብ ይሆንለታል ።

ጉዮ

ከፍጥረቱ እንደተሰጠው ለልጅ ጨዋታና ደስታ ከፍስሐ አሳብ የሚገኝ ነጻነት ሁሉ ማድረግ ያስፈልጋል ልጅ አለደስታ ፀሐይ እንደሌለበት ጥቢና ከንፍ እንደሌለው ቢራቢሮ ነው

ማዳም ኔከር ደሶሱር

ደስታ ሰው ከትንሽ ወደ ትልቅ ፍጻሜ ማለፉን ያመለክታል ሐዘን ግን የሰው የሥራ ኃይሉ መጕደሉን ወይም መሰናከሉን ያመለክታል ።

ስፔኖዛ

ሁላችንም ባለንበት ሌሊት ውስጥ አዋቂዎች ከግምብ ይለጠፋሉ ደንቆሮ ግን እልፍኙ መክከል አርፎ ይቀመጣል

አናቶል ፍራንስ

ማስታወቂያ ።

መንግሥት ያወጣውን ደምቡና ሕግ ሳልተላለፍ ደሀ ሳልበድል ፤ የመንግሥቱን ገንዘብ በጥንቃቄ ሠርቼ ቀድሞም ከሚሠራው ሠራተኛ ገቢ ገንዘብ አብልጬ አገባለሁ የሚል ሰው እርሻና እመስኜ ምኒስቴር መጻፊያ ቤት ፤ ሁል ጊዜ ከጧቱ ከ፫ ሰዓት እስከ ፬ ሰዓት ድረስ፡እየመጣ ቢነጋገር በደስታ እንቀበለዋለን ደመወዙም እንደ ሥራው ገቢ እየታየ ይቈረጥለታል ጥቅምት ፲፩ ቀን ፲፱፻፲፰ ዓመተ ምሕረት።

መኰንን ሀብተ ወልድ

ማስታወቂያ

ለራሶችና ለደጃዝማቾች ለሴት ወይዘሮች የሚገባ በየይነቱ ጥሩ ከባ ከኤሮፓ መጥቶልኛል ቤቴም (ባንክ ኦፍ አቢሲንያ) ከእንግሊዞች ባንክ አጠገብ ነውና ይህን ከባ መግዛት ለሚፈልጉ ሰዎች መጥተው እንዲገዙ አስታውቃለሁ።

ኢያሱ ዳንኤል

አ ፔ ማርሲያኖ
የፊያት ኩምፓንያ የአቶሞቢልና የርሻ መኪና በኢትዮጵያ
ዋና ወኪል ።



A.P. MARCIANO
Concessionnaire Exclusif pour l'Ethiopie
des automobiles et tracteurs Fiat.

በልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ

መጀመሪያ ዓመት ፣ ቁጥር ፵፬ ።
1 re ANNÉE № 44

ሐሙስ ጥቅምት ፲፱ ቀን፤፲፱፻፲፰ ዓ ም።
JEUDI 29 OCTOBRE 1925

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraissant tous les jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

የጋዜጣው ዲረክተር ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲረክተሩ ያስታውቁ ።
Gabré Christo Taklé Haymanot
Diréсteur

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie
Un an 5 Thalers
Etranger
Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ስለቅዱስ እስጢፋኖስ በዓል አከባበር ።

ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን አውሮጳ የሄዱ ጊዜ ልዩ የሆነ አውቶሞቢል ለግርማዊት ንግሥት አሰርተውላቸው ነበርና ከቤታቸው ወደግቢ ይዘውላቸው ወረዱ ።

የዚህም የአውቶሞቢል ሥራው ለግርማዊት ንግሥት በመካከሉ የተለየ እጅግ ያማረና የተጌጠ ለጌጥም የተሰናዳ የተሰራበት የተለየ ሳሎን ነው፤በግንባሩ ነጅው ከሚቀመጥበትና ግርማዊት ንግሥት በሚቀመጡበት መካከል ለሶስት ክቡራት ሴት ወይዘሮች መቀመጫ እጅግ ያጌጠ እልፍኝ አለበት ። በስተኋላውም ላራት ክቡራት ሴት ወይዘሮች መቀመጫ እንደዚሁ እልፍኝ ያለበት ከነጂው ጋራ ባንድነት አሥር ሰው የሚይዝ ነው ። ስለዚህ እንዳንድ ባቡር ባጐን ይመስል ነበረ

ጥቅምት ፲፯ ቀን ከጧቱ በ፩ ሰዓት ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ይህንን መታሰቢያ በደስታ ከተቀበሏቸው በኋላ።በዚሁ ባማረ ትልቅ አውቶሞቢል ሁነው ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንንም ባማረ ኦቶሞቢል ተቀምጠው በብዙ አጀብ ታጅበው ከቤተ መንግሥቱ ወጥተው ባራዳ በኩል ባለው በ—ትልቁ መንገድ ወደ እስጢፋኖስ ቤተ ክርስቲያን ሲሄዱ አጀቡ ብዙ ድንቅ ሁኖ ይታይ ነበር ከፍልውሃ መስከ ወጣ ብለው ከቤተ ክርስቲያኑ ሲደርሱ ነጋሪቱ ይጐሰም ጀመር ።

፪ት ሰዓት ሲሞላ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ልዑል አልጋ ወራሽ ከመኳንንቶቻቸው ጋራ በቤተ ክርስቲያኑ ገቡ ሠራዊቱና የቀረውም ሕዝብ ከቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ጀምሮ እስከ ውጭ ድረስ ተገርግሮ ቆሞ ነበር ። ጌቶቹም በገቡ ጊዜ ክህናቱ ዘይሄሊ ልብ አርአየ ኃይሉ ኃይለ ሥላሴ በላዕሌነ ወጸገወነ ሠናይቶ እያሉ ይወርቡ ነበር፤ወዲያው ቅዳሴ ገቡ በጸሎተ ቅዳሴው መሃል የተሰበከው ወኢሃደገ ይስሐጠሙ ሰብእ ወገሠጸ ነገሥተ በእንቲአሆሙ ። ወኢትግሥሡ መሢሐንየ ተብሎ ተሰበከ ድርገትም በወረዱ ጊዜ አለቃ ጽጌ የእስጢፋኖሱ እንዲህ ብለው ተቀኙ ።

ክብር ይእቲ ።

ኢረፈቁ ላዕለ የዋሃን ከዋክብተ ራማ ጠቢብት ።
እስመ እምድኅሬሆሙ መጽአ ዘተጸውዓ ስቅለት ።
ወእመ በገጽ ተሠርዓ ማዕደ መስቀል ሞት ።
ለዘተርፈ እክል አግኅሥቶ ኢተክህሎሙ ኃይላት ።

ዕጣነ ሞገር ።

ውግረተ እዕባን ጐዩ ምድረ እስጢፋኖስ የብስ ።
በኪደተ እግሩ ለዕብን ከመ ትትቀደስ ።
እክለ ሰማዕት ምድረ ከም በመዋዕለ ኖህ መንፈስ ።
እንዘ ሥልሰ ትሜለስ ።
ወእምደዌ ክሕደት ትሕየው በገሚሠ እክል ልብስ ።
ደም እንተ ይውኅዛ ሃይማኖት ዕንስ ።

ዓሠረ ንጉሥ ።

ኢትጥፉዕ እንተ ማኅቶቶሙ ለነገሥተ ሮም ወፋርስ ።
ተነበየ ለነ መልአከ ሰላም ክርስቶስ ።
ኃይለ ሥላሴ አክሊለ ርእስ ።
ለዘጠፍዓ ቅድመ ፀሐይ ንጉሥ ።
መይጠቶ እስመ ስእነት ነፍስ ።

ይህንን ክህናቱ ካለዘቡት በኋላ ። ፬ ሰዓት ሲሆን ታቦቱ ወጥቶ ዑደት ተደረገና ሊቃውንቱና ክህናቱ ወረብ ወርበው ሲያስረግጡ እጅግ አምረው ይታዩ ነበር ።

ከዚህ በኋላ ብፁዕ ዕጬጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ለሕዝቡ ደስ የሚያሰኝ ስብከት ሰበኩ ። ከዚህ በኋላ ግርማዊት ንግሥተ

ነገሥታትና ልዑል አልጋ ወራሽ ከመኳንንቶቻቸውና ከሠራዊታቸው ጋራ ስድስት ሰዓት ሲሆን በቤተ መንግሥት ገቡና ልዑል አልጋ ወራሽ በትልቁ አዳራሽ ሠራዊቱን ግብር ሲያበሉ ዋሉ ፡፡

ካለፈው ቍጥር የቀረ ቃል ፡፡

ስለ ትምርት ፡፡

ትምሕርት ማለት እኔ እንደሚታየኝ አሰስት ይከፈላል መጀመሪያ ያለፈ ነገር ወይም ታሪክ ፡፡ ሁለተኛ የዘወትር በዘመናችን የሆነና የሚደረግ ፤ ፫ተኛ የሚመጣን ለትንቢቱ እነዚህም ክፍሎች ብዙህ ክፍል በያንዳንዳቸው ውስጥ አለባቸው ይኸን ለመጻፍ ብዙህ እረጅም ስለሆነ ባጭሩ አመለክታለሁ ላላፊውም ለዘወትሩም ለወደፊቱም ሲማሩ የሚመሰረቱ መሰረቶች ፡፡ መጀመሪያ ምድር (አገር) የፍጥረት ምንጩዋን ጭምር እንደ አዝርዕትና እጸዋት እንስሳዎችና አውሬዎችን ወሮችን ፪ተኛም ያገሩን የወራትና ያመታት ጊዜዎች ፫ተኛ የሕዝቡን አስተዳደር ነው ፡፡ እነዚህም በየዘመኑ የሆነውን ከመጀመሪያው ጀምሮ እስከ መጨረሻው መርምሮ እንደዚሁ ሁሉ የሰውንም አገር እንደዚሁ ይመረመራል ከዚህ በኋላ እያወዳደሩ ከገዛ አገርም ውስጥ የተገኘውን ነገር (እውቀት) ከውጭ አገር የተገኘንም እውቀት እያወዳደሩ እንደሚቻል ያህል ለሕዝቡ የሚስማማውን መልካሙን ነገር በገር ውስጥ ማስተማር ማስፋት ነው ፡፡

ስለዚህ ሁሉ ነገር ግን ሰው ሳይገነዘበው የሚማረው ትምሕርት አለበት ይኸውም ከናቱ ሆድ ከወጣ ጀምሮ ነው እያጠና ሲል ሲል ከገዛ ቤቱ ወጥቶ እጐረቤት ከጐረቤት አፈር ወሰን ካፈር ወሰን እወረዳ ከወረዳ በሙሉ የገዛ መንግሥቱን ከዚህ በኋላ የውጭ አገር ታሪክና ነገር ልማድና ስልጣኔ የሚማረው እኛ ግን ጋዜጣ ባለመኖሩ እየቤታችን ጋዜጣ በማንበብ ያገራችንን ያለፈውንም ታሪክና ኑሮ በማዕርግ ሳንማር የዛሬውንም ባገራችን በየለቱ እዚያው ሆነን እንደ አገራችን ልማድ ያህል ያንኑ ጥቂቱን የሆነውን በወሬ እንሰማ የነበረውን ተነስተን ሳለን በዚሁም በብዙህ ስናዝንበት የሰው አገር ታሪክንና የለት ወሬን አለመሰረት በመማር ብቻ ስንኖር ዛሬ በብርሃንና ሰላም በጥቅስም በመጣጥም እየገጠመ የሚጻፈውን ያገራችንን ታሪክ አገራችን ሳለን ያላገኘነውን አሜሪካ ድረስ እየመጣልን መማር የዛሬውንም ያገራችንን መንግሥትና የሕዝብ አኳኋን የዘወትር አሳባቸውን የሰብሉን የከብቱን የማዕድኑን ባገራችን የሚገኘውን ነገር ሁሉ በመስማት ሙሉ ኢትዮጵያውያን ብዙህ ትምሕርት እውቀት እንድናገኝ ስላደረገን መጀመሪያ ይኸን አሳስቦ ላስጀመረ እምላክ ክብር ምስጋና አቅርበን እንደዚሁም ይኸን ላቆሙት ለልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን መልካም ስራቸውን እንዲባርክና ወደፊትም እያቀናና እረጅም እድሜ ስለሙሉ ኢትዮጵያ ሲል እንዲሰጥልን እንለምነዋለን፡፡ደግሞም በማሰናዳት በጉልበታቸው የሚረዱት ለሠራተኞቹና ይኸን መልካም ስራ ለማስፋት ለሚረዱ ሁሉ ላገራቸው የሚአስቡ በመሆናቸው ምስጋና ይገባቸዋል እንደዚሁም ጥቅምነቱን አውቀው ጋዜጣን ለሚገዙ ሰዎች ምስጋናቸው ከሠራተኞቹ አያንስም ባይቀበሉትስ አይታተምም ነበረና ፡፡

እንደዚሁ ሁሉ ሰው ከዚህ ዓለም ገንዘቡን ይዞ የሚሄድ የለምና እዚህ ዓለም ትቶት ስለሆነ ብዙኅ መልካም የኢትዮጵያ ባለገንዘብ ሰዎች ሁሉ የገንዘባቸውን አቀማመጥ ገንዘባቸውን ለመልካም ስራ ከሚያደርጉ ሰዎች አይተው ተረድተው አለምስጋና ለብቻ በላተኛ ለሆነ ከመተው ለሙሉ ኢትዮጵያ ማልሚያ ለእንደዚህ የመሰለ ያገር ጥቅም ለብዙህ ዘመን ለስማቸው ክብር በሕይወታቸው ሳሉ እንዲአደርጉት ተስፋ አደርጋለሁ ፡፡

አንተ ሞኝ ኢትዮጵያዊ ለኢትዮጵያ ገንዘብህን ብትሰጣት ታርዛ ሳለች ብታለብሳት ተጠምታ ሳለች ብታጠጣት በድንቁርና ገሮሮዋ ተደፍኖ ሳለ ብትከፍትላት አይኑዋ ተጨፍኖ ሳለ አይን ብትሆናት ኋላ ብድርህን አትከፍለኝም ብለህ ትጠረጥራለህን ፡፡ ከሰባት ሺህ ዘመን በፊት ዠምራ በየታሪኩ ሁሉ ኢትዮጵያ ኢትዮጵያ ስትባል መኖሯን አታውቅምን ይኸን ብታውቅስ ውለታ ብትውልላት እሷ እስከምታልፍበት ዘመን ድረስ ስምህን በመልካም ስትጠራህ ትኖራለች ለኢትዮጵያ ውለታ የዋለ በዚህ አለም ከሥጋ ሕይወቱ በኋላ ስሙ ከኢትዮጵያ ጋራ ሲመሰገን መኖሩ ነፍሱም በማያልፈው ዓለም ከሰማዕታትና ከሐዋርያት ጋራ መቆጠር አይጠረጠርም ፡፡

ኢትዮጵያ ትክበር ለዘለዓለም ትኑር ፡፡

በሻህ ውረድ ሀብተ ወልድ ፡፡

ስለሚተላለፍ በሽታ ጥንቃቄ የሚሰጥ ምክር፡፡

በኢትዮጵያ ከተሞች ይልቁንም በአዲስ አበባ የሚጋባ በሽታ በየዓመቱ እየተነሳ ብዙ ሰው መፍጀቱና በሽታም ከአዲስ አበባ አለመለየቱ ምክንያቱ ምን ይሆን ?

ይኸንን ጥያቄ ብንጠይቅ በሃገራችን ብዙ የተማሩ ሰዎች አሉና በትክክል የሚያጠግብ ምላሽ ለመስጠት እንዲቻላቸው እምናለሁ ፤ እንደዚህም ብዙ የተማሩ ሰዎች በሃገራችን መኖራቸውን ከዚህ ቀደም አስቀድሜ ሳላውቅ በመቅረቴ በሃገራችን ፍሬ ያለው ስራና ሃሳብ የሚያውቅ ሰው እንደዚህ በብዙ የለም እየመሰለኝ አዝን ነበር፡፡ዛሬ ግን ብርሃንና ሰላም የተባለው ጋዜጣ መታተም ከጀመረ ወዲህ በዚያውም ጋዜጣ ውስጥ የሚጽፉትን ሰዎች እውቀት ስለተረዳሁ ልቤ እጅግ አድርጎ መኩራት ዠመረ ፡፡ እኔስ እንደዚህ በብዙው መኖራቸውን አላውቅም ነበር አሁንስ ባሰበው በሃገራችን የሚያስፈልገው የተማሪ ቤትና የሃኪም ቤት ብቻ አይደለም እሱስ ብዙ ጋዜጣም እየታተመ እንዲወጣም ማድረግ ብዙ ጥቅም ኖሮበታል ፤

ይኸንን ከራስኔ በጥያቄ ቃል አድርጌ የጻፍኩትን ምላሹን በሞላ ሌላ ሰው እንዲሰጠኝ ጠይቄ ለመቅረት አይደለም ፈቃዱ የሚሆን ሰው ቢኖር የሃሳቡን ቢያስታውቅ ለኛም ወደፊት ለሃገር ፈውስ ለምንፈልገው ተማሪዎች ይረዳናል ፡፡ እውቀትም ይጨምርልናልና መልካም ስራ ይሆንለታል፡፡

ግን አሁን ለጊዜው እኔም ለራሴ የመሰለኝንና ጥቂት ፈውስ የሚሆን መስሎ የታሰበኝን እንዳመለክት ፈቃድ

ይደረግልኝ ይኸነንም ለማመልከት የምፈቅደውን መንገድ ለመመርመር ነው እንጂ ፈጽሜ ለማስረዳት እውቀቴ የተክናወን አይደለምና የምጀምረውን ነገር ሁሉ እስከ መሰረቱ ለማስረዳት አይቻለኝም ። ይኸነኑም የምሞክረው በተማሪቤት ትምሕርት እወቀቴ አይደለም (ለዚያስ በፍጹም ገና ሕጻን ነኝ) ግን በኢትዮጵያ ተወልጄ በከተሞችዋ አድጊያለሁና አዲስ አበባም የኖርኩበትና ያደኩበት ከተማ ነውና ከዚያ ከልጅነቴ ጀምሬ በማየቴ ዛሬ የታሰበኝን ልጻፍ ። ይኸውም የምጽፈው እስከ ፲፱፻፲፫ ዓመተ ምሕረት ድረስ የማውቀውን ነው እንጂ ከዚያ ወዲህ የተለወጠውን ብዙ አላውቅምና ተለውጦ የሚገኘውን ነገር አልነቅፍም ።

ወዳጄ ሆይ ከቶ በሃገራችን ካለው ልማድ ሁሉ ማንኛው እጅግ ክፉ ይመስልሃል ብለው ቢጠይቁህ ማንኛው ብለህ ትመልስ ይሆን እኔ የማውቀው አንድ ልማድ ክፉቱ ዘወትር ትዝ ይለኛል ይኸውም ልማድ ፈጽሞ ጉዳት የሚያመጣ ስለሆነ ነው አዘውትሮ ትዝ የሚለኝ የዚኸውም የልማድ ስም «ታምሜ ሳይጠይቀኝ ቀረ» ይባላል ።

እንግዴህ ባንተ ቤት ተስቦ ገባ ወይም ሌላ የሚጋባ በሽታ ፈንጣጣ ኩፍኝ የሚያስል በሽታ ወይም እንደዚኹ እነኝህን የሚመስል በሽታ) የቤት ሰዎችህ ሁሉም ይታመማሉ በመጨረሻውም አንተ ትታመማለህ ፤ በዚህም ጊዜ ቁምንገረኞች የሚባሉ ወዳጆችህ ሁሉ እየመጡ ይጠይቁሃል እየመጡም የጠየቁህ ሁሉ በሽታውን እየያዙ ይሄዳሉ ብዙዎችም ወዳጆችህ ካንተ ቤት ባገኙት በሽታም ምክንያት ይታመማሉ ከዚህ በኋላ ደግሞ የነኝህ የታመሙ ሰዎች ቤተሰዋቸው ሁሉ ይታመማል ወዲያውም የነኝህ የሰዎች ወዳጆች እየመጡ ይጠይቃሉ እነኛውም ጠያቂዎች ደግሞ እንደዚኹ በዚህ በበሽታ ይያዛሉ እንግዴህ ይኸ በሽታ መጀመሪያ የገባው ጉለሌ እንደሆን ቀጥሎ ፍሉሃ ይገኛል አልፎም ቀበና ገባ ይባላል ከዚያ በኋላ በከተማው ሁሉ በሽታ ገባ ይባላል ።

ስለ በሽታ አገማመር ።

እረ ይኸ የሚጋባ በሽታ መገመሪያ እዚያ አንድ ሰው አቶ እገሌ ቤት የገባው ። እግዚአብሔር ምክንያት አድርጎ ካቶ እገሌ ቤት በሽታ ጀመረ ወይስ ሌላ ምክንያት ለበሽታ መነሻ ይኖር ይሆን ? ይኸነን ጥያቄ የማያስቸግረውን ልመልስ ግን ሌላውን አልሞክርም ለምን ? ፈጽሜ ለማስረዳት ዕውቀቴ የተወሰነ ነውና ።

እግዚአብሔር ባንድ ሰው ምክንያት አድርጎ ከተማውን በሞላ በበሽታ ሊበክለው ካንድ ካቶ እገሌ ቤት ከእግዚአብሔር የተላከ መቅሠፍት ስለ ሆነ የተጀመረው በዚያ በቤት ሆነ ብንል እግዚአብሔር ደስ ይለው አይመስለኝም ። በእንደዚህ ያለ ምክንያት ሕዝቡን ለመፍጀት ፈቃድ የለውምና፤ነገር ግን ይኸንን የሚጋባ በሽታ ካቶ እገሌ ቤት ጉለሌ የጀመረችው አንዲት ገልቱ አገልጋይ ትሆናለች ክፉን ከደግ ለይታ አላወቀች አንድ ቀን ድግሥ ይመቻችና ብዙ ጥሬ ሥጋ ትበላና ሌላም ቅቅል ከጥብስ ትደበላልቅና ሆዷን ትታመማለች ተቅማጥ ይጀምራታል ወዲያውም እማድቤት ትተኛለች።እንግዴህ ያች ድኻ አገልጋይ በወደቀች ጊዜ ልብስዋን የሚለውጥላት የለ ገላዋ በትኩሳት እየሞቀ እንዳይከረፋ የሚያጥባት የለ ይልቁንም ያገረሻል ይባላል ። አንድ አሥራ አምስት ቀን በቁምዋ ከተንገላወደች በኋላ ትሸነፍና ከነከታቴው ለጓሮ እውጭ መውጣት ያቅታታል ይኸውም ሲሆን የሚያስታውሳት የለም እገላዋ ላይ እየሳተች ቤቱን ሁሉ ማከርፋት ትጀምራለች ። ግን በዚህ በማድ ቤት ውሥጥ የሚጋገረውን እንጀራ ሁሉ የቤቱ ሰዎች ሁሉ በደኅና ይበላሉ ።

አቶ እገሌና እመየት እገሊትም በማድቤታቸው የታመመችይቱን ድሃ ነገር ግና አልሰሙም ። ግን ከጥቂት ቀን በኋላ ያች ድሃ በማድቤት ታማሞተች ማለትን ይሰማሉ ድሃይቱም ተቀበረች እንግዲህ አገር አማን ነው ይመስላቸዋል ግን ከዚያ ከመጥፎ ሽታና ተክርፋት የተነሳ ሆድዋ ተነክቶ የነበረች አንደኛይቱ የማድቤት ሠራተኛ ቀጥላ ትታመማለች ሌላይቱም ደግማ እንደዚያው ትታመማለች ከዚያም በኋላ አቶ እገሌና እመየት እገሊት ይታመማሉ ከዚያ ቀጥሎ አቶ እገሌ ቤት ተስቦ ገብቷል ይባላል።ጠያቂዎችም እንደቱም ነገራቸውና እንደወዳጅነታቸው እጠነከከር ለመጠየቅ መሄድ ይጀምራሉ የሀገራችን ከሚጋባ በሽታ ሰው ቤት እንዳይጋባ የሚከለክል ሥርዓት መንግሥት ገና አላወጣምና ። ሲመለሱም ጠያቂዎች በበሽታው እየተለከፉ ወጥተዋልና ከጥቂት ቀን በኋላ ይታመማሉ እንደዚያው የታመሙት ይበራከታሉ ከዚያ በኋላ በአዲስ አበባ በሽታ ገባ (ተስቦ) ።

አቶ እገሌና እመየት እገሊት ሲታመሙ መኝታቸው እንደዚያች እንደድሃዋ አይከረፋ ቤቱ ንጹሕ ጠያቂዎች በገቡ ጊዜ እንደነኛ እማድቤት ሲሰሩ ሆዳቸው በሽታ (ክርፋት) እንደተነካው ሠራተኞች የሚሸታቸው ነገር የለ ይህ ሕመም ጠያቂዎችን መልከፉ በምን ምክንያት ይሆን ? ብለህ ለመጠየቅ ትፈቅድ ይሆናል ።

ይህንንስ ጊዜ ያላቸው ሰዎች ዕውቀታቸውም ፍጹም የሆነላቸው ብዙ ሰዎች ፈጽመው ለማስረዳት የሚችሉ አሉ ይልቁንም የመድኃኒት ዕውቀት ያላቸውና በሃገራችን ቋንቋ የሰለጠኑ ሐኪሞች አሉና ይህነን በብርሃንና ሰላም እየጻፉ የበሽታን አመጣጥና ወደሰው የሚጋባበትን መንገድ እያስረዱ ሕዝባችንን ከበሽታ እንዲጠበቅ ቢያመለክቱት ኢትዮጵያ በጣም ታመሰግናቸው ይሆናል ። አሁን ለጊዜው ግን ከሚፍ ቀንጥቤ ባጭር ቃል እኔው ልመልስልህ ።

በሽታ ተሸክመው የሚሄዱ እጅግ አድርገው ላይን የረቀቁ ነፍሳቶች (ትሎች) አሉ እነኝህም ነፍሳቶች ከነፋስ እየተደባለቁ ነፋስ እየተሸከመ የሚወስዳቸው ናቸው ርቀታቸውም ከጤፍ ዱቄት ይልቅ ብዙ ጊዜ አብልጠው የረቀቁና የላሙ ናቸው ስንተነፍስም ከምንተነፍሰው አየር እየተደባለቁ ባፋችንና ባፍንጫችን ይገባሉ በሽተኛም ልንጠይቅ በሄድን ጊዜ በልብሳችን ምሉ ተሸክመናቸው እንወጣለን እዚያውም እበሽተኛው አጠገብ ተቀምጠን ሳለን ከአየሩ እየተደባለቁ ባፋችንና ባፍንጫችን ይገባሉ ግን እነኝህ በሽታ የተሸከሙ ነፍሳቶች እጅግ ረቂቆችና ደካሞች ስለሆኑ የገቡበትን አካል ሁሉ አሸንፎ በሽታ ለመሥራት አይቻላቸውም ።

በአካላችን ውስጥ ሁለት አይነት ደም አለ አንደኛው ደማችን ሁላችንም የምናውቀው ቀይ ደም ነው ። ሁለተኛው

አይነት ደማችን ግን ነጭ ደም ነው፤በደም መመልከቻ መነጽር ለመመልከት ከሰውነትህ ትንሽ አድምተህ በዚያ መነጽር ብትመረምረው ውሃ የሚመስል ነገር እንደቀለበት ክፍል ክፍል እያበጀ ይታይሃል እነሆ ያውም ይህ ነጭ ደም የምልህ ነው እነኝህን ሁለቱን አይነቶች ስላስታወስኩህ ደም ሁለት አይነት ብቻ እንዳይመስልህ ግን ዋናዎቹ እኝህ ሁለቱ ናቸው። ሰውነትህ ባለጤና እና ጠንካራ እንደሆን እነኝህ በሽታ ተሸካሚዎች የሆኑ ነፍሳቶች በደምህ ውስጥ በተቀላቀሉ ጊዜ ይኸ ነጭ ውሃ የሚመስል ደምህ የፈላ ውሃ ነፍሳትን ሁሉ እየገደለ እንደሚያስቀር እንደዚኸውም ይህ ነጭ የባለጤና ሰው ደም እነኝህን ነፍሳቶች እየገደለ ያስቀራል ግን ሰውነትህ አስቀድሞ መጠጥ በማብዛት ወይም በዝሙት ወይም የንቅልፍህን ሰዓት በማሳጠር ወይም በማናቸውም ሰውነት በሚያደክም ነገር ሰውነትህ ደክሞ እንደሆን ይኸ በሰውነትህ ውስጥ የሚገኘው ነጭ ደም ዘበኝነቱን ለመጠበቅና የሚመጣበትን ተውሳክ ለመጋደል አይቻለውምና በሽታ ተሸካሚ የሆኑት ነፍሳቶች ደምህን ያሸንፉና በሰውነትህ ውስጥ ይረባሉ ደምህንም ይመሉታል ከዚያ በኋላ ደምህ ይታወክል ደምህም ሲታወክ ሕመመኝ ትላለህ እንደዚህ ሁኖ በሽታ ይፀንስብሃል ይኸውም ሰውነታችን በሰለቸና በደከመ ጊዜ ወደበሽተኛ ቤት እንዳንሄድ ያስታውሰናል ።

በሽታ በጐረቤት በገባ ጊዜ ጐረቤትን ስለመርዳት። ወዳጄ ሆይ አስቀድሜ እንደገለጽኩልህ እውቀቴ የተወሰነ ነውና የበሽታን መምጫ ፈጽሜ በዝርዝር ጽፌ ለማስረዳት አይቻለኝምና ። አንደኛውን በሃገራችን ያለውን ልማድ የበሽታ መነሻ የሚመስለኝን ምክንያት ላስታውቅህ ደፍሬ ሞከርኩት ግን በሽታ የሚመጣበት ምክንያት መንገዱ. እጅግ ብዙ ነው ከመጥሮ ውሃ ይዠመራል ከወተትም ይዠመራል ከጥሬም ሥጋ ይዠመራል ጥሬውን ከሚበላም አታክልት ይጋርመራል በሽታ የሚፀነስበት ብዙ ምክንያት አለው ስንቱን ቆጥሬ ላደርሰው እሞክራለሁ እግዚአብሔር በፈቀደልኝ ጊዜ በሚሰጠኝ እውቀቴና ጉልበቴ የሚሆነውንና ለማድረግ የሚቻለውን ሁሉ በዝርዝር ምክንያቱን ከነፈውሱ ላስረዳህ እመኛለሁ ።

አሁን ግን ለጊዜው መጀመፘ የጀመርኩልህን ሳትረሳው ታምሜ ሳይጠይቀኝ ቀረ ስለሚባለው በሃገራችን ስላለው ልማዳችን የሚጋባ በሽታ ባለበት ቤት በመግባት የተነሣ የሚመጣውን ጉዳት ትንሽ አስረድቸህ እንደሆን እነሆ ከዚህ ተከንቱ ጉዳት ተጠብቀህ ችግር የመጣበትንም ጐረቤትህን ለመርዳትና ለመጥቀም እንዲቻልህ የተዘጋጀህ እንድትሆን ለሕይወት መጠበቂያ እንዲሆን ብለው የዘረጉትን ደንብ የመድኃኒትና የሥጋዊ ፈውስ ለሚሆነው ነገር ሁሉ ሊቃውንቶች በተባሉት ሰዎች የተደነባውን ደንብ እየተከተልኩ ላመልክትህ ።

ምናልባት የሚጋባ በሽታ በጐረቤትህ ወይም በወዳጅህ ቤት በገባ ጊዜ ወዳጅህንና ጐረቤትህን ጨክንባቸውና ችጋርና ውሃ ጥም እንዲፈጇቸው አድርግ ማለቴ አይደለም እኔ ላመለክትህ የምጣጣረው ግን ጐረቤትህንና ወዳጅህንም ጠቅመህ ለራስህም ጉዳት ሳያገኝህ በሽታው ቀጥሎ ወዳንተ ቤት ሳይገባብህ እንዲቀርልህና በሽታውን አራብቶ በከተማው ከመሙላት ከልካይና የሕይወት ዘበኛ እንድትሆን ስለተመኘሁልህ ነው

አንተ ግን እራስህ ሂደህ ካልጠየቅኻቸውና የሚያምራቸውን በቃልህ ጠይቀኻቸው ካልተረዳኸው ወዳጅህና ጐረቤትህ የሚጠቀሙ አይመስልህም ። ለዚህስ የሚሻለውን ነገር እኔ ላመልክትህ ።

የሚጋባ በሽታ ባንድ ቤት የገባ እንደሆነ በዚያ በቤት ያሉት ሰዎች ሁሉ ባንድ ቀን ታመው አይተኙም ግን መጀመፘ አንድ ሁለቱ ይታመሙ ይሆናል ቀጥሎም እነሱ ቀና እስቲሉ ሌሎች ይታመማሉ ፡ ግን እነኝህ በኋላ የሚታመሙት በሕማሙ ተሸንፈው ለመተኛት ሳይደርሱ እነኛ በፊት ታመው የነበሩት በጎ ሁነው ይነሳሉ (መልካም ሐኪም ቢገኝ ወይም እግዚአብሔር ቢምር) በኋላ የወደቁትንም ለማስታመም ይችላሉ ። ግን እነዚህ ገገምተኞች ምግብ ለማሰናዳት ጉልበት አይበቃቸውምና ይህን ጊዜ እውነተኛ ወዳጆች እርዳታቸውን መስጠት ያስፈልጋቸዋል እንግዲህ እንደሚረዳው ላመልክትህ ።

እንጀራውን እቤትህ አስጋግረህ ወጡን አሰርተህ ጠላውን አስጠምቀህ ውሃውን አስቀድተህ የሌሊት መብራት የሚሆን እንኳ ሳይቀር የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ አዘጋጅተህ በታመመው ወዳጅኽ ወይም ጐረቤትህ ቤት ደጃፍ አስቀምጥለትና እቤት ሳትገባ ከደጃፍ ተመልሰህ ሂድ ወይም ሌላ የሚያስፈልጋቸውን ነገር ለመጠየቅ ትፈቅድ እንደሆነ እነኛ ታመው በጎ ሁነው የተነሱ ልጆች አሉና እደጅ እንደሆንኽ አንደኛው ብቅ ብሎ እንዲያነጋግርኽ ተጣራና ብቅ እንዲልልኽ አድርገው ብቅ ብሎም ሊያነጋግርኽ በመጣ ጊዜ በሩቁ እንደሆነ ይቁም ፡ አንተም ነፋስ ከሚመታበት ወገን ቁም ነፋስ ከሚመታበት ገገምተኛው ቁሞ ያነጋግርኽ እንደሆነ በልብሱና በትንፋሹ ያሉትን ነፍሳቶች ነፋሱ ወዳንተ ይነዛቸዋል ፡ በሩቅም እንደቆመ የሚያስፈልጋቸውን የቤት ችግራቸውን ያነጋግርህ በሽተኞቹም ለየብቻቸው የሚያስፈልጋቸውን ነገር ሁሉ እየጠየቀ ይንገርህ አንተም የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ ፈጽመኽ ከሰማኽ በኋላ ተመልሰኽ ሂደኽ ያለ ዝንጋታ በጥንቃቄ በቶሎ ችግራቸውን ፈጽምላቸው እንደዚህ አድርጎ ለማስታመም በሽታው የጠነከረ እንደሆነ ያስቸግራልና በሽታው በጠነከረ ጊዜ የሚደረገውን ልቀጥልልኽ ።

በሽታው ከፍቶ በቤት ያሉት ሰዎች ሁሉ ታመው አስታማሚ ያጡ እንደሆነ ባለሥራ እንደሆንህ ሥራህን የሚያስኬድልህ ሰው ተክተህ ከሥራህ ሁሉ በፍጹም ተሰናብተህ ከውጭም ከገበያ የሚያስፈልግህን ሁሉ ገዝተህ ከቤትህም የሚያስፈልግህን እቃ ሁሉ አዘጋጅተህ የመኝታ አልጋህንና ብዙም የታጠቡ ልብሶችህን አዘጋጅተህ ገንዘብህን ጠቅለህ (ማለት ለጊዜው የሚያስፈልግህን) በታመመው ወዳጅህ ቤት ገብተህ አስታመው ። እንግዴህ አንተ አንድ ጌዜ እዚያ ከገባህ በኋላ በሽተኞቹ ድነው በሽታው ፈጽሞ ከዚያ ከቤት ወጥቶ ገገምተኞቹ ራሳቸውን ችለው እንደ ወትሮአቸው እስቲሆኑ ድረስ ከዚያ ከቤት ወጥተህ ከሰው መጋናኘት ወደገበያ መሄድ ወደአደባባይ ወጥቶ ከሰው መገናኘት እቤተ ክርስቲያን ሂዶ ከሰዎች ጋራ ተቀላቅሎ ማስቆረብ ምንም ቢሆን አይገባህም (እንዲህስ ያደረግህ እንደሆነ በሽታውን ለብዙ ሰው ለማዳረስ ማድረግህ ነው) አንተም እዚያ ለማስታመም ገብተህ ሳለህ የቤቶችህ ወይም ወዳጆችህ

እንደዚያ ቅድም በመላክት ስትረዳ እንደ ነበርከው አሁን ላንተ ይርዳህ ላንተና ለበሽተኞቹም የሚያስፈልገውን አንተን እየጠየቀ እያዘጋጀ ያምጡልህ ።

ከቤትህም የሚመጡትን ልጆች እኔ አልታመምኩም በሽታ አላጋባበቻውም ብለህ ቀርበህ እንዳታነጋግራቸው ተጠንቀቅ እነኛ በሽታ ተሸካሚ የሆኑ ነፍሳቶች ከለህበት ከበሽተኞቹ ቤት አግኝተውህ በልብስህ ሙሉ መኖራቸውን መርሳት አይገባህም ። ይኸ ሁሉ ሲሆን ከዚያ በሽታ ከገባበት ቤት ውስጥ የገባው እቃ ሁሉ ተመልሶ ወደሌላ ቤት እንዳይገባ ክልክል ው።እቃ የሚጋባ በሽታ ወዳለበት ቤት የገባ እንደሆነ ነው እንጂ ከዚያ በሽታ ካለበት ቤት ወጥቶ ወደሌላ ሰው ቤት አይሄድም ። (በሽታው እስቲወጣ) የሄደስ እንደሆን እቃው በሚገባበት ቤት ሁሉ በሽታ እንዲገባ የማዘዝ ያህል ነው በሽታው ከወጣ በኋላ እቃው በፈላ ውሃ እየታጠበ ለየ ባለቤቱ ይመለሳል ። ሲሆን አስቀድሞ በወረቀት መሰሪያና ብዙ ዋጋ በሌለው እቃ መስደድ ነው ምግቡን ሁሉ። ምግቡን በልተው እቃውን እንዲያቃጥሉት ።

እንዴህ አድርገህ በጥንቃቄ ያስታመምህ እንደሆነ ያ የሚጋባ በሽታ ከዚያ መጀመሪያ ከገባበት ቤት ወጥቶ ወደ ሌላ ቤት ገብቶ ተራብቶ ለብዙ ሰው ሳይተርፍ በደኅና ባንድ ቤት ሰው ብቻ ተገላግሎ ብዙ ሕዝብ ሳይጐዳ ይቀራል አስታማሚውም በእግዚአብሔር ፈቃድ በሽታ ሳያገኝህ ወዳጅህን ከነ ቤተ ሰው ረዳኸው የዘለዓለም ውለታ ዋልኽለት በደስታ አብራችሁ ትኖራላችሁ ።

በሽታውም አሸንፎ ሞተህ በነበር መልከም ቁምነገር ስትሰራ ነውና የሚያስቆጭ ነገር የለበትም።መቼም ሞት የማታ ማታ ርስታችን መሆኑ የታወቀ ነው ለወዳጅ ቢሞቱ ጉዳት አይደለም (ትርጓሜው ላገር ማለት ነው) ።

ስለ «ታማሚ ሳይጠይቀኝ ቀረ» ከንቱነት።ወዳጄሆይ ዛሬ ፈንጣጣ ኩፍኝ ተስቦ ይኸንንም ከሚመስሉት ሁሉ አንዱ በቤትህ የገባ እንደሆን በቤትህ ውስጥ ገብቶ የመጣብህን ጉዳት አዋይቶ እግዚአብሔር በቀላሉ ይማርህ ብሎ በቃሉ ሳያነጋግርህ የቀረውን ወዳጅህንና ዘመድህን ጐረቤትህንም ሁሉ ትታዘበዋለህ ልብህም ይጠላዋል«እገሌ ወዳጄ ስለው ስታመምና በሽታ በቤቱ ሲገባ ጊዜ ይሞታል መስሎት መጥቶ ሳይጠይቀኝ ቀረ የዛሬን ዘመን ሰው ወዳጅ ነው ማለት ከንቱ ነው» እያልህ ታማርረዋለህ ታከርፈዋለህም ታዝበም ማኩረፍህን ባወቀ ጊዜ ምነው ወዳጅህን እገሌን አኮረፍከው ብሎ ሲጠይቅህ «ታምሜ ሳይጠይቀኝ ቀረ»ብለህ ምክንያትህን ትናገራለህ ።

ያንኑም ያልታደለ ወዳጅህን ሁለተኛ ለማነጋገር ፈቃድ የለህም ። አዳም ገብቶ ተጨንቆ ብታየው ልትዋሰው አትፈቅድ ይሆናል ቢታሰርም ለማስፈታት ፈቃድ የለህም ። እንግዲህ ታመህ ሳይጠይቅህ ቀርቷልና ፈጽመህ እርምህን አውጥተህ ከዚህ በደለኛ ከመሰለህ ሰውዬ ተለያይተህ መቅረትህ ነው ። እንግዴህ እቤትህ መጥቶ ባንተ ቤት የገባውን በሽታ ሳይካፈል ቀረ ብለህ ነውን የዘለዓለም ወዳጅህን ጠልተህ መቅረትህ? ኃኪም አይደለ አይረዳህ ከበርቴ አይደለ በገንዘቡ እየላከ አይረዳህ፡ገንዘብስ እያለው በሚቻለው ነገር እቤትህ ሳይመጣ ሊረዳህ እየተቻለው ከጨከነብህ አጥፍቷል ። ግን እንዲያው በከንቱ እቤቱ መጥቶ ሳይጠይቀኝ ቀረ ብለህ መቀየምህ ለምን ይሆን?እባክህ ስማኝ ወዳጄ ከንግዲህ ወዲህ በቤትህ በሽታ የገባብህ እንደሆነ ወዳጆቼና ዘመዶቼ መጥተው ሳይጠይቁኝ ቀሩ ብለህ አትቀየምባቸው ። ይልቁንም በቤትህ በሽታ መግባቱን በተረዳህ ጊዜ እደጃፍህ ላይ«በዚህ በቤት የሚጋባ በሽታ ገብቷልና ሰው አይገባም» ብለህ በጉልህ ጽፈህ ብትለጥፍና ብታስታውቅ ያገርህን መንግሥትና ያገርህን ሕዝብ ጉዳት የማትወድ ሰው መሆንህን ማሳየትህ ይሆንልሃል ።

ለራስህም ምንም ቢሆን የሚጋባ በሽታ ባለበት ቤት ደፍረህ አትግባ እዚያው ገብተህ ከሰው ተለይተህ በዚያ በቤት ተከተህ ለማስታመም ካልሆነ በቀር ። በሽታስ እየደፈርህ በሚጋባ በሽታ ቤት እየገባህ እየወጣህ ከቤትህ ሰዎች ጋራ አብረህ ባንድ ቤት የኖርህ እንደሆነ በግድ ለቤትህ ሰዎች በሽታ ለማስያዝ የምትጣጣር ሰው ትመስላለህ።ለምትውልበትም አደባባይ አጋላጭና ነፍስ ለማስፈጀት የሚጣጣር ሰው ትመስላለህ ። የሚጋባ በሽታ አገባበት ቤት እየገቡ እየወጡ ባደባባይ የሚውሉ ሰዎች ሁሉ በፍጹም የሕዝብና ያገር የመንግሥት ጠላት መባል ይገባቸዋል ይመስለኛል ። ለምን እንደ ሃኪሞች ልብሳቸውን መድኃኒት እየቀቡ አይደል የሚሄዱት በዚያ በበሽተኛ ቤት በገቡ ጊዜ እነኛን በሽታ ተሸካሚዎች የሆኑትን ነፍሳቶች በልብሳቸው እየተሸከሙ እየሄዱ በሄዱበት ሁሉ መንዛታቸው የታወቀ ነው ።

በየደጃችን በሬ ሥናርድ ከተማ ሥለማገዱፉችን ።

የአዲስ አበባን ከተማ በሽታ ለማቅለልና ንጹሕ ከተማ ለማድረግ ቱንሽ ይረዳ መስሎ የሚታየኝን ለማመልከት እሞክራለሁ ።

በአዲስ አበባ የሚኖሩ በየስፍራቸው ብዙ ሰው ግብር የሚያበሉ መኳንንቶች እየገቢያቸው በሬ የሚያሳርዱ አሉ በሬ በታረደ ጊዜ እዚያ እቤቶቹ አጠገብ በከተማው መካከል ይታረዳል ደም ይፈሳል ዋና ዋናውን የሚበላውን ሥጋ አንስተው ሥጋ ቤቶች የማያስፈልጋቸውን ለውሾች ትተውት ይሄዳሉ ውሾቹም የሚችሉትን በልተው የተረፈው በመሬት ላይ ይቀራል ይኸውም ደምና የሥጋ ትርፍራፊ ይውል ያድርና ይከረፋል (ሥጋ ቤቶቹ ስልጡኖች እንደሆኑ ላይን እንዳያስቀይም አፈር ረጭተውበት ሂደዋል እንጂ ደሙ እንዳይሸት አድርገው አልጠረጉትምና)።ክርፋቱንም ነፋስ እያነሳ ወደከተማ ይነዛዋል ከዚኸውም ሽታ የተነሳ ሰው ይታመማል ። ይኸንን ስራ ለከተማው ከንቲባ ስልጣን አልተሰጣቸው እንደሆን ስልጣን ሰጥቶ የከተማው ከንቲባ ዘበኞች አበጅተው በሬ የታረደበትን ቦታ ሁሉ እየዞሩ እያዩ የፈሰሰውን ደም እያስጠረጉ ከተማው በንጽሕና እንዲኖር ቢያደርጉ ትልቅ ጥቅም የሚሆን ይመስለኛል ።

ብዙ በሬ እያረዱ ደሙ ለመጠረግ እየበዛባቸው የሚቸገሩ ሰዎች ቢኖሩ ግን ወደመንግሥት ቄራ (ማረጃ) እየወሰዱ እዚያ እያረዱ ሥጋውን እያሸከሙ ማስወሰድ ይገባቸዋል።ግን ለመንግሥቱ ቄራ አሁን የቆመበት ስፍራ ቦታው አይደለም። በመንግሥት ቤት አጠገብ እንዲህ ያለ አየር እያበላሸ ጤና የሚነሳ ነገር ሊኖር አይገባውምና የቄራውን ቦታ በቶሎ መለወጥ ያስፈልጋል ።

በሃገራችን እንጨት መልቶ ሳለ (የደንጊያ ከሰልም አይ ጠፋ ።) በአዲስ አበባና ባውራጃዋም እንጨት ለማገዶ ችግር ሆኖ ይኖራል ። ይኸውም የመንገድና የባቡር ጥፋት ስለመሆኑ ከዚህ በፊት ተነግሩዋል ። አሁን በሸዋ ሜዳ ከአዲስአበባ እልፍ ሳንል ገና ለገዳዲ ስንደርስ የምናየው ችግር አይገር ምምን እንጨት ፈጽሞ ስለጠፋ የከብቱን ፍግ ሁሉ በየደጃቸው አበባ እየተከሉ ለደጃፋቸው ጌጥ እንደመስጠት ሁሉ እየቤታቸው ደጃፍ ይከምሩታል ።

ይኸውም የተከመረው ፈጽሞ የሚከረፋ ጉድፍና የከብት ፍግ ነው ነፋሱም ያነኑ እየመለሰ ሽታውን ወደቤት ያገባዋል ከቶ ሰዎቹም ዘወትር ጉንፋናሞች ያለመሆናቸው እንደዚህ ያለው መንደር አንድላይ ትልቅ እስቲሆኑ ተሰብስበው ባይኖሩ ነው እንጂ አንድ ላይስ ተሰብስበው ከተማ ለመሆን በበቂ ጊዜ በበሽታ ሳይተላለቁ ይቀሩ አይመስለኝም ። ከቶ በአዲስ አበባ ይኸነን የመሰለ ጉድፍ እንዳይበዛ ሕዝቡ ያስብበት ይሆንን ክቡር የአዲስ አበባ ከንቲባ ይኸነን በሚመስለው ነገር ሁሉ አጥብቀው እንዲተጉበት እጅግ አድርጌ እመኛለሁ ። እግዚብሔር ይርዳቸው ።

ከወህኒ ቤትና ከዘብጥያ ስለሚነሣ በሽታ ።

ከዚህ ቀጥዬ ስለምጽፈው የወህኒ ቤትና የዘብጥያ ሹማምንቶች፣ ለማስቀየምና ለማሳጣት ያደረግኩት መስሎ እንዳይታሰብብኝ እንዲህ ያለ ተንኮል በልቤ ያለመኖሩን ለማስታወቅ እፈቅዳለሁ፡እኔ ግን ንጉሥ ሰሎሞን በ፳፫ኛው ምዕራፍ በ፲፩ኛው ቁጥር የተናገረው ቃል ለሃሳቤ አክኼድ ልክ መሆኑን ያስረዳኝ ስለመሰለኝ በልቤ ያለውን ሃሳብ ለመጻፍ ያስደፍረኛል እውነትን የያዘ እንኳ መልካም ሃሳብ ለማስረጃ ከፋውንም እውነት መልካም ለማስመሰያ አድርጎ ይደፍርበታል ። የኔ ግን ከዚህ ቀደም በስሕተትና ባለማወቅ በሀገራችን ስለሚኖረው ጉዳት ለመንግሥታችንና ለሕዝባችን ጥቅም ወደሚሆን ነገር ፊታችንን እየመለስን እንድንመለከት ምኞት ስለኖረኝ ነው ከዚህ ተከትሎ ያለውን ቃል መጻፌ ። ሹማምንቶችና ሠራተኞች ጥፋት እንደሌለባቸው የታወቀ ነውና እኔ አሁን የምጽፈው ከጥንት የቆየነን ልማድ ብቻ ነው ።

ከሥር ቤት ዘወትር የሚጋባ በሽታ አይጠፋም ከሥር ቤት የሚጋባ በሽታ እንዳይጠፋ የሆነበትን ምክንያት ለማስረዳት አሁን የሚበቃ ጊዜ የለኝም ሲቻለኝ አደርገዋለሁ ግን ከሥር ቤት በሽታ ያለመለየቱን ሁላችንም እናውቃለን

አንድ ሰው ትልቅ ጥፋት ያጠፋና ይታሰራል በዚያውም በስር ቤት ብዙ ቀን ይቆይና ተስቦ በሽታ ይይዘዋል ይታመምና ይተኛል ብዙ ቀን ከታመመ በኋላ ሰውነቱ ይከረፋና ልብሱ ያለመጠን ያድፍና በሰውነቱ ቅማል ይሞላል በዚያው በግርብረት ውስጥ ሳለ ከበሽታው በጐ ይሆንና ከተኛበት ቀና እያለ ለመነሳት ይሞክክራል ግን አሁን ከሞት መትረፉ ነው እንጂ ከበሽታው ነጻነት አላገኘም

በዚህ ጊዜ አንድ ሰውዬ ትንሽ ጥፋት ያጠፋና ወንበሮች ይቆጡና ስለጥፋቱ እንዲበርድለት ብለው ወደወህኒ ሂዶ እንዲታሰር ይሰዱታል የወህኒውም ሹም እሰሩ ብሎ ለበታቾቹ ሰራተኞች ይሰጣል እነኛም የበታቾች ሰራተኞች እግር ብረት ይፈልጉና ያገኙ እንደሆነ ለብቻው ሁለት እግሩን ባንድ እግር ብረት ያስሩና በዚያ ብዙ በሽተኞችና ገገምተኞች ባሉበት ቤት ሂዶ እንዲቀመጥ ያደርጉታል ወይም ይልቁን ለብቻው በግር ብረት እንዳይታሰር ለጊዜው እስረኛ ስለበዛ እግር ብረት ሳይገኝ ይቀርና ከዚያ አስቀድሞ ስለትልቅ ጥፋት ታስሮ ከርሞ ተስቦ በሽታ ታሞ ከሞት ተርፎ ገገምተኛ ሁኖ በሰውነቱ ምሉ ቅማል ተሸክሞ የሰውነቱም ክርፋት ሆድ ከሚበጠብጠው ሰውዬ ጋራ ባንድ እግር ብረት ተቆራኝቶ እንዲታሰር አድርገው አስረው ሁለት ሶስት ቀን ካሳደሩት በኋላ ጥፋቱ ቀላል ስለሆነ ይማርና ምሕረት ከተሰጠው በኋላ ከታሰረበት ተፈትቶ ይወጣል ። የዋኹ ሰውዬ ግን ከወህኒ ቤት ብዙ ቀን ሰንብቶ በሽታ ሳይታመም ስለወጣ ደስ ይለዋል እንጂ በጠንካራ እግር ብረት ታስሮ ወደቤቱ መግባቱንና በማይነቀል መርዝ መበላሸቱን አያስበውም በደስታ ወደቤቱ ይገባል በልብሱም ምሉ የተሸከማቸውን ነፍሳቶች በሽታ ተሸካሚዎች የሆኑትን ትሎች ከወህኒ ቤት በሽተኞችና ገገምተኞች ላይ ተነስተው የተጋቡበትን አላወቀም ግን ከጥቂት ቀን በኋላ ይታመማል ሚስቱም ትታመማለች የቤቱ ሰው ሁሉ ይታመማል ከዚያ በኋላ ተስቦ ገባ ይባላል ለከተማው ሰው ሁሉ ይተርፈዋል እንግዲህ ጥፋተኛው ማን ሊባል ይሆን?ወይስ ይህ ሰውዬ በትንሽ ጥፋት ወንበሮችን አናዶ እወህኒ ለመግባት ስለበቃ ጥፋት የሰውዬው ይሁን ወይስ በትንሽ ጥፋት ምክንያት ሰውዬውን ወደወህኒ በመስደዳቸው ወንበሮች ጥፋተኞች ይባሉ ይሆን ወይስ የወህኒ ቤት ሠራተኞች ከበሽተኞች አቀላቅለው በሽታ ስለ አሲያዙት ጥፋት የነሱ ይሆን ይህ ጥፋት የገሌ ነው ለማለት ለኔ አልታየኝም ግን መንግሥትና ሕዝብ መጐዳቱ እርግጥ መሆኑን ለሁላችንም ሳይታየን አይቀርም ይኸ ጉዳት እንደዚኸው እንደሰለጠነብን እንዳይኖር መንግሥትና ሕዝብ ተረዳድቶ ፈውስ ቢያበጅለት የማያስቸግር አይመስለኝም ። መልአኩ በያን ። (አሜሪከ)

ከዚህ የተረፈው ቃል በሚከተለው ቁጥር ይታተማል ።

ስለ ርሻና ንግድ ሥራ ማስፋያ ማህበር ።

ጃንሆይ ዳግማዊ ምኒልክና ግርማዊት ዕቴጌ ጣይቱ የሕዝባቸውን መቸገር አይተው ችግርም የሚቀረው በገንዘብ ማግኘት መሆኑን አውቀው ሕዝባቸውን አነሳስተው ይህ የርሻና የንግድ ማስፋያ ማኅበር እንዲቆም ፈቃድ አደረጉ ይኸውም ማህበር የርሻና የንግድ ማስፋያ ተብሎ በግንቦት ፳፫ ፲፱፻፩ ዓመተ ምሕረት ቆመ ። ጃንሆይ ዳግማዊ ምኒልክና እቴጌ ጣይቱም ሕዝባቸውን ለማነቃቃትና ለመርዳት ሲሉ ፬፻፺፫ሺ ፫፻ ብር ወደ ማህበሩ አገቡ ነጋዴዎችና ሌሎችም ሰዎች ፻፴፪ሺ ፳፻፵ ብር ወደማህበሩ አገቡ ድምሩ ፫፻፳፭ሺ ፳፻፵ ብር መሆኑ ነው።

ነገር ግን ሥራውን ለማስፋትና ብዙ ትርፍ ገንዘብ ለማግኘት ይህ ፫፻፳፭ሺ ፳፻፵ ብር የማይበቃ ስለሆነ ለጊዜው ሥራው በዚህ ይጀመርና ወደ ፊት የማህበሩ (ካፒታል ገንዘብ) ዋና ገንዘብ ፫ ሚሊዮን ፬፻ሺ ብር እንዲሆን ተወሰነ ይኸውም በ፴ሺ (አክሲዮን) ክፍል ተከፈለ አንዱ (አክሲዮን) ክፍል ፻ ብር ነው ።

ለዚሁም ለማኅበሩ ሥራ በመጀመሪ ነጋድራስ በሀብቴ ቀጥሎም አቶ ምትኬ ተሾመው ነበር እነዚኅም ሹሞች ምንም

ለዚህ ሥራ የሚበቃ እውቀት ባይኖራቸው በጊዜው የሚቻላቸውን ያህል ሠርተው ብዙ ትርፍ ለማህበሩ አትርፈዋል ነገር ግን እነዚህ ሁለቱ ሹሞች በብድር ያወጡትን ገንዘብ ሳያስገቡ ስለሞቱ የገንዘቡ ብዛትና ጥፋት የማህበሩ ልማትና ጉዳት ሳይታወቅ ብዙ ጊዜ ቆይቶ ነበረና ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን የጃንሆይ የዳግማዊ ምኒልክና የዕቴጌ ጣይቱ አሳብ ወደፊት እየተፈጸመ እንዲሔድ ማህበሩም የበለጠ ትርፍና ጥቅም እንዲያገኝ ስለ ፈቀዱ የዚህ የርሻና የንግድ ማስፊያ ማህበር ሥራ ከተጀመረበት ከግንቦት ፳፫ ቀን ፲፱፻፩ ዓመተ ምሕረት አንሥቶ እስከ ፲፱፻፲፯ ዓመተ ምሕረት ድረስ እንዲመረመርና ጥፋቱም ልማቱም እንዲታወቅ ትእዛዝ አደረጉ ።

ተመርምሮም ካለቀ በኋላ ዋናው ፫፻፸፫ሺ. ፰፻፴ ብር ሳይጎድል ከትርፉ ብቻ ማኅበሩ የወሰዱት ፪፻፹ ሺ. ፯፻፺፰ ብር ፫ መሐለቅ ሆኖ ተገኘ በዚሁም ሒሳብ ፻ ብር ያገባ ሰው ፹ ብር ፤ ሺ. ብር ያገባ ሰው ፰፻ ብር ፲ ሺ. ብር ያገባ ሰው ፰ ሺ. ብር ማግኘቱ ነው ይኸውም ማኅበሩ በቆመ በ፲፯ ዓመት ነው ። የ፲፯ኛው ዓመት ትርፍ ገና አልተሰጠም ይህንም ያህል ትርፍ መገኘቱ እጅግ የሚያስደንቅ ነገር ነው ። ይኸውም እንኳ ማህበሩ ትርፉን በየመቱ እየወሰዱት ነው እንጂ ትርፉ ወደዚያው እየተመለሰ እየገባ ዋና እየሆነ ተበድሮ ቢሆን ከዚህ የበለጠ ትርፍ እንዲገኝበት ጥርጥር አልነበረም ።

ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ይህን የእርሻና የንግድ ማስፊያ ማህበር ሥራ አስመርምረው ዋናው ፫፻፸፫ ሽ ፰፻፴ ብር ሳይጐድል ትርፍ ፪፻፹ ሽ ፯፻፺፰ ብር እንደ ተገኘበት ነገሩን ከተረዱት በኋላ በቀድሞ ሹሞች ጊዜ በብድር ወጥቶ ተመልሶ ያልገባ ብር ዋናው ከነወለዱ ፰፻፫ሺ. ፫፻፹ብር፲፩መሐልቅ ዋናው ከነወለዱ ተገኘ ይህም ብድር እስከሁን ተመልሶ ሳይገባ የቀረበትን ምክንያት እንዲመረምሩና ምክሩን እንዲቆርጡ በጥቅምት ፲፯ ቀን ማኅበሩን ሁሉ ሰበሰቧቸው ማህበሩም በዚሁ ቀን ተሰብስበው ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል መክረው ቆረጡ ።

መጀመሪያ ።

ይህ የእርሻና የንግድ ማስፊያ ማህበር ወደ ፊት ሥራው እየሰፋ እንዲሄድ ማህበሩ በአክሲዮን ገንዘብ እንዲጨምሩ ተስማሙ ።

ሁለተኛ ።

በቀድሞዎቹ ሹሞች በነጋድራስ በሀብቴና ባቶ ምትኬ ጊዜ በብድር ወጥቶ ተመልሶ ያልገባበትን ምክንያት አስመርምረው እነዚህ ሁለቱ ሹሞች የማህበሩን ገንዘብ እንደ ደንቡ ዋስ ሳይቀጥሩ ፤ መያዣ ሳይቀበሉ እንዲያው በከንቱ ለዘመድ ለወዳጅ ሰጥተውት እንደሆነ ወይም ለየራሳቸው ጉዳይ ወስደውት እንደሆነ ወራሾቻቸው አላፊ እየሆኑ እንዲከፍሉ ተስማምተው ቆርጠዋል።ነገር ግን እንደ ደንቡ ዋስ ተቀብለው መያዣ ይዘው አበድረውት ዋናው ተበዳሪው ወይም ተበዳሪውና ዋሱ የሚከፍሉት አጥተው እየጠፉ ሔደው እንደሆነ ወይም ከሥረው ባገር ተቀምጠው እንደሆነ ለመክፈል የማይችሉ መሆናቸውን ማህበሩ ከተረዱት በኋላ ከሣራው በማህበሩ ላይ ይሆናል እንጂ የቀድሞ ሹሞች ወራሾች አላፊነት የለባቸውም ብለው ተስማምተዋል ።

ደግሞ ዋናው ተበዳሪው ወይም ዋሱ ባገር እንዳሉ ወይም የተበዳሪውና የዋሱ ርስትም ገንዘብም ይገኝ እንደሆነ የዛሬዎቹ አዲሶቹ ሹሞችና የፊተኞቹ ሹሞች ወራሾች ባንድነት እየሆኑ እየያዙ ገንዘቡን እንዲያስገቡ ተስማምተዋል ።

የቀድሞዎቹ ሹሞች ነጋድራስ በሀብቴና አቶ ምትኬ የማኅበሩን ገንዘብ አላገባብ ማበደራቸውንና ባገባብ ማበደራቸውን መርምረው ወራሾቹን አላፊዎች ያደርጋቸው እንደ ሆን ወይም አላፊዎች አያደርጋቸው እንደ ሆነ ፍርዳቸውን ለማኅበሩ የሚያስታውቁ በዚህ ማኅበር ውስጥ ያልገቡ የውጪ ሰዎችን ማኅበሩ ፈቅደው ተስማምተው መርጠዋል ። የተመረጡትም ጸሐፌ ትእዛዝ አፈ ወርቅ ፡ ብላታ ኅሩይ ነጋድራስ አስታጥቂ ፡ አቶ ብርሃን ማርቆስ ፡ ፊታውራሪ ዲሬሳ ፡ አቶ አሸኔ ሙሴ ሻንዋ ናቸው ።

ሦስተኛ ።

ወደ ፊት የዚህ ማኅበር የሥራው መስፋት የገንዘቡ መብዛት በማኅበሩ ፊት ስለ ተወደደ ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ የሀያ ሺ. ብር አክሲዮን ገዝተው አገቡ ።

ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንንም በራሳቸው ስም የአሥር ሺ. ብር አክሲዮን ገዝተው አገቡ ። የቀሩትም ማህበረተኞች የ፲፫ሺ. ብር አክሲዮን ገዝተው አገቡ ። አሁን የተጨመረው ገንዘብ ድምሩ ፵፫ ሺ. ብር መሆኑ ነው ።

አራተኛ

ይህን የማህበሩን ሥራ ከተጀመረበት ዘመን ጀምሮ እስከሁን ያለውን በጥንቃቄ ለማህበሩ ላስታወቁ ሠራተኞች ማህበሩ ወዲያው ተስማምተው ፲ሺ. ብር ሽልማት ሰጥተዋል ።

ይህንም ሁሉ መጻፋችን ብዙ ሰዎች ይህ የርሻና የንግድ ማስፊያ ማህበር ከሠረ እያሉ ብዙ የሐሰት ወሬ ሲያወሩ ነበረና መክሠራችን ቀርቶ ብዙ ትርፍ ማግኘታችንን ለማስረዳት ብለን ነው ። ይህንንም የማህበሩን ሥራ ከሥሩ እስከ ጫፉ መርምረው ያስታወቁን አላፊዎቹ ሙሴ ዋህራም ። አቶ ይታጠቁ ሙሴ ባስልዮስ ናቸው ።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ማህበር ።

ስለ መልካም ሐሳብ ።

ልዑል አልጋ ወራሽ ላገራቸው ለኢትዮጵያ የሚያስቡላት ራስዋን ችላ እንደ አውሮፓ ሰዎች ያለ ፍርሀት ያለ አሳብ እንድትኖር ብለው ነው።አሁን ግን የሀገራችን ሰው በስንፍና ተይዘ መኖሩ በጣም ያሳዝናል።እንዴት ካንድ አዳም ተፈጥረን ሌሎች በሠሩት መዛሪያ እኛ እየተቀበልን እንኩራበት የሰው ጨርቅ አያደምቅ እንደሚሉት እውነት ነው አሁን እያንዳንዳችን ብናስበው በጣም የሚያሳዝን ነው ።

እኛ ግን የያዝነው እውቀት ሌሎች በሠሩት ሥራ ማድነቅ ዛሬከ እንደዚህ እንደዚህ ያለ ነገር አየሁ እያልን ማውራት ነው እንጂ እውነት እገሌ እንደዚህ ያለ ሥራ ሠርቶ አይቻለሁና ቢሆን ከሱ የሚበልጥ አድርጌ እሠራለሁ አለዚያ ደግሞ እንደሱ ልሥራ የሚል የለም ።

ሁለተኛ ደግሞ የሀገራችን ሰው ልጁን ወደውጪ አገር ሲሄድ እንደ ውሀ ፊሶ እንደ ትቢያ በኖ የሚቀር እየመሰለው የብዙ መኳንንት ልጅ ሳይማር በመቅረቱ ልዑል አልጋ ወራሽን ይኸ ከንቱ አሳብ ስላሳዘናቸው እንደ ፈረንጅ አገር ትልቅ ተማሪ ቤት አሠሩ ።

. ልዑል አልጋ ወራሽም ለሀገራቸው ሲሉ ብዙ ገንዘብ ሰጥተው ስላሠሩ የኢትዮጵያ ሕዝብ በጣም ደስ ብሎታል እንዴት ቢሉ ልጆቻቸውን ጥዋትና ማታ አብቶቻቸው ሲያዩዋቸው ደግሞ ትምህርት መማራቸው ሁለት ጥቅም ስለሆነ ደስ ብለዋቸዋል ግን መኳንንቱ ሁሉ ልጁን አሽከሩን ከትምርቱ ቤት እያገባ ያስተማረ እንደሆነ በትክክል ደግሞ ልዑል አልጋ ወራሽ ከሁኑ አብልጠው ትልቅ የትምርት ቤት እንዲያሠሩ የታወቀ ነገር ነው ። ልዑል አልጋ ወራሽ ያስመጡት የጽህፈት መኪና ለኢትዮጵያ ሁሉ ደስ ብሎታል እንዴት ቢሉኝ እነ አፈ ወርቅ እነ ሲራክ ይኸን የመሰለ መጻሕፍት ሁሉ ዋጋው እስተ አምሳ ብር እስተ መቶም ድረስ ይሸጥ እንደ ነበረ ልባችን ያውቃል ፤ ሁለተኛ ደግሞ መግዣ ገንዘብ ያጣ አገሩን ትቶ ዘመዶቹን ጥሎ ያንድ ወር ወይም የሁለት ወር መንገድ ሄዶ ከንድ መምሕር ይማር ነበር ። ኋላ ግን ከንድ መምሕር ወደ አንድ መምሕር ሲገባ ሲወጣ ከንድ አገር ወደ አንድ አገር ሲዞር ሲዞር እድሜውን ሙሉ እየተንከራተተ ይጨርሰዋል ከገሩ ሲወጣ ለትምህርት ብሎ ይወጣል ኋላ ግን ሲቸግረው ጊዜ ትምርት አልገባህም ሲለው ጊዜ ወንበዴ ቀማኛ ሆኖ ይቀራል። አሁን ግን ያ የሚያስቸግር አለ መቶ አለ ሁለት መቶ የማይገኝ የነበረ መጻህፍት ለሕዝባቸው ለሀራቸው ሲሉ ሁሉ ብልህ ሁሉ አዋቂ እንዲሆንላቸው በጥቂትዋጋ እንዲሸጥ አደረጉት

ዛሬ ግን መንከራተቱ ቀረና ሁሉም ብልህ ሁሉ መጽሐፍ ተመልካች ሁኖ ቀረ ስለዚህ ሁሉም እያንዳንዱ ልዑል አልጋ ወራሽ ለዘዓለም ሕያው ይሁኑልን እያለ መጻሕፍቱን ባየ ቁጥር ያመሰግናል ። የተማረ ሰውና ዕውቀት ያደረበት ሰው ምንም ቢሆን ለሀገሩ ጥቃት ሊገባበት አይወድም ራስዋን ችላ ከሁሉ በላይ እንድትሆንለት ነው የሚወድ እንጂ ፤ እኔ ግን ይሀን ቃል መጻፌ የሃገራችን ሰው ትምርት እንዲማር ነጠላ ትቶ ድርብ እንዲለብስ ነዳ ልብስ ትቶ ጥበብ ሸማ እንዲለብስ ብዬ ነው እንጂ እውነት ከነሱ አውቄ በልጬ አይደለም። ዳሩ ግን ኢትዮጵያ ገነት የመሰለች አገር እያለች ፍቅር በማጣትና ትምርት ባለ መማራችን አዝኘ ነው የጻፍኩት ። አሁን ግን ልዑል አልጋ ወራሽ ካሠሩልን ትምርት ቤት ሁላችን ተምረን ራሳችንን ችለን ላየን ሰውና በወሬም ለሰሙን ሰዎች እንዴት ይቆጫቸው ይሆን ምሳሌ። ጠባቂ የሌላቸው በጎችና ትምርት ያልተማረ ሰው አንድ ነው ማለት በጎች ጠባቂ የሌላቸው እንደሆነ ተኩላ ይፈጃቸዋል እንስሶች ናቸውና የሚመጣባቸውን የማያውቁ ስለሆነ፡ ያልተማረ ሰው ደግሞ ጠላት ቢመጣበት አገሩን ሊዘርፈው ቢወጣበት እነ ዚህ ሰዎች ምንድር ናቸው ምን ይሠራሉ ምን ያስባሉ ብሎ አያውቅም አይመረምራቸውም ዝም ብሎ ይዘረፋል እያየ ይታረዳል እንጂ ። የተማረ ሰው ግን የሚመጣበትን ያውቃልና ጠላት የመጣበት እንደሆነ መግቢያውንና መውጫውን ይፈልጋል ስለዚህ እገሌ አዋቂ ነው እገሌ ብልህ ነው እየተባለ ሲፈራ ይኖራል። ባንድ ብልህ አገር ሁሉ እንዲድን የታወቀ ነው ይኸን ስላልሁ ግን እያንዳንዳችን ብንማርና ራሳችንን ብንችል ይገባናል እንጂ የሰውን ብልህነት ከመተማመን የራስ እውቀት ይሻላል

ጋዜጣውን ብርሃንና ሰላም ብለው ስለሰየሙት በጣም ደስ ያሰኛል ታሪክ መመርመርና ብርሃንና ሰላምን ማንበብ ዓለምን ሁሉ ዞሮ እንደማየትና ከዓለም ሕዝብ አብሮ እንደ መጫወት ያለ ነው ። አሁን ግን ልዑል አልጋ ወራሽ ለሀገራቸው ሲሉ ኢትዮጵያ ራስዋን እንድትችል ስለ አሰቡላት እግዚአብሔር እንደሰሎሞን ጥበብ እንደ ማቱሳላ ዕድሜ ይስጥልን። መቼም አምላክ የነገሩትን የማይረሳ የለመኑትን የማይነሳ ነውና ለልዑል ጌታችን ደግ አሳባቸው እንዲፈጸምላቸው በትክክል ተስፋ አለኝ

ቈንጠንጢኖስ ኃይለ መለኮት

ማስታወቂያ ።

በርሻና በመስሪያ ሚኒስትር ሥራ ውስጥ መንግሥት ያወጣውን ደምብና ሕግ ሳልተላለፍ ደህ ሳልበድል ፤ የመንግሥቱን ገንዘብ በጥንቃቄ ሠርቼ ቀድሞም ከሚሠራው ሠራተኛ ገቢ ገንዘብ አብልጬ አገባለሁ የሚል ሰው እርሻና እመስሬ ምኒስቴር መጻፊያ ቤት ፤ ሁል ጊዜ ከጧቱ ከ፫ ሰዓት እስከ ፬ ሰዓት ድረስ፡እየመጣ ቢነጋገር በደስታ እንቀበለዋለን ደመወዙም እንደ ሥራው ገቢ እየታየ ይቈረጥለታል ጥቅምት ፲፩ ቀን ፲፱፻፲፰ ዓመተ ምሕረት። መኰንን ሀብተ ወልድ

ማስታወቂያ

ለራሶችና ለደጃዝማቾች ለሴት ወይዘሮች የሚገባ በያይነቱ ጥሩ ከባ ከኤሮፓ መጥቶልኛል ቤቴም (ባንክ አፍ አቢሲንያ) ከእንግሊዞች ባንክ አጠገብ ነውና ይህን ከባ መግዛት ለሚፈልጉ ሰዎች መጥተው እንዲገዙ አስታውቃለሁ ። ኢያሱ ዳንኤል

አ ፔ ማርሲያኖ

በኢትዮጵያና በፈረንሳይ የቅኝ አገር ሶማሊ በተለየ ፊያት አውቶሞቢልና ትራክተር አስመጭና እንደራሴ ።



A.P. MARCIANO

Concessionnaire Exclusif pour l'Ethiopie
et la cote française des somalis
des automobiles et tracteurs Fiat.

መጀመሪያ ዓመት ፤ ቁጥር ፵፭ ።
1re ANNÉE № 45

ሐሙስ ጥቅምት ፳፮ ቀን ፲፱፻፲፰ ዓ ም።
JEUDI 5 NOVEMBRE 1925

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህነን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት
Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d'Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé "Lumière et paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraissant tous les jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

የጋዜጣው ዲሬክተር ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።
Gabré Christo Taklé Haymanot
Diréсteur

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሲገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ጥቅምት ፲፪ ቀን የአዲስ አበባን ጕምሩክ ሰራተኞች የሥራቸውን አካሄድ ለመጐብኘት በሄዱ ጊዜ የጕምሩኩ ዲሬክተር አቶ ገብረ እግዚአብሔር የተናገሩት ቃል።

ይህች ትውልድ ሥራዋን ፈጽማ ማለፍ ይገባታል ። የወራቷን መራራነት እየተመለከቱ የጊዜዋን ጽዋ መጠጣት ሲአቅታቸው የአገሬ ልጆች የማይቻለውን ነገር ይመኛሉ ፤

እንዲህ እያሉ ሲሆን ከአምሳ ዓመት በኋላ አለዚያም ከ፴ ዓመት በፊት በዚች ዓለም መጥተንበት ቢሆን ደህና ኑሮ እንኖር ነበር።አሁንስ የሰዓቷም ፈተና አልቻልም አለ ግን ይህች አሳብ ለሐዋርያው ቃል አትስማማውም ቅዱስ ያዕቆብ እንዳለው በመከራ የሚታገሥ ሰው ብፁዕ ነው ከተፈተነ በኋላ የሕይወትን አክሊል ይወስዳልና ደግሞ ያለፈችውም የምትመጣውም ትውልድ ሁሉ የመከራን ጊዜ ጠልታ እንደፈቃዱዋ የደስታን ጊዜ ብቻ ብትመርጥ መራራዋ የፈተናዋ ሰዓት በማናቸውም ጊዜ ትድረስ።የቀረውን ዓለም አድርሳለችና መምጣቱዋ የማይቀር ስለ ሆነ በአንደኛው ትውልድ ትደርስ ዘንድ የግድ አለባት ይህችም የፈተና ወራት የደረሰችባት ትውልድ ዕድሏ ነውና አክሊልን ለመቀበል አሸናፊ መሆን የተገባት ነው ።

ሐዋርያ ጳውሎስ እንዲህ አለ ስለ ዚህም ያነን ትውልድ ተቆጣሁ አልሁም ሁልጊዜ በልባቸው ይስታሉ መንገዱንም አላወቁም አሁን ግን ይህች ትውልድ የእውነተኛውን መንገድ ታውቅና ትከተል ዘንድ የግድ ይሆንባታል እረኛዋ በእርግጥ መንገድዋን አግኝቷታልና ሐዋርያ እንዳለ ዛሬ ግን እርሱ የምትበልጥ ማገልገል አገኘ ለምትበልጥ ሥርዓት መካከለኛ ሁኖዋልና በተሻለ ተስፋ ላይ ተመስርታለችና ።

በተሻለ ተስፋ ላይ ከተመሰረተች ከዚች የሚሻል ወራት መቸም አይመጣ ስለዚህ የተሰናዳውን ሽልማትና ስም ላልተሰናዳለች ትውልድ አሳልፎ መስጠት ለሚአልፈው ጊዜያት የማያልፍን መጥፎ ስም ትቶ መሄድ ታላቅ ስንፍናና ውርደት ይሆንብናል የሰው ልጅ መስራት የሚገባው ይልቁንም ከመቃብር በላይ ለሚኖር ስለሆነ ሐሳባችን እንዲፈጸምና እንዲኖር ሥራችን እንዲጸናና እንዲመሰረት የሚአስፈልግ ከሆነ ሐዋርያው የተናገሩትን ቃል መፈጸም የተገባ ነው እንዲህ ሲል ሥርዓትም ወዳለችበት የሥራት ሞት ይመጣ ዘንድ በግድ ይፈለጋል ሥርዓትም በሞቱ ሰዎች ጸንታለችና ይህ ስለተባለ የሚጋደልም ቢሆን አክሊል አይወስድም ለሚገባው እንደሚገባው ካልተጋደለ ይህችንም ወራት ይህችን ጊዜ ስለክብርና ስለስምዎ በጣም የሚመኙዋት ልጆች ይወለዳሉ ነገር ግን አያገኙዋትም ክፍላቸው አይደለችምና ባለክፍሎቹ ግን ሊመረሩ አይገባቸውም የበለጠ ደስታ ወደፊት አላቸውና ትንሽና ትልቁ በስርዓት ፊት ትክክል የሚሆንበት ጊዜ ሐዋርያው እንዳለ እኔም እላለሁ ወራሹ ሕፃን በሆነበት ዘመን ሁሉ በርሱና በባሪያ መካከል ልዩነት የለውም እርሱ የሁሉ ጌታ ሲሆን ደግሞ የዚህ የሕጻኑ የአባቱና የናቱ ልጆች ወንድሞቹ አያሌ ናቸው ይልቁንም በሚመጣው ትውልድ ከአንድ ሐሳብ ማኅፀን ተረግዘው የሚወለዱት በሚሊዮን ይቆጠራሉ ።

ይህንንም ለመረዳት የኢትዮጵያ አልጋ ወራሽ የመንግሥቱ እንደራሴ ተፈሪ መኰንን የተናገሩትን ቃል ማሰብ ይበቃል ልጁን ያላስተማረ ሰው ከነፍሰ ገዳይ ይቆጠራል አሉ ። ይህ

ቃል ለሚሰማው ሰው ከፓላንቲን ይበልጥ ይመዘናል ከፓላንቲም ይበልጥ ዋጋ አለው ነገር ግን ሐዋርያው እንዳለው ልባቸው ታወረ እስከ ዛሬ ድረስ ያ የረጀው ሥርዓት በተነበበ ጊዜ መጋረጃው ይሰውራቸዋል አይገለጥላቸውም በክርስቶስ እንዲሻር እስከ ዛሬ የሙሴ መጽሐፍ እየተነበበ መጋረጃው በልባቸው አለ እውነተኛ ትምሕርት የማይቀበሉባት ጊዜ ይሆናልና ነገር ግን እራሳቸው በፈቃዳቸው ለራሳቸው መምሕራንን ያከማቻሉ ጆሮዋቸውን ደስ የሚያሰኙትን ። ጆሮዋቸውንም ይመልሳሉ እውነት ከመስማት ወደተረትም አንተ ግን በሁሉ ንቃ መከራ ተቀበል የወንጌላዊን ሥራ ሥራ መልእክትን ፈጽም ።

ይህንን መጋረጃ የሚቀደው መሣሪያ ሥራ ተጀምሩዋልና ደግሞ ሐዋርያው እንዳለ አሪት እንግዲህ ለምንድር ናት አሪትስ ስለ ኃጢአት ተሰራች ተስፋ ያለው ዘር እስኪመጣ ድረስ ።

እንግዲህ አንች ትውልድ፤ ተስፋ ያለው ዘር ተጀመረ ደስታሽም ወሰን የሌለው ይሆናል ከዚህም ከዘር የምትጠጭው ወይን ያሰክርሻል አመድ ብቻ በነበረበት ምድጃ ሁሉ እሳት ይቀጣጠላል ብርሃኑም የማይጠፋ እስከሚመጣው ትውልድ ለዘለዓለም ያበራል መልእክቱንም የፈጸመው ሰው የደስታው መጨረሻ ይሆናል ስሙም ከለፉት ነገሥታት መሐከል እንደኃይለ ኛው ኮከብ ያበራል በእውነት ከዚያችና ከዚች ቀን ይህችን ቀን እመርጣለሁ የተመረጠች ስለሆነች ዋጋዋም ታላቅ ነው ለሚገባው በሚገባ የሚጋደሉት የዘለዓለም አክሊል ይወርሱባታልና ።

የአገሬ ልጆች ወንድሞቼ ሆይ እራሱን እራሱ የማያሞኘው ሰው በሕሊናው ላይ ሐሰት የሚናገር ለተናገረው ነገር ሥራው የማይመሰክርለት ሐሳቡና ቃሉ ሥራውና ንግግሩ ጠላቶች ናቸው ሰውንም ለማታለል የሚፈልግ በእንደዚህ ያለ ሐሳብም ተመሥርቶ የሚኖር እራሱን ሲአታልል ይኖራል የቀናውንም መንገድ በክፉ የሚተረጉም የዕውነተኛውን የሥርዓትንና የሥራን መንገድ መከተሉን ትቶ በአረጀ ሥርዓትና ሥራ ላይ ተስፋውን የመሰረተ ለአገሩ አገልጋይነት ለመመረጥ የተገባ አይሆንም ወንድሞቼ ትላንት ስማችሁ ምን ነበረች የዛሬስ ስማችን ምንድር ናት? ልባችሁና ልባችን ያውቀዋል ። ለመንግሥቱና ለጌታው ከመታመን የበለጠ በዚህ ዓለም ላይ ሌላ አገልግሎት ይገኝ አይመስለኝም በዚህ የማያምን ሰው ከሐዲ ነው እምነት ተሰጥቶት በተቀመጠበት ቦታ ላይ ያልታመነ መሆን በረቀቀ የክፋት መንገድ መንግሥቱንና ጌታውን ሲአታልል የሚኖር መንግሥቱን ከሸጠ ልክ ይቆጠራል እንመልከት እናስብም በምንሠራው ሥራ ላይ ከአንድ ሺህ እስከ አምስት ሺህ ከሁለት እስከ አሥራ ሶስት ሺህ ከስምንት እስከ አርባ ሺህ እንደዚህም በየአይነት የደረስንበት ብዙ ቁጥር አለ ስለዚህ ለቄሣር የሚገባውን ለቄሣር ስንሰጠው እኛም ዋጋችንን ልንቀበል የተገባ ነው ። ልባችን ንጹሕ እጃችን ንጹሕ ሆኖ መንግሥታችንን አስመስግነን እኛም ተመስግነን መኖር ከዚህ የበለጠ ደስታ ለሰው ልጅ የለውም በገንዘብ ላይ የተቀመጡት ሽማግሌዎችም ሕጻናቶቹም የመንግሥት ኃይሉ ገንዘብ መሆኑን አይስቱትምና ስለዚህ በሚገባው እንደሚገባ መንግሥታቸውን ሊአግዙት ግዴታ አለባቸው ብለው ጨረሱ።

ከዚህ በኋላም ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን የሚከተለውን ቃል ተናገሩ ።

የዛሬውን ዓመት ሥራችሁን ስለ ዓየሁና ስለ መረመርሁ ለጊዜው የሚገባችሁን ምስጋና ማስቀረት አይገባኝምና ሥራችሁን በሥጋና በነፍስ ምሳሌ ስንግራችሁ ምሥጢሩ እንዳይሰወራችሁ አውቃለሁ ።

በማናቸውም ዓለም ላይ ቢሆን የመንግሥት ትልቅ ሕይወቱ ገንዘብ መሆኑን ማንም ሰው ሊያውቀው ይችላል ። ሥጋ በነፍሱ ሕያው ሁኖ እንዲኖር መንግሥትም ከችግሩ ሁሉ ሕያው ሁኖ የሚኖረው በገንዘቡ ነው ። ነገር ግን ማንም ሰው ቢሆን እግዚአብሔር እስከወሰነለት ዘመን ድረስ ሕይወቱ የምትሆን ነፍሱ ከርሱ እንዳትለየውና መዋቲ እንዳይሆን የሚቻለውን ያህል ማሰቡና መጣጣሩ አይቀርም ። መንግሥትም መንግሥት ተብሎ እስከሚኖርበት ዘመን ድረስ ገንዘቡ ከግምጃ ቤቱ እንዳያልቅ ለመስጠትም እንዳይቸገር የሚቻለውን ያህል ማሰብና ማድረግ ይገባዋል ።

ደግሞ ሥጋ በበሽታ ምክንያት ሕይወቱ ከምትሆን ከነፍስ እንዳይለይ የሃኪም መድኃኒት ያስፈልገዋል፤ በረሀብም ምክንያት ከነፍሱ እንዳይለይ ምግብና መጠጥ ያስፈልገዋል መንግሥትም ገንዘብ ከግምጃ ቤቱ እንዳያልቅበትና ለመስጠት እንዳይቸገር ለየሥራው ሁሉ የታመኑና የሚተጉ ሠራተኞች እንዲያስፈልገው ጥርጥር የለበትም ።

ሥጋ ከነፍሱ ከተለየ በኋላ ለብቻው ሕያው ሆኖ ለመኖር እንዳይችል መንግሥትም በግምጃ ቤቱ ገንዘብ ከሌለው የመንግሥቱን ጉዳይ ሁሉ ለማቃናት ትልቅ ሥራ ለመሥራት አይችልም ። እነዚህም ከሥጋ በሽታ የሚያድን የሃኪም መድኃኒትና ከሥጋ ረሃብ የሚያድን ምግብ የሚገኙ ከመሬት እንደሆነ የመንግሥትም ትልቁ ብልጽግናው የሚገኘው ከንግድ ሥራ ውስጥ ከጉምሩክ መሆኑን በዓለም ላይ የታወቀ ነው ። በሃኪም መድኃኒትና በምግብ ውስጥ መርዝ የገባበት እንደሆነ ማዳኑ ቀርቶ ሌላ በሽታ እንዲጨመርበት ። በመንግሥትም ሥራ ውስጥ የማይረባና ሁከተኛ ሠራተኛ የገባበት እንደሆነ ወደፊት ትርፍ ገንዘብ መገኘቱ ይቅርና ቀድሞ የተገኘው ገንዘብ እንዲጠፋ ጥርጥር የለበትም ።

በቀድሞ ዘመን የጉምሩክ ገንዘብ እጅግ ጥቂት እንደነበረ ሁላችሁም ሳታውቁት አትቀሩም ። ያውም ቢሆን ባመት ይህን ያህል ጨው ይህን ያህል ዳውላ እህል ገባ ይባል ነበር እንጅ የብር ገቢ እጅግ ጥቂት ነበር ደግሞም የቀድሞውን ዘመን የጉምሩክ ገቢ ገንዘብ እንተወውና ባለፈው ዓመት ከአዲስ አበባ ጉምሩክ ብቻ ፩ሚሊዮን ፶፩ሺ ፯፻ ፵፫ ብር ፪ሺ ፯፻ ፵፱ ዳውላ እህል ብቻ ገብቶ ነበር በዛሬው ዓመት ግን ፩ሚሊዮን ፯፻ሺ ብር ፳ሺ ፳፻ ዳውላ እህል ገባ ።

ይህንንም የዛሬውን ዓመት ገቢ ገንዘብ ከቀድሞው ዘመን የጉምሩክ ገቢ ጋራ ብናማዝነው የቀድሞ ያምስቱ ዓመት ገቢ የዛሬውን ያንዱን ወር ገቢ እንዳይተካከለው የታወቀ ነው ።

ይህም ሁሉ መሆኑ መጀመሪያ የንግድ ሚኒስትሩ ነጋድራስ ዘለቀ ለጉምሩክ ሥራ መስፋትና ለገንዘቡ መብዛት መሰናከል ሳይሆን ሠራተኞቹን በመርዳት ነው በርሱም

ሚኒስትርነት ጊዜ የጉምሩኩም ሥራ እየሰፋ ስለ ሔደ ለነጋድራስ ዘለቀ ትልቅ ስምና ክብር ነው ።

ሁለተኛ ዲሬክተሩ አቶ ገብረ እግዚአብሔር በእውቀቱና በትጋቱ ሠራተኞቹን በሥልጣኔ መንገድ በመምራቱ ነው ።

ሶስተኛም እናንተ ሠራተኞች በቀድሞው በጠባቡና በጨለማው ሥራችን ኋኑር ሳትሉ ሰፊና ብርሃን የሆነውን የእውቀት መንገድ በመከተላችሁ እንደ ሆነ ልቤ ተረድቶታል ።

ወደፊትም በየወሩ በየዓመቱ ሥራችሁ ከታችኛው ደረጃ ወደ ላይኛው ደረጃ እየወጣ የጉምሩክ ገቢ ገንዘብ እየበዛ እንዲሔድና በዚሁ ምክንያት በመጀመሪያ እናንተ ተመስግናችሁ ቀጥሎ መንግሥታችንን እንድታስመሰግኑ ጥልቅ የሆነ ምክር እመክራችኋለሁ ።

የናንተም ሥራችሁ እየሰፋ የሔደ እንደሆነ በሙሉ ኢትዮጵያ ውስጥ ላሉት ለጉምሩክ ሠራተኞች ሁሉ መልካም ምሳሌ ትሆናላችሁ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ ።

ከዚህ ቀደም ለድሬዳዋ ጉምሩክ ሠራተኞች እንደተናገርኩት እናንተም እንደዚህ እንድትሆኑ ። ይህችም በሥልጣኔ የተሠራውን የጉምሩክን ሥራ ያየሁባት የዛሬ ቀን ትልቅ የደስታ ቀን መሆኑዋን አስታውቃችኋለሁ።ደስታዬም ስለ ሶስት ነገሮች ነው መጀመሪያ ደስታዬ በሥራችሁ ውስጥ ሁከትና ጭቅጭቅ ሳታደርጉ በፍቅርና በመስማማት ሥራችሁን በመሥራታችሁ ነው መልካም ሥራ ሁሉ የሚፈጸመው በፍቅርና በመስማማት መሆኑን ልቤ ስለ ተረዳው ይህ ትልቅ ደስታ ነው ።

ሁለተኛ ደስታዬ መንግሥታችን ለሚያስፈልገው ጉዳይ ሁሉ ገንዘብ ለማውጣት እንዳይቸገር የጉምሩክ ገቢ ገንዘብ በመብዛቱ ነው ። አባት ልጆቹ በተራበ ጊዜ ምግብ ለመስጠት በንተራው ብዙ እህል መኖሩን ሲያውቅ እጅግ ደስ እንዲለው መንግሥትም ለሠራዊቶቹና ለወታደሮቹ የሚሰጠው ገንዘብ በግምጃ ቤቱ መኖሩን ባወቀ ጊዜ ደስ ይለዋል ።

ሶስተኛው ደስታዬ ዲሬክተሩ አቶ ገብረ እግዚአብሔር ወደ ውጭ አገር ሳትሄድ በዚሁ ባገርሀ ውስጥ ተምረሀ ለጉምሩክ ሥራ መሪ ስለመሆንህ ነው።እናንተም ሠራተኞች በትምሕርት ቤት ሳትገቡ በመስማትና በመጠየቅ በመሥራትና በመልመድ ብቻ ሥራችሁን ስለ ሠራችሁና ከዚህ ደረጃ ስለ ደረሳችሁ ነው።ልጅ ትጉህና አዋቂ ሲሆን ለአባቱ ትልቅ ደስታ እንደሆነ እናንተም በትጋታችሁና በዕውቀታችሁ የጉምሩክን ሥራ በማስፋታችሁ ለመንግሥታችን ታላቅ ደስታ ነውና በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ስምና በኔም በራሴ ስም ሆኜ የሚገባችሁን ምስጋና አመሰግናችኋለሁ ፤

ይህም ደመወዛችሁን መጨመራችን ገበሬ የዘራው እህል በቅሎ ቡቃያውን እንደማየት ያህል ነው ነገር ግን ገበሬ የዘራው ዘር ከበቀለለት በኋላ ቡቃያውን አይቶ አረሙን አርሞ የፍሬው ወራት በደረሰለት ጊዜ እጅግ ደስ እንዲለው እናንተም ሥራችሁን ሁሉ በጣም አጣርታችሁ መጨረሻውን ባሳያችሁኝ ጊዜ የድካማችሁን ፍሬ ትልቁን ምስጋናና ክብር አግኝታችሁ ደስ እንዲላችሁ አይጠረጠርም ብለው ጨረሱ ።

የአዲስ አበባ ጉምሩክ ሥራ አኳኋን ።

በ፲፱፻፲፯ ዓመት በአዲስ አበባ ጉምሩክ ከውጭ አገር የገባውንና ከአገር የወጣውን የንግድ ዕቃ ይልቁንም በወጭና በገቢ ዕቃ የስንትስ ገንዘብ ያህል እንደ ተነገደ ልኩን ለማወቅ የሚያስፈልግ ስለሆነ ስለዚሁ ንግድን ለሚነግዱ ሰዎችና በንግድም በኩል የአገርን መጠን ለመለከት ለሚፈልጉ ሰዎች መለኪያው የሰንጠረጋር ቀመር (ስታቲስቲክ) ስለሆነ እንደሚቻለን መሬ እንዲሆናቸው ብለን በብርሃንና በሰላም ገልጸነዋል ። ይህም ያለ መጠራጠር ለኢትዮጵያ ሕዝብና ለውጭ አገር ሰዎች ሁሉ ደስ ሳያሰኛቸው አይቀርም ፤ ደግሞ አገርንና ሕዝብን የሚያበለጥጉት መሠረቶቹ አራት ነገሮች መሆናቸው በመረመሩትና ባወቁት ሕዝቦች ተመስክሯል ። አገርንና ሕዝብን የሚያበለጥጉት ነገሮች አራት ናቸው ያልናቸው መጀመሪያ ንግድ ሁለተኛ እርሻ ፫ኛ ፋብሪካ አራተኛ የምድር ባቡር የአቶሞቢል የጋሪ መንገድና በያለበት ስልክን መዘርጋት እነዚሁ አራት ነገሮች የመንግሥትና የሕዝብ ሥርና ደሙ ናቸው ፤ ያለነዚሁ ተንቀሳቃሾች ያለም ሕዝብ ቢኖር ከመኖር አይቆጠርም፤ነገርግን ያገራችን ሕዝብ ከዚሁ የበለጠኑሮ በመኖሩ አላመነምና የኑሮ ወሰኑ ይህ የሚኖርበት አነዋወር ይመስለው ነበር።በጭሩ ቃል የኛ አገር ሰው ባለጠጋ ነው የሚባለው በብልጥግናው ሊሠራበት ይገባዋል በሚገባው ቦታ እንደሚገባው የማይሠራ ከመኖር አይቆጠርም ።

ይህም በሰንጠረጋር ቀመር (በስታቲስቲኩ) ውስጥ ያመለከትነው ቁጥር ከውጭ አገር ለሚገባው ዕቃ ዋጋው ልክ ነው ። ነገር ግን ከሀገራችን ለሚወጣው ዕቃ የአገርን ንግድ ለማበርታት ስንል ከገበያው ዋጋ ዝቅ አርገን እንገምተዋለንና ስለዚህ በእውነተኛው ግምት ቢሆን ዋጋው ምን ያህል እንደሆን እናመለክታለን።

ቡን የዓመቱ መካከለኛ ዋጋ	፫፻፳፯ሺ፰፻፲፫ፈረሲላ	X ፱ብ፰	=፫ሚ፻፱ሺ፯፻፹፫ ብር	፳መ
ቆዳ ፣ ፣ ፣	፩፻፴፰ሺ፱፻፲፰ ፣	X ፲ብር	=፩ሚ፫፻፺፱ሺ፻፹ ብር ፣	
ሰም ፣ ፣ ፣	፲፱ሺ፯፻፺፫ ፣	X ፲፩ብር	=፪፻፳፰ሺ፯፻፵፱ ብር ፣	
የበግ ቆዳ ፣ ፣	፰ሺ፳፻፳፰ኮረጃ	X ፰ብር	=፻፳፮ሺ፱፻፳፮ ብር ፣	
ድምር	፬ሚ፱፻፹፮ሺ፱፻፳፮		ብር	፳መ
የጓምሩክ ግምት	፱ሚ ፬፻፺፫ሺ ፯፻፹፱		ብር	፲፩መ
መለየው ፣	፫ሚ፱፻፺፪ሺ፴፻፶		ብር	፲፫መ

እንደዚሁ ሲሆን ከአገር ውስጥ የወጣው ዕቃ ዋጋ ፫ሚ ፺፱ሺ፹፻፲፩ብር ፩መሐልቅ ላልነው የቀረውን የትክክለኛውን የገበያውን ዋጋ ስንጨምርበት ፫ሚ፺፱ሺ፹፻፲፩ ብር ፩መ ተ፫ሚ ፬፻፺፪ሺ፹፻፶ ብር ፲፫ መሐለቅ ፱ሚ፻፺፪ሺ፺፻፶፩ብር ፲፬መሐልቅ ይሆናል ።

እንደዚሁ ሲሆን ከገቢ ዕቃ ዋጋው ፺ሚ፬፻፺፬ሺ፪፻፺፪ብር ፲፩መሐልቅ ከነበረው የወጭው ዕቃ ዋጋ ፱ሚ፻፺፰ሺ፫፻፺፫ብር ፫መሐልቅ ያይላል ስለዚህ ፱ሚ፻፺፰ሺ፫፻፺፫ብር ፫መ በ፲፱፻፲፯ ዓመት ከውጭ አገር ወደ አገር ገባ እንላለን ይህም ታላቅ ዕድል ነው ።

ደግሞ ፩፻፴፰ሺ፱፻፲፰ፈረሲላ ቆዳ ለመስጠት ፩ሚ፫፻፺፱ሺ ፻፹፩ በሬ ላምም አስፈለገ ከነዚህም ስንት ያህል በበሽታ ስንትስ ያህል ለምግብ እንደ ታረዱ ለይተን ቁጥሩን በትክክል አላወቅነውም እንደሚመስለን በአዲስ አበባ ጉምሩክ ተቆርጦ የታረደ በሬ ፲፫ሺ፬፻፳፯ ብቻ ነው ።

በቤተ መንግሥትና በየመኳንንቱ ቤት ደግሞ ለሠርግና ለማናቸውም በየዓይነቱ የሚታረደውን ከብት ብናስበው ከዚህ አይበልጥም ። ስለዚህ በአዲስ አበባ ከተማ ለምግብ የሚታረደው ከብት ፳፯ሺ.፰፻፶፪ ብቻ ነው ። ስለዚህ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጥቅም በከንቱ መቅረቱን ዝርዝሩን ከዚህ ቀደም በብርሃንና ሰላም በ፲፭ ቁጥር ተናግሬዋለኹ፡ደግሞ ለወደፊቱ በአገራችን ላይ በየጠረፉ ጉምሩክ ቆሞ ኢትዮጵያ የንግዷን ልክ በሰንጠረዥ ቀመር (በስታቲስቲክ) እናውቀዋለን ስል ብዙ ተስፋአለኝ ።

ገብረ እግዚአብሔር ።

የአዲስ አበባ ጉምሩክ ዲሬክተር ።

፲፱፻፲፯ ዓ ም ከመስከረም ፩ ቀን እስከ ጳጉሜ ፭ ቀን ወደ ውጭ አገር የሚሄድ ዕቃ ቁጥርና ፈረሱላ የዋጋው ድምር ።

የዕቃው ስም ።	የጥቅል ዓይነት	የቃው ብዛት ቁጥር	ፈረሱላ	ነጥር	የዋጋው ድምር ብር	መ
ቡን	ጆንያ	፳፯ሺ.፪፻፺፯	፫፻፸፯ሺ.፰፻፲፫	፲፫ኑ	፪ሚ.፪፻፹፫ሺ.፯፻፹፫	፭
የበሬ ቆዳ ፤	ቁጥር	፩ሚ.፫፻፶፫ሺ.፯፻፵፩	፬፻፷፫ሺ.፱፻፲፰	፲፯	፩፡፱፻፹፰ሺ.፰፻፷፱	፫
ሰም ፤	ጆንያ	፭ሺ.፱፻፺	፲፱ሺ.፯፻፵፫	፲	፻፲፯ሺ.፱፻፹፩	፱
ክርቤ	፡ ፡	፲	፵		፪፻፹	
ዝባድ	ዋንጫ	ሺ.፪፻፹፯	፵፫ሺ.፱፻ ፬	፭	፹፯ሺ.፰፻ ፱	፫
የዝሆን ጥርስ	ዋሰላ	ሺ.፪፻፺፩	፬፻፺	፯ሩ፩	፹፭ሺ.፰፻ ፰	
ዝንጅብል ከረሪማ አዝሙድ	ጆንያ	፫፻፵፩	ሺ. ፻፺፯	፲፯	፪ሺ. ፺፫	
ቀላድ ገመድ	ጥቅል	፳፭	፫፻፳፯	፲፬	፯፻፴፭	፯
የበሬ ሞራ	ጆንያ	፲፫	፵፪	፲፭	፻፹፬	፳
የፍየል ሌጦ	ከረጂ		፹፬ሺ.፻፯፺፬	፲፯	፫፻፵፪ሺ.፱፻፵፫	
የበግ ቆዳ	፡ ፡		፳ ሺ.፰፻፳፭	፲	፰፪ሺ.፭፻፺፯	፲
ያንበሳ ቆዳ	ቁጥር	፯			፬፻፳	
የነብር ቆዳ	፡ ፡	፲ ሺ. ፻፺፮			፺፯ሺ. ፭	
የጉሬዛ ቆዳ	ከረጂ		፬፻፳፱	፮	፭ሺ. ፲፯	፳
የግስላ ቆዳ	ቁጥር	፲፰			፭፻፵	
ያቆስጣ የዳልግ አንበሳ ቆዳ	፡ ፡	፯፻ ፩			ሺ.፯፻፺፯	
የድኩላ የሚዳቋ የአነር ቆዳ	፡ ፡	፬ሺ.፬፻፲፱			፬ሺ.፪፻፹	
የቀበሮ ቆዳ	፡ ፡	፭፻፷፯			፭፻፷፯	
የሚዳ አህያ የሜዳ ፍየል ያጋዘን ቆዳ	፡ ፡	፲፬			፵	
የዝንጀሮ የጉ የነበራርት የጦጣ ቆዳ	፡ ፡	፻፵፱			፻ ፪	፳
የጨና የጭሮ የሰርባ የፋዬን የፌላማ ቆዳ	፡ ፡	ሺ. ፺፪			፭፻፹፯	
የጥርኝ ቆዳ	፡ ፡	፪፻፹፰			፬፻፴፪	
ያሞራ የግሬት ክንፍና ቆዳ የሰጐን እንቁላል በያይነቱ	፡ ፡	፪፻			፻፺፫	
የዘንዶ ቆዳ ያውሬ ጥርስና ቀንድ በያይነቱ	፡ ፡	፴፭			፴፭	
የጐሽ ያውራሪስ የበሬ የድቁስ ቀንድና ዋንጫ	፡ ፡	፭፻፴፬			፯፻ ፬	
ሙቀጫ ክብሮ ከዘራ የንጨት መሳሪያ በያይነቱ	፡ ፡	፵፯			፻፴፭	
መሶብ አገልግል ጨጮ ስፌት በያይነቱ	፡ ፡	፳፰			፰፱	
ቁርበት ተምቤን የጀማ ትራስ መከዳ	፡ ፡	፵፰			፺፩	
ጨበ ጦር አንካሴ ጋሻ ብረታ ብረት	፡ ፡	፲፯			፰	፳
ጥና መስቀል ጭራ	፡ ፡	፷፰			፻፵፬	
ሽማ ማቅ	፡ ፡	፹፱			፫፻ ፬	
በርበሬ ሸንኩርት	ጆንያ	፻፸፩	፬፻፺፯	፲፭	ሺ.፬፻፲፯	፲፬
ቅቤ፤	ታኒካ	፻፸፰	፻፸	፲	ሺ.፫፻፷፪	፳
የበሬ ሥጋ ያሳማ የበግ ሥጋ ቋንጣ	ጆንያ	፪፻፲፬	፲፱ሺ.፬፻፺		፲፪ሺ.፪፻፷፯	፲፬
ማር ፤	ታኒካ	፲፪	፪		፻፷፫	፳
ኑግ ተልባ ሱፍ ሰሊጥ ሰናፍጭ	ጆንያ	፪፻.፯	፲፫ሺ.፰፻፲፱		ሺ.፫፻፴፬	፬
ማሽላ ዘንጋዳ በቆሎ ፡	፡ ፡	፫፻፲	፴፩ሺ. ፲		፯፻፸፭	፬
ገብስ፡	፡ ፡	፻፺፰	፲፱ሺ.፰፻		፬፻፺፭	

የዕቃው ስም ።	የጥቅሉ ዓይነት	የቃው ብዛት ቁጥር	ፈረሱላ ።	ነጥር	የዋጋው ድምር ብር	መ
ሽምብራ ፡	ጆንያ	ሺ ፺	፻ ፰ሺ		፩ሺ.፪፻	
ባቄላ አተር አደንጓሬ ፡	፡ ፡	፰፻፺፩	፺፱ሺ ፻		፪ሺ.፫፻፲፩	
የስንዴ ዱቄት ገለባ	፡ ፡	፲ ሺ ፵፰	፱፻፸፰ሺ.፫፻		፲፱ሺ.፮፻፴፱	
ምስር	፡ ፡	፳፬	፯ሺ.፬፻		፪፻፹፱	
አራት ማዕዘን ማንቃ እንጨት በየይነቱ	ጥቅል	፻፴፫	፬ሺ.፬፻፴፩	ከ፲ግ		
የባሕር ዛፍ ፍሬ የጉሎ ፍሬ	ጆንያ	፯፻ ፯	፪ሺ.፳፻፳፬		፪ሺ.፳፻፳፬	
ዘወትር እማይገኝ ዕቃ በየይነቱ	፡ ፡	፸፯	፻፸፱	፲፩	፫፻፲፩	፬
ብሬ	ቁጥር	ሺ.፳፻፺፱			፺፯ሺ.፱፻፸	
ፈረስ	፡ ፡	፸			፪ሺ.፳፻	
በቅሎ	፡ ፡	፫፻፳			፲፪ሺ.፳፻	
ከሚበላ ዘይት	ታኒክ	፩			፳	
የሸላ የፋሮ የፋዶት የአራጅ የዩንሹ ቆዳ	ቁጥር	፳፱			፴፰	፬
የምጥማጥ ቆዳ	፡ ፡	፲፳			፱	
የሽኮኮ የዱሮ ቆዳ	፡ ፡	፸፪			፹፬	
አደስ	ጆንያ	፩	፳	፲	፳፰	
ልብስና የቤት ዕቃ የኩቱ	ጥቅል	፫	፪፻			
					፰ሚ፯፻ ፬ሽ፳፻፲፩	፩

፲፱፻፲፯ ዓመተ ምሕረት ከውጭ አገር አዲስ አበባ ጉምሩክ ገቢ በየይነቱ መለያ ።

የዕቃው ስም ፡	ማመልከቻ	የቁጥሩ ብዛት	የዋጋው ድምር ብር	መ
አቡጀዲድ፡	ጣቃ	፩፻፹ሺ.፪፻፸ ፩	፫ሚሊዮን ፻፳፫ሺ.፱፻፺፱	
ኩታና ቆጮ ፡	ኩረጃ	፫ሺ.፱፻ ፬	፹፬ሺ. ፸፰	፬
ድርና ማግ ጥለት በየይነቱ ።	ወረቀት	፻፺፯ሺ.፯፻፺	፩ሚሊዮን ፻፳፫ሺ.፯፻፺፩	
መብሩቅ መርዱፍ ።	ጣቃ	፯ሺ.፪፻ ፳	፸፰ሺ.፫፻፳	፩
ዱማስ ዱርያ ምጥዋ ።	፡ ፡	፯ሺ. ፲	፸፯ሺ.፪፻፺፪	
ሻሽ ደበላ መሕሙዲ መልመሊ ።	፡ ፡	፻፲፯ሺ.፰፻፳ ፫	፫፻ ፯ሺ.፪፻፴፱	፱
ከኪ ኮት የኮት ጨርቅ በየይነቱ ።			፳፯ሺ.፱፻፺፯	፳
ሱቲ ግምጃ ጃዊ ፡			፴ ሺ.፳፻፺፫	፯
ባለዲ ቱቢት ቱክ የጌላስ ጨርቅ ፡			፺፱ሺ.፪፻፹	፩
ማተብ የመኪና ክር ፡			፴፪ሺ.፬፻፺፯	፲
መርፌ በየይነቱ ፡			፲ ሺ.፱፻፳፬	፫
የተሰራ ልብስ የገላ የጅ የግር ሹራብ በየይነቱ ፡			፺፪ሺ.፪፻ ፫	፬
ቁርጥራጭ ጨርቅ መጋረጃ የጠረጴዛ ልብስ ፎጣ ፡			፳፫ሺ.፻ ፳	፩
የብርድ ልብስ ፡	ኩረጃ	፪ሺ.፫፻፹ ፰	፲፱ ፺፬ሺ.፪፻ ፩	፬
ሐር ወርቀዘቦ ጥብጣብ አብድላክኒ ከፋይ ቡቅዳዲ ፡			፻፵፬ሺ. ፻፺፯	፲፰
ሥጋጃ ምንጣፍ ፍራሽ ፡			፺፬ሺ.፫፻፳፫	፯
ሸራ የዝናብ ልብስ ፡			፬ሺ.፬፻፹፱	፳
ጁኒያ ሱትሊ ገመድ ፡			፵፰ሺ.፯፻፺፱	፲፰
ሙሻማ ላስቲክ ፡			፰ሺ.፱፻፺ ፯	፪
ባርኔጣ ክፍያ ፡			፲፰ሺ.፫፻ ፲፱	፫
ጫማ ገምባሌ ፡			፲፩ሺ.፫፻፵	፬
ፊላዊ ባሕር ዓረብ የተሠራ ቆዳ ከነመድኃኒቱ ፡			፲፯ሺ.፯፻ ፺፯	፳
ጃንጥላ ፡			፳ሺ. ፸	፯
ሻሙና ፡			፺፬ሺ.፱፻፵፫	፲፪

የዕቃው ስም፤	ማመልከቻ	የቀረጥ ብዛት	የዋጋው ድምር ብር	መ
አሸቦ ጨው ፡	ጁንያ	፴፩ሺ. ፻፺	፹፰ሺ.፯፻ ፯	
ምግብ በያይነቱ ፡			፹፪ሺ.፪፻፹፯	
ሱካር ፡			፻ ፯ሺ.፫፻፺፬	፬
ቅመማ ቅመም በያይነቱ፡			፸፱ሽ፰፻፹፰	፭
ዕጣን ከርቤ ብርጉድ የሚጤስ ዓይነት ፡			፴፰ሺ.፪፻ ፯	፸
ትምባሆ ከነመሣሪያው ፡			፫ሺ.፬፻፴፪	፲
ክብሪት ፡			፪ሺ. ፡ ፡	
ሻማ ፡			፱ሽ፸፻፸፰	፬
ጋዝ ፡	ማጥን	፲ ሺ.፪፻ ፬ኑ	፹፪ሺ. ፻፲፰	
ቤንዚን ፡		ሺ.፸፻፷ ፰	፸፸ሺ. ፹፰	
የስፌት መኪና ፡			፹፯ሺ.፰፻፲፭	፬
ጋሪ አቶ መቢል ወፍጮ መኪና በያይነቱ ፡			፺፸ሺ.፯፻፶፭	፲፬
ሰዓት መነጽር ይህን የመሰለ ሁሉ ፡			ሺ. ፸፫	፪
ብርሌ ብርጭቆ መስተዋት ማብረጃ መለኪያ ፡			፰፱ሺ.፯፻፴፱	፲፪
ፋኖስ ኩራዝ ፡			፲፪ሺ. ፺፰	፲፬
ሣህን ኩባያ ማንቆርቆሮ ፍንጃል ጭልፋ ድስት ጀበና ብረትምጣድ			፻፸፭ሽ፰፻፰፯	፱
የቤት ዕቃ ፡			፸፬ሺ. ፺፰	፯
ወረቀት እርሳስ ቀለም የጽፈት መሣሪያ ፡			፺፰ሺ.፬፻ ፭	፯
መጋዝ መዋረቢያ መላጊያ ያናጢ መሣሪያ ፡			፲፭ሺ.፯፻፶፰	፯
ብረታብረት ፡			፻፴ ሺ.፯፻፶፪	፰
ነሐስ መዳብ አልሚኒዮም ፡			፴፯ሺ.፯፻፶፱	፸
ጠበንጃ ሽጉጥ ጥይት ባሩድ እርሳስ ቀለሀ ፡			፺፫ሺ.፯፻፸፪	፲፬
ዚንጐ ሲሚንቶ ቅጥራን ፡			፶፬ሺ.፯፻፺፯	፲
ዋርኒሽ የንጨት ቀለም በያይነቱ ፡			፲፱ሺ. ፻፷፫	፫
ቃሩራ በርሜል ባዶ ዕቃ በያይነቱ ፡			፸፪ሺ.፫፻፰፭	
አምበሬ ጭቃ ዘይት ሽቱ በያይነቱ ፡			፺፱ሺ.፰፻፷፭	፯
ዶቃ ጨሌ መቁጠሪያ አዝራር ጉትቻ የጌጥ መሣሪያ ፡			፶፯ሺ. ፻፹፱	
አረቄ መጠጥ በያይነቱ ፡	ደርዘን	፰ሺ. ፺፯ ፭	፻፲፯ሺ. ፻፹፱	፭
ብሽ ውሀ እስቢርቶ የሰዳ መድኃኒት ፡			፲ ሺ.፸፻፴፫	፲፫
መድኃኒት በያይነቱ ፡			፸፬ሺ.፪፻፴፱	፯
ስለ እርሳስና ስለማንተም ፡	ኪሎ	፯ሚ.፯፻፶፭ሽ፱፻፶፯		
ስለ እስታቲስቲክ ፡				
ስለ ኮምባዬር ፡				
የአበል ፡				
ኰቴ ፡				
ዘወትር የማይገኝ ዕቃ በያይነቱ ፡			፸፬ሺ.፯፻፲፯	፭
			፯ሚሊዮን ፱፻፲፱ሺ.፪፻፶፯	፲፭

፲፱፻፲፯ ዓ ም ከመስከረም ፩ ቀን እስከ ጳጉሜ ፭ ያገር ውስጥ ገበያ ዕቃ ቁጥርና የዋጋው ድምር ።

በአገር ውስጥ ምግብና ልብስ ሆኖ የቀረ ።

የዕቃው ስም ።	መለያ	ጭነትና ቁጥር		ፌረሲላ ኪሎ	ነጥር	የዋጋው ድምር ብር	መ
ቡን :	ጭነት	፫ሺ.፪፻፳፪	ኑስ	፳፩ሺ. ፹፭	፲፯ኑ	፻፺፯ሺ.፫፻፺፯	፲
የዘሆን ጥርስ :	ዋስላ	፺፬		፺፯	፲፯ኑ	፫ሺ.፻፺፬	፯
ዝባድ :	ጭነት			፭፻፴		ሺ. ፫	
ሰም :	: :	፭	ኑስ	፫፲		፺፩	፩
ከርቤ :	: :	፴፸	ኑስ	፻፷፸	፯	ሺ.፪፻፲፸	፭
ከረሪማ ዝንጅብል :	: :	፷፯		፪፻፴	፱ኑ	ሺ. ፷፫	፯
ቃጫ ገመድ :	: :	፺፯		፸፻፺	፭	ሺ.፻፷፫	፲፸
ስንዴ እህል በያይነቱ ።	ጆንያ	፯፻፴፱		ኪሎ ፫፸ሺ.፪፻፳፸		፪ሺ.፱፻፺፯	፲፩
አረቄ ሊብርቶ :	ታኒካ	፪ሺ.፬፻፷፫	ኑስ			፳፬ሺ.፯፻፹፭	
ማር :	ጭነት	፲ ሺ. ፺፬		፺ሺ.፯፻፺፬	፲ ፩	፪፻፷፬ሺ.፬፻፳፱	፯
ቅቤ።	: :	፪ሺ.፯፻፷፱		ሺ.፫፻፫፬	፩ ኑ	፷፯ሺ.፯፻፳፫	፲፪
ማቅ	ቁጥር	፳፬ሺ.፱፻፺				፹፬ሺ.፪፻፺፯	፫
ሻማ :	: :	፻፴፯ሺ.፫፻፳፫				፪፻፺፯ሺ.፯፻፴፯	
ብረታ ብረት	: :	፳፩ሺ.፫፻ ፯				፲ ሺ.፸፻	፭
የበቅሎና የፈረስ ዝናር ጠፍር በያይነቱ :	: :	፺ ሺ.፯፻፴፯				፺፫ሺ.፻፳፭	፲፩
ነትና ማስ :	: :	፪ሺ.፸፻፳፸		፸፻፫፬	፲፫	፪ሺ.፭፻ ፺፱	፭
ዋንጫ አውራሪስ ቀንድ :	: :	፸፻፺፫				፻፲፩	፫
ወረንጠ ነሐስ መዳብ ጽና መስቀል በያይነቱ፡	: :	፻፹፭				፻፺፸	፫
የፍየል ሌጦ	ከረጃ	፺፯				፬፻፷	
የበግ ቆዳ፡	: :	፱				፳፯	
ያውሬ ቆዳ	ቁጥር	፯				፫፯	፫
የጉሎ ፍሬ :	: :	፬	ኑስ	፱	፫ኑ	፱	፲
ዘይት ቅባኑግ :	ታኒካ	፲፭				፻ ፭	፲ ፪
ጠስኝ :				ኪሎ ፸		፩	፬
አሽቦ		፩		ኪሎ ፸		፸	፭
የበሬ ድላል ።	ቁጥር	፲፸ሺ.፬፻፳፯					
የበግና የፍየል ድላል :	: :	፺፬ሺ.፭፻፴፫					
የፈረስ ድላል :	: :	፸፻፺፪					
የበቅሎ ድላል :	: :	ሺ. ፻፺					
ያህያ ድላል :	: :	፬ሺ. ፻፳፱					
ከቅመማ ቅመም						፪ሺ.፸፻፺፯	፯
ከዳራገር ገቢ ኮቴ :	ጭነት	፴፬ሺ.፯፻፺፩		በሬ ፸ሺ. ፹			
ገር አገር ከሚሄድ ኮቴ :	: :	፺፸ሺ.፬፻፹፯					
የዲክለራሲዮን ዋጋ :	: :	፳፩ሺ.፯፻፳፱					
ከፈረስና ከበቅሎ ወደ ዲሬደዋ ከሚሄድ ።	: :	፸				፻፳	
						፱፻፺፬ሺ.፫፻፷	፪

ስለ ንግድ ማስፋት ።

በንግድ በሚገኘው ገንዘብ የሚገኘውን የመንግሥት ጥቅም ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን የአዲስ አበባን ጉምሩክ ሥራ አይተው ዘንድሮ የገባው ገንዘብ ካለፉት ዓመታት ከገባው ገንዘብ በጣም ከፍ ያለ ስለሆነ አስተካክለው ተናግረውታል ።

የንግድ ሚንስትሩ ነጋድራስ ዘለቀና ዲረክተሩ አቶ ገብረ እግዚአብሔር በጉምሩክ ከሚሠሩ ሠራተኞች ጋራ በሥራቸው ለተመሰገኑ ብርሃንና ሰላም ደስታውን ይገልጣል ።

እውነትም በዚህ ዘመን ንግድ አንዱ መንግሥት ሌላውን መንግሥት ድል ሊያደርግበት የሚችል አንድ ዋና መሣሪያ ነው

በአዲስ አበባ በኩል የሚወጣው የኢትዮጵያ መንግሥት ንግድ ደኅና ሠራተኞች ስለተገኙበት ብዙ ገቢ ተገኝበት በሌላ በኩል የሚወጣና የሚገባ የንግድ ዕቃ እንደዚሁ በየማዕዘኑ የተገባ የጉምሩክ ሥራ ቢቆምበት የኢትዮጵያ መንግሥት ገቢው በጣም በበዛ ነበር ። በትግሬ በኩል በበጌምድር በኩል በየዳርቻው ወደ ውጭ አገር የሚሄደው ያገራችን ዕቃ ከልክ ያለፈ ነው ።

ሰንጋና እኅል ባዲስ አበባ በኩል እንኳ ወደ ውጭ አገር ባይሄድ የመንግሥታችን ጎረቤቶች የገበያቸው ሀብት ከመንግሥታችን ውስጥ በሚሄደው እህልና ሰንጋ ነው ። እየገዙ ይመገባሉ እየሸጡ ያተርፋሉ በትግሬ በኩል እንደ ተወራ ነጋዴ ይመጣል በማይባልበት በክረምት ውሥጥ ነጋዴ ይገባ ነበር ይባላል ።

ለምሳሌ በሐምሌ ወር ብቻ ወደ አስመራ የገባ በየይነቱ የንግድ ዕቃ አስር ሺ ተ፰፻ ጭነት ያህላል የእየአንዳንዱ ጭነት ክብደቱም ፫፻ ኪሎ ያህል ነው ። በትግሬም በይሉባቡርም በሌላ ውም ይኸን በመሰለ ስለ ቀረጡ የተተከከለ ደምብ ቢያወጣለት የኢትዮጵያ መንግሥት ብዙ ትርፍ ያገኛል።

እንግዲህ ያዲስ አበባ ጉምሩክ ብቻ አይበቃም በየዳር አገሩ ባለ በር ሁሉ ትክክል የጉምሩክ ሥራ ማቆም ያስፈልገናል እንዲህ ብናደርግ ገቢ ገንዘብ ይበዛና መንግሥታችን የፈለገውን ሥራ ለማቆም ይቻለዋል ።

የንግድ ወሬ ፤

ነጋዴዎቹ የበሬና የበግ የፍየልም ቄዳ ሲሸጡ ሚዛኑ እንዲከብድላቸው ብለው የቄየ እንደሆን በቶሎ የሚያበላሸው ነገር ይጨምሩበታል ብሎ የቄዳ አሻሻጥ በሚዛን መሆኑ ቀርቶ በቄዳ ቍጥር እንዲሆን የአስመራ አገረ ገዢ ቈርጧል ።

በያውራጃው ያሉ የኢትዮጵያ አገረ ገዢዎችም ያገራቸውን ነጋዴ ጥቅም እንዲያስቡ ለነጋደው ጉዳት የሚሆን ነገርም ለማራቅ እንዲጣጣሩ ተስፋ እናደርጋለን ።

የፈላስፎች ቃል ።

ሐዮ ጉድ የዋህና አሸናፊ ልጅ ምስጉን ነው ልጅን የመሰለ ሰውም ምስጉን ነው ። ፊቲአበን

ንግግር ጊዜ ነው ዝምታ ግን ዘላለም ነው ። ማርቲሊንክ

አሳብ አንድ ዓለም ነው ሥራ ግን ሌላ ዓለም ነው ያሰቡትን ለመፈጸም አለመቻል ምንኛ ችግር ነው እውነት ማሰብ በርግጥ ማድረግ ነበር ነገር ግን እውነት ማለት ምን ያደርጋል ሰዎች እውነትን መሸከም ላለመቻል እንደከብት ከሆኑ ሰዎቹን ለዚህ ማስገደድ ይገባልን ። ሮሜን ሮላን

የሀብት ምሥጢር በጃችን ያለው ደስታ ነው ራሱን የሚረዳ ሰው ከአማልክትና ከሰው የታደለ ነው ።

ኤሜርሰን ።

በሕመማችን ራሳችንን ብቻ እንከሰስ ። ላሮሸፎኮልድ

ብዙ ሠርቶ ትንሽ ለማምረት መጣር ነው የተጠነቀቁበት እንደሆነ በኑሮ ሁሉ ምርት ይገኛል ገና ለሥራ የሚቀር ምንጭ አይገኝም ። ሜን ደ ቤራ።

አለሥራ የዋሉበት ቀን እንቅልፍ እንደተጫነበት ሌሊት ያደክማል ። ፐቲ ሴን

ከጠጠት በቀር ከንቱ የሆነ ነገር የለም ። ማርክ ኦሬላ

ለዛሬ መሥራት ረብ ያለው ሥራ የመሥራት ብልሃት ነው እጅግ አርቆ ማየት ግን ዘወትር ከንቱ የሆነና አደገኛም ነው ። ሚሼሌ

ማስታወቂያ ።

በርሻና በመስሪያ ሚኒስትር ሥራ ውስጥ መንግሥት ያወጣውን ደምብና ሕግ ሳልተላለፍ ደህ ሳልበድል ፤ የመንግሥቱን ገንዘብ በጥንቃቄ ሠርቼ ቀድሞም ከሚሠራው ሠራተኛ ገቢ ገንዘብ አብልጬ አገባለሁ የሚል ሰው እርሻና እመስሪ ምኒስቴር መጻፊያ ቤት ፤ ሁል ጊዜ ከጧቱ ከ፫ ሰዓት እስከ ፬ ሰዓት ድረስ፤እየመጣ ቢነጋገር በደስታ እንቀበለዋለን ደመወዙም እንደ ሥራው ገቢ እየታየ ይቈረጥለታል ጥቅምት ፲፩ ቀን ፲፱፻፲፰ ዓመተ ምሕረት። መኰንን ሀብተ ወልድ

ማስታወቂያ

ለራሶችና ለደጃዝማቾች ለሴት ወይዘሮች የሚገባ በየይነቱ ጥሩ ካባ ከኤሮፓ መጥቶልኛል ቤቱም (ባንክ ኦፍ አቢሲንያ) ከእንግሊዞች ባንክ አጠገብ ነውና ይህን ካባ መግዛት ለሚፈልጉ ሰዎች መጥተው እንዲገዙ አስታውቃለሁ። ኢያሱ ዳንኤል

አ ፔ ማርሲያኖ

በኢትዮጵያና በፈረንሳይ የቅኝ አገር ሶማሊ በተለየ ፊያት አውቶሞቢልና ትራክተር አስመጭና እንደራሴ።



A.P. MARCIANO

Concessionnaire Exclusif pour l'Ethiopie
et la cote française des somalis
des automobiles et tracteurs Fiat.

በልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ

መጀመሪያ ዓመት ፤ ቍጥር ፵፮ ።
1 re ANNÉE № 46

ሐሙስ ኅዳር ፫ ቀን ፤ ፲፱፻፲፰ ዓ ም።
JEUDI 12 NOVEMBRE 1925

ብርሃንና ሰላም

LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት
Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraissant tous les jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

የጋዜጣው ዲሬክተር ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።
Gabré Christo Taklé Haymanot
Dirécteur

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ፤ በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ከ፵፭ ቍጥር የቀረ ቃል ።

ከወህኒ ቤትና ከዙብጥያ ስለሚነሣ በሽታ ።

ያ ደግሞ ታሞ የከረመ እስረኛ በገሙ ሁኑኦልና ስለ ከባድ ኃጢአቱ ተፈርዶበት እንዲቀጣ ወይም መንግሥት በቸርነቱ እንዲምረው ወደችሎት እንዲቀርብ ያወጡታል ። እችሎቱም በቀረበ ጊዜ ኃጢአቱ የጠነከረ ነውና ወደላይ ወደ ወንበሮቹ መቀመጫ ተጠግቶ እንዲመረመር በጣም ያቀርቡታል በዚያን ጊዜ በሱ ልብስ ያሉ በሽታ ተሸካሚዎች የሆኑ ትሎች የረቀቁ ነፍሳቶች ከአየሩ (ከነፋሱ) ጋራ እየተደባለቁ ወደ ወንበሮቹ ይሄዳሉ ይልቁንም ኃጢአቱ እጅግ የከበደና የጠነከረ እንደሆነ ልዑል ነገሩን እንዲሰሙት ተብሎ ባልጋ ወራሽ ችሎት ይቀርብና እንደዚኸው በልዑል መቀመጫ ተጠግቶ ይመረመራል

እንግዲህ እነኚህ በሽታ ተሸካሚ የሆኑ ነፍሳቶች ንጉሥ አልጋ ወራሽ ይፈሩ ይመስላችሁ ይሆንን ። በርግጥ እነሱ ያለመድኃኒት በተቀር ሌላ የሚፈሩት ነገር የላቸውም ጌታውንም ሎሌውንም ንጉሡንም ሕዝቡንም ሁሉንም እኩል ደፍረው ያበላሻሉና በዚህ ነገር የወህኒ ቤት ሹማምንቶች አጥብቀው እንዲተጉበትና እንዲያስቡበት ያስፈልግ ይመስለኛል ።

ለሃገራችን የከብት ሃኪም ማስፈለጉን የሚያስታውስ ።

በሃገራችን የሚወለዱ ሕፃናቶች መቅሰፍት የሚበዛባቸው ዋናው በሽታ ከወተት የሚመጣባቸው ይመስለኛል ። በሽታ ያላቸውን ላሞች ለይቶ ለማወቅ እጅግ ያስቸግራል በሽታ አድሮባት እያለ እስከ ብዙ ዓመት ድረስ ጠጕሯ እየለሰለሰ መልኳ እያማረ ስትታለብ ትኖራለች መቼም በሃገራችን ያሉ ላሞች ሁሉ በሃኪም እየተመረመሩ አይደለምና የሚኖሩት በሽተኞቹ ላሞች ሁሉ እየታለቡ የበሽተኛ ወተታቸውን ሕጻናቶች እየተመገቡ የታመሙበት ምክንያት ሳይታወቅ እየታመሙ በሕጻንነታቸው ወራት እየተሸነፉ ብዙዎቹ ልጆች ያልቃሉ ። አሳስት እንደሆን ነው እንጂ ለዚህ የሚያስረዳ ምሳሌ ለመስጠት እችል ይመስለኛል ።

በሃገራችን አንድ አንድ ሰዎች የሚታለሉበት አንድ በሽታ የሾተላይ የሚሉት አለ በዚኸውም ምክንያት የሚወዷልቸው ልጆች ሁሉ ይሞቱበት እየመሰለው ስለዚህ ፈውስ ይሆናል የተባለ ያለማወቅ ነገር አለበት ወንድ ልጅ በተወለደ ጊዜ በወንድነቱ መጠራቱ ቀርቶ በሴትነት የተጠራ እንደሆን ያድጋል ይባላል ። ሴትም ስትወለድ እንደዚኸው ሴትነቷ ቀርቶ በወንድነት ትጠራለች ።

ጊዜ እያጋጠመ የእግዚአብሔር ፈቃድ እየሆነ እነዚህ እንደዚህ እየተጠሩ ያደጉ ልጆች አንድ አንድ ይገኛሉ ። ይህ ልጆች ሲወለዱ የሚፈጀው ባላጋራ ግን ሾተላይ የሚባለው ነገር አይመስለኝም ። ግን ለኔ የሚመስለኝን አስከትዬ ልጻፍ ።

አንድ ሰው አንድ ላም ትኖረዋለች ያችውም ላም ሳይታወቅባት በሽታ ይኖርባታል ይህችውም ላም ትወልዳለች የተወለደችቱም ጥጃ ከናቷ ማህጸን ይህ የሚጋባ በሽታ አግኝቷት ከደሟ ተቀላቅሎ አለ ። እነዚህ ላሞች ግን ደህና ይመስላሉ በዚያውም ጊዜ የዚህ የሰው ሚስት ልጅ ትወልዳለች ይኸውም ልጅ በተወለደ ጊዜ የዚያችን የላም ወተት ይመገብና በሽታ ያድርበታል ያደረበት በሽታ ሳይታወቅ ይህ ሕፃን ይሞታል ያች ላም ግን መርበት ትጨምራለች የቧም ዘሮች በረት ይሞሉ ይሆናል

ግን እነኚህ ከአንድ እናት የመጡ ላሞች ሁሉ በሁሉም ደም ውስጥ ከናታቸው የመጣ ደም ሲወርድ ሲዋረድ እየደረሰባቸው ሁሉም ባለጤናዎች አይደሉም ይህንም ምልክት ሲያሳዩ ከጥቂት ዘመን በኋላ በገሚሶቹ ሰው እስቲያውቅላቸው እየታመሙ እየሳሉ እያከኩ ተበላሽተው ይሞታሉ ። ያች ልጅ የሞተባት ሴቲዮ ግን ወላድ ነችና ደግሞ ሌላ ልጅ ትወልዳለች ያም

የተወለደው እንደዚያው እንደሚቹ ወንድሙ ታሞ ይሞታል እንደዚሁም አራት አምስት ልጅ ይሞትባትና ተቀብራለች ከዚህ በኋላ የከሊትን ልጆች የሚፈጅባት የሾተላይ ነው ይባላል ። ይህ የሾተላይ የሚባል ነገሩ ምሥጢሩ የታወቀ ነገር በሆነ አልነቀፈውም ነበር ግን ምሥጢሩ ሳይታወቅ ስለቀረ ሴቷን ወንድ ወንዱን ሴት እያስመሰሉ በመጥራታቸው ነገሩ የስህተት መሆኑ ገባኝ እግዚአብሔር እንዲህ በግርግር የሚታለል አምላክ አይደለምና ይህንን የመሰለውን ነገር ከማመን መመርመር ይሻለኛል አሁን እዚህ ሁኜ እንደሚታየኝ ምሥጢሩ እንደዚሁ ከራስጌ እንዳስረዳሁት ይመስለኛል ። እንግዲህ ወደዠመርኩት ነገር ወደ ወተት በሽታ ልመለስ የሾተላይን ልተውና ይኸውም ይሆናል አ ልሁ አልሁ እንጂ ነው አላልሁምና አልነቀፍ ።

አስቀድሜ መታመማቸው ሳይታወቅ እየታለቡ በሽታ ከሚገኝባቸው ላሞች ጀመርኩ እንጂ እንዲያውስ ብዙዎቹ ላም የሚያረቡ ሰዎች እየታወቃቸው የበሽተኛዋን ላም ወተት እያሳለቡ ወደገበያ እየላኩ እየሸጡ ብዙ ሰው የሚያስፈጁ ጨካኞች መች ይጠፉና ። ከብዙዎቹ ላሞች መካከል ያንደኛዋ በሽታ ይጠነክርባትና እየሳለች እየከሳች እየኮሰሰች ስትሄድ ባለላም ሳል መታመሟን ይረዳል ከዚህ በኋላ የሷን ወተት ለመጠጣት አይፈቅድም ግን እሷን የያዘ ሳል በቀሩት ላሞች የሚጋባ መሆኑን አያስብምና ዝም ብሎ በላሞች መካከል ያኖራታል ። ወተትዋም እየታለበ ወደገበያ እየሄደ ይሸጣል እንደ የልጅ እናት ወተት ለልጇ አገኘሁለት እየመሰላት እየገዛች ለልጅዋ ታጠጣዋለች ። ልጅዋም ከትቂት ወራት በኋላ ይታመምና ጤና አጥቶ ከስቶ መንምኖ እናቱን ብዙ ወራት ካስጨነቀ በኋላ ይሞትባታል ።

የከብት ሐኪም ለሃገራችን ያስፈልገዋል ብል መጀመሪያ የሰው ሃኪም አልተገኘም የከብት ሃኪም ይላል የሚለኝ ሰው አይጠፋም እውነት ነው የሰው ሃኪሞች ለሃገራችን በብዙ እንዲያስፈልገን የታወቀ ነው ቢቸግረው ነው እንጂ መንግሥታችንም ይኸነን ፈጽሞ ተረድቶታል ። ግን የከብት ሃኪምም በጣም ያስፈልገናል ። አገራችን የላም አገር ነው ሺህ ሺህ የማያረቡ ውረኞች አሉና ለነዚያ ከብቶች ሁሉ የሚመረምራቸው ሃኪም ቢያገኙ በሽታ ያለበትን ሃኪም እየመረመረ ከከብቱ መካከል እያስወጣ እያሳረደ ደህናው ከብት ብቻ እየተረባ ቢኖር የሃገራችን ሕጻናቶች እንደዚህ በሕጻንነታቸው ወራት ከሚያገኛቸው መከራ እያመለጡ እያደጉ ለአባትና እናቶቻቸው ደስታ ይሆናሉ ለመንግሥትም የሚያገለግል ብዙ ጅግና እየወጣ ያድግ ይሆናል ።

እንግዲያውስ አሁን በየሃገሩ ከወጣነው ልጆች በምስር በውሮፓ በሜሪካ ታለነው ሁሉ ገሚሳችን የሰው ሐኪም ገሚሳችን የከብት ሐኪም ገሚሳችን ያፈር ሐኪም ገሚሳችን ማህንዲስ ገሚሳችን የፖለቲክ እውቀት ገሚሳችን የኤሌትሪክ መሃንድስ ገሚሳችን ያስተማሪነት ይኸነን የመሳሰለ ሥራ ተምረን ለሀገራችን ለመድረስ እንብቃ ። እኛም እስትንደርስ ልዑላችን ባስከፈቱልን ተማሪቤት እየተማሩ የሚወጡትን ልጆች ባይናችን እያየን እግዚአብሔርን ለማመስገን እንበቃይሆናል ። ክቡር ፊታውራሪ ዴሬሳም በመልካም ሃሳባቸው ያስጀመሩት የተማሪ ቤት ሐሳብ ብተከናወነ ጊዜ ከዚያ ከተማሪ ቤት የሚወጡት ልጆች ሁሉ ልባቸው በሃገራችው ፍቅር የተቃጠለ ሁኖ እንደዚህ የቸገራትን እየተመለከቱ እየተማሩ ለኢትዮጵያ ጥቃት ጠባቂዎች እዲሆኑልን እንመኝ ። ግን እንደዚህ የሃገራችን ልጆች ተምረው ሕዝባችንን በሚማሩት እውቀት ከሚከለክል መቅሰፍትና አደጋ ሁሉ እስቲጠብቁትና ለመጠበቅ እስቲደርሱ ድረስ አገሩንና የሃገሩን ሕብዝና መንግሥት የሚወድ ላም አርቢ ሁሉ ከላሞቹ መካከል አንደኛዋ ሳል ወይም ሌላ የሚጋባ በሽታ መታመሟን ባወቀ ጊዜ በቶሎ ብሎ ያችን ቃማ የተገኘች ላም ገድሎ ከከብቶቹ መካከል እንዲያጠፉት አመለክተዋለሁ ይኸንን ማድረግ ትቶ የበሽተኛ ላም ወተት እያለበ በገበያ የሚሸጥ ሰው ሰው የሚፈጅ መርዝ ወተት ነው እያለ የመሸጥ ያህል ነው ጥፋቱ እሱውም የብዙ ሰው ነፍስ ገዳይ ሊባል ይገባዋል እንዲህ ያለ ሰው በተያዘ ጊዜ ተፈርዶበት በነፍስ ዋጋ ገንዘብ ከፍሎ በገንዘቡ ሊቀጣ ይገባዋል ።

ላንባቢዎች ይህ ነገር ቀላል ይመስላቸዋል ይሆናል ግን ባይመረመር ነው እንጂ ከንደዚህ ያለ በሽታ እያገኛቸው የሚያልቁ ሰዎች ባመት ሰባት ስምንት ሺህ ሳይሆኑ አይቀሩም በአሜሪካ ማህበር መንግሥት ውስጥ ብቻ በርግጥ ተቆጥሮ የታሰበው ከንደዚህ ያለ በሽታ በንደዚህ ሳል በሚታመሙ ላሞች ምክንያት ከሚገኘው በሽታ በደዌ የሚኖርው ሕዝብ ሁለት ሚሊዮን ሕዝብ ነው ። እስቲ ተመልከቱት በአሜሪካ ሃኪም በሞላበት አገር እንዲህ ሲከፋ በኢትዮጵያ ሃኪም በሌለበት አገር እንዴት ይሆን ይመስላችኋል በዚኸው በሽታ እየታመመ የሚሞተው ሰው ባመት አንድ መቶ ሺህ ነው እንደዚህ ያለው በሽታ ያሰጋ አይመስላችሁምን ።

የዛሬ ሁለት ዓመት በአንደኛው ወረዳ ሐረርጌን በሚያሀለው አገር ብቻ (፭፻፴፱ ሺህ ፰፻፲፯) ዓምስት መቶ ሰላሰ ዘጠኝ ሺህ ስምንት መቶ አስራ ሰባት የቀንድ ከብት በከብት ሃኪሞች ተመረመረ ከዚኸውም ከተመረመረው ከሞላው የቀንድ ከብት አስራ ዘጠኝ ሺህ ስምንት መቶ አምሳ (፲፱ ሺህ ፰፻፶) የቀንድ ከብት የሚጋባ በሽታ ይዞአቸው ተገኙ (ሳል በሽታ) ይኸነንም ሁሉ ከብት ወዲያው ተከብቱ መካከል አስወጥተው እንዲታረድ አደረጉት ።

አሁን በዛሬው ዘመናችን የገዛ ልጆቻችን ተምረው ክልደረሱልን መቼም ለማድረግ የምንችለው ነገር የለም ግን አሁን ለጊዜው የማመለክትህ ይህንን ነው ወዳጄ ለልጆችህ የምታልባቸውን ላሞች ቢቻልህ በየጊዜው ሃኪም ይመርምራቸው ባይቻልህ ግን አንተው እራስህ በጥንቃቄ ተመልከታቸው የበሽታ ምልክት ባንደኛይቱ ላምህ ላይ ያየህባት ለት ወተትዋ እንዳይጠጣ ከልክል ወደ ገባያም ልጆች ወስደው እንዳይሸጡ ክልክል አድርግ በሽተዋ እርግጥ መሆኑን በተረዳህ ጊዜ ግን ላሚቱን ፈጽመህ እንድታጠፉት እረዳት ። እንዲህ ያደረግህ እንደሆን ልጆችህን ባንድ መንገድ መጠበቅህ ነው ። ልጅ እወዳለሁ እያሉ ቢያወሩት ፍሬ የለውም ልጅም በሞተ ጊዜ ሃዘን ቢያበዙ ፍሬ የለውም ፍሬ ያለው ነገር የልጁን ህይወት የሚነሳውን ነገር ሁሉ በህይወት እንዲኖር ተጠንቅቆ ማሳደግ ብቻ ነው ።

መልአኩ በያን ። (አሜሪካ)

ከዚህ የተረፈው ቃል በሚከተለው ቁጥር ይታተማል ።

ከፖርቱጊስ ለልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ስለ ሽልማታቸው በቴልግራም የመጣ የደስታ ቃል ።

ልዑል ራስ ተፈሪ

የፖርቱጊዝ ሬፑብሊክ መንግሥት አመልክቶኝ ለልዑልነትዎ የቱርና የኤፔ (la grand croix de l' ordre de la tour et epée) የታላቅ መስቀል ማዕርግ እሸልመዎታለሁ ። ስለዚሁም በፖርቱጊ ሕዝብ ስም ለልዑልነተዎና ለኢትዮጵያም መልካም ሕዝብዎ ተድላና ልማት እንዲሆን እየተመኘሁ እንኳን ደስ ያልዎ ብዬ ምስጋናዬን አቀርብልዎታለሁ ።
የፖርቱጌዝ ሬፑብሊክ ፕሬዚዳን ።

ቴክሴራ ጎሜስ

LISBONNE

Sous proposition du Gouvernement de la Republique je viens de conferer à votre Altesse Imperiale la grand croix de l'ordre de la Tour et epée. Je felicite votre Altesse très sincerement avec les voeux que au nom du peupile portugais je formule pour le bonheur du noble peuple Ethiopien

Teixera gomes
Président République Portugais

ስለ ቴሌግራሙ ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን የመለሱት ቃል ።

ይድረስ ክክቡር ሙሴ ቴክሴራ ጎሜስ የፖርቱጊዝ ሬፑብሊክ ፕሬዚዳን ።

ሊሲቦን

ክቡር ፕሬዚዳን ሆይ በሬፑብሊክ መንግሥት ስም ሆነው ስለ ግራንድ ክሮዋ ደ ለ ኦርድር ደ ላ ቱር ኤፔ ኒሽን ሽልማት የላኩልኝ ቴሌግራም ደረሰልኝ ። ይህንኑም በደስታ መቀበሌን ደግሞ የኢትዮጵያና የፖርቱጊዝ መንግሥት ወዳጅነት ከብዙ ዘመናት በፊት ተመሥርቶ የቆየ መሆኑ በኢትዮጵያ ታሪክ የታወቀ ነውና ይህ ያሁኑ አሳብ ያንኑ ተመሥርቶ የቆየውን ወዳጅነት የሚያድስና የሚያጸና መሆኑን ስለተረዳሁት ለዚሁ ምስጋናዬን አቀርባለሁ ። ወደ ፊትም ኢትዮጵያና ፖርቱጊዝ በፍቅር ተሳሥረው ወዳጅነታቸው እየጸና ይኖራል ብዬ ተሥፋ አደርጋለሁ ።

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና እንደራሴ ተፈሪ መኰንን ጥቅምት ፲፰ ቀን ፲፱፻፲፰ ዓመት ።

SON EXCELLENCE
Monsieur TEKSERA GOMES
PRESIDENT DE LA REPUBLIQUE PORTUGAISE
LISBONNE.

Le télégramme que vous m'avez adressé au nom du Gouvernement de la Republique au sujet de la décoration de GRAND CROIX de l'ordre de la TOUR d'EPÈE m'est parvenu. jel'ai reçu avec joie.

L'amitié qui existe depuis trés longtemps entre l'ETHIOPIE et le PORTUGAL est attestée par l'histoire de l'ETHIOPIE.

Je suis convaincu que cette nouvelle manifestation des sentiments qui vous animent renouvellera et renforcera l'amitié qui nous unit, Je vous prie à cette ocasion de vouloir bien agréer mes remerciements,

Je fais des voeux pour que les liens d'affèction qui unissent l'ETHIOPIE et le PORTUGAL subsistent éternellement'

TEFERI MEKONNEN, HERITIER DU TRONE
ET REGENT DE L'EMPIRE D'ETHIOPIE.
Addis-Abeba, 18 Tekemt 1918, An de Grâce.
(28, Octobre 1925)

ይድረስ ካቶ ገብረ ክርስቶስ ፤ የሚከተለውን ቃል በብርሃንና ሰላም እንዲያገቡልኝ እለምንዎታለሁ ።

ስለ መሐልቅ ምንዛሬ።

መንግሥታችን ብዙ መሐልቅ አምጥቶ ሕዝቡ ብር እየሰጠ ባንድ ብር አሥራ ስድስት መሐልቅ እንዲገዛ በማድረጉ እጅግ ደስ ብሎኝ እኔም የመሐልቅ ችግር ነበረብኝና በጥቅምት ፳፰ ቀን አንድ ብር ወደመሐልቅ ለመለወጥ መሐልቁ ወደሚለወጥበት ቦታ ሄድሁ። ወደስፍራውም በደረስኩ ጊዜ ከሰው ብዛት የተነሳ ብር እየተቀበለ መሐልቅ የሚሰጠውን ሰውዬ እንኳ ማየቱ ቸገረኝ ። እቀርባለሁ ብዬ ብሞክርም ግፊያውና የሰዉ ብዛት ተበራትቶ የማይወጣ መሆኑን አይቼ መረገጡንና መጨቄኑን ቀምሼ አቅቶኝ ሳላገኝ ተመለስኩ ። መሐልቅ የሚፈልጉ ሰዎችም ብራቸውን ለመስጠት በጨርቅ እየቋጠሩ በዘንግ ጫፍ እያሠሩ መሐልቅ ለያዘው ሰው ያሳዩ ነበር ። አንዳንዱም በልብስ እየጠቀለሉ ይጥሉለታል።ለኔ ለኔ ብሎ የሚጮኸውም ሰው ጆሮ ያደነቁራል ።

ሥራ ፈት ባይሆን ባለ ሥራ ሰው ግን አንድ ብር እለውጣለሁ በማለት የቀን ሥራውን ዋጋ ሊያጠፋ የሚወድ ይገኝ አይመስለኝም ፤ ሥራውን እንኳ ቢፈታም የሚያገኝ መስሎ አልታየኝም እኔም ደግሞ በሥራዬ ብዙ ገንዘብ አገኛለሁ። የሥራዬ ዋጋም ለጌታዬ ብዙ ትርፍ ያለው ነው ። ስለዚህ አንድ ብር ወደ መሐልቅ እለውጣለሁ ስል ብዙ ገንዘብ የሚገኝበት የሥራዬን ጊዜ አላጠፋም ብዬ ፤ ሥራዬን ፈትቼ ብቆይም መሐልቁን ለማግኘት እንዳልተቻለኝ ተረድቼ ተስፋ ቈርጬ በቶሎ ወደሥራዬ ተመለስኩ ።

ሰው ሁሉ ይህን ያህል መሐልቅን መውደዱ ብርንም መናቁ ምክንያቱ ምንድር ነው ? በሥርዓትስ አለመገኘቱ ምክንያቱ ምን ይሆን ? መሐልቁ ከመንግሥት እየወጣ በገበያ የመሐልቅ ምላሽ ጨርሶ መጥፋቱስ በምን ምክንያት ነው ? መሐልቅ ወጥቶ ለሕዝብ መገበያያ ካልሆነ በገባያ ካልተገኘ ምን ተጠቀምን ? መንግሥታችንስ ትርፉ ምን ይሆን ? ።

መቼም ያንድ ብር መሐልቅ ካስራ ስድስት በላይ አይወጣም ቢሆን ይወርዳል እንጂ ስለዚህ ገዠቼ ባስቀምጠው ያተርፈኛል ለዚያም ዋጋውን አያጐድልብኝም ብሎ እየገዛ የሚያብቀው ሰው ይኖር ይሆን ? ስለመሐልቁ ምንዛሬ የሚያጕረመርሙ ሰዎች ብዙ ናቸውና ለዚህ ጥያቄ ሁሉ ምላሽ ሊሰጡ የሚገባቸው ክቡር የገንዘብ ምኒስትሩ ናቸው ። ክቡር የገንዘብ ምኒስትሩም ስለዚህ ነገር የተሻለ መንገድ እንዲያስቡና ለሕዝቡም የሚበጀውን ነገር እንዲያደርጉ ሙሉ ተስፋ አለን ። (እ እ።)

በይግባኝ ችሎት የተሰጠ

ፍርድ

እኛ የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና እንደራሴ ተፈሪ መኰንን ።

በርስት ቦታ ነገር መዳም ቴዎፊሉ ከሳሽ ሁና ማዘጋጃ ቤት ተከሳሽ ሁኖ በልዩ በቆመው የፍርድ ቤት ተነጋግረው በ፯ ነሐሴ ፲፱፻፲፯ ዓመተ ምሕረት የተፈረደውን ፍርድ መዳም ቴዎፊሉ አልቀበልምና ይግባኝ ብላ በይግባኙ ደምብ በእኛ ችሎት ቀርበው ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈውን ቃል ተነጋግረዋል ።

መጀመሪያ መዳም ቴዎፊሉ በጳጉሜ ፬ በ፲፰፻፺፱ ዓ ም በ፵፭ ቍጥር የተጻፈ ፱ሺ ፳፯ ሜትር ካሬ ቦታ ካርታው በቀድሞው የርስት ቦታ ሹም ማኅተም የታተመ ምስክር በእጄ ይገኛል ። እኔ በአዲስ አበባ በሌለሁበት ጊዜ የቦታዬ ጠባቂ ሙሴ ዲሚትሪ ፓፓዶፑሎስ በሐሰት የሚስቴ የመዳም እሌኒ ቦታ ነው ብሎ ፣ አስቀድሞ እኔ በዚህ ቦታ የርስት ካርታ መቀበሌን ደብቆ ሹሙን አታሎ በሐምሌ ፫ ቀን ፲፱፻፫ ዓ ም በ፫፻፲፭ ቍጥር የተጻፈ በሚስቱ ስም ሌላ ካርታ ተቀብሎበት ተገኘ ።

ሁለተኛ ከብዙ ዘመን በኋላ የኔን ርስት በሚስቱ ስም አዛውሮ ሌላ ካርታ መቀበሉን ብሰማ ለቆንስላችን ለሙሴ ሐጅዮአኑ ነገሬን አመለከትሁ ። ቆንስላችንም አስቀድሞ የተቀበልሁትን የርስት ወረቀቴን አይቶ ርስትነቱ የሚገባው ለመዳም ቴዎፊሉ ነውና ለመዳም እሌኒ ምንም ርስት የላትም ብሎ ፈረደ ወዲያውም በ፫፻፲፭ ቍጥር የተጻፈው የመዳም እሌኒ ካርታ የማይረባ ነውና ካርታው ለሌላ ሰው ተዛውሮ እንዳይሸጥ ማዘጋጃ ቤት ፈቃድ እንዳይሰጥብኝ ብሎ በጥር ፳፩ ቀን ፲፱፻፲፪ ዓ ም ለማዘጋጃ ቤት ሹም ለከንቲባ ማተቤ በጽሕፈት አስታወቀልኝ ።

ሶስተኛ ከዚህም በኋላ ባለርስት መሆኔን የሚመሰክርልኝን በቀድሞው የርስት ቦታ ሹም በቢትወደድ ኃይለ ጊዮርጊስ ማኅተም የታተመውን የፊተኛውን ካርታ ለአዲሱ ማዘጋጃ ቤት ሹም አሳይቼ በታሕሣሥ ፩ ቀን ፲፱፻፲፯ ዓ ም እንደ ደንቡ በ፱፻፴፬ ቍጥር የታደሰ አዲስ ካርታ ተቀበልሁ ።

አራተኛ ይህም ቦታ የኔ ርስት መሆኑ በፊተኛውና በኋለኛው ካርታ ተደላድሎ ከተመሰከረልኝ በኋላ ስለ ችግሬ ቦታዬን ለዶክቶር ላምቢ ሸጥሁለት ። በኋላ ግን ገንዘቤን ጨርሼ ሳልቀበል ባንክ አፍ አቢሲኒያ ይህን ቦታ በዕዳ በመያዝ ይገዛዋልሁና ገንዘቡ ለመዳም ቴዎፊሉ እንዳይሰጥብኝ ብሎ አሲያዘብኝ ። ይህንንም ለቆንስሌ ለዶክቶር ዜርቦስ ባመለከት መዳም ቴዎፊሉ በ፵፭ ቍጥር በተቀበለችው በርስት ወረቀት ላይ ሙሴ ዲሚትሪ ፓፓዶፑሎስ የርስት ቦታዋ ሹም አታሎ በሚስቱ ስም የተቀበለው በ፫፻፲፭ ቍጥር የተጻፈው ካርታ ዋጋ የሌለው የማይረባ መሆኑን በዝርዝር አስረድቶ ለማዘጋጃ ቤት ሹም ለከንቲባ ነሲቡ በጽሕፈት አስታወቀልኝ ።

ይህም ሁሉ ከሆነ በኋላ ማዘጋጃ ቤት ነገሬን ባይጨርስልኝ ሥራዬን ትቼ በአዲስ አበባ ከተቀመጥሁ ብዙ ወራቶች ሆኑ አሁንም ይህ ርስት የሚገባኝ መጀመሪያ በ፬ ጳጉሜ ፲፰፻፺፱ ዓ ም የርስት ወረቀት ለተቀበልሁት ለኔ ነውና የቦታዬን ዋጋ ጨርሼ እንድቀበል ለዚሁም ጉዳይ የከሠርሁትን ከሣራ ሁሉ ማዘጋጃ ቤት እንዲከፍለኝ ይፈረድልኝ ብላ ነገሯን አመለከተች ። እኛም በፊትም በኋላም የተቀበለችውን የሁለቱንም ካርታ ኰፒውን ቆንስሎቹ ሙሴ ሐጅዮአኑና ዶክቶር ዜርቦስም ለከንቲባ ማተቤና ለከንቲባ ነሲቡ የጻፉትን ደብዳቤዎች አቅርበን መረመርን ።

ምርምር ።

በጳጉሜ ፬ ቀን ፲፰፻፺፱ ዓ ም በ፵፭ ቍጥር የተነሣውን ካርታ ብናየው ፱ሺ ፳፯ ሜትር ካሬ ሁኖ ተገኘ ። በ፩ ታሕሣሥ ፲፱፻፲፯ ዓ በ፱፻፴፬ ቍጥር የታደሰውን ካርታ ብናየው ግን ፲፫ሺ ፫፻ ሁኖ ተገኘ ።

እንደዚህም አድርጎ የተበላለጠበትን ምክንያቱን ለመረዳት ብለን በማታለል በመዳም እሌኒ ስም ተነሥቶ ባንክ አፍ አቢሲኒያ በዕዳ በመያዝ ይዞታል የተባለውን በሶስት መቶ አሥራ አምስት ቁጥር የተጻፈውን ካርታ ኰፒውን አስመጥተን ብናየው አሥር ሺ ሶስት መቶ ሜትር ካሬ ሆኖ ተገኘ ።

ባ፵፭ቁጥርና በ፫፻፲፭ ቁጥር በ፱፻፴፬ ቁጥር የተጻፈው ሶስቱም ካርታ መበላለጡን ከተረዳነው በኋላ ቦታው አንድ ከሆነ ሜትር ካሬው መበላለጡ በምን ምክንያት ነው ብለን ማዘጋጃ ቤቶችን ብንጠይቃቸው ቦታው አንድ መሆኑ እርግጥ ነው ፣ ነገር ግን በ፵፭ቁጥር በተለካ ጊዜ መሐንዲስ አልነበረምና አንድ ሰው በገመድ እየለካ ካርታ ይሰጥ ነበር በገመዱ ልክ ዘጠኝ ሺ ሀያ ሰባት ሜትር ካሬ ሆነ ። በሶስት መቶ አሥራ አምስት ቁጥር በተለካ ጊዜ ግን በመሐንድስና በሜትር በትክክል ስለ ተለካ የገመዱ ልክ ተሳስቶ አሥር ሺ ሶስት መቶ ሜትር ካሬ ሆነ እንጂ ። ቦታው ሌላ ሆኖ አይደለም ብለው ተናገሩ ።

ባርባ አምስት ቁጥርና በሶስት መቶ አሥራ አምስት ቁጥር የተነሣው ካርታ መበላለጡ በዚህ በገመዱና በሜትሩ መሳሳት ምክንያት ነው ካላችሁ ። በዘጠኝ መቶ ሰላሳ አራት ቁጥር የተነሣው ካርታ አሥራ ሶስት ሺ ሶስት መቶ ሜትር ካሬ መሆኑ ስለ ምን ነው ብለን ብንጠይቃቸው መዳም ቴዎፊሉ ቦታዋን አሁን በኋላ ባዲሱ ደንብ ስታስለካ የቀድሞውን ወሰንዋን ተላልፋ ድንበሬ ይህ ነው ብላ ለመሐንድሱ ስለ አሳየች መሐንድሱ አዋሳኞቿን ሳያቀርብ እሷ ባመለከተችው ወሰን ልክ ለክቶ ካርታውን ስላነሣው መበላለጡ ስለዚህ ነው ብለው ተናገሩ ።

ፍርድ ።

እኛም ከዚህ በላይ የተጻፈውን ቃል ስለ ሰማንና ነገሩን ስለ መረመርነው ከዚህ ቀጥሎ እንደ ተጻፈው ፈርደናል ።

መጀመሪያ ፡ መዳም ቴዎፍሎ በጳጉሜ ፩ ቀን ፲፱፻፶፱ ዓ ም ፺፫ ቁጥር የተጻፈ የርስት ወረቀት በእጅዋ ሳለ ሙሴ ዲሚጥሪ ብሐሰትና በማታለል በሚስቱ በመዳም እሌኒ ስም በ፲፱፻፷፭ ዓ ብ፫፻፲፫ ቁጥር አስነሥቶ የወረሰው ከርታ አይረጋለትምና ርስትነቱ ለመዳም ቴዎፍሎ ይረጋላታል ።

ሁለተኛ ፡ የግሪክ ቆንሲል ሙሴ ሐጅዮአኑ በመዳም እሌኒ ስም በ፫፻፲፫ ቁጥር የተነሣው ከርታ በሐሰት ነውና ለሌላ ሰው እንዳይሸጥ ብሎ ለማዘጋጃ ቤት ሹም ለከንቲባ ማተቤ በጽሑፈት ካስታወቀ በኋላ ማዘጋጃ ቤት ይኅን ከርታ ከቆንሲሉ ጋራ ተነጋግሮ በመቀበልና በመቅደድ ፋንታ እንደገና የመዳም እሌኒ ርስት መሆኑን መስክሮ ባንክ ኦፍ አቢሲኒያ መያዣ አድርጎ ገንዘብ እንዲበደርበት ፈቃድ ከሰጠ አላፊው ማዘጋጃ ቤት ነውና የባንኩን ዕዳ ማዘጋጃ ቤት ይከፍላል። ቦታው ግን ለጥንቱ ባለርስቷ ለመዳም ቴዎፍሎ ይረጋላታልና ለመሸጥም ለመለወጥም ትችላለች ።

ሶስተኛ ፡ በጳጉሜ ፩ ቀን ፲፱፻፶፱ ዓ ም የርስት ቦታ ሹም በ፺፰ ቁጥር ለመዳም ቴዎፍሎ የሸጠላት ቦታ ፱ሺ፳፯ ሜትር ካሬ ነበር ። ነገር ግን በፊት መሐንድስ ስለሌለ በገመድ ስለተለካ በኋላ በመሐንድስ በሜትር በትክክል ቢለክ ፲ሺ፫፻ ሜትር ካሬ ሆነ ከተባለ ይህ ይረጋላታልና የዚህን ዋጋ ከሸጠችለት ሰው ትቀበል። አስቀድሞ የርስት ቦታ ሹም የሸጠላትን ወሰን አልፋ በ፱፻፴፩ ቁጥር የወሰደችው ከርታ ግን ፲፫ሺ፫፻ ሜትር ካሬ ስለ ሆነ ብልጫው ፪ሺ፲፪፻፶፩ ሜትር ካሬ ሆኑዋልና የዚህ ዋጋ ታስቦ ከዋጋው ላይ ተነሥቶ ወደ ማዘጋጃ ቤት ይገባ እንጂ መዳም ቴዎፍሎ ለመውሰድ አይገባትም። ለዚህም ወሰን አልፋ ለወሰደችው ለ፪ሺ፲፪፻፶፩ ሜትር ካሬ የከፈለችው እሹራ እንደመቀጫ ሁኖ ይቀራል እንጂ ይመለስልኝ ለማለት አትችልም

አራተኛ ፤ መዳም ቴዎፍሎ የሚገባትን ርስቷን ብትሸጥ ባንክ ኦፍ አቢሲኒያ ገንዘቧን ማስያዙ ማዘጋጃ ቤት የመዳም ቴዎፊሉን ርስት መዳም እሌኒ በሐሰት በስሙዋ ማስለወጧን ካወቀ በኋላ ባንክ ለዕዳው መያዣ አድርጎ እንዲይዝ ፈቃድ በመስጠቱ ነውና ገንዘቧ ከተያዘባት ቀን ጀምሮ እስከሁን ታስቦ ወለዱን ማዘጋጃ ቤት ይክፈላት ብለን ፈርደናል ።

አምስተኛ ፤ ማዘጋጃ ቤት ይህንኑ በስሕተቱ ያደረገውን ነገር ብቶሎ ባለመጨረሱ መዳም ቴዎፊሉ ገንዘቧ ስለ ተያዘባት ሥራዋን ትታ በሙግት ምክንያት ብዙ ወራቶች በአዲስ አበባ ተቀምጣለችና ከሥራዋንና ለጠበቃ ያወጣችውን ገንዘብ የማዘጋጃ ቤት ይክፈላት ። የዳኝነቱንም የማዘጋጃ ቤት ይክፈል ብለን ፈርደናል ።

ይህም ፍርድ ከተፈጸመ በኋላ የማዘጋጃ ቤት በስሕተቱ ለባንክ ኦፍ አቢሲኒያ ፈቃድ ሰጥቶ በዕዳ ያስያዘውን የመዳም እሌኒን ከርታ ከባንክ ተቀብሎ ይሠርዛል ።

ይድረስ ከቶ ገብረ ክርስቶስ የብርሃንና ሰላም ጋዜታ ዲሬክተር ከዚህ ቀጥሎ ያለውን በጋዜታ ታትሞ ልዑል እንዲያዩት ቢያደርጉልኝ እጅግ አመሰግንዎታለሁ ።

ልዑል ሆይ ።

ይህችን ቀጥላ የተጻፈችውን የኔን ያንድ ድሀዎን ማስታወሻ ያንብቧት ለዙፋኑ ደጋፊነት ብዙ አዋቂዎችና መካሮች መኖራቸውን አውቃለሁ እኔም ይህነን አገበቡ ያልተዋሃደ ቃል ደፍሬ በመጻፌ ይቅርታዎን እለምናለሁ ። እኔም ምንም ትምርት ባይኖረኝ ስለ ሐገሬ ፍቅር መንፈሴ ቢደፍር ነው እንጂ ለከንቱ ውዳሴ ብዬ አልጻፍኩትም ።

ከዚህም ምኞቴ የሚበልጠው የተሰናዳ መልካሙ አሳብ ሁሉ በልዕልናዎ ልብ ተመስርቷል ደግሞም በሐሳብ ብቻ አይደለም እየተሠራና እየገፋ ሲሄድ እናየዋለን ብዙዎቹም ሠራተኞችዎ አለስንፍና ያግዙዎታል ።

ማስታወሻን በምሳሌ ለማስረዳ ።

እኔ የፍርድ ሹም ለመሆን አልመኝም ከላይ እስከ ታች ያሉት የፍርድ ሹማምንቶች ባንድ ቃል የሚፈርዱበት ደንብ አውጭዎች ያሰናዱት ለፍርዳችሁ አገባብ ይህ መሪ ይሁናችሁ ሕዝቡም ይህነን ያነበበ እንደሆነ የሚፈረድበትን ያውቀዋልና ሥራውን ትቶ ለከንቱ ነገር አይደክምም ኃይለኛም ደካማውን አያጠቃም ከዚህ አትለፉ በዚህ ፍረዱ ብሎ መንግሥት የሰጣቸው ለይቶ የሚያስረዳው የደምቡ መጽሐፍ የት አለ?

እኔ የጭፍራ አለቃ ለመሆን አልመኝም ያለቆቹንና የወታደሩን ሕግ ለይቶ የሚያስረዳው የደንቡ መጽሐፍ የት አለ ?

እኔ የርሻ አለቃ ለመሆን አልመኝም ለመንግሥትና ለሕዝብ ጥቅም የሚሆነው ንጉሡ ፤ ለርሻው አለቃ የሰጠው ሕዝቡ የሚበለጽግበት የደንቡ መጽሐፍ የት አለ ?

እኔ ያገር ግዛት አለቅነት አልመኝም ያገር ግዛት አለቃ መንግሥቱንና ሕዝቡን ለመጥቀም እንዴት ያለ የውቀት ነገር እንደሚያስፈልገው ለይቶ የሚያመለክተው የደንቡ መጻፍ የታለ

እኔ ሌላውንም ሹመት አልመኝም ያዛዡንና የታዛዡን ሕግ ሁሉ ለይቶ የሚያስረዳው ደንብ አውጭዎች ያሰናዱት ሕዝብ ሁሉ የሚያነበውና የሚያውቀው ሹሙ ከዚህ አይለፍ ደሀው ከዚህ አይለፍ ተብሎ የተጻፈው ለሐገሩ ሕዝብ የሚስማማው የደንቡ መጽሐፍ የት አለ?

እኔ ይህን ሁሉ ማለቴ ያገራችን ዳኞችና አለቆች ፍርድ አያውቁም ለማለት አይደለም ሁሉም በየራሱ የሚፈርደውና የሚያስበው ሁሉ መልካም ነው እንዳገሬም አለቆች ብልህና ፍርድ አዋቂዎች ያለ አይመስለኝም። ነገር ግን በደንብ ያልቆመ በጽሕፈት ያልተወሰነ ሁሉም በየአሳቡ የሚያደርገው ፍርድና ሕግ ሁሉ ብብዙ ስፍራ ያንዱ አሳብ ካንዱ መለያየቱ አይቀርም ለዚህ ማስረጃም አንድ ምሳሌ ልናገር፤ ሁለት ሰዎች ባንድ ጋሻ መሬት ይጣሉና በጭቃ ሹም ተዋውሰው እጅግ ይደርሳሉ ዱጉ ላንደኛው ይፈርዳል ያ የተፈረደበት ከምስለኔው ቃል ያመጣል ከምስለኔው ይደርሱና እሱም እንደታሰበው መጠን ላንደኛው ይፈርዳል ያ የተፈረደበት ከሻለቃ ወንበር ቃል ያመጣል እወምበሩ ይደርሱና ላንደኛው ይፈርዳል ያ የተፈረደበት ከሻለቃው ቃል ያመጣል እሻለቃው ይደርሱና እሱም ላንደኛው ይፈርዳል ያ የተፈረደበት ከንጉሥ ወንበር ቃል ያመጣል እንጉሡ ወምበር ይደርሱና ላንደኛው ይፈርዳል ያ የተፈረደበት ከራ ንጉሥ ቃል ያመጣል እራ ንጉሥ ላንደኛው ይፈርዳሉ ያ የተፈረደበት ከንጉሥ ቃል ያመጣል ንጉሥም ላንደኛው ይፈርዱና የነገሩ መጨረሻ ይሆናል ከዚያ በኋላ የተፈረደበትም የተፈረደለትም ፪ቱም ሰዎች እረፍት ያገኛሉ። ነገር ግን ይኸ ሁሉ ፍርድ እስኪተላለፍ ድረስ ብዙ ዘመን ያልፍ ይሆናል ፤ ይኸም ሁለቱ የሚ

ጣሉበት መሬት ባለመታረሱ ምክንያት የመንግሥትንም የሕዝብንም የባለቤቶቹንም ጥቅም ያጉል ይሆናል ። ይህም ባንድ ጋሻ መሬት ምክንያት ላንዲኛው ሰው የተፈረደለት በሰው አሳብ እንጂ በተጻፈው ደንብ ታይቶ ስላልተፈረደ ከብዙ ዘመን በኋላ በሌላው ሹም ሌሎች ሰዎች ቢሟገቱ ለፊተኛው ሰው እንደተፈረደለት መሆኑ ቀርቶ የተለወጠ ፍርድ ይሆን ይሆናል ። ያ የኋለኛው ሰው ግን የፊተኛውን ፍርድ አይቶ በልቡ አቆይቶ ባይነሳ ብዙ ድካም አያገኘውም ነበር ነገር ግን ከትልቁ እስከ ትንሹ የሚፈርድበት በየፍርዱ ዓይነት የደንቡ መጽሐፍ ፩ድ አይነት ቢሆን ደግሞ ሕዝቡ በጣም ሲሰለጥን የሚለወጥና የሚጨመርም ቃል ቢኖር ይኸው የሚጨመረውና የሚለወጠውም ከዚያው ቀጥሎ ቢጻፍ የሚሻል መሆኑ ምንም አስተካክዬ ባልሰማው የኤውሮፖች ሁሉ ደምብ እንደዚሁ ይመሳሰላል ይላሉ

ባገራችን አንድ የባላገር ንግግር አለ እሱም ለምሳሌ የሚያሻኝ ስለሆነ እናገረዋለሁ ያገሬ ሰው እንዲህ ይላል፡ ብርን ተቀባዩም ቆጥሮ መቀበል ሰጭውም ቆጥሮ መስጠት ይገባቸዋል ይባላል፡ እንዲሁ ከመንግሥት የሚቀበሉት ሹመት ሁሉ ክብር ይበልጣል ይኸ ምሳሌ ግን እንደዚሁ ባጭሩ የታወቀ ነው ።

የብልሁ የትጉሁ አልጋ ወራሽም አሳብ እንዴህ ይመስለኛል ሕዝቡ ሳይማር ያስተዳደሩን ደምብ ብንሰጠው ግራ ይገባዋል የሚጠቀመው ነገር የሚጎዳ መስሎ ይታየዋልና በዚህ ምክንያት ትምርትን አስቀድም ብለው ይሆናል።አሳብዎም እጅግ መልካም ነው ግን ባለጸጋውም ደሀውም በያሳቡ ነቃቅቶ እውቀትን ቶሎ ለማግባት ሳይጣጣር ጊዜ እንዴት ይሆናል።ትምሕርትን በያይነቱ ለማስፋት አሳብ የሚያስፈጽም ገንዘብ ስለሆነ ከክብታሙም እንደክብታምነቱ በደሃውም እንደድህነቱ ሁሉም እንደ መጠኑ ፈሰስ ተጥሎበት ብዙ ገንዘብ በቶሎ ተሰብስቦ የትምህርቱ ስራ ቢቻኮል ለአሳብዎ አጋዥ ይሆንዋል።ገንዘብም እንኳን አገርን ከችግር ለሚያድን ትርፉ በቶሎ ለሚገኝ ለትምህርትና ላረቄና ለማይጠቅም ነገር ሁሉ ስናጠፋው እንኖራለን ።ለትምህርትም አጋርነት ገንዘብን ከሕዝብ ለመሰብሰብ በብርሃንና ሰላም ጋዜታ ሙሴ ከቀዲያ የጻፉት መልካም የመሪነት ቃል አለው።

ትምሕርትም እስኪስፋፋ ድረስ እስከዚያውም ለስራው አጋዥ እንዲሆን ብዙ ብልሆችና አዋቂዎች በብዙ ዘመንና ድካም የለፉበትን በያይነቱ በየሹመቱ ለሚያስፈልገው ስራተኛ አውሮፖች የጻፉትን ደምብና ፍትሐ ነገሥት ቋንቋ የተማሩት ያገሮችም ብልሆች በትጋት ቢገለብጡት ደግሞ ይህኑ የሚገለብጡትን ያውሮፓን ሕግና ስርአትን ደምብና ፍትሐ ነገሥት ለኢትዮጵያ ሕዝብ እንደሚስማማ ፳ የሚያህሉ ብልሆችና ሊቃውንቶችም ተመርጠው ቢያስማሙት እንዴት መልካም አሳብ ይመስላል አስቦ ለመመስረት ነውንጂ ሰው የመሰረተውን ለማቃናትና ከፋ ለማ ለማለት ማንም አያቅተውምና እነዚሁም የሚመረጡት ከየሻለቃው አገር አንዳንድ ቢሆኑ በዚሁም ስራቸው ላይ የያገራቸውን ጉዳትና በደል የሕዝቡን አሳብ ከያገራቸው የሕዝብ ጉባኤ የሚመጣላቸውን መልክት ለዋናቹ የመንግሥት አማካሪዎች የሚያስታውቁ ቢሆኑ ይሻል ይመስለኛል

ልዑል ሆይ እኔ ፩ጊዜ ይቅርታ ስለለመንኩ የታሰበኝን ሰውነቴን ሳልገታና ይኸ ጸያፍ ይሆንብኛል ሳልል ደፍሬ ጻፍኩ እንጂ ለአውቀቶችዎ የተሰናዱ ብዙ ማስታወሻዎች እንዳሉዎ አምናለሁ ይኸንንም ግሙኔ እየተሰራና እየገፋ መሄድ በመጀመሩ ነው ።

ደግሞ ምንም ስራ ቢበዛብዎ ያስተዋዮችዎን አሳብ ሁሉ ለማንቃት መልካሙን አሳብና ምክር ሁሉ ለማስተዋልና ለመፈጸምም እንዲያስቡ እሰማለሁ ። እኔ እንደሚመስለኝ የነጋድራስ ገብረሕይወት መጽሐፍ ቃል ብቻ እንኳን ቢፈጸም እንዴት ትልቅ የጥቅም መጀመሪያ ነው ይልቁንም አስተዋጽአና አጼምኒልክ በሚለው መጽሐፋቸው ላይ ያለው አሥሩ ነገር አጭር በመሆኑ ቶሎ ለመጀመር አያውክምና ።

ይድረስ ከአቶ ገብረ ክርስቶስ የልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ማተሚያ ቤት ዲሬክተር የፍቅር ሰላምታዬን አቀርባለሁ ።

ሰው በተቻለውና በተሰጠው መጠን በብርሃንና ሰላም ሊያስታውቅ ልዑል አልጋ ወራሽ ፈቅደውለታል ።

አሁን ግን የኢትዮጵያ መንግሥት ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ለኢትዮጵያ ልጆች ብርሃንና ሰላምን ስለአወጡልን ብርሃንና ሰላምን ለርሳቸው ይሁን አሜን ።

አሁን ደሞ ከብዙ ዘመን ጀምሮ የሚቈረቍረኝ ሀሳቤን በብርሃንና ሰላም ጋዜጣ ልገልጸው ፈቃዴ ነውና በሚመጣው መስመር ተመልከት ። ኢትዮጵያ ትምህርትና አንድነት አጥታ እጅግ እንደ ተጐዳች የምታውቁ ሰዎች በጣም ብዙዎች ናችሁ ። ነገር ግን እኔ ዓይኔ በሚያየውና ዦሮዬ በሚሰማው ትግሬን እንሥቼ ልናገር ።

የትግሬ ገዦች ወይም ደሞ መኳንንቶች በጣም አልተማሩምና በሥርዓትና ባገባብ እጅግ መጥፎ ናቸው እንደምን ብትለኝ (ጠያቂ) እንዲኽ ነው የጨዋ እነዋወርና የወታደር እነዋወር የገበሬ እነዋወርና የነጋዴ እነዋወር አያውቁም ስለዚህ የጨዋ ልጅ ቢከፋውና ቢቸገረው ደሞ እንደርሱ የከፋቸውና የቸገራቸው በጣም ብዙዎች ናቸውና እነሱን አብብሎ ገዢ ሲለወጥ ታርቀን እንገባለን ብሎ ባንድ ሁነው ሽፍትነት ይሄዳሉ ሄደው ሲያበቁም ውድቅት ሲሆን ባንድ ባላገር ቤት ገብተው እርሱን አስረው የተገኘውን በልተው እንደ መጠኑ ተገላግለው ይሄዳሉ ።

ማለዳ ሲሆን ግን ባላገሩ ካገረገዦው መጥቶ እንዴኽ ብሎ ይጮኻል ሽፍታ ከቤቴ ገብቶ እኔን አሥሮ ገንዘቤን ወሰደብኝ ብሎ ይላል ። አገረ ገዦው ግን እንዴኽ ብሎ ይመልስለታል ዬት አገር ክፍል ናችሁ ። ሀጸበ ነን ይለዋል ሀጼቦማ ጥንትም ሽፍታ አትከለክሉም አሉ ብሎ አመኻኝቶ ሺ፭፻ ብር ክፈሉ ይላቸዋል እግዚአብሔር ያሳይዎ አንሰኝ ስል ተነቀሰኝ ከየት አምጥተን ሽፍታ በዘበዘን ብለን ብንጮኽስ ደሞ ሁለተኛ ልንከፍል እግዚአብሔር ያሳይዎ ብለው ይጮኻሉ ።

አገረ ገዢው ግን እንዲህ ብሎ ይመልስላቸዋል እናንተማ ጥንትም ኃይለኞች ናችሁ አሉ በሉማ ቀኛዝማች እገሌና ግራዝማች እገሌን ሂዳችሁ ሺ፭፻ ብር አምጡልኝ በየቤቱም ተሰሬ አግቡበት ይላቸዋል እነሱም ሄደው በየቤቱ ተሰሬ ይመሩበታል ወርቁ እስቲከፈል ድረስ በባላገሩ ቤት አንድ ወር ይቀመጣሉ

ኋላ ግን ጌታዬ ሥጋ አማራቸው ተበሉ ፲ብር የሚያወጣው ሙክት ያርዱበታል እንዲሁ ወተቱንም በእርጎው ይጠጡበታል

ንቡንም አለጊዜው እሳት አግብተው ይበረብሩበታል እንደዚህ ሲያደርጉም በእሳት የሚቃጠለው ቤት እጅግ ብዙ ነው ባላገሩ ግን እንዲህ አድርገው ገንዘቡን ሲያጠራቅሙና ሲያስቀምጡት ጊዜ የደረሰውን ወርቅ ተበድሮ ይከፍልና ምሽቱና ልጆቹን ሳይሰናበት ወልቆ ይጠፋል ። በንደዚህ ያለ ነገር የኢትዮጵያ ገባር እውነተኛ ጠባቂ አጥቶ ከሴቱ የቀኑ ቢብሰው ወደውጭ አገር ሂዶ አለቀ ይባላል ።

አሁን ግን የኢትዮጵያን ዜጋ ብንገምተው ከኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገዛው በውጭ አገር መንግሥት የሚገዛው ሕዝባችን እንደሚበልጥ ልክ የታወቀ ነው ። በምን ምክንያት ነው አገሩን ትቶ ከሌላ መንግሥት መገዛቱ ብትለኝ ? ምክንያቱ እንዲህ ነው ንብ ትጉ ሠራተኛ ነው በመትጋቱም ማር ተመግበ እኛንም ማር ሲመግበን ይኖራል ነገር ግን በሚሠራበት በታ ገብተው በቀንና በሌት የሚያውኩት ጠላቶች ያገኘ እንደ ሆነ ማሩን ትቶ እንዲሄድ ሁላችን እናውቃለን እንዲሁ ደግሞ ሕዝባችንን እጁን እያሰርን ቤቱን እየዘረፍን ብናስጨንቀው አገሩን ትቶ ከሌላ አገር መሄዱ በዚህ ምክንያት ነው ብዬ እመልስልኻለሁ ።

ወደ ውጭ አገር ስለ መሸጥና መለወጥ ።

ባዲስ አበባና ባዲስ አበባ ውጭ ያለ ሕዝብ ከብታችንና እህላችን ወደ ውጭ አገር ብንሸጠው ረሐብ ይሆንብናል እያለ ያወራል ተብሎ በብርሃንና ሰላም ጋዜጣ ሰማን ። እውነት ነው ቍስሉ ያልታወቀው ሰው ወደ ሀኪም ቤት መሄድ አያስፈልገውም እንዲሁ ደግሞ ሕዝባችን ጉዳቱና ጥቃቱ አልታወቀውም ጉዳቱና ጥቃቱ ቢታወቀውስ የድንቁርና ምንጭ ያረቄ መመላለሻ ሁኖ ባልቀረም ነበር ። አሁን ደግሞ ብንሰማ ፲፪ መኪና አረቄ የሚነጥርበት ባዲስ አበባ ውስጥ አለ አሉን ደግሞ ከትልልቆቹ ፮ መኪና በቀን ፪ሺ ኪሎ እህል ያነጥራል ከ፬ እንስተኞች ደግሞ ፩ በቀን ሺ፰፻ ኪሎ እህል ያነጥራል ተብሎ በብርሃንና ሰላም ሰማን

እንግዲያ በ፳ቱ ትልልቆች ፪ሺ በ፬ቱ እንስተኞች ደግሞ ሺ ፰፻ ኪሎ ባንድ ቀን ከነጠረ ከዚያ ተርፎ ለናንተ የሚበቃ ወዴት አለ ደግሞ የሚያስፈልገው እህልም ጤፍ ነው አሉ አያችሁ ፩ ዳውላ ጤፍ ባ፲ ብር ቢቀናልን ፲ ብር ስንት ቁምነገር ይሆን ነበር ።

ነገር ግን እኛ ጉዳታችን አልታወቀንምና ፩ ዳውላ ባ፩ ብር አቅንተን ኋላ ደግሞ ባ፩ ብር ፪ ጠርሙስ ገዝተን እንጠጣለን ዞረን ዞረን ብንመለስ ከረቄ ቤት አልወጣንም ።

ደግሞ አረቄ የሚነጠርበት መኪና የኛ ነው ወይስ የውጭ አገር ነው ብለን ብንጠይቅ የውጭ አገር ነው አሉን ። እንግዴህ እንባቢ አስተውል ፲፪ቱ መኪና የውጭ አገር ከሆነ ደግሞ ባንድ ቀን ይህን ያህል ኪሎ ከፈጀ በውጭ አገር እንደተቀና እወቅ እኛ ግን ፲፪ቱ የውጭ አገር መኪና ባ፩ ቀን ፬ መኪና ፪ሺ ፪ሺ ኪሎ እህል ያነጥራል የሚል ቃል እርግጥ ሆነና ወደ ውጭ አገር እንደተቀና ለይተን አወቅን ። አሁን ግን ወደ ውጭ መቅናቱን ካወቅን ፤ ፩ ዳውላ ሰጥተን ፪ ጠርሙስ ከምንገዛ ስም ያለው ወደ ውጭ አቅንተን ፲ ብር ይበልጠናል ።

ደግሞ አንድ ነገር ልናገር ፡ ኢትዮጵያ በዘመን ብሉይ ጀምራ በራስዋ የቆመች መንግሥት ናት ፡ ከስዋ ውስጥም ብዙ ኃይለኞች ነገሥታት አገራቸውን አሳልፈው የማይሰጡ ባሕር ተሻግረው የሚገዙ ጅግኖች እንደ ነበሩበት የምታውቁ ሰዎች በጣም ብዙዎች ናችሁ ።

ነገር ግን ይኸን ብላችሁ አገር እየተዘረፈ ባላገር እየታሠረ ከብት እየታረደ ንቡ እየተበረበረ ነው ነጋዴም በየበሩ እየተቀማ ወታደርም እየተራበ በልተው እያበሉት ነው የነበረ ።

አሁን ግን ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ያገራቸውን ጉዳትና የሕዝባቸውን ድንቁርና አይተው በጃን ሜዳ ላይ የተማሪ ቤት ከሚያስፈልገው ዕቃና መሣሪያ ጋራ አድርገው ማዚያ፲፱ቀን ፲፱፻፲፯ ዓመተ ምሕረት ከፈቱልን ። ደግሞ እኛ እንድንጠቀም ብለው ዘወትር የገንዘባቸውን ኪሣራ አይቆጥሩትም ። ሁለተኛ ባለፉት ነገሥታት ያልተደረገ ሕዝቤን እጠቅማለሁ ሲሉ በገንዘባቸው ኪሣራ ወደ አውሮፓ ተነሥተው ሄዱ ፤ ለኛም ሲሉ በአውሮፓ የከሠሩልን ገንዘብ መጨረሻ የሌለው ነው ። የምንጠቀምበትንም ሕግና ሥርዓት ደንግገው ወስነው ወዳገራቸው ኢትዮጵያ ተመለሱ ። ከተመለሱም በኋላ ሕዝባቸውን ከጨለማ ወደ ብርሃን ከድንቁርና ወደ ዕውቀት ከዙረት ወደ ሥራ ከመተላለፍ ወደ ሥርዓት አደረሱት ።

ሕዝባችን ግን ከጨለማ ኑሮ ወደ ብርሃን ሲወጣ የብርሃን ጮራ ዓይኑን የወጋው መሰለውና ፊቱን ወደ ጨለማ አዙሮ ከብታችንንና እህላችንን ወደ ውጭ አገር አንሸጥም ብሎ ወደ ጉዳቱ ተመለሰ ብለው በብርሃን ነገሩን ።

አሁን ግን እባክኽ ተው ሕዝባችን ፡ ከስንት ድካምና ከስንት ኪሣራ ገብተው ያበጁልንን ሕግና ሥርዓት አናፍርስባቸው ። ደግሞ እስራኤልን እንመልከት እግዚአብሔር ያዘዛቸውን ትተው በእጃቸው ሥራ አመለኩና በራሳቸው ቅጣትን አመጡ ። እንደዚሁ እኛም መንግሥታችን ባዘዘን ያልሄድን እንደሆነ ካንድ ቀን ቅጣት አናልፍም ። ማለት ከእግዚአብሔር ቁጣ ፤ እግዚአብሔርን ፍሩ ለንጉሥ ተገዙ ተብሏልና ።

ተማኙ ሮምሃ ፡ ዓድዋ ።

ብርሃንና ሰላም ይሁን ።

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን በሃገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ፤ ስለዚህ የተማሪ ቤት ደጉ የደጉ ልጅ አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ስላወጡት ለኢትዮጵያ አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ዕድሜዎን ያርዝም መንግሥትዎን ያስፋ እያልን እየለመነ ጥበብን እናቅርበት ድንቁርናን እንጣላት ። ኢትዮጵያ እንድታምርና እንድትጸዳ ሕዝቡም አርነት እንዲወጣ በዚህ በተሰየመው ጋዜጣ ሰላም ተብሎ እኔም እንደችሎቴ ትንሽ ቃል እጽፋለሁ ። ቅንዓተ ቤትከ በልዓኒ ያለው የቅዱስ ዳዊት ቃል አድሮብኝ ። አምሳ ለሚ ላንድ ሰው ሸክሙ ነው ፤ ለአምሳ ሰው ጌጡ ነው ያሉት ተረት ነው ብዬ አስቤ ለአልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ዕድሜ እየለመን ድንቁርናን ሊያጠፉልን የአእምሮን መብራት ከልባችን ሊተክሉልን የተነሱትን እጅግ ደስ እያለን ዕልል እያልን ሴቱ ወንዱ ትልቁ ትንሹ

ለዚህ ተማሪ ቤት ብንደግፍ መልካም ነው ብዬ በዚች በትንሽ እእምሮዬ እለምናለሁ ። ለሃገሬ ለደጊቱ ለኢትዮጵያ በዚህ ብርሃንና ሰላም ተብሎ በተሰየመው ጋዜጣ ለአልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ለደጊቱ ለንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ወለቱ ለዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ፤ በእውነት እናገለግል ዕገሴ ይህ ነው ሥራው ይህ ጠባዩ እያሉ ቤት ለቤት ከመኖር መሥራትና መማር ይሻላል ይመስለኛል ክፋትን ትዕቢትን ሐሰትን ምቀኝነትን ስርቆትን ስንፍናን ድንቁርናና ስካርን ዝሙትን ፤ ዝሙት ማለትም ሥጋዊ ዝሙት ብቻም አይደለ ነገር ግን አለገንዘቡ አለአገባብ የሰውን ገንዘብ መፈለግ ሁሉ ይህ ዝሙት ነው ።

አሁንም ይህን ሁሉ ትተን ልባችንን አንጽተን የእእምሮን ሥራ እንማር እእምሮ ማለትም ጥበብን መማር ሥራን መስራት ነው ። ቅንዑ ለእንተ ተአቢ ጸጋ እንዳለ ሐዋርያ ጳውሎስ ። ለመልካሙ ነገር ሁሉ ብንቀናና ብንደጋገፍ ብንስማማ ጠላት ባላጠቃንም ነበር ። አሁንም እኔ ስለወገኔና ስለሕዝቤ ስለመንግሥቴ ስለሃገሬ ስለሃይማኖቴ ፍቅርና ቅናት ስላደረብኝ ስለዚህ እኔ ዘመድ ቢረዳ ችጋርም አይገዳ እንደሚሉት ምሳሌ ። ባለችኝ አቅሜ ልደግፍ ፈልጌ ብቻ መብላት መጠጣት አይረባም በማለት የተነሣ መብላትና መጠጣት የቀደሙት ነገሥታትና መኳንንቶች ኃብታሞችም አበቶቻችን ቀኑን በዚህ ያሳልፉት ነበር ሌቱንም በምኝታ እንዲህ አድርገው ለኛ ዛሬ ላለነ ልጆቻቸው ጥበብን ሳያስተምሩን በመቅረታቸው በጣም ተጐዳን ስለዚህ ደጊቱ ኢትዮጵያ ሃገራችንን ትተን ከባዕድ ሃገር ተሰደን የሰው አገልጋዮች የሰው ባሮች ሁነን ከሰው በታች ተዋርደን እንኖራለን ። አሁንም ከዚህ ሁሉ ሕዝቤንና ወገኔን አርነት አወጣለሁ አገሬን አጸዳለሁ ከመዋረድ ወደ ክብረት አደርሳታለሁ ብለው አስበው ለተነሡልን አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ለዚህ ተማሪ ቤት በገንዘብ መደገፍና መርዳት ገንዘቡን ከማይጠፋ ስፍራ ማስቀመጥ ነው ። ስንኳንስና ለዚህ ለሚጠቅመው የተማሪ ቤት ዘለዓለም ለሚኖረው ብዙም የሚጠቅም መልካም ፍሬ ለሚያፈራው መልኳ አማረ ብሎ ስንኳ ለአንዲት ነፍስና ሥጋ የምታበላሽ ጋለሞታ ብዙ ነገር ይጠፋላታል አሁንም እኔ ብቻ በገንዘብ መደገፍ አይጠቅም ብዬ ይህን ትንሽ ቃል እጽፋለሁ እኔ የተማርሁ ስለሆንሁ አይደለም ዳሩ ግን የሰው ሞኝ የለውም ብልሃቱ እየቀል ነው ያሉት ተረት አለና ስለዚህ እእምሮዬ ቢሰንፍብኝ ልቡናዬ ባይበራልኝ ባገዶልሁት አትዘንብኝ ሰው ብቻ ለመልካም ታሰበ አያውቅም ብለህ አትለውም ብዬ ግን የሚታይ የልቡናው ንጽሕና ብቻ ነው ስለዚህ የያዘውን ከወረወረ ፈሪ አይባልም ከማለት የተነሣ አሁን እንደ አቅሜ ዛሬ የኢትዮጵያ ልጆች በማኅበር ለማቆም ለጀመሩት ተማሪ ቤት እርዳታ ለመግቢያ ሃምሳ ብር በየመቱ ሀያ ሀያ ብር እሰጣለሁ ተንደዚህም ያለ ቁም ነገር ሥራ ባለዕድል ሁኜ ፈንታየን በማግኘቴ እምላኬን እያመሰገንሁ ልዑል ጌታችንም ዘራቸው ሁሉ ለኢትዮጵያ ደጋፊና ቁም ነገር ሰሪ እንዲሆን እመኝላቸዋለሁ አገርን መውደድና መርዳት ያልጀመሩ ወንድሞቻችንና እኅቶቻችንም የእግዚአብሔር ጸጋ እያደረባቸው እንዳቅማቸው የሚገባቸውን እንዲሠሩ አሳባቸውንም ወደ ደግ ይመልሰው ስል እመኝላቸዋለሁ ። ባሰጋ ውቤ ዘብሔረ ጎጃም

አለሥራ ኑሮ አስቀድሞ ሞት ነው ። ጎቴ

የሥራ ፍሬ ከደስታ ሁሉ ጣፋጭ ነው ። ቦበናርግ

ለሁሉም ነገር ሰውነት የሚችለውን ሠርቶ በተረፈ መብረድና መታገሥ ነው ። ኢፒክቴት

ከሌላው ጥቅሙ ሁሉ ይልቅ ሥራ ጊዜን አሳጥሮ ለማሳመርና እድሜን ለማስረዘም ጥቅም አለው ። ዲደሮ

ማስታወቂያ ።

በርሻና በመስሪያ ሚኒስትር ሥራ ውስጥ መንግሥት ያወጣውን ደምቡና ሕግ ሳልተላለፍ ደህ ሳልበድል ፤ የመንግሥቱን ገንዘብ በጥንቃቄ ሠርቼ ቀድሞም ከሚሠራው ሠራተኛ ገቢ ገንዘብ አብልጬ አገባለሁ የሚል ሰው እርሻና እመስሯ ምኒስቴር መጻፊያ ቤት፤ ሁል ጊዜ ከጧቱ ከ፫ ሰዓት እስከ ፱ ሰዓት ድረስ ፤ እየመጣ ቢነጋገር በደስታ እንቀበለዋለን ደመወዙም እንደ ሥራው ገቢ እየታየ ይቈረጥለታል ጥቅምት ፲፩ ቀን ፲፱፻፲፰ ዓመተ ምሕረት ።

መኰንን ሀብተ ወልድ።

ማስታወቂያ

ለራሶችና ለደጃዝማቾች ለሴት ወይዘሮች የሚገባ በያይነቱ ጥሩ ካባ ከኤሮፓ መጥቶልኛል ቤቱም (ባንክ ኦፍ አቢሲንያ) ከእንግሊዞች ባንክ አጠገብ ነውና ይህን ካባ መግዛት ለሚፈልጉ ሰዎች መጥተው እንዲገዙ አስታውቃለሁ ። ኢያሱ ዳንኤል

አ ፔ ማርሲያኖ

በኢትዮጵያና በፈረንሳይ የቅኝ አገር ሶማሊ በተለየ ፊያት አውቶሞቢልና ትራክተር አስመጭና እንደራሴ።



A.P. MARCIANO

Concessionnaire Exclusif pour l'Ethiopie
et la cote française des somalis
des automobiles et tracteurs Fiat.

በልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ

መጀመሪያ ዓመት ፤ ቁጥር ፵፯ ።
1^re ANNÉE №. 47

ሐሙስ ህዳር ፲ ቀን ፤ ፲፱፻፲፰ ዓ·ም።
JEUDI 19 NOVEMBRE 1925

ብርሃንና ሰላም

LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d'Ethiopie, profondément désireux de voir régner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraissant tous les jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

የጋዜጣው ዲሬክተር ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።
Gabré Christo Taklé Haymanot
Diréceur

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሲገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ከ፵፮ ቁጥር የቀረ ቃል ።

የሕይወት መጠበቂያ ሥራት እንዲበጅልን ማስታወሻ ።

እንግዲህ እዚያም እዚህም ብዘል በቅጡም አጥርቼ የማላውቀውን ነገር ሁሉ ምሳሌ እያደረግኹ ለማስረጃ የሞከርኩበት ምክንያቱ ለመጻፍ የተነሳሁበት ዋናው የጉዳዩ ቅሉ በመጀመሯው ክፍል የጀመርኩትን ነገር ለማስረዳት ነውና እንግዲህ የጅምሬ መፈጸሚያ ስለተቃረበ ወደ ዚያው ወደ መጀመሯዬ ልመለስና ልጻፍ ።

ይህነን ቃል ለሃገሮቼ ሰዎች ለማስታወቅ ማሰብ ከጀመርኩ ከሁለት ዓመት በለጠኝ ። ግን እንደልብ የልብ ሐሳብ የሚሰጥበት ጋዜጣ ብዙ የለችም ነበርና ለብዙ ሰው ሃሳቤን ለማዳረስ የማይቻል ስለሆነ ቸግሮኝ ልቤን እየቆረቆረው ሲኖር እግዚአብሔር ትምሕርቴን ባስፈጸመኝ ጊዜ መጽሐፍ ጽፌ በምጽፈው መጻሕፍት ሃሳቤን አመለክታቸዋለሁ ብዬ በተስፋ አስችሎኝ ቆይቼ ነበር አሁን ግን ሳላስበው የኢትዮጵያ ብርሃን የሆኑ አልጋ ወራሻችን ልዑል ተፈሪ መኰንን ብርሃንና ሰላም ብለው ሰይመው ጋዜጣ አወጡና ለኢትዮጵያ ሰዎች የምታስቡ ሰዎች ሁሉ መልካም ሃሳባችሁን ለወገኖቻችሁ ለኢትዮጵያ ሰዎች ማካፈል ፈቃድ ቢኖራችሁ እነሆ ያውላችሁ ብርሃንና ሰላም ለኢትዮጵያ ሕዝብ ጥቅም እንዲሆንና የኢትዮጵያ ሕዝብ አዲስ ዓይን አውጥቶ እንዲመለከት ሁላችንም የኢትዮጵያውያን ደም በደም ሥራችን የሚፈስ ሰዎች ሁሉ በየበኩላችን መረዳዳት እንጀምር ተብሎ የሚተረጐም ቃል ያለበት አድርገው ያወጡት መጀመሪያ የታተመው ንምራ በየካቲት ፴ ቀን ፲፱፻፲፯ በደረሰኝ ጊዜ ደስታዬ ተልኮ አለፈ ። ይህነንም ትንሽ ሃሳቤን የምጽፍበት ጊዜ እስቲደርስልኝ ቆይቼ ነበር ተማሪ ቤት ተዘግቶ እርፊት ሰሞን እስቲደርስ ማለቴ ነው አሁን ግን ቀኑ ስለደረሰ የመጀመሯውን ሃሳቤን ከራሴ የጻፍኹትን አጫጭር ክፍሎችና ከዚህ የሚከተለውን ለማስታወስ አደረሰኝ እነሆ ይኸንን ከላይም አስቀድሜ የጻፍኩትን ከኋለኛውም የሚከተለውን ያነሳሳኝን ነገር ወሬ እንደመንገር ያህል አድርጌ ልጻፍላችሁ ።

የዛሬ ሁለት ዓመት እዚህ እተማሪ ቤታችን ሁኜ ሳለሁ አንደኛው የተማሪ ቤት ጓደኛዬ ታመመና ተኛ ይኸውም ልጅ የተኛበት ቤት እኔ በማድርበት ቤት ጐረቤት ነበረና ታምሞ ተኝቷል ማለትን ስንሰማ ጊዜ ካንደኛው የተማሪ ቤት ጓደኛዬ ጋራ አብረን ሂደን አየነው በሽተኛውም በጣም አልጠናበትም ነበርና በቁማችን አልተቀመጥንም ነበር እንኳ አንድ ሶስት ደቂቃ ያህል ቁመን አነጋግረነው ተመልሰን ወደሥራችን ሄድን ግን በታመመ በሶስተኛው ቀን ሃኪሞች በሽታውን መረመሩና ያመመው በሽታ ኩፍኝ ሆኖ አገኙት ። ኩፍኝ መታመሙ ከታወቀ በኋላ በታላቅ ወረቀት በጉልህ ተጻፈና እዚህ ቤት ኩፍኝ አለና ሰው እንዳይገባ በመንግሥት ፈቃድ ክልክል ተደርጓል ብለው ጽፈው በደጃፉ ላይ ለጠፉት በዚያም በቤት ውስጥ የነበሩትን ሰዎች ሁሉ እስከ አራት ሳምንት ድረስ ከዚያ ቤት ወጥተው ከሰውም እንዳይገናኙ የቤትዋንም ደጃፍ ወጥተው ወደሌላ ሰው ቤትም እንዳይሄዱ በመንግሥቱ ሥርአት ተከልክለው ቤታቸውን ዘጉ ከዚያ ከቤት እቃም ምንም ወጥቶ ወደሌላ ሰው ቤትም ወደ ውጭውም እንዳይሄድ ክልክል ነበር ። እቃ ወደዚያ ቤት ይገባ ነበር እንጂ ከቶ መርፌን የምታህል ቲንሺ ዕቃ እንኳ ከቤታቸው እንዳይወጣ በጠነከረ ሥርአት ስለተከለከለ አንድ እንኳ ነገር ወጥቶ አያውቅም ነበር ። ሐኪሙም ይህነን አስከልክሎ ከፈጸመ በኋላ ቀለምና ወረቀቱን ይዞ ገባና ታሞ የተኛውን ልጅ ከታመመ ጀምሮ እየገባ የጠየቀዉን ሰው ሁሉ ስም እንዲነግረው አዘዘው ይኸውም ኩፍኝ ታሞ የተኛ ተማሪ ዝም እያለ እያሰበ እገሌ መጥቶ ጠይቆኛል እገሌም መጥቶ ጠይቆ–

ኛል እያለ እየሄዱ የጠየቁትን ጓደኞቼን ሁሉ ስም ነግሮ አጻፈ ሃኪሙም ያነን የተቀበለውን ስም ሁሉ ይዞ ወጣና ሁላችነንም ሂደን የጠየቅነውን ሁሉ ተየክፍላችን እየጠራ አስወጣን ተጠፍተንም ተየክፍላችን ተገኝተን የወጣነው ድምራችን አስራ ሰባት ተማሪዎች ነበርን ሁላችነንም ሰበሰበና ካገኘን በኋላ በሉዳንግልድ ሥፓንሰን ጓደኛችሁን ሂዳችሁ በተኛበት ቤት ገብታችሁ ጠይቃችሁታልና እሱን ያመመው የሚጋባ በሽታ ኩፍኝ ነውና ሁላችሁም መጽሐፋችሁንና ሌላም የሚያስፈልጋችሁን ዕቃ ሁሉ እየያዛችሁ ወደ እየመኝታ ቤታችሁ ግቡ እስከሰባት ቀን ድረስ በሽታው በዚያ ባላችሁበት ቤት ሰው ሳይዝ እናንተንም ሳያማችሁ የቀረ እንደሆነ የተማሪ ቤቱ ተፈቅዶላችሁ ለትምርታችሁ ትገባላችሁ ግን ይኸ ሰባት ቀን እስቲፈጸም ድረስ ምንም ችግር ቢያገኛችሁ ከመኝታ ቤታችሁ ወጥታችሁ ከሰው እንዳትገናኙ ተከልክላችኋል ይህ ሰባት ቀን እስቲፈጸም ድረስ አንድ ሰው እንኳ ባላችሁበት ቤት የታመመ እንደሆነ እስከ አራት ሳምንት ድረስ ከዚያ ቤት ወጥቶ ከሰው መገናኘት አይፈቀድላችሁም ብሎ እንደዚህ ያለ ፍርድ ፈረደብን ወደ እየመኝታ ቤታችን ገብተን እንድንከተት አዘን ሄደ እኛም እንደታዘዝነው ሁሉ በሙሉ ለመፈጸም እየመኝታ ቤታችን ገባን ። እኔ ባለሁበት ቤትም ሁለት ጓደኞች ነበርን የተጋዝነው ምግባችነን እየሰራን ሳህናችነን እያጠብን ቤታችንን እያጸዳን መቀመጥ ስለተፈረደብን ይህንን ስንሰራ ብዙ ሰዓት እየሄደብን ወደፊት የሚጠናውን ትምህርታችንን በቅጡ እንዳናጠና ታወክን እኔስ ለዚያች ለሰባት ቀን እጅግ አልጨነቀኝም ነበር ግን አንድ ሰው ደግሞ በዚያ በቤት ውስጥ የታመመ እንደሆን ወደፊት አራት ሳምንት ከተማሪቤት መለየቴን አጥብቄ ስለፈራሁ እጅግ አድርጌ አዝኜ ነበር ወደፊትም ትምህርቴን ፈጽሜ አገሬ እስትገባ ድረስ በሽተኛ ሄጄ ላልጠይቅ በልቤ ውስጥ ቃል አደረግሁ ለጊዜውም ወደፈጣሪዬ እጅግ አጥብቄ አዘንኩ እግዚአብሔርም ቸርነት ልማዱ ነውና ምንም ሰው ሳይታመም ቀረና ሰባት ቀናችን በደህና ተፈጽሞልን ወደስራችን ተመለስን ፡፡

በሃገሬ ሳለሁ ያልጋ ወራሽ የልፍኝ አሽከር ነበርኩ ወዳጆቼ በታመሙ ጊዜ ወስላታ መባልን እጠላ ነበርና የታመሙትን ወዳጆቼን ሁሉ እየሄድኩ እየጠየቅሁ ስመለስ ሰተት ብዬ እልፍኝ ገብቼ ስራዬን ስሰራ እውል ነበር እንዴት ያለ እውቀት ትልቅ በደል በድዬ መኖርን ያለፈውን በድንቁርና የበደልኩትን ጥፋቴንና ስህተቴን አሁን ወደ ተማሪቤት ከገባሁ ስለተረዳሁት እጅግ አድርጌ አዘንኩ ይህችን እንኳን ለማወቅ ላበቃኝ ለመልካሙ ጌታዬ ረጅም እድሜ እንዲሰጥልኝ ስስት ቃል ሳልጸልይ አልተኛም ጧትም ያችን ሳልል ስራ መጀመር የማይገባኝ መሆኑን ስለተረዳሁ ዘንግቻት አላውቅም ፡፡ አሁን ግን የኔስ ያጠፋሁት ጥፋት ያለፈ ነገር ሆነ ባዲስ አበባ ያሉ ጓደኞቼ ያለ እውቀት እኔ በስህተት ወዳጆቼ ሲታመሙ የበሽታውን ዓይነት ሳልመርጥ እየሄድኩ እየጠየቅሁ ከበሽተኛ ቤት ተመልሼ እልፍኝ እገባ እንደነበርሁ ሁሉ ዛሬ እነሱም እንደኔ ያለውቀት ልዑላቸውን እንዳይበድሉ ምንም የቅርብ ወዳጃቸው ቢሆን በስልክ እየጠሩ ሰው እየላኩ ወረቀት እየጻፉ ያስጠይቁት እንጂ በሽተኛ ሄዶ ጠይቆ ተመልሶ እልፍኝ ገብቶ ስራ መስራት አይገባቸውም ።(የሚጋባ በሽታ ያለማለቴ ብዙ ሃኪም በሃገራችን የለምና የሚጋባ በሽታ በሰው ቤት በገባ ጊዜ በቶሎ አይታወቅም ብዬ ነው) ይኸንን የኔን ምክር ተከትለው የሄዱ እንደሆን የልፍኝ አሽከሮች መቼም ወዳጅ አያገኙ ግን ወዳጅ ቢቀርባቸው ይሻላል እንጂ የመንግሥቱን ዋናውን የኢትዮጵያን ዓይን ለማጥፋት አይገባቸውም ።

ክቡር የአዲስ አበባ ክንቲባ አንድ የተከናወነ ሥርዓት እንዲያወጡና ይኸነን ያስታወስኩትን ነገር ሁሉ በዝግታ ተመልክተው መሰረቱን እንዲመረምሩ ዋና ተስፋ አደርጋለሁ ።

የሕዝባችን ቍጥር ማነሱን ስለማሰብ ።

ወገኖቼ ሆይ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከአስራሁለት ሚሊዮን አይበልጥም ይባላል የጃፓን ደሴት የኢትዮጵያን የገሚሷን ገሚስ የማታህል አገር ስልሳ ሚሊዮን ሕዝብ ይዛለች የጃፓን አገር ሰዎች ምንም ስርዓታቸው የዚህን ዘመን አኗኗር ጠብቀው በንጹሕ የሚኖሩ ሕዝቦች ባይሆኑ የነሱ እንኳ ያልተመሰገነ አነንዋራቸው ከኛ አገር ሕዝብ አሸለው ያነዋዋር ስርዓት መጠበቃቸውን ያሰረዳናል ። የእንግሊዝ ደሴት እንደዚሁም የኢትዮጵያን የቁራሽዋን ቁራሽ የማታሕል አገር በትላቁ ከተማዋ በሎንዶን ብቻ ሰባት ሚልዮን ሕዝብ ይዛለች እንዲያውም ከነከታቴው ወደፊት ለሚወለዱት ልጆችዋ መግቢያ አይበቃቸውም ይባላል ። ዛሬም በሀገሩ የሚኖሩት ሰዎች ስለ ሀገራቸው መጥበብ በተወለዱበት አገር ሥራ ለማግኘት እያስቸገራቸው የግድ ስደተኞችና የሰው አገር አቅኚዎች እየሆኑ ይኖራሉ የፈረንሳዊ አገር እንደዚሁም ከኢትዮጵያችን እያንሰች ከሰላሳ ዘጠኝ ሚልዮን የሚበልጥ ሕዝብ ይኖርበታል ።

እስቲ የነኝህን ከኢትዮጵያ የሚጠቡ አገሮች እየተመለከትን የሕዝቡን ብዛት እያሰብን እራሳችንን እንጠይቀው ኢትዮጵያችን መልካም አገር ናት እዚህ አስቀድመን ካነሳናቸው አገሮች ሳትሻል አትቀርም እንዲህ አድርጋ ባዶ መሆንዋ በምን ምክንያት ይሆን ? ይኸነን ጥያቄ ማንም ለመመለስ ይቻለው ይመስለኛል የኢትዮጵያ ሴቶች ወላዶች ባይሆኑ ነው እንዳይባል አንዲ ሴት የምትወልዳቸው ልጆች ሁሉ እንኳ በደኅና ቢያድጉ አንድ ወረዳ አገር ለማቅናት ይቻላቸው ነበር ለዚያስ እሩቅ ሳንሄድ በቅርቡ እራሴን ምሳሌ ለመስጠት እችላለሁ የኔ እናት የወለደቻቸው ልጆች ሁሉ ሁሉም በፍጹም አድገውልኝ በነበር ሁላችንም ካንድ ማኅጸን የወጣነው ሁሉ አድገን ተምረን ደርሰን በነበር እነኝህ ካንድ ማኅጸን የተገኘነው ልጆች ብቻ ባንድ አውራጃ ለሚያስፈልገው ላንድ ለሰፊ አገር ሠራተኞች በየይነቱ ላስተማሪ ለሃኪም ለመምሕር ለቤተ ክርስቲያን ለሚያገለግሉም ዲያቆናት ላገር ጠበቃ ለሚሆኑ ተሟጋቾች መንገድና ቤት ለሚያዘጋጁ መሃንድሶች ለጋዜጣ ጽሕፈት ሹማምንት ለሚሆኑ ሠራተኞች ብርና ወርቅ ያለበትን አፈር እየመረጡ ለሚፈልጉ ያፈር ማህንድሶች ለሚረባው ከብት ሃኪም ለሚሆኑ ሃኪሞች ለሀገሩ የሚያስፈልገውን ንግድ በስርዓት የሚያስኬዱ ነጋድራሶች ለባንክ ሹማምንት የሚሆኑ ሠራተኞች ይኸነን ለመሰለው ትላላቅ ሥራ ሁሉ የሚበቃ ጀግና አንድ እናት ብቻ ወልዳ ለማድረስ ትችል ነበር በመልካሚቱ ኢትዮጵያ ውስጥ ከመልካሚቱ ወላድ ይኸንኑ

ያህል ጀግና ይገኛል ። እንደዚህ ካንድ እናት የተወለዱ ልጆች አንድ ትላቅ ኩባንያ ሁነው አንድ ትልቅ ሥራ ቢያወጡ ለኢትዮጵያ ለትላቅ ትጋር መውጫ ለመሆን እንዲቻላቸው እናስብ ። ይህንን ማለት እንዲህ ያለ ለመሥራት የግድ የናት ልጅ ያስፈልጋል ማለቴ አይደለም ግን ካንድ እናት የተገኙ ልጆች ከብዛት የተነሳ ለመሥራት የሚቻላቸውን ጥቅም ማስታወሴ ነው ።

የኢትዮጵያ ልጆች ነጻነታቸውን አጥብቀው ይወዳሉ የሚሉ መልካም ስም በዓለሙ ታሪክ ሁሉ ተጽፎልናል ይህ እጅግ የሚያኮራ ስም ስለሆነ በጣም ደስ ይለናል በዚሁም መልካም ልብ በተሰጣቸው አያቶቻችን ብርታት ይህንን የመሰለ በዓለሙ አልማገዛ ሁሉ ለመግዛት የማይቻለውን መልካም ስም ስለአቆዩን ዛሬ የኢትዮጵያ ልጆች ብቻ በሀገራችንና በተጻፈልን ስማችን በሄድንበት እንደከራን እንኖራለን የቀረው የጥቁር ትውልድ ሁሉ ከዓለም ዳር ጀምሮ እስከ ዓለም ዳር ድረስ አንገቱን የደፋና በነጮችም የተናቀ የወደቀ ሕዝብ ነው ። ዋ ወገኖቼ ሆይ እኔ የኢትዮጵያውያን ነኝ ኢትዮጵያ ነው አገሬ ስል ልቤ በኩራት አፌ በድፍረት ሲናገር ሳየኝ የዓለም ገዢ እኔ እመስላለሁ ከቶ የኢትዮጵያ ሰው መባሌን አስለውጦ በሌላ ስም ለማስጠራት ቍጥር የሌለው ክብረት ቢሰጡኝ አንገቴ በሰይፍ ካልተመታ የምሸጣት አይመስለኝም ለምንድነው እንደዚህ አብዝተን በሀገራችን መኩራታችን ? በሀገራችን መኩራታችን አያቶቻችን ስላቆዩን ስለመልካሙ ታሪካችን ነው ስለለምለሚቱ ኢትዮጵያ ነው ስላልተመታው መንግሥታችን ነው ። ምንም ከዚህ ቀደም በዚህ ዘመን ስልጣኔ ባንመሰገን የዚህንም ዘመን ስልጣኔ በችኮላ መፈለግ ይዘናልና ስለዚህ በኢትዮጵያ በመወለዳችን አናፍርም ግን አብዝተን እንከራለን በኢትዮጵያ ተወልደናልና በቆየው በክርስቲያኑ መንግሥት ውስጥ ግን ነጻ መውጣት በባእድ መንግሥት ከመገዛት ብቻ አይረባም የሚወለደው ሁሉ የመቅሰፍት ተሸናፊ ሁኖ ተቀረ ምንድነው ነጻነቱ ከሰው ገዢ ነጻ ሆን እንጂ ከመቅሰፍት ነጻነት አልተገኘም መቶ ቢወለድ ዘጠናው ሳያድግ ይሞት ይሆናል ነጻነታችንን መውደዳችን በሀገራችን መንግሥት ደስ ብሎን ጥቃት ሳይገባን እንድንኖር ነው እንጂ አንድ ጨካኝ ንጉሥ ነግሦ የሚወለደውን ልጅ ሁሉ በሕጻንነቱ እያስገደለ የወለዱትን እንዳልወለዱ ቢያደርጋቸው የኢትዮጵያ ሰዎች ነፃነት አላቸው አይባልም ነበር ። እንግዲያውስ በውነት ብንመለከት የነፃነትን ስም በምሉ ይዘናታል እንጂ ነፃነታችን ገሚስ ነው ማለት የሃገራችን መንግሥት ሕዝቡን መልካም አድርጎ እንዳባት እየጠበቀ ያኑረው እንጂ ሕዝቡ ከመቅሠፍት ነፃነት ገና አላገኘም ። እንግዲያውስ እውነተኛውን ነፃነት ገና አላገኘንም ። ሚስትህ ማኻን ሁና ስትኖር አንድ ልጅ በስተርጅና ትወልድልህ ይሆናል እግዚአብሔር ሰጠኝ ብለህ ደስ ብሎህ ዓይን ዓይኑን ስታየው አንድ ሶስት ዓመት በፍቅሩ ልብህ ሲቃጠል ከእለታት አንድ ቀን ባንድ ፍሬ በሌለው በቲንሽ በሽታ ሀኪም ለማዳን በሚቻለው ነገር ይታመምና ይወድቃል ። እንግዲህ ይህ ልጅ ያመመውን ነገር ለማስረዳት አይችል ሕፃን ነው ገና ብቻ ያለቅሳል ይጮኻል እናቱንና አባቱን እያስጨነቀ መድረሻ ያሳጣቸዋል ። ወዲያውም ያተኩሰው ና ይቃዣል ። ከዚህ በኋላ ቡዳ በልቶታል የሰው ዓይን ነው ይባላል ወይም አጋንንት ለክፎታል ይባላል ወዲያውም ኡፎጉድ ልጄን ልነጠቅ ነው እያልህ ትሸበራለህ ። ግን ወደ ሀኪም በቶሎ ብትወስደው ልጅህን ያመመው በሽታ ቀላል ሁኖ ይገኝና ሀኪም በእግዚአብሔር ፈቃድ ምክንያት ሁኖ ያድንልህ ይሆናል ። አንተ ግን ወደ ሀኪም አትወስደውም እናቱ ሀኪም አትወድምና ሀኪም ይገልብኛል ትላለች ፤ ሀኪም ሰው ለመግደል አሥራ ሶስት ዓመት በተማሪ ቤት ተማረ ይመስልህ ይሆንን ? እናቱ ግን ተሀኪም መድኃኒት ይልቅ የሀገራችን መድኃኒት የሚባለውን ትወዳለችና የሀገራችን መድኃኒት ይባልና ተየዓይነቱ የተጠራቀመ የንጨት ስር ይመጣና ይህንን ሕፃን በጨርቅ ጀቢቡነህ ታጥነዋለህ የሕፃኑም ትንፋሽ መውጫ ያጣና ሕፃኑ ሲጨንቅ መለፍለፍ ይጀምራል ። በዚያን ጊዜ የወላድ ነገር ተጨንቀኻልና በመድኃኒቱ ኃይል ልጄን የያዘው በሽታ ሊለቅልኝ ነው ትልና ደስ እያለህ በይ ተናገሪ ምንድነሽ ? ማነሽ ? እየተባለ ይጠየቃል ።

ይህም የታመመው ሀጻን ነፍስ ያወቀ ልጅ እንደሆን ከዚህ ከመጣበት መከራ የሚገላግለው ነገር ያስባል ወዲያውም እንደ መልከጥፉ ሴትዮ አይቶ በጕረቤት ልብ ያደርግ እንደሆን እኔ አገሊት ነኝ የበላሁት እያለ ስም እየጠራ ይለፈልፋል ከዚያ በኋላ ልቀቂ ብለው ለቅቂያለሁ አሰኝተው ይተውታል በነገታውም ሌሊት እንቅልፍ አሳጥተውት አድረዋልና በጣም ደክሞት ሰውነቱ ስለተጐዳ እንቅልፍ ይወስደውና ያዩታል በዚያውም ጊዜ ያፍቱን የሆነ መድሃኒት በሽታውን አስወገደለትና ከሞት ተርፏል አሁን እንቅልፍ ወስዶት ተኝቷል ይባላል ሕፃኑ ግን ድካም ተጨምሮ ይልቁን አድክመውታል እንጂ ፈውስ አላገኘምና ከንቅልፉ ሲነሳ ሰውነቱ በጣም የደከመ ሁኖ ይገኛል ወዲያውም ከድካሙ ብዛት የተነሣ ይጠናበትና ይሞት ይሆናል በዚያውም ጊዜ ያች ቡዳ ለቀቅኩ ብላ አታልላ ልጃችንን ገደለችብን ሲሉ ይኖራሉ ። እንደዚህ እየሆኑ ብዙ ሀጻናቶች ማለቃቸው እርግጥ ነው ስለዚኸውም እንደዚህ እየሆንን ከበሽታ ነጻ ያለመሆናችንን እንረዳው ። ስማቸው የተመሰገነ ይሁንና ወንድማችን ክቡር ነጋድራስ ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ ከጻፉልን መጽሐፍ ሲያስረዱ «ነጻነት ሲወጣ በሁሉ ነገር እራስን ችሎ ከድህነት ነጻ መሆን ነው» እንዳሉት ሁሉ ሕዝብ ከድህነትና ከመቅሰፍት ከደዌና ሰው በውቀቱ ሊከለክለው ከሚቻለው በሽታ ሁሉ ነጻ ሁኖ ሕዝብ እየበዛና እየተበራከተ እንዲሄድ ካላደረጉት የመንግሥቱ ነጻነት እንዲያው ለስሙ ነው እንጂ እውነተኛውን ነጻነቱን አግኝቶአል ለመባል አይቻልምና ከበሽታና ከድህነት ነጻነትን እንድናገኝና የበረታ መንግሥት የበረከተ ሕዝብ እንድንሆን እንጣጣር አሁን ያለብንን የመቅሰፍት ኃይል ለተመለከተው ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ ጥቂት ነው መንግሥቱም ደካማ ነው ብሎ የሚንቀን የለም ወደፊት ግን ይኸነን የበሽታ ኃይል ሰብረን የተወለደው ሁሉ እያደገ አገሩን ለማገልገል በደረሰ ጊዜ መሬታችን የያዘችውን እያወጣን መብላት በጀመርን ጊዜ የኢትዮጵያ መንግሥት እንደዛሬዎቹ እንደሃይለኞች መንግሥቶች ሁኖ እንደአንዳቸው ተፈርቶ ለመኖር እንዲበቃ የተረጋገጠ ነገር ይሆናል እንዲህ ለመሆን ያብቃን ።

ይህንን ሁሉ ከመጀመሯው ክፍል ጀምሬ እስከዚህ እስከ መጨረሻው ያስታወስኩትን ነገር ሁሉ እንዲያው በከንቱ መ—

መኘት ሆኖ ይቀራል እንጂ በሃገራችን የተማሬ ቤቶች ተገኝተው ልጆቻችን እየተማሩ ይኸነን ችግራችነን ሁሉ በሃገራችን ተማሬ ቤት እየተማሩ ወጥተው ከልደረሱ የተማረ የሰው አገር ሰው ቢቀጥሩ በኪራይ መሣሪ የማጌጥ ያህል ነው ባለኪራዩ መሣሪውን የወሰደው ለት ድኅነት መውደቅ ነውና እንደዚህ አሁን እኛ እንደምንማረው ብዙ ልጅ ወደ አውሮፓና አሜሪካ እየሰደዱ ቢያስተምሩ ከሣራውም ብዙ ነው ወዲያውም ለችግራችን የሚበቃ ያህል ለማስተማር አይቻልም ። እንግዲያውስ ክቡር ወንድማችን ፊታውራሪ ዴሬሳ እንዳወጡት እንደመልካም ሃሳባቸው እዚያ አገራችን ተራድቶ የትምህርት ቤቶች በቶሎ ማቆምና ልጆችን ማስተማር ብቻ ነው ዋናው መድኀኒት ለሃገራችን ። እኔስ ስለ ፊታውራሪ ዴሬሳ ሃሳብ የተከናወነ መሆኑን ስለ ተረዳሁ ብዙ የሚቻላቸው ኢትዮጵውያኖች በጣም ደስ ብሎአቸው ተሻምተው በቶሎ ስራው እንዲጀመር ያደርጋሉ መስሎኝ ጓጉቼ ነበር አሁን ግን በየሳምንቱ የሚፈርሙትን ሰዎች የስጦታቸውን መጠን ስመለከት በሰጡት እጅግ ደስ አለኝ ግን እስችሎአቸው እስከሁን ስጦታቸውን ሳያስታውቁ የቀሩት ሰዎች በሃገር ባይኖሩ ይሆን ወይስ በሃገር ውስጥ እያሉ እንዲህ ያለ መልካም ሥራ ሲጀመር ለመደበለቅና ከዚህ ከማአረግ አገራቸውን ለመጥቀም ሳይከፈሉ መቅረታቸው ይሆን ብዬ እጅግ መገረም ጀምሬአለሁ ኢትዮጵያስ እንደማንም ብላ ልትቀና ነው ግን ይኸነን የመሰለ ረድኤትን በመከፈያቸው ጊዜ አስችሎአቸው ለሚያልፈው አለም ሰስተው የሚቀሩ ሰዎች እጅግ ያሳዝናሉ ። እኔ ለራሴ ያለሁት በተማሬ ቤት ስለሆን ዛሬ ለጊዜው ይህን ረድኤት ለመከፈል አልተቻለኝም ግን ትምህርቴ ተፈጽሞ ለሃገሬ በበቃሁ ጊዜ በችሎታዬና በማገኘው እውቀት ሁሉ ለመርዳትና ለተማሬ ቤቱ የሚያስፈልገውን በበኩሌ የሚቻለኘን ለመሥራት ዋና ምኞቴ ነው ቢቻለኝ ተገንዘቤ ባይቻለኝ ከጉልበቴ ባመት ባመት ለመገበር ሙሉ ፈቃዴና ምኞቴ መሆኑን አስታውቃለሁ በተማሬ ቤት ያሉ ልጆች ሁሉ ይህን የማይመኝ ይገኝ አይመስለኝም ።

መልአኩ አማኑኤል በያን አሜሪካ ።

ለሰው ኑሮ መሠረት ።

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ። ሕዝባቸው የልቡን ሀሳብ ለመግለጽ ነጻነትን እንዲያገኝ በደግነታቸው አስበው የጽሕፈት መኪና (ማተሚያ ቤት) የብርሃንና ሰላም ጋዜታ ስላወጡ ዝናቸው በዓለም ሁሉ አብርቷል ።

ለልዑል ጌታችን ከነልጆቻቸውና ከነቤተ ሰባቸው ብዙኅ እድሜና ጤና እንዲሰጣቸው ሁሉ የሚቻለውን አምላክ እለምናለሁ ። ዳሩ ግን የልቤን ሀሳብ አልኩ እንጂ ። የልዑልማ ምስጋናቸው ስንኳንስ በዚህች በኔይቱ እውቀትና በሙሉ ኢትዮጵያ እውቀት ሊከናወን አይቻልም ። ማለት እንደሥራቸው መጠን የልዕልና ምስጋናቸው ብዙህ ነውና ።

እንግዴህ መንግሥቴንና አምላኬን አመስግኜ የሚቀጥሉትን ቃሎች ልጽፍ ደፈርኩ ።

መጀመሪያ እግዚአብሔር ለሰው ክፉና በጎን ለይቶ የሚያውቅ ሁለት ግዕዛን ሰጥቶ በዚህ ዓለም በወደደው ሊኖር ኋላም እንደሥራው መጠን ዋጋውን ወይም ፍዳውን እንዲቀበል የተመሠረተ ሕግ ማድረጉን ሰው ሁሉ አይስተውም ። ይህም ክፉንና በጎን መለየት ከተፈጥሮው ሕሊና ከትምሕርትና ከማስተዋል መገኘቱ አያጠራጥርም ።

ሁለተኛ ሕግን ሰርቶ ለሰው ልጆች ሰጠ ሕግም ልጆቿን አክብረቻቸው የሚፈልጓትንም በረድኤት ተቀበላቸዋለች ። እሷንም የወደደ ሕይወቱን ወደደ ። ወደሷም የሚገሰግሥ ደስታን ይጠግባል ፡ አጽንቶም የያዛት ክብርን ይወርሳል ። ሲራክ ፲፩ ፲፬ ። እንግዴህ እንመልከት እናስተውልም ሰው እንጂ በዓለም ላይ ደስታና ክብር የሚያገኘው በሥራውና ሕግን በመጠበቁ ነው ። ጥፋትና ኃዘን ግን የሚያገኘው በስንፍናውና ሕግን በመተላለፉ ነው ። ሕግ መተላለፍ ምንድነው ቢባል የያዙትን ሥራ አለማቃናትና አለመፈጸም ነው ። እኛ ግን ሥራችንን ሥንሠራ ከሰው ባገኘነው እውቀት እንራቀቅ በተቸገርንም ጊዜ የመኰንን እገሌና የወይዘሮ እገሊት ልጅ አረስን ቆፈርን ብለን አንታበይ (እነሱስ ሥራቸውን ሰርተው ከችግር ድነው ሄደዋል) ለኛ ለጊዜው የሚያስፈልገንን መሥራት ነው እንጂ ። እንዲህስ እያልን ለመቀላወጥ መንደር ለመንደር ከምንዞርና ከምንመካ ትእቢተኞች ፡ ተዋርዶ የሚያርስና የሚቆፍር ደሀ ይበልጠናል ሲራክ ፳፩ ፳፪ ። ሥራንም ለመሥራት በፈለገን ጊዜ እጃችን ለመሥራት የሚቻለውን ነው እንጂ የማይቻለንንና የማንፈጽመውን ሥራ መጀመር አቅሙን አያውቅ ያሰኛል ። እንዲህም ማለቱ ሲያርሱ ዓይተን እንረስ ። ሲነግዱ ዓይተን እንነግድ ፡ ሲጽፉ ዓይተን እንጻፍ ማለት አይደለም ። አንዱን የምንችለውን ይዘን ያለንበትን ሥራ እያበረታታንና እያሰፋን መሄድ ነው ። ከዚህ የበለጠ መልካም ሥራ ያለ አይመስለኝም ።

ሶስተኛ ፡ እግዚአብሔር በከሃሊነቱ ለሰው ልጆች ዕውቀትን አብዝቶ ሰጥቶ ክፉና በጎ እንድናውቅ አደረገን ጌትነቱንና መፈራቱን ገናንነቱንም ይገልጽ ዘንድ ፍርሃትን አሳደረብን ። ነገር ግን ክፉ ሰው ክፉ ሥራ ሠርቶ ጋኔን አሳተኝ ቢል እራሱን መስደቡ ነው ፡ ሊሰርቅና ሊቀማ ሲሄድ እክሀደከ ሰይጣን አቡነ ዘበሰማያት ማለት የሰማይ አባቴ ጋኔን ነው ማለት ነው ። ሲራክ ፳፩ ፳፯ ሰነፍ ሰው በተቀመጠበት እንደ ዋሻ ድንጊያ ነው የዋሻ ድንጊያ አይናወጥም ሰነፍም ሰው ከመኝታዬ ተነሥቼ ሥራ ልሥራ አይልም ጉስቁላም በሆነ ሥንፍናው ሁሉን ያሰኑፋል ፡ ይህነንም ሥራ አልሠራም ብሎ ሲሰርቅ የገደለው ሰው እጁን ከትቢያ አራግፎ ንጹሕ እንደሚሆን ንጹሕ ነው ። እንዲህ ነውና ሥራ ለማይሠራ ለትዕቢተኛ ሰው እናልቅስለት ፡ ከሞት ይልቅ ሕይወት ከፍቶበታልና እንዲህ እንዳንሆን በምንሠራው ሥራ ሁሉ ብልሆችና ትጉሖች እንሁን በተሾምንበትም እራሳችንን አናስነቅፍ ። ወንድ ልጅ በተሾመበት ሴት ልጅ በተዳረችበት እንዲሉ ፡ የያዝነውንም ሥራ ትንሽ ነው ብለን መናቅ አይገባንም አንዱን ደረጃ ሳይረግጡ ሁለተኛውን ደረጃ ለመድረስ አይቻልምና ያለንበትን ሥራ እናጽና ፡ ሥራ መፍታትም ብዙ ስንፍናንና የልብንም ክዳት ታስተምራለች ።

አራተኛ፡ ማንንም ሰው በሥራ ረገድ ለመስደብ አይገባም ከሥራ ፈቶች በቀር። ሥራ ፈቶች ግን በሰውም በእግዚአብሔርም ዘንድ የተሰደቡ ናቸው ፡ ጳውሎስ እንዳለ ማንም ሰው ከናንተ መካከል ሥራ የማይሠራ ቢኖር እንጀራ አይብላ፡ እኛም ሰምተናል ከናንተ ሰዎች እንዳሉ ያለ ሥርዓት የሚሄዱ አንዳችም አያደርጉም ከዞረት በቀር እኛም እንደዚህ ያሉትን እናዝቸዋለን በጌታም በየሱስ ክርስቶስ እንለምናቸዋለን በቀጥታ ይሠሩ ዘንድ እንጀራቸውንም ይበሉ ዘንድ ፩ተሰ ፫ ፲—፲፫ ተመልከት ፡ ሥራ ፈት ሰው ለመሥራት እጁ ሲቻላት ክርቶ በከንቱ ውዳሴ በልመና ወይም በሥርቆት ገንዘብ ለማግኘት የሚሻ ሰው ጕስቋላ ነው ስንት ሰዎች ይመስሏችኋል ሥራን በመጸየፍ ክፉ መጥፎ ወሬ የሚወራባቸውና ታላቅ ውርደት የሚያገኛቸው ? ዳሩ ግን የሠራተኞችን ክብርና ምስጋና በሙሉው በጋዜጥ ለመጻፍ አንባቢ ይሰለቸኛልና ለመረዳት የሚፈልግ ሲራክ ም ፴፫ እስከ ፴፱ ይመልከት።ደግሞም ክቡር ብላታ ኅሩይ ላባት መታሰቢያ ለልጅ ምክር ብለው በጻፉት መጽሐፍ በ፫ኛ ክፍል ፲፰ ገጽ ተመልከት እኛም በሥራችን ላይ በፍጹም ልባችን ተግተን መንግሥታችንን በተቻለን መርዳትና ማገልገል ነው እንጂ ንጉሥ እኔን አያውቁኝ ለምን እለፋለሁ ብሎ በሥራ መለገም ታላቅ ስሕተት ነው ። ሰው ከንጉሥ የሚተዋወቀውና የሚከብረው በሥራውና በትጋቱ ነው እንጂ ። እንግዲያው ንጉሥ የገሌ ልጅ እገሌ የትነው ብሎ ከቤቱ ፈልጎ ለማወቅ ግድ የለበትም ። ይልቁንም የያዙትን ሥራ እያሰፉና ወደፊት እየገፉ ከሥፍራው መድረስ ነው እንጂ።የራስን ሥራ አስንፎ ሰው ያሰፋውንና ያሳመረውን ለመፈለግ መመቅኘትና መሸቀዳደም ታላቅ ኃጢአት ነው ።ይኸውም ኃጢአት (ኩራት) የቆጡን ፈላጊ የብብቱን ጣለ እንደሚሉ ሁሉ ። ሁሉንም አጥቶ ነቆ የነበረውን ሥራ እስከ መመኘት ያደርሳል ።

አምስተኛ፡እኛ የኢትዮጵያ ልጆች አንድነትና ፍቅር ስለሌለን አንድ ምሳሌ አለ፡ አንድ ሰው አራት ወንዶች ልጆች ነበሩት እነዚህ ልጆች ግን ዘወትር ወንድም ከወንድሙ ባለመስማማት አስቸገሩት ደግ አባት የነዚህን ልጆች ክፉ ልማድ ለማስተው በምሳሌ ይመክራቸው ጀመር እንደዚህ እያለ ልጆቼ ሆይ እነዚህን ባንድነት ያሰርኋቸውን ፬ብትሮች ከናንት አንዳችሁ ለሰበረው ልጅ እሸልመዋለሁና በሉ ስበሩ አላቸው እነኛም በየራሳቸው ለመስበር ሞከሩ ዳሩ ግን ለመስበር አልቻሉም አባታቸው ግን አንዳንዱን በትር እየፈታ አራቱንም ለየብቻ ሰበረው ልጆቹም እንዲህ አሉ እንደዚህማ ለየብቻው ከሆነ እኛም እንሰብር ነበር አሉት አባታቸውም ምሳሌውን ይኸው አያችሁ እናንተም እርስ በርሳችሁ ተስማምታችሁ ባንድነት ብትሆኑ ፬ቱ ባንድነት ታስረው ለመስበር እንዳልተቻሉ እናንተም ኃይል ታገኛላችሁ የሚያጠቃችሁ የለም አለበለዚያ ግን ለየብቻችሁ በጠላታችሁ እጅ ትወድቃላችሁ ብሎ መከራቸው ይባላል።ጳውሎስም እንዲህ ብሏል የትእዛዝ ፍጻሜ ግን ፍቅርና አንድነት ናት ከንጹሕ ልብ ከመልካም ሕሊና ግብዝ ከሌለበትም ሃይማኖት ፩ ጢሞ ፩ ፭ ። እኛም በሥራችን ትጉሆች ሆነን ፍቅርን ለብሰን አንድነትን ብንደርብ በክብር ላይ ክብር በጥበብ ላይ ጥበብ እንዲጨመርልን ጥርጥር የለበትም ።

ሰው በዚህ ዓለም ጥፋቱ የሚፈረድበት በፍትሐ ነገሥት በወዲያኛው ዓለም በወንጌል ስለሆነ ለሰው ይህን ሁለቱን መጽሐፍ ማንበብና መገንዘብ የሚገባው ነው ወንጌሉን ግን ልዑል በብዙ ችሮታዎ ስላሳተሙልን በማተሚያ ቤትዎ በርካሽ ዋጋ ይገኛል ፍትሐ ነገሥት ግን ከቤተ መንግሥት በስተቀር በሌላ ሥፍራ አይገኝምና ለማንበብ ችግር ነው ስለዚህ በሙሉው እንኳ ባይቻል ለኛ ለኢትዮጵያ ልጆች አሁን ለጊዜው የሚያስፈልገንን ሊቃውንቶች መርምረው ከየአንቀጹ አውጥተው ባጭር ባጭሩ ታትሞ ሕዝቡ እሱን እያነበበ የሚመጣበትን ፍርድ እንዲገነዘበውና ከጭከኔ ወደርኅራኄ።ከድንቍርና ወደ እውቀት እንዲመልሰው መሪ የሚሆነው የመሰለኝን ለብዙኀ ችሮታዎና ወሰን ለሌለው ልዕልናዎ አስታውሳለሁ ። ይህንንም ማለቴ የልዑልን ጥልቅ የሆነ የረቀቀ ሀሳብዎን መርምሬ በልቡናዎ አለመኖሩን አውቄ የጻፍሁ አይደለሁም የመሰለኝንና በልቤ ያለውን ስለመግለጽ ነውና ልዑል በከሃሊነትዎ ይታገሡኝ ስል በምድር ወድቄ እለምናለሁ ።

እኔም ለዚችው አላፊ ለምትሆን ኑሮዬ ጥበብን አብዝቼ ሳልማራት መገኛዋ ጊዜ ተላልፎብኝ በድንቍርና መኖሬ ብዙሀ ይጸጽተኛል ወደፊት የሚነሱ የሀገሬ ልጆች ግን በድንቍርና መኖራቸውን አልወድም ያቅሙን ከወረወረ ፈሪ ያለውን ከሰጠ ንፉግ አይባልም እንደሚሉት ሁሉ እኔም እንዳቅሜ በኢትዮጵያ አዲስ ለሚቆመው ተማሪ ቤት ማህበር መግቢያ ፯ብር ወደፊት ባመት ባመቱ ፫ ሶስት ብር እሰጣለሁ ።

አንባቢዎች ሆይ ከዚህ በላይ የተናገርኩትን ለመጻፍ አጋጋርና መሪ ሆኖ ያደፋፈረኝ ከልዑል ማተሚያ ቤቶች የገዘኋቸውን መጻሕፍትና ብርሃንና ሰላም ከማንበብ የተነሣ ጭላንጭል ስለታየኝ ነው እንጂ እውቀቱ ከሰው በልጦ አይደለምና የተሳሳተ ነገር ቢገኝ ነቀፌታ እንዳታደርጉብኝ በትሕትና እለምናችኋለሁ ።

በሰውነታችን ይደርብን ትጋት ።
ቸልተኝነትን አርቀን እንጣላት ።
ፍቅርና አንድነትን ፈጥነን እንመሥርታት ።
በስንፍና እንጂ ነው የሚመጣ ጠላት ።
ሰርተህ ብላ ብሎ አዳምን አዘታል ።
ይሕን ሕግ የሚያፈርስ ይፈረድበታል ።
ለሥራ ብንተጋ ምን ክልከይ አለብን ።
ተፈሪን ሰጥቶናል አሰልጣኝ ዓለምን ።
ስንፍና እንዳይገባ ኢትዮጵያ በርቱ ።
ብርሃንና ሰላም ሆንዋል ለፍጥረቱ ።
እግዚአብሔር ይመስገን ዕድሜ ለዘውዲቱ ።
ዝናው በቅርብ ነው ሮምና ሶርያ ።
መሰረት እንጂ ናት ጥንት ኢትዮጵያ ።

ተስፋዬ ካሣ ።

የከተማ ወሬ ።

በኅዳር ፯ ቀን ዕሁድ በቤተ መንግሥቱ ታላቅ ግብር ሆኖ ልዑል አልጋ ወራሽ ተቀምጠው አበሉ ።

በስምንት ሰዓት ልዑል አልጋ ወራሽ ለመናፈስ ወደ ጉለሌ አዲስ የመጡ መትረየሶች ለመሞከር ሔደው ነበረ ።

አብረውም የነበሩ መኳንንቶች ።

ክቡር ራስ ስዩም ።
ክቡር ራስ ናደው ።
ደጃዝማች ጌታቸው ።
ቀኛዝማች ዓምዴ ።
ደጃዝማች ወልደ ሥላሴ ።
ፊታውራሪ ደስታ ዳምጠው ።

ሌሎችም ብዙ መኳንንቶች ነበሩ ። የሄዱትም በአውቶሞቢል ነበረና ልዑልን የተከተሉ አውቶሞቢሎች ሁለቱ ከፊት አምስቱ ከኋላ ። ባንድነት ስምንት ነበሩና በከተማው ውስጥ አጅግ አምረው በፀጥታ ይሄዱ ነበረ ።

በከብት የሚያጅብ ሰው የለም ነበረና በምን ምክንያት እንደቀረ ብንጠይቅ ለመንገደኛ ሁከት እንዳይሆን ተከልክሎ መቅረቱን ሰማን ። እዚያም በደረሱ ጊዜ አላማው ተተከለና በሁለት ልዩ ልዩ በሆኑ መትረየሶች ሁለት ጊዜ አላማዎቹን ጣሏቸው ። ደጃዝማች ጌታቸውም በመትረየስ ሞክረው ነበረ አላጋጠማቸውም ፤ ባላምባራስ አበበ ረዴ በጠበንጃ አላማውን ጥሎ እጅግ ደስ አሰኘ ። በመፍጠንም በመብለጥም ደስ ያሰኘውን መናገራችን ነው እንጂ ሌሎችም እንደዚሁ አላማውን የጣሉ አሉ ፤ ከዚያም በኋላ በደስታ ተመልሰው ከልዑል ግቢ ደስታ ሆኖ አመሸ ።

ለሥራ ስለ መትጋት ።

በዚህ ሰሞንም የዲስ አበባ መኳንንቶች ጭፍሮቻቸውን እየያዙ መንገዱን ለማደስ በሊጋባ ተከፍሎ ይዘዋል ልዑል አልጋ ወራሽም ሥራውን ያሣመረና ያፈጠነ ለማየት ሠራተኞቹንም ለማትጋት ወዲያና ወዲህ እያሉ የሥራውን አኳኋን ይመለከታሉ ። ስራውም በሁለት ቀን እጅግ ደስ የሚያሰኝ ሆኖ ተሰርቷል የከተማው መንገድ እንዲህ ከተጉበት የበለጠ ሆኖ እንዲያምርና እንዲከናወን ጥርጥር የለውም ። እውነትም መኳንንቱና ሠራዊቱ ከተጉበት ከከተማው ጀምሮ በየመዓዘኑ ወደ ዳር አገር የሚወስደው መንገድ ሁሉ በየጊዜው በያውራጃቸው ያለውን ቢያሠሩ ደኅና መንገድ በማጣት በዝቶ የነበረ መሰናከልና አደጋ ቀርቶ ለመንገደኛና ለነጋዴ ለሠራዊትም ጉዞ የተመቸና የማያሰጋ መንገድ በተገኘ ነበር በያውራጃው ደኅና መንገድ ከተበጀ መንደር ይለማና አገር ይሰፋና ለያውራጃው አገረ ገዥ ነጋዴውን ለመጠበቅ ይመቸዋል ነጋዴውም በመንገዱ ሁሉ በከተማ ውስጥ እንደሚጓዝ ይመስለው ነበር ።

ይህንን መንግሥታችን እንደሚያስበውና እንደሚወደው ዕርግጥ ነው ። መኳንንቱና ወታደሩም የገዛ ራሱንና የገዛ ሀገሩን ጥቅም ወዶ በደስታ እንዲያደርገው ሙሉ እምነት አለን

ነዋሪ መታሰቢያ እናቁም ።

ሀገራችን ክብርት ኢትዮጵያ ቀደምትነቷን ይዛ አባቶቻችንን እስከዚህ ዘመን ድረስ በነጻነት አኖረቻቸው አባቶቻችንም በዘመናቸውና በጊዜያቸው ለኢትዮጵያ ለዚያን ጊዜ የሚያስፈልጋትን ሥራ ባርበኝነትና በጀግንነት እየተጋደሉ ደማቸውን እያፈሰሱ ሲጠብቋት ኑረው ሀገራቸውን ለልጆቻቸው ስላቆዩ አባቶቻችንን እናመሰግናቸዋለን ያለፈውን ሥራ ሁሉ ላላፊው ዘመንና ላባቶቻችን ከምስጋናችን ጋራ ትተን ለሚመጣው ዘመንና ለልጆቻችን የሚያስፈልገውንና የሚስማማውን ሥራ ማሰብ አለብን ። አስበንም ብንመለከተው የሚመጣው ዘመን አነዋወርና አስተዳደር ካለፈው ዘመን ልዩ ስለሆነ በዕውቀታችን ላይ ዕውቀትን እስክንጨምር ድረስ ባንድነትና በመስማማት ሁነን የብርሃንና የሰላም መሪያችን ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ለኛና ለልጆቻችን ጥቅም የሚሆን ሥራ ሲመሠርቱ እያየን እኛም የሥራቸውን ፍለጋ በማድረግና በመፈጸም ለመከተል የተጋን ብንሆን ልጆቻችን ከልዑል ጋራ ያመሰግኑናል ፤ አሁንም ለጊዜው የሚያስፈልገን ዋና ሥራ በኢትዮጵያውያን ማኅበር ለምትቆመው የተማሪ ቤት እንደ አቅማችን አነሰ አደገ ሳንል መታሰቢያ የሚሆን የገንዘብ እርዳታችንን መስጠት ያስፈልገናል ፡ ኢትዮጵያን የሚወዱ የውጭ አገር ሰዎች ሲረዱ እያየን እኛ በኢትዮጵያ የምንወለድ ልጆች በመራዳት ችላ አንበል ለተመልካች ሰው ለዚች የተማሪ ቤት የሚረዳት እያነሰ በሄደ ጊዜ ልብ ያስደነግጣል የኢትዮጵያ ልጆች በገንዘብ ፍቅር እንዳልተነደፍን ታውቋል ብቻ ለጋስነታችንና ቢስነታችን ያላገባብ እንዳይሆን መጠንቀቅ ያስፈልገናል ባንድ ሰው ዕውቀትና ባንድ ሰው ጉልበት የሚገኘውን ገቢ ገንዘብ አሥር ወይም አሥራምስት ሥራ ፈት ሥራ ሳይሠራ ተቀምጦ እየበላ በወጭ ይጨርሰዋል ይኸም ልግሥና መታሰቢያ የሌለው ስለሆነ ያስጠነቅቃል ለሀገርና ለልጅ ጥቅም ለሚሆን ሥራ ሁሉ ገንዘብን መጨበጥ ከከንቱ ሀሣብ የሚፈልቅ ቢስነት ነው ።

ደግሞ ይህቺ የተማሪ ቤት በቆመች ጊዜ ክርስቲያንና እስላም ጋላና ሻንቅላ ሳትል የሁሉንም ልጅ የሰጧትን እየተቀበለች እንደ አባትና እንደ እናት እየመገበች በጥበብ የምታሳድግና የምታሰለጥን ናት ሥልጣኔም ነጻነትን ታስከትላለች ነጻነት ያለ ሥልጣኔ አትገኝም ያልሰለጠነ ሕዝብ በጨለማ ውሰጥ እንዳሉ ሰዎችና በውሀ ውስጥ እንዳሉ አሳዎች ይመስላል ። በጨለማ ውስጥ ያሉ ሰዎች መሄድ በፈለጉ ጊዜ የሚሄዱበትን መንገድ ስለማይታያቸው እርስ በርሳቸው ይጋጫሉ ወይም ከጉድጓድና ከገደል እንዳይገቡ አራዊትም ነጥቀው እንዳይወጧቸው በማሰብና በመሰቀቅ በልተው ጠጥተው ተመኝተው በቀር ሥራ ለመሥራት አይችሉም

በወሀ ውስጥ ያሉ ዓሣዎች ነጻነት የላቸውም ትንንሾቹን ዓሣዎች ትልልቆቹ ከነፍሳቸው ይውጧቸዋልና የዋጡትም ዓሣዎች ደግሞ ይዋጣሉ ። እንደዚሁ እርስ በርሳቸው ከመዋዋጥ በቀር ሌላ ሥራ የላቸውም ። የሰለጠነ ሕዝብ ግን በብርሃና በመሬት እንደሚኖሩ ፍጥረቶች ይመስላል በብርሃን ውስጥ ያሉ ሰዎች መንገድ በፈለጉ ጊዜ ይተላለፋሉ እንጂ እርስ በርሳቸው አይጋጩም በብርሃንና ከበሽተኛ በቀር የሚተኛ የለም ሁሉም ሥራውን በትጋት ይሰራል እንጂ ስለ አራዊትም በብርሃን የሚሰጋ የለም ።

በመሬትም የሚኖሩ ሰዎች ዕፀዋትና አዝርዕትን እያዩ በልምላሜና ባበባቸው ደስ ካላቸው በኋላ ደግሞ የድካማቸውን ዋጋ ፍሬዋን ይመገባሉ በመሬት ያሉ እንስሶችም ነጻነትና ሥርዓት ስለኖራቸው ወተትና ማርን እየሰሩ ለልጆቻቸው መግበው ለሰው ያተርፋሉ ። እንደዚሁም ነጻነት ያለው አነዋወር በብርሃንና በመሬት ከሆነ የተፈጠረበትን መሬት ኢትዮጵያን

በብርሃን እየሰራንና እየጠበቅን በልምላሜዋና ባበባዋ ደስ ክለን በኋላ የእውቀት ፍሬዋን እየተመገብን በሰላም እንድኖር እንትጋ ። ያለ ትምህርት መቅረት በሚመጣው ዘመን የሚደርስብንን ወቀሳና ኃፍረት ያሳስበናል ሌላም ወቃሽ የለን ከልጆቻችን ሌላ የማንም ልጆች ቢሆኑ አባቶቻችን በፈቃዳቸው ለኢትዮጵያና ለኛ ይኸንን መታሰቢያ የሚሆን ሥራ ሠሩላት ብለው ለመናገር ባይችሉ ትልቅ ሀፍረታቸው ነውና ከፈሩ በኋላ መውቀሳቸው አይቀርም እኛም ከወቀሳ እንድንድን አሁን በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ዘመንና በልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ጊዜ ብርሃንና ሰላም የሆነ ሰዓት ካለን ወተትና ማር የምታፈስ ሀገራችንን ባንድነትና በፍቅር ሁነን የሚያስፈልጋትንና የሚጠብቃትን በየጊዜው ለማሰብና ለመስራት የተሰናዳን እንድንሆን ለብርሃንና ሰላም ልጆች በትህትና አሳስባለሁ ።

ኃይለ ጊዮርጊስ ወልደ ሰማዕት ።

ከኤሮ ከሚባለው ጋዜታ ጥቅምት ባ፲፫ ባ፲፱፻፳፩ ከተጻፈ ቁጥር የተገኘ ቃል ።

(ኬር ምሥር ፲፫ ፲ ፳፩)

ያለፈው ክረምት ምሥርን ለማየት ከዓለም ሁሉ በመጡ ባ፲፯ ሺ. ቱሪስት አገር የሚዞሩ ይልቁንም ከአሜሪካን በመጡ ምክንያት የተነሳ ለባለ ሆቴሎቹ ሥራ እጅግ የተመቸ ያማረወራት ሆነ። የሚመጣውም ወራት የበለጠ ይሆናል ይባላል የምሥር የሆቴሉና የቱሪስት ማህበር ባለፈው ባ፲፰ ሐምሌ ሎንዶን ላይ ዌስትሚንስቴር ትስሞፒር በሚባለው ቦታ ጉባዔ አድርጐ የሚያስፈልገውንሁሉ አዘጋጅቷል በምሥር ሥራ ያላቸው ኩባንዮችም ወኪሎች የምድር ባቡር የመርከብ ኩባንያ የፋብሪካ ኩባንያ የቀሩትም እዚሁ ጉባዔ ተሰብስበው ነበር ።

ቱሪስቱ ሁሉ መምጫው አንድ ላይ እንዳይሆን ጊዜው እንዲራራቅ አድርጐ ጉባዔው ሳይሰበሰብ አስቀድሞ ነገሩን አዘጋጅቶታል፡የምሥር የሆቴልና የቱሪስት ማኅበር ስታቲስቲክና በየሆቴሉ በተያዘውእልፍኝ ብዛት አስቀድሞ እንደሚታየው ምሥርንለመጎብኘት ዘንድሮ የሚመጣ ቱሪስት ቊጥር ፳፫ሺ. ይሆናል

ከነዚህ ቱሪስቶች መካከል የሚበዙት ሜዲቴራኔን ለመዞር የሚመጡ አሜሪካኖች ስለሆኑ ከጥቂት ቀን በቀር አይቀመጡም ስለሆነም ከ፫ እስከ ፲ ቀን እንኳን ቢቀመጡ በማእከላዊ አድርጎ በ፯ቀን ብቻ ቢታሰብ አንዳንዱ ቱሪስት በቀን ፫፻፪ ቢያወጣ በምሥር መሬት ላይ እነዚህ ሰዎች ትተውት የሚሔዱት ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ፰ ሺ ፯፻ ይሆናል ።

ወደምሥር የሚመጡ ቱሪስቶች እያደር እንዲበዙ ለማድረግና የምሥርን የጥንት ዕቃ እየሩንና መሬቱን እንዲጎበኙ ለመሳብ ባሜሪካን በእንግሊዝ በቤልጋርክ በጀርመን በሆላንድ በፈረንሳዊ በቀረውም ባለን በቱሪስት ማኅበር መንገድ አያይዘ ብጋዜታም በኢሉስትራሲኦንም በቀረውም በሚታተም ነገር ሁሉ በቊርጥ ማስታወቅ ያስፈልጋል ።

የምሥር የቱሪስት ማህበር የክብር ፕሬዚዳን ግርማዊ ንጉሥ ፎአድ ታላቁን ጠባቂነታቸውን ብቻ አይደለም ይሆን ለምሥር የብልጽግና ምንጭ የሆነ ሥራ ለማስፋፋት በገንዘብም ወገንብለጋስነት እረዱ ።

ሆዋርድ ካርቴር የወረሰው ውብ የሆነ ፈርዖንን እስከ ጌጡ ያገኘው የሎርድ ካርናቦን ሥራ እጅግ የሚገርም ነው በያመቱ የሚመጡ የቱሪስትን አሳብ እየሳበ ይከፈላል ፤

ምሥር ላይ በቅርብ ቀን በሚጀመረው በዓለም ሁሉ በአል አሳብ እንደቅበላ ካርናባል ያበባ የፈረስ እሽቅድድም የኦቶሞቢል እሽቅድድም ይህን የመሰለ ሁሉ ይህም የሚሆነው በሪቤኤራ በኒል በካን በቀረውም ዳርቻ ስለሆነ ይህ እየጐተተው የቱሪስቱ ቊጥር በጣም ይበዛል እንዲህ ሲሆን ምሥር በክረምት ባባይ ዳርቻና በአፍሪካ በውብ ፀሐይ በታች ለመናፈስ ለሚመጡ ሰዎች የተደላደለች የቀጠሮ ቦታ ትሆናለች ።

ውቢቱን ኢትዮጵያን ለመጎብኘት የሚመጡ የአራዊቱን ብዛት ያደኑን መመቸት የጉዘውን ልዩነት የዱሩን ለምለምነት ያሽከሮቹን ታዛጋሪነት የሰማዩን ጥራት የነፋሱን መስማማት የሚያዩ ቱሪስት ምንኛ ያደንቁ ደስታቸውስ እንዴት ያለ የሚያወጡትስ ገንዘብ ምን ያህል ይበዛ ይሆን ። (ባኢኮሊች።)



ስለ ክቡር ነጋድራስ ዘውገ ሞት ።

ክቡር ነጋድራስ ዘውገ ኃይሉ አንኮበር ወረዳ የሐር አምባ ሰው ናቸው ወደ ፈረንሳዊ አገር ሄደው የፈረንሣዊ ቋንቋ ስለ ተማሩ አጼ ምኒልክ ባለሟል አድርገው አክብረው ያኖሯቸው ነበር ባ፲፰፻፹፰ ዓመት ተልከው ሄደው መልክታቸውን ፈጽመው በተመለሱ ጊዜ አጼ ምኒልክን ከአዲስ አበባ ወደአድዋ ሄደው ቢያገኙዋቸው ንጉሡ ወዳሉበት ገሥግሠው ሄደው ቀዳሜ ገብተው እሁድ ከጣሊያን ጋራ ጦርነት ሆነና በሰልፉ ውስጥ ሲዋጉ ውለዋል ከዚያም ሲመለሱ አጼ ምኒልክ አክብረው ሾሙዋቸው ። አሁን በቅርቡም ይሉባቡር ነጋድራስ ሁነው ይኖሩ ነበር ከዚያ በኋላ አልዩ አምባን እየገዙ አዲስ አበባ ላይ በድንገት በሽታ በተወለዱ በ፶፬ ዘመናቸው ፲፱፻፲፰ ዓም ኅዳር ፱ ቀን አረፉ በዚሁ ቀን ብዙ መኳንንትና ወይዛዝር ተሰብስበው በክብር ተቀበሩ ።

ለባለቤታቸውና ለልጆቻቸውም ለቤተ ዘመዳቸውም ሁሉ ብርሃንና ሰላም እግዚአብሔር ያጥናችሁ ይላል።

ፍታሕ ሊተ እግዚኦ ወተበቀል በቀልየ ።

አምላከ ምኒልክ ክርስቶስ ቤዛ ብዙኃን እምእደ ጸላኢ
ወፀር ሕዝበከ አድኅነነ ።
እስመ በስምከ ቅድመ ተወከልነ ።
ወተማኅፀነ በወልታከ ወፍቅር ጥበብ አግዓዚ ሰሐቦ ፍጡነ ።
ለኃያል ኃይለ ሥላሴ እስመ እንዘ በጽድቅ የሐውር ባሕረጠቢብን
ኢስእነ ። ወልድሰ ኃይለ ሥላሴ መድኃኒተ ሥጋ ከነነ ፤
ለውሉደ ዓለም ኢትዮጵያ በብዝኃ ጥበቡ እስመ ረድአነ ።
ወአስከለ ድንግል ንጽሕት ሰአሊ ለነ ።
ኃጢአተ ዓለም ዘይሠሪ አምላከ ምኒልክ ይመሐረነ ።

ገብረ እግዚአብሔር ።

ማስታወቂያ ።

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ላገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሊሆኑ ያሳተሙዋቸው በማተሚያ ቤታቸውም የሚሸጡ መጻሕፍት የሚከተሉ ናቸው

የቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ተግሣፅ ንባቡ ከንትርጓሜው	፲፪	ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከንትርጓሜው . . .	፲፪	ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከን ትርጓሜው . . .	፲	ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከንትርጓሜው . . .	፲	ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ ታሪክ (ደስታና ክብር።) . . .	፱	ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሲራክ ንባቡ ከንትርጓሜው	፯	ብር
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከንትርጓሜው . .	፫	ብር
መዝሙረ ዳዊት ጥራዙ እጅግ ያማረ ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪	ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከንትርጓሜው ። . . .	፪	ብር
ትምህርተ ኅቡዓትና ኪዳን ንባቡ ከንትርጓሜው	፪	ብር
የሕይወት ታሪክ	፪	ብር ተኩል
የቁጥር ትምሕርት	፩	ብር
ያማርኛ ሰዋስው	፩	ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር . . .	፩	ብር
የብዙ መኳንንቶች ሥዕል ያለበት ካርት ፳፬ቱ	፩	ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የአደን መንገዳቸው አኳኋን		አላድ
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ		አላድ
አጭር የዓለም ታሪክ		አላድ
ያማርኛ ፊደል		ሩብ
አሳብና ምኞት		ሩብ
ትምሕርተ ሕፃናት		ሩብ
የበገና ግጥም	፪	መ
ለኢትዮጵያ ልጆች ማመልከቻ ።	፪	መ
የምክር ቃል	፪	መ
የልብ አሳብ ግጥም	፩	መ
ብርሃንና ሰላም አንድ ቁጥር	፪	መ
የገቢና ወጭ ትልልቅ መዝገብ በየዓይነቱ አርእስቱና ሰንጠረዡ የተተከከለ በማለፊያ ወረቀት የታተመ ጠንካራ ጥራዝ ዋጋው . .	፳፭	ብር
ሰንጠረዡ እንደፈለጉት የሚሆን ባለመስመር ደብተር ጥራዙ እንደ ላይኛው ሆኖ	፳፭	ብር።

ማስታወቂያ ።

በርሻና በመስሪያ ሚኒስትር ሥራ ውስጥ መንግሥት ያወጣውን ደምብና ሕግ ሳልተላለፍ ደሀ ሳልበድል፤ የመንግሥቱን ገንዘብ በጥንቃቄ ሠርቼ ቀድሞም ከሚሠራው ሠራተኛ ገቢ ገንዘብ አብልጬ አገባለሁ የሚል ሰው እርሻና እመስሯ ምኒስቴር መጻፊያ ቤት፡ ሁል ጊዜ ከጧቱ ከ፫ ሰዓት እስከ ፬ ሰዓት ድረስ፤ እየመጣ ቢነጋገር በደስታ እንቀበለዋለን ደመወዙም እንደ ሥራው ገቢ እየታየ ይቈረጥለታል ጥቅምት ፲፩ ቀን ፲፱፻፲፰ ዓመተ ምሕረት ።

መኰንን ሀብተ ወልድ።

ማስታወቂያ

ለራሶችና ለደጃዝማቾች ለሴት ወይዘሮች የሚገባ በየይነቱ፡ ጥሩ ካባ ከኤሮፓ መጥቶልኛል ቤቴም (ባንክ አፍ አቢሲንያ) ከእንግሊዞች ባንክ አጠገብ ነውና ይህን ካባ መግዛት ለሚፈልጉ ሰዎች መጥተው እንዲገዙ አስታውቃለሁ ።

ኢያሱ ዳንኤል

አ ፔ ማርሲያኖ

በኢትዮጵያና በፈረንሳይ የቅኝ አገር ሶማሊ በተለየ ፈያት አውቶሞቢልና ትራክተር አስመጭና እንደራሴ ።



A.P. MARCIANO

Concessionnaire Exclusif pour l'Ethiopie
et la cote française des somalis
des automobiles et tracteurs Fiat.

በልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ

መጀመሪያ ዓመት ፤ ቁጥር ፵፰ ።
1re ANNÉE №. 48

ሐሙስ ህዳር ፲፯ ቀን ፣ ፲፱፻፲፰ ዓ ም።
JEUDI 26 NOVEMBRE 1925

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voi regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et paix "

አዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraissant tous les jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

የጋዜጣው ዲሬክተር ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።
Gabré Christo Takié Haymanot
Dirécteur

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል። በየሳምንቱ ሲገዛ ለፊስን በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ስለ ቅዱስ ሚካኤል በዓል አከባበር ።

ኅዳር ፲፪ ቀን ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ልዑል አልጋ ወራሽ በአቶሞቢል ሁነው በመኳንንቱና በሠራዊቱ ታጅበው ጧት ወደየካ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን በአንድ ሰዓት ደርሰው ከቤተ ክርስቲያኑ በገቡ ጊዜ ቅዳሴው ተጀመረ

ይህ ሁሉ ሲሆን ፊታውራሪ ገብረ ማርያምና ግራዝማች ከልክሌ ጭፍሮቻቸውን አሰልፈው ቀበና ከድልድዩ የልዕልት ወይዘሮ መነንን አመጣጥ ይጠባበቁ ነበር።ልዕልት ወይዘሮ መነን ባማረች አቶሞቢል ከተፍ ባሉ ጊዜ የሰላምታ ጥሩምባ ተነፋና ሠራዊቱ ልዕልት ወይዘሮ መነንን አጅበ ወደቤተ ክርስቲያኑ ገቡ

በቅዳሴውም ጊዜ ቄሱ ከፍ ባለ ዜማ ወንጌል ብሎ ወጣና ወአመ ይመጽእ ወልደ እጓለ እመ ሕያው በስብሐቲሁ ወኵሎሙ መላእክቲሁ የሚለውን አነበበ ።

ቅዳሴውም ከተፈጸመ በኋላ የደብሩ አለቃ ፡ አለቃ ገረመድኅ እንዲህ ብለው ተቀኙ ።

ክብር ይእቲ ።

ጸድቀት ትዕማር ገበ ወልድ በቅድመ ይሁዳ ኮናት ።
እስመ ውስተ ዕድ ተረክበ ቀኖተ ኃዊን ኅልቀት ።
ወማእነ ፍርሃት ሃደገ አርአያ ሙሴ ትሑት ።
እስመ ይከይዳ በእግር ለሐዊን ምድረ ምናሴ ቅድስት ።

ዕጣነ ሙገር ።

በጽንፈ ኤርትራ ሜጠሙ ለሕዝበ ፈርዖን ጽሙዕ ።
ሙሴ ጌዴዎን ምሁረ ጸብዕ ።
እስመ ኃይል ዘእግዚኡ ወበሕረ ኤርትራ በግዕ ።
በዘይቀርያ ኢይትመዐዕ ።
ወበዓለ ክህደት እምይበዕ መንግሥቶ ስቍረተ ኤርትራ መርፍዕ
ያኒይስ ይቤሎ ለሙሴ እግዚእ ።

አሠረ ንጉሥ ።

ድቀተ ፀሩ ይሬኢ ኃይለ ሥላሴ እምጣነ ብእሲ ብፁዕ ።
ወይቤ አኅልፉ ለዛቲ ምክረ ጠቢባን ጽዋዕ ።
ወታሥተፌሥሖ ለልበ ሰብእ ።
ወይን ምኒልክ ንግሥት በቃለ ኤልሳዕ ።
እስመ ደብተራሁ አንተ ተከላ ለስምዕ ።

ይህንን ቅኔ ከህናቱ ሲወርቡት ከወረቡ መድመቅ የተነሣ በዚያ የነበረ ሰው ከህኑ ይቅርና ጨዋው ሳይቀር አሸበሸበ ።

፬ት ሰዓት ሲሆን ታቦት ወጣና ቆመ፡ የዚያን ጊዜ ከህናቱ በልዑል አልጋ ወራሽና በመኳንንቱ ፊት ወረብ ወርበው ሲያስረግጡ አምረው ይታዩ ነበር ከዚያ በኋላ ዑደት ተደረገ። ከዑደቱም በኋላ ብፁዕ ዕጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ለሕዝቡ ቃለ እግዚአብሔር አሰምተው መክረው አሳርገው ባርከው አሰናበቱት ።

፭ት ሰዓት ሲሆን ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ልዑል አልጋ ወራሽ ከቤተ ክርስቲያን ወጥተው ባማረ አጀብ ወደ ቤተ መንግሥቱ ለመመለስ ተነሡ በየመንገዱ አያሌ የተቸገረ ድኻ አቤት ሲልም ልዑል አልጋ ወራሽ እያቀረቡ ሰምተው ነገሩን ያቀኑለት ነበር ። ፮ት ሰዓት ሲሆን ወደቤተ መንግሥቱ ገቡ የቅዱስ ሚካኤል በዓል አከባበር እንዲህ ሁኖ በደስታ ተፈጸመ ።

የኅዳር ሚካኤል ዕለት አንድ ትልም እርሻ ያለው ሰው እንኳ ቢሆን ጢስ የማያጤስ የለም ምክንያቱም ኅዳር ከታጠነ በኋላ በሽታ ይቀላል ይባላል ። ዕውነትም በቈላ አገር እንደ ቀስት የሚወረወር በሽታና መቅሠፍት ይበርዳል የታመመውም ሁሉ

ይድናል ። ይኸውም የጢስ ምክንያት ቀድሞ በአሮን ጊዜ በሽተኞቹንና ደኅነኞቹን እሱ በመካከል ሁኖ ባጠነላቸው ጊዜ ጢሱ በመካከል ተጋርዶ ደዌ አይተላለፍባቸውም ነበር ዘኍ ፲፯ ፵፩—፵፱ ።

ለጌዴዎንም መልአኩ ምልክት ነግሮት መሥዋዕት ቢሠዋና መልአኩ በዘንግ ሥጋውን ቢነካው ተቃጠለ መልአኩም በጢሱ ተሰወረ መሳ ፮ ፳፩ ዘካርያስም ዕጣኑን በሚያቀርብበት ጊዜ በጢሱ ምክንያት ጸሎትህ ከእግዚአብሔር ፊት ደረሰልህ ብሎ መልአክ ነገረው ሉቃ ፩ ፲፫ ።

ዮሐንስም በራእዩ ፰ ፬ ቍ ሰባተኛውን ቍልፍ በከፈተ ጊዜ መልአክ መጥቶ በመሠዊያው ፊት ቆመ ብዙ ዕጣን አቅርብልን ብለው ስጡት ከቅዱሳን ጸሎት ጋራ የዕጣኑ ጢስ ዓረገ ይላል

ይህን ሁሉ ምልክት ይዘው የቀድሞ አባቶች ያደረጉት ይመስላል ዘመን እየራቀ ትርጓሜ እየረቀቀ ነው እንጂ ልማድ ሁሉ አንዳንዱ ከመጻሕፍት ቃል አይርቅምና ይህ ከአበው ተያይዞ የመጣው ልማድ ከመጻሕፍት የተስማማ ይመስላል እንጂ እንዲያው ከንቱ ልማድ አይመስልም ።

ስለ ዕውቀት አስተዳደግ ።

ዓለም ሲፈጠር ሰው በመጀመሻ ዕራቁቱን ይሄድ ነበር ቆይቶም ቅጠል እየሰፋ ጭረት እየገመደ ለበሰ፡ኋላ ግን የጥጥ ብልሃት ታወቀና እየፈተለ መልበስ ተማረ ይላሉ ። መኖሪያውም ከየወንዙ ዳርና ከየዳገቱ ጕድጓድ እየማሰ እንደ ቀበሮ በጕድጓድ ውስጥ ሲያድር ነበር ። የጦር መሣሪያውም ወንጭፍና ቀስት ሁኖ ሲኖር በቀን ብዛትና ሐሳቡን በማዘውተር እያይነቱ የጨርቅና የሐር አይነት ካባ ላንቃ ደማስ እየሠራ ለበሰ ። ያጌጠና ያማረ አዳራሽና ቤተ መንግሥት አሥር አሥራ አምስት ፎቅ ያለበት የደንጊያ ቤት ለመሥራት በቃ፡እንዲሁም የወርቅና የብር የብረት የከሰል ምዕዳንን እያገኘ አዲስ አዲስ ዓይነት ብረት እየለዋወጠ ሊያዘወትር ጀመረ ። ዱሮ ብመት ተሠርቶ የማያልቀውን ሥራ ሁሉ በሰዓት ግማሽ የሚያደርስ ልውጥ ልውጥ መኪና አወጣ ። ካንዱ አገር ወዳንዱ በበቅሎና በፈረስ ለመሄድ ብዙ ቀን ሲያስፈልገው የነበረ ባቡርና አውቶሞቢል ሌላም ትንሽ መሄጃ አበጅቶ የወሩን ጎዳና በቅጽበት ደረሰበት ። ያንድ አገር ወሬ ወዳንድ አገር እስኪተላለፍ ብዙ ዓመት ያስፈልግ የነበረውን የስልክ ሽቦና ያለ ስልክ የሚሄድ ሳንፊል የተባለውን ስልክ አውጥቶ የዓለምን ወሬ በቅጽበት ለመስማት ደረሰ ። ከሁሉ በላይ ደግሞ የዕውቀት ተአምር ሁኖ በጣም የሚያስደንቅ እንደ አሞራ በሰማይ የሚበረውን አይሮፕላንና ዲሪገቢል አስቦ ማውጣቱ እጅግ ይገርማል ።

ይህ ሁሉ የሚገኘው ትምርትን ከማብዛት ዕውቀትን ከመመርመር ያዩትንና የተማሩትን ትምርት ከማዘውተር ነው እንጂ ፡ ዕውቀትና ብልሀት አብሮ አይፈጠርም ። ምሳ ፫ ፲፱ ።

ማስተዋልና ዕውቀት የተሰጠው የተመሰገነ ነው፡ምሳ ፫ ፲፫ ደንቆሮ ሳይሆን አዋቂ የሚሆን የለም፡አንዱ ካንዱ እየተበደረ ብዙ እስከ ማወቅ ይደርሳል። ዕውቀት ከብዙ ወርቅና ብር ትበልጣለች ምሳ ፰ ፲ ።

ተማሪ በመጀመሻ ፊደል በሁለተኛ ግዕዝ በሶስተኛ ንባብ ከዚያም እየቀጠለ ከፍ ወዳለው መዓርግ እንዲወጣ እንዲሁ በመጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ቀጥሎ የንጉሥን ሃሳብና የንጉሥን ደምብ ሁሉ ፈጽሞ አገርን ማፍቀር አንድነትንና መረዳዳትን አጥብቆ ማሰብ ያስፈልጋል ። ከዚያ በኋላ በጥቂት በጥቂቱ ሁሉንም ለማድረግ ይቻላል ። ብዙ ታሪክ ተራኪዎች እንደሚነግሩን ብዙ ፈላስፎች አንድ ሥራ አስበው ለማውጣት ጀምረው ሳይፈጽሙት እየቀሩ ሃሳባቸው በልጆቻቸው ይፈጸማል ይላሉ ። ማናቸውንም ሥራ በቶሎ ጨርሶ ለመሥራት የሚችል ሰው የለም ። ግን በቀን ብዛት ትንሽ ትንሽ ሲባል ከብዙ ይደረሳል ። ከቤት ላይ ወደ መሬት የምትንጠባጠበው ትንሽ ነጠብጣብ በቀን ብዛት ደንጊያ ትፈልጣለች ይባላል ። አሁን በዚች በኢትዮጵያ ባገራችን ባዲስ አበባ ውስጥ እግዚአብሔር ብቻ ለንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ንግሥታችንና ለልዑል አልጋ ወራሻችን ተፈሪ መኰንን እድሜያቸው ይርዘምልን እንጂ ሕዝቡ የዕውቀትን መንገድ ለመያዝ ራሱን እንደ አቅናና የንጋትን ነፋስ ተመስላ ዕውቀት በጆሮው እንደ ነፈሰችበትና እንዳደመጣት በጣም ያስረዳል ። የጠቢባን መላስ ዕውቀትን ያሳምራል የሰነፎች አፍ ግን ስንፍናን ያፈልቃል እንደ ሚለው ሰሎሞን፡እንዲሁ አልጋ ወራሻችን ልዑል ተፈሪ መኰንን እጅግ ብልህ ዕውቀት የመላባቸው ስለ ሆኑ ዛሬ በኅቸው ጊዜ የዕውቀትና የስልጣኔ ያገር ፍቅርና የመረዳዳት ጊዜ ከሚሆን በቀር የስንፍናን ወሬ የሚያወራ ልጅና አዋቂ አይገኝም ። ልዑል አልጋ ወራሻችን ተፈሪ መኰንን ስለ ሕዝባቸው ስልጣኔና ስላገራቸው አስበው ገንዘባቸውን እያወጡ ትምርትን የፈለገ የኢትዮጵያን ልጅ ሁሉ አውሮፓ እየሰደዱ በኪሳራቸው ያስተምራሉ ፡ ከዚህ ከሐሳባቸው ውስጥም ያማረና የተተከከለ ተማሪ ቤት አቆሙ ። ራብኝ ጠማኝ ታረዝኹ አገር አነሰኝ በቅሎ ፈረስ ጐደለኝ ብሎ ለለመናቸውም ሕዝብና መኳንንት የልቡን ሐሳብና ምኞት ሁሉ ይፈጽማሉ ። የከተማውን ጥዳት ለከተማ የሚገባውን ደምብ አቋቍም የመንገዱን ሥራ አጀማመር የዘበኛውን ሰልፍና ትምርት ይህን የመሰለ ከሁን በፊት ያልነበረውን ሁሉ እጅግ ደስ የሚያሰኝ አጀማመር ጀምረዋል ። ይህ ከተጀመረ ቅርብ ጊዜ ነው ፡ ስለዚህ ባንድና በሁለት ዓመት ይህን ያህል ሥራ ከተሠራ ለሚመጣው አሥርና አሥራ አምስት ዓመት እግዚአብሔር በእድሜ ያቆየው ። በዚህ በከተማችንና ባገራችን ውስጥ ብዙ ነገር ሊታይበት ነው ብለን ተስፋ እናደርጋለን ። ስለሆነ ግን ያልሰለጠነውን ሕዝብ አስተምሬ አሰለጥናለሁ ብሎ የሚነሣ ንጉሥ በመጀመሪያ ጊዜ ብዙ ልፋትና ድካም ያገኘዋል እንጂ ለጊዜው ምስጋና አያገኝም ። ይህም ከአውሮፓ መጻሕፍት ታሪክ ይገኛል ። ንጉሡ ለሕዝቡ ጥቅም ብሎ በመጀመሻ የሚያወጣው አዲስ ነገር ሁሉ ለጊዜው ሕዝቡ ደስ አይለውም ንጉሡ ለራሱ ጥቅም አግኝቶበት የሚደነባው ይመስለዋል እንጂ፡አገርን የሚያኰራና የሚያለማ ሆኖ ሐሳብ ያቆመው አይመስለውም ። ንጉሡ ግን ልፋቱና ድካሙ ላገሩ ነውና የሕዝቡን ክፋት እየተወ ሐሳቡ በጥቂት በጥቂት ይፈጸማል ሉቃ ፳፫ ፴፬ ። አገሩን ነጻ ካደረገ በኋላ ሕዝቡም እውቀት ያድርበትና የንጉሡ ሃሳብና ልፋት ለሕዝቡና ላገሩ እንደነበረ አስቦ ይወደውና ያመሰግነዋል የደጉ የንጉሣችን ልጅ እያለ እስተ ልጅ ልጅ እንዲያስብ ይሆናል ።

ለኔ እንደሚመስለኝ የንጉሥ ሃሳብ ሁሉ ለሕዝቡ ነው ። እውነትም የሚነግሠው ሕዝብን ለመጠበቅና ለመ ዠት ነው ክብሩና ኃይሉ ከገር ልማትና ከሕዝብ ብዛት ከሆነ ምንም ጨካኝ ንጉሥ እንኳ ቢነግሥ የሕዝቡን ጥቃትና ያገሩን ጕስቍልና የሚያስብና የሚወድ ያለ አይመስለኝም ። ትርፉ ሁሉ ከገሩና ከሕዝቡ ከሆነ እንዴት ያገሩን ጕስቍልናና የሕዝቡን ጥቃት አዘቅዝቆ ይመኛል ፤ ይህ ሃሳብና ምርማሬ ከንቱ ነው የሚነግሡው ከእግዚአብሔር ዘንድ ተመርጦ ሃሳቡና አካሄዱ ሁሉ በእግዚአብሔር እጅ ነው ስለዚህ ምንም ክፉ አገዛዝ የሚገዛ ንጉሥ እንኳ ቢኖር በጥፋቱ እግዚአብሔር ይገስጸው እንጂ ከንጉሥ ፈቃድ የሚወጣና በንጉሥ ላይ ክፉ የሚያስብ ሁሉ በዚህ ዓለም ብቻ አይደለም በእግዚአብሔርም ዘንድ የተጠላና የተረገመ ነው ። ምሳሌ ፰ ፲፭ ምሳሌ ፳፩ ፡ ፩ ። ሮሜ ፲፫ ፡ ፩ ።

ንጉሥ ማለት ስለኛ ሆኖ የሚያስብልንና የሚያስተዳድረን ጠላት ከውጭ እየመጣ እንዳያጠቃን የሚከላከልልን አገሬ ተጕዳ ብሎ አዝኖ የሚያድነን አባታችን ነው ። እኛ ሁላችን ለጊዜው ለምንበላውና ለምንለብሰው እናስባለን እንጂ በቤተ ዘመዶችንና በሃገራችን በርስታችን ለሚመጣብን አደጋ ሁሉ የሚያስብልን የሃሳባችን ሁሉ ተሸካሚ ንጉሣችን ነው ። ስለዚህ ሰው ሁሉ የንጉሡን ፈቃድ መፈጸምና አገሩን መውደድ ይገባዋል ። የኢትዮጵያ የሃገሬን ምቀኛ ያጥፉ አንድነትዋን ለማጥፋት በጨለማ ለሚያስብ ኃጢአቱ በብርሃን ይገለጥ ፤ መንግሥትዋን ያሰንብት እድሜያቸውን ያርዝም ስላገራቸው የሚያስቡትን ሁሉ ያስፈጽምልን ብዬ የግጥም ምስጋናዬን አቀርባለሁ ።

ከሸዋ እስከ ትግሬ ባዘቱ በልክ
ብጀት ትክክል የሌለው እንከክ ።
አደጨክን ስሕዝቡ መሐሪ እንደ አምላክ
ኢትዮጵያ ደክማ ስትብረከረክ ።
ደገፉት ተፈሪ ከስማደ ቢላክ ።
ኢትዮጵያ ታማ አደኑዋን ብትጨፍን
አክማት ተፈሪ የዓለሙ ብርሃን ።
ገለጠው እመሚን የተሠወረውን ።
ልትማር ጀመረች ስልጡን ልትሆን ።
ወዳጅዋም ደላለው ጠላቷም ሲያዝን
እድሜ ለተፈሪ ሁላችን እንበልን ።
ስላገሩ ልማት የሚያሳስበውን ።
እንድንወዳደር ከጐረቤታችን ።
እንድንበረታ ድኳም እንዳይገባን ።
ትልቁም ትንሹም አንድ ላይ ሁነን ።
ኢትዮጵያ አገሬ እንኳን ደስ አለሽ ።
የወሰንሽ ከልካይ ተፈሪ ጋሻሽ ።
ሕዝብሽን አደላዳይ ላንቺም ኩራትሽ ።
እጅሽ ላይ መድረሱ ዛሬ ታየልሽ ።
የሕዝቡ ሰብሳቢ አንድ ልጅ ወልደሽ
እግዚአብሔር ያኑረው ደባረክልሽ ።

ኢትዮጵያ ለም ናት ቁላና ደጋዋ።
አባይነው ጣናነው ትልቁ ምንጭዋ
ወርቅነው ብርነው ፈርጥነው ጭ ነጫዋ
ሙቀትነው ብርድነው ምቹነው ዓየርዋ
ማርና ቅቤነው ስንዴነው ፍሬዋ ።
ብልህ ነው ጎደለኛ ተፈሪ ልጅዋ ።
ኢትዮጵያ ጠባቂሽ እጅግ ብርቱ ነው
ወቅያኖስ ተሻግሮ እሚጕበኘው ።
ቀኑንም አይደክመው እረፍትም የለው
ሌቱንም አይተኛ እንቅልፍ አይወስደው
ልፋቱ ላንቺነው በጣም እወቂው ።
ኢትዮጵያ አገሬ አስውቀት ስትኖሪ ።
የእውቀት መንገድ አጥተሽ ስትደናበሪ ።
አይንሽን ታውረሽ ስትፈልጊ መሪ ።
በስተሸዋ ወጣ አዋጅሽን ነጋሪ ።
ከሆድሽ በቀለ መኰንን ተፈሪ ።
ዘውዲቱ ተፈሪ ሁለቱ ሁነው ።
ፍቅር አስተማሩ ድፍን ሃበሻው ።
አገሩንም ለማ ብርታት አደረው ።
ጠላትሽም ጠፋ አጣ መድረሻው ።
ምቀኛም በረረ ገባ እየዋሸው ።

ፊታውራሪ ቢራራ ።

በብርሃንከ ንርአይ ብርሃነ ።

ክብርት ኢትዮጵያ ለምለምዋ ሀገራችን ሆይ ደስ ይበልሽ ታላቅም ደስታ ይገባሻል ትሑታን ልጆችሽም የዕውቀት ፍሬ ሊያፈሩ አብበዋል ። አበባቸውም ለዘለዓለም የማትረግፍ ናትና ከሁንም ቀደም ያልተለመደና ያልተወሰነ የሥልጣኔ ሕግጋት አሁን በጾጉ ዘመን በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ በልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ብብዙኅ ሞገሳቸውና በእግዚአብሔር ፈቃድ ሞላው ሕግጋት ባይፈጸም አንድ አንድ የሥልጣኔ ሕግጋት ስለተፈጸመልን እኛ የኢትዮጵያ ልጆች ለመልካሞቹ ጠባቂዎቻችን ለዕውቀት መኾችን ሀብትና ዕድሜ ይስጥልን ስንል ቸሩ አምላክን እንለምን ። እንደዚህም ሁሉ የክብርት ኢትዮጵያ መንግሥት ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሬ መኰንን ባዘጋጁት ትምሕርት ቤት ክቡራን የክብርት ኢትዮጵያ ልጆች ተምራችሁ ታላቅም ጥበብ አውቃችሁ ሀገራችንን ክብርት ኢትዮጵያን እንድትጠብቋት በመከከላችሁ በጠራ መንገድ ያለውን እንቅፋት የሚሆን ደንጋይ እንዳለ ከናንተ ውስጥ አርቃችሁ ጣሉት ከዚህም ወዲያ በተጠረገ መንገድ እንደልባችሁ ጥበብን ብልሃትን ልዩ ልዩ ሥራን እየሄዳችሁ ታገኛላችሁ ።

ለዚህም አዲስ ማኅበር ለተጀመረው ትምሕርት ቤት ስለ ድኅነቱ ብዛት እያዘንሁ ባለኝ አቅሜ አንድ ብር እረዳለሁ ስል ፌርማየን ሰጥቻለሁ ። ክቡራን የክብርት ኢትዮጵያ ልጆች ወንድሞቼ ሆይ በትንሽም በትልቅም ቢሆን ባለን አቅማችን እንድንረዳዳ እግዚአብሔር መልካም ልብ ይስጠን አሜን ።

ነገር ግን እኔ እንደራሴ ኃሣብ ካለፈው ዘመን አሁን ያለንበት ዘመን ይሻል ይመስለኛል ። እንደምን ማለት የዱሮ ኃሣብና የዛሬው ኃሣብ ልዩ ልዩ እንደሆነ እናስብ ። አንድ አንድ የጥንት ሽማግሌዎች የጥንት ኃሳባቸውን ሲጫወቱ በሰማሁ ጊዜ ገና ያምስት ዓመት ወይንም የሰባት ዓመት ልጅ ሲሆን የሚመኘው ምኞት ጠር መሰልንና ሰይፍና ኃኔ ለመታጠቅ ዘሆን አደንን ፋኖ መዝመትን ቧልታ ጨዋታን ይኸንንም የመሰለ ምኞት ይመኛል ፤ ግን የዛሬ ዘመን ልጆች በሁለትና በሰስት ዓመቱ እናትና አባቱን አውቆ አባባ እማማ እንዲል በዕድን ለይቶ እንዲያውቅ ኃሣባቸው ፊደል መቁጠር ከዚህም ከፍ ሲሉ ሀገራችንን ተምረን አንድ አንድ ጥበብ ሠርተንላት ለኛም ተጠቅመን ሀገራችንም ክብርት ኢትዮጵያ ከሁሉ በላይ ሆናልን ከጠረፍ እስከዚህ አለምናምን መሣኛ እንድንመላለስ በሀገራችንም በክብርት ኢትዮጵያ ላይ የጦርነት ሥራ እንዲቀር በአንድ ንጉሥና በአንድ ልብ ሆነን እንድንገዛ እያሉ ያስባሉ ብለው የጥንት ሽማግሌዎች ሲጫወቱ እየሰማሁ ያሁኑ ዘመን ይሻል የመሰለኝ ስለዚህ ነው ። እውነትም አሁን በሀገራችን የተያዘው ጥበብ ማስፋት ክብርት ኢትዮጵያን ለማኵራት ነውና የጀመርነውን ኃሣብ እግዚአብሔር ይፈጽምልን አሜን ። በትንሽ ዕውቀቴ አመለክታለሁ ።

ሥዩም ወልደ ገብርኤል ።

ይድረስ ክብርሃንና ሰላም ጋዜጣ ዲረክተር ።

የከበረ ሰላምታዬን አቅርቤ ከዚህ በታች የጻፍኳቸውን ቃሎች በብርሃንና ሰላም ጋዜጣ እንዲያትሙልኝ በጥልቅ ክብረት እለምናለሁ ።

እንደ ፈረንጆች ቁጥር በጥቅምት ባሥራ ሰባት ቀን አንድ ሞከተም የሚባል ጋዜጣ በዓረብ ቋንቋ በምስር ከተማ የሚ

ታተም የከበረች ያገራችን የኢትዮጵያ ወሬ እያመሰገነ ይናገር ነበር ። የሚናገረውንም ቃል በሰማሁ ጊዜ እጅግ አጥብቆ ደስ አለኝ፤ ቃሉም እንዲህ ነው፤ ዘንድሮ የመስቀል ለት የወታደሩንና የሰልፉን ማማር አይቶ መጀመሪያ ጊዜ ነው በኢትዮጵያ እንዲህ ያለ ትንግርት ነገር የተደረገ ይል ነበር፡ደግሞም ኢትዮጵያ ከዚህ ሁሉ መድረሷ በልዑል አልጋ ወራሽ ትጋት ነው እያለ ያመሰግን ነበር፤ እንዳሁኑ እያያዘ ልዑል አልጋ ወራሽ ቢተጉበት ሕዝቡም ቢረዳቸው ኢትዮጵያ ከሁለትና ከሶስት ዓመት በኋላ እንደ አውሮፓ ሳትሆን አትቀርም አለ ። ቀጥሎ የአዲስ አበባ መንገድ መበጀቱንና ማማሩን የአውቶሞቢሉን ብዛት ተናገረ ። በአዲስ አበባ አምሳ የሚሆን አውቶሞቢል አለ ይላል ከአንድ ዓመትና ከሁለት ዓመት በኋላ ግን አውቶሞቢሉም እየበዛ መንገዱም እያማረ ሁሉም እየተሰናዳ ይሄዳል፤ ልዑል አልጋ ወራሽ ከሰነበቱ እንደ አውሮፓ ሳያደርጉት አይቀሩም እያለ ሲመኝ እኔም የሐገሬን ብርሃን እሳየኝ እያልኩ ወደ እግዚአብሔር እለምን ነበር ። ሶስተኛ በዲስ አበባ ትልቅ ሆፒታል ተሰርቷል፤ ይኸውም በተፈሪ መኰንን ስም ተጠርቷል ይላል፤ ይኸ ሁሉ የተደረገ በልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ጊዜ ነው ብሎ ምስጋናውን ጨረሰ ። ይህነን በሰማሁ በሶስተኛው ቀን እንደ ፈረንጆች ቁጥር በጥቅምት በሐያ ቀን ። አንድ ምስር በሚባል ጋዜጣ በዓረብ ቋንቋ በምስር ከተማ የሚታተም ክፉ የሚያሳዝን ወሬ አወራ በልዑል አልጋ ወራሽ ላይ ክፉ የመከሩ ሰዎች ተይዘው ለሞት ተፈርዶባቸው የሚል ቃል ተጽፎ አገኘሁ፤ ይህነን በሰማሁ ጊዜ ደስታዬ ወደ ኃዘን ተለወጠ። ይኸውላችሁ አንዳንድ ክፉ ሰዎች ያገራችንን ስም ያጠፉሉ፤ ቡዳ በወዳጁ ይጀምራል እንደሚሉት በልዑል አልጋ ወራሾችን በተወደዱ አምሳያ በሌላቸው ጌታችን ላይ ክፉ ምክር መምከራቸው ሕንት የሚያሳፍር፤ ምንኛ የሚያስንቅ፤ ከቶ ስንት የሚያስጠይፍ ለሰሚውስ ግራ የሆነ ነገር ተሠራ እግዚአብሔር አንድ ብርሃን ለኢትዮጵያ ቢፈጥርላት ያነኑ አንዱን መብራት አጥፍተን በጨለማ እንኑር ብለው የሚያስቡ እንዴት ያሉ እብዶች አእምሮ የሌላቸው ናቸው ። እነዚህ ሰዎች አንድ ብርሃን ያጠፉ መስሏቸው ይሆናል ። ነገር ግን የሙሉ ኢትዮጵያን ዓይን ሊያጠፉ እንደተነሱ ያ ደንቆሮው ልቡናቸው አላሰበውም ኑሯል የሕዝበ ኢትዮጵያ አምላክ እግዚአብሔር ግን በመከሩት ምክር በጠመዱት ወጥመድ እነሱን ጣላቸው ። ይኸን ሁሉ መናገሬ ፈራጅ ሁኜ አይደለም ።

ብቻ የኢትዮጵያ ሕዝብ የተባለ ሁሉ በየልቡናው የሚፈርደውን ቃል የኢትዮጵያ ልጅ በመሆኔ አብሬ ፈርጄ መናገር ኗው እንጅ በማቴ ወን በ፭ ምዕ ፲፯ ቍጥ ኢመጻእኩ ከመ እስአሮሙ ለኦሪት ወለነቢያት አላ ከመ እፈጽሞሙ እንዳለ ልዑል አልጋ ወራሻችን እንዲህ ይሉናል ። ጃንሆይ አፄ ምኒልክ የጀመሩትን እንፈጽመው እንግፋበት ይኸው ተማሪ ቤት ሰፋልን ለኢትዮጵያ ሕዝብ አንድ ተማሪ ቤት አይበቃውምና ብዙው ከድንቁርና ወደ እውቀት ከድሕነት ወደ ባለጠግነት ከለመቻል ወደ መቻል እንድረስ እያውቀኑም ከመባል እንወቅ ከመናቅ እንከበር ራሳችንን እንቻል ይኸነን የመሰለ ሁሉ እናድርግ እያሉ ሊመክሩ ማገዛችንና መርዳታችን ቀርቶ ከቶውንም ክፉ ምክር ልንመክርባቸው ይገባናልን? የልዑል አልጋ ወራሻችን ወረታ ይኸ ይሁንን? ወንድሞቼ ሆይ ተኝታችሁ ወይም ብቻችሁን ሁናችሁ ብታስቡት ምንኛ የሚአስለቅስ ነገር ኖርዋል። ያለፈው አለፈ ለንግዴሁ ግን እንወቅ እንጠንቀቅ ቍርጥ ፈቃድ አድርገን እናግዛቸው ብዬ ከጫማችሁ ወድቄ እለምናለሁ ።

ጌኛ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ሁሉ
እንዲህ ማለት ይገባናል በየልቡናችን ።
ማሪኝ በድያለሁ ኢትዮጵያ እናቴ ።
ክልብ የምወድሽ አገሬ ክብሬቴ ።
ክንቺ ተወልጄ ሳልማር መቅረቴ ።
በቸልታ ብዛት በየዋህነቴ ።
ያን ያህል ስትመክሪኝ ሌት ተቀን በፊቴ
ያንተ አለ መማር ነው የኔ ድህነቴ ።
ድኸነን እያሰብኩ ይበሽቃል አንጀቴ ።
ጠጠት ሁሮኝ ቀረ እስተ ጊዜ ሞቴ ።
እጅግ የሚገርመው ትልቁ ጥፋቴ ።
የተማርኩ መስዬ ራሴን ማኩራቴ ።
እንዲህም ስላልኩኝ
ተጋፋም አልቈረጥኩኝ ።
ሳስብ ስብከንከን ስወድቅ ስነሳ ገነን
ብሏሒቴ
ጠላትም አይደፍረው ተፈሪ ነው ቤቴ

ስለ መማርና መማማር የሚአሳስብ ።

ተማሪውስ ማነው መሐሪውስ ማነው ።
የሚማረውማ ትንሽ ትልቁ ነው።
ተፈሪ አባ ጠቅል መሐሪ ጌታ ነው።
አውቆ ላላጠፋ ምንም በደል የለው።

ሰው ሁኖ ላገሩ እንዴተጋና እንዴቀና
ማስታወሻ ።

ተክበናል አሉ በዳያው በላቴ ።
መትጋት መቀዳደም መስራት መጠንከር
ነው ለዚህ መድኃኒቱ።
ተፈሪ ላሴን ላሰችን ዘውዴቴ ።
የተፈረው ጊዜያት እንዳይመሽ በከንቴ
እዬት ላልተማረ ብዙ ነው ጠላቴ።

ጳውሎስ ወርቅነህ በምስር ከተማ።

ይድረስ ለብርሃንና ሰላም ዲሬክተር ።

ወንድሞቻችን የኢትዮጵያ ልጆች በእውቀታቸውና በትጋታቸው ገንዘባቸውን አዋጥተው የትምሕርት ቤት ለማቆም በማሰባቸውና በማድረጋቸው እጅግ ደስ ስላለኝ ለዚሁ ለሚያቆሙት የትምሕርት ቤት እርዳታ አሁን በመጀመሪያ መቶ ብር እሰጣለሁ በየመቱ የሚከፈለውንም እስከሚቻለኝ ዘመን ድረስ አምሳ አምሳ ብር እሰጣለሁ ።

ደግሞ በዚህ ወር በሕዳር ፫ ቀን የወጣውን በብርሃንና ሰላም የተጻፈውን ጋዜጣ ሳነብ በስሕተት የተጻፈ ቃል ስለ አገኘሁበት የጻፈው ሰውዬ ነገሩን በጣም ሳይመረምርና ሳይረዳው በመጻፉ ብዙ አደነቅሁ ።

ይህም ሰው በጻፈው ክፍል ውስጥ የተናገረው ዋናው ቃሉ ለየሹሞቹ የተሰጠ የደንብ መጽሐፍ የለምና ሹም ለመሆን አልመኝም የሚል ነው።ይህ ሰውዬ ይህን የመሰለ ትልቅ ነገር ሲጽፍ ስሙን አልጻፈምና እርሱን ፈልጌ ለየሹሞቹ ሁሉ የደንብ መጽሐፍ መስጠቱን በቃል ለማስረዳት አልተቻለኝም።ደግሞም ለእርሱ ብቻ በቃል አስረድቼ ብተወው ይህ በሕዳር ፫ ቀን በብርሃንና ሰላም ጋዜጣ የታተመው ለየሹሞቹ የተሰጠ የደንብ መጽሐፍ የለም የሚለው ቃል ከኢትዮጵያ አውራጆች በብዙ ስፍራ ደርሶአልና አንባቢዎች ሁሉ እውነት ይመስላቸዋል እንጂ በስሕተት የተጻፈ መሆኑን አያውቁትም ይልቁንም የብርሃንና ሰላም ጋዜጣ በውጭ አገሮች ደርሶአልና በውጭ አገር የሚኖሩ የኢትዮጵያ ልጆች ለየሹሞቹ የተሰጠ የደንብ መጽሐፍ የለም ተብሎ ተጽፎ ሲያገኙት ትልቅ ኃፍረትና ጠጠት ይሆንባቸዋል ። ስለ ዚህ ይህ ሰውዬ ለየሹሞቹ የተሰጠ የደንብ መጽሐፍ የለም ብሎ ያሳተመው ቃል ስሕተት መሆኑን ገልጬ ለማስረዳት በግድ የሚያስፈልግ ስለ መሰለኝ ከዚህ ቀጥሎ ያሉትን ቃሎች እጽፋለሁ ።

ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን የአውሮፓን ሥልጣኔ ለራሳቸው በመስማትና በማወቅ ብቻ አልቀሩም ነገር ግን አገራቸው ኢትዮጵያ የምትለማበትን ፡ ሕዝቡ የሚሰለጥንበትንና የሚበለጥግበትን ሥራ ሁሉ ለማሰራት ለየሚኒስትሮቹና ለየሹሞቹ ልዩ ልዩ የሆነ የደንብ መጽሐፍ ሰጥተዋል ። በዚሁም በተሰጠው ደንብ የመንግሥቱ ሥራ እየሰፋና እየተሻለ መሔዱን ብዙ ሰዎች ያውቃሉ ።

ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ከዚህ ቀድሞ ለየሹሞቹ የሰጧቸው ደንብ ቁጥር ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈው ነው

አንደኛ ፡ የፍርድ ሚኒስቴር ደንብ ፡
ሁለተኛ ፡ የገንዘብ ሚኒስቴር ደንብ ፡
ሶስተኛ ፡ የጽፈት ሚኒስቴር ደንብ ፡
አራተኛ ፡ የርሻ ሚኒስቴር ደንብ ፡
አምስተኛ ፡ የንግድ ሚኒስቴር ደንብ ፡
ስድስተኛ ፡ የስልክና የፖስታ ሚኒስቴር ደንብ ፡
ሰባተኛ ፡ የመዘጋጃ ቤት ደንብ ፡
ስምንተኛ ፡ በልዩ የቆመው የፍርድ ቤት ደንብ ፡
ዘጠኘኛ ፡ የትምሕርት ቤት ደንብ ፡
አስረኛ ፡ የውል መመርመሪያ ደንብ ፡
አስራ አንደኛ ፡ የምድር ባቡር ዘበኞች ደንብ ፡
አሥራሁለተኛ ፡ የባርያ ነጻነት ደንብ ፡
አሥራሶስተኛ ፡ የጠመንጃና የጥይት ደንብ ፡
አሥራአራተኛ ፡ የይለፍ (የፓስፖርት) ደንብ ፡
አስራአምስተኛ ፡ የርሻና የንግድ ማስፊያ ማህበር ደንብ
አሥራስድስተኛ ፡ የሐረር አውራጃ ደንብ ፡
አሥራሰባተኛ ፡ የድሬዳዋ ማዘጋጃ ቤት ደንብ ፡
አሥራስምንተኛ ፡ የጅጅጋ አውራጃ ደንብ ፡
አሥራ ዘጠኘኛ ፡ የጨርጨር አውራጃ ደንብ ፡
ሀያ ፡ የኢየሩሳሌም ገዳማችን ደንብ ፡

ይህም ከዚህ በላይ የተጻፈው የደንቡ መጽሐፍ ቁጥር በጠቅላላው ዋና ዋናው ደንብ ብቻ ነው እንጂ በየደንቡ ውስጥ በዋናው ሹም በታች ላሉት ሹሞች የተሰጠው ደንብ ክፍሉ እጅግ ብዙ ነው ።

ከነዚሁም በአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤትና በሐረር አውራጃ በዋናው ደንብ ውስጥ ከዋናው ሹም በታች ላሉት ሹሞች የተሰጡትን ደንቦች እንጽፋለን ።

በአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት የተሰጡ ደንቦች ።

መጀመሪያ ፡ የከንቲባው ደንብ ።
ሁለተኛ ፡ የዲሬክተሩ ደንብ ።
ሶስተኛ ፡ የከተማ ዘበኞች አለቃ ደንብ ።
አራተኛ ፡ የማዘጋጃ ቤት ዳኛ ደንብ ።
አምስተኛ ፡ ከንቲባው ሰበር የሚያይበት ደንብ ።
ስድስተኛ ፡ የማዘጋጃ ቤት ገንዘብ ጠባቂ ደንብ ።
ሰባተኛ ፡ የመንገድና የርስት ቦታ ሹም ደንብ ።

በሐረር አውራጃ የተሰጡ ደንቦች ።

መጀመሪያ ። የዋናው እንደራሴ ደንብ ።
ሁለተኛ ፡ የጦር አለቃ ደንብ ።
ሶስተኛ ፡ የዲሬክተሩ ደንብ ።
አራተኛ ፡ እንደራሴው ሰበር የሚያይበት ደንብ ።
አምስተኛ ፡ የወንበር ደንብ ።
ስድስተኛ ፡ የግምጃ ቤት ሹም ደንብ ።
ሰባተኛ ፡ የአዛጋር ደንብ ።
ስምንተኛ ፡ የዋና ጸሐፊ ደንብ ።
ዘጠነኛ ፡ የሥራ ሹም ደንብ ።
አሥረኛ ፡ የስልክ ሹም ደንብ ።
አሥራንደኛ ፡ የዘብጥያ ሹም ደንብ ።
አሥራ ሁለተኛ ፡ የጉምሩክ ደንብ ።
አሥራ ሶስተኛ ፡ የአማካሪዎች ደንብ ነው ።

በጨርጨርም አውራጃ በሐረር አውራጃ የተሰጡት ደንቦች ሁሉ ተሰጥተዋል ፡ ይልቁንም የመሬት አለካክ ደንብ ፡ የመሬት ግብር ደንብ ፡ ባለቤት የሌለው መሬት የሚሸጥበት ደንብ ። የኑዛዜ ደንብ ፡ የጋብቻና የፍቺ ደንብ ተጨምረው ተሰጥተዋል ።

ደግሞ በዚህ ላይ በ፲፱፻፲፮ ዓመተ ምሕረት ወደ አውሮፓ ሔደው ሲመለሱ ለየሚኒስቴሮቹ ሁሉ የሥራቸውን ደንብ ማመልከቻ በፈረንሳዊ ቋንቋ የተጻፉ ልዩ ልዩ መጻሕፍት አምጥተው ሰጥተዋቸዋል ።

ከዚህም ጋራ እንደ ደንብ የመሰለ ልዩ ልዩ የሆነ አዋጅ በያመቱ ያስነግራሉ በየቀኑም በቃልም በጽሕፈትም ደንብ የሚሆን ትእዛዝ ለየሹሞቹ መስጠታቸው አልቀረም ።

ስለዚህ ለየሹሞቹ የተሰጠ የደንብ መጽሐፍ የለም ተብሎ በህዳር ፫ቀን የተጻፈው ቃል ስሕተት መሆኑን የብርሃንና ሰላም ጋዜጣ አንባቢዎች ሁሉ እንዲያውቁት አመለክታለሁ ።

ነገር ግን ይህ ሰውዬ ለየሹሞቹ የተሰጠ የደንብ መጽሐፍ የለም ብሎ በመጻፉ ትልቅ ስሕተት አድርጓል ብዬ አልፈርድበትም ስለ ምን ብሎ የሚጠይቅ ሰው ቢኖር ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል እመልስለታለሁ ።

ይህ ሰውዬ ለየሹሞቹ የተሰጠ የደንብ መጽሐፍ የለም ብሎ መጻፉ ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ለየሚኒስቴሮቹና ለየሹሞቹ የደንብ መጽሐፍ መስጠታቸውን ያልመረመረና ያላወቀ ፡ በውጭ የሚኖር ሰው ቢሆን ነው እንጂ የመረመረና ያወቀ ፡ የቤተ መንግሥት ሰው ቢሆን ለየሹሞቹ የተሰጠ የደንብ መጽሐፍ የለም ብሎ ባልጻፈም ነበር ፡ ደግሞም ይህ ሰውዬ የጻፈው ቃል ስሕተት ነው ማለቴ እንደ አገራችን ልማድ ነው እንጂ እንደ አውሮፓ ልማድ ቢሆን ይህ ሰውዬ ይህን ለመጻፍ ይገባኛል ለማለት ይችላል ። በአውሮጳ መንግሥቱ ለሕዝብ የሚጠቅም አንድ ደንብ ያወጣ እንደሆን ሕዝቡ ሊሰሙት ከማይገባቸው ከመንግሥቱ ምስጢር በቀር በጋዜጣ ወይም በመጽሐፍ ታትሞ በቶሎ ሕዝቡ ሁሉ ይሰሙታል በሀገራችን ግን የጋዜጣና የመጽሐፍ ማተሚያ ሥራ በጣም ስለ አልተለመደና ስለ አልሰፋ መንግሥታችን ያቆመውን ደንብ ሁሉ ከነዚያው ከሹሞቹ በቀር የሚያውቀው ሰው የለም ።

ወደ ፊት ግን ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ሕዝብ ሊሰማው ከማይገባው ከዋናው የመንግሥት ምስጢር በቀር ለየሹሞቹ የሚሰጡትን ደንብ በጋዜጣ ወይም በመጽሐፍ እያሳተሙ ሕዝቡ ሁሉ እንዲያውቀው ያደርጋሉ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ እስከዚያውም ድረስ ለየሹሞቹ የተሰጠ የደንብ

መጽሐፍ የለም ብሎ የጻፈ ሰውዬ ለልቡ እረፍት እንዲያገኝ ልዑል አልጋ ወራሽ ለየሹሞቹ የሰጡትን የደንብ መጽሐፍ ለማንበብ እንዲፈቀድለት አመለክታለሁ ።

ልዑል እግዚአብሔር በቸርነቱ ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ለልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ። እረጅም ዕድሜ ከጤና ጋራ ይስጥልን እያልን እንለምን እንጅ በውጭ አገር በጆሮዎችን የሰማነውን ባይናችን ያየነውን መልካሙን የደንብ መጽሐፍ ሁሉ በገራችን በኢትዮጵያ ሳናየው አንቀርም ።

ብላታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ።

ይድረስ ለክቡር አቶ ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት የብርሃንና ሰላም ዲሬክተር ያክብሮት ሰላምታዬን አቀርባለሁ

ክቡር ሆይ ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈውን ሐሳቤን በብርሃንና ሰላም ጋዜታ ማተሚያ እንዲያትሙልኝ እለምናለሁ ።

፩ኛ ፤ በሙሉ ኢትዮጵያ ላይ የትምህርት ቤት እንዲሠራብዬ ካሁን ቀደም ትኒሽ ቃል ስለጻፍኩ እርግጥ በሙሉ ኢትዮጵያ የትምሕርት ቤት እንዲቆም የሚያስፈልገው ብዙ ገንዘብ ስለሆነ የሕዝብ ማሰልጠኛ ግብር ተብሎ በሙሉ ኢትዮጵያ ሕዝብ መጠነኛ ግብር እንዲከፍል መንግሥታችን የግብሩን አቀባበል አስቀድሞ የጠበቀ ሕግ እንዲያቆም የግድ ያስፈልጋል ።

፪ኛ ፤ ሕጉ ከቆመ በኋላ በየሐገር ቤት የታመኑ ሠራተኞች እንዲሳኩ ያስፈልጋል ግን ካገር እንዲቀበሉ መንግሥት ቆርጦ በሕጉ ላይ የተጻፈውን ግብር ብቻ የደረሰኝ ጉርድ ወረቀት ለባለ ገንዘቡ እየሰጡ እንዲቀበሉ ያስፈልጋል ። እነዚህ ሠራተኞች በሕጉ ላይ የተጻፈውን ግብር ትተው ሌላ የበለጠ ገንዘብ አምጡ ለማለት እንዳይችሉና በሕጉ ላይ ያልተጻፈውን ገንዘብ እንዳይቀበሉ በሕጉ ውስጥ ትእዛዝ እንዲጻፍ ያስፈልጋል ።

፫ኛ ፤ በሕጉ ላይ ያልተጻፈውን ገንዘብ ሠራተኞቹ ተቀብለው የተገኙ እንደሆን በሕግ ተላላፊ ስም እንዲቀጡ ቅጣቱ በሕጉ ላይ እንዲጻፍ ያስፈልጋል ሠራተኞቹ ሥራቸውን የሚያጠፉና የሚያታልሉ እንዳይሆኑ ። ከሚገኘው ገንዘብ ደህና ደመወዝ እንዲቆረጥላቸው ደንብ ያስፈልጋል ይኸነን አድርጎ መንግሥት የበረታ ትእዛዝ በየሀገረ ገዡው ያሳለፈ እንደ ሆነ ባመት ሲያንስ ፭ት ሚሊዮን ብር ይገኛል ።

፬ተኛ ፤ ይኸውም ገንዘብ እባንክ ተቀምጦ የሚያስፈልገውን አይነት የትምርት ቤት መሥሪያና ለሱም የሚያስፈልገውን ያህል የትምርት መማሪያ ይገዛበታል ፤ ይህም ከሆነ ከጥቂት ቀን በኋላ ባገራችን በኢትዮጵያ ያውሮፓ ዕውቀት እንዲገባ ያለ ጥርጥር የታወቀ ነው ፤ ደግሞ ይኸነን የመሰለ ለሀገር ማሰልጠኛ የሌሎቹ አገሮች መቶና ሁለት መቶ ሚሊዮን ብር እየተበደሩ አገርን ያሰለጥኑበታል ። ገንዘቡንም ለባለ ገንዘቡ በቀን ብዛት ይከፍሉታል እንጂ ፤ ገንዘብ የለንም ብለው ከስልጥንና ተለይቶ የሚኖር አንድም መንግሥት የለም እንዲሁ ላገር ጥቅም የሚሆን አዲስ አዲስ የሥልጥንና ምንጭ እየፈለጉ ባመት ባመት ይጨምሩበታል ፤ ግን በኛ መንግሥት ላይ እኛ እንደምናውቀው አንድም ብድር የለብንም ፤ ደግሞም ብድርም የሚያስፈልግ ጉዳይ የለብንም ።

፭ተኛ ፤ ሰውን ሳያስጮሁ በሕጉ ላይ እየተጻፈ በትንሽ በትንሹ ግብር መንግሥት ከሕዝቡ ላይ ቢያደርግ እንኳን የትምርት ቤትና በሙሉ ኢትዮጵያችን የራሳችንን ባቡርና ቴሌግራም ስልክ ፖስታ ፤ ደግሞ በየሀገሩ መኪና መንገድና ድልድይ ይሠራበታል ፤ ይህም ከሆነ ጥቅሙ የሀገርና የሕዝቡ ነው ። አገሩ ከለማና ሕዝቡ ከተጠቀመ ጢትና ማታ የገዦችን የመንግሥታችን ዕድሜ ይርዘምልን እያለ ሕዝቡ ወደ እግዚአብሔር ይጸልያል ፤ ገዢውም ተገዢውም በፍቅር ተሳስበው አገሯን በሥልጥንና ስም ለማስጠራት ያበቋታል ።

፮ተኛ ፤ ደግሞ ለመንግሥት አንድ ነገር አመለክታለሁ በኢትዮጵያ አገር ብዙ የገባር መሬትና ቀላድ ጉልት እየተባለ አለ ነገር ግን ባለመሬቱ የመሬቱን ዳር ድምበሩን አያውቅም የኔ መሬት ቁመቱ ይኸነን ያህል ገመድ ጐኑም ይኸነን ያህል ገመድ ነው እያለ ከጐረቤቱ ጋራ ዘለዓለም ሲሟገትና ሲጨቃጨቅ ይኖራል ። እሱም ነገሩን ሣይጨርስ ከመሬቱ ዋጋ ይበልጥ ገንዘብ ይከስራል ። ወደ ሀገሩም ተመልሶ ሳይገባ ሙግቱንም ሣይጨርስ ባለመሬትም መሆኑን ሳያውቅ በመካከሉ ይሞታል ልጅ ደግሞ ያባቴ እርስት ነው አባቴ ከወሰነተኛው ጋራ ሲሟገት ነገሩን ሳይጨርስ ሞተ ። አሁንም ያባቴ እርስት የኔ እርስቴ ነውና እሟገታለሁ እያለ ሲጨቃጨቅና ሲሟገት አስርና ሐያ ዓመት ይኖራል ። በመካከሉ ወይም ይሞታል እንደዚሁ ባለመሬቱ ሁሉ መሬቱ የሱ መሆኑን ሣያውቅ እስካሁን ድረስ እንዲያው በጭቅጭቅ ይኖራሉ ። ይህ እንዳይሆን እንደ አውሮፓ ደምብ መሬት የተባለ ሁሉ እንደ አዲስ አበባ ከተማ ካርታ እንዲነሣና ሰውም ባለ እርስት እንዲሆን መንግሥት እንደ አውሮፓ ሕግ ቢያቆም መልካም ነው ። ካርታም ሲነሣ ለመሬቱ ደረጃ ደረጃ ማድረግ ያስፈልጋል ። ማለት ለሙሉን የለማ፡ጠፉን በጭራሽ ጠፍ እንደ መሬቱ አኳሁን ካርታ ቢነሣ የርስት መቀበያ ወረቀት አሹራ ያለ ጥርጥር በደስታ ይከፍል ነበር ። ለዚሁም ብዙ ሚሊዮን ብር ለመንግሥታችን ጓዳ ይገባል ።

ባለ መሬቱም ከጥንቱ ጭቅጭቅና ሙግት ይድናል ካርታ ከተነሣ እርስቱም ለባለርስቱ ልክ መሆኑ ከታወቀ ብዙ እርሻ ያርሳል ደግሞ ብዙ አይነት አታክልት ይተክላል ለራሱና ለቤተ ሰቡ የሚበቃ ያህል አስቀርቶ የተረፈው ወደ ውጭ አገር ለመሸጥ ይችላል ። ከውጭም አገር ለራሱና ለቤተ ሰቡ የሚሆነውን እቃ ያስመጣል ግን መሬት ለባለ መሬት ነጻነት ካለገኘ ባለመሬትም መሬቱ የሱ መሆኑን የሚመሰክር እርግጠኛውን ሕግ ካላገኘ ምንጊዜም ቢሆን ሃብታም ባለመሬት ለመሆን መንግሥቱን ለመጥቀም አይችልም እያደር እየደከመና እየደኸየ ይሄዳል ። ሰባተኛ ። ይኸንንም የመሰለ አገሩንና ሕዝቡንም የሚጠቅሙ ብዙ ደናግል የሆኑ ሥራዎች በሐገራችን አሉ ለመንግሥታችን ፈቃድ ቢሆን ለዚህ ሥራ ሕግ ቢያቆምለት እጅግ መልካም ነበር ለመንግሥታችንም በግዛቱ ውስጥ ያለው የጋሸው ልክ ቁጥሩ ይታወቃል ይኸንንም የርስት ካርታ የሚያነሱ መሐንድሶች በዛሬ ጊዜ በርካሽ ዋጋ ይገኛሉ ። ስለምን ዛሬ ከመስኮብ አገር ተሰደው ከሌላ አገር ያሉት የመስኮብ መሐንድሶች ብዙ አሉ ይባላል አሁን ጊዜያቱ ሳያልፍ በያለበት ቢፈልጓቸው አይታጡም ግን ወቅቱ ካለፈ ከዛሬ ዋጋ በላይ

እጥፍ ያስፈልጋል ልጆቻችንን አስተምረን እነሱ ይሰራሉ ከማለት እኛም እየሰራን ወደፊት እንሂድ ። እነሱም በቶሎ በቶሎ እየተማሩ ይድረሱብንና ሐገራቸውን እንዲረዱ ማሰብ ይገባናል ።

ነጋድራስ በሻህ ።

በ፺፫ ቁጥር በ፲፱፻፲፰ ዓመተ ምሕረት በ፲፪ ጥቅምት ስለ ሐረር ዘብጥያ አስፋው አበጀ በብርሃንና ሰላም ጋዜጣ ላሳተመው ቃል ምላሽ ።

በሐረር ያለ ዘብጥያ (የእስር ቤት) ክስር ዓመት በፊት ከፊተኛው የተሻለ ሆኖ ውስጡም በየክፍሉ ተቆርጦ የተሠራ ነው ። ከዚሁም ግን የሚሻል ሥፍራ ለመለወጥ ብዙ ጊዜ ሹሞቹ ሲደክሙበት አይተናል ። የሐረር ቦታ የርስት ቦታ ስለ ሆነ ሰፊ ቦታ ያላቸው ሰዎች ከሚገባቸው በላይ ብዙ ዋጋ እየጠየቁ ስለ አወኩ ለጊዜው አልተፈጸመላቸውም እንጂ አስፋው አበጀ ለእስረኞች የሚሻል ቦታ ብቻ በሆነ የጻፈው ምላሽ ባልፈለግንለትም ነበር ። ነገር ግን ባንድ ወር ውስጥ በሽታ የሞቱ ሰዎች ሰባት ይሆናሉ ፤ አንዱ ሰው ሰድቦ በካሣ ምክንያት ፣ ሶስቱ ባባሪነት ሳይረቱ ሁለቱ በሌብነት አንዱም በዳኝነት ነው ላለው ምላሽ ልሰጠው የሚያስፈልገኝ ሆነ ።

አንድ ሰው በካሣ ምክንያት ሁለቱ ሰው ከሶስቱ ባባሪነት ካላቸው አንዱ ሰው በዳኝነት ምክንያት ሞቱ ያላቸው ሐሰት ነው ። ሶስት ካላቸው ካባሪዎች የሞተው አንዱ ብቻ ነው ። ይኸውም ሰው የታሠረበት ምክንያት አንዲት የጨዋ ሴት ልጅ ከባልንጀሮቹ ጋራ ጠልፎ ደብድበው ወስደው ስለሞተች አብሮ ማጣለፉን ስላመነ ነው ፤ የሙዋች፡ ወገኖች ግን እንገላለን ስላሉ ሐረር ደብኛን ለማጋደል ፈቃድ ስለሌለ ወደ አዲስ አበባ ለመውጣት ተዘጋጅቶ ሳለ ታሞ ሞተ ። በየንዳንዱ ወር ክሶስት እስከ ሰባት ይሞታል ስላለውም ሐሰት ነው ።

ክ፲፱፻፲፯ ዓመተ ምሕረት መስከረም ፩ ቀን ጀምሮ እስከ ፲፱፻፲፰ ዓመተ ምሕረት መስከረም ፩ ቀን ድረስ በስር ቤት የሞቱ ፲፬ ናቸው ከነዚሁም ከ፲፬ቱ ሰዎች ስምንቱ በነፍስ ግዳይ አንዱ በባሻ ሽያጭነት ፣ አንዱ ሰው በጥይት መትቶ ። አንዱም ሰው በጨቤ ወግቶ ። አንዱም ሱማሌ በጥይት ንግድ ተይዞ ። አንዱም መሠረተ ሌባ ፤ አንዱም በሌብነት ታስረው የነበሩ ናቸው ። እነዚሁም ሰዎች ገሚሶቹም ጥፋታቸውን በቃላቸው ያመኑ ገሚሶቹም የተመሰከረባቸው ናቸው ። የጥፋታቸውም ልክ ሁሉ በመዝገብ ተጽፎ የሚገኝ ነው ። የመዝገቡንም ግልባጭ ረቺ ወይም ተረቺ የሆነው ወገን የፈቀደው አሳትሞ መውሰድ ይችላል ይኸውም ከተለመደ ብዙ ጊዜው ነው ።

በሰውም ካሳ መንግሥት አያስርም ተካሽው የተካሰውን ለመንግሥት ከለቀቀ በቀር ። ይኸውም ቢሆን ዋስ የሚያገኝ ሰው በማናቸውም ምክንያት ስለገንዘብ አይታሠርም ዋስም አጥቶ በዳኝነት ወይም በተቆረጠበት የገንዘብ ቅጣት እስቲከፍል የሚታሠረው ከሌባ ጋራ አደለም ከዚያው ከየክፍሉ የተለየ ሥፍራ አላቸው አስፋው አበጀ እንደጻፈው ሁሉንም አስተካክሎ ያየ አይመስለኝም ። ይሁን እንጂ ይኸንን እላይ ያለውን ቃል በመጻፉ ለስረኞች የሚሻል ነገር እንዳይሆንላቸው ወይም ታሥረው ቢሞቱ በጥፋታቸው ምን አለበት ለማለት አይደለም በማያሳስር ነገር ታሥረው እንዳልሞቱ ለማመልከት ነው እንጅ እኔስ በጅምላው በኢትዮጵያ ሁሉ ይልቁንም በየዋናው ከተማ ላሉት የስር ቤቶች መላኩ በያን ባ፺፬ ቁጥር ባ፲፱፻፲፰ ዓመተ ምሕረት በጥቅምት ፲፱ቀን በብርሃንና ሰላም ጋዜጣ ላይ እንዳስታወቀው ሁሉ መንግሥትና ሕዝብ ተረዳድቶ የሚሻል አነዋወር እንዲያደርግላቸው ዘወትር የምመኘው ነው ።

ተፈራ ገብረ ጻድቅ ።(ሐረር)

ስለ ግርማዊት ንግሥት አሌክሳንድራ ሞት ።

የእንግሊዝ ንጉሥ የግርማዊ ጆርጅ ፭ኛ ፤ እናታቸው ግርማዊት ንግሥት አሌክሳንድራ እንደ አውሮጳ ቁጥር በሕዳር ፳ በ፲፩ ሰዓት ተሩብ በሲንድሪንግሐም ቤተ መንግሥታቸው ማረፋቸውን የእንግሊዝ መንግሥት ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር ምስተር ቻርልስ ቢንቲክ በኅዳር ፲፬ ቀን ለግርማዊት ንግሥት ዘውዲቱና ለልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን አስታወቁ ።

የገዛ ሰውነቱን ስለ መግደል ።

ሙሴ መሐመድ የሙሴ ሐናፊ ልጅ በኅዳር ፲፫ ቀን በገዛ እጁ ሽጉጥ ጠጥቶ ሞተ የሞተበትም ምክንያት ከቤቱ ወጥቶ አምሽቶ እቤቱ ተመልሶ ከገባ ብኋላ እናቱ መዳም ሐናፊ ስለምን ጊዜ አለጊዜ መጣህ ብላ የናትነት ቃል ብትናገረው እናቱ ደህና ሰንብች ብሎ በለሰለሰ ቃል ተናግሮ ከንሮ በሽጉጥ በገዛ እጁ ተመትቶ ወድቆ እናቱ ደንግጣ ወጥታ ብታየው እንደዚህ ሆኖ አገኘችው ። ያን ጊዜ የናቱ ኀዘን እንዴት የመረረ ይሆን፡ወዮ ግሩምነው ።ከዚያም በኋላ ሀኪሞች ተጠርተው አይተው ት ከሌሊቱ በ፲ ሰዓት ሞተ ። ብርሃንና ሰላም መዳም ሐናፊና ሙሴ ሐናፊን እግዚአብሔር ያጥናችሁ ይላል ።

ለዚህም ያደረሰው ምክንያት መጠጥ ያዘወትር ነበርና ስካር ይጸናበታል ወደ ዝሙትም እንደሚያደላ ብልግናው የተገለጠ ነበር ፤ ለሚያሰክር መጠጥ ስለ ተገዛ አባቱና እናቱ ዘወትር ይገሥጹትና ያዝኑ ነበር ። ምክራቸውንም ባለመስማቱ ለገዛ ራሱ ጥፋት ለወላጆቹም ፀፀት ሆኖ ቀረ ።

መጠጥንም ለሚያዘወትሩ ሰዎች ስካር ይከተላቸዋል ። የዝሙት ፆርም አጥብቆ ይቃወማቸዋል ። ንዴትና ክፉ በሽታም አይለያቸውም ፍሬያቸውም ለገዛ ራሳቸው ጥፋት ለዘመዶቻቸውም ብርቱ ኀዘንና ጉዳት ይሆናል ። ስለዚህ ወደ ጥፋት ከሚያደርሰን መጠጥ አጥብቀን እንሽሽ ።

ጠጅ ዋዛ ነው ስካርም መጃጃት ነው ይህን የለመደ ሁሉ ብልሀተኛ አይሆንም ምሳሌ ፳ ም ፩ ቍ ።

ይህንም የጻፍንበት ምክንያት መጠጥን ለሚያዘወትር ሰው ሁሉ በመጠጥ ምክንያት የሚመጣ አደጋ እንዳያገኘው ለማስጠንቀቅና ለመምከር ብለን ነው እንጂ የሱን ኃጢአት ለማውራት አይደለም ።

የከተማ ወሬ ።

በኅዳር ፲ቀን ሌሊት አራዳ ውስጥ አንቱአን የሚባል አንድ የግሪክ መንግሥት ዜጋ ያለበት ሱቅ በሌቦች እጅ ተሰበረና አራት መቶ አሥራ አምስት ብር ተሰርቆ ወዲያው

የመጀመሪያ ከሚሳሪያ ፤ ማለት የሥራ አዛዥ ክፍል ዘበኞች ሲፈልጉ አድረው ሁለት መቶ አርባ ስምንት ብር ከሃምሳ ሳንቲሙን ከነሌቦቹ ይዘው ገንዘቡን ለባለቤቱ አስረከቡት ፤ የቀረው ገንዘብ ግን ባንክ ኖት ማለት የወረቀት ገንዘብ ስለሆነ ገና አልተገኘላቸውም ። ነገር ግን ይህኑ ቀሪ ገንዘብ ለማግኘት ዘበኞቹ ተስፋ ስላላቸው አሁንም አጥብቀው ይመረምራሉ ።

ሁለተኛ ።

ኅዳር ፱ቀን የእንግሊዝ ሌጋሲዮን አሽከሮች እርስ በራሳቸው ተጣልተው ከመካከላቸው አንዱን የሌጋሲዮን አሽከር የሆነውን ሂንድ በዱላ ገደሉትና ዋናው ደብዳቢ አመለጠ ። አብሮ የሄደው ጠብ አንሺ የሆነው አሽከር ግን ተይዞ በዘበኞች እጅ ታስሯል ይህንም ። ደብድቦ ያመለጠውን ሰው የከተማ ዘበኞች አጥብቀው ይፈልጉታል ከከተማ ውጭ ባለው አገርም ሁሉ በየበሩም እየተጠበቀ ተፈልጎ እንዲያዝ ትእዛዝ ተሰጥቱዋል ።

በኢትዮጵያውያን ማህበር ለሚቆመው ተማሪ ቤት እርዳታ እንሰጣለን ብለው ፊርማቸውን የሰጡ ሰዎች

ከ፴፮ ቍጥር የመጣ ድምር ፳ የምስር ወርቅ ፺ሺ፪፻፺፯ብር ተ፩ብ

ብላታ ሓሩይ መጀመሪያ ፻ ብር ባመት ባመት	፶	ብር
ፊታውራሪ ቀንዓ።	፴	ብር
አቶ ጣሰው ውቤ መጀመሪያ ፶ ብር ባመት ባመት	፳	ብር
አቶ ተስፋዬ ካሣ መጀመሪያ ፳ ብር ባመት ባመት	፫	ብር

ድምር ፳የስምር ወርቅ ፺ሺ፫፻፵፯ ብር ተ፩ብ

ማስታወቂያ ።

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ላገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሊሆኑ ያሳተሙዋቸው በማተሚያ ቤታቸውም የሚሸጡ መጻሕፍት

የቅ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ተግሣፅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪	ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪	ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነ ትርጓሜው	፲	ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲	ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የኢየሩሳሌምና የውሮጳ መንገድ ታሪክ (ደስታና ክብር።)	፱	ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሲራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፯	ብር
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫	ብር
መዝሙረ ዳዊት ጥራዙ እጅግ ያማረበኪስ የሚያዝ	፪	ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነተርጓሜው ።	፪	ብር
ትምህርተ ኅቡዓትና ኪዳን ንባቡ ከነትርጓሜው	፪	ብር
የሕይወት ታሪክ	፪	ብር ተኩል
የቁጥር ትምሕርት	፩	ብር
ያማርኛ ሰዋስው	፩	ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩	ብር
የብዙ መኳንንቶች ሥዕል ያለበት ከርት ፳፬ቱ	፩	ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የአደን መንገዳቸው አኳኋን		አላድ
የል ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ		አላድ
አጭር የዓለም ታሪክ		አላድ
ያማርኛ ፊደል		ሩብ
ሒሳብና ምኞት		ሩብ

ትምሕርተ ሕፃናት		ሩብ
የበገና ግጥም	፪	መ
ለኢትዮጵያ ልጆች ማመልከቻ ።	፪	መ
የምክር ቃል	፪	መ
የልብ አሳብ ግጥም	፩	መ
ብርሃንና ሰላም አንድ ቁጥር	፪	መ

ማስታወቂያ ።

በርሻና በመስሪያ ሚኒስትር ሥራ ውስጥ መንግሥት ያወጣውን ደምብና ሕግ ሳልተላለፍ ደሀ ሳልበድል ፤ የመንግሥቱን ገንዘብ በጥንቃቄ ሠርቼ ቀድሞም ከሚሠራው ሠራተኛ ገቢ ገንዘብ አብልጬ አገባለሁ የሚል ሰው እርሻና እመስሬ ምኒስቴር መጻፊያ ቤት፣ ሁል ጊዜ ከጧቱ ከ፫ ሰዓት እስከ፱ ሰዓት ድረስ ፤ እየመጣ ቢነጋገር በደስታ እንቀበለዋለን ደመወዙም እንደ ሥራው ገቢ እየታየ ይቈረጥለታል ጥቅምት ፲፩ ቀን ፲፱፻፲፰ ዓመተ ምሕረት ።

መኰንን ሀብተ ወልድ።

ማስታወቂያ

ለራሶችና ለደጃዝማቾች ለሴት ወይዘሮች የሚገባ በያይነቱ ጥሩ ካባ ከኤሮፓ መጥቶልኛል ቤቱም (ባንክ አፍ አቢሲንያ) ከእንግሊዞች ባንክ አጠገብ ነውና ይህን ካባ መግዛት ለሚፈልጉ ሰዎች መጥተው እንዲገዙ አስታውቃለሁ።

ኢያሱ ዳንኤል

አ ፔ ማርሲያኖ

በኢትዮጵያና በፈረንሳይ የቅኝ አገር ሶማሊ በተለየ ፊያት አውቶሞቢልና ትራክተር አስመጭና እንደራሴ።



A.P. MARCIANO

Concessionnaire Exclusif pour l'Ethiopie et la cote française des somalis des automobiles et tracteurs Fiat.

በልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ

መጀመሪያ ዓመት ፤ ቁጥር ፵፱ ።
1re ANNÉE № 49

ሐሙስ ህዳር ፳፬ ቀን ፤ ፲፱፻፲፰ ዓ ም።
JEUDI 3 DECEMBRE 1925

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት
Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voi regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraissant tous les jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

የጋዜጣው ዲሬክተር ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።
Gabré Christo Taklé Haymanot
Dirécteur

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል። በየሳምንቱ ሲገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ስለ ኅዳር ጽዮን በዓል አከባበር ።

ኅዳር ፳፩ ቀን በ፩ ሰዓት ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ልዑል አልጋ ወራሽ ባማረች አቶሞቢል ሁነው ወደ እንጦጦ ማርያም በብዙ አጀብ ታጅበው መጓዝ ጀመሩ ሁለት ሰዓት ሲሞላ ከቤተ ክርስቲያን ደረሱ ።

ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ልዑል አልጋ ወራሽም በደረሱ ጊዜ ካህናቱ ባማረ ዜማ ታቦተ ሕጉ መንበረ ፀሐይ ለምኒልክ ንጉሠ ነገሥት።ንጉሥኪ ወለተ ሚካኤል ኢይትመዋዕ ለፀር።ወኢየኃድጋ ለሀገር መንበረ ፀሐይ እያሉ ይወርቡ ነበር ሁለተኛም ካህናት በቅኔ ማኅሌት ሁነው ጽላት ዘሙሴ ዕፀ ጳጦስ ዘሲና እያሉ ግሩም አድርገው ዘመሩት።አቋቋማቸውና ጸናጽል አጣጣላቸው ከመቋሚያ አያያዛቸው ጋራ እጅግ የተባበረ ነበር ። ሽልማታቸውም በጣም ያማረና የተዋበ ስለሆነ በሕዝቡ ላይ አምረው ይታዩ ነበር ።

ሦስት ሰዓት ሲሆን ዲያቆኑ መስቀል ይዞ ፤ እምነ ጽዮን ይብል ሰብእ ፤ ወብእሲ ተወልደ በውስቴታ ፤ ወውእቱ ልዑል ሣረራ ። ብሎ ሰበከና ሕዝቡ በዚሁ ቃል ተቀበሉት።ወዲያው ቄሱ ወንጌል ብሎ ወጣና ማቴ ፳፫ ፩ ። ኵሎ ዘአዘዙ ክሙ ግበሩ ወዘመሐሩክሙ ዕቀቡ ወዘከመ ምግባሮሙሰ ኢትግበሩ የሚለውን እስከ መጨረሻው አነበበና ። ሰማይና ምድር ያልፋል ቃሌ ግን አያልፍም ብሎ በተመለሰ ጊዜ ካህናቱ መስቀሉን ከዲያቆኑ ተቀበሉና አይ ይእቲ ዛቲ እንተ ታስተርኢ እምርኁቅ ከመ ማኅቶት ። ብርህት ከመ ፀሐይ። ሙሴኒ ርእያ ሀገር ቅድስት ዕዝራኒ ተናገራ።ዳዊት ዘመራ ብለው አመለጡ

ከዚህ በኋላ አራት ሰዓት ተሩብ ሲሆን ታቦት ወጣና ዑደት ተደረገ።በዚያን ጊዜ ዘበኛው ሁሉ በሥርዓት ዙሪያውን ከባቢ ሁኖ ቆሞ ነበር።ሕዝቡም በሦስቱ ቅጽር ሁሉ እንደ ሮማን ፍሬ ተጨናንቆ ቆሞ ነበር።ባራት ሰዓት ተሩብ ታቦቱ ቆመና ልዑል አልጋ ወራሽ ተቀምጠው እጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ከፍ ካለው ከመጀመሪያው ቅጽር ላይ ሆኑና ዝቅ ካለው ከሁለተኛው ቅጽር ከመስኩ ላይ ሁነው ያማረ ወረብ ወርበው ሲያስረግጡ እጅግ ደምቆላቸው ነበር ። አራት ሰዓት ተኩል ሲሆን ብፁዕ ዕጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ የታቦተ ጽዮንን ታሪክ ተርከው ለመቤታችንም ምሳሌ እንደሆነ ገልጠው አስረድተው ለሕዝቡ ለነፍሱና ለሥጋው የሚጠቅም ምክር መክረው አሳርገው ባርከው አሰናበቱት።ብፁዕ ዕጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ሲመክሩና ሲያስተምሩ እሳቸው ከፍ ካለ ቦታ ሕዝቡ ዝቅ ካለ ቦታ ስለ ሆኑ ሠራዊቱ ሁሉ ለመስማት ተመችቶት ነበር ሕዝቡ ብዙ ሲሆን ጫጫታና ንግግር ትቶ በፀጥታ ይሰማ ነበር።ብፁዕ ዕጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ስብከታቸውን በጨረሱ ጊዜ መድፍ ተተኰሰና ወዲያው እምቢልታና መለከቱ ይንጫጫ ጀመር ።

አምስት ሰዓት ሲሆን ከቤተ ክርስቲያን ወጡና በመኳንንቶቻቸውና በሠራዊታቸው ታጅበው ጉዞ ተጀመረ አጀቡም በቍልቍለቱ ሲወርድ እጅግ አምሮ ይታይ ነበር እንዲሁ እንደ አማረ ሆኖ በሰባት ሰዓት ከታላቁ ቤተ መንግሥት ገቡ ።

በዓሉም የሚከበርበት ምክንያት የመቤታችን ምሳሌ የምትሆን ታቦተ ኪዳን በኢሎፍላውያን እጅ ተማርካ ኋላ እግዚአብሔር በታምራት እንዲመልሰዋት ግድ ብሎ ስለ መለሳት ነው ፩ ሳሙ ም ፬ እስከ ፯ ተመልከት።ዛሬም በኢትዮጵያ ያሉ በመቤታችን ስም የተጠሩ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ይኸነን የታቦተ ጽዮን መታሰቢያ በዓል ያከብሩታል።ይልቁንም አክሱም ጽዮን ለመሳም በያመቱ ብዙ ሰው ወደአክሱም ይሄዳል።

ለጎንደር ጽዮን ልዕልት ወይዘሮ መነን ወጨጫ ማርያምን ለማክበር ሄደው ነበር።እስከ አቃቂ በማረ አውቶሞቢል ሄዱ። ከዚያ ወዲያ ግን እጅግ ባጌጡ በቅሎ ስሉሴዋ እንገቷ ላይ እየተንሹዋሸዋ በ፱ ሰዓት ወጨጫ ደረሱ ታቦቷ ወጥታ በልልታ በደስታ ዑደት ተደርጎ ቅዳሴ ገቡ ልዕልት ወይዘሮ መነንም አስቀድሰው ለሠራዊታቸው ግብር ተደርጎለት ጥቂት ዕረፍት አድርገው ከማታው በ፲፪ ሰዓት ተመልሰው ገቡ ።

ለመንግሥት ኃይሉ ምንድር ነው ?

ከሁሉ በፊት ሁሉን የሚችል እግዚአብሔርነው።እንዲሁም ባሰተዋይ ንጉሥ (ምሳሌ ፳፩ ፩፫) እግዚአብሔርሳ በምን አመካኝቶ ወይም በምን አድርጎ ኃይል ይሰጠዋል ባስተዋይ ንጉሥ በጠለቀ ትምርትና ምክር በጅግኖችና በልባሞች መኳንንቶች በታመኑ ወታደሮችና በብርቱ መሣሪ ያገራቸውን ጠረፍ በሚያውቁ በጣም በተማሩ መሐንድሶች በማይደነግጡና ባገራቸው ፍቅር በተያዙ ሕዝብ አድርጎ ነው የሚጠብቀውና የሚያበረታው እንደዚሁ በመሰለ በሌላ ብዙ ነገርም ነገር ግን ይህን ሁሉ እንዴት በኛ ሊገኝ ይቻላል እንዴትስ እናገኘዋለን? እንጃ ?ለንም ነገር ግን ይኸን ሁሉ ሊያመጣ የሚችል አንድነገር አለ ፈጽሞ ሁሉን ስበ የሚያመጣ እርሱም ስሙ ማግኔት (ሳቢ) ይባላል እርሱም ገንዘብ ነው።ግን ይህን ያህል ኃይል ያለው ገንዘብ ከወዴት ይምጣ?ከገራችን ከተባረከችው ከኢትዮጵያ ይመጣል አዎን መኖርስ እንኳን ወርቅ ብር ሌላም በያይነቱ አለ ግን ማን ያውጣው ይህስ እውነት ማውጣቱን አንችልም ሌሎች ቢያወጡትም ይወስዱብናል ነገር ግን እሱን ሳይቀር የሚስብልንና አጥርቶ የሚሰጠን እኛ የምናውቀው ብልሃት አለን፡እንጃ ምን ይሆን እርሱ ባጭሩ እርሻና ከብት ማገድ፡ በርሻና ከብት በማገድሳ ምን እናገኛለን ።

በዚሁ ምን እንዳገኙ በርሱ የሚኖሩ አያሌ የኤውሮጳን ንግሥታት እንጠይቅ መቼም እግዚአብሔር ቢሰጣቸው በሁሉ ተሸለው ያሉ እነሱ ናቸውና መንግሥታቸው በምን ከመጣ ገንዘብ ተረድቶ ታግዞ ይኸን ያህል ቁም ነገርና ብርታት እንዳገኘ እንይ እንግዲያስ በዚህ ናቸው ሁሉን የሚያገኙ አገሩ ብር የሚወጣበትና በዚሁ የሚረዳ አለ ፤ አገሩ ወርቅ የሚወጣበትም በርሱ ተረድቶ የሚኖር አለ ፤ አገሩ እኽል ብቻ የሚገኝበትም ትርፉ መዝገቡ እርሱ ብቻ የሆነም አለ ፤ እርሱም ያነን በያገሩ እየሰደደና እየሸጠ ይረዳል እንዲሁም ፍሬም እንጨትም ከሰልም እንኳ ሳይቀር በያገሩ በሚወደድበት እየሸጡ መንግሥታቸውን የሚያቆሙ አሉ እኛ ኢትዮጵያውያን ግን ብሩን የሚይዝ ጣት ሳንዘረጋ ብሩ ባገራችን ይቁምልን ማለት ሳንዘራ ፍሬ አጭዳለሁ ማለት እንደሆነ ፈጽመን አልመረመርንም ይመስለኛል ወይስ ተሸጦ ብሩን አጽምዶ የሚይዝልን ነገር ካልሰደድን እንዴት አድርገን ልንሰበስብ እንችላለን ማናቸው ነገር ሲመጣ የኛን ሸጠን ካላስቀረንስ እንዴት አድርጎ ብሩ ላገራችን ይገኝልን ወይስ ብሩ ከወዴት ይምጣ እንግዲያስ እኛ የምንችለው ባገራችንም የሚገኝ እህልና ከብት ነው አያሌ ሰዎች ግን ይህን ስላልኩ ይህ ሰው እብድ ነው የሚሉኝ ብዙ ናቸው ነገር ግን እንዲህ ያለ ነገር ብናደርግ ሽፍታ ከገራችን ፈጽሞ በጠፋ ነበር ።

ስለምን ከእርሻው ያገኘውን ሁሉ የሚገዛለት ቢያገኝ ያን ሰውን ለመግደል ተደብቆበት የሚውልን ጫካውን መንጥሮ እህል በዘራ ነበር በከተማው ስራ ፈትቶ ዘበኞችን ሲያውክ የሚውልና የሚያድርም በሌብነት ከሚያመጣው ገንዘብ በድካሙ የሚያመጣው እንዲበልጥ ባወቀና ወደ ደጉ ሄዶ ምድረበዳ ሁኖ ያለ በረሐውን አሳምሮ በዘራውና በቀናው ። ስለ ዚህም መንግሥት ኩወንበዶች በህውከትና በማጥፋት ፈንታ ሰላምና ጥቅም ባገኙላቸው ነበር።በዚሁ ምክንያት አገራችን ራብ የገባበትና የተጐዳ እንደሆንሳ እንጐዳ የለምን አዎን ለዚሁ እግዚአብሔር መርጦ የቀባቸው መንግሥት ደህና ሰው መርጠው ለዚህ ስራ ሊያቆሙበት ይገባል ስለምን ባያሌ ፍሬ እህል የሚከተትበት የመንግሥት ቤት ሲሰራ ኋላ እየተመዘነ ከገበሬዎች እንደ ዋጋው እየተገዛ በዚያ ሊከተት ፤ የኋለኛው ዓመት እህል ከታየ በኋላ ከወርኃ ታኅሣሥ ጀምሮ ካለፈው ዓመት የተከማቸውን እህል ወደሚወደድበት አገር ተመርምሮ እየተመዘነ ይሸጣል ይለወጣልም በዚያን ጊዜ የሚገባ ደግሞ እየተመዘነ ፊተኛው በነበረበት ይከተታል እስከ ኋለኛው ዓመት ዘመኑ እንደ ዱሮው ዘመኑ ደኅና የሆነ እንደሆነ ታይቶ እንደፊተኛው ይሸጣል ዘመኑ የሚራብ እንደሆነ ግን ከገሩ እንዳይወጣ ተከልክሎ ተመልሶ ለባለገሮች ይሸጣል ። እስቲ በዚህ የማይጠቀምና በዚህ የሚጎዳ እንዳለ እንመርምር።በዚህ ነገር የሚጠቀሙ ከሁሉ በፊት ስራ ፈቶች ከሁሉ ክፉ አሳብ ድነው ወደሥራ በመሄዳቸውና የሰሩትን ሥራ ሸጠው ገንዘብ አግኝተው ለቁም ነገር በመሆናቸው ይጠቀማሉ ።

ሁለተኛ።እህል ቢያገኝም ባያገኝም ብዙ ትርፍ የማይገኝበት የነበረ ገበሬ በድካሙ ትርፍ ስላገኘ ይጠቀማል ።

ሶስተኛ።መንግሥት በብዙ ድካምና ስቃይ በብዙ አሣብና ትጋት ከሚጠብቃት አገሩ በግብርም በንግድም ባገሩ ልጆች ጥቅምም ይጠቀማል ።

አራተኛ።አገሩ ሁሉ መንግሥቱ በዚህ መንገድ ተረድቶ ለሕዝቡ ረድኤት የሚሆን ነገር በመቻሉና በማበጀቱ ይጠቀማል እንዲሁም ብዙ ነገር ነው በዚሁ የሚጠቀም በዚሁ የሚጎዳ ክፉ የለም ከጸላት በተቀር ፤ ያልደከመ እንዴት እንዲሆን በምሳሌ ም ፳፬ ከቍ ፴ እስከ ፴፬ እንዲህ ይላል በታካች ሰው እርሻ በሰነፍ ሰው የወይን ቦታ አለፍሁ እነሆም ሁሉ እሜከላ መልቶበታል ፊቱንም እሾህ ሸፍኖታል የቅጽሩም ድንጊያ ፈርሷል ባየሁትም ጊዜ በልቤ ተመለከትሁት ለማወቅም ምክር ተማርሁ አልሁም ጥቂት ትተኛለህ ጥቂትም ታንቀላፋለህ ትተኛም ዘንድ ጥቂት እጅህን ታጥፋለህ እንደ መንገደኛም ሰው ድኅነት ትመጣብሐለች ችጋርኽም ስለት እንደታጠቀ ሰው ይላል እንግድያስ ያገር ፍሬ መሸጥ በረከት ነው ። እንዲሁም ባገሩ የረባ ከብት የምትወልድ እንስት ሁሉዋ ቀርታ ተባት ተባቱንም በቁጥር በየዓመቱ ይኸን ያህሉ ይብቁ ብሎ መንግሥት ባቆመው ነገር በሚከብሩበት አገር ቢሸጡ መንግሥታችን በንደዚህ ያለ መንገድ ብዙ ገንዘብ ካገኘ በኋላ የወርቅና የብር የብረት የናስ ይኸን የመሰለ ሁሉ ማውጣት የሚችሉ በብዙ መንገድ የተመረመሩ መምሕራን አምጥቶ ጥንብ እንዳዩ አሞሮች የሚዘሩበትን አገሬ

በረከት አውጥተው የተሰወረ መዝገብ ላላት አገራቸው ክቡር ምስጢሯን እንዲመረምሩ ከልጆችዋ ሊያስተምር ምሉ ፈቃዱን ሊፈጽም በተቻለ ነበር ።

የዚያን ጊዜም በረከትን መግዛት እንጂ በረከትን ከመሸጥ ዘወርቋና በብሩዋ በተከለከለች ነበር የማያወጣ ነጋዴ ሊያገባ አይችልም በዚህ ስራ ግን ቀላድ የተባለ ሁሉ ተጽፎ ግብሩ ተለይቶ እየዞሩ የሚያዩት ሰዎች ተመድበው በየመከሩ ሊመረምሩት መሬቱን በእህል በታክልት በማናቸውም ነገር ከሁሉ ያሳመረ እንዲሸለም መንግሥት አስተውሎ የሰጠውን ማእርግና ስጦታም እንዲቀበል ወረታውም በክቡር የመንግሥት ደብተር እንዲጻፍ ። ቀላዱን ያላሣመረ መሬቱን በሚያምርና በሚረዳ ፍሬ ለጥቅም በማድረግ ፈንታ እሾህና አሜከላ እንዲበቅልበት ያደረገውን ሰው ግን ለፊተኛው ዓመት በጥቂቱ ሊቀጣ እንደፊተኛ ጊዜው ያበላሸው እንደሆን ግን ጭራሽ ከርሱ ተወስዶ ለሚያሳምረው ሊሰጥ ይልቁን አዲስ ያልተለመደ በያይነቱ የፍሬና ያታክልት ዓይነት የሚገኝበት ሰው ከፍ ያለ በረከት ከመንግሥት ሲያገኝ የተኛው ይነቃል ያንቀላፋውም ይነቃል የደከመም ይበረታል የመሬቱ ግብርም እግዚአብሔርን በሚፈሩ አእምሮ ባላቸው ሰዎች ሊወሰን እንጂ የደከሙበትን በታ የሚያበላሽ በጊዜውና አለጊዜውም የሚያውክ እንዳይሾምባቸው ቢከለከል እንዲሁም ብዙ ሌላ በምክርና በማስተዋል ደምቡ ቢጸናና ቢቀጥል መንግሥታችን እንዴት በተረዳ ነበር አንድ ነገርም ሰው ምሉ አካሉ በጤና አካል እስካለ ድረስ ለምኖ ሲበላ የተገኘ ቢቀጣ ሰርተው ከመብላት ለምነው መብላት የበለጠ ማዕርግ መስሎ የሚሰማቸው ብዙ ሰዎች አሉ ። ከዚህ ነገር የተነሣም መንግሥቶችን ሰርቼ የምኖርበት ትዳር ስጡኝ ከሚሉ እንዲያው እርዱኝ የሚሉ ይበዛሉ ከምሉ አካላቸው ሳሉ ለምነው መኖር የሚፈልጉና በከተማ ያሉ ጌታ የሌላቸው እከካሞች ውሾች የሚያሰድቡን ያሉ ስድብ ቊጥርም የለውም ። አፍረን ምላሽ እስክናጣ ድረስም ነውና እነኚህ መጠረጋቸው ይገባል ። እግዚአብሔር አዳምን ከገነት ካወጣው ብኋላ ምን እንዳለውም ማመልከታቸው ያስፈልጋል ስራ የሌለው ሰው ጉዳቱ ባለመስራቱ ብቻ አይደለም ስራ ስለ ፈታ ነገር በመስራቱ ደግሞ እንጂ ። ትጋትና ሥራ መውደድም ከምን እንዲያደርስ በምሳሌ ምዕ ፤ በቍ ፱ና ፲ የሚለውን እንመልከት ላይንህ እንቅልፍ አትስጥ ለሽፋሽፍቶችህም እንጉልቻ እንደ ምዳቋ ከጅ ተድን ዘንድ እንደ ኦፎችም ከጽማድ እጅ የማይሰራ አይብላ ይላል መጽሐፍ እያንዳንዳችን በሚገባን ሥራ ተግተን ለምሉ ጥቅም ለመሆን እግዚአብሔር ይርዳን አሜን ።

ከዚህ የቀረው ቃል በሚከተለው ቁጥር ይታተማል ።

ይድረስ ።

ከአቶ ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት ።

በነሐሴ ወደ ምስር ሂጄ ነበረና እግዚአብሔር ይመስገን በደኅና መጣሁ ። ደግሞ በምስር ያየሁትን ስለ አገራችን ሁናቴ ማስረጃ ከዚህ አስከትዬ ጽፌልዎታለሁና በብርሃንና ሰላም እንዲታተም እለምንዎታለሁ ፤

እኔም ገና ከመርከብ ወርጄ ፖርት ሳይድ ስገባ ያገሩን ሁናቴ የከተማውን የቤቱን አኳኋን አይቼ እጅግ ተገረምሁ ከዚያም ወዲያ ካይሮና ወደ እስክንድርያ ሂጄ የከተማውን ስፋት የቤቱን የመንገዱን አሰራር የኤሌክትሪኩን መብራት በከተማ ውስጥ ሰዎች የሚመላለሱበትን ትራሞይ ሌላም ብዙ ነገር በማየት ለጊዜው ብዙ ደስ አለኝ፡ኋላም አዙሬ የአገሬን ሁናቴ በማሰብና ከምስር ጋራ በማመዛዘን ትልቅ ኃዘን ሆነኝ እኔም ምነው መጥቼ ማየት በቀረብኝ ይኸ ንዴት ባላገኘኝ ነበረ ብዬ በመሄዴ ተፀፀትኹ፡ያገሩ ሀብትና ሥልጣኔ ካገራችን እንደ ሰማይና እንደ ምድር ርቋል፡ይልቁንም የሚገርመው በምስር ዝናም ጥቂት ነውና እርሻው በመስኖ ነው፡ደግሞም ያገሩ መሬት አሸዋ ነው የኢትዮጵያ አፈር ከአባይ ውሃ ጋራ በጎርፍ ሂዶ የኛው አፈር ደለል ሁኖ ከተኛበት መሬት በቀር ሌላው ሥፍራ አንድ ፍሬ እህል ወይም ሳር ሊያበቅል አይችልም ተዚህ ባጎርፍ በሄደው በኢትዮጵያ አፈር ጥጥ ዘርተው በዚያ በጥጥ ሺያጭ ይኸንን የሚያህል ጌትነት አገኙ ባላገሩ ወደ ከተማ መጥቶ ዕቃ ሊገዛ ከሱቅ ገብቶ የዕቃውን ዋጋ ለመክፈል ተኪሱ ገንዘብ ሲያወጣ በያንዳንዱ ገበሬ እጅ አንድ መቶ ሁለት መቶ ጂኒ ይገኛል ። እኔም ከምን ያገኛሉ ብዬ ብጠይቅ ከጥጥ እርሻ ነው እነሱ ካመት እስከመት መንግሥት ወይም ሹም ለምንም አይጠራቸውም ሥራቸውን ብቻ ይሠራሉ ግብር ብቻ በቁርጥ አንድ ጊዜ ይገብራሉ ለመንግሥትም እንዲሁ እንደ ሀብታቸው መጠን ይሰጣሉ አሉኝ እኔም የኢትዮጵያ ሀብት ማነሱ ያገሩ ሕዝብ ግብሩ ባመት በቁርጥ ስላልሆነ በጭቅጭቅ ለርሻና ለመከር ጊዜ በማጣት ከዓለም ልትመረጥ የሚገባትን ኢትዮጵያን ከዓለም ሁሉ በኋላ መጨረሻ ያደረጋት ይኸ መሆኑን ተረዳሁ ። ሕዝብ ሥራ የሚሠራበት የሥራ ጊዜ ካጣ ድሃ መሆኑ እርግጥ ነው ፤ በቀረ ምስር ባንድ ውሃ ጎርፍ በሄደ አፈራችን የምስር ነጋዴ ሀብት ከሁሉ ኢትዮጵያ ባንድ ጥጥ እርሻ በልጦ ሲታይ ዋናውን የኢትዮጵያ አፈር የያዝን ሰዎች ይኸን ያህል ከድህነት እግር በታች ወድቀን ድህነት ባልደቀደቀን ነበረ ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ጊዜው በከንቱ እንዳይጠፋ ለርሻ ጊዜ እንዲገኝለት ቢደረግለትስ በጥጥ እርሻም የምስርን ጥጥ ሀብት የሚበልጥ ሐብት እናገኛለን በእህልም እርሻ ከምስር ጥጥ የበለጠ ሐብት እናገኝ ነበር ከብት በማርባትም የምስርን ጥጥ የሚያህል ሐብት እናገኛለን በቡናም በሌላም አታክልት እንደዚሁ ነበረ ሌላ ሁሉ ቀርቶ ኢትዮጵያ የስልጣኔ ትምሕርት ብታገኝ የወርቅ የብር የነሐስ የብረት የሁሉም ቀርቶ በድንጋይ ከሰል ሺያጭ ብቻ ከምስር የበለጠ ሐብት ባገኘን ነበር አሁንም ደግሞ ጊዜው ቀርቦዋልና በንግሥት ግርማዊት ዘውዲቱ ፈቃድና በልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ትጋት ኢትዮጵያ ወደ ፊት መራመድ ጀምራለችና ኢትዮጵያ ከቀድሞ ሁናቴዋ ወደፊት ስልጣኔ ፍለጋ መራመዱዋ ከዓመት ወዲህ በጣም በጉልህ ይታያል ። እኔም ማስረጃ ምስክር የሌለው ከንቱ ውዳሴ ላመሰግናቸው አይደለም ለኢትዮጵያ ጥቅም የሰሩትን ሥራ አሁኑን ከዚህ አስከትዬ እጽፋለሁ ዓለም በየጊዜው ያገሩን ትልቅ ሰው ምንም ቢሆን እያውቀውም አይታወቀውም ከለፈ በኋላ ነው እንጅ ለኋላ ትውልድ የሚታወቅ ።

፩ኛ ከሊግኦፍኔሽን ፤ ከዓለም መንግሥታት ማህበር መግባታቸው።፪ኛ፡የኢትዮጵያን ልጆች ለማስተማር የልዑል አልጋ ወራሽ የትምርት ቤት መከፈት ።፫ኛ ፡ የኢትዮጵያን ልጆች ለማሰልጠን ወደ ውጭ መላክ ። ፬ኛ ፡ የልዑል አልጋ ወራሽ ወደ ኤሮፓ መሄድ።፭ኛ ፡ የጋዜታ መታተም እሱም ለኢትዮጵያ ልጆች ብርሃን መሬ።፮ኛ ፡ የወንበሮች ደንብ መተከል ፯ኛ ፡ ለኢትዮጵያ መጽሐፍ ለመተታም የማሕተም ቤት መቆም ፰ኛ ፡ የሌባሻይ መቅረት እሱም ክፉ ቀምበር ከኢትዮጵያ ልጆች አንገት ወለቀ።፱ኛ ፡ የከተማ መንገድ ሊሰራ መጀመሩ

ሌላውማ ትንንሹ ስንቱ ይቆጠራል።የሆነ ሆኖ ግን የንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ስምና የልጃቸው የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ስም ከኢትዮጵያ ነገሥታት እንደ ስሜን ተራራ ልቆ መታየቱ የታወቀው ወደፊት በሚጻፈው ታሪክና ጋዜታ ስማቸውን በትልቅ ክብር የሚያስጠራቸው ለሚመጣው ትውልድ እስከ ህልፈተ ዓለም የሚያስመሰግናቸው ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈውን ፫ ደምብ በቆመ ጊዜ ነው ።

፩ኛው የስልጣኔን ትምሀርት ቤት አሁን ዛሬ በቀረጥ ከታሰበው ሌላ ከጉምሩክ ከሚገኘው ገንዘብ ከ፲ ፪ቱን ሰጥተው የስልጣኔ ትምህርት ቤት በኢትዮጵያ አውራጃ በፍጥነት ቢዘረጉ አለሱ መዳኛ የለንምና ። ሁለተኛ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ለባለገሮች ቍርጥ አደር የሆነ የብር ግብር ደንብ እንደ ዓለም መንግሥታት ደንብ ቢያወጡለት ማለት ገጋሮቹ ለሁሉም ነገር አንድ ጊዜ ብር እንዲቀበሉ አሁን ሕዝቡን ያደኸየው ገንዘብ መስጠት አይደለም በመከርና በዘር በስራ ጊዜ ለ፩ሽክም እንጨት ለ፩ቁና ጌሾ በየከተሞቹ ሁሉ አንድ ወር ሁለት ወር ስራ መፍታቱ ለወሳኙም ላይጠቀም ሕዝቡን አደኸይቶ አገሩን ጠፍ ያደረገው ይኸ ነው ። ፫ተኛ ለነጋዶች ኬላ በሚባለው ስፍራ ሁሉ እንዳይጉላሉ የተከከለ የጉምሩክ ደንብ እንደሌላው ዓለም መንግሥታት ደምብ ቢያወጡላቸው ኢትዮጵያን ከድህነትና ከድንቁርና ከችግር አወጧት ማለት ነው ለስማቸውም ትልቅ ክቡር ስም ማቆም ነው ።

ኢትዮጵያም ከዓለም መንግሥታት በስልጣኔና በሐብት መተከከሉዋ ነው ። ስም ማለት ንጉሥ መሆን ብቻ አይበቃም በኢየሩሳሌም ብዙ ነገሥታት ነበሩ ግን ስማቸው እንደ ሰሎሞን አይጠራም እሱ በጥበቡ ትልቅ ስም አግኝቷልና ። በፈረንሳዊ ብዙ ነገሥታት ነበሩ ግን ስማቸው እንደናፖሊዮን አይጠራም የናፖሊዮን መልካም ስሙ ጉብዝናው አይደለም ለፈረንሳዊ ትልቅ የነጻነት ደንብ በማውጣቱ የተከከለ የፍትሐ ነገሥት ደንብ ላገሩ በማቆሙ ነው እንጂ ይኸነኑ እሱም ተናግሮታል እንደዚሁም ከዓለሙ ነገሥታት ውስጥ ላገራቸው ትልልቅስራ የሰሩ ስማቸው በትልቁ የሚጠራ ጥቂቶች ናቸው ነገሥታት ግን ብዙ ናቸው ።

አሁንም ከኢትዮጵያ ነገሥታት ትልቅ ስም የሚያገኝ ይኸነን ፫ቱን ነገር ያቆመ ሰው መሆኑ የታወቀ ነውና ። ይኸነን ክቡር ስም ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ለሌላ ሰው አሳልፈው ይሰጣሉ ብዬ አልጠረጥርም ደግም ከኢትዮጵያ ጌቶችና መኳንንት በዚህ በነገሩ የሚከፋቸው ምናልባት ቢኖሩ ስህተት ነው ጌቶቹ እንደ እውቀቱ መጠን ላመልከታችሁ ስሙኝ ጌትነት ታስሮ በአንድ ቤት አይኖርም ዛሬ ጌታ ሆኖ ገባር የሚገዛ ነገ ልጁ ገባር ሆኖ ለአንድ የደሃ ልጅ ይገዛል ያም አባቱ ጌታ የነበረው ልጅ መልካም ደንብ ባለመኖሩ ትልቅ ሃዘን ያገኘዋል መልካሙን ደንብ ቢመኝም ከየት ያገኘዋል አባቱ ደንብ ለማስተካከል ኃይልና ጊዜ ሳለው ትቶታልና ለሌላ ሰው ልጅ ያቆምከው ደንብ ነገ ለገዛ ልጅህ ወጥመድ ሁኖ ይቆየዋል ።

ያለፉትን ጌቶች ልጆቻቸውን አስተውል አንባቢ ሆይ በልጅም አይደርስም ብለህ አትጠርጥር በርግጥ ይቆየዋልና ነገር ግን አንድ አንድ ሰዎች እኔ በጊዜዬ ልብላ እንጂ ልጄ እንደ ሀብቱ ይሁን የሚሉ አሉ ይኸ ግን የማይገባ ንግግር ነው ፤ ሰው እንዴት ለልጁ ጉዳተ እንዲቆየው በገዛ አፉ ፈርዶ ያቆየዋል ። ደግሞም ለራሱ ኳንንት አገረ ገጋር የሆነ ሰው የተተከከለ ደንብ ግብሩ በቁርጥ የሆነ ለባላገር ቢደነባ ነገ ልጁ ወይም ራሱ ተሽሮ ሹመት ቢቀርበት አይዋረድም በየሰው ደጅ ሂዶ አይጉላላም መቼም እርስት ብዙ አለውና በጌትነት ተቀምጦ ያሳርሳል በቀረ ግን እኔ ዛሬ በጊዜዬ እንደፈለገኝ ላድርግ ቢባል ነገ በልጅ መድረሱን ወይም ዕለት ተሽሮ በራስ መድረሱን በጣም ልንረዳው ይገባናል ። ደግሞም ይኸንን ነገር ለመረዳት የሚፈልግ ልባም ሹመታቸውን ከተሻሩ ወዳጆቹ የሚማከር ትልቅ ብልህ ነው ።

ደግሞ ይኸ ደንብ ሲቆም ላገረ ገጋርና አገር ማደሪ ብለው ለሰጧቸው ወታደሮች ሰማንያ ጥብቅ ኩዳድ ያመት በዓል የወር ጨው የሚባለው ይኸንንም የመሰለ ደንብ ሁሉ ሲቀር ጉዳት ይሆንባቸዋል ፤ ስለዚህ ከመተፋፈር በቀጥታ መነጋገር የውቀት መንገድ ነውና ይኸን አገር ገዦች ዱሮ የሚአገኙትን ገንዘብ እንዳይጐልባቸው ገባር በቁርጥ የሚያወጣላቸውን ግብር እንዲበቃቸው በዛ አድርጎ መቁረጥ ነው ባለመሬቱ ገባር ግን ገንዘብ ምንም ያሀል ቢሰጥ ቀድሞ በየአደባባዩ ሁሉ በደጅ ጥናት የሚያጠፋውን ጊዜ ወደ ሥራ ይጨምረዋልና አይጐዳም አገረ ገዦችም ደግሞ የሚበቃቸውን ገንዘብ ካገኙ ድኃ በየደጃችን ተሰብስቦ ሥራ ፈትቶ ደጅ ካልጠና የሚሉ አይመስለኝም ይኸ ነገር የኢትዮጵያን ባላገር ጨርሶ ለማጥፋት ትንሽ እንደቀረው የማይመሰክር የለምና የመንግሥትና የወታደር እናቱ መሰረቱ ባላገር ነው ባላገር ከጠፋ ግን እናቱ የሞተችበት የሚጠባ ጥጃ መሆናችንን እንረዳው ። ገንዘብ የሚገኝ ሥራ በመሥራት ነው ሰው የሥራ ጊዜ ከጠፋበት ገንዘብ ከየት ያመጣል ። አሁን ሰዎች ሲናገሩ አገረ ገዦች ግብር ቁርጥ መሆኑን አይወዱም ይላሉ ።

ለኔ እንደሚታየኝ ግን አገረ ገዦቹ ቁርጥ አደር ግብር ደንብ ሆኖ መቆሙን ጠልተው አይደለም መንግሥት ባላገሩ ለአገረ ገዦች የሚገብረውን ግብር አሳንሰው ከባላገሩ የሚወጣው ግብር ለአገረ ገዦቹ የማይበቃቸው ስለሆነ ሕዝቡ በደጅ ጥናት ሲጉላላ ገንዘብ ይሰጣል በማለት ነው እንጂ ያገሩን ጥፋት ማን ይወዳል ስለዚህ መንግሥት ባላገር የሚገብረውን ግብር በዛ አድርጎ ቢደነባ አገረ ገዦቹ የሚበቃቸውን ገንዘብ ካገኙ ሌላ ምን ይፈልጋሉ አገረ ገዦቹ ግብር ቁርጥ መሆኑን የሚጠሉበት ምክንያት ይኸ ነው እንጂ ሕዝብ ስራ ፈቶ ገባራቸው ቢደኸይ ቢጠፋ መቼ ይወዳሉ መንግሥት ከደነበው ግብር አትርፈው ቢወስዱ ይከሰሳሉ ይቀጣሉ ያው-

ይብቃን ብለው እንዳይቀመጡ የማይበቃ ነው ስለዚህ ባላገሩም ከጭቅጭቅ አርፎ ስራውን ቢሰራ ብዙ ጥቅም ያገኛልና ብዙ ቢገብር አይጐዳም እንዳሁኑ ደንብ ግን ለባላገሩም ገንዘብ መስጠቱም አልቀረም የስራ ጊዜም አላገኘም በሁለት ወገን ይጐዳል ።

ፊታውራሪ ዴሬሳ ።

ስለ ጠመንጃ ተኩስና ጠመንጃ ።

ዳግማዊ አጼ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ከኢጣልያኖች ዘመቻ ወዲህ ነገሩን አይተው ሠራዊቱ እንደ ወደደ ይያዝ ብለው ጠመንጃ የወደደ እየገዛ ይይዝ ነበረ ወዲያውም እየገዛ ሲይዝ ጥይቱም በገፍ ይገዛ ነበረና ሰውም በልማድ በማናቸውም ነገር ባጥንቱም በወረቀቱም እዱርም ባለው አውሬ እየተኰሰ ሁሉም ባይሆን አብዛኙ ሰው በጣም ተኳሽ ሞልቷል ይልቁንም እንደሰማነው ከውጭ አገር ሰዎች እነሱም የሕዝቡን ሥራ እየጠየቁ እንዳገኙት የትግሬ ሰው የጐንደር ሰው የጐጃም ሰው የወሎ ሰው ይተኩሳል ተብሎ ተመሥግኑዋል አምሐራ በጉብዝናና በጐራዴ በመማታት በብልሃት ተመስግኑዋል ።

ጋሎች በፈረሰኝነት ተመስግነዋል ደግሞ አንድ ወታደር በወገቡ የሚታጠቀው ጥይት ለማጌጫ ሃምሳ ይሆናል እሱ በጣም ተኩሱን ስላለየው ከምሳው በሆያው ተኩስ ተምሮ ሰላሳውን ታጥቆ ቢጠባበቅ ነው የሚሻለው እንጂ እንዲያው ቢታጠቀው ያልታወቀ ነገር ይሆንበታል አሁን ለተኩስ የሚሆን ቦታ እንደ ስርዓቱ ተከተማ ማይርቅ በመሐንዲስ እየታየ አራት ስፍራ ቢያዝ መልካም ነው አንዱ ለመኳንንትና ተኩስ ለሚፈልጉ ወይዛዝሮች ። ሰስቱ ክፍል ለወታደር ዛሬ ቦታው ማይመርመር ቢቀር መንግሥት ስራ በሚያዝበት ቦታ ሁሉ ዛፍ እየተተከለ ቤት እየተሰራ ስራውን አላስኬድ ይለዋል አሁን ቦታው ተይዞ ቢቀመጥ ሁሉም ጊዜውን ይጠብቃል እንጂ በኋላ አይቀርም የሚተኩሰውም ሰው ሁሉ በዚያ በይላማ ቦታ እንዲያው ሄዶ ለመተኰስ አይሆንለትም ሰው እየተጻፈ ባለቃው እሚመታውም ይላማ) በወረቀት እየታሰበ ነው በኋላም ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን የመብጀቱን ልክ አይተው የተመታውንና ያልተመታውን ወረቀት እየለየ የሚያቀባብለውን መኪና ሊያስመጡት ፈቃዳቸው መሆኑ አይቀርም የመኪናውም ዋጋ ቀላል ነው ከነዚህም ከወታደሮች አንድ ወታደር አስር ጥይት ያለው ሰው ተኩስ በተባለ ጊዜ አስሩን ሁሉ ተኩሶ ባንዱ ተመታ እንዳጋጣሚ ያለ ተኩስ ነው እንጂ ደግ ሥራ ተብሎ አይመሰገንም በልማዱ በትምሕርት እንዲሆን ብዬ ነው እንጂ መጻፌ የሚነወር ነገር እንዳይመስላችሁ እኔው ራሴ የወንጭፍ ድንጊያ ለማወንጨፍ የማልችል ሰው ነበርኩ ነገር ግን ከብልሆች ጋራ ስለ ቆየሁ ሚስጥሩን አገኘሁት ተመልክቱት ።

አንባቢዎች ምንም ቢሆን ለሚመጣው ጥቃት አላፊና ተሰያፊ ወታደር መሆኑን የሚስቱው የለምና ተእንግዲህ ወዲህ የሚወለዱት ልጆች ባጭር ተከልክለዋልና እንደዚህ ያለ ስርዓት ካልተበጀ የፍጻሜው ነገር ለመንግሥትም ሆነ ለሕዝብ ጉዳት ይሆናል ደግሞ በተኩሱ መከከል ያለው ሼርጥ ለመኳንንቶችና ለወይዛዝሮች የወርቅ ዋንጫና የብር ዋንጫ ቀጥሎም የብሩ በብልጫ ማግኘት ከመንግሥት ደስ ያሰኛቸዋል በቀድሞው ልማድ የሚተኰስ ታቦት ነግሶ ሲገባ፣ ወደ ሰማይ ወላዶች ሁሉ ሲገላገሉ ወይም በመርዶ ምክንያት ። ከመስቀል ገምሮ በየመትባሉ በመሼታ ተርታ በየ ድግሱ ቤት እየተተኰሰ በመከከሉ ወስላታው ሁሉ እንዱ ባንዱ ላይ እየተነጣበት ሰው እየሞተ ይገኝ ነበር ሌሊት ጊዜ አለጊዜ እየተደናቆረ አስቸግሮ ነበር ከድካማቸው ጋራ ክቡር ከንቲባ ነሲቡ ከነ ዘበኞቻቸው ጭጭ አሰኙት ። ለዚሁም ክቡር ምስጋና ይገባቸዋል አሁንም ፊት ለራስ አውቆ በኋላ ለሰው ነውና እንድናውቅ ማንም ቢሆን ዛሬ በቀድሞ ልማድ ደምብ የሚሠራ የለም ነገር ግን እስከ አራት መቶ ሺ ዘመን ድረስ በሀገራችን ጠመንጃ ማይተኰስ ቢቀር ደስ የሚላቸው ሰዎች ሞልተዋልና ንግግሬ ከናንተ እንዳይለይብኝ እለምናችኋለሁ።

ግራዝማች ገብረ ዮሐንስ ።

መረዳዳትና መደጋገፍ እንደሚያስፈልገን ።

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያን ልጆች ካባታችንና ከናታችን አብልጠው እንደሚወዱንና እንደሚደግፉን ይኸ በዓለም ሁሉ የታወቀ ነው ።

እንደምን ብትሉ አባታችንና እናታችን የለት ልብስና የለት ቁራሽ ነው የሚሰጡን ልዑል አልጋ ወራሻችን ግን ለኛ በቅዶ ለልጆቻችን የሚተርፍ ጥበብና ዕውቀት ልናገኝ ብለው በገንዘባቸው ከሣራ የተማሩትን ወደሥራ ያልተማሩትንም ወደ ተማሪ ቤት በማግባታቸው ደግሞ ወደውጭ አገር ትምሕርት የሚፈልጉ ልጆች የተገኙ እንደሆነ በገንዘባቸው ከሣራ በማስተማራቸው እጅግ አብልጠው እንደወደዱንና እንደደገፉን በዚኽ እንረዳለን ። ደግሞ ለተማሪ ብቻ እንዳይመስለን ለገበሬም እንዲሁ በነጻነት ሊያሳድሩት ፈቃዳቸው ነው ማለት በልክና በሥርዓት

ደግሞ ለገበሬ ብቻ እንዳይመስለን ለነጋዴም እንደዚሁ በየበሩ ተቀማ ከንግዱ ጥፋቱ በዛ ብለው አዝነው እንግዲህ ወዲህ በልክና በሥርዓት ሊያሳድሩት ፈቃዳቸው ነው ። ደግሞ ለነጋዴ ብቻ እንዳይመስለን ለወታደርም እንዲሁ ማገልገል ብቻ ሆኖ በቀለብ በደሞዝ አልተጠቀመም ብለው አዝነው እንግዲህ ወዲህ በደምብና በሥርዓት ሊያሳድሩት ይህም ፈቃዳቸው ነው ከሁን በፊትም ከብዙ ቀን ጀምረውታል ።

ደግሞ ለወታደር ብቻ እንዳይመስለን እንዲሁ በከተማ ውስጥ ለሚኖር ሰውም ሰፈር አውጥተው ሸቀጥ አግብተው ሊያሳድሩት ይህም ፈቃዳቸው ነው ማለት ለሙሉ ኢትዮጵያ መሆኑን ያስረዳል

አያችሁን ያለፉት ነገሥታት እንደ ልዑል አልጋ ወራሻችን አድርገው ቢሠሩልንና ቢያስቡልን እስከሁን ድረስ እንደ ውጭ አገር እንደምናያቸው መንግሥት በሆን ነበር ማለት በገዛ እጃችን ሠርተን ራሳችንን በቻልን ።

ነገር [illegible]ን ያለፈው አልፈዋልና በሚመጣው ዘመን እንትጋ ወደ ሀኪም ቤት እንቀዳደም ማለት ወደ ትምህርት ቤት አዝመራ ሳያልፍብን እንዝራ ማለት አልጋ ወራሻችን ሳሉ በአዝመራ ወራት ያልዘራ ገበሬ በመከር አያጭድምና እንዲሁም ደሞ እኛ የትምህርታችን ቀን ሳያልፍ ወደፊታችን እንሩጥ ማለት እውቀት በሚባል ጐዳና አቅንተን እንሂድ ።

ምነው አባት ሳለ አጊጥ ጀምበር ሳለ ሩጥ ነውና እኛ ደግሞ ልዑል አልጋ ወራሽን የሚያህል ጌታና አባት አግኝተን ሳለን በቶሎ እንሩጥ በቶሎ እናጊጥ ብዬ እለምናችኋለሁ ።

ከዚህ ቀጥዬ ደግሞ አንድ ያየሁት ነገር መታሰቢያ የሚሆን ልንገራችሁ አንድ ቀን ባስመራ ከተማ ቁመን ሳለን ወራቱም ነሐሴ ነበርና በዝናም ብዛት የተነሣ መንገዱ እጅግ ጭቃ ሁኖ ነበር

ኋላ ግን አውቶሞቢል ብዙ ኵንታል እንደያዘች መጣችና ከጥልቅ ጭቃ ገብታ ለመሄድ ኃይል ብታጣ አንድ ሰዓት ተኩል ከዚያው ቈመች እርሷን ለማየት የተሰበሰብን ሰዎች ደግሞ ፪፻ እንሆን ነበር ።

ኋላ ግን የአውቶሞቢል ዋና እጇን አጨብጭቦ እንዲህ ብሎ ለመነን እባካችሁ በሥላሴ አንድ ጊዜ አጋፉኝ አለን እኛም ስለ ሥላሴ ብለን በፊት በኋላ በቀኝ በግራ ሁነን ደግፈን አወጣናትና መንገዷን አቅንታ ሄደች እኛ ግን ለያንዳንዳችን አንድ ኃሳብ ነበረንና ፫ ጓደኛ ሁነን እንዲህ ብለን ተጫወትን

ለካ ኢትዮጵያ ድንቁርና ከሚባል ጭቃ ገብታ እስከ አሁን ድረስ መቈየቷስ ደጋፊ ብታጣ ነው ብለን ተባባልን ኋላ ግን እውነት ነው ብለን አዝነን ተለየን ።

አሁን ደግሞ የኢትዮጵያ መኳንንትና የኢትዮጵያ ልጆች እንዲሁ ተጋግዘን አንድነት በሚባል በትር ደግፈን ድንቁርና ከሚባል ጭቃ እንድናወጣት ይህ ኃሳባችን እንዲሆን እለምናችኋለሁ ። ያ ደገፋም ትምሕርት ቤት ነው ማለት በያገሩና በያውራጃው ማቆም ነው ።

እስቲ ደግሞ ተመልከቱ ኢትዮጵያን የመሰለች ክብርት እመቤትስ ትምሕርት የማይወዱ አረቄ የሚያዘወትሩ ልጆች መውለድ ይገባታልን ።

አሁን ግን ያለፈው አልፏልና እንግዴህ ወዲህ ስለሀገራችን ስለ ሕዝባችን ብለን ልንጋደል ይገባናል ። እንዲህ ስናረግም መከራ ጭንቅ ያገኘን እንደሆን ይህ ለኛ መጀመሪያ ሃይማኖታችን ነው ምነው ስለሀገርህና ስለ ወገንህ ልትሠራና ልትጨነቅ የተገባ ነውና ።

ደግሞ አንድ ነገር ልናገረው የምፈልግ አለኝ እርሱም ይህ ነው።ልዑል አልጋ ወራሻችን የኛን ችጋርና የኛን ጉዳት አይተው ለኛ የሚጠቅም አስበው ቢሰሩልን ይሻላል እንጂ እርስ በርሳችን መጣላትና መከራከር እንተው፡እባካችሁ እንታዘዝ የሳቸው ግፍ እንዳይጥለን ።

ደግሞ የሰው አካል መመርመር ያስፈልገናል ። ሰው ሁሉ ፊት ቁጭ ብሎ ራሱ ያስባል ኋላ ግን ራስ ባሰበው የቀሩት አካላት በራስ ሂሳብ ተመርተው ሥራቸውን ያፈጥናሉ እንግዲያስ ራስ የአካላት ዳኛ መሆኑ ካወቅን ደግሞ ራስ ባሰበው ተከተለው መሥራታቸውን ካወቅን እንዲሁ ደግሞ ለኛ ልዑል አልጋ ወራሽ አስበው በመሩን መሄድ ያስፈልገናል ። ምነው እራሳቸው ራስ ይመስላሉ እኛ ግን እጅ እግር ዓይን አፍንጫ እንዲሁ ሙሉ አካል እንመስላለን ።

አሁንስ ይብቃኝ አንድ ቃል ልናገር ።

የኢትዮጵያ መኳንንትና የኢትዮጵያ ሕዝባችንን እንጠቅማለን አገራችንን እናስፋለን ብላችሁ ድንቅና ጥልቅ የሆን ሐሳባችሁን በብርሃንና ሰላም ስላስታወቃችሁን እናመሰግናችኋለን

ደግሞ የሰው ልብ በየነጋው አዲስ ፍሬ እንደ ምትሰጥ አትክልት የምትመስል ነችና እንዲሁ ደግሞ አዲስ አሳባችሁን በብርሃንና ሰላም ጋዜታ ልታስታውቁን እንለምናችኋለን ።

አሁን ግን ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ከጨለማ ውስጥ የነበርን ሕዝብ በብርሃን እንድንመላለስ ብለው ብርሃንና ሰላም የሚባል ጋዜታ አወጡልን እንግድያስ ብርሃን ሳለን በብርሃን እንመላለስ ወአንሶስዉ እንዘ ብክሙ ብርሃን ነውና እውነተኛ ብርሃን እንደሆነም በጥቅሱ ተመልከት ብርሃን ዘበአማን ዘያበርህ ለኵሉ ሰብእ ለእለ ይነብሩ ውስተ ኢትዮጵያ ደግሞ ተመልከት ብርሃን መጽአ ውስተ ኢትዮጵያ ለእለ ንነብር ውስተ ጽልመት ወጽላሎተ ሞት ወአርትዓ ዕገሪነ ውስተ ፍኖተ ሰላም እንዲል ነገር ግን ስለዚህ ሁሉ ትልቅ ዕድሜና ትልቅ ኃይል ለልዑል አልጋ ወራሻችን ይሁን ብለን የፍቅር ሰላምታችንን ባንድነት ልናቀርብ ይገባናል ደግሞ ብርሃንና ሰላም ለምትጽፉና ለምታነቡ ሰዎች በያንዳንድ ሰላም እንዳንላችሁ ልክና ቁጥር የሌላችሁ እጅግ ብዙች ናችሁና ስለዚህ የፍቅር ሰላምታችንን ባንድነት እናቀርብላችኋለን ።

በሌላ ቀን ደግሞ እንደተቻለኝ እጽፋለሁ ።

ተማኑ ሮምሃ ዓድዋ ።

ስለ ግርማዊት ንግሥት አሌክሳንድራ ሞት የተደረገ ውሎ ።

የእንግሊዝ ንጉሥ የግርማዊ ጆርጅ እናት ማረፋቸውን ብርሃንና ሰላም በህዳር ፲፯ ቀን ለዓንባቢዎቹ አስታውቋል

ደግሞ በሀገራችን በኢትዮጵያ ጌታም ዘመድም ወዳጅም ቢሆን በሩቅ አገር የሞተ እንደሆነ ቀን ተቀጥሮ ዘመድና ወዳጅ ተሰብስቦ የሐዘን ውሎ እንዲደረግ በፈረንጆችም ሥርዓት እንደዚሁ ይደረጋልና ስለ ግርማዊት ንግሥት አሌክሳንድራ ማረፍ በዚሁ ወር በሕዳር ፲፱ ቀን በአዲስ አበባ በእንግሊዝ ሌጋሲዮን ትልቅ የሐዘን በዓል ተደርጎ ነበር ። በዚሁም ቀን ከጧቱ በ፫ ሰዓት ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን መኳንንቶቻቸውን አስከትለው ወደ እንግሊዝ ሌጋሲዮን ሂደው ነበር ልዑል አልጋ ወራሽን ተከትለው የሔዱ መኳንንቶች ክቡር ራስ ሥዩም፡ክቡር ደጃዝማች ወልደ ገብርኤል የግቢ ሚኒስቴር፡ክቡር ደጃዝማች ሙሉ ጌታ የገንዘብ ሚኒስቴር ፤ ክቡር ደጃዝማች ወልደ ሥላሴ፤ ሀኪም ወርቅነህ፡ከንቲባ ነሲቡ ብላታ ኅሩይ፡አቶ ማህሌ ፀዳሉ ነበሩ ።

በእንግሊዝ ሊጋሲዮን በትልቁ ቤት በደጃፉ ላይ ጥቁር ልብስ ተሰቅሎ ነበር ባንዲራውም እንደ አውሮጳ ሐዘን ልማድ ዝቅ ብሎ ተሰቅሎ ነበር ።

በትልቁም በር የህንድ ወታደሮች አንገታቸውን እየደፉ ጠመንጃቸውን እየዘቀዘቁ ይዘው ቆመው ነበር ።

በእንግሊዝ ሌጋሲዮን ያሉት የመንግሥት ሰዎች ከሚኒስትሩ ጀምሮ ሁሉም የማዕርግ ልብሳቸውንና ኒሻናቸውን አድርገው በስተ ግራ ክንዳቸው ላይ የጥቁር ልብስ ቁራጭ አስረው ነበር ።

በመካከለኛውም አዳራሽ ፊት ለፊት የንጉሥ ጆርጅና የንግሥት ማሪ ፎቶግራፍ በቀኝና በግራም የንጉሥ ኤድዋርድና የሟችቱ የንግሥት አሌክሳንድራ ፎቶግራፍ ተሰቅሎ ይታያል።

የንግሊዝ መንግሥት ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር ምስተር ቻርልስ ቤንቲንክ በአዳራሹ መካከል ፊት ለፊት ነበሩ ።የቀሩ-

ትም እንግሊዞች በስተግራቸው ነበሩ ፤ ልዑል አልጋ ወራሽም በሚኒስትሩ ፊት ለፊት በመካከል በተለየ ባለ ከፈይ ወንበር ቀርበላቸው ተቀምጠው ነበር መኳንቶቻቸውም በስተግራ ነበሩ።

ደግሞ በአዲስ አበባ የሚኖሩ የውጭ አገሮች ሚኒስትሮች ሁሉ ለዚሁ የኃዘን በዓል ወደ እንግሊዝ ሌጋሲዮን ሂደው በርና በእንግሊዙ ሚኒስትር በስተቀኝ በኩል በተራ ተቀመጡ መጀመሪያ የዛሬው የሚኒስትሮች ተቀዳሚ (ዱ.ያ) የቤልጅክ ሚኒስትር ክቡር ሙሴ ገርራር ፤ ቀጥሎ የፈረንሳዊ ሚኒስትር ክቡር ሙሴ ጎስን ፤ ቀጥሎ የኢጣልያ ሚኒስትር ክቡር ኮንት ኮሊ።ቀጥሎ የጀርመን ሚኒስትር ክቡር ሙሴ ዋይስ፤ቀጥሎ የግሪክ ቆንስል ክቡር ሙሴ ዘርቦስ ነበሩ።

ሌሎችም በአዲስ አበባ የሚኖሩ የእንግሊዝ አገር ሰዎች ወንዶችም ሴቶችም ሂደው ነበር ደግሞ የስዊድን የወንጌል መልክተኞችና የአሜሪካ የወንጌል መልክተኞች ሂደው ነበር

በእንግሊዝ ሚኒስትር በስተግራ መዳም ሳንፎርድ ስለ ሐዘኑ ፒያኑ ለመምታት ተዘጋጅተው ይጠብቁ ነበር ።

ስለ ሐዘኑም የመጡት እንግዶች ሁሉ ተሰብስበው በገቡ ጊዜ የእንግሊዝ ሚኒስትር ምስተር ቸርልስ ቤንቲንክ ተነሥተው ቆመው ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል ተናገሩ ።

ግርማዊት ንግሥት አለክሳንድራ ንጉሥ ኤድዋርድን አግብተው ከሃገራቸው ከዲንማርክ ወደእንግሊዝ አገር በሄዱ ጊዜ የእንግሊዝ ሕዝብ ሁሉ አክብሮ በደስታ ተቀበላቸው ንግሥትም ከሆኑ በኋላ ለእንግሊዝ ሕዝብ እጅግ መልካም ሥራ ስለሠሩ ሕዝቡ ሁሉ ይወዳቸው ነበርና አሁን በሞታቸው ትልቅ ሐዘን ተደረገ ብለው ጨረሱ ።

ከዚህም በኋላ ስለ እንግሊዝ ንጉሥ ክብር የሚዘመረው ጎድ ሴብ አውር ግሬሲውስ ኪንግ የሚለው መዝሙር በፒያኖ ተዘመረ

God save our gracious King እምላክ ደጉ ንጉሣችንን ይጠብቅ
Long live our noble King የተከበረ ንጉሣችን ዕድሜ ይርዘም
God save the King እምላክ ንጉሣችንን ይጠብቅ
Sand him victorious ድል መንሳት ይስጠው
Happy and glorious ደስታና ክብር ይስጠው
Long to reign over us በኛ ላይ ረጅም ዘመን እንዲነግሥ
God save the King እምላክ ንጉሣችንን ይጠብቅ

ከዚህም በኋላ(Peace perfect peace)ሰላም ፍጹም ሰላም የሚለውን መዝሙር ንግሥት አሌክሳንድራ በሕይወታቸው ሳሉ የሚወዱትና የሚዘምሩት ነበር ተብሎ ተዘመረ።

ከዚህም በኋላ ከመጽሐፈ መክብብ ከ፫ኛውና ከ፭ተኛው ከ፫ኛውም ምዕራፍ ስለሞትና ስለነፍስ የሚናገረውን ቃል እየ ጠቀሱ አነበቡ ከዚህ ቀጥሎ ሌላ መዝሙር ተዘመረ።

ከዚህም ቀጥሎ የንግሊዝ ሌጋሲዮን ጸሐፊ ምስተር ቶማስበመጀመሪያ ለቆሮንቶስ ሰዎች ከተጻፈው ከጳውሎስ መልእክት አሁን ግን ክርስቶስ ከሙታን ተነሣ ላንቀላፉትም (ለሞቱትም) መጀመሪያ ሆነ የሚለውን ቃል አነበቡ ፤ ፩ቆሮ ፲፭ ፳—፶፰ ። ከዚህም በኋላ ሚኒስትሩ ቀጥሎ ያለውን ቃል ተናገሩ ፤ ግርማዊት ንግሥት አሌክሳንድራ አሁን ሥጋቸው በመሬት ቢቀበር በኋለኛው ጊዜ እንዲነሡ እናምናለን ፤ ጌታችንም እኔ ትንሣኤና ሕይወት ነኝ ያመነብኝ ቢሞትም ይነሣል ብሏል ፤ ዮሐ ፲፩.፳፫ ፳፯ ፤

ከዚህም በኋላ እየተንበረከኩ ጸሎት አደረጉ በመጨረሻውም ሁሉም እንደ ተንበረከኩ መዳም ሳንፎርድ ብቻ ፒያኖ እየመቱ በዝምታና በፀጥታ ጸሎተ ሐሊና ተደረገ በዚህም አደራረግ የኃዘኑ በዐል ተጨረሰ ፤ ከዜህም በኋላ ልዑል አልጋ ወራሽ ለመሄድ ተነሡ።ምኒስትሩ ምስተር ቤንቲንክም እስከ በር ወጥተው የኃዘናችን ተካፋይ ሆነው ወደ ሌጋሲዎን መምጣትዎን ለግርማዊ ንጉሥ ጆርጅ አስታውቃለሁ ብለው ምስጋና አቅርበው ሸኝተው ተመለሱ ፤ የቀሩትም የውጭ አገሮች ሚኒስትሮች ሁሉ እየተሰናበቱ በየቤታቸው ሄዱ ይህም ቀን ስለ ልማዱ የኃዘን በዐል ተባለ እንጂ በማየት ቢሆን የትንሣኤ በዓል ይመስል ነበር እንዲህም መሆኑ ትንሣኤ ሙታንን በማመናቸው ሞትን ስለ ናቁት ነው ። የዚህም ፍሬ ነገሩ በሀገራችን ጌታም ወዳጅም ዘመድም ቢሆን ስለሞቱ የሐዘን ውሎ በተደረገለት ጊዜ ምንም በሥጋ መለየታችን ጥቂት እንኳ ብናዝን ትንሣኤ ሙታን መኖሩንና በነፍስ ሕያው መሆኑን እናምናለንና ፊታችንን በመንጨት ፤ ደረታችንን በመምታት እንደ አረማውያን የቀቢፀ ተስፋ ሐዘን ከማዘን ይልቅ ደስታ ማድረግ እንዲገባን መጻሕፍትና ሊቃውንት የነገሩንን መቀበል ይገባናል ለማለት ነው።

የከተማ ወሬ ።

ካያሌ ጊዜ ጀምሮ አዲስ አበባ ከተማውን በየመንገዱ ያረቂ ሽታ አለ ልክ አጥፍቶት ነበር ። በዚህ ሰሞን ግን ያረቂ ሽታ ያለቀቀው ትንሽ ሰፍራ ብቻ ነው ፤ ስለዚህ ለመንገድ አላፊ የሚያስቀይም ያረቂ ሽታ እጅግ አይገኝም ፤ ይኸም መሆኑ መንግሥታችንና የከተማችን ሹሞች ስለጠነከሩና ሞኖፖሉም ሥራውን አስተካክሎ ስለያዘና ስለ በረታ ነው ። ዱሮ በከተማ ሲያልፉ ብዙ የሰከረ ሰው መንገድ አላፊውን ያስቸግር ነበር አሁን ግን በዚህ ሰሞን ኅዳር ፲፱ ቀን ከሥራ ወደ ቤታችን ስንሄድ የሰከረ ይኖር ይሆን ብለን ብንመለከት አንድ ሙሴ ቴሎስ የተባለ ሰው ብቻ ሰክሮ ሁለት ሰዎች ተሸክመውት አየን የተሸከሙትን ሰዎችም በግሪክና ባማርኛ ይሰድባቸው ነበር ። የወደቀ ዕቃውን እያነሣ ይከተለው የነበረ ባልንጀራውን ብንጠይቀው ትልቅ ሰው ነው ግን መጠጥ በጠጣ ጊዜ እንደዚህ ይበላሻል አለን ። ምነው ባይጠጣ ብንለው ባይጠጣ ደግሞ ኃይል የለውም እንደ ምውት ይሆናል አለን ። የሚያሰክር መጠጥ አመል ቢያጡት ከገደለ ፤ ቢያገኙት ካሰከረ በሁለቱም ወገን ጉዳት እንጂ ጥቅም ካልተገኘበት የማይለቅ ቊራኛ በሽታ ከሆነ ያልለመደውም ሰው እንዳይለምደው የለመደውም ሰው ጨክኖ ሊተወው ይገባል ።

ልዑል አልጋ ወራሽ የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤትንእንደ ጎበኙ ።

በኅዳር ፳፬ ቀን ልዑል ተፈሪ መኰንን ከግቢያቸው ውለው ለባለጉዳይ እስከ ፯ሰዓት ጉዳዩን ሲፈጽሙ ቆዩ ከዚያ በኋላ ግብር ሆኖ ቆየ ልክ ፱ሰዓት በአውቶሞቢል ሆነው ወደ ከተማው ማዘጋጃ ቤት ሄዱ እዚያም በደረሱ ጊዜ ክቡር ከንቲባ ነሲቡ ተሰናድተው ይጠብቁ ነበር ዋናውም የፖሊሱ አለቃ ግራዝማች ማህሌ ወታደሩን አሰልፈው ሰላምታ ሰጡ ጥሩምባውም በማረ ድምጽ ተነፋ ልዑልም ሰላምታ ሰጥተው ወደ ማዘጋጃ ቤት

ገቡ ከዘጠኝ እስከ ፲፩ ሰዓት ቆይተው መጡ ሲወጡም እንዲሁ በማእርግ ሆኖ ሰልፉ ይጠብቅ ነበር ።

ስለ እሳት አደጋ።

ኅዳር ፳፱ ቀን ማታ ለሁለት ሰዓት ሩብ ጉዳይ ሲሆን ጉለሌ በወይዘሮ አሰለፉች ቤት አጠገብ ባለ ቦታ ከንዲት ትንሽ ጎጆ እሳት ተነሣና የባሻ ደነቀ ክፍል ዘበኞች ጥሩምባ እስነፍተው በፍጥነት መጥተው ወደ ሌላ ቤት ሳያልፍ በቶሎ አጠፉት ።

26 NOVEMBRE 1923

ROMA — TAFARI MACONNEN Erede et Reggente Impero Etiopico telegrafò da Addis Abeba a Mussolini espressioni simpatia vive felicitazioni pello scampato pericolo commosso Mussolini rispose profondamente sensibile cortesi felicitazioni che Vostra Altezza compiacquesi inviarmi pregola gradire miei rispettosi ringraziamenti et conferma mia piú alta deferenza et considerazione.

TRADUCTION

TAFARI MAKONNEN Héritier et Régent de l'Empire d' Ethiopie a tèlégraphié d' Addis Abeba à Mussolini Ses expressions de sympathie et Ses vives felicitations pour avoir èchappé à l' attentat. Mussolini profondément èmu à répondu qu'il a été sensible aux courtoises félicitations que Son Altesse a eu l'amabilité de lui envoyer et LE priait de vouloir bien accepter ses respectueux remerciements et LUI confirmait ses olus hautes deférence et considérations.

ከኢጣልያ ሌጋሲዮን የመጣ የቴሌግራም ቃል ።

ሮማ ፤ ንጉሡ የእንግሊዝ ንጉሥ እናት ስለ ሞተችበት ምክንያት ከግቢው ሁሉ ላ፲፫ ቀን የኀዘን ምልክት እንዲደረግ ትእዛዝ ሰጡ፡ ጀኔራል ሴናተር በናሊ ሞተ ። ለአሜሪካ መንግሥት ስለ ከፈለው ዕዳ መርዳት ነገሩ በብዙ ደስታ ከሞላው ኢጣልያ ገብቷል ። ብዙ ልዩ ልዩ ማህበሮች ሕዝቡን ሁሉ ወደዚሁ የርዳታ ሥራ እየጠሩ እነሱ ራሳቸውም በርዳታ መዝገብ እንዲጻፉ ለፊዮርሰኒ ለመኑት ። የቤተ ክርስቲያኑ ደምብ ክህናቱ ሁሉ ለዚሁ ያገር ጥቅም የሆነ ሥራ ለማስፋት እንዲረዱ ክህናቱን ሁሉ ጠራቸው ።

ፓሪ ፤ የሬፑብሊኩ ፕሬዚዳን ስማቸው ስለ ተጠሩ ፔንለብና ብሪያን ነገሩን ለመፈጸም መመርመር ጀምሯል እንዲሁም ስመ ጥሩ ለሆኑት የገንዘብ መመርመር መልክተኞች ፕሬዚዳን ሥራ ይመረምራል ዱሜርና ፔሬ ድሩሲዮች ከሚርዲዩዎም እንደ ለቀቁና ከሃሰባያንም ፈጽመው እንደሸሹ ከቤይሩት የርግጥነት ወሬ መጣላቸው ከሬዳያ ሰፍረው ለነበሩ አዲስ አደጋ የጣለ ጠላት ተሸነፈ ።

ቤርሊን ፤ ካንቺሌር ሉቴር ስለ ሎካርኖ ነገር የተዋዋሉትን ሕግና ጀርመን ወደ መንግሥታት ማህበር መግባቷን አስታወቀ ካስታወቀበት ጉባኤም ሚኒስትሮችና የያገሩ አለቆች ሁሉ ብዙም ሕዝብ አብረው ነበር ።

ማስታወቂያ ።

በርሻና በመስሪያ ሚኒስትር ሥራ ውስጥ መንግሥት ያወጣውን ደምብና ሕግ ሳልተላለፍ ደሀ ሳልበድል፤ የመንግሥቱን ገንዘብ በጥንቃቄ ሠርቼ ቀድሞም ከሚሠራው ሠራተኛ ገቢ ገንዘብ አብልጬ አገባለሁ የሚል ሰው እርሻና እመስሪ ምኒስቴር መጻፊያ ቤት፤ ሁል ጊዜ ከጧቱ ከ፫ ሰዓት እስከ ፬ ሰዓት ድረስ ፤ እየመጣ ቢነጋገር በደስታ እንቀበለዋለን ደመወዙም እንደ ሥራው ገቢ እየታየ ይቈረጥለታል ጥቅምት ፲፩ ቀን ፲፱፻፲፰ ዓመተ ምሕረት ።

መኰንን ሀብተ ወልድ።

ማስታወቂያ

ለራሶችና ለደጃዝማቾች ለሴት ወይዘሮች የሚገባ በያይነቱ ጥሩ ካባ ከኤሮፓ መጥቶልኛል ቤቴም (ባንክ አፍ አቢሲንያ) ከእንግሊዞች ባንክ አጠገብ ነውና ይህን ካባ መግዛት ለሚፈልጉ ሰዎች መጥተው እንዲገዙ አስታውቃለሁ ።

ኢያሱ ዳንኤል

አ ፔ ማርሲያኖ ፡

በኢትዮጵያና በፈረንሳይ የቅኝ አገር ሶማሊ በተለየ ፊያት አውቶሞቢልና ትራክተር አስመጭና እንደራሴ።



A.P. MARCIANO

Concessionnaire Exclusif pour l'Ethiopie
et la cote française des somalis
des automobiles et tracteurs Fiat.

በልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ

መጀመሪያ ዓመት ፤ ቊጥር ፶ ።
1re ANNÉE № 50

ሐሙስ ታሕሣሥ ፩ ቀን ፲፱፻፲፰ ዓ ም።
JEUDI 10 DECEMBRE 1925

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voi regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hebdomadaire paraissant tous les jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

የጋዜጣው ዲረክተር ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲረክተሩ ያስታውቁ ። Gabré Christo Taklé Haymanot Diréctеur	የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።	Abonnements Ethiopie Un an 5 Thalers Etranger Un an 7 Thalers le numero 2 piastres

ከ፵፱ ቊጥር የቀረ ቃል ።

ለመንግሥት ኀይሉ ምንድነው ።?

የትጉ እጅ ትገዛለች የታካች እጅ ግን ትገብራለች ። ምሳሌ ፲፪ ፳፬ ፤ ነገር ግን ሕዝቡ በሥራ አይተጋም ሰነፍ ነው የሚሉ ብዙ አሉ ይልቁንም የውጭ አገር ሰዎች እነሱስ እንዴት አድርገው ፈጣኖችና ትጉዎች ሆኑ ብለን እስቲ እንጠይቅ ፡ አዎን ለሥራ ቀንና ሌሊት ሳይቀር እንዲተጉ የሚያነቃቃቸው አለ ፤ እርሱ እንግዲያስ በሥራቸው ብቻ ያ ክብረት ማዕርግ ሀብት የሚባል ፍሬ የሚያጭዱበት ስለ ሆነ ነው ፤ ስለዚህም ከግርማዊት ንግሥታችንና ከልዑል አልጋ ወራሻችን ጀምሮ እስከ ትንሾቹ መኳንንቶቻችን ድረስ ከሀብታሞቻችን ጀምሮ እስከ ድሆችን ድረስ የሰራተኛ ፍቅር እንዲያድርብን እግዚአብሔርን እንለምን ፤ እስከሁን ያጠቃን ምክንያት የተሠወረ አይደለም ፡ ለሠራተኛ ላናጺ ለንዳቂ (ማለት ለገምቢ) ለብረት ሠሪ ግንቦቻቸውንም ሥራ ለሚሠራ ሀብታሞቻችን በማስፈራራት ድሆችን በመለመን ሊሠሩለት እንጂ ገንዘቡን ሰጥቶ ሊያሠራቸው ይወድ ስላልነበረ ነው ። እንግዴህ ግን እግዚአብሔር ለረድኤታችን ቀብቶ በሰጠን ጌታችን ይህ ሁሉ ሊለወጥ በምሉ ተስፋ አለን ። እንግዲያስ ሥራ የሚያውቅ ሁሉ ደኅና ሥራ የሠራ ሥራው ቢታይ ይመሰገናልና ፡ ደኅና ሥራን የሠራችሁ ሁላችሁ የተሻለውን ሥራችሁን ይዛችሁ ኑ ተብሎ ቢነግር ከብረት ሠሪ ጀምሮ እስከ መጥረጊያ ሠሪ እንዲመጣ እንዲሁም እንደ መጣ በየክፍሉ ሊሰበሰብ ፡ ኋላ በብልጫቸው የሚያገኙት ማዕርግና ስጦታ ምሉ የመንግሥት አእምሮ የመደበው በሶስት በሶስት ወይም በራት በራት ሊቆም ፡ ብረት ለሚያወጡና ለሚሠሩ በሶስት ፤ ብር ለሚሠሩም በሶስት ፡ እስከ ባለ መጥረጊያም እንዲሁ ሊቆም ይገባል ። ከዚህ በኋላ ዕውቀቱና ዓቅም ሳያጣ ሥራ ፈት ሁኖ የሚኖር ሁሉ ባለቤቱ በተንኰሉ ባለሙ ሁሉም በእንደዚህ ያለ ነገር ነው የኑቃ ፤ ያገራችን የኢትዮጵያ ሕዝብ ደግሞ ከያሉ ሌሎች የተሻለ አእምሮና ስጦታ እንዳለው የታወቀ ነገር ነው ። ለብዙ የውጭ አገር ሰዎች እንዲመስላቸውም ሰነፍ አይደለም ፤ በተጻፈ ፍትሐ ነገሥቱ ሆነ ፤ በመኳንንቱ ሥራት ሆነ በገበሬው ሕግ ሳይቀር የሚደረግ ብንመለከት እርግጥ ባለ አእምሮ ነው ። አሁን ግን ባለቤቱ ሳይቀር ሰነፍ ይመስለዋል ፡ አገራችንን የሚጎዱ ደግሞ ሁለት ባላጋሮች አሉን ፡ እነርሱም በልማድ መታሰርና አልችልም ማለት ነው ። እችለዋለሁ ማለት አንድ ዓይነት ሕይወት ነው ። አልችልም ማለት ደግሞ ፩ አይነት ሞት ነው ፡ እኛ የምንደነቅበትን ሥራ የሚሠሩ እግዚአብሔር ላንተ ከሰጠው አካላት አንድ ብልጫ እንደሌላቸው እይ የሚል ሰው ቢመጣብን የምንሰጠውን ምላሽ ከማሰብ አንፈርፍ ። ጥቅሙንና ጉዳቱን ሳይመረምሩ ያበቆቻችን ልማድ ይሻለናል የሚሉ ሕዝቡ የሚጎዱበትን እንመልከት ።

ክቡር አንባቢ ሆይ እስቲ እኛኽን ለመመልከት ማስተዋል በሚባል ዓለሙን ሁሉ የሚያሣይኽን ተራራ ውጣና ከእስያ የዓለም እናት ጀምረኽ ዓይንህን በሁሉ ላይ ጣል ። የሕዝቡን ታሪክም አንብብ የዚያን ጊዜ ባከሄድ በልብስ በሥራ ምን ብለን ልንቈጥረው በኑረታችን በሚገኝ ሁሉ ከባቶቻችን ልማድ አንወጣም የሚሉ ሁሉ ከሁሉ በታች ሁነው እንደሚኖሩ ታያለህ የለመዱትን ለመተው የማይችሉ ለመቀበልም ከቶ አይሆንላቸውም ። እስቲ አንድ ታሪክ አለ ልተርክልኽ ፤ አንድ ሰው አባቱ የሰጠውን ብረት ተሸክሞ ይሄድ ነበር ፤ ኋላ ሌላ ሰው በመንገድ ተገናኘውና ብረቱን ጣልና ይህን ወርቅ አሰጥሐለሁ አለው ሰውዬው ግን በትልቅ ንቀትና ኩራት ፊቱ በዚያ ቶመን በነበሩ ሰዎች ዘወር አድርጎ ይኸ አባቴ የሰጠኝ ከጥንት የነበረኝ ለምን

እጥለዋለሁ ብሎ ትንሽ ሣያነጋግረው እየሣቀበትና ባገኛቸው ሰዎች ፊት እያፌዘበት ትቶት አለፈ ። በዚያ ቁመን የነበርን ሰዎች ግን እኩሌታችን ሳቅንበት እኩሌታችን ግን ናቅነው እኩሌታችን ደግሞ እንዴት ያለ ጠባዩንና ያባቱን ልማድ የማይተው ጅግና አለ እያልን አመሰገነው ። ክቡር አንባቢ ሆይ በዚህ ሰው ላይ ምን ትፈርድ ይሆን ። ግና በዚያ ሣለን ግን ሌላ የያዘው ነገር የሌለው የድኃ ልጅ መጣ ስለ ባለወርቁ አሣብና ስለ ባለብረቱ ስንፍናም አጫወትነው ፤ እርሱ ይኸን ከሰማ በኋላ ከኛ መነጋገር ትቶ አሻቅቦ የባለወርቁን ፊት እየተመለከተ ጥቂት በጥቂት ቀረበው ፤ ባለወርቁም የዚያን ልጅ ፈቃድ ካወቀ በኋላ እውቀት ከተባለው ከወርቅ ሰጠው እርሱም እንደሰጠው ተቀብሎ መንገዱን ቀጠለ ። ከዚያ ከባለ ብረቱ አገራቸው አንድ ስለነበረም ባገራቸው ተገናኙ ኋላ ባለ ወርቁ የሚያስፈልገውን ገዛና በሰገነቱ ላይ እየተመላለሰ ደስ ሲለው ሳለ ባለብረቱ በታች በመሬት ጨርቅ ለብሶ ሰውነቱም ክብረቱ መክበድ የተነሣ ደቆ ተስፋ ቆርጦ አሻቅቦ አየው። በዚያ እርሱ የናቀው ወርቅ እንደሆነ ክብሮ ያለ ካወቀ በኋላ ደግሞ ከጸጸት የተነሣ ሰውነቱ ተንቀጠቀጠ በከተማ ያሉ ልጆችም በመንቀጥቀጡ ይስቁበት ነበር ። እስቲ በዚህ ልምድ የተባለ ብረት የወረደን መከራና ጉዳት እዩ ። እስቲ በጭፉስ አጠገብህ ባሉ ሻንቅሎች ከባታቸው ሕግና ልማድ እንዳይወጡ ሲሉ ራቁታቸውን መሄዳቸውን ዓይተኸ በልምድ በሚመጣባቸው ስንፍና ላይ ፍረድ ኵሎ አጽምኡ ወሠናየኒ አጽንኡ የሚለውን ውል አትርሣ ። ዓይንህ ሣያየው ክፉ ነው መላስኸ ሣይቀምሰው መራራ ነው ማለት ስሕተት እንደሆነ ነገርን ሁሉ ሳትመረምር መናቅም እንዲሁ ነው ።

ክሁን በፊት ስማቸውን የጠራን እስያ የሚባሉ ሕዝብን እስከሁን አጥቂታቸው የሚኖር በየይነቱ የሆነ ያባቶች ልማድ ብዙ ሣሉ ጥቂቶች ብርቱውች ሣሉ ደካሞች ሁነው ይኖራሉ አእምሮ ያላቸው የታደሉ ሰዎች ግን ልማዳቸው ሣይቀር በየመቱ ለተሻለ ቅድ ይለውጣሉ በኛ ግን እንጃ ያ ልማድ የተባለ የጨለማ ንጉሥ መቼ ድል እናደርገው ይሆን? እርሱ ሰውን ዘግቶ የሚኖር የብረት መዝጊያ ይባላል እርሱ ምሉ አካላት ቈማምጦ የሚጥል ቍምጥነት ይባላል ፤ እርሱ ዓይንን የሚያማውር ፊንጣጣ ይባላል ፤ እርሱ ወደሞት የሚያንከባልል የሞት መቃጠቂያ የታጠቀ ዘንዶ ይባላል ፤ እኔስ እረ ልምድ ፍጹም ክዲያብሎስና ከሌሎች ጸላቶች የባሰ ባለጋራ ሁኖ አገኘዋለሁና ከብዙ ጠላቶች የበዛ መዓት እንዲጥልብን ይሰማኛል ከለዚህም ከሁሉ አብልጬ እጠላዋለሁ ልማድ ስንፍና የሚባል ወፍራም በግብዞች ፊት ያማረ ሁኖ የሚታይ ጥፋት የሚፈልቅበት ምንጭ ነው እርሱ የማይለቅ ሰንሰለት ነው እርሱ የቲጋትን ባሕርይ የሚቆርጥ የተሳለ ሰይፍ ነው እርሱ የደነዘዙ ሰዎች የሚጕርፉበት የገማ ያየው የሚጸየፈው ወንዝ ነው እርሱ ገሃነም እሳት ነው እርሱ ልጆችን የማያሳድግ መርዝ የሞላበት ነጭ ወተት ነው እርሱ በማይድኑ ሕዝብ ንጉሠ ነገሥት ዘጥፍአት ብሎ ይፈርማል ስሙስ ቢጻፍ ትልቅ መጽሐፍ አይጠቀመውም ይህን ንጉሥ አሸንፈው ድል ያደረጉ ሰዎች ያነን ቀን ሊያከብሩት እንዴት በተገባቸው ነበር ክቡር የክብርቲቱ ድንግል የኢትዮጵያ ልጅ እግዚአብሔር ልትመረምርበት የሰጠኸን አእምሮ ከንቱ አታድርገው ክፉውን ዓይተህ ጣለው መልካሙንም በደስታና በፍጥነት ተቀበለው ኢትልክፍ ኢትግስሥ ማለት የስንፍና ድምጽ ነውና በልብህ አታንግሠው እስቲ ጥቂት ልምድን በላይኸ ማንገሥ መጠበቅ እንዴት ያለ ጥፋት እንዳለው ልምድን መርገጥ መናቅ ግን እንዴት ያለ ጥቅም እንዳለው አልፈን አልፈን እንመልከት ደግሞ በራስህ ብቻ ያለን ልማድ ማየት ቅዱስ ይመስልሐልና በሌላ ዓለም ያለም እንይ በአረቦች ላይ ብናይ ከጥንት ብንመለከት የስልጠና በኵር ናቸው እስከ ማለት ልንደፍር እንችላለን ፤ አሁን ግን እንዴት አድርገው ወደኋላ እንደ ቀሩ እናያለን ወደኋላ መቅረታቸው በልምድ ስለ ታያዙ እንደሆነም በትንሹ እንመልከት አስቀድመው ስለ ሃይማኖታቸው ሲሉ ስንት ሰው በማረድ ሕዝቡ በሕውከት ይኖር ነበር የበለጠ በምስር ያም ያባቴ ያም ያባቴ ሲል መንግሥቱን እስከ ማጥፋት ድረስ ደረሰ ይኸ ብቻም አይደለም ልብሳቸውም መብላቸውም ሕጋቸውም ጋብቻቸውም ከቶ አይለወጥም ።

አሁን እስቲ እዩ አረቦች እንዴት ፎጣ የምትመስል በንገታቸው ተንጠልጥላ እየወደቀች እያነሱዋት የምትኖር እንለቅም ብለው በርስዋ ምክንያት መልካቸውን አክፍተው ይኖራሉ የረቦች መልክ ያማረ ነው ግን አንዳንዱስ ሱሬ ለመታጠቅ እንኳ አይፈልጉም ስለዚህም ያባት ደምብ እንዳይፈርስባቸው ሲሉ ባለንች ሁነው ይታያሉ ምስሮችም የሚበዙ ልክ የሴቶች ቀሚስ በሚመስልና በሚያህል ልብስ ለብሰው አንድ በፀሐይም በዝናብም የማትረዳ ቆብም ደፍተው ያማረ መልካቸውን ያጠፋሉ ሕንዶችም ሀይናኖችም እንዲሁ በአጠገባችን ያሉ በጭፉም ብንመለከት ዕንቍ ሰክተው ሐፍረታቸውን ይሰውራሉ እንጂ ራቁታቸውን የሚሄዱ አሉ ግማሾቻቸውም ቆዳ ይታጠቃሉ ግማሾቻቸውም ጭራሽ ራቁታቸው ይኖራሉ ። ከነሱ የተሻልን ነን የሚሉ ደግሞ ከባቶቻቸው የቆየ ነውና ነጩን ልብሳቸውን በቅቤ ነክረው የሚያጸይፍና ደህና ሰው ሊጠጋቸው የማይችል እስኪሆኑ ድረስ እድፋሞች ይሆናሉ ድሆች ስለሆኑ አቅም አጥተው እንጂ እየጠሉት ሁኖም አይደለም ያባታቸው ልምድ ነውና በደስታ በትዕቢት ሁሉም ከነሱ ያነሠ እነሡም ከሁሉ የተሻሉ እየመሰላቸው ነው ።

እስቲ ወደራሣችን እንመለስ እንዴት ነን እንደነሱ በልምድ የተያዝነ እረ ልማድ የሚባል ባላጋራ ባያስረንስ ደኸና ወደፊት የምንገፋ ሰዎች ነበርን እስቲ ልማድን በገዙ ሰዎች ኃይላቸውም በልማድ ላይ ድል ያደረጉትን እንመልከት የልብስ ብልሐት ሣያገኙ ቆዳን እያለፉ ይታጠቁ የትዳር የኑረት ነገር ስለ አላስተካከሉም አደን አድነው እየተመገቡ ይኖሩ ነበር ፍጹም አሁን በሻንቅሎች እንዳለ ኑረት እንዳባቶቻቸው ደንብ ይኖሩ ነበር አሁን ግን ልምድን ከናቁና ከጣሉ በኋላ በስንተኛው የዕውቀት ደረጃ ወጥተው ዘቅዝቀው ይመለከቱናል ። እኛስ ልምድ በተባለ ወደታች በሚጐትት ሰንሰለት ታስረን በዬትኛው የዘቀዘቀ ደረጃ ሁነን አሻቅበን እናያቸዋለን ይችን ሰንሰለት እግዚአብሔር ቢበጥስልን ወደላይ ለመውጣት ብንጣጣር መንገዱም ፊተኞች ሒደውበታልና አያውከንም ነበር ብቻ ሰንሰለቱ በተበጠሰልን ።

ምነው የተወደዳችሁ የኢትዮጵያ ሽማግሎችና የለመለማችሁ ጐበዛዝት ይችን ሰንሰለት እየተረዳዳችሁ ብትበጣጥሷት አንዳንዱስ አዲስን ነገር የሚናፍቅ ሰው ሲናገር የሰሙ እንደሆን አገሩን እኮ ንቆ ነው ያገሩን ሰው እኮ ጠልቶ ነው የሚሉ እንኳ አሉ እኔንም አሁን እኮ ይህ አገሩን እየናቀ ነው ሌሎችን መምሰል የወደደ የሚሉኝ እንዲገኙ ይሰማኛል ግን አገሬንስ እወዳታለሁ ለምለሚቱንስ አከብራታለሁ ሕዝቧ በኔ ዘንድ የተወደደ አካላትን አድርጌ እንዳይስ እመሰክራለሁ ወርቅ ከለበሰ ሌላ ሕዝብም ጨርቅ የለበሰ ሕዝቤን አፈቅራለሁ ።

ከሌሎች ሊቃውንትም ደንቆሮዎችዋን እሰማለሁ ነገር ግን ጨርቂዋን አውልቃ ወርቅ ልትለብስ ድንቁርናን ጥላም ጥብብን ልትይዝ የከበረ ጥላ ወርቅን ልትሸከም ቀንና ሌሊት እመኛለሁ ነነ የሚሉ የሚስቁበትን ገንዘብ ቀብሬ ሰው የሚያመሰግነውን መዝገብ እንድታገኝ እመኛለሁ እዎን ጨለማን አውጥታ ብርሃንን ልታገባ እናፍቃለሁ ። ሰሎሞን በመክብብ ስለጥበብና ድንቁርና ልዩነት ብርሃን ከጨለማ እንዲበልጥ እንዲሁም ጥበብ ከድንቁርና እንድትበልጥ ለይቼ አወቅሁ ይላል ይኸንን ሁሉስ መልከም ግን መቼም ሁሉ በትዕግሥት ነው የሚሉ አሉ ግማሾቸው ግን አሁን ካልሆነ እኛ በሕይወታችን ሳለን ካላየነው ምን ይሆናል የሚሉ አሉ ግን የሁለቱም ስሕተት ነው በዚህ ትእግሥት ስሕተት መሆኑ እንዲህ ነው፤ አንድ ተረት አለ ለመብለጥ ተጣጣር እንጂ ስንፍናስ አውቆ ይገባል እንዲሁም አንድ ተደርጓል የሚባል ታሪክ አለ እርሱም ይህ ነው ሁለት ልጆች ነበሩ ዘመኑ የራብ ዘመን ነበርና ሰው በራብ እየሞተ ጅብ ይበላው ነበር ፤ እነዚያ ልጆች እንግዲያስ አንድ ሌት በበረኃ ሁነው ጅብ እንዳይሰማን አንነጋገር ተባባሉና ተኙ ኋላ ድንገት ጅብ መጣና ያንዱን እግር ይበላ ጀመረ ያ የሚበላ ልጅ እንግዲያስ ባልንጀራውን ቀስ በል እንዳይሰማን እንጂ ጅብ እኮ ይበላኛል አለው ። ብዙም እንደዚህ ያለ ትእግሥት አለ እንደዚህ ያለ ትእግሥት ግን በሽታ ወይም ሞት ይባላል እንጂ ትእግሥት አይባልም መቸኰልም የሚነቀፍበት ይህ ነው ፤

ዛሬ ካልሆነ ለመቼ ይሆናል እንግዲያስ እንዲህስ ከሆነ ቢቀርም ቢጠፋም ማለት ነው በቶሎም ተስፋ መቁረጥህን ግን ተሳስተሃል ለዛሬ ብለህ ማፋጠንህ ደግ ነው ዛሬ እምቢ ቢልህሳ ለነገ ነገ የማይሆን የሆነ እንደሆንሳ ተነገወዲያ ግን መልከም እስተዚያስ ትል ይሆን ። እዎን ከቡር አንባቢ ሆይ እስከ ሞትህ ነው ተስፋ የሚቆርጥ ፈጣን ተስፋ የሌለው ሰው ማለት ነው ተስፋ መቁረጥ ኃጢአት ነው እንደሚባል ፍጠን ተስፋ ግን አትቍረጥ ተቆጣ ተስፋ ግን አትቍረጥ ።

ተወልደ ብርሃን መድኅን ።

የሰው ሁሉ ዓይን ተስፋ ከሚያደርገው ከገበሬ ድካም ስለሚገኝ ንግድ አኳኋን ።

ድንቁርናን አርቆ ዕውቀትን ለማሠልጠን ምኞት ባለው አሳብ እየመረመራችሁ ብርሃንና ሰላምን በፍጹም ደስታ የምታነቡ ክቡራን አንባቢዎች ሆይ ። እናትና አባቴ የትምርትን ጣዕም ስላላወቁ በተማሪ ቤት ሳያስደጉኝ ቀርተው የትምሕርት ፍሬ የሚሆን ዕውቀቴን ባለማግኘቴ የታሰበኝን ነገር አከናውኖ ለመጻፍ ስላልሆነልኝ እያዘንኩና እየተፀፀትኹ የምጽፈውን ይህንን አሳቤን በሙሉ ፈቃዳችሁ ተቀብላችሁ ባለመሰልቸት እንድትመለከቱት ትሑት ልመናዬን አቀርባለሁ ።

ነገር ከሥሩ ወሀ ከጥሩ እንደሚሉ ከጥንት ጀምረን በሰውነታችን ውሥጥ ያለውን አንዋዋር በማስተዋል ብንመረምረው ጳጳሳትና መነኰሳት ። ቀሳውስትና ዲያቆናት ። ጸሐፍትና ካህናት ። ደግሞ ነገሥታትና መሳፍንት ። ራሶችና ደጃዝማቾች መኳንንትና ወታደሮች ፤ ቀራጮችና ነጋዴዎች ። ሽማኔዎችና ብረት ቀጥቃጮች እየተባሉ የሚጠሩ ብዙ ወገኖች እናገኛበታለን ። እነዚህም በየክፍላቸው የተቈጠሩ ወገኖች ሁሉ በያለቃቸው ሥራቸውን ለመንግሥት እያስታወቁ የሥራቸውን ዋጋ እንደ ሥራቸው መጠን ሹመት ሽልማትም ቢሆን ወይም ገንዘብ ከመንግሥት ሲቀበሉ ከቶ ለነዚህ ሁሉ ምግብ አሰናጂ የሆነ ገበሬን ከቍጥር የሚያገባው አጥቶ በመሾምና በመሸለም ፈንታ ያ ከረፈፍ ባላገር መጣ እየተባለ መሰደቡ በምን ምክንያት ይሆን ?

ይህንን እንደዚህ ያለውን ከንቱ ልማድ እየመረመሩና እየጠየቁ ካገር እንዲጠፉ የሚያደርጉ የመንግሥት አደባባይ ጠባቂዎች የተባሉ ወንበሮችና አገር ጠባቂዎች ተብለው በየአውራጃው የተሾሙ ሹማምንቶች አልነበሩምን ? ይኸ ከረፈፍ ባላገር ተብሎ የሚሰደበውን ገበሬ እንኳ ከብቶቹን የሚጠብቅለት እረኛ በዶሞዝ ይቀጥርና ያ በደሞዝ የተቀጠረው እረኛ ከብቶቹን ያላገባብ ሲያጉላላቸው ባየ ጊዜ ሳይጠብቃቸውም ቀርቶ የሰው እህል ባጠፋ ጊዜ ደሞዙን ቆርጦ እንደ ተቻለው እረኛውን ይቀጣል ። እረ መንግሥታችን ለሕዝቡ ጠባቂዎችና እረኞች አድርጎ የሾማቸው መኳንንቶች ሁሉ ይህንን እንደዚህ ያለውን ነገር ለመንግሥት እያስታወሱ አገር እንዲለማ አለማድረጋቸው ሲያውቅ ዝም ብሎ የሚመለከታቸው ስለምንድነው ።

እንደኔ ምኞትና አሳብ ቢሆን በኢትዮጵያ መንግሥት አገር ግዛቶች ውስጥ በያውራጃው ያሥራት እህል ወደ ጎተራ የሚያገቡ ገበሬዎች ሁሉ ከጎተራ ያሥራቱን እህል ሲያገቡ ስንት ዳውላና ስንት ቁና እንዳገቡ በሚጻፍበት ደብተር ስማቸው እየተጻፈ የእገሌ አገር እገሌ ይኸንን ያህል ዳውላ ከዚህን ያህል ቁና ያሥራት እህል አገባ ተብሎ ከገበሬዎች ሁሉ የበለጠ መሆኑን ለመንግሥት የሚያስታውቁ ሹማምንቶች አሠልጥኖ እነዚያ ሹማምንቶች እገሌ አንደኛ እገሌ ሁለተኛ እያሉ ለመንግሥት ቢያስታውቁ መንግሥትም እነዚህን በየአገሩ አውራጃ ያሉ ገበሬዎችን ሁሉ በሥራቸው ጠንክረው ወደ መንግሥታቸው ጐተራ ያገቡትን እኅል ብዛቱን ካወቀ በኋላ በነዚሁ በገበሬዎች ሥራ ላይ የሚቆም አዲስ ደምብና አዲስ ሥርዓት አቁሞ ሹመት ለሚገባው ሹመት ። ሽልማት ለሚገባው ሽልማት እየሰጠ በያሉበት አገር በደስታና በክብር ቢመልሳቸው ከዚህ ቀደም ወደ መንግሥት ጐተራ ይገባ ከነበረው ያሥራት እህል ይልቅ ወደፊት የሚገባው እህል እየበዛና እየተረፈ እንዲሄድ በትክክል የታወቀ ነገር መስሎ ይታየኛል ።

ከዚህ በፊትም ለጸሐፊና ለወታደር ቀለብ ብቻ የነበረው የጐተራ እህል ከጸሐፊና ከወታደር ቀለብ ተርፎ በመንግሥታችን ፈቃድ ወደ ውጭ አገር እየሄደ ለነዚሁ ለገበሬዎች ረዳት

የሚሆን የርሻ መሣሪያ በያይነቱ እንዲመጣላቸው ማድረጉን ማንም አይስተውም እንኳን የሰለጠነ የርሻ መሣሪያ አግኝተውና እንደዚሁ በብዙ ድካማቸው እጃቸው እግር መስሎ ስለ ታዬያ ቆርፋዳ ገበሬ ያውና እየተባሉ እነዜህን በየወገናቸው የተጠፉትን ሁሉ ሲመግቡ የሚኖሩ ጥቂቶች ገበሬዎች አይደሉም ?

እንግዲያስ እንደዚህ ከሆነ ምድራዊ ንጉሥን አያዬኝም ብዬ ትእዛዙን ባፈርስ ሰማያዊ ንጉሥ ክርስቶስ በነፍስ በሥጋ ይቀጣኛል የሚል የምድራዊ ንጉሥም ትእዛዝ የሰማይና የምድር ንጉሥ ትእዛዝ መሆኑን የሚያውቅ ሰው ፈልጎ አዲስ ሥርዓትና ደንብ ደንግጎ ሰጥቶ ይህንን ሥራ በየገሩ አውራጃ ሁሉ በትክክል እንዲያቆም ከዚህ አስቀድሞ በባለሟሎች ዘንድ ይደረግ የበለጠ ሥልጣን መስጠት ለመንግሥታችን ያስፈልገዋል ይኸ ተመርጦ አዲስ ሥርዓትና ደምብ የተቀበለውም ሰውዬውም ደግሞ እንደርሱ የሆኑ ሰዎች እየፈለገ ብዙ ረዳቶች እየፈለገ በየሀገሩ አውራጃ ሁሉ ማስቀመጥ ያስፈልገዋል።እነዜህንም ከዚህ ባዲስ ደምብ ላይ የተሾሙ አዲሶቹን ሹሞች በሥራቸውና በክሒዳቸው የሚያደርጉትን ነገር ሁሉ ዕለት ዕለት እየመረመሩ የሚያስፈልጋቸውን ጉዳይ ለመንግሥት እስታውቆ ረዳት ሊሆናቸው ይገባዋል።የርሻን ሥራ ሳይጠሉ የሚያርሱት መሬት እጥተው ድኅነት ራሳቸው ላይ ወጥቶ በየውራጃው የሚጐላሉ ሌሎች ሰዎችንም እየፈለገ ደሞዛቸውን ከጐተራ እህል ሰጥቶ ይህንኑ የገበሬዎችን ሥራ በያይነቱ ሊያሠራቸው ያስፈልጋል እንደዚህም የሆነ እንደሆነ መንግሥታችን ትክክል የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ ለማግኘት የሚከለክለው ምንም ምክንያት የለበትም ።

ነገር ግን መንግሥታችን ይኸንን የሥጋዊን ጥበብ ሁሉ መጀመሪያና መጨረሻ የሚሆን እርሻን ከማሰልጠን የተነሣ በውጭ አገር የሚገኝ ንግድን ለማግኘት የሚቻለው በመጀመሪያ ሰማይና ምድርን ፈጠረ በሰማይና በምድር ያሉ ፍጥረታትንም ብሎ ፤ የነዚህ ሁሉ ፍጥረታት ገዢ የሚሆን አዳምን ፈጥሮ በገነት አኖረው ካለ በኋላ ፡ አዳም ትእዛዝ ቢያፈርስ በአዳም ላይ እንዴት ያለ ጽኑ ፍርድ የፈረደበት እግዚአብሔር አምላክችንን መስሎ መንግሥት ሊሰፋበትና ሕዝብ ሊጠቀምበት የወሰነውንና የደነበውን ትእዛዝ እንዳይመለከቱ ማማለጃና ጉቦ ለመቀበል ልባቸው የተደፈነ ሹማምንት ቢገኙ ለቅጣት አሳልፎ ቢሰጣቸው ነው ። እንደዚህም ማለቱ ከሹመታቸው ይሻሩ ቀል አይደለም አዳም የፈጠረውን ንጉሥ ትእዛዝ ቢያፈርስ ያለድካም ሊመግበው የተዘጋጀለትን አጥቶ በሕይወተ ሥጋ ሳለ ወጥቶ ወርዶ ወዙ ተንጠፍጥፎ እንዲመገብ ከሞተ በኋላም ወደሲኦል እንዲወርድ ነውና የፈረደበት እንደዚሁ ሁሉ በሰማያዊ ንጉሥ ምሳሌ የተቀመጠ መንግሥታችንም ትእዛዙን በሚቃወሙ ሁሉ ላይ ትእግሥትና ርኅራኄ ሊያደርግላቸው አይገባውም የፈጣሪውን ትእዛዝ እየጠበቀ መንግሥቱ የሚሰፋበትንና ሕዝቡ የሚጠቀምበትን ትእዛዙን ከመጠበቅ የራቁትን ሁሉ ትእዛዙን ከማፍረሳቸው አስቀድሞ በተድላና በደስታ ይሠሩት የነበረ ሥራቸውን በመፍራትና በመንቀጥቀጥ ያለ ዕረፍት እንዲፈጽሙት ያድርጋቸው ስል ነው ።

የመንግሥታችን መልሚያ የሕዝባችን መጠቀሚያ መስሎ የታየኝ ይኸ ምኞቴም ለሰው ሁሉ የተሰጡ ሀብታት የሚገኙበትና የሚሰበሰቡበት መሆኑን የሚያስረዳ ምስክር የሚፈልግ ቢኖር ። ምቀኝነት ነግሦባቸው በነበሩ ወንድሞች እጅ ተሸጦ የነበረ የዮሴፍን ታሪክ የሚነግሩ ቃላት አሉለትና ኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ ፵፩ና ደግሞ ምዕራፍ ፵፯ ቍ ፲፫—፳፮ ልብ አድርጎ ይመልከት።ይኸ ስደተኛ ሆኖ በሰው አገር የነበረ ዮሴፍም በምስር አገር በፈርዖንዘንድ እግዚአብሔር ያዘጋጀለትን ሥልጣን ከተቀበለ በኋላ በምሥር አገር የሚገኘውን እህል በያይነቱ በከተሞችና በየገሩ ዙሯ ማንም ሠፍሮ ሊቆጥረው እንደማይችል አድርጎ አከማችቶ ፡ ብዙ ገንዘብና ከብት እያላቸው እህል ከማጣታቸው የተነሣ ሕይወታቸው ልትጠፋ የቀረበች ብዙ ወገኖችን ከዚህ ከሰበሰበው እህል ሸምተው እንዲመገቡ በማድረጉ ለፈርዖን በዚያ ዘመን ከነበረ የበለጠ ሀብትና ብልጽግናን እንዳዘጋጀለት ማንም አይስተውም

እንግዲህ የዚህን የዮሴፍን ለፈርዖን የታመነና እጅግ የሚያስደንቅ አገልጋይነቱን የሚያመለክቱ እነዚህን ቃላት ከነበብን በኋላ፡በገራችን ውስጥ ያሉ ሹማምቶችን በየውራጃው ከጭቃ ሹሞች አንሥተን እስከ ታላላቆቹ ድረስ ብንመለከታቸው ይኸንኑ የሁላችን መጋቢ የሆነ ገበሬን የሚያጐላሉ ብዙ ጭፍሮች አሰልጥነው ጊዜ ያለው እርሻውን ከጊዜው አሳስተው ከማጕላላት በቀር ሌላ ለሕዝብ የሚጠቅም አዲስ ደምብና ሥርዐት አውጥተው መንግሥታቸውን የሚያስከብር ምኞት እንኳ እንዳላቸው የሚመሰክር ሥራ እናገኝባቸው መስሎ አይታየኝም ። ሲያለሰልሰው የከረመውን መሬት ዘር የሚዘራበት ወራት በደረሰ ጊዜ ግን የእገሌ ተዝካር ነውና ዱቄት ጭነህ ወደ እገሌ አገር ሂድ የሚል ትእዛዝ ብቻ ሰጥተው ዘሩን ሳይዘራበት እንዲቀር ማድረጋቸውን የሚመሰክሩ ብዙ ምስክሮች እናገኛለን ።

እንደዚህ የሆነበት ምክንያቱ ምን ይሆን ብሎ የሚጠይቅ ሰው ቢኖር የራስን ጥቅም ከመፈለግ የተነሣ (ባልንጀራህን እንደ ነፍስህ ውደድ) የሚለውን ቃል ረስቶ መማለጃና ጉቦን መቀበል ነው ። ከእንደዚህ ያለ ስሕተት የሚያደርስ የሚል ምላሽ ይገኝ ይመስለኛል ፡ የሀገር ልማድ ስለ ሆነ ትንሹም ትልቁም ሊያገኘው የሚመኘው ያገኙትም ሹማምቶች የሕዝብን ጥቅም ፈልገው ትክክለኛ የሆነ እውነተኛ ፍርድን እንዳይፈርዱ ልባቸውን የደፈነ የጉቦን ነገር ከዜህ ማስታወሴ ጊዜ ስላጋጠመኝ መንግሥታችን አገር የሚለማበትና ሕዝብ የሚጠቀምበትን ብዙ አይነት ማዕርግ አዘጋጅቶ የቤተ ክህነቱን በቤተ ክህነት ፡ የቤተ መንግሥቱን በቤተ መንግሥት ሊያዙና ሊናዝዙ ሹሞ የሾለማቸው ሁሉ በዜህ በከንቱ ልማድ እየተንደዱ ሕዝብ የሚጠቀምበትን አስበው አለመሥራታቸው ቢያሳዝነኝ ነው እንጂ ፡ በጉቦና በመማለጃ ምክንያት በየገሩና በየአውራጃው የሚደረገውን ግፍ ሁሉ በያይነቱ ለመጻፍ የሚችል ኃይልና ዕውቀት አግኝቼ አይደለም ፡ እኔስ የኢትዮጵያ ተስፋ ልዑል ተፈሪ መኰንን ከሰው ልቡና ድንቁርና ጨለማን የሚያርቁ ቅዱሳት መጻሕፍትን ሊያሳትሙበት በፀሐይ ምሳሌ ካቆሙት ማተሚያ ቤት ውስጥ የሚወጣ ብርሃንና ሰላም የሰውን አሳብ ገልጦ የሚያሳይ ስለሆነ፡መኖሬዬ የማይታወቅ ፍጹም ድኅነቴን ሳውቀው ፡ የፈቀደውን ለማድረግ ሥልጣን የተቀበለ ሰው መስዬ በየውራጃው ሁሉ ካሉ ገበሬዎች ድካም

ከሚገኝ ሀብትና ብልጽግና የተነሣ መንግሥታችን ወደ ዓለም መንግሥታት ሁሉ የሚደርስ ልዕልና ያለው የንግድ ማኅበርን ለማቆም በሁሉ ዘንድ የተወደደ ሥልጣን አለው የሚል ምኞቴን አምልቶና አስፍቶ ለመጻፍ ዕውቀቴ ስላነሰብኝ ብዙ ተቸግሬሁ

አሁንም የሁሉን ምኞትና አሳብ የሚፈጽም እግዚአብሔር አምላካችን ነውና የተጀመረውን እንዲፈጽም ያልተጀመረውን እንዲያስጀምር ለመንግሥታችን ኃይል ይስጥልን እያልኩ ብርሃንና ሰላምን ለሚያነቡ ክቡራን አንባቢዎች ሁሉ ምኞቴን በትሕትና አቀርባለሁ ።

ወልደ ጊዮርጊስ ደለለኝ።

ስለ ዕውቀት ሥራ መስማማት ።

ኢትዮጵያ ቀድሞ በኦሪት ሕግ ቀንታ በኋላም በወንጌል ሕግ ጸንታ መንፈሳዊ ጥበብ ሃይማኖትን ጾም ጸሎትን ስግደትን እንግዳ መቀበልን ቸርነትን ይህን የመሰለውን ሁሉ የበጎ ትሩፋት አከናውና የምትሠራ በመንፈሳዊ ጥበብ ረገድ ከዓለማት ሁሉ ከፍ ያለች የተመሠከረላት ናት ነገር ግን በሥጋዊ ጥበብ ረገድ በዙሉ ከውጭ አገር እንደ ምንሰማው ወሬ በጥበብ ሥልጣኔ ከደረጁ መንግሥታት ጋራ አስተካክሎ ለመጻፍ ሲቸግረን ሲኖር በአምጣነ ጽልመታ ከማሁ ብርሃና እንዲል በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ዘኢትዮጵያ ሐዋብ በልዑል ተፈሪ መኰንን ጥበብ ከሁን ቀድሞ ያልታየ የእውቀት ብርሃን አበራልን ውጋጋኑም የሚያንጸበርቅ ጨለማ የማይሸንፈው ባህር የማይጋርደው ነውና በውጭ አገር ለሚኖሩ ወንድሞቻችን ብቅ ብሎ ጭላንጭሉ ቢታያቸው በዚሁ በታየው በሰሌዳ ብርሃን ላይ ለሃገራችን ጥቅም የሚሆን ነገር የጻፉ ሰዎች ብዙዎች ናቸው ደግሞ ለጥበብ ትምርት ቤት እርዳታ ብለው ገዘንብ የሠጡ አሉ እንደዚሁ ሁሉ ፈርማቸውንም ፈርመው እንደ አቅማቸው ገንዘብ እንረዳለን ያሉ አያሌ ሰዎች ይሆናሉ ። ምድረ ገነት ዳግሚት ሰማይ ኢትዮጵያ ሆይ አብሪ አብሪ ደስ ይበልሽ እንግዴህ ልጆችሽ ኢትዮጵያውያን ሀብታም በከብቱ ደሀ በጉልበቱ ካህን በትምርቱ አዋቂ በእውቀቱ እንደ አንድ ልብ መክሪ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ ሆኖ እውቀትን ለማስፋት እርስ በርሱ ተስማምቶ የቀድሞ ልጆችሽን ሲጐዳ የኖረ ምቀኝነት የሚባል ጠላትሽን አጥፍቶ አሁን እንደምናየው ውጥን ሁሉም በሚቻለው ነገር ከተረዳዳ ይህ ምኞት ወደታላቁ ሥጋዊ ጥበብ ሥልጣኔ ደረጃ በቶሎ እንዲደርስ ያለጥርጥር እርግጥ ነው ደግሞ ክቡር ወንድማችን ፊታውራሪ ዴረሳ እንዳሰቡት የተማሪ ቤትን በቶሎ ለማቆም የሚረዳ ነገር ለኔ እንደሚመስለኝ በኢትዮጵያ መንግሥት ግዛት ውስጥ በቀላድ ካልተለካውና በፊሃ ካልሆነው ምድር በቀር በቀላድ ተለክቶ ለሰው የተሠጠው ሥራ ፈቶ የሚኖር ሰፊ ጋሻ ምድር አይታጣም።ሕዝቡ በዓመት በዓመቱ በአንድ ጋሻ ምድር አንድ አንድ ብር ለትምርት ቤት እርዳታ በመንግሥት ትእዛዝ ያወጣ እንደሆነ በየራሱ ፈቃድ ከሚወጣው ገንዘብ ጋራ ብዙ የትምርት ቤት ሳያቆም አይቀርም ይህም አሁን ያልኩት የተማሪ ቤት እርዳታ ገንዘብ አወጣጥ በመንግሥት ትእዛዝና ደምብ ቢሆን ይሻላል ። ጠያቂ እንደምን ያልከኝ እንደሆነ በሃገራችን በጣም ባይበዛ አልፎ አልፎ አንዳንድ ሰው የቀደሞው ልማድምንም መጥፎ ነገር ቢገኝበት ቢለወጥና ቢሻሻል የማይወድ ይታጣ አይመስለኝም ። ሁለተኛ በሃገራችን እስላሞችና አረመኔዎች ብዙዎች ይገኛሉ በራሳቸው ፈቃድ ገንዘብ አውጥተው የትምርት ቤት ያቆማሉ ለማለት እጅግ ያስቸግራል ስለዚህ በመንግሥት ትእዛዝ የሆነ እንደሆነ የኢትዮጵያ መንግሥት ዜጋ የሆነ ሁሉ ክርስቲያን እስላም አረመኔ ሳይለይ በትክክል እርዳታውን እንደ ደንቡ ቃል ያወጣል ለጌዜው ቅር የሚለው እኳን ቢኖር በኋላ የትምርት ቤት ከቆመ ዘንድ በእውቀት እየሠለጠነ የሃገር ፍቅርን የጥበብን አኳኋን ጣዕሙን እያወቀው በአንድ ጋሻ መሬት አንድ ብር ማውጣቱ ይቅርና ያለውን ንገዘቡን ሁሉ ለትምርት ቤት እርዳታ ይሁን ለማለት አይመለስም ።ስለዚህ የሚያስረዳ ሁለት ምሳሌ አለ አንደኛ አሁን ለጊዜው ኮሶ መሪር ነው ለዓይን የሚገርም ለጉሮሮ የሚመር መሆኑን ማንም ሰው ያውቀዋል ። ሰው በጠጣው ጊዜ መልኩ ጠቁሮ ጉልበቱ ደክሞ ይውላል በሶስተኛው በራተኛው ቀን የታየ እንደሆነ ደም ግባቱ አምሮበት ኃይል ተሰጥቶት ይገኛል ። ሁለተኛ ምሳሌ አሁን የሀገራችንን ትምርት አልማርም ዳዊት አልደግምም ብሎ ሳይማር ሳይመረምር የቀረ ልጅ የትምርት ዘመኑ ካለፈ በኋላ ምነው አባቴ እጄን በሰንሰለት እግሬን በግር ብረት አሥሮ አስተምሮኝ በሆነ እያለ ይፀፀታል አባቱም እንኳን በተማሪ ቤት አሥሮ ስለ አላስተማረው በእውቀት ከጓደኞቹ ስላነሰ ያባቱን ነፍስ አይማር እያለ በሕይወቱ ዘመን ሁሉ ሲረግመው ይኖራል ።

የተማረ ልጅ ግን ያባቱን ሥጋውን በምድር ያለምልም ነፍሱን በሰማይ ይማር እያለ ሲመርቀው ይኖራል ስለዚህ ግርማዊት ንግሥታችንና ልዑል አልጋ ወራሻችን ደንብ አድርገው ባመት ባመቱ ባንድ ጋሻ ምድር አንዳንድ ብር እየወጣ የትምርት ቤት እየቆመ የሀገራችን ልጆች የተማሩ እንደሆነ ዕውቀት እየሰፋ ድንቍርና እየጠፋ ይሄዳልና የንግሥትን መንግሥት ያስፋልን የልዑልን ዕድሜ ያርዝምልን እያለ ሲመርቅ ይኖራል አሁን ባንድ ጋሻ ምድር ላይ የሚኖር ትውልድ ከሁለት እስከ አስራ ስድስት አይታጣም እንግዴህ ገንዘብ ያወጣ እንደሆነ ድርሻው አንዳንድ መሐልቅ ይሆናል ከዚህም ቢያንስ እስከ ስምንት ትውልድ አይታጣም ድርሻውም ሁለት ሁለት መሐልቅ ይሆናል እንግዲህ አሁን እንደተባለው ባንድ ጋሻ ምድር አንዳንድ ብር እየወጣ በማኅበር የትምርት ቤት ብናቆም የሚያገኘን ጉዳት አንዳች የለም የሀገርን ጉዳትና ድንቍርና የሚያመጣ የትምሕርት ማነስና ልማድን አለማሻሻል ነው እንጂ የተማሪ ቤት ማቆም አይደለም ።

ክቡራን ወንድሞቼ ሆይ የትም ተወለድ እንኮበር እደግ እንደሚባል ፡ የከተማ ሕዝብ የሠለጠነ ነው ሲሉ እንሰማ ነበር አሁን በከተማችን ውስጥ በሀገራችን መንግሥት ስም የተሠራውን ብርና አላድ ሩብ መሐለቅ አንቀበልም የሚሉ ነጋዴዎችና ቸርቻሪዎች አሉ ። ይህ መሆኑ ምንድር ነው ፡ የንግድ ሥራ ባለማወቅና ከጥበብ ሥልጣኔ መጕደል ነው ፡ ከዚህ አስቀድሞ የትምርት ቤት ቁሞ የንግድና የሒሳብን የሀገር አስተዳደርና ደምብ አውቆ ቢሆን ፡ የሀገሩን ገንዘብ ባልነቀፈም ነበር ፡ ያገሬ ሰው ባለቤቱ ያቃለለውን አሞሌ ባለ ዕዳ አይቀበለውም ሲሉ

ይህን ተረት ትሰማለህ ይህ ፈረንሳይ ነው ፡ ይህ ጥሩ ነው ፡ እያልኽ ያገርኽን ገንዘብ አዋርደኽ በውጭ አገር ስም ብታወ ማለት ሰው ያለ ስሙ ቢጠሩት አቤት እንደማይል ምሳሌ ይሆንብኻል ።አሁን በሙሉ አውሮፓ ያንዱን መንግሥት ገንዘብ ወዳንዱ ሲተላለፍ ርካሽ ይሆናል ይባላል እንጂ በሃገሩ ላይ ሆኖ እንኳን በውጭ አገር ስም ይጠራና ከበሬታው ከሌላው መንግሥት ገንዘብ ሶስትና አራት እጅ ይሆናል ይባላል ። ይህም በዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ስም የታተመ ግርማዊ አንበሳ ያለበት ገንዘብ ሁሉ የሃገራችን ዓይነተኛ ገንዘቦችን እንደሆነ በግልጽ የታወቀ ነውና ለመንቀፍ አንችልም ይኸነንም ቃል በጋዜታ ማስታወቂ የሃገሬ ነጋዶች ያለፈውን ስሕተት እንዲረዱት ነው እንጂ ለወደፊቱማ ልጅ ያለው ልጁ እየተማረ ልጅ የሌለው ራሱ እየተመራመረ የትምሕርት ቤት ከቆመ እንደሚቻለው በዕውቀት በኵል ይሰንፍ አይመስለኝም ግን በልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ጊዜ ልጁን ሳያስተምር እንደ ቀድሞው ዘመን በብልግና በማቀማጠል አኖረዋለሁ የሚል ሰው ቢኖር ወዮለት ለዚያ ሰው ከላይ እንደ ተጻፈው በሕይወቱ ዘመን ሁሉ በፀፀት ይኖራልና እግዚአብሔር በግርማዊት ንግሥትና በልዑል አልጋ ወራሽ አድሮ ያስጀመረውን የብርሃን ጥበብ ጽርጊያ ጐዳና የኢትዮጵያን ልጆች በሰላም እንድንሄድበት ያብቃን አሜን ።

በቀለ አበዬ ያባታችን አጋፋሪ ።

የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ወደ ደብረ ሊባኖስ መሔድ ።

በኅዳር ፳፰ ቀን ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ወደ ደብረ ሊባኖስ ሊሔዱ ተቆርጦ ነበርና ማታውን በልዑል ግቢ አድረው አብረው ለመሔድ የታዘዙ መኳንንት ፡ ክቡር ራስ ስዩም ክቡር ራስ ናደው ፤ ደጃዝማች ወንድ ይራድ ፡ ደጃዝማች ገድሌ ደጃዝማች ስዩም ሉልሰገድ ፤ ቀኛዝማች ዓምዴ ፤ ደጃዝማች ወልደ ሥላሴ ፤ ፊታውራሪ ደስታ ዳምጠው ፤ ፊታውራሪ አደፍርሰው ናቸው ።

ከሌሊቱ በ፲ ሰዓት ተኩል ፲፱ አውቶሞቢል ተቀጣጥሎ መጓዝ ተጀመረ እንጦጦ ዳገት ላይ ጥቂት የሴትሮዋ አውቶሞቢልና የፎርድ አውቶሞቢል መውጣት ሲያውካቸው በቀር የቀሩት የፊያትና የረኖ አውቶሞቢሎች በኃይል ወጡ ። በዝግታ ጭምር እየሔዱ ደብረ ሊባኖስ አፋፍ እስቲደርሱ ፊታውራሪ ደስታ ዳምጠው ባልደረባቸውን የፈረስ ዘበኛውን ያንዳንድ ሰዓት መከተል አዘውተ ኑሮ በልክ በልክ ቦታ እየተሰለፈ እየሸኘ ከተወሰነበት ቦታ ሲደርስ ተተኪውና ተመላሹ በንድነት ማማሩ ግሩም ነበረ ።

የልዑል አውቶሞቢል መንገዱን ጨርሶ እደብረ ሊባኖስ አፋፍም በደረሰ ጊዜ ባንድ ወገን ፊታውራሪ ገብረ ማርያም አጋፋሪ ወልደ ማርያም ከነሰዋቸው ተሰልፈው አምረው በቀኝ በኵል ሁነው ይጠብቁ ነበረ ። ባንድ ወገንም ደጃች ወንድ በወሰን ከክቡር ራስ ካሣ ታዘው ለመቀበያ በቅሎች አሰናድተው ተሰልፈው ሲጠብቁ ልክ በ፯ ሰዓት ደረሱ ።

ደጃች ወንድ በወሰንም እጅ ነስተው ተገናኝተው ቁልቁለቱን መውረድ ተጀመረ ።

የክቡር ደጃዝማች ማሞ እድል ።

ቁልቁለቱን ጨርሰው ከሜዳዋ ሲደርሱ ልጅ ግርማ ማሞ ክቡር ራስ ካሣ ደጃዝማች ወልደ ጻድቅ ባንድነት ሆነው አልጋ ወራሽ ወዳሉበት ቀረብ ብለው እንደሚገባው ተላቅሰው ። አጽሙ ወዳለበት ቀርበው አራግበው ሲላቀሱ ቆዩ የካህናቱ ማማርና የፍታቱ መድመቅ ድንቅ ሆኖ ይታይ ነበር ፤ በኋላም ፍታቱ አልቆ ከቤተ ክርስቲያኑ አሳልመው በክርስቶስ ጉባዔ እስከምንሰበሰብበት ማቆያ አረፉ ። ልጅ ግርማ ማሞ ያባቱን አፅም በሕይወት ያሉ አስመስሎ ከገሙ ድረስ አምጥቶ በለቅሰውም ጊዜ ሰዉ ዝብርቅርቅ ሳይል የደስታ ቀን መስሎ ፈረስ በቅሎው አምሮ ተጭኖ እምቢልታው እየተነፋ በማከናወኑ እጅግ ተመሰገነ።እነሆ መልካም ልጅ የመውለድ ፍሬው እንዲህ ነው ። ቅዱስ ዳዊት ወዘኢያጽአለ አዝማዲሁ እንዳለው ።

ከቀብርም በኋላ ክቡር ራስ ካሣ ለልዑል መስተንግዶ ወዳሰናዱት ዳስ ገብተው ልዑልም ኃዘንተኞቹን ተገናኝተው እነርሱም የዚህ ዓለም ሰው ኩራቱና ደስታው እስከዚህ ድረስ ነው እግዚአብሔር ውለታዎን ይክፈልዎ ብለው አመስግነው ግብር ገባ እጅግ ያማረ ድግስ ለተከታዩም ለኃዘንተኞቹም በተለየ ቦታ ሆኖ ተበላ ። ይህ ለሟቹ ኃዘን ለቆመው ደስታ የሆነ ቀን በመልካም ተፈጸመ ።

ማክሰኞ በ፳፱ ቀን ልዑል ያሠሩትን የንዳያን መጦሪያ ቤተ ሰሊሆምን ጐብኝተው በ፪ሰዓት ተኩል ከክቡር ራስ ካሣ ተሰነባብተው ካፋፍ ተነሱ፤ፈረስ ዘበኛው እንደ ትላንቱ እያማረ ትእዛዙን ፈጽሞ አሳለፈ።

ስሉልታ ሲደርሱ ድንኳን ተተክሎ የልዕልት ወይዘሮ መነን ድግሥ ተከታዩንም ተቀባዩንም ደስ አሰኝቶ ተበልቶ በ፲ሰዓት ተኩል ከልዑል ግቢ ደረሱ ።

አንባቢ ሆይ ። ደብረ ሊባኖስ የሶስት ቀን መንገድ ነበር ርቀቱ አያስደንቅም፤ነገር ግን በሶስቱ ቀን መንገድ ድንኳን ተተክሎ ተከታዩ በልቶ ፈረስ በቅሎው ገፈራ ሣር በልቶ ነበር አዳሩና ጉዞው ፡ እስቲ የባላገሩን ችግር ምንም ዘርዝረን ባንጽፈው በየልባችሁ ገምቱት ። ይኸን ከባድ ሸክም ከባላገሩ ከሕዝባቸው ለማቅለል መንገዱን አስጠርገው ፡ ጉዳዩ ፫ ቀን የሚያበላሸው በ፩ ቀን እንዲፈጸም ላደረጉ ለልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ዕድሜ ሰጥቶ ሐሳባቸውን ያስፈጽምልን ማለት ይገባናል ።

ሄራልድ ከሚባል ከአሜሪካ ጋዜጣ የተገለበጠ ። የሚያስደንቅ ማጥናት ።

በዓለም የነበሩ ታላላቆችና ታናናሾች ሰዎች ይህ ኅብርሆ ለማለት ለማይቻል የማጥናት ምሳሌ ሆነዋል ። አጋሲዝ የተባለ ዝናው የታወቀ የፍጡራንን ባሕሪ ሁሉ የሚያውቅ ፤ አምስት ሺ ልዩ ልዩ የሆኑ የአራዊትና የእንስሳ ስም ለይቶ ያውቅ ነበር እንዲሁም አሣ ግሬ የተባለ የአሜሪካን የአታክልትን ባሕሪ ሁሉ መርምሮ የሚያውቅ ስምንት ሺ አታክልቶች በስምና በመልክ ያውቅ ነበር ቴሚስቶክሌስ ፳ ሺ ከተማ ኑዋሪዎች ስም ያውቅ ነበርና ስለዚህ እርሱ በነበረበት ዘመን አቴና ዲሬክተር እምብዛም አላስፈለጋት ። እንድ ሞዛት የተባለ ሰው ነበርና የማናቸውንም

ዜማ አካሄድ ሁለት ጊዜ ከወጡለትና ከደመጠ በኋላ ከጫፍ እስከ ስር በአንጻፍታ አጥንቶ አስተካክሎ ብቻውን ይዘምረው ነበረ ። ብዙ ዘማሪዎች እንዲሁ በማድመጥ ብቻ አጥንተው ከጧት እስከ ማታ ለመዘመር ይችላሉ ። ከመሬ ጌቶችም የሚበዙት መምሬታቸውን እንዲያው ያለ ሙዚቃ ያስኬዱት ነበር ። ጆርጅ ባይደር የተባለ ከበርቱ በሎንዶን ይኖር ነበር እርሱም በ፲፰፻፸፰ ዓመተ ምሕረት ሞተ ። ዕድሜው ፲ ዓመት ሲሆን በ፪ት ደቂቃ የአራት ሺ ዓርባ አራት ጂኒ ወለድ በ፬ሺ ፬፻፵፬ ቀን በመቶ ሁለት ተኩል ጂኒ ሲወልድ ምን ያህል እንዲሆን አስቦ አወጣው ። በ፸ ዓመቱ ከሞቱ በፊት ሁለት ቀን ሲቀረው በአንጻፍታ ፲፫ አይነት የሚሆን የቊጥር አካሄድ አወጣ ይህም ቊጥር በጣም የሚጠቅም ሆነ ። ብዙ ሰዎች በቃል ለማጥናት የተሰጠ የሚያስደንቅ ችሎት አላቸው ። ካጠኑትም በኋላ በአዕምሮዋቸው ተጣብቆ ይኖራል ። አንድ በኢጣልያን ተማሪ ቤት የነበረ (ፕሮፌሶር) ሊቅ ምስጢረ መለኮት የሚባል ታላቅ መጽሐፍ በቃሉ አጥንቶ ሳያሳስት ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ሳያቋርጥ አነበበ በ፭ ሰዓት ዘለቀው ። ከዕለታት አንድ ቀን በአፍሪካ የሚኖር አንድ ወንጌላዊ ለባላገሮች ጉባኤ ሲያሰማ አንድ ጉልማሳ ተቀምጦ ያዳምጥ ነበርና ጉባኤው ተነግሮ ከተጨረሰ በኋላ እንደገና ሌላ ሰዎችን ሰብስቦ የሰማውን ስብከት እንደ ሰማው አድርጎ ሳያሳስት ቃል በቃል ነገራቸው ።

ስለ ገንዘብ ሥራ አጀማመር ።

አስቀድሞ መዓድኖች እንደ ገንዘብ ተሰርተው መግዣና መሸጫ ሳይሆኑ እንዲያው ይመዘኑ ነበሩ፡ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሂሳባቸውና ሚዛናቸው በያንዳንዱ ገንዘብ ላይ የመቅረጽ ብልሃት ተለመደ ይኸም ብልሃት የወርቅ ጂኒና ሼክል (ድሪም) የተባለ የአይሁድ ገንዘብ በሚገኙበት አገሮች በሶርያና በባቢሎን ነው መጀመሪያው። በ፯፻ ዓመትከክርስቶስ በፊት በዮናኒ የነበሩ ግሪኮች ገንዘብን ለመሥራት በአስፈለገው አሳብ ቀደምቶች ናቸው በየገንዘቡ ላይም ያገራቸውን መሣሪያና ማኅተም ይቀርጹበት ነበር፡ለሕዝባቸውም የገንዘቡ ሚዛን ዋጋው ትክክል መሆኑን እስታውቀው አላፊነትም ነበረባቸው ። ይኸም ልማድ በቶሎ ተስፋፋ የገንዘብም ቀደምት የነበረው የባቢሎን የወርቅ ድሪም ነው ። የዛሬውም ዘመን ገንዘቦች የሚበዙት ሚዛናቸው የሚሠራው ጥንት ባቢሎናውያን በወጠኑት አካሄድ ነው ። ከገንዘብ መሠራት በፊት ስለ መግዣና መሸጫ ብዙ ነገሮች ስለ ገንዘብ እየሆኑ ይገበያዩባቸው ነበር እስከ ዛሬም በንዳንድ ባልሰለጠኑ አገሮች ይነግዱባቸዋል የኛንም የአሜሪካንን ሂንዲዎች ከዛጐል የተሠራ መታጠቂያ እንደገንዘቢሁኖ ብዙ ጥቅም ያደርግላቸው እንደ ነበረ ምሳሌውን አግኝተነዋል ። ደግሞ ከባሕር ቅርፊት የተቀረጹ ልካቸው ልዩ ልዩ የሆነ በህንዲዎች መካከል ይገኙ ነበር እንዲህም ሆነው የተቀረጹት ገንዘቦች በገመድ ይሰኩ ነበርና ይህም ገመድ በመንግሥት ሕግ እንደ ቆመ ገንዘብ ተቆጥሮ ሕዝቡም እንዲቀበሉት የግድ ነበረባቸው ። ይኸንንም የዛጐል ዓይነት ገንዘብ ሁሉ በአፍሪካ ክፍሎችና በእስያ ክፍሎች በፓሲፊክ ደሴቶችም እንደ ገንዘብ አድርገው ይገበያዩበታል ከአሸዋም ውስጥ የሚገኙትን ቅርፊቶች ሁሉ ባላገሮች እንደ ገንዘብ እየቀረጹ በሐር ገመድ እየሰኩ በአንገታቸውና በወገባቸው ያስሩታል ከባላገሮችም አንዱ ሚሊዮኒር የሆነ እንደሆነ እርሱ ባንድ ወገን ገንዘቡ ባንድ ወገን ተደርጎ ከክብረቱ ጋራ ይመዘዘናል ። በሳንታ ክሩዝ ደሴት ውስጥ የሚኖሩ ሕዝብ ገንዘባቸው ከፓሮት (ከቀይ ወፍ) የሚገኝ ላባ ነው ። ይህችንም ወፍ ለመያዝ እጅግ ችግር አለባቸው ግማሾቹም ገንዘባቸው ሩዋጭ ከሆነ ቀበሮ ጠጉር የተሠራ ነው ። አንዳንዶቹም ከነጭ አሞጫ የተሠራ ፊግፍገው አስተካክለው ይገበዩበታል ። እኩሌቶችም ከሳር የተሠራ ገሣ ሥርተው ስለ ገንዘብ ያደርጉታል ። የኢትዮጵያም የጨው ቅርጽ (አሞሌ) ስለ ገንዘብ ይቀበሉታል ። በአፍሪካ ውስጥ ከባድ የዘሆን ጥርስ አምባርና ከናስ ወይም ከመዳብ የተሠራ የግር አምባርና የናስ አምባር ይገበይበታል ። ደግሞም ለጌጥ ይረባል ፤ እነዚህም የግርና የእጅ አምባሮች የሮም ቄሣር የእንግሊዝን አገር በወሰደ ጊዜ ያገኛቸውን የምስራውያንን ገንዘቦች ይመስላሉ ። በአፍሪካም በአንዳንዱ ክፍሎች ከመዳብ እየሠሩ ስለ ገንዘብ ወይም መሥኘ ያደርጉታል ። ከመዳብ ወይም ከነሐስ የተሠሩ ዘንጎች ደግሞም የሚያበሩ እንደ መቁጠሪ ሁነው የተሠሩ በአፍሪካ ክፍል ውስጥ ዋና መገበያያ ገንዘብ ሁነው ይገኛሉ ።

ስለ ስልከኞች ምክር የሚሆን ሄራልድ ከሚባል ጋዜጣ የተገለበጠ ቃል።

በስልክ ሲነጋገሩ የሚደረገው የትሕትና ንግግር እንደ ሌላው ትሕትና ሁሉ የሚያስፈልግና የተወደደ ነገር ነው ። በስልክ የሚደረገውን የትሕትና ንግግር ሁሉ ከቶ የሚተከከለውና የሚበልጠው ነገር የለም በሥራም ውስጥ ያለውን መልካም ፈቃድ እያዳበረ ያስኬደዋል ። ስልክን በደወልህ ጊዜ ወይም በተደወለልህ ጊዜ ምን ዓይነት ሰው እንደሆንህ የምታደርገው ነገር ጠባይህን አስፍቶ ይገልጽብሃል ።ሰዎችም ያንተን በስልክ አደራረግ አይተው አገልግሎትህን ሊረዱት ይችላሉ ።ክፉም ጠባይ ቁጡነት እንዳለብህ ወደትሕትና ወደ ትዕግሥት ለውጠው ።እንዲህ ካላደረግህ እስከ ዘመንህ ፍጻሜ ተጣብቆብህ ይኖራል በስልክም ስትነጋገር ፊትህ ብሩህ ይሁን ።እንዲህም ያደረግህ እንደሆነ የምታነጋግራቸው ሰዎች ትሕትናን ይረዱታል። የብልግና ንግግር ከሚናገሩት ሰው ይልቅ ተናጋሪውን ይጐዳል በተደረገልህም ቸርነት ለምታመሰግነው ምስጋና ገንዘብ አታወጣበትም ይህነንም የሚያደርጉ ሰዎች መልካም አስተዳደግ ያላቸው ናቸው ይባላሉ ። ትሕትና ዋጋው የከበረ ሊገመትም የማይቻል ነው።ነገር ግን ምንም ዋጋ አይከፈልበትም በሰላ መላስ ከቆሰለ ቊስል ይልቅ ፤ በካራ የቆሰለ በቶሎ ይድናል አዕዋፍ በእግሮቻቸው ይጠመዳሉ ሰዎች ግን በመላሳቸው ይያዛሉ።መልካም ንግግር እንደ ክፉው ይበዛል ትሕትናን የሚዘራ ወዳጅነትን ያጭዳል (ያመርታል)ትሕትና የሚሰጡትን ሰዎች ከልናቁ ተቀባዮች ይበለጽጋሉ።ክፉ ንግግር እንደ ተባይ ነው በስልክ ነውና አያውቀኝም አትበል በሌላ ቦታ ሁኖ በስልክ የሚያነጋግርኅን አጠገብህ እንዳለ አድርገህ አክብረው የሚፈልገውንም ጉዳይ በቶሎ አከናውንለት ።

ይህን መጻፋችን ያገራችን ስልከኞች እንዲመለከቱትና ያገኙበትን ምክር ለማድረግ እንዲተጉ ደግ ባሕሪያቸውንም ለማበርታት እርዳታ ይሆናቸዋል ስንል ነው ።

በቴሌግራም የመጣ ቃል ።

ማድሪድ ፤ በውሽንፍር ብዛት የተነሣ በጭራሽ ነው እስተ ማለት ድረስ የስልክና የተሌፎን ሺቦ እጅግ ተበላሽቶ ትናንት ማድሪድ ከማንም ይሁን ከውጭ መንግሥቶች በስልክ መገናኘት አቅቷት ዋለች።

ራባት ፤ ተያይዞ ከተነሣ ትልቅ ማዕበል በፌዝ ከተማ ላይ ብዙ ጉዳድትን አምጥቷል። በአሪዮፕላን ሰፈር እንግዴህ ያንድ ሀንጋር (ዳስ) አንድ ክፍል በጭራሽ ፈርሷል። ከአሪዮፕላን ሠራተኞች ፳ ሰው ቈስሏል። የውጭ መንግሥቶች ጭፍራ ሠፈር ብዙ ተጐድተዋል አንዳንድ ቤቶች ፈርሰዋል። ፫ ሰዎች ሙተዋል ፲፫ ቈስለዋል ።

ሮማ ፤ የግሪክ ውጭ ጉዳይ ምኒስትር ከኢጣልያ በተጻፈው ቃል የኢጣልያና የግሪክ ፍቅር የሚያሳይ ስለሆነ ከመንግሥትም ከባላገርም በንግድ ሊስማሙ ናቸው ብሎ ትሪቡና ጋዜጥ ያወራል ።

ኤሰን ፤ በባኩም ዘንድ ካለ ሚኔር የሚወጣበት ላትሪጀን ከሚባል ቦታ ጋዝ ፈንድቶ ፬ ሰዎች ሙተዋል ፲፪ም የቈሰሉ ከነዚሁም ፬ቱ ጠንቶባቸዋል ።

ጄኔብራ ፤ በግሪክና በቡልጋር ማኸከል በተነሣው ጠብ ለመመርመር ከዓለም መንግሥቶች ማህበር የተላኩ ሽማግሎች ሥራቸውን ፈጽመው ወደ ጄኔብራ ተመልሰዋልና ፊራሪስ የተባለ የኢጣሊያ እንደራሴ ኋላ ለዓለም መንግሥት ማኅበር ምክር ቤት ሊነገር ያለው የነገሩን አኳሆን አሁን ለማህበርተኞቹ ሁሉ ልከላቸው ሲያቆም ዛሬ ወደ ኢጣሊያ ደርሰዋል

ፓሪስ ፤ ብሪያንድ በነሐሴ ተቋርጦ ቀርቶ የነበረው የጦር የዕዳ ነገር ለማስነሣት ሹርሺ ከሚባል ሰው ነገ ንግግር ሊጀምር ነውና የዋሺንግቶን መንግሥትም የፈረንሳይ መንግሥትም ምን ሊል እንዳለው ሊያስተውል ነው ብለው ጋዜጦች ያወራሉ

ኢጣሊያ ፤ ለስታቲ ኡኒ በምትከፍላቸው የዕዳ ገንዘብ ሊያነሣ የፈቃደኞችን መቀዳደም አይቶ ማተን ጋዜጥ ኢጣልያኖች ይህነን ሥራ ለመፈጸም የጠነከሩ ሊሆኑ ይገባቸው ብሏል

ሉንዶን ፤ በሾሎዋይ ፕሬዚዳንትነት ታች የሆኑ የኢጣሊያ መልክተኞች ወዲህ ደርሰው ሲያቆሙ የኢጣሊያ አምባሳዶር ከነሰዎቹ ሁሉና የውጭ ጉዳይ ምኒሥትር እንደራሴዎች ተቀብለዋል ።

አርቡሬ፤ ኮንተ ቦልፒ ከሌሎቹ የኢጣልያ መልክተኞች ጋራ ደርሰዋልና የኢጣሊያ ቈንስልም የፈረንሳዊ መኳንንትም በማክበር ተቀብለውታል ። ሚኒሥትር ቦልፒ በሱ መሪነት ሥራውን በደስታ እንዲያልቅ እያመሰገነ ኩሊጅ የሚባል የስታቲ ኡኒ ፕሬዚዳን በሥልክ የላከው ምስጋና ከለይ ከሚባል የስታቲ ኡኒ ጸሐፊ ትእዛዝ ተቀብሎዋል።ኮንተ ቦልፒ ከመልክተኞቹ ጋራ ወደ ፓሪስ ለመሄድ ይነሣልና ለሚመጣው እርብ ሮማ ሊገባ ነው ።

ማስታወቂያ ።

በዓለም ባሉ ጋዜጣ ቤቶች ሁሉ በጋዜጣ እንዲታተምለት እየጻፈ ሰው ሁሉ የሚያቀርበውን ለማተም አለመቻሉ የታወቀ ነው ። አንደኛ ደብዳቤዎቹ ይበዙና ይቈያሉ ጊዜያቸውም ያልፋል ። ሁለተኛ አንዳንዱ ሰው ሐሳቡን እንጂ ዘሩን አይጠነቅቅምና ማረም ያስፈልጋል ስለ ሌላም ምክንያት ቢሆን ።

ብርሃንና ሰላም ያንኑ የተጠራበትን ስሙን ለመፈጸም ነውና አሳቡ ጸሐፊዎቹን ስለምን የኛ ሳይታተምልን ቀረ ብሎ መጠየቅ እንደማያስፈልጋቸው እናስታውቃለን ።

ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት ።

ማስታወቂያ ።

በርሻና በመስሪያ ሚኒስትር ሥራ ውስጥ መንግሥት ያወጣውን ደምብና ሕግ ሳልተላለፍ ደሀ ሳልበድል ፤ የመንግሥቱን ገንዘብ በጥንቃቄ ሠርቼ ቀድሞም ከሚሠራው ሠራተኛ ገቢ ገንዘብ አብልጬ አገባለሁ የሚል ሰው እርሻና እመስሪ ምኒስቴር መጻፊያ ቤት፤ ሁል ጊዜ ከጧቱ ከ፫ ሰዓት እስከ ፮ ሰዓት ድረስ ፤ እየመጣ ቢነጋገር በደስታ እንቀበለዋለን ደመወዙም እንደ ሥራው ገቢ እየታየ ይቈረጥለታል ጥቅምት ፲፮ ቀን ፲፱፻፲፰ ዓመተ ምሕረት ።

መኰንን ሀብተ ወልድ።

ማስታወቂያ

ለራሶችና ለደጃዝማቾች ለሴት ወይዘሮች የሚገባ በያይነቱ ጥሩ ካባ ከኤሮፓ መጥቶልኛል ቤቱም (ባንክ ኦፍ አቢሲንያ) ከእንግሊዞች ባንክ አጠገብ ነውና ይህን ካባ መግዛት ለሚፈልጉ ሰዎች መጥተው እንዲገዙ አስታውቃለሁ።

ኢያሱ ዳንኤል

አ ፔ ማርሲያኖ

በኢትዮጵያና በፈረንሳይ የቅኝ አገር ሶማሊ በተለየ ፈያት አውቶሞቢልና ትራክተር አስመጭና እንደራሴ።



A.P. MARCIANO

Concessionnaire Exclusif pour l'Ethiopie
et la cote française des somalis
des automobiles et tracteurs Fiat.

በልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ

መጀመሪያ ዓመት ፡ ቁጥር ፶፩ ።
1re ANNÉE № 51

ሐሙስ ታሕሣሥ ፰ ቀን ፲፱፻፲፰ ዓ ም።
JEUDI 17 DECEMBRE 1925

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት
Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voi regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraissant tous les jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

የጋዜጣው ዲሬክተር ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።
Gabré Christo Taklé Haymanot
Diréctuer

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ስለ መላው ሕዝብ ጥቅም ።

ሰው ሁሉ የግል ጥቅሙን ብቻ ቢያስብ የጋራ ባይፈልግ የሚረባ ሰው ሊባል አይችልም ። እኛ ኢትዮጵያውያን መንግሥታችን ሊጸና ሕዝባችን ሊሰለጥንና ተስማምቶ በርትቶ ሊቆም የምንወድ ወገን ነን ። ስለዚህ የጋራ ጥቅማችንን ልናስብና ላገራችን ሰው ሁሉ ወደሚገባው ብልጥግና እንዲደርስ በምሉ ልባችን ልንጥር ያስፈልገናል ።

ከዚህ በፊት መስማማትና አብሮ መሥራት እንደሚያስፈልግ በብርሃንና ሰላም ብዙ ጊዜ ተናግረናል ። ግን በጣም ስር እንዲሰድ ሳናቋርጥ ልንነጋገርበት ልንተጋበት የሚያስፈልግ ነው ። በያገሩና በየመንግሥቱ ብዙ ሰው አለ፤ እያንዳንዱ ሰውም በሥጋዊ ሆነ በመንፈሳዊ ለየራሱ ማሰቡ አይቀርም ግን አንድ መንግሥትና አንድ ሕዝብ ተብሎ የተጠራ ሊያስብበትና ቆሞ እንዲኖር በምሉ ኃይሉ ሊመክትበት የተገባ የልቡ ሕዋሳትንም የሚያገናኝ አንድ ነገር አለ።እርሱም የገዛ መንግሥቱ መቆም የሚያመለክት «ሰንደቅ አላማው ነው ። ብዙ ጀግኖች ሰንደቅ አላማቸውን ለመጠበቅና ለማቆም የታገሉ የመከቱ ራሳቸውንም እስከሞት ድረስ መሥዋዕት አድርገው ያቀረቡ በታሪክ እናነባለን ። ብዙ ኢትዮጵያውያንም ስለ ሰንደቅ አላማቸው በጠመንጃ በጦር በጐራዴ በጋሻ መክተዋል ተዋግተዋል ሙተዋልም ስለዚህም ሰንደቅ አላማችን ይኸው ቁማለች ።

እንግዲህ ይህች ጀግኖች የሞቱላት ሶስት ቀለሞች ሰንደቅ አላማችን የሁላችንን ልብና ሐሳብ ማገናኛ ናትና ለማቆምዋ አንድ ልብ ሁነን እናስብ እንሥራም ሰንደቅ አላማችን ቆማ የምትኖርበት መንግሥታችን የሚጸናበት መንገድ በዚህ ዘመን ብትምሕርት በሚገኘው ሥልጣኔና ብልሃት ነው ።

መንግሥቱን የማይወድ ሰንደቅ አላማውም ቆማ እንድትኖር የማይመኝ ኢትዮጵያዊ አይገኝም ። ግን ለየዘመኑ ጦር መመከቻ የሚሆን የዘመኑን መሣሪያ እንደሚያስፈልግ ጥርጥር የለበትም ። አሁን ዘመን የብልሃት ዘመን ነው ስለዚህ ባሁኑ ዘመን ያለ ትምሕርትና ብልሃት መፎከከርና መመከት ይሆንልኛል ማለት እንደ ቀልድ ነው ።

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ይህነን ስላወቁ ትምህርት እንዲስፋ ብልሆች ልጆችም እንዲገኙ ገንዘብዎ ለተማሪ ቤት ያፈሳሉ በሐሳብዎ ሌት ተቀን ይደክማሉ ይሠራሉም የጀመሩትንም በጎ ነገር እግዚአብሔር ሳያስፈጽምዎ አይቀርም ።

ግን ትልቅ ተማሪ ቤት እንኳን ባታቆሙ እንደመጠኑ ተማሪ ቤት ልታቆሙ የምትችሉ ራሶች ደጃዝማቾች ፊታውራሪዎችም የኢትዮጵያም ሃብታሞች ሰዎች ምን ትጠብቃላችሁን?

የገዛ ራሳችሁን ጥቅም ብቻ ባታስቡ።የመላው ሕዝብ ጥቅምና መንግሥት እንዲጸና ሰንደቅ አላማችንም ከነበረችው በበለጠ ክብረት ቆማ እንድትኖር ካሰባችሁ በያውራጃው ተማሪ ቤት ለማቆም ምንም የሚቸግራችሁ ነገር የለም ። ይህን ማለታችን ዝምታችሁ ትዕግሥት አሳጥቶን ነውና አትዘኑብን። በሕይወት ሳሉ ሲቻለው ላገሩ ቁም ነገር አለመስራት ትልቅ ስንፍና ነው።

ትንሽ ለተንቀሳቀሱ ደግሞ ምስጋናችንን እናጕድልባቸውም እርሳቸውም ክቡር ደጃዝማች ሃብተ ማርያም የወለጋ ገዥ ናቸው እርሳቸው ብዙ ልጆች ለማስተማር ብዙ ገንዘብ ሰጥተዋል ባገራቸውም ተማሪ ቤት ለማቆም ቍርጥ ሐሳብ እንዳላቸው ሰምተናል ።

ያገራችን መኳንንት ለሽልማትና ሰፊ ግዛት ለመያዝ ትቀዳደማላችሁ ምነው ይልቅ ለነዋሪ ስም አትቀዳደሙ አትፎከከሩ ብዙ መኳንንትና መሳፍንት ከብረው አጊጠው አልፈዋል

ሲመሰገኑ የሚኖሩ ግን እነዚያ ላገራቸው ነዋሪ ነገር ትተው የሞቱ ናቸው ። ሲቻለው ቁም ነገር ሳይሰራ የሞተ ስሙ ሞተና ተቀበረ ነው።ላገሩ ነዋሪ ነገር አቍሞ የሞተ ግን ምንም ቢሞት ሕያዋን ያመሰግኑታልና ስሙ በሕይወት ከሉ በላይ ነው ።

እንግዴህ ያለፈ አልፏልና አሁን ተስማምተን በትጋት የሚገባንን መሥራት ያስፈልገናል ፤ በጀግንነት ላይ ብልህነት ብገር መውደድ ላይ ትጋትና መስማማት ሲጨመር ስንት ያምር ይመስላችኋል ፤ ስለዚህ ጌታ በጌትነቱ ሠራተኛም በጉልበቱ ወታደርም በወታደርነቱ ላገራችን የሚሆን የስልጣኔ ትምርት ቤትን ለማቆም እንበርታ ፤ እንዲህ ብናደርግ ካሰብነው ለመድረስ ቅርብ ነው ።

ስለ ተስቦ በሽታ የሚስጠንቅቅ ምክር ።

በየመቱ ለብዙ ሰዎች ሞት ምክንያት የሚሆኑ ብዙ ዓይነት የሆኑ ባገር የታወቁ በሽቶች አሉ።አይነተኛውም በሽታ ታይፋስ (ባማሪኛ ቋንቋም ተስቦ) የተባለው ነው ይኸም ከበሽቶቹ አንዱ ሊወገድ የማይቻለው ነው ነገር ግን በኢትዮጵያ ገና አልተወገደም እንዲሁም በኤውሮፓ በንዳንድ አገሮች ውስጥ እንኳ አልተወገደም ደግሞም በሰፈሮቹና በጣም በሰለጠኑት አገሮች በአሜሪክና በእንግሊዝ በፈረንሣዊና በጣልያን በጀር መንም እንኳ ቢሆን ለጤና መጠበቅ ባላቸው በዚያ ሁሉ ትጋት ያልታወቀ ደምበኛ ሆኖ ይገኛል ይኸም በሽታ የሚመጣበት መሠረቱ ከነዚያ ከታናሾች ፍጥረቶች ልብሳቸውን ለማጠብ የማይችሉትንና ድሆችን ከሚያስጨንቁት ቅማል ከሚባሉት ነው፤ደግሞም ከቁንጫም ቢሆን ይመጣል፡ተስቦ የሚነሳበት ነገር እብዛኞኙ ተስቦ ከታመመ ሰው በሚጋባው በቅማል ተጋብት ነው።እነዚህ ከበሺተኛው የተጋቡ ቅማሎች ጤነኛውን በነከሱት ጊዜ የመታመሙ ምክንያት ይጀምራል። የበሺታውም መተላለፍ ዋናው ልማድ እንዲህ ነው።ሰዎች አንድ ላይ ታፍገው በሚተኙበት ቦታ ወይም የበሽተኛውን ጨርቅ ከባለ ጤናው አልጋ ሰር በማስቀመጥ ምክንያት ቅማሉ በጤነኛው ልብስ ይጋባና ሰውዬው በለበሰው ጊዜ በቅማል ተበልቶ ከስምንት ቀን በኋላ በክፉ ራስ ምታትና ትኩሳት ይጀመርና በጣም ይታመማል፤ቅማል እንደ በላውም አያስበው ወይም በጭራሽ ይረሳዋል ነገር ግን ደሐች ትንሽ ፍጥረት ከፏ መርዟን አጋብታለችና ስለዚህ የሞቱ ምክንያት ትሆናለች ይኸንንም በሽታ ለመከላከል የታሰበ እንደሆነ ቅማልን ድራሹን ማጥፋት ያስፈልጋል ግን ልብሳቸውን ቶሎ ቶሎ ከማያጥቡና ከማይለውጡ ጋራ የሚኖር ለሆነ ሰው ይኸን ለማድረግ እጅግ ያስቸግራል፡ደግሞም ቅማል የማይወደው አንድ ነገር አለ።ይኸውም ብርድ ነው ። ሁለተኛውም የማይወደው ነገር መኖሪያውን ሲለውጡበት ነው እንዴሁም ልብሳችንን ብናጥብ እንኳ ዘወትር ብንለዋውጠው ያወለቅነውንም ልብስ በቀዘቀዘ ቦታ ሰቅለን ብናናፍሰው ስለዚህ ቅማል ከልብሳችን ለቆ ይሄዳል ደግሞም ቅማል የፀሐይን ሙቀት አይወድምና ልብሳችንን እፀሐይ አውጥተን ብናሰጣው ስለ ታጠበ ያህል ነው።ቅማል እንዲሞቀው ይወዳል እንጂ የጸሐይን መፋጀት አይወደውም በለሰለሰ ገላ ነክ ልብስ ውስጥም ለመኖር ውዴታ አለው ይህም ለስላሳ ገላ ነክ የሆነ ልብስ በድሎት በመልካም እንዲመገብ ይረዳዋል።ግን ቀዝቃዛ ቦታ የሆነ እንደሆነ እንዲጎዳ ያውቃልና ሆቴሉን ለመለወጥ አይወድም ስለዚህ ቅማል ብዙ ቀን በተለበሰ ልብስ ቅጫምን ይጥልና ቷኊኊሽ ቅማልን ይፈለፍላል ለዚህም ቅጫም ማጥፊያ የሚያስፈልገው ነገር ልብስን በአፍላል አግብቶ በውኃ መቀቀል ነው፤ በዚህም አገር ልዩ ልዩ ወገን የሆኑ ብዙ ድሆች አሉ ለጤና መጠበቂያ የሚጠቅም ደምብም መንግሥታችን እስኪያበጅልን ድረስ ምናልባት ጊዜ ያስፈልግ ይሆናል።ነገር ግን አእምሮ ያላቸው ሰዎች ከዚህ ከክፉ በሺታ ለጊዜው ጤናቸውን የሚጠብቁበትን ነገር እንዲያውቁት እንመኛለንና ከዚህ ደምብ ካልነው ጥቂት ከዚህ በታች ጽፈን እናመለክታለን ፤ ፩ኛ።ቀን ለብሰኸው በዋልኸበት ልብስ አትተኛ ፤፪ኛ። እንደተቻለህ መጠን ልብስኅን ቶሎ ቶሎ እጠብ ፫ኛ።አገልጋዮችኅ ልብሳቸውን ቶሎ ቶሎ እንዲያጥቡ አስጠንቅቃቸው ፤ ፬ኛ።ንጹሕ ያልሆነውን አገልጋይ ልብስ አልብሸ ወይም አንጣፊ አታድርገው ። ፭ኛ፡ ባመት ሁለት ወይም ፫ት ጊዜ ቤትህን በኖራ አስለቅልቅ ። ፮ኛ፡ቢቻልህ ቤትህን በሳንቃ ወይም በጡብ አስነጥፈው ቷንኊሽ ነፍሳትም እንዳይሰወሩበት ጥፍጣፉ በጣም የሠመረ ይሁን።ነገር ግን ቤትህ በሳንቃ ወይም በጡብ ያልተነጠፈ የሆነ እንደሆነ ዘወትር ንጹሕ እየሆነ ይጠረግ ይለቅለቅም።የቤትህንም ምንጣፎች ቶሎ ቶሎ እጸሐይ ዘርጋቸው። ፯ኛ፡ይኸንም ድርጊት ለጐረቤቶችህ ብትነግርና ብታስተምር በቅማል ላይ ጦር ማወጅኅ ነው።እነዚህ ፍጥረቶች ሲታዩ የማይጐዱ ይመስላሉ፡ነገር ግን ታላቅ ጉዳት ያመጣሉ የሞትም ምክንያት ሆነው በየመቱ ብዙ መቶ ሕዝብ ይፈጃሉ ፰ኛ።ደግሞም ሌላው ነገር ልናስብበት የሚገባን ከውሾች ጋራ አለመወዳጀትን ነው።ውሾች በየእድፋም ቦታና ቤት ይሄዱና ከዚያ ሲመለሱ ለቤታችን በሺታ ይዘው ይመጣሉ። ፱ኛ፡አንተ ወይም አገልጋይህ ያተኰሳችሁ እንደሆነ በቶሎ ወደሃኪም ሂደህ ምክር ጠይቀው፡እርሱም በሺታህ ምን እንደሆነ ሊነግርህ ይችላል ፤ ፲ኛ።ከገልጋዮችህ አንዱ የታመመ እንደሆነ ቢቻል ዝም ብሎ በቤቱ እንዲታመም አድርግ ቤተ ሰብም ከበሺተኛው ጋራ እንዲሆኑ አትፍቀድ ።

ዶክቶር ቶ አ ለምቢ ።

ስለ መሰልጠን እውቀትን ለማሳደስ የሚመራ ።

መጀመሪያ ለሰው የስም ክፋት ሳያገኘው ስሙ ለመኖር ጥበብን ለማሳመር መለስ ብሎ በጣም ማየት ያስፈልጋል ይኸውም በአራት ማዕዘን ነው የሚቆመው አንዱ እውቀትን ማብዛት ሁለተኛው ልብን ብልህ ማድረግ ሶስተኛው አመልና ልማድን ማሳመር አራተኛው ስልጥንና ማበጀት መውደድ መዋደድ ነው ።

፩ኛ። ለእውቀት ዋና ምሰሶው እውነትን መትከል ነው እውነት የሁሉም ማቆሚያ ማህቶት ስለ ሆነ በሱ ሐሰት ነገር የገባበት እንደሆነ የደስታ መንገድ ሊሆን አይችልም ።

፪ኛ፤ ዳኛ የሚሆን ህብታም ቸር ትልቅ አጥባቂ የሚፈራ በደግ ያደገ አመሉ ጥሩ የሚችል ይኸን ሁሉ የጠቀለለ ሂሳብ አእምሮ የዕውቀትን እብነት በሙሉ ፈጽሞ የጠቀለለ መሆን ያስፈልገዋል ይኸንን ሁሉ ታላወቀ የሰጡትን ሥርአት የሚ-

ችል አይሆንም ካልቻለ የግድ አማካሪ ያስፈልገዋል።ምናልባት አማካሪዎቹ ለጥቅማቸው ሲሉ ከሥርአት ያዘሩታል የሚፈርደው ሁሉ በከንቱ ይሆናል በዚያን ጊዜ ሕዝብ ሁሉ ይቸገራል

፱ኛ ፤ ይህ ዳኛ ብልህ ንቁ ባለሀብታም ልብ ይሁን ሰነፍ የሆነማ እንደሆነ ከልቡ ላይ እውቀት ቢአርፍበት ስፍራ ያጣል የዚያን ጊዜ ሥርአት ይጠፋል ፍርዱም ሁሉ ይነዋወጣል ባለእውነት ያጣና እውነት ያልያዘ ያገኛል ።

፲ኛ ፤ ይኸ ዳኛ ከሁሉም ዓይነት የማይከጀል ልቡ ባለጠጋ ይሁን የልብ ባለጸጋ የማያልቅ ወርቅ ማለት ነው በዳኛ ልብ መከጀል የገባ እንደሆነ ከሥርአትና ከመጠን አውጥቶ እገደ ወፍራም መጋረጃ ሆኖ የሕዝቡን ጥቅም እንዳያይ ይከለክለዋል።ሕዝብም ማልቀስና መዛት ጣቱን መንክስ ይበዛበታል፡መንግሥቱንም ያሳድፋል።የማይቸኩል ይሁን አለመቸኰል ወደ እውነት አድርሶ ሐሰትን ያጠፋል።የማይሰክር የማይጠጣ ይሁን መጠጥ አካላትን የሚጐዳ ስለ ሆነ አብሶም ልብን አጥፍቶ እውቀትን አብርሮ ንቁነትን ያሳጣል ይልቁንም ዳኛ ሰክሮ ስርአት የጠፋ እንደሆነ ለመንግሥትም እንቅፋት ይሆናል ።

፲፩ኛ፡ዳኛ የሆነ ሰው ጕበዝ ግርማዊ ደፋር ሲነጋገር በቀጥታ የሚነጋገር ይሁን ። ጉብዝና ካልናቸው ነገሮች ጋራ ጋሻ ነው ክፉውን ሁሉ ይከለክላቸዋል ዋና የነውር ነውር ዳኛ ፈሪ ሲሆን ነው አለዚያ የዳኛ ፈሪ በነፍስ እንደሚነቃነቅ ላባ ነው እንዲሁ ነው ።

፲፪ኛ ፤ ማስተካከል ዋና የፍርድና የዕውቀትን ጤና ደግ የእውነትን መንገድ ለማቆም የሕዝብን ልጅ ሁሉ በትክክል አንዱን ካንዱ ሳይለዩት ትልቁን አቅርቦ ትንሹን ሳያበሩት ሀብታምን አስጠግቶ ደሐውን ሳያርቁት ጉልበተኛውን ወዶ ደካማውን ሳይጠሉት ሁሉንም በትክክል ነፋስ እንዳይገባው በሥርአት መመልከት ይገባል ። ሁሉም እሚጠቀምበት ስፍራ ግዜ አለው ስለ ዜህ ሁሉንም እንደ ሰራው መጠን ማየት ነው

፲፫ኛ ፤ ባለጸጎች የሚደርስ ጉልበት እንዳላቸው ትንንሾች ድሆች የሚደርሱ መሳሪያዎች ናቸው ጣቶች ባይኖሩ እጅ ብቻውን ሊሰራ አይችልም።ድሆች ባይኖሩ ባይሰሩ የባለጸጎች ንግድ አይቆምላቸውም ገንዘባቸውም አይጠበቅም ቤታቸውም ፎቅ አይሰራላቸውም ዘፋናቸውም አይቀናላቸውም ነበር ።

፲፬ኛ ፤ ባለጠጋ በደስታ ስፍራ ውሎ ወደ ቤቱ ሲመለስ ከዙፋኑ ተቀምጦ የቤቱን ጌጥ ሲያስተውል ቤቱን የሰራው ድኃ በበጋና በክረምት ድንጋይና ጭቃ ሲያግዝ ፀሐይና ብርድ ሲመታው ለፍቶ ወደ ቤቱ ሲመለስ ደረቅ እንጀራውን ከታረዙትና ከተራቡት ልጆቹ ጋራ በልቶ ድካሙን ለብሶ ባለቀው ኬሻ ላይ የሚተኛውን ድኃ አያስብም ለድኃ ይህ ብቻ አይበቃውምና ነውን ድኃ የሚጠቃው ።

፲፭ኛ ፤ በውነት መንገድ ያድኃ የተነጠለው አለአሉ ጉልበት እንዳይሆላቸው ሲያውቁ ደኃን መበደል ሥርአት ይቀበላል ወይ።

፲፮ኛ፤ ለምድነው ባደባባይ የባለጸጋ ድምጽ ብቻ ተሰምቶ እውነት የሚአገኘው ።

፲፯ኛ ፤ የበዛው ሕዝብ ድሐ ሆኖ ለንጉሥ አደጋ የሚመልስ የድሐ ጩኸቱ የማይሰማው ስለምን ይሆን ሥርዓት አስተካክሉ ይል የለምን ? ለሁሉም ጥቅም የሚሆነውን ንግድና እርሻ ስለሆነ እነዚህ ላይ የሚያልፍባቸውን መከልከል የሚያስፈራውንና እንቅፋት የሚሆነውን አንሥቶ አማን እንዲሆን ሥራ ለሚሠሩ ሰዎች ሰዓትና ወሰን ማድረግ ። አጉል ልዩ ንግድ ማስፋት የሚከለክለውን ሁሉ ማስነሳት ። ብልሆ የሆኑትን ልጆች ልባቸውን ደስ ማሰኘትና የሠሩትን ሥራ የወለደውን ፍሬ መልቀም እንዲመቻቸው ማድረግ ፡ ወደሥራ መራመድ የሚከለክለውን ማቆምና አዝመራን ከጊዜው እንዳያልፍ ማስቸከል ፤ በሥርዓት የሚያጉላላቸውን ሁሉ መከልከል ፡ ለመሬት የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ በወራቱ መስጠት ነው ።

፲፰ኛ ። የኢትዮጵያ ልጆች ወንድሞቼ ሆይ ወገን ሳልለይ በዚህ ወረቀት ላይ የተጻፈውን እንድትመለከቱት እለምናችኋለሁ ። በሰማይ ላይ እንደ አሞራ የሚበረውን አይሮፕላን በባሕር ውስጥ የሚሄደውን ሱማራ ፤ በባሕር ላይ የሚሄደውን መርከብ ፡ በመሬት ላይ የሚሄደውን ባቡር ሠርተው ያወጡ ሰዎች ሁሉ ሲወለዱ እንደናንተው ነው የተወለዱ እንጂ ሲወለዱ ከናታቸው ሆድ የእውቀትንና የገንዘብን መክፈቻ ይዘው አልተወለዱም ። ግን መንግሥት ባቆመላቸው ተማሪ ቤት ገብተው ተምረው ነው ለዚህ ሁሉ ሥራ የበቁ ፤ ይልቁንም የኢትዮጵያ ልጆች የበሕርይ ንቃት አላችሁና መንግሥት በከፈተላችሁ ትምርት ቤት ብትተጉ እንደዚህ ሰዎች መሆን ትችላላችሁ ። የዛሬ ሕፃናት የነገ ጉልማሶችና ጀግኖች እናንተ ናችሁና መንግሥታችሁ ሊያሳድጋችሁ ስለነቃ የመንግሥታችሁን አሳብ በሰፊ ልቡናችሁ ተቀብላችሁ ተማሩ እውቀት እንዳያመልጣችሁ ስል የእውቀቱን ያህል ጽፌ አመለክታለሁ ሳትንቁ ትመለከቱት ዘንድ ።

ይላል ሐጂ ዓብዱላሂ ሺሪፍ አፈንዲ ።

በማኅበር እርዳታ ስለሚቆመው ትምርት ቤት ፤

ባለፈው ሳምንት ኢጣልያ ለአሜሪካ ስለምትከፍለው ዕዳዋ ለመርዳት ኢጣልያኖች በሚሽቀዳደሙት አሽቀድድም ከእንግሊዝ የፖሌቲካ ሴርክሎች ብዙ መደነቅና ልብ የሚነካ የደስታ ነገር አነሣስቷል ፤ ደግሞ ከ፳፯ የመንግሥቱ ዋና ዋና የሥራ ቤት የገባው ፥ ገና ለወደፊቱም ሊጨመርበት ያለው ሕዝቡ ለእርዳታ የሰው ዶላር ፳ ሚሊዮን ሊሬ ሁኖዋል የመንግሥቱ ዋና ሕዝቡን ወደዚሁ እርዳታ ለጠራቸው ጥሪ በኩራት የደስታ ምላሽ እየሰጡ እርዳታቸውን ስላቀረቡ ነገሩ በታሪክ መጽሐፍ ሊጻፍ የሚገባ ነው የሚል ጋዜጣ ባነበብሁ ጊዜ ከዚህ ቀጥሎ የሚከተለውን ለመጻፍ አሰብሁ ። ክቡር ፊታውራሪ ዴሬሳ ሕዝቡ ሁሉ ተረዳድቶ የማኅበር ትምርት ቤት ሊያቆም እንደሚገባው ጥቅሙን ሁሉ እየገለጹ ባለፈው ወራት ከብርሃንና ሰላም ጽፈውት የነበረውን ባነበብሁ ጊዜ ከልቤ የተሰማኝ ደስታ ወሰን የለውም እንዲሁም በዚሁ ነገር ደስ ያላቸው ሰዎች ብዙዎች ናቸው ስለዚህም ሁሉ እንደያቅሙ የሰጠው እርዳታ እጅግ ብዙ ነው ። ነገር ግን አኳሆኑ ሁሉ እንዲህ ይሆናል ብለን ተመኝተነው ከነበርን አሳብ አንድ መቶኛ አልሆነም ይህ ከላይ የጻፍኩት ስለ ኢጣልያኖች አረዳዳት የሚያወራ ጋዜጣ ሳነቡ

ሳለሁ አንድ ትልቅ ሰው አብሮኝ ነበርና ማንበቤን ሳልጨርስ አቋርጦ እየተቻኰለ እንዲህ ሲል ጠየቀኝ ።

እረ እኔስ እጅግ ይገርመኛል ሕዝባችን ተስፋ የሚያስቈርጥ ነው መሰለኝ ? ስለምን ሕዝባችን አለመማር የተባለ ትልቅ ዕዳ እንዳለብን ገና አላወቀም መሰለኝ አብሶ ተስፋ ያስቈረጠኝ ደግሞ ብዙ ትልልቆች ሰዎች ያዲሱ ሥልጣኔ ሥራ በትክክል የሚያስኬዱ ከኛ አብልጠው ይልቅ የትምርትን ጥቅም የሚያውቁ እንዲሁም ብዙዎች ያዲሱ ሥልጣኔ ትምርት የተማሩ በአእምሮ ሆነ በጸጋ ከኛ አስር ጊዜ የሚበልጡ ሰዎች ለዚሁ የማኅበር ትምርት ቤት እርዳታቸውን ሳይሰጡ በመቅረታቸው ነው አለኝ ። እኔም ይህ ነገር እውነት አይመስለኝም ስል ብመልስለት በፍጥነት አከታትሎ እነ እገሌ እነ እገሌ እገሌ እያለ ያዘንብብኝ ጀመር ። እውነትም ብዙ ሰዎች ቈጠረልኝ ። ነገሩን እያሰብሁ ከተረዳሁት በኋላ የሚበዙቱ ነገ ተነገ ወዲያ እንሰጣለን እያሉ ይሆናል የቀሩቱ ደግሞ ሥራ ስለ በዛባቸውና የሚያስታውሳቸው ስለ ታጣ ይሆናል እንጂ እውነትስ በሐፍረት ራሳችንን አስጐንብሶ የሚያስኬደን አለመማር የተባለ ብርቱ ዕዳ ሳለብን አድፍጠው ዝም እንደማይሉ አስር ጊዜ አስረግጥሃለሁ ስል መለስኩለት ።

ነገር ግን የዚሁ ሰው ንግግር ብዙ ሐሳብ አነሳሳብኝ የዚሁ በእርዳታ የሚቆም ትምርት ቤት ነገሩ ሲጀመር ባሳቤ ብቻዬን ሁኜ የኢትዮጵያ ሕዝብ ቢያንስ ቢያንስ ፲፰ ሚሊዮን ይሆናል እንግዲህ እያንዳንዱ ሰው አንዳንድ ብር ቢሰጥ ፲፰ ሚሊዮን ብር መሆኑ ነው ። ፲፰ ሚሊዮን ብር ከተሰበሰበ ደግሞ በሶስት ወይም ባራት ትልልቅ ዋና የኢትዮጵያ ከተሞች ጥሩ ጥሩ ትምርት ቤት ሊቆምልን ነው እያልኩ ነገሩን አሳካው ነበር ። እርዳታው በብርሃንና ሰላም ማስታወቅ ተጀምሮ ሁለት መቶ ብር ሶስት መቶ ብር እንሰጣለን የሚሉ ሰዎች መገኘታቸውን ካነበብሁ በኋላ በመላው ኢትዮጵያ ብዙ ትምርት ቤቶች ሊቆሙ ናቸው የሚል የተስፋ አሳብ በልቤ እየበረታ ሄደ ። ሕዝቡ አከታትሎ የሚረዳውን እያስታወቀ ከ፰ የምስር ወርቅና ከ፺ሺ፰፻፵፫ ብር ተሩብ ሲደርስ ቀጥ ብሎ መቆሙን ብየሁ ጊዜ ግን በጣም ደነገጥሁ አሳቤ ሁሉም ተስፋ እንደ መቁረጥ አለ ። እርዳታቸውን ያስታወቁ ሰዎች የሰጡት ገንዘብ እጅግ ብዙ ነው የተስፋ አሳቤን እንደመቁረጥ ያደረገው ምክንያት ግን እርዳታቸውን ያስታወቁ ሰዎች በጣም ጥቂቶች ስለሆኑ ነው ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሉስ ይቅርና እንዲሁም የትምርት ነገር ለይቶ ጥቅሙን የማያውቅ ሰውስ ይቅርና አዲስ አበባ ያሉ ያዲሱን ሥልጣኔ ትምርት የተማሩ ሁሉ ለጥቀው እርዳታቸውን ቢሰጡ ትምርት ቤቱ በፍጥነት ሥራውን ባዘጋጀ ነበር ።

አሁን ግን ከኔ ጋራ ሲነጋገር ለነበረው ሰው እንደመለስኩለት ቃል የሚበዙቱ ነገ ተነገ ወዲያ እያሉ ይሆናል የቀሩቱ ደግሞ ሥራ ስለ በዛባቸውና የሚያስታውሳቸው ስለ ታጣ ይሆናልና ስለዚህ የትምርት ቤቱ ማኅበር አምስት ሽማግሌዎች መርጦ ማቆም ባስፈለገው ይመስለኛል ፤ እኒህ ሽማግሌዎችም ቢሆን በመላው ኢትዮጵያ አለዚያ እስከዚያው ድረስ በከተማው ሁሉ እየዞሩ ሰውን ሁሉ ለዚሁ ትምርት ቤት እርዳታ እንዲሰጧቸው እየለመኑ ገንዘብ የሰጣቸውን ገንዘቡን ሌላ ምላሽ የሰጣቸውንም ምላሹን በብርሃንና ሰላም ቢያስታውቁ ሥራው እየሰፋ ይሄድ ይመስለኛል ። እንዲህ አድርጎ እርዳታ ጠያቂዎች ሽማግሌዎች ማቆምም አሁን መጀመሩ አይደለም ከሰለጠኑት አገሮች ሁሉ ሁል ጊዜ እንዲህ ይደረጋልና ስለዚህ መከተሉን የሚያስፈልግ ይመስለኛል። ኪዳነ ማርያም አበራ ።

ሔዋን ሕይወት ወይም የትውልድ ምንጭ ።

እናት ከተፈጥሮዋ ትውልዷን በመመገብና በመጠበቅ ለማብዛት ትጥራለች ከአዕዋፍ እስከ አራዊትና እስከ የቤት እንስሳ ለትውልዳቸው እጅግ ይሳሳሉ አጥፊ ሲመጣባቸው ለመከላከል ይቀድሙላቸዋል ። ቀድሞ መንገድ ስሄድ ከበረሃ ቋያ ተነሥቶ ጫጩቶች ያሉበትን ያሞራ ጐጆ እሳት ቢያያዘው እናቲቱ በክንፏ አቅፋቸው አብራ እንደተቃጠለች ቁሜ አይቼ እስከ ዛሬ ትዝ ይለኛል ። እንደዚሁ የዶሮዋን ጫጩት እባብ ጉርሶባት እናቲቱ እየጮኸች እየዘለለች የባቡዋን ዓይን ዓይንዋን እየሟጨረች ስትጋደል እግር አድርሶኝ ገላግያለሁ እንኳን የሔዋን ልጅ መንፈስ እግዚአብሔር ያደረበት እናት የንስሳን የናት ፍቅር ዕለት ዕለት ልንመለከተው እንችላለን ግን የሰው ዕውቀቱ ያየውንና የሰማውን ያሕል ነው ። እናቶቻችን የውቀታቸውን ሕፃን ሲወለድ ዕለቱን ለስታ ቅቤ ያውጡታል ኋላም የፍቅራቸውን ከሚቀምሱት ሁሉ ጠጅም አረቂም ቡንም ቢሆን ለሕፃን ያለመበጀቱን ሳይመለከቱ ያቀምሱታል ይህም ልምድ ሆኖ አብሮ ያድጋል ። ያገር ቤት ሰዎችም ሕፃናቱ አፋቸውን መፍታት ሲጀምሩ ማነው ባልሽ ማናት ሚስትህ እያሉ ያስተምሮአቸዋል የማይገባ ወግም ከፊታቸው እየተጫወቱ ልባቸውን ይመርዙታል ይህ ሁሉ ያለ እውቀት ነው ። በያገሩ የትውልድ አጥፊዎች እርገው የሚሰዷቸውና በመንግሥት ደምብና በሐኪሞች ብርታት የሚአደክሟቸው ቂጥኝንና የሚአሰክርን መጠጥ ነው እንዲህ ያለውን የትውልድ ባላጋራ የምትቃወም የተማረች የትውልድ እናት ናትና ሴቶች ልጆቻችን እንደሚገባ የተማሩ እንደሆን እንኳንስ ለተወለደው ለጽንሱ ጤና አስቀድመው ይጠበባሉ ኋላም ለእግዚአብሔርና ለመንግሥት የሚመች ሕዝብ ያበዛሉ ጤናማ ሕዝብ ቁጥሩ እየበዛ እውቀቱ እየሰፋ ኃይሉ እየበረታ አገርም ሲጠበው የሰነፉን እያቀና ትዳሩንም አገሩንም ያሰፋል ይህን ከሩቅ የታሰበ ቃል ማስቀደሜ ለወንዶች ልጆች አስተዳደግ የትምሕርት ቤት በታሰበው መጠን በሙሉዋ ኢትዮጵያ ለሴቱም ትምሕርት ካሁን ቀደም የታሰበው በፍጥነት ቢወጠን የሰውን ሁሉ ደኅንነት የሚሻ አምላክ ያሰፋዋል ። ከባይ ማዶ ያሉ ብዙ የጥንት ክርስቲያን ነገዶች ያረቄ መጠጥ ልባቸውን አስንፎት የጠበንጃን አጥፊነት እየረሱ ወንድሙን ወንድሙ በትንሽ ምክንያት ያጠፋዋል ስለዚህ ከዋናው መንግሥት ከተማ ለራቁ ለጥንት የክርስቲያን ነገዶች ከዋና ዋና ሥፍራ ላይ የውቀት ትምሕርት ቤት የበሽተኛም ማስታመሚያ ቤት ቢሠራና ቢቆም እጅግ ይበጅ ነበር ። ከቆመ በኋላ የገንዘብም እርዳታ አይገድም በደምብ እየወረዳው ራሱን እንዲችል ይመከር ነበር ሰው በደሀ ልቡናው ብዙ ይመኛል የሚበጀውን ፈጻሚ ግን መንግሥትና እግዚዚአብሔር ነው።

ከንቲባ ገብሩ ።

ማስታወሻ ።

ከቡራን ወንድሞቼ ሆይ ። እኔ እንደሚመስለኝ የኢትዮጵያ ሰዎች ይኸንን ያህል ዘመን ምሉ ጥበብ ጉድላብኝ የኖረችው እርስ በርሳችን ባለ መስማማታችንና አንዱ የሰራውን አንዱ በመንቀፉ ሌላው የተቻለውን ሐሳብ ሲያስታውቅ ያንን እያየን ማፌዝና ለበጥ ማውጣት ነው እንጂ የተያዘልን ፤ እንደምናያቸው ሕዝቦችማ ለሀገራችን ብንጣጣርና ሐሳብ ቢገባን መች እንደዚህ ወደ ኋላ እንቀር ነበር ። ሰው ክፉም መልካምም ቢሰራ መንግሥትና ሕዝብ አገርን ከሚጐዳ በቀር ያንን ሥራውን ቢያመሰግኑለት ጥንት ያጠፋውን እያሳመረ ሰውነቱም ደስ እያለው ዕውቀቱም እየሰፋ ይሄዳል ፤ መቼም ሰው ሁኖ ተፈጥሮ እኔ አውቃለኹ ይላል እንጂ ፡ አላውቅምን የሚያስበት የለምና የተቻለውን ነገር በጋዜጣ ሲያስታውቅ ማተሚያ ቤቶችም መርምረው ከታተመ በኋላ አንባቢዎች ቢነቅፉትም መልካም ሰው የነበረው በእፍረት እየጐሰቈለ የተገለጸለትም ዕውቀት እየተሠወረ ይሄድበታል ፡ ማለት ከሰው ስሕተት ከረመኔ ክህደት አይጠፋምና ከንግግሩ መጥፎ ቃል ቢገኝበት ስህተቱን እንዲያውቅ በጋዚጣ ማስታወቅ ይሻላል ይመስለኛል እንጂ ፡ ዕውቀቱን ሊያሰፋ አስቦ ያደረገውን በልብ ሐሜታ ልንስቀበት አይገባንም እኔም ይኸንን ማለቴ ሌላ የማውቀው ቋንቋ የለኝም ፡ ዕውቀት የጠፋችብኝ መሪ የሌለኝ ዕውር ነበርኹ ፡ መሪም ባይኖረኝ ብርሃን በልዑል ተፈሪ መኰንን ተገልጻለችና ፡ ብወድቅም አልሰበር በማለት እየተፍገመገምኹ ላመልከታችሁ ፡ ከቡር ዳዊት በመዝሙር ፻፳፰ ቁጥር ፲፫ እንዳለው ። ለድንቁርናማ ንግግሩ ይመሰክር የለምን ፤ እግዚአብሔር ያዘዛቸውን መብላት ትተው ለሰው ስራ ለበጥ የሚያወጡ ብዙ ሥራ ፈቶች መልተዋልና ይመልከቱት ።

አወይ ድንቁርና በኛ ላይ ስትከሪ ፤
ምን እበላ ሳትይ ያላሳብ እዳሪ ፡
መጣልን ተፈሪ አንቺን የሚያበር ፤
ለክፉ መልከኛ ሰጥተውን ነበር ፤
ትእዛዝሽ ክፉ ሁሉ ወደ ግራ ፤
በብርሃኑ ቀርቶ የጨለማ ሥራ ፤
እመት ድንቁርና እስከሁን ገዛሺ ፤
እንግዴህ ይበቃል እከትሽን አንሺ ፤
እስቲ ዘወር እያልሽ አገርሽን ጉብኚ ፤
እንደኛ ያል ገበር መቼም አታገኚ ፡
መልከም ሰው ተፈሪ የመኰንን ልጅ ፤
ዕውቀትን አግብቶ አሰፋፋት እንጅ ፡
ይቅር መንቃቀፍ የሥራ ለበጥ ፡
መልካምን ውዱዱ እንዳይለወጥ ፤
አንዱ የሠራውን አንዱ ሲነቅፈዉ ፤
ብዙ ለበጥ ወጣ ብልህ በሠራዉ፡
እናንተን ለመምከር እኔ መቼ ቺዬ ፤
ይህ ነገር ይገርማል ዋሆዬ ዋሆዬ ፤

ወለጋ ሰዮ ደምሴ ወልደ ሥላሴ።

ሥራን በትክክል ስለ መሥራት ።

በመንግሥት ሥራ ውስጥ ላሉ ሠራተኞች የሥራቸውን ጥዳትና ማማር እየታየ ቀለብና ደሞዝ የሚያድግላቸው ቢሆን ለወደ ፊት ከቀድሞው ይበልጥ አድርጎ የጸዳ (ያማረ ሥራ በሰሩ ነበር ፡ ነገር ግን የ፶ብር የ፩ ብር ሥራ ወይም ከዚህ ይበልጥ እየሠራ ቀለቡ አላድ አንድም ብር እንዲያው ያለቀለብ የሚሠራ ሠራተኛ ይኖር ይሆናል ። ይህ ሠራተኛ ያለቀለብ ያለደሞዝ ሲኖር የሚለብሰውና የሚጐርሰው ከወዴት እያመጣ የሚለብስ የሚጐርስ ይመስላል ። ይህ ነገር ከሥራው ትርፍ ያገኘበት ይመስላል ወይም በሌላ ባልታወቀ መንገድ ሥራውን እየሠራ የሚያገኝ ይመስላል ። ይህንኑ ሥራ ለሌላ በክራይ ሲሰራ የመንግሥቱ ሥራ በመሐከል ሣይሠራ ይቀራል ። መንግሥትም እንደዚህ ያለ ሥራ ይምጣ ባለ ጊዜ ያሠራተኛ ለሌላ ክራይ ሲሰራ የመንግሥቱ ሥራ ሳይደርስለት ይቀርና እሱ በክራይ የሰራውን ከፈረንጅ ቤት ይገዛል ይህ ለመንግሥት ሁለት ፊት ጉዳት መሖኑ እጅግ ያሳዝናል ። ግን ከውጭ የተገዛበት ዋጋ ገንዘብ ለሠራተኛ ቢሰጡት ከውጭ ባልተገዛ ነበር ።

ደግሞ ለመንግሥት ተቈጣጥሮ ገንዘብ የሚያገባ ሰውም ቢገኝ ለዚያ ለመንግሥት የገባውን ትርፍ ገንዘብ አይቶ ቀለብና ደሞዝ የሚያሳድግለት አለቃ ቢኖረው ይበልጥ አድርጎ ብዙ ገንዘብ ለመንግሥት ባገባ ነበር ።

ነገር ግን የዛሬ ዘመን አለቃ የራሱን ቀለቢና ደሞዙ ለማሳደግ ነው እንጂ የሚጥረው ለመንግሥት ደክሞ ገንዘብ ላገባ ተቈጣጣሪ ምንም እንዳያገኝ የታወቀ ነገር ነው ።

ነገር ግን ደህና አለቃ የሆነ እንደሆን ተቈጣጥሮ ያገባውን ገንዘብ አይቶ ይህ ሰው ለመንግሥት ያገባው ገንዘብ ከዚሁ ወር እስከዚህ ወር ከዚህ ዘመን እስከ ዚህ ዘመን ይህን ያህል ነው ቀለቡም ደሞዙም ትንሽ ነው ቀለቡንና ደሞዙን ያሳድግንለት እንደሆነ ከዚህ ይበልጥ ያገባል እንጂ አያሳንስም ብሎ ወደላይ ቢያመለክትለት ደግ እንደሆነ የታወቀ ነው ያም ሠራተኛ ከዚህ በላይ የተጻፈውን ቃል አይቶ እንደ ተጻፈው አድርጎ ብዙ ገንዘብ ለመንግሥት ሊያገባ ይችላል ከላሳደጉለትና ከልጨመሩለት ግን እኔ ቀለብ የለኝ ለመንግሥት ይህን ያህል ዘመን ስኖርና ሳገለግል ለመንግሥት ብዬ ከሕዝብ ስጣላ ያገባሁት ገንዘብ ይህን ያህል ሲሆን ምን ተደርጎልኛል ብሎ አስቦ ቀድሞ በሚያገባው ልክ ቀርቶ ጭራሹን አሳንሶ ወይም ሥራውን ለቆ ለሌላ አሽከርነት ይገባል ።

ከዚህ ቀደም ለመንግሥት የሚገባው ገንዘብ በመሃከል ሳይገባ ይቀራል ። ይህ ለመንግሥት ባለመግባቱ እጅግ ያሳዝናል

ደግሞ ለመንግሥት ገቢ ሳይኖራቸው ሥራም ሳያውቁ በጉቦና በመተያያ ቀለባቸውንና ደመወዛቸውን ያሳደጉ ሰዎችም ቢገኙ የነዚህን ሥራ የሚመረምር አንድ ሹም (ዳኛ) በየሥራው ያስፈልጋል ። እነዚህም ሰዎች ሥራ ባለ መሥራታቸውና ባለ ማወቃቸው አይቈረቈሩም ። ቀለብ ማደጉንና ከሰው መብለጣቸውን ያያሉ እንጂ ። ሥራ የሚያውቅ ረዳት የሌለው ድሃ ግን እንዲያው ለመንግሥት ሲያገለግልና ሲደክም መኖሩን ላየ ሰው እጅግ ያሳዝናል ።

በፈቃዱ ወልደ መስቀል ።

ኢትዮጵያ ታሪክ ተቸግራ እስከሁን
ማራኪ ደርሶባት ሊአገበባት እግሩን ።
ልጆቹአን ንቋቸው አደቆአቸው እንደ ሙት ።
ተፈክሮ ነበር ሁሉም እስቲሰሙት ።
በሕልምም በትንቢት ጊዜውን ቢቆጥሩ።
የመስጴጠኞችን ጠጭቱዋቸው ወበኑ ።
ተስፋ ቆርጠውብን በዕውቀት የረቀቁ ።
ደህ ነገር ጸጽቶኝ ስኖር እያለቀስኩ ።
ሐዘኔም ቀረልኝ የሰው መልክ አገኘሁ።
ብርሃንና ሰላም አጥናኝ ሰዎች አየሁ ።
ደድረስ ካባቶቼ ጠና ላላችሁት ።
ደግሞም ለኩዮች ኀልመስ ላላችሁት ።
ለትንንሾቹም ገና ለምታድጉት ።
ደድረስ ለሁላችሁ ለትንሽ ትልቁ ።
እውቀት ባገራችን መግባቱአን ዕወቁ ።
ድንቁርና ሸሸች ለቀቀች ታገሩ ።
የዕውቀት ምንጩአ ብዙ ወንዙ ግን አንድ ነው ።
መልካው ካልተገኘ ሰው እያሸግዷው ።
ድልድዩ ዳኝነት ሁሉ የሚፈልገው ።
ዋናው የውቀት መልካ የልብ ደግነት ነው ።
የኢትዮጵያ ልጆች እስቲ ደስ ደበለን ።
ንፃን ተንቀልፋችን ብርሃን ደኸው አየን
ኢትዮጵያ እናታችን ደች ቅድስት አገር ።
ትሳቅ ደስ ደበላት እሮደ ብላ ትደር ።
ልጆቹአ ተነሱ ታጠቁ ባንድ አደቅር።
ጠላት እንዳደመጣ ጦር እንዳደወረውር።
ስሚ የምስራች ኢትዮጵያ ክብር ።
እንጋፋሺ ተፈሪ ደኸ ፃኛ መምህር ።
ብርሃንና ሰላም አውጥቶ ምክር ።
መሳሪያ አስታጠቀን ብርግጥ የሚአስ ፎክር ።
በቂም ነገር ገመድ አስሮ እየጎተተን።
ጣንድ ቤት አግብቶ በውል ቦታ አቆመን ።
እንዳንወሳልት እዳንጠፋ ሾልከን ።
እዩት ብርቱነቱን በውቀት እንዳሰረን ።
ባህል ተለወጠ ዛሬ በኛ ዘመን ።
በራስ መኰንን ቤት አደስ ጨረር አየን ።
ደህ ጨረር ደበርታ ጣደ ሆኖ ደሙቀን ።
ተጩዝጠን ሳለን በብርድ በቆፈን ።
የኢትዮጵያ ልጆች በውቀት የታሰርን ።
ማነው የሚፈታን ድል አድርጎ እውቀትን።
በክንቱ አንቸገር ሰውም አደሳቅብን ።
በውቀት እንታሰር ትኑር በላያችን ።
አደለንም እስረኞች ያላወቀም ቢያየን ።
ሁሉ ደመኛታል መች ብታስንቅፈን ።
ጉድ ነው ያለመጠን ትንግርት የኛ ዘመን
ብርሃንና ሰላም አውጥቶ እሚአሳየን ።
ንጉሥ ተወለደ ጥበበ ሰሎሞን ።
እንኳን በኢትዮጵያ ለልጅቹአ እሚሆን።
አልፎ የሚሠራ ርቆ ከወሰን ።
ተፈሪ መኰንን ታወቀ እስፋ ወሰን ።

ሰ ሎ ሚ ።

የከተማ ወሬ ።

ኅዳር ፳፱ ቀን ፲፱፻፲፰ ዓመተ ምሀረት የበዓለ ወልድ ዕለት በመድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን የዳጃዝማች ጌታቸው ልጅ ክርስትና ነበር ። ለዚህ ክርስትና ለማቋቋም የተሰበሰቡ ብዙ መኳንንት እጅግም የሴት ወይዘሮች ነበሩ ።

ነገር ግን አቶ ተወልደ ብርሃን መድኅን በብርሃንና ሰላም እንዳስታወቁን በቀድሞ ልማድ ታስረናልና እንኳን እኔ ጌቶችም እንዳያይዋቸው ፊታቸውን ሸፍነው ነበር ። ደግሞ ከልብሳቸው በላይ መልካሙ አቋቋማቸው እንዳይታይ በመጋረጃ ስለ ነበሩ እነወይዘሮ እገሊት ነበሩ ብዬ ለመጻፍ አልሆነልኝም ስማቸውንም የጻፍኋቸውን አላየኋቸውም ። ግን ጌቶች አሽከሮቻቸውን ባዩ ጊዜ እንሜቴ ይሆናሉ ብለው እጅ ሲነሱ እኔም አብሬ እጅ ነስቼ ነበርና በወሬ ነው እንጅ አይቻቸው አይደለም ። ስለ ዜህ ስማቸውን በያንዳንዳቸው ለመጻፍ አልሆነልኝም እንጅ የሴት ወይዘሮችስ እጅግ ብዙ ነበሩ ። ወይ ዓለም እጅግ ታስቸግራለች እስቲ የሮፓ ሴቶች ደረታቸውን መግለጥ የኛ ሴት ወይዘሮዎች ፊታቸውን መሸፈን የሚያስደንቅ ነገር ነው ። ሽማግሌ ቢገኝ የኒህን የፊታቸውን መሸፈኛ ለኒያ ደረት መሸፈኛ መስጠት ነበር። ግን ምን ይሆናል ሰው ልማዱን ይወዳልና እንደ ፀሐይ የሚያበራ ፊታቸው እንዴት ነውር ያለበት ይመስል ይሸፈን።መሸፈንስ እንኳን ለነሱ ለሚከተሏቸው ገረዶችም አይገባ ። ይህ ልማድ መቸም በወንዶች ቅናት የተነሳ በቱርክ አገር ነው የተጀመረው ኋላ ወደ ግብፅ ኋላም ወደኛ ደረሰ አሁን ግን ቱርክ ትቷል ሴቶችም ፀሐይ ወጣልን እያሉ ደስ ብሏቸዋል ይባላል።የመሸፈን መምሕሮች ሲተውት ተማሮቹ ለምን አንተወውም ቱርከስ መቸም እንዳሸው ነበር ክርስቲያን ግን ማድላት አይገባውምና ሚስቴን ሰው አይይብኝ ቃለ ሴትም ባሌን ሰው አይብኝ ማለት ይገባታል በግድ የተጀመረ መሸፈን በመቆየት ጌጥ መሰለ አንተ የጌታ ልጅ በል እስቲ አባትህ በነጻነት ሲኖር እናትህ እንዴት ታስራ ትኑር ተው አባትህን ምከርና ነፃ ትውጣ በብርሃን ጊዜ።ነገሩ አሳዘነኝና አበዛሁት መሰለኝ። እንግዴህ ወደፊተኛው ልመለስ ከቅዳሴ ከወጡ በኋላ ወደ ደጃዝማች ቤት ተመለስን ያጀቡና የመኳንንቱ ብዛት እጅግ የሚያስደንቅ ነበር የሴት ወይዘሮዎችም እኩሎች በበቅሎ እኩሎች በአውቶሞቢል መኳንንት በፈረስና በበቅሎ ሁነው ገቡ ወዲያው የሚያስደንቅ የጦም ምግብ ከተመገብን በኋላ የሚገበ መጠጥ ቀረበልን የሚፈልግ አንድአንድ ጠጣ እያዝን ለራሱ ግን ደጋገመና የያዘውን ይዞ ጸጥ ብሎ ተቀምጠ ነበረ።ያገሬ ሰው እንደ ዱሮው አልተሳከረም ሊጠነቀቅ ይሆን እያልሁ ደስ አለኝና ቀና ብዬ ባይ ሊቀመኳስ መንገሻ ውቤና ፊታውራሪ ደስታ ተሰማ የይቴጌ ጣይቱ የእኅታቸው የወይዘሮ አዛለች ልጅ በብርጭቆ ውሀ እየቀዱ ሲጠጡ አየሁና ፈጣሪዬን አመሰገንሁ የመጠጥን መርዝነት ታላላቆችማ ታወቁት ሕዝቡን ለጥቅም አስመስለው በመጠጥ መጉዳታቸውን ሊተዉና በልክ ሊያጠጡት አይደለምን ብየ እጅግ ደስ አለኝ።ከሁለተኛው ግብር በኋላ አዝማሪ ገባና ነገሩን በመንፈሳዊ ጀመረው ።

እግዚአብሔር ያጥናሽ አልናት ወይ ፡
ወልዳልሞታትሞ ወይ ፡
ወልድማ ቢሞት ይነሣል ፡
አብነቱን ያውቃል ፡

እያለ ሲያሳዝን ቆየና ፡ ወደ ሥጋዊው ተመለሰና እንዲህ አለ ።

የቴዎድሮስ መፈራት ፡
በጋሻ ነበር በጕልበት ፡
የንግሥት ዕድል ደግ ነው ፡
ቃላቸው ተፈሪ ነው ፡
ደጃች ጌታቸው ልንገርሁ ፡
አስቸገረኝ ግብርሁ ፡
ያን ቄልማማ እንጨት እንሥተው ፡
ራስሁን ሊሉሁ ነው ፡
በተጣራ ጠጅ በወይን ፡
አቃጥለውታል ሆዴን ፡
እኔንስ እንዴት ደስ ባለኝ ፡
ራስሁን ቢሉልኝ ፡

አለና ዜማውን ለውጦ እንዲህ አለ ፡

ተሰው ጋር ንግግር የማልወደውን ፡
አሳማኝ ምኒልክ ያራቱን ማዘን ፡ አለ

የጥልቅነቱን ነገር ለመናገር ነው እንጂ ፡ ጥቂት የጻፍሁለት የተናገረውን ሁሉ ለመጻፍስ ቢሆን ብዙ ጊዜ ያስፈልግ ነበር ወይ ያገሬ ሰው ፤ ይህን የመሰለ አዋቂ እንዴት ትንቀዋለህ ። ባለሙያውን ሁሉ ናቅህ ፡ እጅ ያለውን ባለጅ ቡዳ እያልህ ትሰድበዋለህ ፤ ጠፍር ፡ መጫኛ ፡ መኝታ ፤ ጀንዲ ፡ ነት ፤ የሚሰራልህን ፋቂ እያልህ ትሰድበዋለህ ፤ የተማረውን ተማሬ ብለህ ትሰድበዋለህ ፤ ይህ ስድብ ባያሳፍረው እስከሁን ሠራተኛ ሁሉ-

ስንት ብልሀት ያወጣ ነበር ይመስለኛል፡ወይ አለመታደል ሠራተኛ መሰደብ ዘራፊ መመስገን፤አዝማሪ ማለት አመስጋኝ ማለት ነው።ቀድሞ የክህናት ሥራ እንደነበረ ዳዊት ይነግረናል። መዝሙር ፻፶ ቁጥር ፫፤ሰብሕዎ በመዝሙር ወበመሰንቆ እንዲል ኋላ ግን ቤተ ክርስቲያን ከተጕዳች በኋላ፡ተግራኝ ወዲህ ምግብና መጠጥ ወዳለበት ጠጋ ያሉ ይመስለኛል። በምንም ምክንያት ስድብ አይገባም፤መምከር ነው እንጂ፤ነገሩን በትንሹ ጀምሬው ነበር። ነገሩ ሁሉ ትዝ እያለኝ ስላበዛሁባችሁ አታሚዎች አንባቢዎች ሁሉ ማሩኝ ይላል ትንሹ ወንድማችሁ

ማኅተመ ወርቅ እሸቴ።

ስለ ዳግማዊ ምኒልክ ዕረፍት መታሰቢያ።

ታኅሣሥ ፫ ቀን፤ዳግማዊ ምኒልክ ካረፉ ፲፪ ዓመት ሁኖ ነበር። ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ለዚሁም መታሰቢያ ተዝካር ቅዳሚት ያዲስ አበባን አድባራት ካህናት በሙሉ ዕሁድ ወታደሩን ግብር አበሉ። ግብሩም እጅግ የተመሰገነ ነበረ ሰኞ ለነዳያን ሲያበሉ ምጽዋት ሲያሰጡ ዋሉ።

የልዕልት ወይዘሮ መነን ተማሪ ቤት መጐብኘት።

ታኅሣሥ ፳ ቀን ልዕልት ወይዘሮ መነን በማረች አቶሞቢል ሁነው አምስት ሰዓት በሆነ ጊዜ በተማሪ ቤቱ ከተፍ አሉ። ስድስት ሰዓት እስኪሞላ ተማሮቹ በሚበሉበት ቤት በተሰናዳላቸው ወንበር ቁጭ ብለው ለተማሮቹ ያዘዙላቸውን ምሳ እንዲሰናዳ ሠራተኞቹን ያፋጥኑ ነበር ፯ ሰዓት ሲሆን ተማሪዎቹ ከትምርት እንዲወጡ ደወል ተደወለና ፪ ሁለት እየሆኑ ቀድሞ በሚቀመጡበት ስፍራቸው ተቀመጡ።በልዕልት ፊትም የቀረበላቸውን ምግብ ደስ ብሏቸው ተመገቡ። ከምግቡ በኋላም አቶ ማኅተመ ወርቅና ልጅ መስፍን የሚከተለውን ቃል ተናገሩ።

ልዕልት ሆይ።

የልግሥናዎና የትኅትናዎን መብራት ወደ ምስር ብሔድ ከዚያ ሲአበራ ቆየኝ ወደ ኢየሩሳሌም ብሔድ ደግሞ ፀሐይ ሁኖ ብዙ ድሆች ሲሞቁት በየገዳሙ ሁሉ ሲአበራ ብርሃኑ ሰፍቶ በውጭ ላሉት ሁሉ ሲታይ አየሁት።

ወደ ኢትዮጵያ ብመለስ የበለጠ ሁኖ ታየኝ ይልቁንም በተማሪ ቤቱማ ያየሁትን ለመናገር ምሳሌ አጣሁለት የልዑል አልጋ ወራሽስ እድል እንዴት ያለ ነው ሥልጣንና ትህትና መልካም ሚስት እውቀትና ርህራሄ እኒህን አንድ አድርጎ ያገኝ ከርሳቸው በቀር ሌላ ሰው በዓለም አልተገኘም ሰሎሞን ከሺህ ሴቶች አንድ አላገኘሁም አለ። አልጋ ወራሽ ግን ከመጋርመኛቸው አገኙ አንዲቱ የተባረኩ ሆኑላቸው የተማሪ ቤት ባለ መቶሙ ብዙ ሊቃውንቶች እየተናደዱ ሞቱ እናንተ ተማሪዎች አስቀድማችሁ ከንዲህ ያለ ጊዜ ያደረሳችሁን እምላክ አመስግኑ ቀጥላችሁም ይህችን ብርሃናችሁን እንዲያቆይላችሁ አምላክን ለምኑ። ይህ ማእርጋችሁና መወደዳችሁም እንደአበቃችን እንደ አዳም እንዳይሆንባችሁ ተጠንቀቁ ምስጋናማ እያደረጋችሁ በውቀት ላይ እውቀት ስትጨምሩ ታመሰግንዋቸዋላችሁ እኔ ግን የትምሕርት ጊዜዬ በከንቱ ስላለፈብኝ እውቀት አንሶኝ እንደሚገባዎ መጠን ላመሰግንዎ አልሆነልኝምና የማይቸግረው አምላክ ላይኛይቱ ቤትዎን ያሳምርልዎ በዚህም ዓለም እምመኝልዎን ይስጥዎ ስል ቸሩን አምላክ እለምናለሁ።

ማኅተመ ወርቅ እሸቴ

ልዕልት ሆይ።

በተወደደና በተከበረ ፊትዎ መቅረብ ለኛ ብዙ ማዕርጋችን ነው ነገር ግን የሀገርዎ ፍቅርና የጥበብ ውዴታዎ እኛን ብርቾዎን የመጐብኘት ዘወትር በትጋት ያመላልስዎታል ይልቁንም ለኢትዮጵያ ልጆች ሲሳይ የሆነች እጅዎ ዘላለም ወደ ተማሪ ቤት ስለተዘረጋች የተፈሪ መኰንን ተማሪ ቤት ታመሰግናለች ልጆቹም ይደነቃሉ።

፪ተኛ፡ የልዕልትነስ ቸርነትና ጥበብ መውደድዎን እንኳን በሀገርዎና በምስርም የቤክቶርያን ኮሌጅ ለማዩት በሄዱ ጊዜ ለተማሪ ቤት ያደረጉትን ችሮታዎንና የፍቅር ቃልዎን በኢየሩሳሌም የመንገድ ታሪክዎ ተረድተን ስንገረም የሰማነውን ባይናችን አይተን ከረድኤትዎ ተካፈልን።

፫ተኛ፡ ሐዋርያት ከኢየሱስ ክርስቶስ ገበታ ተካፍለው መንፈስ ቅዱስ እንዳደረባቸው እኛም የተፈሪ መኰንን ተማሪዎች ከመቤታችን ገበታ ተካፍለን ጥበብና እውቀት ይደርብን ስንል እንመኛለን።

፬ተኛ፡ ልዕልት ሆይ ደግሞም ጉለሌ መነን የምትባል ለሴቶች ተማሪ ቤት ማቆምዎ ለዛሬው አርአያ ነው እንጂ ወደፊት በልዑልና በርስዎ ጊዜስ ብዙ ተማሪ ቤት ቁሞ ሴቱም ወንዱም በትምሕርት እንዲሰለጥን ታላቅ ተስፋ አለኝ።

፭ተኛ፡ ለሀገራቸው ፍቅር ብለው እኛን የኢትዮጵያን ልጆች አስበው ገንዘባቸውንና ኃሳባቸውን ከኛላይ አድርገው ለሚጠብቁንና ለሚአሳድጉን ጌቶቻችን ረጅም የደስታ ዘመን ይስጥልን ዘራቸውን ይባርክልን ሐሳባቸውን ያቅናልን ብለን ክርስቶስን እንለምናለን።

መስፍን ቀለመ ወርቅ።

የውጭ አገር ወሬ።

ከታይምስ ጋዜጣ እንዳገኘነው ለግርማዊ ንጉሥ ጆርጅ ስለ እናታቸው ስለ ግርማዊት ንግሥት አሌክሳንድራ ሞት ከዓለም ሁሉ የኃዘናቸውን ተካፋይነት የሚነግር ልክ የሌለው የቴሌግራም ቃል ደረሰላቸው።

ግርማዊት ንግሥት አሌክሳንድራ ሲሞቱ ዕድሜያቸው ከ፹ ዓመት ይበልጥ ነበር።

በታይምስ ጋዜጣ ስለ ሕይወታቸውና ስለ ደግነታቸው የሚተርከው እጅግ ብዙ ነው። ከመጋባታቸው ጀምሮ እስከ ሽምግልናቸውም በክልሼ ተነሥቶ በጋዜጣው በየተራው ግሩም ሁኖ ይታያል።

በፓሌስቲና ተቆፍሮ የተገኘ ነገር።

ሳኦል ንጉሥ ድል ሁኖበሞተ ጊዜ የሱን መሳሪያ የተቀመጠ በትአስታሮት በተባለ ጣዖት መቅደስ ተቆፍሮበይዝራኤል ሸለቆት እስተ ዓምዱና ብዙ ሌላ ቅርጽ ተገኝቷል ፩ ሳሙ ፴፩ ፲።

በሉክሶር ተቆፍሮ የተገኘ ነገር።

በቱትንቀሄም በሉክሶር ዱር የተቀበረ ሬሳ ያለበት ቦታ መቈፈር ከተጀመረ ቆይቷል አሁን ግን ያንድ ንጉሥ ሬሳ ከብዙ ልዩ ልዩ የወርቅ ዕቃ ጋራ ጨርሶ ተገኝቷል።

አፍሪቃን አቋርጠው የተመለሱ በራሪዎች ።

የእንግሊዝ በራሪዎች በአውሮፕላን ከካይሮ ተነሥተው ኢትዮጵያን በስተግራ ትተው በካርቱም አልፈው በኤልፋሸር አድርገው ወደ ካኖ ወደ ኑጌሪያ ደርሰው ተመለሱ ። ከካይሮ እስከ ካኖ ያለውን መንገድ ደግሞ በሶስት ቀን ጨረሱት ።

መልካም ምክር ።

፩ኛ ፤ እግዚአብሔር ሁለት ጆሮና አንድ አፍ ሰጠህ ። ይህ ምን ያስተምርሃል ? ለመስማት እንድትፈጥን ለመናገር ግን እንዳትቸኩል ።

፪ተኛ ፤ እግዚአብሔር ሁለት ዓይን አንድ አፍ ሰጠህ ። ይህ ምን ያስተምርሃል ? ለማየት እንዳትታክት ከብዙ ንግግር ግን ልትጠነቀቅ ።

፫ተኛ ፤ እግዚአብሔር ሁለት እጆች አንድ አፍ ሰጠህ ይህ ምን ያስተምርሃል ? ለሥራ ሁለት ለመብል ግን አንድ ብዬ የነገርኩህን አትርሳ ። ምክሬን ስማ በምግባርህም ፈጽመው ይላል መካሪው ።

የቴሌግራም ቃል ።

ሮማ ፤ በቺረናይካ ዳር መሬት ያህል በኢጣሊያና በግብጽ መካከል የሆነው መስማማት ተካይሮ ዘንድ ተፈርመዋልና በፖለቲክ ሥራት ከቅኚ ግዛታችን እርቃ ስትኖር የነበረች ዲያራቡት (አገር) የኢጣሊያ እንደመሆንዋ ስለተገለጸ ኢጣሊያ አሁን ባልነው መስማማት እጅግ ደስ ብሏታል ።

ጄኔብ ፤ በግሪክና በቡልጋር መካከል በሆነው ጠብ ነገር የዓለም መንግሥቶች ማኅበረተኞች ምክር ቤት በሻሎያ ፕሬዚዳንትነት ተሰብስበው መመርመር ጀምረው ሲያቆሙ የግሪክና የቡልጋር ነገረ ፈጆች እያንዳንዱ ሁሉ ከየመንግሥታቸው ያመጡትን ቃል ተናግረዋል ።

በርሊን ፤ ፕሬዚዳን ሬይች ጋቢኔት (ሚኒስትር ሥራ) በተሰናበተው ምክንያት አኋሁን ሁሉ እንዴት እንደመሆኑ ከእያይነቱ ክፍል አለቆች ተነጋግሮዋል ።

ሮማ ፤ በሮማ በ፲፱፻፳፬ ዓ ም በጉባዔው ተመርምሮ ለመቆም ተወስኖ የነበረው በመስደድ የሆነው የሽምግልነት ሥራ መጀመሪ ክፍል ያርባ አምስት ገዦች እንደራሴዎች መጥተው አብረውበት በነበሩ ጊዜ ኪጊ ከሚባል አዳራሽ ተመርቀዋል ሙሶሊኒ ከዚሁ ላሉቱ ሁሉ ሰላምታ አቅርቦላቸው ሲያቆም በ ያህል ሮማን ወደፊት ለማሰኘት ሽማግሎቹ የጉባዔውን ተግባር እየቀጠሉ እንዲሄዱ እያመለከቱ በመንግሥት ስም ዲስኩርን ተናግሯል ።

ፓሪስ ፤ ብርዱ በጣም እየበረታ ሄዷል ያለፈው ሌሊት ከዜሮ በታች በፓሪስ ፲፫ በዲጂዮን ፲፮ በመትዝ ፲፫ በእስትራስቡርጅ ፲፯ ማዕርግ ደርሰዋል ።

ሮማ ፤ ከቆላው መሬት በቀር ጌብ የሚባል (ያገራችን ሰሜን በረዶ ዓይነት) በመውረድ ብዛት ጌበው በኢጣሊያ በስተ ምዕራብ አገር ባ፮ ሜትር ተኩል ከፍታ ያህል ባቡሮችን መሄድ እስተ መከልከል ደረሰ ብርዱ እጅግ በርትቷል ።

ጄኔብራ ፤ የዓለም መንግሥት ማኅበር ሚኒስትሮች ። በግሪክና በቡልጋር ዳር መሬት ለመመርመር ተልከው በነበሩ ሽማግሎች ሥራ ላይ ፤ የግሪክና የቡልጋሪ ነገረ ፈጆች እያንዳንዱ ሁሉ ከየመንግሥቱ ባመጡት ቃል የተናገሩትን ንግግር ሰምተው ነገሩን በጣም እንዲመረመር ከእንግሊዝና ከዣፓን እንደራሴዎች ሽማግሌ ይለፍ ብለዋል ።

የታኅሣሥ ፬ ቀን የለት ወሬ ።

ሊስቦን ፤ ቤርናርዲኖ ማካዶ የሬፑብሊኩ ፕሬዚዳን እንዲሆን ተመርጧል ።

ማስታወቂያ ።

በርሻና በመስሪያ ሚኒስትር ሥራ ውስጥ መንግሥት ያወጣውን ደምብና ሕግ ሳልተላለፍ ደሀ ሳልበድል ፤ የመንግሥቱን ገንዘብ በጥንቃቄ ሠርቼ ቀድሞም ከሚሠራው ሠራተኛ ገቢ ገንዘብ አብልጬ አገባለሁ የሚል ሰው እርሻና እመስሪ ምኒስቴር መጻፊያ ቤት፣ ሁል ጊዜ ከጧቱ ከ፫ ሰዓት እስከ ፬ ሰዓት ድረስ ፤ እየመጣ ቢነጋገር በደስታ እንቀበለዋለን ደመወዙም እንደ ሥራው ገቢ እየታየ ይቈረጥለታል ጥቅምት ፲፩ ቀን ፲፱፻፲፰ ዓመተ ምሕረት ።

መኰንን ሀብተ ወልድ ።

ማስታወቂያ

ለራሶችና ለደጃዝማቾች ለሴት ወይዘሮች የሚገባ በያይነቱ ጥሩ ካባ ከኤሮፓ መጥቶልኛል ፤ ቤቱም (ባንክ ኦፍ አቢሲንያ) ከእንግሊዞች ባንክ አጠገብ ነውና ይህን ካባ መግዛት ለሚፈልጉ ሰዎች መጥተው እንዲገዙ አስታውቃለሁ ።

ኢያሱ ዳንኤል

አ ፔ ማርሲያኖ
በኢትዮጵያና በፈረንሳይ የቅኝ አገር ሶማሊ በተለየ ፊያት
አውቶሞቢልና ትራክተር አስመጪና እንደራሴ ።



A.P. MARCIANO
Concessionnaire Exclusif pour l'Ethiopie
et la cote française des somalis
des automobiles et tracteurs Fiat.

መጀመሪያ ዓመት ፤ ቁጥር ፶፪ ።
1re ANNÉE № 52

ሐሙስ ታኅሣሥ ፲፭ ቀን ፲፱፻፲፰ ዓ ም።
JEUDI 24 DECEMBRE 1925

ብርሃንና ሰላም

LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voi. regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraissant tous les jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

የጋዜጣው ዲሬክተር ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።
Gabré Christos Taklé Haymanot
Dirécteur

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ስለ ተፈሪ መኰንን ሆስፒታል የተደረገ ግብዣ ።

አስቀድሞ ዶክቶር ላምቢ መኳንንቱንና ትልልቆች ሰዎችን እንደሚከተለው ቃል « እኛ ዶክቶር ላምቢና ሚሲስ ላምቢ ለተፈሪ መኰንን ሆስፒታል ለምናደርገው ክብር ታሕሣሥ ፲፪ ቀን ፲፱፻፲፰ ዓም ። ሰኞ ለት ባ፲ ሰዓት ሻይ እንዲጋበዙልን ፈቃዳችን ነውና እንዲመጡልን በማክበር እንለምንዎታለን ። ከሻይ በኋላ በሆስፒታሉ ላሉት በሽተኞች የፍቅር እርዳታ እንዲሆን ለልደት ስጦታ የሚሆን አሻንጉሊት እንሸጣለን ። ልዑልአልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንንም ይመጣሉ « ብለው ጠርተው ነበርና ስለዚህ በታኅሣሥ ፲፪ ቀን ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ባማረ አውቶሞቢል ሆነው ከክቡራን መኳንንቶቻቸው ጋራ ልክ ባ፲ ሰዓት ከሆፒታሉ ደረሱ። በሆፒታሉም ብዙ ሰው ተሰብስቦ የልዑልን አመጣጥ ይጠባበቅ ነበር ። ዘበኞቹም ልዑልን ለመቀበል ተሰልፈው ይጠባበቁ ነበርና ልዑል አልጋ ወራሽ ከዘበኞቹ አጠገብ በደረሱ ጊዜ የሚገባ ሰላምታቸውን ሰጡ ። ልዑል አልጋ ወራሽና ክቡራን መኳንንቶቻቸው ከአውቶሞቢል ወርደው ወደ ቤት በገቡ ጊዜ የሻዪ ግብዣ ተጀመረ ። ልዑል አልጋ ወራሽን የተከተሉ ክቡራን መኳንንቶች ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ፡ የጦር ምኒስትር ራስ ስዩም ፤ ራስ ናደው ፤ ደጃዝማች ወልደ ገብርኤል ፤ ደጃዝማች ጌታቸው ያገር ግዛት ምኒስትር ፤ ደጃዝማች ወልደ ሥላሴ ደጃዝማች ሙሉ ጌታ የገንዘብ ምኒስትር ፡ ጸሐፌ ትእዛዝ ወልደ መስቀል የጽፈት ምኒስትር ፡ ጸሐፌ ትእዛዝ አፈ ወርቅ ፡ አዛዥ ደገፌ የርሻ ምኒስትር ነጋድራስ ዘለቀ የንግድ ምኒስትር ፤ ከንቲባ ነሲቡ ፤ ፊታውራሪ ደስታ ፤ ብላታ ኅሩይ ነበሩ ።

ደግሞ የውጭ አገር ምኒስትሮችና ሚሲዮኖች ፡ ነጋዴዎችም ተሰብስበው ነበር ፡ ላ፲፩ሰዓት ሩብ ጉዳይ ሲሆን የሻዪ ግብዣ እንደሚገባ ሆኖ ተፈጸመና ልዑል አልጋ ወራሽ በክቡራን መኳንንቶቻቸው ታጅበው ፡ የውጭ አገር መኳንንትና ወይዛዝሮች ፡ ትልልቆች ሰዎችም ፡ አብረዋቸው ወደ ሆስፒታሉ ሄዱ ። የሆስፒታሉን ደረጃ ሲወጡም እጅግ አምሮ ይታይ ነበር ። ልዑልም እየተዘዋወሩ በየክፍሉ የተኙትን በሽተኞች ሁሉ ጠየቋቸው ። ልክ ባ፲፩ሰዓት ልዑል ለሆስፒታሉ እርዳታ የሚሆን የሐራጅ ዕቃ ወደ ተሰናዳበት ቤት ገብተው ተቀመጡ። በዚህም ሥፍራ ከልዑል ፊት ለፊት በየዕቃው ሆኖ በተራ ተቀምጦ የነበረው አበባ ግሩም ሆኖ ይታይ ነበር ።

በዚያን ጊዜ ሰው ሁሉ ተሰናድቶለት በነበረው ወንበር ተቀመጠና ዶክቶር ላምቢ እራሳቸው በእንግሊዝና ባማሪኛ እንደሚከተለው ተናገሩ ።

ሆስፒታልን ለማሠሪያ የሚሆን ገንዘብ ወይም ለሆስፒታሉ የሚያስፈልገውን መሣሪያ የሚሰጥ ሰው በተሻለና በታመነ መንገድ ለሰዎች ፍቅሩን ይገልጻል ። ለዚህም ለሆስፒታል ሥራ ላስፈለገው ጉዳይ የበለጠ ገንዘብ የሰጡትንና ዋጋቸውን ለመቀበል የሔዱትን ሚስተር ጆርጂን እናስባቸዋለን ። የሚስተር ጆርጂም መልካም አድራጎት ከርሳቸው በኋላ ይኖራል ። ደግሞ ቸርነታቸው ለበዛው ለወዳጃችንና ለተስፋችን ዳግመኛም ፍቅራቸውንና ርኅራኄያቸውን ለዚህው የስማቸው መጠሪያ ለሆነው ሆስፒታል ይኸን ታላቅ ስጦታ በመስጠት ፍቅራቸውን ለገለጹት ለልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን የማክበር ምስጋናችንን እናቀርባለን ። ከኔ ይልቅ አብልጠው በጣም በተስማማ ቃል እንዲያመሰግኑልን ሚኒስተራችንን ሚስተር ቤንቲንግን እለምናቸዋለሁ ። ደግሞም ሆስፒታሉ ያደርገው ዘንድ የሚፈትነውን ነገር በጥቂት ቃሎች ለመግለጽ ይገባኛል ። ይኸም ሆስፒታል ለኢትዮጵያ ሕዝብ መጀመሪያ እንደሆነ ታስቧል ፡ ለሁሉም

ብየረገዱ እንዲያገለግልም ፍላጐቱ ነው ። ለመታከሚያም ገንዘብ ለመክፈል የማይችሉትን ተቀብሎ ሲማከም እምቢ አይልም ለመክፈልም ከሚችሉት ሰዎች እንደ አቅማቸው የሰጡትን ይቀበላቸዋል ። ሥራው የፈጀውን ገንዘብ እንኳ ለማስተካከል ቢፈልግ በእንደዚህ ያለ ስጦታና ከአሜሪካ እንደምናገኘው ያለ ስጦታ ነው የሚመዘዘነው ። የሆስፒታሉም ሥራ ሊያልቅ ተቃርቧል ከዕዳም ነፃ ሊሆን ነው ። ከበሩና ከቦታው ዋጋ በቀር ሆስፒታሉ ብቻ የተሠራበት ገንዘብ የሚሊዮን ሩብ ብር ነው ለሆስፒታሉም የሚሆን መሣሪያ ገና በሙሉ አልመጣልንም እንደዚህ ያለም እርዳታ ካላገኘን በቀር መሣሪያውን በሙሉ ለማምጣት ዓመት ፣ ወይም ሁለት ዓመት ይወስድብናል ። ነገር ግን አንዳንድ ወዳጆቻችን ረድተው ይኸም የመሣሪያ መምጣት እይዘገይብንም በማለት ተስፋ እናደርጋለን ። የሆነ ሁኖ ሁሉም በጊዜው ይሆናል ።

የተሰበሰብነውም ሁሉ እንበተናለን ምናልባት እኔ ነገ ሟች እሆናለሁ ። ነገር ግን ይህ ሆስፒታል እንደሚመስለኝ ብጥቂት ባሰበው መቶ ዓመት ይኖራል ፤ የኛንም ቦታ የሚይዙ ሀኪሞችና የሃኪም ረዳቶች ይመጣሉ የሆስፒታሉም ክፍል ሁሉ ይሞላል ብዙ ሰዎችም ከሕመማቸው ይፈወሱበታል ፤ ሌሎችም ሕንፃዎች ይጨመራሉ የኢትዮጵያ ልጆችም ሃኪምነትንና የሃኪም ረዳትነትን የሚማሩበትም የተማሪ ቤት ይሠራል ፤ በዚያን ጊዜም ሆስፒታሉ ከሚጠራበት ከተፈሪ መኰንን ስም በቀር እዚህ ያለነው ሁሉ እንረሳለን ፤ ዓይነተኛውም ነገር ከብዙ ዓመት በኋላ ከሚሆነው ነገር ጋራ ተባብሮ የተፈሪ መኰንን ሆስፒታልና በርሱም የተሠራው በኢትዮጵያ ላሉ ሕመምተኞች ጥቅም አድራጊ እንዲሆን አምናለሁ ። ግርማዊት ንግሥት ዘውዲቱም ላገራቸው ጥቅም ሲሉ ከዚህ ቀደም እንደረዱን ወደ ፊትም በዚህ ሥራ እንዲረዱን ምኞታችንን እንገልጻለን ። ብለው በጨረሱ ጊዜ ዳር ከዳር ተጨበጨበ ።

The man who gives money to build or equip a hospital shows his love for his fellow men in the best and truest way. We remember Mr. George who gave the most of the money needed for this hospital and who has already gone to his reward. Mr. George's good deeds live after him.

To our kind friend and benefactor His Imperial Highness Tafari Makonnen who has again shows his love and sympathy for this work which bears his name by this excelent gift, we express our sincere thanks and we are going to ask Our Minister Mr. Bentinck to do so in more suitable words than I could.

I should like to give a few words of explanation of what the hospital is trying to do. This hsopital is intended primarily for the people of Ethiopia. It seeks to minister to all cllasses. It will not turn any one away if they have no money to Pay. From thoes who can pay, it will accept only as much as they can afford to pay and I may say that in no case will it be as much as the work costs The balance will always have to be made up by gifts like this or from America.

The building itself is practically finished and almost free of dept. It has cost a quarter of a million dollars is round numbers not including the property costs and the gate. The equipment has not all come and unless we get more help like this it must wait for a year or two. We hope that some friends may come to our help and that we may not have to wait.

It will all come in time. This audience will scatter. Dr. Lambie may die tomorrow but this building will stand for I hope at least a hundred years and doctors and nurses will come to take our places; every room will be filled, many lives will be saved. Other buildings will be erected. It is the hope that a medical school for training Abyssinians as doctors and nurses will be formed. In that time all who are here may be forgotten, excepting that one whose name the hospital bears, Tafari Makonen, and I believe that in after years one of the greatest things that will be connected with his name is the Tafari Makonen Hospital and the work it has done and will do for the sick Abyssinia. It is our expectation that Her Imperial Majesty Zaouditou will in the future assist in the cayrring on of this work as she has done once before.

ከዚህ በኋላ የእንግሊዝ መንግሥት ባለሙሉ ሥልጣን ሚንስትር ክቡር ሙሴ ቤንቲንግ የሚከተለውን ቃል ተናገሩ ።

ልዑል ሆይ ወይዛዝሮችና ክቡራንም ፦

ከአትላንቲክ ማዶ ያለችውን የታላቂቱ እኅታችንን መንግሥት ጥቅም በዚች አገር እንድጠብቅ የሚገባኝ ስለ ሆነ ልዑል ለተፈሪ መኰንን ሆስፒታል ለሰጡት የልግስና ስጦታ ዶክቶር ላምቢ የሞቀ ምስጋናቸውን ለልዑል ተፈሪ መኰንን እንዳቀርብላቸው ለምነውኛል ይህም ስጦታ እጅግ የተከበረ መሆኑንና በዶክቶር ላምቢም እጅ በሚገባ እየሆነ መውጣቱን ለልዑል አረጋግጣለሁ ። ባለፈው ነሐሴ እኔው ራሴ እዚሁ ሆስፒታል ታምሜ ተኝቼበት ስለነበረ ደግሞም አንድ የእንግሊዝ ሱማሌ በሐምሌ ወር ሲሞት እዚሁ ስለነበርሁ ራሴ በመረመርሁትና በተረዳሁት ነገር እተፈሪ መኰንን ሆስፒታል የሚገቡትን በሽተኞች ግሩም አድርገው እንደሚያስታምሙዋቸውና እንደሚጠነቀቁላቸውም ልናገር እችላለሁ ። ከዚህም በቀር በሚስዮኖችና ይልቁንም በሚስዮን ሕክምና ምክንያት በዓለም ላይ የተደረገውን በጎ ነገር ሁሉ ከብዙ ዘመን ጀምሮ ስለተረዳሁ ልናገርላቸው እችላለሁ ። ጌታችን ራሱ ወዲያና ወዲህ ሲመላለስ በጎ ነገር እያደረገ በሽተኞችንም እያዳነ ይሔድ ስለነበረ ፍለ-

ጋው·ን ተከትለን እንድንሄድ ምሳሌ ተወልን ፡፡ እኔም ለዚሁ ሚስዮ·ን ደህንነትና መከናወን የልብ ተስፋ ማድረጌን ገሬ ጨልናገገር እመኛለሁ· እናንተም ዛሬ በዚህ የተሰበሰባችሁ ሁሉ ይህ ሆስፒታልና ተማሪ ቤት እየገነነና ወደፊትም ለዘወትር እየተስፋፋ እንዲሔድ የሥጋዊና የመንፈሳዊ ችግራቸውንም በማስታመም ለብዙ ሐበሾች ረድኤት ሊሆን እንዲችል ምኞታችሁ እንደሆን ብርግጥ ይሰማኛል ፡፡

አሁንም ለልዑል አልጋ ወራሽና ለዚህም ለበጉነት ሥራ የልባችሁን መውደድ ለመግለጽ በደግነታችሁ ለተሰበሰባችሁ ሁሉ ምስጋናዬን እያቀረብሁ የልዑል እግዚአብሔር በረከት እንዲያርፍበት እመኛለሁ· ብለው· በጨረሱ· ጊዜ ዳር ተዳር ተጨበጨበ ፡፡

ከዚህ በኋላ ልዑል አልጋ ወራሽ ለመናገር በተነሱ ጊዜ በዚያን የነበረ ሰው ሁሉ ተነስቶ በቀጥታ ቆመ ቃሉም ከዚህ ቀጥሎ እንደተጻፈው ነው ፡፡

ባገር ውስጥ ለበሽተኞች መታከሚያ ሆስፒታል ፤ ለጥበብና ለዕውቀት መማሪያ የትምሕርት ቤት ማቆም ለሕዝብ ትልቅ ጥቅም መሆኑ የታወቀ ነው ፡፡ ጃንሆይ ዳግማዊ ምኒልክም የዚህኑ ጥቅምነት አውቀው በመጀመሪያ የዕውቀትና የትምሕርት ቤት አቆሙ ፡፡

አሁን በቅርቡ በ፲፱፻፲፬ ዓመተ ምሕረት ዶክቶር ላምቢ ወደ አዲስ አበባ መጥተው ይህ ሆስፒታል እንዲቆም ባመለከቱኝ ጊዜ ለሕዝብ ጥቅም መሆኑን ስለተረዳሁት በሚቻለኝ ነገር ሁሉ ለመርዳት ቃሌን ሰጥቼ እንዲቆም አደረግሁ ፡፡

ደግሞ እኔ ለዚህ ሆስፒታል የረዳሁት እርዳታ ምንም ብዙ ባይሆን እንኳ ሆስፒታል በስሜ ስለተጠራ ለሥራው መሪ የሆኑትን ዶክቶር ላምቤንና የሆስፒታሉን ማኅበር በፍጹም ልቤ አመሰግናለሁ ፡፡

ደግሞ የአሜሪካው ጆርጅ ይህን የሚያህል ገንዘባቸውን ሰጥተው በኢትዮጵያ ውስጥ እንደዚህ የመሰለ ትልቅ ሆስፒታል ስለ ተሠራበት በዚህ ሆስፒታል የሚታከሙ በሽተኞችና እኛ ሁላችንም ልናመሰግናቸው ይገባናል በዘመንም ብዛት የኢትዮጵያ ባለጠጎች ገንዘባቸውን እያወጡ ማህበር እየሆኑ ለወገኖቻቸው መታከሚያ ሆስፒታል ሳያቆሙ አይቀሩምና ምስተር ጆርጅ ለዚህ መልካም ሥራ ምሳሌ በመሆናቸው ስማቸው በኢትዮጵያ አይረሳም ፡፡

ይህም ሆስፒታል ከቆመ ምንም ዘመኑ ቅርብ ቢሆን እንኳ በዚሁ በቅርቡ ዘመን ብዙ የኢትዮጵያ ሰዎች እየታከሙ እንደዳኑበት እርግጥ ነው ይልቁንም ደግሞ ገንዘብ የሌላቸውን ሰዎች አለዋጋ እናክማለን ብለው ዶክቶር ላምቤ አሁን ዛሬ በመናገራቸው የብዙ ድኆች ጥቅም መሆኑን ያስረዳልና ደስታዬ ከልክ ያለፈ ሆነ በዚህ ሆስፒታል የኢትዮጵያ ሰዎች እየታከሙ ጥቅም የማያገኙበት ቢሆን በስሜ መጠራቱ ብቻ ደስ አያሰኘኝም ነበር ነገር ግን ባለገንዘብ በገንዘቡ ሲታከም ገንዘብ የሌለውም እንዳለው ሰው ሆኖ በትክክል መታከሙ ፤ ለችግረኞች ትልቅ ተስፋ ነውና እጅግ ደስ ያሰኛል ፡፡

ደግሞ በዚሁ በሆስፒታል ውስጥ የኢትዮጵያ ልጆች የህክምና ሥራ እንዲማሩ ይሆናል ብለው አሁን ዶክቶር ላምቢ ስለተናገሩ ወደፊት ለሚነሳው ለኢትዮጵያ ትውልድ ታላቅ ተስፋ መሆኑ አይጠረጠርም ፡፡

አሁንም ወደፊት ይህ የሆስፒታል ሥራ እየሰፋ እንዲሄድና ብዙ የኢትዮጵያ ሰዎች እንዲጠቀሙበት ጥልቅ የሆኑ ምኞቴን ከማስታወቅ ጋራ ይህን ትልቅ ደስታ ለመካፈል ዛሬ የተሰበሰባችሁትን ሰዎች ሁሉ አመሰግናለሁ ፡፡

ኢትዮጵያ ሕያው ትሁን ፤ ዕድሜ ለንጉሥታችን ብለው በጨረሱ ጊዜ ረጋም የደስታ ጭብጨባ ተጨበጨበ፡፡

ፊታውራሪ ሁሰን መ ገ አዛድ የሙሐመድ አሊ ኩባንያ ሰው እንደዚህ ብለው ተናገሩ ፡፡

ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንንና ወይዘዝሮች ጌቶችም ፡፡

በሙሐመድ አሊና በኩባንያው በህንድ ማኅበር ስም ሁኜ ስለ ተፈሪ መኰንን ሆስፒታል ለመናገር እፈልጋለሁ ፡፡

አዲስ አበባ ከብዙ ጊዜ ጀምሮ እንዳሁኑ ጊዜ ሁኖ የተሰናዳ ሆስፒታል ያስፈልጋት ነበረ ፤ ይህ መሻቷም በዚሁ ሆስፒታል ተፈጸመ ፡፡

ልዑል አልጋ ወራሽን ለዚህ ሆስፒታል ስለሚረዱት የደግነት እርዳታቸው አመሰግናቸዋለሁ ፡፡ ምስተር ጆርጅንም ይህን ሆስፒታል ለማሠራት በቸርነት ብዙ ገንዘብ ስለ መላካቸው አመሰግናቸዋለሁ ፡፡ ዶክቶር ላምቢን ደግሞ ስለ ደግነታቸውና በርትተው ስለ መሥራታቸው አመሰግናቸዋለሁ ፡፡

የሆስፒታሉ ኑሮ ለበሽተኞቹ ከቤታቸው ኑሮ ይልቅ የተሻለ ሆኖ ይሰማቸዋል ፤ ለማለትም እደፍራለሁ ፤ በእውነት ብንናገር ለበሽተኛው የተመቸ ቤት ነው እንጂ ፡፡ ሆስፒታል አይደለም ፡፡

ይህ ሆስፒታል ባጭር ጊዜ ስመ ጥሩ ሁንዋል ፤ እንዲህ የሆነበት ምክንያትም በዶክቶር ላምቢና በሆስፒታሉ ሠራተኞች ደግነት ነው ፡፡ ይህ ሥራ ለኢትዮጵያውያን ብቻ የተወሰነ አይደለም ፡፡ ግን ለያንዳንዱ ሰው ሀብታም ሆነ ድኃ ለውጭ ሰው ሆነ ለኢትዮጵያዊ የሚሆን ሥራ ነው ፡፡

ለሆስፒታልና ለተማሪ ቤት የወጣ ገንዘብ ኪሳራ እንዳልሆነ የታወቀ ነው ፤ ግን እንደሚወልድ ገንዘብ ነው ፤ ወለዱም ለሰጭው ብቻ አይደለም ፤ በሰፊው ለሁሉ ጥቅም የሚሆን ነው ፡፡

የልዑል አልጋ ወራሽንና የምስተር ጆርጅን አብነት ይዘን ይህንን ሆስፒታል ለመርዳት እንበርታ ፡፡

የዚህ ሆስፒታል ሥራ ወደ ፊት መግፋትና የሥራውን ፍጻሜ እመኛለሁ ብዬ ነገሬን አሳጥሬ እጨርሳለሁ ባሉ ጊዜ ዳር ተዳር ተጨበጨበ ፡፡

ላ፲፪ ሰዓት ፳ ደቂቃ ሲቀረው ሐራጅ ተጀመረ በሐራጁ የገዙት ሰዎችና የተገዛው ዕቃ እስከ ዋጋው እንደሚከተለው ነው

የተለየ ስጦታ		
አልጋ ወራሽ ፡	፺፱	ጂኒ
ኮንት ኮሊ ፡	፲	ጂኒ
አሻንጉሊት የገዙ ሰዎች ፡		
አልጋ ወራሽ ፡	፲	ብር
ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ፡	፭	ብር
ሚስተር ዴ ኤ ሳንድፎርድ ፡	፵	ብር
አቶ ሚካኤል ብሩ ፡	፵	ብር
ክቡር ሲ ኤች ቤንቲንክ ፡	፳፭	ብር
ሙሐመድ አሊና ኩባንያው ፡	፭	ብር
አቶ ማህሌ ፀዳሉ ፡	፵	ብር

ነጋድራስ ዘለቀ ፡	፭	ብር
ሚስተር ኪወርኮፍ ፡	፳	ብር
ኮንት ኮሊ	፫	ብር
ደጃች ሙሉ ጌታ ፡	፲	ብር
አልጋ ወራሽ ፡	፲	ብር
ወይዘሮ ተናኘ ወርቅ ፡	፭	ብር
ደጃች ጌታቸው ፡	፲፱	ብር
ነጋድራስ ዘለቀ ፡	፲፱	ብር
ራስ ናደው ፡	፲፭	ብር
ደጃች ወልደ ገብሬል ፡	፱	ብር
ሙሐመድ አሊና ኩባንያው ፡	፲	ብር

ሙሴ ኮሊዬ ።	፳ ብር
ክቡር ሴ ኤ ቤንቲንዓ ።	፳፭ ብር
ክንቲባ ነሲቡ ።	፶ ብር
ቀኛዝማች አምዴ ።	፳ ብር
ሚስተር ሳሙኤል	፴ ብር
እቶ ፋሲካ ።	፴ ብር
ሙሐመድ አሊና ኩቦንያ ።	፶ ብር
እዛጋር ደገፌ ።	፳ ብር
ሚስተር ጋኖታኪስ ።	፶ ብር
የሚካኤል ብሩ ልጅ ።	፶ ብር
የሚካኤል ብሩ ልጅ ።	፶ ብር
ደጃች ወልደ ሥላሴ ።	፳ ብር
ጸሐፊ ትእዛዝ አፈ ወርቅ ።	፳ ብር
ብላታ ኅሩይ ።	፴፭ ብር
ቀኛዝማች ኃይሌ ።	፲፭ ብር
ማህሌ ፀዳሉ ።	፲ ብር
ንግሥት ።	፪፻ ብር
ወይዘሮ መነን ።	፻ ብር
ሙሐመድ አሊና ኩባንያ ።	፳፭ ብር
ሙሴ ጂን ማርቢስ ።	፳፭ ብር
ሚስተር ጊቦንስ ።	፳፭ ብር
ሚስተር ኤባሌት ።	፶ ብር
ሙሴ ጋውስን ።	፳ ብር
ሙሴ ላረቤር ።	፳ ብር
ሚስ ስቴል ።	፲ ብር
የሙሴ ኢ.ኤል ጋርዲነር ባለቤት	፭ ብር
ሚስተር ቤ ።	፲ ብር
ጸሐፊ ትእዛዝ ወ መስቀል ።	፴ ብር

ድምር ፪ሺ ፬፻፳ ብር ።

ይኸም ብዙ ገንዘብ ለአሸንጉሊት መክፈል ለሆስፒታሉ የእርዳታ ስጦታ እንደሆነ ይታሰባል ስለዚህ የተፈሪ መኰንን ሆስፒታል አገልጋዮች ሁላችንም ለሻይ የተጋበዙትንና ቸርነት ያደረጉትን ሁሉ በታላቅ ምስጋና እናመሰግናቸዋለን ይኸንም ስጦታ መስጠታቸው የኢትዮጵያን ድሆች ለመርዳት አስበው ነው ብለው የሆፒታሉ አገልጋዮች አመስግነዋል ።

ልክ በ፲፪ ሰዓት ሥራው ተፈጸመና ልዑል ከመኳንንቶቻቸው ጋራ ለመሄድ ተነሡ ልዑል አልጋ ወራሽም በአቶሞቢል ተቀምጠው ሲመለሱ የተከተላቸው አቶሞቢል እጅግ ብዙ ነበረና ድንቅ ሁኖ ታየ ።

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና የጦር ሚኒስትሩ ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ፡ ይህንን ያህል መኳንንትም በዚያ ቦታ ሲገቡ እንደ ዱሮ ልማድ ቢሆን አጅበ የመጣ ሠራዊት ግቢውንና ውጭውን መልቶ ግፊያውና ጫጫታው እጅግ ያስቸግር ነበር ። በዚያ ስፍራ የነበረም አትክልትና አበበ ፈጽሞ በተበላሸ ነበረ ።

አሁን ግን እንደዚህ ያለውን ረብ የሌለው ልማድ መኳንንቶቻችን ስለ ጠሉት በሥልጣኔ መንገድ መሄድን ወደው ብዙ ሰው ሳያስከትሉ መጥተው በጸጥታና በርጋታ ወደየስፍራቸው በደኅና ተመለሱ ።

የኢትዮጵያ ደህንነት ።

ብርሃንና ሰላም ሆይ አኒህን የሚከተሉ ቃላት ከውስጥህ አግብተህ ወደ ኢትዮጵያ ልጆች ሁሉ ብታደርስልኝ የስራህን ራስ ነገር ለሕዝባችን ብርሃንና ሰላምን መሆኑን እየታመንኩልህ ብዙ ምስጋና አቀርብልሃለሁ እግዚአብሔርም ይኸው የታጠቅኸውን ቅዱስ መልእክትህን በኢትዮጵያችን መሃል እጅግ እንዲባርከው በምሉ ልቤ እየለመንኩልህ የኢትዮጵያችን ደህንነትና ጉዳት የሚሆኑበትን ባጭር ለመናገር እልፋለሁ ።

ከሁሉ ነገር በፊት ቤት ጸንቶ ሊኖር መሠረቱን እንደሚገባ ማቅናት ግድ ዓይነተኛ ነገር እንደሆነ እንዲሁም ሕዝብና መንግሥት ለእውነተኛው ኑሮው መሠረት አለውና በርሱ ማሰብ እርሱንም በጣም ማቅናት ያስፈልጋል ይህ መሠረት ባይቀና ሕዝብና መንግሥት ይጠፋል እንጂ ከቶ ሊቆም አይችልም ይህ ከሆነ ሕዝባችንና መንግሥታችን ሊመሠረቱበቸው የሚገባቸውን ከእውነተኞች መሠረቶች አንዳንድ ለማስታወቅ እወዳለሁ

፩ኛ ፡ የእግዚአብሔር እውነተኛው ፍርሃትና የቃሉ ዕውቀት በሕዝባችን ማኻል በጣም ማሰልጠን ።

የሕዝብና የመንግሥት ፊተኛው ብዕና የሚገኝበት ነገር ይህ እንደሆነ በቅዱስ መጽሐፍ የገዛ እራሱ ምስክርና በዓለም በታየውም በሕዝብና በመንግሥታት እናኑዋር የተረዳ ነገር መሆኑን ብዙ ምስክር ሳመጣ በቻልኩኝ።የእውነተኛው በጎ ነገር ሁሉ ምንጭ ወይም መፍለቂያ አንዱ እግዚአብሔር በራሱ ነው እግዚአብሔርም በቅዱስ ቃሉ ብቻ በጉነቱን ሁሉ ይገልጽልናል በቃሉ ኃይልም እሱን እስክንመስል ድረስ ያድሰናል ለራሳችንና ለሕዝባችንም የሚጠቅሙ ለመሆን ያስችለናል የሕይወታችንና የባሕርያችን ወይም የጠባያችንም ምሉ መታደስ የሚያመጣ የእግዚአብሔር ቃል ብቻ ነው።ስለዚህ እንደፊተኛው ነገር አድርጎ የሕዝብና የመንግሥት ደህንነት በሌላ ነገር መፈለግ ከንቱ ነገር ነው ። ከዚያ ከተመሠረተው በቀር እርሱም ክርስቶስ ማንም ሌላ መሠረት ይመሠርት ዘንድ የሚችል የለምና እንዳለ ይኸው ነገር ማለት እግዚአብሔርን መፍራትና የቃሉንም ዕውቀት በልባችን በመሰልጠን ብቻ እንደሆነ ብርሃንና ሰላም የሚያመጣ ብዙዎች የመንግሥታት ሚኒስትሮች የሚታመኑለት ነገር ነው ።

የኢትዮጵያችን ሕዝብ ከጥንት የክርስቲያን ሕዝብ በመሆኑ ብዙ ያኰራናል ዳሩ ግን የእግዚአብሔር ቃል ትምሕርት በሕዝቡ ስላልሰለጠነ ያሳዝናል ደግሞ የእግዚአብሔር ቃል ለነፍሳችን ብቻ የሚሆነውን ረብ አይገልጽልንም በቅን ከተማርነውና ካስተዋልነውም ደግሞ ለሥጋችንና ለሕዝባችን ለገዛ መንግሥታችንም የሚሆነውን ይገልጽልናል።እምልክት ግን በሁሉ ይረባል ለርሱም ተስፋ አለው በዚህ ዓለም ሕይወት በሚመጣውም ደግሞ (፩ ጢሞ ፬ ፰። እግዚአብሔር እውነተኛው ፍርሃትና ፍቅር የቃሉም እውቀት ያለው ሰው አገሩንና መንግሥቱን ሳይወድ እንዴት ይቀራል ። የእግዚአብሔር ቃል ለባልንጀራችንና ለሕዝባችን ለመንግሥታችንም ልንፈጽመው የሚገባንን ሥራ ያሳየናል በፍቅር እሳትም ያቃጥለናል።የሕዝባችንን ኑሮ ለማየትም ዓይኖቻችንን ይከፍታል እርሱንም ልንረዳበት የሚያስችለን መንገድ ይመራናል።ይህ የሃይማኖት ትምሕርትና የእግዚአብሔር ቃል ፍሬ ብቻ እንደሆነ ባንድ በሚከተለው ምስክር እናጸናዋለን አንድ ትልቅ ሰው ያንድ ኰሎኒ አጋፓ የነበር በመጽሐፉ እንዲህ ብሎ ጽፈል።ይህ ፓትርዮቲስም የገዛ አገሩን መውደድ ከሁን በፊት በኢትዮጵያ ሕዝብ የለም ከሁን በፊትም ከቶ አይታሰብም ዳሩ ግን ይህ የሃይማኖት ትምሕርት እንደሚያነቃቃው እርግጥ ነው ስለዚህ የሆነው ይሁን እንዲህ ያለው ትምርት በኰሎኒያ ብዙ የሚያስፈራ መራራ ፍሬ ያፈራብናል ። ስለዚህ የሃይማኖት ትምህርት ባይደረግ በተሻለ እንድቀንም ምድሩ አንበሶች ሳይወልድብን አይቀርም።ይኸው ነገር እውነት መሆኑን እነሆ ባይናችን እናየዋለን ስንት ብዙችናቸው በሃይማኖት ትምሕርት ኃይል ብቻ አገራቸውን በጽኑ ፍቅር ሊወዷት የተማሩ የልዩ ልዩ ሕዝብ ታሪክ ማንበብና ኑሯቸውንም ማወቅ እጅግ ብዙ ይጠቅማል ያንድ ሕዝብ መነሣትና መውደቅ እንዴት እንደሚሆን በጣም ገልጦ ያሳያልና።

ይህ ሳይቀር ቅዱሳት መጻሕፍት ይህን እውነት በምሉ ብርሃን ጉልህ አድርገው ያሳያሉ ደግሞም ለገዛ ሕዝቡና

መንግሥቱ ደግ ስራ መስራት ከእውነተኛው ሃይማኖት በንዳች እንደማይለያይ ያስረዳል እንግዴህ የገዛ አገሩንና መንግሥቱን በእውነተኛው ፍቅር የማይወድ እግዚአብሔርን እወዳለሁ ባለ አምልክ ነኝ አይበል እኒያ ቅዱሳን ሁላቸው እንደነ ሙሴ ሳሙኤል ሰምሶን ዳንኤል ሌሎችም ስለ ሕዝባቸው እንዴት የፍቅር ነበልባል ከልባቸው ውስጥ እንደተቃጠለ የተረዳ ነገር ነው ይህ ሁሉ የእግዚአብሔር ቃል ኃይል ነበር ። ዛሬሳ አገሩንና መንሥቱን በመውደድ በእንዴት ያሉ ሰዎች ይበረታል ይህ ደህና አእምሮ ያለው ሰው የሚፈርደው ነገር ነው ስለዚህ ለሕዝባችን ደህንነት እንደ ፊተኛው መሰረት እንደገና ይህ ነገር እናጸናለን በሕርያችንንና ውስጣችንንም የሚያጸራ የሚቀድስ ፤ ለመልካም ነገር ሁሉ ምሉ ኃይል ያለው እንደዚህ አድርጎ የሚያሳድገን ደገኞች ሰዎችም ሊያደርገን የሚችል የእግዚአብሔር ቃል ትምሕርት በሕዝባችን በጣም ማሰልጠን ነው ።

አንድ ጸሐፊ ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት ኃይል እንዲህ ብሎ ይጽፋል ፤ ባለፉ መቶዎች ዓመታት እግዚአብሔርን ከሚከዱና ከቤተ ክርስቲያን ጠላትነት የተነሣ ቅዱሳት መጻሕፍት ከብዙች የኤውሮጳ ወገኖች ቤት ተጣሉ ። ከዚሁ የመጣ የትዳር ደግነት ጠፋ ቃል ዳኪን ፈረሰ መታለልና ተንኰል በመተማመን ስፍራ ገባ የሕዝቡ ኑሮ እስከ ልቡ ውስጥ ድረስ ታመመ ። ከፉውን ለማራቅ የተሻለውን አንደኛው ነገር ልናደርገው የምንችል ጥቅም ያለው አንደኛው ነገር ለነዚህ ወገኖች የእግዚአብሔር ቃል እንደገና መስጠት ከርሳቸው የራቀውን መጽሐፍ ቅዱስን እንደገና ከቤታቸው ማግባት ነው ለፈረንሳይ ለኢጣሊያ ለቤልጂክ ለስፓንያ ለጶርቱጋል ለአውስትሪያ በአገራችን የቲፈተነውንና በአያሌነገርም የተደረገውን ለእያንዳንዱ ትዳር ቅዱሳት መጻሕፍት ሰጡ።እኒያስ የቤተ መንግሥት ሰዎች ሁላቸው በስራቸው ሁላቸውም አገራቸውን የሚወዱን ሰዎች መነቃቃት ሊያመጣው ከሚችል ነገር አብልጠ የሚያመጣ ነው በኤውሮጳም ትልቅ መለወጥ ሊታይ ነው ። The Leisure Hour ከእስፓርጂን (Spurgeyn) ተጠቅሶ ።

እንግዴህ የኢትዮጵያችን ሕዝብ ልብ በእግዚአብሔር ቃል ሳይታደስ ምሉ መልካም ነገር ሊመጣ ተስፋ ማድረግ ሕንቱ ነው።የሰማያዊው ንጉሥ ሕግ በቅዱሳት መጻሕፍት እንደተሰጠን ለመጠበቅ ሕዝቡን ቢያስተምሩ የቸሩንና የደገኛው መንግሥት ትእዛዛትን ለመፈጸም እጅግ ያግዛል።እረ እውነተኛውና ፊተኛው መሰረቱ ለዚህ (የሕዝብ ደህንነት) የእግዚአብሔርን ሕግ መጠበቅ ነው።ስለዚህ ኢያንዳንዱ እግዚአብሔርን ቢወድ ቢታዘዝም ለመንግሥቱ ዳኞችና ፈራጆች ስንት የከበደውን ስራ ባቀለላቸው ነበር።ይኼው ልዩ ልዩ ቀጣፊ በከተማውና በየመንገዱ የጨለማውንና የዓመጻን የሁከትንም ስራ ለማድረግ «ዓይን አትየኝ» እያለ ጨለማንና ቅስጥናን የሚጠብቅ ባላነሰምን?መግደል ስርቆት ስካር ዝሙት ከንቱ ጨዋታ ይህንንም የመሰለ ነገር ከሕዝቡ ማኸል ሲርቅ ሕዝባችን በእውነተኛው መንገድ ሔዶ ለኋላውም «ብርሃን ሰላምና» ሊነግሥበት ማለት ነው ። እንግዴህ ከቡሩን ቄሶችና መምሕራንም በኋለኛው ቀን «እንደ ከዋክብትና እንደ ጸሐይ በእግዚአብሔር መንግሥት ልታበሩ» ሕዝባችንን በጻችሁ ባለው በእግዚአብሔር ቃል እንድታስተምሩ እንለምናችኋለን የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው ሰነፎች ግን ትምሕርትንና ዕውቀትን ይንቃሉ (ምሳ ፩ ፡ ፯ ።)

፪ተኛ ። የእጅ ስራና የአእምሮ የምርመራ ስራ ሁሉ ከዚህ በፊት ስድብና ነውር ሁኖ ይታይ የነበረ እጅግ ክቡርና ከፍያለ ነገር መሆኑ በሕዝባችን ማኸል በልዩ ልዩ ትምሕርት ማሳየትና ማሰልጠኑ ።

ከክርስቲያን ሕዝብ ከሚባለው ሁሉ በዚህ ነገር አጥብቆ የደኸየ ሕዝብ እንደ ኢትዮጵያችን የለም ። ምክንያቱም የእግዚአብሔርን ቃል እጅግ ከብረት የሚቀጥረው ስራን እጅግ ነውር የሚያስጸይፍ ስራ ሁኖ በመቈጠሩ ነው ። በሁሉ ባለፈው ዘመናት ምስጋናና ክብር ትልቅ ስጥወታም የሚገባው ስራ ትርፉ ስድብና ነውር ነበር ። አዬ ጉድ ነገር ዛሬ ግን እግዚአብሔር ይመስገን አያሌዎች የስራ ክብር ለማየት አይኖቻቸው ለመከፈት ስለ ጀመሩ የእጅ ስራ ዓይነት የሆነውም የጥበብ ስራ ለማወቅ ጥማት ያደረባቸው ብዙች ናቸውና ይኼው ነገር ብዙ ተስፋ ያስደርገናል።

ሕዝባችን በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት በልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ መምራት ወደ መልካም ዘመን ለመድረስ ጀምሯል ዳሩ ግን እሊህ ነገሮች ለሕዝብ ከፍታ መሠረት መሆናቸው የታያቸው ስንት ናቸው ። ከከበሩ መኳንንቶቻችንና ከታላላቆቻችንስ ዕውቀትንና ጥበብን ሥራንም ለማሠልጠን በይሆን ለመቃወሙ የሚታጠቁ እንዳሉስ አይመስለንም ። ግን አንዳንድም የማይታጡ ቢሆኑ ምን እናውቃለን፡ብዙ ጊዜ በሩቅ ላለ ሰው ይህ ነው ለማለት ይቸግረዋል፡ቢሆን አንዳንዱ ይህን ነገር ሳይጠይቅ ወይም እንዲህ ብሎ ሳይናገር ይቀር ይሆን ፡ ዕውቀትና ጥበብ ይህ የአውሮጳ ትምርት የሚባለውሳ ምንድር ነው ፡ ከዚህ ቀድም እንዴት ኑረናል፡ዛሬስ ምን እንሆናለን ፡ ቢመጣማ አያመጣም እንጂ በጕረዶቻችንና በጦራችን ማን ይቀርበናል ፡ እንዲህ የሚሉ ሰዎች ያሉ እንደሆንም እጅግ እናመሰግናቸዋለን እንጂ አንነቅፋቸውም ። አገሬ ሲያስፈልጋት ደሜን አፈስበታለሁ ፡ እኔ ሳለሁ አገሬ አትደፈርም አትነካም ማለት ፡ እጅግ ምስጋና የሚገባው ነገር ነው ፡ ይህም ብቻ አይደል ፡ የኢትዮጵያን ደምበር በሥፍራው ለመመለስ ማሰብ እጅግ ትልቅ ያገር ፍቅር ነው ። ዳሩ ይህ ሁሉ ነገር እያንዳንዱ የኢትዮጵያ ባላገር ሊያደርገው ከሚገባው ነገር አንድ ገጽ ብቻ ነው እንጂ ። ሁሉም አይደል ፡ ደግሞ ከሁሉ በፊት አስቀድሞ በዕውቀትና በጥበብ መሣሪ ሊታጠቁ እንደሚገባቸው አይርሱ ፡ ከዚህ ላይ ይልቅስ በጥበብና በዕውቀት በማስተዋልም የበለጠው የንጉሥ ሰሎሞንን ምክር መከተል ይሻላል ። ይኸው ንጉሥ እሊህን ከዚህ የሚጠቀሱ ያሉ ቃላት ሲናገር ሳለ ። የእስራኤል መንግሥት በዘመኑ እጅግ ለማና በሀብት በሠራዊት በፈረስ በልዩ ልዩ ዕቃ ጦርም ታጥራ እንደ ነበረች ልናስብ ይገባናል ። ይህ ሳይቀር ግን ጥበብንና ዕውቀትን ከዓርበኞቹና ከኃይል ከጋሻና ከጦር ይልቅ ከፍ አድርጎ እንደ አመሰገነ እናያለን ። መክ ፱ ፲፫ – ፲፰ ፡ ምዕ ፯ ፲፱ ፡ ጦር ሲሆንም አያሌ ጊዜ ድል መንሣት በጥበብ እንደሚገኝ የአምላክ ቃል ይመሰክራል ። ምሳ ፳፬ ፮ ነቢይም ይላል ፤ ዕውቀት የሌለው ሕዝብ ይወድቃል ፤ ሆሴ ፬ ፲፬ ፡ ኢሳይያስም ይላል ፡ ስለዚህ ወገኔ ተማ

ረከ ያውም ዕውቀት ቢያንሰው ነው ኢሳ ፭ ፲፫ ። ዕውቀት በመንፈሳዊ ወይም በሥጋዊ ነገር ከሁሉ የበለጠ ነገር ነው። እንግዲህ ጌቶቼና ወንድሞቼ ሆይ ዕውቀትንና ጥበብን ሥራንና መልካም ነገርም የሆነውን ሁሉ በሕዝባችን ውስጥ ለማስልጠን እንትጋ ። ስንፍናችንና ጉድለታችንንም እየታመነ የተሻለውን ነገር ወደ መያዝ እንራመድ እንጂ ከንቱ መጓደዳችን አይረባንም ስለዚህ ይህ ተሆነ ለዚሁ ላዲስ የኢትዮጵያችን ትውልድየመንግሥታችን ተስፋ የሆነ ለማስተማር እንታጠቅ ፡፡

ከዚህ የቀረው በሚከተለው ጋዜጣ ይታተማል ። በውጭ ያለ የኢትዮጵያ ልጅ ።

ስለ ዘመንና ወራት ልዩነት ።

የምርመራ ወራት መጣች የፍዳ ወራትም ደረሰች እስራኤል ያውቃታል ። ሆሴ ፱ ፯ በተቀደሰችቱና እጅግ ባማረቺቱ ኢትዮጵያ ውስጥ የምትኖሩ ልጆቿ ሁሉ በዕውቀትና ደስ በሚያሰኝ አሳብ ለመመከከር ፈቃድ ያላችሁ ወንድሞቼ ። ከኛ በፊት ባለፉት ዘመናት አባቶቻችን በነበሩበት ጊዜ የዕውቀትና የሥልጣኔ ትምሕርት የሕጻናትም አስተዳደግ እንዴት አድርጎ ብዙ ልዩነት እንዳለው እናያለን ። ከኛ በፊት የነበሩ አባቶቻችን አንድ አንድ ሽማግሎች የዘመኑን ታሪክ የሚያውቁ መልካሚቱ የኛ ዘመን ነበረች እያሉ ሲጫወቱ ሰምቼ በዘመናችሁ እንዴት ትኖሩ ነበር ብዬ ጠየቅኋቸው ። በኛ ጊዜስ የረፋድ መንገድ ቢሆን ወይም የኩለ ቀን ወደ ገቢያም ቢሆን ስንሄድ አስር አስራምስት ሁነን ከነዚህ መሀከልም የታወቁ ጀግኖች ጋሻ መክተው ጕራዴ አብተው የጦር አፍሬ አሳይተው በፊትና በኋላ ሁነው ጀሌውን እየጠበቁ ነው እንጂ እንዲህ እንዳሁኑ ቀጭን ዘንግ ይዞ እያረገረጉና ለብቻ እየተጓዙ ወዳሰቡት አገር መሄድ የለም ነበር አሉኝ ።

እኔም ይህን ንግግር በሰማሁ ጊዜ እንኳን መልካም ነገር እንዳዩና ሽታው እንኳ እንዳልደረሳቸው ተረዳሁና ብዙ አሳዘነኝ ወይ ግሩም ይህችንስ የሰላምና የዕረፍት ጊዜ አይተው ቢሆኑ ምን ይሉ ኑረዋል ። ይልቁንም አቶ ማኅተመ ወርቅ እንደጻፉት በሀገራችን በኢትዮጵያ ሸማ የሚሠሩና ብረት የሚቀጠቅጡ የከብት ቆዳ የሚያለፉና እንጨት የሚጠርቡ አንዳንድ ብልሆች ቢኖሩ ሠራተኞችን ሥራ የማያውቁ ተቀማጮች ሸማኔውንም ይህ ቀፋዳ ሸማኔ ፤ ብረተኛውንም ይህ ብረት አንካች ፤ ቆዳ የሚያለፋውንም ይህ ጥምብ ፋቂ ፤ ጠራቢውን ይህ አናጢ እያሉ እየተሳደቡ ይኸው ጥቂቱ ዕውቀታችን እንኳ ሊቀር ቀርቦ ነበር የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት አጤ ምኒልክ ግን በተሰጣቸው ዕውቀት እንዴት ሥራ የሚያውቀውን ሥራ የማያውቀው ይሰድበዋል ከእንግዲህ ግን በዚህ ነገር አንዱን አንዱ እንዳይሰድበው ብለው አዋጅ አደረጉለት ፤ አባት ያሳየውን መልካም መንገድ ልጅ እንደሚከተል ግርማዊት ንግሥት ዘውዲቱና ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ አባትና እናት የሆኑ ሰው ሁሉ ሥራውን እያስታወቀ እንደ ሥራው ልክ በየማዕርጉ ለመንግሥት እያገለገለ የድካሙን ፍሬ እንዲመገብ እንጂ ሠራተኛው ሲሠራው የዋለውን የሠራተኛውን ደመወዝ ተቀማጩ እንዳይቀማው ብለው ፈቃድ ስላደረጉ ። ሠርተው የጉልበታቸውን ድካም የሚመገቡ ብዙ ሰዎች ለኢትዮጵያ እንዲህ ያለ ዕውቀት የተሰጠው ጠባቂ የሰጠሃት ተመስገን እያሉ በፊት አምላካቸውን ቀጥለው መንግሥታቸውን ሲያመሰግኑ ሰማሁ ።

ደግሞ በሀገራችን በኢትዮጵያ ውስጥ ለቤተ ክርስቲያን ማገልገያ የሚሆን የግዕዝ ትምሕርት እንጂ ለዕውቀትና የስራ ማሰልጠኛ የሚሆን የትምሕርት ቤት ከዚህ በፊት ስላልቆመ በከተማና ከከተማም በገጠር በየዳር አገር ያሉት ሕዝብም በሕፃንነታቸው በሥልጣኔ ትምሕርትና በጥንቃቄ በልክና በስርዓት የሚያሳድጋቸው ስላጡ ሥራ ተምረው ሠርተው በመብላት ፈንታ ሲቀሙና ሲገሉ የጕልማሳ ምሽት ሲጎትቱና ድኃ ሲያስጨንቁ ሁለጊዜም መሸታ ሲያዘወትሩ ከጠጡም በኋላ ልባቸው ያላሰበውን መናገሩም የማይገባውን ንግግር ሲናገሩ ይታያሉ ። ወዮላቸው ጠጅ ለመጠጣት የሚበረቱ የሚያሰክረውንም ለመደባለቅ ለሚጨክኑ የሚለውን የነቢዩን ቃል ስላልመረመሩ ነው ። ኢሳ ፭ ፲፪ ። ስለዚህ ርኅራኄ የመላባቸው ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ይህን የድንቁርና ቀምበር ከሃገሬ ከኢትዮጵያ እሠብራለሁ ብለው ልክ የሌለው ገንዘባቸውን አውጥተው በብዙ አሳብና በብዙ ድካም ለጥቅም የሚሆን የትምሕርት ቤት አቆሙልን ። ቀጥሎም ኢትዮጵያ በዕውቀትና በስልጣኔ ጎረቤቶችዋን እንድትመስል ለጥቅሟ የሚሆን የትምሕርት ቤት እንዲቆም ተብሎ በታሰበው ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ልዑል አልጋ ወራሽ የከበረ ፈቃዳቸውንና የዕርዳታቸውን ልክ ከከበሩ ብዙ መኳንንቶች ጋራ በብርሃንና ሰላም ሲያስታውቁ ወደ ኋላ የቀሩ ብዙ ሰዎች ይገኙ ይመስለኛል ። ከቶ ባይሰሙ ይሆን ? እንጃ ያልሰሙስ አይመስለኝም ። ይህን ቀና አሳብ ዓለም ጠማማ አስመስላ አሳይታቸው ይሆናል እንጂ ለሃገራቸውስ የኢትዮጵያ ጀግኖች እንኳን ገንዘባቸውን ነፍሳቸውም ቢሆን እንዲያሳልፉላት ጥርጥር የለውም ።

ግን የከበራችሁ ወንድሞቼ ይህን የቀና አሳብ አጣመን ሳንመለከት በገርነት ብንተጋገዘው ይሻል ይመስለኛል ። ወዮላቸው መልካሙን ክፉ ለሚሉ ክፉውንም መልካም ጨለማውን ብርሃን ለሚያደርጉ ብርሃኑንም ጨለማ ጣፋጩን መራራ ለሚያደርጉ መራራውንም ጣፋጭ ባይናቸው ጠቢባን ለሚሆኑ ወዮላቸው የተባለው እንዳይደርስብን ። ኢሳ ፭ ፳ ። ነቢያት ስለ ክርስቶስ መምጣት አስቀድመው ቢነበዩ ትንቢታቸው ተፈጸመ እንጂ አልቀረም ። እንዲሁ ለኛም ለሃገራቸው ልማትና ለሕዝባቸው ዕውቀት ቅንዓት ያደረባቸው ወንድሞቻችን በብርሃንና ሰላም ምክር ተጀመሩ ብዙ ቀናቸው ነው ። ይህ ሁለጊዜ የሚመከሩን ቃል በጊዜው ሳይፈጸም አይቀርምና መልካሙን ምክራቸውን ተከትለን በቀናው መንገድ ብንሄድ ይሻለናል የነቢዩን ቃል እያሰብን ማነው ጠቢብ ይህችንስ የሚያስተውል አስተዋይ የሚያውቃትም የእግዚአብሔር መንገድ የቀናች ናት ጻድቃን ይሄዱባታል ተላላፎች ግን ይወድቁባታል ። ሆሴ ፱ ፲፬ ከዚህ ቀጥዬ ትንሽ የግጥም ቃል እጽፋለሁ ።

ኢትዮጵያ አሁንስ ጎረቤቶችሽን ሳትመስይም አትቀሪ ።
ትጉህ ሠራተኛ ይዘሻል ተፈሪ ።
በዕውቀት ዝቅ ብለሽ ተጠቅተሽ ስትኖሪ ።
በብርሃን ልትሄጅ ምንም ምን ሳትፈሪ ።
ከፍ ታለው ደረጃ ለመድረስ ጠንክሪ ።

ክከበርቶች ጋራ ልትነጋገሪ ።
ባንድ የፍቅር ገመድ ታስረሽ ልትኖሪ ።
በክንቱ እቅር ብለሽ አትጠራጠሪ ።
ጥቅም የለውምና ለተጠራጣሪ ።
 በምሕረት ዓይን ያየሽ አምላክ ይመስገን ።
ከጨለማ ወጥተሽ ልታዩ ብርሃን ።
ይሰንብት ብቻ እንጂ ተፈሪ ያንች ዓይን ።
ሸዋ አዲስ አበባ የተሠራውን ።
የውቀቱን መንጠር ባንድነት ይዘን ።
በጐጃም በጐንደር በትግሬ ያለን ።
በየዳር አገርም በጋላ የሆንን ።
ብርሃን በተፈሪ ልናይ ተስፋ አለን ።
ጥርጣሬንና ሐሜትን ትተን ።
ብምንት መጠበቅ ነው ለኛ እሚገባን ።
አቤቱ አምላካችን አንተ እርዳን እያልን ።
እንቅልፍ ሳናበዛ ስንፍናን ጥለን ።
ብውነት ተነገርነው ባንድ ልብ ሁነን ።
ፈጥኖ ይሰማናል ቸር ነው ጌታችን ።
ይህም እንዲፈጸም እላለሁ አሜን። ቄስ ባድማ ያለው።

ስለ መረዳዳት ።

ህዳር ፲፯ ቀን በ፵፰ተኛው ቍጥር በብርሃንና ሰላም ጋዜጣ ነጋድ ራስ በሻህ ስለ ጻፉልን መልክም አነጋገር ተናገሩ ይህ ነገር እውነት ነው ምን ይሆናል ሰሎሞን ምን ይላል ነገርን ከመጀመር መፈጸም ይሻላል አለ ። በቶሎ እንዲሆንልን ለዚህ ሥራ ምንጭ የሆኑ ጌቶቻችንን የመንግሥት አማካሪዎች ልብ፤ ልዑል እግዚአብሔር ያነሳሳልን ብለን እንጸልይ ። ፈርኦን ሕልም አለመ ዮሴፍ ተረጐመ ሥራውን ስልጣኔውን ዕለቱን ተቀብሎ አደረ ነገሩም ተፈጸመ።ይኸውና ለልጅልጅ ይነገርበታል የተመሰገነም ሆኖ ቀረ።ፈርኦን ሕልሙን ለዮሴፍ ነገረ ዮሴፍም ስለተረጐመ ሥራውንና ሥልጣኔውን ሳይጀምር ችላ ቢለው ሕዝቡ በረሐብ አልቀው ይተፉ ነበር ። አሁንም ይሕ የነጋድ ራስ በሻህ ምክር ለኢትዮጵያ ለሐገራችን ዮሴፍ ለደህንነት የተረጐመውን ይመስላል ። ልዑል እግዚአብሔር ሕዝቡን እስራኤልን ከምድረ ግብጽ ከባርነት ሲያወጣቸው ሙሴንና አሮንን ላከላቸው።እግዚአብሔርም በባሮያው በሙሴ እጅ ታምራቱን ሁሉ ያሳያቸው ነበረ ። ኤርትራን ባሕር ከፍሎ በደረቅ ምድር (መሬቸው) አሳለፋቸው ጠላቶቻቸው ግን ለማጥፋት ሲከተሏቸው ውሀው አሰጠማቸው።ሙሴ እግዚአብሔርን እየለመነ ከሰማይ ሕብስተ መና እያወረደ ከድንጋይ ውሃ እያፈለቀ ሲመግባቸው እስራኤል ስለልባቸው ክፋት ሙሴን ሊወግሩት ያስቡ ነበር።ሙሴ ግን ጠሉኝ ብሎ አልጠላቸውም ስለ ርሳቸውም ወደ እግዚአብሔር ይጸልይላቸው ነበር።እነሱንስ ስታጠፋ እኔን ከመጽሐፍ ፋቀኝ እያለ ። ያውም ከዚህ በበለጠ ሕዝብ አለቃ አደርግሃለሁ ብሎ ባምላካዊ ቃሉ ሲነግረው አልጨከነም አጥብቆ ለመነ ይላል።እንደዚሁም ዛሬ በኛ ዘመን ግርማዊት ንግሥትንና ልዑል አልጋ ወራሽን እግዚአብሔር እንደ ሙሴና እንደ አሮን ሰጠን ምንም የኛ ክፋት ቢበዛ ልዑል አልጋ ወራሽ ለሕዝባቸው ሐሳባቸውን አይተዉም ።

ግርማዊት ንግሥትና ልዑል አልጋ ወራሽ እንደሙሴና እንደ አሮን ሆነው እንደኤርትራ የሆነ የድንቁርናን ባሕር ሲያሻግሩን ጊዜ እግዚአብሔርን ማመስገን የነሱን ዕድሜ መለመን ይገባናል እንጂ ማስቀየም ትእዛዛቸውን መተላለፍ አይገባንም እሥራኤልስ በሙሴ ቢያንጐራጉሩ ባሕሩን ከተሻገሩ በኋላ ነው እኛስ ገና በምህሉ ነን ። ከቡራን ኢትዮጵያውያን ሆይ በሐገር ቤት ያሉትና ባዲስ አበባ ያለነው ሕዝብ አሳባችን እየቅል ነው እኔ እንዳሳቤ ይህ የወር ተራ የሚሉት መልክም ሕግ ተጀምሯል ። ከባላገር የመጡ የመንግሥት ወታደሮች ሺል ያለ ኑሮ ለምደው ሰን በተው ይሄዳሉ ። ይህን ሐሳብ ሳይፈጽሙልን ይቀራሉ አይመስለኝም ስለሆነ መዋል ማደሩ በተማሪ ቤት ናፍቆት ልባችን በጣሙን እንዲቃጠል በኋላ ትእዛዙ ባለፈ ጊዜ ሕዝቡ ያለማንጐራጐር ደስ ብሎት በቶሎ ይፈጽመዋል በማለት ይመስላል ። እውነትም የዛሬው ጊዜያችን እጅግ ደስ ይላል የክቡር ዳዊት ትንቢት የደረሰልን ይመስልላ ቸርነትና እውነት ተገናኙ ጽድቅና ሰላምም ተሳሰሙ መዝ ፹፭ ቍ ፲

ደግሞ ከዚህ ሁሉ ጋራ እንዲህ እንበል።ልባችንን ወደ ጥበብ እንድናገባ ዘመናችንን እንቈጥር ዘንድ አስታውቀን አቤቱ ተመለስ እስከ መቼ ትዘገያለህ።ለባሮችህም እዘን ማለዳ ቸርነትህን አጽግበን ።በዘመናችንም ሁሉ ደስ ይለናል ሐሴትም እናደርጋለን ። ባሮችህ ሥራህን ያዩ ዘንድ ልጆቻችንም ግርማህን መዝ ፺ቍ ፲፮።ይህ ሁሉ ትንቢት በኢትዮጵያ ያለን ሰው ሁሉ እግዚአብሔር በቸርነቱ ከሰጠን ንብረት ከበረከቱ አገራችን እንድትለማ እንደምንሰማው አገሮች ሁሉ እንድትሆን ልጆቻችን እንዲማሩ ለምትቆመው ተማሪ ቤት ልባችንን እንድናነሳሳው ነው ።ጥበብን መፈለግ ሥራውን መተው።ምን ይላል በመጽሐፈ ነገሥት ካልእ ም ፲፯ቍ ፴፫ እግዚአብሔርን ይፈሩ ነበሩ ። አምላኮቻቸውን ደግሞ ያመልኩ ነበሩ። ወደ ሰማርያ እንደወጡት እንደአሕዛብ ልማድ አለ ። ይህንን ትርጓሜው አይሳተንም አንሳተው ። ስለኢትዮጵያ ጥቅም የሚያስፈልጋትን በትክክል ባ፵፱ኛው ቍጥር ብርሃንና ሰላም ክቡር ፊታውራሪ ድሬሳ ጽፈውልናል ልጨምር አያሻኝም ።

እንግዲህ ተረዳድተን ይችን የታሰበችውን ተማሪ ቤት አቁመን ልጆቻችንን ካላስተማርን ምንም ብዙ ሺህ ብር ብናቆያቸው እርግማን አይቀርልንምና ልብ እናድርገው የልብ ንጽሕና የሚወድ ጌጋ በከንፈሩ ላይ ትሆናለች ንጉሥም ወዳጁ ይሆናል እንደተባለ ። አንድ ምሳሌ ያየሁት አለና ልንገራችሁ አምላክ በቸርነቱ በሰጠኝ አዲስ አበባ ከተማ ከገባሁ እስከ ፲፫ ዓመት ተቀምጬ በትንሽ ምክንያት ወደውጭ አገር ስሄድ ። እጅግ ሐሩር በጋ ሆኖ በምሄድበት ጐዳና ስለ ድካሜ ከትልቅ ገደል አፋፍ ጥላ አይቼ አረፍሁ ።አንድ በሬ የሚበላው ሣር አጥቶ ሲቅበዘበዝ መጣ ፀሐይ ተኩሶት ከዚህ ጥላ ስር ሊቆም ይሆናል ብዬ ስመለከተው በገደሉ አፋፍ ተጠግታ የበቀለች ለምለም ሣር አይቶ እሷን ነጭቶ ሊጐርስ ቢል አልደርስበት አለ።እኔም ይችን ሳር እበላለሁ ሲል ይህ በሬ ገደል ሊገባ ነው እያልኩ ስመለከተው የፊት እግሮቹን ሁሉቱንም አጥፎ አድርጎ ተንበርክኮ ያችን ሳር ደረሰባትና ጐረሳት።በኋላ ከስዋ አልፍ ያለች ለምለም ሣር አየና ለመብላት ቢንበረከክ አንገቱን ቢዘረጋ የማይደርስ ቢሆን ከዚያ

ተነስቶ ወደሜዳው ከጥላ ስር ተኛ በዚህ እንስሳው አእምሮ እንደተሰጠው እያደነቅሁ ስሄድ ደግሞ በጕዳና መሐከል አንድ ትልቅ ቅምቡርስ ትል ወድቆ አንድ ገብረ ጕንዳን በላዩ ላይ ትወጣለች ትወርዳለች ።ምን ልታደርግ ይሆን እስቲ ጥቂት ልመልከታት ብዬ እንደቆምኩ ተቅምቡርሱ ላይ ወርዳ እግድማ ሮጠች የዚህን ታሪክ ሳላይ አልሄድም አልኩና ተቀመጥሁ ። ጕሬዋ ቅርብ ኖሮ ሩጣ ጥልቅ አለች ። እንግዲህ ገባች ልሂድ አልኩና ስነሳ ከጕሬው ውስጥ እንደውሀ ሙላት ሆኖ ብዙ ገብረ ጕንዳን ተጕልጕሎ ወጣ ከዚያ ቅምቡርስ ላይ ሰፈረና እንደ ኳስ እያንከባለለ ወስዶ ተጕሬው አገባው።።እኔም ከዚያም በፊት አመሌ ክፉ ከሰው የማልስማማ ነበረ ።ባልንጀራ እንዲጠቅም አወቅሁና መንገደኛውን ሁሉ እንደናት ልጅ አፈቅር ጀመረ ፡፡ ጭራሽ አሁንማ ኩራትን በጥፊ ብዬ ከጠገቤ አባርሬዋለሁና ሻል ያለ ኑሮ በሥጋዬ ሳላገኝ አልቀርም በማለት ተስፋ አለኝ።ቅምቡርስ ለገብረ ጕንዳን እንደትልቅ ተራራ ነው።ስለመረዳዳታቸው እንደፈቃዳቸው ወሰዱት።እኛም በፍቅር ተረዳድተን እንደመናገሻ እንደዝቋላ እንደየረር እንደ ሱሉልታ የሆነ የድንቁርናን ጋራ ለመናድ ይቻለናል በብርሃንና ሰላም ጋዜጣ ለምትቆመው ተማሪ ቤት ይህን ያህል ገንዘብ እንረዳለን እያሉ የፈቀዱ ሰዎች ሁሉ በጉባዔ ተሰብስበው ይህን ጋራ ለመናድ ምክር እንዲሰጡ እመኛለሁ።ስፍራውን ለይቶ ጊዜውን ቆርጦ ጉባዔ የምናደርግበትን ጊዜ መንግሥት ለመሰብሰብ ይችላል።፫፻፲፰ ሊቃውንት በሃይማኖት እበው የሚነገሩ ቀድሞ አይተዋወቁም ነበሩ ። ጻድቅ ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ ከሰበሰባቸው በኋላ እንዳንድ ቃል ተናጋሪ እንዳንድ ልብ መካሪ ሆነው ተባብረው ለተዋህዶተ መለኮት መስክረው ተገኙ።ቆስጠንጢኖስ ብዙኅ አድንቆ አመነ። እኔማ አድርጌ አዝናለሁ አባቴ በጨለማው ውስጥ እንዳሉ አለፉ እኔ ደግሞ ክብርሃኑ አልደረስኩም ጥቂት ጭላንጭል ይታየኛል ይህነንም ጭላንጭል ማየቴ በደጉ ንጉሥ በጼ ምኒልክ ነው ነፍሳቸውን ይማርልን የብርሃን መሪ ናቸውና ለተማሪ ቤት መናፈቄና መጣጣሬ ልጄ በጨለማ ውስጥ እንደኔ ተሸፍኖ እንዳይቀር ነው ።

ድንቁርና ገብቶ ቢያደል አገራችን
ቀፈረን አስነሳ ቃሉ ያምላካችን ።
ዘውዲቱን ያስነሳት ለኛ ለሁላችን ።
እቶ ድንቁርና እንዲህ ብትቆጣ ።
አንተ ባታውቀው ነው የመጣብህ ጣጣ
ዓደንህ ሲጠፋ ነው በተማሪቤት።
ኢትዮጵያ ገብተህ እንዲህ ስትዋትት ።
እንዲህ እንደዋዘ ስምደህ መሞላቀቅ ።
ተፈሪ ተነስቶዋል በጊዚያቱ ልቀቅ ።
ጥንትም ተሩቅ አገር ተሰደ የመጣው ።
ደህን ያህል ኖረ አጥቶ የሚያስወጣው ።
አሁን ምን አባቱ ነቃቅተንበታል ።
እደስማም ድምጡ መናገሩ የታል ።
ለገንዘብ ሳስታችሁ እርዳታ ብትክዱ ።
ጠላት ይታዘባል ተውን ወጊዱ ።
እንዲትችላ እንበላት ደችን ወንገ ወለላ
ጌታ እምታስመስል ቢበላም ባደበላ ።
ምኒልክ እንጂ መጀመሪያው ፀሐይ ።
አስማምቶ ከፈተው ብርሃንን እንድናይ
ብንነት ትለምልም የምኒልክ ነፍሱ ።
በዳኘው ትገኝ ንባብና ማሱ።
አገራችን ገብቶ እንዲህ ሲቀናጣ ።
ቀፈሪ ነቃበት አሁን መድረሻ አጣ ።
ንቆን ከመረገጥ እንዲህ እንዳመደ ።
መንግሥትን ለማጥናት እየተረዳዳ ።
ሞት አይሻልም ወደ ስምን ሲያዋርደ ።
ልብ ያላችሁ ሰዎች እስቲናንት ፍረዱ ።
ለሰው ባሪያ ሆኖ ቀምበር ከመግባት ።
ተረዳድቶ ማጥናት ይሻላል መንግሥት ።
አንዱ ገንዘብ ወይ ሌላው በፍራት ።
የሀገሩን መንግሥት ቸለል የሚላት ።
ወዮለት ለኋላው ያለበት ውርደት ።
ባገሩ ያልሆነ ብለው ሲሰድቡት ።
ጠላቶች በስላቅ ሲዘባበቱት ።
ያለበት መከራ ያለበት ሐፍረት ።
እስተወደያው ድረስ ክፉ ስም ጠጣት።
ሌላ መንግሥት ወደ የጠላመንግሥቱን።
የዚህ ምሳሌ አለው የሚገልጥ እውነቱን
ውሻማውን ወደ ዋና ቀጣሪቱን
ቤቱን የሚፈታ የቃል ኪዳን ሚስቱን ።
መክብብ ደስታ ።

ስለ በዓለ ልደት የምስራች።

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ በዓለ ልደት ለክርስቲያን ሁሉ ትልቅ የደስታ በዓል ነውና በታሕሣሥ ፲፮ ቀን(ዲሴምብር ፳፭)የልደትን በዓል ለሚያከብሩ ወንድሞቻችን ክርስቲያን ሁሉ የትልቅ ደስታና የልብ ሙቀት የሚገኝበት በዓል እንዲሆንላቸው ብርሃንና ሰላም ጥልቅ ምኞቱን ያቀርባል ።

ማስታወቂያ ።

በርሻና በመስሪያ ሚኒስትር ሥራ ውስጥ መንግሥት ያወጣውን ደምብና ሕግ ሳልተላለፍ ደሀ ሳልበድል ፤ የመንግሥቱን ገንዘብ በጥንቃቄ ሠርቼ ቀድሞም ከሚሠራው ሠራተኛ ገቢ ገንዘብ አብልጬ አገባለሁ የሚል ሰው እርሻና እመስሯ ምኒስቴር መጻፊያ ቤት፣ ሁል ጊዜ ከጧቱ ከ፫ ሰዓት እስከ ፬ ሰዓት ድረስ ፤ እየመጣ ቢነጋገር በደስታ እንቀበለዋለን ደመወዙም እንደ ሥራው ገቢ እየታየ ይቈረጥለታል ጥቅምት ፲፮ ቀን ፲፱፻፲፰ ዓመተ ምሕረት ።

መኰንን ሀብተ ወልደ።

ማስታወቂያ

ለራሶችና ለደጃዝማቾች ለሴት ወይዘሮች የሚገባ በያይነቱ ጥሩ ካባ ከኤሮፓ መጭቶልኛል ቤቴም (ባንክ ኦፍ አቢሲንያ) ከእንግሊዞች ባንክ አጠገብ ነውና ይህን ካባ መግዛት ለሚፈልጉ ሰዎች መጥተው እንዲገዙ አስታውቃለሁ።

ኢያሱ ዳንኤል

አ ፔ ማርሲያኖ
በኢትዮጵያና በፈረንሳይ የቅኝ አገር ሶማሊ በተለየ ፊያት አውቶሞቢልና ትራክተር አስመጭና እንደራሴ።



A.P. MARCIANO
Concessionnaire Exclusif pour l'Ethiopie
et la cote française des somalis
des automobiles et tracteurs Fiat.

በየኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ።

መጀመሪያ ዓመት ፤ ቁጥር ፶፫ ።
1re ANNÉE № 53

ሐሙስ ታኅሣሥ ፳፪ ቀን ፤ ፲፱፻፲፰ ዓ ም ።
JEUDI 31 DECEMBRE 1925

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d'Ethiopie, profondément désireux de voi regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé "Lumière et paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraissant tous les jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

የጋዜጣው ዲሬክተር ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።
Gabré Christos Taklé Haymanot
Diréčteur

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ደከፈላል ።
በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ደሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ስለ ብርሃንና ሰላም
መጀመሪያ ዓመት ።

ብርሃንና ሰላም መታተም ከተጀመረ ነገ ታሕሣሥ ፳፫ ቀን አንድ ዓመት ይሞላል ። ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ብርሃንና ሰላም ብለው የሰየሙት ጋዜጣችን እውነት እንደ ተሰየመው የብርሃንና ሰላም ሥራ ሠርቷል ይህ መሆኑም የብርሃንና ሰላም አምላክ ሥራው እንዲሰፋ ፈቅዶት አከናውኖት ነው ። ስለዚህ ለአምላካችን አስጀምሮ አንድ ዓመት ሙሉ በደኅና ስላስፈጸመን ወሰን የሌለው ምስጋና እናቀርባለን ለሚመጣው ዘመናትም ብርሃንና ሰላም በበለጠ እንዲዘረጋ ረድኤቱን እንለምናለን።ደግሞ ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ለልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን እድሜያቸው ይርዘምልን እያልን ምኞታችንን እናቀርባለን ።

ብርሃንና ሰላም በዚህ ባንድ ዓመት ውስጥ ካሰብነው በበለጠ ተዘርግቷል ። በመወደድ ላይ መወደድ እያገኘ እንደሄደና ስመ ጥሩ እንደሆነ ከብዙ ብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ምስክር አግኝተናል። በዚህም ነገር ሥራውን ለማስፋት ያለንን ተስፋ ለማበርታት ምክንያት አግኝተናል ። ስለዚህ የብርሃንና ሰላም አንባቢዎች የበለጠ ደስ እንዲላቸው በብዛት ላይ ብዛት እንዲጨምሩ የሚጽፉ ትጉሃን ብልሆች ወንድሞቻችንም የጻፉትን ለማግባት ስፍራ እንድናገኝ በማለት ስምንት ገጽ ካደረግነው አያሌ ጊዜ ነው ። ወደፊትም ስምንት ገጽ እየሆነ ይታተማል ።

በየሳምንቱም አንድ ፤ ወይም ሁለት ክልሸ (ሥዕል) እያገባን እንድናትም ተስፋ እናደርጋለን ።

ከዚህ በፊት ብርሃንና ሰላምን በደስታ ተቀብለው የሚያነቡና እየጻፉ የሚልኩልን ማኅበረተኞቻችንን በጣም እናመሰግናቸዋለን

የሚያስፈልገን አካላዊ ብርሃን ብቻ አይደለም ። በትምሕርትና በዕውቀት የሚገኝ ረቂቅ የልቡና ብርሃንም አጥብቆ ያስፈልገናል ። አንድ ምሳሌ «ዕውነትና ዘይት ይንሳፈፋል» ይላል ።

እንዲሁ ደግሞ ብርሃንና ሰላም በእምላክና በሰው ፊት የተወደደ ነውና ብርሃንና ሰላም እየሰፋና እየተወደደ እንዲሄድ የአምላክ ፈቃድ እንደሆነ ሙሉ እምነት አለን ። በዚሁ ዓመት ብቻ እንኳ በብርሃንና ሰላም።ከብልሆች ወንድሞቻችን ያገኘነው ምክርና ትምርት እጅግ ብዙ ነው ።

በእግዚአብሔር ፈቃድ ። በብርሃንና ሰላም ስብከት እየተሻሻለ የሄደ ነገርም አያሌ ነው ።

ኢትዮጵያዊ ሆይ ብርሃንና ሰላም የሚጠቅምህና የሚያስፈልግህ ነውና ከሁሉ አብልጠህ እንድትፈልገው እንለምንሃለን

ብርሃን ድል አድርጓል ድልም ሊያደርግ ነው ። ጨለማውንም ያባርራል ብርሃን ከሠለጠነ ጨለማ ከራቀ በሰላም ለመመላለስ እንችላለን ።

ኢትዮጵያ በብርሃንና ሰላም እንድትኖር የዓለም ብርሃን ክርስቶስ ይጠብቃት ።

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ሠራተኞች ብርሃንና ሰላም አንድ ዓመት ስለ ሞላው የገጠሙትና የተቀኙት የምስጋና ቅኔ ።

በ፲፱፻፲፯ ዓመት ። በታሕሣሥ ፳፫ የወጣው መብራት ፤
ለውሮች ዓይን ነው ላላወቁ ዕውቀት ።
ለሃንካሳን እግር ለሰነፍ ትጋት ።
የጨለማ ብርሃን ኮከብ የንጋት ።
ድማቅ ነው ብርሃኑ ተግተው ለሚያዩት ።
ለትጉህ ሕይወት ነው ለሰነፎች ሞት ።

ብርሃንና ሰላም ብዙ ፍሬ አፈራ ።
ንጉሥ የማያውቀው ስሙ ያልተጠራ ።
ቆሎ ተሰማነው ሳንል ነግ ሰልሥት ።
እኛን ልጆቹ አርጎ ሁኖ አባት እናት ።
ተግቶ ይመክረናል ሳይቆጥር ሰዓት ።
ብንደኛማ ቢሆን ያ የንጀራ አባት ።
ይላል ምን ቸገረኝ የሞተ ቢሞት ።
ኢትዮጵያ አገሬ አትሁን ተላላ ።
ብልህ እየመሰልህ እንዳትቀር በኋላ ።
ብርሃንና ሰላም ዳኝነቱ ዕውነት ።
ሰነፍና ብልሁን ለየው ባንድ ዓመት ።
ሰነፎች ተገኙ ብልሆች ነን ሲሉ ።
ደግሞ አሉ ብልሆች ሰነፎች ሲባሉ ።
ልዑል አልጋ ወራሽ የሾሙት ወንበር ።
ከቤታቸው በታች ከዋነኛው በር ።
ጉቦ አምጡልኝ አይል አይቀበል ብር ።
ይዋል ይደር አይል ሥራ አይመረር ።
ዘወትር ሲመክር በጥበብ በፍቅር ።
አይዟችሁ እያለ ከዳር እስከ ዳር ።
ያመቱን ሥራ ቢያይ በውቀት መነጥር ።
ብዙ ልጅ አገኘ ላገሩ እሚጥር ። ቄስ በድማያለው ።

መወድስ ።

ብርሃንና ሰላም ዮሐንስ ጸያሒ ፍኖት ።
እመ ተፈኖከ ታርሁ አናቅጸ መንግሥት ምክር ።
ማኅተመ ተፈሪ ጥበብ ሐፀነተከ በግብር ።
ወአጥመቀ ሕዝበ ተዋሕዶ ውስተ ባሕር ፍቅር ።
ነስሐ እንዘ ትብል ፡ አምጣነ ይእቲ ቀርበት መንግሥተ ሰማያት
ብርሃን ክብር ።
ለብርሃንሂ ቃለ ዓዋዲ ነቢየ ልዑል ኄር ።
ዘአልበ የአብየከ እምትውልደ ጥበብ በዲበ ምድር ።
ወምጽአተ ወልድ ጥበብ እንዘ ትኄጽር ።
አድያመ ዮርዳኖስ ኢትዮጵያ ቃላተ ወንጌል ትሜህር ።
አሥራ ዘጠኝ መቶ አሥራ ስድስት ዓመት
ልዑል ከአውሮጳ የተመለሱ ለት
ብርሃንና ሰላም ሰልፉን ሲመሠርት
ሰንደቅ አላማውን አሲዞ በሥራት
ልምላሜና አበባ ተስማምቶት ባንድነት
ለተከታዮቹ ሆኑዋቸው ምልክት
ግንባር ቀደም ሆነ ከሰልፈኞቹ ፊት ።
ልዑል አኳሁኑን ተገረሙ አይተው
ሰልፉን ያሳምራል ይረዳል ብለው
ቢልኩት እሺ ባይ እምቢታ የለው
ለትንሽ ትልቁ ታዛጋ እሱ ነው ።
አሥራ ዘጠኝ መቶ አሥራ ሰባት ሲሆን
በወርኃ ታሕሣስ በሐያ ሶስት ቀን
ብርሃንና ሰላም የተማረው ዲያቆን
ሥልጣን ተቀበለ ከኢቶጵያ አቡን ።
አቡኑ ተፈሪ ሥልጣን ሲሰጠው
ኢትዮጵያን አንጻት ቀድሳት አለው ።
ሥልጣን ተቀብሎ ተሆነ መምር
ብርሃንና ሰላም ሕዝቡን ሲመክር
ወንጌሉን ተርጉሞ ረቂቅ ምሥጢር
ሐተታውን ሳይተው ደግሞ ምርምር
ጥቅሱን ሳያሳስት ሳይረሳ ቁጥር
ፍቅርን አጽኑ ይላል ከዳር እስከ ዳር ።
ብርሃንና ሰላም እጅግ ብልህ ነው
የዓለሙን ታሪክ ባንድ ዓመት ያዘው ።
አይሮፕላን የለው የምድር ባቡር
ይህነን ሁሉ ዓለም ባንድ ዓመት ሲዞር
ንጉሡ ጨለማ አውጥቶት ታገር
ብርሃንና ሰላም በውጪ ሲኖር
ነውር ሳይኖርበት ሳይለውጥ ግብር ።
ባሥራ ዘጠኝ መቶ አሥራ ሰባት ዓመት
ብርሃንና ሰላም ጦሩ ደርጅቶለት
ተጨለማ ጋራ ተጋጥሞ ጦርነት
ድል ለሱ ሆነና ገባ ከሁሉ ቤት ።
ንጉሡ ጨለማ ጠፋበት ጎዳና
ጭፍሮቹ ተማርከው ሰልፉ ተፈታና
ብርሃንና ሰላም ተፈሪ ነውና ።
ብርሃንና ሰላም አገር በጄ ብሎ
አዋጁን ነገረ ቀጥሎ ቀጥሎ ።
ባዋጁ ብንጸና ጠብቀን ቃሉን
የምንመኘውን ቶሎ ባገኘን ።
ብርሃንና ሰላምን ይጠብቅልን
የውቀት መማከሻ እንድትሆነን ዓይን
ይህነን አንድ ዓመት እንዳስፈጸመን
አሥራ ዘጠኝ መቶ አሥራ ስምንቱን
ጠብቆ እንዲያቆየን ከምላክ ተስፋ አለን
የሰላምን አባት ደግሞ የብርሃን
እግዚአብሔር ተፈሪን ያሰንብትልን
በዚሁ ጨርሰን እንበል አሜን
ለዓለመ ዓለም አሜን ለይኩን ። ሰሎሞን የኔነህ ።

መወድስ ።

ብርሃንና ሰላም ነሥኡ ወልታ ተፋቅሮ ፤ የፍቅር ጋሻ
ካልያዙ ጠላትን ማጥቃት አይሆንምና ።
እያንቀሳቃቸው ጥበብ (ኃያል) አዲሱ መኪና ።
አልጋ ወራሽሰ ፈጣሪሃ።ለጥበብ የሰው መከበሻ የአምሮ መጠና
ወያንሶሱ በብርሃና ።
እስመ ቃለ ብርሃን ተሰምዓ ከመ ቃለ ጴጥሮስ ወልደ ዮና ።
ብርሃንሰ (ሰላምሰ) አልጋ ወራሽ ዘየዓውዶ ደመና ።
እምኑፀተ አሳሔል ይቀድም ለአበኔር (ለድኩም) ድንቁርና ።
የኖህ መርከብ ጌታ ተፈሪ እንዲህ ብሎ ማለ በጸና ።
በድንቁርና ማየ አይህ ለኢትዮጵያ (ዳግመኛ) ኢያማስና ።
ዘገየ ተገኝ

ሥላሴ ።

ያበርህ ላዕለ ጻድቃኑ ብርሃን ዘመጽአ ውስተ ዓለም ፤ እም
ኃይለ ሥላሴ ጠፈር ማኅደሩ እስመ ወረደ ቀዲሙ ።(በአቅሙ)
ወአዘዘ አጽናፈ ዓለም ይስብኩ በስሙ ።
ለዘተወክፍዎ ሕዝብ ብሂሎ ውሉደ ሰላም አንትሙ ።
ለእመ ትእዛዝየ ዓቀብክሙ ።
እስመ ትበልዑ ፍቅረ ከራሜ ከራሚክሙ ።
ወሰላመ አኃድግ ለክሙ ።

መወድስ ።

ላዕከነ ብርሃን ይግበሩ በዓለ ፍሥሐ ፤ አምጣነ ወረደ ሎሙ-
ኃይለ ሥላሴ መንፈስ ቅዱስ ።
አሐተ ዕለተ እምነ ዕለታት ሐምስ ።
ወእለ ይሜሕሩ ዓለማተ ፤ ተሰምዓ እንዘ ይትናገሩ በልሳን ሐዲስ
ለእመ ወርዘዉ በለብዎ ዘእንበለ ሥጋ ሰላም እስመ ኢትቀ-
ውም ነፍስ ።
ስሎሞንሂ ኃይለ ሥላሴ ዘየዓውዶ ሞገስ ።
ያስተራትዕ መሠረታ ለጥበብ ቤተ መቅደስ ።
እምጣነ ይቤ ያዕቆብ ልሳነ ምኒልክ ንጉሥ ።
ዝየ ትትሐነፅ ወበኃይለ ነፋስ ኢይትከወስ ።

ተክለ ጊዮርጊስ ።

ስለ ቅዱስ ገብርኤል በዓል አከባበር ።

ታኅሣሥ ፲፱ ቀን የቅዱስ ገብርኤል በዓል ተከበረ እንደዚሁ ደግሞ ታኅሣሥ ፳፪ ቀን እመቤታችንን ስላበሠራት ክብሩ ነው ። ይኸም በዓል የሚከበር መጋቢት ፳፱ ቀን ነበረ ግን ሊታውንት በብያኔ ከዓቢይ ጾም ላይ እንዳይሆን ብለው እዚህ አምጥተው ሠርተውታል ስለታሪኩም በስንክሳር ታኅሣሥ ፳፪ ቀን ተመልከት ።

ታኅሣሥ ፲፱ ቀን ጧት ልዑል አልጋ ወራሽ ወደ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን እንዲሄዱ ታውቆ ነበርና መኳንንቱና ሠራዊቱ መጥቶ ሲጠባበቅ ግቢውን አስጨንቆ ነበር ።

ልዑልም ባማረች በቅሎ ተቀምጠው ከመንገዱ ሲገቡ ሠራዊቱ ሁሉ በየደንቡ የሐምሴን አሠሣ መስሎ ይጓዝ ጀመር።

የሰራዊቱም ብዛት እጅግ ያስደንቅ ነበር ደስ የሚለን ነገርም ሠራዊቱ እንደዚህ በዝቶ ሳለ ሊጋባ ጋዳጅ ዘንጋቸውን ይዘው ያጋፍሩ ነበር እንጅ እንደ ቀድሞ ዘመን ሰው መጋፋትና መማታት አልነበረም ።

ክቡር ደጃዝማች መሸሻ ወልዴም በመንገዱ ቀኝ ለወርተራ ለመግባትና ትእዛዝ ለመቀበል በተደነባው ደንብ ሰዎቻቸውን አስገብተው ነበርና ብዙ ሠራዊት ታየ።እሳቸውም ጠበንጃቸውን ይዘው ሰውን እስከ ጫፉ ለማሳየት በእግራቸው ሲሄዱ እጅግ ያምሩ ነበር ።

ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት አስቀድሞ በጧት ገብተው ነበረና ልዕልት ወይዘሮ መነንም ባማረች አቶሞቢል ተቀምጠው ወዲያው ደረሱና ከቤተ ክርስቲያኑ ገቡ ።

ልዑል አልጋ ወራሽም ሶስት ሰዓት ተኩል ሲሆን መጡና በትልቅ አጀብ ገቡ።ይህ ሁሉ ሲሆንም ነጋሪቱ ይጐሰም ነበር ከዚህ በኋላ ዲያቆኑ መስቀሉን ይዞ ብቅ አለና ፡ ፈለግ ዘይውኅዝ ያስተፌሥሕ ሀገረ እግዚአብሔር ፡ ቀደሰ ማኅደሮ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ውስተ ማዕከላ ኢትትሐወክ ብሎ ሰበከ ሕዝቡም ይኸኑ ቃል ተቀበሉና ቄሱ ወንጌል ብሎ ወጥቶ ከሉቃስ ወንጌል ምዕ ፩ ለዘካርያስና ለመቤታችን ቅዱስ ገብርኤል ተልኮ የተናገረውን የምሥራች አነበበ ።

ከዚህ በኋላ መዘመራኑ ወእንዘ ትፈትል ወርቀ ወሜላተ አስተርአያ ገብርኤል ግብተ ወይቤላ እስመ፡ረከብኪ ሞገሰ በኀበ እግዚአብሔር።ወትቤሎ ይኩነኒ በከመ ትቤለኒ ብለው አመለጠኑ ። ይህኑ ወልደ አማኑኤል የተባለ ደብተራ ጉድ አድርጎ መለሰውና እጅግ ደመቀ ። የድምፁም ላህይና ወዝ ለሰው ሁሉ አስገረመ ።

፬ት ሰዓት ተኩል ሲሆን ታቦት ወጣና ቆመ ልዑል አልጋ ወራሽም ክቡራን መኳንንቶቻቸው ግራና ቀኝ ከበዋቸው ከመስኩ ላይ በወንበር ተቀምጠው ነበርና ካህናቱ ወትቤሎ ይኩነኒ።እያሉ በልዑል አልጋ ወራሽ ፊት ሲያሸበሽቡ አምረውታዩ። ዑደቱም ባምስት ሰዓት ተጨረሰና አባታችን አቡነ ማቴዎስ አሳርገው ታቦቱ ገባ ።

ከ፺፪ ቁጥር የቀረ ቃል ።

የኢትዮጵያ ደህንነት ።

፫ኛ ፡ አገራችንን መንግሥታችንን በጣም ማፍቀር ለእርስዋም እጅግ የታመን መሆን ይህ ከዓይነተኞች ነገርም አንድ ራስ ነገር የሆነ በሕዝባችን ማኸል መዝራት በማስተማር በጋዜጣ በመጻሕፍት በመነጋገርም የሕዝባችንን ልብ ለዚህ ትልቅ ያገር ፍቅር (ፓትሪዮቲስም)ማነቃቃት ።

ፍቅር ብዙ ዓይነት ነው።በእንዴት ያለፍቅር ነው አገራችንን ልወንድ የሚገባን?ፍቅር ማለት ፤ ያችው የተወለድነባት መንደር ፡ ያባት ወይም የእናት ርስት ብቻ አይደለም በሰፊውና በጥሩው አሳብ እንዲህ ነው እንጅ ፤ መንግሥቱንና በመንግሥቱ ውስጥም ያሉትን ልዩ ልዩ ሕዝቦች ደማቸው አጥንታቸው ምድራቸው ስርዓታቸው ጠባያቸው ፡ አእምሮዋቸው ቋንቋቸውም አንድ ። ወይም ካንድ ስር የወጣ የሆነ እነዚህን እንዳንድ አድርጎማፍቀር ማለት ነው ። ደግሞም የራሳችንን ጥቅም በመሻት ብቻ ታስረን እስካለን ጊዜ አገራችንን እንደሚገባ ልናፈቅራት አይሆንልንም ። አስቀድሞ እንዲህ ያለ መንፈስ ከያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ልብ ይራቅ ፤ ምን አግዶኝ የሌላው እኔን ይመቸኝ ይህነንም የሚመስል ። እንዲህ ያለ የዓመፃ አሳብ የገዛው ሰው ከሰው ቍጥርም ሊገባ አይገባውም አገራችንና የከበረችውን መንግሥታችንን በሚሰራ ነገር ራሳችንን መሥዋዕት እያቀረብን ብንሽቀዳደም እውነተኛውን ፍቅር በልባችን እንደገባ እናስረዳለን እንዲህ ያለ የከበረ ምሳሌም ከልዑላን መሪዎቻችን እናየዋለን ።

ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ልዑል አልጋ ወራሽ የኢትዮጵያን ደህንነት ብቻ ስለፈለጉ ራሳቸውን በፍቅር መሠዊያ ዕለት ዕለት እንደሚያቀርቡ በሁሉ ተመስክሮላቸዋል ።እኒያም ሌሎች ክቡራን መኳንንቶች ምኒስትሮችም በጅግ የልብ ፍቅርና እምነት የኢትዮጵያን ደህንነት ይሰራሉ ይባላል ኢትዮጵያችንም

እንዲህ ያሉ የታመኑ የሕዝባቸውን ልዕልና የሚፈልጉ መሪዎች ስለአገኘች የተመረጠችና የታደለች ናት ልንላት ይቻለናል እያንዳንዱም ትልቅ ሆነ ትንሽ የዚህ ትልቅ ሥራ ረዳት መሆን እንደሚገባው ይወቅ ።

ስለዚህ ክቡራን መኳንንትና የሕዝባችን ትልልቆች በሥጋዊው በመንፈሳዊው መሪዎች ለመሆን ከፈጣሪ እጅ አደራ የተሰጣችሁ በያገሩ በያውራጃው በሸዋ ባማራ በትግሬ የኢትዮጵያ ሰንደቅ አላማ በሚምበለበልበት ስፍራ ሁሉ ያላችሁ አገሬ መንግሥቴ ሕዝቤ በሚል መንፈስ ሕዝባችሁን ከውስጥና ከውጭ ሊመጣ ከሚቻል ጉዳት እንድትጠብቁ ራሳችሁን በመሠዋት ለኋለኛው ቀንም ሐሳብ የምትሰጡለት ሥራ መሆኑን አጥብቃችሁ እንድትረዱት እናሳስባችኋለን። አባትና እናት ልጆቻቸውን ዕለት ዕለት ልባቸውን እንዲጥሉባቸው እንዲሁም እናንተም የሕዝባችሁን ሕይወት እንድታዩ ሁላችንም አገራችንና መንግሥታችንን ለማዳን የሲምሶንን መሥዋዕት ያህል ማቅረብ ያስፈልገናል ነፍሴ ከፍልስጥኤማውያን ጋራ ትጥፋ ብሎ ነፍሱን ለሞት አሳልፎ ጠላትን ተበቅሎ አገሩን አዳነ። ወንድሞቼ የኢትዮጵያችን ደህንነት ከያንዳንዳችን ይፈልጋል። አዩ፡ ከዚያ የባሕርያቸው ጀግንነት ጋር ይኸው ያገሩ ፍቅር በአፅላፉት የኢትዮጵያችን ልጆች ልብ እንደ ብርቱ እሳት ቢቃጠል አገራችን በጣም በታፈረችና በተፈራች ነበር ደማችንም እጅግ በከበረ. ስለ አገራቸው ፍቅር ነፍሳቸውን የሰጡ ሰዎችን ታሪክ ስንሰማ ልባችንን ስንት ያቃጥላል። እንዲህ ያለውን ትልቅ ሥራ ራሴን ይመቸኝ እኔን የገዛ ራሱን ለመውደድ እንደ ደንጊያ የደነጋ ልብን ሳይቀር እንኳ ባቀለጠ ነበር። ወንዶች ሆኑ ሴቶች ሆኑ ስለ አገራቸው ፍቅር ብለው ሲደነቅለት የሚኖር የጀግንነትን ሥራ አሳይተዋል ሥልጣኔ ባላቸው ሕዝቦች በያንዳንዳቸው ይህን የመሰለ መታሰቢያ አላቸው ይልቁንም የእስጳርታን እናቶች እንዴት እንደነበሩ ብንሰማ እንዲያው ተደንቀን መቅረታችን ነው

በኢትዮጵያ መንግሥት ማገልገል ያደሩ አገልጋዮችም ሁላቸው እጅግ የታመኑና መንግሥታቸውንም የሚወዱ ለመሆን ሊማሩ ይገባቸዋል። ወታደሮችም የነበረችውን የኢትዮጵያችን መንግሥት ወታደሮች እንጂ የንዳንድ ራስ ወይም ያንዳንድ ደጃዝማች ወይም ያንዳንድ ሹም ወታደሮች እንዳልሆኑ ራሳቸውን ይቍጠሩ። ከንዳንዱ ሹም በታች ቢሆኑ መንግሥት ከሹሙ እጅ በታች ያስቀመጣቸው ናቸው። መንግሥት ሲፈቅደው ጊዜ ሹሙ ሊለወጥ ይቻላል። ወታደሮች ግን የመንግሥት ናቸው ግን ከነዚህ ወታደሮች የኢትዮጵያ መንግሥት ወታደሮች እንጂ ያንዳንዱ ሹም እንዳልሆኑ የሚያውቁ ስንት ናቸው ምክንያቱሳ ምንድር ነው? ቀድሞ በገራችን በሌሎች ሕዝብ እንደነበረ እያንዳንዱ ስለ የራሱ ሹመትና ክብር ለማግኘት እርስ በርሱ ይዋጋ ነበረ የከበረው የሰው ያውም የወንድም ደም በሁሉ ስፍራ እንደ እንስሳው ደም ይፈስ ነበር። ወታደሩም ያበላውንና ያጠጣውን እንጂ ከዚያ አልፎ የመንግሥትን ነገር አያውቅም ነበር። ነገር ሲሆንም ጌታዬ ማነው የሚዋጋ ብሎ አይጠይቅም ከመንግሥት ሆነ ከሽፍታው መሆን ለወታደሩ ሁሉ አንድ ነገር እንደሆን ነበር። እንዲህ ሁኖም ስለ አገሩና ስለመንግሥቱ በሰፊው አሳብ አስቦ የሚሠራ አልነበረም ስለ ራሱ ትዕቢትና ስለ ገዛ ሹመቱ ስለ ማይረባ ባላባትነት የሚባል የደንቆሮው አሳብ ደም ማፍሰስና ዘመቻ ሽፍትነትም ትልቅ ጀግንነት ይቈጠር ነበር ።

ዛሬ ግን እውነተኛው ጀግንነት ይህ እንዳይደለ ለማየት ብዙች ስለ ጀመሩ ብዙ ደስ ያሰኛል። ከክቡራን መኳንንቱና ከትልልቆች ከሕዝቡም እውነተኛው ጀግንነት ለገዛ አገሩ ማሰብ ማዘን ለገዛ ደሙ መውደድ ስለ አገሩ ደህንነትም በሚቻለው ሁሉ መሥራት ከሌላው ሁኖ ክብርና ተመችቶት መኖር በመንግሥቱ ማገልገል ውስጥ ተዋርዶና ተቸግሮ መኖር እንደሚበልጥ ወደማወቅ ስለደረሱ ብዙ ተስፋ ያስደርጋል ቢሆን ብዙ የተደረገ የለምና የልዑላን መሪዎቻችን አሳብ እየተመለከትን ፍለጋቸውን መከተል ይገባል ።

አገራችንን ሊያድንዋትና ሊያከብሯት የሚደክሙ ስለ አገኘች አምላክን እናመሠግናለን። አንድ ያሁኑ ያገሩ ጉዳት ያለውን ሲናገር ሳለ፡ በጋዜጣ እንደተገኘው እንጠቅሳለን «እንደ የሠለጠኑ የሕዝብ ማኅበር እርስ በርሳቸው በመከባበር መኖር፡ ለእንግዴህ ሀበሻውንና የበካራ ካናቶ ሰው ማክበር የጀመረ፡ ለ ፡ ፡ ፡ ፡ ለወደፊት የሚደርስ አለመሆኑ እውነት ነው እውነት አይደለም ባሞራልና (የልብ ደግነት) በፖለቲክ በገንዘብም (በዚህ በሶስቱ) ክሳራ ወይም መውደቅ ነው ያለነ፤ እውነትን ነው ወይስ እውነት አይደለም፤ ለዚህስ አበሰኛው ማን ነው፤» ይህ ሳይቀር የኢትዮጵያችን ሕዝብ ክብርና ነጻነት ከጥንት ዘመን ጀምሮ እንደሆነ ስለ ሕዝባችን በተጻፈው ታሪክ ይታያል ። ኢትዮጵያችንን ከውጭ ያዋረዳት የለም ። ከዚህ በፊትስ የሕዝባችን ጉዳት የነበረው ከውስጥዋ ብቻ ነበር ። ጥቂት ነካ ነካ እንዳደረግነው ። ዛሬም የቀድሞ ስፋትን እንኳ ባትይዝ ነጻነትዋንና ክብርዋን ለማጽናት ብዙ የታጠቀች ናት ።

ሕዝባችን እያንዳንዱ ሰው በእንዲህ ያለ የፍቅር እሳት ሲቃጠል፤ ጠላት እንደሚበርደው እርግጥ ነው ። መንግሥታችንም ያገልጋዮቹን ሞያና ደግ ሥራ ሁሉ በምስጋና ሳያስበውና ሳይክሰው አይቀርም ።

፬ ፤ አንድነት ከሁሉ የበለጠ ኃይል ነው ። ለሕዝብና ለመንግሥት ሕይወትም አንዱ ከዓይነተኞች መሠረት ነው ።

አንድነት ባለበት ሁሉ ብዙ ኃይል እንዳለ እያንዳንዱ በቶሎ ሊረዳው የሚቻል ነገር ነው ። በዚህ ኃይል ብቻ ነው የሕዝብና የመንግሥት ጽናት የሚገኝ ። ይህ ያያሌዎችን ሕዝብ ኑሮ ብንመለከት የምናየው ነገር ነው ። የያንዳንዱ የአሁኑ የሠለጠኑ መንግሥታትና ሕዝብ ። የሕዝባቸው አንድነት ሳይታወቅና ሳይፈጸም እንዴት ያለ የተጠቃና የደከመ የድህነት ኑሮ ይኖሩ እንደነበር የገዛ ታሪካቸው ይነግር የለምን፤ የሕዝባቸው አንድነት ከታወቀና ከተፈጸመ ወዲህ ግን በጭር ዘመን ወደ ኃይልና ወደ ሀብት ወደ ክፍታም ሲደርሱ እናያለን ። ከዚህ ሁሉ ጋር ደግሞ ዛሬ ሕዝቦች ወደ ጥፋትና ወደ መዋረድ በሚያደርሳቸው የሕይወት ሕማም ተይዘዋል ። የሕዝብ አንድነት (በፓርቲቲ) (በሴራ ብዛት) ሲታወክ ይኖራል ።

እንዴህ ክቡራን መኳንንቶች ሆይ ባንድነት ማሰሪያ ታሥራችሁ የኢትዮጵያን ደኅንነት ብቻም ሲሆን አሳባችሁ እንዴህ እያደረጋችሁም ወደ ቀኝና ወደ ግራ ስትመክቱበት የዘለዓለም ክብርና ድል መንሣትም የናንተ እንደሆነ እናው-

ራላችኋለን ። የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት ወዳጆችም አንድነትዋን ለማጽናት ይሠሩ ይሆናል፤ዳሩ ግን ጳላትና ምቀኛ ሲገኝ የአገራችን ነጣነትንና ክብርንም የማይወድ እንዳለ የሆነ እንደሆን ምንም ሥራ ቢሥራ አገራችን ለመጉዳት ይህን አንድነትን ለማፍረስና ለማጥፋት መንገድ ለማግኘት ፡፡መሥራት ባይሆን ምቀኛ ሲገኝ ግን ይህን ፖለቲክ ፊተኛው ስራውን ባደረገ ፤ እርስ በርሱ በማጣላት ወዳጅና መከሬ መስሎ ረድኤት ለመስጠት ማታለል ማቆላመጥ እርስ በርሱ ጥርጥርንና አለመታመንን ማስነሳት እንዲሁም የሚመስሉ ነገሮችን ። የሚያንጸ ባርቁ ተስፋ በወርቅ ጽዋዕ በሚመስሉ ሲቀርቡልን መቀመስም አይገባም ። ራሳችንንና አገራችንን ያጠፋሉ እንጂ ምን ጥቅም እናገኝባቸዋለን ። ያያሌዎች ሰዎች ቢኦግራፊ (የሕይወታቸውና የሥራቸው ታሪክ) ብናነብ የራሳቸውን ክንቱ ረብ ለማግኘት ብለው የማይገባውን ግም ሥራ በመሥራት ራሳቸውን እንደ ጐዱ እናያለን ። ያለሙትን ጥቅም ወይም ሹመት ይሁን ክብር ለማግኘት ተፈትነው የነበራቸውን አጠፉ እንጂ ምንምን አላገኙም ። ፌድሮ የቀበሮና የቁራም ምሳሌ በለቲና እንደጻፈው ። በዓለም ታሪክም ብናይ ይሁዳ መቃቤዎስ የሶርያን ጠላትነትና ኃይል ይበረታብኛል ብሎ የሮማውያንን ረድኤት በመፈለግ በሮማውያን በመጠጋቱ የገዛ አገሩን ነጣነት አጠፋ እንጂ አልተረዳም ።

ለሕዝባችን ደህንነት አንዳንድ መሠረቶች ከተናገርን ደግሞ ለሕዝብና ለመንግሥት ጉዳት ከሚሆኑ ነገሮች አንድ አንድ መንከት እንሻለን ። እርሳቸውም የሕዝብና የመንግሥት መውደቅ ዓይነተኞች ምክንያት ሁነው ለእግዚአብሔር ቃልና በዓለም ታሪክ ብርሃን እንደሚታዩ ናቸው ። ፩ «ጽድቅ ሕዝብን ታነሣለች ፡ ኃጢአትም ወገንን ታነውራለች ። » (ምሳ ፲፬ ፡ ፴፬)

ያለም ሕዝብ የአካሔዳቸው ወይም የኑሮዋቸው ሕግ ። ዓለምን በሚመራ በእግዚአብሔር ፊት አንድ ሕግ ብቻ ነው ያለ።

ለድሮው የዓለም ሕዝብ የስልጥንናቸው ወይም የመውደቃቸው ምክንያት የሆነ ። ዛሬም ላሉ ሕዝብና መንግሥታት እንዲሁ የማይለወጥ ምክንያት ሆኖ ይቀራል ። የእግዚአብሔር ሕግና የአደራረጉ መንገድ እንደገዛ ራሱ አይለወጥምና።ዓለም ከተፈጠረች ጀምራ በሁሉ ዘመናት የሕዝብ አኗኗርና አካሄድ በእግዚአብሔር እጅ ብቻ ነው ። ስለዚህ እግዚአብሔር ሕዝብን አንድ ጊዜ ክብረት ፡ አንድጊዜም ፡ ውርደት አንድ ጊዜም ሀብት አንድጊዜም ድህነት።አንድጊዜ መንግሥት ። አንድጊዜም በጠላት ሕዝብ እንደሚጠቁ ማድረግ ። እንደዚህ ያለ ክፍና ዝቅ በማሳየት ትልቅ አሳብ ያለው ነገር ነው እንጂ የማድላት ነገር በርሱ የለም ። ለያንዳንዱ ሕዝብ ወገናቸውንና ስፍራቸው ዘመናቸውን እየወሰነ ወይም ዳርቻ እያደረገላቸው በዓለም የሚመራቸው እርሱ ነው ። ግብረ (ሐዋ ፲፯ ፳፮ ። መዝ ዘዳ ፴፪ ፰ ። ኋለኛው ትንሽ ክፍል) ምንስ የዛሬው መንግሥታትና ሕዝብ ይኸውና እውነት ለአእምሮዋቸው ባይስማማ ግድ የለም የጥፋታቸውን ትልቅ የማያሳስት እውነተኛ ምልክት ነው ። ዛሬም የዓለም ሕዝብ በርሱ (በእግዚአብሔር) ይነሣሉ በርሱም ይወድቃሉ ። (ኢዮ ፲፪ ፳፫ ።

በዓለም ሕዝቦች ማኅበር ምክርም እግዚአብሔር ይገለጣል።ምክሩንና ፈቃዱንም ተቋቁሞ የሚወጣ የለም። (ኢዮ ፳፣ ፲፪ ፲፬ ፡ ምዕ ፴፬ ፲፰ ፴ ምዕ ፴፯ ፴፩ ፡ ኢሳ ፳፱ ፲ ። ዳን ፩ ፴፰ ፴፯ ።) ስለዚህ ከዓለም ሕዝቦች መሰብሰብና ምክር መቶባበርም ፡ እግዚአብሔር ይሆን ዘንድ ከልፈቀደው ነገር ሕዝቦችን የጠቀማቸውንና ያዳናቸውን ዓይነተኛ ነገር አልተደረገም ባሰባቸው እንጅ ። (ኢሳ ፰ ፲፩ ፡ ፲፫ መዝ ፪ ፩ ፫) ። ይኸው የእግዚአብሔር ሁሉ ቻይነቱና አምላክነቱ እጅግ ተረስቷልና ሕዝቦች ወደ ጥፋት አፋፍ ደርሰዋል ። በአያሌዎች የቀድሞ ሕዝብ ማኻል ብዙ የሚያስደንቅ ስልጣኔ ኑሮዋቸዋል ። የሥራቸውንና የጥበባቸው ቅሬታ እንደሚመሰክርላቸው ። ዳሩ ግን የመታሰቢያቸው ሥራ ሲኖር እርሳቸው ጠፍ ፡ ከተሞቻቸውም ፍራሾችና በረኻ ሁነው ቀርተዋል ። ይህ ሁሉ ምክንያቱም የእግዚአብሔርን ጽድቅ ስለተላለፉ ነው ። ስለዚህ ኃጢአት በሕዝቡ መኻል ሲሰለጥን ሕዝብ ጠፋ ማለት ነው ። ሕዝቡም ከኃጢአቱ ሲመለስ የእግዚአብሔር የጽድቁን ትእዛዛት ሲከተልም ዳነ ማለት ነው ።

በውጭ አገር ያለ የኢትዮጵያ ልጅ ።

ከዚህ የቀረ ቃል በሚመጣው ቍጥር ይታተማል።

ስለ መረዳዳት ሁለተኛው ።

ጋላም ዝም አማራም ዝም የሚሉ ተረት ደረሰብን በዚያው ሰሞን ለሐገራቸው የሚሳሱ የሚያስቡ እንደአውሮጳ እንድት ሰለጥን የሚጣጣሩ የኢትዮጵያ ልጆች ለሚቆመው ተማሪ ቤት ይህን ያህል እንረዳለን እያሉ በየሳምንቱ ብርሃንና ሰላም ስማቸውን እየያዘ ሲመጣ እንደማርና እንደወተት እየጣፈጠን የሱ ደስታ ደስ እያሰኘን አጥንታችንን ያለመልመው ነበር አሁን ግን እረዳለሁ የሚል ያንድ ሰው ስም ስላልተገኘበት እኔ እንዲህ ያዘንኩ ብርሃንና ሰላም እንደምን ያዝን ይሆን በማለት የድንጋጤ ሐሳብ ወደቀብኝ ። መቅረትስ ለሐገሩ የማያስብ ሕዝብ አይፈጠርምና ይቀራል ተብሎ አይጠረጠርም ። ከዘገዩ ተስፋ የተፈጸመች ፈቃድ እንደተባለ ስለሆነ በፈቃዱ ያቀረበው ደስ ያሰኘን ነበረ ። አሁንስ እባክህ ብርሃንና ሰላም ሆይ ተወኝ እንደልቤ የጻፍኩትን አትምልኝ አንተ ከሰው እንድትስማማ ደግደጉን ስትጽፍ ተግሣፁ ይቀራል ከልቤ ነዷልና ከሰነፍ መቶ በትር ላስታዋይ ሰው ተግሣፅ ወደልቡ ጠልቆ ይገባል እንደተባለ ። ኤሳው ብኵርናውን ለምስር ወጥ ለያዕቆብ ከሸጠ በኋላ ብኵርናውን በሀዘንና በለቅሶ ቢፈልጋት እንዳልተገኘች አሁንም እኛ ለልጆቻችን ለሥጋቸውና ለነፍሳቸው ሕይወት የምትሆን የተማሪ ቤት ተረዳድተን እንሥራ ሲባል ጊዜ ለሚያልፈው ንብረት ብንለውጣት እንደኤሳው ባለጠጠት ሆነን መቅረታችን ያለጥርጥር ይሰማናል የሐገራችን የኢትዮጵያ አርበኞች ጀግኖች ሐብታሞች እንግዴ ተቀባዎች ጉልበታሞች ትሕትናሞች ተብሎ እንደተጻፈላቸው በፊሎሶፎች ታሪክ መጽሐፍ ተጽፎ ተገኝቷል እውነት ነው እንዲሁ ናቸውና ጀግንነት ማለት ከልብ የወጣ ንቃት ነው ጠሩ ሲፋፋም ፈሪ ያመሉን እቀበሮ ጉድጓድ ሲገባ ጀግኖች ጋሻ መክተው ጠመንጃ አንግተው ጐራዴ መዘው እየፈከሩ በሚገላምጠው ውጊት ውስጥ ይገባሉ ፈሪ ስለደፈጠ ጦሩ አይፈታም ድል ለሰጠው ይሰጣል ኃይሉ የልዑል እግዚአብሔር

ነው አሁንም ይችን ለሕዝብ ብርሃን ልትገልጥ የተጀመረች ሐሳብ ስለገንዘብ መሳሳት ችላ የሚሉ ሰዎች ቢኖሩ መስራቷ ላይቀር ያገር ፍቅር የለባቸውም የመባልን ስም ያተርፋሉ ። በብርሃንና ሰላም ሳነብ የክቡር ያቶ ሚካኤል ብሩ ልጆች ለሴቶቹ ተማሪ ቤት ይህን ያህል እንረዳለን የሚል ቃል ባገኘበት ስለሐገራቸው ፍቅር የልብ ሐሳብ ሞኞች መስሎኝ የተቀደሰ ሐሳብ ነው ብዬ በጣሙን አመስግኝ ነበር ። አቶ ማኅተመ ወርቅ በጻፉት ቃል ከብርሃንና ሰላም ውስጥ ተረዳሁት ሐገራቸውንማ የሚወዱ ቅዱስ ጴጥሮስ እንደመሰከረላት እንደሳራ የተመረቀ እንደዚህ ዓለም ወይዛዝሮች ለሚያልፈው ጌጥ ያልሳሱ ልዕልት ወይዘሮ መነን የሴቶችን ተማሪ ቤት ስለማሰራታቸው የማያልፈውን ስም ያዙ ። ይህ ሥራ ለኢትዮጵያ መጀመሪያ ነው እጅግ ያስደንቃል ክቡር ዶክተር ላምቤ እንደ ተናገሩት በዚህ አሁን የተቀመጥነው ሰዎች እንረሳለን በዚህ ሆስፒታል ላይ የተጻፈው ስም ግን ለዘላለም መታሰቢያ ሆኖ ይቀራል እንዳሉት ያለ ነው።ጥል ክርክር ፍቅር እንዳትገባ ትቢት የተማሪ ቤት እንዳትቆም ንፍገትን የምታመጣ በልባችን የምትታወከው ምቀኝነት አይደለችምን ይህን ሁሉ አጥፍታ ያአንድነትን ብርታት የምታመጣ ትምርት ነበረች ልዑል እግዚአብሔር ይመስገን እስከሁን ኢትዮጵያን የጠበቀልን ዘመናችንን በከንቱ ፈጽመናታል ይህ በከንቱ አናንዋራችን ለልጆቻችን እንዳይቆይ እንትጋበት ። ደግሞም ብርሃንና ሰላም ይሰለቸኛል ብዬ ነው እንጅ ከተግሣፁ እጨምርበት ነበር ስለሆነ ካምሳ ሁለተኛው ቍጥር ብርሃንና ሰላም የተረፈውን የግጥም ቃል ላስከትል ።

ውሽማውም ንቃው ትታዘበዋለች
ለቃል ኪዳን ሚስቱ ያልሆናት ትላለች ።
የኔም ለት ይኸው ነው ብላ ትንቃለች ።
ከከንቱነት ግብሩም ትታዘበዋለች ።
ገንዘቡን ጨርሳ ሂድ ውጣ ትላለች ።
የዚህም ምሳሌው ትርጓሜው ባጭር ።
ሰውየው ባለርስት ባገር የሚኖር ።
ንጉሥ በሰጠውም በጉልቱ እሚያድር።
የቃል ኪዳን ሚስትም መንግሥትና አገር
ውሽማው ንፍገት ነው ጠላት የሚታልል
እያለሰለሰ አገር ሲሰልል ።
በመልካም ንግግር ደህና በመምሰል ።
ድህነት የሚሰድ ካገር የሚነቅል ።
ፍጻሜው ይኸ ነው የንፍገቱ ኃይል ።
መንግሥትንም ማፍረስ ያለውልውል ።
ሌላም ምሳሌ አለው እውነት ምልክቱን ።
የንጀራ አባት ወደ የሚገል አባቱን ።
ፍጹም እብድ ይባላል ልብ የሌለው ጥንቱን ።
ሕይወቱን የማይወድ የመረጠ ሞቱን ።
መነቀል የሚሻ እርስቱና ጉልቱን።
ከንጀራ አባት ጋራ አባቱን ቢገድል
ያየንጀራ አባቱም ታግቦ በውል ።
ላባቱ ያልሆነ ይህ ምን ይረባል ።
የኔም ለት ይኸው ነው ብዙ ያስፈራል ።
ባይቀድመኝ ልቅደመው ብሎ ያሳበባል
በተመቸው ጊዜ ገደል ይሰዳል
ልብ ያላችሁ ሰዎች ይህን እስተውሉ ።
ምሳሌውን እውነት ቸለል አትበሉ ።
ካባት ጋራ ተጣልቶ በጥቂት ነገር።
ከንጀራ አባቱ ጋራ የሚተባበር ።
ፍጹም ደንቆሮ ነው ዓይን የለው ዕውር
የዚህም ምሳሌው ትርጓሜው ክሱት ።
አባት መንግሥት ነው አገርም እናት ።
ያየንጀራ አባትም የሕዝብ ጠላት ።
ከልብ የወጣ ነው ንፍገት የሚሉት ።
ጋሻውና ጦሩ ይባላል ከፋት ።
በጣም አደንቁሮ ለመንቀል እርስት
ይህንን ምሳሌ ለሚመረምር ።
ከጥቂት ቀን ምኞት ይሻላል አገር ።
ትርቦ ተጠምቶ ልጅን ማስተማር ።
ልጁን ያስተማረ ትርቦ ተጠምቶ ።
ኋላ ደስ ይልዋል ፍሬውን አግኝቶ ።
መንግሥትን መውደድ ለሐገር
ማሰብ የሚገኝ በትምርት ነው።የተማሩ
የአውሮጳ ሴቶች በስሐገራቸው ፍቅር
ከወንዶች ጋር ተሰልፈው ተዋጉ ይሉናል
ልብ ከዘነጋ ከሌለች ዕውቀት ።
እንደምን ይገኛል ርስትና ጉልት ።
እርሶ መብላት ያለም እንኳንስ ማዘት።
ቀለብ ድርጎ የለ እንደያው መዋተት ።
እየተጠጡ በረሐብ መሞት ።
የምትሰሙ ሁሉ ይህን ልብ አድርጉት ።
እኔ ነግሬያለሁ ውርድ ነው ከራሴ።
ሕሊናዬ አደንቅፈኝ አቴቅሰኝም ነፍሴ።
በፍቅር እንኑር እንዳይሆን ድምሳሴ ።
አገር በመጠበቅ በሹም በእንደራሴ ።
እንደተባበሩ እሥራኤል ከሙሴ ።
ኦሪት ዘፀአት ም ፲፯ ቍ ፲፩ ፲፪ ።
ተባብረን እንሥራ ተዉ በሥላሴ ።
ስላገሩ መንግሥት የሚተጋ ሰው ።
ከሁሉ የሚበልጥ ታላቅ ስም አለው ።
በታሪክ የሚጻፍ የሚያስከብረው ።
በአውሮጳ አገር መንግሥት ወዳጆች ።
ሴቶች ይተጋሉ እንኳንስ ወንዶች ።
በድንገት ተነስቶ ጦር በበልጅጎች ።
ደግሞም ሁለተኛ በፈረንሳይዎች ።
ተጣልተው ነበሩ ሁለት መንግሥቶች ።
ጀርመን ፈረንሳይወች ጥንት ባለደምች።
አገራቸው ገብተው ፈጥነው ጀርመኖች።
ጦርነት ተነስቶ ሲዋጉ ጀግኖች ።
በጦር ቢበረቱ ጸንተው ጠላቶች ።
እንደጐርፍ ብዛት ማገድ ባይመች ።
ሴቶችም እረዱ አልፈሩም እንዳች ።
ሞት ይሻላል ብለው ከጠላት ማጥቃት ።
ሴቶችም ተዋጉ በጦር በጥይት ።
በረር መሐል ገብተው ያሳንዳች ፍራት።
እንደወንድ ታጥቀው ሳይመስሉ እንደ ቤት ።
ደግሞም በሴትነት ብዙ እያለቀሱ ።
መስለው ቀረቡና ቍስለኛ እሚያነሱ ።
በሽጉጥ ገደሉ ደምን ሲመልሱ ።
የባል የወንድም የልጅን በቀል ።
ሴቶቹም እንደወንድ በጦሩ መሐል ።
በመናደድ ቀርበው በሽጉጥ መግደል ።
እጅግ ያስደንቃል እንደሃል ፍቅር ።
ልባቸው አንድ ሆኖ በመተባበር ።
መንግሥትን ለማጥናት ለማዳን አገር ።
ወንድ ልጅ አልቀረም የሚያነሳ ጦር ።
ተሰልፎ ገባ ሽማግሌ አሽከር።
እንኳንስ ወንድ ልጅ የሚጠነክር።
ጠንተው ተጋደሉ ሴቶቹ ሳይቀር ።
አገርን ለማልማት መንግሥት ለማክበር
ይህ ነው ታላቅ ነገር ዓይነተኛ ውል ።
ስላገሩ ብሎ ጸንቶ መጋደል ።
እንዲህ ሲረዳዱ ለሚያልፈው ንብረት ።
እንዴት ቸላ እንበላት የተማሪን ቤት።
ጥበብ እንዳሰብን አወቀው ዓለም ።
ኢትዮጵያ ገባ እንግዲህ ሰላም ።

መክብብ ደስታ ።

የከተማ ወሬ ።

በታሕሣሥ ፲፰ የተደረገ ሹም ሽር ።

የሥራ ምኒሥትር ቤት ሹም ተብሎ።አቶ ፋሲክ ፤
ቀኛዝማች ፀምሩ።የንጨት ቀረጥ ሹም ፤
ባላምባራስ ታፈሰ የኢሉባቦር ነጋድራስ ፤
ቀኛዝማች ጽጌ ያሊዩ እንባ ነጋድራስ ፤
ልጅ ኃይሌ ወልደ መስቀል ያተቆጣጣሪዎችና የጻሐፊዎች ፈታሽ ቢሮ ቤት አለቃ ።

ክቡራን ሹማምንት ሆይ ስራችሁ ደስ የሚያሰኝ ፍሬ እንዲገኝበት ተስፋ እያደረገ ብርሃንና ሰላም እንኳን ደስ አላችሁ ይላል ።

ስለ ድሬ ዳዋ ጐርፍ ።

የድሬ ዳዋ ሹማምንቶች በጐርፉ ምክንያት የከተማውን ጉዳት ለልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን እስታውሰው ልዑልም በሰፊው ዕውቀታቸውና ቸርነታቸው እስካሁን ባለመሠራቱ ተጸጽተው ከተማውን ውሀ እንዳይመታው በጠንከራ ሥራ ሆኖ በኖራና በአሸዋ ተገንብቶ እንዲገደብ ለሹማምንቶቹ ትእዛዝ ሰጥተዋል፤ሹማምንቶቹም የዚህን የጐርፍ ማገጃ ግድብ የሚሠራውን መሐንዲስ ዋጋውን ያጫርታሉ ።ይኸውም ግድብ ቢበዛ ቢበዛ እስከ አምስትና እስከ ስድስት ወር ድረስ ተሠርቶ እንድናየው ተስፋ እናደርጋለን ። በድሬ ዳዋም ውስጥ ያለው ሕዝቡ የከተማው ልማትና ጥፋቱ ለሁሉም ስለሆነ ለዚህ ለጐርፍ መገደቢያ ለሚወጣው ገንዘብ እርዳታው የተስናዳ መሆኑን በትክክል ይታወቀናል ስለዚሁም የድሬዳዋው ሹም ሕዝቡን አነቃቅቶ ይህ ሥራ በቶሎ እንዲፈጸም ያደርጋል ብለን ሙሉ ተስፋ አለን ።

ፊታውራሪ ኃይሌ ።

ሄራልድ ከሚባል ጋዜጣ የተገለበጠ ።

ድንች መጀመሪያ የተገኘው በደቡብ አሜሪክ ነው ። እስከ ዛሬም በፔሩና በችሊ በሞንቴቢዶ አገሮች በዱር እየበቀለ ይገኛል አስቀድሞም ኤውሮጳች ያወቁበት ዘመን በ፲፬፻፺፰ ዓመተ ምሕረት ነው ። (ማለት የዛሬ ፬፻፳፯ ዓመት) አሁን ግን ከዓለም በሚበልጠው ክፍል ተዳርሷል ። ሲናር ወይም ገሬማ እስከ ዛሬ በኢትዮጵያ ራሙቻ ሁኖ ይኖራል ላገሩም የባሕርዩ ገንዘቡ እንደሆነ ገና አሁን ታውቆ ይሆናል ። ስንዴና አጃ መጀመሪያው በሴቤሪያና በታርታሪ ነው ። በቆሎ ወይም የባሕር ማሺላ መጀመሪያ የተገኘው ሜክሲኮ በሚባል አገርና በሰሜን አሜሪክ ውስጥ ባሉት አገሮች ክፍል ነው ። የእስጳንያርድ ሰዎችም ሜክሲኮን አግኝተው እጅ እስከደረጉበት ቀን ድረስ ይህ በቆሎ የሚባል እህል በኤውሮጳ ገና አልታወቀም ነበር የሻይ መጀመሪያው በቻይናና በጃፓን አገር ነው ። የቡና በአረብ አገር ነው አተል ወይም ቱፋህ በዓለም ሁሉ በብዙ ክፍል ይገኛል ነገር ግን ከመጀመሪያ ባሕርዩ ጥጥር ነበርና ሰዎች በመትጋትና በመትከል ምክንያት አራብተው የከበረ ምግብ እንዲሆን አደረጉት ። የኮክ መጀመሪያው በፋርስ ነው እርሱም በመጀመሪያ መራራና ቱንሽ ነበር ፤ ቀስተንቻ የተገኘው ከእስያ ነው ። የጐመን መጀመሪያው ከሆላንድ ነው ፤ እሩዝ ከኢትዮጵያና ከምሥራቅ ኢንዲስ ነው የሸንኩርት መጀመሪያው ከአፍሪክ ነው ። የሸንኮር አገር መጀመሪያው ከቻይና ነው ። የሱክርም ፋብሪክ የተጀመረው በቻይና ነው ። ከዚያም ወደ አረብ አገር ተዛመተ ። ከአረብ አገርም ወደ ምስር ደረሰ ። እንዲሁም ሙርስ የሚባሉ ሕዝብ ወደ እስጳን አደረሱት ። ከዚያም ወደ ምዕራብ ኢንዲስና ወደ ብራዚል አገር ደረሰ ። ትንባሆ መጀመሪያ የተገኘው በአሜሪክ ነው ከዚያም በኤልሳቤጥ በእንግሊዝ ንግሥት ዘመን አንድ ሰር ወልተር ራሌ የተባለ የንግሥቲቱ ባለሟል አሜሪክን ለማየት ሄዶ ነበርና ከዚያ በኋላም ያን አገር ለማቅናት እስበ ያገሩን ሰዎች ወደ አሜሪክ ለመስደድ ብዙ ጊዜ ፈትኖ ሳይከናወንለት ስለቀረ ወደ አገሩ ሲመለስ ድንችንና ትንባሆን ወደ እንግሊዝ አገር ይዞ ተመለሰ በእንደዚህ ምክንያት በዓለሙ ሁሉ ተዳረሰ ክቡራን አንባቢዎች ሆይ ይኸን ከዚህ በላይ ያለውን ታሪክ ገልብጬ የጻፍኩበት ምክንያት ከዚህ ቀደም ይኸን ነገር የተረዱትን ሰዎች ለማስታወስ ላልተረዱትም እንዲረዱበት ይጠቅማል ብዬ ነው ። ይልቁንም ነገር ሁሉ መጀመሪያና መጨረሻ አለው ደግሞም የሩዝ መጀመሪያው በኢትዮጵያና በምሥራቅ እንዲህስ እንደሆነ ሄራልድ በሚባለው ጋዜጣ ባነበብሁ ጊዜ እጅግ ደስ ብሎኝ እንደኔ ከዚህ ቀደም ያልሰሙ ይኖራሉ በማለት ጻፍኩት ደግሞም ገሬማ የኢትዮጵያ የባሕርዩ ሲሆን እራሙቻ ሁኖ ይኖራል ። ነገር ግን በአውሮጳና በአሜሪክ በሰው አገር ክብሮ አንዱ ንጥር ከስር ወቄት በቆርቆሮ እዚህ እየመጣ እንዳይነቱ ከአንድ ብር እስከ ብር ተሩብ ይሸጣል ። የሩዙንም ነገር ብዙዎች ታውቂታላችሁ ቀስተንቻም መጀመሪያው በእስያ ነው ተባለ እንጂ እኔ እንደ ሚመስለኝ የኢትዮጵያም ገንዘቧ ሳይሆን አይቀርም ። ለዚህም የሚያስረዳ በአገራችን በቆላውም በደጋውም በበረሃውም በለሙም አገር ውስጥ በብዙ ቦታ እየበቀለ ይገኛል የጥንትም ሰዎች ብዕር እየቀረጹ ይጽፉበት ነበር ፤ ነገር ግን ዛሬ በአውሮፓ ዋጋ ያለው ምግብ ሆኑዋል ። እንግዴህ ሩዝ ባገራችን መጀመሪያ ሲሆን መጨረሻ ሁኖ ባገራችን አለመብቀሉን ገሬማም ራሙቻ የሆነበትን ምክንያት ከተረዳነው ፤ አየሩና አገሩ የሚስማማውን ቦታ እየመረመርን ሩዙም እንዲዘራ ገሬማውም ሰብል እንዲሆን ብንፈትን መልካም ነበረ ።

ተፈራ በልሁ ።

የቴሌግራም ቃል።

ያ፲፰ ታሕሣሥ ፲፱፻፳፭ ዓ ም ።

ሮማ ፤ የፐሩ መልክተኛ ከመንግሥት ያመጣውን የፐሩ ግራንድ ኮርዶን (ኒሻን) በተቀበለ ጊዜ ሙሶሊኒ መሪው ይህን ያህል ከፍታ ያለው ማዕርግ በመቀበሉ ደስ ብሎት ለመልክተኛው የደስታዬን ብዛት ለፐሩ መንግሥት አስተርጉምልኝ ብሎ ለመነው ። ከንፌደራሲዮን እንደራሴዎች ከምክር ቤት ፕሬዚዳን በተነጋገሩት የተነሣ ይህነን ሥራ ትልቅ ምክር የያዘ ማሕጸን ሳይሆን አይቀርምና ይህ ፌደራሴዮን የፋሽስት ግራንድ (ትልቅ) ፌደራሲዮን ተብሎ ይጠራ ብለው አቁመዋል ። ሰናተር ይሁን ብሎ ከሕግ እንዲታተም አቁሟል ።

ፓሪስ ፤ የሉሸር ምክር ዱመር የገንዘብ ሚኒስትር ተሹሟል

ጄኔብራ ፤ ከእንግሊዝና ከቱርክ መልክተኞች ምኞት በቀር ዳርቻዋ ብሩክሰለስ ከሚባል ትይዩ ሁኖለት ለጊዜው እንዲሁ እንዲቆይ በማለት ፍርድ አንድነት ሁነው የዓለም መንግሥት ማኅበረተኞች የቱርክንና የኢራክን ዳር አቁመውታል ። እንደ ቢላየት ወሬ ግን ሞሱልና ኢራክ በመላው ለሠላሳ አራት ዓመት በንግሊዝ ሳይመራ አይቀርም ።

ባይሩት ፤ ራኪያና ራስኪያ በሚባሉ አገሮች መሐከል ለድሩሲ እንገዛለን ሲባል ራኪያ ከሚባል የክርስቲያን መንደር ዙሪያ የድሩሲ ጭፍራ እንዳሉ ያስረዳል ።

ሮማ ፤ ዛሬ ጧት ጳጳስ በካርዲናልንነት አንብሮ እድ ፭ አዲሶች ቀይ ልብስ ለማልበስ በግልጽ ከቅዱስ ጴጥሮስ ቤተ ክርስቲያን የካርዲናሎች ጉባዔ አድርገዋል ። በዓሉ በብዙ ምዕመናን ፊት በጣም ተከብረዋል ቤተ ክርስቲያኖች ለንጉሥ እናት ንግሥት ጤና ለማስገኘት (እንደተለመደ) የሶስት ቀን ጸሎት ማድረግ ጀምረዋል ።

ቦርዶገራ ፤ እንደመጨረሻ ወሬ የንጉሥ እናት ንግሥት ከብዙ ቀን ጀምሮ የሳምባ በሽታ ማነሳሳ በቀኝ ጐድን አግሬጥ ተይዘው እስካሁን ድረስ ትኩሳት ፴፱ ፴፰ ድግሬ ደርሷል ሲተነፍሱም ብዙ ያማቸዋል ።

ቶኪዮ ፤ ከማንርክ የሚገኙ የዣፓን ጭፍሮች በአጉልነት እንዲኖሩ የጠና ትእዛዝ ተቀብለዋል ።

ቤርሊን ፤ ሂንደቡርግ ኮከን ተቀብሎት ሲያበቃ) ኮክ በተናገሩት ቃል ጓደኞቹ አይሆንም እንዳሉት ስለነገረው ምንም በተላከው ሥራ ቁም ነገር ባያቆም እሱ ስለሞከረውና ቁርጡንም ስላስታወቀው ኮክን አመስግኖታል ።

ዎሺንግቶን ፤ በዕዳ በሆነው የሰናተር ጉባዔ እንደ አውሎ ነፋስ ሁኑዋል ሆወል የሚባል ሰናተር ከኢጣልያ ጋራ ባቆመው ስምምነትና ተወስኖ ባለው ጊዜ መከከል እስታቲ ኡኒ ከዕዳው ዋና ገንዘብ አንድ በመቶ ብቻ ወለዱንም በመቶ አንድ ስምን

ተኛ እጅ ሊቀበል ነው ። ብሎ ተናግረዋል ቀጥሎም ሆወል ኢጣልያን ዕዳ ውሳኔ ላሜሪኩ ነጋዴዎች ሶስት ሶስት ሚሊያርድ ዶላር ጉዳት ያመጣባቸዋል ብሎ ገልጽዋል እስም የሚባል ደግሞ ኢጣልያ ተወስኖባት ባለው ጊዜ መክፈል መቻሏ ያጠራጥራል ብሏል ።

ሮማ ፡ ጀበልጀ ከሚባል አገር የፈረንሳዊ ወገን በመሰለ እንግዛለን ባይ እየሰፋ ይሄዳል የሚልና ፡ በጦርነት ያሀል አብደልከሪም ይጨነቃል የሚል ቃል ከፌዝ የመጣ ወሬ ደርሰዋል ።

ሉፖሉ ፡ ተጀነብሩ የመጣ ሻምበርለን የንግሊዝ ውጭ ጉዳይ ምኒስትር ወዲህ ደርሰዋል ።

ሎንዶን፡ሊዮድ ጂዮርጂ ወደ ኢጣሊያ ለመሄድ ተነስቷል

ሮማ ፡ በትእዛዙ ምክር ቤት ፕሬዚዳን ምኞት የሥራ ክባሌር ምክር ቤት ዱካ አብሩሲን በቅኔ ማዓርግ በታች የስራ ክባሌር ይባል የሚል ምኞት ተቀብሏል ።

ሮማ ፡ ፕሬዚዳን ሙሶሊኒና ብዙዎች መኳንንቶችም አለቆችም ባሉበት ቁማ ያለችው ደግ የሆነች የፋሺስቲ ሥራ በከምቢዶሊዮ አገር በማክበር በዓል ተደርጎላታል ፤ ሙሶሊኒ ብዙ ዲስኩር ተናገረ ።

አንጎራ ፤ በሞሱል የሆነ ነገር የዓለም መንግሥታት ማኅበረተኞች የፈረዱትን ፍርድ የሰውን ፍርድ ስለመሰለ ጋዜጠኞች አንድ ቃል ሁነው ማላገጫ ነው ብለው ያወራሉ ።

ቦርዲጋራ ፡ የንጉሥ እናት ንግሥት ገና አሙዋቸዋል ።

ፓሪስ፤ በሲርያ የሚኖሩ የፈረንሣዊ ወታደሮችና ሠራተኞች የተቀበሉትን ደምብ በመፈጸማቸው መንግሥትንም በሰላማዊት ፖለቲክነቱና ባስተዳዳሪነቱም ሥራውን በመታመን ስላደረገ ጂዩበልንም ባስተማሪነት ያሀል ሥራው በማሰልጠኑ ፤ በሲርያ በሆነው ነገር ተሰብስቦ የነበረ ጉባኤ በተቀበሉት ደምብ ሥራውን በመፈጸም ሁላቸው በማመስገን ሥራውን ፈጽመዋል ።

ፓርቱሰዳን ፤ ንጉሥ አሊ የሐጃዙን አልጋ (መግዛት) ትቶታል ።

ሚላኖ ፤ የጥዳት ፕሮፌሰር ምክር ቤት በሚከተለው ምክንያት ለሙሶሊኒ የመዓርግ ብልጫ ምስክር እንደሚከተለው ፈቅዶለታል ። ማለት ለትልቁ ከንድ የገማ ፍራሽ ድንገትም ከሚገኝበት ከምር ሐናጺ እንደገና ሐናጺ ።

ዋሽንግቶን ፤ የአሜሪካ መንግሥት ወይ በጽሕፈት ምኞቱን በማስታወቅ ወይም መንግሥት ባለቤቱ በመጨረስ ካልሆነ በቀር ብረትን በማስጣል ከሚሰበሰበው ጉባኤ ሥራውን የሚመለከት መስደድ ሐሳብ የለውም ።

ሮማ ፤ ጉባዔው ከዋሽንግቶን የመስማማት ምኞት ንግግር የሆነውን ሥራ ይቀጽላል ቢያማርከ የሚባል በኢጣልያ የተደረገው ተግባር ትልቅ መታመን ሥራ ነው በማለት ገልጦ ቀጥሎም ኢጣልያ በውጭ ልትሠራው ያላትን የስምምነት ሥራ እያመሰገነ ቀጥሎም ዓለም ሁሉ ሁኖለት ያለ ማግኘት የሚያቆያት የጥንት አገራችው ለንደዚሁ ለያደረሱዋት የሚሹ ወንድሞቻችን ጨካኞችና የከሩ ናቸው ብሎ አቁሟል።ሚኒስትሮ ቦልፒ ደግሞ ከፍ ባለ ቃል የዋሺንግቶን ስምምነት ያጠነክራል ቀጥሎም ከዚሁ መስማማት በቀር ምንም ቢሆን ከስታቲ ኡኒ ሌላ ውል ተደርጎ የቆመ የለም ብሎ ሲያቆም በመጨረሻው ሁለቱ አገሮች ለወደፊት ለየመንግሥታችን የሚረባ ሥራ ለማግኘት የሚያሳይ ሥራ ሠርተናል ይላል ጆሊቲም ጉባዔውም ምኞቱን ተቀብለውታል ።

ማስታወቂያ ።

በርሻና በመስሪያ ሚኒስትር ሥራ ውስጥ መንግሥት ያወጣውን ደምብና ሕግ ሳልተላለፍ ደሀ ሳልበድል ፤ የመንግሥቱን ገንዘብ በጥንቃቄ ሠርቼ ቀድሞም ከሚሠራው ሠራተኛ ገቢ ገንዘብ አብልጬ አገባለሁ የሚል ሰው እርሻና እመስሯ ምኒስቴር መጻፊያ ቤት፤ ሁል ጊዜ ከጧቱ ከ፫ ሰዓት እስከ፮ ሰዓት ድረስ ፤ እየመጣ ቢነጋገር በደስታ እንቀበለዋለን ደመወዙም እንደ ሥራው ገቢ እየታየ ይቈረጥለታል ጥቅምት ፲፮ ቀን ፲፱፻፲፰ ዓመተ ምሕረት ።

መኰንን ሀብተ ወልድ።

ማስታወቂያ

ለራሶችና ለደጃዝማቾች ለሴት ወይዘሮች የሚገባ በያይነቱ ጥሩ ካባ ከኤሮፓ መጥቶልኛል ቤቱም (ባንክ ኦፍ አቢሲንያ) ከእንግሊዞች ባንክ አጠገብ ነውና ይህን ካባ መግዛት ለሚፈልጉ ሰዎች መጥተው እንዲገዙ እስታውቃለሁ።

ኢያሱ ዳንኤል

አ ፔ ማርሲያኖ

በኢትዮጵያና በፈረንሳይ የቅኝ አገር ሶማሊ በተለየ ፊያት አውቶሞቢልና ትራክተር አስመጭና እንደራሴ።



A.P. MARCIANO

Concessionnaire Exclusif pour l'Ethiopie
et la cote française des somalis
des automobiles et tracteurs Fiat

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ።

BRITISH MUSEUM 22 MAY 25